# ማውጫ


| ርዕስ | ገፅ |
|---|---|
| የጸሐፊው መልእክት፡ ይህ ሐተታ እንዴት ይረዳዎታል? | i |
| ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ፡የተፈተነ እውነትን በግል ለመፈለግ | iii |
| የዮሐንስ ወንጌል መግቢያ | 1 |
| ዮሐንስ 1 | 7 |
| ዮሐንስ 2 | 35 |
| ዮሐንስ 3 | 46 |
| ዮሐንስ 4 | 65 |
| ዮሐንስ 5 | 81 |
| ዮሐንስ 6 | 94 |
| ዮሐንስ 7 | 118 |
| ዮሐንስ 8 | 131 |
| ዮሐንስ 9 | 145 |
| ዮሐንስ 10 | 153 |
| ዮሐንስ 11 | 162 |
| ዮሐንስ 12 | 176 |
| ዮሐንስ 13 | 191 |
| ዮሐንስ 14 | 202 |
| ዮሐንስ 15 | 220 |
| ዮሐንስ 16 | 229 |
| ዮሐንስ 17 | 239 |
| ዮሐንስ 18 | 251 |
| ዮሐንስ 19 | 265 |
| ዮሐንስ 20 | 277 |
| ዮሐንስ 21 | 287 |
| የ1ኛ ዮሐንስ መልእክት መግቢያ | 294 |
| አንደኛው የዮሐንስ መልክት 1፡1-2፡2፣ | 299 |
| አንደኛው ዮሐንስ 2:3-27 | 309 |
| የዮሐንስ መልዕክት 2:28-3:24 | 325 |
| 1ዮሐንስ ምዕራፍ 4 | 344 |
| 1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ 5 | 354 |
| 2ኛ ዮሐንስ መልዕክት | 368 |

3ኛ ዮሐንስ መልእክት………………………………………………………………………………….. 376
ተጨማሪ መግለጫ አንድ/የግሪክ ሰዋሰዋዊ ቃላት አጭር መግለጫዎች ………………………………… 384
ተጨማሪ መግለጫ ሁለት/ጽሑፋዊ ትንተና ……………………….…………………….……………… 394
መግለጫ ሶስት/የቃላት ፍቺ………………………………………………………………………… 398
ተጨማሪ መግለጫ አራት/የእምነት መግለጫ ………………………………………………………….. 410

# ልዩ ርዕስ ማውጫ


ርዕስ ገጽ

ልዩ ርዕስ፡ አሪኬ ........................................ 10
ልዩ ርዕስ፡ የጌታ መላእክ ........................................ 11
ልዩ ርዕስ፡ እምነት፣ ማመን ወይም ተአማኒ (ፒስቲስ (ስም)፣ ፒቴዎ (ግስ)፣ ፒስቶስ (ገላጭ) ........................................ 12
ልዩ ርዕስ፡ ስለ ኢየሱስ ምስክርነት ........................................ 14
ልዩ ርዕስ፡ ማወቅ (የዘዳግም መጽሐፍን እንደ እይታ መነጽር በመጠቀም) ........................................ 15
ልዩ ርዕስ፡ ሥጋ (ሳርካ) ........................................ 16
ልዩ ርዕስ፡ ክብር (ዶክሳ) ........................................ 17
ልዩ ርዕስ፡ ቸርነት (ሄሴድ)........................................ 18
ልዩ ርዕስ፡ ማመን፣ እምነት እና ታማኝነት በብሉይ ኪዳን ውስጥ ........................................ 18
ልዩ ርዕስ፡ ጳውሎስ ስለ ሙሴ ሕግ የነበረው አመለካከት ........................................ 21
ልዩ ርዕስ፡ ፈሪሳዊያን ........................................ 26
ልዩ ርዕስ፡ የሐዋርያት ስም ዝርዝር ሰንጠረዥ ........................................ 30
ልዩ ርዕስ፡ የናዝሬቱ ኢየሱስ ........................................ 31
ልዩ ርዕስ፡ አሜን ........................................ 33
ልዩ ርዕስ፡ ሰማይ ........................................ 34
ልዩ ርዕስ፡ ስለ መጠጥ እና ስለ መጠጥ ሱሰኝነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከት ........................................ 37
ልዩ ርዕስ፡ የጥንት ምስራቃዊያ የክብደት እና የሊትር መሊያ (ሜትሮሎጂ) ........................................ 39
ልዩ ርዕስ፡ ፋሲካ ........................................ 42
ልዩ ርዕስ፡ "አመነ" የሚለው ግሳዊ ይዘት የዮሐንስ አጠቃቀም ........................................ 45
ልዩ ርዕስ፡ የአይሁድ ሸንጎ ........................................ 47
ልዩ ርዕስ፡ የእግዚአብሔር መንግስት ........................................ 50
ልዩ ርዕስ፡ እስትንፋስ፣ ንፋስ፣ መንፈስ ........................................ 52
ልዩ ርዕስ፡ እግዚአብሔር በሰውኛ ሲገለጽ ........................................ 54
ልዩ ርዕስ፡ አስቀድሞ መወሰን (ካልቪኒዝም) እና የሰው ነፃ ፈቃድ (አርሜኒያኒዝም)........................................ 55
ልዩ ርዕስ፡ ማህተም ........................................ 62
ልዩ ርዕስ፡ ዘረኝነት ........................................ 67
ልዩ ርዕስ፡ ብሉይ ኪዳን ትንቢት ........................................ 71
ልዩ ርዕስ፡ የአዲስ ኪዳን ትንቢት ........................................ 74
ልዩ ርዕስ፡ አባት ........................................ 76
ልዩ ርዕስ፡ መሲሐ ........................................ 76
ልዩ ርዕስ፡ የእግዚአብሔር ፍቃድ (ቴሌማ)........................................ 78

ልዩ ርዕስ፡ ፊውስ በሁሉም ዘመናት ውስጥ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነውን …………………………….. 85
ልዩ ርዕስ፡ "ይቅር የማይባ ኃጢአት" የሚለውን በትክክል ለመፍታት
ልንከተለው የሚገባን ሥነ መለኮታዊ መርሆዎች ……………………………………………….. 87
ልዩ ርዕስ፡ መላክ (አፖስትሎ) ………………………..……………………………….. 88
ልዩ ርዕስ፡ ሰዓቱ ……………………………..………………………………………........................ 88
ልዩ ርዕስ፡ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ስብከት ………………………………………………………… 91
ልዩ ርዕስ፡ በኢየሱስ ዘመን በፍልስጤም ውስጥ አገልግሎት ላይ ይውል የነበረው ገንዘብ ……….…..... 97
ልዩ ርዕስ፡ ዐስራ ሁለት ቁጥር ………..……………..……………..………………….…......... 99
ልዩ ርዕስ፡ የመለኮት ስሞች ………..………………………..………………………….………...... 100
ልዩ ርዕስ፡ የክርስቲያኖች የድነት ማረጋገጫ …..…………..…………………………………...….... 105
ልዩ ርዕስ፡ የ"እውነት" ጽንሠ ሀሳብ በዮሐንስ ጽሁፎች ውስጥ ……..…………..……………......... 109
ልዩ ርዕስ፡ ዘላለም (አላም) ……..………………………………..………………………..…….......... 110
ልዩ ርዕስ፡ ዕርገት ……..……………..……………..……………………..…………..……..….......... 112
ልዩ ርዕስ፡ መንፈስ (ኒዩማ) በአዲስ ኪዳን ……..…………..………..………..……….…….......... 113
ልዩ ርዕስ፡ ክህደት (አፌሰቴማይ) …….………………..………..……………………..…….......... 113
ልዩ ርዕስ፡ ድፍረት (ፓርሲያ) ……..………..………..………………..……………..…….......... 120
ልዩ ርዕስ፡ አጋንታዊ (ርኩስ መንፈስ) ……..……………………..………………………….......... 123
ልዩ ርዕስ፡ የመጽናት አስፈላጊነት ……..……………..………..……..…..…………..……........... 138
ልዩ ርዕስ፡ ኖስቲካዊነት ……..………..…..………..……………..………..……..…..……........... 141
ልዩ ርዕስ፡ መዳንን ለመግለጽ እጥቅም ላይ የዋሉ የግሪክ ግሦች ……..……………………......... 148
ልዩ ርዕስ፡ የእምነት ቃል ……….……………………..……………………………..…….......... 149
ልዩ ርዕስ፡ ጥፋት (*apollumi*/*አፖሉሚ*) ……..……………..…………………..……........... 155
ልዩ ርዕስ፡፡ መቀባት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ (BDB603) ………..……..………………….......... 164
ልዩ ርዕስ፡ የሐዘን ልማዶች ………..………………………..……………………..……….......... 167
ልዩ ርዕስ፡ ሴቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ………..……………………..………..…….......... 168
ልዩ ርዕስ፡ የቀብር ልማዶች ………..………..……………………..…………..…………..…..... 172
ልዩ ርዕስ፡ ክፋት ………..………..……………..…………..……..……………..…………........ 185
ልዩ ርዕስ፡ ጦርነት በሰማያት ላይ (በራዕይ መጽሐፍ ላይ ከሰጡት ማብራሪያ የተወሰደ) ……….…..... 186
ልዩ ርዕስ፡ ልብ ………..…………..…………..…………..……………..…………..……......... 188
ልዩ ርዕስ፡- በዮሐንስ ጽሑፎች ውስጥ "ትዕዛዝ" የሚለው ቃል አጠቃቀም ………………………......... 190
ልዩ ርዕስ፡ የመጀመሪያው ክ/ዘ የአይሁድ እምነት የፋሲካ በዓል ደንብ ……………………………..... 194
ልዩ ርዕስ፡ አስቆርቱ ………..…………..…………..………..………………..…………......... 198
ልዩ ርዕስ፡ ሙታን የት ይኖራሉ ………..………..…………..……………..…………..…….......... 205
ልዩ ርዕስ፡ ውጤታማ ፀሎት ………..………..…………..………..……..…………..…………..... 210
ልዩ ርዕስ፡ የእግዚአብሔር ስም/የጌታ ስም ………..………..…………..……………..…………..... 211

ልዩ ርዕስ: ኢየሱስ እና መንፈስ ……….…………………………………….……….…………….....  212
ልዩ ርዕስ: *Cosmos* (ዓለም) የሚለው ቃል በጳውሎስ አጠቃቀም ……….……….……………….. 213
ልዩ ርዕስ: በዚያን ቀን ……….………………………………….……………………………………. 214
ልዩ ርዕስ: ሥላሴ ……….………………………………….………………………………….…. 216
ልዩ ርዕስ፡ የመንፈስ ስብእና /ማንነት ……….……….………………………………………….... 217
ልዩ ርዕስ: ክርስቲያን እና ሰላም ………………………………………………….…………………. 218
ልዩ ርዕስ: እሳት ……….………………………………….………………………………………..... 223
ልዩ ርዕስ፡ አብርሆት ……….………………………….…………………….…………………….. 233
ልዩ ርዕስ፤ መመረጥ …………………………………….………………………………………….. 241
ልዩ ርዕስ: "እውነት" (ቃሉ) በዮሐንስ ፅሑፎች ውስጥ ……….…………………………………. 242
ልዩ ርዕስ: ቅዱስ ……….………………………………….…………………………………………. 245
ልዩ ርዕስ: መመረጥ/አስቀድሞ መወሰንና የሥነ-መለኮታዊ ሚዛን አስፈላጊነት ……….……….…….…. 254
ልዩ ርዕስ: የናዝሬቱ ኢየሱስ ……….………………………………….…………………………. 255
ልዩ ርዕስ: የፕራይቶሪየም ጠባቂ ……….………………………………….……………………. 260
ልዩ ርዕስ: ጴላጤናዊው ጲላጦስ ……….………………………………….……………………. 261
ልዩ ርዕስ: ኢየሱስን የተከተሉት ሴቶች ……….………………………………….………. 272
ተጨማሪ የጥናት ርዕስ: የቀብር ቅመማ ቅመሞች ……….………………………………….…. 275
ልዩ ርዕስ: የኢየሱስ ድህረ-ትንሣኤ መልኮች/ግጽታዎች ……….……………………………. 281
ልዩ ርዕስ፡ መልክ (TUPOS) ……….………………………………….……………………. 284
ልዩ ርዕስ: ዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 1 ከ1ኛ ዩሐንስ ምዕራፍ 1 ንጽጽር ……….……………….. 301
ልዩ ርዕስ: *ኮይኖኒያ* ……….………………………………….…………………………………….. *303*
ልዩ ርዕስ: ክርስትና ህብረት ነው ……….………………………………….…………………….. 303
ልዩ ርዕስ: "ብትኖሩ" በዩሐንስ ጽሁፎች ……….………………………………….………….. 314
ልዩ ርዕስ: ማወቅ (በዘዳግም መጻሐፎች አጠቃቀም የተወሰዱ ምሳሌዎች) ……….……….….... 316
ልዩ ርዕስ: የሰው ልጅ መንግስት ……….………………………………….………………. 317
ልዩ ርዕስ:ይህ ዓለም ፣የሚመጣው ዓለም ……….………………………………….……. 320
ልዩ ርዕስ: ቅዱሱ ……….………………………………….……………………………….. 321
ልዩ ርዕስ: ስለ ክርስቶስ መመለስ የተጠቀሱ የአዲስ ኪዳን ቃላት የሰው ልጆች
ኢየሱስን የሚገናኙበት ……….………………………………….………………….. 327
ልዩ ርዕስ፡ ጽድቅ ……….………………………………….…………………………….. 328
ልዩ ርዕስ: አዲስ ኪዳን ስለ አንድ ሰው ድነት የሚያቀርበው ማስረጃ ይህ የተመሠረተው
በኢየሱስ ባለው ……….………………………………….……………………………. 331
ልዩ ርዕስ፡ መቀደስ ……….………………………………….……………………….. 334
ልዩ ርዕስ: የእግዚአብሔር ልጅ ……….………………………………….………………. 336

ልዩ ርዕስ፡ ፀሎት፤ ያልተገደበ ነገር ግን የተገደበ ……….……….……………………..………… 340
ልዩ ርዕስ፡ ክርስትያኖች አንዱ በሌላው ላይ ሊፈርዱ ይገባል? ……….……….……………….. 346
ልዩ ርዕስ፡ መወርወር ለሚለው የተሠቱ የግሪክ መጠሪያዎች እና የእነርሱ እንደምታዎች …… 346
ልዩ ርዕስ፡ የቦብ ኢቫንጀሊካል አመለካከት ……..………………….………..……….……………….. 351
ልዩ ርዕስ፡ የድነት ማረጋገጫ ……….……….…………………….………..……….……………….. 359
ልዩ ርዕስ፡ የምልጃ ፀሎት ……….……….…………………….………..……….…………………… 361
ልዩ ርዕስ፡ ኃጢአት ሞት የሚገባው ምንድ ነው? …………..………..……..……………………. 363
ልዩ ርዕስ፡ ሽማግሌ ….……….…………………….……….……….………..……………………………. 370
ልዩ ርዕስ፡ ቤተክርስትያን (ኤክሴስያ)….……….…………………..……….……….……………….. 380

## የጸሐፊው መልእክት፡
## ይህ ሐተታ እንዴት ይረዳዎታል?

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጓሜ አስተውሎት እና መንፈሳዊ ሂደት ያለበት የጥንቱን ተመስጧዊ ጸሐፍት በዚህ መልኩ ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን መልእክት በዘመናችን ለመረዳትና ለመተግበር የተዘጋጀ ነው።

መንፈሳዊ ሂደቱ ወሳኝ እና ለመግለጽ አስቸጋሪ ነው። ለእግዚአብሔር መሰጠትንና ግልጽነትን ይጠይቃል። (1) ለእሱ፣ (2) እሱን ለማወቅ እና (3) እሱን ለማገልገል ጉጉትን ይፈልጋል። ይህ ሂደት ደግሞ ጸሎት፣ ንስሐ እና የሕይወትን አኗኗር ለመለወጥ ፍቃደኝነትን ይጠይቃል። በትርጓሜ ሂደት መንፈስ ወሳኝ ነው፣ ዳሩግን ትሑታንና፣ የእግዚአብሔር ሰዎች የሆኑ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን በተለየ መልኩ እንደሚረዱት ምስጢር ነው።

የማስተዋሉን ሂደት ለመግለጽ ቀላል ነው። እኛ ለጽሑፉ የማናወላውልና ተገቢ ልንሆን፣ በራሳችን ወይም በእምነት ክፍላችን አስተሳሰብ ላንወሰድ ይገባል። ሁላችንም በታሪካዊ ሁኔታዎች ውስጥ ነን። ማናችንም ብንሆን ጉዳዩ የማይነካንና ገለልተኛ ተርጓሚዎች አይደለንም። ይህ ሐተታ በጥንቃቄ ማስተዋል ሂደት የተቀመረ ሦስት የትርጓሜ መርሖዎችን አዋቅሮ የያዘና አድልዎአዊ የሆኑ አስተሳሰቦቻችንን ለመቅረፍ የሚረዳ ነው።

### የመጀመሪያው መርሕ

የመጀመሪያው መርሕ የቅዱሱ መጽሐፍ ክፍል የተጻፈበትን ታሪካዊ መቼት ማጤን ነው፤ እንዲሁም የጸሐፊውም የወቅቱ ታሪካዊ ሁኔታ ይታያል። ዋነኛው ጸሐፊ ለማስተላለፍ የፈለገው ተግባርም ሆነ መልእክት አለው። ጽሑፉ ለእኛ አንዳች የሚሆን ዋነኛው፣ ጥንታዊው፣ ተመስጧዊው ጸሐፊ የጻፈው አይደለም ማለት ፈጽሞ አይደለም። የእሱ ፍላጎት– የእኛ ታሪካዊ፣ ስሜታዊ፣ ባህላዊ፣ ግላዊም ሆነ ክፍል ሃይማኖታዊ ፍላጎት አይደለም– ቁልፉ ነው። ተግባር ዋነኛው ጓደኛ ነው፣ በትርጓሜ ሰዓት፣ ዳሩግን ሁልጊዜ ትክክለኛ ትርጓሜ ተግባርን መቅደም ይኖርበታል። እሱም ደግሞ የሚያጠናክረው እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፍ አንድ እና አንድ ብቻ ፍቺ እንዲኖረው ነው። ይህም ፍቺ የሚሆነው ዋነኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊ በመንፈስ ተመርቶ በዘመኑ ሊለው የፈለገውና ሊገናኝበት ያለውን ነው። ይሄው አንዱ ፍቺ ምናልባት በርካታ አማራጭ አግባቦች ለተለያዩ ባህሎችና ሁኔታዎች ሊኖረው ይችላል። እነዚህ አገባቦች ግን ከዋነኛው ጸሐፊ ማዕከላዊ እውነት ጋር የተገናኙ መሆን ይኖርባቸዋል። በዚህን ምክንያት፣ ይህ የጥናት መመሪያ ሐተታ የተነደፈው ለእያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ መግቢያ እንዲሆን ነው።

### ሁለተኛው መርሕ

ሁለተኛው መርሕ ሥነ ጽሑፋዊ አሀዶችን መለየት ነው። እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ሙሉ ዶሴ ነው። ተርጓሚዎች አንደኛውን የእውነት ገጽታ ከሌሎች የመነጠል መብት የላቸውም። ስለሆነም እያንዳንዱን የመጽ/ፍ ቅዱስ ክፍል ከመተርጎማችን በፊት የሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ ዓላማ መረዳት ይኖርብናል። ተናጠላዊ የሆኑት ክፍሎች ማለትም– ምዕራፎች፣ አንቀጾች፣ ወይም ቁጥሮች ሙሉው ክፍል ያላለውን የማይሉ ላይሆኑ ይችላሉ። ትርጓሜ ከሙሉ አጠቃላይ አቀራረብ ወደ ዝርዝር ክፍላዊ አቀራረብ መሆን ይኖርበታል። ስለሆነም የዚህ የጥናት መመሪያ ሐተታ የተነደፈው ተማሪዎች የእያንዳንዱን ጽሑፋዊ ክፍል በአንቀጽ በመተንተን እንዲገነዘቡት ለመርዳት ነው። የአንቀጽን ሆነ የምዕራፍ ክፍሎች ተመስጧዊ አይደሉም፤ ነገር ግን የዋና ሐሳብ ክፍሎችን ለመገንዘብ ያስችሉናል።

ዓረፍተ ነገርን፣ ንዑስ አንቀጽን፣ ሐረግን ወይም በቃል ደረጃ ሳይሆን በሙሉ አንቀጽ ደረጃ መተርጎም፣ የመጽሐፍ ቅዱሱን ጸሐፊ ዋነኛ ሐሳብ ለመረዳት ቁልፉ ነገር ነው። አንቀጾች ብዙውን ጊዜ የተመሠረቱት አንድነት ባለው ርዕስ፣ ማለትም ጭብጥ ወይም መሪ ዓረፍተ ነገር በሚባለው ነው። እያንዳንዱ ቃል፣ ሐረግ፣ ንዑስ አንቀጽ፣ እና ዓረፍተ ነገር በአንቀጹ ውስጥ ያለው፣ ይብዛም ይነስም ከዋነኛው ጭብጥ ጋር ይገናኛል። ይወስኑታል፣ ያስፋፉታል፣ ያብራሩታል፣ ብሎም/ወይም ይጠይቁታል። ለትክክለኛ ትርጓሜ ቁልፉ ነገር የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ መከተል ሆኖ አንቀጽ በአንቀጽ ላይ በተመሠረተ አካሄድ የመጽሐፍ ቅዱሱን መጽሐፍ ባስገኙት በተናጠላዊ የጽሑፍ ክፍል በሚደረግ አግባብ ነው። ይህ የጥናት መመሪያ የሆነ ሐተታ የተዘጋጀው ተማሪዎች አዲሶቹን የእንግሊዝኛ ትርጉሞች እያነጻጸሩ እንዲያዩ ለመርዳት ጭምር ነው። እነዚህ ትርጓሜዎች ተመራጭ የሆኑበት ምክንያት የተለያዩ የትርጓሜ ንድፈ-ሐሳቦችን በመጠቀማቸው ነው፡

1. የተባበሩት መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበረሰብ የግሪክ ቅጂ የተለከሰው አራተኛ እትም (የተመጽማ[4])። ይህ ጽሑፍ በዘመናዊ የጽሑፍ ሊቃውንት አንቀጹ ተሰናድቶለታል።
2. አዲሱ የኪንግ ጀምስ ቅጂ (አኪጀቅ) ቃል በቃል የተደረገ ጥሬ ትርጉም ሲሆን የተመሠረተውም የግሪክ የእጅ ጽሑፍ ባህል በሆነው ቴክስተስ ሪሴፕትስ በሚባለው ነው። የአንቀጽ አደራደሩ ከሌሎቹ ትርጉሞች ረዘም ይላል። እነዚህ ረጃጅም ክፍሎች ተማሪዎች የተዋሐዱትን ርዕሶች እንዲረዱ ያስችላቸዋል።
3. አዲሱ የተከለሰው መደበኛ ትርጉም (አየተመት) ስልታዊ የሆነ የቃል በቃል ትርጉም ነው። እሱም የሚከተሉት ሁለት ዘመናዊ ቅጅዎች ማዕከላዊ የሆነ ነጥብ ይዟል። የአንቀጽ አደራደሩ ርዕስ ጉዳዮችን ለመገንዘብ በእጅጉን ይረዳል።
4. የጊዜው እንግሊዝኛ ትርጉም (የጊእት) ዋነኛ አቻ ትርጉም ሲሆን በተባበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ሶሳይቲ (ማኅበረሰብ) የታተመ ነው። የመጽሐፍ ቅዱሱ ትርጉም የሚሞክረውም ዘመናዊ እንግሊዝኛ አንባቢ ወይም

ተናጋሪ የግሪኩን ትርጉም እንዲረዳው ማድረግ ነው። በተለይ ደግሞ የወንጌላትን አንቀጾች የሚደረድረው በርዕሰ-ጉዳዩ ሳይሆን በተናጋሪው ቃል ነው የሚደረድረው፣ በአኢት እንደተደረገው። ለተርጓሚዎች ተግባር ይሄኛው የሚረዳ አይሆንም። እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ሁለቱም (የተየመቅሶ[4]) እና (የጊእት) የታተሙት በአንድ ዓይነት አሀድ ሆኖ አንቀጻቸው ይለያያል።

5. የኢየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ (ኢመቅ) ዋነኛው አቻ ትርጉም ሲሆን በፈረንሳይ ካቶሊክ ትርጉም ላይ ነው። የአውሮጳውያንን የአንቀጽ አደራደር ስልት ለማነጻጸር በእጅጉን ይረዳል።
6. በ1995 የታተመው የተሻሻለው አዲሱ የአሜሪካን መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ (አአመመቅ)፣ የቃል በቃል ትርጉም ነው። ይህንን የአንቀጽ አደራደር ተከትሎም የየቁጥሩ አስተያየቶች ሰፍረዋል።

## ሦስተኛው መርሕ

ሦስተኛው መርሕ ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስን የተለያዩ ትርጉሞችን በማንበብ ሰፋ ያለ የትርጉም አገባቦችን ማወቅ ይቻላል (በትርጉም መስክ) የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ወይም ሐረጎች የያዙትን። ብዙ ጊዜ የግሪክ ሐረግ ወይም ቃል በተለያየ መንገድ ነው መረዳት የሚቻለው። እነዚህ የተለያዩ ትርጉሞች እነዚህን አማራጮች በማቅረብ የተለያዩ የግሪክ አማራጭ ጽሑፎችን ለመለየት ያስችላሉ። ይህም መሠረተ እምነትን አይጻረርም፣ ዳሩግን ተመልሶ ወደ ዋናው ጽሑፍ በመውሰድ በተመስጦ የጻፈው የጥንቱ ጸሐፊ ጋ እንድንጓዝ ይረዱናል።

ይህ ሐተታ፣ ፈጠን ባለ ሁኔታ፣ ተማሪ የራሱን ትርጉሞች ይመረምር ዘንድ እንዲረዳው የታሰበ ነው። ይህም ማለት ግብ ሙሉ ለሙሉ ፍጹም ነው ማለት ሳይሆን መረጃ ሰጪ እና በጥልቀት እንድናስብ የሚያነቃቃ ነው። እርግጥ ሌሎች አማራጭ ትርጉሞችም ይረዱናል፣ አስተጋቢ፣ ቀኖናዊ፣ ወይም በመሠረተ እምነት የታጠርን እንዳንሆን። ተርጓሚዎች ሰፋ ያለ የትርጉም ዳርቻዎች እና አማራጮች ያሿቸዋል፣ የጥንቶቹ ጽሑፎች የቱን ያህል አሻሚ እንደነበሩ ለመረዳት። በጣም የሚረብሸው ነገር መጽሐፍ ቅዱስ የእውነት ምንጫችን ነው የሚሉት ክርስቲያኖችም ያላቸው ስምምነት ጥቂት መሆኑ ነው።

እነዚህ መርሖዎች ብዙዎቹን ታሪካዊ ችግሮቼን እንዳሸንፍ ረድተውኛል፣ ከጥንቱ ጽሑፍ ጋር እንድተጋ በማስገደድ። እርሶንም ደግሞ እንደሚባርክዎት ተስፋ አደርጋለው።

ቦብ አትሊ
ኢስት ተክሳስ ባፕቲስት ዩኒቨርሲቲ
ሰኔ 27፣1996

## ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ፡
## የተፈተነ እውነትን በግል ለመፈለግ

እውነትን ለማወቅ እንችላለን? የት ይገኛል? ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ለማረጋገጥ እንችላለን? የመጨረሻ ወሳኝ ይኖር ይሆን? ሕይወታችንንም ሆነ ዓለማችንን ሊመሩ የሚችሉ የተሟሉ (ፍጹማን) ይኖራሉ? ለሕይወት ትርጉም አለው? እዚህ መሆናችን ለምድነው? የትስ እንሄዳለን? እነዚህ ጥያቄዎች፣ አስተዋይ ሰዎች የሚሰላሰሏቸውና ከዘመናት መጀመሪያ አንሥቶ የሰዎችን እውቀት የሚፈትሹ ናቸው (መክ. 1፡13-18፤ 3፡9-11)። የኔን ግላዊ ጥናት የማስታውሰው የሕይወቴ ዋነኛ ማዕከል አድርጌ ነው። በኢየሱስ አማኝ የሆንኩት በወጣትነት ጊዜዬ ነው፤ በቅድሚያም በዋነኛነት በሌሎች የቤተሰቤ አባላት ምስክርነት። እየጎለመስኩ ስመጣ ስለራሴም ሆነ ስለ ዓለሜ ያሉኝ ጥያቄዎች እያደጉ መጡ። ተራ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ድግግሞሾች ስለ አነበብኳቸውና ስለተረዳኋቸው የሕይወት ልምዶች፣ ትርጉም ሊሰጡ አልቻሉም። የውዥንብር ፤ የምርምር፣ የመናፈቅ እና ብዙውን ጊዜም ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ነበር፣ በምኖርበት በድን በሆነው ደንዳና ዓለም ውስጥ።

ለእነዚህ ዋነኛ ጥያቄዎች ብዙዎች ምላሽ እንዳላቸው ይናገራሉ፣ ነገር ግን ከፍተሻ እና ከማገናዘብ በኋላ የእነሱ መልሶች የተመሠረቱት (1) በግል የሕይወት ፍልስፍናዎች፣ (2) በጥንታዊ አፈ-ታሪኮች፣ (3) በግል የሕይወት ልምዶች፣ ወይም (4) በሥነልቦናዊ ቅድመ እይታዎች ላይ ነው። በማስተዋል የሆነና ስለ ዓለም ያለኝ አመለካከት መሠረት፣ የሕይወቴ ዋነኛ ማዕከል፣ የመኖሬ ዋነኛ ምክንያት ላይ ማረጋገጫ አስፈልጎኝ ነበር፣ ማስረጃ።

እነዚህን መጽሐፍ ቅዱስን ሳጠና አገኘኋቸው። ታማኝ እንዲሆንም ማስረጃ መፈለጌን ጀምሬ ያገኘሁትም፣ (1) በጥንታዊ ቅርስ ምርምር ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የተገኘው ታሪካዊ ማረጋገጫ፣ (2) የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ትክክለኛለት፣ (3) በአስራ ስድስት መቶ የመጻፍ ጊዜው ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ የመልእክት ኅብርና መኖር እና (4) ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ከተገናኙ በኂላ ፍጹም የሕይወት ለውጥ ያገኙት ሰዎች የግል ምስክርነት ናቸው። ክርስትና ኅብር እንዳለው የእምነትና የሃይማኖት ሥርዓት የሰው ልጆችን ውስብስብ ጥያቄዎች የመመለስ ችሎታ አላቸው። ይህን በማድረግም የማስተዋል ውቅር ብቻ አይሰጥም፣ ነገር ግን በፍትነታዊ ገጽታው የመጽሐፍ ቅዱስ እምነት የስሜት ደስታ እና መረጋጋትን ይሰጣል።

እንደማስበው፣ የሕይወቴን ዋነኛ ማዕከል– ክርስቶስን በቃሉ ውስጥ አግኝቼዋለሁ። በሕይወት ልምዴ ንቁ እና ስሜተ-ስሱ ነበርኩ። ቢሆንም እስካሁን ድረስ የማስታውሰው ወገግ ሊልልኝ ሲል የነበረብኝን ነውጥ እና ሥቃይ ሲሆን፣ የቱን ያህል የመጽሐፉ ትርጓሜዎች እንደሚከራከሩና፣ አልፎ አልፎም በአንድ አብያተ ክርስቲያን እና አስተምህሮዎች እንዳሉ ሳይ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን የተመስጦ መሆንና ጠቃሚነቱን ማረጋገጥ የመጨረሻው ሳይሆን የመጀመሪያው ብቻ ነው። የተለያዩ እና ተቃርኖ ያላቸውን የመጽሐፉን ከባባድ አንቀጾች ትርጓሜዎች፣ ሁሉም ትክክለኛ እና በሥልጣን ነን እያሉ እንዴት አድርጌ እንደምቀበል ወይም እንደምተው ላውቅ እችላለሁ?

ይህም ተግባር የሕይወቴ ግብ እና የእምነቴ ምናኔ ሆነ። የተረዳሁት ነገር በክርስቶስ ያለኝ እምነት፣ (1) ታላቅ ሰላምና ደስታ እንዳመጣልኝ፣ (2) የተቀናቃኝ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች (የዓለም ሃይማኖቶች) ቀኖናዊነት፤ እና (3) የአንድ ክፍለ ሃይማኖት ዕብሪተኝነት እንዳለበት ተረድቻለሁ። የጥንታዊውን ሥነ ጽሑፍ ትርጓሜ ተገቢ ዋጋ ያለው ፍለጋዬን ሳካሂድ ያስደነቀኝ ነገር ቢኖር የራሴን የግሌን ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ክፍለ ሃይማኖታዊ እና በሕይወት ልምድ አድልኦዎች መለየት ነው። የራሴን አመለካከት ለማጠናከር መጽሐፍ ቅዱስን እንደዋዛ አዘውትሬ አነባለሁ። የራሴን ያልተሟላ ዋስትናና የብቃት ማነስ ሲያመላክተኝ ሌሎችን የማጠቃበት ቀኖናዊ ምንጭ አድርጌ እወስደዋለሁ። ይህንን ሀቅ መረዳት ለእኔ የቱን ያህል አስቸጋሪ ነበር!

ምንም እንኳ የተሟላ ተጨባጭነት ባይኖረኝም የመጽሐፍ ቅዱስ ደኅና አንባቢ ለመሆን እችላለሁ። ያሉብኝን አድሏዊነቶች ለመለየትና እንዳሉም እውቅና በመስጠት የተወሰኑ ላደርጋቸው እችላለሁ። ከእነሱ ገና አሁንም ነጻ አይደለሁም፣ ነገር ግን ከራሴ ድክመት ተሟግቻለሁ። ተርጓሚ ዘወትር የመልካም መጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ጠላት እንደሆነ ነው!

እስቲ ጥቂት ቅድመ ግምቶችን፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቴ ያገኘኋቸውን እርሶ አንባቢው ከእኔ ጋር ሆነው ይመረምሯቸው ዘንድ ልዘርዝራቸው፡

I. **ቅድመ ግምቶች**

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ተመስጧዊ የሆነ የእውነተኛው አምላክ የራሱ መገለጥ መሆኑን አምናለሁ። ስለሆነም፣ መተርጎም ያለበት በዋነኛው መነሻ ብርሃን መለኮታዊ ጸሐፊ (መንፈስ) ሆኖ በተወሰነ ታሪካዊ ወቅት በነበረ ሰው ጸሐፊነት ነው።

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ለተራ ሰዎች፣ ለሁሉም ሰዎች እንደተጻፈ አምናለሁ! እግዚአብሔር ለእኛ በግልጽ ለመናገር በታሪካዊና በባህላዊ አግባብ ራሱን አዘጋጅቶልናል። እግዚአብሔር እውነትን አይሸሽግም– እንድንረዳው ይፈልጋል! ስለሆነም በእኛ ሳይሆን በራሱ ጊዜ ብርሃን የግድ መተርጎም አለበት። መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ ከሰሙት ወይም ካነበቡት በተለየ መንገድ የምንረዳው ማለት አይደለም። በተራ ሰው ልቦና ሊረዱት የሚችል እና ተገቢ የሆነ የሰው ልጆች መግባቢያ አግባቦችና ስልቶችን የሚጠቀም ነው።

ሐ. መጽሐፍ ቅዱስ ኅብር ያለው መልእክትና ተግባር እንዳለው አምናለሁ። ምንም እንኳ አያአዎአዊ የሆኑ አንቀጾች ቢኖሩትም ራሱን በራሱ አይቃረንም። ስለሆነም፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ዋነኛው ተርጓሚ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ነው።

መ. እያንዳንዱ አንቀጽ (ትንቢታትን ጨምሮ) አንድ እና አንድ ብቻ ትርጉም እንዳላቸውና ይህም በዓይነተኛው ተመስጧዊ ጸሐፊ መነሻ ሐሳብ መሆኑን አምናለሁ። ምንም እንኳ ፍጹም ርግጠኞች ባንሆንም የዓይነተኛውን ጸሐፊ ሐሳብ እንረዳዋለን፣ ብዙ ጠቋሚዎች አቅጣጫውን ስለሚያመላክቱን፡

1. የዘውግ (የሥነ ጽሑፋዊ) ዓይነቱ፣ መልእክቱን ለማስተላለፍ የተፈለገበት
2. ጽሑፉ ሊያወጣ የፈለገው እውነት ታሪካዊ ዳራ እና /ወይም የተለየ ዐውድ
3. የአጠቃላይ የመጽሐፉ ሥነ ጽሐፋዊ ሁኔታ እና እንዲሁም የእያንዳንዱ የጽሑፍ አሀድ
4. ጽሑፋዊ ንድፉ (ዋና ዋና ይዘቱ) ማለትም የእያንዳንዱ ጽሑፍ አሀድ ከአጠቃላይ መልእክቱ ጋር ያለው ዝምድና
5. መልእክቱን ለማስተላለፍ የተጠቀመበት የተለየ ሰዋሰዋዊ ባሕርይ
6. መልእክቱን ለማቅረብ የተመረጡት ቃላት
7. ትይዩ አንቀጾች

በእነዚህ በእያንዳንዳቸው አካባቢ የሚደረገው ጥናት በአንቀጽ ላይ የምናደርገው ጥናት ዓላማ ሆኗል። ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚሆነውን የእኔን ዘዴ ከመግለጤ በፊት ጥቂት ተገቢ ያልሆኑ በአሁን ጊዜ ጥቅም ላይ በመዋል ላይ ያሉትንና በርካታ የተለያዩ ትርጉሞች እንዲፈጠሩ ያደረጉትና የግድ መወገድ ያለባቸውን ላመላክት፡

## II. ተገቢ ያልሆኑ ዘዴዎች

ሀ. የመጽሐፍ ቅዱስን መጻሕፍት ሥነጽሑፋዊ ዐውድ ችላ በማለት እያንዳንዱን ዓረፍተ ነገር፣ ሐረግ እንዲያውም ግለሰባዊ ቃላትን እንደ እውነታዊ መግለጫ፣ ከጸሐፊው ዓላማ ባልተገናኘ መልኩ ወይም ከሰፊው የጽሑፉ ክፍል ጋር ባልተያያዘ ሁኔታ መውሰድ። ይህም ዘወትር "የጽሑፍ ማጣራት" ይባላል።


ለ. የመጻሕፍቱን ታሪካዊ ዐውድ ችላ በማለት እና በግምታዊ ታሪካዊ ዳራ በመቀየር ከጽሑፉ ጋር መጠነኛ ግንኙነት ወይም ምንም ዓይነት ድጋፍ በሌላቸው ጋር ማያያዝ

ሐ. የመጻሕፍቱን ታሪካዊ ዐውድ ችላ በማለት እንደ አካባቢያዊ የጧት ጋዜጣ ዓይነት ቀድኖውኑ ለዘመናዊ ክርስቲያን እንደተጻፈ ዓይነት ማንበብ


መ. የመጻሕፍቱን ታሪካዊ ዐውድ ችላ በማለት ለጽሑፉ ተምሳሌታዊ ፍቺ በመስጠት ፍልስፍናዊ/ሥነ-መለኮታዊ በማድረግ በመጀመሪያ ቃሉን ከሰሙት እና ዋናው ጸሐፊ ሊል ከፈለገው ሐሳብ በማይገናኝ መልኩ መያዝ

ሠ. ዋነኛውን መልእክት ችላ በማለትና የራስን የሥነ-መለኮት ሥርዓት፣ አባባይ መሠረተ- እምነት፣ ወይም የወቅቱን ጉዳይ በመቀየር፣ እና ከማይገናኝ ጋር በማያያዝና፣ ዋናው ጸሐፊ ሊል ከፈለገው ቁምነገርና ከተቀመጠው መልእክት መውጣት። ይህ የአካሄድ ክስተትም ዘወትር የሚደረገው የተናጋዊውን ሐሳብ ለማጠናከር በቅድሚያ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማንበብን ነው። ይህን ዘወትር፣ "የአንባቢ ምላሽ" ("ጽሑፉ ለእኔ የሚሰጠኝ" ትርጉም ተብሎ ይታወቃል።

በሰዎች የጽሑፍ መግባቢያ ላይ ቢያንስ ሦስት አካላት ያስፈልጋሉ፡




ቀደም ሲል የተለያዩ የምንባብ ስልቶች ከሦስቱ በአንደኛው ክፍሎች አተኩረው ነበር። ነገር ግን በእውነት ለማጽናት ልዩ የሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ ተመስጦ የተሻሻለው ንድፍ ይበልጥ ተገቢነት አለው።



እንደ እውነቱ ሦስቱም አካሎች በትርጓሜ ሂደት የግድ መካተት ይኖርባቸዋል። ለማረጋገጥ ያህልም የእኔ ትርጓሜ ያተኮረው በቀዳሚዎቹ በሁለቱ አካላት ላይ ነው፡ ዋነኛው ጸሐፊ እና ጽሑፉ። ምናልባት የእኔ ተቃርኖ ባስተዋልኩት ተገቢ ያልሆነ ሁኔታ ላይ ይሆናል። (1) ተምሳሌታዊ ወይም መንፈሳዊ በተደረጉ ጽሑፎች እና (2) "የአንባቢ ምላሽ" (ለእኔ የሚረዳኝ) ትርጓሜዎች። በዛባት በሁሉም ደረጃ ላይ ሊከሰት ይችላል። ዘወትር የእኛን መሻት፣ አድሏዊነት፣ አግባብ፣ እና አፈጻጸማችንን መመርመር ይኖርብናል። ምንም ዓይነት ወሰኖች ለትርጉሞች በሌሉበትኝ፣ ገደብና መስፈርት በሌለበት እንዴት አድርገን መፈተሽ እንችላለን? ለዚህ ነው የጸሐፊው መነሻ ሐሳብና የጽሑፉ አወቃቀር የተወሰኑ መስፈርቶችን ሰጥቶኝ ዳራውን ለመወሰንና ተገቢ የሆነ ይሁንታ ያለው ትርጓሜ እንዳደርግ ያስቻለኝ።

በእነዚህም ተገቢ ባልሆኑ ስልቶች ጭላንጭል ምን ዓይነት ታሳቢ አግባቦች ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ እና ትርጓሜ በተረጋገጠ ደረጃ የሚያመጡ እና ቋሚነት ያላቸው ሊኖሩ ይችላሉ?

## III. ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ተገቢ አገባቦች

በዚህ ነጥብ የተወሰኑ የትርጓሜ ዘውጎችን የተለዩ ስልቶችን አላብራራም፤ ነገር ግን ለሁሉም ዓይነት የቅዱሳን መጻሕፍት አጠቃላይ የጽሑፍ ትርጓሜ ተገቢ መርሖዎች ላይ ነው። ለተወሰነ ዘውጋዊ አግባብ መልካም የሆነው መጽሐፍ፣ መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ ጠቀሜታው እንዴት እንደሚነበብ፣ በጎርዶን ፊ እና ዳግላስ ስቱአርት፣ በዞንደርቫን የታተመው ነው።

የኔ ዘዴ በመነሻው ያተኮረው አንባቢ ለመንፈስ ቅዱስ መጽሐፍ ቅዱስን ያበራላቸው ዘንድ ሲፈቅዱ የሚያልፉባቸውን አራት የግል የንባብ ዑደቶችን ነው። ይህም መንፈስን፣ ጽሑፉን እና አንባቢውን ቀዳሚ ያደርጋቸዋል፣ ተከታይ ሳይሆን። ይህም ደግሞ አንባቢው በተንታኞች ሐሳብ አለቅጥ እንዳይወሰድ ያደርገዋል። ሲባል የሰማሁትም፣ "መጽሐፍ ቅዱስ እጅግ ብርሃን በሐተታዎች ላይ ያበራል" የሚል ነው። ይህም ማለት ግን የጥናት መርጃዎችን ለማንኳሰስ አይደለም፣ ነገር ግን ለአጠቃቀማቸው ተገቢ ጊዜ ማስፈለጉን ለማመላከት ነው እንጂ።

ትርጓሜዎቻችንን ከቃሉ ከራሱ ለማስደገፍ መቻል ይኖርብናል። አምስቱ አካባቢዎች ምናልባት የተወሰኑ የእውነት ማረጋገጫ ይሰጡናል፡

1. የዋናው ጸሐፊ
   ሀ. ታሪካዊ መቼት
   ለ. ሥነ-ጽሑፋዊ ዐውድ
2. የዋናው ጸሐፊ ምርጫ
   ሀ. ሰዋሰዋዊ መዋቅር (አገባብ)
   ለ. የተመሳሳይ ሥራዎች አጠቃቀም
   ሐ. የጽሑፍ ዓይነት (ዘውግ)
3. የእኛ ተገቢ የሆነውን የመረዳት ችሎታ
   ሀ. ጠቃሚ ትይዩ አንቀጾች

ከትርጓሜአችን ጀርባ ምክንያቶችንና አመክኖዎችን (ሎጂክ) ማሳየት መቻል አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ ብቸኛው የእምነትና የድርጊት ምንጫችን ነው። ቢያሳዝን መልኩ፣ ክርስቲያኖች በሚያስተምረው ወይም በሚያጸናው ላይ ዘወትር አይስማሙም። ይህም መጽሐፍ ቅዱስ ተመስጧዊ መሆኑን ተቀብሎ ከዚያም አማኞች ለሚያስተምረውም ሆነ ለሚጠይቀው ላለመስማማት መቻል በራስ እንደመሸነፍ ነው!

አራቱ የንባብ ዑደቶች የተነደፉት የሚከተለውን ጠለቅ ያለ ትርጓሜ ለመስጠት ነው።

ሀ. የመጀመሪያው የንባብ ዑደት

1. መጽሐፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ ያንብቡት። ከተለያዩ የትርጉም ንድፈ ሐሳቦች አገኛለሁ ብለው ተስፋ በማድረግ በድጋሚ በተለያዩ ትርጉሞች ያንብቡት
   ሀ. ቃል በቃል (አኪጀት፣ አአሰመቅ፣ አየተመት)
   ለ. ንቁ ቀጥተኛ (የአእቅ፣ ኢመቅ)
   ሐ. ማብራሪያ (ሕያው ቃል፣ የተብራራ መጽሐፍ ቅዱስ)
2. የሙሉ ንባቡን ማዕከላዊ ሐሳብ ይፈልጉ። ጭብጡን ይግለጡት።
3. የጽሑፋዊ አህዱን (ከተቻለ) ይለዩት፤ ምዕራፍ፣ አንቀጽ ወይም ዓረፍተ ነገር በትክክል ሊያብራራ የሚችለውን፣ የጭብጡን ማዕከላዊ ሐሳብ ለማግኘት።
4. ዋነኛውን ገፀ የሥነ-ጽሑፋዊ ጭብጥ ዘውግ (ዓይነት) ይግለጡት
   ሀ. ብሉይ ኪዳን
      (1) ይዕብራይስጥ ትረካ
      (2) የዕብራይስጥ ቅኔ (መጽሐፈ- ጥበብ፣ መዝሙራት)
      (3) የዕብራይስጥ ትንቢት (ስድ ንባብ፣ ቅኔ)
      (4) ሕግጋት
   ለ. አዲስ ኪዳን
      (1) ተራኪ (ወንጌላት፣ ግብረ-ሐዋርያት)
      (2) ምሳሌዎች (ወንጌላት)

(3) ደብዳቤዎች/መልዕክቶች
(4) ትንቢታዊ ሥነ-ጽሑፍ

ለ. ሁለተኛው የንባብ ዑደት

1. ሙሉ መጽሐፉን እንዳለ በድጋሚ ያንብቡት፣ ዋናውን ርልሰ-ጉዳይ፣ ቁም-ነገሮች ለመለየት ፈልጉ
2. ዋናዎቹን ርዕሶች በዋና ሐሳብ ለይተው አጠር ባለ እና በቀላል መግለጫ ይዘቱን ያስቀምጡ
3. የድርጊት መግለጫውን ይፈትሹና ሰፋ ያለ የርዕሰ ጉዳይ ዝርዝር በጥናት መርጃ ይጠቀሙ

ሐ. ሦስተኛው የንባብ ዑደት

1. ሙሉ መጽሐፉን በድጋሚ ያንብቡት፣ ለጽሑፉ ታሪካዊ መቼትና የተለየ ዐውድ ለማግኘትና ለመለየት ከራሱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይሞክሩ.
2. በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱትን ታሪካዊ ዓይነቶች ይዘርዝሩ
   ሀ. ጸሐፊው
   ለ. ዘመኑ
   ሐ. ተቀባዮች
   መ. ለመጻፍ የተለየ ምክንያት
   ሠ. ከመጽሐፉ ዓላማ ጋር የተያያዙ ባህላዊ መቼቶች ገጽታ
   ረ. ከታሪካዊ ሰዎችና ሁነቶች የሚጠቀሱ
3. የምትተረጉመውን ያንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የዋና ፍሬ ሐሳቡን ዝርዝር ወደ አንቀጽ ደረጃ አስፋፉት። ዘወትር የሥነ ጽሑፉን አሀድ ለዩት፣ እንዲሁም የፍሬ ሐሳቡን ዝርዝር አውጡ። ይህም ምናልባት በርካታ ምዕራፎች ወይም አንቀጾች ይሆናል። ይህም የዋናውን ጸሐፊ የሐሳብ ተገቢነት (ሎጂክ) ጽሑፋዊ ንድፍ ለመከተል ያስችልዎታል።
4. የጥናት መረጃዎችን በመጠቀም የርሶን ታሪካዊ መቼት ይፈትሹ።

መ. አራተኛው የንባብ ዑደት

1. የተለየውን የጽሑፍ ክፍል በልዩ ልዩ ትርጉሞች ያንብቡት
   ሀ. ቃል በቃል (አኪጀት፣ አአሰመቅ፣ አየተመት)
   ለ. ንቁ አቻ (የአእቅ፣ ኢመቅ)
   ሐ. ማብራሪያ (ሕያው ቃል፣ የተብራራ መጽሐፍ ቅዱስ)
2. ሥነ-ጽሑፋዊ ወይም ሰዋሰዋዊ መዋቅሮችን ይፈልጉ
   ሀ. ተደጋጋሚ ሐረጎች፣ ኤፌ. 1፡6፣12፣13
   ለ. ተደጋጋሚ ሰዋሰዋዊ መዋቅሮች፣ ሮሜ. 8፡31
   ሐ. ተጻጻራሪ ጽንሰ-ሐሳቦች
3. የሚከተሉትን ዓይነቶች ይመዝግቡ
   ሀ. ወሳኝ ቃላት
   ለ. ያልተለመዱ ቃላት
   ሐ. ዋነኞቹ ሰዋሰዋዊ መዋቅሮች
   መ. የተለዩ አስቸጋሪ ቃላት፣ ሐረጎች፣ እና ዓረፍተ ነገሮች
4. ዋነኞቹን ትይዩ አንቀጾች ይለዩ
   ሀ. ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር በጣም ግልጽ የሆነውን የማስተማሪያ አንቀጽ ይፈልጉ
      (1) "ስልታዊ ሥነ-መለኮት" መጻሕፍት
      (2) የማጣቀሻ መጽሐፍ ቅዱስ
      (3) የቃላት ዝርዝር
   ለ. በርዕሰ ሐሳብህ ዙሪያ ተስማሚ አያዎአዊ ጥንዶችን ከጽሑፉ ይፈልጉ። አብዛኞቹ የቅዱሳት መጻሕፍት እውነታዎች የሚቀርቡት በአከራካሪ ጥንዶች ነው፤ በርካታ የመሠረተ እምነት ግጭቶች የሚመነጩት ከጽሑፍ አቃቂር ማውጣት ማለትም ከፊል ከሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ክርክሮች ነው። መላው መጽሐፍ ቅዱስ ተመስጧዊ ነው፣ እኛም የተሟላውን መልዕክት በመፈለግ፣ የመጽሐፍ ቅዱስን ሚዛን በትርጓሜአችን መጠበቅ ይኖርብናል።
   ሐ. በዛው በመጽሐፉ ውስጥ ፣ በዛው ጸሐፊ ወይም በዛው የሥነ ጽሐሁፍ ዓይነት፣ አቻዊ ትይዩ ይፈልጉ፤ መጽሐፍ ቅዱስ የራሱ ምርጥ ተርጓሚ ነው፤ ምክንያቱም፣ አንድ ብቸኛ ጸሐፊ ስላለው– መንፈስ ቅዱስ።
5. ታሪካዊ መቼቱንና የተለየ ዐውዱን ለመፈተሽና ለማስተዋል የጥናት መረጃዎችን ይጠቀሙ።
   ሀ. የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ
   ለ. የመጽሐፍ ቅዱስ ዐውደ-ጥበባት፣ መምሪያ መጻሕፍ እና መዝገበ ቃላት
   ሐ. የመጽሐፍ ቅዱስ መግቢያዎች
   መ. የመጽሐፍ ቅዱስ ሐተታዎች (በዚህ ነጥብ ላይ በጥናትዎ፣ አማኝ የኅብረተሰብ ክፍሎችን፣ ማለትም የቀደምቱም ሆኑ ያሁኖቹ የራስዎን ጥናት ለማገዝና ለማረም ይጠቀሙባቸው።)

## IV. የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ አተገባበር

በዚህ ነጥብ ወደ አተገባበር እንቃኛለን። ጽሑፉን ከዋናው መቼት አንጻር ለመረዳት ጊዜ ወስደዋል፤ አሁን ደግሞ ይሄንኑ በሕይወትዎ፣ በባህልዎ ሊተገብሩት ይገባል። የመጽሐፍ ቅዱስ የመረዳት ሥልጣን ማለት በእኔ አገላለጽ፣ "ዋናው የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊ በእሱ ጊዜ ሊለው የፈለገውን መረዳትና ያንን በራሳችን ጊዜ መተርበር" ማለት ነው።

ድርጊት መከተል ያለበት የዋናውን ጸሐፊ የትርጓሜ ሐሳብ በጊዜም ሆነ በሎጂክ አኳያ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን አንቀጽ በጊዜው ምን ለማለት እንደፈለገ እስካላወቅን ድረስ በዘመናችን ልንተገብረው አንችልም! የመጽሐፍ ቅዱስ አንቀጽ ሊለው ያልፈለገውን ፈጽሞ ሊሆን አይችልም!

የእርስዎ የተዘረዘረ የዋና ሐሳቦች ዝርዝር በአንቀጽ ደረጃ (የንባብ ዑደት ቁጥር 3)፣ የእርስዎ መመሪያ ይሆናል። ትግበራ መደረግ ያለበት በአንቀጽ ደረጃ እንጂ በቃላት ደረጃ መሆን የለበትም። ቃላት ትርጉም የሚኖራቸው በከፊለ-ጽሑፍ ደረጃ ነው፤ ሐረጎች ትርጉም የሚኖራቸው በከፊለ- ጽሑፍ ደረጃ ነው፤ ዓረፍተ ነገሮች ትርጉም የሚኖራቸው በከፊለ- ጽሑፍ ደረጃ ነው። ብቸኛው ተመስጧዊ ሰው በትርጓሜው ሂደት ውስጥ ዋነኛ ጸሐፊው ነው። በመንፈስ ቅዱስ አብራሪነት (ማብራሪያ) የእሱን ምሪት ብቻ መከተል ይኖርብናል። ማብራሪያ ግን ተመስጦ ማለት አይደለም። "እግዚአብሔር እንደዚህ ይላል፣" ለማለት ከዋናው ጸሐፊ ሐሳብ ጋር የግድ መኖር አለበት። ትግበራ በተለይ መያያዝ ያለበት በሙሉ መጽሐፉ ሐሳብ ላይ ሲሆን፣ የተለየው የጽሑፍ አሀድ እና በአንቀጽ ደረጃ እያደገ በሚሄድ መልኩ።

የዘመናችን ጉዳዮች መጽሐፍ ቅዱስን እንዲተረጉሙ አትፍቀዱ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገር! ይህ ምናልባት የተወሰኑ ከጽሑፉ እንድናወጣ ይጠይቀን ይሆናል። ይህም ተገቢ የሚሆነው ጽሑፉ ለመርሖቹ ድጋፍ ሲሆን ነው። በሚያሳዝን መልኩ ግን፣ ብዙውን ጊዜ የእኛ መርሖዎች፣ "የእኛ" መርሖዎች ናቸው— የጽሑፉ መርሕ በመሆን ፈንታ።

መጽሐፍ ቅዱስን ለመተግበር፣ (ከትንቢት ብቻ በቀር) ማስታወስ የሚገባን ጠቃሚ ነገር ለእያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አንድና አንድ ብቻ ትርጉም እንዳለው ነው። ያም ትርጉም ግንኙነቱ ከዋናው ጸሐፊ ሐሳብ ጋር፣ እሱም የዘመኑን ውድቀትም ሆነ ፍላጎት እንዴት እንዳቀረበው ነው። በርካታ ተስማሚ ድርጊቶች ከዚህ ከአንዱ ትርጉም ሊመነጩ ይችላሉ። አተገባበሩም የሚመሠረተው በተቀባዮቹ መሻት ላይ ሆኖ፣ መገናኘት ያለበት ግን ከዋናው ጸሐፊ ሐሳብ ላይ ነው።

## V. የትርጓሜ መንፈሳዊ ገጽታዎች

እስካሁን አመክኖአዊ የሆነ እና የሥነ ጽሑፋዊ ሂደት በምን መልኩ በትርጉምና በአተገባበር ላይ መሆን እንዳለበት ለማብራራት ሞክሬአለሁ። አሁን ደግሞ ስለ ትርጉም መንፈሳዊ ገጽታ በአጭሩ ላብራራ። የሚከተሉት የመቆጣጠሪያ ዝርዝሮች ረድተውኛል፡

ሀ. ለመንፈስ ርዳታ ይጸልዩ (1ኛ ቆሮ. 1:26-2:16)።

ለ. ከሚታወቅ ኃጢአት በግልዎ ምሕረትንና መንጻትን እንዲያገኙ ይጸልዩ (1ኛ ዮሐንስ 1:9)።

ሐ. ስለ እግዚአብሔር ለማወቅ ከፍተኛ ፍላጎት እንዲያድርብዎ ይጸልዩ (መዝ. 19:7-14፤ 42:1፤ 119:1)።

መ. አዲስ ማስተዋልን በሕይወትዎ ወዲያውኑ ይተግብሩ።

ሠ. ትሑትና ለመማር የተዘጋጁ ይሁኑ።

በሎጂካዊ ሂደት እና በመንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ መሪነት መካከል ያለውን ሚዛን ለመጠበቅ በጣም አዳጋች ነው። የሁለቱን ሚዛን ለመጠበቅ የሚከተሉት ጥቅሶች ረድተውኛል፡

ሀ. ከ ጀምስ ደብሊዩ. ሲር፣ *ቃሉን መጠምዘዝ (ማጣመም)* ገጽ 17-18

> "ማብራሪያ የሚመጣው ወደ እግዚአብሔር ሕዝቦች ሐሳብ ነው— ወደ መንፈሳዊ ምሑር ሳይሆን። በመጽሐፍ ቅዱስ ክርስትና የተለየ የመማሪያ ክፍል የለም፣ ምንም የተለየ የሚያብራራ፣ ተገቢው ትርጓሜ የሚመጣላቸው የተለዩ ሰዎች የሉም። እና ስለዚህ፣ መንፈስ ቅዱስ ልዩ የጥበብ፣ የእውቀት፣ እና መንፈስን የመለየት ጸጋ ሲሰጥ፣ እነዚህ ባለጸጋ ክርስቲያኖች ብቻ የቃሉ ሥልጣናዊ ተርጓሚዎች እንዲሆኑ መመደቡ አይደለም። ሁሉም የራሱ ሕዝቦች ሊማሩ፣ ሊዳኙ እና ሊለዩ፣ በእነሱ፣ እግዚአብሔር የተለየ ችሎታ ለሰጣቸው እንኳ ሥልጣን ያለውን መጽሐፍ ቅዱስ መጥቀስ እንደሚችሉ ነው። ለማጠቃለል፣ በሙሉው መጽሐፍ ያቀረብኩት ሐሳቤ መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛው የእግዚአብሔር መገለጥ ለሰው ልጆች ሁሉ ነው፣ በሚናገረው ሁሉ የመጨረሻው ባለሥልጣን ነው፤ በጥቅሉ ምሥጢራዊ ሳይሆን በማንኛው ባህል ባሉ ተራ ሰዎች በበቂ መልኩ ለመረዳት የሚቻል ነው።"

ለ. በኬርክጋርድ፣ በቤርናንድ ራም በሚገኘው፣ የፕሮቴስታንት የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ፣ ገጽ 75፡

> እንደ ኬርክጋርድ ከሆነ ሰዋሰዋዊ፣ ቃላዊ፣ እና ታሪካዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች አስፈላጊ ናቸው፤ መቅደም ያለበት ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ልባዊ ንባብ ነው። "መጽሐፍ ቅዱስን እንደ እግዚአብሔር ቃል ለማንበብ፣ ማንም አፍ ከልብ ሆኖ፣ በተጠንቀቅ ሆኖ፣ በጉጉትና ተስፋ በማድረግ፣ ከእግዚአብሔር ጋር እየተነጋገረ ማንበብ አለበት። መጽሐፍ ቅዱስን በሐሳበ ቢስነት ወይም በግዴለሽነት ወይም እንደ ትምህርት ወይም እንደ ልዩ ሞያ ማንበብ መጽሐፍ ቅዱስን እንደ እግዚአብሔር ቃል ማንበብ አይደለም። አንዱ የፍቅር ደብዳቤ እንደሚነበብ የሚያነበው ከሆነ እሱ እንደ እግዚአብሔር ቃል እያነበበው ነው።"

ሐ. ኤች. ኤች. ሮውሊ *በየመጽሐፍ ቅዱስ ጠቀሜታ*፣ ገጽ 19፡

> "የተሻለ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሑራዊ መረዳት፣ ምንም ያህል ፍጹም ቢሆን ሁሉንም ሀብቶች ሊያስገኝ አይችልም። ይህን መሰሉን መረዳት ዝቅ ለማድረግ አይደለም፣ ለፍጹም መረዳት አስፈላጊ ነው። ነገር ግን ፍጹም ይሆን ዘንድ ወደ መጽሐፉ መንፈሳዊ ሀብቶች የሚያመራ መንፈሳዊ መረዳት ማስፈለጉን ለማሳየት ነው። እናም

ለዛ መንፈሳዊ መረዳት ከምሑራዊ ንቁነት የተሻለ ነገር ያስፈልጋል። መንፈሳዊ ነገሮች በመንፈሳዊነት የሚለዩ ናቸው፤ እናም የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ የመንፈሳዊ ተቀባይነት አዝማሚያ ሊኖረው ይገባል፣ ራሱን ይሰጥ ዘንድ እግዚአብሔርን ለመፈለግ ጉጉት ያለው፣ ከሳይንሳዊ ጥናቱ ባሻገር ወደ ተትረፈረፈ ሀብት ወራሽነት ወደሚያስገኝ ወደዚህ ከመጻሕፍት ሁሉ ታላቅ ወደ ሆነ።"

VI. የሐተታው ዘዴ

የጥናት መመሪያ ሐተታው የተሰናዳው የእርስዎን የትርጉም አግባብ በሚከተሉት መንገዶች ለማገዝ ነው፡

ሀ. እያንዳንዱን መጽሐፍ የሚያስተዋውቅ አጭር ታሪካዊ የዋና ሐሳብ መግለጫ። "የንባብ ዑደት ቁጥር 3" ካነበበ በኋላ ይህን መረጃ ያረጋግጡት።

ለ. ጽሑፋዊ ማብራሪያዎች በየአንዳንዱ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ ይገኛል። ይህም ሥነ ጽሑፋዊ አሀዱ እንዴት እንደተዋቀረ ለመመልከት ይረዳል።

ሐ. በእያንዳንዱ ምዕራፍ ወይም ሥነ ጽሑፋዊ አሀድ፣ የአንቀጽ ክፍሎች እና መግለጫ ጽሑፎች ከተለያዩ በርካታ ዘመናዊ ትርጉሞች ተሰጥተዋል፡

1. የመጽሐፍ ቅዱስ ኅብረት ሶሳይቲ የግሪክ ጽሑፍ፣ አራተኛ እትም (የተመቅሶ)
2. አዲሱ የአሜሪካ መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ፣ 1995 የተሻሻለ (አአመመቅ)
3. አዲሱ ኪንግ ጀምስ ዕትም (አኪጀዕ)
4. አዲሱ የተከለሰው መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ (አየመመቅ)
5. አዲሱ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ (አእመቅ)
6. ኢየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ (ኢመቅ)

የአንቀጽ ክፍሎች ተመስጧዊ አይደሉም። ከጽሑፉ መረጋገጥ ይኖርባቸዋል። ከተለያዩ የትርጉም ንድፈ ሐሳቦች እና ሥነመለኮታዊ አስተሳሰቦች የተለያዩ ዘመናዊ ትርጉሞችን በማወዳደር የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን ለመተንተን እንችላለን። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድ ዋነኛ እውነት ይዟል። ይህም "መሪ ዓረፍተ ነገር" ወይም "የጽሑፉ ማዕከላዊ ሐሳብ" ተብሎ ይጠራል። ይህም ኅብር ያለው ሐሳብ አግባብነት ላለው ታሪካዊ፣ ሰዋሰዋዊ ትርጉም ቁልፉ ነው። ማንም ከአንድ አንቀጽ ባነሰ መተርጎም፣ መስበክ ወይም ማስተማር አይኖርበትም! በተጨማሪም እያንዳንዱ አንቀጽ ከአካባቢው አንቀጾች ጋር እንደሚዛመድ አስታውሱ። ለዚህ ነው በአንቀጽ ደረጃ ያለ የዋና ሐሳቦች ዝርዝር ለሙሉ መጽሐፉ በጣም አስፈላጊ የሆነው። በዋናው ተመስጧዊ ጸሐፊ የተገለጠውን ርዕሰ ጉዳይ አመክኖአዊ ፍሰት መከተል መቻል ይኖርብናል።

መ. የቦብ ማስታወሻዎች በትርጓሜ የሚከተሉት ቁጥር በቁጥር የሆነውን አግባብ ነው። ይህም የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ እንድንከተል ያስገድደናል። ማስታወሻዎቹ ከብዙ አካባቢዎች መረጃዎችን ይሰጡናል።

1. ሥነ ጽሑፋዊ ተጓዳኝ ጽሑፍ
2. ታሪካዊ፣ ባህላዊ መረዳቶች
3. ሰዋሰዋዊ መረጃ
4. የቃላት ጥናቶች
5. ጠቃሚ ትይዩ አንቀጾች

ሠ. በተወሰኑ ነጥቦች በሐተታው ውስጥ፣ አዲሱ የአሜሪካን መደበኛ ትርጉም (በ1995 የተሻሻለ) የኅትመት ጽሑፍ፣ ከሌሎች በርካታ ዘመናዊ ትርጉሞች በደጋፊነት ይኖራሉ፡

1. አዲሱ የኪንግ ጀምስ ቅጂ (አኪጀቅ)፣ የጽሑፋዊ እጅ ጽሑፎችን ማለት "ቴክስተስ ሪሴፕተስ" የሚከተል ነው።
2. አዲሱ የተከለሰው መደበኛ ቅጂ (አየተመቅ)፣ ማለትም ቃል በቃል የሆነ ትርጉም ሲሆን፣ እሱም የተከለሰው መደበኛ ትርጉም ከቤተክርስቲያን ብሔራዊ ምክር ቤት ነው።
3. የጊዜው እንግሊዝኛ ትርጉም (የጊእት)፣ ከአሜሪካን የመጽሐፍ ቅዱስ ሶሳይቲ የተሻሻለ አቻ ትርጉም ነው።
4. የኢየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ (ኢመቅ)፣ ከፈረንሳይ ካቶሊክ የተሻሻለ አቻ ትርጉም ላይ የተመሠረተ የእንግሊዝኛ ትርጉም ነው።

ረ. ግሪክኛን ለማያነቡ፣ ተነጻጻሪ እንግሊዝኛ ትርጉሞች በጽሑፉ ውስጥ ያሉትን አስቸጋሪ ክፍሎች ለመረዳት ይጠቅማሉ፡

1. የእጅ ጽሑፍ ልዩነቶች
2. አማራጭ የቃላት ፍቺዎች
3. ሰዋሰዋዊ አስቸጋሪ ጽሑፎችና አወቃቀሮች
4. አሻሚ ጽሑፎች

የእንግሊዝኛ ትርጉም እነዚህን ችግሮች ባያቃልልም እንኳ፣ ጠለቅ እና ውስጣዊ የሆነ ጥናት ይደረግ ዘንድ ዒላማና ስፍራውን ያሳያሉ።

ሰ. በእያንዳንዱ ምዕራፍ መዝጊያ ላይ ጠቃሚ የውይይት ጥያቄዎች ተሰጥተዋል፣ እነዚህም የምዕራፉን ዋነኞቹን የትርጓሜ ጉዳዮች ዒላማ ለማድረግ የሚሞክሩ።

# የዮሐንስ ወንጌል መግቢያ

**መክፈቻ ቃል**

ሀ. የማቴዎስ እና የሉቃስ ወንጌላት የሚጀምሩት ከኢየሱስ መወለድ ሲሆን፤ ማርቆስ የሚጀምረው ከእርሱ ጥምቀት ነው፤ ነገር ግን ዮሐንስ የሚጀምረው ከፍጥረት በፊት ካለ ነገር ነው።

ለ. ዮሐንስ ከመጽሐፉ የመጀመሪያው ምዕራፍ የመጀመሪያው ቁጥር አንስቶ የናዝሬቱ የኢየሱስን አምላክ መሆን ሲገልጽ ይህንን ሃሳብ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ከፍተኛ አጽኖት ሰጥቶታል። በተመሳሳይ ወንጌል ውስጥ ይህ እውነት እስከ መጨረሻዎቹ ምዕራፎች ድርስ ተሸፍኖ ቆይቷል። ("የመሢሑ ምስጢር")

ሐ. ዮሐንስ ተመሳሳይ ወንጌላት በተቀበሉት መሠረታዊ ሀሳቦች ላይ ተመርኩዞ ወንጌሉን ጽፏል። በቀደምት ቤተ ክርስቲያ (በመጀመሪያው ምዕተ አመት መጨረሻ አካባቢ) ፍላጎት ላይ በመመሥረት የኢየሱስን ሕይወት እና አስተምህሮ ተርጉሞ አቅርቧል።

መ. ዮሐንስ ስለ መሲሑ ስለ ኢየሱስ የጻፈው ጽሑፍ የሚያጠነጥነው ከዚህ በታች በተጠቀሱ ነገሮች ዙሪያ ላይ ነው።

1. ሰባቱ ተአምራት/ምልክቶች እና እነርሱ ትርጓሜአቸው
2. ሃያ ሰባት ቃለ መጠይቆች እና/ወይም ከግለሰቦች ጋር የተደረገ ውይይት
3. የተወሰኑ አምልኮዎች እና የበአላት ቀናት
   - ሀ. ሰንበት
   - ለ. የፋሲካ በዓል (ምዕራፍ 5-6 ያለውን ይመልከቱ።)
   - ሐ. የድንኳን በዓል (ምዕራፍ 7-10 ያለውን ይመልከቱ።)
   - መ. ሃኑካ (ምዕራፍ 10 ያለውን ይመልከቱ።)
4. "እኔ እኔ ነኝ" የሚለው ቃል
   - ሀ. ከመለኮታዊ ስም ጋር ይያያዛል (ያሕዌ)።
     1. እኔ እርሱ ነኝ (4፡26፣ 8፡24፣ 28፣ 13፡9፣ 18፡5-6)
     2. አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ (8፡54-59)
   - ለ. ባለቤት
     1. እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ (6፡35፣ 41፣ 48፣ 51)
     2. እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ (8፡12)
     3. እኔ የበጎች እውነተኛ በር ነኝ (10፡7፣ 9)
     4. እኔ እውነተኛ እረኛ ነኝ (10፡11፣ 114)
     5. እኔ ሕይወት እና ትንሳዔ ነኝ (11፡25)
     6. እኔ ሕይወት፣ መንገድ እና እውነት ነኝ (14፡6)
     7. እኔ እውነተኛ የወይን ግንድ ነኝ (15፡1፣ 5)

ሠ. በዮሐንስ ወንጌል እና በሌሎች ወንጌላት መካከል ያለው ልዩነት

1. ምንም አንኳ የዮሐንስ ዋነኛ አላማው ስነ መለኮታዊ ቢሆንም መልከዓ ምድርን እና ታሪክን በትክክል እና ጠለቅ ባለ ሁኔታ ተጠቅሟል። በዮሐንስ ወንጌል እና በሌሎች ወንጌላት መካከል ያለው ልዩነት ምክንያት እስከ አሁን በግልጽ አልታወቀም።
   - ሀ. በይሁዳ አውራጃ በመጀመሪያው ሰሞን የነበረው አገልግሎት (ቤተ መቅደሱን በቅድሚያ ማጽዳቱ)
   - ለ. የኢየሱስ የሕይወቱ የመጨረሻው ሳምንታት የጊዜ ቅደም ተከተል እና ቀናት
   - ሐ. ታሪኮችን ለስነ መለኮታዊ ዓላማ እንደገና ማዋቀሩ
2. በዮሐንስ ወንጌል እና በሌሎች ወንጌላት መካከል ያለውን ልዩነት ትንሽ ጊዜ ወስደን መመልከቱ ጠቃሚ ይመስለኛል። ጆርጅ ኢለዶን ላድ "የአዲስ ኪዳን ስነ መለኮት" በተሰኘ መጸሐፉ ያለውን በዚህ ስፍራ ላይ በዋቢነት ልጥቀስ፡
   - ሀ. "አራተኛው ወንጌል ከሌሎች ተመሳሳይ ወንጌላት ልዩ በመሆኑ ምክንያት በትክክል የሚገጥመን ጥያቄ ይህ ወንጌል የኢየሱስን ትምህርት በትክክል አስተላልፏል ወይ ወይም የክርስትና እምነት ትውፊቶችን እንደሚያሻሻሉ በመቀበል ታሪካዊ ገለጻዎች በስነ-መለኮታዊ ትርጓሜዎች መዋጣቸውን መቀበል አለብን።" (ገጽ 215)
   - ለ. "በእጃችን ያለው አሳማኝ መረጃ በዮሐንስ አስተምህሮዎች ውስጥ ያሉት የኢየሱስ አስተምህሮዎች ናቸው። ይህ ትክክለኛ መፍትሔ ከሆነ እንዲሁም ይህ አራተኛው ወንጌል በዮሐንስ አስተምህሮዎች የተመራ ከሆነ ከዚህ በመቀጥል የሚነጠይቅ በጣም አስፈላጊ ጥያቄ የሚከተለው ይሆናል፡ የአራተኛው ወንጌል ስነ-መለኮት ምን ያህል ከኢየሱስ አስተምህሮ የዮሐንስን ይዟል? ከኢየሱስ ቀጥተኛ ትምህርት ይልቅ የዮሐንስን ትርጓሜ በእጃችን የሚገኝ ከሆነ የዮሐንስ አእምሮ ምን ያሉን የኢየሱስን ትምህርቶች በትክክል ይዟል?" (ገጽ 215)
   - ሐ. ላድ ከዚህ በተጨማሪ ደብልዩ. ኤፍ. አልብሪይት የአዲስ ኪዳን ታሪካዊ ዳራ እና የመጨረሻው ዘመን "ስለ ዮሐንስ ወንጌል በፊልስጤም ውስጥ በቅርብ ጊዜ የተገኙ ግኝቶች" ከሚል መጽሐፋቸው ላይ ይህንን ሃሳብ በመውሰድ አስፍረዋል።

     "በዮሐንስ ወንጌል እና በተመሳሳይ ወንጌላት መካከል ይህን ያህል የጎላ ልዩነት የለም፤ በእነዚህ ወንጌላት መካከል ያሉት ልዩነቶች በተወሰኑ መልኩ ያሉት በክርስቶስ አስተምህሮዎች በተለይም

ከኢሴንሳዊያን አስተምህሮ ጋር ተቀራራቢነት ያላቸው ላይ ሲሆን የልዩነቱ ምንጭም የተከተሉት ትውፊቶች ላይ ነው፡፡

ከኢየሱስ አስተምህሮዎች የትኞቹም መበላሸታቸውን ወይም በውሸት መለወጣቸውን ወይም በጣም የጎላ ነገር መጨመሩን የሚያመለክት ነገር ፈጽሞ የለም፡፡ የጥንት ቤተ ክርስቲያ በወንጌል ውስጥ የተወሰኑ ነገሮች እንዲጨመሩ ተጽእኖ ማድረጓን አንክድም፡፡ ነገር ግን በዚያ ዘመን የነበረችው ቤተ ክርስቲያን እነዚህ ነገሮች እንዲጨመሩ መፈለጓ ግን ቤተ ክርስቲያንን የዚያ ነገረ ፈጣሪ ወይም ለእነርሱ ስነ መለኮት አስፈላጊ ነገር ፈጣሪዎች የሆኑ አያሰኛቸውም፡፡

የአዲስ ኪዳን ጥልቅ ስነ-መለኮት ተንታኞች እና ስነ መለኮታዊያን ዘንድ አንድ እንግዳ የሆነ ታሳቢ የሚያደርጉት ነገር አለ፤ ይኼውም የኢየሱስ አእምሮ የተወሰነ ከመሆኑ የተነሳ በዮሐንስ እና በተመሳሳይ ወንጌላት ያለው ልዩነት የተከሰተው በቀደምት ክርስትያኖች ስነ መለኮት መካከል ባለ ልዩነት የተነሳ ነው ይላሉ፡፡ ማንኛውም ታላቅ ሰው በጓደኞቹ እንዲሁም በሚሰሙት ሰዎች በተለያየ እይታ ይታያል እንዲሁም እነዚህ ሰዎች ስለዚህ ሰው የሰሙት እና ያዩትን ነገር ጠቃሚ የሚሉትን ነገር ይጽፋሉ፡፡" (171)

መ. እንደገና ግርጎር ኢ. ላድፍ

"ልዩነታቸው ዮሐንስ ስነ-መለኮታዊ ሀሳብን መጻፉ እንዲሁሜ ሌሎች ይህንን አለማድድጋቸው አይደለም ነገር ግን ሁሉም የወንጌል ጸሐፊት ስነ- መለኮታዊ እይታ አላቸው፡፡ ታሪክን በመተርጎም በጽሑፍ ማስቀመጥ ዝም ብሎ በቅደም ተከታል ታርኩን ከመዘርዘር የታርኩን እውነተኛ ገጽታ ይገልጻል፡፡ የዮሐንስ ወንጌል ስነ መለኮታዊ ትርጓሜ መሆኑን ከተቀበልን ይህ የሚያሳየኝ ዮሐንስ በታሪክ ውስጥ እንደተፈጸመ ያመነበትን ነገር ታሪክን በመተርጎም ያስቀመጠልን ነገር ነው፡፡ ተመሳሳይ ወንጌላት የኢየሱስን ንግግር ቃል በቃል ማስቀመጥ እርሱ ወይም የእርሱን የግል ታሪክ መጻፍ ግባቸው አለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ዓላማቸው እርሱን እና የትምህርቱን እጣሬ መጽሐፍ ነው፡፡ ማቴዎስ እና ሉቃስ በማርቆስ ውስጥ ያውን ጽሑፍ ቅደም ተከተል እነርሱ በሚፈልጉት መንገድ ቅደም ተከተሉን ለማስተካል ነጻ ነበሩ እንዲሁም የኢየሱስን ትምህርት ፍጹም በሆነ ነጻነት ለመግለጽ ችለዋል፡፡ ዮሐንስ ከማቴዎስ እና ከሉቃስ የበለጠ ነጻ ሆኖ ከጻፈ ይህንን ያደረገው ኢየሱስን ይበልጥ ጥሩ በሆነ መልኩ ለመግለጽ ፈልጎ ነው፡፡ (ገጽ 221-222)

**ደራሲው**

ሀ. የዚህ ወንጌል ጸሐፊ ማን እንደሆነ ባይታወቅም ጸሐፊው ዮሐንስ እንደሆነ ግን የተወሰነ አመልካች ነገሮች አሉ፡፡

1. ጸሐፊው የዓይን ምስክር ነው (19፡35 ያነጻጽሩ)
2. "የተወደደው ደቀ መዝሙር" የሚለው ቃል (ይህ ሰው ሐዋርያው ዮሐንስ እንደሆነ ፖሊካርፕ እና ኤራኔዎስ ተናግረዋል)
3. ዮሐንስ፣ የዘብዴዎስ ልጅ፣ በስም አልተጠቀሰም

ለ. ይህ ታሪክ የተፈጸመበት ታሪካዊ ዳራ በወንጌሉ ውስጥ ግልጽ ነው፤ ስለዚህም የዚህ ወንጌል ጸሐፊ ማን መሆኑን በስነ ፍታቴ ውስጥ ጠቀሜታው ይህን ያህል አይደለም፡፡ በመንፈስ ቅዱስ የተነዳ ጸሐፊ ይህንን ወንጌል እንደጻፈው መቀበል ግን ይህንን ወንጌል በትክክል ለመተርጎም እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

ይህ ወንጌል በማን እና መቼ ተጻፈ የሚለው ሀሳብ የዚህን ወንጌል በእግዚአብሔር እስትንፋስ የመጻፍ እውነታ ላይ እንዲሁም በትክክል መፍታት ላይ ተጽእኖ አያመጣም፡፡ ብዙ በዚህ መጽሐፍ ላይ የተጻፉ የመጽሐፍ ቅዱስ መፍቻ ጸሐፊዎች የዚህን መጽሐፍ ታሪካዊ ዳራ፣ ይህ ወንጌል እንዲጻፍ ምክንያት የሆኑ ነገሮችን ለማግኘት ይጥራሉ፡፡ አንድ ሰው የዮሐንስን የሁለትዮሽ ሀሳብ ጋር ማነጻጸር ይጠበቅበታልን፡

1. የአይሁዳዊያ ሁለት ዘመናት
2. የቁምራን የመቀደስ አስተማሪዎች
3. ዞአስተሪያን ሃይማኖት
4. ስለ ኢየሱስ ልዩ አመለካከት ካላቸው ጋር

ሐ. ቀደምት የሆኑ ትውፍቶች የዘብዴዎስ ልጅ ሐዋርያው ዮሐንስ ሰዋዊ የዓይን ምስክር እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ይህ ማብራሪያ የሚያስፈልገው ነገር ነው ምክንያቱም በሁለተኛ ምዕተ አመት ውስጥ የነበሩት ውጫዊ መረጃዎች ይህ ወንጌል የተጻፈው በሌላ ሰው እንደሆነ ስለሚያመለክት ነው፡፡

1. በዚያ ጊዜ የነበሩ አማኞች እና በኤፌሶን የሚገኙ ሽማግሌዎች ይህ ወንጌል የተጻፈው በሐዋርያው እንደሆነ ያስባሉ (እዮስበስ ክላይመንት የተባለው ሰው ዋቢ አድርጎ እንደጻፈው)፡፡
2. ከእርሱ ጋር ሐዋርያ የነበረው እንድሪያስ (ከሙራቶሪያን ቁርጥራጭ ግኝቶች፣ 180-200 ዓ.ም፣ ከሮሜ)

መ. አንዳንድ በዘመናችን ያሉ የስነ መለኮት ምሁራን የዚህን ወንጌል የአጻጻፍ እና የሚዳስሳቸውን ርዕስ ጉዳዮችን በመመልከት የዚህ ወንጌል ጸሐፊ ሌላ እንደሆነ ያስባሉ፡፡

1. ይህ ወንጌል የተጻፈው የዮሐንስን ትምህርት በሚያስታውሱ በዮሐንስ ደቀ መዝሙርት ነው ይላሉ (ጄ. ዌሴ፣ ቢ. ላይትፉት. ሲ.ኤች. ደድ. ኦ. ኩልማን. አር.ኤ. ኩልፔፐር. ሲ.ኬ ባራት)
2. ይህ ወንጌል የተጻፈው "በሽማግሌው ዮሐንስ" (በእሲያ ውስጥ ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ሽማግሌ በነበረው እና በሐዋርያው ዮሐንስ ስነ መለኮት እና ከቃላት ተጽእኖ በነበረበት ሰው የተጻፈ ነው ይላሉ)፤ ይህ አመለካከት

ፓፓሲ (70-146 ዓ.ም) ውስጥ ከተጻፈ መጽሐፍ ግልጽ መረጃ እንዲሁም በኢዮስበስ (280-339) በዋቢነት ከተወሰደ መረጃ ላይ የተገኘ ሀሳብ ነው፡፡

ሠ. ይህንን ወንጌል ለመጻፍ የመጀመሪያ መረጃ ሆኖ ያገለገለው ዮሐንስ እራሱ ነው፡፡

1. የውስጥ ማስረጃዎች
   ሀ. የዚህ ወንጌል ጸሐፊ የአይሁዳዊያንን ትምህርት እና ስርአት ጠንቅቆ የሚያውቅ እና የእነርሱን የብሉይ ኪዳን ንጽረተ ዓለም የሚጋራ ነው፡፡
   ለ. የዚህ ወንጌል ጸሐፊ ፍልስጤምን እና ኢየሩሳሌምን ከ70 ዓ.ም በፊት የነበረችበትን ሁኔታ ጠንቅቆ ያውቃል፡፡
      1. 1፡14
      2. 19፡35
      3. 21፡24
   ሐ. የዚህ ወንጌል ጸሐፊ ከሐዋርያት መካከል አንዱ መሆን አለበት ምክንያቱም እነዚህም ነገሮች ያውቃልና፡
      1. በምሽት ኢየሱስ የተያዘበትን ጊዜ እና ቦታ ማወቁ
      2. እያዳንዷን ቁጥር ማወቁ (ስለ ውሃ ግንቦዎች በ2፡6 እና ዓሳ 21፡11)
      3. ስለ ሰዎች በጥልቀት ማወቁ
      4. ጸሐፊው ስለ ነገሮች እና ሰዎች ለእነዚያ ነገሮች የሰጡትን ምላሽ በጥልቀት ማወቁ
      5. የዚህ ወንጌል ጸሐፊ "የተወደደው ደቀ መዝሙር" ተብሎ ይጠራል
         ሀ. 13፡22፣ 25
         ለ. 19፡ 26-27፣ 34-35
         ሐ. 20፡ 2-5፣ 8
         መ. 21፡7፣ 20-24
      6. የዚህ ወንጌል ጸሐፊ ከጴጥሮስ ጋር ለኢየሱስ በጣም ቅርብ ከነበሩት መካከል አንዱ ነው፡፡
         ሀ). 13፡24
         ለ). 20፡2
         ሐ). 21፡7
      7. የዘብደዮስ ልጅ ዮሐንስ የሚለው ስም በዚህ ወንጌል ውስጥ አንድ ጊዜም አልተጠቀሰም ስለዚህም እርሱ ከሐዋርያት መካከል ለኢየሱስ በጣም ቅርብ ከሆኑት መካከል አንዱ በመሆኑ ምክንያት ይህ ያልተለመደ ነገር ነው፡፡
      8. ውጫዊ ማስረጃዎች
         ሀ) ይህ ወንጌል የሚታወቀው በእርሱ ስም መሆኑ
            1. ከፖልካርፕ ጋር ግንኙነት የነበረው ኤራኔዎስ (120-202 ዓ.ም) ሐዋርያው ዮሐንስን ያውቀዋል (ይህን ኢዮስበስ በተባለ ሰው ከተጻፈ የቤተ ክርስቲያ ታሪክ 5፡20፡6-7)- በኢየሱስ ደረት ላይ ተኝቶ የነበረው የጌታችን ደቀመዝሙር የሆነው ዮሐንስ እንዲሁም በኢስያ ውስጥ በምትገኘው ኤፌሶን ውስጥ እርሱ እራሱ ይህን ወንጌል እንደጻፈ ይናገራል (ሄርሞን 3፡1፤1፣ የቤተ ክርስቲያ *ታሪክ* 5፡8፡4)
            2. አሌክሳንደሪያው ቀልመንጦስ (1534-217 ዓ.ም)- "ይህንን መንፈሳዊ ወንጌል ዮሐንስ በጓደኞቹ እና በመንፈስ ቅዱስ ተገፋፍቶ ጽፎታል" (ኢዮስበስ የቤተ ክርስቲያ *ታሪክ* 6፡14፡7)፡፡
            3. ሰመአቱ ጀስቲን (110-165) *ከታሪፎ ጋር ባደረገው ክርክር* 81፡4 ላይ
            4. ጠርቱልያን (145-220)
         ለ) የዚህ ወንጌል ጸሐፊ ዮሐንስ መሆኑን በብዙ የቀድሞ ምስክሮች ተቀባይነትን ያገኘ ጉዳይ ነው፡፡
            1. የሰማሪያ ኤጴስቆጶስ የሆነ ፖሊካርፕ (ዓ.ም 155) (በኤራኔዎስ በ70-156 ዓ.ም እንደተዘገበው)
            2. ፓፓሲ (70-146 ዓ.ም ከሮም እና ከኢዮስበስ ማርኮናዊያንን በመቃውም በጻፈው ጽሑፍ መግቢያ ላይ ጠቅሷል)፤ ይህ ሰው በፐሪጂያ ውስጥ በምትገኘው የሄራፖሊስ ኤጴስቆጶስ ሲሆን የዚህ ወንጌል ደራሲ ዮሐንስ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ሰ. የተለመደውን የዚህን ወንጌል ደራሲ ማንነት ከመጠራጠር የሚያገለግሉ ምክንያቶች
   1. ይህ ወንጌል ግኖስቲክ ጭብጥ ሀሳብ ጋር ያለው ግንኙነት
   2. ምዕራፍ 21 ላይ ያለው ግልጽ የሆነው ተጨማር ሃሳብ
   3. የዚህ ወንጌል ከተመሳሳይ ወንጌላት ጋር ያለው ቅደም ተከተላዊ ጥቃቅን ልዩነቶች
   4. ዮሐንስ እራሱን "የተወደደው ደቀመዝሙር" ብሎ አለመጥራቱ
   5. የኢየሱስ ዮሐንስ ከወንጌላት የተለየ ቃላትን እና የስነ ጽሑፍ ይዘት መጠቀሙ

ሸ. ይህ ወንጌል የተጻፈው በሐዋርያው ዮሐንስ ነው ብለን ካሰበን ሰውየው ምን ሊሆን ነው?
   1. የጻፈው ከኤፌሶን ነው (ኤራኔዎስ "ይ ወንጌል የተጻፈው ከኤፌሶን" ነው)
   2. ከሽመገለ በኂላ ነው የጻፈው (ኤራኔዎስ ዮሐንስ ተራጃን ተባለው ንጉሥ እስከነገሰበት ሰአት ዮሐንስ እንደኖረ ተናግሯል 98-117)

**ተጻፈበት ዘመን**

ሀ. የዚህ ወንጌል ጸሐፊ ሐዋርያው ዮሐንስ ከሆነ

1. ከ70 ዓ.ም በፊት የሮም ጀነራል ኢየሩሳሌምን ፈጽሞ ከማጥፋቱ በፊት በቲቶ ዘመን
   - ሀ) ዮሐ 5:2 "በኢየሩሳሌምም በበጎች በር አጠገብ በዕብራይስጥ ቤተ ሳይዳ የምትባል አንዲት መጠመቂያ ነበረች፤ አምስትም መመላለሻ ነበረባት"
   - ለ) የሐዋርያት ቡድን ለማመልከት "ደቀ መዛሙርት" የሚለውን የተለመደ ቃል ይጠቀማል
   - ሐ) የኖስቲክ ሀሳብ ያለውን ነገር የዴድ ሲይ ጥቅሎች ከተገኚ በኋላ በውስጥ እንዳሉ መመልከታችን የሚያሳየው በመጀመሪያው ምእተ አመት ላይ ይኖሩ የነበሩ ክርስቲያኖች ይጠቀሙ የነበሩት ከባባድ ስነ መለኮታዊ ቃላት መኖራቸውን ነው።
   - መ) በ70 ዓ.ም ስለ ፈረሰው ቤተ መቅደስ እና ስለ ኢየሩሳሌም ከተማ ምንም አለማለቱ
   - ሠ) ታዋቂው አሜሪካዊው አርኮሎጂስት ደብ ልዩ. ኤፊ አልብራይት ይ ወንጌል የተጻፈበጽ ጊዜ በ70ዎቹ መጨረሻ ወይም በ80ዎቹ መጀመሪያ አከባቢ መሆኑን ገልጸዋል።
     9. በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን መጨረሻ አከባቢ
   - ሀ) ከፍታ እድገት ያሳየው የዮሐንስ ስነ-መለኮት
   - ለ) የኢየሩሳሌም መፍረስ በዚህ ወንጌል ውስጥ ያልተጠቀሰበት ምክንያት ይህ ሁኔታ የተፈጸመው ከ20 አመታት በኋላ በመሆኑ ነው።
   - ሐ) የኖስቲክ አስተምህሮ ሀረጎች እና ትኩረት የሚሰጡ ነገር ዮሐንስ መጠቀሙ
   - መ) የቤተ ክርስቲያን ቀደምት ትውፊት
     1. ኤራኔዎስ
     2. ኢዩስበስ

**ተደራሲያን**

ሀ. ይህ መጽሕፍ የተጻፈው በኢስያ ማይነር በተለይም በኤፌሶን ላሉ ቤተ ክርስቲያናት ነው።

ለ. ስለ ናዝሬቱ ኢየሱስ ሕይወት እና ስብእና በጣም ቀላል እና ጥልቅ በሆነ መልኩ መግለጹ ምክንያት ይህ ወንጌል ለሄሌንስትክ አሕዛብ አማኞች እና ለኖስቲክ አባላት ተመራጭ መጽሐፍ ያደርገዋል።

**የመጽሐፉ ዓላማ**

ሀ. ይህ ወንጌል የወንጌል ስርጭት ዓላማ እንዳለው ይገልጻል 20:30-31

1. ለአይሁዳዊያን አንባቢዎች
2. ለአሕዛብ አንባቢዎች
3. ለኖስቲክ አንባቢዎች

ለ. ይህ ወንጌል በውስጡ አቃቤ እምነታዊ ይዘት ያለው ይመስላል

1. መጥመቁ ዮሐንስን የሚከተሉ ሰዎችን ለመቃወም
   1. የኖስቲክ የስህተት ትምህርት አስተማሪዎችን በመቃወም (በተለይም መግቢያው)፣ ይህ የኖስቲክ ስህተት ትምህርት የአዲስ ኪዳን መጽሐፍት ታሪካዊ አውደ ነው።
   - ሀ. ኤፌሶን
   - ለ. ቆላስያስ
   - ሐ. የመጋቢያን መልዕክት (1 እና 2 ጢሞቴዎስ፣ ቲቶ)
   - መ. 1 ዮሐንስ (1 ዮሐንስ ለዮሐንስ ወንጌል የውጭ ሽፋን ሆኖ ልያገለግል ይችላል)

ሐ. በ20:31 ላይ የተገጸው የመጽሐፉ ዓላማ የመጽናት አስተምህሮን ተደርጎ ልወሰድ ይችላል እንዲሁም የወንጌል ስርጭት መልዕክትም ተደርጎ ልወስድ ይችላል ምክንያቱም ይህ ክፍል በውጡ የአሁን ጊዜን አምልካች ቃል ስላለ ድነትን ስምገልጽ ነው። በዚህ መልኩ ዮሐንስ እንደ ያዕቆብ ሁሉ በአንዳንድ በኢስያ ማይነር በሚኖሩ ቡድኖች መካከል ያለውን የጳውሎስን አስተምህሮ በማለዘብ ሚዛናዊ እንደሆን ያደርጉታል። (2 ጴጥሮስ 3:15-16) የቀደምት የቤተ ክርስቲያን ትውፊቶች ከኤፌሶን ከጳውሎስ ጋር ሳይሆን ከዮሐንስ ጋር አያይዘው መናገራቸው የሚያስደንቅ ነው። (ኤፍ. ኤፍ. ብሩስ *ጴጥሮስ፣ እስጥፋኖስ፣ ያዕቆብ እና ዮሐንስ፡ ከጳውሎስ ውጭ ያለ ክርስትና ጥናት ገጽ* 120-121)

መ. የማጠቃለያው ምዕራፍ (ምዕራፍ 21) የቀደምት ቤተ ክርስቲያንን ልዩ ችግር ለመቅረፍ የተሰበ ይመስላል።

1. ዮሐንስ የተመሳሳይ ወንጌላትን ሀሳብ ይደግፋል። ነገር ግን በይሁዳ አገልግሎቱ፣ በተለይም ኢየሩሳሌም አገልግሎቱ ላይ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል።
2. ተጨማሪ በሚባለው ክፍል (ምዕራፍ 21) ውስጥ የተመለሱ ሶስት ጥያቄዎች
   ሀ. የጴጥሮስ እንደገና መመለስ
   ለ. የዮሐንስ ለረጅን አመት መኖር
   ሐ. የኢየሱስ ዳግም ምጻት መዘግየቶች ናቸው።

ሠ. ዮሐንስ የበተ ክርስቲያን ስርዓቶቸን ሆን ብሎ ቸል በማለት እና በጽሑፉ ውስጥ ባለማካተት ወይም በምዕራፍ 3 (ስለ ጥምቀት) እና ምዕራፍ 6 (ስለ ጌታ እራት) ላይ ብቻ ትንሽ ገለጻ ከሰጠበት በስተቀር ትኩረት ስነሳቸው አንዳንዶች ለመመልተከት ችለዋል።

## የዮሐንስ ወንጌል የአደረጃጀት ውቅር

ሀ. ፍልስፍናዊ/ ስነ መለኮታዊ መቅድም (1፡1-8) እና ተግባራዊ ማጠቃለያ (ምዕራፍ 21)

ለ. በኢየሱስ የሕዝብ አገልግሎት ውስጥ የተፈጸሙ ሰባት ተአምራት (ምዕራፍ 2-12) እና ትርጓሜያቸው፡
1. በቃና ዘገልላ ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ  መለወጡ (2፡1-11)
2. በቅፍረናሆም ኢየሱስ የሹሙን ልጅ እንደ ፈወሰ  (4፡46-11)
3. በኢየሩሳሌም በቤተሳደ የውሃ መጥመቂያ ቦታ ኢየሱስ አንድ ሽባ ሰው መፈወሱ (5፡1-18)
4. በገሊላ ኢየሱስ አምስት ሺህ ሰዎችን መመገቡ (6፡1-15)
5. ኢየሱስ በገሊላ ባሕር ላይ እየተራመደ መሄዱ (6፡16-21)
6. በኢየሩሳሌም ውስጥ ኢየሱስ ከልጅነቱ ጀምሮ ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው ማዳኑ (9፡1-41)
7. በቤታኒ አልዓዛርን ከሞት ማስነሳቱ (11፡1-57)

ሐ. ከግለሰቦች ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ እና ውይይት
1. መጥመቁ ዮሐንስ (1፡19034፣ 3፡22-36)
2. ደቀ መዛሙርት
   ሀ.  እንድሪያስ እና ጴጥሮስ (1፡35-42)
   ለ.  ፊልጶስ እና ናትናኤል (1፡43-51)
3. ኒቆዲሞስ (3፡1-21)
4. በሰማሪያ ያለችው ሴትዮ (4፡1-45)
5. በኢየሩሳሌም ከሚገኙ አይሁዳዊያን ጋር (5፡10-47)
6. በገልላ ውስጥ ከምገኙ ሰዎች ጋር (6፡22-66)
7. ከጴጥሮስ እና ደቀ መዛሙርቱ (6፡67-71)
8. የኢየሱስ ወንድሞች (7፡1-13)
9. ኢየሱስ በኢየሩሳሌም (7፡14-8፡59፣ 10፡1-42)
10. ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር (13፡1-17፡26)
11. አይሁዳዊያን ኢየሱስን ያዙት እንዲሁም ወነጀሉት (18፡1-27)
12. የሮማዊያን ውንጀላ (18፡28-19፡16)
13. የድህረ ትንሳዔ ውይይት 20፡11-29
    ሀ. ከማሪያም ጋር
    ለ. ከአስሩ ደቀ መዛሙርት ጋር
    ሐ. ከቶማስ ጋር
14. ማጠቃለያ ከጴጥሮስ ጋር ያደረገው ንግግር 21፡1-25
15. (7፡53-8፡11፤ በምንዝር የተያዘችው ሴት ታሪክ፣ ይጀ,ህ በመጀመሪያው የዮሐንስ ወንጌል ውስጥ አልነበረም!)

መ. የተወሠነ አምልኮ/ የበዓል ቀናት
1. ሰንበት (5፡9፣ 7፡22፣ 9፡14፣ 19፡31)
2. የፋሲካ በአል (2፡13፣ 6፡4፣ 11፡55፣ 18፡28
3. የድንኳን በአል (ምዕራፍ 8-9)
4. ሃኑካ (የብርሃን በዓል፣ 10፡22 ጋር ያነጻጽሩ)

ሠ. "እኔ ነኝ" የሚለውን ቃል የተጠቀመበት ሁኔታ
1) "እኔ እርሱ ነኝ" (4፡26፣ 6፡20፣ 8፡24፣ 28፣ 54-59፣ 13፡19፣ 18፡5-6፣8)
2) እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ (6፡35፣ 41፣ 48፣ 51)

3) እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ (8:12፣ 9:5)
4) እኔ የበጎች እውነተኛ በር ነኝ (10:7፣ 9)
5) እኔ እውነተኛ እረኛ ነኝ (10:11፣ 114)
6) እኔ ሕይወት እና ትንሳዔ ነኝ (11:25)
7) እኔ ሕይወት፣ መንገድ እና እውነት ነኝ (14:6)
8) እኔ እውነተኛ የወይን ግንድ ነኝ (15:1፣ 5)

**የመጀመሪያው ዙር ንባብ**

ይህ <u>ምሪት</u> የሚሰጥ የመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻ ነው፤ ይህም ማለት ለምትደርስበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ኃላፊነት የምትወስደው አንተ እራስ ትሆናህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን ባለን ብርሃን መጠን ልንመላለስ ይገባል ማለት ነው። በስነ አፍታት ሂደት ውስጥ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ዋነኛውን ስፍራ ትይዛላችሁ። ይህንን እድል ለመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻዎች አሳልፈህ አትስጥ።

መጽሐፉን በአንድ ጊዜ አንብበህ ጨርስ። የመጽሐፉን ማዕከላዊ ጭብጥ በራስህ ቃል ግለጽ።

1) የመጽሐፉን በሙሉ ጭብጥ
2) የመጽሐፉን ስነ ጽሑፋዊ ይዘት

**ሁለተኛ ዙር ንባብ**

ይህ <u>ምሪትን</u> የሚሰጥ የመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻ ነው፤ ይህም ማለት ለምትደርስበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ኃላፊነት የምትወስደው አንተ እራስ ትሆናህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን ባለን ብርሃን መጠን ልንመላለስ ይገባል ማለት ነው። በስነ አፍታት ሂደት ውስጥ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ዋነኛውን ስፍራ ትይዛላችሁ። ይህንን እድል ለመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻዎች አሳልፈህ አትስጥ።

መጽሐፉን በአንድ ጊዜ ለሁለተኛ ጊዜ አንብበህ ጨርስ። ዋና ዋና ሀሳቦችን ግለጽ እንዲሁም ዋናውን ሀሳብ በአንድ አረፍተ ነገር ግለጽ

1) የመጀመሪያውን አንቀጽ ዋና መልዕክት
2) የሁለተኛውን አንቀጽ ዋና መልዕክት
3) የሦስተኛውን አንቀጽ ዋና መልዕክት
4) የአራተኛውን አንቀጽ ዋና መልዕክት
5) ወዘተ

# የዮሐንስ 1

## በዘመናችን የሚገኙ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጞች የአንቀጽ ክፍፍል

| UBS$^4$ | NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| *ቃል ሥጋ ሆነ* | ዘላለማዊው የእግዚአብሔር ቃል | *መግቢያ* | የሕይወት ቃል | *መቅደም* |
| 1:1-5 | 1:1-5 | 1:1-5 | 1:1-5 | 1:1-18 |
| | ዮሐንስ ስለ እውነተኛ ብርሃን | | | |
| 1:6-13 | 1:6-13 | 1:6-9 | 1:6-9 | |
| | *ቃል ሥጋ ሆነ* | | | |
| 1:14-18 | 1:14-18 | 1:14-18 | 1:14 | |
| | | | 1:15 | |
| | | | 1:16-18 | |
| *የመጥመቁ ዮሐንስ* | በበርሃ የሚጮኽ ድምጽ | *የዮሐንስ ምስክርነት* | *የመጥመቁ ዮሐንስ መልዕክት* | *የዮሐንስ ምስክርነት* |
| 1:19-28 | 1:19-28 | 1:19-28 | 1:19-28 | 1:19-28 |
| | | | 1:20 | |
| | | | 1:21 | |

**ሦስተኛ ዙር ንባብ**
*በአንቀጽ ደረጃ የመጽሐፉ ጸሓፊ ሊያስተላልፍ የፈለገውን ሀሳባ መከተል*

ይህ <u>ምሪትን</u> የሚሰጥ የመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻ ነው፤ ይህም ማለት ለምትደረስበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ኃላፊነት የምትወስደው አንተ እራስ ትሆናህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን ባለን ብርሃን መጠን ልንመላለስ ይገባል ማለት ነው። በስነ አፍታት ሂደት ውስጥ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ዋነኛውን ስፍራ ትይዛላችሁ። ይህንን እድል ለመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻዎች አሳልፈህ አትስጥ።

*መጽሐፉን በአንድ ጊዜ ለሁለተኛ ጊዜ አንብበህ ጨርስ። ዋና ዋና ሀሳቦችን ግለጽ እንዲሁም ዋናውን ሀሳ በአንድ አረፍተ ነገር ግለጽ።*

1. *የመጀመሪያውን አንቀጽ ዋና መልዕክት*

---

*ተመስጧዊ ባይሆኑም፣ የአንቀጽ ምድቦች የሚከተለውን የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ ለመረዳት ቁልፍ ናቸው። እያንዳንዱ ዘመናዊ ትርጉም አንቀጾቹን መድቦ ማጠቃለያውን እንዲያቀርብ ተደርጓል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድ ማዕከላዊ ርዕሰ-ጉዳይ፣ እውነት፣ ወይም እሳቦት አለው። እያንዳንዱ ቅጂ ያንን ርዕስ በራሱ የተለየ መንገድ አጽዕሮቱን አስፍሯል። ጽሑፉን ስታነበው፣ የትኛው ትርጉም በርዕሰ ጉዳይም ሆነ በቁጥር ምድቦች ከአንተ መረዳት ጋር እንደሚስማማ ራስህን ጠይቅ።

በእያንዳንዱ ምዕራፍ በቅድሚያ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ይኖርብናል፣ እንዲሁም ርዕሰ ጉዳዮቹን መለየት (አንቀጾቹን)፣ አኪያም የእኛን መረዳት ከአዲሶቹ ትርጉሞች ጋር ማወዳደር አለብን። መጽሐፍ ቅዱስን ልንረዳ የምንችለው የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ ምን እንደሆነ የሱን አምክኖአዊ (ሎጂክ) እና አቀራረቡን ስንረዳ ነው። ዋነኛው ጸሐፊ ብቻ ነው ተመስጧዊው– አንባብያን መልዕክቱን ለመቀየርም ሆነ ለማሻሻል መብት የላቸውም። የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢዎች ተመስጧዊውን እውነት በየዕለቱና በሕይወታቸው ሁሉ ተግባራዊ ለማድረግ ኃላፊነት አለባቸው።

**ማስታወሻ፦ ሁሉም ሙያዊ ቃላትና አጽሕሮተ ቃላት በሙሉ በቅጥያ አንድ፣ ሁለት፣ እና ሦስት ላይ ተብራርተዋል።**

2. የሁለተኛውን አንቀጽ ዋና መልዕክት

3. የሦስተኛውን አንቀጽ ዋና መልዕክት

4. ወዘተ

**ለምዕራፍ1፡1-18 አውዳዊ አብርሆት**

ሀ. የግጥሙ/የመዝሙሩ/የኃይማኖት መግለጫው ሥነ መለኮታዊ አወቃቀር
1. ዘላለማዊ፣ መለኮታዊ፣ ፈጣሪ፣ አዳኝ ክርስቶስ (ቁ. 1-5) (ኢየሱስ እንደ ቃል)
2. ስለ ክርስቶስ የተሰጠ ትንቢታዊ ምስክርነት ቁ. 6-9፣ 15 (ኢየሱስ እንደ ብርሃን)
3. ትስብእት የሆነው ክርስቶስ እግዚአብሔርን ገለጠ ቁ. 10-18 (ኢየሱስ እንደ ልጅ)

ለ. ሥነ መለኮታዊ ውቅር እና ዋናው ጭብጥ
1. ኢየሱስ ከእግዚአብሔር አብ ጋር ይኖር ነበር (1ሀ)
2. ኢየሱስ ከእግዚአብሔር አብ ጋር ቅርበት የተሞላበት ግንኙነት ነበረው (1ለ፣2፣ 18ሐ)
3. ኢየሱስ የእግዚአብሔር አብን ባሕርይ ሙሉ በሙሉ ይጋራል (1ሐ፣ 18ለ)
4. የእግዚአብሔር አብ የድነት መንገድ እና ጉድፈቻ (12-13)
5. ትስብእት፣ የአምላክ ሰው መሆን (9፣14)
6. መገለጥ፣ የአምላክ ሙሉ በሙሉ መገለጥ እና ሰዎች መረዳታቸው (18መ)

ሐ. ቃል (ሎጎስ) የሚለው ቃል የዕብራይስጥ እና የግሪክ ታሪካዊ ዳራው
1. የዕብራይስጥ ታሪካዊ አውዱ
   ሀ. የተነገረ ቃል ኃይል (ኢሳ 55፡11፣ መዝ 33፡6፣ 107፡20፣ 147፡15፣18)፣ በስነ ፍጥረት እንደታየው (ዘፍ 1፡3፣6፣9፣11፣ 14፣ 20፣ 24፣ 26፣ 29) እንዲሁም የአባቶች ባርኮት (ዘፍ 27፡1 እና ቀጣዮቹ ቁጥች፤ 49፡1)
   ለ. ምሳ 8፡12-13 በሰውኛ የተገለጸችው "ጥበብ" እግዚአብሔር የመጀመሪያው ፍጥረት ሆና ተገልጻለች እንዲሁም የሌሎች ፍጥረታት ሁሉ በእርሷ በኩል እንደተፈጠሩ ተገልጸዋል (ይህንን መዝ 33፡6 እና ቀናኖናዊ መጻፍ ያልሆነው የሰለሞን ጥበብ የሚባለው መጽሐፍ 9፡9 ጋር ያናጻጽሩ)
   ሐ. ታርጉም (የአረማይክ ቋንቋ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም እና መፍቻ) የእግዚአብሔር ቃል የሚለውን "ሎጎስ" በሚለው ተክቶታል ምክንያቱም በሰውኛ የተገለጹ ቃላት ስለማይመቿቸው ነው፡፡
   10. የግሪክ ታሪካዊ አውድ
   ሀ. ሄራክሌቱስ- ዓለም በለውጥ ላይ ናት፣ አካላዊ ያልሆነ ግኡዝ እና የማይለወጥ ሎገጎስ በአንድ ላይ አያይዞዋታል እንዲሁም የሚለወጠውን ሂደት ይመራል፡፡
   ለ. ፕላቶ- አካላዊ ያልሆነው እና የማይለወጠው ሎጎስ ፕላኔቶችን በምህዋሮቻው ላይ በስራአት እንዲጓዙ ያደርጋል እንዲሁም ጊዜያትን ይወስናል፡፡
   ሐ. ስቶኮስ- ሎጎስ የዓለማችን አመክንዮ ነው ወይም አስተዳዳሪ ነው ነገር ግን ንዑስ አካላዊ ነው፡፡
   መ. ፊሎ- የሎጎስን ጽንሰ ሃሳብ በሰውኛ የሚገልጸው ሲሆን "በእግዚአብሔር ፊት የሰው ልጆቸን ነፈስ እንደሚያቀርብ ሊቀ ካህን አድጎ ይመስለዋል" ወይም "በሰዎች እና በእግዚአብሔር መኻላ መካከለኛ የሚሆን" ወይም "የፕላቶን ዓለም የሚያንቀሳቅሰው ዓለምን ሁሉ የሚያቀሳቅሰው ጎማ" በማለት የጠራዋል፡፡

መ. የሁለተኛው ምዕተ አመት የገኖስቲኮች ስነ መለኮት/ፍልስፍና እድገት ባሕርያት
1. በመንፈስ እና በቁስ መካከል ዘላለማዊ የባሕርይ ጠላትነት መኖሩ
2. ቁስ አካላዊ የሆነ ነገር ክፉ እና ችኮ ሲሆን መንፈሳዊ የሆነ ነገር ሁሉ መልካም ነው፡፡
3. የኖስቲኮች አመለካከት በመለአክት መካከል ደረጃ እንዳለ በማሳየት (አዮን) መላእክት ከፍተኛ መላእክት፣ መልካም አማልክት እና ትንንሽ አማልክት (ቁስ አካላዊ የሆኑ ነገሮች የፈጠሩ) አሉ በማለት ይከፋፍሏቿል፡፡
4. ድነት የሚገኘው
   ሀ. ምስጥራዊ እውቀት ወይም ከእግዚአብሔር ጋር ለመዋሃድ በሚያደርጉት ጥረት መካከል የመላእክቱን ደረጃ ለማለፍ የሚያስልጋቸው ማለፊያ ቃል ነው፡፡
   ለ. በሰዎች ሁሉ ውስጥ የሚገኝ መለኮታዊ ብልጭታ ሲሆን ይህም ነገር ሰዎች ምስጥራዊ እውቀትን እስግያገኙ ድረስ መኖሩን እንኳ አያውቁትም
   ሐ. ለሰው ልጆች ይህንን እውቀት መስጠት የሚችል ልዩ የሆነ መገለጥ ያለው መልዕክተኛ (የክርስቶስ መንፈስ)

1. ይህ አመለካከት የኢየሱን አምላክነት የሚቀበል ቢሆንም የትስብእትን እውነተኝት እና ቋምነት እንዲሁም በድነት ውስጥ ያለውን ማዕከላዊነት ይክዳል፡፡

ሠ. ታሪካዊ ዳራ

1. ከ1-18 የአይሁዳዊያን እና የግሪካዊያን አእምሮ ሎጎስ የሚለውን ቃል በመጠቀም ለማዛመድ ጥረት ያደርጋል፡፡
2. በዚህ በዮሐንስ ወንጌል መግቢያ ላይ በጥሩ ሁኔታ የተገለጸው ፍልስፍናዊ ሀሳብ የግኖስቲኮችን ኑፋቄ ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ እስከ ሁለተኛው ምዕተ አመት ድርስ ግኖስቲክ የሚለው ስነ መለኮታዊ እሳቤ አይታወቅም ነበር፡፡ ነገር ግን  በዴድ ሲ ይ ስክሮል እና በፊሎ ጽሑፎች ውስጥ የግኖስቲኮች ቁርጥራጭ አመለካከቶች ተገኝተዋል፡፡
3. ተመሳሳይ ወንጌላት(በተለይም የማርቆስ ወንጌል) የኢየሱስን አምላክን እስከ መስቀል ላይ ሞት መሸፈኑ (የመሢሑ ምስጥር ተብሎ የሚታወቀው) እንመለከታለን ነገር ግን  ከማርቆስ በኂላ ብዙ ቆይቶ የጻፈው ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ ሙሉ አምላክነት እና ሙሉ ሰዎነት እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነ ሀሳብን በምእራፍ አንድ ጽፏል (የሰው ልጅ የሚለውን ከሕዝቄል 2፡1 እና ከዳንኤል 7፡13 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡

ረ. ልዩ ርዕስ፡ ዮሐንስ 1 ከ1 ዮሕንስ 1፡1 ጋር የተነጻጸረበትን ተመልከት፡፡

**የቃላት እና የሀረግ ጥናት**

| |
|---|
| **የNASB (የተሻሻለው) ጥቅስ 1፡1-5**<br>[1]**በመጀመሪያው ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ፡፡** [2]**ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡፡** [3]**ሁሉ በእርሱ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም፡፡** [4]**በእርሱ ሕይወት ነበረች፥ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች፡፡** [5]**ብርሃንም በጨለማ ይበራል፥ ጨለማም አላሸነፈውም፡፡** |

1፡1 "**በመጀመሪያ**" ይህ ሀሳብ የዘፍጥረት 1፡1 ሀሳብ ያንጸባርቃል፤ በተመሳሳይ መልኩም ይህ ሀሳብ በ1ዮሐ 1፡1 ላይም ትስብእትን አስመልክቶ ይህ ሀሳብ በድጋሚ ተጠቅሷል፡፡ የ1 ዮሐንስ መልዕክት ለዮሐንስ ወንጌል የሽፋን ደብዳቤ ሊሆን ይችላል፡፡ ሁለቱም የሚያወሱት ስለ ግኖስቲክ ሀሳብ ነውና፡፡ ቁጥር 1-5 ላየው ኢየሱስ ከፍጥት በፊት በመለኮት መኖሩን የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡ (1፡15፣ 8፡56-50፣ 16፡28፣ 17፡5፣ 2ቆሮ 8፡9፣ ፊል 2፡6-7፣ ቆላ 1፡17፣ ዕብ 1፡3፣ 10፡5-8)፡፡

አዲስ ኪዳን እንዲህ ይገለጻል

1. በውድቀት የማይበላሸው አዲስ ፍጥረት (ይህ ማለት ዘፍ 3፡15 ለሰው ልጆች ፍጻሜን አገኘ ማለት ነው)

2. አዲስ ውርስ (የተስፋይቱ ምድር)
3. አዲስ ዘጸአት (የትንቢቶች ፍጻሜ)
4. አዲሱ ሙሴ (ሕግ ሰጭ)
5. አዲሱ ኢያሱ (ከዕብ 4፡8 ጋር ያነጻጽሩ)
6. አዲሱ የውሃ ላይ ተአምር (ከዕብ 3-4 ጋር ያነጻጽሩ)
7. አዲሱ መና (ዮሐንስ 6 ጋር ያነጻጽሩ)

በተለይ በዕብራዊያን መጽሐፍ ውስጥ ሌሎች በጣም ብዙ ይንን የመሰሉ ነገሮችን መመልከት ይችላል፡፡

▣ **"ነበር"** (ሦስት ጊዜ) ይህ ቃል በላፊ ጊዜ በቀጣይነት የተከናወነ ነገርን ያሳያል፡፡ ይህ ስዋሰው በአገልግሎት ላይ የዋለው ሎጎስ ቀድሞ ይኖር እንደነበር ለማሳየት ነው (8፡57-58፤ 17፡5፣ 24፤ 2ቆሮ 1፡17፤ ዕብ 10፡5-7 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡ ይህ በቁጥር 3፣ 6 እና 14 ጋር በኤሪስ ቴንስ (በአላፊ ጊዜ ስዋሰው) ከተገለጸው ጋር ያነጻጽሩ፡፡

▣ **"ቃል"** ሎጎስ የሚለው የግሪኩ ቃል የሚያመለክተው መልዕክት እንጂ አንድ ቃልን አይደለም፡፡ በዚህ አውድ ውስጥ ይህ የግሪክ ቃል የሚገልጸው ግሪኮች "የአለማችን አመክኒዮ" የሚሉትን እንዲሁም ዕብራዊያን "ጥበብ" ብለው ከሚገልጹ ጋር ይመሳሰላል፡፡ ዮሐንስ ይህን ቃል በመምረጥ የተጠቀመው የእግዚአብሔር ቃል አካላዊ እና መልዕክት መሆኑን ለማለክት ነው፡፡ አውዳዊ አብርሆት ሐ የሚለውን ይመልከቱ፡፡

▣ **"ከእግዚአብሔር ጋር ነበር"** በቁ. 1ሀ ላይ ያለው ሰዋሰው በአላፊ ጊዜ ሆኖ በቀጣይነት የተከናወነ ነገርን የሚያመለክት ግስ ነው፡፡ ከአምላክ ጋር የሚለው ቃል መስተአምር ዬለውም (ባለቤቱ ዮቱ እንደሆነ የሚያመለክት ነገር ዮለም ስለዘህ ነገር F.F. Bruce, ANswers to QuesttioNs, p.66 ይመልቱ፡፡) ነገር ግን እግዝኢብሔር (ቴዎስ) የሚለው ቃል መጀመሪያ በመምጣቱ ምክንያት አጽኖት ለመስጠት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ይህ ቁጥር እና ቁጥ 18 ለሎጎስ (ቃል) ከፍጥረት በፊት መኖሩ እና ሙሉ መለኮተትን ጠንካራ መከራከሪያ ሀሳቦች ናቸው፡፡ (5፡18፤ 8፡50፤ 10፡10፤ 14፡9፤ 17፡11፤ 20፡28፤ ሮሜ 9፡5፤ ዕብ 1፡8፤ 2 ጴጥ 1፡1 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡ ኢየሱስ ፍጹም አምላክ እና ፍጹም ሰው ነው (1 ዮሐ 4፡1-3)፡፡ ከእግዚአብሔር አብ ጋር አንድ አክል አይደለም ነገር ግን እንደ አብ ሁሉ እርሱ አንድ አይነት መሎኮታዊ ባሕርይ አለው፡፡

አዲስ ኪዳን የናዝሬቱን የኢየሱስን ሙሉ መለኮታዊነት አስረግጦ ይናገራል፡፡ ነገር ግን ኢየሱስን ከአብ በአካል የተለየ መሆኑንም ይናራል፡፡ አንድ አይነት መለኮታዊ ባሕርይ እንዳላቸው በአጽኖት የሚገልጽባቸው ቦታዎች ዮሐ 1፡1፤ 5፡18፤ 10፡30፣ 34-38፤ 14፡9-10 እና 20፡28 ሲሆኑ ልዩነታቸው የተገለጹባ ቦታዎች ደግሞ ዮሐ 1፡2፣ 14፣18፤ 5፡19-23፤ 8፡28፤ 10፡25፣29፤ 14፡11፣12፣13፣16 ናቸው፡፡

1፡2 ይህም ከቁጥር 1 ጋር ትይዩ ነው፡፡ እንዲሁም ከ6-5 ዓም ውስጥ የተወለደው ኢየሱስ ከእግዚብሔር አብ ጋር በአብሮ መኖሩ እና መለኮት መሆኑን አጽኖት ሰጥቶ መናገሩ በአንድ አምላካዊ ለሆነ ሕዝብ እጅግ አስደንጋጭ እውነት ነበር፡፡

1፡3 **"ሁሉ በእርሱ ሆነ"** ሎጎስ (ቃል) የሚታየውን እና የማይታየው ዓለም የተፈጠረበት የእግዚአብሔር አብ የፍጥረት

---

**ልዩ ርዕስ፡ አሪኬ**

"አሪኬ" የሚለው ቃል ትርጓሜ የአንድ ነገር "መጀመሪያ" ወይም "ምንጭ" ማት ነው፡፡

1. ፍጥረት ስርአት መጀመሪያ (ዮሐ 1፡1፤ 1 ዮሐ 1፡1፤ ዕብ 1፡10 ጋር ያነጻጽሩ)
2. የወንጌል መጀመሪያ (ማር 1፡1፤ ፊል 4፡15፤ 2 ተሰ 2፡13፤ ዕብ 2፡3 ጋር ያነጻጽሩ)
3. የመጀመሪያ የዐይን ምስክሮች (ሉቃ 1፡2 ጋር ያነጻጽሩ)
4. ከምልክቶቹ የመጀመሪያው (ተአምራ ዮሐ 2፡11 ጋር ያነጻጽሩ)
5. የመርሆዎቹ የመጀመሪያ (ከዕብ 5፡12 ጋር ያነጻጽሩ)
6. በወንጌል እውነት ላይ የተመሠረተ የመጀመሪያው መስተማመኛ (ዕብ 3፡14 ጋር ያነጻጽሩ)
7. የመጀመሪያ ቆላ 1፡18፤ ራዕ 3፡14

በኋላ ላይ ይህ ቃ "መግዛትን" ወይም "ስልጣንን" ማመልከት ጀመረ

1. የመንግስት በለስልጣናትን
   ሀ. ሉቃ 12፡11
   ለ. ሉቃ 20፡20
   ሐ. ሮሜ 13፡3፤ ቲቶ 3፡1
2. የመለኣክትን ስልጣን
   ሀ. ሮሜ 8፡38
   ለ. 1 ቆሮ 15፡24
   ሐ. ኤፌ 1፡21፤ 3፡10፤ 6፡12
   መ. ቆላ 1፡16፤ 2፡10፣ 15
   ሠ. ይሁ ቁ.6

እነዚህ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች በሰማይም በምድርም ያለውን ስልጣን ያጣጥላሉ፡፡ ጋጠወጣዊ ነጻነትን ይሻሉ፡፡ በእግዚአብሔር፣ በመለኣእክት፣ በመንግስት በለስልጣነት እና በቤተ ክርስቲያን ፊት እራሳቸውን እና የእነርሱን ፍላጎት ያስቀድማሉ፡፡

---

ሠራተኛ ነው (ቁ 10፤ 1ቆሮ 8:6፣ ቆላ 1:16፣ ዕብ 1:2)፡፡ ይህ በመዝ 33:6 እና ምሳሌ 8:12-23 ውስጥ ጥበብ ከተጫወተችው ሚና ጋር ተመሳሰይ ሚና አለው (በዕብራዊያን ዘንድ ጥበብ የሴት ጾጳ አላት)፡፡

▣ **"ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም"** ይህ ሀረግ የግኖስቲኮችን አመላካከት ውድቅ የሚያደረግ ሲሆን በእነርሱ አመለካከከት አዮን በመባል የሚታወቁ ከፍተኛ፣ መልካም አማልክ እና ትንሽ መንፈሳዊ አካላት ከዚያ በፊት መፈጠራቸውን የሚያስተምር ነው፡፡

**1:4 "በእርሱ ሕይወት ነበረች"** ይህ ሀረግ ትኩረት ሰጥቶ የሚናረው "ሕይወት" እራሷ ከልጁ፣ ከቃል እንደመጣች ነው፡፡ ዮሐንስ "ዜዎ" የሚለውን ቃል የሚጠመው ለትንሳኤ ሕይወት፣ ለዘላለማዊ ሕይወት፣ ለእግዚአብሔራዊ ሕይወት ነው (1:4፤ 3:15፣ 36፤ 4:14፣ 36፤ 5:24፣ 26፣ 29፣ 39፣ 40፤ 6:27፣ 33፣ 35፣ 40፣ 47፣ 48፣ 51፣ 54፣ 63፣ 65 ወዘተ ከሚሉ ክፍሎች ጋር ያነጻጽሩ)

▣ **"ሕይወትም የሰው ልጅ ብርሃን ነበረች"** ብርሃን ዮሐንስ በጽሑፉ ውስጥ እውነትን እና እግዚአብሔራዊ እውቀትን ለማመልክት አዘውትሮ የሚጠቀምት ምሳሌያዊ ነግግር ነው (1 ዮሐ 3:19፤ 8:12፤ 9:5፣ 12:46)፡፡ ሕይወት ለሰው ልጆች ሁሉ እንደሆነ አስተውሎ (የመዝ 36:5-9 ካው ክፍል የተወሰደ ልዮን ይችላል)፡፡ ብርሃን እና ጨለማ የሚሉ ምሳሌዎች በዴድ ሲ ስክሮልስ ውስጥ በብዛት የምስተዋሉ ምሳሌዎች ናቸው፡፡ ዮሐንስ አዘውትሮ እራሱን የሚገልጸው ሁለትዮሽ (ንጽጽራዊ) በሆኑ ቃላት እና ክፍፍሎሽ ነው፡፡

**1:5 "ብርሃንም በጨለማ ይበራል"** ይህ ሀረግ የተገለጸበት ስዋሰው የአሁን ጊዜ አመልካች በመሆኑ ድርጊቱ ቀጣይነት እንደላው ያሳያል፡፡ ኢየሱስ ሁል ጊዜ ያለ ሲሆን አሁን ግን በቃሉ ውስጥ በግልጽ ታይቷል (8:12፤ 9:5፤ 12:46) በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር በሰው ቅርጽ ስገለጥ ወይም በአካላዊ ማንነት ስገለጥ ይህ ብዙ ጊዜ የጌታ መለአክ እንደተገለጠ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ (ዘፍ 16:7-13፤ 22:11-15፤ 31:11፣ 13፣ 48:15-16፤ ዘጸ 3:2፣3፣ 4፤ 13:21፣ መሳ 2:1፣ 6:22-23፣ 13:3-22፣ ዘካ 3:1-2)፡፡ አንዳንዶች በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር በሰው መልክ የተገለጠውን ሎጎስ (ቃል) ትስበእት ሳይሆን በፊት አድርገው ይወስዱታል፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ የጌታ መላእክ**

በብሉይ ኪዳን ውስጥ መለኮት በሰውኛ መልክ መገለጡ እውነት ነው፡፡ በአሃዱ ሥሉስ ለሚያምኑ ሰዎች የሥላሴ ዔትኛው አካል ነው የተገለጠው የሚል ጠትያቄ ነው፡፡ እግዚአብሔር አብ (ያሕዌ) እና የእርሱ መንፈስ ቁስ አካላዊ እስካልሆኑ ድርስ በብሉይ ኪዳን ውስጥ በሰውኛ የተገለጠው መሚሑ ትስብእት ሳይሆን በፊት ነው ማለት ይቻላል፡፡
አንድ ሰው ከመላእክት ጋር አንድ ሰው ስገናኝ ስለሚገጥመው ችግር ልገልጹልን የሚችሉ እነዚህም ምሳሌዎችን መመልከት ይቻላል

1. የጌታ መላእክት እንደ መላእክ
   - ሀ. ዘፍ 24:7፣40
   - ለ. ዘጸ 23:20-23፣32:34
   - ሐ. ዘኍ 22:22
   - መ. መሳ 5:23
   - ሠ. 2ሳሙ 24:16
   - ረ. 1 ዜና 21:15-30
   - ሰ. ዘካ 1:12-13
2. የጌታ መላእክ በሰውኛ
   - ሀ. ዘፍ 16:7-13፤ 18:1-19:1፤ 22:11-15፣ 31:11፣13፤ 48:15-16
   - ለ. ዘጸ 3:2፣4፤ 14:19 (13:21)
   - ሐ. መሳ 2:15፣ 6:22-24፣ 13:3-23
   - መ. ሆሴ 12:3-4
   - ሠ. ዘካ 3:1-5

▣

| | |
|---|---|
| NASB፣ NKJV | **"ጨለማም አለሸነፋም"** |
| NRSV | **"ጨለማም አልቻለውም"** |
| TEV | **"ጨለማ ሊያስወጣው አልቻለም"** |
| NJB | **"እናም ጨለማ ከእርሱ በላይ በኃይል ልበረታ አልቻለም"** |

*"ካታላባና"* የሚለው ቃል የሥረወ ግንዱ ትርጉም *"መያዝ"* የሚል ነው፡፡ ስለዚህም የዚህ ቃ ትርጉም (1) መብለጥ፣ ማሸነፍ ማቴ 16:18) ወይም (2) መረዳት ወይም ማወቅ ሊሆን ይችላል፡፡ ዮሐንስ ይህንን ቃል በመጠቀም ማስተላለፍ የፈለገው ሁለቱንም ሃሰብ ሊሆን ይችላል፡፡ የዮሐንስ ወንጌል የሚታወቀው በሚያቀርባቸው ሁለትዮሽ ሀሳቦች ነው፡፡ (ለምሳሌ "ከላይ መወለድ እና ዳግም መወለድ" 3:3 እና "ንፋስ" እና "መንፈስ" 3:8)

*"ኀታላባኖ"* የሚለው ግስ በዮሐንስ ጽሑፎች ውስጥ ሁለት ጊዜ ብቻ አገልግሎት ላይ የዋለ ሲሆን (8፡3፣4 ላይ ነው)። በ1፡5 ላይ ጨለማ መረዳት/ማሸነፍ አይችልም የሚል ሲሆን በ12፡35 ላይ ብርሃንን (ኢየሱስ/ወንጌል)የተቃወመው ጨለማ እንደሚወስድ ያወራል። አለመቀበል ግራ መጋባትን ሲያስከትል መቀበል ደግሞ አምልኮን ያስከትላል።
ማንፊሬድ ቲ. ባሩሃ የተባለ ሰው " AbusiNg Scripture" P 35 ላይ የሰው ልጆች ሁኔታ እንዲህ ስል ገልጸዋል።

1. መጥፋት ሉቃ 15
2. ጨለማ ዮሐ 1፡5
3. ጠላትነ ሮሜ 5፡10
4. መለየት ኤፌ 2፡15-17
5. ያለ አምላክ መሆን ሮሜ 1፡18
6. ከእግዚአብሔር ሕይወት መለየት ኤፌ 4፡17-18
7. የሰው ልጆች ኂጢአት ጥሩ እጣሬ የኒገኘው በሮሜ 1፡18-3፡23 ላይ ነው።

**የNASB (የተሻሻለው) ጥቅስ 1፡6-8**
**[6]ከእግዚአብሔር የተላከ ስሙ ዮሐንስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ፤ [7]ሁሉ በእርሱ በኩል እንዲያምኑ ይህ ስለ ብርሃን ይመሰክር ዘንድ ለምስክር መጣ። [8]ስለ ብርሃን ሊመሰክር መጣ እንጂ: እርሱ ብርሃን አልነበረም።**

**1፡6-8** እነዚህ ቁጥሮች እና ቁጥር 15 መጥመቁ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የመሰከረውን ምክርነት እንደገና የሚያስተጋቡ ናቸው። እርሱ የብሉይ ኪዳን ነብይ ነበር። ይህንን ቁጥር በግጥም መልክ ማስቀመጥ እጅግ አስቸጋር ነገር ነው። በስነ መለኮት ምሁራን ዘንድ ይህ ክፍል ግጥም ወይስ ስድ ንባብ ነው በምለው ላይ ብዙ ክርክር አለ።

መጥመቁ ዮሐንስ የብሉይ ኪዳን የመጨረሻው ነበይ ነው (ይህ መልዕክቱን እና እይታውን በተመለከተ ማለት ነው)። በሚል 3፡1 እና 4፡5 የተገለጸው ከፊት ለፊቱ የሚሄደው ነው (ዮሐ 1፡20-25 ከምለው ጋር ያነጻጽሩ)። ሐዋርያው ዮሐንስ ቁ.6-8 ያለውን ሀሳብ ያስገባው ምንአልባም በመጥመቁ ዮሐንስ ዙሪያ ቀደም ስል አንዳንድ ብዥታዎች በመኖራው ምክንያት ሊሆን ይችላል (ሉቃ 3፡15፣ የሐዋ 18፡25፤ 19፡3 ጋር ያነጻጽሩ)። ከሌሎች የወንጌላት ጸሓፊ በኂላ ወንጌሉን የጻፈው ዮሐንስ የችግሩን እድግት ሳይመለከት አልቀረም።

የሚገርመው ነገር ኢየሱስ የተገጸው አላፊ በሆነ ጊዜ ነገር ግን ተጽእኖው አሁን እንዳለ በሚያመለክት ሰዋሰዋዊ ቀመር ሲሆን መጥመቁ ዮሐንስ ግን በአላፊ ጊዜን ብቻ በሚያመለክት እና ተግባሩም የተጠናቀቀ ወደ አሁን ጊዜ የማይሻገር መሆንን በሚያመለክት የሰዋሰው ቀመር ነው። (ቁ6) ኢየሱስ ሁል ጊዜም የሚኖር ነው።

**1፡7 "ሁሉ በእርሱ በኩል እንዲያምኑ ነው"** ይህ ዓላማን የሚያመለክት ሀረገ ነው። የዮሐንስ ወንጌል እንደ ሌሎች ወንጌላት ሁሉ የወንጌል ትራክት ነው። ይህ እጅግ በጣም ጥሩ የሆነ የድነት የምስራን የሚያበስር ሲሆን ይህም የምስራች የሚሰራው የዓለም ብርሃን በሆነው በኢየሱስ በማመን ነው። (ቁ. 12፣ ዮሐ 3፡16፤ 4፡42፤ 20፡31፤ 1ጢሞ 2፡4፤ ቲቶ 2፡11፤ 2ጴጥ 3፡9፤ 1ዮሐ 2፡1፤ 4፡14 ጋር ያነጻጽሩ)።

**1፡7፣12 "እንነዲያምኑ"** ይህ ግስ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ 78 ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን 24 ጊዜ ደግሞ በዮሐንስ መልዕክቶች ውስጥ ተጠቅሷል። የዮሐንስ ወንጌል የዚህ ቃል ግሳዊ ይዘት እንጂ ስማዊ ይዘቱን ፈጽሞ አለመጠቀሙ የሚገርም ነው። ማመን በመጀመሪያ ደረጃ አእምሮዊ ወይም ስሜታዊ ነገር አይደለም ነገር ግን በፍቃደኝነት የሚደረግ ምላሽ ነው። ይህ ቃል በቁ 11 ላይ "መቀበል" እና ቁ 12 "መቀበል" ተብሎ ተተርጉሟል። ድነት ነጻ የእግዚአብሔር ስጦታ እና በኢየሱ ሥራ የተጠናቀቀ ነው ነገር ግን ይህንን የጠጠናቀቀ ስጦታ ግን መቀበል አለበት። ድነት የራሱ ጠቀሜታዎች እና ኃላፊነት ያለበት ቃል ኪዳናዊ ትስስር ነው።

**ልዩ ርዕስ፡ እምነት፣ ማመን ወይም ተአማኒ (ፒስቲስ (ስም)፣ ፒቴዎ (ግስ)፣ ፒስቶስ (ገላጭ)**

ሀ. ይህ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እጅግ ወሳኝ የሆነ ቃል ነው (ዕብ 11፡1፣6 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህ ቃል የኢየሱስ የመጀመሪያዎቹ ስብከቶች ማዕከላዊ ጭብጥ ነበር (ማር 1፡15 ይመልከቱ፡)። ቢያንስ ቢያንስ ሁለት ቃል ኪዳዊ ግዴታዎች አሉት ንስሓ እና እምነት (1፡15፣ ሐዋ 3፡16፣19፣ 10፡21 ጋር ያነጻጽሩ)

ለ. የቃሉ ሥረወ ግንድ

1. በብሉይ ኪዳን ይህ ቃል ያለው ትርጓሜ ታማኝት፣ የሚታመን የሚል ሲሆን የእግዚአብሔርን ባሕሪይ እንጂ የሰው ልጆችን ባሕርይ አያመለክትም።
2. ይህ ቃል የመጣው ከዕብራይስጡ (ኢሙን፣ ኢሙነሃ) ከሚለው ሲሆን ትርጓሜውም "እርግጠኛ መሆን ወይም መረጋጋት" ማለት ነው። የሚያድን እምነት የአንድ ሰውን አእምሮዊ (እውነቱን መቀበል)፣ ግብረገባዊ አኗኗርን (የኗኗር ዘይቤን) እና በዋነኝነት ትስስርን (መቀበልን) እና በፍቃደኝነት መስጠትን (ውሳኔን) ያካትታል።

ሐ. የብሉይ ኪዳን የቃሉ አጠቃቀም

የአብረሃም እምነት ስለ ወደፊቱ መሲሕ ሳይሆን ልጅ እንደሚኖረው እና ዘሩ እንደሚበዛ መሆኑን አጽኖት መስጠቱ አስፈላጊ ነው (ዘፍ 12፡2፤ 15፡2-5፤ 17፡4-8፤ 18፤14 ያነጻጽሩ)። አብረሃም ለተገባለት

የተስፋ ቃል በእግዚአብሔር አመነ፡፡ ከዚያን በኋላም ቢሆን ስለ ተስፋ ቃሉ ጥርጣሬዎች እና አንዳንድ ችግሮች ነበሩት፡፡ ይህም የተስፋ ቃል ፍጻሜን ለማግኘት ሠላሳ አመት ያክል ጊዜ ወስዶበታል፡፡ ፍጹም ያልሆነው እምነቱ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ በእምነት ለእርሱ እና ለተስፋ ቃሉ ምላሽ ለምሰጠው በራሱ መቆም ከማይችለው ሰው ልጅ ጋር እግዚአብሔር ለመስራት ፍቃደኛ ነው፤ ይህ ማለት ምንም እንኳ እምነቱ የሰናፍጭት ቅንጣት ታክል እንኳ ብትሆንም ማለት ነው (ማቴ 17:20 ይመልከቱ፡፡)፡፡

መ. የአዲስ ኪዳን የቃሉ አጠቃቀም

ፒስቲዎ የሚለው የግሪኩ ቃል "ማመን"፣ "እምነት" ተብሎ ልተረጎም ይችላል፡፡ ለምሳሌ ያክል የዚህ ቃል ስማዊ ይዘቱ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ አይገኝም ነገር ግን ዮሐንስ የተጠቀመው የቃሉን ግሳዊ ይዘት ነው፡፡ በ1ዮሐ 2:23-25 ድረስ ሕዝቡ የናዝሬቱ ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን ለመቀበበል እንደተቸገሩ ያመለክታ፡፡ የዚህ ቃል ታይታዊ አጠቃቀም ምሳሌ በዮሐ 8:31–59 እና ሐዋ 8:13፣ 18-24 ላይ መመልት ይቻላል፡፡ እውነተኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ከመጀመሪያው ምላሽ መስጠት ያልፋል፡፡ በደቀ መዝሙርነት ሂደት መደገፍ አለበት (ማቴ 13:20-22፣ 31-32 የሚሉትን ይመልከቱ፡፡)፡፡

ሠ. ከመስተአምር ጋር ቃሉ ስመጣ

1. ኤስ የሚለው የግሪክ መስተአምር ትርጓሜው "በ" ማለት ነው፡፡ ይህ ቃል ማመን ከምለው የግሪ ቃል ጋር ስመጣ ትርጓሜው በኢየሱስ ማመን ያመለክታል፡፡
   ሀ. በስሙ (ዮሐ 1:12፣ 2:23፣ 3:18 እና 1ዮሐ 5:13)
   ለ. በእርሱ (ዮሐ 2:11፤ 3:15፤ 4:39፤ 6:407:5፣ 31፣ 39፣ 48፤ 8:30፤ 9:36፤ 10:42፤ 11:45፣ 48፤ 17:37፣ ማቴ 18:6፤ የሐዋ 10:43፤ ፊል 1:29፤ 1ጴጥ 1:8)
   ሐ. በእኔ (ዮሐ 6:35፣ 7:38፤ 11:25፣ 26፤ 12:44፣ 46፤ 14:1፣12፤ 16:9፤ 17:20)
   መ. በልጁ (ዮሐ 3:36፤ 9:35፤ 1ዮሐ 5:10)
   ሠ. በኢየሱስ (ዮሐ 12:11፣ የሐዋ 19:4፣ ገላ 2:16)
   ረ. በብርሃን (ዮሐ 12:36)
   ሰ. በእግዚአብሔር (ዮሐ 14:1)
2. ኢን የሚለው የግሪክ መስተአምር "ውስጥ" የሚል ትርጓሜ አለው ዮሕ 3:15፣ ማር 1:15፣ የሐዋ 5:14
3. ኢፒ የሚለው የግሪክ መስተአምር "በእርሱ" የሚል ትርጓሜ አለው፡፡ ማቴ 27:42፣ የሐዋ 9:42፣ 11:17፣ 16:31፣ ሮሜ 4:5፣ 24፤ 9:33፤ 10:11፤ 1ጢሞ 1:16፣ 1ጴጥ 2:6
4. ካለ መስተአመር ስመጣ በገላ 3:6፣ ሐዋ 18:8፣ 27:25፣ 1ዮሐ 3:23፣ 5:10
5. ሆቲ የሚለው የግሪክ መስተአመር የሚያመለክተው "ምክንያትን" ሲሆን ምን እንደሚያምኑ ይገልጻል
   ሀ. ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቅዱሱ እንደሆነ (ዮሐ 6:69)
   ለ. ኢየሱስ እኔ እኔ ነኝ እንሆነ (ዮሐ 8:24)
   ሐ. ኢየሱስ በአብ እንዳለ እናም አብም በእርሱ እንዳለ (ዮሐ 10:38)
   መ. ኢየሱስ መስሑ እንደሆነ (ዮሐ 11:27፣ 20:31)
   ሠ. ኢየሱስ የእግዘኢብሔር ልጅ እንደሆነ (ዮሐ 11:27፣ 20:31)
   ረ. ኢየሱስ በአብ እንደተላከ (ዮሐ 11:42፤ 17:8፣21)
   ሰ. ኢየሱስ ከአብ ጋር የነበረ መሆኑን (ዮሐ 14:10-11)
   ሸ. ኢየሱስ ከአብ ጋር መምጣቱን (ዮሐ 16:27፣ 30)
   ቀ. ኢየሱስ ከአብ ቃል ኪዳናዊ ስም ጋር እራሱን አመሳስሏል "እኔ እኔ ነኝ" (ዮሐ 8:24፤ 13:19)
   በ. ከእርሱ ጋር እንኖራን (ሮሜ 6:8)
   ተ. ኢየሱስ ሞቶ ሞትን ድል ነስቶ መነሳቱ (1 ተሰ 4:14)

1:8 ኢየሱስ ስያስተምር ባልሰሙት ወይም ኢየሱስን በልተቀበሉ የመጥመቁ ዮሐንስ ተከታዮች መካከል የተነሳውን ውዝግብ ምክንያት በኋላ የተነሳውን ችግር ሐዋርያው ዮሐንስ ከሁለም የወንጌላት ጸሐፊት በኋላ በመጻፉ ምክንያት ተምልክቶ ሊሆን ይችላል (ሐዋ 18:25-19:7 ይመልከቱ፡፡)፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ ስለ ኢየሱስ ምስክርነት**
*ምስክር የሚለው ቃልን የሚያመልተው የግሪክ ቃል "ማርቱሪያ" (ስም) ሲሆን ግሱ ደግሞ "ማርቱሪዎ" ነው፡፡ እነዚህ ቃላት ለዮሐንስ ቁልፍ ቃላት ናቸው፡፡ ስለ ኢየሱስ የሚመሰክሩ ብዙ ሰዎች አሉ፡፡*

1. *መጥመቁ ዮሐንስ* (ዮሐ 1፡7፣8፣15፤ 3፡26፣28፤ 5፡33)
2. *ኢየሱስ እራሱ* (ዮሐ 3፡11፤ 5፡31፤ 8፡13-14)
3. *ሰማሪያዊቷ ሴት* (ዮሐ 4፡39)
4. *ኢግዚአብሔር አብ* (ዮሐ 5፡32፣34፣37፤ 8፡18፤ 1ዮሐ 5፡9)
5. *መጽሕፍ ቅዱስ* (ዮሐ 5፡39)
6. *አላዛር ከሞት ስነሳ የተመለከቱት ሰዎች* (ዮሐ 12፡17)
7. *መንፈስ ቅዱስ* (ዮሐ 15፡26-27፣ 1ዮሐ 5፡10፣11)
8. *ደቀ መዛሙርቱ* (ዮሐ 15፡27፣ 19፡35፣ 1ዮሐ 1፡2፤ 4፡14)
9. *ጸሓፊው እራሱ* (ዮሐ 21፡24)

**የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ 1፡9-13**
***ለሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛው ብርሃን ወደ ዓለም ይመጣ ነበር፡፡ በዓለም ነበረ: ዓለሙም በእርሱ ሆነ: ዓለሙም አላወቀውም፡፡ የእርሱ ወደ ሆነው መጣ: የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም፡፡ ለተቀበሉት ሁሉ ግን: በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤ እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም፡፡***

**1፡9 "እውነተኛ ብርሃን"** *በዚህ ስፍራ ላይ እውነተኛ ተብሎ የተጠቀሰው ዝም ብሎ ከውሸ ተቃራኒ መሆኑን ለማሳየት ሳይን ትክክለኛ መሆኑን ለማሳየት ነው፡፡ ይህ በመጀመሪያው ምዕተ አመት ውስጥ ከተነሱት ትክክለኛ ይልሆኑ ስነ ክርስቶሳዊ እሳቤዎች ጋር ይያያዛል፡፡ ይህ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ብዙ ጊዜ አገልግሎት ላይ የዋለ ገላጭ ቃል ነው* (3፡25፤ 4፡23፣37፤ 6፡32፤ 7፡28፤ 15፡1፤ 17፡3፤ 19፡35 *እና ዮሐ* 2፡8፤ 5፡20 *እና በራዕይ መጽሐፍ ቅስጥ ደግሞ አስር ጊዜ ያህል ተጥቅሷል*)፡፡ *በ በ*6፡55 *እና* 14፡17 *ላይ ያለውን እውነት የሚለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት፡፡ ኢየሱስ የዓም ብርሃን ነው* (3፡19፤ 8፡12፤ 12፡46፤ 1*ዮሐ* 1፡5፤ 2፡8፣910)፡፡ *አማኞች ደግሞ የእርሱ ብርሃን ያንጸባርቁ ዘንድ ይጠበቅባቸዋል* (*ፊል* 2፡15)፡፡ *ይህ በግኑዙ አለም ውስጥ በአመጽ ምክንያት የተፈጠረው ጨለማ ንጹሕ ንጽጽር ነው፡፡*

1. *ሰዎች*
2. *መላእክት*

▣ *"ወደ ዓለም ይመጣ ነበር" ዮሐንስ ይህንን ሀረግ አዘውትሮ የሚጠቀመው ኢየሱስ ሰማያዊውን ስፍራ ትቶ በሰአት እና በቦታ የተገደበውን ቁሳዊ ወደ ሆነው ዓለም መምጣቱን ለማመልከት ነው፡፡* (6፡14፤ 9፡39፤ 11፡27፤12፡46፤ 16፡28)፡፡ *ይህም ቁጥር የሚያመለክተው የኢየሱስን ትስብእት መሆንን ነው፡፡ ይህ አንዱ የዮሐንስ የሁለትዮሽ ገለጻ ነው (ይህ ማለት የላይኛው እና የታችኛው ብሎ ዮሐንስ እንደጻፈው ማለት ነው)፡፡*

▣

| | |
|---|---|
| NASB | *"ሰዎችን ሁሉ የሚያበራ"* |
| NKJV | *"ለሰዎች ሁሉ ብርሃን የሚሰጥ"* |
| NRSV | *"ሰዎችን ሁሉ የሚያበራ"* |
| TEV | *"በሰዎች ሁሉ የሚያበራ"* |
| NJB | *"ለሰዎች ሁሉ የሚያራው"* |

*ይህንን ሀረግ በሁለት መንገድ መረዳት ይቻላል፡፡ በመጀመሪያ የግሪካዊያንን ባሕላዊ ዳራ ቅድመ እሳቤ ውስጥ በማስገባት በሰዎች ሁሉ ውስጥ ያለ ውስጣዊ አብርሆትን፣ ሰማያዊ መገለጥን ያመለክታል ማለት ይቻላል፡፡ ክውከርስ የተባሉ ሰዎች ይህንን ሀረግ የሚተረጉምት እንድህ ባለ መንገድ ነው፡፡ ነገር ግን እንዲህ ያለው አመለካከት ፈጽሞ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ አይገኝም፡፡ ለዮሐንስ "ብርሃን" የሰው ልጆችን ክፋት የሚያጋልጥ ነው* (3፡19-21)

*ሁለተኛው ይህ ሀረግ ተፈጥሮአዊ መገለጥን አያመለክትም (ማለትም ሰዎች በተፈጥሮ አማካኝነት እግዚብሔርን ማወቅ የሚችሉበትን ማለት ነው (መዝ* 19፡1-5፣ *ሮሜ* 1፡19-20) *ወይም ውስጣዊ ግብረገባዊነትንም አያመለክትም (ሮሜ* 2፡14-15) *ነገር ግን እግዚአብሔር በልጁ አማካኝት ያዘጋጀውን እውነተኝ ብርሃን እና ድትን ነው የሚያመለክተው፡፡*

**1፡10 "ዓለም"** *ዮሐንስ "ኮስሞስ" የሚለውን ቃል የተጠቀመው በሦስት መንገድ ነው፡፡*

3. *ቁሳዊ ዓለምን ለማመልከት* (1፡10፣11፤ 11፡9፤ 16፡21፤ 17፡5፣24፤ 21፡25)
4. *ሰዎችን ሁሉ ለማመለክት* (1፡10፣29፤ 3፡16፣17፤ 4፡42፤ 6፡33፤ 12፡19፣ 42፤ 18፡29)
5. *የወደቀው የሰው ልጅ ማህበረሰባዊ አደረጃጀት እና ከእግዚአብሔር ውጭ የሚያደርጋቸው ነገሮች* (7፡7፤ 15፡18-19፤ 1*ዮሐ* 2፡15፤ 3፡1፣13)

በዚህ አውድ ውስጥ በተራ ቁጥር 2 ላይ የተሰጠው አማራጭ ከአውዱን ጋር ተስማሚ ነው። ልዩ ርዕስ 14:17 ይመልከቱ።

▣ ***"ዓለምም አላወቀውም"*** የወደቀው የሰው ልጆች የሆኑት አሕዛቦችም ሆነ የተመረጡት አይሁዳዊያ ኢየሱስ ተስፋ የተገባለት መስሑ እንደሆነ አላወቁም። "ማወቅ" የሚለው ቃል የዕብራዊያንን ምሳሌያዊ አነጋር የሚያመለክት ሲሆን ከአእምሮ እውቀት ይልቅ ግንኙነታዊ ቀረቤታን ያመለክታል (ዘፍ 4:1፣ ኤር 1:5)።

| |
|---|
| **ልዩ ርዕስ: ማወቅ (የዘዳግም መጽሐፍን እንደ እይታ መነጽር በመጠቀም)**<br>በዕብራይስጥ "ማወቅ" የሚለው ቃ የተለያዩ ትርጓሜዎች አሉ<br>1. መልካሙን እና ክፉውን መለየት - ዘፍ 3:22፤ ዘዳ 1:39፤ ኢሳ 7:14-15፤ ዮና 4:11<br>2. በመረዳት ማወቅ- ዘዳ 9:2፣3፣6፤ 18:21<br>3. በልምድ ማወቅ- ዘዳ 3:19፤ 4:35፤ 8:2፣3፣5፤ 11:2፤ 20:20፤ 31:13፤ ኢያ 23:14<br>4. እንደ አማራጭ መያዝ- ዘዳ 4:39፤ 11:2፤ 29:16<br>5. በግል ማወቅ<br>ሀ. ግለሰብብን- ዘፍ 29:5፤ ዘጸ 1:8፤ ዘዳ 22:2፤ 33:9<br>ለ. አምላክ- ዘዳ 11:18፤ 13:2፣6፣ 13፤ 28:64፤ 29:26፤ 32:17<br>ሐ. ያሕዌ- ዘዳ 4:35፣ 39፤ 7:9፤ 29:6፤ኢሳ 1:3፤ 56:10-11<br>መ. ግብረስጋዊ- ዘፍ 4:1፣ 17፣ 25፤24:16፤ 38:26<br>6. በመማር የተገኘ ክህሎት ወይም እውቀት - ኢሳ 29:11፣ 12፤ አሞ 5:16<br>7. አስተዋይ መሆን- ዘዳ 29:4፤ ምሳ 1:2፤ 4:1፤ ኢሳ 29:24<br>8. የእግዚአብሔር እውቀት<br>ሀ. ስለ ሙሴ - ዘዳ 34:10<br>ለ. ስለ እስራኤል- ዘዳ 31:21፣27፣ 29 |

**1:11 *"የእርሱ ወደ ሆነው መጣ: የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉት"*** በቁ. 11 ላይ "የእርሱ ወደ ሆኑት" የሚለው ሀሳብ ሁለት ጊዜ ተጠቅሷል። የመጀመሪያው የሚያመለክተው (1) ሁሉንም ፍጥረታት ወይም (2) ወደ ይሁዳ ወይም ኢየሪሳሌም መምጣቱን ሲሆን ሁለተኛው የሚያመለክተው ወደ አይሁዳዊያን መምጣቱን ነው።

**1:12 *"ለተቀበሉት ሁሉ ግን"*** ይህ ሀረግ የሚያሳየው በድነት ውስጥ የሰው ልጆች ድርሻ መኖሩን ነው (ቁ 16)። በክርስቶስ አማካኝነት ለቀረበላቸው ጸጋ የሰው ልጆች ምላሽ መስጠት አለባቸው። (3:16፤ ሮሜ 3:24፤ 4:4-5፤ 6:23፤ 10:9-13፤ ኤፌ 28-9 ይመልከቱ።)። እግአዚብሔር ሉአላዊ አምላክ መሆኑ እርግጥ ነው ነገር ግን ሉአላዊ አምላክ በመሆኑ ምክንያ ከወደቀው የሰው ልጅ ጋር በሁኔታዎች የተገደበ ቃል ኪዳናው ግንኙነት ጀመረ። የወደቀው የሰው ልጅ በመጀመሪያ ኃጢአቱን መናዘዝ፣ ማመን፣ ታዘዝ እና በእምነት ጸንቶ መቆም አለበት።

"መቀበል" የሚለው ይህ ሀሳብ "መናዘዝ" ከሚለው ሀሳ ጋር ስነ መለኮታዊ ትይዩነት አለው። ይህም በሰዎች ፊት በኢየሱስ ማመንን መግለጽን ይጠይቃል። (ማቴ 100:32፤ ሉቃ 12:8፤ ዮሐ 9:22፤ 12:42፤ 1 ጢሞ 6:12፤ 1ዮሐ 2:23፤ 4:15)። ድነት ሰዎች ልቀበሉት እና ልያምኑበት የሚገባ ስጦታ ነው።

በቁ. 12 ላይ ኢየሱስን "የተቀበሉ" እርሱን የላከውን አባቱን ተቀብለዋል ይላል። (5:43፤ 13:20)። ድነት ከአሃዱ ሥሉስ አምላክ ጋር ያለ ግላዊ ግንኙነት ነው።

▣ ***"ሥልጣንን ሰጣቸው"*** "ኤክዞሳ" የሚለው የግሪክ ቃል ትርጓሜ (1) ሕጋዊ ስልጣ ወይም (2) መብት ወይም ጥቅም ሊሆን ይችላል (5:27፤ 17:2፤ 19:10፣ 11) በኢየሱስ ልጅን እና መለኮታዊ ተልዕኮ አማካኝነት ወድቆ የነበረው የሰው ልጅ እግዚአብሔርን ማወቅ እና እርሱ እንደ አምላክ እና አባት ለመቀበል ችሏል።

▣ **"የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ"** የአዲስ ኪዳን ጸሐፍት ክርስትናን ለማመልከት ቤተሰባዊ ምሳሌዎችን አዘውትረው ይጠቀማሉ፡ (1) አባት፤ (2) ልጅ፤ (3) ዳግም መወለድ፤ እና (4) ጉድፈቻ። ክርስትና እንዲሁም ወደ ሰማይ መሄጃ ቲኬት ወይም የእሳት አደጋ ዋስትና ሳይሆን ከቤተሰብ ነባዊ ሁኔታ ጋር ተመሳሳይነት አለው። በክርስቶስ ያመኑት የመጨረሻው ዘመን "የእግዚአብሔር ሕዝቦች" ሆነዋ። እንደ ልጆች የአባታቸውን ባሕር ማሳየት ይጠበቅባቸዋል (ቁ 14፤ 3:16) ልጅ (ኤፌ 5:1፤ 1ዮሐ 2:19፤ 3:3)። ለኃጢአኞች ምንኛ የሚያስደነግጥ ማዕረግ ነው (1152፤ ሮሜ 8:14፣ 16፣ 21፤ 9:8፤ ፊል 215፤ 1ዮሐ 3:1፣ 2፣10፤ 5:2፤ ሆሴ 1:10 በሮሜ 9:26 እና 2 ቆሮ 6:18 ላይ እንደተጠቀሰው)።

በግሪክ ቋንቋ ልጅን ለማመልከት አገልግሎት ላይ የሚውሉ ሁለት ቃላት ስኖሩ ከሁለቱ ቃለት አንደኛው ለኢየሱስ ብቻ አገልግሎት ላይ ውሏል። (ሂዩስ) የሚለው ለኢየሱስ ብቻ ስውል ቴክና የሚለው ግን የክርስቲያኖችን ልጅነት ለማመልከት ውሏል። ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው ነገር ግን ልጅነታቸው የእግዚአብሔር ልጅ ከሆነው ከኢየሱስ ልጅ በሆነበት መንገድ አይደለም። እርሱ ከአባቱ ጋር ያለው ግንኙነት ልዩ ነው።

"ቤተ ክርስቲያን" (ኤክልሺያ) የሚለው ቃል በማርቆስ፣ በሉቃስ ወይም በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ዬለም። እነዚህ ጸሐፊት የተጠቀሙት የእነዚህ ግለዘቦችን ስብስብን የሚገልጽ እና በጋራ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በጋር የሚያደረጉትን ህረት የሚያመለክትን ምሳሌያዊ ንግግር ነው።

▣ "*ለሚያምኑት*" ይህ ሀረግ የሚያመለክተው በእምነታቸው የሚቀጥሉትን ነው። ይህንን ትርጓሜ እንድንዝ የሚረዳን የቃሉን ሥረወ ግንድ ማጥናት ነው። በዕብራይስጥ ይህ ቃል የሚያመለክተው ቋም የሆነ ሰው ነው። ከዚያም በኋላ ይህ ቃል ተአማኝ የሆነ ሰውን፣ የምታመን ሰውን መግለጫ መሆን ጀመረ። የዚህ ቃል የግሪክ አቻው በአማርኛ እምነት፣ ማመን የሚል ትርጓሜ አለው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት በመጀመሪያ እኛ የሚናደረግው ነገር ሳይሆን እምነታችንን የምንጥልበት ሰው ነው። የምታመነው እግዚኢብሔር ነው። የትኩረት አቅጣጫችን እኛ ሳንሆን እርሱ ነው። የወደቁት የሰው ልጆች የእግዚብሔርን ታማኝት ያምናሉ፣ የእርን ታማኝት ያምናሉ። ትኩረቱ የእምነታቸው መጠን አይደለም ነገር ግን የሚያምኑት ነገር ነው። ልዩ ርዕስ 1፡7 እና 2፡23 ይመልከቱ።

▣ "በስሙ" በብሉይ ኪዳን የሰዎች ስም እጅግ ጠቃም ነበር። ምክንያቱም የሰውዮውን ማንነት እና ባሕርይ የሚገልጽ ተስፋ/ሊሆን የሚችል ትንቢት ነው። በስሙ ማመን ማለት ሰውዮውን ማመን እና መቀበል ማለት ነው (2፡23፤ 3፡18፤ 20፡31፤ 1ዮሐ 5፡13)። ልዩ ርዕስ፡ የጌታ ስም በ15፡16 ላይ ይመልከቱ።

1፡13

NASB፣ NKJV፣

NRSV "ከደም፣ እንደ ሥጋ ፍቃድ ወይም በሰዎች ፍቃድ ያልተወለዱ"

TEV "በተለመደው መንገድ ከአባት በመወለድ የእግዚአብሔር ልች አልሆኑም"

NJB NJB "በሰዎች ፍላጎት ወይም ከሥጋ ምኞት ወይም በሰው ፍቃድ አልተወለዱም"

አንዷን የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አባቶች (ኤራኔዎስ፣ ኦሪገን፣ ትርቱሊያን፣ አምብሮስ፣ ጀሮም፣ ኦግስቲም) ይህ ሀረግ ኢየሱስን እንደሚያመለክት ተናግረዋል። ነገር ግን የሚያስገርመው የግሪክ ማስረጃዎች ይህ ሀረግ ብዙ ቁጥር አመልካች በመሆኑ ምክንያት ይህ ቁጥር የሚያመለክተው በኢየሱስ ያመኑ ሰዎች እንደሆ ነው (3፡5፣ 1ጴጥ 1፡3፣ 23)። ስለዚህም የዚህ ሀረግ ትርጓሜ የዘር ጥቅምን ወይም የሰው ልጅ በግብረስጋ ግንኙነት የተገኙ እንዳልሆኑ ነው ነገር ግን በልጁ ያመኑ የእግዚአብሔር ምርጦች እና ወደ እርሱ የቀረቡትን ሰዎችን ያመለክታል። ቁጥር 12 እና 13 በእግዚአብሔር ሉአላዊነት እና በሰው ልጅ መካከል ያን ቃል ኪዳናዊ ምዛናዊነትን የሚያመለክት ነው።

የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ 1፡14-18

***ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ: አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነው ክብሩን አየን። ዮሐንስ ስለ እርሱ መሰከረ እንዲህም ብሎ ጮኸ። ከእኔ በኋላ የሚመጣው እርሱ ከእኔ በፊት ነበረና ከእኔ ይልቅ የከበረ ሆኖአል፤ ስለ እርሱ ያልሁት ይህ ነበረ። እኛ ሁላችን ከሙላቱ ተቀብለን በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናልና ሕግ በሙሴ ተሰጥቶ ነበርና፤ ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ።መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፤ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው።***

1፡14 "*ቃልምሥጋ ሆነ*" የክርስትናን እምነት ከግሪኮች ኢአማኒያ አመለካከት ጋር ለመቀላቀል የሚሞክሩትን የግኖስቲኮችን አመለካከት ዮሐንስ በዚህ ሀረግ ይቃወማል። ስለ አማኑኤል የተደረገው ትንቢት ፍጻሜ (ኢሳ 7፡14) አማካኝት ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ሰው እና አምልክ ነበር (1 ዮሐ 4፡1-3)። እግዝኢብሔር በወደቁት የሰው ልጆች መካከል አደረ (በመካከላቸው ድንኳንን ተከለ)። ለዮሐንስ "ሥጋ" የሚለው ቃል የኃጢአት ባሕርን አያመለክትም። በጳውሎስ ጽሑፎች ውስጥ ግን ይህ ቃል ኃጢአታዊ ባሕርን ያመለክታል።

**ልዩ ርዕስ፡ ሥጋ (ሳርካ)**

ይህ ሰዋዊ ወይም ዓለማዊ መሥፈርትን ያመለክታል (1 ቆሮ 1፡20፤ 2፡6፣8፤3፡18)። ጳውሎስ "ሥጋ" የሚለውን ቃል የሚጠቀመው በተለያየ መንገድ ነው

የሰው ልጅ አካል (ሮሜ 2፡28፣ 1ቆሮ 5፡5፤7፡28)

የሰው ልጅ ዘር (አባት- ልጅ፤ ሮሜ 1፡3፤ 4፡1፤1 ቆሮ 10፡18)

የሰው ልጆችን ሁሉ በተመለከተ (1 ቆሮ 1፡26፣ 29)

በዘፍጥት 3 ላይ የሰው ልጆች በኃጢአት በመውደቃቸው ምክንያት የሰው ልጆች ድካም (ሮሜ 6፡19፣ 7፡18)

▣ "በእኛ *መካከል አደረ*" ይህ ሀረግ አይሁዳዊያ በምድረ በዳ በነበሩበት ወቅት የነበረውብ የመገናኛ ድንኳን ዳራ አለው (ራዕ7፡15፤ 21፡3)። አይሁዳዊያን ያንን በበረሃ የተንከራተቱበትን ጊዜ በእግዚአብሔር እና በኢስራኤል መካል የነበረ የ"ጫጉላ ሽርሽር" ጊዜ ብለው ይጠሩታል። እግዚአብሔር እንደዚያ ወቅት ወደ እስራአኤል ቀርቦ አያውቅም። በዚህ ጊዜ እስራኤላዊንን ይመራ የነበረው መለኮታዊ ዳመና "ሻከና" ይባላል የቃሉም ትርጓመ "ከእነርሱ ጋር ማደር" ማለት ነው።

▣ "ክብሩን አየን" የብሉይ ኪዳኑ ካቦድ (ክብር) አሁን ሰው ሆኖ ተገለጠ፤ ትስብእት ሆነ። ይህ የሚያመለክተው (1) በኢየሱስ ሕይወት ውስጥ የተወሰ ጊዜን ነው እነርሱም ኢየሱስ የተለወጠበትን ወይም እርገቱን (ይህ ማለት የሐዋርያት ምስክርነት፣ 2 ጴጥ 1፡16-17) (2) የማይታየው ያሕዌ አሁን መታየት እና ሙሉ በሙሉ ለመታወቅ ችሏል። ይህ ከዮሐ 1፡2-4 ጋር ተመሳሳይነት አለው። ይህ ከግኖስቲኮች በመንፈስ እና በቁስ መካከል ትልቅ ጠላትነት አለ ከምለው የስህተት አስተምህሮ በተቀራን የኢየሱስ አምላክነት ላይ ትልቅ አጽኖት ይሰጣል።

በብሉይ ኪዳን ላይ "ክብር" ተብሎ የተተረጎመው ቃል በመጀመሪያ የነበረው ትርጓሜ "ክብድት" ሲሆን ከዚያ በኋላ እዚህ ቃል ላይተጨማሪ ብርሃን እና አስፈርነት ታክሎበታል። (በመጀመሪያ በስና ተራራ ላይ የእግዚአብሔር ክብር ተገልጦ እንመለከታን፣ ዘጸ 13፡21-22፤ 24፡27፣ ኢሳ 4፡5፤ 60፡1-2)። እርሱ ብቻ ነው ክብር የሚገባው። ይህንን ክብር ለመመልከት የሰው ልጅ አይችልም። (ዘፍ 33፡17-23፣ኢሳ 6፡5)። እግዚአብሔር በእውነት ልታወቅ የሚችለው በክርስቶስ በኩል ብቻ ነው። (ኤር 1፡14፤ ማቴ 17፡2፣ ዕብ 1፡3፤ ያዕ 2፡1)።

"ክብር" የሚለው ቃል ትንሽ በዥታን ይፈጥራል

1. ከእግዚአብሔር ጽድቃ ጋር ይመሳሰላል
2. የእግዚአብሔር ቅድስና ወይም ፍጹምነት ልያመለክት ይችላል
3. የሰው ልጅ የተፈጠረበት የእግዚብሔርን መልክ ልያመለክት ይችላል (ይህ የሰው ልጆች መልክ በውድቀታቸው ምክንያት ልበላሽ ችሏል (ዘፍ 1፡26-27፣ 5፡1፤ 9፡6)።

ይህ ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ አግልግሎት ላይ የዋለው ያሕዌ በደመና አምሳሌ ለሕዝቡ ስገለጥ ነው (ዘጸ 16፡7፣ 10፤ ዘለ 9፡23፤ ዘኑ 14፡10)።

**ልዩ ርዕስ፡ ክብር (ዶክሳ)**

ክብር የሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሀሳብ ለመግለጽ እጅግ በጣም አስቸጋር ቃል ነው። የአማኞች ክብር ወንጌልን ይረዳ እና በእግዚአብሔር ያላቸቸውን ክብር ይረዱ ዘንድ እንጅ በራሳቸው አይደለም (1፡29-31፣ ኤር 9፡23-24)

በብሉይ ኪዳን ላይ "ክብር" ተብሎ የተተረጎመው ቃል በመጀመሪያ የነበረው ትርጓሜ "ክብድት" ሲሆን ከዚያ በኋላ እዚህ ቃል ላይተጨማሪ ብርሃን እና አስፈርነት ታክሎበታል። (በመጀመሪያ በስና ተራራ ላይ የእግዚአብሔር ክብር ተገልጦ እንመለከታን፣ ዘጸ 13፡21-22፤ 24፡27፣ ኢሳ 4፡5፤ 60፡1-2)። እርሱ ብቻ ነው ክብር የሚገባው። ይህንን ክብር ለመመልከት የሰው ልጅ አይችልም። (ዘፍ 33፡17-23፣ኢሳ 6፡5)። እግዚአብሔር በእውነት ልታወቅ የሚችለው በክርስቶስ በኩል ብቻ ነው። (ኤር 1፡14፤ ማቴ 17፡2፣ ዕብ 1፡3፤ ያዕ 2፡1)።

"ክብር" የሚለው ቃል ትንሽ በዥታን ይፈጥራል

1. ከእግዚአብሔር ጽድቃ ጋር ይመሳሰላል
2. የእግዚአብሔር ቅድስና ወይም ፍጹምነት ልያመለክት ይችላል
3. የሰው ልጅ የተፈጠረበት የእግዚብሔርን መልክ ልያመለክት ይችላል (ይህ የሰው ልጆች መልክ በውድቀታቸው ምክንያት ልበላሽ ችሏል (ዘፍ 1፡26-27፣ 5፡1፤ 9፡6) ይህ ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ አግልግሎት ላይ የዋለው ያሕዌ በደመና አምሳሌ ለሕዝቡ ስገለጥ ነው (ዘጸ 16፡7፣ 10፤ ዘለ 9፡23፤ ዘኑ 14፡10)።

▣

| | |
|---|---|
| NASB፣ NKJV | **"ከአባቱ ዘንድ የሆነ አንዲያ ልጅ ክብር"** |
| NRSV | **"የብቸኛ ልጅን ክብርን"** |
| TEV | **"እንደ አባት ብቸኛ ልጅ የተቀበልነው ክብር"** |
| NJB | **"እርሱ የአባቱ ብቸኛ ልጅ የመሆኑን ክብር"** |

"አንድ" (ሞኖጄኔስ) ማለት "የተለየ፣" "ተመሳሳይ የሆነ" (ዩሐ 3-16፡18፤1 ዩሐንስ 4-9፤ ኤፍ-ኤፍ-ብሩስ Answers to Questions፤ ገጽ 24-25ን ይመልከቱ) የላቲኑ ትርጉም (ቩልጌት) "አንድያ ልጅ" ብሎ ሲተረጉመው፤ የቀድሞዎቹ የእንግሊዘኛ ትርጉሞችም ይህን ተከትለውታል (ሉቃ 7-12፤8-42፤9-38፤ዕብ11-17ን ያስ) እዚህ ላይ ትኩረት የተደረገበት አንድ እና ለየት ማለትን እንጀ ፃታዊ መዋለድን አይደለም።

▣ "አባት" ብሉይ ኪዳን እግዚአብሔርን በቤተሰብ ምሳሌያዊ ቋንቋ በመጠቀም ይገልጻል

1. እስራኤል የምትባል ሀገር ብዙ ጊዜ የያሕዌ ልጅ እንደሆነች ይገለጻል (ሆሴ 11፡1፤ሚል 3፡17)
2. በዘዳግም መጽሐፍ ውስጥ እግዚአብሔር እንደ አባት ሆኖ ተጥቅሷል (1፡31)
3. በዘዳግም 32 እስራኤል "የእርሱ ልጆች" እና እግዚአብሔር ደግሞ "አባታቸው" እንደሆነ ተጥቅሷል--
4. ይህ ምሳሌያዊ ንግግር በመዝ 103፡13 እና በ68፡5 ላይ ተጠቅሷል (ወላጆች የሌላቸው አባት)
5. በነብያትም ዘንድ ተለመደ ነበር 9ኢሳ 1-2፤63-8፡- እስራኤል እንደ ልጅ፣ እግዚአብሔር እንደ አባት ተገለፀበት ኢሳ 63-16፤64-8፤ኤር 3-4፡19፤31-9)።

ይህንን ምሳሌያዊ ንግግር ኢየሱስ በመውሰድ ይበልጥ በማጎልበት የቤተሰባዊ ግንኙነትን ይበልጥ አጠንክሮታል በተለይም በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ዮሐ 1፡14፣ 18፤ 2፡16፤ 3፡35፤ 4፡21፣ 23፤ 5፡17፣ 18፣ 19፣ 20፣ 21፣22፣23፣ 26፣ 27፣ 36፣ 37 ፣ 43፣ 45፤ 6፡27፣ 32፣ 37፣ 44፣ 45፣ 46፣ 57፤ 8፡16፣ 19፣ 27፣ 28፣ 38፣42፣ 49፣ 54፤

10:15፣ 17፣ 18፣ 25፣ 29፣ 30፣ 32፣36፣ 37፣ 38፤ 11:41፤ 12:26፣ 27፣ 28፣ 49፣ 50፤ 13:1፣ 14:2፣ 6፣ 7፣ 8፣ 9፣ 10፣ 11፣ 12፣ 13፣ 16፣ 20፣ 21፣ 23፣ 24፣ 26፣ 28፣ 31፤ 15:1፣ 8፣9፣ 10፣ 15፣ 16፣ 23፣ 24፣ 26፤ 16:3፣ 10፣ 15፣ 17፣ 23፣ 25፣ 26፣ 27፣ 28፣ 32፤ 17:1፣ 5፣ 11፣ 21፣ 24፣ 25፤ 18:11፤ 20:17፣ 21!

▣ *"ሙሉ ጸጋ እና እውነት" የብሉይ ኪዳን ቃል የሆነው "ሄሴድ" (የቃል ኪዳን ፍቅር እና ታማኝነት) "ከኢሜዝ" (ከታማኝነት) ጋር በጥምረት መምጣቱ* በዘጸ 34:6፤ *ነህ* 9:17፣ *መዝ* 103:8 *ለይ የተገለጠ እና በደንብ የተብራራ ነው። እነዚህ ሁለት ቃላት በመዝ* 16:6 *ላይ በጥምረት ይገኛሉ። ይህ የኢየሱስን ባሕርይ በብሉይ ኪዳን ቋንቋ የሚገልጽ ነው። ልዩ ርዕስ* 6:55 *እና* 17:3 *ይመልከቱ።*

**ልዩ ርዕስ፡ ቸርነት (ሄሴድ)**

*ይህ የተለያዩ ትርጓሜዎች ያሉት ቃል ነው።*

*ሀ. ከሰዎች ጋር በተያያዘ መልኩ በእነዚህ ስፍራዎች ላይ አገልግሎት ላይ ውሏል።*
1. *ለሌሎች ሰዎች የሚደረግ ቸርነት* (ምሳሌ 1 ሳሙ 20:14፣ 2ዜና 24:22)
2. *ለተቸገሩት እና ለድሆች የሚደደር ቸርነት* (ምሳሌ ሚል 6:8)
3. *ፍቅ* (ኤር 2:2፣ ሆሴ 6:4)
4. *መገኘት* (ኢሳ 40:6)

*ለ. ለእግዚአብሔር አገልግሎት ላይ ስውል*
1. *ቃል ኪዳናዊ ታማኝት እና ፍቅር*
   - *ሀ. "ከጠላቶች እና ከችግር መታደግ"* (ኤር 31:3፤ ሕዝ 27:28፤ 9:9)
   - *ለ. "ሕይወትን ከሞት መታደግ"* (ኢዮ 10:12፤ *መዝ* 86:13)
   - *ሐ. "መንፈሳዊ ሕይወትን ማስነሳት"* (*መዝ* 119:41፣ 76፣ 88፣ 124፣ 150
   - *መ. "ከኃጢአት ማዳን"* (*መዝ* 25:7፣ 51:3)
   - *ሠ. "ቃል ኪዳኑን መጠበቅ"* (2ዜና 6:14፣ *ነህ* 1:5፣ 9:32)
2. *መለኮታዊ ባሕርይን ይገልጻል* (ዘጸ 34:6፣ *ሚክ* 7:20)
3. *የእግዚአብሔር ለጋስት (ችርነት)*
   - *ሀ. "እጅግ የበዛ መሆኑ"* (ነህ 9:17፣ 103:8)
   - *ለ. "እጅግ ትልቅ መሆኑ"* (ዘጸ 20:6፣ ዘዳ 5:10፣ 7:9)
   - *ሐ. "ዘላለማዊ መሆኑ"* (1 ዜና 16:34፣ 41፣ 2 ዜና 5:13፣ 7:3፣6፤ 20:21፤ *ዕዝ* 3:11)
4. *በቸርነት የተሞላ ተግባሩ* (2 ዜና 6:42፣ *መዝ* 89:2፣ ኢሳ 55:3፣ 63:7፣ ሰቆ ኤር 3:22)

**ልዩ ርዕስ፡ ማመን፣ እምነት እና ታማኝነት በብሉይ ኪዳን ውስጥ**

I. *መክፈቻ ቃል*

*ይህ የአዲስ ኪዳን እጅግ ወሳኝ ቃል ስነ መለኮታዊ ሀሳብ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ትርጓማ በግልጽ ልተቀመጠም።*

*የብሉ ኪዳን*
1. *የግለሰቦች እና የማህበረሰብ*
2. *የግለሰብ ግንኙነት እና ቃል ኪዳናዊ ትዕዛዝ*

*እምነት የግል እና የእለት ተእለት የኗኗር ዘይቤ ነው። በቃላት ምፍቻ ውስጥ ትርጓሜውን ከማስቀመጥ ይልቅ በሰዎች ሕይወት ውስጥ መግለጹ ቀላል ና። ይህ የሕይወት ዘይቤን በደንብ የሚገልጽልን ምሳሌ*
1. *አብረሃም እና ዘሮቹ*
2. *ዳዊት እና እስራኤል*

*እነዚህ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ተገናኝጀ ከዚያም ሕይወታቸው ሁሉ ፈጽሞ ተለወጠ። (ይህ ማለት ፍጹም የሆነ ኑሮን መኖር ጀመሩ ማለት ሳይሆን ቀጣይነት ያለው እምነት ኑሮን መኖር ጀመሩ)። መፈተናቸው ያላቸውን ድካም ስገልጥ ያላቸውን ጥንካሬ ደግሞ ያበረታል ነገር ግን ቅርበታቸው፣ በእምነት የተሞላው ግንኙነታቸው በጊዜያት ሁሉ ውስጥ ቀጣይነት አለው። በፈተና ይጠራል ነገር ግን በመሰጠታቸው እና በአኗኗር ዘይቤአቸው ይታያል።*

II. *ይህንን ለማመልት የተጠቀሙት ቃል ሥረግንድ*

*ሀ. አሜን*

1. *ግስ*
   - *ሀ. ማገዝ፣ መንከባከብ* (2 *ነገ* 101፣5፣ *አስ* 2:7፣ *ሰነ መለኮታዊ ያሆነ የቃሉ አጠቃቀም*)
   - *ለ. እርግጠኛ መሆን፣ ማጽነት፣ ታማኝት፣ ተአማኒነት*
     - (1). *ለሰዎች ኢሳ* 8:2፤ 53:1፤ *ኤር* 40:4
     - (2). *ለነገሮች ኢሳ* 22:23

(3) ለእግዚአብሔር ዘጸ 7፡9፣ 12፣ ኢሳ 49፡7፣ ኤር 42፡5

ሐ. ጸንቶ መቆም፣ ማመን

1. አብረሃም እግዚአብሔርን አመነ ዘፍ 15፡6
2. ኢስራኤላዊያ በግብጽ አመኑ ዘጸ 4፡31፤14፡31
3. ኢስራኤላዊያን እግዚአብሔር በሙሴ በኩል እደተናገራቸው አመኑ ዘጸ 19፡9፤ መዝ 106፡12፣ 24
4. አኃዝ እግዚአብሔርን አላመነም ኢሳ 7፡9
5. በእርሱ የሚያምን ኢሳ 28፡16
6. ስለ እግዚአብሔር በእውነት የሚነገረውን ማመን ኢሳ43፡10-12

2. ስም፡ ታማኝ (ዘዳ 32፡20፣ ኢሳ 25፡2፣ 26፡2)

3. ገላጭ፡ በእውነት፣ እስማማለሁ፣ እንደዚያው ይሁን (ዘዳ 27፡15-26፤ 1ነገ 1፡36፣ 1ዜና 16፡36፣ ኢሳ 65፡16፣ ኤር 11፡5፣ 28፡6)ይህ በብሉይ ኪዳን እና በአዲስ ኪዳን ውስጥ አሜንን የሚተካ ነው፡፡

ለ. አማት - ጽናት፣ ታማኝት፣ እውነት

1. ለሰዎች ኢሳ 10፡20፣ 42፡3፣ 48፡1
2. ለእግዚብሔር ዘጸ 34፡6፣ መዝ 117፡2፣ ኢሳ 38፡18፣ 19፤ 61፡8
3. ለእውነት ዘዳ 32፡4፣ 1 ነገ 22፡16፣ መዝ 33፡4፣ 98፡3፣ 100፡5፣ 119፡30፣ ኤር 9፡4፣ ዘካ 8፡16

ሐ. አሙኑሃ- መጽናት፣ ታማኝነት

1. ለእጅ- ዘጸ ፲፯፡፲፪
2. ለጊዜ ኢሳ 33፡6
3. ለሰዎች ኤር 5፡3፣ 7፡2፣ 3፣፣ 6፡28፣ 9፡2
4. ለእግዚአብሔር መዝ 40፡11፣ 88፡12፣ 89፡2፣ 3፣ 6፣ 9፤ 119፡138

III. ይንን የብሉይ ኪዳን ሀሳብ ጳውሎስ የተጠቀመበት መንገድ

ሀ. ጳውሎስ ስለ ያሕዌ እና ስለ ብሉይ ኪዳን ያለውዋ 9፤22፤26

ለ. ለእርሱ ስለ አሜን ያለው መረዳት አጋዥ የሆነለት ሁለት የብሉይ ኪዳን ምንባባት ድጋፍ አግኝቷል

1. ዘፍ 15፡6- የአብረሃም ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት (ዘፍ 12) በእምነት እንድኖር አድርጎታል (12-22)፡፡ ይህንን ሀሳብ ጳውሎስ በሮሜ 4 እና ገላ 3 ላይ ተጠቅሞበታል፡፡
2. ኢሳ 28-16- በእርሱ የሚያምኑበት (እግዚአብሔር የተፈተነ እና ፀንቶ የቆመ የማዕዘን ድንጋይ ነው)
   ሀ. ሮሜ 9-33፤ "አያፍሩም" "ወይም "አይፀፀቱም"
   ለ. ረሜ 10-11፤ ከላይኛው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

3. ዕባ 2፡4- የእግዚአብሔርን ታማኝነት የሚያውቁ ሰዎች እርሱን ታምነው ይኖራሉ (ኤር 7፡28)፡፡ ጳውሎስ ይህንን ክፍል በሮሜ 1፡17 እና ገላ 3፡11 ላይ ተጠቅሞበታለ (እድሁም ዕብ 10፡38)

IV. የጴጥሮስ የብሉይ ኪዳን አጠቃቀም

ሀ. የጴጥሮስ ውህደት

1. ኢሳ 8ለ14- 1ጴጥ 2፡8 (የመሰናከያ ዐለት)
2. ኢሳ 28፡16- 1 ጴጥ 2፡6 (የማዕዘን ድንጋይ)
3. መዝ 11፡22- 1ጴጥ 2፡7 (የተናቀው ድንጋይ)

ለ. እሳራኤል ልገልጽ ወደሚችል ልዩ ቃላት ስመለስ እንመለከታለን "የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉስ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ"

1. ዘዳ 10፡15፣ ኢሳ 42፡21
2. ኢሳ 61፡6፣ 66፡21
3. ዘጸ 19፡6፣ ዘዳ 7፡6

እነዚህ ሁሉ አሁን በክርስቶስ ላመኑ ክርስቲያኖች ተጠቅሟል፡፡

V. ይህንን ሀሳብ ዮሐንስ የተጠቀመበት መንገድ

ሀ. የአዲስ ኪዳን አጠቃቀም

"ማመን" የሚለው ቃል በግሪከኛ (ፒስቲዮ) ይባላል፡፡ ይም ቃል "ማመን"፣ "እምነት" ተብሎ ልተረጎም ይችላል፡፡ የዚህ ቃል ስማዊ ይዘቱ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ አገልግሎት ላይ ያልዋለ ሲሆን ግን ግሳዊ ይዘቱ ግን ብዙ ጊዜ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ በ1ዮሐ 2፡23-25 ሕዝቡ የኢሱስ መሲሕነትን ማመናቸው በእርግጠኝነት መናገር አይቻልም፡፡ ይህን ቃል በዘፈቀደ አገልግሎት ላይ የዋለበትን ሌላኛው ምሳሌ በዮሐ 8፡31-59 ላይ እና በሐዋ 8፡13፣ 18-24 ነው፡፡ እውነተኛ መስጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት በመጀመሪያ ምላሽ ከመስጠት ያልፋል፡፡ በደቀ መዝሙርነት ሂደት ውስጥ ማለፍ አለበት (ማቴ 13፡20-22፣ 31-32 ያነጻጽሩ)

ለ. ከመጽዓረ ቃል ጋር ስመጣ

1. ኤሲ የሚለው የግሪክ መጻረቃል ትርጉም "በ" ማለት ሲሆን ይህ መጻረቃል ከእምነት ጋር ስመጣ የሚያመለክተው በኢየሱስ ማመናቸውን ነው፡፡
   ሀ. በስሙ (ዮሐ 1፡12፣ 2፡23፣ 3፡18፣ 1ዮሐ 5፡13)

ለ. በእርሱ (ዮሐ 2፡11፣ 3፡15፣ 18፣ 4-39፣ 6፡40፣ 7፡5፣ 31፣ 39፣ 48፣ 8፡30፣ 9፡36፣ 10፡42፣ 11፡45፣ 48፣ 17፡37፣ 42፣ ማቴ 18፡6፣ ዮሐ 10፡43፣ ፊል 1፡29፣ 1ጴጥ 1፡8)

ሐ. በእኔ (ዮሐ 6፡35፣ 7፡38፣ 11፡25፣ 26፣ 12፡44፣ 46፣ 14፡1፣ 12፣ 16፡9፣ 17፡20)

መ. በልጁ (ዮሐ 3፡36፣ 9፡35፣ 1ዮሐ 5፡10)

ሠ. በኢየሱስ (ዮሐ 12፡11፣ የሐ 19፡4፣ ገላ 5፡፡10)

ረ. በብርሃን (ዮሐ 12፡36)

ሰ. በእግዚአብሔር (ዮሐ 14፡1)

2. "ኤን" የሚለው ተግሪክ ምጸረቃል "ውስጥ" የሚል ትርጓሜ በዮሐ 3፡15፣ በማር 1፡15፣ በሐዋ 5፡14 ላይ አለው፡፡
3. "ኤፒ" የሚለው የግሪክ መጻረቃል "ውስጥ" ወይም "በ" የሚል ትርጉም አለው፡፡ ማቴ 27፡42፣ ሐዋ 9፡42፣ 11፡17፣ 16፡31፣ 22፡19፣ ሮሜ 4፡5፣ 24፣ 9፡33፣ 10፡11፣ 1ጢሞ 1፡16፣ 1ጴጥ 26
4. በገላ 3-6፤ ሐዋ18-18፤27-25፤ 1ዩሐንስ 3-23፤5-10 ለይ መስተዋድድ ሳይኖር በተሳቢነት ያገለግላል::
5. እምነትን የሚያመለክተው ግሪክ ቃል "ሆቲ" ከሚለው ምጻረቃል ጋር ከመጣ ትርጓሜው "ታምኑ ዘንድ" የሚል ይሆና

ሀ. ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ (ዮሐ 6፡69)

ለ. ኢየሱስ እኔ ነኝ ነው (ዮሐ 8፡24)

ሐ. ኢየሱስ በአብ ውስጥ ነው አብም በእርሱ ውስጥ ነው (ዮሐ 10፡38)

መ. ኢየሱስ መስሑ ነው (ዮሐ 11፡27፣ 20፡31)

ሠ. ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው (ዮሐ 11፡27፣ 20፡31)

ረ. ኢየሱስ የተላከው በአባቱ ነው (ዮሐ 11፡42፣ 17፡8፣ 21)

ሰ. ኢየሱስ ከአባቱ ጋር የነበረ ነው (ዮሐ 14፡10-11)

ሸ. ኢየሱስ ከአባቱ ዘንድ ነው የመጣው (ዮሐ 16፡27፣ 30)

ቀ. ኢየሱስ እራሱን የአብ የቃ ኪዳን ስም በሆነው ጠርቷል (ዮሐ 8፡24፣13፡19)

በ. ከእርሱ ጋር እንኖራለን (ሮሜ 6፡8)

ተ. ኢየሱስ ሞቶ ሞትን ድል ነስቶ ነስቷል (1 ተሰለ 4፡14)

VI. *ማጠቃለያ*

*መጽሐፍ ቅዱሳዊው እምነት ከመለኮታዊ ቃል/ተስፋ የሰው ልጆች ምላሽ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሁል ጊዜም የመጀመሪን ድርሻ የሚወስድ* (የሐ 6፡44፣ 65) *ሲሆን የእርሱ መለኮታዊ ተግባቦት የሰው ልችን ምላሽ ይጠባበቃ፡፡*

*ሀ. ማን*

*ለ. ቃል ኪዳናዊ መታዘዝ*

*መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት*

1. *ግላዊ ግንኙነት* (*የመጀመሪያው እምነተ*)
2. *መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን መቀበል* (*በእግዚአብሔርን መገለጥ ማመን*)
3. *ለእርሱ በመታዘዝ ተገቢ የሆነ ምላሽ መስጠት* (*የእለት ተዕለት እምነት*)

*መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት መንግስተ ሰማያት መግቢያ ትኬት አይደለም ወይም የኢንሹራን ፖልሲ አይደለ፡፡ ነገር የግል ግንኙነት ነው፡፡ ይም እግዚአብሔር የሰው ልጆችን በእርሱ አምሳል እና መልክ የመፍጠሩ ዋነኛ አለማ ነው* (ዘፍ 1፡26-27)፡፡ *ይህ "የቅርበት" ጉዳይ ነው፡፡ እግአዚብሔር የተወሰነ ስነ መለኮታዊ አቋም እዲኖረን ሳይሆን ከእርሱ ጋር ሕብረት እንድኖረን ይፈልጋል፡፡ ነገር ግን ከቅዱስ እግዚአብሔር ጋር ሕብረት ማድርግ "የቤተሰብን" ልጆች ባሕርይን ማሳየትን ይጠይቃል፡፡* (*ቅድስና ከዘላ* 19፡2 *ጋር ያነጻጽሩ፤ ማቴ* 5፡48፣ *1ጴጥ* 115-16)፡፡ *የሰው ልጆች በኃጢአት መውደቃቸው በአግባቡ ምላሽ መሸጠት የሚችበትን ችሎታ አበላሸ* (ዘፍ 3)፡፡ *ስለዚህም እግዚአብሔር በእኛ ፈንታ በመንቀሳቀስ* (ሕዝ 36፡27-28) *"አዲስ ልብን" እና "አዲስ መንፈስን" በእምነት እና በንሰሓ ከእርሱ ጋር ሕብረት ማድርግ እንችል እና እንታዘዘው አንድ ሰጠን፡፡*

*ሶስቱም እጅግ በጣም ጠቃሚ ናቸው፡፡ ሶስቱም መጠበቅ አለባቸው፡፡ አላማው እግዚብሔር ማወቅ ነው እንዲሁም በሕይወታችን የእርሱን ባሕርይ እናንጸባርቅ ዘንድ ነው፡፡ የእምነት ግብ አንድ ቀን ወደ ሰማይ እንሄድ ዘንድ አይደለም ነገር ግን በየእለቱ ክርስቶስን እንመስ ዘንድ ነው!*

*ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ለማድርግ የሰው ልች ታማኝነት መሰረት ሳይሆን ውጤት ነው፡፡ የአዲስ ኪዳን የድነት አመላካከት ማእከል የሰው ልጆች በመጀመሪያ ምላሽ መስጠት አለባቸው ሲሆን እንዲሁም በክርስቶስ የታየውን ጸጋ እና ምህረት በቀጣይነት ማሳየት ነው፡፡ ወዶናል፣ ልኮናል እንዲሁም የሚያስፈልገን ሁሉ ስለሰጠን በእምነት እና በታማኝነት ምላሽ መሸጠት አለብን፡፡* (ኤፌ 2፡8-9 እና 10)

*ታማኝ የሆነው እግዚአብሔር እራሱን ታማኝ ላልሆኑት ለመግለጥ እና በእርሱ እንዲያምኑ ለማድረግ ታማኝ የሆኑ ሰዎችን ይፈልጋል፡፡*

**1፡15 "እርሱ ከእኔ በፊት ነበረ"** ይህ የመጥመቁ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ ዘላለማዊነት ያለው ጥንካራ አስትምህሮ መገለጫ ነው፡፡ (1፡1፣ 8፡56,59፣ 16፡28፣ 17፡5፣ 2ቆሮ 8፡9፣ ፊል 2፡6-7፣ ቆላ 1፡17፣ ዕብ 1፡3፣ 10፡5-8)፡፡ የኢየሱስ ዘላለማዊነት

አስምህሮ እና ቅድመ ትንብቶች ከታርክ በላይ የሆነ አምላክ እንዳለ ያስተምራሉ፡፡ ነገር ግን ይህ አምላክ በታርክ ውስጥ ይሰራል፡፡ ይህ የክርስና/የመጽሐፍ ቅዱስ ንጽረጸ ዓለም አካል ነው፡፡

▣ ይህንን ቁጥር ግልጽ ለማድረግ ብዙ ለውጦች በቁጥሩ ላይ በጽሐፊዎች አማካኝነት ተደርዋል፡፡ ይህንን ለመረዳት ብሩስ ኤም. ሜዝገር የተባለው ሰው የጻፈውን A Textual CommeNtary pN the Greek New TestameNt የተባለውን መጽሐፍ ገጽ 197-198 ይመልከቱ፡፡

እንዲሁም ደግሞ የግሪክ ቋንቋ ጊዜ አመልካች ግሦች እንዴት መመዘኛ ሊሆኑ እንደማይችሉ ጥሩ ምሣሌ ሊሆን የሚችል ነው፡፡

1፡16-18 የዮሐንስ ወንጌል አንዱ መገለጫው ታሪካዊ ድርጊቶችን፣ ንግግሮችን፣ ትምህርቶችን ወይም ስብከቶችን ከራሱ አስተያየት ጋር አጣምሮ ማቅረቡ ነው፡፡ በኢየሱስ፣ በሌላኘው ሰው እና በዮሐንስ ሀሳብ መካከል ልዩነት ማድርግ እጅግ አዳጋች ነው፡፡ ብዙ የስነ መለኮት ምሁራን ቁጥር 16-19 ያለውን ክፍል የጸሓፊው የዮሐንስ አስተያየት እንደሆነ ይስማማሉ (3፡14-21)፡፡

1፡16 **"ከሙላቱ"** ይህንን የሚያመለክተው የግሪክ ቃል "ፕሌሮማ" ይባላል፡፡ ይህ በኖስቲኮች ተብለው በሚጠሩ የስህተት ትምህርት አስተማሪዎች አማካኝነት በትልልቆቹ መላእክት እና በትንንሾቹ መንፈሳዊ አካላት መካከል ያለውን ልዩነት ያሳያል፡፡ በሰዎች እና በእግዚአብሔር መካከል መካከለኛ የሆነው ኢየሱስ ብቻ በው (ይህ ማለት እውነት እና በሙላት ማለት ነው(፡፡ (ቆላ 1፡19፣ 2፡9፣ ኤፌ 1፡23፣ 4፡13 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡ በዚህ ስፍራ ላይም ዮሐንስ ኖስቲኮች ስለ ገዛዱ አለም ያላቸውን እውነታ እየተቃወመ ነው፡፡

▣

| | |
|---|---|
| NASB፣ NRSV | **"እንዲሁ በጸጋ ላይ ጸጋን"** |
| NKJV | **"እንዲሁም ከጸጋ ወደ ጸጋ"** |
| TEV | **"ከአንዱ ወደ አንዱ ባርኮት ተሰጥቶናል"** |
| NJB | **"አንዱ ስጦታ ሌላውን ስጦታ ተክቶታል"** |

ይህን ክፍል ለመረዳት የሚያግዘን ጥያቄ "ጸጋ" የሚለውን ቃል እንዴት ነው የምንረዳው፡፡ ይህ ማለት

1. ለድነት የሚሆን በክርስቶስ የሆነልን የእግዚአብሔር ምህረት ነውን
2. ለክርስቲያናዊ ሕይወት የሚያስፈልግ የእግዚአብሔር ምሕረት
3. በአዲስ ኪዳን ውስጥ በክርስቶስ በኩል የሚገኝ የእግዚአብሔር ምህረት

ዋናው ሀሳብ "ጸጋ" የሚለው ነው፤ የእግዚአብሔር ጸጋ በኢየሱስ ትስታብእ በሚያስገርም ሁኔታ ተሰጥቷል፡፡ ለወደቀው የሰው ልጅ ኢየሱስ የእግዚአብሔር "አዎንታ" ነው (2ቆሮ 1፡20 ያነጻጽሩ)፡፡

1፡17 **"ሕግ"** የሙሴ ሕግ መጥፎ አልነበር ነገር ግን ማዘጋጃ እና ድነትን በተመለከተ ሙሉ ድነት ለመስጠት በቂ አልነበርም፡፡ (5፡39-47፣ ገላ 3፡23-29፤ ሮሜ 4 ያነጻጽሩ)፡፡ ከዚህ በተጨማር የዕብራዊያን መልዕክትም በሙሴ እና በኢየሱስ መካከል ያለውን ሥራ/ መገለጥ/ቃል ኪዳን ያነጻጽራል፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ ጳውሎስ ስለ ሙሴ ሕግ የነበረው አመለካከት**

ሕግ መልካም እና ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠ ነበር (ሮሜ 7፡12፣ 16 ያነጻጽሩ)

ሀ. ወደ ጽድቅ የሚያመረን መንገድ አይደለም እንዲሁም በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት የሚንከተለው አይደለም (መረገም ሊሆንብ ይችላል ገላ 3 ጋር ያነጻጽሩ)

ለ. አሁንም ቢሆን እግዚአብሔር ለአማኞች ያለው ፍቃድ ይህ ነው ምክንያቱም የእግዚአብሔር ድነት ስለሆነ (ጳውሎስ አማኞችን ለመውቀስ እና ለመገሰጽ ብዙ ጊዜ ብሉይ ኪዳንን ይጠቀማ)

ሐ. አማኞች በብሉይ ኪዳን ብዙ ትምህርት ያገኛሉ (ሮሜ 4፡23-24፤ 15፡4፤ 1ቆሮ 10፡6፣11) ነገር ግን በብሉይ ኪዳን ግን ድነትን አያገኙም (ሐዋ 15፤ ሮሜ 4፣ ገላ 3፣ ዕብ)

መ. በአዲስ ኪዳን እነዚህን ግልጋሎቶች ይሰጣል፡

1. ኃጢአትን ያሳያል (ገላ 3፡15-29)
2. ለተዋጀውን የሰው ልጅ በማህረሰቡ ውስጥ ምሪትን ይሰጣል
3. ለክርስቲያኖች ክርስቲያናዊ ስነ ምግባር የተሞላበት ውሳኔን እንድያስተላልፉ ይረዳል፡፡

ይህ በስነ መለኮት ውስጥ ከእርግማን ወደ ባርኮት እና ጠቃሚነት መሸጋገር የሚታይ ጽንፍ ሲሆን ጳውሎስ ስለ ሙሴ ሕግ ያለውን መረዳት ለመገንዘብ በጣም አዳጋች ነው፡፡ ጀምስ ስትዋርት የተባለ ሰው A MaN iN Christ፤ በተሰኘ መጽሓፉ የጳውሎስን እርስ በእርሳቸው የሚጋጩ የሚመስሉ አስተሳሰቦች እና ጽሑፎችን ገልጸዋል፡፡

"አንድን አመለካከት እና አስተምህሮን በማዳበር ላይ ያለ አንድ ሰው በተለመደው ሁኔታ የሚጠቀመውን ቃል በተቻለው መልኩ ግለጽ በሆነ እና በማያሻ መልኩ ያስቀምጣል፡፡ የመልክቱን ዋና ሀሳብን የያዘውን ቃል በተቻለው መልኩ በማያሻማ መልኩ ለማስቀመጥ ጥረት ያደርጋል፡፡ በአንድ መጽሐፍ ውስጥ ቃሉ የሚኖረው ፍች በሁሉም

መጽሐፍት ውስጥ ተመሳሳይ ፍች ይኖራቸዋል፡፡ ነገር ግን ከጳውሎስ ጽሑፎች ውስጥ እነዚህን ለመመለክት ብትሙክሩ ተስፋ አስቆራጭ ይሆንባችኋል፡፡ ብዙ ቃላቶቹ ቋምነት የሚጎላቸው ናቸው፡፡ "ሕግ ቅዱስን" ነው ብሎ በአንድ ስፍራ ላይ ይጽፋል፤ "በእግዚአብሔር ሕግ በአእምሮዬ እደሰታለሁ" በማለት ይገልጻል (ሮሜ 7፡21፣ 22) ነገረ ግን በሌላ ስፍራ ላይ ደግሞ የሕግን ሌላኛውን ገጽታ በመግለጽ "ክርስቶስ ከሕግ እርግማን ዋጅቶናል" በማለት ይጽፋል፡፡ (ገላ 3፡13)፡፡

▣ "ጸጋ" በኃጢአት ለወደቁት ለሰው ልጆች የእግዚአብሔር ያልተገባ ፍቅር ነው (ኤፌ 2፡8)፡፡ ጸጋ (ካሪስ) የተሰኘው ቃል በጳውሎስ ጽሑፎች ውስጥ እጅግ ጠቃሚ ቢሆንም በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው በዚህ ስፍራ ላይ ብቻ ነው (1፡14፣ 16፣ 17 ይመልከቱ፡፡)፡፡ የአዲስ ኪዳን ጸሓፊት በመንፈስ ቅዱስ ምርት አማካኝነት የፈለጉት ቃላት፣ ምሳሌ እና ብህሎችን ተጠቅመው ጽፈዋል፡፡

በኤር 31፡31፤ ሕዝ 36፡22-28 ያለውን "የአዲስ ኪዳን" እውነትን ኢየሱስ እውን ልያርግ ችሏል፡፡

▣ "እውነት" ይህ ቃል አገልግሎት ላይ የዋለው (1) ታማኝነትን ወይም (2) እውነት እና ሐሰትን ለማነጻጸር ነው (1፡14፤ 8፡32፤ 14፡6)፡፡ አስተውሉ እውነትን እና ጸጋ፤ ሁለቱም የመጡት በኢየሱስ በኩል ነው (ቁ 14)፡፡ በ17፡3 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልቱ፡፡

▣ "ኢየሱስ" በመቅደሙ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ለማሪያም ልጅ ሳዊዊ ስም አገልግሎት ላይ የዋለበት ሥፍራ ነው፡፡ ቀድሞ ይኖር የነበው ልጅ አሁን የትስብእት ልጅ ሆነ!

**1፡18 "መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም"** አንዳንዶች ይህ ሀሳብ በዘጸ 33፡20-23 ካለው ሀሳብ ጋር ይጋጫል ይላሉ፡፡ ነገር ግን በዘጸአት መጽሐፍ ውስጥ የሚንመለከተው የዕብራይስጥ ቃል የሚያመለክተው "ጥላ" እንጅ እግዚአብሔር በአካል መመልከትን አይደለም፡፡ የዚህ ክፍል መልዕክት እግዚብሔርን በሙላት የገለጸው ኢየሱስ ብቻ መሆኑ ነው (14፡8)፡፡ ኃጢአተኛ የሆነው ማንም የሰው ልጅ እግዚአብሔርን አላየውም (6፡46፤ 1ጢሞ 6፡16፣ 1ዮሐ 4፡12፣ 20 ይመልከቱ፡፡)፡፡

ይህ ቁጥር የናዝሬቱ ኢየሱስ የእግዚአብሔርት ልዩ መገለጥ መሆኑ ላይ አጽኖት ይሰጣል፡፡ እርሱ የመለኮት ብቸኛ እና ሙሉ መገለጥ ነው፡፡ ኢየሱስን ማወቅ ማለት እግዚአብሔርን ማወቅ ማለት ነው፡፡ ኢየሱስ የአብ የራሱ የመጨረሻ መገለጥ ነው፡፡ ከእርሱ በስተቀር መለኮትን መረዳት አይቻልም (ቆላ 1፡15-19፣ ዕብ 1፡2-3 ያነጻጽሩ)፡፡ ኢየሱስን አብን "አይቷል" እንዲሁም አማኞችም በእርሱ አማካኝነት አብን "ያያሉ" (በሕይወቱ፣ በቃሉ እና በተግባራቱ)፡፡ እርሱ የማይታየው አምላክ ሙሉ መገለጥ ነው (ቆላ 1፡15፣ ዕብ 1፡3 ይመልከቱ፡፡)፡፡

▣

| | |
|---|---|
| NASB፣ | "ብቸኛው አምላክ" |
| NKJV | "ብቸኛው ልጅ" |
| NRSV | "የእግዚብሔር ብቸኛው ልጅ" |
| TEV | "ብቸኛው ልጅ" |
| NJB | "ብቸኛ ልጅ የሆነው" |

በሞኖጋኔስ በ1፡14 ላይ የተሰጠውን ማብራሪያ ተመልከት፡፡ ኢየሱስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነው፡፡ ሙሉውን ማብራሪያ በ1፡1 ላይ ይመልከቱ፡፡

በዚህ ስፍራ ላይ በግሪክ የመጀመሪያ ቅጅዎች መካከል ልዩነት አለ፡፡ ቴዎስ/አምላክ የሚለው ቃል p[66] p[75] እና c "አምላክ" በሚለው ስፍራ ላይ "ልጅ" በሚለው ተተክቷል፡፡ ዩብኤስ[4] "አምላክ" ለሚለው "ቢ" የሰጠው ሲሆን (ይህ የሚያመለክተው ለእውታው የተቃረበ መሆኑን ነው)፡፡ "ልጅ" የሚለው ቃለ የመጣው ምናልባትም ጸሓፊቱ በዮሐ 3፡16፣ 18 እና በ1ዮሐ 4፡9 ላይ ያለውን ቃል በማስታወሳቸው ሊሆን ይችላል (Bruce M. Metzger's A Textual CommeNtary oN the Greek Nw TestameNt p 198 ይመልከቱ፡፡)፡፡ ይህ የኢየሱስ አምላክነትን ሙሉ ለሙሉ የሚያረጋግጥ ክፍል ነው፡፡ ምናልባትም በዚህ ክፍል መሰረት ኢየሱስ ሦስት ማዕረጎች አሉት (1) ብቸኛው ልጅ (2) አምላክ እና (3) በአባቱ እቅፍ ያለው ፡፡

ትክክለኛ የሆኑ ጸሓፍት በዲ ውስጥ ያለውን ለውጠውት ሊሆን ይችላል የሚል ከፍተኛ ማብራሪያ የተሰበት የኢሃሪማ መጽሐፍ አለ *The Orthodox CorruptioN of Scripture*, p. 78-82 ይመልከቱ፡፡

▣ "በአባቱ እቅፍ ያለ" ይህ "ከእግዚአብሔር ጋር" የሚል ትርጓሜ ከአለው በቁጥር 1 እና 2 ላይ ከሚገኘው ሀሳብ ጋር ይመሳሰላል፡፡ ይህ ያላቸውን የጠበቀ ቅርርብ ያሳያል፡፡ እንዲሁም (1) የእርሱ ቅድመ መገኘታዊ ህብረት እና (2) እንደገና የታደሰው ግንኙነት (ማለት ከትንሳዔ በኋላ ያለውን) ልያመለክት ይችላል፡፡

▣

| | |
|---|---|
| NASB፣ | "እርሱ አስረዳ" |
| NKJV | "እርሱ ገለጠው" |

NRSV፣ NJB "እንድታወቅ ያደረገው እርሱ ነው"
TEV "እርሱ እንድታወቅ አደረገው"

ኤክስጂሰስ የተባለው የእንግልዘኛ ቃል ያገኘነው በ1፡18 ላይ ከተገለጸው የግሪክ ቃል ነው፤ ትርጓሜውም ሙሉ እና ፍጹም የሆነ መገለጥ ማለት ነው፡፡ የኢየሱስ ዋነኛ ሥራ አብን መግለጥ ነው (ዮሐ 14፡7-10፣ ዕብ 1፡2-3)፡፡ ኢየሱስን ማየት እና ማወቅ ማለት አብን ማወቅ እና ማየት ማለት ነው፡፡ (ይህም ኃጢአተኞችን መውደድ፣ ደካሞችን መርዳት፣ የተገለሉትን መቀበል፣ ሕጻናትን እና ሴቶችን መቀበል ማለት ነው፡፡)፡፡

ይህ ቃል በግሪክ የሚያመለክተው መልዕክትን፣ ሕልም ወይም መረጃዎችን የሚያብራሩ እና ትርጓሜን ለሚሰጡ ሰዎችን ነው፡፡ በዚህ ስፍራ ላይ ለአይሁዳዊያን እና ለአሕዛብ ለሁለቱም ትርጉም በምሰጥ መልኩ ተጠቅሞት ይሆናል፡፡ (እንደ ሎጎስ ሁሉ ማለት ነው)፡፡ በዚህ መቅደም ውስጥ ዮሐንስ ለአይሁዳዊያን እና ለአሕዛብ መልዕክት እያስተላለፈ ይገኛል፡፡ ይህ ቃል ከዚህ በታች የተጠቀሱት ልያመለክት ይችላል፡

1. ለአይሁዳዊያን ሕግን የሚያስረዳ ወይም የሚተረጉም
2. ለአሕዛብ አማልክትን የሚያስዳ ማለት ሊሆን ይችላል፡፡

ኢየሱስ እና በእርሱ ብቻ ሰዎች አብን ማየት የሚችት፡፡

### የውይይት ጥያቄዎች

ይህ <u>ምሪትን</u> የሚሰጥ የመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻ ነው፤ ይህም ማለት ለምትደረስበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ኃላፊነት የምትወስደው አንተ እራስ ትሆናህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን ባለን ብርሃን መጠን ልንመላለስ ይገባል ማለት ነው፡፡ በስነ አፍታት ሂደት ውስጥ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ዋነኛውን ስፍራ ትይዛላችሁ፡፡ ይህንን እድል ለመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻዎች አሳልፈህ አትስጥ፡፡

እነዚህ የመወያያ ጥያቄዎች በመጽሐፉ ውስጥ ይህንን ክፍል እንድትረዳ ያግዙሃል፡፡ እንድታስብ የሚያደርጉህ እንጂ የሚገድቡህ እንዲሆኑ አልታሰቡም፡፡

1. ሎጎስ ተርጉም እዲሁም የጥንት ሃይማኖታዊ፣ አለማዊ እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጉሙን ግለጽ፡፡
2. የኢየሱ የቅድመ መገኘት አስተምህሮ ይህን ያል በጣም አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት ምንድነው?
3. የሰው ልጆች በድነት ውስጥ ያላቸው ድርሻ ምንድነው፤ አንድ ሰው ኢየሱስን እንዴት መቀበል ይችላል?
4. ቃል ሥጋ መሆን ያስፈለገበት ምክንያት ምንድነው?
5. ይህን ክፍል በአስተዋጽኦ ለማስቀመጥ አስቸጋር የሚሆነው ለምንድነው?
6. ኢየሱስን ለመገልጽ ግልጋሎት ላይ የዋሉ ስነ መለኮታዊ እውነቶችን ግለጽ (በትንሹ 8)፡፡
7. ቁ. 18 በጣም አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት ምንድነው?

### ከቁጥር 19-51 ያለውን ክፍል ለመረዳት እጅግ ወሳኝ የሆነ አውዳዊ አብርሆት

ሀ. ስለ መጥመቁ ዮሐንስ የሚያወሳው ይህ ክፍል የቀደምት ቤተ ክርስቲያን ሁለት ስህተቶች ያወሳል፡፡

1. በመጥመቁ ዮሐንስ ሕይወት ዙሪያ የሚያጠነጥን እና በቁ 6-9፣ 2021፣ 25 እና 3፡22-36 አጠራጣሪ ክፍሎች ናቸው፡፡
2. በኢየሱስ ማምነት ዙሪያ የሚያጠነጥኑ እና በቁ 32-34 ላይ የተጠቀሱት፡፡ ተመሳሳይ የኖስቲክ አስተምህሮ በ1 ዮሐ 1 ላይ ምላሽ ተሰጥቶበታል፡፡ 1 ዮሐንስ ለዮሐንስ ወንጌል የሽኝ ደብዳቤ ሆኖ ያገለግላል፡፡

ለ. የዮሐንስ ወንጌል የኢየሱስን በመጥመቁ ኢየሱስ እጅ መጠመቅ ምንም አያወራም፡፡ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ስለ ክርስቶስ አኗኗርን በተመለከተ፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን፣ ጥምቀት እና የጌታ እራት ሥርዓትን በሚመለከት ምንም አያወሳም፡፡ ስለአለማውሳቱ ሁለት ምክንያቶችን መስጠት ይቻላል፡

1. በጥንት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተለያዩ ሥርዓቶች መነሣታቸው ዮሐንስን እንዲህ ያለው ክርስትና ላይ ትኩረት እንዳይሰጥ አድርጎታል፡፡ የእርሱ ወንጌል ግንኙነታዊ እንጂ ሥርዓታዊ አይደለም፡፡ ስለ ሁለቱ ሥርዓቶች፤ ስለ ጥምቀት እና የጌታ እራት ምንም አላለም፡፡ እነዚህ ይኖራሉ ተብለው የሚጠበቁ ሥርጫቶች አለመኖራቸው ትኩረትን ወደ እርሱ ልስብ ችሏል፡፡
2. ዮሐንስን ከሌሎች የወንጌል ጸሓፊት በኋላ በመጻፉ ስለ ኢየሱስ ሕይወት የጻፈው የሌሎች ወንጌላትን ላማገዝ ነው፡፡ ሌሎች ተመሳሰይ ወንጌላት ስለ ሥርዓቶቹ በቂ በሆነ ሁኔታ ስለ ጻፉ ዮሐንስ በጊዜው በአከባቢው ስለ ተደረጉ ተጨማር ነገሮች ልጽፍ ችሏል፡፡ ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን በላይኛው ክፍል ውስጥ ይደረግ የነበረው የእርስ በእርስ ንግግር እና የተለያዩ ክንዋኔዎች ናቸው (ምዕራ 13-17) ነገር ግን ይህ ትክክለኛው የእራት ጊዜ አልነበረም፡፡

ሐ. የዚህ ዘገባ ዋና ትኩረት መጥመቁ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ የሰጠው ምስክርነት ነው። ዮሐንስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ስነ ክርስቶሳዊ ምስክርነቶችን ሰጥቷል፡
   1. ኢየሱስ የእግዚአብሔር በግ ነው (ቁ 29)፤ ይህ መጠሪያ በዚህ ስፍራ እና በራዕይ መጽሐፍ ውስጥ ብቻ ግልጋሎት ላይ ውሏል።
   2. ኢየሱስ አስቀድሚ መኖር (ቁ 30)
   3. ኢየሱስ የመንፈስ ቅዱስ ተቀባይ እና ሰጭ ነው (ቁ 33)
   4. ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው (ቁ. 34)

መ. ስለ ኢየሱስ ማንነት እና ሥራ የተነገረው እውነት እየጎለበተው የመጣው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምስርነቶች ነው፡
   1. መጥመቁ ዮሐንስ
   2. አንድሪው እና ስሚኦን
   3. ፊልጶስ እና ናትናኤል

   ይህ በዚህ ወንጌል ውስጥ አገልግሎት ላይ የዋለ የተለመደ ስነ ጽሑፊዊ ይዘት ነው። በውስጡም ስለ ኢየሱስ ወይም ከኢየሱስ ጋር የተደረጉ ሃያ ሰባት ንግግሮችን ወይም ምስክርነቶችን ይዟል።

### የቃላት እና የሀረጎች ጥናት

**የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 1፡19-23**
**አይሁድም፤ አንተ ማን ነህ? ብለው ይጠይቁት ዘንድ ከኢየሩሳሌም ካህናትንና ሌዋውያንን በላኩበት ጊዜ፡ የዮሐንስ ምስክርነት ይህ ነው። መሰከረም አልካደምም፤ እኔ ክርስቶስ አይደለሁም ብሎ መሰከረ። እንኪያስ ማን ነህ? ኤልያስ ነህን? ብለው ጠየቁት። አይደለሁም አለ። ነቢዩ ነህን? አይደለሁም ብሎ መለሰ። እንኪያስ። ማን ነህ? ለላኩን መልስ እንድንሰጥ፤ ስለራስህ ምን ትላለህ? አሉት።እርሱም፦ ነቢዩ ኢሳይያስ እንዳለ። የጌታን መንገድ አቅኑ ብሎ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ እኔ ነኝ አለ።**

1፡19 **"አይድም"** በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ይህ ቃል የሚያመለክተው (1) በይሁዳ ሀገር ውስጥ የሚኖሩ ለኢየሱስ ጠላት የሆኑ ሰዎችን ወይም (2) የአይሁዳዊያን የሃይማት መሪዎችን ብቻ (2፡18፤ 5፡10፤ 7፡13፤ 9፡22፤ 12፡42፤ 18፡12፤ 19፡38፤ 20፡19 ጋር ያነጻጽሩ)። አንዳንድ የስነ መለኮት ምሁራን አይሁዳዊያን ሌሎች አይሁዳዊያን እንድህ በሚያንቋሽሽ መልኩ አይናገሩም ብለው ይከራከራሉ። ነገር ግን አይሁዳዊያን በክርስቲያኖች ላይ ያላቸው ጥላቻ በጣም የተባባሰው በ90 ዓም ከጃማኒያ ጉባኤ በኋላ ነው።

"አይሁዳዊ" የሚለው ቃል የመጣው ከይሁዳ ዘር ነው። አስራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች በ922 ዓዓ ለሁለት ከተከፈሉ በኋላ ይሁዳ የሚለው ስያሜ በደቡብ በኩል የቀሩት የሦስቱ ነገዶች መጠሪያ ሆነ። የአይሁዳዊያን መንግስታት የሆኑ ሁለቱም፤ እስራኤል እና ይሁዳ ወደ ግዞት ተወሰዱ፤ ነገር ግን በጣም ጥቂት፣ በተለይም ከይሁዳ ከሄዱ መካከል በቁሮስ ትዕዛዝ መሰረት በ538 ዓዓ ለመመለስ ችለዋል። ከዚያ በኋላ ቃሉ በፊልስጤም ውስጥ ለሚኖሩት እና በሜድትራኒያን አከባቢ ለተበተኑት የያዕቆብ ዘሮች መጠሪያነት ውሏል።

በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ይህ ቃል አሉታዊ መልክ ስኖረው ለአጠቃላይ ቃሉ አጠቃቀም 2፡6 እና 4፡22 ይመልከቱ።

▣ **"ካህናትን እና ሌዋዊያን"** መጥመቁ ዮሐንስ ከካህናት ወገን ነበር (ሉቃ 1፡5 ይመልከቱ።)። በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ "ሌዋዊያን" የሚለው ቃል የሚገኘው በዚህ ስፍራ ላይ ብቻ ነው። እነዚህ ሰዎች የቤተ መቅደሱ ጠባቂዎች ልሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ሰዎች በእየሩሳሌም ከሚገኙ የሃይማኖት ባለስልጣነት ዘንድ ወደ ኢየሱስ መረጃን ለመሰብሰብ የተላኩ ሰዎችን ያመለክታል (ቁ. 24)። እነዚህ ሁለቱም ቡድኖች መጥመቁ ዮሐንስ በመጠየቁ ሂደት ውስጥ ተሳትፎ አድርገዋል። እነዚህ የፖለቲካ እና የሃይማት ሃይሎች ኢየሱስን እና ተከታዮቹን ተቃሙመዋል።

▣ **"አንተ ማን ነህ"** ይህ ጥያቄ ኢየሱስን በ8፡25 ላይ ከተጠየቀው ጋር ተመሣሣይ ነው። ዮሐንስ እና ኢየሱስ ያስተምሩ የነበሩት የሃይማኖት መሪዎቹ በማይስማማቸው መንገድ ነበር ምክንያቱም ሁለቱም የብሉይ ኪዳን ስለ መጨረሻው ዘመን ያለወን አስተምህሮ ጠንቅቀው ያውቁ ስለ ነበር ነው። ስለዚህም ይህ ጥያቄ ተዛማጅነት ያለው አይሁዳዊያን ይመጣል ብለው ከሚጠብቁት የመጨረሻው ዘመን ጋር ነው።

1፡20 **"መሰከረም አልካደምም፤ እኔ ክርስቶስ አይደለሁም ብሎ መሰከረ"** ይህ ዐረፍተ ነገር በጣም ጠንካራ ነው፤ ሶስት አሉታዊ ምላሾችን በመስጠት እርሱ የሚጠበቀው መሲሕ እንዳልሆነ ተናግሯል። "መሰከረ" ለሚለው ቃል በ9፡22 ላይ ያለውን ልዩ ርዕሰ ጉዳይ ተመልከት።

▣ **"ክርስቶስ"** ክርስቶስ የሚለው ቃል "መሲሕ" የሚለው የዕብራይስጥ ቃል የግሪክ ትርጓሜው ነው። ትርጉሙም "የተቀባው" ማለት ነው። በብሉይ ኪዳ ውስጥ የመቀባት ሀሳብ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ልዩ ጥርን እና ለልዩ ተልዕኮ ማስታጠቁን ነው። ነገስታት፣ ካህናት እና ነብያት የተቀቡ ናቸው። ከዚያም ይህ ቃል አዲሱ የጽድቅ ዘመን ከሚያመጣው ሰው ጋር ተያይዞ ተገለጸዋል። ብዙ ሰዎች ይመጣል ተብሎ ተስፋ የተገባው መሲሕ መጥመቁ ዮሐንስ

እንደሆነ አስበው ነበር፡፡ (ሉቃ 3፡15) ምክንያቱም ከብሉይ ኪዳን ጸሓፊዎች አራት መቶ አመታት በኋላ በእግዚአብሔር መንፈስ በመነዳት ያሕዌን በመወከል ይነገር የነበረ ሰው በመሆኑ ነው፡፡

በዚህ ስፍራ ላይ ያለኝን አስተያየት በዳኔ 9፡26 ላይ ስለ "መስሑ" በተባለው ላይ አስተያየቴን በመስጠት አጠናቅቃለሁ፡፡

*ዳን* 9፡26
NASB፣ *"መሲሑ"*
NKJV *"መሲሕ"*
NRSV፣ *"የተቀባው"*
TEV *"የተመረጠው መሪ"*
NJB *"የተቀባው"*

ይህንን ቁጥር ለመተርጎም የሚያስቸግረው ነገር መሲሕ ወይም የተቀባው ከሚለው ቃል ጋር ተያይዞ ያሉት ትርጓሜዎች ናቸው፡፡

1. ለአይሁድ ነገሥታት ውሏል (ምሳሌ 2፡10፤ 12፡3)
2. ለአይሁዳዊያን ካህናት ውሏል (ምሳሌ 4፡3፣ 5)
3. ለቂሮስ ውሏል (ከኢሳ 7 ጋር ያነጻጽሩ)
4. ቁ. 1 እና ቁ. 2 መዝ 110 እና ዘካ 4 በአንድነት መያዙ
5. አዲሱን የጽድቅ ዘመን ለማምጣት በዳዊት ንግሥና ከሚመጣው ንሥ ጋር ተያይዞ ይነሳል
   ሀ. የይሁዳ ዘር (ዘፍ 49፡10 ጋር ያነጻጽሩ)
   ለ. ከእሴይ ቤት (2 ሳሙ 7 ጋር ያነጻጽሩ)
   ሐ. ዓለማቀፋዊ ንግሥና (መዝ 2፣ ኢሳ 9፡6፤ 11፡1-5፤ ሚል 5፡1-4ጋር ያነጻጽሩ)

እኔ በግሌ "የተቀባው" የሚለውን ቃል ከናዝሬቱ ኢየሱስ ጋር ያያዝኩበት ምክንያት

1. በምዕራፍ ሁለት ላይ አራተኛውን ንጉሥ ከዘላለም መንግስት መግባት ጋር ስላያያዘው
2. በ7፡13 "የሰው ልጅ" የሚለው ቃል ለዘላለማዊ መንግስት መግቢያ ስሚያደረገው
3. በ9፡24 ላይ ያለው የመዋጀት ሀረግ የወደቀው ዓለም ፍጻሜን ስለሚያመለክት
4. ኢየሱስ የዳንኤል መጽሐፍን የተመለከተበት መንገድ (ማር 24፡15፣ ማር 13፡14 ይመልቱ)

**1፡21 "እንኪያስ ማን ነህ? ኤልያስ ነህን?"** ኤልያስ ስላልሞተ ነገር ግን ወደ ሰማይ ስለተነጠቀ (2 ነገ 2፡1) ከመስሑ በፊት እንደሚመጣ ይጠበቅ ነበር (ሚል 3፡1፣ 4፡5)፡፡ መጥመቁ ዮሐንስ ኤልያስን ይመስል ነበር እንዲሁም ድርጊቱ ሁሉ እርሱን ይመስል ነበር (ዘክ 13፡4)

▣ **"አይደለሁም አለ"** መጥመቁ ዮሐንስ እራሱን የኤልያስን የመጨረሻ ዘመን የስራ ድርሻ የሚፈጽም አድርጎ አይመለክትም ነበር ነገር ግን ኢየሱስ በትንብተ ሚልኪያስ ውስጥ የተነገረው ትንቢት ፍጻሜ እንደሆነ ግን ይናገር ነበር (ማቴ 11፡14፣ 17፡2)

▣ **"ነቢዩ ነህን?"** ሙሴ እርሱን የሚመስል ከእርሱ በኋላ እንደሚመጣ ተናግሯል (ዘዳ 18፡15፣ 18፤ ዮሐ 1፡25፤ 6፡14፤ 7፡50፤ ሐዋ 3፡22-23፤ 7፡37)፡፡ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይቃል በሁለት የተለያዩ መንገዶች አገልግሎት ላይ ውሏል (1) ከመስሑ የተለየ በመጨረሻው ዘመን ከሚመጣ አንድ ሰው ጋር ወይም (2) መስሑ (ሐዋ 3፡22)፡፡

**1፡23 "በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ እኔ ነኝ አለ"** ይህ የተወሰደው የብሉይ ኪዳን የግሪክ ትርጉም ከሆነው ከኢሳ 40፡3 ላይ ነው እንዲሁም ከሚል 3፡1 ጋርም ይመሳሰላል፡፡

▣ **"የጌታን መንገድ አቅኑ"** ይህ የተወሰደው ከኢሳ 40፡3 ሲሆን ይህም የሚከኘው ኢሳ 40-54 ውስጥ የአገልጋዩ መዝሙር ተብሎ በሚታወቀው ውስጥ ነው (42፡1-9፤ 49፡1-7፣ 50፡4-11፣ 52፡13-53፡12 ያነጻጽሩ)፡፡ ይህ በመጀመሪያ የሚያመለክተው እስራኤልን ሲሆን ነገር ግን 52፡13-53፡12 ያለው ግን ግለሰብን የሚያመለክት ነው፡፡ ይህ መንገድን የማቅናት ሀረግ አገልግሎት ላይ የዋለው የነገሥታት ጉብኝት የሚደረግ ዝግጅትን የሚያመለክት ነው፡፡ "ቀጥተኛ" የሚለው ቃል ሰረወ ግንድ "ከጽድቅ" ጋር ተያያዥነት አለው፡፡ ልዩ ርዕስ 1ዮሐ 2፡29 ይመልከቱ፡፡

ሙሉ አንቀጹ የሚያገለግለው ሐዋርያው ዮሐንስ የመጥመው ዮሐንስን ስለ መለኮታዊ ጠቀሜታ ለማብራራት ሲሆን ምክንያቱም ብዙ የስህተት ትምህርቶች መጥመቁ ዮሐንስ መንፈሳዊ መሪያቸው እንደሆነ አድግረው ስለተነሱ ነው፡፡

**የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 1፡24-28**
**የተላኩትም ከፈሪሳውያን ነበሩና፡፡ እንኪያስ አንተ ክርስቶስ ወይም ኤልያስ ወይም ነቢዩ ካይደለህ፡ ስለ ምን ታጠምቃለህ? ብለው ጠየቁት፡፡ ዮሐንስ መልሶ፡ እኔ በውኃ አጠምቃለሁ፤ ዳሩ ግን እናንተ የማታውቁት በመካከላችሁ ቆሞአል፤ እኔ የጫማውን ጠፍር ልፈታ የማይገባኝ፡ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ ይልቅ የሚከብር ይህ ነው አላቸው፡፡ይህ ነገር ዮሐንስ ያጠምቅበት በነበረው በዮርዳኖስ ማዶ በቢታንያ በቤተ ራባ ሆነ፡፡**

1:24 **“የተላኩትም ከፈሪሳውያን ነበሩና”** ይህ ክፍል ትንሽ ግራ የሚያጋባ ነው። (1) ፈሪሳዊያን ዮሐንስን ለመጠየቅ ተላ (ቁ፣ 19) ወይም (2) ጠያቂዎሱ ራሳቸው ፈርሳዊያን ናቸው፤ ይህ ያልተለመደ ነገር ነው ምክንያቱም ብዙዎቹ ካህናት ሳዱቃዊያን ነበሩና (ቁ.9)። ስለዚህ በቁ. 19 ላይ ያለው የሚያመለክተው ሌሎች ቡድኖችን መሆን አለበት።

**ልዩ ርዕስ፡ ፈሪሳዊያን**

I. ይህ ቃ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ከአንዱ ውስጥ የተገኘ ነው

ሀ. “መለየት” እነዚህ ቡድኖች ተጀመሩት በማቃቢያን ዘመን ነው። (ይህ በጣም ተቀባይነት ያለው አመለካከት ነው)።

ለ. “ማካፈል” ይህ ለተመሳሰይ የዕብራይስጥ ቃል ያለው ፊች ነው። አንዳንዶች ይህ ቃል ተርጓም የሚል ትርጓሜ እንዳለው ይናገራሉ (2 ጢሞ 2፡15)

ሐ. “ፐሪሲያን” ይህ ለተመሳሳይ የአራማክ ቃል ያለው ትርጓሜ ነው። የፈሪሳዊያን አንዳንድ አስተምህሮዎች ከፓሪሲያን ዞሮአስቴሪያ ዱዋልዝም ጋር ተመሳሳይነት አለው።

II. በማቃባያን ዘመን ሄዶይዝ (ባሕታዊያን) ከተባሉ ወገኖች ያደጉ ናቸው። በአንቲኦክ ኤፌፋን ላይ በማመጽ የሄሌንስቶኮችን በመቃወም ብዙ ኢሴንሶች ተንሰው ነበር። ፈሪሳዊያን በጆሴፌስ መጽሐፍ የአይሁዳውያን አመጽ በተሰኘ መጽሓፉ ውስጥ 8.5.1-3 ለይ ለመጀመሪያ ግዜ ተጠቅሰዋል።

የእነርሱ ሦስት ዋና ዋና አስተምህሮዎች

ሀ. በመስሑ መምጣት የምናሉ፡ ይህም ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጭ ባሉ ስነ ጽሑፎች እነደ 1 ሔኖክ ተጽእኖ የፈጠሩት ነው።

ለ. እግዚአብሔር በእለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ የሚያደረግ ነው። ይህ ከሳዱቃዊያን አስተሳሰብ ጋር ተቃራን ነው። ብዙ የፈሪሳዊያን አስተምህሮ ለሳዱቃዊያን የተሰጠ ምላሽ ይመስላል።

ሐ.ከሞት በኂላ ያለው ሕይወት የሚወሰነው በምድር ላይ ባለው ሕይወት ነው፤ ይህም ሽልማትን እና ቅጣት ያጠቃልላል (ዳን 12፡2)

መ. የብሉይ ኪዳናት እና የትውፊቶች (ታልሙድ) ስልጣን፡ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳናት ውስጥ ለሰጠው ትዕዛዛት ይገዛሉ እንዲሁም በመምህራኖቻው ትምህርት ቤት ውስጥ ትርጓሜ ይሰጧቸዋል እንዲሁም በሕይወታቸው ለመተርጎም ይጥራሉ። (ሻማይ የሚባው ትምህርት ቤት የወግ አጥባቂዎቹ ትምህርት ቤት ስሆን ሂላል ደግሞ የልብራሎቹ ነው)። የመምህራኖቹ ስነ አፈታት በሁለት የተለያየ አስተምህሮ ባላቸው መምህራን በኩል በምደረግ ውይይት ላይ ያተኮረ ነው። በቅዱሳት መጽሐፍት ትርጓሜ ላይ በሁለት ሰዎች መካከል የምደረገው የቃል ውይይት በሁለት መንገድ ይጻፋል፡ የባቢሎናዊያን ታልሙድ እና ያልተጠናቀቀው የፊልስጤማዊያን ታልሙድ። ሙሴ በስና ተራራ ላይ ይህንን ትርጉም እንደተቀበለ ያምናሉ። እንዲህ አይነቱ ውይይት በዕዝራ ዘመን የተጀመረ ሲሆን የሚደረገውም በ”ታላቁ ምኩራብ” ውስጥ ነበር (ይህም በኂላ ሳንድርያን ተብሎ ተጠርቷል)

ሠ. በጣም ትልልቅ ምሳሌዎችን መጠቀም፡ ይህም ጥሩ እና መጥፎ መንፈሳዊ አካላትን መጠቀምን ያካትታል። ይህ ከፐሪሺያዊያን ሁለትዮሽ እና በቅዱሳት መጽሓፍት ውጭ ባሉ መጽሐፍት አፈታት የዳበረ ነው።

1፡25 **“ስለ ምን ታጠምቃለህ?”** አሕዛቦች ወደ አይሁዳዊያን ሃይማኖት መጠመቅ ከፈለጉ እንዲህ አይነቱ ጥምቀት ሽጥንት አይሁዳዊያን ዘንድ የተለመደ ነገር ነው ነገር ግን አይሁዳዊያን እራሳቸው መጠመቃቸው ግን ያልተለመደ ነገር ነው (በቁምራን ማህበረሰብ ውስጥ የነበሩ ጸሓፊት እራስን የማጥመቅ ተግባሪን ይፈጽሙ ነበር እንዲሁም ወደ ቤተ መቅደሱ ከመግባታቸው በፊት ይታጠቡ ነበር)። ስለ መስሑ ጥምቀት ልያወሱ የሚችሉ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች (ኢሳ 51፡15፣ ሕዝ 36፡25፣ ዘካ 13፡1)

▣ **“እንኪያስ አንተ ክርስቶስ ወይም ኤልያስ ወይም ነቢዩ ካይደለህ”** ዴድሲ ጥቅል ተብለው በሚታወቁት ውስጥ እነዚህ ሶስቱ መሲሕ እንደሆነ የሚያምኑ ኢሴንሳዊያ መኖራቸው የሚያስገርም ነው። እንዲሁም አንዳንድ የጥንት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከኢየሱስ ዳግም ምጻት በፊት ኤልያስ በአካል እንደሚመጣ ማመናቸው የሚያስገርም ነው (ክርስቶሶም፣ ጀሮም፣ ገሬጎሪይ እና ኦግስትን)።

1፡26 **“እኔ በውኃ አጠምቃለሁ”** “በ” የሚለው መስተዋድድ “ከ” ተብሎ ሊገለፅ ይችላል የትኛውም አማራጭ ይወሰድ ነገር ግን “መንፈስ”ን በሚመለከት በቁጥር 33 ላይ ከተጠቀሰው ንፅፅር ጋር መዛመድ አለበት።

▣ **“ዳሩ ግን እናንተ የማታውቁት በመካከላችሁ ቆሞአል”** “ቆሞአል” የሚለው ግስ ላይ በጥንት ቅጂዎች መካከል ልዩነት አለ።

1፡27 **"እኔ የጫማውን ጠፍር ልፈታ የማይገባኝ"** ይህ አንድ ሎሌ ጌታው ወደ ቤት ስመጣ የጌታውን ጫማ የመፍታት ተግባሪን ያሳያል፡፡ የአይሁዳ መምህራን የመምህራኑ ደቀ መዛሙርት መምህሩ ያዘዛቸውን ሁሉ፤ የጫማውን ማሰሪያ ከመፍታት ውጭ እንደሚያደርጉ ያረጋግጣሉ፡፡ ይህ ትህትናን ይጠይቃል፡፡

**የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 1፡29-34**
**በነገው ዮሐንስ ኢየሱስን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ፡ እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ፡፡ አንድ ሰው ከእኔ በኋላ ይመጣል: ከእኔም በፊት ነበርና ከእኔ ይልቅ የከበረ ሆኖአል ብዬ ስለ እርሱ ያልሁት ይህ ነው፡፡ እኔም አላውቀውም ነበር: ዳሩ ግን ለእስራኤል ይገለጥ ዘንድ ስለዚህ በውኃ እያጠመቅሁ እኔ መጣሁ፡፡ ዮሐንስም እንዲህ ብሎ መሰከረ፡፡ መንፈስ ከሰማይ እንደ ርግብ ሆኖ ሲወርድ አየሁ፤ በእርሱ ላይም ኖረ፡፡ ዮሐንስም እንዲህ ብሎ መሰከረ፡፡ መንፈስ ከሰማይ እንደ ርግብ ሆኖ ሲወርድ አየሁ፤ በእርሱ ላይም ኖረ፡፡ እኔም አይቻለሁ እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ መስክሬአለሁ፡፡**

1፡29 **"እነሆ . . . የእግዚአብሔር በግ፡፡"** የፋስካ በአል ሩቅ አልነበርም (2፡13)፡፡ ስለዚህም ይህ ምናልባትም ከግብጽ (ዘጸ 12) ነጻ ማጣትን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል (ይኼውም ድነትን)፡፡ ዮሐንስ የኢየሱስን ሞተ የፋስኮ በግ የሚታረድበት ቀን ላይ አድርጎታል (ይኼውም የዝግጅት ቀን)፡፡ ነገር ግን ሌሎች አተረጓጎሞች አሉ፡

1. ይህ ምናልባት መከራን የሚቀበለውን አገልጋይ ልያመለክት ይችላል ኢሳ 53፡7
2. በዘፍ 22፡8 ላይ በሀረግ የተያዘውን በግ ልያመለክት ይችላል
3. በየዕለቱ በቤተ መቅደሱ ውስጥ የሚቀርበውን መስዋዕትን ልያመለክት ይችላል (ዘጸ 29፡ 38-46)

ከዬትኛው ጋር በቀጥታ ይገናኝ ይህ በግ የተላከው ለመስዋዕትነት ነው፡፡ (ማር 10፡45)

ይህ አይነቱ የኢየሱስ መስዋእትነትን የሚያመለክት ምሳሌ በጳውሎስ መልዕክቶች ውስጥ የማይገኝ ሲሆን ዮሐንስም እነዚህ በጣም ጥቅት ጊዜ ተጠቅሞአቸዋል፡፡ (1፡29፣ 36 እንዲሁም ሐዋ 8፡32 እና 1ጴጥ 1፡19):: ይህ "ትንሽ ጠቦት" ለሚለው የተሰጠ የግሪኩ መጠሪያ ነው (ትንሽ የተባለበት ምክንያት የአንድ ዓመት እድሜ ስላለው እና ለመሥዋዕቶነት የሚቀርቡት እንስሳት የተለመደው እድሜ በመሆኑ ነው)፡፡ በ21፡15 ላይ ዩሐንስ ተለየ ቃል ሲጠቅስ በዩሐንስ ራዕ ደግሞ ስምንት ጊዜያት ያህል ተጠቅሷል፡፡

መጥምቁ ዩሐንስ ለተጠቀመበት ሥዕላዊ አገላለፅ አንድ ተጨማሪ አማራጭ አለ፡፡ ይህም "በጉ" እንደ ድል ነሺ የተገለፀበት ዝምታው ጊዜ ፅሑፍ መሥዋዕት፡- መሆኑ የአሁን ጊዜ ሲሆን ነገር ግን በጉ በነገረ ፍፃሜ እንደ ፈራጅ መጠቀሉ በቅርብ የሚሆን ክስተት ነው (ራዕይ 5፡5-6፤12-13)፡፡ "ይገለጥ ዘንድ"

▣ **"የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ"** "የሚያስወግድ" የሚለው ቃል ትርጉም "የሚሸከም" እና "ዞር የሚያደርግ" ማለት ነው፡፡ ይህ ግስ በዘለ 16 ከተጠቀሰው "ከሚለቀቀው ፍየል" ሀሳብ ጋር ይመሳሰላል፡፡ የዓለም ኃጢአት በዚህ ስፍራ ላይ መጠቀሱ የሚያመለክተው የበጉ ሥራ ምን ያህል ዓለም አቀፋዊ እንደሆነ ያሳያል፡፡ (9፣ 3፡16፣ 1ጢሞ 2፡4 ፣ 4፡10፤ ቲቶ 2፡11፤ 2ጴጥ 3፡9፤ 1ዮሐ 2፡1፤ 4፡14)፡ በዚህ ስፍራ ላይ ኃጢአት በብዙ ቁጥር ሳይሆን በነጠላ ቁጥር መጠቀሱን ልብ ልንል ይገባል፡፡ ኢየሱስ የሰው ልጆችን የ"ኃጢአት" ችግር ፈትቶታል፡፡

1፡30 **"ከእኔም በፊት ነበርና"** ይህ ሀረግ በቁ 15 ላይ ለአጽኖት እንደገና ተጠቅሶ እናገኛለን፡፡ ይህ የመሲሁን አስቀደመ መኖር እና መለኮታዊነት አጽኖት የሚሰጠው ነገር ነው፡፡ (ዮሐ 1፡1፣ 14፤ 8፡58፤ 16፡28፤ 17፡5፣ 24፤ 2ቆሮ 8፡9፤ ፊል 2፡6-7፤ ቆላ 1፡17፤ ዕብ 1፡3)፡፡

1፡31 **"ለእስራኤል ይገለጥ"** ይህ የዮሐንስ የተለመደ ቃል ነው (2፡11፤ 3(21፤7፡4፤ 9፡3፤ 17፡6፤ 21፡14፤ 1ዮሐ 1፡2፤ 2፡19፣ 28፤ 3፡2፣ 5፣ 8፣ 4፡9) ነገር ግን ይህ ነገር በተመሳሳይ ወንጌላት ወስጥ በብዛት አይገኝም በማር 4፡22 ላይ ይገኛል፡፡ ይህ "ማወቅ" የሚለው የዕብራይስጥ ቃል ላይ ያለ የቃላት ጫወታ ሲሆን የሚያመለክተውም ከአንድ ሰው ጋር ግላዊ ግንኙነት መኖሪ እንጂ ስለ አንድ ሰው ማወቅን አይደለም፡፡ የዮሐንስ ጥምቀት ዓላማ ሁለትዮሽ ነው (1) ሰዎችን ለማዘጋጀጽ (2) መሲሁን ለመግለጽ፡፡

(ፓኔሮ) የሚለው ግሥ "መታየት" (አፓካሊፕቶ) የሚለውን ግሥ በዮሐንስ ፅሑፍ ውስጥ የሚተካው ይመስላል፡፡ ኢየሱ የእግዚአብሔርን ማንነት እና መልዕክቱን በግልፅ ወደ ብርሃን /መታየት የሚያመጣ ነው!

1፡32-33 ይህ በኢየሱስ ላይ መንፈስ መውረዱ እና በእርሱ ላይ ማረፉን አጽኖት የሰጠበት የሶስትዮሽ ገለጻ ነው፡፡

1፡32 **"መንፈስ ሰማይ እንደ ርግብ ሆኖ ሲወርድ አየሁ"** ይህ ኢሳያስ መሲሁን የገለጸበጽ መንገድ ነው (ኢሳ 40-66) (ኢሳ 42፡1፤ 59፡21፤ 61፡1)፡፡ ይህ ኢየሱስ ከዚያ በፊት መንፈስ አልነበረውም ወደሚል መደምደሚያ አያመራንም፡፡ ይህ የእግዚአብሔር ምርጥ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ ይህ በመጀመሪያ ጠቀሜታው ለኢየሱስ ሳይሆን ለመጥመቁ ዮሐንስ ነው፡፡

አይሁዳዊያን ሁለት ዘመናት እንዳሉ ያማናሉ (በ1ዮሐ 2፡17 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከቱ)፡፡ እነዚህም ዘመናት የአሁን ክፉ ዘመን እና የሚመጣው የጽድቅ ዘመን ናቸው፡፡ ይህ አዲሱ ዘመን የመንፈስ ቅዱስ ዘመን ተብሎ ይታወቃል፡፡ ይህ ራዕይ ለመጥመቁ ዮሐንስ እንዲህ ብሎት ይሆናል (1) ይህ መስሑ ነው እና (2) አዲሱ ዘመን መጥቷል፡፡

▣ **"ርግብ"** ይህ ቃል አገልግሎት ላይ ከዚህ በታች ባለው መልኩ ውሏል

1. መምህራን እስራኤልን ለማመልከት ተጠቅመውበታል (ሆሴ 7፡1)
2. በታርጉም ውስጥ በዘፍ 1፡2 ላይ እንስት ርግብ በእግዚአብሔር ፍጥረታትን ስፈጥር ትሰፍፍ የነበረችን ለማልከት ውሏል
3. ፊሎ የጥበብ ለማመልከት ተጠቅሞበታል
4. መንፈስ ቅዱስ የወረደበትን መንገድ ለማሳየት ውሏል (መንፈስ ርግብ አይደለም)

▣ **"በእርሱ ላይም ኖረ"** በ1ዮሐ 2፡10 "ማደር" የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

**1፡33 "እኔም አላውቀውም ነበር"** ይህ የሚያመለክተው መጥመቁ ዮሐንስ ኢየሱስን እንደ መሲሕ ከዚህ በፊት አለማወቁን እንጂ ፊጽሞ እርሱን አለማወቁን አያመለክትም፡፡ ዘመዳማቾች እንደመሆናቸው በእርግጥ በቤተሰብ ጉባኤዎች ወይም ሃይማታዊ በአላት ላይ ሳይገናኙ አልቀረም፡፡

▣ **"ዳሩ ግን በውኃ አጠምቅ ዘንድ የላከኝ እርሱ . . . አለኝ"** ለብሉይ ኪዳን ነብይት ይናገር እንደነበረው እግዚአብሔር እንዲሁ ለዮሐንስም ተናግሮታል፡፡ ዮሐንስ መሲሁን ያወቀው በጥምቀቱ ወቅት በእርሱ ላይ በታዩት ልዩ ምልክቶች አማካኝነት ነው፡፡

የዮሐንስ ጥምቀት ሃይማታዊ ስልጣን ነበረው፡፡ ከእየሩሳሌም ተወክለው የመጡት ሰዎች (19-28) የእርሱ ስልጣን ምንጭ ማን እንደሆነ ይነግራቸው ዘንድ ጠይቀውታል፡፡ የኢየሱስ የመንፈስ ጥምቀት ከዮሐንስ የውሃ ጥምቀት ይበልጥ ነበር፡፡ የኢየሱስ የራሱ የውሃ ጥምቀት የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ምሳሌ ነው፤ ወደ አዲሱ ዘመን መካተትን ያመለክታል፡፡

▣ **"በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ እርሱ ነው"** ከ1 ቆሮ 12፡13 እንደሚንረዳው ይህ ጥምቀት የሚያመለክተው ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ በመጀመሪያ መቀላቀያን ነው፡፡ መንፈስ ስለ ኃጢአት ይወቀወሳል፣ ወደ ክርስቶስ ይቀላቅላ እንዲሁም በአዳዲሶቹ አማኞች ውስጥ ክርስቶስን ይስላል፡፡ (ዮሐ 16፡8-13)፡፡ በ1 ዮሐ 2፡20 ላይ ቅድሱ የተባለው ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

**1፡34 "እኔም አይቻለሁ . . . መስክሬአለሁ"** ይህ ሀረግ የሚያመለክተው አላፊ ጊዜ ድርጊት ወደ ፍጻሜ መምጣቱን እና ቀጣይነቱን ነው፡፡

▣ **"እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ"** የግሪክ ቃል የሆነው ፓኢስ "አገልጋይ" ተብሎ ይተረጎማ፣ የሚያሳየውም በ ሰባ ልቃናት ውስጥ የዕብራይስጡን "ልጅ" ነው፡፡ ይህ ከሆነ ዘንዳ ኢሳ 53 (በ1፡29 ላይ እዳለው የእግዚአብሔር በግ ነው ማለት ነው) ከብሉይ ኪዳን የተወሰደ እንጂ ከዳን 7፡13 አይደለም ማለት ነው፡፡ ኢየሱስ ልጅም አገልጋይም ነው፡፡ አማኞችን ወደ ልጅነት ያሸጋግራቸዋል እንጂ ወደ ባርነት አይወስዳቸውም፡፡

በ1፡49 ላይ ተመሳሳይ ማዕረግ ለናትናኤል አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ እንዲሁም በማቴ 4፡3 ላይ ለሴጣንም ተሰጥቷል፡፡ በMSS[5] እና N የተወሰኑ ልዩነቶችን እንመለከታለን፤ ይኸውም "የእግዚአብሔር ልጅ" ከማለት ይልቅ "የእግዚአብሔር ምርጡ" የሚል ይገኛል፡፡ (ዩቢኤስ "የእግዚአብሔር ልጅ" ለሚለው ቢ ነጥብ ሰጥቶታል፡፡" በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ "የእግዚአብሔር ልጅ" የሚለው ሀረግ ብዙ ቦታ ላይ ይገኛል፡፡ ነገር ግን የቴክስቿል ክርትስዝም መንገድ ከተከተልን በአውዱ ውስጥ የሚገጥም መስሎ የማይታየው ነገር ትክክል ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡

> "በዮሐንስ 1፡34 ላይ መጥምቁ ዩሐንስ ያለው "ይህ የእግዚአብሔር ልጅ ነው" (ኬ.ጄ.ቪ.፤አር.ኤስ.ቢ.) ወይስ "ይህ የእግዚአብሔር ምርጥ ነው" (ኤን.ኢ.ቢ.ጄ.ቢ.)? የMS ምንጭ ማስረጃ በቀደምት ጥቅሶች እንኳ የተከፋፈለ ነው "ልጅ" የሚለው ስያሜ ቁልፍ በሆኑ የአሌክስነደሪያ ምሥክሮች ($P^{66}$፣$P^{75}$፣B፣C፣L $Cop^{bo}$) እንዲሁም በበርካታ የ OL (our፣c፣flg) እና ኃላኞቹ የሶርያ ምንጮች ውስጥ የሚገኝ ሲሆን "ምርጥ" የሚለው ስያሜ በአሌክሳደሪያ $p^{5}$፣N፣$cop^{5a}$ እንዲሁም ደግሞ በOLMSSa፣b፣e፣$ff^{2}$ በዋርያ ብሎይ ኪዳን የሚገፍ ነው፡፡
>
> "ጥያቄው በመጨረሻ ሊወሰን የሚገባው በውስጣዊ መሠረቶች ላይ ነው፡፡ ምንጩ ሲገለበጥ ባለው እድል ላይ አንድ ነገር ግልጽ ነው፤ የተለያየ መልክ እንዲኖረው መደረጉ ሆን ተብሎ የታሰበበት እንጂ የአጋጣሚ ጉዳይ አይደለም (Bart D.Ehrman *The Orthodox Corruption of* Scripture ገጽ 69-70)፡፡ ነገር ግን በሁለተኛው ክፍለ ዘመን የነበረው ፀሐፊ የጉዲፈቻ ነገር ክርስቶስ ለመደገፍ ይቻለው ዘንድ ጥቅሱን ቀይሮታል ወይስ አንድ ኦርቶዶክስዊ (ቀጥተኛ) ፀሐፊ "ምርጥ" የተባለውን ስያሜ ጉዲፈቻን እንዲደግፍ እና ኦርቶይክሳዊ ለሆነ ምክንያት የለወጠው ነው? ካለው ዕድል አንፃር የኃለኛው በጣም የሚመስል ነው፣ በተለይ "ልጅ" የሚለው ስያሜ በየትኛውም የወንጌል ክፍል ውስጥ የጉዲፈቻ አመለካከትን በመደገፍ ካለመለወጡ አንፃር ስንመለከተው፡፡
>
> "ነገር ግን የመጨረሻው ውሳኔ ለመጀመሪያዎቹ የመልዕክቱ ተቀባዮች የነበረውን ትርጉም የሚያካትት ሊሆን ይገባል፡፡ ከመጀመሪያውም መጥምቁ ዮሐንስ የተናገረው ክርስትያናዊ ሥነ መለኮትን ለማመልከት ሳይሆን መሲሐዊ በመሆኑ ሊነሣ የሚገባው ጥያቂ እንደ መዝሙር 2፡7 ኢይነቶቹን መሲሐዊነትን ያመለክታል ወይ የሚለው መሆን አለበት ወይም እንደ ኢሳያስ 42፡1 አይነቱን ማለት ነው፡፡ ከመከራው አንፃር ወይም በዮሐንስ 1፡29 ላይ ከተጠቀሰው በግ መነሻ ሃሳብ አንፃር "ምርጥ" የሚለው ስያሜ ከወንጌሉ ዓውድ ጋር (ገጽ 431-432) ይስማማል ማለት በእርግጠኝነት የሚያከራክር ጉዳይ ነው፡፡

**የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 1:35-42**
**በነገው ደግሞ ዮሐንስ ከደቀ መዛሙርቱም ሁለት ቆመው ነበር፡ ኢየሱስም ሲሄድ ተመልክቶ። እነሆ የእግዚአብሔር በግ አለ። ሁለቱም ደቀ መዛሙርት ሲናገር ሰምተው ኢየሱስን ተከተሉት። ኢየሱስም ዘወር ብሎ ሲከተሉትም አይቶ። ምን ትፈልጋላችሁ? አላቸው። እርሱም፦ ረቢ፡ ወዴት ትኖራለህ? አሉት፤ ትርጓሜው መምህር ሆይ ማለት ነው። መጥታችሁ እዩ አላቸው። መጥተው የሚኖርበትን አዩ፡ በዚያም ቀን በእርሱ ዘንድ ዋሉ፤ አሥር ሰዓት ያህል ነበረ። ከዮሐንስ ዘንድ ሰምተው ከተከተሉት ከሁለቱ አንዱ የስምዖን ጴጥሮስ ወንድም እንድርያስ ነበረ። እርሱ አስቀድሞ የራሱን ወንድም ስምዖንን አገኘውና። መሢሕን አግኝተናል አለው፤ ትርጓሜውም ክርስቶስ ማለት ነው።**

1:35 ***"ሁለቱ የእርሱ ደቀ መዛሙርት"*** *ማር* 1:16-20 *የእነዚህን ሁለት ደቀ መዛሙርት መጠራት ሌላኛውን ታርክ የሚነገርን ይመስላል። በኢየሱስ እና በገልላ ባሉ የእርሱ ደቀ መዛሙርት መካከል ምን ያህል ግንኙነት እንዳለ በእርግጥ ማወቀ አይቻልም። ኢየሱስ በኖረበት ዘመን የአንድ አስተማሪ ደቀ መዛሙርት ለመሆን የተለያዩ የደቀ መዝሙርነት ደረጃዎች እንዳት የታወቀ ነው። ይህ ደረጃ በመምህራን ጽሑፎች ውስጥ የታየ ነው ነገር ግን በወንጌላት ታርክ ውስጥ ግን በትክክል አልተገለጹም። እነዚህ የተጠቀሱት ደቀ መዛሙርት እንድሪያስ* (ቁ 40) *እና ሐዋሪያው ዮሐንስ ናቸው (በወንጌሉ ውስጥ አንድ ጊዜም እንኳ በስሙ አልተጠቀሰም)።*

*ደቀ መዝሙር የሚለው ቃል* (1) *ተማር እና/ወይም* (2) *ተከታይ የሚል ትርጉም ልኖረው ይችላል። ይህ ኢየሱስ ስጠበቅ የነበረው መሲሕ እንደሆነ ላመኑ አማኞች የተሰጠ ስም ነው። የአዲስ ኪዳን ጥር ለደቀ መዝሙርነት እንጂ ለውሳኔ ብቻ እንዳልሆነ ልንገነዘብ ይገባል (ማቴ* 13፤ 28:18)። *ክርስትና የመጀመሪያ ውሳኔን የምጠይቅ (ንሰሐን እና እምነት) እንዲሁም በየዕለቱ ለመታዘዝ እና ጽንቶ መቆምን የሚጠይቅ ጉዳይ ነው። ክርስትና የእሳት አደጋ የዋስትና ፖሊስ አይደለም ወይም ወደ ሰማይ መግቢያ ትኬት አይደለም ነገር ግን የእለት በእለት አገልግሎት/ እና ከኢየሱስ ጋር የወዳጅነት ግንኙነት ነው።*

1:37 ***"ሁለቱም ደቀ መዛሙርት ሲናገር ሰምተው"*** *መጥመቁ ዮሐንስ ከእርሱ ባሻገር ወደ ኢየሱስ አት ልክቷል* (3:30)።

1:38 ***"ረቢ"*** *በመጀመሪያው ምዕተ አመት ይኖሩ በነበሩ አይሁዳዊያን ዘንድ የሙሴ ሕግን እና የአፈተ ታርኮችን የሚተረጉም እና የሚያራሩ ሰዎች በዝህ ማዕረግ ይጠሩ ነበርዘ። በመጥመቁ ደቀ መዛሙርት ይህ ቃል የተወሰደው "አስተማር" በሚል መልኩ ነው።* (11:8፣ 28፤ 13:13-14፤ 20:10)። *ዮሐንስ የተጠቀመው ቃል ማብራራቱ የሚያመለክተው ይህንን መጽሐፍ የጻፈው ለአሕዛብ መሆኑን ነው።*

▣ ***"ወዴት ትኖራለህ?"*** *ይህ በተለምዶ በአስተማር እና በተማር መካከል ያለውን ግንኙነት ለማጠንከር የተለመደው መንገድ ነው። ጥያቄቸው እንደሚያሳየው ከኢየሱስ ጋር ብዙ ጊዜ ማሳለፍ መፈለጋቸውን እንጂ ጥቅት ጥያቄዎችን ለመጠየቅ ማሰባቸውን አይደለም* (ቁ 39)።

*"ሜኖ" (መኖር) የሚለው ስያሜ በቁጥር* 38-39 *ውስጥ ሦስት ጊዜያት ተጠቅሷል ስያሜው አካላዊ ወይም መንፈሳዊ ሥፍራን ሊያመለክት ይችላል። ሶስቱ አጠቃቀሞች የቃላት መራቀቅን በተዘዋዋሪ የሚያመለክቱ ይመስላሉ። ሁለትን እንደምታዎች ማጣመር በዩሐንስ ወንጌል ውስጥ ተለመደ አካሄድ ነው* (1:1:5፤3-3፤4-10-11፤12:32)። *ይህ ሆን ተብሎ የተደረጋ አሻሚነት የዩሐንስ ፅሑፎች መለያ ባህርይ መገለጫ ነው።*

1:39 ***"አሥር ሰዓት ያህል ነበረ"*** *ዮሐንስ ታሳቢ ያደረገው* (1) 12:00 *የሚጀምረውን የሮማዊያንን የሰአት አቆጣጠር ይሁን* (2) 6:00 *የአይሁዳዊያንን የሰአት አቆጣጠር እንደሆነ በግልጽ መናገር አይቻልም። አንድ ሰው ዮሐ* 19:14 *ከማር* 15:25 *ጋር ስያነጻጽረው የሮማዊያን የጊዜ አቆጣጠርን የሚከተል ይመስላል። ነገር ግን ዮሐ* 11:9 *ደግሞ የአይሁዳዊያን የጊዜ አቆጣጠርን የተከተለ ይመስላል። ዮሐንስ ምናባትም ሁለቱንም የጊዜ አቆጣጠሮች ተጠቅሞ ሊሆን ይችላል።*

1:40 ***"ከዮሐንስ ዘንድ ሰምተው ከተከተሉት"*** *ሐዋርያ ዮሐንስ በዚህ ወንጌል ውስጥ የራሱን ስም ጠቅሶ አልጻፈም* (21:2)። *በእርግጥ መጥመቁ ዮሐንስ ስናገር ከሰሙት ሁለት ሰዎች መካከል አንዱ የዘብድዮስ ልጅ ዮሐንስ እራሱ ሊሆን ይችላል (ማቴ* 4:21፤ *ማር* 1:19)

1:41

| | |
|---|---|
| NASB፣ | ***"በመጀመሪያ ወንድሙን አገኘው"*** |
| NKJV NRSV፣ | ***"በመጀመሪያ ወንድሙን አገኘው"*** |
| TEV | ***"አንዴ ወንድሙን አገኘው"*** |
| NJB | ***"በመጀመሪያ ወንድሙን አገኘው"*** |

*ትርጓሜው ላይ ተጽእኖ ልፈጥር የሚችል የቅጅዎች ልዩነት አለ። ያሉት አማራጮች*

1. *በመጀመሪያ እንድሪያስ ያደረገው*
2. *በመጀመሪያ ያገኘው ሰው*
3. *እንድሪያ ሄዶ ለመናገር የመጀመሪያው ሰው ነው*

▣ *"መሢሕን አግኝተናል አለው፤ ትርጓሜውም ክርስቶስ ማለት ነው"* በ1፡20 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት

**1፡43 "ኢየሱስም ተመልክቶ"** ይህ ሀረግ የሚያመለክተው "አተኩሮ መመልከትን" ነው፡፡

▣ *"አንተ የዮና ልጅ ስምዖን ነህ"* በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለ ጴጥሮስ አባት ትንሽ ግራ መጋባት አለ፡፡ በማቴ 16፡17 ጴጥሮስ የ"ዮና ልጅ" ተብሏል፡፡ ዮና የሚለው ስም በMMS A B[3] K እና በሌሎች የቅርብ ጊዜ ቅጂዎች L MS B ላይ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ ነገር ምንም ግልጽ የሆነ ነገር ዬለም፡፡

▣ *"አንተ ኬፋ ትባላለህ አለው፤ ትርጓሜው ጴጥሮስ ማለት ነው"* ኬፋ የሚለው ቃል የጴጥሮስ የአራማይክ ስም ነው፡፡ የስሙ ትርጓሜም እርጋታ፣ ጥንካሬ እና የማያልቅ መሆኑን ያሳያል፡፡

ይህ የዚህ ወንጌል ጸሐፊ በወንጌሉ ውስጥ ለአሕዛብ አንባቢዎቹ ስለ ኢየሱስ አስተምህሮ እና ሕይወት ለማስረዳት ከሰጣቸው ብዙ ትንታኔዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ሥነ አፈታት ዙሪያ ያሉ ሁለት ቃለት በዚህ ቁጥር ላይ መገኘታው እጅግ የሚያስገርም ነው፡፡

1. በ1፡18 ላይ ኤክስጂሰስ (ፊታቴ)
2. 1፡42 ሄሪሜኑቲክስ (ስነ አፈታ)

> **የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 1፡44-52**
> **በነገው ኢየሱስ ወደ ገሊላ ሊወጣ ወደደ: ፊልጶስንም አገኘና። ተከተለኝ አለው። ፊልጶስም ከእንድርያስና ከጴጥሮስ ከተማ ከቤተ ሳይዳ ነበረ። ፊልጶስ ናትናኤልን አግኝቶ። ሙሴ በሕግ ነቢያትም ስለ እርሱ የጻፉትን የዮሴፍን ልጅ የናዝሬቱን ኢየሱስን አግኝተነዋል አለው። ናትናኤልም። ከናዝሬት መልካም ነገር ሊወጣ ይችላልን? አለው። ፊልጶስ። መጥተህ እይ አለው። ኢየሱስ ናትናኤልን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ ስለ እርሱ። ተንኰል የሌለበት በእውነት የእስራኤል ሰው እነሆ አለ። ናትናኤልም። ከወዴት ታውቀኛለህ? አለው። ኢየሱስም መልሶ፡ ፊልጶስ ሳይጠራህ: ከበለስ በታች ሳለህ: አየሁህ አለው። ናትናኤልም መልሶ፡ መምህር ሆይ: አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ፤ አንተ የእስራኤል ንጉሥ ነህ አለው። ኢየሱስም መልሶ፡ ከበለስ በታች አየሁህ ስላልሁህ አመንህን? ከዚህ የሚበልጥ ነገር ታያለህ አለው።እውነት እውነት እላችኋለሁ: ሰማይ ሲከፈት የእግዚአብሔርም መላእክት በሰው ልጅ ላይ ሲወጡና ሲወርዱ ታያላችሁ አለው።**

**1፡44 "በነገው"** ዮሐንስ በወንጌሉ ውስጥ የጊዜ ቅደም ተከተልን ለማስቀመጥ ሞክሯል (1፡29፣ 35፣ 43፤ 2፡1)፡፡ አጠቃላይ አውዱ (1) በቁጥር 19 ላይ ይጀምራል፣ ይህ ምናልባትም የመጀመሪያው ቀን ሊሆን ይችላል (2) ቁጥር 29፣ 35፣ 43 ሁለተኛው ቀን ይገልጻል እና (3) 2፡1 ደግሞ ሦስተኛ ቀን ነው፡፡

▣ *"ሊወጣ ወደደ"* ዮሐንስ ኢየሱስ በገሊላ የነበረውን የመጀመሪያውን አገልግሎቱን ከሌሎች ተመሳሳይ ወንጌላት ይልቅ ገልጸዋል፡፡ የዮሐንስ ወንጌል ትኩረት የኢየሱስን የይሁዳ እና የኢየሩሳሌም አገልግሎት ላይ ትኩረት መስጠት ነው፡፡ በዚህ ስፍራ ላይ ወደ ገሊላ መሄድ ያስፈለገው ምናልባትም በቃና ዘገልላ ወደ ሚደረገው ሰርግ ለመሄድ አስቦ ሊሆን ይችላል (ዮሐ 2) ፡፡

▣ *"ተከተለኝ"* ይህ አይነቱ ጥር ታዋቂ ደቀ መዝሙር ለመሆን የሚደረግ የመምህራን ጥር ነው፡፡ አይሁዳዊያን እንዲህ አይነቱን ግንኙነት ምን መመስል እንዳለባት የሚያመለክት መመሪያዎች አሏቸው፡፡
**1፡45 "ፊልጶስም . . . ከቤተ ሳይዳ ነበር"** የዚህ ከተማ ስም ትርጉም "የዓሳ ቤት" ማለት ነው፡፡ ይህች ከተማ የእንድሪያስ እና የጴጥሮስም ከተማ ናት፡፡

**1፡46 "ናትናኤል"** ይህ የእብራይስጥ ስም ትርጓሜው "እግዚአብሔር ሰጠ" ማለት ነው፡፡ ይህም ሰው በተመሳሳይ ወንጌላት ውስጥ በስም አልተጠቀሰም፡፡ በዚህ ሰመን ባሉ የስነ መለኮት ምሁራን ዘንድ ይህ "በርጤለሜዎስ" ተብሎ የተጠራው እንደሆነ ይታመናል ነገር ግን ይህም ብሆን ግምት በነው፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ የሐዋርያት ስም ዝርዝር ሰንጠረዥ**

| | ማቴ 10፡2-4 | ማር 3፡16-19 | ሉቃ 6፡14-16 | ሐዋ 1፡12-18 |
|---|---|---|---|---|
| **የመጀመሪያው ቡድን** | መጀመሪያው ጴጥሮስ የተባለው ስምዖን ወንድሙ እንድርያስም: የዘብዴዎስ ልጅ ያዕቆብም ወንድሙ ዮሐንስም: | ስምዖንንም ጴጥሮስ ብሎ ሰየመው፤የዘብዴዎስንም ልጅ ያዕቆብን የያዕቆብንም ወንድም ዮሐንስን ቦአኔርጌስ ብሎ ሰየማቸው: የነጎድጓድ ልጆች ማለት ነው፤ እንድርያስንም | ጴጥሮስ ብሎ እንደ ገና የሰየመው ስምዖን: ወንድሙም እንድርያስ: ያዕቆብም ዮሐንስም: | ጴጥሮስና ዮሐንስም: ያዕቆብም: እንድርያስም |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **ሁለተኛው ቡድን** | ፊልጶስም በርተሎሜዎስም: ቶማስም ቀራጩ ማቴዎስም: | ፊልጶስንም በርተሎሜውስንም ማቴዎስንም ቶማስንም | ፊልጶስም በርተሎሜዎስም: ማቴዎስም ቶማስም: | ፊልጶስም: ቶማስም: በርተሎሜዎስም: ማቴዎስም: |
| **ሦስተኛው ቡድን** | የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብም ታዴዎስም የተባለው ልብድዮስ: ቀነናዊውም ስምዖን ደግሞም አሳልፎ የሰጠው የአስቆሮቱ ይሁዳ:: | የእልፍዮስን ልጅ ያዕቆብንም ታዴዎስንም ቀነናዊውንም ስምዖንን: አሳልፎ የሰጠውንም የአስቆሮቱን ይሁዳን:: | የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብም ቀናተኛ የሚባለው ስምዖንም: የያዕቆብ ይሁዳም: አሳልፎ የሰጠውም የአስቆሮቱ ይሁዳ ናቸው:: | የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብም: ቀናተኛ የሚባለው ስምዖንም: የያዕቆብ ልጅ ይሁዳም:: |

▣ **"በሕግ እና በነቢያት"** ይህ ከአይሁዳዊያን ቅዱሳት ሦስት ክፍሎች ሁለቱን ይወክላል፡ መጽሐፍቶቻው ሕግ፣ ነቢያት እና ጽሑፎች ተብለው ይከፈላሉ፡፡ ስለዚህ ይህ ንግግር ሙሉ ብሉይ ኪዳንን እንደማለት ነው፡፡

▣ **"የዮሴፍን ልጅ የናዝሬቱ ኢየሱስን"** ይህ በአይሁዳዊያን ዘይቤ ልንገነዘበው ይገባ፡፡ ኢየሱስ ይኖር የነበረው በናዝሬት ነው እንዲሁም ይኖርት የነበረው ቤት አባወራ ዮሴፍ ይባላል፡፡ ይህ ኢየሱስ በቤተልሔም መወለዱን መካድ አይደለም (ሚል 5፡2) ወይም ከድንግ መወለዱን አይክድም (ኢሳ 7፡14)፡፡ ከዚህ በታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት፡፡

**ተጨማሪ የጥናት ርዕስ የናዝሬቱ ኢየሱስ**

አዲስ ኪዳን ኢየሱስን ለመጥቀስ የሚጠቀማቸው በርካታ የተለያዩ የግሪክ ስያሜዎች አሉ፡፡

ሀ. የአዲስ ኪዳን ስያሜዎች

1. **ናዝሬት**፡- በገሊላ የምትገኝ ከተማ (ሉቃስ 1:26፤2:4፤39፤51፤4:16፤ሐዋ 10:38)፡፡ ይህች ከተማ አሁን ባሉት ምንጮች አልተጠቀሰችም ነገር ግን በኃለኛቹ የድንጋይ ላይ ፅሑፎች ተገኝታለች፡፡
   ኢየሱስ ከናዝሬት መሆኑ የሚያስመስግነው ነገር አልነበረም (ዮሐንስ 1:46 ን ያስ)፡፡ በክርስቶስ መስቀል ላይ ተደረገው ምልክት ይህችን ሥፍራ ማካተቱ የአይሁዳዊያ ንቀት ምልክት ነበር፡፡
2. **ናዛሪኖስ**፡- ጂኦግራፊያዊ ሥፍራን የሚያመለክት ይመስላል (ሉቃስ 4:34፤24:19ን ያስ)፡፡
3. **ናዞራዮስ**፡- ከተማን ሊያመለክት ይችላል፤ ነገር ግን "ቅርንጫፍ" በሚለው የእብራይጡ መሲሐዊ ስያሜ ላይ ተደርገ የቃላት መራቀቅም ሲሆን ይችላል (netzer ኢሳ 4:2፤11:1፤53:2፤ ኤር 23:5፤33:15፤ ዘካ 3:8፤6:12፤ በአዲስ ኪዳን ራዕ 22:6)፡፡ ሉቃስ ኢየሱስን ለማመለከት ይህንን ይጠቅላል 18:37 እና ሐዋ 2:22፤3:6፤4:10፤6:14፤22:8፤24:5፤26:9)፡፡

4. በቁጥር 3 ላይ *ናዚር* ከሚለው *ጋር* የሚዛመድ ነው ይህም "በመሐላ አማካኝነት የተለየ" ማለት ነው፡፡

ለ. ከአዲስ ኪዳን ውጪ ያለው ታሪካዊ አጠቃቀም

1. የአይሁድን (ቅድመ ክርስትና) የኑፋቄ ቡድንን ያመለክት ነበር (አራማይክ፣ ናሶራያ)፡፡
2. በአሁድ ዘንድ በክርስቶስ ያሉትን አማኞች ለማመልከት ይጠቀስ ነበር (ሐዋ 245፡14፤28:22፤ኖስሪ).
3. በሶሪያ (አራማይክ) ቤተክርስትያናት ያሉትን አማኞች ለማመለክት የተለመደ መጠሪያ ሆነ፡፡ "ክርስትያን" የሚለው መጠርያ በግሪክ ቤተክርስትያናት ውስጥ ያሉትን አማኖች ለማመልከት ይጠቀስ ነበር፡፡
4. በአንድ ወቅት ከኢየሩሳሌም መፍረስ በኃላ ፈሪሳዊያን በጃምኒያ ተሰባደበው በምኩራብ እና በቤተክርስትያ መካከል ግልፅ የሆነ ልዩነት እንዲኖር አቀነባበሩ፡፡ ክርስትያኖን በሚመለከት ያስተላለፉት የእርግማን ቀመር ምሣሌ በቤራኮት 28ለ-29ሀ ላይ በተጠቀሰው "አስራ ስምንቱ ቡራኬዎች" በሚለው ላይ የሚገኝ ሲሆን ይህም አማኞችን "ናዝራዊያን" ብሎ ይጠራቸዋል፡፡

"ናዝራዊያንና መናፍቃን በቅፅበት ይጥፉ፤ ከሕይወትም መፅሐፍ ይጥፉ ከሚታመኑት ጋርም አይፃፉ"፡፡

5. ቃሉ በጀስቲን ማርቲየር ተጠቅሶ ነበር *Dial 126:1* እርሱም ኢሳያስ ኢየሱስን "ቅርንጫፍ" ብሎ የገለፀውን የጠቀሰ ነበር፡፡

ሐ. የፀሐፊው አስተያየት

ምንም እንኳ በብሉይ ኪዳን ውስጥ እንዳለው "ጀሽዋ" በእብራይስጡ በርካታ እና የተለያዩ የቃላት አፃፃፍ እንዳሉት የማይሰማ ባይሆንም በስያሜው የተለያዩ የቃላት አፃፃፍ መደነቂ አልቀረም፡፡ ቁርጥ ያለ ትርጉሙን በሚመለከት የሚከተሉት ነገሮች እርግጠኛ እንዳልሆን ያደርጉኛል፤

1. "ቅርንጫፍ" (netzer) ከሚለው መሲሐዊ መጠሪያ (ስያሜ ጋር ያለው ቅርበት፣ ያለው ግኑኝነት ወይም "ናዚር" ከሚለው ተመሳሳ ስያሜ ጋር ለው ግንኝነት (በመሐላ አማካኝነት ተለይዩ የተሰጠ ማለት ነው)፡፡
2. ገሊላ የሚለው ስያሜ ያለው አሉታዊ ድባብ
3. በገሊላ ስላለችው የናዝሬት ከተማ አሁን ያለው በጣም ውስን የሆነ መረጃ ወይም ምንም መረጃ አለመኖር
4. ነገረ-ፍፃሜን በሚያለክት ሁኔታ ከአጋንንት አንደበት መስማቱ ("በውኑ ስተጠፋን መጣህን?")

የዚህን ቃል ወገን በሚመለከት ሙሉ የሆነ ጥናት ለማድረግ የሚረዳዎት ዋቢ መፃሕፍት የከሊን ከራውንን *New International Dictionary of New Testament Theology* ቁጥር 2፣ ገጽ 346 ወይም ሬይሞንድ.ኢ.፡- Birth- ገጽ 209-213፣ 223-225 ይመልከቱ፡፡

**1፡46 "ከናዝሬት መልካም ነገር ሊወጣ ይችላልን? አለው"** በእርግጥ ፊልጶስ እና ናትናኤል የብሉይ ኪዳን ትንብቶችን ያውቃሉ፤ መስሑ ከእየሩሳሌም አቅራቢያ ከሚትገኘው ከቤተልሔም (ሚል 5፡2) እንጂ ከአሕዛበ ከተማ በገሊላ ከሚትገነው ናዝሬት አይደለም ነገር ግን ኢሳ 9፡1-9 ይህንን ይላል!

1፡47

| | |
|---|---|
| NASB፣ NKJV | |
| NRSV፣ | **"ተንኮል የሌለበት"** |
| TEV | **"ምንም ሀሰት የሌለበት"** |
| NJB | **"ማታለል የሌለበት"** |

ይህ ማለት ምንም የተደበቀ መነሻ ሀሳብ የሌለው ቀጥተኛ ሰው (ፊል 32፡2)፤ የተመረጡት ሕዝቦች፣ የእስራኤላዊያን እውነተኛ ወክል ማለት ነው፡፡

**1፡48 "ኢየሱስም መልሶ፡ ፊልጶስ ሳይጠራህ: ከበለስ በታች ሳለህ: አየሁህ አለው"** በእርግጥ ኢየሱስ ለናትናኤል ምልክት ስሰጠው እና መሲሕ እንደሆነ ስነገረው ልእለ ተፈጥሮአዊ እውቀቱን በዚህ ስፍራ ላይ ተጠቅሚል (ይህም ማለት 2፡24-25 4፡17-19፤ 2፡61፣ 64፣ 71፤ 13፡1፣ 11፣ 27፣ 28፤ 16፡19፣ 30፤ 18፡4)፡፡

የኢየሱስ አምላክነት እና ሰውነት እንዴት ተግባራቸውን እንደሚፈጽሙ መረዳት አዳጋች ነው፡፡ በአንዳንድ ምንባባት ላይ ኢየሱስ መለኮታዊ ኃይሉን ወይስ ሰዋዊ ችሎታውን እየተጠቀመ እንደሆነ መለየት ያስቸግራል፡፡ በዚህ ስፍራ ላይ ግን መሎታዊ ችሎታውን ያሳያል፡፡

**1፡49 "ናትናኤልም መልሶ፡ መምህር ሆይ: አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ፤ አንተ የእስራኤል ንጉሥ ነህ አለው"** ሁለቱ ማዕረጎችን አስተውሉ፡፡ ሁለቱም ሀገራዊ የመሲሕነት ትርጓሜ እንዳላቸው ተመልከቱ፡፡ (መዝ 2 ይመልከቱ፡፡) እነዚህ የጥንት ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን በአይሁዳዊያን መረዳት ነው የሚረዱት፡፡ የእርሱን ስብእና እና መከራን የሚቀበል አገልጋይ መሆን እስከ ትንሳዔ ድርስ ሙሉ በሙሉ አልተረዱትም (ኢሳ 53)፡፡

1፡51

| | |
|---|---|
| NASB፣ | **"እውነት እውት እለችኂለሁ"** |
| NKJV | **"በእርግጠኝነት እላችኂለሁ"** |
| NRSV | **"በእውነት እላችኂለሁ"** |

TEV "እውነቱን እነግራችኋለሁ"
NJB "በእውነት"

የዚህ ነገር ደረቅ ትረጉሙ "አሜን! አመተን!" ማለት ሲሆን ኢየሱስ ይህንን ቃል በተከታታይ ሁለት ጊዜ የተጠቀመው በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ሲሆን ሃያ አምስት ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል። "አሜን" የዕብራይስጥ ቃል ሲሆን ትርጓሜ እምነት ማለት ነው። (ልዩ ርዕስ 1፤14 ይመልከቱ።)። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ለመረጋጋት እና ለመታመን የሚያመለክት ምሳሌ ሆኖ ቀርቧል። "እምነት" ወይም "መታመን" ተብሎ ይተረጎማል። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ማረጋገጫ ወይም መስማማትን ለመግለጽ አገልግሎት ላይ ይውላል። በዚህ ዓፍተ ነገር ውስጥ በመጀመሪያ መምጣቱ የኢየሱስ ንግግር እውነተኝነትን ወይም ከያሕዌ ያገኘው መገለጥ መሆኑን ለማረጋገጥ ውሏል (ከ 1:51፤ 2:3፣ 5፣ 11፣ 5:19፣ 24፣ 25፤ 6:26፣ 32፣ 47፣ 53፤ 8:34፣ 51፣ 58፤ 10:1፣ 7፤ 12:24፤ 13:16፣ 20፣ 21፣ 38፤ 14:12፤ 16:20፣ 23፤ 21:18)።

በብዙ ቁጥር ላይ (ተውላጠ ስም እና ግሥ) ያለውን ለውጥ ያስተውሉ ይህም በዚያ ለነበሩት በሙሉ የተሰጠ ምንሻ መሆን አለበት።

**ልዩ ርዕስ፡ አሜን**

1. ብሉይ ኪዳን

ሀ. "አሜን" የሚለው ቃል የመጣው ከዕብራይስጥ ቃል
   1. "እውነት"
   2. "እውነተኛ"
   3. "እምነተ" ወይም " የሚታመን"
   4. "ታማኝ"

ለ. የቃሉ ሥረወ ግንድ ምንጭ አካላዊ አለመዋዠቅ ነው። የዚህ ቃል ተቃራኒ የማይጸና፣ ተንሸራታች (ዘዳ 28:64-67፤ 38:16፤ መዝ 40:2፤ 73:18፤ ኤር 23:12)። ከዚህ የቃሉ ቀጥተኛ ትረርጉም ምሳሌያዊ ትርጓሜው ተወስዷል ይኼውም ታማኝነት፣ የሚታመን፣ ሀቀኛ እና የመሳሰሉት ናቸው (ዘፍ 15:16፣ እንባቆም 2:4)

ሐ. ልዩ የቃሉ አጠቃቀም
   1. አማድ 1 ነገስት 18:16 (1 ጢሞ 3:15)
   2. ማረጋገጫ ዘጸ 17:12
   3. የማይናወጥ ዘጸ 17:12
   4. የተረጋጋ ኢሳ 33:6፤ 34:5-7
   5. እውነት 1 ነገ 10:6፤ 17:24፤ 22:16፤ ምሳ 12:22
   6. ጽናት 2 ዜና 20:20፤ ኢሳ 7:9
   7. የሚታመን መዝ 119:43፣ 142፣ 151፣ 168

መ. በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚሰራ እምነት ለማመልከት ሌላ የዕብራይስጥ ቃል አገልግሎት ላይ ውሏል
   1. ባታህ፣ መታመን ማለት ነው
   2. ያራ መፍራ፣ ማክበር፣ ማልከም ማለት ነው

ሠ. የዚህ ቃል ሥነ መለኮታዊ እሳቤ የሰው ልጆች ታማኝነት ሳይሆን የያሕዌ ታማኝነት ነው (ዘጸ 34:6፣ ዘዳ 32:4፤ መዝ 108:4፤ 115:1፤ 117:2፤ 138:2)። የወደቀው የሰው ልጅ ብቸኛ ተስፋ የያሕዌ ምህረት የሞላበት የቃል ኪዳን ታማኝነት እና የእርሱ የተስፋ ቃል ነው። ያሕዌን የሚያውቁት ሁሉ እንደ እርሱ ልሆኑ ይገባል (ዕባ 2:4) መጽሐፍ ቅዱስ እግዚኢብሔር በሰው ልጆች ውስጥ መልኩን ለመመለስ የሚያደርገው ጥት ታርክ እና ዘገገባ ነው (ዘፍ 1:26-27)። ድነት የሰው ልጆችን ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቅ ግንኙነት የማድግ ብቃትን የሚመለስበት ነው። ለዚህም ነው እኛ የተፈጠርነው።

II. አዲስ ኪዳን

ሀ. "አሜን" የሚለው ቃል የተለያዩ ሀይማታዊ አዎንታዎች ትክክለኝነታቸውን ለማረጋገጥ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ብዙ ጊዜ አገልግሎት ላይ ውሏል። (1ቆሮ 14:16፣ 2ቆሮ 1:20፣ ራዕ 1:7፣ 5:14፣ 7:12)

ለ. ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከጸሎጾች ጋር ተያይዞ ይገኛል (ሮሜ 1:25፤ 9:5፤ 11:36፤ 16:27፤ ገላ 1:5፤ 6:18፤ ኤፌ 321፤ ፊል 4:20፤ 2 ተሰ 3:18፤ 1ጢሞ 1:17፤ 6ለ16፤ 2ጢሞ 4:18)።

ሐ. ይህንን ቃል በጣም ጠቃሚ አረፍተ ነገርን ለመጀመር የተጠቀመበት ኢየሱስ ብቻ ነው (ይህም በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ተከታታይ ሆኖ ተገልጾዋል) (ሉቃ 4:24፣ 12:37፤ 18:17፣ 29፤ 21:32፤ 23:43)

መ. በራዕ 3:14 ላይ የኢየሱስ ማዕረግ ሆኗል (ምናልባትም ከኢሳ 65:16 የያሕዌ ማዕረግ ሊሆን ይችላል)።

ሠ. የታማኝነት ወይም የእምነት፤ የመታን የሚሉ ቃላት የግሪክ ቃል የሆነው ፒስቶ ወይም ፒስቲስ የሚያመለክቱ ሲሆን ወደ አማርኛ ስተረጎሙ "መታመን"፣ "እምት" ወይም" ማመን" ማለት ነው።

▣ "ሰማይ ሲከፈት" በዚህ ሀረግ ውስጥ የብሉይ ኪዳን የሰውኛ ዘይቤአዊ አገላለጽ ይንጸባረቅበታል።
1. ሕዝ 1:1
2. ኢየሱስ፤ ማቴ 3:16፤ ማር 1:10፤ ሉቃ 3:21
3. እስጥፋኖስ፣ ሐዋ 7:56

4. *ቆርኔሎዮስ ሐዋ* 10፡11
5. *ዳግም ምጻት ራዕ* 19፡11

*ይህ ድርጊቱ መጠናቀቁን የሚያሳይ ገላጭ ቦዝ አንቀፅ ሲሆን በተዘዋዋሪ የሚጠቅሰው የሰማያትን መከፈት ነው። "ሰማያት" የሚለው መጠሪያ የብዙ ቁጥር ነው ምክንያቱም በእብራይስጥም ቃሉ ብዙ ቁጥር ነውና። ይህም ሊያለክት የሚችለው* (1) *በዘፍጥረት ላይ እንዳለው ከምድር በላይ ያለውን አየር ወይም* (2) *የእግርአብሔር ሕልወና የሚገኝበትን ነው።*

**ልዩ ርዕስ፡ ሰማይ**

*በብሉይ ኪዳን ሰማይ ብዙ ቁጥር ነው። የዕብራይስጡ ቃል ትርጓሜ "ከፍታ" ማለት ነው። እግዚአብሔር በከፍታዎች ውስጥ ያድራል። ይህ ሀሳብ የሚያንጸባርቀው የእግዚብሔርን ቅድስና እና ምጡቅነት ነው።*

*በዘፍ* 1፡1 *ብዙ ቁጥር የሆነው "ሰማይ እና ምድር" በእግዚአብሔር እንደተፈጠረ ተገጸዋል* (1) *ከዚህ ፒላኔት ውጭ ያለው ከባቢ ወይም* (2) *ለሁሉም ነበራዊ ሁኔታል ለማሳየት ሊሆን ይችላል። ከዚህ መሰረታዊ ጥቅስ በመነሳት ሌሎች ጥቅሶች ይህንን በመውሰድ የሰማያትን ደረጃዎች ይናገራሉ "ሰማይ ሰማያት" ብለው ያወራሉ።* (*መዝ* 68፡33)(*ዘዳ* 10፡14፣ 1*ነገ* 8፡27፤ *ነህ* 9፡6፤ *መዝ* 148፡4)። *መምህራን ይህንን ስጠቀልሉት*

1. *ሁለት ሰማያት እዳሉ* (*አር. ይሁዳ*፣ *ሐጌ*)
2. *ሦስት ሰማያት*
3. *አምስት ሰማያት* (3 *ባሩክ*)
4. *ሰባት ሰማያት*
5. *አስር ሰማያት* (2 *ሄኖክ* 20፡3፤ 22፡1)

*እነዚህ ሁሉ ለማሳየት የታለሙት እግዚብሔር ከግኡዙ ዓለም የተለ መሆኑን እና ምጡቅ መሆኑን ነው። በአብዛኛዎቹ በይሁዳ የሚገኙ አይሁዳዊያን አመለካከት ሰማያት ሰባት መሆናቸው ነው።*

*ጳውሎስ በ*2 *ቆሮ* 12፡2 *የእግዚአብሔርን ግላዊ፣ ንጉሣዊ ክብር ለማሳየት ስለ ሦስተኛ ሰማይ ጠቅሶዋል። ጳውሎስ በግሉ ከእግዚአብሔር ጋር ተገናኝቷል!*

▣ **"የእግዚአብሔርም መላእክት . . . ሲወጡና ሲወርዱ"** *ይህ ያዕቆብ በቤተልሔም ከተለማመደው ነገር ላይ የተወሰደ ነው* (*ዘፍ* 28፡10)። *እግዚአብሔር የያዕቆብን ፍላጎት ሁሉ ለማሟላት የተስፋ ቃልን እንደገባ ሁሉ የእርሱንም ፍላጎቶች እንደሚያሟላ እየገለጸ ነበር።*

▣ **"የሰው ልጅ"** *ይህ ኢየሱስ ለራሱ የሰጠው ስም ነበር። ይህ የዕብራዊያን ሀረግ ሲሆን የሰው ልጅ መሆንን ያመለክታል* (*መዝ* 8፡4፣ *ሕዝ* 2፡1)። *ነገር ግን በዳንኤል* 7፡13 *ላይ የተገለጸው ግን መለኮታዊ ባህርን ያመለክታል። ይህ ቃል ሀገራዊ ጀግንነትን ወይም ወታደራዊ ይዘት ዬለውም ነገር ግን በመምህራንም ጥቅም ላይ አልዋለም። ኢየሱስ ይህንን ቃል የመረጠበት ምክንያት የእርሱን ሁለት ህሪያት ጥንቅቆ ስለሚይዝ ነው* (*መለኮታዊ እና ሰዋዊ ባህሪያቱን* 1 *ዮሐ* 4፡1-3 *ጋር ያነጻጽሩ*)። *ዮሐንስ ኢየሱስ ይህንን ቃል* 13 *ጊዜ ያህል ስጠቀምበት በጽሑፉ ውስጥ አስቀምጧል።*

***መወያያ ጥያቄዎች***

*ይህ ምሪትን የሚሰጥ የመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻ ነው፤ ይህም ማለት ለምትደረስበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ኃላፊነት የምትወስደው አንተ እራስ ትሆናህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን ባለን ብርሃን መጠን ልንመላለስ ይገባል ማለት ነው። በስነ አፍታት ሂደት ውስጥ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ዋነኛውን ስፍራ ትይዛላችሁ። ይህንን እድል ለመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻዎች አሳልፈህ አትስጥ።*

*ከዚህ በታች የተጠቀሱት የመወያያ ጥያቄዎች በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ባሉት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ማሰላሰል እንድትችሉ ለማገዝ የተዘጋጁ ናቸው። የሚገድቡህ ሳይሆን የማሰላሰል ምናብን እንዲያሰፉልህ የታቀዱ ናቸው።*

1. *ከእየሩሳሌም የተላኩት ሰዎች ለምን መጥመቁ ዮሐንስን በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከተጠቀሱት ሰዎች መካከል ዬትኛው እንደሆነ እንድነግራቸው ጠየቁት?*
2. *በቁ* 19-30 *ውስጥ መጥመቁ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ ከተናገራው ነገሮች መካከል ስነ ክርስቶሳዊ የሆነው አረፍተ ነገር የቱ ነው?*
3. *ተመሳሳይ ወንጌላት እና የዮሐንስ ወንጌል በደቀ መዛሙርቱ ጥር ላይ የሚለያዩት ለምንድነው?*
4. *እነዚህ ሰዎች ስለ ኢየሱስ የተረዱት ምንድ ነው; በምን ማዕረግ እንደጠሩት አስተውል* (*ቁ* 38)
5. *ኢየሱስ እራሱን ምን ብሎ ይጠራ ነበር፤ ለምን?*

# ዮሐንስ 2

## የዘመናችን የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀጽ ክፍፍል

| UBS[4] | NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| የቃና ዘገሊላ ሰርግ | ውሃ ወደ ወይን መለወጡ | የቃና ዘገልላ ሰርግ | የቃና ዘገልላ ሰርግ | የቃና ዘገልላ ሰርግ |
| 2፡1-11 | 2፡1-12 | 2፡1-11 | 2፡1-3 | 2፡1-10 |
| | | 2፡4 | | |
| | | 2፡5 | | |
| | | 2፡6-10 | | |
| | | 2፡11 | | 2፡11-12 |
| 2፡12 | 2፡12 | 2፡12 | | |
| ቤተ መቅደሱን ማጥራቱ | ቤተ መቅደሱን ማጥራቱ | ቤተ መቅደሱን ማጥራቱ | ቤተ መቅደሱን ማጥራቱ | ቤተ መቅደሱን ማጥራቱ |
| 2፡13-22 | 2፡13-22 | 2፡13-22 | 2፡13-17 | 2፡13-22 |
| | | | 2፡18 | |
| | | | 2፡19 | |
| | | | 2፡20 | |
| | | | 2፡21-22 | |
| ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ያውቃል | የልብ አዋቂ | | ኢየሱስ የሰው ልጆችን ባሕርይ ማወቁ | ኢየሱስ በእየሩሳሌም |
| 2፡23-25 | 2፡23-25 | 2፡23-25 | 2፡23-23 | 2፡23-25 |

**ሦስተኛ ዙር ንባብ**

***በአንቀጽ ደረጃ የመጽሐፉ ጸሓፊ ሊያስተላልፍ የፈለገውን ሀሳባ መከተል***

ይህ ምሪትን የሚሰጥ የመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻ ነው፤ ይህም ማለት ለምትደረስበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ኃላፊነት የምትወስደው አንተ እራስ ትሆናህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን ባለን ብርሃን መጠን ልንመላለስ ይገባል ማለት ነው፡፡ በስነ አፍታት ሂደት ውስጥ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ዋነኛውን ስፍራ ትይዛላችሁ፡፡ ይህንን እድል ለመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻዎች አሳልፈህ አትስጥ፡፡

መጽሐፉን በአንድ ጊዜ ለሁለተኛ ጊዜ አንብበህ ጨርስ፡፡ ዋና ዋና ሀሳቦችን ግለጽ እንዲሁም ዋናውን ሀሳ በአንድ አረፍተ ነገር ግለጽ፡፡

1. የመጀመሪያውን አንቀጽ ዋና መልዕክት

2. የሁለተኛውን አንቀጽ ዋና መልዕክት

3. የሦስተኛውን አንቀጽ ዋና መልዕክት

4. ወዘተ

ለ2፡1-11 አውዳዊ አብርሆት

ሀ. ኢየሱስ በዘመኑ ከነበሩት የሃይማት መሪዎች የተለየ ነበር፡፡ መጥመቁ ዮሐንስ ከበራሃ የመጣ ግላዊ ሰው ነበረ ሲሆን ኢየሱስ ግን በሰዎች መካከል የነበረ ግላዊ ሰው ነበር፡፡

ለ. የመጀመሪያው ምልክቱ አከባቢያዊ እና ቤተሰባዊ ነበር፡፡ እንክብከካቤ እና ለተራ ሰዎች መቆም የኢየሱስን አንዱ ባህርይን የሚያሳይ ሲሆን በሌላ በሉል ደግሞ የሃይማት መሪዎች ባላቸው እራስን የማጽደቅ ባህርይ ይበሳጭ ነበር፡፡ ለሕዝቦች እንጂ ለትውፊት ቅድሚያ አይሰጥም፤ ይም የኢየሱስን ነጻነት ያሳያል እንዲህም ሆነ ለባሕሉ ትልቅ አክብሮት ነበረው፡፡

ሐ. ዮሐንስ የኢየሱስን ባህርይ እና ኃይል ለመገልጽ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀማቸው ሰባት ምልክቶች እነዚህ ናቸው

1. ውሃን ወደ ወይን መቀየሩ (2፡1-11)
2. አንድ ልጅን መፈወሱ (4፡46-54)
3. ሽባውን መፈወሱ (5፡1-18)
4. ሕዝቡን መመገቡ (6፡1-15)
5. በውሃ ላይ መራመዱ (6፡16-21)
6. ዐይነ ስውሩን መፈወሱ (9፡1-41)
7. አላዛርን ከሞት ማስነሳቱ (111-57)

የቃላት እና የሀረጎች ጥናት

**የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 2፡1-11**
**በሦስተኛውም ቀን በገሊላ ቃና ሰርግ ነበረ: የኢየሱስም እናት በዚያ ነበረች፤ ኢየሱስም ደግሞ ደቀ መዛሙርቱም ወደ ሰርጉ ታደሙ፡፡ የወይን ጠጅም ባለቀ ጊዜ የኢየሱስ እናት፡፡ የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም አለችው፡፡ ኢየሱስም፦ አንቺ ሴት: ከአንቺ ጋር ምን አለኝ? ጊዜዬ ገና አልደረሰም አላት፡፡ እናቱም ለአገልጋዮቹ፡፡ የኢየሱስም፦ ጋኖቹን ውኃ ሙሉአቸው አላቸው፡፡ እስከ አፋቸውም ሙሉአቸው አላቸው፡፡ እስከ አፋቸውም ሞሉአቸው፡፡ሚላችሁን ሁሉ አድርጉ አለቻቸው፡፡ አይሁድም እንደሚያደርጉት የማንጻት ልማድ ስድስት የድንጋይ ጋኖች በዚያ ተቀምጠው ነበር: እያንዳንዳቸውም ሁለት ወይም ሦስት እንስራ ይይዙ ነበር፡፡ አሁን ቀድታችሁ ለአሳዳሪው ስጡት አላቸው፤ ሰጡትም፡፡አሳዳሪውም የወይን ጠጅ የሆነውን ውሃ በቀመሰ ጊዜ ከወዴት እንደ መጣ አላወቀም፤ ውኃውን የቀዱት አገልጋዮች ግን ያውቁ ነበር፤ አሳዳሪው ሙሽራውን ጠርቶ፡፡ ሰው ሁሉ አስቀድሞ መልካሙን የወይን ጠጅ ያቀርባል: ከሰከሩም በኋላ መናኛውን፤ አንተስ መልካሙን የወይን ጠጅ እስከ አሁን አቆይተሃል አለው፡፡ ኢየሱስ ይህን የምልክቶች መጀመሪያ በገሊላ ቃና አደረገ፤ ክብሩንም ገለጠ: ደቀ መዛሙርቱም በእርሱ አመኑ፡፡**

2፡1 "ሰርግ ነበር" በመንድር ውስጥ ሰርግ አንድ ዋነኛ የማህበረሰብ ተግባር ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ማህበረሰቡን ሁሉ ያካትታል እንዲሁም ለብዙ ጊዜያት ይቆያል፡፡

▣ "ቃና" ይህ ቃል በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ብቻ ተጠቅሶ ይገኛል (2፡1፣ 11፤ 4፡46፤ 21፡2)፡፡ ስለዚህም ትንሽ ነገሮችን እናውቃን

1. የናትናኤል የትውልድ ቁዬው እንደሆነ
2. ኢየሱስ ለመጀመሪያ ጊዜ ተአምራ መድረግ የጀመረበት ቦት
3. ለቅፍረናሆም ቅርብ መሆኑን

ይህንን ስፍራ በተመለከተ ሦስት ልሆኑ ይችላሉ የተባሉ ስፍራዎች ይኖራሉ

1. ኢን ቃና፤ ከናዝሬት በሰሜን በኩል አንድ ማይል ርቀት ላይ የሚትገኝ ከተማ
2. ካፋር ካና፤ ከናዝሬት በሰሜን ምስራቅ በኩል ሦስት ማይል ርቃ የሚትገኝ ከተማ
3. ቅርበት ቃና፤ ከናዝሬት በሰሜን በኩል ተራራ ላይ ስምንት ተኩል ማይል ርቆ የሚገኝ ከተማ
4. ቃና በሾቺሽ ረባዳማ ቦታ ላይ የሚገኝ፣ በጆሴፈስ ተጠቅሷል

በአራተኛው ተራ ቁጥር ላይ ያለው ለዚህ አውድ ተስማሚ ይመስላ፡፡

▣ "የኢየሱስም እናት በዚያ ነበረች" ማርያ በዚያ ስፍራ ላይ የሰርጉ ሥነ ስረዓት ላይ ታግዛቸው ነበር፡፡ ይህ (1) አገልጋዮችን በማዘዝ ሊሆን ይችላል (ቁ 5) (2) ስለ መዝናኛ ነገሮች ማሰቧ (ቁ 3)፡፡ ምናልባትም ዘመዶቿ ወይም ጓደኞቿ ልሆኑ ይችላሉ፡፡

2:3 **"ወይን ጠጁ ማለቁ"** በዕብራዊያ ባህል መሠረት ለእንግዳ የወይን ጠጅ ማቅረብ ግዴታ ነው። እርግጥ ነው ወይኑ የሚያሰክር ነው። ይህንን የምንረዳው (1) አስተናጋጁ ከምሰጠው አስተያየት ነው ቁ 9-10 (2) ኢየሱስ በኖረበት ዘመን የአይሁዳዊያን ባህል ወይም (3) የንጽና ወይም የኬምካል ነገሮች አለመኖራቸው።

**ልዩ ርዕስ: ስለ መጠጥ እና ስለ መጠጥ ሱሰኝነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከት**

I. መጽሐፍ ቅዱስ ቃላት

ሀ. ብሉይ ኪዳን

1. *ያይን* ይህ ለወይን አጠቃላይ ቃል ነው፣ 141 ጊዜ ተጠቅሷል። የዚህ ቃል ሥረወ ግንድ አይታወቅም ምክንያቱም መሠረቱ የዕብራይስጥ ቃል ስላልሆነ ነው። ሁል ጊዜም ትርጓማ የሚያሰክር የፍራፍሬ ጭማቂ፣ ብዙ ጊዜ ደግሞ የእንጆር ማለት ነው። ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑ ክፍሎች ዘፍ 9:21፣ ዘጸ 29:40፣ ዘኍ 15:5፣ 10 ናቸው።
2. *ቲሮሹ* ይህ "አዲስ ወይን" ማለት ነው። በምስራቅ አከባቢ ካለው የአየር ሁኔታ የተነሳ አንድ ጭማቂ ከተጨመቀበት ጊዜ አንስቶ በስድስት ሰአታት ጊዜ ውስጥ መፍላት ይጀምራል። በዚህ ሂደት ውስጥ ያለውን ወይን ለመመልከት የሚጠቀሙበት ቃል ነው። ለዚህ ተስማሚ ክፍሎች ዘዳ 12:17፣ 18:4፤ ኢሳ 62:8-9፤ ሆሴ 4:11 ናቸው።
3. *አሲሱ* ይህ በግልጽ አልኮልነት ያላቸው መጠጦችን ያመለክታል (ኢዮ 1:5፤ ኢሳ 49:26)
4. *ሰካር-* ይህ ማለት " በጣም የሚያሰክር መጠጥ" ማለት ነው። የዚህ ቃል ሥረወ ግንድ "መስከር" ወይም "ሰካራምነት" ያመለክታል። ይበልጥ እንዲያሰክር ተጨማር ነገሮች ይጨመሩበታል። ከያይን ጋር ተቀራቢ ነው። (ምሳ 20:1፤ 31:6 ኢሳ 28:7)።

ለ. አዲስ ኪዳን

1. *ኦኢኖስ-* ከያይን ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የግሪክ ቃል ነው
2. *ኒኦስ ኦኢኖስ* (አዲስ ወይን)- የቲሮሽ የግሪክ ተመጣጣኝ ቃል ነው (ማር 2:22)
3. *ግሌችኦስ ቪኖስ* (ጣፋጭ ወይን፣ አሲስ)- በመፍላት ላይ ያለ ወይን (ሐዋ 2:13 ጋር ያነጻጽሩ)።

II. መጽሐፍ ቅዱሳዊ የቃሉ አጠቃቀም

ሀ. ብሉይ ኪዳን

1. ወይን የእግዚአብሔር ስጦታ ነው (ዘፍ 27:28፤ መዝ 104:14-15፤ መክብብ 9:7፤ ሆሴ 2:8-9፣ ኢዮ 12:19፣ 24፣ አሞ 9:13፤ ዘካ 10:7)
2. ወይን ለመስዋእትነት ከምቀርቡት ነገሮች መካከል ነበር (ዘጸ 29:40፣ ዘለ 23:13፣ ዘኍ 15:7፣ 10፣ 28:14፤ ዘዳ 14:26፤ መሳ 9:13)
3. ወይን እንደ መዳንትነት ያገለግላል (2 ሳሙ 16:2፤ ምሳ 31:6-7)
4. ወይን ትልቅ ችግር ልፈጥ ይችላል (ኖህ- ዘፍ 9:21፤ ሎጥ ዘፍ 19:33፣ 35፤ ሳምሶን መሳ 16:19፣ ናባል 1 ሳሙ 25:36፤ ሪሃ 2 ሳሙ 11:13፤ አምኖን 2 ሳሙ 13:28፤ ኢላ 1 ነገ 16:9፣ ቢልዳድ 1ነገ 20:12፣ ገዥዎች አሞጽ 6:6 እና ሴቶች አሞጽ 4)
5. ወይን ለመጥፎ ተግባርም ልውል ይችላል (ምሳ 20:1፣ 23:29-35፣ 31:4-5፣ ኢሳ 5:11፣ 22፤ 19:14፤ 28:7-8 ሆሴ 4:11)
6. ለተወሰኑ ሰዎች ወይን ተከልክሏል (በስራ ላይ ላሉ ካህናት ዘለ 10:9፣ ሕዝ 44:21፣ ለናዝራዊያን ዘኍ 6 እና ለገዥዎች ምሳ 31:4-5፣ ኢሳ 56:11-12፤ ሆሴ 7:5)
7. ወይን ከመጨረሻው ዘመን ጋር ተያይዞ ተገልጾዋል (አሞ 9:13፣ ኢዮ 3:18፣ ዘካ 9:17)።

ለ. ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ ያሉ ማስረጃዎች

1. በመጠኑ የሚወሰድ ወይን ጠቃሚ ነው (መክብብ 31፤27-30)
2. መምህሩ እንዲህ ይላል "ወይን ከመዲሃኒቶች ሁሉ ፍትሁን መዳኒት ነው፤ ወይን በሌለበት መደሃኒቶች አስፈላጊዎች ናቸው"

ሐ. አዲስ ኪዳን

1. ኢየሱስ ብዙ ውሃን ወደ ወይን ጠጅነት ለውጧል (ዮሐ 2:1-11)
2. ኢየሱስ ወይንን ጠጥቷል (ማቴ 11:18-19፣ ሉቃ 7:33-34፣ 22:12)
3. በጴንጤቆስጤ ቀን ጴጥሮስ አዲስ ወይንን እንደጠጣ ተደርጎ ተወስዷል (ሐዋ 2:13)
4. ወይን እንደ መዳኒት ልወሰድ ይችላል (ማር 15:23፣ ሉቃ 10:34፤ 1ጢሞ 5:23)
5. መሪዎች ጠጭዎች መሆን ዬለባቸው። ይህ ማለት ግን ፈጽሞ የማይጠጡ ማለት ግን አይደለም። (1 ጢሞ 3:3፣ 8፣ ቲቶ 1:7፣ 2:3፣ 1ጴጥ 4:3)
6. ወይን ከመጨረሻው ዘመን ጋር ተያይዞ ቀርቧል (ማቴ 22:1 ራዕ 19:9)
7. ጠጭነት ተኮንኗል (ማቴ 24:49፣ ሉቃ 12:45፣ 21:45፣ 21:45፣ 21:34፣ 1ቆሮ 5:11-13፣ 6:10 ገላ 5:21፣ 1ጴጥ 4:3 ሮሜ 13:14-14

III. ሥነ መለኮታዊ አብርሆት

ሀ. ውጥረቶች

1. ወይን የእግዚአብሔር ስጦታ ነው
2. ጠጭነት ዋነኛ ችግር ነው
3. በአንዳንድ ባሕል ውስጥ ያሉ አማኞች ለወንጌል ስሉ ነጻነታቸውን መገደብ አለባቸው (ማቴ 15፡1-20፣ ማር 7፡1-23፣ 1ቆሮ 8-10 ሮሜ 14)

ለ. ከተፈቀደው በላይ የመሄድ ዝንባሌ
1. እግዚብሔር የመልካ ነገሮች ሁሉ ምንጭ ነው
2. የወደቀው የሰው ልጅ የእግዚአብሔር መልካም ስጦታ ከተፈቀደለት በላይ በመውሰድ ያበላሸዋል፡፡

ሐ. ጥፋቱ ከነገሪ ሳይሆን ከአጠቃቀሙ ነው፡፡ በተፈጥሮአዊው ነገር ውስጥ ምንም ክፉ ነገር ዬለም (ማር 7፡18-23፣ ሮሜ 14፡14፣ 20 1ቆሮ 10፡25-26፣ 1ጢሞ 4፡4፣ ቲቶ 1፡15)፡፡

IV. የመጀመሪያው ምዕተ አመት አይሁዳዊያን እና ፌርሜንቴሽ
ሀ. የወይን ጭማቅ ከተሰራበት ጊዜ አንስቶ በስድስት ሰአታት ውስጥ ፌርመንቴሽን ይጀምራል፡፡
ለ. በላይኛው ክፈፉ ላይ ትንሽ አረፋ መሰል ነገር መታየት ስጀምር ወይን መሆን ይጀምራል፡፡ ይህም "አዲስ ወይን" ይባላል ወይም "ጣፋጭ ወይን" ይባላል፡፡
ሐ. የመጀመሪያው የፈርመንቴሽን ሂደት የሚጠናቀቀው ከአንድ ሳምንት በኋላ ነው፡፡
መ. ሁለተኛው የፈርመንቴስን ሂደት ወደ 40 ቀናት ያህል ይወስዳል፡፡ በዚህ ደረጃ ላይ ያለ ወይን "የበሰለ ወይን" ይባላል እንዲሁም በመሰወዋው ላይ ልቀርብ ይችላል፡፡
ሠ. ይህ የበሰለ ወይን መልካም ቢሆንም ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት በደንብ ልጣራ ይገባዋል፡፡
ረ. አንድ ወይን የበሰለ ልባል የሚችለው ብዙ ጊዜ ለአንድ አመት በፈርመንቴሽን ሂደት ውስጥ ካለፈ በኋላ ነው፡፡ ሦስት አመት ደግሞ አንድ ወይን ሳይበለሽ ልቀመጥ የሚችልበት ዕድሜ ነው፡፡ እንዲህ አይነቱ ወይን " ያረጀ ወይን" ይባላል እንዲሁም በውሃ ልበረዝ ይገባዋል፡፡
ሰ. ባለፉት መቶ አመታት ግን በተለያዩ ኬምካሎች ምክንያት እነዚህ ጊዜያት ልያጥሩ ችለዋል፡፡ በጥንት ዘመን ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ግን ወይንን ፈርመንቴሽን ማስወገድ አልቻሉም ነበር፡፡

V. ማጠቃለያ ሀሳብ
ሀ. ልምዳችሁ፣ ሥነ መለኮታችሁ እና መጽሐፍ ቅዱስን የምትፈቱበት መንገድ የኢየሱስን ማንነት እና የመጀመሪያውን ምዕተ አመት አይሁዳዊያንን/ክርስቲያቸን ባሕል እንዳያባለሽ ጥንቃቄ ልታደርጉ ይገባል፡፡ በእርግጠኝነት መናገር የሚቻለው እነርሱ ወይን የምጠጡ እንደነበር ነው፡፡
ለ. እኔ ሰዎች አልኮል እንዲጠጡ የማበረታታ ሰው አይደለሁም፡፡ ነገር ግን ብዙዎች መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚናረውን ነገር በጣም በመለጠጥ እና በባህል/ በቤተ እምነት ተጽእኖ አማካኝነት ከፍጸኛ ጽድቅ እንዳላቸው ቆጥረዋል፡፡
ሐ. ለእኔ ግን ሮሜ 14 እና 1 ቆሮ 8-10 አብሪሆትን እና መመሪያዎችን ይሰጡኛል፤ ይህምም መመሪያ ፍቅን መሠረት ያደረገ እና ለአማኞች አክብሮት እና ለወንጌል በባህላችን ውስጥ መሰራጨት የሚያግዝ ነው፡፡ ይህ የግል ነጻነትን እንዲሁም ሰዎች ላይ መፍረድን አያበረታታም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የእምነታችን እና የልምምዶቻችን ብቸኛ ምንጭ ከሆነ ስለዚህ ጉዳይ እንደገነ ማሰብ ይገባና ማለት ነው፡፡
መ. ከዚህን ነገር ፈጽሞ መጻቀብን እንደ እግዚአብሔራዊ መንገድ አድርገን ከወሰድነው ስለ ኢየሱስ ምን እያልን ነው እንዲሁም በዘመናችን ባህል ውስጣ ስላሉ ሰዎችስ ምን እያልን ነው (ምሳሌ አውሮፓዊያን፣ ኢስራኤል፣ አርጀንቲና)

2፡4 "ሴት" በአማርኛ ቋንቋ ይህ ምናልባትም ጥሩ ንግግር ላይመስል ይችላል፡፡ ነገር ግን በዕብራይስጥ ፈልጣዊ ንግግር የአክብሮት የማእረግ ስም ነው (4፡21፣ 8፡10፣ 19፡26፤ 20፡15 ያነጻጽሩ)

▣

| | |
|---|---|
| NASB፣ | "ይህ ከእኛ ጋር ምን ያገኛኘዋል" |
| NKJV፣ | "የአንች ችግር ከእኔ ጋር ምን ያገናኘዋል" |
| NRSV | "ለአንች እና ለእኔ ይህ ምን ችግር ነው" |
| TEV | "ምን እንደማደረግ ልትነግርኝ አይገባም" |
| NJB | "ከእኔ ምን ትፈልጊያለሽ" |

ይህ የእብራዊያን ፈልጣዊ አነጋገር ነው (መሳ 11፡12፤ 2 ሳሙ 16፡10፤ 19፡22፤ 1ነገ 17፡18፤ 2 ነገ 3፡13፤ 2 ዜና 35፡21፤ ማቴ 8፡29፤ ማር 1፡24፤ 5፡7፤ ሉቃ 4፡34፤ 8፡28፤ ዮሐ 2፡4)፡፡ ይህ ምንአልባትም ኢየሱስ ከቤተሰቡ ጋር የነበረው ግንኙነት አዲስ መንገድ ነው (ማቴ 12፡46፤ ሉቃ 11፡27-28)

▣ "ጊዜዬ ገና አልደረሰም" ይህ የሚያሳየው ኢየሱስ የተላከበትን አላማ ጠንቅቆ ማወቁን ነው (ማር 10፡45)፡፡ ዮሐንስ "ጊዜ" የሚለውን ቃ በብዙ መንገድ ተጠቅሞበታል፡፡
1. ለሰአት (1፡39፤ 4፡6፣ 52፣53፤ 11፡9፤ 16፡21፤ 19፡14፤ 19፡27)
2. ለጊዜ መጨረሻ (4፡21፣ 23፤ 5፡25፣ 28)
3. ለመጨረጻዎቹ ቀናት (መያዝ፣ ችሎት፣ ሞት 2፡4፤7፡30፤8፡20፤12፡23፤27፤13፡1፤16፡32፤17፡1)፡፡

▣ *"የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ አለቻቸው" ማሪያም ኢየሱስ ስለ ሁኔታው የሰጠውን ምላሽ አልተረዳችም።*

2፡6

| | |
|---|---|
| NASB፣ | *"ለአይሁዳዊያን የመንጻት ስርአት"* |
| NKJV፣ | *"እንደ መንጻት ስርአት"* |
| NRSV | *"በአይሁዳዊያን የመንጻጽ ስርአት"* |
| TEV | *"አይሁዳዊያን የመጥበት ስርአተን በተመለከተ ደንቦች አሏቸው"* |
| NJB | *"በአይሁዳዊያ ዘንድ የመንጻትን በተመለከተ ያለ ልምድ"* |

እነዚህ ውሃ የያዙ ገንዳዎች እግር፣ እጅ፣ እና እቃዎችን ለማጠብ ስርአት የሚውሉ ናቸው። ዮሐንስ ይህንን አስተያየት የሰጠበት ምክንያት አሕዛቦች ስለ ሁኔታው ግንዛቤ እንዲያገኙ ለመርዳ ነው።

2፡6-7 *"ስድስት የድንጋይ ጋኖች"* እንደ ተለመደው ዮሕንስ ይህን ሀሳብ የገለጠው በሁለት ምክንያት ነው።

1. የሁለቱ ጥንዶችን ጋብቻ ለማገዝ
2. ይህ ምልክት ኢየሱስ የአይሁዳዊያን የመጨረሻው ፍጻሜ መሆኑን እያመለከተ ነበር። ከዚህ የመጨረሻው አረፍተ ነገር ያለው ምክንያት ምናልባት
    ሀ. "6" ቁጥር የሰው ልጆች ጥረትን የሚያመለክት ስለሆነ
    ለ. ኢየሱስ እያንዳንዱን ጋኖች በውሃ እንድሞሏቸው መጠየቁ ተጨማር ወይን ከመስጠት በዘለለ ተምሳሌታዊ ትርጉም ልኖረው ይችላል
    ሐ. ትንንሽ የመንደር ሰርጎች ውስጥ ልገኝ ከሚችለው በላይ ብዙ ወይን መኖሩን
    መ. ወይን የአዲሱ ዘመን የተትረፈረፈ በረከት ምልክት ነው (ኤር 31፡12፤ ሆሴ 2፡22፤ 14፡7፤ ኢዮ 3፡18፤ አሞ 9፡12-14)

▣ ***"እያንዳንዳቸውም ሁለት ወይም ሦስት እንስራ ይይዙ ነበር"*** በዚህ ስፍራ ላይ የተጠቀሰው የእብራዊያን መለኪያ መሠሪያ ባዝ ይባላል። ኢየሱስ በኖረበት ዘመን ሦስት ባዝ አይነቶች አገልግሎት ላይ ይውሉ ነበር ነገር ግን ይህ ተአምራት ብዙ ወይን እንደተገኘ ያመለክታል።

**ልዩ ርዕስ፡ የጥንት ምስራቃዊያ የክብደት እና የሊትር መሊያ (ሜትሮሎጂ)**

በጥንት በግብርና በሎተዳደሩ ምስራቅ አከባቢ የሚኖሩ ሕዝቦች ዘንድ የክብደት እና የተለያዩ ነገሮች መለኪያ መስፈርቶች እጅግ በጣም አስፈላጊ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ አይሁዳዊያን እርስ በእርሳቸው በሚያደርጉት ግንኙነት መካከል ፍትሓዊ እንደሆኑ ያሳስባል። (ዘለ 19፡35-36፣ ዘዳ 25፡13-16፣ ምሳ 11፡1፤ 16፡11፤ 20፡10)። ችግሩ የነበረው ሀቀኝነት ብቻ ሳይሆን በፍልስጤም ውስት ደረጃቸውን ያልጠበቁ መስፈርቶች አገልግሎት ላይ ይውሉ ስለነበር ነው። ሁለት አይነት የክብደት መለኪያ መሠሪያዎች ያሉ ይመስላል ፡ "ቀላል" እና "ከባድ"።

ብዙዎቹ ቁመት ተኮር የሆኑ መለኪያዎ የሰው ልጅን አካል፣ የእንስሳትን የጭነት አቅም እና የገበሪዎችን መያዥያዎች ያማከሉ በመሆናው መስፈርትን አያሟሉም። ስለዚህም ብዙ ግምት እና ጊዜዊ ናቸው። ክብደት እና ርዝማኔን የማሳያ ቀላሉ መንገድ እርስ በእርስ ያላቸው ግንኙነት በሰንጠረዥ ማሳየት ነው።

I. ብዙ ጊዜ መጠንን ለመግጽ የሚያገለግሉ ቃላት
  ሀ. የደረቅ መለኪያ
    1. ሆመር (ምናልባትም የ"አህያ ጭነት" ሊሆን ይችላል) ምሳሌ ዘለ 27፡6፤ ሆሴ 3፡2
    2. ሌቴከሃ (ምናልባት ከሆሴ 3፡2 ተወስዶ ሊሆን ይችላል)
    3. ኢፋሃ ምሳሌ ዘጸ 16፡36፤ ዘለ 19፡36፤ ሕዝ 45፡10-11፣ 13፣ 24
    4. ሲሃ ዘፍ 18፡6፣ 1ሳሙ 25፡18፤ 1ነገ 18፡32፤ 2ነገ 7፡1፣ 16፣ 18
    5. ኦሜር ምሳሌ ዘጸ 16፡16፣ 22፣ 36፣፤ ዘለ 23፡1-15
    6. ያኢሳሮን (የኢፋፍ አንድ አስረኛ) ምሳሌ ዘጸ 19፡40፤ ዘለ 12፡21፤ ዘኑ 15፡4፤ 28፡5፣ 13
    7. ቋቢ ምሳሌ 2 ነገ 6፡25
  ለ. የፈሳሽ መለኪያ
    1. ኮር ምሳሌ ሕዝ 45፡14 (ለደረቅ ነገርም መለኪያ ሊሆን ይችላል 2 ዜና 2፡10፤ 27፡5)
    2. ባዝ ምሳሌ 1ነገ 7ለ26፣ 38፤ 2 ኤና 2፡10፤ 4፡5፤ ኢሳ 5፡10፤ ሕዝ 45፡10-11፣ 14
    3. ሁን ምሳሌ ዘጸ 29፡40፤ ዘለ 19፡36፤ ሕዝ 45፡24
    4. ሎግ ምሳ ዘለ 14፡10፣ 12፣ 15፣ 21፣ 24
  ሐ. ሰንጠረዥ (ከሮላንድ ዲ.ቫውክስ Ancient Israel, ቁጥር 1፣ ገጽ 201 እና Encyclopedia Judaica, ቁጥር 16፤ገጽ 379 የተወሰደ)።

| | | |
|---|---|---|
| ሆመር (ደረቅ) ቦር (ፈሳሽ ወይም ደረቅ) | 1 | |
| ኤፓህ (ደረቅ) ባዝ (ራሳሽ) | 10 | 1 |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሴ'አ (ደረቅ) | | 30 | 3 | 1 | | | | |
| ሂን (ፈሳሽ) | | 60 | 6 | 2 | 1 | | | |
| ኦሜር /ኢሳሮን (ደረቅ) | 100 | 10 | - | - | 1 | | | |
| ካብ/ካብ (ደረቅ | 180 | 18 | 6 | 3 | - | 1 | | |
| ሎግ (ፈሳሽ) | | 720 | 72 | 24 | 12 | - | 4 | 1 |

II. የክብደት ስያሜዎች ብዙውን ጊዜ የተጠቀሱት

*ሀ. ከሁሉም ተለመዱት ሦስቱ መመዘኛዎች ታለንት፣ ሰቅል እና ጌራህ ናቸው፡፡*

1. በብሉይ ኪዳን ትልቁ ክብደት ታለንት ነው፡፡ ከዘፍ 38:25-26 እንደምንረዳው አንድ ታለንት 3,000 ሰቅል ይመዝናል (ማለትም "አጠቃላይ ክብደት" BDB 503)::
2. ሰቅል የሚለው ስያሜ (BDB 1053፤ "ክብደት") የተጠቀሰው በግምት እንጂ በጥቅሉ አልተጠቀሰም /አልተገለፀም ሰቅልን በሚመለከት በብሉይ ኪዳን ውስጥ በርካታ መመዘኛዎች አሉ፡፡
   ሀ. "የገበያ ዋጋ" (ኤን-ኤ-ኤስ-ቢ፡-ዘፍ 23-16)
   ለ. "የመስዊያው ስቅል (ኤን-ኤ-ኤስ-ቢ፡- ዘፍ 30:13)
   ሐ. "በንጉሱ ክብደት" (ኤን-ኤ-ኤስ-ቢ፡- 2ሳሙ 14-26) እንዲሁም ደግሞ በኤሌፋንታይን ፓፒረስ "ንጉሳዊ ክብደት" ይባል ነበር፡፡
3. ጌራህ (BDB 176 II ) በ20 ስቅል ይመዘናል (ዘፍ 30:13፤ ዘሌ 27:25 ዘሕ 3:47፤ 18:16፤ ሕዝ 45:12)፡፡ እነዚህ ድርሻዎች ከሚስፓታሚያ እስከ ግብፅ ድረስ የተለያዩ ናቸው፡፡ እስራኤል ተከተለችው በከነዓን ከሁሉም የተለመደውን መሥራርት ነው (የከነዓን ምንጭ)፣
4. ሚና (BDB 548) በ50 ወይም በ60 ሰቅሎች ይመዘናል፡፡ ህ ስያሜ በብዛት የሚገኘው በኃለኛቹ ብሉይ ኪዳን መፃህፍት ውስጥ ነው (ሕዝ 45:12፤እዝራ 2:69፤ ነህ 7:70-71)፡፡ ሕዝቅኤል 60 ለ 1 በሆነ ድርሻ ሲጠቅስ ከነፃን ደግሞ 50 ለ1 በሆነ ድርሻ ይገልፀዋል፡፡
5. ቤካ (BDB132) ፤ "የሰቅል ግማሽ" ዘፍ 24:22ን ያስ.) በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሁለት ጊዜ ብቻ ስጠቀሰ (ዘፍ 24:22፤ ሀፍ 38:26) የሚመዘነውም በሰቅል ግማሽ ነበር፡፡ የስሙ ትርጉምም ማካፈል ማለት ነው፡፡

*ለ. ቻርት*

1. *በፔንታቱክ መሠረት*

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| *ታለንት* | 1 | | | |
| *ሚና* | 60 | 1 | | |
| *ሰቅል* | 3,000 | 50 | 1 | |
| ቤካ | 6,000 | 100 | 2 | 1 |
| *ጌራህ* | 60,000 | 1,000 | 20 | 10 |

2. በሕዝቅኤል *መሠረት*

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| *ታለንት* | 1 | | | | |
| *ሚና* | 60 | 1 | | | |
| ሰቅል | 3,600 | 60 | 1 | | |
| ቤካ | 7,200 | 120 | 2 | 1 | |
| *ጌራህ* | 72,000 | 1,200 | 20 | 10 | 1 |

2፡8
NASB፣ "አሰዳር"
NKJV፣ "የድግሱ አሳላፊ"
NRSV "አለቃ"
TEV "ለድግሱ አለቃ"
NJB "ለድግሱ ፕረዘዳንት"

*ይህ ሰው (1) የድግስ ፕሮግራሙን የሚቆጣጠር የተከበረ እንግዳ ወይም (2) እንግዶቹን በማስተናገድ ላይ ያለ አገልጋይ ሊሆን ይችላል፡፡*

2፡10 ዋናው ነጥብ ጥሩው ወይን የሚሰጠው በመጀመሪያ ነው፡፡ እንግዶቹ መስከር ከመ,ጀመሩ በኋላ ጥሩ ያልሆነው ወይን ይሰጣል፡፡ በዚህ ስፍራ ላይ ግን የተሻለው ወይን የቀረበው በመጨረሻ ላይ ነው፡፡ ይህም ምናባትም በኢየሱስ አማካኝነት የአሮጌው ቃል ኪዳን (ያረጀው ወይን) እና አዲሱ ቃል ኪዳን (አዲሱ የወይን ጠጅ) የተነጻጸሩበት ሁኔታ ሊሆን ይችላል፡፡ የኢየሱስ ቤተ መቅደሱን የማንጻት (በ2፡13-15 የተገለጸው በዮሐንስ የጊዜ ቅደም ተከተሉን ባልጠበቀ መልኩ የተቀመጠበት ምክንያት ምንአልባትም ስነ መለኮታዊ አላማ ልኖረው ይችላል) ይህንን እውነትም ለማሳየት ይሆናል፡፡

2፡10 "የእርሱ ምልክት መጀመሪያ" የዮሐንስ ወንጌል የተገነባው በሰባት ምልክቶች እና ትርጓሜአቸው ዙሪያ ነው፡፡ ይህም የመጀመሪያው ነው፡፡ ልዩ ርዕስ 1፡1 አርኬ የሚለውን ተመልከቱ፡፡

▣ **"ክብሩንም ገለጠ: ደቀ መዛሙርቱም በእርሱ አመኑ"** የተአምራቶቹ ዋና አላማ የኢየሱስን ክብር መግለጽ ነው፡፡ እንደ ሌሎቹ ተአምራቶች ሁሉ ይህም ተአምራት ዒላማ ያደረገው ደቀ መዛሙርቱን ነው፡፡ ይህ የእነርሱን የእምነት መጀመሪያ ተግባርን የሚያመለክት አይደለም ነገር ግን የእርሱን ማንነት እና ሥራ ላይ ያላቸው ሂደታዊ መረዳት እንጂ፡፡ ምልክቶቹ ስለ መስሑ ማንነት እና ስራ የሚገልጡ ናው፡፡ እንግዶቹ ምን እንደተፈጠረ ማወቅ አለማወቃቸውን በግልጽ ማወቅ አይቻልም፡፡

**የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 2:12**
**[12]ከዚህ በኋላ ከእናቱና ከወንድሞቹ ከደቀ መዛሙርቱም ጋር ወደ ቅፍርናሆም ወረደ: በዚያም ጥቂት ቀን ኖሩ፡፡**

2:12 **"ቅፍርናም"** የናዝሬት ሰዎችን ያለማመን ተከትሎ (ሉቃ 4:16-39) ይህ ኢየሱስ የአገልግሎት ማዕከል የነበረው ገሊላ ነው (ማቴ 4:13፤ ማር 1:21፤ 2:1፣ሉቃ 4:23፣ 31፤ ዮሐ 2:12፤ 4:46-47)፡፡

▣ በቃና ዘገሊላ በተደረገው ተአምራት መነጽር ኢየሱስ ከቤተሰቦቻ ጋር የነበረው አገለግሎት ነጸብራቅ ነው፡፡

**በ2:13-25 አውዳዊ አብርሆት**

*ሀ.* በአዲስ ኪዳን ስነ መለኮት አዋቂዎች ዘንድ ኢየሱስ ምን ያህል ጊዜ ቤተ መቅደሱን አጽድቷል ለምለው ጥያቄ ብዙ ውይይት አለ፡፡ ዮሐንስ ይህ ቤተ መቅደሱን የማጽዳት ሂደት በኢየሱስ አገልግሎት መጀመሪያ አከባቢ እንደተፈጸመ የሚገልጽ ሲሆን ነገር ግን በተመሳሳይ ወንጌላት ውስጥ ግን (ማቴ 21:12፤ ማር 11:15 እና ሉቃ 19:45) በኢየሱስ የአገልግሎት የመጨረሻ ጊዜያት አከባቢ እንደተደረገ ይላልጻሉ፡፡ በእነዚህ ዘገባዎች ልዩነት መሰረት አንድ ሳይሆን ሁለት የቤተ መቅደስ ማጽዳት ክንዋኔ እንደተደረገ ማሰብ ይቻላል፡፡

ነገር ግን ዮሐንስ የኢየሱስን ድርጊት ለስነ መለኮታዊ አላማ አቀናጅቶት ሊሆን ይችላል (ይህም ማለት ከምዕራፍ አንድ የኢየሱስን አምላክነት በማረጋገጥ)፡፡ እያንዳንዱ ጸሓፍት በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ስር ሆነው የኢየሱስን ድርግቶች እና ትምህርቶች ለመምረጥ፣ ተስማሚ እንዲሆኑ ለማድረግ፣ ለማስተካከል እና አሳጥሮ ለማቅረብ መብቱ አላቸው፡፡ ነገሮችን በኢየሱስ አፍ ውስጥ በማስቀመጥ እነርሱ መናገር የሚፈልጉት ነገር በእርሱ በኩል መናገር እንደሚችሉ ግን አላምንም፡፡ ማስታወስ የሚገባ ነገር ወንጌላት በዘመናዘን እንዳሉት የሕይወት ታርኮች አይደሉም ነገር ግን ለወንጌል ስርጭት የሚያገለግሉ እና ለተወሰነ ተደራሲያን የተጻፉ ናቸው፡፡ ወንጌላት የጊዜ ቅደም ተከተልን ጠብቀው የተጻፉ አይደሉም ወይም ኢየሱስን ቃል ቃል በቃል የጻፉልን አይደሉም፡፡ ነገር ግን እነዚህን ነገሮች እርግጠኝነታቸውን አያስወግዱብንም፡፡ የምስራቂያዊያን ስነ ጽሑፋዊ ዘይቤ ከምዕራባዊያን ስነ ጽሑፋዊ ዘይቤ ይለያል፡፡ ስለዚህ ጉዳይ "መጽሐፍ ቅዱስን ለሁለተናዊ ክብር ማንበብ" የሚለውን የጎርደን ፌ መጽሐፍን ያንብቡ፡፡

*ለ.* የኢየሱስ የቤተ መቅደሱን የማጸት ተግባር ከዮሐንስ ስነ መለኮታዊ ዓላማ ጋር የሚስማማ እና ኢየሱስ የመጀመሪያው ተግባር ከአይሁድ ሕዝብ ጋር መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህ በምዕራፍ 3 ላይ ከንቆዶሞስ ጋር ባደረገው ውይይት ውስጥ በግልጽ ይታያል፡፡ ነገር ግን በምዕራፍ 4 ላይ ከዚህ ሰፋ ካለ ቡድን ጋር ስነጋገር እንመለከታለን፤ ይህንንም የጀመረው ከሰማሪያዊቷ ሴት ጋር በመወያየት ነው፡፡

**የቃላት እና የሀረጎች ጥናት**

**የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 2:13-22**
**የአይሁድ ፋሲካም ቀርቦ ነበር: ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ፡፡ በመቅደስም በሬዎችንና በጎችን ርግቦችንም የሚሸጡትን ገንዘብ ለዋጮችንም ተቀምጠው አገኘ፤ የገመድም ጅራፍ አበጅቶ ሁሉን በጎችንም በሬዎችንም ከመቅደስ አወጣቸው: የለዋጮችንም ገንዘብ አፈሰሰ ገበታዎቻቸውንም ገለበጠ: ርግብ ሻጪዎችንም፡፡ ይህን ከዚህ ውሰዱ፤ የአባቴን ቤት የንግድ ቤት አታድርጉት አላቸው፡፡ ደቀ መዛሙርቱም፡፡ የቤትህ ቅናት ይበላኛል ተብሎ እንደ ተጻፈ አሰቡ፡፡ ስለዚህ አይሁድ መልሰው፡፡ ይህን ስለምታደርግ ምን ምልክት ታሳየናለህ? አሉት፡፡ ኢየሱስም መልሶ፦ ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት: በሦስት ቀንም አነሣዋለሁ አላቸው፡፡ ስለዚህ አይሁድ፡፡ ይህ ቤተ መቅደስ ከአርባ ስድስት ዓመት ጀምሮ ይሠራ ነበር: አንተስ በሦስት ቀን ታነሣዋለህን? አሉት፡፡ እርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ቤተ መቅደስ ይል ነበር፡፡ ስለዚህ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ይህን እንደ ተናገረ አሰቡና መጽሐፍንና ኢየሱስ የተናገረውን ቃል አመኑ፡፡**

2:13 **"ፋሲካ"** ይህ አመታዊ ክብረ በዓል በዘጸ 12 እና ዘዳ 16:1-6 ለይ ተገልጸዋል፡፡ ይህ በዓል የኢየሱስን የአገልግሎት ዘመን ለማወቅ የሚያስችለን ብቸኛ መረጃ ነው፡፡ ተመሳሳይ ወንጌላት የኢየሱስ አገልግሎት ለአንድ አመት ብቻ እንደሆነ ያመለክታሉ (ምክንያቱም አንድ የፋሲካ በዓን ብቻ ነው የሚጠቅሱት)፡፡ የዮሐንስ ወንጌል ግን ሦስት የፋሲካ በአላትን ያነሳል (1) 2:13፣ 23 (2) 6:4 እና (3) 11:55፤ 12:1፤ 13:2፤ 18:28፣ 39፤ 19:14፡፡ እንዲሁም አራተኛ በዓል ልኖርም ይችላል 5፥1፡፡ የኢየሱስ የአደባባይ አገልግሎቱ ምን ያህል እንደቆየ ማወቅ አይቻልም ነገር ግን የዮሐንስ ወንጌል ቢያንስ ሶስት አመት እንደሆነ ይገምታል እንዲሁም አራት ወይም አምስትም ሊሆን ይችላል፡፡

ዮሐንስ ወንጌሉን ያዋቀረው በአይሁዳዊያን በዓል ዙሪያ ነው (ፋሲካ፣ የድንኳን በዓል እና ሃኑካሃ) ሪቻርድ ኤን- ሎጀንከር፤ *Biblical Exegesis in the Aposticlic Period፣* ሁለተኛ እትም፤ ገጽ 135-139.

**ልዩ ርዕስ፡ ፋሲካ**

I. *መክፍቻ ቃል*
   *ሀ.* በግብታያን ላይ የወረደው መለኮታዊ ቅጣ እና የእስራኤላዊያን ነጻ መውጣት የያሕዌን ፍቅር እና የእስራኤልን እንደ ሕዝብ መቆም ሕያው ምስክሮች ናቸው፡፡
   ለ. ዘጸአት ያሕዌ ለአብረሃም በዘፍ 15፡12-21 የገባው የተስፋ ቃል ፍጻሜ ነው፡፡ የፋሲካ በዓም ይህንን ማስታወሻ ነው፡፡
   ሐ. ይህ ያሕዌ በግብጻዊያን ላይ ከላከባቸው ዐስርት መቅሰፍቶች መካከል አሳማኝ እና አስቸጋርው ነው፡፡

II. *የቃሉ ፍች*
   *ሀ.* የስሙ ፍች በእርግጠኝነት አይታወቁም
      1. ከመቅሰፍት ጋር ተያይዞ ይህ ቃል *"መምታ"* የሚል ትርጉም ይሪዋል (ዘጸ 11፡1)፤ የያሕዌ መለአክ የእንስሳቱን እና የሰዎች የመጀመሪያ ልጅ መታ
   ለ. የግሱ ትርጉም
      1. *"ማለፍ"* (2 ሳሙ 4፡4) በዚህ መልኩ ቃሉ የተጠቀሙበት "ምልክት የተደረገባቸው ቤቶች ማለፍ" (ዘጸ 12፡13፣ 23፣ 27)
      2. *"መደነስ"* (2 ነገ 18፡21)
      3. አካዲያ - *"መዝለል"*
      4. ግብጽ- *"መምተት"*
      5. ትይዩ በኢሳ 31፡5 *"መጠበቅ"*
      6. በዕብራይስጡ ፓሻኅ እና በግሪኩ ፓሽኮ መካከል ያለው የቃላት ጫወታ *"መከራን መቀበል"*
   ሐ. ከዚህ ቀደም የሆነው ታሪካዊ ክንውን
      1. እረኞች አዲስ ዓመትን አስመልክቶ መስዋዕትን ያቀርባሉ
      2. ድንኳኖቻቸውን ከቦታ ቦታ ሲያዘዋውሩ እረኞች የሚያቀርቡት መስዋእት
      3. ስለ ክፋት ዘላኖች የሚያቀርቡት መስዋእት
   *መ.* የቃሉ ትርጉም ማወቅ አስቸጋር ነው ነገር ግን በሌሎች የጥንት ባህሎች ውስጥ የፋሲካ በዓል መኖሩ የቃሉን ምንጭ ማወቅ አስቸጋር ያደረገዋል
      1. የጸደይ ቀን
      2. በስም መልክ ያለው የቃሉ ሥረወ ግንድ አለመታወቅ
      3. ከማታ እይታ ጋር መያያዙ
      4. ደም መጠቀሙ
      5. መላእክት/ ዳቢሎስን የሚያመለክት ሚሳሌን መጠቀሙ
      6. ልዩ ምግብ
      7. የግብርና ውጤቶች (ያልቦካ ዳቦ)
      8. ካህናት ለመኖራቸው፣ አከባቢ ተኮር

III. በዓሉ
   *ሀ.* ይህ በዓል በዘጸ 11-12 ላይ ተገጻዋል
   ለ. ስለ አመታዊ በአሉ በዘጸ 12 ላይ ተብራርቷል እንዲሁም ስምነት ቀን ከሚፈጀው የቅጣ በዓል ጋር ተዋህዶ ቀርቧል፡፡
      1. በመጀመሪያ የአንድ አከባቢ በዓል ነበር ዘጸ 12፡21-23፤ ዘዳ 16፡5 (ዘኍ 9)
         *ሀ.* ካህነት ዪሉም
         ለ. ልዩ መሰዊያ ዩለም
         ሐ. ደም ልዩ በሆኑ አገልግሎት ላይ ይውል ነበር
      2. በዋናው የአምል ሥፍራ ላይ መከናወን ጀመረ
      3. ይህ የአከባቢው መስዋእቶች ቅልቅል (ይህ ማለት የሞት መላእክትን ለማስታውስ የሚፈሰው የበጠቦት ደም) እና በማእከላዊ የሚደረገው የመከር በዓላ የሚደረገው በወሪሃ አቢቢ ወይም ኒሳን 14 እና 15-21 ነው
   ሐ. የሰዎች እና የእንስሳት የመጀመሪያ ልጅ እና የእነርሱ ድነት ምልክታዊ ጠቀሜታው በዘጸ ላይ ተገልጸዋል፡፡

IV. የዚህ ነገር አከባበር ታካዊ ገጽታው
   *ሀ.* የመጀመሪያው የፋሲካ በአል የተከበረው በግብጽ ምድር ነው ዘጸ 12
   ለ. በሜሬብ ተራራ/ ሲና ዘኍ 9
   ሐ. የመጀመሪያ ፋሲካ በከነዓን(ገሊላ) ውስጥ ነው የተከበረው ኢያ 5፡10-12
   *መ.* የሰለሞን ቤተ መቅደስ በተገለጸበት ጊዜ 1 ነገ 9፡25 እና 1 ዜና 8፡12 ላይ (በግምት እንጂ በእርግጠኝነት አልተገለጸም)

መ. በሕዝቂያስ ንጉሥ በነበረበት ጊዜ 2 ዜና 30 ላይ
ሠ. ኢዮስያስ ተሃድሶ ጊዜ 2 ነገ 23:21-23፤ 2 ዜና 35:1-18
ረ. 2 ነገ 23:22 እና 2ዜና 35:18 እስራኤል ይህንን አመታዊ ክብረ በዓል ማክበር መተዋን በመውቀስ ተጽፎ እናገኛለን።

V. ጠቀሜታው

ሀ. ይህ ከሦስቱ ልከበሩ የሚገባቸው በዓላት መካከል አንዱ ነው (ዘጸ 23:14-17፤ 34:22-24፤ ዘዳ 16:16)
1. የፋሲካ/የቂጣ በዓል
2. የሳምንት በዓል
3. የቡዝ በዓል

ለ. ሙሴ በዘዳግም መጽሐፍት ውስጥ ይህ በዓል በማእከላዊ የአምልኮ ስፍራ እንደሚከበር አመላክቷል።

ሐ. ኢየሱስ የአመታዊው የፋሲካ በዓል የሚዘጋጀው ምግብ በሚበላበት ዕለት (ወይም ከዚያ አንድ ቀን አስቀድሞ) ይህንን በዓል የአዲስ ኪዳን ወይን እና ዳቦ ምሳሌ በማድረግ ተጠቅሞበታል ነገር ግን ጥቦቱን ግን አልተጠቀመብም።
1. የጋራ መአድ
2. የድነት መስዋእት
3. ለቀጣዩ ትውልድ ያለው ቀጣይ ጠቀሜታ

▣ **"ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ"** አይሁዳዊያን ስለ እየሩሳሌም ሲያወሩ ከመልካምድራዊ አቀማመጧ ይልቅ ከሥነ መለኮታዊ ጠቀሜታው አንጻር ያወራሉ።

2:14 **"በመቅደስም"** የታላቁ ሄሮዶስ ቤተ መቅደስ በሰባት ትልልቅ ክፍሎች ተከፈለ ነበር። ውጨኛው ክፍል የአሕዛብ ክፍል ሲባል፤ በዚህም ስፍራ ላይ ነጋዴዎች መስዋእት ማቅረብ እና መባ መስጠት ለሚፈልጉ ሰዎች አስፈላጊውን ነገር ለማቅረብ ሱቃቸውን አኑረዋል።

▣ **"ሬዎችንና በጎችን ርግቦችንም"** ረጅም ጉዞ ተጉዘው የመጡ ሰዎች ተቀባይነት ያለው መስዋእትን ለማቅረብ መግዛት ይጠበቅባቸው ነበር። ነገር ግን የካህናቱ ቤተሰቦች እነዚህን ሱቆች ተቆጣጥረዋቸው ነበር፤ ለእንስሳቱም ከፍተኛ ገንዘብ ያስከፍሉ ነበር። ሰዎች የራሳቸውን እንስሳት ይዘው ቢመጡ ካህናቱ እነዚህ ለመስዋእት መቅረብ የማይችሉ ናቸው ይሏቸው ነበር። ስለዚህም ከእነዚህ ሰዎች እንስሳቱን መግዛት ነበረባቸው።

▣ **"ንዘብ ለዋጮችን"** እነዚህ ሰዎች ያስፈለጉበት ምክንያትን ለማስረዳት በሁለት መንገድ ይቻላል (1) ቤተ መቅደሱ የሚቀበለው ብቸኛው የገንዘብ አይነት ሼክል ይባላል። የአይሁዳዊያን ሼክል የገንዘብነት አገልግሎቱን መስጠቱን ካቆመ ረጅም ጊዜ ስለ ሆነው ነው። (2) የሮም ነገሥታት ምስል ያለው ማንኛው ገንዘብ ተቀባይነት ዬለውም።

2:15 **"የገመድም ጅራፍ አበጅቶ . . . ከመቅደስ አወጣቸው"** በዚህ ክፍል ውስጥ የኢየሱስን ንዴት በግልጽ መመልከት ይቻላል። የያሕዌ መታወቂያ ስፍራ የነበረው በተ መቅደስ የአምልኮ እና የእግዚአብሔር መገለጥ ያለበት ስፍራ መሆኑን አቁሞል። ንዴት በራሱ ኃጢአት አይደለም! በኤፌ 4:26 ያለው የጳውሎስ ንግግር ከዚህ ጋር ልያያዝ ይችላል። እኛል ልያናድደን የሚችል አንድ ነገር ልኖር ይችላል።

2:16 **"ይህን ከዚህ ውሰዱ"** ይህ በግሪኩ ቋንቋ ትዕዛዝ አዛል ድርጊት ገላጭ ግሥ መሆኑን ለማሳየት ትኩረት የተደረገበት ን፤ "እነዚህን ነገሮች ከዚህ አስወጡ"

▣ **"የአባቴን ቤት የንግድ ቤት አታድርጉት አላቸው"** ይህ የአሁን ጊዜ ትዕዛዝ ሲሆን ማስቆም እና ድርጊቱ በሂደት ላይ መሆኑን ያመለክታል። ሌሎች ወንጌላት (ማቴ 21:13፣ ማር 11:17፣ ሉቃ 19:46) ከኢሳ 56:7 እና ኤር 7:11 ላይ በመውሰድ ጽፈዋል። ነገር ግን በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የብሉይ ኪዳን ትንቢት አልተገለጸም። ይህ ምናባት በዘካ 14:2 ላይ ካለው ስለ መሲሕ ከተነገረው ትንቢት ላይ የተወሰደ ሊሆን ይችላል።

2:17 **"ደቀ መዛሙርቱም። . . . አሰቡ"** ይህ ክፍል እንደሚያመለክተው በኢየሱስ አገልግሎት እይታ እና በመንፈስ ቅዱስ እርዳታም ቢሆን የኢየሱስን ድርጊት መንፈሳዊ እውነት የተረዱት በኋላ ላይ እንደሆነ እንመለከታለንለለ (ቁ 22፤ 12:16፤ 14:26)

▣ **"እንደ ተጻፈ"** ይህ የብሉይ ኪዳ በእግዚአብሔር እስትንፋስ መጻፍ ጽኑ ማረጋገጫ ነው (6:31፣ 45፤ 10:34፤ 12:14፤ 20:30)። ይህ ከሰባ ልቃናት መዝ 69:9 የተወሰደ ነው። ይህ መዝሙር እንደ መዝ 22 ሁሉ የኢየሱስ ስቅለት ጋር ተስማሚ ነው። ኢየሱስ ለእግዚአብሔር እና ለእርሱ እውነተኛ አምልኮ የነበረው ቅንአት ወደ ሞት መርቶታል፤ ይህም የእግዚአብሔረ ፍቃድ ነው። (ኢሳ 53:4፤ ሉቃ 22:22፤ ሐዋ 2:23፤ 3:18፤4:28)

2:18

NASB፣ *"ይህን ለማድርግ ስልጣን እንዳለህ በምን ምልክት ልታሳየን ትችላለህ"*

NKJV፣ *"እነዚህን ነገሮች በማድረግህ ምን ምልክት ልታሳየን ትችላለህ"*

NRSV *"ይህንን ለማድረግህ ምን ምልክት ልታሳየን ትችላለጅ"*

TEV *"ይህንን ለማድረግ መብት ለማሳየት እንዳለህ ምን አይነት ተአምራት ልታርግ ትችላለህ"*

NJB *"እንድህ ለማድረግህ ምን ምልክት ልታሳየን ትችላለህ"*

ይህ አይሁዳዊያን ስለ ኢየሱስ ያላቸው ጥያቄ ማዕከል ነው። ፈርሳዊያን የእርሱ ስልጣን ምንጭ ዲቢሎስን ነው ይላሉ (8፡ 48-49፣ 52፤ 10:20)። መስሐ የተወሰኑ ነገሮችን በተወሰነ መንገድ እንደሚያደረግ ያምናሉ። ይህን ሳያደርግ ስቀር ስለ እርሱ ግራ መጋባቶች ተፈጠሩ። (ማር 11:28፤ ሉቃ 20:2)።

2:19 **"ህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት: በሦስት ቀንም አነሣዋለሁ አላቸው"** "ሂሮን" በቁ 14 እና 15 ላይ ያለው የግሪክ ቃል የሚያመለክተው የቤተ መቅደሱን አከባቢ ነው። ነገር ግን በቁ 19፣ 20፣ 21 ላይ የሙገኘው "ናኦስ" የሚለው ቃል የቤተ መቅደሱን ውስጠኛ ክፍል ያመለክታል። ስለዚህ ቃል ትርጓሜ ብዙ ውይይቶች ተደርገዋል። በእርግጥ በማቴ 26:10 ፣ በማር 14:57-19፣ በሐዋ 6:14 ላይ ይህ የሚያመለክተው ስለ ኢየሱስ ስቅለት እና ትንሳኤ ነው። ነገር ግን በዚህ አውድ ውስጥ ግን ቤተ መቅደሱ እራሱ በ70 ዓም እንደሚፈርስ ያመለክታል። (ማቴ 24:1-2)። እነዚህ ሁለት አረፍተ ነገሮች ኢየሱስ አዲስ የአምልኮ ስርአትን እንደሚመሰርት እና ይህም ከአይሀደሁዳዊያን ጋር እንደማይመሳሰል ይልጻል (4:21-24)። እንደገና ዮሐንስም በሁለት መንገድ ተጠቅሞታል።

2:20 **"ይህ ቤተ መቅደስ ከአርባ ስድስት ዓመት ጀምሮ ይሠራ ነበር"** የታላቁ ሄሮድ ቤተ መቅደሱን ማስፋፋት እና እንደገና ማነጽ አይሁዳዊያንን ለማስደሰት የታለመ ነው። ጆሴፈስ እንደሚማገረው ይህ ቤተ መቅደስ መገንባት የጀመረው በ20 ወይም በ19 ዓዓ ነው። ይህ እውነት ከሆነ ይህ ተግባር የተፈጸመው በ27-28 ዓም ነው ማለት ነው። ይህ የቤተ መቅደስ ግንባታ ሥራ እስከ 64 ዓም መቀጠሉን እናውቃለን። ይህ የአይሁዳዊያን ትልቅ ተስፋ ሆኖ ነበር (ኤር 7)። አዲሱ ቤተ መቅደስ በሆነው በኢየሱስ ተተክቷል። በ1:14 ላይ ድንኳኑን እንደተካ ተመልክተናል አሁን ደግሞ ቤተ መቀደሱን። ከናዝሬት ከመጣው አናጺ የተሰጠው ምሳሌ ምንኛ አስደንግጭ ነው። እግዚአብሔር እና የሰው ልጆች በኢየሱስ ውስጥ መገናኘት ችለዋል እንዲሁም በእርሱ ውስጥ ሰዎችም እግዚአብሔርን ማምለክ ችለዋል።

2:21 **"እርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ቤተ መቅደስ ይል ነበር"** ኢየሱስ ይህንን ስናገር ሳለ ደቀ መዛሙርቱ አልተረዱትም ነበር (ቁ 17)። ዮሐንስ ከአመታት በኂላ እየጻፈ መሆኑን አስታውሱ

ኢየሱስ ለምን እንደመጣ ያውቃ። በትንሹ ሶስት ዓላማዎች አሉት።

1. እግዚአብሔርን ለመግለጥ
2. ትክክለኛ ሰው ምን ማለት እንደሆነ ለማሳየት
3. ለብዙዎች ሕይወቱን ቤዛ አድርጎ ለመስጠት

የመጨረሻው ዓላማ በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ተንጸባርቆ እናገኘዋን (ማር 10:45፤ ዮሐ 12:23፣ 27፤ 13:1-3፤ 17:1)።

2:22 **"ደቀ መዛሙርቱ ይህን እንደ ተናገረ አሰቡ"** ብዙ ጊዜ የኢየሱስ ቃላት ንግግሩት ከሚሰሙት ይልቅ ለደቀ መዛሙርቱ ጥቅም የታሰቡ ነበሩ። በጊዜው ሁል ጊዜ አይረዱትም ነበር።

▣ **"መጽሐፍትን አመኑ"** ምንም እንኳ ክፍሉ ዬትኞቹን መጽሐፍት እንደሆኑ ባይገልጥም ምናልባት መዝ 16:10 ኢየሱስ ስለ ትንሳኤ የጠቀሰውን ሊሆን ይችላል (ሐዋ 2ለ15-32፤ 13:33-35)። ይህ ተመሳሳይ ክፍል ቦሐ 20:9 ላይ ተጠቅሷል።

**የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 2:23-25**

[23]**በፋሲካ በዓልም በኢየሩሳሌም ሳለ: ያደረገውን ምልክት ባዩ ጊዜ ብዙ ሰዎች በስሙ አመኑ፤ነገር ግን ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ያውቅ ነበር፤ ስለ ሰውም ማንም ሊመሰክር አያስፈልገውም ነበርና አይተማመናቸውም ነበር፤ ራሱ በሰው ያለውን ያውቅ ነበርና።**

2:23 **"ብዙ ሰዎች በስሙ አመኑ"** "አመኑ" የሚለው ቃል ከግሪኩ (ፒስቶ) የመጣ ሲሆን ትርጓሜውም "ማመን"፣ "መታመን" "እምነት" ማለት ነው። ይህ ቃል በስም ይዘት በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ጥቅም ላይ ያልዋለ ሲሆን የግስ ይዘቱ ግን ብዙ ጊዜ ውሏል። በዚህ ስፍራ ላይ ሕዝበ ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን ማመናቸውን በእርግጠኝነት መናር የሚያስችል ነገር ዬለም። የዚህ ቃል ታይታዊ አጠቃቀም ምሳሌ የሚሆነን ዮሐ 8:31-59 እና ሐዋ 8:13. 18-24። እውነኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ከመጀመሪያ ማመን ይለያል። በደቀ መዝሙርነት ሂደት መታገዝ አለበት (ማቴ 13:20-22፣ 31-32)

በዚህ ስፍራ ላይ ጊዜያዊ አማኞች በኢየሱስ ተአምራት በመማረክ ወደ እርሱ መምጣታቸውን እንመለከታለን (2:11፤7:31)። አላማቸውን የኢየሱስን ማንነት እና ስራ ማረጋገጥ ነው። ነገር ግን መገንዘብ ያለብን በኢየሱስ ታአምራታዊ ስራዎች ማመናችን ብቻ በቂ አይደለም:(4:38፤ 20:29) የሚናምነው ኢየሱስን መሆን አለበት (20፣ 30-31)። ተአምራቶች ሁል ጊዜ የእግዚአብሔር ምልክቶች አይደሉም (ማቴ 24:24፤ ራዕ 13:13፤ 16:14፤ 19:20)። የኢየሱስ ሥራዎች ሁሉ ዓላማቸው ሰዎችን በእርሱ እንዲያምኑ ለማድረግ የታለሙ ናቸው (2:23፤ 6:14፤ 7:31፤ 10:42)። ብዙ

ጊዜ ሰዎች ምልክቶችን ይመለከታሉ ነገር ግን ለማመን አሻፈረኝ ስሉ መመልከት የተለመደ ነው (6፡27፤ 11፡47፤ 12፡37)፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ "አመነ" የሚለው ግሳዊ ይዘት የዮሐንስ አጠቃቀም**

ዮሐንስ በዋነኝነት "እመነትን" ከምጻረ ቃላት ጋር በማዋህድ ይጠቀማል

1. *"ኢሸ" "በ" ማለት ነው፡፡ እምነት የሚለው ቃል ከዚህ ምጻረ ቃል ጋር ስመጣ የሚያሳየው የአማኞችን በኢየሱስ ማመን ነው፡፡*
   - ሀ. በስሙ (ዮሐ 1፡12፤ 2፡23፤ 3፡18፤1ዮሐ 5፡13)
   - ለ. በእርሱ (ዮሐ 2፡11፤ 2፡15፣18፤ 4፡39፤ 6፡40፤ 7፡5፤ 31፣ 48፤ 8፡30፤ 9፡36፤10፡42፤ 11፡45፣ 48፤ 12፡37፣ 42)
   - ሐ. በእኔ (ዮሐ 6፡35፣ 7፡38፤ 11፡25፣ 26፤ 12፡44፣ 46፤ 14፡1፣ 12፤ 16፡9፤ 17፡20)
   - መ. እርሱ በላከው (ዮሐ 6፡28-29)
   - ሠ. በልጁ (ዮሐ 3፡36፤ 9፡35፤ 1ዮሐ 5፡10)
   - ረ. በኢየሱስ (ዮሐ 12፡11)
   - ሰ. በብርሃን (ዮሐ 12ለ36)
   - ሸ. በእግዚአብሔር (ዮሐ 12፡44፤ 14፡1)
2. "ኢን" ማለት "ውስጥ" ዮሐ 3፡15 (ማር 1፡15)
3. *ያለ መስተዋደድ ያለውን የመስተዋድ ተሳቢነት የሚያመለክት ነው* (ዮሐንስ 4፡50፤ ዮሐንስ 3፡23፤5፡10)፡፡
4. *ሆቲ "ዘንድ" ማለት ሲሆን ምን እንደሚናምን የሚነግር ነው፡፡ ለዚህ አንዳንድ ምሳሌወች የሚሆኑን*
   - ሀ. ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ (6፡69)
   - ለ. ኢየሱስ እኔ እኔ ነኝ መሆኑ (8፡24)
   - ሐ. ኢየሱስ በአባት ውስጥ መሆኑ አብም በእርሱ ውስት መሆኑ (10፡38)
   - መ. ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ (11፡27፤ 20፡31)
   - ሠ. ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ (11፡27፤ 20፡31
   - ረ. ኢየሱስ በአብ እንደ ተላከ (11፡42፤ 17፡8፣ 21)
   - ሰ. ኢየሱስ ከአብ ዘንድ የነበረው እንደሆነ (14፡10-11)
   - ሸ. ኢየሱስ ከአብ ዘንድ እንደመጣ (16፡27፣ 30)
   - ቀ. ኢየሱስ እራሱን በአብ የቃል ኪዳን ስም "እኔ ነኝ" በምል ጠርቷዋል፡፡ (8፡24፤ 13፡19)

*መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ሰዋዊ እና መልዕክት ነው፡፡ ይህ የሚታየው በመታዘዝ፣ በፍቅር እና ጸንቶ በመቆም ነው፡፡*

2፡24-25 ይህ በግሪኩ አንድ አረፍተ ነገር ሲሆን "መተማመን" የሚለው ቃል በዚህ ስፍራ የተገለጸው የኢየሱስን ተግባር እና አመለካከት ለመግለጽ ነው፡፡ ይህ የመጀመሪያውን ምላሽ ወይም ስሜታዊ ምለሽን አያመለክትም፡፡ ይህ አረፍተ ነገር የኢየሱስን ሰውነተን እና የሰው ልጅን ክፉ ልብ ያመለክታል (የእግዚአብሔርን እውቀት ያሳያል ዘፍ 6፡11-12፣ 13፤ መዝ 14፡1-3)፡፡ ይህ አንቀጽ በኒቆዶሚዎስ በምዕራፍ 3 ላይ ተብራርቷል፡፡ ምንም እንኳ ሃይማኖታዊ ቢሆንም የእርሱ ጥረት፣ እውቀት በእግዚአብሔር ፍት ተቀባይነት እንዲኖረው አላደረገውም፡፡ ጽድቅ የሚመጣው በኢየሱስ እምነት ብቻ ነው (ሮሜ 1፡16-17፤4)፡፡

### *መወያያ ጥያቄዎች*

ይህ ምሪትን የሚሰጥ የመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻ ነው፤ ይህም ማለት ለምትደረስበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ኃላፊነት የምትወስደው አንተ እራስ ትሆናህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን ባለን ብርሃን መጠን ልንመላለስ ይገባል ማለት ነው፡፡ በስነ አፍታት ሂደት ውስጥ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ዋነኛውን ስፍራ ትይዛላችሁ፡፡ ይህንን እድል ለመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻዎች አሳልፈህ አትስጥ፡፡

ከዚህ በታች የተጠቀሱት የመወያያ ጥያቄዎች በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ባሉት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ማሰላሰል እንድትችሉ ለማገዝ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ የሚገድቡህ ሳይሆን የማሰላሰል ምናብን እንዲያሰፉልህ የታቀዱ ናቸው፡፡

1. ኢየሱስ ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ ለምን ለወጠ፤ ይህ ምንን ያመለክታል?
2. ኢየሱስ በኖረበት ዘመን ይኖሩ የነበሩ ሰዎች የጋብቻ ሁኔታ ምን እንደሚመስል ግለጽ፡፡
3. የሄሮዶስን ቤተ መቅደስ መሰረት ፕላን መሳል ትችላለህን ሻጮቹ እና ገዥዎቹ ያሉበትን ስፍራ ማመልከት ትችላለህን?
4. ተመሳሳይ ወንጌላት የቤተ መቅደሱን በመጀመሪያ ላይ መንጻጽ ለምን አልዘገቡትም?
5. ኢየሱስ የሄሮድ ቤተ መቅደስ እንደሚፈርስ የሚያመለክት ትንቢትን ተናግሮ ነበርን?
6. "ማመን"፣ መታመን፣ እምነት ተብለው የተተረጎሙ የግሪክ ቃላትን ተርጉም አብራራ፡፡

# ዮሐንስ 3

## የዘመናችን የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀጽ ክፍፍል

| UBS[4] | NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| ኢየሱስ እና ኒቆዶሞስ | አዲስ ውልደት | ኢየሱስ እና አይሁዳዊያ | ኢየሱስ እና ኒቆዶሞስ | ከኒቆዶሚዎስ ጋር የተደረገ ውይይት |
| 3፡1-15 | 3፡1-21 | 3፡1-10 | 3፡1-2 | 3፡1-8 |
| | | | 3፡3 | |
| | | | 3፡4 | |
| | | | 3፡5-8 | |
| | | | 3፡9 | 3፡9-12 |
| | | | 3፡10-13 | |
| | | 3፡11-15 | | |
| | | | 3፡14-17 | |
| 3፡16-21 | | 3፡16 | | |
| | | 3፡17-21 | | |
| | | | 3፡18-21 | |
| ኢየሱስ እማ መጥመቁ ዮሐንስ | መጥመቁ ዮሐንስ ክርስቶስን ከፍ ከፍ ማድረጉ | የዮሐንስ ሌሎች ምስክርነቶች | ኢየሱስ እና ዮሐንስ | ዮሐንስ ለመጀመሪያ ጊዜ መስክርነት መስጠቱ |
| 3፡22-30 | 3፡22-36 | 3፡22-24 | 3፡22-24 | 3፡22-24 |
| | | 3፡25-30 | 3፡25-26 | 2፡25-26 |
| | | | 3፡27-30 | |
| ከሰማይ የሚመጣው እርሱ | | | ከሰማይ የሚመጣው እርሱ | |
| 3፡31-36 | | 3፡31-36 | 3፡31-36 | |

**ሦስተኛ ዙር ንባብ**
*በአንቀጽ ደረጃ የመጽሐፉ ጸሓፊ ሊያስተላልፍ የፈለገውን ሀሳባ መከተል*

ይህ ምሪትን የሚሰጥ የመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻ ነው፤ ይህም ማለት ለምትደረስበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ኃላፊነን የምትወስደው አንተ እራስ ትሆናህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን ባለን ብርሃን መጠን ልንመላለስ ይገባል ማለት ነው። በስነ አፍታት ሂደት ውስጥ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ዋነኛውን ስፍራ ትይዛላችሁ። ይህንን እድል ለመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻዎች አሳልፈህ አትስጥ።

*መጽሐፉን በአንድ ጊዜ ለሁለተኛ ጊዜ አንብበህ ጨርስ፡፡ ዋና ዋና ሀሳቦችን ግለጽ እንዲሁም ዋናውን ሀሳ በአንድ አረፍተ ነገር ግለጽ፡፡*

1. *የመጀመሪያውን አንቀጽ ዋና መልዕክት*
2. *የሁለተኛውን አንቀጽ ዋና መልዕክት*
3. *የሦስተኛውን አንቀጽ ዋና መልዕክት*
4. *ወዘተ*

***የቃላት እና የሀረግ ጥናት***

| |
|---|
| የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 3፡1-3<br>**ከፈሪሳውያንም ወገን የአይሁድ አለቃ የሆነ ኒቆዲሞስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ፤ እርሱም በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጥቶ። መምህር ሆይ፡ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ በቀር አንተ የምታደርጋቸውን እነዚህን ምልክቶች ሊያደርግ የሚችል የለምና መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ መጣህ እናውቃለን አለው። ኢየሱስም መልሶ፦ እውነት እውነት እልሃለሁ፡ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም አለው።** |

3፡1 *"ፈሪሳዊያን" የእነዚህ ፖለቲካዊ/ሃይማኖታዊ ፓርቲዎች አጀማመር ወደ መቃቢያን ዘመን ይሄዳል፡፡ መጠሪያቸው ትርጓሜ "የተለዩ" ሊሆን ይችላል፡፡ የእግዚአብሔር ሕግ በትውፊት ውስጥ እንደተብራራው ለመጠበቅ የተሰጡ እና ከልባቸው የሚሹ ሰዎች ናቸው፡፡ እንደ ዛሬው ሁሉ አንዳንዶቹ እውነተኛ የቃል ኪዳን ሕዝቦች ናቸው (ኒቆዶሞስ፣ የአርማታው ዮሴፍ) ነገር ግን አንዳንዶቹ ግን እራሳቸውን የሚያጸድቁ፣ ወግ አጥባቂዎች፣ ፈራጆች፣ የቃል ኪዳን ሕዝብ "የሚመስሉ" ናቸው (ኢሳ 6፡9-10፤ 29፡13)፡፡ ልባቸው ዋነኛ ነገር ነው! "የአዲስ ኪዳን" (ኤር 3131-34) በውስጥ መነሻ ላይ የሚያተኩር ሲሆን (ይህም ማለት አዲስ ልብ፣ አዲስ አእምሮ፣ በልብ የተጻፈ ሕግ)፡፡ የሰው ልጅ ጥረቶች እንደዚህ ቀደሙ ሁሉ በቂ ሆነው አልተገኙም፡፡ በዘዳ 10፡16፤ 30፡6 ውስጥ የተጠቀሰው የልብ ግርዘት መታዘዝን እና የእርካታን ሕይወት የሚያመለክት ዘይቤያዊ አነጋር ነው፡፡*

*ሃይማኖታዊ ወግ አጥባዊነት እና/ወይም ልብራልነት በጣም መጥፎ ነገር ነው፡፡ ሥነ መለኮት ከፍቅር እና ከእምነት ልጀምር ይገባዋ፡፡ ልዩ ርዕስ፡ 1፡24 ፈሪሳዊያን የሚለውን ይመልከቱ፡፡*

▣ *"ኒቆዶሞስ" በፍልስጤም ውስጥ የሚኖር አንድ አይሁዳዊ የግሪክ ስም ስኖረው የሚያስገርም ነው (ፍልጶስ እና አንድሪያስ እንዳላቸው ሁሉ ማለት ነው 1፡40፣ 43) የዚህ ሰው ስም ትርጓሜ "የሕዝቡ ገዥ" ማለት ነው፡፡ (7፡50፤ 19፡39)፡፡*

▣

| | |
|---|---|
| NASB፣ NKJV | ***"የአይሁዳዊያን ገዥ"*** |
| NRSV፣ NJB | ***"የአይሁዳዊያን መሪ"*** |
| TEV | ***"አይሁዳዊ መሪ"*** |

*በዚህ አውድ ውስጥ ለምኩራብ መሪ የምሰጥ ቴክኒካል ስም ነው፤ ይኼውም በእየሩሳሌም ካሉ የአይሁድ ሕዝብ መሪዎች፤ ከ70ዎቹ መካከል አንዱ ማለት ነው (በሌላ አውድ ውስጥ ግን የአንድ ምኩራብ መሪ ሊሆን ይችላል)፡፡ የእነዚህ ሰዎች ስልጣን በሮማዊያን በጣም ተገድቦ ነበር ነገር ግን ለአይሁድ ሕዝብ ብዙ ተምሳሌታዊ ጠቀሜታ ነበራቸው፡፡ ከዚህ በታች ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡*

*ዮሐንስ ኒቆዶሞስን በመጀመሪያው ምእተ አመት ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ትክክለኛ አይሁዳዊያንን እንዲወክል ተጠቅሞበት ሊሆን ይችላል፡፡ በመንፈሳዊ ህይዋቸው የበቁ የሚመስላቸው እንደገና እንድጀምሩ ልነገራቸው ይገባል፡፡ በኢየሱስ ከማመን ውጭ ለሕግጋት ታማኝ መሆን ወይም የዘር ሀረግ ማንንም ወደ እግዚአብሔር መንግስት አያስገባም፡፡ እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል የሰጠው ስጦታ እንጂ የሰው ልጅ ሃይማታዊነት በመለኮት ዘንድ ተቀባይነትን አያስገኝም፡፡ ኒቆዶሞስ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ መምህር እንደሆነ ተቀብሎታል፤ ይህ ምንም እንኳ ትክክል ቢሆንም በራሱ ግን በቂ አይደለም፡፡ የግል እምነት፣ ኢየሱስ መሲሕ እንደሆነ ሙሉ እምነተ ለወደቀው የሰው ልጅ ብቸኛ ተስፋ ነው (1፡12)*

| |
|---|
| ***ልዩ ርዕስ፡ የአይሁድ ሸንጎ*** |
| I. *የመረጃ ምንጮች*<br>*ሀ. የአዲስ ኪዳን እራሱ*<br>*ለ. ፍላቪዩስ ጆስፈስ* |

ሐ. የታልሙድ ሚሽን ክፍል

የሚገርም ሁኔታ አዲስ ኪዳን እና የጆሰፈስ ጽሑፎች አይመሳሰሉም፤ ይህ የሚያመለክተው በእየሩሳሌም ውስጥ ሁለት የአይሁድ ሸንጎ መኖሩ ሲሆን አንደኛው ወገን የካህናት ሲሆን (ሳዱቃዊያን በመባል ይጠራሉ) እነዚህ በልቀ ካህኑ ይመራሉ፤ እነዚህ የፍትሃ ቢሔር እና የወንጀል ጉዳዮችን ስመለከቱ ሁለተኛው ቡድን ደግሞ በፈሪሳዊያን እና ጸሓፍት የተዋቀረ ነው። እነዚህ ሃይማታዊ እና ትውፊታዊ ጉዳዮችን ይመለከታሉ። ነገር ግን በ200 ዓም የተገኘው የጸሐፍት ጽሑፎች የሚያመለክቱ ኢየሩሳሌም በ70 ዓም ከወደቀች በኂላ ያለውን ሁኔታ ነው። አይሁዳዊያን ሃይማታዊ የአኗኗር ዘይቤያቸውን እንደገና ጃማኒያ በተባለው ቦታ ላይ አቋቁሟል ከዚያም ወደ ገሊላ ተዘዋውረዋል።

II. ቃላት

ከዚህ ሸንጎ አካል ጋር ተያይዞ የሚነሳው ችግር በተለያዩ ስሞች የመጥራቱ ነው። በኢዬሩሳሌም አይሁዳዊያን ማህበረሰብ ውስጥ እንዲህ ያሉትን የፍርድ ሸንጎዎችን የሚገልጹ ብዙ ቃላት አሉ።

ሀ. ሄሮሲያ - "ሴናት" ወይም "ካውንስል"። ይህ በጣም ጥንታዊ ስያሜ ሲሆን በፐሪሽያዊያን ዘመን መጨረሻ አከባቢ የተጀመረ ነው። በሐዋ 5:21 ላይ ከአይሁድ ሸንጎ ጋር ተያይዞ ተጠቅሷል።

ለ. ሲኔደሪዮን- ይህ የሁለት ቃላት ውህደት ነው። ይህ ቃል በሚያስገርም ሁኔታ በአራማይክ ቋንቋ ውስጥ አገልግሎት ላይ የዋለ ሲሆን ነገር ግን የግሪክ ቃልን ያሳያል። የመቃቢያን ጊዜ ማብቂያ አከባቢ ይህ በእየሩሳሌም ውስጥ ባሉ አይሁዳዊያን ዘንድ ከፍተኛ ችሎቶቸችን የሚያመለክት ቃል ሆኖ ነበር። (ማቴ 26:59፣ ማር 15:1፤ ሉቃ 22:66፤ ዮሐ 11:47፤ ሐዋ 5:27)። ችግሩ የተከሰተው ይህ ቃል ከእየሩሳሌም ውጭ ላሉ የአከባቢ የፍርድ ሸንጐች መዋል ስጀምር ነው። (ማቴ 5:22፤ 10:17)

ሐ. ፐሪስፓተሮን- "የሸንጎ መሪ" (ሉቃ 22:66) ለአንድ ጎሳ መሪ ተሰጠ ስም ነው። ነገር ግን ይህ ቃል በእየሩሳሌም ውስጥ ላለ የፍርድ ሸንጎ መዋል ጀመረ (ሐዋ 22:5)

መ. ቦዩሌ- ይህ "ሰንጎ" የሚለው ቃል በጆሴፈስ የተለያዩ የፍርድ ሸንጎዎችን ለማመልት አገልግሎት ላይ ዋለ። (1) በሮም ውስጥ ያለውን ሴኔት (2) የሮምን የአከባቢ ሸንጎ (3) በኢየሰሩሳሌም ያለው የአይሁዳዊያን ትልቁ ሸንጎ እና (4) የአይሁዳዊያን የአከባቢ ሸንጎ። የአርማቲያው ጆሴፍ በእነዚህ አይነቱ ሸንጎ አባል እንደሆነ ተገልጸዋል (ማር 15:43፤ ሉቃ 23:50)።

III. ታሪካዊ እድገቱ

በመጀመሪያ ታላቁን ምኩራብ የጀመረው ዕዝራ እንደሆነ ይታመናል፤ ይኼውም በድህረ ገዞት ዘመን ሲሆን ኢየሱስ በነበረበት ዘመን የነበረው ሸንጎም ተመሳሳይ ነው። (በሰለሞን መዝሙር 6:1 ታርጉም ላይ)

ሀ. ምሽና (ታልሙድ) በእየሩሳሌም ውስጥ ሁለት ሸንጎ እንደነበር ዘግቧል (ሳንሃ 7:1)

1. አንደኛው ሰባ (ወይም ሰባ አንድ) አባላት ያሉት ሲሆን (ሳንደ 1፡ 6 ላይ ሙሴ በዘኑ 11 ላይ የመጀመሪያውን ሸንጎ እንዳቋቋመ ይናገራል ይህንን ከዘኑ 11:16-25 በመመልከት ያነጻጽሩ)።
2. ሌላኛው 23 አባላት ያሉት ሲሆን (ይህ ምናልባትም የአከባቢ ሸንጎን ልያመለክት ይችላል)
3. አንዳንድ የአይሁዳዊያን ምሁራን በእየሩሳሌም የነበሩት ሸንጎዎች አባላት ቁጥር 23 ሆነው ብዛታቸው ሦስት እንደሆነ ይናገራሉ። እነዚህ ሦስቱ በሁለት መሪዎች አከማካኝነት ሲገናኙ 71 አባላት ያሉትን "ትልቁን ሸንጎ" ይፈጥራሉ።
   ሀ. አንዱ የካህናት (ሳዱቃዊያን)
   ለ. አንዱ ሕጋዊ (ፈሪሳዊያን)
   ሐ. አሪስቶክራትክ (ሽማግሌዎች)

ለ. በድህረ ግዞት በኂላ የተመለሰው የዳዊት ዘር ዘሩባቤል ነበር እንዲሁም የተመለሰው የአሮን ዘር ኢያሱ ነበር። ዘሩባቤል ከሞተ በኂላ የዳዊ ዘር አልቀጠለም፤ ስለዚህም የፍርድ ሕደቱ ለካህና ብቻ ተሰጠ (1መቃ 12:6) እና የአከባቢ ሽመግሌዎች (ጆህ 2:16፤ 5:7)

ሐ. ይህ የካህናት በሄሌንስቲክ ጊዜ ይሠሩት የነበረው የመፍርድ ሥራ በዲኦዶሮስ 40:3-፤ 4-5 ተመዝግቦ ይገኛል።

መ. የእነዚህ ካህናት የአስተዳደራዊ ኃላፊነት ሴሉሲድ እስከተባለው ጊዜ ቀጥሏል። ጆሰፈስ "ታላቁ" አንቲክኦስ ሦስተኛን (223-197 ዓዓ) እማኝ በማድርግ ጽፏል።

ሠ. በሮማዊያን ጊዜ የሶሪያ ገዥዎች አምስት ክልላዊ "ሸንጎዎችን" አቋቁመው ነበር።

ረ. ብዙዎቹ የሸንጎ አባላት ከሄሮዶስ ጋር ግጭት ውስጥ የነበሩ ሲሆን በ37 ዓም በተነሳው አመጽም ብዛቹ የሸንጎ ከፍተኛ የአመራሪ አባላት ተገድለዋል።

ሰ. በሮሜያዊያን በተሾመ መሪ አማካይነት (6-66 ዓም) ጆሴፈስ እንዘገበው እንደገና ጥሩ ስልጣን እና ተጽዕኖ ማምጣት ወደሚችሉበት ደርሰዋል። (ማር 14:55) በአዲስ ኪዳን ውስጥ እነዚህ የፍረርድ ሸንጎ አባላት የፍርድ ሂደት የሚያከናውኑበት ሦስት ሁኔታዎች ተጠቅሰወዋል።

1. በኢየሱስ ላይ የቀረበ ክስ (ማር 14:53-15:1፤ ዮሐ 18:12-23፣ 28-32)
2. የጴጥሮስ እና የዮሐንስ ጉዳይ (ሐዋ 4:3-6)
3. የጳውሎስ ጉዳይ (ሐዋ 22:25-30)

ሸ. አይሁዳዊያን በ66 ዓም ባመጹ ጊዜ ሮማያን በዚያን ወቅት የአይሁድን ሕዝብ እና እየሩሳሌምን በ70 ዓም ፈጽመው አጥፍተዋል። ምንም እንኳ በጀማኒያ ያሉ ፈሪሳዊያን የፍርድ ሂደቱን በእነርሱ ሥር ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ቢያደርጉም የአይሁዳዊያን ሸንጎ የምባሉ ግን ከዚያን ጊዜ አንስቶ ጠፍቷል።

IV. አባልነት

ሀ. በእየሩሳሌም ስለ ነበረው ከፍተኛ ሸንጎ ለመከመሪያ ጊዜ የተጠቀሰው በ2 ዜና 19:8-11 ላይ ነው። ይህም ሸንጎ (1) ከሌዊያዊያ (2) ከካህናት እና (3) የቤተሰብ መሪዎች (ሽማግሌዎች ይህን 1 መቃቢ. 14:20፤ 2 መቃቢ. 4:44 ጋር አነጻጽር) የተዋቀረ ነው።

ለ. በመቃቢያዊያ ጊዜ ይህ በአብላጫው ተይዞ የነበረው (1) በሳዱቃዊያን የካህናት አባላት እና (2) በአከባቢ መሪዎች ነበር (ከ1 መቃቢ. 7:33፤ 11:23፤ 14:28 ጋር ያነጻጽ)። በእነዚህ ጊለኞቹ ዘመናት "ጸሓፊት" (የሙሴ ሕግ አዋቂዎች፣ ብዙ ፈሪሳዊያን ናቸው) ተጨመሩበት፤ ይህም የተደረገው በአሌክሳንደር ጃናዩስ ምስት በሳሎሜ አማካኝነት ነው (76-67 ዓዓ)። ከዚህ በተጨማር ፈሪሳዊያን የዚህ ፍርድ ሸንጎ ከፍተኛውን ቁጥር መያዝ ይገባታል ትል ነበር።

ሐ. ኢየሱስ በኖረበት ዘመን ይህ የፍርድ ሸንጎ የተዋቀረው

1. በልቀ ካህኑ ቤተሰቦች
2. በአካባቢው በሚኖሩ ሃብታሞች
3. ጸሓፊት (11:27፤ ሉቃ 19:47 ያነጻጽሩ)

V. ማጣቀሻ መጽሐፍት

ሀ. DictioNary of Jesus aNd the Gospel, IVP pp 728-732

ለ. The ZoNdervaN Pictorial Encyclopidia of the Bible Vol 5 pp 268-273

ሐ. The New Schaff- Herzog Encyclopidia of Religious Knowledge vol 10 pp 203-204

መ. The INterpreter's DictioNary of the Bible vol 4 pp 214-218

ሠ. Encyclopedia Judica vol 14 pp 836-839

3:2 **"በሌሊት"** መምህራን ሕግጋትን ለማጥናት ሌለት እጅግ በጣም ተስማሚ የሆነ ጊዜ እንደሆነ ይናገራሉ ምክንያቱም የሚያቋርጣቸው ነገር ባለመኖሩ ነው። ኒቆዶሞስ ከኢየሱስ ጋር መታየት አልፈለገም ይሆናል (ከእርሱ ጋርም ሌሎችም ልኖሩ ይችላሉ) ስለዚህም በሌሊት መጥቶ ሊሆን ይችላል።

አንድ ሰው በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ሁለት ትርጓሜ ልኖር እንደሚችል እንዴት ልያስብ ይችላል። ዮሐንስ የሚታወቀው በጨለማ እና በብርሃም መካከል በሚሰራው ንጽጽር ነው።

▣ **"መምህር"** በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ያለው ትርጓሜ "አስተማር" ማለት ነው (1:38፤ 4:31፤ ማር 9:5፤ 11:21)። አይሁዳዊያን መሪዎችን በጣም ያስቸገራቸው ነገር ኢየሱስ በዬትኛውም የአይሁድት የስነ መለኮት ትምህርት ቤት ውስጥ ገብቶ አለመማሩ ነው። በናዝሬት ከተማው ውስጥ ከሚገኝ ምኩራብም የታልሙድ ትምህርትም አልተከታተለም።

▣ **"ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ መጣህ"** ይህ ሀረግ በዓረፍተ ነገሩ መጀመሪያ ላይ የመጣበት ምክንያ ለአጽኖት ነው። ይህ ምናልባትም በዘዳ 18:15፣ 18 ላይ የተጠቀሰውን ትንቢት ወስዶ ሊሆን ይችላል። ኒቆዲሞስ የኢየሱስነ ቃል እና ሥራ እውቅና ሰጥቶታል ነገር ግን ይህ ማለት እርሱ ከእግዚብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት አለው ማለት ግን አይደለም።

▣ **"እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ በቀር"** ይህ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ሲሆን ሊሆን የሚችል እውነተን ሚያሣይ ነው።

3:3፣ 5፤11 **"እውነት እውነት"** ይህ ቀጥተኛ ትርጓሜው "አሜን አሜን" ማለት ነው። ይህ የተወሰደው ከቢሉይ ኪዳን "እምነት" ከሚለው ቃል ነው። የቃሉም ሥረወ ግንድ "ጸንቶ መቆም" ማለትነው። ይህን ቃል ኢየሱስ የሚጠቀምበት በጣም ጠቃሚ የሆነ ዐረፍተ ነገርን አስቀድሞ ነው። በዓረፍተ ነገር መጀመሪያ ላይ ተመሳሳይ ቃላትን ሁለት ጊዜ መጠቀም በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ብቻ የሚናገኘው ነገር ነው። "አሜን" የሚለው ቃል ሁለት ጊዜ ተደጋግሞ በኢየሱስ እ በኒቆዲሞስ ውይይት ውስጥ እናገኘዋለንለ። በ1:51 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ አሜን የሚለው ይመልከቱ።

3:3 **"ከሆነ በቀር"** ይህ በ3:2 ላይ ኒቆዲሞስ እንደተናገረው ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ነው።

▣

NASB፣ ›NKJV

| | |
|---|---|
| TEV | **"ከላይ መወለድ"** |
| NRSV፣ NJB | **"ዳግም መወለድ"** |

የዚህ ቃል ትርጓሜ

1. "በአካል እንደገና መወለድ"
2. "ከመጀመሪያው መወለድ" (ሐዋ 26:4)
3. "ከላይ መወለድ" ይህ ከዚህ አውድ ጋር ተስማሚ ነው (3:7፣7፣ 31፤ 19:11 ጋር ያነጻጽሩ)

ይህ ምናልባት ዮሐንስ የሁለትዮሽ የቃላት ትርጉም አጠቃቀም ምሳሌ ሊሆን ይችላል፤ እንዲሁም ሁለቱም ልክ ልሆኑ ይችላሉ።

▣ **“ሊያይ አይችልም”** ይህ ዘይቤአዊ ንግግር ከቁ. 5 “መግባት አይችልም” ጋር ትይዩ ነው፡፡

▣ **“የእግዚአብሔር መንግስት”** ይህ ሀረግ በዮሐንስ ወንጌል ውስት ሁለት ጊዜ ብቻ አገልግሎት ላይ የዋለ ነው (ቁ 5)፡፡ ይህ በተመሳሳይ ወንጌላት ውስጥ እጅግ በጣም ወሳኝ ቃል ነው፡፡ የኢየሱስ የመጀመሪያው እና የመጨረሳ ስብከቱ እንዲሁም አብዛኛዎቹ ምሳሌዎቹ ስለዚህ ጉዳይ ያወሳሉ፡፡ ይህ ሀረግ የሚያመለክተው በሰው ልጆች ውስጥ እግዚአብሔር አሁን መንገሡን ነው፡፡ ዮሐንስ ይህንን ሀረግ ሁለት ጊዜ ብቻ መጠቀሙ የሚያስገርም ነው (ያውም በምሳሌዎቹ ውስጥ አይደለም)፡፡ ከዚህ በታ ያለውን ልዩ ርዕስ ተልከት፡፡ ለዮሐንስ “ዘላለማዊ ሕይወት” የሚለው ቃል እጅግ ወሳኝ ቃል ነው፡፡

ይህ ሀረግ ከኢየሱስ ስለ መጨረሻው ዘመን አስተምህሮ አቋም ጋር ከፍተኛ ተዛምዶ አለው፡፡ ይህ “የሆነ” ነገር ግን “ሙሉ በሙሉ ያልተፈጸመ” የሚለው እርስ በእርሱ የሚጋጭ የሚመስል ሀሳብ ከአይሁዳዊያን የሁለት ዘመን ጽንሰ ሀሳ ጋር ተዛማጅነት አለው፡፡ እነዚህም ዘመናት ክፉው ዘመን እና የጽድቅ ዘመን የሚባለው ነው፡፡ ይህ የጽድቅ ዘመን በመስሑ መምጣት የሚጀመር ይሆና፡፡ አይሁዳዊያን በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ አንድ ወታደራዊ መሪ እንደሚመጣ ይጠብቃሉ (በብሉይ ኪዳን ውስጥ እንዳሉት መሳፍንት ማለት ነው)፡፡ የኢየሱስ ሁለትዮሽ አመጣጥ ሁለቱ ዘመናት አንዱ በአንዱ ላይ እንድደረብ አድርጎታል፡፡ በቤተልሔም በተከሰተው ትስብእት (ትስጉት) ምክንያት የእግዚአብሔር መንግስት ወደ ሰው ልጆች ታርክ ሰብሮ ለመግባት ችሏል፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ በራዕ 19 ውስጥ እንደተገለጸው ወታደራዊ መሪ ሆኖ እስካሁን አልመጣም ነገር ግን እንደ መከራን እንደሚቀበል አገልጋይ ሆኖ እንጂ (ኢሳ 53) እንዲሁም እንደ ትሁት መሪ ሆኖ መጥቷል (ዘካ 9፡9)፡፡ ስለዚህም መንግስቱ መጥታለች (ማቴ 3፡2፤ 4፡17፤ 10፡7፤ 11፡12፤ 12፡28፤ ማር 1፡15፤ ሉቃ 9፡9፣ 11፤ 11፡20፤ 21፡ 31-32) ነገር ግብ አልተፈጸመችም (ማቴ 6፡10፤ 16፡28፤ 26፡24)፡፡

አማኞች በእነዚህ ሁለት ዘመናት መካከል ባለ ውጥረት ውስጥ ነው የሚኖሩት፡፡ የትንሳዔ ሕይወት አላቸው ነገር ግን በአካላቸው ይሞታሉ፡፡ ከኃጢአት ኃይል ነጻ ወጥተዋል ነገር ግን ኃጢአትን ያደርጋሉ፡፡ በተፈጸመ ነገር ግን ሙሉ በሙሉ ባልተጠናቀቀ የመጨረሻው ጊዜ ውጥረት ውስጥ ይኖራሉ፡፡

በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ያለውን የተከሰተ ነገር ግን ገና ሚከሰት የሚለውን ሐሳብ ለማስረዳት ጠቃሚ የሆነ ገለፃ በፍራንክ ስታግ New Test a ment Theology በሚለው መጽሐፍ ውስጥ ይገኛል

“የዮሐንስ መንገድ ወደፊት ስለሚመጣው በአፅንኦት ከመናገሩም ባሻገር (14፡3፤18፡28፤16፡16፤22) “በመጨረሻው ቀን” ስለሚሆነው ትንሣኤና ፍርድ በግልፅ ይናገራል (5፡28ንይመ፤6፡9ንይመ፤44፤54፤11፡24፤12፡48)፤ነገር ግን በዚህ አራተኛ ወንጌል ውስጥ ሁሉ የዘላለም ህይት እና ትንሳኤ የአሁን ጊዜ እውነተዎች ናቸው (3፡18ንይመ፤4፡23፤5፡25፤6፡54፤11፡23ንይመ፤12፡28፡31፤13፡31ንይመ፤14፡17፤17፡26)” (ገጽ 311)፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ የእግዚአብሔር መንግስት**

በብሉይ ኪዳናት ውስጥ ያሕዌ የእስራኤል ንጉሥ እንደሆነ ይታሰብ ነበር (1 ሳሙ 8፡7፤መዝ 10፡16፤ 24፡7-9፤ 29፡10፤ 44፡4፤ 89፡18፤ 95፡3፤ ኢሳ 43፡15፤ 44፡4፣ 6) እንዲሁም መስሑም ንጉሣቸው እንደሆነ ያምናሉ (መዝ 2፡6፤ ኢሳ 9፡6-7፤ 11፡1-5)፡፡ ኢየሱስ በቤተልሔም ውስጥ በመወለዱ ምክንያት የእግዚአብሔር መንግስት ወደ ሰው ልጆች ታርክ በአዲስ ኃይል እና ድነት ሰብራ ገብታለች (አዲሰ ቃል ኪዳን ኤር 31፡31-34፤ ሕዝ 36፡27-36)፡፡ መጥመቁ ዮሐንስ የዚህን መንግስት መምጫ መቃረብ ያውጅ ነበር (ማቴ 3፡2፤ ማር 1፡15)፡፡ ኢየሱስም በእርሱ እና በትምህርቱ የእግዚአብሔር መንግስት መምጣቷን ያውጅ ነበር (ማቴ 4፡17፣ 23፤ 9፡35፤ 10፡7፤ 11፡11-12፤ 12፡28፤ 16፡19፤ ማር 12፡34፤ ሉቃ 10፡9፣ 11፤ 11፡20፤ 12፡31-32፤ 16፡16፤ 17፡21)፡፡ ነገር ግን የእግዚአብሔር መንግስት እንዲሁም ወደ ፊትም የሚትመጣ ጭምር ናት (ማቴ 16፡28፤ 24፡14፤ 26፡29፤ ማር 9፡1፤ ሉቃ 21፡31፤ 22፡16፣ 18)፡፡

በተመሳሳይ ወንጌላት ውስጥ በማርቆስ እና በሉቃስ ውስጥ “የእግዚአብሔር መንግስት” የሚሉ ሀረጎችን እንመለከታለን፡፡ ይህ በኢየሱስ ትምህርት ውስጥ የተለመደው ርዕሰ ጉዳይ እግዚአብሔር አሁን በሰዎች ልብ ውስጥ መንገሱን ነገር ግን ከእለታት አንድ ቀን በምድር ሁሉ ውስጥ እንደሚነግስ ያመለክታል፡፡ ይህ በኢየሱስ ጸሎት ውስጥ የተንተባረቀ (በማቴ 6፡10) ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ ለአይሁዳዊያን የተጻፈ በመሆኑ ምክንያት የእግዚአብሔር መንግስት ከሚለው ሀረግ ይልቅ መንግስተ ሰማያት የሚለውን ሀረግ ተጠቅሟል፡፡

ይህ በተመሳሳይ ወንጌላት ውስጥ እጅግ በጣም ወሳኝ የሆነ ርዕሰ ጉዳይ ነው፡፡ የኢየሱስ የመጀመሪያ እና የመጨረሻ ስብከቱ እንዲሁም አብዛኛዎቹ ምሳሌዎቹ ይህንን ርዕሰ ጉዳይ የሚመለከቱ ነበሩ፡፡ ይህ አሁን እግዚአብሔር በሰዎች ልብ ውስጥ መንገሡን የሚያመለክት ነው፡፡ ዮሐንስ ይህንን ሀረግ ሁለት ጊዜ ብቻ መጠቀሙ እጅግ በጣም የሚያስገርም ነው (አንድም ጊዜ በኢየሱስ ዘይቤአዊ ነግግሮች ውስት አልተጠቀመበትም)፡፡ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ “ዘላለማዊ ሕይወት” የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ቁልፍ ሀሳብ ነው፡፡

ከዚህ ሀረግ ጋር ተያይዞ ያለው ውጥረት የኢየሱስ ሁለት ጊዜ መምጣት ነው፡፡ ብሉይ ኪዳን የመሲሁን አንድ ጊዜ ብቻ መምጣት አጽኖት የሚሰጠው ሲሆን ይኼውም ወታደራዊ፣ ፈራጅ፣ በታላቅ ክብር ስለሚመጣው መሲሕ የሚያወሳ ነው፤ ነገር ግን አዲስ ኪዳን በኢሳ 53 ውስጥ እንደ ተጠቀሰው አይነት መከራን የሚቀበል አገልጋይ እና እንደ ዘካ 9፡9 ትሁት ንጉሥ ሆኖ መምጣቱን ያሳየናል፡፡ የአይሁዳዊያን የሁለት ዘመናት ጽንሰ ሀሳብ፤ የክፉ እና የጽድቅ ዘመናት ተደራርበው መጥተዋል፡፡ ኢየሱስ በአሁን ወቅት በአማኞች ልብ ውስጥ ነግሦ እናገኘዋለን ነገር ግን አንድ ቀን በፍጥረታት ሁሉ ላይ ይነግሳል፡፡ በብሉይ ኪዳን ውስጥ በተነገረለት መልኩ ይመጣል፡፡ አማኞች የሆነ ነገር ግን ፈጽሞ ባልተጠናቀቀ የእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ ይኖራሉ፡፡

**የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ: 3:4-8**
***ኒቆዲሞስም:: ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን? አለው:: ኢየሱስም መለሰ: እንዲህ ሲል፦ እውነት እውነት እልሃለሁ: ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም:: ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው: ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው:: ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል ስላልሁህ አታድንቅ:: ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል: ድምፁንም ትሰማለህ: ነገር ግን ከወዴት እንደ መጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም፤ ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲሁ ነው::***

**3:5 "ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር"** ይህ ምልባት በእነዚህ መካከል እያነጻጸረ ይሆናል፡፡
1. በቁሳዊ እና በመንፈሳዊ
2. ምድራዊ እና ሰማያዊ

ይህ ንጽጽር በቁ 6 ላይም ተንጸባርቋል
በዚህ ስፍራ ላይ ውሃ የተባለው ነገር ምን እንደሆነ የተሰጡት መላ ምቶች
1. የአይሁድ መምህራን የወንድ የዘር ፍሬ ነው ይላሉ
2. ልጅ ስወለድ ያለው ውሃ ነው
3. የመጥመቁ ዮሐንስ የንሰሓ ጥምቀት (1:26፣ 3:23 ጋር ያነጻጽሩ)
4. የብሉይ ኪዳን የኋላ ዳራ ሲኖረው በመንፈስ የመረጨትን ስርአትን ያመለክታል (ሕዝ 36:25-27)
5. የክርስቲያኖችን ጥምቀት (ምንም እንኳ ነቆዲሞስ እንደዛ ባይረዳው ጀስቲን እና ኤራኔዎስ የተባሉ የቤተ ክርስቲያን አባቶች እንደዛ ብለው ትርጉመውታል)፡፡

▣ **"የእግዚአብሔር መንግስት"** በጥንት የግሪክ ቅጂዎች እንዲሁም በጥንት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ጽሑፎች ውስጥ "መንግስተ ሰማያት" ተብሎ ተቀምጧል፡፡ ይህ በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ የተለመደ ቃል ነው፡፡ ነገር ግን "የእግዚአብሔር መንግስት" የሚለው ቃል በቁ 3 (3 እና 5 ላይ የሚገኝ ነው)፡፡ ዮሐንስ እንደ ማርቆስ እና ሉቃስ ሁሉ ለአሕዛቦች የጻፈ ስለሆነ አይሁዳዊያን የአምላክ ስምን አይጠቀምም፡፡

**3:6** ይህ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የተለመደው (ቁ.11 ንይመ) ከላይ ወደታች የሆነ ዱዋሊዝም ነው፡፡

**3:7 "አንተ...አንተ"** የመጀመሪያው በነጠላ ቁጥር የተገለጠ እና ኒቆዲሞስን የሚያመለክት ሲሆን ሁለተኛው ግን የብዙ ቁጥር ሆኖ አጠቃላይ መርሕን የሚያመለክት እና በሰው ሁሉ ላይ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ነው (በቁ11 ላይ በነጠላ እና ብዙ ቁጥር ላይ እንደሆነው የቃላት መራቀቅ ማለት ነው)፡፡
አንድ ሰው ይህንን አባባል አይሁድ በዘር ሐረጋቸው ላይ ከላቸው ትምክህት አንፃር ለመተርጎም ሊፈተን ይችላል (4:12፤8:53 ንይመ) ዮሐንስ በመጀመሪያው ክፍለዘመን መጨረሻ አካባቢ እንይመፃሩ የኖስቲሰዊያንን የኑፋቄ አስተምህር እንዲሁም የአይሁድን ዘር ትምክህት ለመቃወም መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

▣ "አለብህ" ***ዴይ*** የሚለው የግሪኩ ግሥ (ቃል በቃል "ወሳኝ" ማለት ነው፤ (BAGB 172)፤ ድርጊት ገላጭ አመልካች ግሥ) በምዕራፍ 3 ውስጥ ሦስት ጊዜያት ተጠቅሷል (ቁ. 7፣14፤30)፡፡ ግሡ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር እቅድ ወደፊት እንዲንቀሳቀስ (እንዲቀጥል) መከሰት ስላለባቸው ነገሮች ነው (4:24፤9:4፤10:16፤12:34፤20:9)፡፡

**3:8** በእብራይስጡ (እና በአራማይኩ) ቃል (ሩሐክ) እና በግሪኩ ቃል (ኒውማ) ላይ የቃላት ቃላት መራቀቅ አለ፤ ይህም ማለት "ነፋስ" "እስትንፋስ" እና "መንፈስ" የሚል ነው፡፡ ዋናው ነጥብ ልክ እንደመንፈስ ሁሉ ነፋስም ነፃነት አለው አንድ ሰው ነፋስን አያይም፤ ይልቁንም ክስተቱን እንጂ መንፈስም ደግሞ እንዲሁ ነው፡፡ የለውም ድነት በራሱ ቁጥጥር ያለ ሳይሆን በመንፈስ ቁጥጥር ውስጥ ያለ ነው (ሕዝቅኤል 37 ንይመ)፡፡ እንዲሁም ደግሞ ቁ.5-7 ይህን ተመሳሳይ እውነት እንደሚያንፀባርቅ ማየት ይችላል፡፡ ደነት የመንፈስ ቀስቃሽነት (6:44፤65 ን ይመ) እና የግለሰቡ እምነት/ ንስሐ ምንሽ ጥምረት ነውና (1:12፤3:16፤18)፡፡
የዮሐንስ ወንጌል በተለየ ሁኔታ በመንፈስ ማንነት እና ሥራው ላይ የሚያተኩር ነው (14:17፤25-26፤16:7-15)፡፡ ዮሐንስ አዲሱን የድድቅ ዘመን የሚመለከተው እንደ እግዚአብሔር መንፈስ ዘመን ነውና፡፡
ቁጥር 8 አፅንኦት የሚሰጠው አንዳንዶች ወንጌልን ሲሰሙ/ሲያዩ ለምን እንደሚያምኑና ሌሎች ደግሞ ለምን እንደማያምኑ ባለው ሚስጢራዊ ጉዳይ ላይ ነው፡፡ ዮሐንስ አስረግጦ የሚናገረው በመንፈስ ካልተነካ በቀር (1:13፤6:44፤65) ማንም ሊያምን እንደማይችል ነው፡፡ ይህም ጥቅስ ያንን ሥነ-መለኮት የሚያጠናክር ነው፡፡ ይሁን እንጂ የቃል ኪዳን ምላሹ (የሰው መለኮታዊ ቸርነትን መቀበል) አሁንም ቢሆን የሚያመለክተው መንፈስ የትኛውንም ሰው እንደሚነካ ነው፡፡ አንዳንዶቹ ለማመን ለምን በእምቢተኝነታቸው እንደሚፀኑ  እንቆቅልሽ/ ነው (የሰው ውድቀት ያመጣው እኔነት ነው)፡፡ እድሜዬ እየጨመረ በሔደ ቁጥር፣ መጽሐፍ ቅዱሴን የበለጠ ባጠናሁ ቁጥር የእግዚአብሔርን ሕዝብ የበለጠ ባገለገልኩ ቁጥር በሕይወት ውስጥ ያለውን "እንቆቅልሽ" የበለጠ እየፃፍኩ እሔዳለሁ ሁላችንም አሁን የምንኖረው እጅግ ጭጋጋማ

በሆነው (1ቆሮ 13:12) የሰው ልጅ አመፅ ውስጥ ነው! በሌላ አባባል ሐሳቡን ለማስቀመጥ ምርጫን የተከተለ ሥነ መለኮትን ማስኬድ እግዚአብሔርን በክርስቶስ የማመንን ያህል አስፈላጊ አይደለም ኢዮብ "ለምን" እንደሆነ አልተነገረውምና!

**ልዩ ርዕስ፡ እስትንፋስ፣ ንፋስ፣ መንፈስ**

*የዕብራይስጥ ቃል የሆነው ሩሃ እና የግሪክ ቃል የሆነው ኑማ "መንፈስ"፣ "እስትንፋስ" ወይም "ንፋስ" ተብሎ ልተረጎም ይችላል። (ዮሐ 3፡5፣ 8) መንፈስ ብዙ ጊዜ ከስነ ፍጥረት ጋር ተያይዞ እናገኘዋን (ዘፍ 1፡2፤ እዮ 26፡13፤ መዝ 104፡29-30፤ 147፡14-18)። ብሉይ ኪዳን በእግዚአብሔር እና በመንፈስ መካከል ስለላለው ግንኙነት በግልጽ አይገልጽልንም። በእዮ 28፡26-28፤ መዝ 104፡24 እና ምሳ 3፡19፤ 8፡22-23 ላይ እግዚአብሔር ፍጥረታትን ለመፍጠር ጥበብን መጠቀሙን እናያለን። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ኢየሱስ የእግዚአብሔር የፍጥረት ሰራተኛ እንደሆነ ይናገራል (ዮሐ 1፡1-3፤ 1ቆሮ 8፡6፤ ቆላ 1፡15-17፤ ዕብ 1፡2-3)። እንድ ድነት ሁሉ በስነ ፍጥረት ውስጥም የሥላሴ ሦስቱ አካላት ተሳትፈዋል።*

የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 3፡9-15
***ኒቆዲሞስ መልሶ፦ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? አለው።ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፦ አንተ የእስራኤል መምህር ስትሆን ይህን አታውቅምን? እውነት እውነት እልሃለሁ: የምናውቀውን እንናገራለን ያየነውንም እንመሰክራለን: ምስክራችንንም አትቀበሉትም። ስለ ምድራዊ ነገር በነገርኋችሁ ጊዜ ካላመናችሁ: ስለ ሰማያዊ ነገር ብነግራችሁ እንዴት ታምናላችሁ? ከሰማይም ከወረደ በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም: እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው። ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ይገባዋል።***

3፡9-10 *ኒቆዲሞስ የኢሱስን ምሳሌያዊ አነጋገር* (1) *በአይሁዳዊያን ዘንድ ባለው የፖሮስተላይት ጥምቀት* (2) *የዮሐንስ የንሰሐ ጥምቀት አማካኝት ተገንዝቦታል።*

*ይህ ሆን ተብሎ የሰው ልጆች እውቀት ከንቱነት ለማሳየት የተደረገ ነው፤ የአይሁዳዊያን መሪ የሆነው ኒቆዲሞስ እንኳ ይህንን መንፈሳዊ እውቀት ልያውቅ አልቻለም። የዮሐንስ ወንጌል አንዱ የተጻፈበት አላማ የድነት መንገድ እውቀት እንደሆነ የሚያስተምሩ ኖስቲክ የሚባሉ የንፋቄ ትምህርትን ለመቃወም ነው። ኢየሱስ ለጥቅት ቡድኖች ብቻ ሳይሆን ለሁል እውነተኛ ብርሃን ነው* (ቁ 9)

3፡11 *"የምናውቀውን እንናገራለን" ይህ ብዙ ቁጥር የሚያመለክተው ኢየሱስ እና ደቀ መዛሙርቱን ነው* (ቁ 11) *ወይም ኢየሱስን እና አባቱን፤ ይህም በቁ* 12 *ካለው አውድ ጋር ይስማማል። ወንጌል ተራ የሰዎች ግምት ሳይሆን መለኮታዊ መገለጥ ነው።*

▣ ***"ምስክራችንንም አትቀበሉትም"** ዮሐንስ ብዙ ጊዜ መቀበል የሚለውን ቃል ይጠቀማል፤ ይህም*

1. *ኢየሱስን መቀበል*
   *ሀ. በአሉታዊ መልኩ* (1፡11፤ 3፡22፤ 5፡47)
   *ለ. አዎንታዊ መልኩ* (1፡12፤ 3፡11፣ 33፡ 5፡43፤ 113፡20)
2. *መንፈስን መቀበል*
   *ሀ. በአሉታዊ መልኩ* (14፡17)
   *ለ. አዎንታዊ መልኩ* (7፡39)
3. *ብዙ ጊዜ የኢየሱስን ቃል መቀበል*
   *ሀ. በአሉታዊ መልኩ* (12፡48)
   *ለ. አዎንታዊ መልኩ* (17፡8)

*በ1፡8 ላይ ለኢየሱስ መመስከር የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።*

3፡12 *"ብ…ብ" የመጀመሪያው አንደኛ መደብ ሁኔታዊ አረፍተ ነገር ሲሆን ይህም ከፀሐፊው እይታ አንፃር እውነት ተይርጎ የተወሰደ ወይም ለሥነ-ፅሑፊዊ ዓላማው ሲባል የተደረገ ነው። ሁለተኛው ግን ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ አረፍተ ነገር የሆነና ድርጊት ለመፊፀም እድል መኖሩን ያመለክታል።*

▣ *"አንተ" ተወላጠ ስ እና ግሦቹ ብዙ ቁጥር ናቸው። ኒቆዲሞስ ኢየሱስ ሲመጣ የራሱ ደቀመዛመርት ወይም ፈሪሳዊያን አብረውት ሳይኖሩ አልቀረም ወይም ደግሞ ንግግሩ በአጠቃላይ (ኒቆዲሞስ አብረውት የመጡትን ወክሎ እንደሚናገር) በቁጥር* 7 *እና* 11 *ላይ እንዳለው የማያምኑትን አይሁድ ሊያመለክት ይችላል።*

3:13 ይህ የኢየሱስን አብን መግለጥ እውነተኛ፣ ሙሉ፣ ብቸኛ እንደሆነ ለማሳየት ነው (1:1-14 ጋር ያነጻጽሩት)፡፡ ይህ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ያለ ወደ ላይ ተደረገ የሁለትዮሽ ሀሳብ ነው፤ ሳማይ እና መሬት፣ ቁሳዊ እና መንፈሳዊ፣ የኒቅዲሞስ ምንጭ እና ኢየሱስ ምንጭ (1:51፤ 6:33፣ 38፣ 41፣ 50፣ 51፣ 58፣ 62)፡፡ ይህ ቁጥር (1) አምላክነቱን (2) አስቀድሞ መኖሩን እና (3) የሥላሴ ሁለተኛ አካል የሆነው ወልድ ትስብእት መሆኑን ያረጋግጣል (14:26 ላይ ያለውን አሃዱ ሥሉስ አምላክ ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡)

▣ **"የሰው ልጅ"** ይህ ኢየሱስ እራሱን ይጠራበት የነበረ ስም ነው፡፡ በመጀመሪያው ዘመን አይሁዳዊነት ውስጥ ይህ ምንም አይነት ሀገራዊ፣ ወታደራዊ፣ መስሐዊ ትርጉም አልነበረውም፡፡ ይህ ቃል የመጣው ከሕዝ 2:1 ና መዝ 8:4 ሲሆን በእነዚህ ክፍሎች ውስጥም "የሰው ልጅ" የሚል ትርጓሜ አለው ነገር ግን በዳን 7:13 ግን መለኮትን ያመለክታል፡፡ ይህ ቃል የኢሱስን ፍጹም አምላክነት እና ሰውነት ያሳያል (1ዮሐ 4:1-3)

3:14-21 በኒቆዲሞስ እና በኢየሱስ መካከል የነበረው ውይይት ዬቱ ጋር እንደተቋጨ መለየት አስቸጋር ነው፡፡ እንዲሁም አስተያየቱን የተሰጠው ሐዋርያው ዮሐንስ ይሁን ኢየሱስ ዮቱ ጋር እንደሚጀምር መለየት ያስቸግራል፡፡ ተመሳሳይ ወንጌላት የኢየሱስ የአደባባይ አገልግሎት ስዘግቡ ዮሐንስ ግን ከኢየሱስ ጋር የነበረው የግል ጊዜ ጽፎ ሊሆን ይችላል፡፡ ቁጥር 14-21 ያውን ክፍል እንዲህ ልገለጽ ይችላል

1. 14-15 ከኢሱስ ጋር ተያኘነት ያለው
2. 16-17 ከአብ ጋር ተያያኘነት ያለው
3. 18-21 ከሰው ልጆች ጋር ተያያኘነት ያለው

የተናገረው ኢየሱስ ይሁን ዮሐንስ የንግግሩን እውነት ሊቀይረው እንደማይችል ያለተውሉ፡፡

**3:14 "ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ"** ይህ ክፍል የሚያመለክተው ዘኍ 21:4-9 ውስጥ በበረሃ ውስጥ የተከሰተውን ነገር ነው፡፡ ማእከላዊው እውነት የሰው ልጆች ምንም እንኳ ሙሉ በሙሉ ሁኔታው ባይረዱት እግዚአብሔርን ማመን እና ቃሉን መታዘዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከእባብ ንድፋቱ ለመዳን አስራኤላዊያ ያላቸው ብቸኛ አማራጭ መማመን ብቻ ነው፡፡ ይህ እምት ደግሞ የሚቻለው ለቃሉ/ለተስፋ ቃሉ በመታዘዝ ነው፡፡ (ዘኍ 21፤8)፡፡

▣ **"ማንሳት/መስቀል"** ይህ የግሪክ ቃል (8:28፤ 12፤32፣ 34) ላይ "ማንሳት" ብሎ ተተርጉሟል (ሐዋ 2:33፤ 5:31፤ ፊል 2:9) እግዚአብሔር በእባብ የተነደፉ ሰዎች ፈውስ የሚሂንላቸው በእግዚአብሔር ቃል ሲያምኑ እና የተሰቀለውን የእባ ምስልም መመለክት ስችሉ ነው፡፡

**3:15-18 "ማመን"** ማመን ቀጣይነት ያለው እምነት ነው፡ለ በ1:12 ላይ ያለውን ማብራሪያ እና በ1:7 እና 2:23 ላይ ያለው ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

▣ **"በእርሱ"** ይህ ስለ ኢየሱስ ስነ መለኮታዊ እውነታዎችን የሚያመለክት ብቻ ሳይሆን ከእርሱ ጋር የግል ግንኙነትንም ያሳያል፡፡ ድነት (1) የሚታን መልዕክት (2) ልቀበሉት እና ልታዘዙት የሚገባ ሰው እና (3) እንደ እርሱ መኖርን ይጠይቃል፡፡

በዚህ ሥፍራ ያለው ስዋሰዋዊው ሥርዓት ያልተለመደ ነው፡፡ በዚህ ሥፍራ ብቻ ከመስተዋድዱ (en) ጋር ተጣምሮ የሚገኘው ተውላጠ ስሙ ነው፤ በተለምዶ ግን መስተዋድዱ eis ነው፡፡ "የዘላለም ሕይወት ይኖረው ዘንድ" ከሚለው ጋር ሊጣመር ይገባዋል ማለትም ይችላል (The New Testament in Basic English:- ሐሮን ግሪንሊ የፃፈውን ያለተውሉ)፡፡

**3:15፣16 "ዘላለማዊ ሕይወት"** የግሪክ ቃል ሆነው ዞኤ የሚለው ቃል ይዘት እና ጥራትን ያመለክታል፡፡ (5:24)፡፡ በማቴ 25:26 ላይ ለዘላለማዊ መለየት ተመሳሳይ ቃልን ተጠቅሞ እናገኛን፡፡ በዮሐንስ ውስጥ ዞኤ የሚለው ቃል (በምዕራፍ 5 እና 6 ላይ 33 ጊዜ ያህል ጥቅም ላይ ውሏል)፡፡

የዮሐንስ ወንጌል "በዘላለማዊ ሕይወት" ላይ በማተኮሩ ይታወቃል፡፡ የዚህ ወንጌል ዋና መልዕክት እና ግብ ነው (3:15፤ 4:36፤5:39፤ 6:54፤ 10:28፤ 12:25፤ 17:2፤3)፡፡

**የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 3:16-21**
**በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና። ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ: በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና። በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል። ብርሃንም ወደ ዓለም ስለ መጣ ሰዎችም ሥራቸው ክፉ ነበርና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ስለ ወደዱ ፍርዱ ይህ ነው። ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላልና: ሥራውም እንዳይገለጥ ወደ ብርሃን አይመጣም፤ እውነትን የሚያደርግ ግን ሥራው በእግዚአብሔር ተደርጎ እንደ ሆነ ይገለጥ ዘንድ ወደ ብርሃን ይመጣል።**

3:16 "እግዚአብሔር . . . ወዶአል" ይህ በአላፊ ጊዜ የተፈጸመ እና የተጠናቀቀ ነገር ያመለክታል፡፡ ቁ 16-17 በቅድሚ የአብን ፍቅር የሚያሳይ ሲሆን (1ዮሐ 4:7-21 በተለይም 9-10)፡፡ "ፍቅር" የሚለው አጋፔ ሲሆን በክላሲክ ግሪክ ብዙም

አገልግሎት ላይ አልዋለም። የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ይህንን ቃል በመውሰድ ልዩ ትርጉም ሰጥታዋለች። በአንዳድ ክፍሎች ውስጥ በአባት እና በልጅ መካከል ያለውን ግንኙነት ሲያመለክት ነገር ግን አንዳንዴ ጊዜ በሰዎች መካከል ያለውን አሉታዎ ፍቅርንም ያሳያል (3፡19፤ 12፡43፤ 1ዮሐ 2፡15)። ይህ ቃል በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከሚገኘው ሄሴድ ጋር ተለዋዋጭ ሲሆን የእግዚአብሔር የቃል ታማኝነት እና ፍቅርን ያሳያል። በኮይኒ ግሪክ አጋፔ እና ፊሎ የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ናቸው (3፡35 እና 5፡20 ያነጻጽሩ)።

**ልዩ ርዕስ፡ እግዚአብሔር በሰውኛ ሲገለጽ**

I. በብሉይ ኪዳን ውስጥ እንዲህ ያሉ ቃላት የተለመዱ ናቸው (አንዳድ ምሳሌዎች)
   ሀ. አካላዊ ክፍሎች
      1. ዐይኖች- ዘፍ 1፡4፣ 31፤ 6፡8፤ ዘጸ 33፡17፤ ዘኁ 14፡14፤ ዛዳ 11፡12፤ ዘካ 4፡10
      2. እጆች- ዘጸ 15፡17፤ ዘኁ 11፡23፤ ዘዳ 2፡15
      3. ክንድ- ዘጸ 6፡6፤ ዘኁ 11፡23፤ ዘዳ 4፡34፤ 5፡15
      4. ጆሮዎች- ዘኁ 11፡18፤ 1ሳሙ 8፡21፤ 2 ነገ 19፡16፤ ዘም 5፡1፤ 10፡17፤ 18፡6)
      5. ፊት- ዘጸ 32፡30፤ 33፡11፤ ዘኁ 6፡25፤ ዘዳ 34፡10፤ መዝ 114፡7
      6. ጣቶች ዘጽ 8፡19፤ 31፡18፤ ዘዳ 9፡10፤ መዝ 8፡3
      7. ድምጽ- ዘፍ 3፡8፣ 10፤ ዘጸ 15፡26፤ 19፡19፤ ዘዳ 26፡17፤ 27፡10
      8. ስሜት- ዘጸ 24፡10፤ ሕዝ 43፡7
      9. በሰው መልክ- ዘጸ 24፡9-11፤ መዝ 47 ኢሳ 6፡1፤ ሕዝ 1፡26
      10. የእግዚአብሔር መለዓክ ዘፍ 16፡7-13፤ 22፡11-15፤ 31፡11፤ 48፡15-16፤ ዘጸ 3፡4፣ 13-21፣ 14፡19፤ መሳ 2፡1፤6፡22-23፤ 13፡3-22
   ለ. አካላዊ ድርጊት
      1. የስነ ፍጥርት ሂደት አድርጎ ማውራት ዘፍ 1፡3፣ 6፣ 9፣ 11፣ 14፣ 20፣ 24፣ 26
      2. በኤደን ውስጥ መራመድ (ድምጽ) ዘፍ 3፡8፤ 18፡33፤ እን 3፡15
      3. የኖህን መርከብ በር መዝጋ- ዘፍ 8፡21፤ ዘለ 26፡31፤ አሞ 5፡21
      4. ወደ ታች መውረድ- ዘፍ 11፡5፤ 18፡21፤ ዘጸ 3፡8፤ 19፡11፣ 18፣ 20
      5. ሙሴን መቅበር ዘዳ 34፡6
   ሐ. የሰው አይነት ስሜት (ትንሽ ምሌዎች)
      1. መጸጸት/ ንሰሐ- ዘፍ 6፡6፣ 7፤ ዘፍ 32፡14፤ መሳ 2፡18፤ 1ሳሙ 15፡29፣ 35፤ አሞ 7፡3፣ 6
      2. ቁጣ- ዘጸ 4፡14፣ 15፡7፤ ዘኁ 11፡10፤ 12፡9፤ 22፡22፤ 25፡3፣ 4፤ 32፡10፣ 13፣ 14፤ ዘዳ 6፡5፤ 7፡4፤ 29፡20
      3. ቅንአት- ዘጸ 20፡5፤ 34፡14፤ ዘዳ 4፡24፤ 5፡9፤6፡15፤32፡16፣21፤ ኢያሱ 24፡19
      4. መፀየፍ/መጥላት - ዘሌ 20:23፤ 26:30፣ዘዳ 32:19
   መ. የቤተሰብ ቃላት (ምሳሌ)
      1. አባት
         ሀ. ለእስራኤል - ዘጸ 4፡22፣ ዘዳ 141፤ 39፡5
         ለ. ለንጉሥ 2 ሳሙ 7፡11-16፤ መዝ 2፡7
         ሐ. ለአባታዊ ድርግቶች ምሳሌ - ዘዳ 1፡31፤ 8፡5፤ 32፡1፤ መዝ 27፡10፤ ምሳ 3፡12፤ ኤር 3፡4፣ 22፤ 31ለ20፤ ሆሴ 11፡1-4፤ ሚል 3፡17
      2. ወላጅ- ሆሴ 11፡1-4
      3. እናት- መዝ 27፡10
      4. ወጣት ታማኝ አፍቃር ሆሴ 1-3
II. በዚሀ አይነት መንገድ ለመጠቀሚ ያስፈለገበት ምክንያት
   ሀ. እግዚአብሔር ለሰው ልጆች እራሱን መግልጥ አስፈላጊ ነው። እግዚአብሔር እንደ ተበእት ጾታ ቢገለጥም እግዚአብሔር ግን መንፈስ ነው።
   ለ. እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ዋና ዋና የሚባሉ መገለጫዎችን ወስዶዋል፤ ይህንንም በመጠቀም ለሰው ልጆች እራሱን ገልጦዋል (አባት፣ እናት፣ ወላጅ፣ አፍቃር)
   ሐ. እግዚአብሔር ግን በማናቸው አካላዊ ነገሮች ግን አይገደብ (ዘጸ 20 እና ዘዳ 5)
   መ. ትልቁ የእግዚአብሔር በሰውኛ መገለጡ በኢየሱስ ትስብእት ውስጥ ይታያል! እግዚአብሔር አካላዊ፣ የሚዳሰስ ሆነ (1ዮሐ 1፡1-3)። የእግዚብሔር መልክ የእግዚአብሐየር ቃል ሆነ (ዮሐ 1፡1-18)።

▣ "እንዲሁ" ይህ ቃል በቃል ሲወሰድ "በዚህ ሁኔታ" ማለት ነው (7፡46፤11፡48፤18፡22)። ቃሉ የሚገልፀው ሁኔታን ወይም ዘዴን እንጂ ስሜትን አይደለም! እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለውን ፍቅር (ሮሜ5፡8ን ያስ) የገለጠው አንድያ ልጁን በእነርሱ ምትክ (ኢስ 53፡ ሮሜ 3፡25፤2ቆሮ 5፡21፤1 ዮሐንስ 2፡2) እንዲሞት በመላክ ነበር (ቁ17 ሁለቱም በግሪኩ ድርጊት ገላጭ አመልካች ግሦች ናቸው)።

▣ ***"ዓለም"*** *እግዚአብሔር ኮስሞስ የሚለውን ቃል በተለያየ መንገድ ነው የተጠቀመው።* (1፡10 ላይ እና በ13፡1 ላይ *ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።)።*

*ይህ ጥቅስ በተጨማሪ በመንፈስ (እግዚአብሔር) እና በቁስ መካከል ያለውን የኖስቲሳዊያንን ዱዖሊዝም የተቃወመ ነው። ግሪኮች ብዙውን ጊዜ ቁስን ከክፉ ጋር አጣምረው ይመለከቱ ነበር። ለእነርሱ ቁስ (የሰው አካል) በሁሉም የሰው ልጆች ውስጥ ያለ የመለኮት ፍንጣቂ የሚገኝበት እሥር ቤት እንደ ማለት ነው። ዮሐንስ ቁስን ክፉ ነው ብሎ አይገምትም። እግዚአብሔር ዓለምን (የምኖርባት ፕላኔት፣ ሮሜ* 8:18-22*ን ያስ) እና በውስጧ ያሉትን የሰው ልጆች (ሥጋ፣ ሮሜ* 8:23) *ይወዳል። ይህም በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የተለመደው* (1:5፤3:3:8) *ሆን ተብሎ የጠደረገ አፃሚነት ነው (ጣምራ አገባብ)።*

▣ ***"አንዲያ ልጅ"*** *ይህ "ብቸኛ" ልጅ ማለት ነው።*

▣ ***"በእርሱ የሚያምን"*** *ይህ የመጀመሪያውን እምነት የሚያመለክት ነው።* በ1:14 እና 2:23 *ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።* በቁ 15 *ላይ ይህ እውነት እንደገና ተጠቅ እናገኛለን። "ሁሉ" የሚለው ቃል ስላለ እግዚአብሔር ይመስገን! ይህም በአንድ የተለየ ቡድን ላይ (በዘር፣ በእውቀት ወይም በሥነ-መለኮት) የሚደረግን ያላፊ ትኩረት ሚዛኑን እንዲጠብቅ የሚያደርግ/ያለመስማማታቸው ጉዳይ አይደለም፣ ይልቁንም ሁለቱም እውነት ናቸው! እግዚአብሔር ሁልጊዜም ቢሆን ለምላሹ ሁኔታውን ሕብረት የሚያገናኘው በቃል ኪዳን አማካኝነት ነው። በመሆኑም ሰዎች እግዚአብሔር ለሚያቀርብላቸው ጥሪ እና ተዛማጅ ኃላፊቶች ምላሽ ሊሰጡበት ይገባል! ይህ ነው እንግዲህ ሰዎች ለእርሱ ያላቸው ፍቅር የሚገለጥበት።*

---

***ተጨማሪ የጥናት ርዕስ፡ አስቀድሞ መወሰን (ካልቪኒዝም) እና የሰው ነፃ ፈቃድ (አርሚኒያኒዝም)***

*ቲቶ* 2:1 *የቅዱሳንን መመረጥ በሚመለከት በሚናገሩ ሌሎች የአዲስ ኪን ምንባቦች ላይ ሚዛንን የሚያስጠብቅ ጥቅስ ነው። የራሴን ማብራሪያዎች ከሮሜ* 8:29 *እንዲሁም ከሮሜ* 9 *እና ከኤፊሶን/አንፃር መስጠቱ ሥነ-መለኮታዊ ጠቀሜታ ሊኖረው እንደሚችል አስባለሁ።*

1. *ሮሜ*8:29-*ጳውሎስ "አወቃቸው" ("ፕሮጊኖስኮ" አስቀድሞ ማወቅ") የሚለውን ሁለት ጊዜ ይጠቅሳል፤ በዚህ ሥፍራ እና* በ11:2 *ላይ።* በ11:2 *ላይ ቃሉ የሚያመለክተው ከዘላለም በፊት ወይም ጊዜ ከመጀመሩ በፊት እግዚአብሔር ለእስራኤል ያለውን የቃል ኪዳን ፍቅር ነው። "ማወቅ" የሚለው ቃል በእብራይስጥ ቋንቋ በጣም የቀረበን ግላዊ ግኑኝነትየሚሳይ እንጂ ስለአንድ ሰው ያለውን እውነታ አይደለም (ዘፍ* 4:1፤*ኤር*1:5)። *በዚህ ሥፍራ በዘላለማዊ የእይታት ስንስለቶች የተካተተ ነው (ሮሜ* 8:29-30 *ንያስ)፡፤ ስያሜው የተያያዘው ከአስቀድም መወሰን ጋር ነው። ይሁን እንጂ ለምርጫ የእግዚአብሔር አስቀድሞ ሁሉንም ማወቅ መሠረት ሊሆን እንደማይችል በግልፅ መታወቅ አለበት ምክንያቱም እንዲህ ከሆነማ ምርጫ የሚመሠረተው የወደቀው የሰው ዘር ወደፊት በሚሰጠው ምላሽ ላይ ነው ማለት ነው፤ ይህም የሰው ጥረት ውጤት ነው እንደማለት ነው። በተጠማሪ ስያሜው በሐዋ* 26:5፤ *(ጵጥ)*:2:20 *እና* 2*ጵጥ* 3:17 *ላይ ይገኛል።*
    - *ሀ. "አወቃቸው" (ፕሮጊኖስኮ፤ "ከመጀሚረያውም ማወቅ")*

      *"ማወቅ" እና "አስቀድም መወሰን" የሚሉት ስያሜዎች ሁለቱም "አስቀድም" የሚለው መስተዋድድ ያለቸው ድርብ ቃላት ስለሆኑ "አስቀድሞ ማወቅ"፣ "አስቀድሞ ዳርቻን መወሰን" ወይም "አስቀድሞ መገደብ" ተብለው ሊተረጎሙ ይገባል። አስቀድሞ በመወሰን ላይ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በግልፅ የተቀመጡ ምንባቦች ሮሜ* 8:28-30፤ *ኤፌ* 1:13-14፤ *ሮሜ* 9 *ናቸው። እነዚህ ክፍሎች የሚያተኩሩት እግዚአብሔር ሉዓላዊ አምላክ እንደሆነ ነው። እርሱ ሁሉንም ነገሮች ይቆጣጠራል። በጊዜ ሒደት የሚወራ ወይም የሚከናወን የአሁን የእግዚአብሔር እቅድ አለ። ይሁን እንጂ ይህ እቅድ በዘፈቀደ ወይም እየተመረጠ የሚሆን አይደለም። ይህን እቅድ በእግዚአብሔር ሉዓለዊነት እና ሁሉን በሚያወቅ ማንነቱ ብቻ ሳይሆን በማይለወጠው ፍቅሩ፣ ምህሩቱና ገደብ የለሽ ፀጋው የሚመሠረት ነው እንጂ።*

      *የእኛ ግለሰባዊነት (የአሜራካኖች) ወይም ቀናተኝነት ይህንን አስደናቂ እውነት እንዳያደበዝዝብን ልንጠነቀቅ ይገባል። ከዚህም ባሻገር በአውገስጢን እና ፔላጊየስ ወይም በካልቪኒዝም እና አርሚኒያኒዝም መካከል በሉት ታሪካዊ እና ሥነ-መለኮታዊ ግጭቶች ከመዋጥም ራሳችንን መጠበቅ ይገባል።*
    - *ለ. "አስቀድሞ ወሰናቸው" (ፕሮሪዞ፤ "አስቀድሞ ዳርቻን መወሰን")*

      *አስቀድሞ መወሰን የእግዚአብሔር ፍቅር ፀጋው እና ምህረቱን ለመገደብ ተቀመጠ አስተምህሮ ወይም አንዳንዶቹን ከወንጌል ውጭ ለማድረግም አያይዞም ከዚህ ይልቅ ሐሳቡ እይታቸው በማስተካከል አማኞችን ማጠንከር ነው። እግዚአብሔር ለሁሉም የሰው ዘር ነው (ጢሞ* 2:4፤2*ጵጥ* 3:9 *ን ይስ)። እግዚአብሔር ሁሉንም ይቅጣጠራል ከእርሱ ፍቅር ማን ወይስ ምን ሊለየን ይችላል (ሮሜ* 8:31-39 *ን ያስ)። እግዚአብሔር ሁሉንም ታሪክ የሚያየው እንደ አሁን ነው፤ የሰው ልጆች ግን በጊዜ የተገደቡ ናቸው። የእኛ እይታና የአእምሮ ብቃታችን ውሱን ነው። በመሆኑም በእግዚአብሔር ሉዓለዊነት እና በሰው ነፃ ፈቃድ መካከል ምንም አይነት ተቃርኖ የለም። ይህ የቃል ኪዳን ይዘት ነው። ይህ እውነት በዚይቤያዊ አነጋገር ተወስኖ ለመቆየቱ*

ሌላው ማሣያ ነው። የመጽሐፍቅዱስ አስተምህሮዎች ከተለያዩ እይታዎ አንፃር ይቀርባሉ፤ ብዙውን ጊዜም ተቃራኒ በሚመስሉ አካሄዶች ይቀርባሉ/ይመስላሉ። እውነታው ግን ያለው ተቃራኒ በሚመስሉት ጣምራዎች ነው። በመሆኑም አንዱን እውነት እየጠስን ብቻ ያውን ውጥረት ስናስወግደውም አይገባም።

የትኛውንም መጽሐፍቅድሳዊ እውነት ነጥለነው ማስቀምጥም የለብንም።

ከዚህም ባሻገር የመመረጥ ዋና ግቡ ስንሞት መንግስተ ሰማይን መውረስ ብቻ ሳይሆን አሁን ክርስቶስን መምሰል ነው (ሮሜ 8:29፤ኤፌ1:4፤2:10 ንያስ) እኛ የተመረጥነው "ቅዱሳንና ያለ ነቀፋ" እንሆን ዘንድ ነው። እግዚአብሔር እኛን የመረጠን ሊለውጠን እና ለውጡንም ሌሎች ተመልክተውት በክርስቶስ አማካኝነት ወደ እግዚአብሔር ይመጡ ዘንድ ነው። አስቀድም መወሰን የግል መብት ሳይሆን የቃልኪዳን ግዴታ ነው። ይህ የምንባቡ ዋናው እውነት ነው። የክርስትናም ግብ ነው። ቅድስና እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ አማኝ ያለው ፈቃድ ነው። የእግዚአብሔር ምርጫ ክርስቶስን ለመምሰል (ኤፌ 1:4 ንያስ) እንጂ የተለየ ሥፍራን ለማግኘት አይደለም። በፍጥረት ጊዜ ለሰው ልጅ ተሰጥቶት የነበረው የእግዚአብሔር መልክ (ዘፍ 1:26፤5:1:3፤9:6) አሁን ደግሞ በእግዚአብሔር ምርጫ ተሃድሶን ያገኛል።

ሐ. "የልጁን መስክ ይመስሉ ዘንድ" የእግዚአብሔር የመጨረሻው ግን በውድቀት ጊዜ ጠፍቶ የነበረውን የእግዚአብሄርን መስክ ደግሞ መመለስ ነው። በመሆኑም አማኞች ክርስቶስን መስሉ ዘንድ (ኤፌ 1:4 ንያስ0 አስቀድመው ተመስነዋል።

II. ሮሜ 9

ሀ. ሮሜ 9 በእግዚአብሔ ሉዓላዊነት ላይ ከተሰጡት የአዲስ ኪን ምንባቦች ጠንካራው ሲሆን (ሌላው በኤፌ 1:13-14 ላይ ያለው ነው) ምዕራፍ 10 የሰው ልጆችን ነፃ ፈቃድ በግልፅ እና በተደጋጋሚ ይገልፀዋል ("ሰው ሁሉ" ቁ 4፤ "ማንም" ቁ 11:13፤ "ሁሉ" ቁ 12 (ሁለት ጊዜ)። ጳውሎስ ይህንን ሥነ-መለኮታዊ ውጥረት ለማስታረቅ ምንም አይነት ጥረት አያደርግም ሁለቱም እውነት ናቸውና! ብዙዎቹ የሥነ-መለኮት ሥርዓቶች ግማሽ እውነቶች ናቸው አውገስጢኒያኒዝም እና ካልቪኒዝም ወይም ከፊል ፔላጊያኒዝም እና አርሜኒያኒዝም የእውነት እና የስህተት ነገሮች አሉባቸው። አስቀድሞ ከታሰበበት እና እየታረሙ ከተፃፈ፤ ቀኖናዊ ከሆነ፤ምክናታዊ እና ሥነ-መለኮታዊ ሥርዓት ይልቅ በአስተምህሮዎች መካከል ያለ ውጥረት የተሻለ ነው።

ለ. ተመሳሳይ እውነት (በሮሜ 9:23 የሚገኝ) በሮሜ 8:29-30 እና ኤፌ 1:4፤1) ላይ ተገልጿል። ይህ ምዕራፍ በአዲስ ኪዳን ከሚገኙት እና የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት ከሚገልፁጽ ከጉሉም ጠንካራው ነው። እግዚአብሔር በመፍተር እና በመቤዠት ሥራው ኃላፊነት እንዳለበት ብዙም የሚያከራክር ጉዳይ አይደለም። ይህ ታላቅ እውነት ሊደበዝዝ ሆነ ሊጠፋ የማይገባው ነው። ይሁን እንጂ በአምሳ ከተለጠፈው የሰው ልጅ ሕብረት ለማድረግ ከመረጠውየቃል ኪዳን አካሄድ ጋር ሚዛኑን ሊጠብቅ ይገባል። በብሉይ ኪዳን ያሉ አንዳንድ ኪዳኖች ለምሳሌ እንደ ዘፍጥረት 15 አይነቱ ሁሉንም የሰው ልጆች ምላሽ እንዲሰጡ የሚመለከት አይደለም ነገር ግን ሌሎች ኪዳኖች በሰው ምላሽ ላይ የተመሠረቱ ናቸው (ምሳ፤ ኤደን፣ ኖህ ሙሴ ዳዊት)። እግዚአብሔር ፍጥረቱን የሚቤዥበት እቅድ አለው ይህንንም እቅድ ማንም ሊለውጠው ኤችልም። እግዚአብሔር ሰዎች በእርሱ እቅድ ውስጥ እንዲሳተፉ እድልን ሰጥቷል። ይህ ለመሳተፍ ያለው እድል በሉዓላዊነቱ (ሮሜ 9) እና በሰው ነፃ ምርጫ (ሮሜ 10) መካከል ያለ ሥነ-መለኮታዊ ውጥረት ነው። አንድን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አፅንኦት መርጦ ሌላውን ቸል ማለት አግባብ አይደለም የምሥራቅ ሰዎች እውነትን በዚይቤያዊ ወይም ውጥረትን በተሞሉ ጣምራዎች ስለሚያቀርቧቸው በአስተምሮዎች መካከል ውጥረት አለ። እውነትም የብዙ እውነቶች ስብሰብ ነውና።

III. ኤፌሶን 1.

ሀ. መመረጥ አስደናቂ አስተምህሮ ነው። ይሁን እንጂ ለማዳላት የሚደረግ ጥሪ ሳይሆን ሌሎች መዳን መሣሪያ ለመሆን እንጂ! በብሉይ ኪዳን ስያሜውን ይጠቀሙበት የነበረው በመጀመሪያ ለ አገልግሎት ነበር ፤ በአዲስ ኪዳን ግን ድነትን ለመግለፅ ይጠቀሳል። መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር ለዳሳዊነት እና በሰው ነፃ ፈቃድ መካከል ያለውን ተቃርኖ ለማስተረቅ በፍፀም አይምክርም ይልቀንም ሁለቱንም ይደግፋቸዋል እንጂ! ለዚህ ጥሩ ምሣሌ የሚሆነን በሮሜ 9 ላይ በእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ላይ የተሰጠው እና በሮሜ 10 ላይ በሰው ልጅ አስፈላጊ ምላሽ ላይ (10:11-13) ያለው ነው።

ለዚህ ሥነ መለኮታዊ ውጥረት ቁልፍ የሚሆነው በ1:4 ላይ ያለው ነው። ኢየሱስ በእግዚአብሔር የተመረጠ ነበር እንዲሁም ደግሞ ሁሉም በእርሱ ተመርጠዋል (ካርስ ባርትዝ)። ኢየሱስ ለወደቀው የሰው ዘር ፍላጎት የእግዚአብሔር "አዎን" ነው (ካርል ባርትዝ)። ኤፌስን ምዕራፍ 4 ትም አስቀድሞ የመመረጥ ዋናው ዓላማ መንግሥት ሰማይ ብቻ ሳይሆን ቅድስና እንደሆነ (ክርስቶስን መምሰል) በይበልጥ የሚያብራራ ነው። ብዙውን ጊዜ እኛ ወደ ወንጌል በርከቶች እንዳላለን ነገር ግን ኃላፊነቶቹን ቸል እንላለን! የእግዚአብሔር ምርጫ ለጊዜውም እንዲሁም ደግሞ ለዘላለምም ነው።

አስተምህሮች ከሌሎች ጋር ተዛምደው ይመጣሉ እንጂ ተነጥለው ብቻቸውን አይደለም፤ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ሕብረ ከዋክብት እና አንድ ኮከብ የሚለው ነው። እግዚአብሔር እውነትን የሚያቀርበው በምሥራቃዊያ እንጂ በምዕራባዊያን አባባል አይደለም በዚይቤያዊ አነጋገር (ተቃራኒ በሚመስሉ) አማካኝነት የተፈጠሩውን የአስተምሮአዊ እውነት ጣምራዎችን ልናስወግዳቸው አይገባም (እግዚአብሔር እንደ ታላቅ እና እግአዚአብሔር እንደቅርብ፣ የድነት ዋስትና እና ፅናት ኢየሱስ ከአብ ጋር እኩል ነው ወይስ ከአብ ያሰ ነው፣ ክርስትያናዊ ነፃነት ወይስ የክርስትያን ኃላፊነት ወዘተ)።

"ቃል ኪዳን" የሚለው ሥነ-መለኮታዊ እይታ/መረዳት የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት (ሁል ጊዜ ተነሳሽነቱን የሚወስደውና ጉዳዩን የሚያደራጀው) ከሰው ልጆች ከሚሰጠው የንስሐ ምላሽ ጋር ያጣምረዋል። አንዱን ተቃርኖ

እየደገፍን ሌላውን ከማንኳሰስ ስንጠነቀቅ ይገባናል፣ ከዚህም ባሻገር ለራሥህ ተወዳጅ አስተምህሮ ወይም ሥነ-መለኮት እንዳትወግን መጠንቀቅም አለብህ።

ለ. *"መረጠን"* የሚለው በኤፌሶን 1፡4 ላይ የሚገኘው የግሪኩ ድርጊት ገላጭ *ግሥ የመሐል* አመልካች ሲሆን የሚያተኩረውም በድርጊት ፈፃሚው በባለቤቱ ላይ ነው። ይህም ጊዜ ከመጀመሩ በፊት አብ አስቀድሞ የነበረውን ምርጫ ላይ የሚያተኩር ነው። የእግዚአብሔር ምርጫ ሙስሞች እንደሚያምንበት የእግዚአብሔር ምርጫ ወይም እንደ አንዳንዶች ካልቢኒስቶች አተርጓጎም ሳይሆን ሊታይ የሚገባው ከቃል ኪዳን አንፃር ነው። እግዚአብሔር የወደቀውን የሰው ዘር እንደሚቤዥ አስቀድሞ ተናግሯል (ዘፍ 3፡15)። ሁሉንም የሰው ልጆች ለመምረጥ እግዚአብሔር አብርሃምን አስቀድሞ መረጠ (ዘፍ 12፡3 ዘፀ 19፡5-6)። እምነትን በክርስቶስ የሚለማመዱትን ሁሉ እግዚአብሔር ወደ ራሱ ጠርቷቸዋል። እግዚአብሔር ድነትን በሚመለከት ሁል ጊዜ ቀዳሚውን ሥፍራ ይወስዳል (ዮሐንስ 6፡44-65)። ይህ ጥቅስ እና ሮሜ 9 አስቀድሞ ስለመወሰን ቀደም ሲል በአውግስጢን እና በካልቪን ትኩረት ለተሰጠበት መፅሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ናቸው።

እግዚአብሔር አማኞችን የመረጠው ለድነት ብቻ (ድድቅ) ሳይሆን ለቅድስናም (ቆላ 1፡12) ጭምር ነው። ይህም ሲገኝን የሚችለው (1) በክርስቶስ ካለን ሥፍራ ጋር (2 ቆሮ 5፡21) ወይም (2) እግዚአብሔር የራሱን ባህሪይ በልጆች ውስጥ ለመፍጠር ከለው መሻት ጋር ነው (2፡10፤ሮሜ 8፡28-29፤ገላ 4፡19)። እግዚአብሔር ለልጆቹ ያለው ፈቃድ አንድ ቀን ወደፊት በመንግሥተ ሰማይ እንዲሆኑ አሁን ግን ክርስቶስን እንዲመስሉ ነው።

"በእርሱ" የሚለው በኤፌ 1፡4 ቁልፍ ሐሳብ ነው። የአብ በረከቶች ፀጋና ድነት በክርስቶስ ያልፋሉ (ዮሐ 14፡6 ን ያስ)። በቁ.3" በክርስቶስ" ቁ.4 "በእርሱ" ቁ.7 "በእርሱ"፣ ቁ.9 *"በእርሱ"*፣ ቁ.10፣ በክስቶስ"፣ "በእርሱ"፣ ቁ.12፣ "በክርስቶስ" እና ቁ.13 "በእርሱ" (ሁለት ጊዜ)፦ ኢየሱስ ለወደቀው የሰው ዘር የእግዚአብሔር "አዎን" ነው (ካርስ ባርትዝ)። ኢየሱስ ተመረጠው ሰው ስለሆነ ሁሉም በእርሱ ደግሞ ሊመረቱ ችለዋል። ሁሉም የአብ በረከቶች በክርስቶስ አማካይነት ወደ እኛ ይተላለፋሉ።

"ዓለም ሳይፈጠር" የሚለው ሐረግ በማቴ 25-34፣ ዮሐንስ 17፡24፤ 1ጴጥ 1፡19-20 እና ራዕ 13፡8። ይህ የሚያሳየው ከዛፍ 1፡1በፊትም የነበረውን የሥላሴን የመቤዠት ሥራን ነው። ሰዎች ለጊዜ ባላቸው ትርጉም የተወሰኑ ናቸው። ሁሉም ነገር ለእኛ ያለፈ፣ የአሁን እና የወደፊት ነው፤ ይህ ግን ለእግዚአብሔር አይሠራም። አስቀድሞ የመወሰን ግብ ቅድስና እንጂ ሙብት አይደለም የእግዚአብሔር ጥሪ ለተወሰኑ የአዳም ልጆች ሳይሆን ለሰው ልጆች ሁሉ ነው! የሰው ዘር በሙሉ ወደ እርሱ መልክ እዲመጣ እርሱን እንዲመስል (1 ተስ 5፡23፤2 ተስ 2፡13) እግዚአብሔር ያደረገው ጥሪ ነው። (ዘፍ 1፡26-27)። አስቀድም መወሰንን ከተቀደሰ ሕይወት ይልቅ ቁንፅል ወደ ሆነ ሥነ-መለኮታዊ እውነት መለወጥ እጅግ የሚያሳዝን ነገር ነው። ለዚህ ነው ጊዜ የእኛ ሥነ-መለኮቶች ከመፅሐፍ ቅዱስ ቃል ይልቅ ድምፃቸው ጉልቶ የሚሰማሙ።

*"ያለ ነውር"* (አምፖስ) ወይም "ነቀፋ የሌለበት" የሚለው ስያሜ የተጠቀሰው (91) ኢየሱ ለማመልከት (ዕብ 9፡14፤ 1ጴጥ 1፡19)፣ (2) ዘካርያስን እና ሌልሳቤጥን ለማመለክት (ሉቃ 1፡6ን ያስ) ለማመልከት፣ (3) ጳውሎስን ለማመልከት (ፊልጵ 3፡6) ለማመለክት እንዲሁም (4) ሁሉንም እውነተኛ ክርስትያኝን (ፊል 2፡15፤ 1ተስ 3፡13፤5፡23) የማመልከት ነው። እግዚአብሔር ለሁሉም ክርስትያኖች ያው የማይለወጥ ፈቃዱ በኋ ለ ወደ ምነግሥተ ሰማይ እንዲሄድ ብቻ ሳይሆን አሁን ክርስቶስን እንዲመስሱ ነው እንጂ /ሮሜ 8፡29-30፤ ገላ 4፡19፤ 1ጴጥ 1፡2)። ለወንጌል ዓማ ስሉ አማኞች ለጠፋው ዓለም የእግዚአብሔርን ባህርይ ማንፃባረቅ ይገባቸዋል።

ከሰዋሰው አንፃር "በፍቅር" የሚለው በዚህ ጥቅስ ላይ የሚገኘው ሐረግ ከቁ 4 ወይም 5 ጋር አብሮ ሊሄድ ይችላል። ይሁን እንጂ ይህ ሐረግ በኤፌስን መልዕክት ውስጥ በሌላ ሥፍራዎች ሲጠቀስ ሁል ጊዜ የሚያመለክተው ሰው ለእግዚአብሔር ያለውን ፍቅር ነው (3፡17፤4፡2፤15-16)።

ሐ. በኤፌ 1፡5 ላይ "አስቀድሞ ወሰነን" የሚለው ሐረግ የግሪኩ ድርጊት ገላጭ የዝ አንቀፅ ነው። ይህ የግሪክ ስያሜ "አስቀድሞ" እና "መገደብ" የሚሉት ጣምራ ነው። አስቀድሞ የተወሰነን የእግዚአብሔርን የማዳን እቅድ የሚያመለክት ነው (ሉቃ 22፡22፤ ሐዋ 2፡23፤4፡28፤17፡31፤ሮሜ 8፡29-30)። አስቀድሞ መወሰን ከሰው ልጅ ድነት ጋር አንፃር ከጸገለጠ በርካታ እውነቶች አንዱ ነው። የሥነ-መለኮታዊ ንድፍ ዌም ተከታታይና ተዛመጅ ከሆኑት እውነቶች አንዱ ክፍል ነው። ለብቻው ትኩት ተሰጥቶት/ተገልሎ ትርጉም እንዲኖረው የታሰበበት አይደለም! መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ውጥረትን በተምሉ እና ተቃራኒ በሚመስ ጣምራዎች የተሰጠ ነው። አንድ ቤተ-እምነትን የማጥበቅ አካሄድ አንዱን ዲያሌክቱካዊ /ዘይቤያዊ/ አባባል ብቻ በመውሰድ መፅሐፍ ቅደሳዊውን ውጥረት ለማስወገድ ሲጥር ቆይቷል (እቀድሞ ወሰን ወይስ የለው ነፃ ምርጫ፤የአማካኝ የደህንነት ዋስትና ወይስ የቅዱሳን ፅናት፣ የውርስ ኃጢአት ወይስ የፈቃድ ኃጢአት፣ ኃጢአት የለሽነት ወይስ ከኃጢአት መላቀቅ እምነት ወይስ ሥራ፣ ክርስትያናዊ ነፃነት ወይስ ክርስትያናዊ ኃላፊነት፣ የእግዚአብሔር ታላቅነት ወይስ የእግዚአብሔር ቅርብነት)።

የእግዚአብሔር ምርጫ ሰው የሚያደርገውን ጥረት አስቀድሞ በማወቁ ላ የተመሠረት ሳይሆን በእርሱቸርነት ላይ ነው (ቁ. 9 እና 11)። እግዚአብሔር ሁሉም (እንደ ቀደሙት ኖስቲሳዊያን ወይም እንደ ዘመናችን ሁሉን አቀፍ ካልቪኒስቶች አንዳንዶቹን) የሰው ልጆች ይድኑ ዘንድ ይፈለልጋል።

(ሕ 18፡21-23፤32፤ዮሐንስ 3፡-17፤ 1ጢሞ 2፡4፤4፡10፤ቶቶ 2፡11፤2 ጴጥ 3፡9)። የእግዚአብሄር ምህረት አስቀድሞ መመሰንን (ሮሜ 9-11) በሚመለከት ባሉት ሌሎች ምንባቦች ላይ ቁልፍ ሚና እንዳለው ሁሉ የእግዚአብሔርም ፀጋ (የእግዚአብሔር ባህርይ) ለዚህ ምንባብ ቁልፍ የሆነ ሥነ-መለኮት ነው (ቁ.6ሀ፣ 7ሐ፡9ለ)።

ወደቀው የሰው ዘር ብቸኛ ተስፋ የእግዚአብሔር ፀጋ እና ምህረት ነው (ኢሳ 53፡6 እ በሮሜ 3፡9-18 ላይ

የተጠቀሱ ሌሎች የብሉይ ኪዳን በርካታ ጥቅሶች)። ሐዋርያው ጳውሎስ ከሰው ልጅ ጥረት ጋር የማገናኙትን እነዚህ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ማድረጉን በሚመለከት አስቀድሞን ሥነ-መለኮታዊ ጠቀሜታ ያላቸውን እነዚህን ወሳኝ ምዕራፎች በጥንቃቂ መተርጎም ወሣኝ ጉዳይ ነው፤ አስቀድሞ መወሰን (ምዕ1)፤ ፀጋ (ምዕ-2)፣ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ የመቤዠት እቅድ (ሚስጥር 2:11-3:13)። ይህም ሁኔታ የሐሰት አስተማሪዎች በሰው ሥራና እኔላት ላይ የሰጡትን አፅንኦት በተቃራኒው ሚዛኑን እንዲጠብቅ ለማድረግ የሚያስችል ነው።

▣ **"እንዳይጠፋ"** ይህ ቃል የሚያመለክተው አንዳንዶች እንደሚጠፉ ነው። የመጥፋታቸው ምክንያት በኢየሱስ በለማመናቸው ነው። (1125)። እግዚአብሔር እንዲያምኑ አያደረጋቸውም (ሕዝ 18:23፣ 32፤ 1ጢሞ 2:4፤ 2ጴጥ 3:9)።

አንዳንድ ሰዎች ይህንን ቃል በቀጥታ በመውሰድ ኃጢአትን ፈጽመው ይተፋሉ ወደሚል መደምደሚያ ደርሰዋል። ይህ በዳን 12:2 እና ማቴ 25:46 ላይ ከተገለጸው ጋር ይጣረሳል። ይህ በጠንካራ ሥዕላዊ አገላለፅ የተሞላውን የምሥራቃዊያን ሥነ-ፅሑፍ በትርጉም ወደተሞላው የምዕራባዊያን ሥነ-ፅሑፍ (ቀጥተኛ እና ምክንያታዊ) ለሚገፉት የዋህ ክርስትያኖች ጥሩ ምሣሌ ሊሆን የሚችል ነው፤ ይህንን ቃል በሚመለከት ጥሩ የሆነ ግንዛቤን ለመጨበጥ የሮበርት ገርድልስቶንን *Synonyms of the Old Testament* የሚለውን መፅሐፋቸውን በገጽ 275-277 ላይ ይመልከቱ። በ10:10 ላይ ያውን ጥፋት (አፖሉሚ) የሚለውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስንም ይመለከቱ።

ከዚህም ባሻገር ዮሐንስ በዱዋሊስቲክ ጣምራ ምድቦች እንዴት እንደሚያስብና እንደሚፅፍ ያስተውሉ (ለምሳሌ መጥፋት ወይስ የዘላለም ሕይወት)። በሌሎች ወንጌላት እና በዮሐንስ ወንጌል መካከል ያሉት የኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት የቃል እና የሥነ- መለኮት አወቃቀር በፍፁም የተለያዩ ናቸው። በዚህም አንድ ሰው የወንጌል ፀሐፊዎች ኢሱስን በሚመለከት ወንጌልን ለሰሚዎቹ ለማዘጋጀት ምን ያህል ነፃነት (በመለኮት ምሪት፣ እስትንፋሰ እግዚአብሔር) እንደነበራቸው ሳይገርመው የሚቀር አይመስለኝም በተጨማሪ የጎርደን ፊ እና ዳግላስ ስትዋር ትን *How to Read The Bible For All Its Worth* የሚለውን መጽሐፍ በገጽ 127-148 ለላ ይመልከቱ።

**3:17 "በዓለም እንዲፈርድ"** በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ኢየሱስ እንደ አዳኝ እንጂ እንደ ፈራጅ እንዳልመጣ ብዙ ክፍሎች ያሳያሉ (3:17-21፤ 8:15፤ 12:47)። ነገር ግን ሌሎች ኢየሱስ እንደ ፈራጅ ሆኖ መምጣቱን እንዲሁም ለወደፊትም እንደሚመጣ የሚያመለክቱ ክፍሎች አሉ (5:22-23፣ 27፤ 9:39 ከዚህ በተጨማር ሌሎች የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ሐዋ 10:42፤ 2ጢሞ 4:1፤ 1ጴጥ 4:5)።

በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ ስነ መለኮታዊ ትንታኔዎች ተሰጥተዋ

1. እግዚብሔር ስነ ፍጥረትን እና ድነትን ለኢየሱስ የመክበሩ ምልክት እንዲሆኑ እንደሰጠው ሁሉ እንዲፈርድም ሰጥቶታል
2. ኢየሱስ በመጀመሪያ ስመጣ የመጣው ለመፍረድ አልነበረም ነገር ግን ለማዳን (3:17) ነገር ግን ሰዎች አልተቀበሉትም ስለዚህም እራሳቸው ላይ ፈርደዋል
3. ኢየሱስ የነገሥታት ንጉሥ እና ፈራጅ ሆኖ እንደገና ይመጣል (9:39)

**3:18** ይህ ክፍል ነጻ በሆነው ድነት እና በሰዎች ጥረት መካከል ያለውን ልዩነት ያሳያል። እግዚአብሔር ሰዎች ወደ ሲኦል አይሰዳቸውም። ነገር ግን እራሳቸው ነው የሚልኩት።ማመን ቀጣይነት ያለው ውጤት ስኖረው አለማመንም እንዲሁ ነው። በ2:23 እና 9:7 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።

**3:19-21 "ሰዎች . . . ጨለማን ስለ ወደዱ"** ብዙ ሰዎች ወንጌልን ሰምተው አልተቀበሉትም አመክኖዊነት ስለሚጎለው ወይም በባህላቸው ምክንያት ሳይሆን በዋነኝነት በግብረገባዊነቱ ነው (እዬ 24:13)። ብርሃን የሚያሳየው ክርስቶስን ነው (1:9፤ 8:12፤ 9:5፤ 12:46) እንዲሁም የእግዚአብሔር የፍቅር መልዕክት፣ የሰው ልጆች ፍላጎት፣ ክርስቶስ የሰራው ስራ እና የሚያስፈልገው ምላሽ አለ።

**3:19 "ፍርዱ ይህ ነው"** ፍርድ እንደ ድነት የአሁን ጊዜ ገጽታ አለው (3:19፤ 9:39) ሲኖረው የወደፊት ፍጻሜም አለው (5:27-29፤ 12:31፣ 48)። አማኞች ተፈጻሚነት ባለው የመጨረሻ ዘመን ውስጥ ቢኖሩም ግን ገና ሙሉ ለሙሉ ፍጻሜን ባገኝ የመጨረሻው ዘመን ውስጥ ግን እየኖሩ አይደለም። የክርስትና ሕይወት ሐሴት እና በጣም አስቸጋር ሆኑ ነገሮች የሞላበት ነው፤ ለዚህም ነው ጸንተን እንድንቆን ጥብቅ ማስጠንቀቂያ የተሰጠን።

**3:21 "እውነትን የሚያደርግ"** "ብርሃን" የሚለው ቃል ኢየሱስን የሚያመለክት ከሆነ (ቁ 19፣ 20 (2 ጊዜ፣ 21) ስለዚህ እውነት ዩለው ቃል እርሱን ያመለክታል።

*መወያያ ጥያቄዎች*

*ይህ ምሪትን የሚሰጥ የመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻ ነው፤ ይህም ማለት ለምትደረስበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ኃላፊነት የምትወስደው አንተ እራስ ትሆናህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን ባለን ብርሃን መጠን ልንመላለስ ይገባል ማለት ነው። በስነ አፍታት ሂደት ውስጥ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ዋነኛውን ስፍራ ትይዛላችሁ። ይህንን እድል ለመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻዎች አሳልፈህ አትስጥ።*

*ከዚህ በታች የተጠቀሱት የመወያያ ጥያቄዎች በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ባሉት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ማሰላሰል እንድትችሉ ለማገዝ የተዘጋጁ ናቸው። የሚገድቡህ ሳይሆን የማሰላሰል ምናብን እንዲያሰፉልህ የታቀዱ ናቸው።*

1. *"እንደገና መወለድ" የሚለው ሀረግ ትርጉም ምንድነው?*
2. *በቁ 5 ላይ ያለው ውሃ ምንን ያመለክታል። ለምን?*
3. *"እምነት" (የሚያድን እምነት) ምን ማለት ነው?*
4. *ዮሐ 3፡16 ኢየሱስ ለሰው ልጆች ያለውን ፍቅር ወይስ የአብን ያሳያል።*
5. *ካልቬንስቶች ዮሐ 3፡16 እንዴት ይገነዘቡታል?*
6. *"መጥፋት" የሚለው ቃል ፈጽሞ መወገድን ያመለክታልን?*
7. *"ብርሃን" የሚለውን ቃል ትርጓሜ ግለጽ።*

**ቁጥር 22-36 ላለው አውዳዊ አብርሆት**

- ሀ. *ዮሐንስ ወንጌልን ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ ዚህ ስፍራ ድረስ የኢየሱስ ክርስቶስን ፍጹም አምላክነት ገልጸዋል። ይህም ምዕራፍ ተመሳሳይ ይዘት ይዞ ቀጥላል።*
- ለ. *የዮሐንስ ወንጌል በመጀመሪያው ምእተ አመት መጨረሻ አከባቢ በመጻፉ መምክንያት ተመሳሳይ ወንጌላት ከተጻፉ በኋላ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለ ተነሱ ችግሮች ያወሳል። ከእነዚህ ችግሮች መካከል ከመጥመቁ ዮሐንስ ጋር ተያይዞ ያለ የስህተት ትምህርት ነው። (ሐዋ 18፡24-19፡7)። በ1፡6-8፣ 19-36 ላይ መጥመቁ ዮሐንስ ከኢየሱስ እንደሚያንስ እንዲሁም የኢየሱስን የመሲሕነት ሚና ገልጸዋል።*

***የቃላት እና የሀረጎች ጥናት***

| |
|---|
| **የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 3፡22-24**<br>**ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ይሁዳ አገር መጣ: በዚያም ከእነርሱ ጋር ተቀምጦ ያጠምቅ ነበር። ዮሐንስም ደግሞ በሳሌም አቅራቢያ በሄኖን በዚያ ብዙ ውኃ ነበርና ያጠምቅ ነበር: እየመጡም ይጠመቁ ነበር ዮሐንስ ገና ወደ ወኅኒ አልተጨመረም ነበርና።** |

3፡22 **"ወደ ይሁዳ አገር መጣ"** *ይህ የኢየሱስ የይሁዳ እና ገሊላ የመጀመሪያው አገልግሎት በሌሎች ተመሳሳይ ወንጌላት ውስጥ አልተጠቀሰም። ወንጌላት የጊዜ ቅደም ተከተልን የተከተሉ የኢየሱስ የሕይወት ታሪኮች አይደሉም።*

▣ **"በዚያም ከእነርሱ ጋር ተቀምጦ"** *ኢየሱስ ለሕዝቡ ይሰብክ ነበር ነገር ግን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ግብ ብዙ ጊዜ ወስዶ ይወያይ ነበር። በእነርሱ ውስጥ ሕይወቱን አፍስሷል።*

▣ **"ያጠምቅ ነበር"** *በ4፡2 ላይ እንደሚንመለከተው ኢየሱስ እራሱ አያጠምቅም ነበር ነገር ግን የእርሱ ደቀ መዛሙርት ያጠምቁ ነበር። በመጀመሪያ የኢየሱስ መልዕክት ከመጥመቁ ዮሐንስ መልዕክት ጋር ተመሳሳይ ነበር። ይህም የብሉ ኪዳ የንስሐ እና የዝግጅት መልክት ነበር። በዚህ ስፍራ ላይ የተጠቀሰው ጥምቀት የክርስቲያኖች ጥምቀት አይደለም ነገር ግን የንስሐ ጥምቀት እና መንፈሳዊ ተሃድሶን የሚያመለክት ነው።*

3፡23 **"ዮሐንስም ደግሞ በሳሌም አቅራቢያ በሄኖን በዚያ ብዙ ውኃ ነበርና ያጠምቅ ነበር"** *ይህ ስፍራ ዬት እንደሆነ በእርግጠኝነት አይታወቅም።*

1. *አንዳንዶች ፔራ በሚባል ከዮርዳኖስ ወንዝ በሻገር የሚገኝ እንደሆነ ያምናሉ*
2. *አንዳንዶች በሰሜን ምስራቅ ሰማሪያ የሚገኝ አከባቢ እንደሆነ ያምናሉ*
3. *አንዳንዶች ደግሞ ከሼኬም በምስራቅ በኩል ሦስት ማይል ርቀት ላይ የሚገኘ ነው ብለው ያምናሉ*

*ሄኖን የሚለው "ጅረት" ማለት ስሆን በተ.ቁ 3 ላይ ያለው ከአውዱ ጋር ተስማሚ ነው። ትክክለኛው ቦታ የትኛውም ይሁን ኢየሱ በይሁን ያገለግል እንደ ነበር እና ዮሐንስም ከእርሱ በስተሰሜን በአጭር ርቀት ላይ ይገኝ እንደ ነበር ነው የምንረዳው።*

3:24 **"ዮሐንስ ገና ወደ ወኀኒ አስተጨመረም ነበርና"** በዚህ ነጥብ ላይ ይህ የጊዜ ቅድም ተከተል ለምን እንደተጨመረ የሚታወቅ ነገር የለም አንዳንዶች ይህ የዮሐንስን የጊዜ ቅድመ ተከተል ከወንጌላት ጋር (ማቴ 14:1-12፤ ማር 6:14-29) ለማስማማት የተደረገ ሙከራ ነው ይላሉ። የጊዜ ቅድም ተከተሉ በክርስቶስ ሕይወት ውስጥ የተፈፀመውን ክስተት እንደ ጊዜ አመለካች ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

| |
|---|
| የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 3:25-30<br>**ስለዚህም በዮሐንስ ደቀ መዛሙርትና በአይሁድ መካከል ስለ ማንጻት ክርክር ሆነ። ወደ ዮሐንስም መጥተው። መምህር ሆይ: በዮርዳኖስ ማዶ ከአንተ ጋር የነበረው አንተም የመሰከርህለት: እነሆ: እርሱ ያጠምቃል ሁሉም ወደ እርሱ ይመጣሉ አሉት። ዮሐንስ መለሰ: እንዲህ ሲል፦ ከሰማይ ካልተሰጠው ሰው እንዳች ሊቀበል አይችልም። እናንተ። እኔ ክርስቶስ አይደለሁም: ነገር ግን። ከእርሱ በፊት ተልኬአለሁ እንዳልሁ ራሳችሁ ትመሰክሩልኛላችሁ። ሙሽራይቱ ያለችው እርሱ ሙሽራ ነው፤ ቆሞ የሚሰማው ሚዜው ግን በሙሽራው ድምጽ እጅግ ደስ ይለዋል። እንግዲህ ይህ ደስታዬ ተፈጸመ። እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል።** |

3:25 **"በዮሐንስ ደቀመዛሙርትና በአይሁድ መካከል ክርክር ሆነ" ክርክር"** (ኤን.ኤ.ኤ.ቢ.NRSV.NJB) "አለመግባባት" ወይም "መጋፈጥ" ለሚለው ጠንካራ ስያሜ ነው። አንዳንድ የግሪክ ምንጮች "አይሁድ" የሚል የብዙ ቁጥር አላቸው ጥንታዊያን የግሪክ ምንጮች በእኩል የተከፈሉ ናቸው። ነጠላው ቁጥር ብዙም ያልተለመደ በመሆኑ (ማለትም MSSP[25]፣N[2]፣A፣B፣L፣W) ምናልባት የመጀመሪያው ሊሆን ይችላል። የዩ-ቢ-ኤስ[4ኛ] ትርጉም የ"B" ደረጃን ይሰጠዋል (ለእርግጠኝነት የቀረበ ማለት ነው)። የቀድሞዎቹ ፀሐፍት ዝንባሌ ጥቅሱን ለማስማማትና ጥንካሬውን ለመቀነስ ነበር። ከዚህም ባሻገር የዮሐንስ ደቀመዛሙት ክርክሩን ሊያነሣሡም እደሚችሉ ማጤኑ ጠቃሚም ጉዳይ ነው።

▣
NASB፣ NKJV፣

| | |
|---|---|
| NJB | "ስለ መንጻት" |
| TEV | "ስለ መንፈሳዊ እጥበት" |

ስለዚህ ክርክር ብዙ መላምቶች ተሰጥተዋል።

1. የዮሐንስ እና ኢየሱስ ተከታዮቻቸው ስለ ጥምቀታቸው እና ከአይሁድ ትውፍት ጋር ስላለው ግንኙነት ተወያይተው ሊሆን ይችላል፤ በቁጥር 2:6 ላይ ተመሳሳይ ቃል አገልግሎት ላይ ውሏል።
2. አንዳንዶች በዚህ አውድ ውስጥ ኢየሱስ እርሱ ሕይወት እና ትምህርት የአይሁዳዊያን ሁሉ ነገር ፍጻሜ መሆኑ ጋር የሚስማማ እንደሆነ ይናራሉ

3:26 **"በዮርዳኖስ ማዶ ከአንተ ጋር የነበረው አንተም የመሰከርህለት: እነሆ: እርሱ ያጠምቃል ሁሉም ወደ እርሱ ይመጣሉ አሉት"** እነዚህ ደቀ መዛሙር ዮሐንስ በዮርዳኖስ ከዚህ ቀደም የእግዚአብሔር በግ በማለት የሰጠውን ምስክርነት አስታውሰዋል (1:19-36)። እንዲሁም በእርሱ ስኬት ትንሽ ቀንተዋል፤ ኢየሱስ የፉክክር መንፈስ እንዳይኖር ጥንቃቄ አድርጓል። ለአማኖች የተሰጣቸው ማናቸውም ነገር በእግዚአብሔር ጸጋ ያገኙት ነው።

3:27 **"ከሰማይ ካልተሰጠው ሰው አንዳች ሊቀበል አይችልም"** ይህ በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ ምንም አይነት ውድድር ሊኖር እንደማይገባ በቀጥታ የተደረገ ንግግር ነው። አማኞች ያላቸው ሁሉ ነገር በእግዚአብሔር ፀጋ አማካኝነት የተሰጣቸው ነው። ይሁን እንጂ "በተሰጠው ነገር" እና "በተቀባዩ" ምንነት ላይ ብዙ የሚያከራክር ነገር አለ፤

1. አንዳንዶች "ተቀባይ" አማኙን ሲያመለክት "የሚሰጠው" የሚለው ደግሞ ለድነት ወደ ክርስቶስ የሚመጣን ሰው ያመለክታል ይላሉ። (እግዚአብሔር ሲቀሰቅስ ሰዎች ደግሞ ምላሽ ብቻ ይሰጣሉ፤ ዮሐንስ 6:44፤65 ን ያስ)።
2. ሌሎች ደግሞ "ተቀባዩ" ኢየሱስን ሲያመለክት "ተሰጠ" የሚለው ደግሞ አማኞችን ያመለክታል ይላሉ (ዮሐንስ 6:39፤10:29፤17:2፤9:11፤24)።

በእነዚህ በሁለቱ አመለካከቶች መካከል ያለው ልዩነት "ተሰጠ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የአንድን አማኝ ድነት ወይም ሁሉም ለኢየሱስ የተሰጡት አማኞች ከእግዚአብሔር የተሰጡ ናቸው (17:2 ንይመ) የሚል ነው።

3:28 **"እኔ ክርስቶስ አይደለሁም"** በ1:20 ላይ እንዳደረገው ሁሉ መጥመቁ ዮሐንስ መሲሑ እንዳልሆነ መስክሯል። ነገር ግን ከእርሱ በፊት የሚመጣው መንገድ ጠራጊው እንጂ። ይህ ግልጽ የሆነ ከሚል 3:1፤ 4:5-6 ተወስዶ ከኢሳ 40 ጋር የተዋሃደ ነው (ዮሐ 1:23)። "መሲሕ" የሚለውን በ1:41 ላይ የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ።

3:29 **"ሙሽራይቱ ያለችው እርሱ ሙሽራ ነው"** በዚህ ከብሉይ ኪዳን በተወሰደ ምሳሌያዊ ንግግር ውስጥ በእስራኤል እና በእግዚአብሔር መካከል ስላለ ግንኙነት የሚያወሳ ብዙ ነገር አለ። (ኢሳ 54:5፤ 62:4፣ 5፤ ኤር 2:2፤ 3:30፤ሕዝ 16:8፣ 23:4፤ ሆሴ 2:21)። ጳውሎስ ኤፌ 5:22 ላይ ይህን የሚመስል ነገር ተጠቅሞ እናገኛን። ክርስቲያናዊ ጋብቻ ለቃል ኪዳናዊ ግንኙነት በጣም ጥሩ ምሳሌ ነው።

▣ *"እንግዲህ ይህ ደስታዬ ተፈጸመ"* ከፉክክር መንፈስ ይልቅ መጥመቁ ዮሐንስ የራሱን ቦታ በማወቅ በኢሱስ ሐሴትን ያደርግ ነበር፡፡

3፡30 **"እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል"** በዚህ ስፍራ ላይ "ያስፈልጋል" የሚለው ቃል እጅግ ወሳኝ ቃል ነው፡፡ ከዚህ በፊት በቁ 3፡14 እና 4፡4 ላይ ተጠቅሶ እናገኘዋለን፡፡ እጅግ በጣም ጠቃሚ እና ትልቅ የሆነው የኢየሱስ አገልግሎት እርሱ አዘጋጅ ብቻ መሆኑን ዮሐንስ ተቀብሎታል፡፡

> የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 3፡31-36
> **ከላይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው፤ ከምድር የሚሆነው የምድር ነው የምድሩንም ይናገራል፡፡ ከሰማይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው፡፡ ያየውንና የሰማውንም ይህን ይመሰክራል፡ ምስክሩንም የሚቀበለው የለም፡፡ ምስክሩን የተቀበለ እግዚአብሔር እውነተኛ እንደ ሆነ አተመ፡፡ እግዚአብሔር የላከው የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራልና፤ እግዚአብሔር መንፈሱን ሰፍሮ አይሰጥምና፡፡ አባት ልጁን ይወዳል ሁሉንም በእጁ ሰጥቶታል፡፡ በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤ በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቍጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም፡፡**

3፡31-36 ይህ ቁጥር እንዴት መተርጎም እንዳለበት በመጽሐፍ ቅዱስ መፍቻዎች መካከል ብዙ ውይይት አለ፡፡
1. የመጥመቁ ዮሐንስ የቃል ማረጋገጫ
2. የኢየሱስ ቃል (3፡11-12)
3. የሐዋርያው ዮሐንስ

3፡31 **"ከላይ የሚመጣው"** እነዚህ ሁለት ማእረጎቸ የመሲሁን አስቀድሞ መኖር እና ፍጹም አምላክነቱን የሚያስረግጡ ናቸው፡፡ እንዲሁም የእርሱን ትስብእት እና እግዘኢብሔር የሰጠውን ተልዕኮ ያሳያሉ (በቁ 31 እና 34 በተዘዋወሪ መንገድ እንደተገለጠው)፡፡ "ከላይ" የሚለው ቃል "ከዳግም መወለድ" ከሚለው ጋር ተያይዞ መጥቶ ነበር ቁ 3፡፡

ይህ የእግዚአብሔር ዓለም እና የምድራዊው ዓለም ተብሎ ከላይ ወደታች የተገለፀው ዲዋሊዝም የዮሐንስ ወንጌል መለያ ባህርይ ነው፡፡ ይህም ነገረ- ፍፃሜን ከሚያለክተቱ የሙት ባህር ጥቅሎች ዲዋሊዝም የተለየ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መንፈስ እና ቁስ ተብሎ ከሚታወቀው የኖስቲሳዊያን ዲዋሊዝምም የተለየ ነው፡፡ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ግን ፍጥረት ራሱ እና የሰው አካል በራሳቸው ክፉ ወይም ኃጢአት ሊባሉ የሚችሉ አይደሉም፡፡

▣ **"ከሁሉ በላይ . . . ከሁሉ በላይ"** የዚህ ቁጥር የመጀመሪያው ክፍል የኢየሱስን መለኮታዊነት እና ቅድመ ሁነት፣ ከሰማይ መምጣቱን ያሳያል (1፡1-18፤ 3፡11-12)፡፡ ሁለተኛው ደግሞ እርሱ ከእግዚአብሔር ፍጥረት ሁሉ በላይ መሆኑን ያሳያል፡፡ በግሪኩ ጥቅስ ላይ "ሁሉ" የሚለው ሁሉንም የሰው ዘር ወይም ሁሉንም ነገሮች ለማመልከት በወንድ ፆታ አመልካች ወይም በግዑዝ ፆታ አመልካች መጠቀሱ የሚታወቅ አይደለም፡፡ "ከሁሉ በላይ" የሚለው ሐረግ በአንዳንድ የግሪክ ትርጉሞች ውስጥ አልተገለፀም፡፡ የዩ.ቢ.ኤስ 4 መጽሐፍ ቅዱስ በመካተቱ ላይ ሊወስን አይችልም፤ ነገር ግን በጥቅስ ላይ የሚሰጠው ማብራሪያ (ማውጫ 23 ይመልከቱ) መካተቱን ይመርጣል፡፡

▣

| | |
|---|---|
| NASB፣ | "ምድራዊ የሆነ ከሚድር ነው እንዲሁም ስለ ምድር ይናራል" |
| NKJV፣ | "ከምድር የሆነ ምድራዊ ነው እንዲሁም ስለ ምድር ይናገራል" |
| NRSV፣ | "ከምድር የሆነ የምድር ነው እንዲሁም ስለ ምድር ይናራል" |
| TEV | "ከምድር የሆነ ምድራዊ ነው ስለ ምድራዊ ነገሮች ይናገራል" |
| NJB | "እርሱ ራሱ ከምድር ሆነ ምድራዊ ነው እነዲሁም በምድራዊ መንገድ ይናጋራል" |

ይህ ስለ ዮሐንስ የተነገረ አሉታዊ ንግግር አይደለም፡፡ በዚህ ስፍራ ላይ ያለው ምድራዊ ተብሎ የተተረጎመው (12፡32፤ 17፡4፤ 1ዮሐ 5፡8 ነገር ግን በራዕ 76 ጊዜ ያህል ተጠቅሷል)፡፡ "ዓለም" ከሚለው ቃል ጋር አይደም፡፡ ይህ "ዓለም" የሞለው ቃል በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ብዙ ጊዜ አሉታዊ በሆነ መልኩ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ ይህ ቃል የሰው ልጆች ከሚያውቁት፣ ከምድራዊ ነገር ኢየሱስ ግን ከሚያውቀው ከሰማያዊ ነገር ይናጋራል ማለት ነው፡፡ ስለዚህም የኢየሱስ ምስክርነት ከማንኛውም ነብይ ወይም ሰባክ እጅግ በጣም ይበልጣል (ዕብ 1፡1-4)፡፡

3፡32 **"ያየውንና የሰማውንም ይህን ይመስክራል"**፡፡ በዚህ ጥቅል ባለው የጊዜ አመልካች ግሥ ላይ የቃላት መራቀቅ ይስተዋላል፤ (1) "ያየውን" የተጠናቀቀ ጊዜ አመልካች ነው፤ (2) " የሰማውን" የግሪኩ ተደራጊ የጊዜ አመልካች ግሥ ነው፤ (3) "ይመሰክራል" የአሁን ጊዜን አመልካች ነው፡፡ ኢየሱስ የእግዚአብሔር የመጨረሻው መገለጥ ነው (1ቆሮ 8፡6፤ ቆላ 1፡13-20፤ ዕብ1፡2-3)፡፡ እርሱም የሚናገረው (1) ከአብ ጋር ባለው የግል ልምምዱ መሠረት እና (2) ከራሱ መለኮታዊ ነት ነው፡፡

▣ **"ምሥክሩንም የሚቀበለው የለም"** ይህ የጥንት ሩቅ ምሥራቃዊያን ንግግር ነው ምክንያቱም ቁጥር 23-26 ብዙዎች ወደ እርሱ ይመጡ እንደነበር ያመለክታልና፡፡ ይህ ሐረግ የአይሁድ እምነትን በአጠቃላይ የሚያመለክት (3፡11 ን ያ) እንጂ በቅርብ ያለው ዓውድ አይደለም፡፡

**3፡33 "የተቀበለ"** የሚለው ቃል የእርሱ ያልተገደበ፣ ለሰዎች ሁሉ ያለውን ፍቅር ያሳያል። አንድ ሰው ካመነ እና ንስሐ ከገባ ለእግዚአብሔር ወንጌል እንቅፋ የሚሆን ነገር ዬለም (ማር 1፡15፤ ሐዋ 20፡21) ነገር ግን ግብዣው ለሰዎች ሁሉ ነው (1፡12፤3፡16-18፤ ሕዝ 18፡23፣ 32፤ ዮሐ 3፡16፤ 4፡42፤ 1ጢሞ 2፡4፤ ቲቶ 2፡11፤2ጴየት 3፡9፤ 1ዮሐ 2፡1፤ 4፡14)።

▣ **"ምስክሩን የተቀበለ"** ይህ የሚያሳየው እምነት የእግዚአብሔርን ድነት ለመቀበል የመጀመሪያው ውሳኔ ብቻ ሳይሆን የሕይወት ዘመን ሁሉ ደቀ መዝሙርነት ነው። በ፡12 እና 3፡16-18 ላይ የተገለጸው ለመቀበል ይህ በጣም አስፈላጊ ነው። ምሥክርነቱን በመቀበል (ቁ 33) እና በእርሱም መኖር (ቁ. 36) መካከል ያውን ሁለትዮሽ (ዲዋሊዝም) ያስተውሉ። "መቀበል" የሚለው ቃል "እምነት" እንደሚለው ቃል ሁሉ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሁለት አንድምታዎች (ትርጉሞች) አሉት።

1. ክርስቶስን በግል መከተል እና በእርሱም መኖር
2. በወንጌል ውስጥ ያሉትን እውነቶችና አስተምህሮዎችን መቀበል (ይሁን 3፡20 ን ያስ)

▣

| | |
|---|---|
| NASB፣ | **"ማህተሙን አተመ፤ እግዚአብሔር እውነት ነው ብሎ"** |
| NKJV፣ NRSV፣ | **"እግዚአብሔር እውነት እንደሆነ አረጋገጠ"** |
| TEV | **"በዚህ እግዚአብሔር እውነተኛ እንደሆነ አረጋገጠ"** |
| NJB | **"እግዚአብሔር እውነት እንደሆነ ያረጋግጣል"** |

አማኞች የግል እምነታቸውን በክርስቶስ ላይ ሲያደርጉ እግዚአብሔር ስለ ራሱ፣ ስለ አለም፣ ስለ ሰው ልጆች እና ስለ ልጁ የተናገረውን ነገር ይቀበላሉ ማለት ነው (ሮሜ 3፡4)። ይህ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ዋነኛ ጭብጥ ነው (3፡33፤ 7፡28፤ 8፡26፤ 17፡3፤ 1ዮሐ 5፡20)። ኢየሱስ እውነት ነው ምክንያቱም የመጨረሻ ግቡ አንድ እውነተኛ አምላክን መግለጽ ነው። (3፡7፣ 14፤ 19፡11)።

"አተመ" ለሚለው ግሥ (የግሪኩ ድርጊት ገላጭ አመልካች ግሥ) የሚከተለውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስን ይመለከቱ።

---

**ልዩ ርዕስ፡ ማህተም**

ማህተም በጥንት ጊዜ እነዚህን ነገሮች ለማመልከት ውሏል

1. እውነት (ዮሐ 3፡33)
2. ባለቤትነትን (ዮሐ 6፡27፤ 2ጢሞ 2፡19፤ ራዕ 7፡2-3)
3. ደንነትን ወይም ጥበቃን (ዘፍ 4፡15፤ ማቴ 27፡66፤ ሮሜ 15፡28፤ 2ቆሮ 1፡22፤ ኤፌ 1፡13፤ 4፡30)
4. የእግዚአብሔር የስጦታ ተስፋ ቃል እውነተኝነት ማረጋገጫ ምልክት ነው (ሮሜ 4፡11 እና 1ቆሮ 9፡2)

የዚህ ማህተም ጠቀሜታ የእግዚአብሔር ቁጣ እንዳያገኛቸው እግዚአብሔርን ሕዝች ለመለየት ነው። የሴጣን ምህተም የእርሱ የሆኑትን ለመለየት ሲያገለግል፤ እነዚህም የእግዚአብሔር ቁጣ የሚያርፋባቸው ናቸው። በዮሐንስ ራዕይ ውስጥ "መከራ" (ትሊፕሲስ) ያላመኑት የሚያምኑትን ሲያሳድዱ ካለው ሃሳብ ጋር ሲገናኝ ፍርድ/ቁጣ *(ኦርጅ ወይም ቱምስ)* ሁል ጊዜ የሚገናኘው ያላመኑት በኃጢአታቸው ተፀፅተው ወደ ክርስቶስ በእምነት ዘወር ይሉ ዘንድ ከእግዚአብሔር የሚመጣባቸው ፍርድ ነው። ይህ አዎንታዊ የሆነ የእግዚአብሔር ፍርድ በዘዳ 27-28 ላይ ከተገለፁት የኪዳን እርግማኖች/በረከቶች ላይ የሚታይ ነው።

"ሕያው አምላክ" የሚለው ሐረግ ያህዌህ በሚለው መጠሪያ ላይ (ዘፍ 3፡14 መዝ 42፡2፤84፡2፤ ማቴ16፡16) የተደረገ የቃላት መራቀቅ ነው፡፤ ይህ ተመሣሣይ የሆነ አጠቃቀም ብዙውን ጊዜ መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆኑ መሃላዎች ላይ የሚገኝ ነው፡- "ሕያው እግዚአብሔርን"

---

**3፡34 "እግዚአብሔር የላከው የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራልና"** በቁ 34 ላይ የኢየሱስ ስልጣን ከእግዚብሐየር እንደመጣ የሚያሳዩ ሁለት ትይዩ አረፍተ ነገሮች አሉ

1. እግዚአብሔር ያላከው
2. መንፈሱን ሰፍሮ አይሰጥምና።

▣ **"መንፈሱን ሰፍሮ አይሰጥምና"** ይህ ዓረፍተ ነገር አሉታዊ ስለሆነ በሌላ ቋንቋ የሚያነቡ ሰዎች በድንብ ላይረዱት ይችላሊ። የመንፈሱን በሙላት መስጠት በሁለት መንገድ መረዳት ይቻላል

1. ኢየሱስ ለአማኞች መንፈሱን በሙላት ይሰጣቸዋል (4፡10-14፤ 7፡37-39)
2. ይህ በሙላት የሚሰጠው ነገር እግዚአብሔር መሲሁን መስጠቱን ያመለክታል (ቁ 35)

የአይሁዳዊያን መምህራን "መስፍር" የሚለውን ቃል እግዚአብሔር ነቢቱን መላኩን ያመለክቱበታል። ከዚሀ በተጨማሪ እነዚህ መምህራን ዬትኛውም ነቢያ ሙሉ እግዚአብሔር መንፈስ እንዳልተሰጠው ይገልጻሉ። ስለዚህ ኢየሱስ ከነቢያቱ በላይ ነበር ማለት ነው (ዕብ 1፡1-2) እንዲሁም እግዚአብሔር ሙሉ መገለጥ ነው።

**3:35 "አባት ልጁን ይወዳል"** ይህ አዎንታዊ ቃል በ5:20 እና 17:23-26 ላይ ተገልጾ እናገኛለን። የአማኞች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት የተመሠረተው እርሱ ለመስሑ ባለው ፍቅር ላይ ነው (ዕብ 1:2፤ 3:5-6፤ 5:8፤ 7:28)። ሰዎች ኢየሱስ መሲሕ እንደሆነ ማመን እንዳለባቸው ብዙ ምክክንያተቶች በዚህ ቁጥር ላይ መቀመጡን ልናስተውል ይገባል።

1. ምክንያም እርሱ ከላይ ነው እንዲሁም ከሁሉም በላይ ነው (ቁ 31)
2. ምክንያቱም የድነትን ተልዕኮ አስመልክቶ ከእግዚአብሐየር ዘንድ የተላከው እርሱ ስለሆነ (ቁ 34)
3. ምክንያቱም እግዚአብሔር መንፈሱን በሙሉ ለእርሱ መስጠቱን ስለምቀጥል (ቁ 34)
4. ምክንያቱም እግዚአብሔር ስከሚወደው (ቁ 35)
5. ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር በእጁ ላይ ስላስቀመጠ (ቁ 35)

በግሪክ የተለያዩ የሰው ለልጆችን "የፍቅር" ሁኔታ የሚያመለክቱ የግሪ ቃላት አሉ። አጋፔ እና ፊሎ የሚያመሳስላቸው ነገር አለ። ሁለቱም እግዚአብሔር ለልጁ ያለውን ፍቅር ለማሳየት ውሎዋል።

1. 3:35፤ 17:23፣ 24፣ 26 - አጋፔኦ
2. 5:20- ፊሎ

ኢየሱስ ከጴጥሮስ ጋር በ21:15-17 ባደረገው ንግግር አውዳዊ ልዩነት ያለ ይመስላል። "ዓውድ፤ ዓውድ፤ ዓውድ" የሚልን ያስተውሉ። ትርጉም የሚልጠው በአውዱ እንነጂ በማብራሪያ/በመዝገበ-ቃላት አይደለምና!

▣ **"ሁሉንም በእጁ ሰጥቶታል"** ይህ ስልጣብ በሌላ አካል መሰጠቱን የሚያመለክት የአይሁዳዊያን ምሳሌያዊ አነጋገር ነው (ማትም፣ 10:28፤13:3፤ ሐዋ 4:28፤13:11)። ይህ በጣም ደስ የሚል ሀረግ እና በውስጡ ብዙ ትይዩ ናቸው (ዮሐ 13:3፤ 17:2፤ ማቴ 11:27፤ 28:28፤ ኤፌ 1:20-22፤ ቆላ 2:10፤ 1ጴጥ 3:22)።

3:36

| | |
|---|---|
| NASB፣ | **"በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤ ነገር ግን ልጁን የማይታዘዝ ሕይወትን አያይም"** |
| NKJV፣ | **"በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤ በልጁ የማያምን ግን ሕይወትን አያይም"** |
| NRSV፣ | **"በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤ ልጁን የማይታዘዝ ግን ሕይወትን አያይም"** |
| TEV | **"በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤ ልጁን የማይታዘዝ ግን ሕይወትን አያይም"** |
| NJB | **"ልጁን የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት አለው፤ በልጁ የማያምን ግን ሕይወትን አያይም"** |

ምንም አይነት ስሜታዊነት ወይም እውነተኝነት ይኑረው እምነት ከአንድ ጊዜ ውሳኔ በጣም ይለያል። (ማቴ 13:20) ይህ ማንም ኢየሱስን ሳያውቅ አብን ማወቅ እንደማይችል ያረጋግጣል (ዮሐ 12:44-50 እና 1 ዮሐ 5:10) ። ድነት ልገኝ የሚችለው ከልጁ፣ ከኢየሱስ ጋር ቀጣይነት ያለው ግንኙነት በመመስረት ብቻ ነው። (10:1-18፤ 14:6)።

ይህ አማኞች ያላቸው ግን ገና ያልተፈጸመ ነገር ነው። ነገር ግን የአሁኑን የድነት እውነታን እንጂ። አማኞች አሁን ያላቸው አንዳች ነገር ሲሆን ሙሉ በሙሉ ግን አልተፈፀመም የሆነ እና ገና የሚሆን የሚለው የሁለቱ ዘመናት ዲዋሊዝም ነው (የአሁኑ ዘመን እና ሊመጣ ያው ዘመን (1ዮሐንስ 2:17) የሚለውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስ ይመልቱ)። በ9:7 ላይ ያለውም ለድነት የዋለውም ግስ ስዋሰው የሚለውን ርዕስ ይመልከቱ።

በተጨማሪም በዚህ ጥቅል ላይ "ማመን" እና "መተዘዝ" የሚሉትን ቃላት ተቃርኖ ማየት ጠቃሚ ነው። ወንጌል እኛ የምንቀበለው ስብእና እና መልዕክት ብቻ ሳይሆን ልንኖረው የሚገባን ሕይወት ጭምር ነው (ሉቃ 6:46፤ ኤፌ2:8-10)።

▣ **"የእግዚአብሔር ቍጣ በእርሱ ላይ ይኖራል"** "ቁጣ" የሚለው ቃ በዮሐንስ ጽሑፎች ውስጥ (በራዕይ ውስጥ 5 ጊዜ ያህል ከመጠቀሱ በስተቀር) ዬለም። ይህ ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውል እና ከፍርድ ጋር ተያያዥነት ያለው ነጥብ ነው። "እምነት" "መታዘዝ" እና "ቁጣ" የሚሉ ቃላት ቀጣይነት ያላቸው ነባራዊ ሁኔታዎች ሲሆን ለወደፊት ግን ወደ ፍታሜ የሚደርስ ነው። ይህ በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ የሆነ ነገር ግን ወደ ፊት የሚፈጸም መሆኑን ያመለክታል። ስለ እግዘኢብሔር ቁጣ ሙሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንታኔ በሮሜ 1:18-3:20 ያለውን ይመልከከቱ።

*መወያያ ጥያቄዎች*

ይህ <u>ምሪትን</u> የሚሰጥ የመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻ ነው፤ ይህም ማለት ለምትደረስበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ኃላፊነት የምትወስደው አንተ እራስ ትሆናህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን ባለን ብርሃን መጠን ልንመላለስ ይገባል ማለት ነው። በስነ አፍታት ሂደት ውስጥ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ዋነኛውን ስፍራ ትይዛላችሁ። ይህንን እድል ለመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻዎች አሳልፈህ አትስጥ።

ከዚህ በታች የተጠቀሱት የመወያያ ጥያቄዎች በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ባሉት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ማሰላሰል እንድትችሉ ለማገዝ የተዘጋጁ ናቸው። የሚገድቡህ ሳይሆን የማሰላሰል ምናብን እንዲያሰፉልህ የታቀዱ ናቸው።

1. የኢየሱስ የአገልግሎቱ መጀመሪያ መልዕክቶች እንዴት ከመጥመቁ ዮሐንስ መልዕክቶች ጋር ይመሳሰላል
2. ይህ ጥምቀት ከክርስቲያኖች ጥምቀት ጋር አንድ አይነት ነውን
3. በዮሐንስ ወንጌል መጀመሪያ አከባቢ ለምን የዮሐንስ ንግግሮች አጽኖት ተሰጣቸው
4. የዮሐንስ ወንጌል ጸሓፊፊ በመጥመቁ ዮሐንስ እና በኢየሱስ መካከል ያደረገውን የንጽጽር አይነት እና ቁጠር ጻፍ

5. በቁ 33 ላይ ያለው “መቀበል” የሚለው ቃል በቁ 36 ላይ ካለው “ማመን” ከሚለው ቃል ጋር ያላቸውን ግንኙነት ግለጽ፤ በቁ 36 ላይ ያለው “አለመታዘዝ” የሚለው ቃል ከዚህ ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ግለጽ፤
6. ሰዎች ለመዳን በናዝሬቱ ኢየሱስ ማመን ብቸኛው አማራጫቸው እንዲሆነ የሚገልጽ ምክንያቶችን ግለጽ (ቁ 31-36)
7. በቁ 36 ላይ ያውን “ቁጣ” የሚለውን ቃል አሁን ጊዜ ግስን በሚያመለክት መልኩ ግለጸው፤

# ዮሐንስ 4

## የዘመናዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች አንቀጽ ክፍፍል

| UBS[4] | NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| ኢየሱስ እና ሳማራዊቷ ሴት | ሰማሪያዊቷ ሴት ከመስሐዋ ጋር ተገናኘች | ኢየሱስ እና ሰማሪያዊያን | ኢየሱስ እና ሰማሪያዊያን | ኢየሱስ በሰማሪያዊያን ዘንድ |
| 4፡1-6 | 4፡1-26 | 4፡1-6 | 4፡1-4 | 4፡1-10 |
| | | | 4፡5-6 | |
| | | 4፡7-15 | 4፡7-8 | |
| | | | 4፡9 | |
| | | | 4፡10 | |
| | | | 4፡11-12 | 4፡11-14 |
| | | | 4፡13-14 | |
| | | | 4፡15 | 4፡15-24 |
| 4፡6-16 | | 4፡16-26 | 4፡16 | |
| | | | 4፡17ሀ | |
| | | | 4፡17ለ-18 | |
| | | | 4፡19-20 | |
| | | | 4፡21-24 | |
| | | | 4፡25 | 4፡25-26 |
| | | | 4፡26 | |
| | የነጣው አዝመራ | | | |
| 4፡27-30 | 4፡27-38 | 4፡27-30 | 4፡27 | 4፡27-30 |
| | | | 4፡28-30 | 4፡31-38 |
| | | 4፡31-38 | 4፡31 | |
| | | | 4፡32 | |
| | | | 4፡33 | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | 4፡34-38 | |
| | የዓለም ሁሉ አዳኝ | | | |
| 4፡39-42 | 4፡39-42 | 4፡39-42 | 4፡39-40 | |
| | በገሊላ መልካም አቀባበል ማድረጋቸው | ኢየሱስ እና አሕዛብ | ኢየሱስ ሹሙ ልጅ መፈወሱ | ኢየሱስ በገሊላ ውስጥ |
| 4፡43-45 | 4፡43-45 | 4፡43-45 | 4፡43-45 | 4፡43-45 |
| | የታዋቂው ሰው ልጅ መፈወሱ | | | ሹሙ ልጅ መፈወሱ |
| 4፡46-54 | 4፡46-54 | 4፡46-54 | 4፡46-48 | 4፡46-53 |
| | | | 4፡49 | |
| | | | 4፡50-51 | |
| | | | 4፡54-53 | |
| | | | 4፡54 | 4፡54 |

## ሦስተኛ ዙር ንባብ

*በአንቀጽ ደረጃ የመጽሐፉ ጸሓፊ ሊያስተላልፍ የፈለገውን ሀሰባ መከተል*

ይህ ምሪትን የሚሰጥ የመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻ ነው፤ ይህም ማለት ለምትደረስበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ኃላፊነት የምትወስደው አንተ እራስ ትሆናህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን ባለን ብርሃን መጠን ልንመላለስ ይገባል ማለት ነው። በስነ አፍታት ሂደት ውስጥ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ዋነኛውን ስፍራ ትይዛላችሁ። ይህንን እድል ለመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻዎች አሳልፈህ አትስጥ።

መጽሐፉን በአንድ ጊዜ ለሁለተኛ ጊዜ አንብበህ ጨርስ። ዋና ዋና ሀሳቦችን ግለጽ እንዲሁም ዋናውን ሀሳ በአንድ አረፍተ ነገር ግለጽ።

1. የመጀመሪያውን አንቀጽ ዋና መልዕክት
2. የሁለተኛውን አንቀጽ ዋና መልዕክት
3. የሦስተኛውን አንቀጽ ዋና መልዕክት
4. ወዘተ

## ከቁ 1- 54 ላለው አውዳዊ አብርሆት

ሀ. በምዕራፍ 3 እና 4 ምክንያታዊ ውቅር አለ
   1. ሃይማኖታዊው ሰው (ኒቆዲሞስ) እና የተናቀቸው ሴት (በውሃ ቦታ ያገኛት ሴት) ንጽጽር
   2. እየሩሳሌምን ያማከል አይሁዳዊነት (ትክክለኛው) ከሰማሪያዊ አይሁድነት (ኑፋቄያዊ) ጋር ስነጻጸር

ለ. ስለ ኢየሱስ ማንነት እና ሥራ እውነተኛው ነገር ይበልጥ ስብራራ
   1. በውሃ ስፍር ከገኛት ሴት ጋር ባደረገው ውይይት (ቁ 1-26)
   2. ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ባደረገው ውይይት (ቁ 27-38)
   3. የመንደሩ ሰዎች በሰጡት ምስክርነት (ቁ 39-42)

4. የገሊላዊያን አቀባበል (ቁ 43-45)
5. ኢየሱስ በደዌ ላይ ያለው ስልጣ ምልክት/ተአምራ

***የቃላት እና የሀረግ ጥናት***

**የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 4፡1-6**
***እንግዲህ፡፡ ኢየሱስ ከዮሐንስ ይልቅ ደቀ መዛሙርት ያደርጋል ያጠምቅማል ማለትን ፈሪሳውያን እንደ ሰሙ ጌታ ባወቀ ጊዜ፡ ይሁዳን ትቶ ወደ ገሊላ ደግሞ ሄደ፤ ዳሩ ግን ደቀ መዛሙርቱ እንጂ ኢየሱስ ራሱ አላጠመቀም፡፡ በሰማርያም ሊያልፍ ግድ ሆነበት፡፡ ስለዚህ ያዕቆብ ለልጁ ለዮሴፍ በሰጠው ስፍራ አጠገብ ወደምትሆን ሲካር ወደምትባል የሰማርያ ከተማ መጣ፤ በዚያም የያዕቆብ ጕድጓድ ነበረ፡፡ ኢየሱስም መንገድ ከመሄድ ደክሞ በጕድጓድ አጠገብ እንዲህ ተቀመጠ፤ ጊዜውም ስድስት ሰዓት ያህል ነበረ፡፡***

4፡1 ***"ጌታ"*** ከአመታት በፊት ስለተከሰተው ነገር ዮሐንስ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ኢየስታወሰ "ጌታ" እና "ኢየሱስ" የሚለው ቃል ኢያስዋወጠ ይጠቀም ነበር፡፡ ሁለቱም ቃላት የሚያመለክቱት አንድን ሰው ነው፡፡
ብዙ የአዲስ ኪዳን የጥንት ቅጂዎች በቁጥር 1 ላይ ያላቸው "ኢየሱስ" የሚለውን ሲሆን ነገር ግን አንዳንድ ቅጂዎች ግን "ጌታ" የሚለው አላቸው፡፡ ምንም እንኳ "ጌታ" የሚለው ቃል በጥንት የአዲስ ኪዳን ቂጂወዎች የተጠቀሰ በሆንም ዩቢአስ የተባለው መጽሐፍ ግን ኢየሱስ የሚለው ተጠቅሟል፡፡

▣ ***"ፈሪሳዊያን"*** በ 1፡24 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

▣ ***"ኢየሱስ ከዮሐንስ ይልቅ ደቀ መዛሙርት ያደርጋል ያጠምቅማል ማለትን ፈሪሳውያን እንደ ሰሙ"*** ኢየሱስ አከባቢውን ለቆ የሄደበት ምክንያት በፈሪሳዊያን አማካኝነት በኢየሱስ ደቀ መዛሙርት እና በመጥመቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት መካከል ልነሳ ያለውን ውዝግብ አስደቅዶ በመመልከት ለማርገብ ነው፡፡ ተመሳሳይ ወንጌላት ጊን ኢየሱስ አከባቢውን ለቆ የሄደበትም ምክንያት አንቲፓስ የተባለው ሄሮድ መጥመቁ ዮሐንስ ይዜ ወደ ወይህን ስላስገባው ነው (ማቴ 4፡1፤ ማር 1፡14፤ ሉቃ 3፡20)፡፡

▣ 4፡2 ***"ኢየሱስ ራሱ አላጠመቀም"*** ይህ በጥምቀት ላይ የተሰጠ ጽኑ አስተያየት አይደለም (ማቴ 28፡19፤ ሐዋ 2፡38፤ 8፡12፤ 16፡33፤22፡16)፡፡ ነገር ግን የሰው ልጆችን ራስ ወዳድንን የሚያሰይ ነው (ይህ ማለት "እኔ በኢየሱስ ነው የተጠመቅሁት" ወይም ጳውሎስ 1 ቆሮ 1፡17)፡፡ በእርግጥ ኢየሱስ በአገልግሎቱ መጀመሪያ አከባቢ ሰዎችን ያጠምቅ ነበር (3፡22) ነገር ግን በኂላ ላይ አቁሟል፡፡ ዮሐንስ በዚህ ስፍራ ላይ የፈሪሳዊያንን የሐሰት ንግግር እያስተካከለ ነው፡፡

▣ 4፡3 ***"ይሁዳን ትቶ ወደ ገሊላ ደግሞ ሄደ"*** ይህ ሀረግ የኢየሱስን መልከዓምድራዊ እንቅስቃሴ አጽኖት የሚሰጥ ነው፡፡

4፡4 ***"በሰማርያም ሊያልፍ ግድ ሆነበት"*** "ሆነበት" የሚለው ቃል በግሪክ ዴኢ በዚህ አውድ ውስጥ ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል (3፡7፣14፣ 30)፡፡ ብዙ ጊዜ "ግዴታ" ወይም "የሚያስፈልግ" ተብሎ ይተረጎማል፡፡ በዚህ በኢየሱስ የጉዞ መንገድ ውስጥ መለኮታዊ ዓላማ ነበር፡፡ በጣም አጭር መንግድ ሲሆን ጆሴፈስ እንደሚናረው ከገሊላ የሆኑ አይሁዳዊያን ይህንን መንገድ አዘውትረው ይጠቀሙታል፡፡ ነገር ግን ከይሁዳ የሆኑት አይሁዳዊያን ግን ሰማሪያን ስለሚጠሉ የእነርሱን ሀገር አቋርጠው አይሄዱም፤ ምክንያቱም እነርሱ ሃይማኖታዊ ቅይጥነት አለባቸው ብለው ስለሚመስቡ ነው፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ ዘረኝነት**

I. *መግቢያ*
   *ሀ.* ይህ በአንድ ማህረሰብ ውስጥ ያሉ በኃጢአት የወደቁ ሰዎች ሁሉ አለማቀፋዊ መገለጫ ነው፡፡ ይህ የሰው ልጆች "እኔነት" ሲሆን በሰው ልጆች ጀርባ እራሱን ለመደገፍ ያስባል፡፡ ዘረኝነት በብዙ መልኩ የዘመናችን መገለጫ ሲሆን ሀገራዊነት ግን የጥንት የማንነት መግለጫ መንገድ ነው፡፡
   *ለ.* ሀገራዊነት የተጀመረው በባቤል (ዘፍ 11) ላይ ነው፡፡ ይህን የሰው ልጆች ሁሉ ዘር ምንጭ ከሆኑት የኖህ ሦስት ልጆች ሲሆን ከዚህም ዘር የሚባል ነገር መጣ (ዘፍ 10)፡፡ እርግጥ ነው የሰው ልጆች ሁሉ ከአንድ ምንጭ መሆናቸው እውነት ነው (ዘፍ 1-3፤ ሐዋ 17፡24-26)
   *ሐ.* ዘረኝበት ከብዙ ትምክህቶች አንዱ ነው፡፡ ሌሎች ደግሞ (1) የእውቀት ትምክህት (2) ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ኩራት (3) ራስን ብቻ የሚያፅድቅ ኃይማኖታዊ ወግ አትባቂነት እና (4) ትምክህትን የተሞሉ ፕለቲካዊ ትስስሮች ናቸው፡፡
II. *መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃዎች*
   *ሀ.* ብሉይ ኪዳን
      1. ዘፍ 1፡27- የሰው ልጆች ሁሉ፤ ወንድ እና ሴት፤ በእግዚብሔት መልክ እና ምሳሌ ተፈጥረዋል፣ ይህም እነርሱን ከሌሎች ነገሮች ሁሉ ልዩ ያደርጋቸዋል፡፡ ይህ ግላዊ ጠቀሜታቸውን እና ክብራቸውን ያሳያል

(ዮሐ 3፡16)፡፡

2. ዘፍ 1፡11-25- “እንደ ወገኑ . . . “ የሚል ቃል ዐስር ጊዜ ሰፍሮ እናገኛለን፡፡ ይህ ብዙ ጊዜ የዘር ልዩነትን የሚደግፍ ሀሳብ እንደሆነ ብዙ ጊዜ ስነገር ይሰማል፡፡ ነገር ግን ከአውዱ እንደሚንመለከተው ይህ የሚያመለክተው የእጽዋትን እና የእንስሳትን ልዩነት እንጂ የሰው ልጆችን እንዳሊሆን መረዳት ይቻላል፡፡
3. ዘፍ 9፡18-27- ይህ የዘር የበላይነት ለመደገፍ ሰዎች ስጠቀሙበት ይስተዋላል፡፡ ማስታወስ የሚገባን እግዚአብሔር ከነዓንን አልረገመውም፡፡ ኖህ ከስካሩ ከነቃ በኋላ 孌ልጁን ልጅ ረግሞታል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ይህን እርግማን እግዚአብሔር እንዳጸደቀው በዬትም ስፍራ ለይ አንመለከትም፡፡ እግዚአብሔር ይህንን አድርጎታል ብባ እንኳ ይህ እርግማን ጥቁር ሕዝቦችን ጋር ምንም ግንኙነት ዬለውም፡፡ ከነዓን የፍልስጤም ምድር ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች አባት ነው እንዲሁም በግብጽ የግድግዳ ስእሎች ላይ የሚንመለከታቸው ስእሎች እንደሚያመለክቱት እነዚህ ሰዎች ጥቁሮች አይደሉም፡፡
4. ኢሳ 9፡23- ይህ ቁጥር አንድ ዘር ከሌላው እንደሚበልጥ የሚደግፍ ሀሳብ ተደርጎ ይወሰድ ነበር፡፡ ነገር ግን ከአውዱ እንደሚንረዳው ጋቦናዊያን እንደ ሌሎች አይሁዳዊያን ሁሉ የአይሁድ ዘር ናቸው፡፡
5. ዕዝ 9-10 እና ነህ 13- ይህም ክፍል ከዘር ጋር ተያይዞ ብዙ ጊዜ ይነሳል- ነገር ግን አውዱ ግልጽ እንደሚያደርገው ጋብቻ የተከለከለው በዘር ምክንያት ሳይሆን በሃይማኖት ምክንያት ነው፡፡

ለ. አዲስ ኪዳን

1. ወንጌላት
   ሀ. ኢየሱስ ብዙ ጊዜ በአይሁዳዊያን እና በሰማሪያዊን መካከል ያለው ጥላቻ ትክክል አለመሆኑን የሚያመለክቱ ብዙ ነገሮችን አድርጓል
      1) የመልካሙ ሳምራዊ ምሳሌ (ሉቃ 10፡25-37)
      2) በውሃ ጉድጓድ አጠገቢ ያዋራት ሴትዮ (ዮሐ 4)
      3) አመስጋኙ ለምጻም (ሉቃ 17፡7-19)
   ለ. ወንጌል ለሰው ልጆች ሁሉ መሆኑ
      1) ዮሐ 3፡16
      2) ሉቃ 24፡46-47
      3) ዕብ 2፡9
      4) ራዕ 14፡6
   ሐ. የእግዚአብሔር መንግስት ሰዎችን ሁሉ የሚያካትት ነው
      1) ሉቃ 13፡29
      2) ራዕ 5
2. ሐዋርያት ሥራ
   ሀ. ሐዋ 10 የእግዚአብሔር አለማቀፋዊ ፍቅር እና የወንጌል አለማቀፋዊ መልዕክትነት መገለጫ ክፍል ነው፡፡
   ለ. ጴጥሮስ በምዕ 11 ላይ ስላሳየው ባህርይ ተግሳጽን ተቀብሏል እንዲሁም ይህ ችግር በምዕ 15 ላይ በተደረገው የኢየሩሳሌም ጉባኤ እስክፈታ ድረስ ቀጥሎ ነበር፡፡ በመጀመሪያው ምእተ አመት ይኖሩ የነበሩ አይሁዳዊያን እና አሕዛብ መካከል ያለው ውጥረት እጅግ የከፋ ነበር፡፡
3. ጳውሎስ
   ሀ. በክርስቶስ ምንም አይነት የልዩነት ግድግዳ ዬለም
      1. ገላ 3፡26-28
      2. ኤፌ 211-22
      3. ቆላ 3፡11
   ለ. እግዚአብሔር ሰዎችን አይለም
      1. ሮሜ 2፡11
      2. ኤፌ 6፡9
4. ጴጥሮስ እና ያዕቆብ
   ሀ. እግዚአብሔር ሰዎችን አይለም 1 ጳየት 1፡17
   ለ. እግዚአብሔር ፊት አይቶ እንደማያዳላ ሁሉ እኛም የእርሱ ሕዝብ እንደመሆናችን እንዲሁ ልናደረግ ይገባል ያዕ 2፡1
5. ዮሐንስ
   ሀ. የአማኞች አንዱ እና ትልቁ ኃላፊነት በ1 ዮሐ 4፡20 ላይ ተገልጸዋል፡፡

III. ማጠቃለያ

ሀ. ዘረኝነት፣ እንዲያውም ማንኛወውም አይነት መድሎ ከእግዚአብሔር ልጆች የሚጠበቅ ነገር አይደለም፡፡ በዚህ ሥፍራ ላይ የክርስትያንን የሕይወት ተልእኮ በሚመለከት ሄንሊ ባርኔት በግሎሬታ ኒው ሜክሲኮ ፎረም ካደረጉት ንግግር (1964) የተወሰደ ጥቅስ አለ፤

“ዘረኝነት ሳይንሳዊ አለመሆኑን መግለፅ ባይቻልም ኑፋቄ ነው ምክንያቱም ህ መፅሐፍ ቅዱሳዊም ሆነ ክርስትያናዊም አይደለምና፡፡”

ለ. እንዲህ አይነቱ ችግር ለክርስቲያኖች ክርስቶስን የሚመስል ፍቅር፣ ይቅርታ እና መረዳተ ለጠፋው አለም መስጠት የሚችሉበትን መንገድ ያመቻችላቸዋል። በዚህ መልኩ ነገሮችን መከወን የተሳነው ክርስቲያን አለመብሰለን ያሳያል እንዲሁም የአማኖችን እምነት፣ መተማመኛ እና እድገት ይሸረሽራል። ከዚህ በተጨማር ሰዎች ወደ ክርስቶስ እንዳይመጡ እንቅፋት ይሆንባዋል።

ሐ. ምን ማድረግ እችላለሁ;

በግልህ

- ★ ከዘር ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ችግሮች ለመፍታት የራስህን ድርሻ ተወጣ
- ★ በዘር ከአንተ ከተለዩ ሰዎች ጋር ጸሎት፣ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እና ህብረት በማድርግ ከዘረኝነት የጸዳ ሕይወት ለመኖር ተጣጣር።
- ★ የዘር ልዩነትን የሚያባሱ ሰዎች ጋር ያለህን አቋም ግለጽ።

በቤተሰብ ሕይወትህ

- ★ ስለ ሌሎች ዘሮች ስለሚኖርህ አመለካከት የቤተሰብ አመለካከት ተጽእኖ እንደሚፈጥር አስተውል
- ★ ወላጆች ከሌሎች ዘሮች ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት ክርስቲያናዊ ምሳሌ ለመሆን በጥንቃቄ ነገሮችን መከወን አለባቸው።
- ★ የቤተሰቡን ጓደኞች ምርጫ ላይ የተለያዩ ዘር ያላቸው ሰዎችን ማከተት

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ

- ★ ስለ ዘር መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነትን በማስተማር እና በመስበክ ማህበረ ምዕመኑ ለማህበረሰቡ ምሳሌ የሚሆን ነገርን እንዲያደረግ መገፋፋት
- ★ አምልኮ፣ ህበረት እና የተለያዩ አገልግሎቶች ለሁሉ ሰዎች ክፍት መሆናቸውን ማረጋገጥ

በዕለት ተእለት ኑሮ ውስጥ

- ★ በሥራ ዓለም ውስጥ የዘር ልዩነቶችን እንዳይኖሩ የበኩሎን ጥረት መወጣት
- ★ ለሰው ልጆች እኩል መብት እና እድል እንዲኖር በሚያደርጉ በሁሉም የማበረሰብ አገልግሎቶች ውስጥ መሳተፍ፤ አስተውሉ ልወገድ የሚገባው የዘር ችግር እንጂ ሰዎቹ አይደሉም። አላመው ትክክለኛ መረዳን ማዳበር እንጂ ቅም በቀለን ለመፍጠር አይደለም።
- ★ በዘር እኩልነት ላይ የሚወጡ አዋጆችን እና ሕግጋቶችን እንድጸድቁ ድጋፍ መስጠጥ እንዲሁም ለፖለቲካ ጥቅም ስባል የዘር ልዩነትን የሚጠቀሙትን መቃወም። የጋራ ሕግጋት በእኩልነት ተፈጻሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣ በሰው ልጆች ሁሉ ውስጥ የክርስቶስን አመለካከት እና መንፈስ የሞላት ግንኙነት እንዲኖር መጣር።

▣ **"በሰማሪያ"** ከስምንተኛው አመተ ዓም አንስቶ በሰማሪያዊያን እና በአይሁዳዊያን መካከለ ትልቅ ጥላቻ ነበር። በ722 ዓዓ የሰሜኑ የእስራኤል መንግስት ከዐሥሩ ነገዶች ጋር፤ ከዋና ከተማቸው ጋር በአሶራዊያን እጅ ወደቀ (2 ነገ 17፡6)። ሌሎች የተማረኩ ሕዝቦች በሰሜን ፍልስጤም ውስጥ እንዲሰፍሩ ተደደረገ (2 ነገ 17፡24)። እነዚህ አሕዛቦች በፍልስጤም ውስጥ ከቀሩ አይሁዳዊያን ጋር እርስ በእርስ እየተጋቡ ቆዩ። አይሁዳዊያን ሰማሪያዊያን ሃይማኖተዊ ዲቃላ እና ኑፋቄዎች እንደሆኑ ይቆጥሯቸዋል። ይህ ለቁ.9 ትክክለኛ አውድ ይሰጠናል።

▣ 4፡5 **"ሲካር ወደምትባል የሰማርያ ከተማ መጣ"** (ዘፍ 33፡18፣ 19፤ ኢሳ 24፡32)። ምንም እንኳ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ባይጠቀስም ብዙ ሰዎች ሲካር ሼክም እንደሆነ ያስባሉ።

▣ 4፡6 **"በዚያም የያዕቆብ ጉድጓድ ነበረ"** ይህ ወደ 100 ጫማ የሚጠጋ ጥልቀት ያለው ጉድገዋድ ነው። ይህ የወራጂ ውሃ ሳይሆን የተጠራቀመ የዝናብ ውሃ ነው። ይህ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተጠቀሰ ስፍራ አይደለም ነገር ግን በአባቶች ትውፊት የተጠቀሰውን ይመስላል።

▣ **"ኢየሱስም መንገድ ከመሄድ ደክሞ"** በዚህ ስፍራ የኢየሱስን ሰዋዊ ተፍጥሮን እንመለከታለን (ሉቃ 2፡52) ነገር ግን ሰዎችን ለመውደድ ግን አልደከመም ነበር።

▣

ኤንኤሲቢ፣ NKJV፣
ጀቢ — **"ጊዜውም ስድስት ሰዓት ያህል ነበረ"**
NRSV፣ TEV — **"ከሰዓት ነበር"**

የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 4፡7-14

**"ከሰማርያ አንዲት ሴት ውኃ ልትቀዳ መጣች። ኢየሱስም፦ ውኃ አጠጪኝ አላት፤ ደቀ መዛሙርቱ ምግብ ሊገዙ ወደ ከተማ ሄደው ነበርና። ስለዚህ ሳምራዊቲቱ። አንተ የይሁዳ ሰው ስትሆን ሳምራዊት ሴት ከምሆን ከእኔ መጠጥ እንዴት ትለምናለህ? አለችው፤ አይሁድ ከሳምራውያን ጋር አይተባበሩም ነበርና። ኢየሱስ መልሶ፦ የእግዚአብሔርን ስጦታና። ውኃ አጠጪኝ የሚልሽ ማን መሆኑንስ ብታውቂ: አንቺ ትለምኚው ነበርሽ የሕይወትም ውኃ ይሰጥሽ ነበር አላት።**

**ሴቲቱ። ጌታ ሆይ: መቅጃ የለህም ጕድጓዱም ጥልቅ ነው፤ እንግዲህ የሕይወት ውኃ ከወዴት ታገኛለህ? በእውኑ አንተ ይህን ጕድጓድ ከሰጠን ከአባታችን ከያዕቆብ ትበልጣለህን? ራሱም ልጆቹም ከብቶቹም ከዚህ ጠጥተዋል አለችው። ኢየሱስም መልሶ፦ ከዚህ ውኃ የሚጠጣ ሁሉ እንደ ገና ይጠማል፤ እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም አይጠማም: እኔ የምሰጠው ውኃ በእርሱ ውስጥ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆናል እንጂ አላት።**

4:7 **"ከሰማርያ አንዲት ሴት . . . መጣች"** ይህች ሴት በቀኑ ባልተለመደ ሰአት ረጅም ርቀት ተጉዛ ነው የመጣችው ምክንያቱም በመንደሩ ውስጥ በማህበረሰቡ ዘንድ ባላት ቦታ የተነሳ ነው።

▣ **"'ውኃ አጠጪኝ"** ይህ የግሪኩ ትእዛዝ አዛል ድርጊት ገላጭ ግሥ ሲሆን የአስችኳይነትን ድባብ የያዘ አባባል ነው።

4:8 ይህ ቁጥር ኢየሱስ በግሉ አይሁዳዊያን ኑፋቄያዊያን ብለው ከሚጠሩዋቸው ሰዎች ጋር ያደረገውን የግል ውይይት ያሳያል። ይህ በዮሐንስ የተሰጠ ማስታወሻ ነው።

4:9 **"አንተ የይሁዳ ሰው ስትሆን ሳምራዊት ሴት ከምሆን ከእኔ መጠጥ እንዴት ትለምናለህ?"** አይሁዳዊያን ሰማሪሪያዊያን ከተጡበት ጉድጓድዳኃ መጠጣት እንኳ አይፈቀድላቸው እንኳን አብረው ለማውራት ይቅርና። (ዘለ 15)። ኢየሱስ ሁለት ባህላዊ ግድግዳዎችን አስወግዷል (1) ከሰማሪያዊ ጋር ማውራትን (2) ሴት ልጅን በአደባባይ ማውራት

▣ **"(አይሁድ ከሳምራውያን ጋር አይተባበሩም ነበርና።)"** የተሰጠው ቅንፍ (NASB፣ NRSV) ከዮሐንስ የተሰጠ ሌላ የማብራሪያ ጭማሪ ሲሆን በMSSℵ* እና D ምንጮች ውስጥ ባይጠቀስም በP63፣66፣75፣76፣ A፣B፣C፣L ምንጮች ውስጥ ግን ተጠቅሷል። በመሆኑም የዩ.ቢ.ኤስ 4ኛ ትርጉም ለመካተቱ የ"A" ደረጃን ይሰጠዋል (እርግጠኛ የሆነ)።

4:10 **"ብ. . . "** ይህ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ አረፍተ ነገር ሲሆን ይህም "'ከእምነታዊ የሚቃረን" ሊባል ይችላል። ሐሰት የሆነን ማጠቃለያ ማስረገጥ የሚደረግ ንግግር ራሱ ሐሰት ነው።

ይህ *"ሥጦታ"* የሚለው ቃል በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የሚገኝ ብቸኛ ቃል ነው። በዚህ ቦታ የተጠቀሰው ኢየሱስ የተዘላለምን ሕይወት የሚሰጥ የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑን (3:16ን የስ) ለማመለክት ነው። በዮሐንስ 7:38-39 እና በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የመንፈስ ቅሱስን መስጠት ለማመለክት ተጠቅሷል (ሐዋ 2:38፤8:20፤10:45፤11:17) ትኩረቱ ግን በክርስቶስ እና በመንፈስ ቅዱስ የተገለጠውን የማይገባ እና ወሰን የሌለውን የእግዚአብሔርን ፀጋ ለማመልከት ነው።

▣ **"የሕይወት ውሃ"** ይህ ቃል የብሉይ ኪዳን ዘይባዊ አነጋገር ዳራ አለው መዝ 36:9፤ ኢሳ 12:3፤ 44:3፤ ኤር 2:13፤ 17:13፤ ዘካ 14:8 ያነጻጽሩ)። ኢየሱስ የ"ሕይወት ውሃ" የሚለው ቃል ከ"መንፈሳዊ ሕይወት" ጋር ተለዋዋጭ ቃል አድርጎ ተጠቅሞታል። ነገር ግን በሰማሪያ ያገኛት ሴት ግን እርሱ እያመለከተ ያለው ከተጠራቀመው ውሃ ይልቅ ወራጅ ውሃን መስሎዋታል። ይህ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ኢየሱስ (ዓለም ብርሃን) የሆነው ብዙ ጊዜ ሰዎች በትክክል እንደልተረዱት መሳየት አንዱ የመጽሐፉ ባሕርይ ነው። ምድራዊው፣ ይህ የወደቀው ማንነት ሰማያዊውን ዓለም መረዳት አይችልም።

4:11 **"ጌታዬ ሆይ"** ይህ ኩሪዮስ የተሰኘ ቃል የተጠቀመበት ነው። ይህ ሁለት ትርጉሞች ሲኖሩት አንደኛው በትህትና አንድ ሰውን መጥራት ሊሆን ስችል ሌላኛው ደግሞ ሥነ መለኮታዊ ትርጓሜ ኖሮት የኢየሱስን ፍጹም አምላክነት በቁጥር 1 እና በሮሜ 10:13 ላይ እንዳለው ማሳየት ነው። በዚህ ስፍራ ላይ ትህትናን የሚያሳይ ይመስላል።

4:12 **"በእውኑ አንተ ይህን ጕድጓድ ከሰጠን ከአባታችን ከያዕቆብ ትበልጣለህን?"** ይህ ሰዋሰዋዊ ቀመር የሚብቀው ምላሽ "አይ" የሚል ነው። ይህ ግልጽ የሆነ ምጸታዊ አረፍተ ነገር ነው። ሰማሪያዊቷ ሴት የዘር ሀረግ ሰማሪያዊያን በኤፍሬም እና ሜናሴ በኩል ወደ እስከ ያቆብ እንደሞቶጥሩ አሳይታዋለች። የሚያስገርመው ነገር ኢየሱስ ብልጫ ልክ እንደተናገረው መሆኑ ነው።

ይህ ንግግር ሁለት ሥነ መለኮታው ጉዳዮችን ይዳስሳል

1. የእግዚአብሔር/ኢየሱስ የተጣሉት መውደድ (ሰማሪያዊያንን፣ ሴቶችን)
2. ኢየሱስ ከአይሁዳዊነት እና የዘር ትምክት እንደሚበልጥ

4:13-14 **"እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም አይጠማም"** ይህ ምሳሌያዊ ንግግር መሲሕያዊ ነው (ኢሳ 12:3፤ 48:21፤ 49:10)። ይህ ሀረግ ሁለትዮሽ አሉታዊ ሲሆን በግስ ጫወታ ነው። ቁጥር 13 ደጋግሞ መጠጣትን የሚያመለክት ሲሆን ቁ. 14 አንድ ጊዜ መጠጣትን ያሳያል።

4:14 **"ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ"** ይህ ማለት ያለማቋረጥ መፍለቅ ነው (ኢሳ 58:11 እና ዮሐ 7:18)። በበረሃ ለምኖሩ ሰዎች ውሃ የሕይወት እና የመለኮታዊ አቅራቦት ምልክት ነው።

**የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ: 4:16-26**
**ሴቲቱ። ጌታ ሆይ: እንዳልጠማ ውኃም ልቀዳ ወደዚህ እንዳልመጣ ይህን ውኃ ስጠኝ አለችው። ኢየሱስም፦ ሂጂና ባልሽን**

**ጠርተሽ ወደዚህ ነዪ አላት።ሴቲቱ መልሳ። ባል የለኝም አለችው። ኢየሱስ፦ ባል የለኝም በማለትሽ መልካም ተናገርሽ፤አምስት ባሎች ነበሩሽና: አሁን ከአንቺ ጋር ያለው ባልሽ አይደለም፤ በዚህስ እውነት ተናገርሽ አላት። ሴቲቱ። ጌታ ሆይ: አንተ ነቢይ እንደ ሆንህ አያለሁ።አባቶቻችን በዚህ ተራራ ሰገዱ፤ እናንተም። ሰው ሊሰግድበት የሚገባው ስፍራ በኢየሩሳሌም ነው ትላላችሁ አለችው።ኢየሱስም እንዲህ አላት፦ አንቺ ሴት: እመኚኝ: በዚህ ተራራ ወይም በኢየሩሳሌም ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል። እናንተስ ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ፤ እኛ መዳን ከአይሁድ ነውና ለምናውቀው እንሰግዳለን።ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኖአል፤ አብ ሊሰግዱለት እንደ እነዚህ ያሉትን ይሻልና፤እግዚአብሔር መንፈስ ነው: የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።ሴቲቱ። ክርስቶስ የሚባል መሲሕ እንዲመጣ አውቃለሁ፤ እርሱ ሲመጣ ሁሉን ይነግረናል አለችው።ኢየሱስ፦ የምናገርሽ እኔ እርሱ ነኝ አላት።**

4፡15 ይህች ሴት እንደ ኒቆዲሞስ ሁሉ ኢየሱስን የተረዳቸው በአካላዊ ገጽታው ነበር። ይህ ለደቀ መዛሙርቱም ቢሆን እውነት ነበር። ብዙ ጊዜ የእርሱን ዘይቤያዊ አነጋገሮችን በትክክል አይረዱም ነበር (ዮሐ 4፡31-33፤ 11፡11-13)

4፡16 የዩ-ቢ-ኤስ[4] ትርጉም ግን "ኢየሱ" የሚለው መጠሪያ ለመጨመር ያውን እድል ኤገልፅም (ኤን-ኬ-ጄ-ቪ፣ኤን-አር-ኤስ.ቪ፣NJB፣REB)። የNET ስሙን ለማካተቱ ማስረጃን ይጠቅሳል (ገጽ 1903፤ ማለትም MSSN*,c፣A፣C[2]፣D፣L እና W፣ ነገር ግን ስሙ ከMSSP[66]፣75፣B፣C፣ ላይ ተገድፏል)። ፀሐፊዎችም ጥቅሱን ግልፅና ለመከተል ቀለል እንዲሆንም ጥረት አድርገዋል።

▣ **"ሂጂና ጥሪ"** ይህ የግሪኩ ትእዛዝ አዘል ድርጊት ገላጭ ግሥ የሚከተለው የአሁን ጊዜ ትዕዛዝ አዘል ድርጊት ገላጭ ግሥ ነው።

4፡17 **"ባል የለኝም አለችው"** ኃጢአት በአግባቡ መታየት አለበት። ኢየሱስ አይደብቅም እንዲሁም አይፈርድም ነበር።

4፡18 **"አምስት ባሎች ነበሩሽ"** ኢየሱስ ሴትቱን ከቁሳዊ ዓለም ወደ መንፈሳዊ ዓለም ለማዘዋወር ልዕለ ተፈጥሮአዊ እውቀቱን ተጠቅሟል። (1፡ 48 ጋር ያነጻጽሩ)

4፡19 **"ነብይ እንደሆንህ አያለሁ"** ሴትቱ መሲሁን ወደ መረዳት አልመጣችም። ስለ እግዚአብሔር ያላትን መረዳት ከዚህ ጋር በማጣጣም እየሞከረች ነበር። ዋናውን ሐሳብ እየነካካች... (ልክ በ3፡2 ላይ ኒቆዲሞስ እንዳደረገው)።

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ መፍቻ ጸሓፊት ይህንን የሴትቱን ሀሳብ ከዘዳ 18፡ 15-22 ጋር በማያያዝ መሲሁን ለማመልከቻነት ይጠቀሙበታል።

**ልዩ ርዕስ፡ ብሉይ ኪዳን ትንቢት**

I. *መግቢያ*
   *ሀ. መክፈቻ ሀሳብ*
   1. የእመነት ማህበረሰብ እንዴት ትንብቶች መፈታት እንደሚገባቸው ስምምን ዬለም። ሌሎች እውነቶች በዘመናት ውስጥ ትክክለኛ የሆነ አቋም ስንይዝ በዚህ ጉዳይ ላይ ግን መያዝ አልቻልንም።
   2. በብሉይ ኪዳን ምንባባት ላይ በጣም ግልጽ የሆኑ ደረጃዎች አሉ።
      *ሀ.* ከነገሥታት በፊት
         1) ግለሰቦች ነብያት ተብለው ተጠርተዋል
            ሀ. አብረሃም - ዘፍ 20፡7
            ለ. ሙሴ - ዘኑ 12፡6-8፤ ዘዳ 18፡15፤ 34፡10
            ሐ. አሮን- ዘጸ 7፡1 (የሙሴ አፍ)
            መ. መሪማ- ዘጸ 15፡20
            ሠ. ሜዳድ እና ኤልዳድ ዘኑ 11፡24-30
            ረ. ዲቦራ- መሳ 4፡4
            ሰ. ስሙ ያልተጠቀሰ- መሳ 6፡7-10
            ሽ. ሳሙ 1ሳሙ 3፡20
         2) ነብያትን እንደ አንድ ወገን ለመጥቀስ-ዘፍ13፡1-5፤18፡20-22
         3) የነብያት ወገን ወይም ማህበር-1ሳሙ 10፡5-13፤19፡20፤ 1ነገ20፡35፡41፤22፡6፡10-13፤2 ነገ 2፡3፡7፤4፡1፡38፤5፡22፤6፡1፤ ወዘተ።
         4) መሲሑ ነብይ ተብሎ ተጠርቷል፦ ዘዳ 18፡15-18
      ለ. ነገስታት ሆነው ከ      በፊት
         (1) ጋድ- 1ሳሙ 22፡5፤ 2 ሳሙ 24፡11፤ 1ዜና 29፡29
         (2) ናታን- 2 ሳሙ 7፡2፤ 1ነገ 1፡23

(3) አኪ.ያ- 1 ነገ 11፡19
(4) ኤሁ- 1ነገ 16፡1፣ 7፣ 12
(5) ስሙ ያልተጠቀሰ- 1 ነገ 18፡4፣ 13፣ 20፡13፣ 22
(6) ኤልያስ- 1 ነገ 18- 2 ነገ 2
(7) ሚልክያስ - ነገ 22
(8) ኤልሳ- 2 ነገ 2፡8፣ 13

ሐ. የሚፅፉ ነብያት (ለሕዝቡም ሆነ ለንጉሱ መልዕክትን የሚያመጡ)፤ ኢሳያስ-ሚልኪያስ (ከዳንኤል በስተቀር)

ለ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት

1. ሮሃ: "ተመልካች" 1 ሳሙ 9፡9፡፡ በዚህ ጥቅስው እንኳ ስንመለከት ትርጓሜው ነብይ የሚል ነው፡፡ ሮሃ የሚለው ቃል የመጣው አየ ከሚል ቃል ነው፡፡ እንዲህ ያለው ሰው የእግዚብሔርን መንግድ የሚመለከት እና የሚያቅድ እንዲሁም በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ እግዘአብሔርን መንገድ እንዲያረጋግጥ የሚጠየቅ ሰው ነው፡፡
2. ሆዜሃ: "ተመልካች" 2 ሳሙ 24፡11፡፡ በመሠረታዊ ሀሳቡ ከሮሃ ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡ የ"ማየት" ያለልተለመደ ቃል ነው፡፡
3. ናቢ: "ነቢይ" ማለት ነው፡፡ ይህ ቃል ከአካዲያን ናቡ: "መጥራት" ጋር ተመሳሳይ ሲሆን እንዲሁም ከአረብ ናባአ : "መናር" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ይህ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ነቢይን ለማመልከት በብዛት የዋ ቃል ነው፡፡ ወደ 300 ያህል አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ የዚህ ቃል ትክክለኛ ሥረወ ግንድ አይታወቅም ነገር ግን "መጥራት" የሚለው ቃል ለሁን የተሸለ ይመስላል፡፡ለዚህ ነገር ጥሩ ምሳሌ የሚሆን ሙሴ በአሮን አማካኝነት ለሙሴ የሆነውን ነው (ዘጸ 4፡1–16፤ 7፡1፤ ዘጸ 7፡1፤ ዘዳ 5፡5፡፡ ነቢይ ለሕዝቡ እግዚአብሔርን ወክሎ የሚናገር ሰው ነው (አሞ 3፡8፤ ኤር 1፡7፣ 17፤ ሕዝ 3፡4)
4. ሦስቱም ቃላት ነ1 ዜና 29፡29፤ሳሙኤል- ሮሃ፤ ናታን- ናቢ እና ጋድ ሆዙሃ ነቢይን የሚያመለክቱ ቃላት ናቸው፡፡
5. ኢሽ ሃ ኤሎሂም- የሚለው ሀረግ "የእግዚአብሔር ሰው" ማለት ሲሆን ቃሉን ሰፋ አድርገን ስንመለከት እግዚአብሔርን ወክሎ የሚናገር ሰው ማለት ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ይህ ሀረግ 76 ጊዜ አገልግሎት ላይ "ነቢይን" ለማመልከት ውሏል፡፡
6. "ነቢይ" የሚለው ቃል በመጀመሪያ የግሪክ ቃል ሲሆን ይህ ቃል የመጣው (1) ፒሮ : "ቀዳሚ" ወይም በፊት ማለት ነው እንዲሁም (2) ፊሚ : ‹መናገር" ማለት ነው፡፡

II. የትንቢት ትርጓሜ

ሀ. "ትንቢት" የሚለው ቃል ከአማሪኛ ይልቅ በእብራይስጥ ቋንቋ ሰፊ ትርጉም አለው፡፡ ከኢያሱ መጽሐፍ ጀምሮ እና ነገስት መጽሐፍ ድረስ ከሩት መጽሐፍ በስተቀር በአይሁዳዊያን "ቀደምት ነቢያት" ተብሎ ይጠራል፡፡ አብረሃም (ዘፍ 20፡7፣ መዝ 105፡5) እና ሙሴ (ዘዳ 18፡18) ነቢያት ተብለው ተጠርተዋል (መሪማ ዘጸ 15፡20)፡፡

ለ. "ትንቢታዊነት በመለኮታዊ ዕይታ፣ በመለኮት ዓላማ፣ በመለኮት ተሳትፎ ታርክ መረዳት ትርጓሜ ካለው ተቀባይነት ያለው ትርጓሜ ይሆናል" INterpreter's DictioNary of the Bible, vol 3, p.896.

ሐ. "ነቢይ ፈላስፋ ወይም የሥነ መለኮት ምሁርም አይደለም ነገር ግን አሁን ያሉብትን ሁኔታ እንዲገነዘቡ እ እንዲያስተካክሉ በማድረግ የወደፊቱን ሁኔታ ማስተካከል እንዲችሉ የእግዚአብሔርን ቃል ለህዝቡ የሚያቀብል የቃል ኪዳን መካከለኛ ነው" "Prophets aNd Phrphecy," Encyclopedia Judaica Vol. 13p. 1152

III. የትንቢት ጠቀሜታ

ሀ. ትንቢት እግዚብሔር ለሕዝቡ የሚናገርበት፣ ምሪትን የሚሰጥበት እንዲሁም ሕይወትን እና የዓማችን እያንዳንዷ ነገር እንደሚቆጣጠር በማሳየት ተስፋ የሚሰጥበት መንገድ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ መልዕክታቸው የጋራ ነው፡፡ ለመገሰጽ፣ ለማበረታታት፣ እምነትን ለማጽነት እና ለንሰሐ እንዲሁም ለእግዚአብሔር ሕዝብ ስለ እግዚአብሔር ማንነት እና ዕቅድ ለመነገር የታለመ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከእግዚብሔር ጋር በገባው ቃል ኪዳን መሠረት ጸንቶ እንድቆም ያደርጉታል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ መነሳት ያለበት እግዚአብሔር እርሱን ወክለው የሚናገሩ ሰዎችን ይመርጣል (ዘዳ 13፡1-3፤ 18፡20-22)፡፡ ይህ በመጨረሻ የሚወስደን ወደ መስሑ ነው፡፡

ለ. ብዙ ጊዜ ነቢያት አንድን በዘመናቸውን ያለን ታሪካዊ ወይም ስነ መለኮታዊ ችግርን በመውሰድ ወደ መጨረሻው ዘመን ይለጥጡታል፡፡ ይህ በመጨረሻው ዘመን እይታ ታርክን መመልከት በእስራኤል ዘንድ የነበረ ልዩ ነገር ነው እንዲሁም የመለኮታዊ ምርጫ እና ቃል ኪዳንን የተስፋ ቃልን በውስጡ የያዘ ነው፡፡

ሐ. የነቢያት ቢሮ (ኤር 18፡18) የእግዚአብሔርን ፍቃድ ለማወቅ የሊቀ ካህኑን ብሮ ሚዛናዊነት ለመጠበቅ እና ለማገዝ ነው፡፡ ዩሪም ተመም ከእግዚአብሔር ወክል ከሚነገር የቃል ንግግር ይበልጣል፡፡ ከሚልክያስ በኋላ የነቢያት ቢሮ ቆሟል፡፡ ይህ ቢሮ መጥመቁ ዮሐንስ እስከ መጣበት ጊዜ ድረስ ለ400 አመታት አልታየም፡፡ የአዲስ ኪዳን የትንቢት ስጦታ ከከብሉይ ኪዳን ነቢያት ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ግልጽ አይደለም፡፡ የአዲስ ኪዳን ነቢያት (ሐዋ 11፡27-28፤ 13፡1፤ 14፡29፣ 32፣ 37፤ 15፡32፤ 1ቆሮ 12፡10፣ 28-29፤ ኤፍ 4፡11) አዲስ መገለጥን ወይም መጽሐፍትን የሚሰጡን አይደሉም ነገር ግን ነባራዊ ሁኔታውን የሚያሳውቁን እና አስፈላጊ ሆኖ ስገኝ የወደፊቱን የሚነግሩን ናቸው፡፡

መ. ትንቢት በዋነኝነት መጭውን ጊዜ መናገር አይደለም፡፡ የእርሱን ቢሮ እና መልዕክት ማረጋገጫ አንዱ መንገድ

ነው ነገር ግን አንድ ልንገነዘበው የሚገባን ነገር በብሉይ ኪዳን ውስጥ ካሉ ትንቢቶች መካከል 2% ብቻ መሲሁን የሚመለከት ነበር፡፡ ከ5% በታች ስለ አዲሱ የቃል ኪዳን ዘመን የሚያወራ ነበር፡፡ ከ1% በታች ያለው ደግሞ ለወዲፊት ስለሚመጣው ነገር የሚያወሳ ነው፡፡

ሠ. ነቢያት በሰዎች ፊት የእግዚአብሔር ወኪል ሲሆኑ ካህናት ደግሞ በእግዚብሔር ፊት የሰዎች ወኪሎች ናቸው፡፡ ይህ አጠቃላይ ሀሳቡ ነው፡፡ ነገር ግን እን ዕንባቆም ያሉ እግዚብሔርን የሚጠይቁም አሉ፡፡

ረ. ነብያትን ለመረዳት የሚያስቸግረን አንዱ ምክንያት መጽሐፍቶቻቸው እንዴት እንደ ተዘጋጁ ማወቅ አንችልም፡፡ ነገር ግን በጊዜ ቅደም ተከተል እንዳልተጻፉ ግን እናውቃለን፡፡ በርዕስ ጉዳይ እንደተዋቀሩ እናስባለን ነገር ግን ሁል ጊዜ እንደዚያ ነው ማለት ግን አይቻልም፡፡ ብዙ ጊዜ ግልጽ የሆነ ታሪካዊ ዳራ፣ የጊዜ ወይም ግልጽ የሆነ በታርክ መካከል ልዩነት አናይም፡፡ እነዚህ መጽሐፍት አስቸጋሪዎች ናቸው (1) በአንድ ጊዜ ለማንበብ አስቸጋሪዎች ናቸው (2 በርዕስ ርዕስ አስተዋጽኦ ለመስራት ያስቸግራሉ እንዲሁም (3) በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ የሚያስተምረውን እውነት ለመናገር ያስቸግራሉ፡፡

IV. የትንቢት መገለጫዎች

ሀ. በብሉይ ኪዳን ውስጥ የትንቢት እና የነቢያት ጽንሰ ሀሳብ በደንብ የተገነባ ይመስላል፡፡ በቀደምት እሳራኤላዊያን ዘንድ የነቢያት ጉባኤ የሚባል እና በአንድ ጠንካራ ካሪዝማትክ መሪ እንደ ኤልያስ ወይም ኤልሳ ባሉ የሚመራ ጉባኤ ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜ የነቢያት ልጆች የሚባሉትም በዚህ ቡድን ውስጥ ይካተቱ ነበር (1 ሳሙ 10፡10-13፤ 19፡18-24)

ለ. ነገር ግን ይህ ጊዜ በፍጥነት በማለፍ በግል ነቢያት ወደ ሆኑ ሰዎች ተሸጋግሯል፡፡ (እውነተኛ እና የሐሰት) የሆኑ ነቢያ እራሳቸው ከነገስታት ጋር በማቀናጀ በቤተ መንግስቱ ውስጥ የሚኖሩ ነበሩ (ጋድ፣ ናታን)፡፡ እንዲሁም ከማንም ጋር እራሳቸው ያላያዙ ከእስራኤል ከተለመደው ነገር ጋር እራሳቸውን ያላቀራኙ ነቢያትም ነበሩ (አሞጽ)፡፡ እነዚህ ነቢያት ወንድም ሴትም ነበሩ (2 ነገ 22፡14)

ሐ. ነቢያት ብዙ ጊዜ የወፊቱን ነገር ገላጮች ናቸው፤ የሰዎችም ምለሽ ወዲያውኑ ነበር፡፡ ብዙ ጊዜ የነቢያት የሥራ ድርሻ የእግዚአብሔርን ለፍጥረት ሁሉ ያለውን በሰው ልጆች የማይበላሸውን አለማቀፋዊ እቅድ መግለጽ ነው፡፡ ይህ አለም አቀፋዊ የመጨረሻው ዘመን እቅድ በጥንት ምስራቅ ሕዝቦች ዘንድ እንግዳ ነገር ነበር፡፡ የወደፊቱን መናገር እና ለኪዳን ታማኝሆኑ እንዲኖሩ ማበረታት የነቢያት መልክት ማዕከል ነው፡፡ ይህ የሚገልጽልን ነቢያት በዋነኝነት የጋራነገር ላይ እንደሚያተኩሩ ያሳየናል፡፡ ብዙ ጊዜ ሁሌም ባይሆን ስለ ሀገራት ይናገራሉ፡፡

መ. ብዙዎቹ የትንቢት መልዕክቶች የተላለፉት በንግግር ነው፡፡ በኋላ ላይ በጭብጥ፣ በጊዜ ቅደም ተከተል ወይም በጥንት ምስራቅ አከባቢ በሚኖሩ ሰዎች የስነ ጽሑፍ ዘይቤ መሠረት ልደራጁ ችለዋል፡፡ በንግግር የቀረቡ ስለ ነበር በጽሑፍ እንዳሉ ግጥሞች በስርአት የተቀናጁ አልነበሩም፡፡ ይህ መጽሐፉቱን ሙሉ ለሙሉ ለማንበብ አስቸጋር ያደርገዋል እንዲሁም ታሪካዊ ዳራውን ሳናው መገንዘብ እንዳልንችል ያደርገናል፡፡

ሠ. ነቢያት መልዕክታቸውን ለማስተላለፍ ብዙ አይነት መንገዶችን ተጠቅመዋ

1. የፍርድ ቤት ሥርዓት - እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ሕዝቡን ወደ ፍርድ ቤት ይዞ ሲሄድ ይታያል፤ ምክንያቱም ምስቱ የሆነችው እስራኤል ታማኝ ሳትሆን ስለ ቀረች ነው (ሆሴ 4፤ ሚል 6)
2. የቀብር ሥነ ስረዓት- ይህ አይነቱ መልዕክት ልዩ መልዕክት ሲሆን መለያውም "ወዮላችሁ" የሚል ነው፡፡ (ኢሳ 5፤ ዕባ 2)
3. የቃል ኪዳን የተስፋ ቃል ንግግሮች- የቃል ኪዳን በሁኔታዎች ላይ የተወሰነ መሆኑን አጽኖት የሚሰጠው ነገር ሲሆን የወደፊት ውጤቱም አዎንታዊውም አሉታዊውም ውጤት በግልጽ ይገለጻል፡፡

V. ትንቢትን በመተርጎም ሂደት ውስጥ ጠቃሚ የሆኑ መመሪያዎች

ሀ. የትንቢት ተናጋሪውን የመጀመሪያ ሀሳብ ለማወቅ ጣር፤ ይህንንም የምታደርገው ታሪካዊ ዳራውን እና ስነ ጽሑፋዊ ዳራው በማወቅ ነው፡፡ ይህ ብዙ ጊዜ እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር የገባቸውን ቃል ኪዳን በመስበሯ ይሆናል፡፡

ለ. ሁሉንም ትንቢት በአንድ ጊዜ አንብበህ ለመተርጎም ሞክር፡፡ ሁሉን የመጽሐፍ ክፍል በአስተዋጽኦ መልክ አስቀምጥ

ሐ. በጽሑፉ ውስጥ ምሳሌያዊ ንግግር እንደሆነ የሚያመለክት ነገር እስካልተመለከተክ ድርስ የጽሑፉን ቀጥተኛ ትርጉም ውሰድ፡፡ ከዚህ እነዚህያን ምሳሌያዊ ንግግሮች በጽሑፍ መለክ ግለጻቸው፡፡

መ. የተለያዩ ተምሳሌቶችን በታሪካዊ ዳራው እና በተመሳሳይ ክፍሎች በመታገዝ ለመረዳት ሞክር፡፡

ሠ. ስለ ወደፊት የሚናገሩ ክፍሎችን በጥንቃቄ ተመልከት፡

1. እነዚህ ጸሐፊው በነበረበት ዘመን ብቻ የሚፈጸሙ ናቸውን
2. በእስራኤል ታርክ ውስጥ በቀጣይነት ዩት ይፈጸማሉ
3. ገናዳ ፊት የሚፈጸሙ ነገሮች ናቸውን
4. አሁን የሚፈጸሙ ሆነው ወደ ፊት የሚፈጸም ነገር አላቸውን
5. ምላሽን የመጸሐፍ ቅዱስ ጸሓፊት እንጂ የዘመናችን ጸሓፊት እንዲመሩት አታድርግ

ረ. ልዩ ትኩረት

1. ለወደፊት እንደሚፈጸም የተነገረው ትንቢት በምላሽ ላይ የተመሠረተ ነውን
2. ይህ ትንቢት ለማን እንደ ተነገረ በግልጽ ማወቅ ይቻላልን (እና ለምን)
3. በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በታርክ ለዚህ ትንቢት በድግግሞሽ ፍጻሜን ማግኘት ይችላልን

4. የአዲስ ኪዳን ጸሐፊት በመንፈስ ቅዱስ ምሪት አማካኝት ለእኛ ግልጽ ካልሆኑልን ክፍሎች ውስጥ ስለ መስሑ ማውጣት ችለዋል፡፡ ብዙ ጊዜ ተመሳሌታዊ ወይም የቃላት ጫወታዎችን ተጠቀመዋል፡፡ እኛ እንደ እርሱ በመንፈስ ቅዱስ የምንነዳ ባለመሆናችን እንዲህ አይነቱን መንገድ ለእነርሱ ልንተውላቸው ይገባል፡፡

VI. ጠቃሚ መፃህፍት

ሀ. *A Guide to Biblical Prophecy:-* በ ካርል ኢ. አሜንዲንግ እና ደብለው ዋርድ ባስክ

ለ. *How to read the bible for All its worth:- በጎርደርን ፊ እና ዳግላስ ስቱዋርት*

ሐ. *My servants the Prophets:- ጄ. ያንግ*

መ. *Plawshares and Pruning hooks: rethinking the language of Biblical (Prophecy and Apocalyptic:- በ ዲ. ብረንት ሐንዲ*

ሠ. *New International Dictionary of Old Testament Theology and Exegesis:- ገጽ 1067-1078.*

**ልዩ ርዕስ፡ የአዲስ ኪዳን ትንቢት**

I. የአዲስ ኪዳን ትንቢት እንደ ብሉይ ኪዳን፤ ከያሕዌ ቀጥተኛ መገለጥ ያለው አየደለም (ሐዋ 3፡18፣ 21፤ ሮሜ 16፡26)፡፡ ነቢያት ብቻ ነው ቅዱስ መጻሕፍን መጻፍ የሚችሉት፡፡

ሀ. ሙሴ ነቢይ ተብሎ ተጠርቷል (ዘዳ 18፡15-21)

ለ. የታርክ መጽሐፍት (ኢያ - ነገስት (ከሩት በስተቀር) ያሉት መጽሐፍ "ቀደም ነቢያት" ተብለው ተጠርተዋል

ሐ. ነቢያት ከእግዚአብሔር መረጃን በመቀበል የልቀ ካህናቱን ቦታ ይይዛሉ (ኢሳ- ሚል)

መ. የዕብራይስጥ መጽሐፍት ሁለተኛው ክፍፍል "የነቢያት" መጽሐፍት ተብሎ ይጠራል (ማቴ 5፡17፤ 22፡40፤ ሉቃ 1616፤ 24፡25፣ 27፤ ሮሜ 3፡21)፡፡

II. በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይህ ጽንሰ ሀሳብ በብዙ መንገድ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡

ሀ. ብሉይ ኪዳን ነቢያት እና በእግዚአብሔር እስትንፋስ ምሪት የተሰጠውን መልዕክታቸውን (ማቴ 223፤ 5፡12፤ 11፡13፤ 13፡14፤ ሮሜ 1፡2)

ለ. ለጋራ ሳይን ለግል መልዕክት የሚያመጡ ሰዎችን ለማመልከት (ይህ ማለት የብሉይ ኪዳን ነቢያት በዋነኝነት የተናገሩት ለእስራኤል ነበር)

ሐ. መጥመቁ ዮሐንስን (ማቴ 11፡9፤ 14፡5፤ 21፡26፤ ሉቃ 1፡76) እና ኢየሱስን የእግዚብሔር መንግስት ሰባኪያዊያን መሆናቸውን ለማሳየት (ማቴ 13፡15፤ 21፡11፣ 46፤ ሉቃ 4፡24፤ 7፡16፤ 13፡33፤ 24፡19)፡፡ ኢየሱስ ከነቢያት እንደሚበልጥ ተናግሯል (ማቴ 11፡9፤ 12፡41፤ ሉቃ 7፡26)

መ. በአዲስ ኪዳን ውስጥ የነበሩ ሌሎች ነቢያት

1. የኢየሱስ የልጅነት ሕይወቱ በሉቃስ ወንጌል ውስጥ ተዘግቧል (ይህ ማለት ማሪያም ከምታስታውሰው ማለት ነው)
   - ሀ. ኤልዛቤት (ሉቃ 1፡41-42)
   - ለ. ዘካሪያስ (ሉቃ 1፡67-79)
   - ሐ. ስምኦን (ሉቃ 2፡25-35)
   - መ. አናኒያ (ሉቃ 2፡36)
2. ምጸታዊ ትንቢቶች (ዮሐ 11፡15)
   - ሠ. ወንጌል የሚሰብክ ሰውን ያመለክታል (በ1 ቆሮ 12፡28-29፤ ኤፌ 4፡11 ላይ የንግግር ስጦታዎችን ዝርዝር)
   - ረ. ለቤተ ክርስቲያን በቀጣይነት የተሰጣትን ስጦታ ያመለክታል (ማቴ 23፡24፤ ሐዋ 13፡1፤ ሮሜ 12፡6፤ 1ቆሮ 12፡10፣ 28-29፤ 13፡2፤ኤፌ 4፡11)፡፡ ይህ አንዳንድ ጊዜ ሴቶችን ያመለክታል (ሉቃ 2፡36፤ ሐዋ 2፡17፤ 21፡9፤ 1ቆሮ 11፡4-5)፡፡
   - ሰ. የራዕይ መጽሐፍን አቡቃልብስስ ያመለክታል (ራዕ 1፡3፤ 22፡7፣ 10፣ 18፣ 19)

III. የአዲስ ኪዳን ነቢያት

ሀ. የብሉይ ኪዳን ነቢያት ያደረጉትን ዓይነት በእስትንፋሰ እግዚአብሔር መገለጥን የዲስ ኪዳን ነቦያት አይሰጡንም፡፡ እንዲህ ያለውን አረፍተ ነገር መናገር በድፊረት የሚያስችለን በሐዋ 6፡7፣ 13ለ8፤ 14፡22፤ ገላ 1፡23፤ 3፡23፤ 6፡10፤ ፊል 1፡27፤ ይሁ 3፡20 ላይ "እምነት" (ይህም ማለት የተጠናቀቀ በሞመስል መልኩ) ስላለ ነው፡፡

ይህ ሀሳብ በይሁዳ 3 ላይ ባለው ሀረግ ግልጽ ነው "ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት" ፡፡ አንድ ጊዜ ፈጽሞ የተሰጠው እምነት ፣ አስተምህሮ፣ ሀሳብ፣ የክርስትና ንጽረተዓለም ናቸው፡፡ ይህ አንድ ጊዜ መሰጠቱ አጽኖት የተሰጠበት ነገር በእስትንፋሳ እግዚአብሔር መነዳት የሚለው ነገር መለኮታዊ ሀሳብ በአዲስ ኪዳን ዘመን ብቻ የነበረ መሆኑን ለማስረገጥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ነው እንዲሁም በኋላ ላይ የተጻፉ ወይም ሌሎች ማናቸው ጽሑፎች የተገለጡ አለማሆናቸውን ያሳያል፡፡ በአዲስ ኪዳን ውስር አሻሚ፣ የማይታወቁ ክፍሎች ልኖሩ ይችላል ነገር ግን አማኞች ለእምነታች እና እንድንኖርበት

የሚያስፈልገን ሁሉ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በግልጽ ተቀምጦልና ብለው ያምናሉ፡፡ ይህ ሀሳብ በመገለጽ ሦስት ማእዘን ልገለጽ ይችላል

1. እግዚአብሔር እራሱን በጊዜ- ቦታ እና ታርክ ውስጥ ገልጦዋል (መገለጥ)
2. የእርሱን ሀሳብ ይዘግቡ እና ተግባሩንም ያብራሩ ዘንድ ከሰዎች መካከል የተወሰኑትን መርጦዋል (በእግዚአብሔር መንፈስ መነዳ)
3. እነዚህ ጽሑፎች ሰዎች በተከፈተ አእምሮ እና ልብ መረዳት እንዲችሉ እንዲያግዛቸው መንፈሱን ሰጥቶዋቸዋል ይህም ለድነት እና ለክርስትና ሕይወት በቂ ነው (አብርሆት)፡፡ የዚህ ነጥብ ዋና ሀሳብ በእግዚአብሔር መንፈስ መነዳት የሚለው ሀሳብ መጽሐፍ ቅዱስን ለመጻፍ ብቻ እንደሆነ ነው፡፡ ሌሎች ተጨማሪ ጽሑፎች፣ ራዕዮች ወይ መገለጦች ዬሉም፡፡ ቀኖና ዝግ ነው፡፡ ለእግዚአብሔር ተገቢ በሆነው መልኩ ምላሽ ለመስጠት የሚስፈልገንን ሁሉንም እውነት አለን፡፡

ለ. በአንዳንድ መልኩ የአዲስ ኪዳን ነቢያት እንደ ብሉይ ኪዳን ነቢያት ናቸው
1. ለወደፊት ስለሚሆኑ ነገሮች በመተንበይ (ጳውሎስ ሐዋ 27፡22፤ አጋቦስ 11፡27-28፤ ሌላ ስሙ ያልተጠቀሰ ነቢይ ሐዋ 20፡23)
2. ስለ ፍርድ በመናገር (ጳውሎስ ሐዋ 13፡11፤ 28፡25-28)
3. አንድን ተግባር በግልጽ መናገር የሚችሉ ምስላዊ ተግባሮች (አጋስ ሐዋ 21፡11)

ሐ. የወንጌልን እውነት አንዳንድ ጊዜ ወደ ፊት እንደሚፈጸም አድርገው ይሰብካሉ ሐዋ 11፡27-28፤ 20፡23፤ 21፡10-11) ነገር ግን ይህ ዋና ትኩረታቸው አይደለም፡፡ በ1 ቆሮ የትንቢት መናገር መሠረታዊ ሀሳቡ ወንጌልን ለሰዎች ማስተማር ላይ ነው (14፡24፣ 39)

መ. ለእያንዳንዱ ሁኔታ፣ ባሕል ወይም ጊዜ የወቅቱን እና ተግባራዊ የሆነውን የእግዚአብሔርን እውነት መንፈስ የሚጠቀምበት መንገድ ነው፡፡ (1 ቆሮ 14፡3)

ሠ. በቀደምት የጳውሎስ ቤተ ክርስቲያናቶች ዘንድ (1 ቆሮ 11፡4-5፤ 12፡28፣ 20፤ 13፡209፤ 14፡1፣ 3፣ 4፣ 5፣ 6፣ 22፣ 24፣ 20፣ 31፣ 32፣ 37፣ 39፤ ኤፌ 2፡20፤ 3፡5፤ 4፡11፤ 1 ተሰ 5፡20)፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በመጀመሪያው ወይም በሁለተኛው ምዕተ አመት አከባቢ በተጻፈው ዴዳኬ በተሰኘው መጻፍ ላይ ተጠቅሶ እናገኛን እንዲሁም ሞኖታኒዝም በሁለተኛ እና በሦስተኛ ምእተ አመት ላይ ነሰሜን አፍርካ እንዲሁም፡፡

IV. የአዲስ ኪዳን ስጦታዎች ቆመዋልን

ሀ. ለዚህ ጥያቄ መልስ መስጠት እጂግ አስቸጋር ነው፡፡ ስለ ሁሌታው ግልጽ ለማድረግ የስጦታዎችን ዓላማ በትክክል ማስቀመጥ ጠቃሚ ነው፡፡ በመጀመሪያ የተሰበከውን ስብከት ለማረጋገጥ አላማቸው ነውን ወይስ ቤተ ክርስቲያን በቀጣይነት የሚታገልግልበት ወይም ለጣፈው አለም የምትሰበብክበት መንገድ ነው

ለ. አንድ ሰው ለእነዚህ ጥያቄዎች ምለሽ ለመስጠት የቤተ ክርስቲያን ታርክን መመልከት አለበት ወይስ አዲስ ኪዳንን ብቻ ነው፤ በአዲስ ኪዳን ውስጥ መንፈሳዊ ስጦታዎች ጊዜያዊ ናቸው የሚል ነገር አንመለከትም፡፡ 1 ቆሮ 13፡8-13 ላይ ያለውን የሚጠቀሙ ሰዎች የመጽሐፍን ሀሳብ በትክክል አልተረዱትም፡፡

ሐ. እኔ በበኩሌ ስልጣን ያለው የቤተ ክርስቲያነ ታርክ ሳይሆን አዲስ ኪዳን ስለሆነ አማኞች መንፈሳዊ ስጦታዎች እንዲቀጥሉ ማመን አለባቸው እላለሁ፡፡ ነገር ግን ባህል መጽሐፍ ቅዱን የሚንፈታበትን መንገድ ያዛባል፡፡ አንዳንድ ግልጽ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን በዘመናችን መተግበር አንችልም (ለምሳሌ ቅዱስ አሳሳም፣ ሴት ልጅ መሸፋፈን፣ በቤት ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ማድረግ)፡፡ ባህል እንግዲ ይህን ያህል የስነ አፈታታችን ላይ ተጽእኖ ማሳደር ከቻለ የቤተ ክርስቲያን ታርክስ

መ. ይህ በቀላሉ ልመለስ የሚችል ጥያቄ አይደለም፡፡ አንዳንድ አማኞች "የጸጋ ስጦታዎች እንደቆሙ" ያስተምራሉ እንዲሁም ሌሎች "አልቆመም" ይላሉ፡፡ በዚህ ስፍራ ላይ እንደ ስነ አፈታት ሁኔታዎች ሁሉ የአማኞችም ዋነኛ ጉዳይ ነው፡፡ አዲስ ኪዳን አሻሚ እና ባሕላዊ ነው፡፡ አስቸጋሪው ነገር የትኞች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በባሕል ተጽእኖ ሥራ ናቸው ዬትኞቹስ አይደሉም ብሎ መለየት ነው፡፡ በሮሜ 14፡1-15፡13 እና በ1 ቆሮ 8-10 ላይ ባሉ ጉዳዮች ላይ ለውይይት የሚሆኑ ነገሮች
1. እያንዳንዱ አማኝ ባለው ብርሃን መመላለስ አለበት፡፡ እግዚአብሔር ልባችንን እና መነሻ ሀሳባችንን ይመለከታል፡፡
2. እያንዳንዱ አማኝ ሌላው ባለው መረዳት እንድኖር መፍቀድ አለበት፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ገደብ ውስጥ ሰዎች እርስ በእርሳቸው መቻቻል አለባቸው፡፡ እግዚአብሔር እንደ ወደደን እርስ በእርሳችን እንድንዋደድ ፈልጋል፡፡

ሠ. ነገሩን ለመጠቅለል ክርስትና የእምነት እና የፍቅር ኑሮ እንጂ የፍጹም ሥነ መለኮት አይደለም፡፡ ከእርሱ ጋር ያለን ግንኙነት ከሌሎች ሰዎች ጋር ባን ግንኙነት ላይ ተጽእኖ ማምጣቱ እንጂ ባለን መረጃ ወይም የእምተ መገግለጫ ፍጹምነት አይወሰንም፡፡

**4፡20 "አባታችን"** ይህ የሚያመለክትው አብረሃምን እና ያዕቆብን ነው (ዘፍ 12፡7፤ 33፡20) ይህ በቃል ኪዳን ውስጥ ለመካተቷ ማረጋገጨዋ ነው (8፡31-59)፡፡

▣ **"በዚህ ተራራ ሰገዱ"** ይህ እግዚአብሔር (ያሕዌ) ልመለክ የሚገበው በዬት ነው የሚል ስነ መለኮታዊ ጥያቄ ነው፡፡ አይሁዳዊያን በሞራህ ተራራ ላይ መሆን አለበት ይላሉ (ይህም የአይሁዳዊያን ቤተ መቅደስ የሚገኝ ስፍራ ነው)፤

ሰማሪያዊያ ደግሞ በገሪዝም ተራራ ላይ መሆን አለባት ይላሉ (የሰማሪያዊያን ቤተ መቅደስ በጆን ሄራኑስ በተባለው ሰው በ129 ዓዓ ፈጽሞ ተደምስሷል)፡፡

ይህ እንግዲህ በዘመናችን ሰዎች ስለክርስቶስ አዳኝነት እና ከእርሱም ጋር ሊኖራቸው የሚገባውን ሕብረት ስንመሰክርላቸው አፍራሽ ወይም አሳሳች ይዘት ያለውን ሥነ-መለኮታቸውን በማቅረብ ላለመቀበል ጥረት ሲያደርጉ ይታያሉ፡፡ ሰዎች የራሳቸውን ስብእና እስካልነካ ድረስ (3:19-21ን ያስ.) ኃይማኖትንና ፍልስፍናን በመመራመር ለመደሰት ይጥራሉ፡፡

4:2 1 **"በዚህ ተራራ ወይም በኢየሩሳሌም ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል"** ይህ ለእርሷ እና ለእርሱ ደቀ መዛሙርቱ በጣም አስደንጋጭ ንግግር ነው፡፡ ዬት ሳይሆን ማን ነው መመለክ ያለበት!

4:22 **"መዳን ከአይሁድ ነውና"** ይህ መስሑ ከዬት እንደሚመጣ ማረጋገጫ ነው (ዘፍ 12:2-3፤ 49:8-12፤ ኢሳ 2:3፤ ሮሜ 9:4-5)፡፡

4:23 **"ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኖአል"** ይህ ምን አልባት ከሚል 1:11 ስለ አለም አቀፋዊ አምልኮ የተወሰደ ሊሆን ይችላል፡፡ ኢየሱስ የዘላለማዊ ሕይወትን ስጦታ በምድር ላይ በኖረበት ጊዜ እንዲሁም ከሞቱ በኂላ ይዞ መጥተዋል፡፡ ይህ ዓረፍተ ነገር በመስሑ ሁለት ጊዜ መምጣት መካከል ያለውን ውጥረት ያመለክታል፡፡ የአይሁዳዊያ የሁለት ዘመን አሁን ተደርቦ መጥቷል፡፡ የመንፈስ አዲሱ ዘመን ጀምሯል ነገር ግን አሁን በአሮጌው የክፋት እና ያኃጢአት ዘመን ውስጥም እንኖራለን፡፡

ኢየሱስ አፅንኦት እየሰጠ የነበረው አዲሱ ዘመን በእርሱ መጀመሩን ነው፡፡ የመንፈስ ዘመን፣ የመሲሑ ዘመን ተመርቆ ተከፍቷል!

▣ **"በመንፈስ እና በእውነት"** "መንፈስ" የሚለው ቃል (ልዩ ርዕስ 3:8 ይመልከቱ፡፡) በቦታ ያልተወሰነ አምልኮን ያመለክታል፡፡ "እውነት" የሚለው ቃል በግሪክ የአእምሮ ሁኔታን የሚያመለክት ሲሆን በዕብራይስጥ አመለካከት ደግሞ እውነተኝነት ያሳያል፡፡ ልዩ ርዕስ እውነትን በ6:55 እና 17:3 ይመልከቱ፡፡

▣ **"አባት"** በአዲስ ኪዳን ውስጥ አባትን ከኢየሱስ ልጅነት ጋር ሳያያዙ መጽሐፍ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተለመደ አጻጻፍ አይደለም፡፡

**ልዩ ርዕስ: አባት**

ብሉይ ኪዳን እግዚአብሔርን እንደ አባት በማስቀመጥ የቤተሰባዊ ቅርርብን ለማመልከት ተጠቅሞበት እናገኛለን

1. የእስራኤል ሕዝብ ብዙ ጊዜ የያሕዌ "ልጆች" ተብለው ይጠራሉ (ሆሴ 11:1፤ ሚል 3:17)
2. በዘዳ መጀመሪያ አከባቢ እንኳ እግዚአብሔርን እንደ አባት ሆኖ ተጠቅሷል (1:31)
3. ዘዳ 32 እስራኤል "ልጆቹ" እና እግዚአብሔር ደግሞ "አባታቸው" ተብሎ ተጠርቷል
4. ይህ ምሳሌያዊ ንግግር በመዝ 103:13 ላይ ተገልጾዋል እንዲሁም በመዝ 68:5 ላይ ተሻሽሎ ቀርቧል፡፡
5. በትንቢት መጽሐፍት ውስጥ የተለመደ ቃል ነው (ኢሳ 1:2፤ 63:8፤ እስራኤል እንደ ልጅ፤ እግዚአብሔር እንደ አባት 63:16፤ 64:8 ኤር 3:4፤፣ 19፤ 31:9)

ኢየሱስ ይናገር የነበው ቋንቋ አራማይክ ስለሆነ ብዙ ስፍራ ላይ "አባት" ብሎ ስናገር የተጠቀመው የግሪክ ቃል ፓተር ሲሆን በአራማይክ ደግሞ አባ ነው (14:6) ይህ የቤተሰብ ቋንቋ የሚያሳየው ከአባቱ ጋር የነበረውን ግንኙነት ነው፡፡ ይህንን ለተተከተሉት ሰዎች መግለጹ ከአባቱ ጋር ያለንን ግንኙነት እንድናጠነክር ይረዳናል፡፡

▣ **"አብ ሊሰግዱለት እንደ እነዚህ ያሉትን ይሻልና"** እግዚአብሔር ጠፋው የሰው ልጅን ይፈልጋል (ኢሳ 33፤ ሕዝ 18:23፣ 32፤ ሉቃ 19:10፤ ዮሐ 1:12፤ 3:16)፡፡

4:24 **"እግዚአብሔር መንፈስ ነው"** በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ እግዚአብሔርን ባህሪይ የሚገልጹ ብዙ አጫጭር ዓርፍተ ነገሮች አሉ፡፡ (1) እግዚአብሔር ፍቅር ነው (2) እግዚብሔር ብርሃን ነው (3) እግዘኢብሔር መንፈስ ነው፡፡ ይህ (1) ቁሳዊነት ዬለውም (2) በአንድ ስፍራ አይገደብም (3) በጊዜ አይገደብም (4) ሰማያዊ እንጂ ምድራዊ አይደለም ሊሆን ይችላል፡፡

4:25 **"መሲሕ እንዲመጣ"** መስሑ የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሁለት ጊዜ ብቻ የተጠቀሰ ሲሆን ይሄውም በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ነው (1:41፤ 4:25)፡፡

**ልዩ ርዕስ: መሲሕ**

ይህ የተወሰደው ከዳንኤል መጽሐፍ የእኔ የመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻ ወስጥ ነው፡፡ ይህንን ቃል መተርጎም አስቸጋሪ

የሚያደርገው መስሑ ወይም የተቀባው ከሚለው ቃል ጋር ተያያዥነት ያላቸው ነገሮች ስላሉ ነው

1. ለአይሁድ ነገስታት ውሏል (1ሳሙ 2፡10፤ 12፡3)
2. ለአይሁድ ካህናት ውሏል (ዘሌ 4፡3፣ 5)
3. ለቂሮስ (ኢሳ 45፡1)
4. በመዝ 110 እና ዘካ 4 ላ በቁ 1 እና ቁ 2 ላይ የተጠቀሱት ሀሳቦች ተዋህደው ቀርበዋል
5. ልዩ የሆነው የእግዚአብሔር መልክኛን ለማመልት ውሏል፡፡ አዲሱን የጽድቅን ዘመነ የሚያመጣው የዳዊ ንጉስ ለማመልከት ውሏል፡፡
   ሀ. የይሁዳ ዘር (ዘፍ 49፡10)
   ለ. የእሴይ ቤት (2 ሳሙ 7)
   ሐ. አለማቀፋዊ ንግሥና (መዝ 2፣ ኢሳ 9፡6፤ 11፡1-5፤ ሚል 5፡1-4)

እኔ በግሌ ወደ ናዝሬቱ ኢየሱስ የተሳብኩበት ምክንያት

1. በሁለተኛው ምዕራፍ ላይ አራተኛው ንጉስ ዘላለማዊውን ንጉስ ስለሚስተዋውቅ
2. በ7፡13 ላይ የስተዋወቀው "የሰው ልጅ" ዘላለማዊ መንግስት ሰለ ተሰጠው
3. 9፡24 ላይ ያለው የድነት ሀረግ የወደቀው አለም ማብቃ እንደሆነ ስለሚያሳይ
4. በአዲስ ኪዳን ውስጥ ኢየሱስ የዳንኤልን መጽሐፍ ስለተጠቀመ (ማቴ 24፡15፤ ማር 13፡14)

▣ *"እርሱ ሲመጣ ሁሉን ይነግረናል"* ይህ የሚያሳይ ሰማሪያዊያን የመሲሁን መምጣት መጠባበቃቸውን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሚያሳየን የሚጠብቁት መሲሕ የእግዚአብሔር ሙሉ መገለጥ እንደሚሰጣቸው ያምናሉ፡፡

4፡26 **"የምናገርሽ እኔ እርሱ ነኝ አላት"** ይህ ምንአልባት ከኢሳ 52፡6 ላይ የተወሰደ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ግልጽ የሆነ የእርሱን አምላክነት የሚያረጋግጥ ነገር ነው፡፡ ይህ "እኔ" የሚለው ቃል ላይ የተደረገ የቃላት ጫወታ ነው፡፡ "እኔ" የሚለው ስም በብሉይ ኪዳን ውስጥ የቃል ኪዳን አምላክ የሆነው የያሕዌ መጠሪያ ነው (ዘጸ 3፡12፣ 14) ኢየሱስ ይህንን የብሉይ ኪዳንን የእግዚአብሔርን ስም የተጠቀመበት የያሕዌ ሙሉ መገለጥ በኢየሱስ በኩል መሆኑን ለማሳየት ነው (ዮሐ 8፡24፣ 28፣ 58፤ 13፡19፤ 18፡5 ከኢሳ 41፤4፤43፤10፤ 46፡4)፡፡ ይህ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ከተጠቀማቸው "እኔ" ቃላት የተለየ ነው፡፡

**የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 4፡27-30**
***በዚያም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ መጡና ከሴት ጋር በመነጋገሩ ተደነቁ፤ ነገር ግን፡፡ ምን ትፈልጊያለሽ? ወይም፡፡ ስለ ምን ትናገራታለህ? ያለ ማንም አልነበረም፡፡ "ሴቲቱም እንስራዋን ትታ ወደ ከተማ ሄደች ለሰዎችም፡፡ ያደረግሁትን ሁሉ የነገረኝን ሰው ኑና እዩ፤ እንጃ እርሱ ክርስቶስ ይሆንን? አለች፡፡ ከከተማ ወጥተው ወደ እርሱ ይመጡ ነበር፡፡***

4፡27 *"ከሴት ጋር በመነጋገሩ ተደነቁ"* እንዲህ ያለ ነገር በትክክለኛ አይሁዳዊያን የሚደረግ ነገር አይደለም፡፡

▣ *"ምን ትፈልጊያለሽ? ወይም፡፡ ስለ ምን ትናገራታለህ? ያለ ማንም አልነበረም"* ይህ የዮሐንስ የዐይን ምስክርነት ነው፡፡ ይህንን እጅግ በጣም አስደንጋጭ የሆነ ሁኔታን በጣም የስታውዋል፡፡
4፡28 *"ሴቲቱም እንስራዋን ትታ"* ይህ የሚያምር የዐይን እማኝነት ነው፤ ታሪካዊ ማስታወሻው እንደሚያመለክተው ወደ መንደሩ የተመለከተችውን ለመመስከር እየሄደች ምን ያህል ተገርማ እንደነበር ነው፡፡ (ቁ 29-30)

4፡29 *"እንጃ እርሱ ክርስቶስ ይሆንን?"* አለች፡፡ የስማሰው ቀመሩ "አሉታዊ" ምላሽ ነው ነገር ግን አውዱ እንደሚያመለክተው ግን እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ እንደሚታምን ነው፡፡

**የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 4፡31-38**
***ይህም ሲሆን ሳለ ደቀ መዛሙርቱ፡፡ መምህር ሆይ: ብላ ብለው ለመኑት፡፡ እርሱ ግን፦ እናንተ የማታውቁት የምበላው መብል ለእኔ አለኝ አላቸው፡፡ ስለዚህ ደቀ መዛሙርቱ፡፡ የሚበላው አንዳች ሰው አምጥቶለት ይሆንን? ተባባሉ፡፡ ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፦ የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው፡፡ እናንተ፡፡ ገና አራት ወር ቀርቶአል መከርም ይመጣል ትሉ የለምን? እነሆ እላችኋለሁ: ዓይናችሁን አንሡ አዝመራውም አሁን እንደ ነጣ እርሻውን ተመልከቱ፡፡ የሚያጭድ ደመወዝን ይቀበላል: የሚዘራና የሚያጭድም አብረው ደስ እንዲላቸው ለዘላለም ሕይወት ፍሬን ይሰበስባል፡፡ አንዱ ይዘራል አንዱም ያጭዳል የሚለው ቃል በዚህ እውነት ሆኖአልና፡፡ እኔም እናንተ ያልደከማችሁበትን ታጭዱ ዘንድ ሰደድኋችሁ፤ ሌሎች ደክሙ እናንተም በድካማቸው ገባችሁ፡፡***

4፡32 ይህ የሰማይ እና የምድር፣ የመንፈሳዊ እና የቁሳዊ ንጽጽር አይደለም፡፡ ኢየሱስ ወንጌላዊነት፣ የመገልጥ ተልእኮ ነበረው፡፡ ቅድሚያ የሚሰጠው ለሰዎች ነው፡፡

**4:34 "የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው" ዮሐ** 17 አባቱ ኢየሱስ እንዲያደርግለት እንደሚፈልግ ኢየሱስ ግልጽ መረዳት እንደነበረው ያሳያል (ማር 10:45፤ ለቃ 19:10፤ ዮሐ 6:29)

ኢየሱስ ከሰማይ መላኩ የሚነጻጸረው ከእግዚአብሔር መገኘት፣ ከአባቱ ዘንድ አባቱን የመግለጽ ተልዕኮ እና የእርሱን ፍቃድ ለመፈጸም መምጣቱን ነው፡፡ ይህ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የሚንመለከተው የወደ ላይ ያለ ሁለትዮሽ እንመለከታለን (ወደ ላይ እና ወደ ታች፣ መንፈሳዊ እና ስጋዊ)

ኢየሱስ መላኩን የሚያመለክቱ ሁለት ቃላት አገልግሎት ላይ ውለዋል

1. *ፖፔ* (4:34፣ 5:23፣24፣ 30፣ 37፣፤ 6:38፣ 39፣ 40፣ 44፤ 7:16፣ 18፣ 28፣ 33፣፤ 8:16፣ 18፣ 26፣ 29፣፤ 9:4፤ 12:44፣ 45፣ 49፤ 14:24፤ 15:21፤ 16:5)
2. *ፖስትሎ* (3:17፣ 24፤ 5:36፣ 38፤ 6:29፣ 57፤ 7:29፤ 8:42፤ 10:36፤ 11:41፤ 17:3፣18፣ 21፣ 23፣ 25፤ 20:21)

ይህ በ2):21 ጋር ከተገለጸው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ እንዲሁም አማኞች ለመዋጀት አላማ ወደ ጠፋው አለም በአብ አማከካኝነት መላካቸውን ያመለክታል፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ የእግዚአብሔር ፍቃድ (ቴሌማ)**

**የዮሐንስ ወንጌል**

- ኢየሱስ የመጣው የአባቱን ፍቃድ ለመፈጸም ነው (4:34፤ 5:30፤ 6:38)
- አብ ለልጁ የሰጣቸው ሁሉ በመጨረሻው ቀን ከሞት ይነሳሉ (6:39)
- ሁሉም በልጁ ያምኑ ዘንድ (6:29፣ 40)
- ከእግዚአብሔር ፍቃድ ጋር የተያያዙ ጸሎቶች ምላሽ ያገኛሉ (9:31 እና 1ዮሐ 5:41)

**በተመሳሳይ ወንጌላት**

- የእግዚአብሔር ፍቃድ ማድረግ እጅግ በጣም ጠቃሚ ነቀወ (ማቴ 7:21)
- የእግዚብሔርን ፍቃድ ማድረግ አንድን ሰው ከኢየሱስ ጋር ወንድም እና እህት ያደርገዋል (ማቴ 12:50፤ ማር 3:35)
- ማንም ሰው እንድጠፋ የእግዚአብሔር ፍቃድ አይደለም 9ማቴ 26:42፤ ሉቃ 22:42)

**በጳውሎስ ደብዳቤዎች ውስጥ**

- የሁሉም አማኞች ብስለት እና አገልግሎት (ሮሜ 12:1-2)
- አማኞች ከዚህ ክፉ አለም ነጻ ይወጡ ዘንድ (ገላ 1:4)
- የእርሱ የድነት እቅድ የእግዚብሔር ፍቃድ ነው (ኤፌ 1:5፣ 9፣ 11)
- የአማኞች በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሕይወት እና ልምምድ እንድኖራቸው (ኤፌ 5:17-18)
- አማኞች በእግዚአብሔር እውቀት የሞሉ ዘንድ (ቆላ 4:12)
- አማኖች ይቀደሱ ዘንድ (1 ተሰ 4:3)
- አማኞች በሁሉም ነገር ያመሰግኑ ዘንድ (1 ተሰ 5:18)

**በጴጥሮስ ደብዳዎች ውስጥ**

- አማኞች ትክክለኛውን ነገር ያደርጉ ዘንድ (ለመንግስት አካላት መገዛት) እና በዚህም ሞኞችን ዝም ያሰኙ እና ለወንጌል ምች ሁኔታ ይፈጥሩ ዘንድ ነው (1 ጴጥ 2:15)
- የአማኞች መከራ (1 ጴጥ 3:17፤ 4:19)
- አማኞች ራስን ያማከለ ሕይወት መኖር አይገባቸውም (1 ጴጥ 4:2)

**በዮሐንስ ደብዳዎች ውስጥ**

- አማኞች ከእርሱ ጋር ለዘላለም ተጣብቀው ይኖሩ ዘንድ (1 ዮሐ 2:17)
- አማኞች የጸሎታቸው ምለሽ ያገኝ ዘንድ (1 ዮሐ 5:14)

**4:35 "ገና አራት ወር ቀርቶአል መከርም ይመጣል ትሉ የለምን?"** ይህ ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን የሚያመለክተውም መንፈሳዊ ምላሽ ብዛት መኖሩን ያሳያል፡፡ ሰዎች ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ወቅት በእርሱ በማመን ይድኑ ነበር፤ ይህ እርሱ ከሞት ከተነሳ በኂላ ብቻ የሆነ ነገር አይደለም፡፡

**4:36-38 "አንዱ ይዘራል አንዱም ያጭዳል"** ይህ ቁጥር ምናልባትም የነቢያትን አገልግሎት ወይም የመጥመቁ ዮሐንስ አገልግሎት ያመለክታል፡፡ ይህ እንዲሁም በ1 ቆሮ 3:6-8 በጳውስ እና በሓዋሪያቱ መካከል ስላለ ግንኙነትን ተገልጽዋል፡፡

የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 4:39-42

**ሴቲቱም፡፡ ያደረግሁትን ሁሉ ነገረኝ ብላ ስለ መሰከረችው ቃል ከዚያች ከተማ የሰማርያ ሰዎች ብዙ አመኑበት፡፡ የሰማርያ ሰዎችም ወደ እርሱ በመጡ ጊዜ በእነርሱ ዘንድ እንዲኖር ለመኑት፤ በዚያም ሁለት ቀን ያህል ኖረ፡፡ ስለ ቃሉ ከፊተኞች ይልቅ ብዙ ሰዎች አመኑ፤ ሴቲቱንም፡፡ አሁን የምናምን ስለ ቃልሽ አይደለም: እኛ ራሳችን ሰምተነዋልና፤ እርሱም በእውነት ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት እንደ ሆነ እናውቃለን ይሉአት ነበር፡፡**

4:39 **"የሰማርያ ሰዎች ብዙ አመኑበት"** ዮሐንስ "እምነት" የሚለውን ቃል ከሌሎች ቃላት ጋር በማዋሃድ ሲገለገልበት እንደመለከታለን፡፡ "በእርሱ ማመን"፤ "ታምኑ ዘንድ" እማ ብዙ ጊዜ "በእርሱ ታምኑ ዘንድ" የሚለውን ይጠቀማል (2፡11፣ 23፤ 3፡16፣ 18፣ 36፤ 6፡29፣ 35፣ 40፤ 7፡5፣ 31፣ 38፣ 48፤ 8፡30፤ 9፡35፣ 36፤ 10፡42፤ 11፡25፣ 26፣ 45፣ 48፤ 12፡11፣ 37፣ 42፣ 44፣ 46፤ 14፡1፣ 12፤ 16፡9፤ 17፡20)፡፡ በመጀመሪያ ሰማሪያዊያን ያመኑት ሴትቱ ስለመሰከረችላቸው ነው፡፡ (39) ነገር ግን ኢየሱስ ስናገር ከሰሙት በኂላ ስለ ሰሙት አምነዋል ((41-42)፡፡ ኢየሱስ የመጣው ለጠፉት የእስራኤል በጎች ነው ነገር ግን ወንጌሉ ግን ለሰው ልጆች ሁሉ ነው፡፡

▣ **"ስለ መሰከረችው ቃል"** እግዚአብሔር የዚህችን በስህተት ውስጥ ያለች ግበረገብ የጎደላትን ሴት ምስክርነት ከተጠቀመ የእኛን የአብዛኛዎቹ ምስክርነትም ይጠቀቀማል፡፡ ይህ ቁጥር የግል ምስክርነት ምንኛ አስፈላግ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ልዩ ርዕስ ስለ ኢየሱስ መመስከር የሚለውን በ1፡8 ላይ ያለውን ተመልክቱ

4፡40

| | |
|---|---|
| NASB፣ NRSV | "ጠየቁት" |
| NKJV | "አስገደዱት" |
| TEV፣ NJB | "ለመኑት" |

ይህ ጠንካራ የግሪክ ቃል ሲሆን "ማስገደድን" "መለመንን" ያመለክታል፡፡ የዚህ ቃ አጽኖት በቁ 47 ባለው ቃል ልታይ ይችላል (ሉቃ 4፡38)

4:42 **"የዓለም መድኃኒት"** በ1 ዮሐ 4፡14 ላይ ተመሳሳይ አለም አቀፋዊ ማዕረግ አገልግሎት ላይ ውሎ እናገኛለን፡፡ ይህ ቃ የእግዚአብሔርን ለሰው ልጆች ሁሉ ያለውን አለም አቀፋዊ ፍቅርን ለማሳየት አገልግሎት ላይ ውሎ እናገኛለን፡፡ (1 ጢሞ 2፡6፤ ዕብ 2፡9፤ 1ዮሐ 2፡2)፡፡ በዘፍ 3፡15 ላይ የተገባው የተስፋ ቃል ተፈጽሟል፡፡ በመጀመሪያው ምዕተ አመት ይህ ሀረግ ቄሳርን ለማመልከት ይውል ነበር፡፡ የሮማዊያን ስደት የተነሳበት ምክንያት ክርስቲያኖች ይህንን ማዕረግ ለኢየሱስ ብቻ የሚገባው ነው ብለው መናገር ስለጀመሩ ነው፡፡ ይህ መጠሪያ እንደሚያመለክተው የአዲስ ኪዳን ጸሐፍት የእግዚአብሔር አብን ስም ለልጁ ይጠወሙበታል፡ ቲቶ 1፡33- ቲቶ 1፡4፤2፡10፤ 2፡13፤3፡4፣6

አይሁዳዊያን ኢየሱስ አልተቀበሉትም (1፡11) ነገር ግን ሰማሪያዊያን በፍጥነት እና ቀላል በሆነ ሁኔታ ተቀብለውታል (1፡12)

> የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 4፡43-45
> **ከሁለቱ ቀኖችም በኂላ ከዚያ ወጥቶ ወደ ገሊላ ሄደ፡፡ ነቢይ በገዛ አገሩ እንዳይከበር ኢየሱስ ራሱ መስክሮአልና፡፡ ወደ ገሊላም በመጣ ጊዜ: የገሊላ ሰዎች ራሳቸው ደግሞ ለበዓል መጥተው ነበርና በበዓል በኢየሩሳሌም ያደረገውን ሁሉ ስላዩ ተቀበሉት፡፡**

4፡43 ይህ ቁጥ የሚያመለክተው በተመሳሴ ወንጌላት ከተገለጸው በላY ኢየሱስ በነጻነት በይሁዳ እና በገሊላ መካከል ብዙ ጊዜ ይዘዋወር ነበር፡፡

4፡44 ይህ ያልተለመደ ቁጥር ነው ምክንያቱም ከዚህ በፊት ካሉ ሃሳቦች ጋር አብሮ አይሄድም፡፡ ምናልባትም በመጀመሪያ አከባቢ ያለውን የገሊላ አገልግሎቱን ሊያመለክት ይችላል (4፡3)፡፡ ይህ ምሳሌያ አገለለት በማቴ 13፡57፣ ማር 6፡4፤ ሉቃ 4፡24 ላይ ይገኛል፡፡ በተመሳሳይ ወንጌላት ውስጥ ገሊላን የሚያመለክት ሲሆን በዚህ ስፍራ ግን ይሁዳይ ያመለክታል፡፡

4፡45 **"የገሊላ ሰዎች ተቀበሉት"** በፋስካ ሰሞን በኢየሩሳሌም የነበረውን አገልግሎት እና ትምህርት ተመልክተው ነበር፡፡ ይህ የሚያመለክተው ኢየሱስ በእግዚአብሔር የተላከው መሲሕ እንደሆነ መቀበላቸውን (1፡12) ቢያንስ በተወሰነ መልኩ (48)፡፡

> የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 4፡46-54
> **ኢየሱስም ውኃውን የወይን ጠጅ ወዳደረገባት ወደ ገሊላ ቃና ዳግመኛ መጣ፡፡ በቅፍርናሆምም ልጁ የታመመበት ከንጉሥ ቤት አንድ ሹም ነበረ፡፡ እርሱም ኢየሱስ ከይሁዳ ወደ ገሊላ እንደ መጣ ሰምቶ ልጁ ሊሞት ስላለው ወደ እርሱ ሄደ ወርዶም እንዲፈውስለት ለመነው፡፡ ስለዚህም ኢየሱስ፦ ምልክትና ድንቅ ነገር ካላያችሁ ከቶ አታምኑም አለው፡፡ ሹሙም፡፡ ጌታ ሆይ: ብላቴናዬ ሳይሞት ውረድ አለው፡፡ኢየሱስም፦ ሂድ፤ ልጅህ በሕይወት አለ አለው፡፡ ሰውዬውም ኢየሱስ የነገረውን ቃል አምኖ ሄደ፡፡እርሱም ሲወርድ ሳለ ባሮቹ ተገናኙትና፡፡ ብላቴናህ በሕይወት አለ ብለው ነገሩት፡፡ እርሱም በጎ የሆነበትን ሰዓት ጠየቃቸው፤ እርሱም፦ ትናንት በሰባት ሰዓት ንዳዱ ለቀቀው አሉት፡፡ አባቱም ኢየሱስ፦ ልጅህ በሕይወት አለ ባለው በዚያ ሰዓት እንደ ሆነ አወቀ፤ እርሱም ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር አመነ፡፡ይህም ደግሞ ኢየሱስ ከይሁዳ ወደ ገሊላ መጥቶ ያደረገው ሁለተኛ ምልክት ነው፡፡**

4፡46

| | |
|---|---|
| NASB፣ NRSV NJB | "ከንጉሥ ቤት አንድ ሹም" |

NKJV "አንድ የታወቀ ሰው"
TEV፣ "የመንግስት ባለስልጣን"

ይህ የመንግስት ባለስልጣን የሄሮዶስን ቤተሰቦች የሚያገለግል ነው፡፡

4፡48 **"ምልክትና ድንቅ ነገር ካላያችሁ ከቶ አታምኑም አለው"** ኢየሱስ ይህንን ሰው የተናገረው በብዙ ቁጥር ነው፡፡ አይሁዳዊያን ምልክትን ይሻሉ (2፡18፤ 6፡2..0፤ መቴ 12፡38፤ 16፡1)፡፡ ነገር ግን ይህ የሄሮዶስ አገልጋይ ምልክትን ሳይመለከት አምኖ ነበር፡፡

4፡49 **"ልጅ"** በሦስት ቁጥሮች ውስጥ ሦስት የተለያዩ ቃላትን ተጠቅሟል

1. ቁ. 49 - ፓዲኦን ("ልጅ")
2. ቁ. ሃኢኦስ (ልጅ)
3. ቁ. 51 ፓስ (ልጅ)

በእርግጥ እነዚህ ቃላት ተለዋዋጭ ቃላት ናቸው፡፡

4፡50 ይህ ቁጥር የዮሐንስን ዋና ሀሳብ የያዘ ነው- በኢየሱስ ማመን፣ በቃሉ ማመን፣ በሠራው ስራዎች ማመን፣ በማንነቱ ማመን፡፡ የዚህ ሰው እምነት የኢየሱስን የተስ ቃል ሳይመለከት ማመኑን እንመለከታለ፡፡

4፡53 **"እርሱም ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር አመነ"** ይህ የአንድ ሰው እምነት የብዙዎች ላይ ተጽእኖ መፍጠሩ ከተጠቀሰባቸው ብዙ ስፍራዎች መካከል አንዱ ነው፡፡

1. ቆርኖሎዮስ (ሐዋ 10፡44-48)
2. ልዲያ (ሐዋ 16፡15)
3. ፊልጶስ (ሐዋ 16፡31-34
4. ክሪፖስ (ሀዋ 18፡8)
5. ስቴፈን (1 ቀሮ 1፡16)

4፡54 የመጀመሪያው የአደባባይ ተዓምር በቃና ዘገልላ የተደረገው ተአምራት ነው (2፡1-11)

***መወያያ ጥያቄዎች***

ይህ <u>ምሪትን</u> የሚሰጥ የመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻ ነው፤ ይህም ማለት ለምትደረስበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ኃላፊነት የምትወስደው አንተ እራስ ትሆናህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን ባለን ብርሃን መጠን ልንመላለስ ይገባል ማለት ነው፡፡ በስነ አፍታት ሂደት ውስጥ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ዋነኛውን ስፍራ ትይዛላችሁ፡፡ ይህንን እድል ለመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻዎች አሳልፈህ አትስጥ፡፡

ከዚህ በታች የተጠቀሱት የመወያያ ጥያቄዎች በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ባሉት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ማሰላሰል እንድትችሉ ለማገዘ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ የሚገድቡህ ሳይሆን የማሰላሰል ምናብን እንዲያሰፉልህ የታቀዱ ናቸው፡፡

1. ኢየሱስ የይሁዳ አከባቢን የለቀቀበት ምክንያት ምን ነበር?
2. ዮሐንስ የሮማዊያን ወይም የአይሁዳዊያን የጊዜ አቆጣጠርን የተጠቀመበት ምክንያት ምንድነው?
3. ኢየሱስ ከሰማሪያዊቷ ሴት ጋር ያደረገው ውይይት ይህን ያህል ጠቃሚ የሆነበት ምክንያት ምንድ ነው?
4. ቁ 20 ላይ ያለው ሀሳብ በተለያዩ ቤተ እምነቶች መካከል ባለው ግንኙነት ላይ ያለው ተጽእኖ ምንድ ነው?
5. በቁ. 26 ላይ ኢየሱስ ንግግሩን የጀመረበት አረፍተነ ነገርን አብራራ፡፡
6. ገሊላዊያን እውነተኛ እምነትን ተለማምደው ነበርን?

# ዮሐንስ 5

## የዘመኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀጽ ክፍፍል

| ዩቢኤስ[4] | NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| በመጥመቂያ ቦታ ላይ የተደረገ ፈውስ | በቤተ ሳይዳ መጥመቂያ አንድ ሰው ተፈወሰ | በመጥመቂያ ቦታ የተደረገ ፈውስ | በመጥመቂያ ቦታ የተደረገ ፈውስ | በቤተ ሳይዳ መጥመቂያ ስፍራ የታመመ አንድ ሰው መፈወሱ |
| 5:1-9ሀ | | | | |
| | 5:1-15 | 5:1 | 5:1-6 | 5:1-9ሀ |
| | | 5:2-9ሀ | | |
| | | | 5:7 | |
| | | | 5⁝8-9ሀ | |
| 5:9ለ-18 | | | | |
| | | 5:9ለ-18 | 5:9ከ-10 | 5:9ለ-18 |
| | | | 5:11 | |
| | | | 5:12 | |
| | | | 5:14 | |
| | የአባቱ እና የልጁ ክብር | | | |
| | 5:16-23 | | 5:16 | |
| | | | 5:15-17 | |
| | | | 5:18 | |
| የልጁ ስልጣን | | | | |
| | | ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት | የልጁ ስልጣን | |
| 5:19-29 | | 5:19-24 | | |
| | | | 5:19-23 | 5:19-47 |
| | ሕይወት እና ፍርድ በልጁ ነው | | | |
| | 5:24-30 | | 5:24-29 | |
| | | 5:25-29 | | |
| | | ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር ስላለው ግንኙነት ማረጋገጫ | የኢየሱስ ምስክርነት | |
| | | 5:30 | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 5፡30 | | | 5፡30 |
| የኢየሱስ ምስክርነት | አራቱ ምስክርነቶች | 5፡31-38 | |
| 5፡31-40 | 5፡31-47 | የእርሱን ቢሮ ያልተቀበሉትን ሰዎች ኢየሱስ ገሰጻቸው | 5፡31-40 |
| | | 5፡39-47 | |
| 5፡41-47 | | | 5፡41-47 |

**ሦስተኛ ዙር ንባብ**

*በአንቀጽ ደረጃ የመጽሐፉ ጸሓፊ ሊያስተላልፍ የፈለገውን ሀሳባ መከተል*

ይህ <u>ምሪትን</u> የሚሰጥ የመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻ ነው፤ ይህም ማለት ለምትደረስበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ኃላፊነት የምትወስደው አንተ እራስ ትሆናህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን ባለን ብርሃን መጠን ልንመላለስ ይገባል ማለት ነው። በስነ አፍታት ሂደት ውስጥ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ዋነኛውን ስፍራ ትይዛላችሁ። ይህንን እድል ለመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻዎች አሳልፈህ አትስጥ።

መጽሐፉን በአንድ ጊዜ ለሁለተኛ ጊዜ አንብበህ ጨርስ። ዋና ዋና ሀሳቦችን ግለጽ እንዲሁም ዋናውን ሀሳብ በአንድ አረፍተ ነገር ግለጽ።

1. *የመጀመሪያውን አንቀጽ ዋና መልዕክት*
2. *የሁለተኛውን አንቀጽ ዋና መልዕክት*
3. *የሦስተኛውን አንቀጽ ዋና መልዕክት*
4. *ወዘተ*

**የቃላት እና የሀረግ ጥናት**

**የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 5፡1-9ሀ**
**ከዚህ በኋላ የአይሁድ በዓል ነበረ: ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ። በኢየሩሳሌምም በበጎች በር አጠገብ በዕብራይስጥ ቤተ ሳይዳ የምትባል አንዲት መጠመቂያ ነበረች፤ አምስትም መመላለሻ ነበረባት። አንዳንድ ጊዜ የጌታ መልአክ ወደ መጠመቂያይቱ ወርዶ ውኃውን ያናውጥ ነበርና፤ እንግዲህ ከውኃው መናወጥ በኋላ በመጀመሪያ የገባ ከማናቸው ካለበት ደዌ ጤናማ ይሆን ነበር።በእነዚህ ውስጥ የውኃውን መንቀሳቀስ እየጠበቁ በሽተኞችና ዕውሮች አንካሶችም ሰውነታቸውም የሰለለ ብዙ ሕዝብ ይተኙ ነበር። በዚያም ከሠላሳ ስምንት ዓመት ጀምሮ የታመመ አንድ ሰው ነበረ፤ ኢየሱስ ይህን ሰው ተኝቶ ባየ ጊዜ: እስከ አሁን ብዙ ዘመን እንዲሁ እንደ ነበረ አውቆ። ልትድን ትወዳለህን? አለው። ድውዩም። ጌታ ሆይ: ውኃው በተናወጠ ጊዜ በመጠመቂያይቱ ውስጥ የሚያኖረኝ ሰው የለኝም ነገር ግን እኔ ስመጣ ሳለሁ ሌላው ቀድሞኝ ይወርዳል ብሎ መለሰለት። ኢየሱስ፦ ተነሣና አልጋህን ተሸክመህ ሂድ አለው። ወዲያውም ሰውዬው ዳነ አልጋውንም ተሸክሞ ሄደ።**

**5፡1 "በዓል"** በተቻላቸው ሁሉ አይሁዳዊያን ወንዶች ልካፈሉት የሚጋባ ሦስት አመታዊ በዓላት አሉ። (ዘሌ 23) (1) የፋሲካ በዓል (2) የጴንጤ ቆስጤ ቀን እና (3) የድንኳን በዓል። ይህ የሚያመለክተው የፋሲካ በዓልን ከሆነ ኢየሱስ ያከበረው አራት እንጂ ሦስት ክብር በዓላትን አይደለም ማለት ነው። (213፣ 23፤ 6፡4፤ 12፡1)። ከመጥመቁ ዮሐንስ በኋላ ኢየሱስ ሦስት በዓላትን እንዳ እንዳከበረ ይታመናል። ይህን ማረጋገጥ የሚቻለው በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የተጠቀሱት የፋሲካ በዓላትን በመመልከት ነው።

▣ **"ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ"** በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ኢየሱስ የፋሲካን በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም መሄዱን የሚያመለክቱ ብዙ ጊዜ ተጠቅሷል። (2፡13፤ 5፡1፤ 7፡10፤ 12፡12)።

ኢየሩሳሌም በሰባት ተራረሮች የተከበበች ከተማ ስትሆን በአከባቢው ካሉ መሬቶች ሁሉ በከፍተኛ ስፍራ ላይ የሚትገኝ ናት። "ወደ . . . ወጣ" የሚለው ሀረግ በአካል ወደ ከፍተኛ ስፍራ መውጣትን ያመለክታል። ነገር ግን ምሳሌያዊ ጠቀሜታም አለው።

5፡2 **"በበጎች በር"** ይህ የበጎች በር ተብሎ የምጠራው ስፍራ የሚገኘው በሰሜን ምስራቅ የኢየሩሳሌም ቅጥር ነው። በነህምያ የከተማውን ቅጥር ግንባታ እና እንደገና የመመለስ ወቅት ይህ ስፍራ ተጠቅሷል (ነህ 3፡1፣32፤ 12፡39)።

▣

| | |
|---|---|
| NASB፤ NKJV | **"በእብራይስጥ ቤተሳይዳ የምትባል መጠመቂያ"** |
| NRSV | **"በእብራይስጥ ቤተ-ዛታ የምትባል"** |
| TEV | **"በእብራይስጥ ቤተ-ዛታ ትባላለች"** |
| NJB | **"በእብራይስጥ ቤተሳይዳ ተብላ ትጠራለች"** |

ይህንን ስም ለመጻፍ የተለያዩ መንገዶች አሉ። ጆሴፈስ የተባለው የታርክ ጸሐፍ በዕብራይስጥ ስሙ ቤተዛይዳ ብሎ ይጠራዋል። በግርክ የጥንት ቅጂዎች ላይ ደግሞ ቤተሳይዳ ተብሎ ተጽፈዋል።

ኢየሱስ በኖረበት ዘመን ይኖሩ የነበሩ አይሁዳዊያን ይናገሩ የነበሩት ቋንቋ ዕብራይስጥ ሳይሆን አራማይክ ነበር። በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ዕብራይስጥ ሲል እየተናገረ ያለው ስለ አራማይክ ነው ማለት ነው። (5፡2፤ 19፡13፣ 17፣ 20፤ 20፡16፤ *ራዕ* 9፡11፤ 16፡16)። ኢየሱስ የተናገራቸው ዓረፍተ ነገሮች ሁሉ በአራማይክ ቋንቋ የተናገራው ነበሩ።

1. *ታሊተሃ ኩም ማር* 5፡4
2. *ኤፌራታ ማር* 7፡34
3. *ኤሎሄ ኣሌሂ ላማ ሳባክታኒ ማር* 15፡34

5፡4 ይህ ቁጥር (3ለ-4) ያለው በኋላ ላይ ጸሐፊት የሰጡት አስተያየት ነው።

1. ህሙማን ሁሉ በመጠመቂያው መሆናቸውን
2. ይህ ሰው በዚያ ስፍራ ለረጅም ጊዜ ለምን እንደቆየ
3. በውሃ ውስጥ እንዲያኖረው ለምን ሌላ ሰው እንዳስፈለገው ቁ 7

ይህ የአሁድ ተረት (አፈታሪክ) መሆኑ ግልፅ ነው። ይህ ጥቅስ በመጀመሪያው የዮሐንስ ወንጌል ውስጥ አይገኝም ለዚህ ጥቅል አለመካተት በማስረጃነት የሚቀርበው፤

1. በ $P^{75}$፣N፣B፣C* እና D ምንጮች ውስጥ ስለማይገኝ
2. ጥቅሱ ከመጀመሪያውም እንደልነበረ ለማሳየት እንዲቻል በኃላ በተጨመሩት ከ20 በላይ በሚሆኑት የግሪክ ምንጮች ላይ ኮከባዊ ምልክት መደረጉ
3. በዚህ አጭር ጥቅስ በዮሐንስ ፅሑፎች ላይ ያልተለመዱ በርካታ ስያሜዎች መጠቀሳቸው የሚሉት ናቸው።

ይህ ጥቅስ በA፣$C^3$፣k እና L እንዲሁም በበርካታ ቀደምት የግሪክ ምንጮች ውስጥ ተካቷል። ከዚህም ባሻገር ጥቅሱ *በዲያትሳሮን* (180 ዓ.ም አካባቢ) እና በተርቱልያን ፅሑፎች ውስጥ (200 ዓ.ም)፤ በአምብሮስ፣ ክርይሶስተም እና በሳይረም ውስጥም ተካቷል። ይህም የሚሳየው የጥንት መሆኑን እንጂ በመንፈስ ምሪት በተፃፈው የዮሐንስ ወንጌል ውስጥ መካተቱን አይደለም። ጥቅሱ በኬ.ጀ.ቪ.ኤን.አር.ኤስ.ቢ. (በ1995 ተሻሽሎ የቀረበው፣ በቅንፎች ውስጥ ተቀምጧል)፣ እና በNKJV፤ ነገር ግን በNASB (1970)ተገድፏል)፣ኤን.አር፣ኤስ፣ቪ፣ኤን፣ጄ፣ቢ፤አር፣ኢ፣ቢ፤የኤን.ኢቲ መጽሐፍቅዱስ፤እና ከአዲስ መደበኛ ትርጉም ውስጥም ተካቷል።

የተለያዩ መልክ ባላቸው ምንጮች ላይ ጥሩ የሆነ ሐሳብን ለማግኘት እንዲረዳዎት የወንጌላዊያን መፃህፍት ሐያሲ የሆነውን የጎርደን ፊ ን፦ *To what End Exegesis* የሚለውን መፅሐፉን ገጽ 17-28 ን ይመልከቱ።

5፡5-6 ኢየሱስ ይህንን ሰው እንደመረጠው ለእኛ ግልጽ አይደለም። ምናልባት በዚያ ስፍራ ለረጅም ጊዜ መቆየቱ ሊሆን ይችላል። በዚህ ሰው በኩል ትንሽ እምነት ብቻ ነበር የሚጠበቀው። እንደሚታየው ኢየሱስ የአይሁድ መሪዎችን ትንሽ ልገስጻቸው የፈለገ ይመስላል። ይህ የራስን መሲሕት ለመናገር ትንሽ ዕድል ይፈጥርለታል። በኢሰ 35፡6 ላይ የመጨረሻው ዘመን ላይ የሚናገረው ጥቅስ ከመስሑ መፈወስ ጋር ይያያዛል።

ኢየሱስ ያከናወናቸው ብዙዎቹ ተአማራት የተደረጉት ለግለሰቦቹ ጥቅም ሳይሆን ለሚመለከቱት ጥቅም ሲባል ነው።

1. ደቀ መዛሙርቱ
2. የአይሁድ ባለ ስልጣናት
3. ለሕዝቡ

ወንጌላት ኢየሱስ ማን እንደሆነ ለማሳየት የተወሰኑ ተአምራትን መርጠውልናል። እነዚህ ተግባሮቹ የእርሱን የእለት ተዕለት ተግባራት የሚያሳዩ ናቸው። ማሳየት የፈለጉት

1. የእርሱን ማንነት
2. ርህራሄውን
3. ኃይሉን

4. ስልጣኑን
5. የአባቱን ግልጽ መገለጥ
6. የመሲሑን ዘመን ግልጽ መገለጥ

5፡8 **"ተነሣና አልጋህን ተሸክመህ ሂድ አለው"** ይህ ትዕዛዝ ነው፡፡
1. የአሁን ጊዜ ትእዛዝ አዘል ድርጊት ገላጭ ግሥ
2. የግሪኩ ትዕዛዝ አዘል ድርጊት ገላጭ ግሥ የሚከተለው
3. ሌላ የአሁን ጊዜ ትዕዛዝ አዘል ድርጊት ገላጭ ግሥ

ፍራሹ ብዙውን ጊዜ ድሆች ለመተኛት የሚጠቀሙት የልብስ ትራስ ነው፡፡ ለእነዚህ የታመሙ፣ አካለ ስንኩላን እና ሽባ የሆኑ ሰዎች በቀን ውሏቸው ፍራሹ እንደመቀመጫ ያገለግላቸዋል (ማር 2፡4፤9፡11፤12፤6፡55፤ ሐዋ 9፡33 ን ያስ)፡፡

| የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 5፡9b-18 |
|---|
| *ያም ቀን ሰንበት ነበረ፡፡ ስለዚህ አይሁድ የተፈወሰውን ሰው፡፡ ሰንበት ነው አልጋህንም ልትሸከም አልተፈቀደልህም አሉት፡፡ እርሱ ግን፦ ያዳነኝ ያ ሰው፡፡ አልጋህን ተሸክመህ ሂድ አለኝ ብሎ መለሰላቸው፡፡ እርሱም፦ አልጋህን ተሸክመህ ሂድ ያለህ ሰው ማን ነው? ብለው ጠየቁት፡፡ ዳሩ ግን በዚያ ስፍራ ሕዝብ ስለ ነበሩ ኢየሱስ ፈቀቅ ብሎ ነበርና የተፈወሰው ሰው ማን እንደ ሆነ አላወቀም፡፡ ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በመቅደስ አገኘውና፡፡ እነሆ: ድነሃል፤ ከዚህ የሚብስ እንዳይደርስብህ ወደ ፊት ኃጢአት አትሥራ አለው፡፡ ሰውዬው ሄዶ ያዳነው ኢየሱስ እንደ ሆነ ለአይሁድ ነገረ፡፡ ስለዚህም በሰንበት ይህን ስላደረገ አይሁድ ኢየሱስን ያሳድዱት ነበር ሊገድሉትም ይፈልጉ ነበር፡፡ ኢየሱስ ግን፦ አባቴ እስከ ዛሬ ይሠራል እኔም ደግሞ እሠራለሁ ብሎ መለሰላቸው፡፡ እንግዲህ ሰንበትን ስለ ሻረ ብቻ አይደለም: ነገር ግን ደግሞ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሎ፡፡ እግዚአብሔር አባቴ ነው ስላለ: ስለዚህ አይሁድ ሊገድሉት አብዝተው ይፈልጉት ነበር፡፡* |

5፡9ለ **"ያም ቀን ሰንበት ነበረ"** የአይሁድ መሪዎች በሽተኛው ሰው ፈውስን ስላገኘ አልተደሰቱም ነገር ግን ከሰንበት ጋር የተገናኘው ሕጋቸው ስለተጣሰ በጣም ተበሳጩ (ቁ. 16፣ 18፣ ማቴ 7፡1-23)

የኢየሱስ በሰንበት መፈወስ በሁለት መንገድ ልገላጽ ይችላል፡፡
1. ኢየሱስ በየዕለቱ ይፈውስ ነበር ነገር ግን ችግሩ የፈጠረው በሰንበት ዕለት መፈወሱ ነው
2. ይህ ሁኔታ ግጭት እንዲፈጥር እና ከሃይማኖት መሪዎች ጋር ስነ መለኮታዊ ክርክር የማድረግ እድል እንድፈጥረለት በዚህ ቀን ለመፈወስ ፈለገ፡፡

ብዙ ጊዜ ኢየሱስ በሰንበት ዕለት ይፈውስ ነበር (ማቴ 12፡9-14፤ ማር 1፡29-31፤ 3፡1-6፤ ሉቃ 6፡6-11፤ 14፡1-6፤ ዮሐ 5፡9-18፤ 9፡14)፡፡ ኢየሱስ አጋንንትን በሰንበት እለት ያወጣ ነበር (ማር 1፡21-28)፤ ሉቃ 13፡10-17)፡፡ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ በሰንበት እለት ስለ መብላታቸው ተሞአግቶላቸዋል (ማቴ 12፡1-8፤ ማር 2፡23-28)፡፡ ኢየሱስ በምኩራብ ውስጥ ጭቅጭቅ የሚያስነሳ ሀሳብን አንስቶ ነበር (ሉቃ 4፡16-30፤ ዮሐ 7፡14-24)፡፡

5፡13 **"ኢየሱስ ፈቀቅ ብሎ ነበርና"** ኢየሱስ በዘመኑ ከነበሩ አይሁዳዊያ አንዱን ይመስል ነበር፡፡ ከሕዝቡ መካከል አይለይም ነበር፡፡

5፡14

| | |
|---|---|
| NASB፣ NRSV፣ NJB | *"ከአሁን በኋላ ኃጢአትን አታድርግ"* |
| NKJV | *"ኃጢአትን አታድርግ"* |
| TEV | *"ኃጢአት ማድረግ አቁም"* |

ይህ አሉታዊ ቦዝ አንቀፅ ያለው የአሁን ጊዜ ትዕዛዝ አዛል ድርጊት ገላጭ ግሥ ሲሆን ብዙውን ጊዜ ያለው ትርጉም በሂደት ላይ ያለን ድርጊት ስለማቆም የሚናገር ሲሆን በዚህ አውድ ግን እንዲህ አይነት ትርጉም ያለው አይመስልም (NET መጽሐፍ ቅዱስ፤ ገጽ 1907፤ ቁጥር8 )፡፡

በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የነበሩት አይሁዳዊያን የሥነ-መለኮታዊ ምህራን ሕመም ከኃጢአት ጋር እንደሚዛመድ ያምኑ ነበር (ያዕቆብ 5፡14-15 ን ያስ)፡፡ ይህ ሁኔታ ኢየሱስ አይነሥውር ሆኖ የተወለደውን ሰው ከመፈወሱ አንፃር (ዮሐንስ 9 ን ያስ.) እና በሉቃስ 13፡1-4 ላይ ከተናገረው አንጻር ስለሁሉም አይነት ሕመሞች በቂ የሆነን ግንዛቤ የሚሰጥ አይደለም፡፡

ኢየሱስ አሁንም ቢሆን የዚህ ሰው መንፈሳዊ ሕይወት ጉዳይ ግድ ብሎታል፡፡ የእኛ ድርጊቶች ልባችንን እና እምነታችንን ያንፀባርቃሉ መጽፍቅዱሳዊ እምነት በድርጊት የሚገለፅ እንዲሁም በስሜታችንም የምንገልፀው ነው (ልባዊ)፣ ማመን ነው፤ ደግሞም ማድረግም ነው፡፡

በዘመናችን አካላዊ ፈውስን በሚመለከት በቤተክርስትያን ዘንድ እንዲህ አይነት ትኩረት ይታያል፡፡ እግዚአብሔር ዛሬም ቢሆን በእርግጥ ያፈውሳል፡፡ ነገር ግን መለኮታዊ ፈውስ በምን ፈፅማቸው ድርጊቶች ቅደም ተከተል ላይ እና በሕይወት ዘይቤያችን መንፈሳዊ ለውጥን ሊያመጣ ይገባል፡፡ ለዚህ ጥሩ ጥያቄ ሊሆን የሚችለው ምናልባት "ለመፈወስ የፈለግህበት/ሽበት ምክንያቱ ምን ይሆን? "የሚል ሳይሆን አይቀርም"

**ልዩ ርዕስ፡ ፈውስ በሁሉም ዘመናት ውስጥ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነውን**

1. ፈውስ ኢየስስ እና የሐዋሪያቱ አገልግሎት ዋና ክፍል ነበር
2. በመጀመሪያ ደረጃ ይህ ስለ እግዚአብሔር እና የእርሱ መንግስት ያላቸው የለውጥ መልዕክት ማረጋገጫ ነበር
3. ለተጎዱ ሰዎች እግዚብሔር ያለውን ልብ ያሳያል
4. እግዚአብሔር አልተለወጠም (ሚል 3፡6) እንዲሁም አሁንም በፍቅር እና በመፈወስ ይሠራል
5. ፈውስ ያልሆነባው የተወሰኑ ክፍሎች በምሳሌነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናገኛን
   ሀ. ጳውሎስ 2 ቆሮ 12፡7-10
   ለ. ትሮፊሙስ 2 ጢሞ 4፡20
6. በመምህራን እና በያዕቆብ ውስጥ ኃጢአት እና በሽታ ተቆራኝተው እናገኛለን (ዮሐ 9፡2፤ ያዕ 5፡13-18)
7. ፈውስ የአዲስ ኪዳን መብት አይደለም፡፡ በኢሳ 53 እና በዘም 103 ላይ የተገለጸው የመስዋእት አካል አይደለም፡፡
8. አንዳንዶች ለምን እንደሚፈወሱ እና ሌሎች ለምን እንደማይፈወሱ እውነተኛ ምስጥር ነው፡፡
9. በዚህም ዘመን ፈውስ ልኖር ይችላል፣ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ዘመን ቁጥሩ እጅግ ጨምሮ ነበር፤ ይህ ቁጥርም እርሱ መመለሻ አከባቢም እንደገና ይጨምራል፡፡

5፡15 **"ሰውዬው ሄዶ ያዳነው ኢየሱስ እንደ ሆነ ለአይሁድ ነገረ"** ለአይድ መሪዎች ለምን መንገር እንደፈለገ በእርግጠኝነት መናር አይቻልም፡፡

1. ምንም ያሰበበት አይመስልም፤ ይህ ዝም ብሎ የተደረገ ነገር የሚያሳየን ፈውስ ሁል ጊዜ የሚጀምረው እና የሚፈጽመው በእምነት ብቻ አይደለም ማለት ነው፡፡
2. ኢየሱስ ያንን እንነዲያደረግ ነገሮታል (ማቴ 8፡4፤ ማር 1፡44፤ ሉቃ 5፡14፤ 17፡4)

5፡16 **"ስለዚህም በሰንበት ይህን ስላደረገ"** ይህ ግን በሰንበት ያደረገው ፈውስ የመጀመሪያም የመጨረሻም አልነበረም፡፡

5፡17

| | |
|---|---|
| NASB፣ | **"ነገር ግን እርሱ ግን እንዲህ ብሎ መለሰላቸው"** |
| NRSV፣ NKJV | **"ኢየሱስ ግን እንዲህ ብሎ መለሰላቸው"** |
| NJB | **"እርሱ ለእነርሱ የመለሰላቸው መልስ"** |

የጥንት ቅጂዎችን የጻፉት ጸሐፊት ከዚህ በታች ያሉትን የማድረግ ዝንባሌ አላቸው

1. ስዋሰውን የማቅላል
2. የሚታወቁ ነገሮችን መጻፊ
3. ሀረጉ ትክክለኛ ስዋሰውን በጠበቀ መልኩ

በቁጥር 17 ላይ ያለው ዬትኛው ትክክል እንደሆነ ማወቅ አስቸጋር ነው፡፡

1. "እርሱ ግን.." $P^{75}$፣N፣B፣W
2. "ኢየሱስ ግን.." $P^{66}$፣A፣D፣L
3. "ጌታ ግን.." ወይም "ጌታ ኢየሱስ"- የሶርያ ትርጉሞች

የዩ.ቢ.ኤስ[4] መጽሐፍቅዱስ ለቁጥር 2 የ "C" ደረጃን ይሰጠዋል (ለመወሰን የሚያስቸግር ማለት ነው)፡፡

▣ **"አባቴ እስከ ዛሬ ይሠራል እኔም ደግሞ እሠራለሁ"** ኢየሱስ ገለጸላቸው እግዘኢብሔር መልካሙን ሥራ በሰንበት እለት መስራቱን አላቆመም ስለዚህም ልጁም አያቆምም፡፡ ይህ ኢየሱስ ከአባቱ ጋር ያለውን ልዩ ግንኙነት መረዳቱን የሚያረጋግጥልን ነው (ቁ 19-29)፡፡

የአይሁዳዊያን አንድ አምላክነት ጽንሰ ሀሳብ (ዘዳ 6፡4) በተግባር በዚህች ዓም ላይ ባለ "የአንድ ክስተት" በሚባለው መንገድ ልገለጽ ይቻላል (መሳ 9፡23፤ እዮ 2፡10፣ መክ 7፡14፤ ኢሳ 45፡7፤ 50፡16፤ ሰቆ. ኤር 3፡33-38፤ አሞ 3፡6)፡፡ እነዚህ ሁሉ ድርግቶች የአንድ እውነተና አምላክ ተገብሮች ናቸው፡፡ ኢየሱስ በአለም ላይ በሚደረጉ ድርግቶች ሁሉ ውስጥ የሁለት የዚህ ተግባር ፈጻሚዎች አሉ ሲል እያረጋገጠ ያለው ለመለኮታዊ ተግባራት ሁለት ስብእናዎች መኖራቸውን፡፡ ይህ ስላሴን ለመረዳት ትልቅ ችግር ነው፡፡ አንድ አምላክ ነገር ግን ሦስት አካላት መገለጣቸውን እንመለከታለን (ማቴ 3፡16-17፣ 28፡19፤ ዮሐ 14፡26፤ ሐዋ 2፡33-34፤ሮሜ 8፡9-10፤ 1ቆሮ 12፡4-6፤ 2ቆረ 1፡21-22፤ 13፡14፤ ኤፌ 1፡3-14፤ 2፡18፤ 4፡4-6፤ ቲቶ 3፡4-6፤ 1ጴጥ 12)፡፡ በ14፡26 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ስላሴ ይመልከቱ፡፡

5፡18 **"ስለዚህም በዚህ ምክንያት አይሁድ ይበልጥ እርሱን ልገሉት ፈለጉ"** አይሁድ ኢየሱስን ልገሉ የፈለጉበት ሁለት ምክንያት ነበራቸው፡፡

1. የሰንት ሕጋቸውን በአደባባይ ሠብሯል
2. ከንግግሩ እንደተረዱ እራሱን ከአምላክ ጋር አስተካክሏል (8፡58-59፤ 10፡33፤ 19፡7)፡፡

**የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 5፡19-23**
**ስለዚህ ኢየሱስ መለሰ እንዲህም አላቸው፦ እውነት እውነት እላችኋለሁ፡ አብ ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ ወልድ ከራሱ ሊያደርግ ምንም አይችልም፤ ያ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ ይህን እንዲሁ ያደርጋልና። አብ ወልድን ይወዳልና፡ የሚያደርገውንም ሁሉ ያሳየዋል፤ እናንተም ትደነቁ ዘንድ ከዚህ የሚበልጥ ሥራ ያሳየዋል። አብ ሙታንን እንደሚያነሣ ሕይወትም እንደሚሰጣቸው፡ እንዲሁ ወልድ ደግሞ ለሚወዳቸው ሕይወትን ይሰጣቸዋል። ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ፡ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም። ወልድን የማያከብር የላከውን አብን አያከብርም።**

**5፡19፣ 24፣25 "እውነት እውነት"** ይህ "አሜን አሜን"እንደ ማለት ነው። "አሜን" የሚለው ቃል የዕብራይስጥ ትርጉሙ ነው። በመጀመሪያ የቃሉ ትርጓሜ የነበረው የሚታመን ማለት ነው። ከዚያም እውነትን ለማረጋገጥ መዋል ጀመረ። በዓረፍተ ነገሮች መጀመሪያ ላይ ይህን ኢየሱስ ብቻ ነበር የሚጠቀመው። በጣም ጠቃሚ የሆኑ ንግግሮቹን በእነዚህ ቃላት ይጀምር ነበር። ይህንን ዓይነቱን የኢየሱስን ንግግር በጽሑፍ ያስቀመጠልን ብቸኛው ሰው ዮሐንስ ነው። በ1፡51 ላይ ያለውን አሜን የተሰኘውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።

**5፡19 "ልጅ"** "ልጅ" የሚለው ቃል ተደጋግሞ መጠቀሱ ሥነ መለኮታዊ ፋይዳ አለው።በዚህ አውድ ውስጥ በተንሹ 8 ጊዜ ያህል ተጠቅሶ እንገኘዋለን። እርሱ ከአባቱ ጋር ያለውን ልዩ ግንኙነት የሚያሳይ ሲሆን እንዲሁም "የሰው ልጅ" እና "የእግዘአብሔር ልጅ" በሚል ማእረጎች ላይም ይነጸባረቃል።

▣ ***"ወልድ ከራሱ ሊያደርግ ምንም አይችልም"*** አዲስ ኪዳን ኢየሱስን ብዙ ጊዜ ተትንሽ ግራ በሚያጋባ ቦታ ላይ ማስቀመጡ እውነት ነው። በዚህ ክፍልም

1. ከአብ ጋር የነበረው እርሱ ነው (1፡1፤ 5፡18፤ 10፡30፣ 34-38፤ 14፡9-10፤ 20፡28)
2. ከአብ የተለየ ነው (1፡2፣ 14፣ 18፤ 5፡19-23፤ 8፡28፤ 10፡25፣ 29፤ 14፡10፣ 11፣ 12፣ 13፣ 16፤ 17፡1-2)
3. እንዲያው እርሱ ለእርሱ አገልጋይ ነው (5፡20፣ 30፤ 8፡28፤ 12፡49፤ 14፡28፤ 15፡10፣ 19-24፤ 17፡8)

ይህ ምናባትም ኢየሱስ ፍጹም አምላክ እንደሆነ ነገር ግን የተለየ፣ የተለየ አካል እንዳለው እና ዘላለማዊ የመለኮት መገለጫ እንደሆነ ለማሳየት ሊሆን ይችላል።

በጆን ሬይሞንድ ኢ-ብራውን የተፃፈው የ The Jerome Biblical Commentary) ማብራሪያ ላይ ጥሩ የሆነ ጥቆማ ተስጥቶበታል፤

"ኢየሱስ ከአብ ማንሱን የገለጠበት አባባል እርሱ የተናገራቸው ቃላት ስብእናውን ብቻ ያለክታል ብሎ ማስብ ትክክል አይደለም… ምክንያቱም ከዮሐንስ ነገር-ክርስቶስ ጋር የሚተላለፍ በመሆኑ። ከዚህ ይልቅ ኢየሱ ትኩረት ያደረገው በአብና በወልድ አሠራር መካከል ያውን ፍፁም የሆነ አንድነትን የሚያመለክት ነበር፤ ይህም ፍፁም የሆነ የባህርይ አንድነትን የሚያሳይ ነው። ተመሳሳይ ሒደትም በ16:12 ላይ መንፈስ ቅዱስንና ወልድን ለማዛመድ ተጠቅሷል። ነገር ግን በዚህ ወንጌል ውስጥ ሠላሴ እንደማይጨበጥ ሥነ-መለኮት ተደርጎም አልታየም ነገር ግን ሁል ጊዜም ቢሆን ያለውን አቀራረብ የምናጤነው ከድነት አንፃር ካለው ዝምድና እንጂ"

▣ ***"አብ ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ"*** የሰው ልጆች እግዚአብሔርን አዬተውት አያውቁም (ቁ 37 እና 1፡18) ነገር ግን ወልድ ግን ከእርሱ ጋር ቅርበት እንዳለው፣ እርሱ በግሉ እንደሚያውቀው እየተናገረ ው (1፡1-3)።

▣ ***"ያ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ ይህን እንዲሁ ያደርጋልና"*** በኢየሱስ ተግባራት እና ትምህርቶች ውስጥ ሰዎች የማይታየውን አምላክ መመልከት ይችላሉ። (ቆላ 1፡15፤ ዕብ 1፡3)።

**5፡20 "አብ ወልድን ይወዳልና፡ *የሚያደርገውንም ሁሉ ያሳየዋል*"** እነዚህ ሁለቱ የአሁን ጊዜ ድርጊት ገላጭ አመልካች ግሦች ሲሆኑ ቀጣይነት ያውን ድርጊት ያስረዳሉ። ይህ ፍቅር (ፊሎ) ለሚለው የግሪኩ ስያሜ ነው። አንድ ሰው ልክ እንደ 3፡35 አጋፔ የሚለውን ስያሜ ሊጠብቅ ይችላል። ፍቅር ለሚለው ቃል የተሰጡት እነዚህ ሁለት ስያሜዎች በኮይኔግሪክ የሴሜቲክ መደራረብ ይታይባቸዋል (ዲ.ኤ.ካርስን፤ *Exegetical Fallncies* 2ኛ እትም፤ ገጽ 32-33፤እና ኤፍ.ኤፍ. ብሩስ *Answers to Questions*፤ ገጽ 73 ን ይመለከቱ)።

▣ ***"ከዚህ የሚበልጥ ሥራ"*** በዚህ አውድ ውስጥ ሙታንን ማስነሳት (ቁ 21፣ 25-26) እና ፍርድን መስጠት (ቁ. 22፣ 27) ናቸው።

▣ ***"እናንተም ትደነቁ ዘንድ"*** ይህ ዓረፍተ ነገር እንደሚያሳየው የተአምራቶቹ አላማ አይሁዳዊያን ኢየሱስ ልጅ እንደሆነ ያምኑ ዘንድ ነው። (ቁ 23፤ ሐዋ 13፡41 (እንባ 1፡5)

**5፡21 "አብ *ሙታንን እንደሚያነሣ* . . . እንዲሁ ወልድ"** በብሉይ ኪዳን ሕይወት መስጠት የሚችለው ያሕዌ ብቻ ነው (ዘዳ 32፡39)። ኢየሱስ ሙታንን የሚያስነሳ ከሆነ ከያሕዌ ጋር እኩል ነው ማለት ነው (ቁ 26) ኢየሱስ ዘላለማዊ ሕይወትን አሁን ይሰጣል (2 ቆረሮ 5፡7፤ ቆላ 1፡13)ይህ ደግሞ ከአዲሱ ዘመን ውስጥ ከሚገለጠው ሕይወት ጋር የተቆራኘ ነው ቁ

26 (1 ተሰለ 4፡13-118)፡፡ ዮሐንስ ከኢየሱስ ጋር ያለውን ሕብረት ምንም እንኳን ወደፊት በሕብረት የሚፈፀም ክስተት ቢኖርም (ፍርድ እና ድነት) አሁን ግን ይህንን ሁኔታ በግለሰብ ደረጃ ይገልፀዋል፡፡

▣ **"ወልድ ደግሞ ለሚወዳቸው ሕይወትን ይሰጣቸዋል"** ወልድ ሕይወት የሚሰጠው ለነማን ነው; ይህ ክፍል ለካልቬንስቶች አስተምህሮ ማረጋገጫ መጠቀም ተገቢ አይደለም ነገር ግን ይህ ክፍል የሚያስተምረው በኢየሱስ ማመን ሕይወተትን እንደሚያስገኝ ነው (1፡12፤ 3፡16)፡፡ ችግሩ ያለው በ6፡44፣ 65 ላይ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ "ሁሉንም" ወይስ "እንዳንዶቹን" ነው የሚመርጠው፤እኔ እንደማምነው የወደቀው የሰው ልጅ መንፈሳዊነትን መጀመር አይችልም ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ስጠራው በንሰሓ፣ በእምነት፣ በመታዘዝ እና በመጽናት ምለሽ መስጠት አለበት፡፡ ምስጥሩ ወንጌልን የሚሰሙ አንዳንድ ሰዎች ለምን "አይ" የሚል ምላሽ ይሰጣሉ፡፡ ይህንን እኔ "ያለማመን ምስጥር" ብዬ እጠራዋለሁ፡፡ ይህ ወንጌላት "ይቅር የማይባለው ኃጢአት" እና በ1 ዮሐ ላይ "ለሞት የሚያበቃ ኃጢአት" ተብሎ የተለጸው ነው ልዩ ርዕስ 1 ዮሐ 5፡16፡፡

---

**ልዩ ርዕስ፡ "ይቅር የማይባ ኃጢአት" የሚለውን በትክክል ለመፍታት ልንከተለው የሚገባን ሥነ መለኮታዊ መርሆዎች**

- ሀ. ወንጌላት አይሁዳዊ አውድን እንደሚያሳዩ አትዘንጉ
  1. ሁለት ዓይነት ኃጢአቶች አሉ (ዘሌ 4፡2፣ 22፣ 27፤ 5፡15፣ 17-19፤ ዘኍ 15፡27-31፤ ዘዳ 1፡43፤ 17፡12-13)
     - ሀ. ያልታቀደ
     - ለ. የታቀደ
  2. ከጴንጤቆስጤ ቀን በፊት የነበረው የአይሁዳዊያ ሁኔታ (የወንጌል እና የመንፈስ ቅዱስ ሙልዓት ገና ሙሉ በሙሉ አልተፈጸመም ነበር)
- ለ. የማርቆስን ወንጌል ስነ ጽሑፋዊ አውዱን አስተውል
  1. የኢየሱስ የራሱ ወላጆች አለማመናቸው (3፡31-32)
  2. የፈርሳዊያን አለማመን (2፡24፤ 3፡1፣ 6፣ 22)
- ሐ. "የሰው ልጅ" የሚለው ስም ‹ወደ "የሰዎች ልጆች" ወደሚል ስም የተቀየረበትን ቦታ አነጻጽር
  1. ማቴ 12፡22-37 (12፡32 "በሰው ልጅ ላይ የተነገረበት"
  2. ሉቃ 11፡14-26፤ 12፡8-12 12፡10
  3. ማር 3፡28 ("የሰው ልጆች የሰሩት ኃጢአት ሁሉ ይሰረያል")

---

5፡22 በጣምራ የተገለፀው ጠንካራ እና የድርጊቱን መጠናቀቅ የሚያመለክተው ግሥ ፍርድን ማድረግ ለወለድ ተላልፎ የተሰጠ መሆኑን በአፅንኦት ይናገራል (5፡25፤ ሐዋ10፡42፤17፡31፤ 2ጢሞ4፡1፤ጴጥ4፡5)፡፡ በዚህ ጥቅስ እና በዮሐንስ 13፡17 መካከል ያለው ጉልህ ቅራኔ የሚያሳየው ኢየሱስ በእነሱስ ክርስቶስ በሚሰጡት ምላሽ የተነሳ በራሳቸው ላይ እንደሚፈርዱ ያሣያል፡፡ የኢየሱስ የሥነ-ፍፃሜ ፍርድ (በማያምኑት ላይ የሚፈርደው) የማያምኑት ኢየሱስን በመቀበላቸውና ባመቀበላቸው ላይ የጠወሰነ ነው፡፡

የዘላለም ሕይወት መስጠት እና የዘላለም የፍርድ መስጠት የ3፡17-21፡36 ጭብጥ ነው፡፡ በክርስቶስ የተገለጠውን የእግዚአብሔር ፍቅር ሰዎች ሲቃወሙት ፍቅሩም ወደ ቁጣ ይለወጣል! ሁለት አማራጮች ብቻ አሉ፡- የዘላለም ሕይወትን ለመቀበል ያለው መንገድ አንድ ብቻ ነው፡፡ በክርስቶስ ማመን (10፡1-10፤14፡6፤1 ዮሐንስ 5፡9-12)!

5፡23 **"ሰዎች ሁሉ . . . ወልድን ያከብሩት ዘንድ"** ይህ ሁሉን የሚያጠቃልል ሀረግ ስለሆነ በመጨረሻው ዘመን ያለ ሁኔታን ያመለክታል (ፊል 2፡9-11)፡፡

▣ **"ወልድን የማያከብር የላከውን አብን አያከብርም"** ይህ ዓረፍተ ነገር በ1 ዮሐ 5፡12 ካለው ጋር አንድ ነው፡፡ ወልድን የማያውቅ አሰው አብንም አያውቀመውም፡፡ እንዲሁም ልጅን የማያከክብር ወይም የማያመሰግን ሰው ወልድን አያከብረውም እንዲሁም አያመሰግነውም፡፡

---

**የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 5፡24-29**

**እውነት እውነት እላችኋለሁ: ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው: ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም፡፡ እውነት እውነት እላችኋለሁ: ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል እርሱም አሁን ነው፤ የሚሰሙትም በሕይወት ይኖራሉ፡፡ አብ በራሱ ሕይወት እንዳለው እንዲሁ ደግሞ ለወልድ በራሱ ሕይወት እንዲኖረው ሰጥቶታልና፡፡ የሰው ልጅም ስለ ሆነ ይፈርድ ዘንድ ሥልጣን ሰጠው፡፡የሰው ልጅም ስለ ሆነ ይፈርድ ዘንድ ሥልጣን ሰጠው፡፡**

---

▣ **"እውነት እውነት"** ይህ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ እጅግ ወሳኝ የሆኑ ዓረፍተ ነገሮችን መጀመሪያ ቃል ነው፡፡

▣ ***"ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው"*** ይህ በእግዚአብሔር አብ ላይ ያለ እምነትን ላይ አጽኖት  (ልዩ ርዕስ 3፡23 ይመልከቱ፡፡) የሚሰጥ ሲሆን ይህ ደግሞ የሚገለጸው በልጁ በማመን ነው (1ዮሐ 5፡9-12)፡፡ በተመሳሳይ ወንጌላት ውስጥ የዘላለም ሕይወት ለወፊት የሚናገኛው በተስፋ የሚንጠብቀው ነገር ነው ነገር ግን በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ይህ ሕይወት የአሁን ጊዜ እውነታ ነው (8፡51፤ 11፡25)፡፡ *"መስማት"* የሚለው *ቃል* ምናልባት የዕብራይስጡ ሼማ ሊሆን ይችላል ትርጓማም *"ትታዘዙ ዘንድ አድምጡ"* ማለት ነው (ዘዳ 6፡4)፡፡

▣ **"የላከኝንም"**አፖስቴሎ የሚለው *ግሥ* (የግሪኩ ድርጊት ገላጭ ቦዝ አንቀፅ) *"ሐዋርያ"* ለሚለው *ቃል* መሠረቱ ነው (ቁ. 36-37)፡፡ ይህ *ግሥ* "በተወሰነ ተልዕኮ የሚላክ ወኪል ባለስልጠን" በሚል ድባብ በአይሁድ የኃይማኖት አስተማሪዎች ይጠቀስ ነበር፡፡ ይህ ስያሜ አብ ኢየሱስ አባቱን ወክሎ መላኩን ለማሳየት በዮሐንስ ወንጌል ውስጥዎ ተጠቅሷል፡፡ በ4፡34 ላይ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ መላክ (አፖስትሎ)**

ይህ መላክን የሚያመለክት የተለመደ የግሪ *ቃል* ነው፡፡ ይህ ብዙ ስነ መለኮታዊ አጠቃቀም አለው፡፡

1. የአይሁድ መምህራን የአንድን ድርጅት ለመወከል የተጠራ እና የተላከ ሰውን ለማመልክት ይጠቀሙበታል፤ (2 ቆሮ 5፡20)
2. ወንጌላት ኢየሱስ በአብ እንደ ተላከ ይናገራሉ፡፡ በዮሐንስ ውስጥ የሚገኘው *ቃል* የመሲሕነት መገለጫ ነው (ከማቴ 10፡40፤ 15፡24፤ ማር 9፡37፤ ሉቃ 9፡48 እና በተለይም  ከዮሐ 4፡34፤ 5፡24፣ 30፣ 36-38፤ 6፡ 29፣ 38-40፣ 57፤ 7፡29፤8፡42፤ 10፡36፤ 11፡42፤ 17፡3፣ 8፣ 18፣21፣ 23፣ 25፤ 20፡21 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡ እንዲሁም ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን መላኩን ለማመልከት ውሏል (ዮሐ 17፡18፤ 20፡21)
3. አዲስ ኪዳን ይህን *ቃል* ለደቀ መዛሙርቱ ተጠቅሟል
   ሀ. በመጀመሪያ ዐስራ ሁለቱን ለማመለከት (ሉቃ 6፡13፤ ሐዋ 1፡21-22)
   ለ. ሐዋርያትን ያግዙ እና አብረው ይሠሩ የነበሩ ሰዎችን ለማመልከት ውሏል
      1) ባርናባስ (ሐዋ 14፡4፣ 14)
      2) ለአንዲራኒቆንና ለዩልያን ሮሜ 16፡7
      3) አፖሎስ (1 ቆሮ 4፡6-9)
      4) የጌታ ወንድም ያዕቆብ (ገላ 1፡19)
      5) ስልዋኖስ ጢሞቴዎስም: 1 ተሰ 2፡1
      6) ምንአልባም ቲቶ ፊል 2፡25
      7) አፍሮዲጡን ፊል 2፡25
   ሐ. ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠ ቀጣይነት ያለው ስጦታ (1 ቆሮ 12፡28-29፤ ኤፌ 4፡11)
4. ጳውሎስ ይህን ማዕረግ የክርስቶስ ተወካይ እንዲሆን በእግዚአብሔር መላኩን ለማመልከት ብዙ ጊዜ ተጠቅሞበት እናገኛን (ሮሜ 1፡1፤ 1ቆሮ 1፡1፤ 2ቆሮ1፡1፤ ገላ 1፡1፤ ኤፌ 1፡1፤ ቆላ 1ለ1 1 ጢሞ1፡1፤ 2 ጢሞ 1፡1፤ ቲቶ 1፡1)

▣ ***"ሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ"*** ይህ ክፍል የሚያመለክተው ያለፈው ነገር ማለፉን ነገር ግን አሁን ያለበት ሕይወት መሆኑን ነው፡፡ የእግዚአብሔር መንግስት የአሁን ጊዜ ናት ነገር ግን ወደ ፊትም ናት፤ ይህም እስከ ዘላለም ነው (ቁ 25-26 እና 1 ዮሐ 3፡14)፡፡ ቁጥር 25 የእግዚአብሔር መንግስት አሁን መሆኗን ያስረግጥልናል፡፡

**5፡25 "ሰዓት ይመጣል እርሱም አሁን ነው"** እንዲህ ያለው ንግግር የዮሐንስ ወንጌል መለያ ባህሪይ ነው፡፡ ቃላት እና ሀረጎች ሁለት ትርጓሜ አላቸው፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ "ሰዓት" የሚለው ቃል

1. የድነተ ሰዓት
2. የፍርድ ሰዓት

የዚህ ሰዓት የጊዜ ገደብ አሁን እና ወደ ፊት ነው (ቁ. 29፤ 6፡39፣ 44፣ 54)፡፡ አንድ ሰው ከኢየሱስ ጋር አሁን የሚያደርገው ነገር ለወዲት ምን እንደሚሆን ይወስናል፡፡ ድነት እና ፍርድ የአሁን ጊዜ ነባራዊ ሁኔታዎች ሲሆኑ ፍጻሜያቸው ግን ለወደፊት ነው (ቁ 28)፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ ሰዓቱ**

ሰዓት የሚለው *ቃል* በወንጌላት ውስጥ በብዙ መልኩ አገልገግሎት ላይ ውሏል

1. ጊዜን ለማመለክት (ማቴ 8፡13፤ ሉቃ 7፡21፤ ዮሐ 11፡9)
2. የመከራ እና የፈተና ጊዜን የሚያመለክት ዘይቤያዊ አነጋገር (ማቱ 10፡19፤ ማር 13፡11፤ ሉቃ 12፡12)
3. ኢየሱስ አገልግሎትን የጀመረበት ጊዜን የሚያመለክት ዘይቤያዊ አነጋገር (ዮሐ 2፡4፤ 4፡23)
4. የፍርድ ቀንን ለማመለከት የዋለ ዘይቤያዊ አነጋገር (ማቴ 24፡36፣ 44፤ 25፡13፤ ማር 13፡32፤ ዮሐ 5፡24፣ 28)
5. የኢየሱስን መከራ ለማመለከት የዋለ ዘይቤያዊ አነጋገር (ማቴ 25፡45፤ ማር 14፡35፣41፤ ዮሐ 7፡30፤ 8፡20፤ 12፡23፤ 27፤ 13፡1፤ 16፡32፤ 17፡1)

▣ ***"ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት"*** ቁጥር 25 የሚያወራው መንፈሳዊ ሞታንን ነው፤ ቁ 29 ደግሞ የሙታን አካላዊ ትንሳኤን ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሦስት አይነት ሞትን ያወራል፡፡

1. መንፈሳዊ ሞት (ዘፍ 3)
2. አካላዊ ሞ (ዘፍ 5)

3. ዘላለማዊ ሞት (ኤፎ 2:2፤ ራዕ 2:11፤ 2:6፣ 14) ወይም የእሳት ባህር፣ ገሃነም

ይህ የሰው ልጅ የሚለው ቃል ከተጠቀሰባቸው ጥቅት ስፍራዎች አንዱ ነው፡፡ በ1 ዮሐን 3:8 ላይ የተጠቀሰውን ልዩ ርዕስ ተመልከት፡፡ ይህ ሀረግ ብዙ ጊዜ አገልግሎት ላይ ያልዋለበት አንዱ ምክንያት ግሪካዊያን ባላቸው ሃይማታዊ አመለካከት ምክንያት ነው፡፡ ኦልምፖስ የተባለው የግሪክ አምላክ ሴትን እንደ ምስቱ በመውሰድ ልጅ ወልዷል፡፡ ነገር ግን የኢየሱስ የእግዚብሔር ልጅነት በግብረስጋ ግንኙነትን የተወለደ መሆኑን የሚያሳይ ሳይሆን ቅርበቱን ያሳያል፡፡ ይህ የአይሁዳዊያን ቤተሰባዊ ቋንቋ ነው፡፡ ኢየሱስ ለዚህ የአይሁዳዊያን መሪ በጣም ግልጽ የሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በመውሰድ አረጋግጦለታል (5:21፣ 26)

**5:26 "አብ በራሱ ሕይወት እንዳለው"** ይህ በዘጸ 3:14 ላይ የተገለጠው የያሕዌ ትርጉም ነው፡፡ ይህ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ስሙ ነው፡፡ ትርጓሜውም ሁል ጊዜ የሚኖር፣ ብቸኛው ነዋሪ ማለት ነው፡፡ በ6:20 የመለኮት ስም በምለው ስር ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

በብሉይ ኪዳን ውስጥ "ሕይወት" በራሱ ያው ያሕዌ ብቻ ነው (1ሞ 1:17፤ 6:16) እንዲሁም ለሌሎች የሚሰጠው እርሱ ብቻ ነው (እዮ 10:12፣ 33:4፤ መዝ 36:9)፡፡ ኢየሱስ ይህን ልዩ ኃይልን ለእርሱም እንደሰጠው ይነናገራል፡፡

▣ **"እንዲሁ ደግሞ ለወልድ በራሱ ሕይወት እንዲኖረው ሰጥቶታልና"** ይህ የኢየሱስን አምላክነት የሚያረጋግጥ ነው፡፡ (1:4፤ 1ዮሐ 5:11)

**5:27** ኢየሱስ በትክክል መፍረድ የሚችልበት (ስልጣን አለው 10:8፤ 17:2፤ 19:11) ምክንያት ፍጹም አምላክ እና ፍጹም ሰው ስለ ሆነ ነው፡፡ እርሱ ሰዎችን ሙሉ በሙሉ ያውቃቸዋል (ዕብ 4:15) እንዲሁም አምላክን ሙሉ በሙሉ ያውቀዋል (1:18፤ 5:30)፡፡

ኢየሱስ እራሱን የሰው ልጅ ብሎ በጠራበት ስፍራዎች ውስጥ (ቁ 19 ሁለት ጊዜ፣ 20፣ 21፣ 22፣23 ሁለት ጊዜ፣ 25፣26)፡፡ የሚለው ስያሜ (ከተለመደው መስተፀኦምር ወጪ) ተጠቅሷል፡፡ ይን እንጂ በተመሳሳይ ሁኔታ (1)3:13:14 እና 3:16-17:18:35:36፤ (2)6:27:53 እና 6:40፤ እንዲሁም (3) 8:28 እና 8:35:36፡፡

ኢየሱስ ልጅ የሚለውን እና የሰው ልጅ የሚለውን ስም በተለዋዋጭት ለራሱ ተጠቅሟል፡፡

**5:28 "በዚህ አታድንቁ"** ይህ አሉታዊ ቦዝ አንቀፅ የአሁን ጊዜ ትዕዛዝ አዘል ገላጭ ግሥ ሲሆን በተለምዶ የሚያመለክተው በሄደት ላይ የነበረን ድርጊት ማቆምን ነው፡፡ ኢየሱስ እስከ አሁን እየነገራቸው የነበረ ነገር ሁሉ ለአይሁዳዊያን መሪዎች ሚያስገርም ቢሆንም የመጨረሻው ንግግሩ ግን እጅግ አስደንቋቸው ነበር፡፡

▣ **"በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት"** ይህ የሚያመለክተው መስሑ ዳግመኛ ስመጣ የሚሰማውን ድምጽ ነው (1 ተሰለ 4:16)፡፡ አላዛር የዚህ ትይነት እውተኛ ምሳሌ ነው (11:43)፡፡ ይህ በ2 ቆሮ 5:6፣ 8 ላይ ያለውን እውነት ጋር ኤታረሰም፡፡ ይህ የልጁን አለማቀፋዊ ፍርድ እና ስልጣን ያሳያል፡፡

የዚህ አውድ በአብዛኛው የሚገኘው አሁንነና በዚህ ሥፍራ የሚፈፀምን የመንፈሳዊ ሕይወት እውነታን ነው (የሚታይ ነገር-ፍፃሜ)፡፡ ነገር ግን ይህ ሐረግ በተጨማሪም የሚያረጋግጠው በመጨረሻው ጊዜ የሚከሰትን የወደፊት ነገር-ፍፃሜን ነው፡፡ ህ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ በተፈፀሙ እና ገና በሚፈፀመው መካከል ያው ውጥረት በወንጌላት ውስጥ በተለይም በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ያለው የኢየሱስ ትምህርት ለይት ያለ ባህሪይ ነው፡፡

**5:29** መጽሐፍ ቅዱስ ኃጢአን እንዲሁም ጻድቃን ትንሳኤ እንደሚኖር ይገልጻል (ዳን 12:2፤ ማቴ 25:46፤ ሐዋ 24:15)፡፡ አብዛኛዎቹ ጥቅሶች የሚያመለክቱት የጻድቃንን ትንሳኤ ብቻ ነው (እዮ 19:23-29፤ ኢሳ 26:19 ዮሐ 6:39-40፣ 44፣ 54፤ 11:24-25፤ 1ቆሮ 15:50-58)፡፡

ይህ ፍርድ በሥራ እንደሆነ አያሳይም ነገር ግን በአማኞች ላይ ያለው ፍርድ በአኗኗር ዘይቤያቸው እንደሆነ ይገልጻል ((ማቴ 25:31-46፤ ገላ 5:19-21)፡፤ በእግዚአብሔር ቃል እና በግዛቱ ሰዎች የዘሩትን እንደሚያጭዱ (ምሣ 11:24-25፤ ገላ 6:6) አጠቃላይ መርሕ አለ፡፡ መዝ11:24-25፤ ገላ 6:6)፡፡ ወይም በብሉይ ኪዳን ጥቅስ ለማስደገፍ "እግዚአብሔር ሰዎችን እንደ ስራቸው ይከፍላቸዋል" (መዝ 62:12፤ 28:4፤ እዮ 24:12፤ ማቴ 16:27፤ ሮሜ 2:6-8፤ 1ቆሮ 5:10፤ ኤፌ 6:8 እና ቆላ 3:25)፡፡

**የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 5:30**
**እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም፤ እንደ ሰማሁ እፈርዳለሁ ፍርዴም ቅን ነው፡ የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻምና፡፡**

**5:30** ኢየሱስ ትስብእት የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ነው እንዲሁም ለአባቱ ይገዛል፡፡ ይህ የመገዛት ሀሳብ በቁጥር 19 ላይ እንደገና ተገልጾ እናገኛል፡፡ ይህ ግን የልጁን ማነስ አያሳይም ነገር በስላሴ መካከል የድነት ሥራ የሥራ ክፍፍል በአብ፣ በወለድ እና በመንፈስ ቅዱስ መካከል መኖሩን ያሳያል፡፡

**የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 5:31-47**
**እኔ ስለ እኔ ስለ ራሴ ብመሰክር ምስክሬ እውነት አይደለም፤ ስለ እኔ የሚመሰክር ሌላ ነው: እርሱም ስለ እኔ የሚመሰክረው ምስክር እውነት እንደ ሆነ አውቃለሁ። እናንተ ወደ ዮሐንስ ልካችኋል እርሱም ለእውነት መስክሮአል። እኔ ግን ከሰው ምስክር አልቀበልም: እናንተ እንድትድኑ ይህን እላለሁ እንጂ። እርሱ የሚነድና የሚያበራ መብራት ነበረ: እናንተም ጥቂት ዘመን በብርሃኑ ደስ ሊላችሁ ወደዳችሁ። እኔ ግን ከዮሐንስ ምስክር የሚበልጥ ምስክር አለኝ፤ አብ ልፈጽመው የሰጠኝ ሥራ: ይህ የማደርገው ሥራ: አብ እንደ ላከኝ ስለ እኔ ይመሰክራልና። የላከኝ አብም እርሱ ስለ እኔ መስክሮአል። ድምፁን ከቶ አልሰማችሁም: መልኩንም አላያችሁም፤ እርሱም የላከውን እናንተ አታምኑምና በእናንተ ዘንድ የሚኖር ቃሉ የላችሁም። እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና እነርሱን ትመረምራላችሁ፤ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው፤ ነገር ግን ሕይወት እንዲሆንላችሁ ወደ እኔ ልትመጡ አትወዱም። ከሰው ክብርን አልቀበልም፤ ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ፍቅር በራሳችሁ እንደ ሌላችሁ አውቃችኋለሁ። እኔ በአባቴ ስም መጥቻለሁ አልተቀበላችሁኝምም፤ ሌላው በራሱ ስም ቢመጣ እርሱን ትቀበሉታላችሁ። እናንተ እርስ በርሳችሁ ክብር የምትቀባበሉ ከአንዱም ከእግዚአብሔር ያለውን ክብር የማትፈልጉ: እንዴት ልታምኑ ትችላላችሁ? እኔ በአብ ዘንድ የምከሳችሁ አይምሰላችሁ፤ የሚከሳችሁ አለ፤ እርሱም ተስፋ የምታደርጉት ሙሴ ነው። ሙሴንስ ብታምኑት እኔን ባመናችሁ ነበር፤ እርሱ ስለ እኔ ጽፎአልና። መጻሕፍትን ካላመናችሁ ግን ቃሌን እንዴት ታምናላችሁ?**

5:31 በብሉይ ኪዳን ውስጥ አንድ ነገር ለመቋጨት የሁለት ሰዎች መስክርነት አስፈላጊ ነው (ዘኍ 35:30፤ ዘዳ 19:15)። በዚህ አውድ ውስጥ ኢየሱስ ስለ እርሱ አምስት ምስክርነቶችን ተሰጥቷል።

1. አባቱ (ቁ 32፣ 37)
2. መጥመቁ ዮሐንስ (ቁ 33 1:19-51)
3. የኢየሱስ የራሱ ሥራዎች (ቁ 36)
4. ቅዱሳት መጽሐፍት (ቁ 39)
5. ሙሴ (ቁ 46) ይህ የሚያሳየው በዘዳ 18:15-22

ልዩ ርዕስ 1:8 ተመልከቱ

▣ "ቢ..." ይህ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ አረፍተነገር ሲሆን ድርጊት ለመፈፀም እድል መኖሩን የሚናገር ነው።

▣ **"ምስክሬ እውነት አይደለም"** ይህ ምስክርነት በ8:14 ላይ ካለው ጋር ይጋጫል። ነገር ግን አውዱ እንደሚያሳየን ይህ ዓረፍተ ነገር የተነገረው በሌላ አውድ ዳራ ውስጥ ነው። በዚህ ስፍራ ኢየሱስ እያሳየ የነበረው ምን ያህል ምስክርነቶች እንዳሉ ነው ነገር ግን በ8:14 ላይ እርሱ ብቻ አስፈላጊ እንደሆነ ነው።

በ6:55 ላይ ያለውን እውነት ሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።

5:32 **"ስለ እኔ የሚመሰክር ሌላ ነው"** ይህ የሚያመለክተው እግዚበእሔር አብን ነው (1 ዮሐ 5:9) ምክንያቱም በዚህ ስፍራ ላይ ሌላ የሚለው ቃል በግሪክ አሎስ ሲሆን ትርጓሜውም "ተመሳሳይ ሆኖ ሌላ" ማለት ነው። ይህ ሄትሮስ ከሚለው የተለያዩ አይነትን ከሚያመለክተው ቃል ይለያል። ምንም እንኳ በኮይኔ ግሪክ ወቅት ይህ አይነቱ ልዩነት እየቀረ የመጣ ቢሆንም ማለት ነው። ኢየሱስ የሚለውን በ1:8 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።

5:33 **"ወደ ዮሐንስ ልካችኋል"** ይህ የሚያመለክተው መጥመቁ ዮሐንስን ነው (1:19)።

5:34 **"እንድትድኑ ይህን እላለሁ እንጂ"** ይህ በግሪኩ የተደረጎ ግሥን ሁኔታ ገላጭ ነው። የድርጊት ተቀባይነቱ ድምፀት የሚያሳየው/የሚጠቁመው የእግዚአብሔርን ወኪል ወይም መንፈስን ነው (6:44:65 ን ያስ.)። አስታውሱ ወንጌላት የወንጌል ስርጭት በራሪ ወረቀቶች ናቸው። ስለዚህም የወንጌል ስርጭት አላማ በውስጣቸው አለ (20:30-31)።

5:35 **"የሚያበራ መብራት ነበረ"** በዮሐንስ የዚግጅት መልዕክት ውስጥ ሌላኛው ብርሃን ላይ ትኩረት ያደረገበት ክፍል ነው (1:6-8)።

5:36 **"ይህ የማደርገው ሥራ: አብ እንደ ላከኝ ስለ እኔ ይመሰክራልና"** የኢየሱስ ተግባራት በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለ መስሑ የተነገሩ ትንብቶች ፍጻሜ ናቸው። በዚያን ዘመን ይኖሩ የነበሩ አይሁዳዊያን ድንቅ እና ተአምራቱን ተመልክተው ማስተዋል ነበረባቸው- ዐይነ ስውራንን መፈወሱ፣ ድሆችን መመገቡ፣ ሽባዎችን መፈወሱ (ኢሳ 29:18፤ 32:3-4፤35:5-6፤ 42:7)። የኢየሱስ ትምህርት ኃይል፣ የጽድቅ ሕይወቱ፣ ርህራሄው እና ታላላቅ ተአምራቱ (2:23፤ 10:25.፣ 38፤ 14:11፤ 15:24) እነዚህ ሁሉ እርሱ ማን እንሆነ፣ ከዬት እንደመጣ እና ማን እንደላከው የሚያሳዩ ነገሮች ናቸው።

5:37 **"እርሱ ስለ እኔ መስክሮአል"** "እርሱም" የሚለው ቃል የሚያመለክተው አብን ነው። ይህ ሀረግ ከብሉይ ኪዳን የጠወሰደ ይመስላል (ዕብ 1:1-3)። ይህ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ያሉ ሁሉንም መሲሁን የሚያመለክቱ ጥቅሶን ያካትታል (ቁ 39)።

▣ **"ድምፁን ከቶ አልሰማችሁም፡ መልኩንም አላያችሁም"** በዚህ ክፍል ውስጥ ኢየሱስ የሚያረጋግጥላቸው ምንም እንኳ አይሁዳዊያን እግዚአብሔርን በቅዱሳት መጽሐፍት አማካኝነት ቢያውቁትም እንዲሁም ቢያመልክቱም በእርግጥ ግን ኤውቁትም ነበር (8፡43፤ ኢሳ 1፡1-15፤ 6፡9-10፤ 29፡13፤ ኤር 5፡21)

በብሉይ ኪዳን ውስጥ መለኮትን መመልከት ሞትን ያስከትላል ተብሎ ይታመናል። ከያሕዌ ጋር ፊት ለፊት ለመናገር የቻለው ብቸኛ ሰው ሙሴ ብቻ ነበር፤ እርሱም ቢሆን ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት የቻለው በዳመና ግርዶሽ አማከካኝነት ነው። ብዙ ሰዎች ዘጸ 33፡23 ከዮሐ 1፡18 ጋር ይጋጫል ብለው አስበዋል። ነገር ግን በዘጸአት ላይ ያለው የዕብራይስጥ ቃል "ከክብር በኂላ" እንጂ አካል አልነበርም።

**5፡38 "እርሱም . . . በእናንተ ዘንድ የሚኖር ቃሉ የላችሁም"** ይህ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ያለ ሁለት ታላቅ ዘይቤያዊ አነጋጋር ነው። የእግዚአብሔርን ቃል መቀበል አለባችሁ፣ አንድ ጊዜ ከተቀበላችሁ በኂላ (1፡27) መኖር አለበት (ዮሐ 8፡31፤ 15፡4፣ 5፣ 6፣ 7፣ 10 1ዮሐ 2፡6፣ 10፣ 14፣ 17፣ 24፣ 15፣ 24)። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ሙሉ መገለጥ ነው። (1ዮሐ 1፡1-18፤ ፊል 2፡6-11፤ ቀቆላ 1፡15-17፤ ዕብ 1፡1-3)። ድነት የሚረጋገጠው ቀጣይነት ባለው ግንኙነት ነው ("ማወቅ" ማለት በዕብራዊያን አመለካከት ዘፍ 4፡1፤ ኤር 1፡5) እንዲሁም የወንጌልን እውነት ትክክል መሆኑን ማመን ነው (በግሪክ አመለካከት "ማወቅ" ማለት ነው 2 ዮሐ 9)።

"መኖር" የሚለው ቃል ቅርበት ያለብት የግል ግንኙነትን እና ከመጽናት ጋር ይያያዛል። መኖር ለድነት ቅድመ ሁኔታ ነው (ምዕራፍ 15)። በየፐሐንስ ወንጌል ውስጥ በብዙ መንገድ አገልግሎት ላይ ውሏል።

1. ወልድ በአብ ውስጥ አለ (10፡38፤ 14፡10፣ 11፣ 20፣ 21፤ 17፡21)
2. አብ በወልድ ውስጥ አለ (10፡38፤ 14፡10፣ 11፣ 21፤ 17፡21፣ 23)
3. ውስጥ ናቸው (10፡56፤ 14፡20፣ 21፤ 15፡5፤ 17፡21)
4. አማኞች በወልድ እና በአብ ውስጥ ናቸው (14፡23)
5. አማኞች በቃል ውስጥ ናቸው (5፡38፤ 8፡31፤ 15፡7፤ 1ዮሐ 2፡14)

1ዮሐ 2፡10 ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።

**5፡39 "እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኂልና እነርሱን ትመረምራላችሁ"**

▣ **"እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው"** ይህ ኢየሱስ የፈጸማቸውን የብሉይ ኪዳናትን የሚያመልክት ነው (1፡45፤ 2፡22፤ 5፡46፤ 12፡16፣ 41፤ 19፡28፤ 20፡9)። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የሚንመለከታቸው የጴጥሮስ (ሐዋ 3፡18፤ 10፡43) እና የጳውሎስ (ሐዋ 13፡27፤ 17፡2-3፤ 26፡22-23፣ 27) የኢየሱስን መሲሕነት ለማመልከት ተጠቅሚል። በ 1ጴጥ 3፡15-16 ላይ ካለው በስተቀር በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለ መጽሐፍት የተናገሩት ሁሉ ስለ ብሉይ ኪዳናት የሚያወሩ ናቸው (1ቆሮ 2፡9-13፤ 1ተሰለ 2፡13፤ 2 ጢሞ 3፡16፤ 1ጾጥ 1፡23-25፤ 2ጴጥ 1፡20-21)። ኢየሱስ እራሱን የብሉይ ኪዳናት ፍጻሜ እና ግብ እንደሆነ አድርጎ በግልጽ ይመለከት ነበር (ማቴ 5፡17-48)።

**ልዩ ርዕስ፡ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ስብከት**

- ሀ. በብሉይ ኪዳን ውስጥ በእግዚአብሔር የተገባው የተስፋ ቃል መሲሕ በሆነው በኢየሱስ መምጣት ፍጻሜን አግኝቷል (ሐዋ 2፡30፤ 3፡19-24፤ 10፡43፤ 26፡6-7፣ 22፤ ሮሜ 1፡2-4፤ 1ጢሞ 3፡16፤ ዕብ 1፡1-2፤ 1ጴጥ 1፡10-12፣ 2ጴጥ 1፡18-19)።
- ለ. ኢየሱስ በጥምቀቱ ወቅት መሲሕ ሆኖ ተቀብቷል (ሐዋ 10፡38)
- ሐ. ኢየሱስ ከተጠመቀ በኂለ በገሊላ አገልግሎቱን ጀምሯል (ሐዋ 10፡37)
- ሐ. አገልግሎቱ በእግዚአብሔር ኃይል መልካም ነገሮችን እና ታላላቅ ነገሮች በማድረግ ይገለጻል (ማር 10፡45፤ ሐዋ 2፡22፤ 10፡38)
- መ. እንደ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ መስሑ ተሰቅሏል (ማር 10፡45፤ ዮሐ 3፡16፤ ሐዋ 2፡23፤ 3፡13-15፣ 18፤ 4፡11፤ 10፡39፤ 26፡23፤ ሮሜ 8፡34፤ 1ቆሮ 1፡17-18፤ 15፡3፤ ገላ 1፡4፤ ዕብ 1፡3፤ 1ጴጥ 1፡2፣ 19፤ 3፡18፤ 1ዮሐ 4፡10)።
- ሠ. ከሞት ተነስቷል እንዲሁም ለደቀ መዛሙርቱ ታይቷል (ሐዋ 2፡24፣31-32፤3፡15፣ 26፤ 10፡44-47፤ 17፡31፤ 26፡23፤ ሮሜ 8፤34፤ 10፡9፤ 1ቆሮ 15፡4-5፣ 12፤ 1ተሰ 1፡10፤ 1ጢሞ 3፡16፤ 1ጴጥ 1፤2፤ 3፡18፣ 21)።
- ረ. ኢየሱስ በእግዚአብሔር ከብሯል "ጌታም" ተብሎ ተጠርቷል። (ሐዋ 2፡25-29፤፣33-36፤ 10፡36፤ ሮሜ 8፡34፤ 10፡9፤ 1ጢሞ 3፡16፤ ዕብ 1፡3፤ 1ጴጥ 3፡22)
- ሰ. የእግዚአብሔር አዲስ ማህበረሰብ ለመመስረት መንፈስ ቅዱስን ሰጥቷል (ሐዋ 1፡8፤ 2፡14-18፣ 38-39፤ 10፡44-47፤ 1ጴጥ 1፡12)።
- ሽ. ለፍርድ እና እንደገና ለማደስ ተመልሶ ይመጣል (ሐዋ 3፡20-21፤ 10፡42፤ 17፡31፤ 1ቆሮ 15፡20-28፤1ተሰለ 1፡10)
- ቀ. መልዕክቱን የሚሰሙ ሁሉ ንስሐ መግባት እና መጠመቅ ይገባቸዋል (ሐዋ 2፡21፣ 38፤ 3፡19፤ 10፡43፣ 47፤ 17፡30፤ 26፡20፤ ሮሜ 1፡17፤ 10፡9፤ 1ጴጥ 321)።

ምንም እንኳን የተለያዩ የአዲስ ኪዳን ፀሐፊዎች የተወሰነውን ክፍል ቢያወጡት ወይም ደግሞ በተወሰኑት ላይ ብቻ አተኩረው ቢሰብኩም ይህ አቀራረብ ለቀደመችው ቤተክርስትያን ወንጌልን ለመስበክ በጣም አስፈላጊ ሆኖ ያገለገለ ነበር። መላው የማርቆስ ወንጌል የጴጥሮስን የእምነት አንቀፅ አካሄድ የሚከተል ነበር። ማርቆስ በልማድ እንደሚነገረው የጴጥሮስን ስብከቶች ያዋቀረ፣ በሮም የሰበከ እንዲሁም በወንጌል መልክ የፃፈው ነው። ማቴዎስና ሉቃስም የማሮቆስን መሠረታዊ አወቃወር የሚከተሉናቸው።

**5፡41-44** ይህ ቁጥር የሚያመለክተው የአይሁድ የሃይማኖት መሪዎች እርሰ በእርሳቸው እንዴ እንደሚበላለጡ መሳየት ያስደስታቸው እንደነበር ነው። ምንም እንኳ ያለፉት መምህራኖቻቸው የተናገሩት በጠቅሱም ከመንፈሳዊ እውርነታቸው

የተነሳ በመካከላቸው የነበረውብ ትልቁን መምህር አጥተውታል፡፡ ይህ ኢየሱስ ከተቃወማቸው በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ከነበሩት የአይሁዳዊነት አንዱ ነበር (በማቴ 21፡33046፤ ማር 12፡1-12፤ ሉቃ 20፡9-19 ያለውን ተመልከቱ)፡፡

5፡41

| | |
|---|---|
| NASB፣ NRSV፣ | "ከሰዎች ክብርን አልቀበልም" |
| NKJV | "ከሰዎች ክብርን አልቀበልም" |
| TEV | "የሰዎችን አድናቆት እየፈለግሁ አይደለም" |
| NJB | "የሰዎች አድቆት ለኔ ምኔም አይደለም" |

"ክብር" የሚለው ቃል በግሪኩ ዶክሳ ሲሆን በአንድ አይነት መልኩ ለመተርጎም አስቸጋር ነው (በ1፡14 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡)፡፡ የዕብራይስጥ ቃል የሆነው ካቦድን የሚያሳይ ሲሆን ይህ የእግዚአብሔርን አንጸባራቅ እና የሚያስፈራ መገኘትን ያሳያል (ዘፍ 16፡10፤ 24፡17፤ 40፡34፤ ሐዋ 7፡2) እናም እግዚብሔርን ስለ ባሕርይው እና ስላ ደረጋቸው ነገር ማመስገን እና ማክበርን ያመለክታል፡፡

1. መላእክት (ሉቃ 2፡9፤ 2ጴጥ 2፡10)
2. የኢየሱስ የበላይነት (ዮሐ 1፡14፤ 8፡54፤ 12፡28፤ 13፡31፤ 17፡1-5፣ 22፣ 24፤ 1ቆሮ 2፡8፤ ፊል 3፡17)፡፡
3. በተዘዋዋር መንገድ ለአማኞች (ሮሜ 8፡18፣ 21፤ 1ቆሮ 2፡7፤ 15፡43፤ 2ቆሮ 4፡17፤ 3፡4፤ 1ተሰ 2፡12፤ 2ተሰ 2፡10፤ ዕብ 2፡10፤ 1ጴጥ 5፡1፣ 14)

ዮሐንስ የኢየሱስ ስቅለት እንደ ክብር እንደቆጠረው ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡ (7፡39፤ 12፡16፣ 23፤ 13፡31)፡፡ ነገር ግን ይህ "ማክበር" ወይም "ማመስገን" ተብሎ ልተረጎም ይችላል፡፡ (ሉቃ 17፡18፤ ሐዋ 12፡23፤ ሮሜ 4፡20፤ 1ቆሮ 10፡3፤ 2ቆሮ 4፡15፤ ፊል 1፡11፤ 2፡11፤ ራዕ 11፡13፤ 14፡7፤ 16፡9፤ 19፡7)፡፡ በዚህ አይነት መንገድ ነው በዚህ አውድ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው፡፡

5፡43 **"አልተቀበላችሁኝም"** በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ዮሐንስ በኢየሱስ ማመን የሚለውን የሚያተኩሩበት ስለ ኢየሱስ ተቀረጸ አስተምህሮ ላይ ሳይሆን ከእርሱ ጋር የግል ግንኙነት ነው፡፡ (39-40) ማመን የሚጀምረው እርሱን ለማመን በመወሰን ነው፡፡ ከእርሱ ጋር የግል ግንኙነት በመጀመር ቀስ በቀስ ወደ አስተምህሮታዊ ብስለት እና ክርስቶስን ወደ መመስል ይታደጋል፡፡

▣ **"ሌላው በራሱ ስም ቢመጣ"** ይህ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ አረፍተ ነገር ነው"

▣ **"እርሱን ትቀበሉታላችሁ"** ይህ የአይሁዳዊያን መምህራን የመጽሓፍት አጠናን መንገድን የነቀፈበት ሁኔታ ነው፡፡

"ሚካኤል ማጊል፡- New Testament Transline በሚለው መጽሐፍጥሩ የሆነ አገላለፅ አለው፤

"'የአይሁድ መሪዎች በእግዚአብሔር እንደተላከ ያላስረገጠን አስተማሪ ወይም ረቢ ቀበለሉ፡፡ መምህር ሲመጣ እንደ እኩዮቻቸው እኩል በሆነ ክብር ይቀበሉታል፡፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ ነቢይ ሲመጣ ለመስማት እና ለመተዘዝ ራሳቸው ዝቅ አደርገው ያቀረባሉ፡፡ ይህ ነው እንንግዲህ የእግዚአብሔር ነብያት ተቀባይነት እያጡ የኖሩበት መሠረት (ገጽ 318).

5፡44 በ17፡3 ላይ የተሰጠውን ማብራሪያ ተመልከት

5፡45-47 ኢየሱስ የሙሴ መጽሐፍት ስለ እርሱ እንደሚመሰክሩ ተናግሯል፡፡ ይህ ምናባ በዘዳ 18፡15-22 ያመለክት ይሆናል፡፡ በቁ 45 ላይ መጽሐፍት ካሳሽ ሆነው ቀርበዋል፡፡ መሆን የሚገባቸው ግን መሪ ነው (ሉቃ 16፡31)፡፡ መሪነቱን ስላልተቀበሉ ጠላት ሆነባው (ገላ 3፡8-14፣ 23-29)፡፡

5፡46፡47፣ **ብታምኑ... ካላመናችሁ"** ቁጥር 46 ሁለተኛ መደብ ሁኔታዊ አረፍተ ነገር ሲሆን ይህም "ከእውነታው ጋር የሚቀረን" ተብሎ ይጠራል፡፡ ይህም የሚያረጋግጠው የአይሁድ መሪዎች ሙሴ በፃፊው እንኳ በእርግጥ እንደማያምኑበት እና ኢየሱስም (የሥነ-ፍፃሜው ሙሴ (በዘዳ 18፡15-19 ላይ የተጠቀሰው ነቢ) በመጨረሻው ቀን የእነርሱ ፈራጅ እንደሚሆን ያስረዳል፡፡ በቁ 47 ላይ "ካላመናችሁ" የመጀመሪያ ደረጃ ሁኔታዎች አርተ ነገርን የሚያሣይ ሲሆን እውነት እንደሆነ የተገመተ ነው( አ.መ.ት "ስለማታምኑ" ይላል)፡፡

*መወያያ ጥያቄዎች*

ይህ <u>ምሪትን</u> የሚሰጥ የመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻ ነው፤ ይህም ማለት ለምትደረስበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ኃላፊነት የምትወስደው አንተ እራስ ትሆናህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን ባለን ብርሃን መጠን ልንመላለስ ይገባል ማለት ነው፡፡ በስነ አፍታት ሂደት ውስጥ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ዋነኛውን ስፍራ ትይዛላችሁ፡፡ ይህንን እድል ለመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻዎች አሳልፈህ አትስጥ፡፡

ከዚህ በታች የተጠቀሱት የመወያያ ጥያቄዎች በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ባሉት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ማሰላሰል እንድትችሉ ለማገዝ የተዘጋጁ ናቸው። የሚገድቡህ ሳይሆን የማሰላሰል ምናብን እንዲያሰፉልህ የታቀዱ ናቸው።

1. በዘመናዊው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቁጥር 4 ያልገባው ለምንድነው?
2. ይህንን ሰውዬ ኢሱስ ለምን ፈወሰው?
3. በዚህ ሰው መፈወስ ላይ እምነት ለምን ተካተተ፤ አካላዊ ፈውስ መንፈሳዊ ፈውስን ያመለክታን?
4. የእርሱ ህመም ከግል ኃጢአት ጋር የተያያዘ ነውን፤ ህመሞች ሁሉ ከኃጢአት ጋር የተያያዙ ናቸውን?
5. አይሁዳዊያን ለምን ኢየሱስን ለመግደል ፈለጉ?
6. በብሉይ ኪዳን ውስጥ የአምላክ ተግባራት የሆኑ ኢየሱስም ሲያደርጋቸው የነበሩት ጻፍ።
7. ዘላለማዊ ሕይወት የአሁን ገጽታ ወይስ የወደፊት ተስፋ ነው?
8. ፍርድ በሥራ ወይስ በእምነት፤ ለምን?

# ዮሐንስ 6

## በዘመናችን ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀጽ ክፍፍል

| UBS[4] | NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| አምስት ሺህ ሰዎችን መገበ | አምስት ሺህ ሰዎችን መገበ | አምስት ሺህ ሰዎችን መገበ | አምስት ሺህ ሰዎችን መገበ | የእንጀራው ተአምር |
| 6፡1-15 | 6፡1-14 | 6፡1-15 | 6፡1-16 | 6፡1-4 |
| | | | | 6፡1-5 |
| | | | 6፡7 | |
| | | | 6፡8-9 | |
| | | | 6፡10-13 | |
| | | | 6፡14-15 | |
| | ኢየሱስ በባር ላይ መራመዱ | | | |
| | 6፡15-21 | | | |
| በውሃ ለይ መራመዱ | | ኢየሱስ በባህር ላይ ተራመደ | ኢየሱስ በባህር ላይ ተራመደ | ኢየሱስ በውሃ ላይ እየተራመደ ወደ ደቀ መዛሙርቱ መጣ |
| 6፡16-21 | | 6፡16-21 | 6፡16-21 | 6፡16-21 |
| ኢየሱስ የሕይወት እንጀራ | ከሰማይ የሆነው እንጀራ | ኢየሱስ፣ የሕይወት እንጀራ | ሕዝቡ ኢየሱስን ፈለጉት | በቅፍራናሆም በምኩራብ ውስጥ የተደረገ ንግግር |
| 6፡22-33 | 6፡22-40 | 6፡22-24 | 6፡22-24 | 6፡22-27 |
| | | | ኢየሱስ የሕይወት እንጀራ | |
| | | 6፡25-40 | 6፡25 | |
| | | | 6፡26-27 | |
| | | | 6፡28 | 6፡28-40 |
| | | | 6፡29 | |
| | | | 6፡30-31 | |
| | | | 6፡32-22 | |
| 6፡34-40 | | | 6፡34 | |
| | | | 6፡35-40 | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | የራሱ የሆኑት አልተቀበሉትም | | | |
| 6:41-51 | 6:41-59 | 6:41-51 | 6:41-42 | 6:41-51 |
| | | | 6:43-51 | |
| | | | 6:52 | 6:52-58 |
| | | | 6:53-58 | |
| የዘላለማዊ ሕይወት ቃሎች | ብዙ ደቀ መዛሙርት ወደ ኃላ ተመለሱ | | የዘላለማዊ ሕይወት ቃሎች | |
| | 6:60-71 | | | |
| 6:60-65 | | 6:60-65 | 6:60 | |
| | | | 6:61-65 | |
| | | | | 6:64-66 |
| 6:66-67 | | 6:66-71 | 66-67 | |
| | | | 6:68-69 | |
| | | | 6:70-71 | |
| | | | | የጴጥሮስ የእምነት ንግግር |
| | | | | 6:76-71 |

**ሦስተኛ ዙር ንባብ**
*በአንቀጽ ደረጃ የመጽሐፉ ጸሓፊ ሊያስተላልፍ የፈለገውን ሀሳባ መከተል*

ይህ <u>ምሪትን</u> የሚሰጥ የመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻ ነው፤ ይህም ማለት ለምትደረስበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ኃላፊነት የምትወስደው አንተ እራስ ትሆናህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን ባለን ብርሃን መጠን ልንመላለስ ይገባል ማለት ነው። በስነ አፍታት ሂደት ውስጥ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ዋነኛውን ስፍራ ትይዛላችሁ። ይህንን እድል ለመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻዎች አሳልፈህ አትስጥ።

መጽሐፉን በአንድ ጊዜ ለሁለተኛ ጊዜ አንብበህ ጨርስ። ዋና ሐሳቦችን ለያቸው። የራስህን የዋና ሐሳብ አከፋፈል ተሻሽለው ከቀረቡት ትርጉሞች ጋር አስተያያቸው ምንም እንኳን በአንቀፅ መከፋፈል በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት የሚከናወን ባይሆንም የአተረጓጎም ምሦሦ የሆነውን የመጀመሪያውን ፀሐፊ ዋና ሐሳብ ለመከተል ግን ቁልፍ ጉዳይ ነው። ዋና ዋና ሀሳቦችን ግለጽ እንዲሁም ዋናውን ሀሳብ በአንድ አረፍተ ነገር ግለጽ።

1. የመጀመሪያውን አንቀጽ ዋና መልዕክት
2. የሁለተኛውን አንቀጽ ዋና መልዕክት
3. የሦስተኛውን አንቀጽ ዋና መልዕክት
4. የአራተኛውን አንቀጽ ዋና መልዕክት
5. ወዘተ

**ለዮሐንስ 6፡1-71 አውዳዊ አብርሆት**

ሀ. የዮሐንስ ወንጌል ምንም እንኳ በላይኛ ክፍል ውስጥ ስለተደረገው ውይይት እና ጸሎት በምዕራፍ 13-17 ላይ በዘግብም ስለ ጌታ እራት ግን ምንም አልዘገበልንም፡፡ በሁለተኛው ምዕተ ዓመት የነበረችው ቤተ ክርስቲያን የተሰጡትን ነገሮች እንደ ቤተ ክርስቲያን ስርዓት መመልከት ጀምራ ነበር፡፡ አንዳንዳቹን የጾጋ መተላለፊያ መንገዶች አድርገው ይ መለከቷቸዋል፡፡ ዮሐንስ ምናልባት ይሄንን ዓይነቱን የቤተ ክርስቲያን ስርዓት አመለካከት ተቃውሞ ጽፎ ሊሆን ይችላል ነገር ግን የጌታን ጥምቀት ወይም የጌታ እራትን አልዘገበልንም፡፡

ለ. የዮሐንስ 6 አውድ አምስት ሺይ ሰዎች በተአምራት የተመገቡበት ነው፡፡ ነገር ግን ግን ብዙ ሰዎች ይህንን ክፍል የጌታ እራትን የቤተ ክርስቲያን ስርዓት እንደሆነ አድርገው ያስተምሩታል፡፡ የሮማን ካቶሊክ ቤተ ክርስያን ትራንሰብስታሴሽን የሚለው አስተምህሮ ምንጭም ይህ ክፍል ነው፡፡(ቁ 53-56)

ምዕራፍ ስድት እንዴት የጌታ እራን ያሳያል የሚለው ጥያቄ የወንጌልን የሁለትዮሽ ባሕሪይ ያሳያል፡፡ እርግጥ ነው ወንጌል የኢየሱስ ሕይወት እና ቃል ነው፤ እንዲሁም ይህ ነገር የተጻፈው የተወሰኑ አስርተ አመታት ካለፉ በኂላ የጸሓፊዎቹ እምነት የተገለጸበትም ጭምር ነው፡፡ ስለዚህም ስለ ደራሲው ዒላማ ሦስት ደረጃዎች አሉት

1. መንፈስ
2. ኢየሱስ እና የመጀመሪያዎቹ ሰሚዎች
3. የወንጌላት ጸሐፊት ችና አንባቢዎቻቸው

አንድ ሰው እንዴት መተርጎም ይችላል; ብቸኛው የተረጋገጠው መንገድ በታካዊ ሁኔታውን ባገናዘበ መልኩ አውዳዊ፣ ስነ ሰዋዊ፣ መዝገበ ቃላታዊ መንገድ የሚከተል እንጂ በተቃራኒው አይደለም፡፡

ሐ. የዚህ ወንጌል ተደራሲያን አይሁዳዊያን እንደሂኑ እና ታሪካዊ ዳራውም መምህራኑ የሚጠብቁት መሲሕ ከሙሴ የሚበልጥ መሆኑን መዘንጋት ዬለብንም (ቁ 30-31)፣ በተለይም እንደ “መና” ካለ የዘጸአት ልምምዳቸው ጋር በተያያዘ መልኩ ማለት ነው፡፡ መምህራን መዝ 72፡16 እንደ ማሳመኛ ጥቅስ ይጠቀሙብታል፡፡ ኢየሱስ (በቁ 60-62፣ 66 ላይ) የሕዝቡን የተሳሳተ የመሲሁን ምስል ሲያፍርስባቸው እንመለከታለን (ቁ 14-15)

መ. የጥንት ቤተ ክርስቲያን አባቶች ይህ ክፍል ስለ ጌታ እራት መናገሩ ላይ ስምምነት ዬላቸው፡፡ የአሌክሳንደሪያው ቄልሜንጦስ፣ ኦርገን እና ኢዩስበስ በዚህ ክፍል ላይ ማብራሪያ ስጽፉ ስለ ጌታ እራት ያሉት ነገር ዬለም፡፡

ሠ. ኢየሱስ በዚህ ስፍራ ላይ የተጠቀማቸው ዘይቤያዊ አነጋገሮች በውሃ ጉድጓድ አጠገብ ከሴትቱ ጋር ስነጋገር ከተጠቀመው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ምድራዊ ውሃ እና እንጀራ ለዘላለማዊ ሕይወት እና መንፈሳዊ ገሃድ እውነታ ምሳሌ ሆነው ተጠቅሰዋል፡፡

ረ. ይህ ዳቦን የማብዛት ተአምራ ከአራቱን ወንጌላት የተጻፈው በዚህ ወንጌል ውስጥ ብቻ ነው (ማቴ 14፡13-21፤ ማር 6፡32-44፤ ሉቃ 9፡10-

ሰ. ሚካኤል ማጊል ኒው ቴስታመንት ትራንስሊን (ገጽ 325) በቅፍርናሆም ስለ ነበሩ የተለያዩ ወገኖች እና ከኢየሱስ አስደንጋጭ ንግግሮች ጋር ያላቸውን ግንኙነት በተመለከተ የሚያስገርም ምልከታን ሰጥቷል፡፡

1. ሕዝቡ ቁ 24
2. አይሁዳዊያን ቁ 41፣ 52
3. ደቀ መዛሙርቱ ቁ 60፣ 66
4. ዐስራ ሁለቱ ቁ 67

ኢየሱስ ውጤታማ በሆነ መልኩ

1. ኢየሱስ ሕዝቡን ስለመገባቱ ንጉሥ እንዳያደርጉት አስቆማቸው (6፡15)
2. የአይሁዳዊያን መሪዎችን ስለ እራሱን በተናገራቸው ነገሮች አሳባቸውን ተቃወመ
3. ለይስሙላ ከተሉት የነበሩት ሰዎች ትተውት እንዲሄዱ አደረገ
4. አስራ ሁለቱ ግን ግልጽ የሆነ ንግግር እና እምነት እንዲኖራቸው አደረገ (6፡68-69)

**የቃላት እና የሀረጎች ጥናት**

**የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 6፡1-14**

**ከዚህ በኂላ ኢየሱስ ወደ ገሊላ ባሕር ማዶ ተሻገረ፤ እርሱም የጥብርያዶስ ባሕር ነው፡፡ በበሽተኞችም ያደረገውን ምልክቶች ስላዩ ብዙ ሕዝብ ተከተሉት፡፡ ኢየሱስም ወደ ተራራ ወጣና በዚያ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተቀመጠ፡፡ የአይሁድ በዓልም ፋሲካ ቀርቦ ነበር፡፡ ኢየሱስም ዓይኖቹን አንሥቶ ብዙ ሕዝብ ወደ እርሱ ሲመጣ አየና ፊልጶስን፡፡ እነዚህ እንዲበሉ እንጀራ ከወዴት እንገዛለን? አለው፡፡ራሱ ሊያደርግ ያለውን ያውቅ ነበርና ሊፈትነው ይህን ተናገረ፡፡ ፊልጶስ፡፡ እያንዳንዳቸው ትንሽ ትንሽ እንኳ እንዲቀበሉ የሁለት መቶ ዲናር እንጀራ አይበቃቸውም ብሎ መለሰለት፡፡ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ የስምዖን ጴጥሮስ ወንድም እንድርያስ፡፡ አምስት የገብስ እንጀራና ሁለት ዓሣ የያዘ ብላቴና በዚህ አለ፤ ነገር ግን እነዚህን ለሚያህሉ ሰዎች ይህ ምን ይሆናል? አለው፡፡ ኢየሱስም፦ ሰዎቹን እንዲቀመጡ አድርጉ አለ፡፡ በዚያም ስፍራ ብዙ ሣር ነበረበት፡፡ ወንዶችም ተቀመጡ ቍጥራቸውም አምስት ሺህ የሚያህል ነበር፡፡ ኢየሱስም እንጀራውን ያዘ፡ አመስግኖም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ፡ ደቀ መዛሙርቱም ለተቀመጡት ሰዎች ሰጡአቸው እንዲሁም ከዓሣው በፈለጉት**

መጠን። ከጠገቡም በኋላ ደቀ መዛሙርቱን። አንድ ስንኳ እንዳይጠፋ የተረፈውን ቍርስራሽ አከማቹ አላቸው። ስለዚህ አከማቹ: ከበሉትም ከአምስቱ የገብስ እንጀራ የተረፈውን ቍርስራሽ አሥራ ሁለት መሶብ ሞሉ። ከዚህ የተነሣ ሰዎቹ ኢየሱስ ያደረገውን ምልክት ባዩ ጊዜ። ይህ በእውነት ወደ ዓለም የሚመጣው ነቢይ ነው አሉ።

6:1 **"ወደ ገሊላ ባሕር ማዶ ተሻገረ፤ እርሱም የጥብርያዶስ ባሕር ነው"** ይህ ውሃ በተለያዩ ስሞች ይታወቃል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ቺኔሬዝ (በነህ 34:11) ተብሎ ተጠርቷል። እንዲሁም የጌኔሳሬት ተብሎ በሉቃ 5:1 እና በሮማን ስም የጥብርጣዶስ ተብሎ በዮሐ 21:1 ላይ ተጠርቷል። በዚህ ስፍራ ላይ ያለው የጸሓፊው አስተያየት የሚያመለክተው መጽሐፉ የተጻፈው ከፍልስጤም ውጭ ላለው ሰዎች መሆኑን ነው (6:4፣6፣ 64፣ 71)።

6:2 ሕዝቡ ለምን እንደተከተሉት አስተውሉ።

6:3 ኢየሱስ ድምጹ በድንብ እንዲሰማ የውሃ እና የተራራ ተፈጥሮአዊ የማስተጋባት ኃይልን ተጠቅሟል። "ተቀመጠ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ደቀ መዛሙርቱን ያስተማረበት ኦፊሳላዊ ጊዜ መሆኑን ያሳያል። አንድ ሰው ተራራዎቹ እንደ ማቴ 5-7 ሁሉ ሙሴን እንድያስታውሰን የቀረበ መሆኑን ልጠይቅ ይችላል።

በዚህ ትልቅ የትምህርት ጊዜ ኢየሱስ ያስተምር የነበረው የተለያዩ ዓይነት ሰዎችን ነበር። በእርሱ እግር አጠገብ የተቀመጡት ደቀ መዛሙርቱ ነበሩ፤ ከእነርሱ ቀጥሎ ደግሞ ማወቅ የሚፈልጉ፣ ሀብታሞች እና ተራ ሰዎች ተቀምጠው ነበር። እንዲሁም ትንሹ የሃይማት መሪዎች ቡድንም በዚህ ስፍራ ላይ ነበሩ።

6:4 **"የአይሁድ በዓልም ፋሲካ ቀርቦ ነበር"** የኢየሱስ የአደባባይ አገልግሎት የጊዜ እርዝማኔ ለማወቅ ብቸኛው መንገድ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የተጠቀሱት የፋሲካ በዓላት ናቸው (በመጀመሪያ 2:13፤ ሁለተኛ 6:4 እና ሦስተኛ 11:55 እና 13:1 ናቸው)። በዮሐ 5:1 ላይ ያለው የሚያመለክተው የፋሲካ በዓልን ከሆነ የአገልግሎት ዘመኑ ሦስት ዓመት ተኩል ይሆናል፤ ማለትም አራት የፋስካ በዓላት ማለት ነው። ስለ ኢየሱስ ብዙ የማናውቃቸው ነገሮች አሉ (20:23፤ 21:25)።

6:6 **"ሊፈትነው ይህን ተናገረ"** በዚህ ስፍራ ላይ ፈተና ተብሎ የተተረጎመው የግሪክ ቃል ፔራዞ ይባላል፤ ብዙ ጊዜ ክፉ ነገሮችን ያመለክታል (በ1ዮሐ 4:1፤ ማቴ 4:1 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።)። ይህ ጥሩ ምሳሌ እንደሚያሳየን ዘመናዊው አፈታትን የሚከተሉ ሰዎች አንዳድ ጊዜ የአዲስ ኪዳን ቃላትን ከትርጓሜያቸው ጋር እንደሚሄድ እንደሚያስገድዱት ጥሩ ምሳሌ ይሆነናል። ኮይኔ ግሪክ ከክላሲክ ግሪክን ብዙ ሰዋሰዋዊ እና የቋንቋ ሕግጋ ልዩነት አለው (በ5:20 ላይ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ)።

ኢየሱስ ፊልጶስን ፈትኖታል ነገር ግን እንዴት;

1. ኢየሱስ እንደ መጋቢ በእርሱ ላይ ያለውን እምነት
2. የብሉይ ኪዳን እውቀቱን (ዘዳ 11:13፤ ሙሴ እግዚአብሔር ምግብ እንድሰጣቸቸው የጠየቀበት)
3. ለሕዝቡ ያለው እንክብካቤ እና ጥንቃቄ

6:7

| | |
|---|---|
| ኤንኤሴስቢ፣ NKJV፣ ጀቢ | **"የሁለት መቶ ዲናር የምገመት"** |
| NRSV | **"የስድስት ወር ዋጋ"** |
| TEV | **"ሁለት መቶ የብር ሳንትም"** |

ዲናር ለአንድ ሠራተኛ እና ለአንድ ወታር ለአንድ ቀን የሚከፈል ዋጋ ነው (ማቴ 20:2)። ይህ ከአማተዊ ክፍያው ሁለት ሦስተኛ ያህል ነው።

**ልዩ ርዕስ: በኢየሱስ ዘመን በፍልስጤም ውስጥ አገልግሎት ላይ ይውል የነበረው ገንዘብ**

I. የመዳብ ገንዘብ
- ሀ. *ቼርማ* - በጣም ትንሽ ዋጋ ነበረው (ዮሐ 2:15)
- ለ. *ቻለካሱ* በጣም ትንሽ ዋጋ ነበረው (ማቴ 10:9፤ ማር 12:41)
- ሐ. *አሳሪኦን* - የዲናር 1/16 የሚሆን የሮማዊያን የመዳብ ሳንትም ነው (ማቴ 5:26)
- መ. *ኮደራንቴሱ* የዲናር 1/64 የሮማዊያ የመዳብ ሳንትም ነው (ማቴ 5:26)
- ሠ. *ሌፐቶኦ* የዲናር 1/128 የሚሆን የአይሁዳዊያን የመዳብ ሳንትም ነው (ማር 12:42፤ ሉቃ 21:2)

II. የብር ሳንትሞች
- ሀ. *አርጉሮስ* ("የብር ሳንትም") - ከመዳብ የተሻለ ዋጋ ያለው ነው (ማቴ 10:9፤ 26:15)
- ለ. *ዲናር*- የአንድ ቀን ሥራ ዋጋ የሆነ የሮማዊያን የብር ሳንትም ነው (ማቴ 18:28፤ ማር 6:37)
- ሐ. *ደራችሜ* - ከዲናር ጋር የሚስተካከል ዋጋ ያለው የግሪካዊያን ሳንትም ነው (ሉቃ 15:9)
- መ. *ዲ-ደራችሞን*- ሁለት ደራችሞን ከአይሁዳዊያ ግማሽ ሼክል ጋር እኩል ነው (ማቴ 17:24)

ሠ. *ስስታቴር*- አራት ዲናር ያክል ዋጋ ያለው የብር ሳንቲም ነው።
III. የወርቅ ብር- ክሩኦስ ("የወርብ ሳንቲም") በጣም ዋጋ ያለው ሳንቲም (ማቴ 10:9)
IV. የብረት አጠቃላይ ክብደት ቃላት
ሀ. *መና* - የላቲን ቃሉ ሚና ሲሆን ከመቶ ዲናር ጋር የሚስተካከል ክብደት ያለው ብረት ነው።
ለ. *ታላንቶኙ* የግሪኮች የክብደት መለኪያ ነው (ማቴ 18:24ለ 25:15፣ 16፣ 20፣ 24፣ 25፣ 28)
1. አንድ ብር 600 ዲናሬ ይናል
2. አንድ ወርቅ 180000 ዲናሬ ይሆናል
ሐ. ሼክል - የአይሁዳዊያን የብር ክብደት መለኪያ ነው (ዘፍ 23:15፤ 37:28፤ ዘጸ 21(32)
1. *ፒም*-2/3 ሼክል
2. *ቤካ* - ½ ሼክል
3. *ጌራሃ*- 1/20 ሼክል
ከባባድ ዕቃዎች መለኪያ
1. *ማኔሃ*- 50 ሼክል
2. *ኪካር*- 3000 ሼክል

**6:8-9 "የስምዖን ጴጥሮስ ወንድም እንድርያስ"** በዚህ አውድ ውስት የእንድርያስን ቀላል እምነት እና በኢየሱስ ችሎታ እና ማንነት ላይ ያለውን እምነት እንመለከታለን።

**6:9 "የገብስ እንጀራ"** ይህ በጣም ርካሽ እና ከሁሉም የማይፈለግ ዳቦ ተደርጎ የሚተይ ነው፤ የድሆች ምግብ ነው። ኢየሱስ ውድ የሆነ ምግብ ለመስጠት መለኮታዊ ኃይሉን አልተጠቀመም!

**6:10 "ሕዝቡን አስቀምጡአቸው"** በዚህ አከባቢ የሚኖሩ ሰዎች የተለመደው ምግብ አመጋገብ መሬት ላይ በመቀመጥ ነው።

▣ **"በዚያም ስፍራ ብዙ ሣር ነበረበት"** ይህ የሐዋርያው የዐይን እማኝነት ምስክር ነው።

▣ **"ወንዶችም ተቀመጡ ቊጥራቸውም አምስት ሺህ የሚያህል ነበር"** በእርግጥ ይህንን የአምስት ሺይ ሰዎች የተመገቡበት ብሎ መጥራት በጣም ተገቢ አይደለም ምክንያቱም በጣም ብዙ ሰዎች ነበሩና። ይህ አምስት ሺህ የሚለው ቃል የተጠጋጋ ቁጥር ነው እንዲሁም የሚያመለክተው ትልልቅ ወንዶችን ብቻ ነው (ይህም ማለት ከ13 አመት በላይ ያሉ ሰዎችን ማለት ነው)። እንዲሁም ይህ ቁጥር ሴቶችን እና ህጻናትን አያካትም (ማቴ 14:21)። ነገር ግን ምን ያህል ሴቶች እና ሕጻናት በስፍራው እንደነበሩ ግን መናገር በእርግጠኝነት መናር አይቻልም። (ማቴ 14:21)

**6:11 "መስግኖም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ"** የማብዛቱ ተዓማራት የተፈጸመው በኢየሱስ እጅ ላይ መሆን አለበት። በአይሁዳዊያን የመስሑ መምጣት ተስፋ አውድ ስውጥ ይህ ተግባር ሙሴ መና እንደሰጠ እንዲሁ ኢየሱስ ያደረገው ምልክት ይህንን ያሳያል።

"ምስጋና መቅረብ" ተብሎ የሚተረጎመው የግሪክ ቃል (ኢዩካሪስቶ) በኋላ ላይ ለጌታ እራት መጠሪያ ስም ለመሆን በቅቷል (1 ቆሮ 11:23-24)። ዮሐንስ ይህንን ቃል ሲጠቀም የወደፊቱን፣ ይህንን ዓይቱን ነገር ታሳቢ አድርጎ ይሆንን; ለኢዩካሪስት ያላመለከቱ ሌሎች ወንጌላት የተጠቀሙ ቃል ሌላ ሲሆን ቃሉም ኢዩሎገኤኦ ናቸው። (ማቴ 14:19፣ ማር 8:6፤ ሉቃ 17:16 ኢዩካሪስቶ የሚለውን ቃል የሚጠቀሙ ሲሆን (ማቴ 15፤36 ማር 6:41 ፤ 18:11) ነገር ግን ሁል ጊዜ በጌታ እራት ዳራ ውስጥ ግን አይደለም። ኢየሱስ የምስጋና ጸሎት ላይ የተጠቀማቸውን ቃላት በቀጥታ የሚጠቀሙ ሲሆን (ማቴ 26:27፤ ማር 14:23 እና ሉቃ 22:17-19 ናቸው)። ስለዚህ የዚህ ቃል አጠቃቀም ወጥ ስላሊሆን ዮሐንስ ይህ ቃል በጌታ እራት ዳራ ውስጥ መተርጎም እንዳለበት ማስተላለፍ ብፈልግ ኖሮ በግልጽ ይናገር ነበር።

**6:12 "እንዳይጠፉ"** *አፖሉሚ* የሚለውን በ10:10 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።

**6:13 "የተረፈውን ቊርስራሽ አሥራ ሁለት መሶብ ሞሉ"** በዚህ ስፍራ ላጥ መሶብ ተብሎ የተተረጎመው ቃል ትልልቅ ቅርጫት አይነት ነው። በተአምራት የተባዛውን ምግብ ኢየሱስ እንድባክን እንዳልፈቀደ መገንዘቢ አስፈላጊ ነው። እንዲሁም ኢየሱሱ የዳቦንም አይነት አለመለወጡንም ማስተዋል ተገቢ ነው።

"ዐስራ ሁለት" የሚለው ቁጥር ተምሳሌታዊ ጠቀሜታ ይኖረው ይሆንን፤ በእርግጠኝት ለመናር ያስቸግራል። የኢስራኤል ዐስራ ሁለቱን እንደሚወክል ተደርጎ ስተረጎም ቆይቷል (ኢየሱሱ ብሉይ ኪዳንን አርክቷል) ወይም ለኢያንዳንዱ ደቀ መዝሙር አንድ መሶብ (ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን አርክቷል እንዲሁም የሚያስፈልጋቸውን ነገር አዘጋጅቶላአዋል) ነገር ግን ይህ የዐይን ምስክር ዝርዝር መረጃ ነው (ቁ 19)።

**ልዩ ርዕስ፡ ዐስራ ሁለት ቁጥር**

ዐስራ ሁለት የሚለው ቁጥር ሁልጊዜ የመደራጀት ምሳሌያዊ ቁጥር ሆኖ ቆይቷል

ሀ. ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጭ
1. ዐስራ ሁለት የዞዲክ ምልክት ነው
2. ዐስራ ሁለት የአንድ አመት ወራት

ለ. በብሉ ኪዳን ውስጥ
1. የያዕቆብ ልጆች (የአይሁድ ዘሮች)
2. ከዚህ በታች ባሉት ውስጥ ተንጸባርቋል
   ሀ. በዘጸ 24፡4 ላይ በዐስራ ሁለቱ መሰዊያዎች
   ለ. በዘጸ 28፡21 ላይ ካህናት በሙታጠቁት ዐስራ ሁለቱ መቀነቶች (እያንዳንዱ ለእስራኤላዊያን ብሔሮችን ያመለክታል)
   ሐ. በዘሌ ውስጥ በመገናኛ ድንኳኑ ውስጥ ባለው ቅዱስ ተብሎ በሚጠራው ቦታ ላይ ያሉትን ዐስራ ሁለት ቅጣዎች
   መ. በዘዳ 13 (ከእያንዳንዱ ነገድ) የተላኩ ዐስራ ሁለት ሰላዮች
   ሠ በዘዳ 17፡2 ውስጠ በቆሬ አመጽ ወቅት (ዐስራ ሁለቱን ነገዶች ለማለከት ውሏል
   ረ. በኢያ 4፡3፣ 9፣ 20 ውስጥ የኢየሱስን ዐስራ ሁለት ድንጋዮች
   ሰ. በ1 ነገ 4፡7 ላይ በሰለሞን አመራር ውስጥ የነበሩ ዐስራ ሁለት አመራሮች
   ሸ. በ1 ነገ 18፡31 ላይ የኤልያስ ለያሕዌ መሠዊያ ሲያዘጋጅ ያስቀመጣቸው ዐስራ ሁለት ድንጋዮች

ሐ. አዲስ ኪዳን
1. የተመረጡት ዐስራ ሁለት ሐዋርያት
2. በማቴ 14፡20 ዐስራ ሁለት መሶብ ዳቦ
3. በማቴ 19፡28 ላይ የተጠቀሰው ዐስራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት የሚቀመጡበት መቀመጫ
4. በ26፡53 ላይ የተጠቀሰው ኢየሱስን ለመታደግ ልላኩ የሚችሉ ዐስራ ሁለት ሌጌዎን የመላዐእክት ሠራዊት
5. በራዕይ ውስጥ ያሉ ተምሳሌቶች
   ሀ. በ4፡4 ላይ በዙፋን ላይ የተቀመጡ ዐስራ ሁለቱ ሽማግሌዎች
   ለ. በ7፡4፤ 14፡1፣ 3 ላይ 144000 (12x12000)
   ሐ. በ12፡1 ላይ ያለችው ሴት ዘውድ ዐስራ ሁለት ኮከቦች
   መ. በ21፡2 ላይ ዐስራሁለት መግቢያ በር፣ ዐስራ ሁለት ሁለቱን ነገዶች የሚያመለክቱ  መላእክት
   ሠ. በ21፡14 በዐስራ ሁለቱ ሐዋርያት ስም ያለበት የኢየሩሳሌም ዐስራ ሁለት መሠረቶች
   ረ. በ21፡16 ላይ ዐስራ ሁለት ሺህ ስታንዲያ
   ሰ. በ21፡7 ላይ ያው 144 ክዩብ ግድግዳ
   ሸ. በ21፡21 ላይ ዐስራ ሁለት መግቢያ መሰሶዎች
   ቀ. በ22፡2 ላይ በአዲስቷ ኢየሩሳሌም ያለው ዛፍ ከዐስራ ሁለት ፍሬዎቹ ጋር

6፡14 **"ነቢያት"** ይህ በዘዳ 18፡15-22 (ሐዋ 3፡22፤ 7፡37 ላይ) የተጠቀሰው ነው፡፡ ሕዝቡ የኢየሱስን ኃይል ተረድቶዋል ነገር ግን የተልዕኮውን እና የምልክቶቹን ባህርይ ግን በትክክል አልተገነዘበም፡፡

**የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 6፡15**
**በዚህም ምክንያት ኢየሱስ ያነግሡት ዘንድ ሊመጡና ሊነጥቁት እንዳላቸው አውቆ ደግሞ ወደ ተራራ ብቻውን ፈቀቅ አለ፡፡**

6፡15 ሕዝቡ በኢየሱስ የመስሑት ለሕዝቡ ምግብን የማዘጋጀት *ሥራ* እጅግ በጣም ተገርመው ነበር፡፡ ይህ በማቴ 4፡3 ላይ የተጠቀሰው የክፉው ፈተና ከሚለው ጋር ይያያዛል፡፡

**የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 6፡16-21**
**በመሸም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ባሕር ወረዱ: በታንኳም ገብተው በባሕር ማዶ ወደ ቅፍርናሆም ይመጡ ነበር። አሁንም ጨልሞ ነበር፤ ኢየሱስም ገና ወደ እነርሱ አልመጣም ነበር፤ ብርቱ ነፋስም ስለ ነፈሰ ባሕሩ ተናወጠ። ሀያ አምስት ወይም ሠላሳ ምዕራፍ ከቀዘፉ በኋላም: ኢየሱስ በባሕር ላይ እየሄደ ወደ ታንኳይቱ ሲቀርብ አይተው ፈሩ። እርሱ ግን፦ እኔ ነኝ፤ አትፍሩ አላቸው። ስለዚህ በታንኳይቱ ሊቀበሉት ወደዱ፤ ወዲያውም ታንኳይቱ ወደሚሄዱበት ምድር ደረሰች።**

6፡17 **"ቅፍርናሆም"** በገዛ ሀገሩ በናዝሬት ሰዎች ስላልተቀበሉት ኢየሱስ በገሊላ ዙሪያ ሲያገለግል በዋነኝነት ይቀመጥ የነበረው እዚህ ነበር (ሉቃ 4፡28-29)፡፡

6:19 **"*ሀያ አምስት ወይም ሠላሳ ምዕራፍ ከቀዘፉ በኋላም*"** ኢየሱስ በውሃው ላይ እየተራመደ ወደ እነርሱ ስመጣ ባህሩ መሃል ላይ ነበሩ። የማቴዎስ ወንጌል ታርኩን በማስፋት ጴጥሮስ በውሃ ላይ የተራመደበትን ሁኔታ ዘግቦልናል።

▣ **"አይተው ፈሩ"** ደቀ መዛሙርቱ አሁንም ኢየሱስን የሚመዝኑት በምድራዊ መሥፈርት ነበር። የደቀ መዛሙርቱ ፍርሃት በማር 6:49 ላይ ሰፍሯል። የዚህ "ተአምራት" ሁኔታ እርሱ ማን እንደሆነ እንደገና እንዲያጤኑ አስገድዶዋቸዋል።

6:20 **"እኔ ነኝ"** ይህ በቀጥታ ኤጎ ኤሚ ማለት ነው። (4:26፤ 8:24፣ 28፣ 54-59፣ 13:19፤ 18:5-6) ውስጥ የተጠቀሰ ሲሆን ይህም በብሉይ ኪዳን ውስጥ በዘጸ 3:12-15 የተጠቀሰውን የቃል ኪዳን ስም የሆነውን ያሕዌን ያመለክታል። ኢየሱስ የሚታይ "እኔ ነኝ" ነው፣ የእግዚአብሔር ሙሉ መገለጥ፣ ትስጉት የሆነ የእግዚአብሔር ቃል፣ እውነት እና ብቸኛው ልጅ ነው። ከዚህ በታ ባለው ልዩ ርዕስ ስር ያለውን መ የሚለውን ነጥብ ተመለክት።

**ልዩ ርዕስ፡ የመለኮት ስሞች**

*ሀ. ኤል*

1. ምንም እንኳ ብዙ ምሁራን ቃሉ የመጣው ከአካዲያን እንደሆነ ቢያምኑም የመለኮት አጠቃላስ ስም የሆነው ቃል ትርጓሜ ምንጭ ምን እንደሆነ በእርግጠኝነት አይታወቅም (ዘፍ 17:1፤ ዘኁ 23:19፤ ዘዳ 7:21፤ መዝ 50:1)።
2. በከነአናዊናን ፓንቶን ትልቁ አምላካቸው ኤል ይባላ (ራስ ሻማራ ጽሑፍ)
3. በመጸሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኤል የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ ከሌሎች ቃላት ጋር በጣምራነት አይመጣም። ነገር ግን እንዲህ አይነቱ ጥምረት አምላክን መግለጫ መንገድ ነው
   ሀ. ኤል-ኤሌዮን (ታላቅ አምላክ) ዘፍ 14:18-22፤ ዘዳ 32:8፤ ኢሳ 14:14
   ለ. ኤል-ሮኢ (እግዚአብሔር ያያል ወይም እራሱን የሚገልጥ አምላክ) ዘፍ 16:13
   ሐ. ኤል-ሻዳይ (ሁሉን ቻይ አምላክ ወይም የምራራ አምላክ ወይም የተራራዎች አምላክ) ዘፍ 17:1፤ 35:11፤ 43:14፤ 49:25፤ ዘጸ 6:3)
   መ. ኤል-ኦላም (ፍጻሜ ዬሌለው አምላክ) ይህ ቃል እግዚአብሔር ለዳዊት ከገባው ቃል ኪዳን ጋር ስነ መለኮታዊ ቁርኝት አለው።
   ሠ. ኤል-ቤሪት (የቃል ኪዳን አምላክ) መሳ 9:46
4. ኤል የሚለው ነገር ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ጋር እኩል ነው
   ሀ. ያሕዌ መዝ 85:8፤ ኢሳ 42:5
   ለ. ኤሎሂም በዘፍ 46:3፤ እዮ 5:8 "እኔ ኤል፣ የአባትህ ኤሎሂም ነኝ"
   ሐ. ሻዳይ በዘፍ 48:25
   መ. "ቀናተኛ" ዘጸ34:14፤ ዘዳ 4:24፤ 5:9፤ 6:15
   ሠ. "መሃሪ" ዘዳ 4:31፤ ነህ 9:31
   ረ. "ታላቅ እና የሚያስፈራ" ዘዳ 7:21፤ 10:17፤ ነህ 1:5፤ 9:32፤ ዳን 9:4
   ሰ. "እውቀት" 1ሳሙ 2:3
   ሸ. "ጠንካራ መሸሸጊያዬ" 2 ሳሙ 22:33
   ቀ. "የሚበቀልልኝ" 2 ሳሙ 22:48
   በ. "ቅዱሱ" ኢሳ 5:16
   ተ. "ኃያል" ኢሳ 10:21
   ቸ. "እኔ ድነት" ኢሳ 12:2
   ፈ. "ብድራን ከፋይ" ኤር 51:56
5. በብሉይ ኪዳን ውስጥ ለእግዚአብሔር የተሰጡ አብይ ስያሜዎች/ስሞች በኢያሱ 22:22 ውስጥ ይገኛሉ (ኤል፣ ኤሎሂም፣ ያህዌህ ተደጋግመው ተጠቅሰዋል።

ለ. ኤሌዮን

1. የቃሉ መሠረታዊ ትርጉም "ከፍ ያለ"፤ የምል ነው (ዘፍ 40:17፤ 1ነገ 9:8፤ 2ነገ 18:17፤ ነህ 3:25፤ ኤር 20:2፤ 36:10፤መዝ 18:13)
2. ከሌሎች ስሞች ጋር ተመሣሣይ በሆነ መልኩ ይህ ቀል አገልግሎት ላይ ውሏል/ለመለኮት ስምነት ውሏል
   ሀ. ኤሎሂም- መዝ 47:1-2፤ 73:11፤107:11
   ለ. ያሕዌ- ዘፍ 14:22፤ 2 ሳሙ 22:14
   ሐ. ኤል- ሻዳይ መዝ 91:1፣ 9
   መ. ኤል- ዘኁ 24:6
   ሠ. ኤልሃ- ብዙ ጊዜ በዳን 2-6 እና ዕዝ 4-7 ላይ አገልግሎት ላይ የዋለ ሲሆን ከኢላር ከሚለው ቃል ጋር ተቆራኝቶ እናገኘዋለን ("ታላቅ አምላክ" ለሚለው የአራማይክ ስያሜ ነው) ፤ፀዳን 3:26፤4:2፤5:18:21
3. እስራኤላዊያን ባሆኑት ብዙውን ጊዜ ይጠቀስ ነበር፡
   ሀ. መልከፀዴቅ፤ ዘፍ 14:18-22
   ለ. በለዓም፤ ዘሕ 24:16

ሐ. ሙሴ፤ ለአህዛብ በዘፍ 32፡8 ላይ ሲናገር

መ. በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለው የሉቃስ ወንጌል ለአህዛብ ሲፅፍ ሁፐሲስቶስ የሚለውን የግሪኩን ቃል ይጠቅሳል (1፡32-35፤ 76፤6፡35፤8፡28፤ሐዋ 7፡48፤16፡17)፡፡

ሐ. ኤሎሂም (ብዙ ቁጥር)፤ ኤልሄ (ነጠላ ቁጥር) በዋናነት በግጥሞች ውስጥ ውሎ እናገኛለን

1. ይህ ቃል ከብሉይ ኪዳን ውጭ አይገኝም
2. ይህ ቃል የእስራኤልን አምላክ ልያመለክት ይችላል ወይም የአሕዛብን አማልክት ልያመለክት ይቻላል (ዘጸ 12፡12፤ 20፡3)፡፡ የአብረሃም ዘመዶች ብዙ አማልክንት ከሚያመልኩ ወገኖች ነበሩ፡፡ (ኢሳ 24፡2)
3. የእስራኤልን መሳፍንት ልያመለክት ይችላል (ዘጸ 21፡6፤ መዝ 82፡6)
4. ኤሎሂም የሚለው ቃል ሌሎች መንፈሳዊ አካላትንም ለማመልከት ውሏል (መላእክትን፣ ዳብሎስን) ዘዳ 32፡8 (ሰባ ልቃናት)፤ መዝ 8፡5፤ ዕዮ 1፡6፤ 38፡7፡፡
5. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ስሙ ነው (ዘፍ 1፡1)፡፡ እስከ ዘፍ 2፡4 ድረስ ይህ ቃል ሌሎችን ያማካተት ነበር፤ ነገር ግን በዚህ ቦታ ላይ ከያሕዌ ጋር ተያይዞ እናገኘዋን፡፡ በመሠረታዊ ሀሳቢ እግዚአብሔር ፈጣሪ፣ ቀጣይ እንድትሆን እና ሕይወት በዚህች ፕላኔት ላይ እንድቀጥል አስፈላጊውን ነገር የሚያደርግ መሆኑን ያሳያል፡፡ (መዝ 104)

   ኤል ከሚለው ስም ጋር ተለዋዋጭ ሲሆን (ዘዳ 32፡15-19)፡፡ እንዲሁም በመዝ 14 ላይ ከያሕዌ(ኤሎሄም) ጋር በዘም 53 (ያሕዌ) ጋር ተመሳሳይ ነው ልዩነቱ የስም ለውጥ ብቻ ነው፡፡
6. ምንም እንኳ በብዙ ቁጥር የሚጠቀስ እና ለሌሎች አማልክት የሚውል ቢሆንም ብዙ ጊዜ ግን የእስራኤል አምላክን ያሳያል ነገር ግን ብዙ ጊዜ ነጠላ ግሥ ጋር አብሮ የሚሄድ ሲሆን የአንድ አምላክ አምላክነት አጠቃቀም አለው፡፡
7. ይህ ቃል ኢስራኤላዊያን ባልሆኑ ሰዎች አፍ ላይ የአምላክ ስም ሆኖ እናገኘዋን፡፡

   ሀ. መልከ ጸዴቅ ዘፍ 14፡18-22

   ለ. በለአም ዘኍ 24፡2

   ሐ. ሙሴ፣ ሰለ ሌለች አሕዛብ ስናገር ዘዳ 32፡8
8. የእስራኤላዊያን አምላክ የሆነን አምላክ መጠሪያ ስሙ በብዙ ቁጥር መሆኑ የሚያስገርም ነው፡፡ ምንም እንኳ ለምን እንደሆነ ማወቅ በእርግጠኝነት ባይቻለም ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ግን አንዳንድ መላ ምቶች ናቸው

   ሀ. ዕብራዊያን ብዙ ቁጥርን አጽኖት ለመስጠት ይጠቀሙበታል፡፡ ከዚህ ጋር ተቀራራቢ የሆነው ነገር በዕብራዊያን ባሕል መሠረት በስዋሰዋቸው ውስጥ "ንጉሣዊ ክብር" የሚባል ነገር አለ፡፡

   ለ. ይህ ምናልባት እግዚአብሐየር አብሮዋቸው የሚሰበሰባቸው የመላእክት ጉባኤን ልያሳይ ይችላል (1 ነገ 22፡19-23፤እዮ 1፡6፤ መዝ 82፡1፤ 89፡5፣ 7)፡፡

   ሐ. ይህ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተገለጠውን አንድ አምላክ በሦስት አካል የሚለውን ልያሳይ ይችላል፡፡ ዘፍ 1፡1 እግዚአብሔር ፈጠረ፣ ዘፍ 1፡2፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ይሰፍፍ ነበር፤ እና ከአዲስ ኪዳን ኢየሱስ የእግዚአብሔር የፍጥረት መሳሪያ ነበር (ዮሐ 1፡3፤ 10፤ ሮሜ 11፡36፤ 1ቆሮ 8፡6፤ ቆላ 1፡15፤ዕብ 1፡2፤ 2፡10)

መ. ያሕዌ

1. ይህ ያሕዌ ቃል ኪዳን የሚገባ አምላ መሆኑን የሚያሳይ ነው፤ እግዚአብሔር አዳኝ ነው፡፡ የሰው ልጆች ቃል ኪዳኑን ሰበሩ ነገር ግን እግዚአብሔር ለቃሉ፣ ለተስፋ ቃሉ፣ ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ነው፡፡ (መዝ 103)

   ይህ ቃል በዘፍ 2፡4 ላይ ከኤሎሂም ጋር ተያዞ ተጠቅሷል፡፡ በዘፍ 1-2 ላይ ሁለት የስነ ፍጥረት ታርክ ዬለም ነገር ግን ሁለት አጽኖቶችን ግን እንመለከታለን፡፡ (1) እግዚአብሔር አጽናፍ ዓለም ፈጣሪ መሆኑን (ቁሳዊ) እና (2) እግዚአብሐየር የሰው ልጆች ፈጣር መሆኑን ልዩ በሆነ ሁኔታ እንመለከታለን፡፡ ዘፍ 2፡4-3፡24 የሰው ልጆች ልዩ ጠቀሜታ ስለ ሆነው ልዩ መገለጥ እናያለን እንዲሁም የሰው ልጆች አላማ፣ የኃጢአት ችግር እና ከዚህ ጋር ተያይዞ ስላለው አመጽ እንመለከታለን፡፡
2. በዘፍ 4፡26 "በዚያን ጊዜም በእግዚአብሔር ስም መጠራት ተጀመረ" (ያሕዌ) ነገር ግን ዘጸ 6፡3 ላይ የቀድሞዎቹ የቃል ኪዳን ሰዎች (አባቶች እና ቤተሰቦቻቸው) እግዚአብሔርን የሚያውቁት ኤል-ሻይዳ በሚል ስሙ ብቻ ነው፡፡ ያሕዌ የሚለው ስም ትርጉም የተሰጠበት አንድ ጊዜ ብቻ ሲሆን ይኼውም በጸ 3፡13-16 ላይ ነው፤ በተለይም ቁ 14 ላይ ነው፡፡ ነገር ግን የሙሴ መጽሐፍት የሚተረጎሙት በቃላት ሥረወ ግንድ ሳይን በቃላት ጫወታ ነው፡፡ (ዘፍ 17፡5፤ 27፡36፤ 29፡13-35)፡፡ ይህ ስም ያለውን ትርጓሜ በተመለከተ ዬተለያዩ መላምቶች አሉ

   ሀ. ከአረብ የቃሉ ሥረወ ግንድ በመነሳት "ጽኑ ፍቅር ማሳየት"

   ለ. ከአረብ የቃሉ ሥረወ ግንድ በመነሳት "ማዕበል" (ያሕዌ እንደ ማዕበል)

   ሐ. ኡጋርቲክ (ከነአናዊያን) የቃሉ ሥረወ ግንድ በመነሳት "መናገር"

   መ. የፊኖሲያዊያንን የጥንት ጽሑፎች በመመልከት "የሚያኖር" ወይም "የሚያጸና"

   ሠ. የዕብራይስጡን በመከተል "ያለና"

   ረ. የዕብራይስጡን በመከተል "የሚኖር"

   ሰ. ከዕብራይስጥ ቃሉን በመከተል "መኖር" (ዘፍ 3፡20) "ሕያው"

ሽ. ከዘፍ 3፡13-16 እንደምንረዳው ያልተጠናቀቀው ግሥ መደብ በተጠናቀቀ ግሥ ትርጉም እንዲጠቀስ ተደርጓል፤ "ቀድምም እንደ ነበርኩት ወደፊትም እሆናለሁ" ወይም "ቀድሞ እንደነበርኩት ወደፊትም እንዲሁ እቀጥላለሁ" ማለት ነው (ጼ.ዋሽ.ዋትስ፦ A *Survery of Syntax in the Old Test ament* ገጽ 67) ያህዌህ የሚለው ሙሉ ስም ብዙ ጊዜ አጠር ተደርጎ የሚገለፅ ወይም በቀድሞው አጠራር ይገለፃል፡፡

(1) *ያ* (*ምሣሌ ሃሌሎ-ያ*፤ BDB 219፣ አፍ 15፡2፤17፡16፤ *መዝ* 89፡9፤104፡35)

(2) *ያሁ* ("ደስ" የለም የመጨረሻ ቅጥያ ምሳ ኢሳያስ)

(3) *ኢያ* ("ኢያ" የለም ጀማሬ ላይ ምሣ ኢያሱ፣ ኢዩኤል)

3. ከሁለተኛው ቤተ መቅደስ በኋላ ባለው አይሁዳዊነት ዘመን ይህ ቃል በጣም ቅዱስ እንደሆነ እየታመነ ስለመጣ አይሁዳዊያን ይህንን ስም መጥራት ስለሚያስፈራቸው ምጻረ ቃላት አወጡለት፡፡
4. እንደ ኤል ሁሉ ያሕዌ የሚለው ቃል ከሌሎች የእስራኤል የቃ ኪዳን አምላክ መገለጫ ባሕርያትን ከሚያመለክቱ ቃላት ጋር ተያይዞ ይታያል

ሀ. *ያህዌ- ያርኤ* (*ያህዌ ያዘጋጃ ማለት ነው*) ዘፍ 22፡14

ለ. *ያህዌ -ሮፊካ* (*ያህዌ ፈዋሽ*) ዘጸ 15፡26

ሐ. *ያህዌ- ነሲ* (*ያህዌ ሰልፌ*) ዘፍ 17፡15

መ. *ያህዌ- መቃዲሽክም* (*ያህዌ ቀዳሼ*) ዘጸ 31፡13

ሠ. *ያህዌ- ሻሎም* (*ያህዌ ሰላሜ*) መሳ 6፡24)

ረ. *ያህዌ-ሰንበት* (*ያህዌ የሰራዊት*) 1 ሳሙ 1፡3፣ 11፤ 4፡4፤ 15፡2) በብዙ ጊዜ በነቢያት

ሰ. *ያህዌ-ሮኢ* (*ያህዌ እረኛዬ*) መዝ 23፡1

ሽ. *ያህዌ- ጽድቅነው* (*ያህዌ የእኛ ጽድቅ*) ኤር 23፡6

ቀ. *ያህዌ-ሽማህ* (*ያህዌ ቅርብ ነው*) ሕዝ 48፡35

6፡21 **"ወዲያውም ታንኳይቱ ወደሚሄዱበት ምድር ደረሰች"** ይህ ሌላኛው ተአምራት ይመስላል፡፡ (22-25 *ጋር ያነጻጽሩ*) ምክንያቱም የማርቆስ ወንጌል የሚነገርን በባህሩ ግማሽ ላየ እንደነበሩ ስለሆነ ነው (ማር 6፡47)፡፡ ነገር ግን በሌሎች ወንጌላት ላይ ይህን ነገር አልተጠቀሰም (ማቴ 14፡32 ወይም ማር 6፡51)፡፡

የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 6፡22-25

**በነገው በባሕር ማዶ ቆመው የነበሩ ሕዝቡ ከአንዲት ጀልባ በቀር በዚያ ሌላ ጀልባ እንዳልነበረች: ደቀ መዛሙርቱም ለብቻቸው እንጂ ሄዱ እንጂ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ታንኳይቱ እንዳልገባ አዩ፤ ዳሩ ግን ሌሎች ጀልባዎች ጌታ የባረከውን እንጀራ ወደ በሉበት ስፍራ አጠገብ ከጥብርያዶስ መጡ፡፡ ሕዝቡም ኢየሱስ ወይም ደቀ መዛሙርቱ በዚያ እንዳልነበሩ ባዩ ጊዜ: ራሳቸው በጀልባዎቹ ገብተው ኢየሱስን እየፈለጉ ወደ ቅፍርናሆም መጡ፡፡ በባሕር ማዶም ሲያገኙት፡፡ መምህር ሆይ: ወደዚህ መቼ መጣህ? አሉት፡፡**

6፡23 **"ጥብርያዶስ"** ይህችህ ከተማ በሄሮዶስ አንቲፓስ በ22 ዓም የተመሰረተች እና ዋና ከተማ ነበረች፡፡

የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 6፡26-34

**ኢየሱስም መልሶ፦ እውነት እውነት እላችኋለሁ: የምትፈልጉኝ እንጀራን ስለ በላችሁና ስለ ጠገባችሁ ነው እንጂ ምልክቶችን ስላያችሁ አይደለም፡፡ ለሚጠፋ መብል አትሥሩ፤ ነገር ግን ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር መብል የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ሥሩ፤ እርሱን እግዚአብሔር አብ አትሞታልና፡፡ እንግዲህ፡፡ የእግዚአብሔርን ሥራ እንድንሠራ ምን እናድርግ? አሉት፡፡ ኢየሱስ መልሶ፦ ይህ የእግዚአብሔር ሥራ እርሱ በላከው እንድታምኑ ነው አላቸው፡፡ እንግዲህ፡፡ እንኪያ አይተን እንድናምንህ አንተ ምን ምልክት ታደርጋለህ? ምንስ ትሠራለህ? ይበሉ ዘንድ ከሰማይ እንጀራ ሰጣቸው ተብሎ እንደ ተጻፈ አባቶቻችን በምድረ በዳ መና በሉ አሉት፡፡ ኢየሱስም፦ እውነት እውነት እላችኋለሁ: እውነተኛ እንጀራ ከሰማይ የሚሰጣችሁ አባቴ ነው እንጂ ከሰማይ እንጀራ የሰጣችሁ ሙሴ አይደለም፤ የእግዚአብሔር እንጀራ ከሰማይ የሚወርድ ለዓለምም ሕይወትን የሚሰጥ ነውና አላቸው፡፡ ስለዚህ፦ ጌታ ሆይ: ይህን እንጀራ ዘወትር ስጠን አሉት፡፡**

6፡26፣ 32፣ 53 **"እውነት እውነት እላችኋለሁ" "አሜን አሜን"** ይህ ሦስት የተለያዩ አጠቃቀሞች ያሉት የዕብራዊያን ሀረግ ነው፡፡

1. በብሉይ ኪዳን ውስጥ ይህ ቃል ‹እምነትን" ለማሳየት ውሏል፡፡ በምሳሌያዊ አጠቃቀሙ የዚህ ቃል ትርጓሜ "መጽናት" ሲሆን በአንድ ያሕዌ ማመንን መግለጽ ነው፡፡
2. የኢየሱስ አጠቃቀመን ስንመለከት ይህ ቃል ለጠቃሚ እና አስፈላጊ ለሆነ ዓረፍተ ነገርን መግቢያ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በዚህ ዘመን አሜን የሚለው ቃል ግን በእንደዚህ አይነት መንገድ አገልግሎት ላይ ስውል አንመለከትም፡፡

3. በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥም እንደ ብሉይ ኪዳን ዘመን ሁሉ ይህ ቃል የአንድን ነገር እውነተኝነት ማረጋገጫ ሆኖ እናገኘዋን።

በ1:51 ላይ ያለውን ስለ "አሜን" ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።

▣ **"የምትፈልጉኝ እንጀራን ስለ በላችሁ"** መነሻ ምክንያታቸው ቁሳዊያን እና ጊዜያዊ እንጂ መንፈሳዊ እና ዘላለማዊ አልነበርም።

▣ **"ስለጠጣችሁ"** ይህ ስያሜ "መርካት" የሚለውን ያመለክታል። ብዙውን ጊዜ የሚጠቀሰው ለእንስሳት ነው (በተለይም ለላሞች)።

6:27 **"አትሥሩ"** ይህ የአሁን ጊዜ መሐከለኛ ትዕዛዛዊ ግሥ ከአሉታዊው ቦዝ አንቀፅ ጋር የተጣመረ ሲሆን በተለምዶ ለው ሐሳብ ቀጣይነት ያለው ድርጊት መቆምን ያመለክታል። የዚህ ክፍል የብሉይ ኪዳን ታሪካዊ ዳራ ኢሳ 5 ነው። ይህ ውይይት በምዕራፍ 4 ላይ ከሴትቱ ጋር ከተደረገው ውይይት ጋር ተመሳሳይ ነው።

▣ **"ለሚጠፋ"** በ10:10 አፖሉሚ የሚለውን ልዩ መልዕክት ተመልከቱ።

▣ **"አትሞታልና"** ይህ መታተም ማለት ነው። ይህ የትክክለኝነት፣ የማንነት፣ የስልጣን እና ማረጋገጫ ነው። (ማቴ 28:8፤ ዮሐ 17:2)። TEV እና ኤንኣቪ "ማረጋገጫ" ብለው ተርጉመውታል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ለኢየሱስ አገልግሎትን ማረጋገጡን ያሳያል። 3:33 መንፈስ ቅዱስ የሚለውን ልዩ ርዕስ ተመልከቱ።

6:28 **"የእግዚአብሔርን ሥራ እንድንሠራ ምን እናድርግ? አሉት"** ይህ በመጀመሪያው ምዕተ አመት ውስጥ ይኖሩ የነበሩ አይሁዳዊያን የነበራቸውን ሃይማኖታዊ ጥያቄ ያሳያል። (ሉቃ 18:18)። ሃይሞናታዊ የሆኑ አይሁዳውያን በእነዚህ ሁለት ምክንያቶች ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት ያሰባሉ (1) በዘር ሀረጋቸው እና (2) በአፈ ታርካቸው ውስጥ በተተረጎመው መሠረት የሙሴን ሕግጋት በመጠበቅ።

6:19 **"እርሱ በላከው እንድታምኑ ነው አላቸው"** "ማመን" የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከድነት ጋር በተያያዘ መልኩ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። በ2:23 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከቱ። ይህ ቃል በመጀመሪያ ፊጹም የሆነ መታመንን የሚያሳይ ነበር። ፔሲቶስ የሚለው ቃል "ማመን"፣ "እምነት" ተብሎ ልተረጎም ይችላል። የሰው ልጆች እምነት "በእርሱ" ፣ እንጂ በሰዎች ማንነት፣ መሰጠት ወይም ትጋት ላይሀ መሆን የለበትም (1:12፤3:6)። የዚህ ክፍል የመጀመሪያው ትኩርት ከኢየሱስ ጋር የግል ግንኙነት እንዲኖር እንጂ ስለ እርሱ ትክክለኛ ስነ መለኮት እንዲኖረን አይደለም ወይም ሃይማኖታዊ ስርአቶችን መከተልን አይደለም። እነዚህ ሁሉ አስፈላጊዎች ናቸው ነገር ግን ቅድሚያ የሚነሰጣቸው ነገሮች ግን አይደሉም። ኢየሱስ በዚህ ስፍራ ላይ ብዙ ቁጥር ያውን "ሥራዎች" የሚለውን ቃል ተጠቅሟል፤ ነገር ግን ጥያቄያቸው ነጠላ ቁጥር ያለው "ሥራ" ነው።

"መላክ" ለሚለው ቃል በ5:24 ላይ መላክ (አፖስቶሎ) የሚለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

6:30-33 ማስታወስ የሚገባን እነዚህ ቡድኖች የኢሱስን የአምስት ሺህ ሰዎችን የመገበበትን ተአምራት ተካፍለዋል። የሚፈልጉትን ምልክቶች አግኝተዋ። አይሁዳዊያን መምህራን የሚመጣው መሲሕ አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ተግባሮችን እንደሚፈጽም ያምኑ ነበር፤ እነዚህም መናን ማውረድ (2 ባሩክ 29:8)። መምህራኑ መዝ 72:6 መስሑ "ለሙሴ" የሚበልጥ መሆኑን ማረረጋገጫ አድርገው ይጠቀሙብታል። (1 ቆሮ 1:22 ን ይመ.)

"በእርሱ ማመን" በሚለው እና "እንዲያምኑህ" በሚሉ ቃል መካከል አስፈላጊ ስዋሰዋዊ ልዩነቶችን አሉ። ቁ. 30። የመጀመሪያው የሚያተኩረው በኢየሱስ ማመን የሚለውን የዮሐንስን የቃላት አወቃቀር ነው። ይህ ግለሰባዊ አቅጣጫ ያለው ነው ሁለተኛው የሚያተኩረው የኢየሱስን ቃላት ማመን ላይ ነው ወይም በይዘት ላይ የሚያተኩር ሃሳብን ያሣያል። ወንጌል ስብዕናም መልዕክትም መሆኑን አስተውል። በ2:23 ላይ ያለውን ልዩ የጥናት ርዕስን ይመልከቱ።

6:31 **"ተብሎ እንደ ተጻፈ"** ከብሉይ ኪዳን በቀጥታ የተወሰደ ነገርን ማሳያ ትክክለኛ መንገድ ነው። የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ስልጣን እንዳለው እና በእግዚአብሔር እስትንፋስ የተጻፈ መጽሐፍ ለመሆኑ የሚያረጋግጥልን ዘይቤያዊ አነጋር ነው። ይህ ጥቅስ ከብሉይ ኪዳን ብዙ ቦታ የተወሰደ ሊሆን ይችላል መዝ 78:24፤105:40፤ ዘጸ 16:4፣ 15 ወይም ነህ 9:15።

6:32 ኢየሱስ አይሁዳዊያን ዘንድ ስለ ተለመወደው ስነ መለኮት እየተናገር ነበር። በዘዳ 18:15፣ 18 ላይ መስሑ ታላላቅ ተአምራትን እንደሚያደረግ ስለሚናር አይሁዳዊያን መስሑ እንደ ሙሴ ያለ ተአምር እንዲያደር ይጠብቁ ነበር። ኢየሱስ ይህንን እሳቤያቸውን በተለያየ ስፍራ ላይ እንዲያስተካክሉ ነገሮዋቸዋል።

1. መናን የሰጣቸው እግዚአብሔር እንጂ ሙሴ አይደለም
2. ምንም እንኳ መና ሰማያዊ እንደሆነ ሕዝቡ ቢያስቡም ሰማያዊ ግን አይደለም (መዝ 78:23-25
3. እውነተና ሰማያዊ እንጀራ ኢየሱስ ነው፤ ይህ ያለፈ ነገር ሳይሆን ነባራዊም ጭምር ነው

**6:33 "ከሰማይ የሚወርድ"** ይህ የዮሐንስ ዋና ሀሳብ ነው (13:13) ይህ ኢየሱስን መለኮታዊ ምንጭ (ቁ 33፣ 38፣ 41፣ 42፣ 50፣ 51፣ 58 እና 62) ያሳያል፡፡ እንዲሁም መና በሚለው ቃል ላይ የተደረገ የቃላት ጫወታ ሲሆን እውነተኛ የሕይወት እንጀራ የሆነው ኢየሱስ ከሰማይ መምጣቱን ያሳያል፡፡

ይህ ቃል በቃል "የእግዚአብሔር እንጀራ ማለት ከሰማይ በቀጥታ የወረደ ማለት ነው"፡፡ በዚህ ሥፍራ የወንድ ፃታ አመልካች የሆነው የአሁን ጊዜ ድርጊት ገላጭ ቦዝ አንቀፅ የሚያመለክተው (1) "ዳቦን" ወይም (2) ሰው የሆነውን ኢየሱስ፡፡ ብዙውን ጊዜ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ እንዲህ አይነቱ አሻሚነት ሆን ተብሎ የሚደረግ ነው (ጣምራ አገባብ)፡፡

◘ **"ሕይወትን የሚሰጥ"** ይህ ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣበት አለማ ነው (3:16፤ ማር 10:45፤2ቆሮ 5ለ21)፡፡ ግቡ "አዲስ ሕይወት"፤ "ዘላለማዊ ሕይወት"፤ "አዲስ የሕይወት ዘመን"፤ "እግዚብሔርን የሚመስል ህይወት" በዚህች ጠፊ በሆነችው ምድር ውስጥ መስጠት እንጂ ለጥቅት ሰዎች መስጠት አይደለም፡፡

6:34
NASB፣ NKJV "ጌታ"
NRSV፣ TEV
NJB፣NET
NIV፣REB "ጌታዬ"

እነዚህ ሁለት ቃላት ኩሪዮስ የሚለው የግሪክ ቃል ያለውን የተለያዩ ትርጉሞችን ያሳያል፡፡ በዚህ አውድ ውስጥ ሁለተኘው ትርጓሜ ተስማሚ ነው፡፡ ሕዝቡ ኢየሱስን ወይም ንግግሩን አልተረዱም ነበር፡፡ እርሱ መሲሕ እንደሆነ አልተገነዘቡም (ዮሐ 4:14፤ 5:7)፡፡

◘ **"ይህን እንጀራ ዘወትር ስጠን አሉት"** ይ በውሃ ጉድጓድ አጠገብ ያገኛ ሴት በ4:14 ካላቸው ንግግር ጋር ተቀራራቢ ነው፡፡ እነዚህ አይሁዳዊያን ኢየሱስ ኢየተናገረ የነበረውን መንፈሳዊ ንግግር እነርሱም አልተረዱትም ነበር፡፡

| |
|---|
| የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 6:35-40<br>**ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፦ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ የሚያምንም ሁልጊዜ ከቶ አይጠማም፡፡ ነገር ግን አይታችሁኝ እንዳላመናችሁ አልኋችሁ፡፡ አብ የሚሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል: ወደ እኔም የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም፤ፈቃዴን ለማድረግ አይደለም እንጂ የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ ከሰማይ ወርጃለሁና፡፡ ከሰጠኝም ሁሉ አንድን ስንኳ እንዳላጠፋ በመጨረሻው ቀን እንዳስነሣው እንጂ የላከኝ የአብ ፈቃድ ይህ ነው፡፡ ልጅንም አይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወትን እንዲያገኝ የአባቴ ፈቃድ ይህ ነው: እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ፡፡** |

**6:35 "የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ"** ይህ ኢየሱስ እራሱን "እኔ ነኝ" ብሎ ከጠራባቸው ስፍራዎች አንዱ ነው፡፡ ይህም የዮሐንስ ወንጌል አንዱ መገለጫ ባሕርይ ነው (6:35፣ 41፣ 48፣ 51፤ 8:12፤ 10:7፣ 9፣ 11፣ 14፤ 11:25፤ 14:6፤ 15:1፣ 5)፡፡ የዮሐንስ ወንጌል ትኩረት የሚሰጠው በኢሱስ ማንነት ላይ ነው፡፡ ይህ ከዮሐንስ ስለ መናው ካለው መረዳት ጋር የተያያዘ ነው እንዲሁም አዲሱ ሕገ ሰጭው እና ከአዲስ ዘጸአት ጋር ይያያዛል፡፡ 8:12 ላይ ያለውን ልዩ ትንታኔ ይመልከቱ፡፡

◘ **"ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ የሚያምንም ሁልጊዜ ከቶ አይጠማም"** እነዚህ በግሪክ ጠንካራ የሆኑ ጣምራ አሉታዊ አባባሎች ናቸው፤ "በፍፁም በፍፁም አይሆንም" ቁ.37 ንያስ.)

"መምጣት" እና "ማመን" በሚሉ ቃላት መካከል ትይዩ ግንኙነት አለ (7:37-38 ላይ መስማት እና ማየት መካከል እንዳለው ግንኙነት ማለት ነው›) የአማኞች መምጣት እና ማመን የአንድ ቀን ውሳኔ ሳይሆን የዚህ የአኗኗር ዘይቤ፣ ጓደኝነት እና ህብረት ጅማሬ ነው፡፡

◘ **"አይራብም . . . አይጠማም"** መራብ እና መጠማት መንፈሳዊ እውነታን ብዙ ጊዜ የሚገልጹ ቃላት ናቸው (መዝ 42:1፤ ኢሳ 55:1፤ አሞ 8:11-12፣ ማቴ 5:6)፡፡

**6:36 "አይታችሁኛል"** አንዳንድ የጥንት ምንጮች (MSSN፣A፣ብዙ የላቲን ብሉይ ኪዳኖች፣ እና የሶርያ ትርጉሞች) "እኔ" የምትለዋን ቃል ይገድፋሉ፤ በዚህም ኢየሱስ ያደረገውን ንግግር ምልክቱን ለማሣየት (ሕዝቡን መመገቡ) ይጠቀማሉ፡፡ ተውላጠ ስሙ በብዙዎች የግሪክ ምንጮች እና እትሞች ውስጥ የተካተተ በመሆኑ የዩ.ቢ.ኤስ[4] መጽሐፍቅዱስ የትኛው የመጀመሪያው እንደሆነ ሊወስን አልችልም፡፡

**6:37 "አብ የሚሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል"** የዚህ ዓረፍተ ነገር ዋና አጽኖት እግዚአብሔር ሉአላዊነት ነው፡፡ የዚህ ስነ መለኮታዊ ሀሳብ ግልጽ ማስረጃዎች ሮሜ 9 እና ኤፌ 1:3-4 ነው፡፡ የሚገርመው ነገር በሁለቱም አውዶች ውስጥ የሰው ልጆች ምለሽ አስፈላጊነቱ መጠቀሱ ነው፡፡ ሮሜ 10 7 ሁሉንም ሰዎች የሚያካትቱ ቃላት አሉ፡፡ ይህ በኤፌ 2 ላይም

እንዲሁ፡፡ 1-7 እግዚአብሔር ጻጋ የተብራራባት ሲሆን ቁ 8 እና 9 ደግሞ ለእምነት የቀረበ ጥር ነው፡፡ ቅድመ ውሳኔ የዳኑ ሰዎች አስተምህሮ እንጂ ላልዳኑ ሰዎች መሰናከያ አይደለም፧፡ ይህንን አስተምህሮን ለመክፈት ቁልፉ የእግዚአብሔር ፍቅር እና የእግዚአብሔር ጻጋ እንጂ ዘላለማዊ ውሳኔ አይደለም፡፡ አስተውሉ እግዚአብሔር ለኢየሱስ የሰጠው ሁሉ ወደ እርሱ ይመጣል፡፡ ሁል ጊዜም የመጀመሪያው እርምጃ የሚወስደው እግዚአብሔር ነው፡፡ (44፣ 65) ነገር ግን የሰው ልጆች ምለሽ መስጠት አለባቸው፡፡ (1፡12፣ 13፤ 3፡16)፡፡ በ3፡16 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከቱ፡፡

▣ **"ወደ እኔም የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም"** ይህ ሌላው ጠንካራ የሆነ ጣምራ አሉታዊ አባባል ነው፡፡ ይህ እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ በደስታ መጥራቱን እና መቀበሉ ላይ አጽኖት ይሰጣል፡፡ በድህነት ማረጋገጫ ላይ ምንኛ ጥሩ ጥቅስ ነው (ሕዝ 18፡21-23፤30-32፤ 1ጢሞ2፡4፤2 ጴጥ3፡9)፡፡ እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ቀደሚውን ሥፍራ ይወስዳል (ቁ44፡65)፤ ነገር ግን ሰዎች ምላሽ ሊሰጡ ይገባል (ማር 1፡15፤ ሐዋ 20፡21)፡፡ (ሮሜ 8፡31-39)፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ የክርስቲያኖች የድነት ማረጋገጫ**

ማረጋገጫ (1) መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት (2) የአማኞች እምነት እና (3) የሕይወት ዘይቤ

- ሀ. ለማረጋገጫ ማጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት
  1. የእግዚአብሔር አብ ባሕርይ
     - ሀ. ዘፍ 3፡15፣ 12፡3
     - ለ. መዝ 46፡10
     - ሐ. ዮሐ 3፡16፤ 10፡28-29
     - መ. ሮሜ 8፡38-39
     - ሠ. ኤፌ 1፡3-14፤ 2፡5፣ 8-9
     - ረ. ፊል 1፡6
     - ሰ. 2 ጢሞ 1፡12
     - ሽ. 1 ጴጥ 1፡3-5
  2. የእግዚአብሔር ወልድ ሥራ
     - ሀ. የክህነት ጸሎቱ  ዮሐ 17፡9-24በተለይም ቁ 12
     - ለ. የትኪ መስዋእትነቱ
       1) ሮሜ 8፡31
       2) 2ቆሮ 5፡21
       3) 1ዮሐ 4፡9-10
     - ሐ. ቀጣይነት ያለው የመማለድ ሥራው
       1) ሮሜ 8፡34
       2) ዕብ 7፡25
       3) 1ዮሐ 2፡1
  3. የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የማስቻል ኃይሉ
     - ሀ. ጥሪው ዮሐ 6፡44፣ 65
     - ለ.  ፊውሱ
       1) 2ቆሮ 1፡22፤ 5፡5
       2) ኤፌ 1፡13-14፣ 4፡30
     - ሐ. የግል ማረጋገጫው/ ምስክርነቱ
       1) ሮሜ 8፡16-17
       2) 1ዮሐ 5፡7-13
- ለ. የአማኞች አስፈላጊ ቃል ኪዳናዊ ምላሽ
  1. የመጀመሪያ እና ቀጣይነት ያለው ንስሐ እና እምነት
     - ሀ. ማር 1፡15
     - ለ.  ዮሐ 1፡12
     - ሐ. ሐዋ 3፡16፣ 20፡21
     - መ. ሮማ 10፡9-13
  2. የድነት ግብ ክርስቶስን መምሰል እንደሆነ ማስታወስ
     - ሀ. ሮሜ 8፡28-29
     - ለ. ኤፌ 1፡4፤ 2፡10፤ 4፡13
  3. ማረጋገጥ የሚቻለው በሕይወት ዘይቤ መሆኑን ማስታወስ
     - ሀ. ያዕቆብ
     - ለ. 1 ዮሐንስ
  4. ማረጋገጫ የሚገኘው በሚሠራ እምነት እና ጸንቶ በመቆም መሆኑን ማስታወስ

| |
|---|
| ሀ. ማር 13፡13<br>ለ. 1ቆሮ 14፡2<br>ሐ. ዕብ 3፡14፤ 4፡14<br>መ. ዕብ 1፡10<br>ሠ. ይሁ 20-22 |

**6፡38 "ከሰማይ ወርጃለሁና"** ይህ ትስብእትን የሚያመለክት ክፍል ነው (ዮሐ 1፡1፤ ኤፌ 4፡8-10) ውጤቱም አሁንም አለ፡፡ ከዚህ በተጨማር የኢየሱስን ከሰማይ መምጣቱን ያሳያል (41፤ 61)፡፡

▣ **"ፈቃዴን ለማድረግ አይደለም እንጂ የላከኝን ፈቃድ"** አዲስ ኪዳን የሥላሴን አንድነት ያረጋግጣል (በ14፡6 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡) ለምሳሌ 14፡8-9 ላይ  እንዲሁም የሦስቱን አካላት ልዩነትም ያሳየናል (14፡8-9)፡፡ ይህ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የኢየሱስን ለአባቱ የመገዛቱን ነገር አጽንቶ የገለጠበት አንዱ ክፍል ነው፡፡

**6፡39 "ከሰጠኝም ሁሉ አንድን ስንኳ እንዳላጠፋ"** በቁጥር 37 ላይ በሚገኘው "ሁሉ" በሚለው ግዑዝ ነጠላ ቁጥር እና በቁጥር 39 ላይ ባለው ግፁዝ ነጠላ ቁጥር መካከል ግልፅ የሆነ ተዛምዶ አለ፡፡ ዮሐንስ ይህንን ያልተለመደ አቀራረብ ለበርካታ ጊዜያት ጠቅሶታል (17፡2፡24ን ያስ.)፡፡ በግልፅ የሚያተኩረውም ጠቅላላውን ነው( ቁ40፡45)፡፡

ይህ የእግዚአብሔር የመጠበቅ የተስፋ ቃል ኃይል ሲሆን ለክርስቲያኖችም ማስተማመኛ ነው (ዮሐ 10፡28-29፤ 17፡2፣ 24፤ በ1ዮሐ 5፡13 ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከቱ)፡፡ በቁጥር 31 ላይ ያለው የጊዜ አመልካች ግሥ የአሁን ጊዜ መሆኑን በቁጥር 39 ላይ ያለው ደግሞ የተጠናቀቀ ድርጊት አመልካች መሆን ያስተውሉ፡፡ የእግዚአብሔር ስጦታ ለዘላለም ይኖራል! ከዚህም ባሻገር በቁጥር 39 ላይ የተሰጡት ማረጋገጫዎች በግሪኩ ድርጊት ገላጭ ናቸው፡፡ ኢየሱስ አብ ከሰጠው አንድም አልጠፋበትም (ቁ.37 እና 38)እንዲሁም ደግሞ የእርሱ የሆኑትን በመጨረሻው ቀን ያስነሣቸዋል (ቁ.44 ን ያስ.)
መለኮታዊ የተስፋ ቃላቱ እነዚህ ናቸው፡፡ (1) ምርጫ እና (2) ማረጋገጫ

ይህ የማጠቃለያ ቀን በተለያዩ መጠርያዎች ተጠርቷል

1. የመጨረሻው ቀን 6፡39፣ 40፣ 44፣ 54፤ 11፡24፤ 12፡48 2ጢሞ 3፡1፤ 1ጸየት 3፡3
2. የመጨረሻው ዘመን 1ዮሐ 2፡18፤ ይሁ 18
3. ያ ቀን ማቴ 7፡22፤2ጢሞ 1፡12፣ 18፤ 4፡8
4. ቀን ሐዋ 17፡31
5. ታላቁ ይሁ 6
6. ቀኑ ሉቃ 17፡30፤ 1ቆሮ 3፡13፤ 1ተሰ 5ለ4ለ እብ 10፡25
7. የእርሱ ቀን ሉቃ 17፡24
8. የጌታ ቀን 1ተሰ 5፡2፤ 2ተሰ 2፡2
9. የክርስቶስ ቀን ፊል 1፡10፤ 2፡16
10. የጌታ የኢየሱስ ቀን 1ቆሮ 1፡8፤ 5፡5፤
11. የጌታ ኢየሱስ ቀን 2ቆሮ 1፡14
12. የክርስቶስ ኢየሱስ ቀን ፊል 1፡16
13. የሰው ልጅ ቀን ሉቃ 17፡24 (ቁ 7 ተመልከት)
14. የፍርድ ቀን ማቴ 10፡15፤ 11፡22፣ 24፤ 12፡36፤ 2ጴጥ 2፡9፤ 3፡7፤ 1ዮሐ 4፡17
15. የቁጣ ቀን ራዕ 6፡17
16. የእግዚአብሔር ታላቁ ቀን ራዕ 16፡14

▣ **"በመጨረሻው ቀን እንዳስነሳው እንጂ"** ይህ የሚያመለክተው የአማኞችን የትንሳኤ ቀን እንጂ የማያምንቱን የፍርድ ቀን አይደለም (ቁ. 40፣44፤5፡25፣28፤ 11፡24 እና 1.ቆሮ.15)፡፡ፍራንክ ሰቴጅ የተባለው ጸሐፊ የአዲስ ኪዳን ሥነ መለኮት በተሰኘው መጽሐፉ ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ጠቃሚ አሳብ ጽፎአል፡፡ እንዲህ በማለት "የዮሐንስ ወንጌል ስለሚመጣው የጎላ ትኩረት የሚሰጥና  (14፡3፣18-28፣16፡16፣22) "በመጨረሻው ቀን ስለሚሆነው ትንሳኤና የመጨረሻ ፍርድ በግልጽ የሚናገር ነው (5፡28ና29፤4፡23፣5፡25፤6፡54፤11፡23ና የሚቀጥሉት ጥቅሶች፤12፡28፣31፤13፡31-32፤14፡17፣17፡26)" (ገጽ. 311)፡፡

**6፡40 "ያባቴ ፈቃድ ይህ ነው፡፡"** ይህ በቁ.28 ላይ "የእግአብሔርን ሥራ እንድንሠራ ምን እናድርግ?" ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ ኢየሱስ የሰጠው መልስ ነው፡፡ በመጨማሪ በምዕ.4፡34 ላይ ‹የእግዚአብሔር ፈቃድ› የሚለውን አርዕስት ይመልከቱ፡፡

▣ **"ልጅንም አይቶ….. ሁሉ"** ‹ማየት›ና ‹ማመን› የሚሉት ተመሳሳይ የአሁን ጊዜ የድርጊት ግሦች (ልክ በቁጥር 35 ላይ እንዳሉት "መምጣት" እና "ማመን" እንደዚሁም "ማየት" እና "መስማት") ናቸው፡፡ እነዚህ እንግዲህ የአንድ ጊዜ ድርጊት ብቻ ሳይሆኑ ቀጣይነት ያላቸው ድርጊቶች ናቸው፡፡ "ማየት" የሚለው ቃል ትርጉም አንድ ነገር ለማወቅ እና ለመረዳት በጓጓ መልኩ "በሙሉ አሳብ ትኩር ብሎ ማየት" ማለት ነው፡፡
እኔ በርግጥ "ሁሉ"  የሚለውን ቃል እወደዋለሁ፡፡

1. ሁሉ በእርሱ በኩል እንዲያምኑ፣ (1:7)
2. ለሰው ሁሉ የሚያበራው፣ (1:9)
3. በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው፣ (3:15)
4. በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ፣ (3:16)
5. ሰዎች ሁሉ.....ወልድን ያከብሩት ዘንድ፣ (5:23)
6. -9 ዮሐንስ 6:37፣39፣40፣45።
10. ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም፣ (11:26)
11. እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ያልሁ እንደሆን ሁሉን ወደእኔ እስባለሁ (12:32)።
12. በእኔ የሚያምን ሁሉ በጨለማ አይኖርም (12:46)።

ይህ የልዕልና ምስጢር ነው (ቁ. 38-39፣ 17:2፣24 እና ነፃ ፈቃድ)። በመጠኑም ቢሆን ተመሣሣይ ናቸው። እንደእኔ እምነት የ"ቃል ኪዳን" ሥነ መለኮታዊ አሳብ በሚገባ ሁለቱንም አንድ ያደርጋቸዋል።

▣ **"በእርሱ የሚያምን"** በመጀመሪያ ደህንነት የግንኙነት ጉዳይ መሆኑን ያስታውሱ። የዶግማ፣የጥሩ ሥነ መለኮት እና የግብረገባዊ ሕይወት ጉዳይም አይደለም (ምዕ. 3:16፣11:25-26)። ትኩረቱ በእምነት ላይ እንጂ በጥልቅ የአስተሳሰብ ብርታት ላይ አይደለም። በ2:23 ላይ ያለውን ልዩ አርእስት ይመልከቱ። በቁ 37ሀ፣39፣44፣65 ላይ ያለውን የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ምርጫ እና በቁ.37ለ፣40 ላይ ያለውን የሰው ዘር የእምነት ምላሽ ሚዛናዊ ትኩረት ልብ ይበሉ። እነዚህ ሁለት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጉዳዮች ባግባቡ ሊያዙ ይገባል። የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት እና የሰዎች ነፃ ፈቃድ መንታ አቅጣጫዎች ያሉትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ኪዳን ይመሠርታሉ።

▣ **"የዘላለም ሕይወት እንዲያገኝ"** ይህ የአሁን ጊዜ ድርጊትን የሚያሳይ ዓረፍተ ነገር ቢሆንም፤ መልስ ግን ያስፈልጋል (1ኛ ዮሐ.5:11)። ደግሞም ቁጥር 39 ብዛትን ሲያመለክት ቁጥር 40 ደግሞ ግለሰብን እንደሚያመለክት ልብ ይበሉ። ይህ ስለድነት እርስ በርሱ የሚጣረስ ይመስላል።

**የNASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 6:41-51**

[41]እንግዲህ አይሁድ፦ ከሰማይ የወረደ እንጀራ እኔ ነኝ ስላለ ስለ እርሱ አንጎራጎሩና፦[42] አባቱንና እናቱን የምናውቃቸው ይህ የዮሴፍ ልጅ ኢየሱስ አይደለምን እንግዲህ፦ እንግዲህ ከሰማይ ወርጃለሁ እንዴት ይላል? አሉ። [43]ኢየሱስ መለሰ አላቸውም፦ እርስ በርሳችሁ አታንጎራጉሩ። [44]የላከኝ አብ ካሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም፤ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሳዋለሁ። [45]ሁሉም ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ ተብሎ በነቢያት ተጽፎአል፤ እንግዲህ ከአብ የሰማ የተማረም ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል። [46]አብን ያየ ማንም የለም ከእግዚአብሔር ከሆነ በቀር እርሱ አብን አይቶአል። [47]እውነት እውነት እላችኋለሁ የዘላለም ሕይወት አለው። [48]የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ። [49]አባቶቻችሁ በምድረበዳ መና በሉ ሞቱም፤ [50]ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት ከሰማይ አሁን የወረደ እንጀራ ይህ ነው። [51] ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፤ እኔም ስለ ዓለመ ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው።

▣ 6:41 **"ስለዚህ አይሁድ ያጉረመርሙ ነበር"** ይህ እንከንን የሚያመለክት ዓረፍተ ነገር የሚያመለክተው በተደጋጋሚ ያጉረመርሙ እንደነበር ወይም ማጉረምረማቸውን ነው። ይህ ሁኔታ በምድረ በዳው የመቅበዝበዝ ዘመን (ዘፀአት እና ዘሑልቁ) ከነበራቸው ማጉረምረም ጋር ተመሳሳይ መሆኑን የሚያስታውስ ነው።በዚያን ዘመን የነበሩ እስራኤላውያን ደግሞ እንጀራ በምድረ በዳ የሰጣቸውን የእግዚአብሔርን ወኪል ሙሴን ይቃወሙ ነበር።

6:42 ይህ ጥቅስ ኢየሱስ ስለራሱ አንደተናገረ አይሁዳውያን መረዳታቸውን ያሳያል። ኢየሱስ ቀድሞም የነበረና መለኮታዊ መሆኑን የአይሁዳውያንን የአባባል ዘዬ በመጠቀም ያውጅ ነበር! ከአንድ ገሊላዊ አናጢ የሚመጡት እነዚህ የኢየሱስ ቃሎች አስደንጋጭ ናቸው! እንደዚህ ባሉ ጠንካራ ቃሎች ኢየሱስ ስለራሱ ይናገር ነበር። ስለዚህ እርሱ፦

1. በሥጋ የመጣ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ በቃሉና በሥራው የዘላለምን ሕይወት የሚያመጣ ነው።
2. አስቀድሞ አስቦ ሐሰትን ያሚያወራ ነው።
3. እብድ ነው (የተወሰደው ከጆሽ ማክዶናልድ፣ኤቪደንስ ዛት ዴማንድስ ኤ ቨርዲክት ነው)።

የኢየሱስ ቃሎች እውነተኛነት የክርስትና ዋና ጉዳይ ነው።

6:43 **"እርስ በርሳችሁ አታንጎራጉሩ"** ይህ የአሁን ጊዜ ትዕዛዝና ተቃርኖአዊ አረፍተ ነገር ነው። ይህ በተለመደ ትርጉሙ በማደግ ላይ ያለን እንቅስቃሴ ለማቆም የተባለ ነው።

6:44 **"የላከኝ አብ ካሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም፣"** ተነሳሽነቱን ሁል ጊዜ የሚወስደው እግዚአብሔር ነው (ቁ. 65 እና 15:16)። መንፈሳዊ ውሳኔዎች ሁሉ የሰው ኃይማኖታዊነት ውጤት ሳይሆኑ የፍቅር መንፈስ ውጤት ናቸው (ኢሳ.53:6)። የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት እና የሰው ኃላፊነት የተሞላበት መልስ ሊለያዩ የማይችሉ ፍጹም በእግዚአብሔር ፈቃድና ምህረት የተያያዙ ናቸው። ይህ የብሉይ ኪዳን የቃል ኪዳን ጽንሰ ሃሳብ ነው።

"የእግዚአብሔር መሳብ" ሚዛኑ በዮሐንስ 12:32 ላይ ከሚገኘው "ሁሉን ወደ እርሱ ይስባል" የሚለው ነው። ይህ ስበት በብሉይ ኪዳን ለእግዚአብሔር ነብያዊ ቃል መልስ የማይሰጠውን የእግዚአብሔርን ሕዝብ የኑሮ ዘዬ ተገላቢጦሽ ነው

(ለምሳሌ፡- ኢሳ 6፡9-13፣ኤርምያስ)፡፡ አሁን እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ የሚናገረው በልጁ ነው እንጂ በእሥራኤል ነብያት አይደለም (ዕብ. 1፡1-3)፡፡ በ5፡24 ላይ ‹ላክ› (አፖስተሎ) የሚለውን ልዩ አርዕስት ይመልከቱ፡፡

6፡45 **"በነብያት ተጽፎአል"** ይህ ጥቅስ የተወሰደው ከኢሳ. 54፡13 ወይም ኤር.31፡34 "አዲሱን ኪዳንን" ከሚያመለክተው የውስጣዊ (አዲስ ልብ፣አዲስ አስተሳሰብ) ማብራሪያ ነው፡፡

▣ **"ከአብ የሰማ የተማረም ሁለኩ ወደ እኔ ይመጣል"** እግዚአብሔርን አውቀዋለሁ እያሉ ኢየሱስ መካድ የማይሆን ነገር ነው (1.ዮሐ.5፡1-12)፡፡

6፡46 **"አብን ያየ ማንም የለም"** የኢየሱስ ማረጋገጫ የሚያመለክተው አንድ ሰው በእርግጥ እግዚአብሔርን ማወቅና መረዳት የሚችለው በእርሱ በኩል ብቻ ነው (ዮሐ.1፡18፣14፡6፣9)፡፡ በእውነት ሙሴም እንኳ *እግዚአብሔር*(ያህዌ)ን በፍጹም አላየውም (5፡12ን ይመልከቱ፡፡)፡፡

6፡47 ይህ ጥቅስ ለሰው ሁሉ የሆነው የኢየሱስ የድነት ሥጦታ እጥርጥር ነው ("በእኔ የሚያምን" የሚለው የአሁን ጊዜ ሳልስ ቅጽል፤ "የዘላለም ሕይወት" 51፣58፤ 3፡15፣16፣36፤ 5፡24፤ 11፡26፤ 20፡31)፡፡ ኢየሱስ እውነተኛው የእግዚአብሔር መገለጥ ነው፤ብቸኛ የእግዚአብሔር እውነተኛ ታዛዥ (በወንጌሉ ብቸኛ የሆነ፣ 10፡1-6፣7-9፤ 14፡6)፣ ደሞም ለአዳም ወንዶችና ሴቶች ልጆች ሁሉ የቀረበ (በወንጌሉ 1፡4፣7፣12፤ 3፡16፤ዘፍ.3፡15፤ 12፡3 የተጻፉት ሁሉ ፍጻሜ) ነው፡፡

6፡50 ይህ ጥቅስ፣ በቁ.31-35 እንዳለው፣ በአካላዊ እንጀራ (መና) እና መንፈሳዊ እንጀራ (ኢየሱስ) ትርጉም ላይ የተደረገ ጨዋታ ነው፡፡ አንደኛው አካላዊውን ሕይወት የሚሰጥና የሚደግፍ የተደጋገመ ስጦታ ቢሆንም ግን በመጨረሻ ሞትን ለማቆም የማይችል ነው፡፡ ሌላኛው የዘላለምን ሕይወት የሚሰጥና የሚደግፍ ሲሆን በሌላ በኩል ግን ሊቀበሉትና ሊመገቡት የተገባና መንፈሳዊ ሞትን (ከእግዚአብሔር ጋር የነበረን ግንኙነት የሰበረ፤ ከኃጢአትና ከራስ ጋር ጥብቅ ቁርኝት) እንዲያበቃለት ያደረገ ነው፡፡

6፡51 "ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ" ይህ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ከሚታወቁት "እኔ" የሚልን ቃል ከያዙ ዓረፍተ ነገሮች አንዱ ነው (6፡35፣48፣51)፡፡ ይህ ኢየሱስ የትኩረትን አቅጣጫ ወደ ራሱ አካላዊነት ያደረገበት ቃል ነው፡፡ መዳን እንደ መገለጥ ሁሉ በመጨረሻ ተጨባጭ ነው፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡- 6፡52-59

**[52]እንግዲህ አይሁድ፣ ይህ ሰው ሥጋውን ልንበላ ይሰጠን ዘንድ እንዴት ይችላል? ብለው እርስ በርሳቸው ተከራከሩ፡፡ [53]ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፡- እውነት እውነት እላችኋለሁ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም፡፡ [54]ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፤ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሳዋለሁ፡፡ [55]ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና፡፡ [56]ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል፤እኔም በእርሱ እኖራለሁ፡፡ [57]ሕያው አብ እንደ ላከኝ እኔም ከአብ የተነሳ ሕያው እንምሆን፣ እንዲሁ የሚበላኝ ደግሞ ከእኔ የተነሳ ሕያው ይሆናል፡፡ [58]ከሰማይ የወረደ እንጀራ ይህ ነው፤ አባቶቻችሁ መና በልተው እንደሞቱ አይደለም፤ ይህን እንጀራ የሚበላ ለዘላለም ይኖራል፡፡ [59]በቅፍርናሆም ሲያስተምር ይህን በምኵራብ አለ፡፡**

6፡52
NASB **"ተከራከሩ"**
NKJV **"ተጋጩ"**
NRSV **"ተከራከሩ"**
TEV **"ቁጣ የሞላበት ክርክር"**
NJB **"መከራከር"**

ይህ በኃላፊ ጊዜ የተጻፈው ቃል ባለፈው ጊዜ ተጀምሮ በዚያው ጊዜ ያላለቀ ድርጊትን ያመለክታል፡፡ ለዚህ ቃል የገባው የግሪኩ ቃል ውጊያን በማመልከት ጠንካራ (የሐዋ.7፡26፤2 ጢሞ.2፡23-24፤ቲቶ 3፡9) እና በ2ኛ ቆሮ.7፡5 እና ያዕቆብ 4፡1-2 ላይ በተምሳሌታዊ አነጋገር አገልግሎት ላይ የዋለ ነው፡፡

▣ **"ይህ ሰው ስጋውን ልንበላ ይሰጠን ዘንድ እንዴት ይችላል?"** ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ በቀጥታ ትርጉሙ ለመረዳት የሚያዳግተውን ሁል ጊዜ በምሳሌያዊ አነጋገር ይናገራል፡ (1) ኒቆዲሞስ፣ 3፡4፤ (2) ሳምራዊቷ ሴት፣ 4፡11፤ (3) አይሁዳውያን ጉባኤ፣ 6፡52፤ እና (4) ደቀመዛሙርት፣ 11፡11፡፡

6፡53-57 በቁጥር 53 እና 54 ውስጥ ያሉት ግሦች በጣም አስደሳች ናቸው፡፡ በቁ.53 "መብላት" እና "መጠጣት" የሚሉት የግሥ ቃላት ቀላል የሆነን ምናባዊ ድርጊትን አመልካች ሲሆኑ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የድርጊት መነሳሳትን

የሚናገሩ ናቸው፡፡ "በላ" እና "ጠጣ" የሚሉት በቁ. 54 ውስጥ ያሉት ቃላት የአሁን ጊዜ ድርጊትን ገላጭ ግሦች ሲሆኑ ቀጣይነት ያለው ድርጊት ላይ ያተኩራሉ (ቁ.56፣57፣58)፡፡ ይህ የሚያመለክተው አንድ ሰው ስለዚህ እውነታ ለኢየሱስ መልስ መስጠት መጀመር እንዳለበትና በመታዘዝም መቀጠል እንደሚገባው ያረጋግጣል (ቁ 44)፡፡

ይህንን ምንባብ ቃል በቃል መውሰድ አይሁዳውያን ደም እንዳይጠጡ የተከለከሉትን (ዘሌ.17:10-14) አለመረዳት መሆኑን ማስታወስ ይገባል፡፡ ኢየሱስ በምድረበዳ ስለነበረው መና የተናገረውን ታሪክ (ቁ.58) ቃል በቃል ወስዶ ከጌታ እራት (ቅዱስ ቁርባን) ጋር አያይዞ መጠቀም ከታሪካዊው ዳራና ከቃሉ አውድ ውጪ ለቤተክርስቲያን ሥርዓት ዓላማ ሲባል ብቻ አላግባብ መጠቀም ነው፡፡

6:54 **"ሥጋዬ...ደሜን"** ይህ አይሁዳውያን ሙሉ ሰውን ልክ እንደ "ልብ" የሚገልጡበት ዘይቤያዊ አነጋገራቸው ነው፡፡

6:55 **"እውነተኛ መብል...እውነተኛ መጠጠ"** ይህ እውነት/እውነታ የሚለው ቃል የዮሐንስ ባህሪያዊ አጠቃቀም ነው (ከታች የተመለከተውን ልዩ አርዕስት ይመልከቱ፡፡)፡፡ የሐንስ፣ከሌሎቹ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ዘግይቶ የጻፈ፣የብዙ የተሳሳቱ ትምህርቶች እድገት (የተጋነነ/የተንጋደዱ ትምህርቶች ስለ መጥምቁ ዮሐንስ፣ ስለ ቅዱሳን ምስጢራት፣ስለ ሰው እውቀት-ኖስቲሲዝም) ተመልክቶ ነበር፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ የ"እውነት" ጽንሠ ሀሳብ በዮሐንስ ጽሁፎች ውስጥ**

ዮሐንስ በግሪክ *አሌቲያ* "እውነት" የሚለውን ቃል የዕብራይስጡን እና የግሪኩን ታሪካዊ ዳራ በማገናኘት ልክ ሎጎስ የሚለውን ቃል በ1÷1-14 ውስጥ እንዳደረገው ትርጉም ያለው አድርጎታል፡፡ በዕብራይስጥ *ኢሜት* የሚያመለክተው እውነተኛ የሆነውን፣ የታመነውን (ብዙ ጊዜ በሰብቱዋጀንት "*ፒሰቴዮ*" ከሚለው ቃል ጋር ተገናኝቶአል) ነገር ነው፡፡ በግሪክ ይህ ቃል ከፕላቶ እውነታዎችና እውነታዎች ያልሁኑ፣ ሰማያዊና ምድራዊ ጽንሠ ሃሳቦች ጋር ተቆራኝቶአል፡፡ ይህም ከዮሐንስ የሁለትዮሽ አስተሳሰብ ጋር ይመሳሰላል፡፡ እግዚአብሔር በግልጽ ራሱን በልጁ ገልጧል (ስርወ ቃሉ *አሌቲያ* መግለጥ፣ አለመደበቅ፣ በግልጽ መታየት ማለት ነው)፡፡ ይህም በተለያዩ መንገዶች ተገልጧል፡፡

1. ስም፡- *አሌቲያ*፣ እውነት
   - ሀ. ኢየሱስ በጸጋ እና በእውነት የተሞላ ነው (1÷14፣17- የብሉይ ኪዳን የቃል ኪዳን ቃሎች ናቸው)፡፡
   - ለ. ኢየሱስ የመጥምቁ ዮሐንስ ምስክርነት ትኩረት ነበር (1÷32-34፤18፡37-የመጨረሻው የብሉይ ኪዳን ነብይ)፡፡
   - ሐ. ኢየሱስ እውነትን ይናገራል (8÷4፣44፣45፣46-መገለጥ አሳባዊና አካላዊ ነው)
   - መ. ኢየሱስ መንገድ፣እውነት እና ሕይወት ነው (14፡6)
   - ሠ. ኢየሱስ በእውነት ይቀድሳቸዋል
   - ረ. ኢየሱስ (ሎጎስ፣ 1÷1-3) እውነት ነው (17÷17)
2. ቅጽል፣ *ልቴስ* ፣ እውነተኛ
   - ሀ. የኢየሱስ ምስክር (5÷31-32፤ 7÷18፤ 8÷13-14)
   - ለ. የኢየሱስ ፍርድ (8÷16)
3. ቅጽል፣ *አለቲመስ*፣ እውነተኛ
   - ሀ. ኢየሱስ አውነተኛው ብርሃን ነው (1÷9)
   - ለ. ኢየሱስ እውነተኛው እንጀራ ነው (6÷32)
   - ሐ. ኢየሱስ እውነተኛው የወይን ግንድ ነው (15÷1)
   - መ. ኢየሱስ እውነተኛው ምስክር ነው (19÷35)
4. *ረዳት ግሥ*፣ *አሌቶስ*፣ በእውነት
   - ሀ. የሳምራዊቷ ምስክርነት ስለ ኢየሱስ የዓለም መድኃኒት (4÷42)
   - ለ. ኢየሱስ እውነተኛው መብልና መጠጥ፣ በሙሴ ዘመን የነበረውን መና ተቃራኒ (6÷55)

እውነት የሚለው ቃልና ከእርሱ የተገኙ ቃላት ሁሉ ደግሞም ሌሎች ምስክርነቶች ስለ ኢየሱስን ይናገራሉ፣ *አሌቴስ*

- ሀ. የመጥምቁ ዮሐንስ ምስክርነት እውነት ነው (10÷41)
- ለ. የዮሐንስ ወንጌል ጸሐፊ የሆነው የሐንስ ምስክርነት እውነት ነው (19÷35፤21÷24)
- ሐ. ሰዎች ኢየሱስን እንደ እውነተኛ ነብይ ተመልክተውታል (6÷14፤7÷40)

እውነትን በተመለከተ ጥሩ ማብራሪያ በብሉይ ኪዳን እና በአዲስ ኪዳን ለማግኘት የጆርጅ ኢ.ለደን የአዲስ ኪዳን ሥነ መለኮት የተሠኘውን መጽሐፍ በገጽ 263-269 ይመልከቱ፡፡

6:56 **"በእኔ ይኖራል እኔም ደግሞ በእርሱ እኖራለሁ"** ይህ እውነት በተመሳሳይ ሁኔታ በዮሐንስ 15:4-7፤ 1ኛ ዮሐንስ 2:6፣27፣28፤3:6፣24 ተመልክቶአል፡፡ መኖር የሚለውን ልዩ ርዕስ በ1ኛ ዮሐንስ 2:10 ላይ ይመልከቱ፡፡ የቅዱሳንን ጽናት በተመለከተ ይህ የአዲስ ኪዳን ቀጣይነት ያለው ትኩረት ነው (ገላ. 6:9፤ራዕይ 2:7፣11፣17፣26፤3:5፣12፣21፣በ8:31 ላይ ልዩ ርዕስ የሚለውን ይመልከቱ፡፡)፡፡ እውነተኛ ምላሽ የሚረጋገጠው ቀጣይነት ባለው ምላሽ ነው፡፡ ይህ የጽናት ትኩረት

በአሜሪካ የወንጌል ማስፋፋት እንቅስቃሴ ውስጥ ጠፍቶአል፡፡ አንድ ሰው በእምነት መጀመር ብቻ አይደለም በእምነትም መጨረስ አለበት (ዕብራውያን 11)፡፡ ጆናታን ኤድዋርድ "የምርጫ እርግጠኛ ማረጋገጫ የአማኙ እስከመጨረሻ በእምነት መጽናቱ ነው፡፡" ብሏል፡፡ ደብልዩ. ቲ. ኮነር ደግሞ "ለድነት የተመረጠ ሰው ድነት በእግዚአብሔር ዓላማና አሳብ ከዘላለም እስከ ዘላለም የተረጋገጠ ነው፣ ተዋግቶ በሚያሸንፍና በሚጸና እምነት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡" ብሎአል፡፡

6:57 "ሕያው አብ" ይህ ሐረግ የተለየ ነው፤ሆኖም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ጊዜ ይታያል፡፡ ይህንን የእግዚአብሔር መጠሪያ ከመነሻው በተለያዩ መንገዶች መተርጎም ይቻላል፡፡

1. የቃል ኪዳኑ አምላክ መሠረታዊ ስም (ዘፀ.3:12፣14-16፤6:2-3፣ በተጨማሪ የ6:20 ልዩ ርዕስ ይመልከቱ)፡፡
2. በእግዚአብሔር መማል፣ "ሕያው እንደምሆን" ወይም በእግዚአብሔር ስም፣ "ጌታ ሕያው እንደሆነ" (ዘሑ.14:21፣28፤ ኢሳ.49:18፤ኤር.4:2)
3. እንደ እግዚአብሔር መግለጫነት (መዝ.42:2፤84:2፤ኢያሱ 3:10፤ አር.10:10፤ዳን.6:20፤ሆሴ.1:10፤ማቴ.16:16፤26:63፤የሐዋ.14:15፤ሮሜ.9:26፤2ኛ ቆሮ.3:3፤6:16፤1ኛ ተሰ.1:9፤1ኛ ጢሞ.3:15፤4:19፤ዕብ.3:12፤9:14፤10:21፤12:22፤ራዕይ 7:2)
4. በዮሐንስ 5:26 ላይ አብ በራሱ ሕይወት እንዳለው እና ለወልድም እንደሰጠው የሚናገረው ዓረፍተ ነገር እና በ5:21 ላይ አብ ሙታንን እንደሚያነሳ እንዲሁ ወልድም እንደሚያደርግ፤

**ልዩ ርዕስ፡ ዘላለም (ኦላም)**

የዕብራይስጡ ስርወ ቃል ‹ኦላም› ትርጉም የተረጋገጠ አይደለም፡፡ ቃሉ በተለያዩ አገባቦች በብዙ ቦታ እጥቅም ላይ ውሎአል (በርግጥ ትርጉሙ በአውድ ይወሰናል)፡፡ ከዚህ የሚከተሉት ጥቅሶ ለምሳሌነት የተመረጡ ናቸው፡፡

1. የጥንት ነገሮች
   - ሀ. ሕዝቦች፣ ዘፍ.6÷4፤1ኛ ሳሙ.27÷8፤ ኤር.5÷15፤ 28÷8
   - ለ. ቦታዎች፣ ኢሳ.58÷12፤61÷:4
   - ሐ. እግዚአብሔር፣ መዝ.93÷2፤ምሳሌ 8÷23፤ ኢሳ.63÷16
   - መ. ነገሮች፣ ዘፍ.49÷26፤ኢዮ.22÷15፤መዝ.24÷:7፣9፤ኢሳ.46÷9
   - ሠ. ጊዜ፣ ዘዳ.32÷7፤ኢሳ.51÷9፤63÷9፣11
2. የወደፊት ጊዜ
   - ሀ. የሰው ሕይወት፣ ዘፀ.21÷6፤ዘዳ.15÷17፤1ኛ ሳሙ.1÷22፤27÷12
   - ለ. ለንጉስ የተደረገ ግነትን፣ 1ኛ ነገ.1÷31፤መዝ.61÷7፤ነህ.2÷3
   - ሐ. ቀጣይ ሕልውና
     1. መሬት፣ መዝ.78÷69፤104÷5፤መክ.1÷4
     2. ሰማያት፣ መዝ.148÷6
   - መ. የእግዚአብሔር ሕልውና
     1. ዘፍ.21÷33
     2. ዘፀ.15፡18
     3. ዘዳ. 32÷40
     4. መዝ. 93÷2
     5. ኢሳ.40÷28
     6. ኤር.10÷10
     7. ዳን.12÷7
   - ሠ. ቃል ኪዳን
     1. ዘፍ.9÷12፣16፤ 17÷7፣13፣19
     2. ዘፀ.31÷16
     3. ዘሌ.24÷8
     4. ዘሑ. 18÷19
     5. 2ኛ.ሳሙ.23÷5
     6. መዝ.105÷10
     7. ኢሳ.24÷5፤55÷3፤61÷8
     8. ኤር.32÷40፤50÷5
   - ረ. ከዳዊት ጋር ልዩ ቃል ኪዳን
     1. 2ኛ ሳሙ 7÷19፣16፣25፣29፤22÷51፤23÷5
     2. 1ኛ ነገ.2÷33፣45፤9፡
     3. 2ኛ ዜና 13÷5

4. መዝ.18፥50፤89፥4፣28፣36፣37
5. ኢሳ.9፥7፤16፥5፤37፡35፤55፥3

ሰ. የእግዚአብሔር መሲህ
1. መዝ.45፥2፤72፡17፤89፥35-36፤110፥4
2. ኢሳ.9፡6

ሸ. የእግዚአብሔር ሕግ
1. ዘፀ.29፥28፤30፥21
2. ዘሌ.6፥18፣22፤7፥34፤10፥15፤24፥9
3. ዘሑ.18፥8፣11፣19
4. መዝ.119፥89፣160
5. ኢሳ.59፥21

ቀ. የእግዚአብሔር ተስፋ ቃል
1. 2ኛ ሳሙ.7፥13፣16፣25፤22፥51
2. 1ኛ ነገ. 9፥5
3. መዝ.18፥50
4. ኢሳ.40፥8

በ. የአብራሃም ዘሮችና የቃል ኪዳኑ ምድር
1. ዘፍ.13፥15፤17፥18፤48፥4
2. ዘፀ.32፥13
3. 1ኛ ዜና 16፥17

ተ. የቃል ኪዳኑ ግብዣ
1. ዘፀ.12፥14፤17፣24
2. ዘሌ.23፥14፣21፣41
3. ዘሑ.10፡8

ቸ. ዘላለማዊ/ዘላለምነት የዘላለም
1. 1ኛ ነገ.8፥13
2. መዝ.61፥7-8፤77፥8፤90፡2፤103፥17፤145፥13
3. ኢሳ.26፥4፤45፥17
4. ዳን.9፥24

ኘ. አማኞች ለዘላለም ስለሚያደርጉት ነገር መዝሙር የሚለው
1. ምስጋና ማቅረብ፣ 30፥12፤79፥13
2. በሕልውናው ማደር 41፥12፤61፥4፣7
3. በምህረቱ መታመን 52፥8
4. እግዚአብሔርን ማመስገን፣ 52፥9
5. ምስጋናን መዘመር፣ 61፥7፤89፥1
6. የእርሱን ፍትህ ማወጅ፣ 75፥9
7. ስሙን ማክበር፣ 86፥12፤145፥2
8. ስሙን መባረክ፣ 145፥1

3. ያለፈና የሚመጣ ጊዜ (ከዘላለም እስከ ዘላለም)
ሀ. መዝ.41፥13 (ምስጋና ለእግዚአብሔር)
ለ. መዝ.90፥2 (እግዚአብሔር ራሱ)
ሐ. መዝ.103፡17 (የእግዚአብሔር ቸርነት)

የቃሉን ትርጉም ቃሉ ያለበት አውድ እንደሚወስን አትርሳ፡፡ ዘላለማዊ ቃል ኪዳኖችና የተስፋ ቃሎች በሁኔታ ላይ የተመሠረቱ ናቸው (አር.7)፡፡ በዘመንህ ስለጊዜ ያለውን አስተሳሰብ ወይም የተቀናጀ የአዲስ ኪዳን ሥነ መለኮት

**6:58** ይህ የብሉይ ኪዳን የአዲስ ኪዳን ንጽጽር ነው፣ ሙሴ እና ኢየሱስ፡፡ (የዕብራዊያንን መጽሐፍ በተለይ ምዕራፍ 3፣4ን ይመልከቱ፡፡)፡፡

▣ **"አባቶቻችሁ መና በልተው…ሞቱ"** የዚህ ክፍል ሥነ መለኮታዊ ጠቀሜታ በዘር ሐረግ ደረጃ ድነት መካዱን ነው (8:33-39) ወይም በሙሴ ሕግ (ቶራህ)፡፡

▣ **"ዘላለም"** ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ልዩ ርዕስ በሳጥኑ ይመልከቱ፡፡

6:59 ኢየሱስ በዘመኑ የአይሁዳዊነትን ተግባር ያከናውን ነበር። በምኩራብ ትምህርት ቤት ተምሮአል፤በምኩራብ አምልኮ ተሳትፎአል፤በምኩራብም ተምሮአል፤ሕግ የሚጠብቅበትን ሁሉ ፈጽሞአል።

ምኩራብ በመሠረቱ የተጀመረው ከክርስቶስ ልደት በፊት 605-538 በነበረው የባቢሎን ምርኮ ገዜ ነው። አሥር አይሁዳውያን ወንዶች ባሉበት ቦታ ሁሉ አምልኮና ትምህርት ለማድረግ በተለየ ቦታ ይሰባሰቡ ነበር። ይህ ቦታ የአይሁዳውያንን ባሕልና ልማድ ለመጠበቅም ያገለግል ነበር። ወደ ይሁዳ በተመለሱ ጊዜም የቤተ መቅደስ ሥርዓትን ሲያከናውኑ እነዚህን የአካባቢ የአምልኮ ማዕከላትን ይጠብቁት ነበር።

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 6÷60-65
**[60]ከደቀ መዛሙርቱም ብዙዎች በሰሙ ጊዜ ይህ የሚያስቸንቅ ንግግር ነው፤ ማን ሊሰማው ይችላል? አሉ። [61]ኢየሱስ ግን ደቀ መዛሙርቱ ስለዚህ እንዳንጎራጎሩ በልቡ አውቆ አላቸው። ይህ ያሰናክላችኋልን? [62]እንግዲህ የሰው ልጅ አስቀድሞ ወደ ነበረበት ሲወጣ ብታዩ እንዴት ይሆናል? [63]ሕይወትን የሚሰት መንፈስ ነው፤ ሥጋ ምንም አይጠቅምም፤ እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው ሕይወትም ነው። [64]ነገር ግን ከእናንተ የማያምኑ አሉ። ኢየሱስ የማያምኑት እነማን እንደ ሆኑ አሳልፎ የሚሰተውም ማን እንደ ሆነ ከመጀመሪያ ያውቅ ነበር። [65]ደግሞ ስለዚህ አልኋችሁ ከአብ የተሰጠው ካልሆነ ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም አለ።**

6:60 **"ከደቀ መዛሙርቱም ብዙዎች"** *"ደቀ መዝሙር"* የሚለው ቃል ሰፊ ትርጉም አለው። በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ *"ደቀ መዝሙር"* እና *"ማመን"* የሚሉት ቃላት እውነተኛውን ተከታይ (ቁ.68) እና ጊዜያዊውን ተከታይ (ቁ.64፤ 8:31-47) ለማመልከት እጥቅም ላይ ውለዋል።

▣ **"ሰሙ…ማድመጥ"** ጨዋታው *"መስማት"* (አኩዎ) በሚለው ቃል ላይ ነው። የኢሱስን ቃል ሰምተዋል፤ ነገር ግን በትክክል ስለአልተረዱት አልታዘዙትም። ይህ የግሪክ ቃል የሚያስረዳው ይህንን ሲሆን ከዕብራይስጡ *ሼማ* (ዘዳ.4:1፤5:1፤6:3፣4፤27:9-10) *ጋር* ተመሳሳይ ነው።

6:62 ይህ ያልተሟላ በሁኔታ ላይ የተመሠረተው የአንደኛ መደብ ዓረፍተ ነገር መደምደሚያውን አያሳይም። የሚጠቁመው ግን እንደሚያዩት ነበር (የሐዋ.1)። ኢየሱስ ከሞተ/ከተነሣ/ካረገ እና መንፈስ ከወረደ በኋላ በርካታ የኢየሱስ ትምህርቶች እና ክንውኖች ትርጉም የሚሠጣቸው ነበር።

▣ **"አስቀድሞ ወደ ነበረበት ሲወጣ"** ይህ ሐረግ የኢየሱስ "ከሰማይ የመምጣቱ" ቀጣይ ትኩረት ነው። ይህ የሚናገረው እርሱ ከአባቱ *ጋር* በሰማይ ስለነበረው ቅድመ ሕልውና እና ከአባቱ *ጋር* ስለነበረው የቅርብ ግንኙነት ነው (17:5፣24)።
6:63፡ ይህ ጥቅስ ምናልባት የዮሃንስ 6 አውድ ሰፊ በመሆኑ ምክንያት በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን መካከል ካለውን ልዩነት ከማነጻጸር *ጋር* የሚገናኝ ይሆናል፤ በሙሴና በኢየሱስ መካከል (ቁ. 58፣ 2ኛ ቆሮ. 3:6፣የሁለቱን ኪዳኖች ንጽጽር በዕብራውያን መጽሐፍ ውስጥ ይመልከቱ።)።

**ልዩ ርዕስ፡- ዕርገት**

የኢየሱስን ወደ ሰማይ ማረግ በተመለከተ የሚያብራሩ ብዙ የግሪክ ቃላት አሉ። የሐዋ.1:2፣11፣22፤ *አናላምባኖ* ወደ ላይ መውሰድ (1ኛ ጢሞ.3:16)፤ ይህ ቃል በሴብትዋጀንት 2ኛ ነገ.2:9፣11 የኤልያስን ወደ ሰማይ ስለመሄዱ እና በ1ኛ መቃቢያን 2:58 ልይም እጥቅም ላይ ውሎአል።

1. የሐዋ.1÷9፣*ኢፓይሮ* ፡ ወደ ላይ ማውጣት፣ ወደ ላይ ማንሳት፣ ከፍ ማድረግ
2. ሉቃስ 9÷51፣ *አናልፐሲሰ* ፡ (ከ1ኛው *ጋር* ተመሣሣይ ነው)
3. *ዲስተሚ* ፡ መሄድ
4. ዮሐንስ 6÷62፣ *አናባየና*፣ ማረግ

ይህ ክስተት በማቴዎስም ሆነ በማርቆስ ወንጌሎች አልተዘገበም። የማርቆስ ወንጌል በ16:8 ላይ ያልቃል፣ ነገር ግን ከኋለኞቹ ሦስት ጸሐፊዎች አንዱ በሆነው ተጨማሪ በሆነው ጽሁፍ 16÷19 ላይ (አናላመባኖ) ጽፎታል።

▣ **"ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ"** ይህ ስለ ኢየሱስና ስለመንፈስ ከሚገልጹ ከብዙ ሐረጎች አንዱ ነው።

1. *መንፈስ* ሕይወትን የሚሰጥ ውኃ ነው (7:38-39)።
2. ኢየሱስ የሕይወት ውኃ ነው (4:10-14)።
3. *መንፈስ* ቅዱስ የእውነት *መንፈስ* ነው (14:17፤ 15:26፤ 16:13)።
4. ኢየሱስ እውነት ነው (14:6)።
5. *መንፈስ* አጽናኝ ነው (14:16፣26፤ 15:26፤16:7)።
6. ኢየሱስ አጽናኝ ነው (1ኛ ዮሐ.2:1)።

በ14:16 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

በዚህ ጥቅስ ውስጥ "መንፈስ" (ኒዩማ) የሚለው ቃል ለየት ባለ ትርጉም ሁለት ጊዜ እጥቅም ላይ እንደዋለ ልብ ይበሉ፡፡

1. *መንፈስ ቅዱስ* (1:32፣33፤ 3:34፤ 7:39፤ 14:17፤ 15:26፤ 16:13)፡፡
2. *መንፈሳዊ* (4:24፤ 11:33፤ 13:21)፡፡

በዮሐንስ 3:5፣6፣8 ላይ ያለውን ትርጉም ለማወቅ አስቸጋሪ ነው፡፡ ዮሐንስን፣ምናልባትም ሁለቱንም፡፡

**ልዩ ርዕስ፦ መንፈስ :ኒዩማ) በአዲስ ኪዳን**

"መንፈስ" የሚለው የግሪኩ ቃል በአዲስ ኪዳን በብዙ መንገዶች እጥቅም ላይ ውሎአል፡፡ ጥቂት ድልድሎችና ምሳሌዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

*ሀ.* ስለ *ሥሉሰ* እግዚአብሔር
1. ስለ አብ :ዮሐ.4:24)
2. ስለ ወልድ :ሮሜ.8፡9-10፤2ኛ ቆሮ.3:17፤ ገላ.4:6፤ 1ኛ ጴጥ.1:11)
3. ስለ *መንፈስ* ቅዱስ :*ማር*.1:11፤ *ማቴ*.3:16፤ 10:20፤ ዮሐ.3:5፣6፣8፤ 7:39፤ 14:17፤ የሐዋ. 2:4፤5:9፤ 8:29፣35፤ ሮሜ.1:4፤ 8:11፣16፤ 1ኛ ቆሮ.2:4፣10፣11፣13፣14፤12:7)

ለ. ስለ ሰብዓዊ ሕይወት *ኃ*ይል
1. ስለ ኢየሱስ :*ማር*.8:12፤ ዮሐ.11:33፣38፤13:21)
2. ስለ ሰው ዘር :*ማቴ*.22:43፤የሐዋ.7:59፤17:16፤20:22፤ ሮሜ.1:9፤8:16፤1ኛ ቆሮ.2:11፤5:3-5፤7:34፤15:45፤16:18፤ 2ኛ ቆሮ.2:13፤7:13፤ፊልጵ.4:23፤ ቆላ.2:5)

ሐ. ስለ *መንፈሳዊ* ዓለም
1. ስለ *መንፈሳዊ* ፍጡራን
   *ሀ.* ጥሩ :መልዓክት የሐዋ.23:8-9፤ ዕብ.1:14)
   ለ. ክፉ :*አጋንታዊ ማቴ*.8:16፤10:1፤12:43፣45፤ የሐዋ.5:16፤8:7፤ 16:16፤19:12-21፤ኤፌ.6:12)
   *ሐ. መናፍስት* :*ሉቃ*ስ 24:37)
2. ስለ *መንፈሳዊ መለየት* :*ማቴ*.5:3፤27:41፤ዮሐንስ 3:6፤4:23፤ የሐዋ.18:25፤19:21፤ ሮሜ.2:29፤7:6፤8:4፣10፤12:11፤1ኛ ቆሮ.14:37)
3. ስለ *መንፈሳዊ ነገሮች* :ዮሐንስ 6:63፤ሮሜ.2:29፤8:2፣5፣9፣15፤ 15:27፤ 1ኛ ቆሮ.9:11፤14:12)
4. ስለ *መንፈሳዊ ሥጦታዎች* :1ኛ ቆሮ.12:1፤14፤1)
5. ስለ *መንፈስ* አነሳሽነት :*ማቴ*.22፤43፤*ሉቃ*. 2:27፤ ኤፌ.1:17)
6. ስለ *መንፈሳዊ* አካል :1ኛ ቆሮ.15:44-45)

*መ*. ባሕሪያት
1. ስለ ዓለም ያለ አስተሳሰብ :ሮሜ 8:15፤11:8፤1ኛ ቆሮ.2:12)
2. የሰዎች የአስተሳሰብ ሂደት :የሐዋ.6:10፤ሮሜ.8:6፤1ኛ ቆሮ.4:2)

*ሠ*. ስለ ቁሳዊ ዓለም
1. ንፋስ :*ማቴ*.7:25፣27፤ ዮሐንስ 3:8፤የሐዋ.2:2)
2. ትንፋሽ :የሐዋ.17:25፤2ኛ ተሰ.2:8)

ይህ ቃል ባለበት አውድ ብርሃንነት መተርጎም እንዳለበት ግልጽ ነው፡፡ የዚህ ቃል የተለያዩ ለየትየት ያሉ ትርጉሞች :1) ቁሳዊውን ዓለም :2) የማይታየውን ዓለም :3)እንደዚሁም የዚህን የቁሳዊውን ዓለም ሰዎችና ወይም የመንፈሳዊውን ዓለም ሊያመለክቱ ይችላሉ፡፡

ከሥሉሰ እግዚአብሔር አካላት አንዱ የሆነው መንፈስ ቅዱስ በዚህ የታሪክ ደረጃ ውስጥ በታላቅነቱ ይሠራል፡፡ አዲሱ የመንፈስ ዘመን መጥቷል፡፡ መልካም፣ ቅዱስ፣ትክክል እና እውነት የሆነ ሁሉ ከእርሱ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ለወንጌል መስፋፋት እና ለእግዚአብሔር መንግሥት ስኬት የእርሱ መገኘት፣ ሥጦታ፣ እና አገልግሎት በጣም አስፈላጊ ነው :ዮሐ.14 እና 16)፡፡ እርሱ የሰዎችን ወደ ራሱ አይስብ፤ ነገር ግን ወደ ክርስቶስ እንጂ :ዮሐ.16:13-14)፡፡ እርሱ አማኞችን ሁሉ ይወቅሳል፣ያሳምናል፣ያፈቅራል፣ያጠምቃል፣ያሳድጋል :ዮሐ.16:8-11)፡፡

6:64 ይህ የሚመሳሰሉ አባላት ያሉበት የሚመስል ቡድን ነገር ግን ሐሰኛ ተከታዮች ወደ ሐሰተኛው ተከታይ-ይሁዳ ያሽቆለቆሉበት ነው (ቁ.70-71፤13:11)፡፡ በእርግጥ ምስጢር የተካተተበት የእምነት ደረጃ በዚህ ውስጥ አለ፡፡

**ልዩ ርዕስ፦ ክህደት (አፌስቴማይ)**

*ይህ አፊስቴማይ* የተባለው የግሪክ ቃል ሰፊ የሆነ የትርጉም መስክ አለው፡፡ የእንግሊዝኛው አፖስታሲ/ክህደት ከዚህ ቃል ቢወጣም የእግሊዝኛው ቃል አጠቃቀም በዘመናዊው አንባቢዎች ላይ ጥላቻን አሳድሮአል፡፡ አውድ

እንደተለመደው ቅድመ ማብራሪያ እንዳይደረግ በመከላከል ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡

ይህ ቃል የሁለት ቃላት ጥምር ሲሆን እነሱም *አፖ* የሚለው መስተዋድድ ትርጉሙ ‹‹ከ›› ወይም ‹‹ከ…ወደ…›› እና *ሂስትማይ* የሚለው ‹‹መቀመጥ፣›› ‹‹መቆም፣›› ወይም ‹‹መወሰን›› ማለት ነው፡፡ የሚከተሉትን (ሥነ መለኮታዊ ያልሆኑ) አጠቃቀሞችን ልብ ይበሉ፡-

1. በአካል ማስወገድ
   ሀ. ከቤተ መቅደስ፣ ሉቃስ 2፥37
   ለ. ከቤት፣ ማር.13፥34
   ሐ. ከሰው፣ ማር.12፥፡12፤14፥50፤የሐዋ.5፥38
   መ. ከማንኛውም ነገር፣ ማቴ.19፥27፣29
2. በፖለቲካ ማስወገድ፣ የሐዋ.5፥37
3. ከግንኙነት ማስወገድ፣ የሐዋ.5፥38፤15፥38፤19፥9፤22፥29
4. በህግ ማስወገድ (ፍቺ)፣ ዘዳ.24፥1፣3 (LXX) እና አ.ኪ. ማቴ.5፥31፤19፥6፤ማር.10፥4፤1ኛ ቆሮ.7፥11
5. እዳን ማስወገድ፣ ማቴ.18፥24
6. ግድ አለመሰኘትን በመተው ማሳይት፣ ማቴ.4፥209፤22፥27፤ዮሐንስ 4፥28፤16፥32
7. ግድ መሰኘትን ባለመተው ማሳየት፣ ዮሐንስ 8፥29፤14፥18
8. መፍቀድ፣ ማቴ.13፥30፤19፥14፤ማር.14፥6፤ሉቃስ 13፥8

ግሡ ደግሞ በሥነ መለኮታዊ ትርጉሙ ሰፊ አገልግሎት አለው፡-

1. ኃጢያትን በመደምሰ፣ይቅር በማለት፣ነጻ ማድረግ፣ ዘፀ.32፥32 (LXX)፤ዘሑ.14፥19፤ ኢዮብ 42፥10 እና አ.ኪ. ማቴ.6፥12፣14-15፤ ማር.11፥25-26
2. ከኃጢያት በመጠበቅ፣2ኛ ጢሞ.2፥19
3. በመራቅ ግዴለሽ መሆን
   ሀ. ሕግ፣ ማቴ.23፥23፤የሐዋ.21፥21
   ለ.እምነት፣ ሕዝ.20፥8 (LXX)፤ሉቃስ 8፥13፤2ኛ ተሰ.2፥3፤1ኛ ጢሞ.4፥1፤ዕብ.2፥13

ዘመናዊ አማኞች ብዙ የአ.ኪ. ጸሐፊዎች ፈጽሞ ያላሰቡትን ብዙ ሥነ መለኮታዊ ጥያቄዎችን ጥያቄ ይጠይቃሉ፡፡ ከእንዚህ ጥያቄዎች አንዱ እምነትን ከታማኝነት ከመለየት ዝንባሌ ጋር ይያያዛል፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል የነበሩ ሰዎች ነበሩና ጥቂት የሆነ ነገር አለ፡፡

1. ብሉይ ኪዳን
   ሀ. 12ቱን (10) ሰላዮች ሪፖርት የሰሙ፣ ዘሑ.14 (ዕብ.3፥16-19)
   ለ. ቆሬ፣ ዘሑ. 16
   ሐ. የኤሊ ልጆች፣ 1ኛ ሳሙ. 2፣4
   መ. ሳኦል፣ 1ኛ ሳሙ. 11-13
   ሠ. የሐሰት ነብያት (ምሳሌዎች)
      1. ዘዳ.13፥1-5፤18፥19-22 (የሐሰት ነብያትን የማወቂያ መንገዶች)
      2. ኤርምያስ 28
      3. ሕዝቅኤል 13፥1-7
   ረ. ሐሰተኛ ሴት ነብያት
      1. ሕዝቅኤል 13፥17
      2. ነህምያ 6፥14
   ሰ. የእስራኤል ክፉ መሪዎች (ምስላዎች)
      1. ኤርምያስ 5፥30-31፤8፥1-2፤23፥1-4
      2. ሕዝቅኤል 22፥23-31
      3. ሚኪያስ 3፥5-12
2. አዲስ ኪዳን
   ሀ. ይህ የግሪክ ቃል ቃል በቃል *አፖስታሲዝ* ነው፡፡ ከሁለተኛ ምፃት በፊት ስለክፉና ሐሰተኛ ትምህርቶች መጠንከር ሁለቱም ብሉይ እና አዲስ ኪዳኖች ያረጋግጣሉ (ማቴ.24፥24፤ማር.13፥22፤የሐዋ.20፥29፣30፤2ኛተሰ.2፥9-12፤2ኛ ጢሞ.4፥4)፡፡ ይህ የግሪክ ቃል በማቴዎስ 13፤ማርቆስ 4፤ እና ሉቃስ 8 ላይ ያለውን ኢየሱስ ስለ መሬት(አፈር) የተናገረው ምሳሌ ሊያንጸባርቅ ይችላል፡፡ እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች ክርስቲያኖች አለመሆናቸው ግልጽ ነው፤ እነሱ የወጡት ግን ከክርስቲያኖች ውስጥ ነው (የሐዋ.20፥29-30፤ 1ኛ ዮሐ.2፥19)፤ ስለሆነም እነርሱ ያልበሰሉ አማኞችን ማባበልና መማረክ ይችላሉ (ዕብ.3፥12)፡፡

   ሥነ መለኮታዎ ጥያቄዎችን የሚጠይቁ ሐሰተኛ መምህራን ወይስ ይልቁን አማኞች? ይህን ጥያቄ ለመመለስ አስቸጋሪ ነው፤ ምክንያቱም በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሐሰተኛ መምህራን ነበሩና (1ኛ

ዮሐ.2÷18-19)። ብዙ ጊዜ ቤተ እምነታዊ ወይም ሥነ መለኮታዊ ልማዳችን ይህንን ጥያቄ ያለ ግልጽ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ ይመልሳል (ጥቅሶችን ከአውዳቸው ገንጥሎ አውጥቶ ለአሳባቸው ድጋፍ መረጃ ለማድረግ ከሚሞክሩት በስተቀር)።

ለ. ግልጽ የሐሰት እምነት
1. ይሁዳ፣ ዮሐ.17÷12
2. ስምዖን የሐዋ.8
3. በማቴ.7÷13-23 ላይ የተገለጹት
4. በማቴ.13፤ ማር.4፤ሉቃስ 8 ላይ የተገለጹት
5. በዮሐንስ 8÷31-59 ላይ ያሉት አይሁዳውያን
6. አሌክሳንደር እና ሄሜኔዮስ፣ 1ኛ ጢሚ.1÷19-20
7. በ1ኛ ጢሞቲዎስ 6÷21 ላይ የገለጹት።
8. ሄሜኒዎስ እና ፊሊጦስ፣ 2ኛ ጢሞ.2÷16-18
9. ዴማስ፣ 2ኛ ጢሞ.4÷10
10. የሐሰት መምህራን፣ 2ኛ ጴጥ.2÷19-22፤ ይሁዳ ቁ.22-19
11. የክርስቶስ ተቃዋሚ 1ኛ ዮሐ. 2÷18-19

ሐ. ፍሬ አልባ እምነት
1. 1ኛ ቆሮንጦስ 3÷10-15
2. 2ኛ ጴጥሮስ 1÷8-11

አልፎ አልፎ ስለእነዚህ ጥቅሶች እናስባለን፤ ምክንያቱም የተቀናጀ ሥነ መለኮታችን (ካልቪኒዝም፣አርሜኒያኒዝም፣ወ.ዘ.ተ) በሞግዚትነት የሚጠቀሙባቸው መልሶች ስለሆኑ ነው። ይህንን ርዕስ ስለአመጣሁ ፈጥናችሁ አትፍረዱብኝ። እኔ ግድ የሚለኝ ትክክለኛ የሥነ ፍታቴ አኪያሂድ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ለእኛ እንዲናገር ማድረግ አለብን እንጂ ወደ ዘመኑ የኃይማኖት አስተሳሰቦች ስብስብ ውስጥ ልናስገባው አይገባም። ይህ የሚያሳዝንና የሚያስደነግጥ ነው፤ ምክንያቱም አብዛኛው ሥነ መለኮታችን ቤተእምነታዊ፣ ባህላዊ፣ ግንኙነታዊ (ወላጆች፣ጓደኞች፣መጋቢዎች) ነው እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። ጥቂቶች በእግዚአብሔር ሕዝብ ውስጥ የነበሩ የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደ አለመሆን ዞረዋል (ለምሳ. ሮሜ.9÷6)።

6:65 ይህ ጥቅስ በቁጥር 44 ላይ ካለው ጋር ተመሳሳይ እውነትን ይገልጻል። የወደቀው ሰው በራሱ አነሳሽነት እግዚአብሔርን ሊፈልግ አይችልም (ሮሜ.3:9-18 ላይ ያሉት ተከታታይ የብ.ኪ. ጥቅሶች የሰውን ኃጢያተኛነት እና አመጸኛነት ላይ የሚያተኩሩ ናቸው)።

**NASB (የተሻሻለው) ምንባብ: 6÷66-71**
**[66]ከዚህም የተነሣ ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎች ወደ ኋላ ተመለሱ፤ ወደ ፊትም ከእርሱ ጋር አልሄዱም። [67]ኢየሱስም ለአሥራ ሁለቱ፡ እናንተ ደግሞ ልትሄዱ ትወዳላችሁን? [68]ስምዖን ጴጥሮስ፦ ጌታ ሆይ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ፤ [69]እኛስ አንተ ክርስቶስ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆንህ አምነናል አውቀናልም ብሎ መለሰለት። [70]ኢየሱስም፦ እኔ እናንተን አሥራ ሁለታችሁን የመረጥኋችሁ አይደለምን? ከእናንተም አንዱ ዲያብሎስ ነው ብሎ መለሰላቸው። [71]ስለ ስምዖንም ልጅ ስለ አስቆሮቱ ይሁዳ ተናገረ፤ ከአሥራ ሁለቱ አንዱ የሆነ እርሱ አሳልፎ ይሰጠው ዘንድ አለውና።**

**6:67** "*አሥራ ሁለቱ*" ዮሐንስ ለመጀመሪያ ስለ ሐዋሪያት የተጠቀመው የመጀመሪያው ጥቅል ስም ነው (6:70፣71፤20:24). ልዩ ርዕስ በ6:13 ላይ ይመልከቱ።

**6:68** "*ስምዖን ጴጥሮስ…መለሰለት*" ጴጥሮስ የአሥራ ሁለቱ ቃል አቀባይ ነው (ማቴ.16:16)። ይህ እነርሱ እርሱ መሪያቸው መሆኑን አያመለክትም (ማር.9:34፤ሉቃስ 9:46፤22:24)።

▣ "*አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ*" ክርስትና (1) "*የዘላለም ሕይወት ቃል*" አውነትን የያዘ መልዕክት እና (2) በኢየሱስ ስብዕና የተገለጠ እውነት ነው። ስለዚህ ወንጌል መልዕክት እና ስብዕና ያለው አካልም ነው። *ፒስቲስ* የሚለው *ቃል* (1) ከመልዕክት (ይሁዳ 3፣20) እና (2) ከስብዕና (ዮሐ.1:12፤3:15-16) ጋር የተያያዘ ነው።

**6:69** "*አምነናል አውቀናልም*" እነዚህ ቃሎች ውጤቱ ላይ ያተኮሩ ያለፈ ጊዜ ድርጊት አመልካቾች ናቸው። *መዳን* በቁ.53 ላይ ባለፈው ጊዜ የተፈጸመ ነው። *መዳን* በቁ.40፣53፣54፣ እና 57 የአሁን ጊዜ፣ ቀጣይም ሂደት ነው። *መዳን* እዚህ ክፍል

ላይ ባለፈው የተፈጸመ፣ የተደመደመ ያለቀ የተጠናቀቀ ድርጊት ሆኖአል፡፡ እውነተኛ መዳን ሁሉንም የግሪክ ጊዜ ግሦች ያካትታል፡፡ ልዩ ርዕስ፡ ለመዳን እጥቅም ላይ የዋሉትን የግሪክ የጊዜ ግሦች በ9፡7 ላይ ይመልከቱ፡፡

▣

NASB, NRSV,
NJB "አንተ የእግዚአብሔር ቅዱስ ነህ"
NKJV "አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ"
TEV "አንተ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣህ ቅዱስ ነህ"

በዚህ ነጥብ ላይ የጽሑፍ ችግር ይታያል፡፡ አጭሩ ምንባብ (NASB, NSRV, NJB) P[75],N,B,C[*],D,L, እና W በተባሉት በጥንት ግሪክ ጽሑፎች የተደገፈ ነው፡፡ በዮሐንስ 11፡27 ከማርታ እምነት ወይም በ16፡16 ከጴጥሮስ እምነት በግልጽ እንደሚታየው የኋለኞቹ ጽሁፎች ለተጨማሪ ቃሎች ክፍት ናቸው፡፡ UBS[4] አጭሩን ምንባብ በ "ኤ" ደረጃ ያቀርባል፡፡

"የእግዚአብሔር ቅዱስ" የሚለው ሐረግ የብሉይ ኪዳን መሲኃዊ ማዕረግ ነው፡፡ ይህም በሉቃስ 1፡35 እና በሐዋ.3፡14 ላይ ተተርኳል፡፡ በ1ኛ ዮሐ.2፡20 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡ ይህ ሌላው የአሥራ ሁለቱ የእምነት መግለጫ ነው፣ ከማቴዎስ 16 ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

6፡70 **"እኔ እናንተን .... የመረጥኋችሁ አይደለምን?"** ይህ በደቀ መዛሙርቱ መለኮታዊ ምርጫ ላይ (ቁ.44 እና 65) የተደረገ ሌላው ትኩረት ነው፡፡ የኢየሱስን ጥያቄ በቁጥር 67 ላይ ያስታውሱ፡፡ መለኮታዊ ምርጫና የሰው ፈቃደኝነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጉዳዮች ሆነው ይኖራሉ፡፡ እነርሱ የቃል ኪዳን ግንኙነት ሁለት ገጽታዎች ናቸው፡፡

▣ **"ከእናንተም አንዱ ዲያብሎስ ነው"** ምን ዓይነት አስገራሚ ቃል ነው! ይህ ሐረግ ወደኋላ ከተመለሱት የደቀ መዛሙርት ወገን ከሆኑት አንዱን የሚገልጽ አይደለም፤ ነገር ግን እምነታቸው በእርሱ እንደሆነ ከሚገልጹት ከአሥራ ሁለቱ ምርጦች አንዱ አንጂ፡፡ ብዙዎች ይህንን ከ13፡2 እና 27 ጋር ያገናኙናል፡፡ በዚህ ጥቅስ ላይ ካለን መረዳት ጋር በተያያዘ ብዙ ጥያቄዎች አሉ፡፡ (1) ኢየሱስ ለምን ዲያብሎስን መረጠ? እና (2) ቃሉ በዚህ አውድ ውስጥ ምን ማለት ነው?

የመጀመሪያው ጥያቄ አስቀድሞ ከተነገረው ትንቢት ጋር የሚገናኝ ነው (17፡12፤መዝ.41፡9)፡፡ ይሁዳ ወደፊት ምን ሊያደርግ አስቦ እንደነበር ያውቅ ነበር፡፡ ይቅርታ ለማይደረግለት ኃጢያት ይሁዳ አይነተኛ ምሳሌ ነው፡፡ ለብዙ ዓመታት አብሮት ከኖረ፣ ከተመለከተው፣ እና ከሰማው በኋላ ኢየሱስን ከዳው?

ሁለተኛው ጥያቄ ሁለት ትርጉሞች ሊኖሩት ይችላል፡፡

1. አንዳንዶች ይህንን ከዲያብሎስ ጋር ያያይዙታል (ያለ መስተፃምር ለሰይጣን በመጠቀም የሐዋ.13፡10፤ራዕይ 20፡2 ይሁዳን በማስገባት 13፡2፣27)፡፡
2. ምናልባት ቃሉ ለሁሉም አገልግሎአል (ልክ በ1ኛ ጢሞ.3፡11፤2ኛ ጢሞ.3፡3፤ ቲቶ 2፡3 ያለ መስተፃምር እጥቅም ላይ እንደዋለ)፡፡

በብሉይ ኪዳን ትርጉም ይሁዳ ልክ እንደ ሰይጣን ከሳሽ ነበር (በ12፡31 ላይ የተመለከተውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡)፡፡ የግሪኩ ቃል እንደሚያመለክተው ከሳሽ ወይም ወሬኛ ነበር፡፡ የግሪኩ ቃል "ወዲያ መወርወር" ከሚሉ ሁለት ቃላት የተጣመረ ነው፡፡

6፡71 **"የአስቆሮቱ ይሁዳ"** ስለዚህ ቃል የተለያዩ ጽንሰ ሃሳቦች አሉ (ቃሉ በተለያዩ የግሪክ ጽሑፎች ውስጥ በተለያየ መንገድ ተጽፎአል)፡፡ የሚከተሉትን ሊያመለክት ይችላል፡፡

1. የቁርዮት ሰው፣ የይሁዳ ከተማ
2. የቃርጣን ሰው፣ የገሊላ ከተማ
3. ገንዘብ ለመያዝ የሚያገለግል የቆዳ ቦርሳ
4. "ማነቅ" ለሚለው የዕብራይስጥ ቃል
5. ለነፍሰ ገዳይ ቢላዋ የሚያገለግል የግሪክ ቃል

1ኛው ተራ ቁጥር እውነት ከሆነ፣ በአሥራ ሁለቱ ውስጥ የነበረው ይሁዳ እርሱ ብቻ ነበር ማለት ነው፡፡ 5ኛው ተራ ቁጥር እውነት ከሆነ ልክ እንደ ስምዖን ቀናተኛው ነበረ ማለት ነው፡፡

ይሁዳን በአዎንታዊ መልኩ የሚገልጽ አንድ መጽሐፍ በቅርቡ ተጽፎአል፡፡ የመጽሐፉ ርዕስ፡ *ይሁዳ፣ አሳልፎ ሰጪ ወይስ የኢየሱስ ወዳጅ?* በዊሊያም ክላሴን፣ ፎርትረስ ማተሚያ ቤት፣ 1996 የሚል ነው፡፡ የእኔ ችግር በዚህ ላይ መጽሐፉ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ያሉትን አስተያየቶች በትክክል አልተመለከተም፡፡

▣ **"አሳልፎ መስጠት"** ለዚህ ቃል የገባው የግሪክ ቃል በስፋት የተተረጎመ እና በአብዛኛው አውድ ውስጥ ገለልተኛ ነው፡፡ ሆኖም ይሁዳ ኢየሱስን ከባለሥልጣናት አሳልፎ ከመስጠት ጋር በተያያዘ የከፋ ትርጉምን ይወስዳል፡፡ በ18፡1 ላይ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ፡፡

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት *መመሪያ* ማብራሪያ ነው፤ ይህ ማለት ስለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን ባገኘነው ብርሃን መመላለስ አለብን። መጽሐፍ ቅዱስን በመተርጎም ረገድ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ እና መንፈስ ቅዱስ ቀዳሚዎች ነችሁ። ለሌላ ተንታኝ/ሐተታ አቅራቢ ብቻ መተው የለብህም።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተነሱት ታላላቅ ጉዳዮች ላይ ታተኩር ዘንድ እንዲረዳህ እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ተሰጥተውሃል። እነዚህ ጥያቄዎች ማለት ለላቀ መረዳት አእምሮ ቀስቃሾች እንጂ ማሳረጊያዎች አይደሉም።

1. ዮሐንስ 6 የሚናገረው ስለ ጌታ ዕራት ነውን? ለምን?
2. "እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ" ሲል ኢየሱስ ምን ማለቱ ነበር?
3. ኢየሱስ ለዚህ ሕዝብ እንደዚህ ያሉ አስገራሚ ነግግሮች ይናገር የነበረው ለምንድ ነው?

# ዮሐንስ 7

## በዘመናዊ ትርጉሞች የአንቀጽ አከፋፈል

| UBS[4] | NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| የኢየሱስ ወንድሞች አለማመን | የኢየሱሰ ወንድሞች አላመኑም | ኢየሱስ የሕይወት ውኃ | ኢየሱስና ወንድሞቹ | ኢየሱስ ለበዓሉ ወደ እና ኢየሩሳለም ወጣ በዚያም አስተማረ |
| 7፡1-9 | 7፡1-9 | 7፡1-9 | 7፡1-9 | 7፡1 |
| ኢየሱስ በዳስ በዓሉ | ሰማያዊ ምሁር | | ኢየሱስ በመጠለያው ክብረ በዓል | 7፡2-9 |
| 7፡10-13 | 7፡10-24 | 7፡10-13 | 7፡10-11 | 7፡10-13 |
| | | | 7፡12-13 | |
| 7፡14-24 | | 7፡14-18 | 7፡14-15 | 7፡14-24 |
| | | | 7፡16-19 | |
| | | 7፡19-24 | | |
| | | | 7፡20 | |
| | | | 7፡21-24 | |
| ይህ ክርስቶስ ነውን? | ክርስቶስ ይሆንን? | | መሲሁ ነውን? | ሕዝቡ ከየት እንደሚመጣ ተወያዩ |
| 7፡25-31 | 7፡25-31 | 7፡25-31 | 7፡25-27 | 7፡25-27 |
| | | | 7፡28-29 | 7፡28፡29 |
| | | | 7፡30-31 | 7፡30 |
| ባለሥልጣናች ኢየሱስ እንዲያዝ ላኩ | ኢየሱስና የኃይማኖት መሪዎች | | ኢየሱስን እንዲይዙ ጠባቂዎች ተላኩ | ኢየሱስ መሄጃው መድረሱን አስቀድሞ ተናግሮ ነበር |
| | | | | 7፡31-34 |
| 7፡32-36 | 7፡32-36 | 7፡32-36 | 7፡32-34 | |
| | | | 7፡35-36 | 7፡37-38 |
| የሕያው ውኃ ተቃራኒ | የመንፈስ ቅዱስ ተስፋ | | ሕይወትን የሚሰጥ ውኃ ምንጭ | የሕያው ውኃ ተስፋ |
| 7፡37-39 | 7፡37-39 | 7፡37-39 | 7፡37-39 | 7፡37-38 |
| | | | | 7፡39 |
| መከፋፈል በሕዝብ መካከል | ማን ነው? | | መከፋፈል በሕዝብ መካከል | ስለመሲሁን መነሻ አዳዲስ ግኝቶች |
| 7፡40-44 | 7፡40-44 | 7፡40፡44 | 7፡40-44 | 7፡40-44 |
| የመሪዎች አለማመን | በመሪዎች ተገፋ | | የአይሁድ መሪዎች አለማመን | |
| 7፡45-52 | 7፡45-52 | 7፡45-52 | 7፡45-52 | 7፡45-52 |

| | |
|---|---|
| | 7፡46 |
| | 7፡47-49 |
| | 7፡50-51 |
| | 7፡52 |

**ሦስተኛው የምንባብ ዑደት (ገጽ 5ን ይመልከቱ፡፡)**
*በአንቀጽ ደረጃ የጸሐፊውን ዋና ሃሳብ መከተል*

ይህ የጥናት *መመሪያ* ማብራሪያ ነው፤ ይህ ማለት ስለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን ባገኘነው ብርሃን መመላለስ አለብን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን በመተርጎም ረገድ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ እና መንፈስ ቅዱስ ቀዳሚዎች ነችሁ፡፡ ለሌላ ተንታኝ/ሐተታ አቅራቢ ብቻ መተው የለብህም፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ዋናውን ሃሳብ ለይ፡፡ የራስህን የዋና ሃሳብ አከፋፈል ከአምስቱ ዘመናዊ ትርጉሞች ጋር አነጻጽር፡፡ በአንቀጽ መከፋፈሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት ውጤት ባይሆንም፣ የጸሐፊውን ዋና ሃሳብ ለመከተል ግን ቁልፍ ጉዳይ ነው፣ ይህም የአተረጓጎም ዋና መሠረት ነው፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ የሚያወራው አንድ እና አንድ ሃሳብ ነው፡፡

1. አንደኛ አንቀጽ
2. ሁለተኛ አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወ.ዘ.ተ.

## የ1-52 ጥቅሶች አውዳዊ እይታ

ሀ. የምዕራፍ 5 እና 6 መነሻ የፋሲካ በዓል ነው፡፡ ከ7:1 እስከ 10:21 ያለው መነሻ የዳስ በዓል ነው (7:2 ጀምሮ)፡፡
ለ. የዳስ በዓል በመጀመሪያ ለመከር ጊዜ የሚደረግ የምስጋና በዓል (የመክተቻ በዓል ይባላል፣ ዘፀ.23:16፤34:22) ነበር፡፡ ይህ በዓል የመውጣታቸውን ታሪክም የሚያስታውሱበት ጊዜ ነው (ይህ የዳስ በዓል ነው ዘሌ.23:29-44 እና ዘዳ. 16:13-15)፡፡ ይህ የሆነው በ *ቲሽሪ* 15ኛ ሲሆን ይህም ከእኛ የመስከረም መጨረሻ ወይም ጥቅምት መጀመሪያው አካባቢ ነው፡፡
ሐ. ምዕራፍ 7 እና 8 ኢየሱስ ሰንበትን በመሻሩ (5:16) እና ከያሕዌ ጋር አንድ መሆኑን በመናገሩ (5:18) አይሁድ በኢየሱስ ላይ ጠላትነትን መጀመራቸውን ያሳያል፡፡ ምንባቡ ለምን ያህል ጊዜ
   1. እርሱን ለመያዝ 7:30፣32፣44፤ 10:39
   2. እርሱን ለመግደል 7:1፣19፣25፤8:37፣40 (ደግሞ 11:53) ሙከራ እንዳደረጉ እንደሚጠቅስ ልብ ይበሉ፡፡

**የቃል እና የሐረግ ጥናት**

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 7:1-9
**[1]ከዚህም በኋላ ኢየሱስ አይሁድ ሊገድሉት ይፈልጉ ስለ ነበር በይሁዳ ሊመላለስ አይወድም ነበርና በገሊላ ይመላለስ ነበር፡፡[2]የአይሁድም የዳስ በዓል ቀርቦ ነበር፡፡ [3]እንግዲህ ወንድሞቹ፡፡ ደቀ መዛሙርትህ ደግሞ የምታደርገውን ሥራ እንዲያዩ ከዚህ ተነሣና ወደ ይሁዳ ሂድ፤ [4]ራሱ ሊገለጥ እየፈለገ በስውር የሚሠራ የለምና፡፡ እነዚህን ብታደርግ ራስህን ለዓለም ግለጥ አሉት፡፡[5]ወንድሞቹ ስንኳ አላመኑበትም ነበርና፡፡ [6]ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፦ ጊዜዬ ገና አልደረሰም፥ ጊዜያችሁ ግን ዘወትር የተመቸ ነው፡፡ [7]ዓለም እናንተን ሊጠላ አይቻለውም፤ እኔ ግን ሥራው ክፉ መሆኑን እመሰክርበታለሁና እኔን ይጠላኛል፡፡ [8]እናንተ ወደዚህ በዓል ውጡ፤ እኔስ ጊዜዬ ገና ስላልተፈጸመ ወደዚህ በዓል ገና አልወጣም፡፡ [9]ይህንም አላቸውና በገሊላ ቀረ፡፡**

**7:1 "ከዚህም በኋል"** ይህ ቀጥተኛ የሆነ የሃሳቡን ቀጣይነት የሚያሳይ ቃል ነው እንጂ ጊዜን አያመለክትም (5:1፤6:1፤7:1፤21:1)፡፡

▣ **"አይሁድ ሊገሉት ይፈልጉ ነበር"** "አይሁድ" የሚለው ስም በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ሁል ጊዜ መጥፎ ትርጉም ነው ያለው (1:19፤2:18፣20፤5:10፣15፣16፤6:41፣52፤7:1፣11፣13፣35፤ 8:22፣52፣57፤9:18፣22፤10:24፣31፣33፤11:8፤19:7፣12፤20:19)።

7:2 **"የአይሁድ የዳስ በዓል"** ይህ በዓል የመገናኛው ድንኳን በመባልም ይታወቃል (ዘሌ.23:34-44፤ዘዳ.16:13-17)፤ ምክንያቱም በመከር ጊዜ በትንንሽ መጠለያ ውስጥ የሚኖሩ አይሁዳውያንን ከግብፅ የወጡበት ሁኔታ ስለሚያስታውሳቸው ነው። ይህ የበዓል ሥነ ሥርዓት ልክ ስለፋሲካ በዓል በምዕራፍ 5-6 ውስጥ እንደሆነው ከ7:1-10:21 ውስጥ ያለውን የኢየሱስን ትምህርቶች ታሪካዊ ዳራ ይሰጠናል።

7:3 **"ወንድሞቹ"** ከ2:12 ወዲህ ስለኢየሱስ ቤተሰብ ሲነሳ ይህ የመጀመሪያው ነው። እነርሱ የእርሱን ሃሳብ፣ብልሃት ወይም ዓላማ እንዳልተረዱ ግልጽ ነው።

▣ **"ከዚህ ተነሳና ወደ ይሁዳ ሂድ"** ይህ የሚያመለክተው የመናኞችን ከገሊላ ተነስተው ወደ ኢየሩሳሌም (ሉቃስ 2:41-44) የሚያደርጉትን ዓመታዊ ጉዞ ነው። የዮሐንስ ወንጌል በኢየሩሳሌም የኢየሱስ አገልግሎት ላይ ትኩረት እንደሚያደርግ ልብ ይበሉ።

7:4 **"በግልጥ"** የሚከተለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።

**ልዩ ርዕስ: ድፍረት (ፓርሲያ)**

ይህ የግሪክ ቃል ‹‹ሁሉ›› (ፓን) እና ‹‹ንግግር›› (ርሲስ) የሚሉ ሁለት ቃላት ቅንጅት ነው። ይህ ነፃነት ወይም ድፍረት በንግግር ውስጥ ሁልጊዜ በተቃዋሚዎች መካከል የሚገለጥ ድፍረትን የሚያሳሳብ ነበር (ዮሐ. 7÷13፤ 1ኛ ተሰ.2÷2)።

በዮሐንስ ጽሑፎች ውስጥ 13 ጊዜ አገልግሎት የሰጠ ሲሆን በአደባባይ የሚደረግን ንግግር ያመለክታል (ዮሐንስ 7÷4፣ በጳውሎስ ጽሑፎች ውስጥም፣ ቆላ.2÷15)። ሆኖም ይህ ቃል አንዳንድ ጊዜ በቀላሉ ‹‹በግልጽ›› (ዮሐንስ 10÷24፤11÷14፤16÷25፣29) ማለት ነው።

ሐዋሪያትም በሐዋሪያት ሥራ ውስጥ በተመሳሳይ ሁኔታ ስለኢየሱስ ይናገራሉ (በግልጽ/በድፍረት) ልክ ኢየሱስ ስለ አብ እና ስለእቅዱ እና ተስፋዎቹ (የሐዋ.2:29፤4:13፣29፣31፤9÷÷27-28፤13÷46፤14÷3፤18÷26፤19÷8፤26÷26፤28÷31)። ጳውሎስ ወንጌልን በፍጹም ግልጽነት መስበክ እንዲችል (ኤፌ.6÷19፤1ኛ ተሰ.2÷2) እና በወንጌል እንዲኖር (ፊል.1÷20) የጸሎት ድጋፍ ይጠይቅ ነበር። ጳውሎስ በክርስቶስ ያገኘው የፍጻሜ ተስፋ በዚህ ክፉ ጊዜ ወንጌልን በድፍረትንና በመተማመንን እንዲሰብክ አስችሎታል (2ኛ ቆሮ.7÷4)።

ይህንን ቃል በተመለከተ አንድ የመጨረሻ እይታ አለ። ዕብራውያን ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብና ስለ እርሱ ለመናገር ለየት ያለ የግልጽነት/ድፍረት ትርጉም በሚሰጣቸው መልኩ ይጠቀሙበታል (ዕብ.3÷6፡4÷16፤10÷19፣35)። አማኞች ከአብ ጋር በወልድ በኩል የቅርብ ግንኙነት ሙሉ ተቀባይነትን አግኝተዋል!

በአ.ኪ. ውስጥ በተለያዩ መንገዶች አገልግሎት ላይ ውሏል።

1. መተማመን፣ግልጽነት፣ ወይም ዋስትና
   ሀ. ከሰዎች ጋር በተያያዘ (የሐዋ.2:29፤4÷13፣31፤2ኛ ቆሮ.3÷12፤ኤፌ.6÷19)
   ለ. ከእግዚአብሔር ጋር በተያያዘ (1ኛ ዮሐ.2÷28፤3÷21፤4÷12፤5:14፤ዕብ.3÷6፤4÷16፤ 10÷19)
2. በግልጽ፣በማያሻማ ሁኔታ ለመናገር (ማር.8÷32፤ዮሐ.7÷4፣13፤ 10÷24፤ 11÷14፤ 16÷25፤ የሐዋ.28÷31)
3. በሕዝብ ፊት ለመናገር (ዮሐ.7÷26፤ 11÷54፤ 18÷20)
4. በአስቸጋሪ ሁኔታዎች መካከል በድፍረት ለመስበክ ሌላ ተመሳሳይ ቃል (ፓሬሲያዞማይ) እጥቅም ላይ ውሎአል (የሐዋ.18÷26፤19÷8፤ኤፌ.6÷20፤1ኛ ተሰ. 2÷2)።

በዚህ አውድ ውስጥ ይህ ቃል የፍጻሜን መተማመን ያመለክታል። አማኞች የኢየሱስን ሁለተኛ መምጣት አይፈሩም፤ በመተማመንና በቅንዓት ይቀበሉታል፤ ምክንያቱም በክርስቶስ ሆነው ክርስቶሳዊ ሕይወት ስለሚኖሩ።

▣ **"ብታደርግ"** ይህ የአንደኛ መደብ ሁኔታዊ ቃል ሲሆን ይህም ከጸሐፊው እይታ አኳያ ቃሉ እውነት እንደሆነ ይገመታል።

▣ **"ለዓለም ራስህን ግለጥ"** በቁ 4 ላይ ያለው "ዓለም" የሚለውን ቃል ጌታ በእነርሱ አጠቃቀም ወስዶ አስተያየቱን በቁ.7 ገልጾአል። ዓለም የሚለው ቃል ለእርሱ ተቀባይነት እኔ ርህራሄ የሌለው ነገር ሲሆን ይልቁን ጠላት ነው (15:18-19፤17:14፤ 1ኛ ዮሐ.3:13)፤ ምክንያቱም እርሱ የዓለም ኃጢያትና ዓመፃ ስለሚገልጥ ነው (3:19-20)።

የኢየሱስ ‹ወንድሞች› ለኢየሱስ ራሱን የመግለጥ አሳባቸው (እርሱም ተአምራት ማድረግ ነው) ከኢየሱስ ዓላማ (መስቀል) በጣም የተለየ ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ ኢሣ.55:8-11 ያለው ትንቢት ልብ ሊባል የሚገባበት ቦታ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

**7:5 "ወንድሞቹ ስንኳ አላመኑበትም ነበርና"** ይህ ሌላኛው የጸሐፊው ኢዲቶሪያል አስተያየት ነው፡፡ በአንድ ቤት ውስጥ አብረው እያደጉ ኢየሱስን እንደ መሲህ መቀበል በጣም አስቸጋሪ ነበር (ማር.3:20-21)፡፡ ኢየሱስ በአንድ በኩል ብቻ ለሚዛመዳቸው ወንድሞቹና እህቶቹ ግድ ይለው ነበር፡፡ ከትንሳኤው በኋላ ከተገለጠባቸው መገለጦች አንዱ የሆነው ለእነርሱ አራሱን ለመግለጥ ነበር፡፡ እነርሱም አመኑ (የሐዋ.1:14)! ያዕቆብ የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን መሪ ሆነ፡፡ ያዕቆብ እና ይሁዳ የጻፉአቸው መጽሐፍ የአ.ኪ. ቀኖና ሆነው ተቆጠሩ፡፡

**7:6 "ጊዜዬ ገና አልደረሰም"** "ጊዜ" (ካይሮስ) የሚለው ቃል እዝህ ቦታ ብቻ (ሁለቴ) እና ቁ. 8 ላይ ብቻ ነው የሚገኘው በዮሐንስ ወንጌል እና ደብዳቤዎች ውስጥ፡፡ BAJD የተሰኘው መጽሐፍ ቅዱስ ሦስት መሠረታዊ ማበራሪያዎችን ይሰጣል፡፡

1. - የአቀባበል ጊዜ (2ኛ ቆሮ.6:2ን ለማለት)
   - ምቹ ጊዜ (ሉቃስ 4:13ን ለማለት)
   - የተቀጠረ ጊዜን (ማር.13:33፤የሐዋ.3:20፤ 1ኛ ጴጥ.1:11)
2. - ትክክለኛ ወይም ተስማሚ ጊዜን
   - ትክክለኛ ጊዜን (ማቴ.24:45፤ ሉቃስ 1:20)
   - የተወሰነ ጊዜን (ዮሐንስ 7:8፤ 2ኛ ጢሞ.4:6)
3. የፍጻሜ ጊዜን (ማቴ.8:9፤ ሉቃስ 21:8፤ ሮሜ 13:11፤ 1ኛ ተሰ.5:1፤ 2ኛ ተሰ.2:6)

ቁጥር 2 እና 3 የትርጉም መደራረብ አላቸው፡፡

ኢየሱስ ተልዕኮው ገብቶታል (12:23፤13:1፤17:1-5)፡፡ ለእነዚህ በወንጌሉ ውስጥ ለተገለጡት ድርጊቶች መለኮታዊ የሆነ መርሃ ግብር ተይዞላቸው ነበር (ሉቃስ 22:22፤ ዮሐንስ 7:30፤ 8:20፤ የሐዋ.2:23፤3:18፤4:28)፡፡

**7:7 "ዓለም"** *ኮስሞስ* የሚለውን ልዩ ርዕስ በ14:17 ይመልከቱ፡፡

7:8

| | |
|---|---|
| NASB | **"ራሳችሁ ወደ በዓሉ ውጡ፤ እኔ ወደ በዓሉ አልሄድም"** |
| NKJV | **"እናንተ ወደዚህ በዓል ሂዱ፡፡ እኔ አሁን አልሄድም"** |
| NRSV, NJB | **"ራሳችሁ ወደዚህ ክብረ በዓል ሂዱ፡፡ እኔ አልሄደም"** |
| TEV | **"ወደ ክብረ በዓሉ ሂዱ፡፡ እኔ አልሄድም"** |

አያሌ የጥንት የግሪክ ቅጂዎች (N, D, እና K) "አሁን" የሚለው ተውሳከ ግሥ የላቸውም፡፡ በቁ.8 እና 10 መካከል ያለ የሚመስለውን ግጭት ለማስወገድ በቶሎ ሙከራ የተደረገ ይመስላል፡፡ ተውሳከ ግሡ በ MSS $P^{66}$, $P^{75}$,B, L, T, W ውስጥ ተካቶ ይገኛል (NKJV፣ የሃያኛው ምዕተ ዓመት አዲስ ኪዳን፣ NIV)፡፡

ይህ ግልጽ ማብራሪያ እንደሚከተለው ሊወሰድ ይችላል

1. ከእናንተ ጋር አልሄድም (ከዓላማችሁ ጋር አልሄድም)
2. በሰምንት ቀን በዓሉ አጋማሽ እሄዳለሁ (በበዓል ምልክትነቱ በኩል ለመገለጥ) በሚል ይረዱታል፡፡

> **NASB (የተሻሻለው) ምንባብ: 7:10-13**
> **[10]ወንድሞቹ ግን ወደ በዓሉ ከወጡ በኋላ በዚያን ጊዜ እርሱ ደግሞ በግልጥ ሳይሆን ተሰውሮ ወጣ፡፡ [11]አይሁድም፡፡ እርሱ ወዴት ነው? እያሉ በበዓሉ ይፈልጉት ነበር፡፡ [12]በሕዝብም መካከል ስለ እርሱ ብዙ ማንጐራጐር ነበረ፤ አንዳንዱም፡፡ ደግ ሰው ነው፤ ሌሎች ግን፡፡ አይደለም፥ ሕዝቡን ግን ያስታል ይሉ ነበር፡፡ [13]ዳሩ ግን አይሁድን ስለ ፈሩ ማንም ስለ እርሱ በግልጥ አይናገርም ነበር፡፡**

7:11 ‹**አይሁድም"** ከኢየሱስ ጋር የሚነጋገሩ አራት የተለያዩ ቡድኖች አሉ በዚህ ቦታ፡፡

1. ወንድሞቹ
2. "አይሁድም" የኃይማኖት መሪዎችን ያመለክታል፡፡
3. "ሕዝቡ" ወደ ዳስ በዓሉ በመንዝ ላይ ያሉትን ተጓዦች ያመለክታል፡፡
4. "የኢየሩሳሌም ሕዝብ" የከተማው ሕዝብ የእሥራኤልን ሽማግሌዎች እና ኢየሱስን ለመግደል የነበራቸውን እቅድ ያውቁ ነበር፡፡

**7:12 "በሕዝብም መካከል ስለ እርሱ ብዙ ማንጎራጎር ነበረ"** ይህ ሁኔታ ወንጌል በመካከላቸው ለሠራው ሥራ አይነተኛ ምሳሌ ነው፡፡ ይህ ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ችሎታዎች እና የመረዳት ደረጃዎች በሰው ሁሉ ውስጥ መኖሩን ነው (7:40-44)፡፡

▣ **“ሕዝቡን ያስታል”** *ፓጎናኦ የሚለው ግሥ የሚያገለግለው*

1. *ለሐሰት መምህራን* (*ማቴ*.24:11፤ 2ኛ *ጢሞ*.3:13፤ 1ኛ *ዮሐ*.1:8፤2:66፤3:7)
2. *ለአሳያ መሲሆች* (*ማቴ*.24:4-5፣24፤ *በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ አይሁድ ኢየሱስ እንዲህ እንደሆነ ያስባሉ* (*ዮሐ*.7:12፣47፤ *ማቴ*.27:63)
3. *እራሳቸውን ለሚያታልሉ ሰዎች* (1ኛ *ቆሮ*.3:18፤ 1ኛ *ዮሐ*. 1:8) *ወይም*
4. *ለተታለሉ* (1ኛ *ቆሮ*.6:9፤ 15:33፤ *ገላ*.6:7፤ *ያዕ*.1:16)
   *ይህ ቃል የኀብረ ከዋክብትን መደበኛ ምህዋር ተከትለው የማይሽከረከሩ ፕላኔቶችን ይገልጣል፡፡ እነርሱም “ዘላኖች” ይባሉ ነበር፡፡*

7:13 **“አይሁድ”** *ይህ ሕዝብ አይሁዳውያን ናቸው፡፡ ይህ ቃል ዮሐንስ በኢየሩሳለም የነበሩ አይሁዳውያን የኃይማኖች መሪዎችን ለማመልከት በተለይ የተጠቀመበት ቃል መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በ*7:1 *ላይ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ፡፡*

**NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 7:14-18**
**[14]*አሁንም በበዓሉ እኩሌታ ኢየሱስ ወደ መቅደስ ወጥቶ ያስተምር ነበር፡፡* [15]*አይሁድም፡፡ ይህ ሰው ሳይማር መጻሕፍትን እንዴት ያውቃል? ብለው ይደነቁ ነበር፡፡* [16]*ስለዚህ ኢየሱስ መለሰ እንዲህም አላቸው፦ ትምህርቴስ ከላከኝ ነው እንጂ ከእኔ አይደለም፤* [17]*ፈቃዱን ሊያደርግ የሚወድ ቢኖር፥ እርሱ ይህ ትምህርት ከእግዚአብሔር ቢሆን ወይም እኔ ከራሴ የምናገር ብሆን ያውቃል፡፡* [18]*ከራሱ የሚናገር የራሱን ክብር ይፈልጋል፤ የላከውን ክብር የሚፈልግ ግን እርሱ እውነተኛ ነው በእርሱም ዓመፃ የለበትም፡፡***

7:14 **“አሁንም በበዓሉ እኩሌታ”** *እስከዚህ ሠዓት ድረስ ኢየሱስ ለምን መቆየት እንደፈለገ ትክክለኛ ምክንያቱ በእርግጠኝነት አይታወቅም፣ ነገር ግን ለኃይማኖት ተጓዦቹ እና ለከተማው ሕዝብ ስለ እርሱና ስለአገልግሎቱ ለመወያየት የተፈቀደው ጊዜ ይህ እንደሆነ ሰው ሊገምት ይቻላል፡፡ የአይሁዳውያን መሪዎችም ጠላትነታቸውን በግልጥ ለመግለጥ የተፈቀደ ጊዜም ነበር* (*ቁ*. 13)፡፡

▣ **“ያስተምር”** *ኢየሱስ የሚናገርባቸው ነገሮች*

1. *የትምህርት፣ ማቴ*.4:23፤5:2፣19፤7:29፣*ወዘተ፤ ዮሐ*.6:59፤ 7:14፣28፣35፤ 8:20፣28
2. *የስብከት፣ ሉቃስ* 4:18፤ 7:22፤ 9:6፤ 20:1

*ባህሪያት አላቸው፡፡*

*እነዚህ ቃላት ኢየሱስ የእግዚአብሔርን እውነት ለእርሱ ሰብዓዊ ፍጥረት ማካፈሉን በማመልከት በተመሳሳይ ጥቅም ያላቸው ይመስላሉ፡፡ መገለጥ ሁለጊዜ መረጃ መስጠት እና መለወጥ ማለት ነበረ፡፡ የሕይወት ለውጥን ቅድሚያ ከመስጠት ጋር አብሮ የሚሄድ ውሳኔ የሚያስፈልገው ነው፤ እውነት ሁሉን ነገር ይለውጣል!*

7:15 **“ይህ ሰው ሳይማር መጽሐፍትን እንዴት ያውቃል?”** *ይህ ማለት ባጭሩ እርሱ ከታወቁት የኃይማኖት አባቶች ትምህርት ቤቶች በአንዱ ውስጥ ገብቶ አልተማረም ማለት ነው፣ ወይም እርሱ በዘመኑ ከነበሩት የኃይማኖት አባቶች የአንዱም እንኳ ደቀ መዝሙር አልነበረም፡፡ “ይህ ሰው” የሚለው ሐረግ አጠቃቀም አክብሮት መከልከልን ያመለክታል* (18:17፣29)፡፡ (1) *በይዘቱ* (2) *በቅርጹ ምክንያት ሁልጊዜ የኢየሱስ ትምህርት አድማጮቹን ያስደንቃል ነበር* (*ማር*.1:21-22፤ *ሉቃስ* 4:22)፡፡ *የኃይማኖት መምህራን እርስ በርሳቸው የጠቃቀሱ ነበር፤ ኢየሱስ እግዚአብሔርን ይጠቅስ ነበር!*

7:16 *ኢየሱስ ለአባቱ ወደ መገዛቱ* (5:19) *ብቻ ሳይሆን የአድማጮቹን ትኩረት ከአባቱ ወደ አገኘው ልዩ እውቀት ደግሞ ስቦአል፡፡ እነርሱ ምድራዊ መምህራን ነበሩአቸው፤ እርሱ ሰማያዊ መምህር ነበረው፡፡*

7:17 *“ቢ.....” ይህ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ቃል ነው፡፡ ይህ ቃል ለድርጊት አቅም ወይም ችሎታ መኖርን ያመለክታል፡፡ ለፍጥረተ ዓለም የተሰጠውን ወንጌል* (1:12፤3:16) *እና የእግዚአብሔርን ሁሉን ገዢነት ሥልጣን* (6:44፣64) *ተጻራሪ ይመስላል ፡፡ መንፈስ ልብን መክፈት አለበት* (16:8-13)፡፡

7:18 *ኢየሱስ ከወደቀው የሰው ልጅ ጋር በማነጻጸር የራሱን የተለየ መሆን አረጋገጠ፡* (1) *የራሱን ክብር አይፈልግም፤* (2) *የአባቱን ክብር ይፈልጋል፤* (3) *እርሱ እውነት ነው፤ እና* (4) *እርሱ ያለ ኃጢያት የሆነ ነው፡፡*

▣ **“የላከውን ክብር”** *በ*1:14 *ላይ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ፡፡*

▣ **“በእርሱ አመፃ የለም”** *ኢየሱስ በእኛ ቦታ ሊሞት ችሏል ምክንያቱም እርሱ ለራሱ ኃጢያት ሊሞት አያስፈልገውም* (2ኛ *ቆሮ*. 5:21)፡፡ *የኢየሱስ ከኃጢያት ነፃ መሆን እጅግ በጣም ጠቃሚ ሥነ መለኮታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ጉዳዩም በተለያዩ መንገዶች ብዙ ጊዜ ተብራርቶአል፤*

1. *ሉቃስ* 23:41

2. ዮሐንስ 6:69፤ 7:18፤ 8:46፤14:30
3. ፊልጵ.2:7-8
4. ዕብ.4፡15፤ 7፡26፤ 9፡14
5. 1ኛ ጴጥ. 1:19፤2:22 (ኢሣ.53:9)
6. 1ኛ ዮሐ. 2:17፤ 3:5፣7

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 7፡19-24
**[19]ሙሴ ሕግን አልሰጣችሁምን? ከእናንተ ግን ሕግን የሚያደርግ አንድ ስንኳ የለም። ልትገድሉኝ ስለ ምን ትፈልጋላችሁ? [20]ሕዝቡ መለሱና። ጋኔን አለብህ፤ ማን ሊገድልህ ይፈልጋል? አሉት። [21]ኢየሱስ መለሰ አላቸውም። አንድ ሥራ አደረግሁ ሁላችሁም ታደንቃላችሁ። [22]ስለዚህ ሙሴ መገረዝን ሰጣችሁ፤ ከአባቶችም ነው እንጂ ከሙሴ አይደለም፤ በሰንበትም ሰውን ትገርዛላችሁ። [23]የሙሴ ሕግ እንዳይሻር ሰው በሰንበት መገረዝን የሚቀበል ከሆነስ ሰውን ሁለንተናውን በሰንበት ጤናማ ስላደረግሁ ትቈጡኛላችሁን? [24]ቅን ፍርድ ፍረዱ እንጂ በመልክ አትፍረዱ።**

7:19 ሰዋስዋዊ መዋቅሩ "አዎ" የሚል መልስን ይጠብቃል፡፡

▣ **"ከእናንተ ግን ሕግን የሚያደርግ አንድ ስንኳ የለም።"** ይህ ዓረፍተ ነገር በኢየሩሳለም በዓል ላይ ላሉ አይሁድ ሁሉ አስደንጋጭ መሆን አለበት።
የሙሴ ሕግ የታሰበበት/የታቀደ ግድያን ይቃወማል፣ መሪዎቻቸው ግን በትክክል ይህንን በማቀድ ላይ ነበሩ። የአካባቢው ሕዝብ ይህንን የሚያውቁ ቢሆኑም ግን ይህን ዕቅዳቸውን ወይም ማጉረምረማቸውን እንኳ ማስቆም ፈቃደኞች አልነበሩም።

▣ **"ልትገሉኝ ስለምን ትፈልጋላችሁ?"** በቁ.20 ላይ ያለው ጥያቄ ለኃይማኖት መሪዎቹ የመጣ አይደለም። ነገር ግን ለበዓሉ ወደ ኢየሩሳሌም ከመጡት ኢየሱስን ለመግደል ሴራ መኖሩን ከማያውቁ ሕዝብ ነው። ዘግይቶ በቁ. 25 ላይ ኢየሱስን ለመግደል ሴራ መኖሩን የኢየሩሳሌም ሕዝብ አወቁ።
ማስተዋሉንና ኃይሉን በማክፋፋት ደግሞ የኃይማኖች መሪዎች አጋንንት አለበት ብለው ኢየሱስን ይከሱት ነበር (ማቴ.9:34፣11:18፣12:234፤ ማር.3:22-30፤ ዮሐ.8:48-52፤ 10:20-21)

7:20 **"ጋኔን አለብህ"** ኢየሱስ መንፈሳዊ ኃይል እንደነበረው ለሚቃወሙት ሁሉ ግልጥ ነበር። ጥያቄው ይህንን ኃይል ከየት አመጣው? የሚለው ነበር። የኢየሱስን "ምልክቶች/ተአምራቶች" የአይሁዳውያን መሪዎች ሊክዱ አልቻሉም ነበር፤ ሆኖም ይህን ኃይል ከሠይጣንና ከአጋንንት የወጣ ነው ይሉ ነበር (8:48-49፣52፤ 10:20)።
በዚህ አውድ ውስጥ የዳስ በዓሉን ለማክበር የመጣው ሕዝብም ተመሣሣይ ነገር ይናገሩ ነበር፣ ነገር ግን በተለየ ትርጉሙ ነበር። ኢየሱስ ድርጊቱ ከምክንያታዊነት ውጪ የሆነና አጠራጣሪ አስጨናቂ ነው እያሉ ይከራከሩ ነበር።

**ልዩ ርዕስ፡ አጋንታዊ (ርኩስ መንፈስ)**
ሀ. የጥንት ሰዎች ፍጥረት ሁሉ መንፈስ አለው ብለው ያምኑ ነበር። የሰውን የስብዕና ባሕሪ ከተፈጥሮ፣ የእንስሳት፣ እና የተፈጥሮአዊ ነገሮች ኃይላት ውጤት (ጋርያዛምዱ/ያቆራኙ) ነበር። ሕይወት የሚገለጠው እነዚህ መንፈሳዊ አካላት ከሰው ልጅ ጋር ባላቸው ግንኙነት ነበር።
ለ. ይህ ተፈጥሮአዊ ነገሮችን በሰውኛ የመግለጽ ልማድ ሰዎችን ብዙ አማልክትን ወደ ማምለክት አመጣቸው። በተለምዶ አጋንንት (ጂኒ) አነስ ያሉ አማልክት ወይም በሥልጣን ተዋረድ ከሌሎች አማልክት አነስ ያሉ (ደግ ወይም ክፉ) በግለሰቦች የዕለት ተዕለት ኑሮ ላይ ተጽዕኖ አላቸው።
1. መስጴጦሚያ፣ ብጥብጥ እና ግጭት
2. ግብፅ፣ ሥርዓትና ተግባር
3. ከነዓን፣ W.F. Albright's *Archaeology aȣd the Religioȣ of Israle,* Fifth Editioȣ, pp. 67-92 ይመልከቱ።
ሐ. ብሉይ ኪዳን የአነስተኛ አማልክትን፣መላእክትን፣ ወይም አጋንንትን ትምህርት ይቃወማል፣ ምናልባት ምክንያቱ አንድ አምላክ ብቻ ከሚል ጠንካራ አቋሙ የተነሳ ነው (ዘፀ.8÷10፤9÷14፤15፡11፤ ዘዳ.4÷35፣39፤6፡4፤ 33÷26፤መዝ.35÷10፤71÷19፤86፡6፤ ኢሳ.46÷9፤ ኤር.10÷6-7፤ ሚክ. 7÷18)። እነዚህ ክፍሎች አውነተኛው አምላክ የማያውቁ ሕዝቦችን የሐሰት አማልክት ይገልጻሉ።
1. ሴኢም (ጣኦታት ወይም ጸጉራማ አጋንንት፣ ዘሌ.17÷7፤ 2ኛ ዜና 11÷15)
2. ሊሊስ (ሴት፣ የምትዳራ አጋንንት፣ ኢሳ.34÷14)
3. ማቬት (ለሞት የእብራውያን ቃል ሆኖ የከነዓንን አምላክ ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሎአል፣ ምት፣ ኢሳ.28÷15፣18፤ ኤር. 9÷21፤ እና ምናልባትም ዘዳ.28÷22)።

4. ሬሼፍ (መቅሰፍት፣ ዘዳ. 33÷29፤መዝ.78÷48፤ ዕብ.3÷5)
5. ዴቨር (ቸነፈር፣ መዝ.91÷5-6፤ ዕብ.3÷5)
6. አዛዜል (ስሙ በእርግጠኝነት አይታወቅም፣ ነገር ግን ምናልባት የበረሃ አጋንንት ወይም የቦታ ስም ሊሆን ይችላል፣ ዘሌ.16÷8፣10፣26)

(እነዚህ ምሳሌዎች የተወሰዱት ከኢንሳይክሎፒዲያ ጁዳካ፣ ቮልዩም 5፣ ገጽ.1523 ነው፡፡)

ሆኖም በብ.ኪ. ከእግዚአብሔር ዘንድ ሁለትዮሽ ወይም መልአካዊ ነጻነት የለም፡፡ ሠይጣን የእግዚአብሔር (ያሕዌ) ባሪያ ነው (ኢዮብ 1-3፤ ዘካርያስ 3)፣ ነፃ አይደለም፣ ራሱን በራሱ የሚመራ ጠላት እንጂ (A.B. Davidsoɴ, *A Theology of the Old Testameɴt*, pp.300-306)፡፡

መ. አይሁዳዊነት ያደገው በባቢሎኒያን ምርኮ ጊዜ (ቅ.ክ. 586-537) ነው፡፡ ሁኔታው በሥነ መለኮት ረገድ በፋርስ በሰው ምሳሌ በተመሰለ ሁለትዮሽን በሚያራምድ ዞሮአስቴሪያኒዝም በተባለ የፋርስ ኃይማኖት፣ ማዘዳ ወይም አረማዝድ የተባለ ከፍ ያለ መልካም አምላክ እና አህሪማን በተባለ ክፉ ተቃዋሚ ተጽዕኖ ውስጥ ወድቋል፡፡ ይህ ከድህረ ምርኮ በኋላ በአይሁዳውያን ውስጥ በያህዌ እና በመልአክቱ እና በሰይጣን እና መልአክቶቹ ወይም አጋንንት መካከል በሰው ምሳሌ የሆነ ሁለትዮሽ አስተሳሰብ እንዲኖር አድርጓል፡፡

በአይሁዳውያን ሥነ መለኮት የክፋት ሰውኛ አገላለጽ ዘ ላይፍ ኤንድ ታይምስ ኦፍ ጂሰስ ዘ መሳያ በሚለው የበአልፍሬድ ኤዴረሼይም ውስጥ በጥሩ ሁኔታ የተብራራ እና የተያዘ ነው (Alfred Edersheim, *The Life aɴd Times of Jesus the Messiah,* vol. 2, appeɴdix XIII, pp.749-863 aɴd XVI, pp.770-776)፡፡ አይሁዳውያን ክፋትን በሦስት መንገዶች በሰውኛ አገላለጽ ይገልጹታል፡፡

1. ሰይጣን
2. ክፌ አሳብ (የተዜር ሃራ) በሰው ልጅ ውስጥ
3. የመልአክት ሞት

ኤዴርሼይም እነዚህን ነገሮች እንደዚህ ይገልጻቸዋል (1) ከሳሽ፤ (2) ፈታኝ፤ እና (3) የሚያስቃይ (vol.2,p.756)፡፡ በድህረ ምርኮ አይሁዳዊነት ሥነ መለኮት እና በአ.ኪ. ጽሑፎች መካከል ክፋትን በተመለከተ ልዩነቶች አሉ፡፡

ሠ. የክፋት መንፈሰዊ ፍጥረቶች በሰው ላይ እና በእግዚአብሔር/ያህዌ (በአይሁዳዊነት ሰይጣን የሰው ልጆች ጠላት ነበረ፤ ለእግዚአብሔር ግን አይደለም) ላይ ያለቸውን የተቃውሞ ሕልውና በተመለከተ አ.ኪ.፣በተለይ ወንጌሎች፣ያረጋግጣሉ፡፡

እነርሱ የእግዚአብሔርን ፈቃድ፣ ሕግ እና መንግሥቱን ይቃወማሉ፡፡ ኢየሱስ እነዚህን አጋንንታዊ ፍጡራንን ደግሞም (1) ርኩስ መናፍስት (ሉቃስ 4÷36፤6÷18) ወይም (2) ክፉ መናፍስት (ሉቃስ 7÷21፤8÷2) ተጋፍጠአል ደግሞም ከሰዎች ውስጥ አስወጥቶአቸዋል፡፡ ኢየሱስ በሕመም (አካላዊ እና አእምሮዋዊ) እና

በአጋንንታዊ ሥራ መካከል ያለውን ልዩነት ግልጽ አድርጎአል፡፡ እርሱ በእውቀቱና እነዚህን ክፉ መናፍት ከሰዎች በማስወጣ ኃይሉንና መንፈሳዊ እውቀቱን አሳይቷል፡፡ እነርሱ ኢየሱስን ያውቁታል ስለእርሱም ለመናገር ይሞክራሉ፣ ነገር ግን እርሱ የእነርሱን ምስክርነት አይቀበልም ነበር፣ ዝም እንዲሉም ያዛቸው ነበር፣ ከሰዎችም ያባርራቸው ነበር፡፡ አጋንንት ከሰዎች እየወጡ ሲሄድ የሠይጣን መንግሥት መሸነፉን ያመለክታል፡፡

በጣም የሚያስደንቀው ነገር በዚህ ጉዳይ ላይ የአ.ኪ. ሐዋሪያዊ ደብዳቤዎች/ጽሑፎች ብዙ የሚሉት ነገር የላቸውም፡፡ አጋንንትን ማስወጣን በፍጹም እንደ ጸጋ ሥጦታ አልተቆጠረም፣ ወጥ የሆነ ዘዴ ወይም አሠራር ለወደፊቱ የአገልጋዮች ትውልዶች ወይም አማኞች አልተሰጠም፡፡

ረ. ክፋት መኖሩ እውነት ነው፤ ክፉ አካላዊ ነው፤ ክፉ አለ፡፡ የክፋት መነሻውም ሆነ ዓላማው አልተገለጠም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የክፋትን መኖር ያረጋግጥ እና ተጽእኖውን በቁጣ ይቃወማል፡፡ በእውነት ውስጥ የመጨረሻ ሁለትነት (ultimate dualism) የለም፡፡ እግዚአብሔር ሁሉን ተቆጣጣሪ ነው፤ ክፉ ተሸንፎአል ተፈርዶበታልም እናም ከፍጥረት ይወገዳል፡፡

ሰ. የእግዚአብሔር ሕዝብ ክፉውን መቃወም አለበት (ያዕ.4፡7)፡፡ በክፉ ቁጥጥር ውስጥ ሊሆኑ አይችሉም (1ኛ ዮሐ. 5፡18)፣ ነገር ግን በክፉ ሊፈተኑና ምስክርነታቸው እና ተጽዕኖአቸው ሊበላሽ ይችላል (ኤፌ.6፡10-18)፡፡ ክፋት በክርስቲያን ንጽረተ ዓለም ውስጥ የተገለጠ ነው፡፡ ዘመናዊ ክርስቲያኖች ክፋትን እንደገና ለመግለጽ መብት የላቸውም (የሩዶልፍ ቡልትማን ክፋትን እንደፈለጉ የመተርጎም ትምህርት-ዴሚቴዎሎጃይዚንግ)፤ ክፋትን የማንነት ክፍል አርጎ በመውሰድ ጤናማውን የሰውነት ባሕሪ የሚያሳጣ ትምህርት (የፓውል ቲሊክ የማህበረሰብ አካላት ትምህርት)፣ ሥነ ልቦናዊ በሆኑ ቃልት ጨርሶ ለመተርጎም ያዳግታል (ሲግመንደ ፍሪውድ)፡፡ ትጽዕኖው ይኖራል፣ ግን ተሸንፎአል፡፡ አማኞች በክርስቶስ ድል ውስጥ መመላለስ አለባቸው!

7:22

| | |
|---|---|
| NASB, NKJB | "(ከሙሴ በመሆኑ ምክንያት አይደልም፣ከአባቶች እንጂ)" |
| NRSV | "(በእርግጥ ከሙሴ አይደለም፣ ከእምነት አባቶች እንጂ)" |
| TEV | "(ሙሴ ባይሆንም እንኳ አስቀድመው የጀመሩት ቅድመ አያቶቻችሁ ናቸው እንጂ)" |

NJB "__በእርሱ አልተጀመረም፣ በጥንት የእምነት አባቶች እንጂ__"

በሙሴ ሕግ ውስጥ የመገረዝ ሥርዓት አልተጀመረም ነበር (ዘፀ.12:48፤ ዘሌ.12:3)፣ ነገር ግን ለአብርሃም ከእግዚአብሔር ጋር ላለው የተለየ ቃል ኪዳን ምልክት እንዲሆን ተሰጥቶ ነበር (ዘፍ.7:9-14፤ 21:4፤ 34:22).

▣ "በሰንበትም ሰውን ትገርዛላችሁ" ዋናው የኢየሱስ ሙግት የነበረው ሕጻን ልጅ እንዲገረዝ የእነርሱን የሰንበት ሕግ ለመተው ፈቃደኞች ነበሩ (ሻብ.132ሀ፤ ሳብህ.18:3፡ 19:1-6)፣ ነገር ግን የሰንበት ሕጋቸውን አንድ አዋቂ ሰው እንዲፈወስ ለመተው ፈቃደኞች አልነበሩም። ኢየሱስ የኃይማኖት መሪዎች የአይሁዳዊነት አስተሳሰብ እና ምርምር ዓይነቶችን በዚህ ክፍል ውስጥ ይጠቀም እንደነበር መገንዘብ ጠቃሚ ነው።

7:23 "ከሆነስ" ይህ የመጀመሪያ ደረጃ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ዓረፍተ ነገር ከጸሐፊው እያታ ወይም ጽንጽሑፋዊ ዓላማ አኳያ እውነት እንዲሆን አስቦአል።

▣ "ሰውን በሁለንተናው በሰንበት ጤናማ ስላደረግሁ ትቆጡኛላችሁን?" ይህ ቃል የሚያመለክተው በ5:1-9 የተመዘገበውን በተመለከተ ወይም በበዓሉ ጊዜ ተደርጎ ያልተመዘበ ሊሆን ይችላል።

"ቁጣ" ለሚለው የገባው የግሪክ ቃል *ቾላዎ* አልፎ አልፎ አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን በአ.ኪ. በዚህ ቦታ ብቻ ነው የሚገኘው። በሁሉም የግሪክ ሥነ ጽሁፎች ውስጥ በጥቂቱ ይገኛል (BAGD, p.881 እና MM, p.689)። "መበሳጨት" (*ቾሌ*፣ ማቴ.27:34) ከሚለው ቃል ጋር ግንኙነት አለው። ኢየሱስ ይህንን ቃል ለምን እንደተጠቀም ግልጽ አይደለም። ምናልባት ለእነርሱ ትርጉም በሚሰጥ መልኩ "መለኮታዊውን ቁጣ" እነርሱ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሚጠብቁ እና ኢየሱስ ደግሞ የእግዚአብሔርን ሕግ የጣሰ ብለው በማሰባቸው የመጣ ቁጣ እንደሆነ ለማመልከት ይሆናል።

7:24፡ "ቅን ፍርድ ፍረዱ እንጂ በመልክ አትፍረዱ" ይህ የአሁን ጊዜ ትዕዛዝ ከአሉታዊ ቅንጣት ጋር ድርጊቱን አቁሙ ማለት ነው። ፍጥነትን የሚያመለክተውን ትዕዛዝ የሚያመለክት ነው። ይህ ምናልባት በኢሳ.11:3 ላይ ያለውን የሚያወሳ ይሆናል።

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 7÷25-31

25እንግዲህ ከኢየሩሳሌም ሰዎች አንዳንዶቹ እንዲህ አሉ። ሊገድሉት የሚፈልጉት ይህ አይደለምን? 26እነሆም፥ በግልጥ ይናገራል አንዳችም አይሉትም። አለቆቹ ይህ ሰው በእውነት ክርስቶስ እንደ ሆነ በእውነት አወቁን? 27ነገር ግን ይህን ከወዴት እንደ ሆነ እውቀናል፤ ክርስቶስ ሲመጣ ግን ከወዴት እንደ ሆነ ማንም አያውቅም። 28እንግዲህ ኢየሱስ በመቅደስ ሲያስተምር። እኔንም ታውቁኛላችሁ ከወዴትም እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ፤ እኔም በራሴ አልመጣሁም ነገር ግን እናንተ የማታውቁት የላከኝ እውነተኛ ነው፤ 29እኔ ግን ከእርሱ ዘንድ ነኝ እርሱም ልኮኛልና አውቀዋለሁ ብሎ ጮኸ። 30ስለዚህ ሊይዙት ይፈልጉ ነበር፤ ነገር ግን ጊዜው ገና ስላልደረሰ ማንም እጁን አልጫነበትም። 31ከሕዝቡ ግን ብዙዎች አመኑበትና። ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ይህ ካደረጋቸው ምልክቶች ይልቅ ያደርጋልን? አሉ።

7:25 "ሊገድሉት የሚፈልጉት ይህ አይደለምን?" የዚህ ጥያቄ ሰዋስዋዊ አወቃቀር "አዎ" የሚለውን መልስ ይጠብቃል (5:17፤7:19)። እስከ ቁ. 36 ድረስ ይህ የመጀመሪያው ጥያቄ ነው።

7:26

NASB, REV,

NET "በአደባባይ ይናገራል"

NKJV "በድፍረት ይናገራል"

NRSV "በግልጥ ይናገራል"

በ7:4 ላይ ድፍረት (*ፓርሄሲያ*) የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።

▣

NASB "በእውነት ይህ ሰው ክርስቶስ እንደሆነ አለቆች አላወቁም፣አወቁን?"

NKJB "በእርግጥ አለቆች ይህ በእወነት ክርስቶስ እንደሆነ አወቁን?"

NRSV "አለቆቹ ይህ ሰው በእውነት ክርስቶስ እንደ ሆነ በእውነት አወቁን?"

TEV "እነርሱ ይህ ሰው በእውነት መሲሁ እንደሆነ በእውነት አወቁን?"

NJB "በእውነት እርሱ ክርስቶስ እንደሆን በእውነት አለቆች አወቁን?"

የሰዋስዋዊ አወቃቀሩ "አላወቁትም" የሚል መልስን ይጠብቃል። ሆኖም፣ ለማወቅ መቻሉንም ይገልጻል (1:31፤4:29)።

7:27 "ነገር ግን ይህ ከወዴት እንደሆነ እውቀናል፤ ክርስቶስ ሲመጣ ግን ከወዴት እንደሆነ ማንም አያውቅም።" ይህ የሚያመለክተው በሚልኪ.3:1 ላይ መሲሁ በድንገት በቤተ መቅደሱ ይገለጣል የሚለውን ታሳቢ ያደረገ የአይሁድ የኃይማኖት መሪዎችን ልማዳዊ አስተሳሰብ ነው። ይህ በ1ኛ ሄኖክ 48:6 እና በእዝራ 13:51-52 ላይ ይገኛል።

7:28 ኢየሱስ በዚህ ክፍል ውስጥ ሁለት ነገሮችን ይናገራል፡፡

1. እግዚአብሔር እንደላከው (3፡17፣34፤5:36፣38፤6:29፤7:29፤8:42፤10:36፤11:42፤17:3፣18፣21፣23፣25፤20:21)፡፡
2. እነርሱ እግዚአብሔርን እንደማያውቁ (5:37፣42፤8:19፣27፣54-55፤16:3)፡፡

ዮሐንስ ኢየሱስ "እንደጮኸ" ጽፎአል (7:37፤12:44፤ማቴ.8:29)፡፡ ኢየሱስ መደመጥ እንዲችል ድምፁን ከፍ ያደርግ ነበር፡፡ ይህ በቃል በቃል ትርጉሙ ልክ ኢየሱስ "አሜን" ወይም "አሜን፣አሜን" የመጀመሪያ አጠቃቀም ይሰራል፡፡ እነዚህን ውስጠ ወይራ የሆኑ ቃሎችን መናገር የፈለገው ለጉዳዩ ትኩረት በማስጠት ነበር! ቁጥር 29 ችግሩን ያመለክታል! እነርሱ እርሱ ከገሊላ እንደሆን ያስባሉ (ቁ.41)፣ ነገር ግን እውነቱ እርሱ ከሰማይ ነው!

▣ **"የላከኝ እውነተኛ ነው"** አብ እውነት ነው (3:33፤ 8:26፤1ኛ ዮሐ.5:20) ወልድም እንዲሁ (7:18፤8:16)፡፡ በ6:55 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

7:29 **"እኔ ግን ከእርሱ ዘንድ ነኝ እርሱም ልኮኛልና አውቀዋለሁ"** በዮሐንስ ውስጥ ከላይ ወደ ታች የሆነ ሁለትዮሽን ለመግለጽ ይህ ሌላው ምሳሌ ነው፡፡ እዚህ ጋ ኢየሱስ የተናገረው ቃል በአይሁድ መሪዎች ዘንድ እንደ ስድብ እና ኢየሱስን የመግደል ዓላማቸውን ተግባራዊ ለማድረግ እንደማረጋገጫ ተወስዶ ነበር፡፡ በ5:24 ላይ "ላከ" (አፖስትሎ) የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

7:30 **"ሊይዙት ይፈልጉ ነበር"** ይህ ግሥ የሚያመለክተው (1) እርሱን ለመያዝ ፍለጋውን እንደጀመሩ፤ ወይም (2) በተደጋጋሚ መሞከራቸውን ሲሆን፤ ነገር ግን እርሱ መሲህ እንደሆነ በሚያምኑ በበዓሉ ዘንድ በተገኙ የኃይማኖት ተጓዦች መካከል የብጥብጥ መንስኤ እንዲሆኑ አልፈለጉም፡፡

▣ **"ነገር ግን ጊዜው ገና ስላልደረሰ"** ይህ ቃል የመለኮትን የጊዜ ሰሌዳ የሚያሳይ እንደገና የተነገረ ነብያዊ አባባል ነው (2:4፤7:6፣30፤8:20፤12:23፣27፤13:1፤17:1)፡፡

7:31 **"ከሕዝቡ ግን ብዞዎች አመኑበት"** ምንም እንኳን በሚሲሃዊ እንቅስቃሴው ላይ የተሳሳቱ አስተሳሰቦች ቢኖሩም እዚህ ጋ ያለው እምነት በኢየሱስ ላይ የሆነ እውነተኛ እምነት ነው፡፡ ማንም "ፍጹም" የሆነ እምነት ያለው የለም (ኖህ፣አብርሃም፣ ሙሴ፣ ዳዊት፣ አሥራ ሁለቱ)፡፡ በ2:23 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

ወንጌል በሚሰበክበት ጊዜ ይህ ሁሉ ይሆናል፡፡ አንዳንዶች ያምናሉ፣ ሌሎች ደግሞ ይጠራጠራሉ፣ ሌሎች ደግሞ ይቆጣሉ፡፡

1. የመለኮታዊ ምርጫ፡ እና
2. የሰው ኃጢያተኝነት፡ የምስጢር ግንኙነት እነሆ፡

እዚጋ ምስጢር አለ፡፡ ብዙ ብርሃን ቦግ ብሎ በርት አለማመን ሁልጊዜ የምደነግጥበት ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ምናልባት የኢየሱስ ቃል በአንድ ቤተሰብ ውስጥ አንዱ በሌላው ላይ ስለመነሳቱ የተናገረው መነሻ ሊሆን ይችላል፡፡ ወንጌል ለጥቂቶች ሠላምን ሲያመጣ ለሌሎች ደግሞ ጥልን ያመጣል!

▣ **"ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ይህ ካደራጋቸው ምልክቶች ይልቅ ያደርጋልን? አሉ"** የግሪኩ ሰዋስዋዊ መዋቅር "አይደልም" የሚል መልስን ይጠብቃል፡፡

ጆርጅ ኢ. ለድ፣ *ኤ ቴዎሎጂ ኦፍ ዘ ኒው ቴስታመንት፣* በተባለው መጽሐፉ በክርስቶስ ማመንን ለማበረታታት የ"ምልክት" ጠቀሜታን በተመለከተ መልካም አስተያየትን ይሰነዝራል፡

> *"የምልክቶች ከእምነት ጋር ያላቸው ግንኙነት ጥያቄ ቀላል አይደለም፣ ምክንያቱም ቃሉ ወደ ሁለት የተለያየ አቅጣጫዎች የሚያመለክት ይመስላል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ምልክቶች ሰዎችን ኢየሱስን ወደ ማመን ለመምራት ታቅደዋል* 2:23፤6:14፤7:31፤10:42)፡፡ *በሌላ በኩል ደግሞ ምልክት አይተው ያለመኑ ሰዎች ነበሩ* (6:27፤11:47፤12:37)፡፡ *ከዚህም በላይ፣ ኢየሱስ አይሁድን በነቀፈበት ጊዜ አይሁድ ምልክትን ካላዩ በስተቀር ማመን ባለመፈለጋቸው ምክንያት ተቃውሟል* (4:48፤6:30)፡፡ *ስለዚህ ለጥያቄው መልሱ የሚገኘው በምልክቶችን እና እምነት መካከል ባለው የተወጠረ የግንኙነት ዓይነት ውስጥ ነው፡፡ ጉዳዩ የምልክቶችን እውነተኛ ፍቺ እና ስለኢየሱስ የሚሰጡትን ምስክርነት እምነት እንዲረዳ የሚጠይቅ ነው፤ እምነት ለሌላቸው፣ ምልክቶች ዝም ብለው ትርጉም አልባ የሆኑ ክስተቶች ናቸው፡፡ ምልክት አይተው ምልሽ ለሚሰጡ ግን ምልክቶች እንደ እምነት ማረጋገጫ እና ማጠንከሪያ ሆነው ያገለግላሉ፡፡ ኢየሱስ ተዓምርን ያቀደው እምነትን ለማጥፋት አለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በሌላ በኩል በኢየሱስ ተልዕኮ ውስጥ ምን እየሆነ እንዳለ ማየት ለቻሉ ሁሉ እርሱ የሚሠራው ሥራ በቂ ምስክር ነው፡፡ የኢየሱስ ሥራዎች ለፍርድ እና ኃጢያተኞች በኃጢያታቸው ለመታወራቸው ምስክር ሆነው ያገለግላሉ"* (ገጽ.274)፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 7፡32-36
[32]ፈሪሳውያንም ሕዝቡ ስለ እርሱ እንደዚህ ሲያንጐራጕሩ ሰሙ፤ የካህናት አለቆችም ፈሪሳውያም ሊይዙት ሎሌዎችን ላኩ። [33]ኢየሱስም፦ ገና ጥቂት ጊዜ ከእናንተ ጋር እቆያለሁ ወደ ላከኝም እሄዳለሁ። [34]ትፈልጉኛላችሁ አታገኙኝምም፤ እኔም ወዳለሁበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም አለ። [35]እንግዲህ አይሁድ። እኛ እንዳናገኘው ይህ ወዴት ይሄድ ዘንድ አለው? በግሪክ ሰዎች መካከል ተበትነው ወደሚኖሩት ሊሄድና የግሪክን ሰዎች ሊያስተምር አለውን? [36]እርሱ። ትፈልጉኛላችሁ አታገኙኝምም እኔም ወዳለሁበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም የሚለው ይህ ቃል ምንድር ነው? ብለው እርስ በርሳቸው ተነጋገሩ።

7፡32 "ፈሪሳውያንም…. የካህናት አለቆችም" ይህ የሚያመለክተው የአይሁድ የኃይማኖት መሪዎችን ጉባኤን ነው (በ3፡1 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።)። አንድ የካህናት አለቃ ብቻ ነበር፣ ነገር ግን በሮም መንግሥት ቅኝ ግዛት ሥር ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ ቢሮው የብዙ ሃብታም፣ አይሁዳዊ ቤተሰቦች እና ከቤተሰብ አባላ ወደ ቤተሰብ አባል የተላለፈ ፖለቲካዊ መከራከሪያ ሆኖአል።

▣ "ሊይዙት ሎሌዎችን ላኩ" ይህ የሚያመለክተው "የቤተመቅደስ ፖሊሶችን" ማለትም ሌዋውያን የነሩትን ነው። እነርሱ ከቤተመቅደሱ ውጪ ያላቸው ሥልጣን የተወሰነ ነው (7፡45፣46፤18፡3፣12፣18፣22)።

7፡33 "ገና ጥቂት ጊዜ ከእናንተ ገር እቆያለሁ" ይህ ሐረግ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የተለመደ ነው (12፡35፤13፡33፤14፡19፤16፡16-19)። ኢየሱስ እርሱ ማን እንደሆነ፣ በእርሱ ላይ ምን እንደሚሆን፣ እና መቼ እንደሚሆንበት ያውቅ ነበር (12፡23፤13፡1፤17፡1-5)።

▣ "ወደ ላከኝም እሄዳለሁ" ይህ የሚያመለክተው የኢየሱስን የማዳን ተልዕኮ የመጨረሻ ነገሮችን፦ ስቅለቱን፣ ትንሳኤውን፣ ዕርገቱን፣ እና ወደ ቀድሞ ክብሩ መግባቱን ነው (17፡1-5፤ የሐዋ.1)።

7፡34 ይህ ነግግር ኢየሱስ ከደቀመዛሙርቱ ጋር የመጨረሻውን እራት በበላበት ሰገነት ላይ ካደረገው ውይይት ጋር ተመሳሳይ ነው (13፡33፣7፡36 እና 8፡21)። ሆኖም ይህ ቃል እዚህ ቦታ የሚናገረው ስለማያምኑ ሰዎች ነው (ማለትም፣እዚያ የተሰበሰበው ሕዝብ፣ የኢየሩሳሌም ሕዝብ፣ እና አይሁዳዊያን መሪዎች)።

7፡35-36 "በግሪክ ሰዎች መካከል ተበትነው ወደሚኖሩት ሊሄድና የግሪክን ሶወች ሊያስተምር አለውን? እርሱ" የግሪኩ ሰዋስዋዊ መዋቅር "አይ" የሚል መልስን ይጠብቃል። ይህ ሌላኛው ውስጠ ወይራ አነጋገር ነው። ይህ ሁል ጊዜም የእግዚአብሔር ፈቃድ ነበረ (ዘፍ.3፡15፤12፡3፤ኢሳ.2፡2-4)። የዳስ በዓል በሚከበርበት ጊዜ ሰባ የሚሆኑ ኮርማዎች ለዓለም ሕዝብ ተሰውተዋል። አይሁዳውያን ለአህዛብ ለመጸለይና ብርሃን ለመሆን ታዘው ነበር። ይህ ድርጊት (ዓረፍተ ነገር) ምናልባት ይህንን ባሕላዊ ሁኔታ የሚያንጸባርቅ ነው። "ግሪክ" የሚለው ቃል "አህዛብ" የሚለው ቃል በሚያገለግልበት ዓይነት ነው እጥቅም ላይ የዋለው። ዲሰፓሪያ የሚለው ቃል አይሁዳውያን ሕዝቦች በአህዛብ ምድር ተበታትነው መኖራቸውን ያመለክታል (ያዕ.1፡1፤1ኛ ጴጥ. 1፡1)። ይህን የኢየሱስን ተምሳሌታዊ ቋንቋ የተሰበሰበው ሕዝብ በተሳሳተ መንገድ ለመረዳታቸው ሌላኛው ምሳሌ ነው።

ይህ የኢየሱስን ከላይ ወደ ታች የሆነው ሁለትዮሽ ሌላው ምሳሌ ነው። ሕዝቡ እርሱን በተሳሳተ መንገድ ተረድተውታል፤ ምክንያቱም ቃሎቹን "ከላይ" እና "ከታች" ያለውን የትምህርቱን ክፍሎች ሳይመለከቱ ቃል በቃል ይወስዱት ነበር። እርሱ የመጣው ከአብ ዘንድ ሲሆን የሚመለሰውን ወደ አብ ነበር።

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 7፡37-39
[37]ከበዓሉም በታላቁ በኋለኛው ቀን ኢየሱስ ቆሞ። ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ። [38]በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ፥ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ብሎ ጮኸ። [39]ይህን ግን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለ መንፈስ ተናገረ፤ ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበርና።

7፡37 "ከበዓሉም በታላቁ በኋለኛው ቀን" ይህ በዓል የሰባት ቀን በዓል ይሁን (ዘዳ.16፡13)፣ ወይም የስምንት ቀን በዓል ይሁን (ዘሌ.23፡36፤ነህ.8፡16፤ 2ኛ መቃቢስ 10፡60 እና ዮሴፍ ወልደ ኮሪዮን-ጆሴፈስ) ጥያቄ አለ። በኢየሱስ ጊዜ በዓሉ ስምንት ቀን የተከበረ ይመስላል፤ ሆኖም ልክ በሰባቱ ቀናት እንደሚደረገው በመጨረሻው ቀን ውኃ ከሰሊሆም ገንዳ ቀድቶ በመሰዊያው ላይ መርጨት አይፈቀድም ነበር። ከ(Tractate sukkah of the) ታልሙድ ከተባለው የአይሁድ ጹሁፎች ስብስብ ከኢሳ 12፡3 ላይ ተጠቅሶ ከተገለጠው ሥርዓት እንማራለን። ይህ ምናልባት በሚታይ መንገድ ለሰብል ለሚሆን ዝናብ የተጸለይ ነው።

▣ "ቢ……" ይህ የሦስተኛ መደብ በሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሊደረግ የሚችል ነገርን አመልካች ቃል ነው።

▣ ***"ማንም የተጠማ"*** በኢየሱስ ወደ ማመን ዓለም አቀፋዊ ግብዣ! በ7:17 ላይ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ።

▣ ***"ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ"*** ኢየሱስ በ4:13-15 ውስጥ ተመሳሳይ የሆነ ዘይቤያዊ አነጋገር ተጠቅሞአል። ይህ ምናልባት ኢየሱስ ውኃን የሚሰጠው መሲሃዊ ዓለት መሆኑን ሊያመለክት ይችላል (1ኛ ቆሮ.10:4)። ይህ በግልጥ በብ.ኪ. ከኢሳ.55:1-3 ውስጥ ካለው ጥሪ ጋር ግንኙነት ያለው እና በበዓሉ ወቅት የሚደረገውን ምሳሌያዊ የውኃ ማፍሰስ ባሕላዊ አጋጣሚ ሊያመለክት ይችላል።

ጥቅት የጥንት የግሪክ ጽሁፎች "ወደ እኔ" የሚለው የላቸውም (MSS, N, aNd D)። ይህ በ$P^{66c}$, $P^{75}$, $N^{c}$, L, T, W, ውስጥ የተካተተ እና በአውድ በተዘዋዋሪ የሚታይ ነው።

7:38 ***"በእኔ የሚያምን"*** ይህን የአሁን ጊዜ ግሥን ልብ ብለው ይመልከቱ። ልክ በዮሐንስ 15 ላይ እንዳለው "ዘላቂ" እንደሚለው በእምነት ላይ የተመሠረተውን ቋሚ የሆነው የግል ግንኙነት ላይ ያለውን ትኩረት የሚያሳይ ነው። በ9:7 ላይ ለመዳን እጥቅም ላይ የዋለውን የግሪክ ግሥ ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።

▣ ***"መጽሐፍ እንዳለ"*** በየትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይ እንደሚገኝ ማወቅ አስቸጋሪ ነው። ምናልባት በኢሳ.12:3፤43:19-20፤44:3፤58:11፤ሕዝ.47:1፤ኢዮኤል 3:18፤ዘካ.13:1፤ ወይም 14:8፣ ሊሆን ይችላል። እነዚህ ክፍሎች በዘይቤያዊ አነጋገር የመለኮትን መገኘት የሚወክለውን የመጨረሻውን ዘመን ውኃ ያመለክታሉ። ይህንን በተመለከተ ለአዲሱ ዓመት ለመከር በረከት ቃል የተገባው ውኃ ወደ አዲሱ ቃል ኪዳን ውስጣዊ ባሕሪ የሚያመለክት ዘይቤያዊ አነጋገር ሆኖ ይለወጣል። መንፈስ በልብ እና በአእምሮ ውስጥ ይሠራል (ሕዝ.36:27-38)።

▣ ***"የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል"*** በተውላጠ ሥሙ ታሪካዊ አመጣጥ ላይ ብዙ ጽንሰ ሃሳቦች አሉ።

1. ኢየሱስ ራሱ (የጥንት የቤተክርስቲያን አባቶች)
2. ክርስቶስን የታመኑ እያንዳንዱ አማኝ
3. ኢየሩሳሌም። በአረማውያን "የእርሱ" የሚለው "የእርሷ" ማለትም ሲሆን ከተማን ሊያመለክት ይችላል (ይህ የአይሁድ የኃይማኖት መምህራን እምነት ነው ሕዝ.47:1-12 እና ዘካ.14:8)።

በቁ.37ለ እና 38ሀ ላይ ትኩረት በማድረግ ሁለቱ ጽንሰ ሃሳቦች ግልጽና ቀላል በሆነ ሁኔታ ተብራርተዋል (NIDOTTE, vol.1, p.683)

ኢየሱስ ራሱን ሕያው ውኃ ብሎ ይጠራል (4:10)። በዚህ አውደ ውስጥ ግን በኢየሱስ ተከታዮች ውስጥ ሕያውን ውኃ የሚያፈልቀው እና የሚሰጠው መንፈስ ቅዱስ ነው (ቁ.39)። ይህ ከመንፈስ ቅዱስ ክርስቶስን በአማኞች ልብ ውስጥ ከማኖር ሥራው ጋር ተመሳሳይ ነው (ገላ.4:19፤ኤፌ.4:13)።

7:39 ***"ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበርና"*** ይህ በግልጽ በዚህ ቃል ጠቀሜታ ላይ (16:7) የዮሐንስን የኂለኛውን አስተሳሰብ የሚያንጸባርር ይመስላል (የአዘጋጁ አስተያየት)። ይህ እንደ "ክብር በሚታዩት የኀልኅታን እና የጴንጤቆስጤን ጠቀሜታ ያሳያል (ዮሐ.3:14፡12:16፣32፤17:1፣5)። በዚህ በዮሐንስ ግልጽ አነጋገር ላይ የአይሁድ የኃይማኖት መምህራን የተለያዩ ሀሳቦች ይስነዝራሉ።

> **NASB (የተሻሻለው) ምንባብ: 7:40-44**
> **[40]ስለዚህ ከሕዝቡ አያሌ ሰዎች ይህን ቃል ሲሰሙ። ይህ በእውነት ነቢዩ ነው አሉ፤ [41]ሌሎች። ይህ ክርስቶስ ነው አሉ፤ ሌሎች ግን። ክርስቶስ በእውኑ ከገሊላ ይመጣልን? [42]ክርስቶስ ከዳዊት ዘር ዳዊትም ከነበረባት መንደር ከቤተ ልሔም እንዲመጣ መጽሐፍ አላለምን? አሉ። [43]እንግዲህ ከእርሱ የተነሣ በሕዝቡ መካከል መለያየት ሆነ፤ [44]ከእነርሱም አንዳንዶቹ ሊይዙት ወደዱ ነገር ግን እጁን ማንም አልጫነበትም።**

7:40 ***"ይህ በእውነት ነብዩ ነው"*** ይህ በዘዳ. 18:15፣18 የሚገኘውን የሙሴን መሲሃዊ ተሰፋ የሚያስታውስ ነው። ብዙዎች ኢየሱስን እንደ ነብይ ያዩት ነበር (4:19፤6:14፤9:17፤ ማቴ.21:11)። ኃይሉን አይተዋል፣ ነግር ግን ስብዕናውን እና ሥራውን አላወቁም ነበር። የእስልምና ኃይማኖት እንኳ ይህንን ማዕረግ ለኢየሱስ ይጠቀሙ ነበር፣ ገነር ግን መልዕክቱን በትክክል አይረዱም ነበር።

7:41 ***"ሌሎች ይህ ክርስቶስ ነው አሉ"*** ይህ አባባል የሚያመለክተው "ክርስቶስ" የሚለው ቃል "መሲህ" ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል ጋር እኩል መሆኑ ሲሆን ትርጉሙም "የተቀባ" ማለት ነው። በብ.ኪ. ነገሥታት፣ካህናት፣ እና ነብያት እግዚአብሔር እንደጠራቸውና እንዳስታጠቃቸው ምልክት እንዲሆን ይቀቡ ነበር። በ11:2 ላይ መቀባት በመጽሐፍ ቅዱስ የሚለው ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።

▣ ***"ሌሎች ግን ክርስቶስ በእውኑ ከገሊላ ይመጣልን?"*** የግሪኩ ሰዋስዋዊ መዋቅር ለዚህ ጥያቄ "አይመጣም" የሚል መልስን ይጠብቃል። ነገር ግን በኢሳ.9:1 ያለውስ?

7:42 የዚህ ዓረፍተ ነገር ሰዋሰዋዊ መዋቅር "አዎ ብሎአል" የሚል መልስን ይጠብቃል፡፡

▣ **"ከዳዊት ዘር"** (2ኛ ሳሙ.7፤ ማቴ.21፡9፡22፡42)፡፡

▣ **"ዳዊትም ከነበረባት መንደር ከቤተ ልሔም"** ይህ ሌላው ውስጠ ወይራ አነጋገር ነው (ሚኪ.5፡2-3 እና ማቴ.2፡5-6)፡፡

7:43 ኢየሱስ እና መልዕክቱ ሁልጊዜ መከፋፈልን ይፈጥራል (7፡48-52፤9፡6፤10፡19፤ማቴ.10፡34-39፤ ሉቃስ 12፡51-53 እና ማቴ.2፡5-6)፡፡ ይህ ነው የዘሪው ምሳሌ ምስጢር (ማቴዎስ 13)፡፡ ጥቂቶች መንፈሳዊ ጆሮ አላቸው፣ ሌሎች ደግሞ የላቸውም (ማቴ.10፡27፤11፡15፤13፡9፣15 ሁለት ጊዜ፣16፣43፤ማር.4፡9፣23፤7፡16፤8፡18፤ሉቃስ 8፡8፤14፡35)፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 7፡45-52
**[45]ሎሌዎቹም ወደ ካህናት አለቆችና ወደ ፈሪሳውያን መጡ፤ እነዚያም፡፡ ያላመጣችሁት ስለ ምን ነው? አሉአቸው፡፡ [46]ሎሌዎቹ፡፡ እንደዚህ ሰው ማንም እንዲሁ ከቶ አልተናገረም ብለው መለሱ፡፡ [47]እንግዲህ ፈሪሳውያን፡፡ እናንተ ደግሞ ሳታችሁን? [48]ከአለቆች ወይስ ከፈሪሳውያን በእርሱ ያመነ አለን? [49]ነገር ግን ሕግን የማያውቀው ይህ ሕዝብ ርጉም ነው ብለው መለሱላቸው፡፡ [50]ከእነርሱ አንዱ በሌሊት ቀድሞ ወደ እርሱ መጥቶ የነበረ ኒቆዲሞስ፡፡ [51]ሕጋችን አስቀድሞ ከእርሱ ሳይሰማ ምንስ እንዳደረገ ሳያውቅ በሰው ይፈርዳልን? አላቸው፡፡ [52]እነርሱም መለሱና፡፡ አንተም ደግሞ ከገሊላ ነህን? ነቢይ ከገሊላ እንዳይነሣ መርምርና እይ አሉት፡፡**

7:46 **"ሎሌዎቹ፡ እንደዚህ ሰው ማንም እንዲሁ ከቶ አልተናገረም ብለው መለሱ"** አሁንም የዮሐንስ ውስጠ ወይራ አነጋገር! ይህ አስገራሚ ምስክርነት ነው፡፡
1. ለእነርሱ ይህ በቂ ምክንያት ነበረና በመካከላቸው ያሉትን ሕዝብ ፈጽሞ አልፈሩም፡፡
2. ሕዝቡ ሲከፋፈል፣ የቤተመቅደሱ ፖሊሶች ስለ ኢየሱስ የነበራቸው አስተያየት ሙሉ ነበረ፡፡
3. እነዚህ ሰዎች ትዕዛዝን የመከተል እንጂ አስተያየት የመስጠት ልማድ አልነበራቸውም፡፡

7:48 **"ከአለቆች ወይስ ከፈሪሳውያን በእርሱ ያመነ አለን?"** በቁ.47 እና 48 ላይ ያለው የግሪኩ ሰዋሰዋዊ መዋቅር "የለም" የሚልን መልስ ይጠብቃል፡፡ "አለቆች" የሚለው ቃል በሊቀ ካህኑ የሚመራው የእስራኤልን ሽማግሌዎች እና የኃይማኖት መሪዎች ጉባኤን ያመለክታል፡፡ እዚህጋ ሰዱቃውያን እና ፈሪሳውያን (መላው ሸንጎ) አሉ፣ በተለምዶ እነዚህ ሁለተ ወገኖች ጥለኞች ናቸው፣ ነገር ግን ኢየሱስን ለመቃወም አንድነት ፈጥረዋል (11፡47፣57፤18፡3)፡፡

7:49 **"ነገር ግን ሕግን የማያውቀው ይህ ሕዝብ ርጉም ነው"** ይህ የሚያመለክተው "በምድሩ ላይ ያላውን ሕዝብ ነው" (*አመሃአሬስ*) ማንኛውንም አፋዊ ልማድ ሁሉ አይተገብሩም ነበርና በኃይማኖት መሪዎች ይናቁ ነበር (ዘዳ.27፡26)፡፡ የዮሐንስ ውስጠ ወይራ አነጋገር ከቁ.51 ድረስ ቀጥሏል፡፡ በዚህ ክፍል ኒቆዲሞስ እነርሱ ራሳቸው በኢየሱስ ላይ በሚያደርጉት ነበር ሕግን የጣሱ መሆናቸውን ይነግራቸው ነበር፡፡

አ፣ የኃይማኖተኝነት አሳዛኝ ቲያትር፡፡ ሕዝብን የሚረግሙ (*ኢፓራቶስ*፣ በአ.ኪ. በዚህ ቦታ ብቻ ይገኛል) ራሳቸው የተረገሙ ናቸው! ብርሃን ጨለማ ቢሆን፣ ጨለማ ምን ያህል ታላቅ ይሆን ነበር! ዘመናዊ፣ ወግ አጥባቂ፣ የተማራችሁ ኃይማኖተኞች ተጠንቀቁ!

7:51 **"ሕጋችን አስቀድሞ ከእርሱ ሳይሰማ ምንስ እንዳደረገ ሳያውቅ በሰው ይፈርዳልን?"** ይግሪኩ ሰዋሰዋዊ መዋቅር "አይፈርድም" የሚልን መልስ ይጠብቃል (ዘፀ.23፡1፤ዘዳ.1፡16)፡፡

7:52 **"አንተ ደግሞ ከገሊላ ነህን?"** ይህ የሸንጎውን በኢየሱስ ላይ የተደረገ በስሜት የተሞላ ተቃውሞን ያመለክታል፡፡

▣ **"መርምር እና እይ"** መርምር የሚለው በአይሁዳዊነት ውስጥ ቅዱሳን መጽሐፍትን ማጥናት የሚል ትርጉም አለው (5፡39)፡፡ ይህ አሁንም የሚያሳየው የዮሐንስ ውስጠ ወይራ አጠቃቀም ነው፡፡ ኤልያስስ (1ኛ ነገ.17፡1) እና ዮናስ (2ኛ ነገ.14፡25)፣ ሆሴዕ እና ናሆም? በዘዳ.18፡15፣19፤ ዘፍ.49፡10፤2ኛ ሳሙ.7 ነብይ ማለታቸው መሆን አለበት፡፡

7:53-8:11 ከምዕራፍ 8 መጀመሪያ ላይ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ፡፡

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ማብራሪያ ነው፤ ይህ ማለት ስለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን ባገኘነው ብርሃን መመላለስ አለብን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን በመተርጎም ረገድ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ እና መንፈስ ቅዱስ ቀዳሚዎች ነችሁ፡፡ ለሌላ ተንታኝ/ሐተታ አቅራቢ ብቻ መተው የለብህም፡፡

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተነሱት ታላላቅ ጉዳዮች ላይ ታተኩር ዘንድ እንዲረዳህ እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ተሰጥተውሃል። እነዚህ ጥያቄዎች ማለት ለላቀ መረዳት አእምሮ ቀስቃሾች አንጂ ማሳረጊያዎች አይደሉም።

1. በምዕራፍ 7 ላይ ላለው የኢየሱስ ቃል የበዓሉ ታሪካዊ ዳራ ምንድን ነው?
2. የ"ዳስ በዓሉን" ዓላማ አብራራ እና ግለጽ።
3. የኃይማኖት መሪዎች ለኢየሱስ ጠላቶች የነበሩት ለምንድን ነው?
4. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በኢየሱስ ላይ የተናገሩትን ልዩ ልዩ ቡድኖች ዘርዝር።

# ዮሐንስ 8

## በዘመናዊ ትርጉሞች የአንቀጽ አከፋፈል

| UBS[4] | NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| በምንዝርና የተያዘች ሴት | አመንዝራዎች የቃሉን ብርሃን ይጋፈጣሉ | በምንዝርና የተያዘች ሴት | በምንዝርና የተያዘች ሴት | አመንዝራዋ ሴት |
| 7፡53-8፡11 | 7፡53-8፡12 | 7፡53-8፡11 | 7፡53-8፡11 | 7፡53-8፡11 |
| ኢየሱስ፣ የዓለም ብርሃን | ኢየሱስ የራሱን ምስክርነት ተከላከለ | ኢየሱስ፣ የዓለም ብርሃን | ኢየሱስ፣ የዓለም ብርሃን | ኢየሱስ፣ የዓለም ብርሃን |
| 8፡12-20 | | 8፡12-20 | 8፡12 | 8፡12 |
| | | | | በኢየሱስ ምስክርነት ላይ ውይይት ከኢየሱስ ጋር |
| | 8፡13-20 | | 8፡13 | 8፡13-18 |
| | | | 8፡14-18 | |
| | | | 8፡19ሀ | 8፡19ሀ |
| | | | 8፡19ለ | 8፡19ለ |
| | | | 8፡20 | 8፡20 |
| እኔ ወደምሄድበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም | ኢየሱስ የሚሄድበትን ተነበየ | | እናንተ እኔ ወደምሄድበት ልትሄዱ አትችሉም | |
| 8፡21-30 | 8፡21-29 | 8፡21-30 | 8፡21 | 8፡21 |
| | | | 8፡22 | 8፡22-24 |
| | | | 8፡23-24 | |
| | | | 8፡25ሀ | 8፡25ሀ |
| | | | 8፡25ለ-26 | 8፡25ለ-26 |
| | እውነት አርነት ያወጣችኋል | | 8፡27-29 | 8፡27-29 |
| | 8፡30-36 | | 8፡30 | 8፡30 |
| እውነት ነፃ ያደርጋችኋል | | | እውነት አርነት ያወጣችኋል | ኢየሱስ እና አብርሃም |
| 8፡31-38 | | 8፡31-33 | 8፡31-32 | 8፡31-32 |
| | | | 8፡33 | 8፡33-38 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | የአብርሃም ዘርና ሰይጣን | 8፡34-38 | 8፡34-38 | |
| አባታችሁ ሠይጣን | 8፡37-47 | | | |
| 8፡39-47 | | 8፡39-47 | 8፡39 | 8፡39-41ሀ |
| | | | 8፡39ለ-41ሀ | |
| | | | 8፡41ለ | 8፡41ለ-47 |
| | | | 8፡42-47 | |
| ከአብርሃም በፊት እኔ ነበርኩ | ከአብርሃም በፊት እኔ ነበርኩ | | ኢየሱስ እና አብርሃም | |
| 8፡48-59 | 8፡48-59 | 8፡48-59 | 8፡48 | 8፡48-51 |
| | | | 8፡49-51 | |
| | | | 8፡52-53 | 8፡52-56 |
| | | | 8፡54-56 | |
| | | | 8፡57 | 8፡57-58 |
| | | | 8፡58 | |
| | | | 8፡59 | 8፡59 |

**ሦስተኛ የምንባብ ዑደት (አንቀጽ 5ን ይመልከቱ፡፡)**
*በአንቀጽ በመከፋፈል የጸሐፊውን ዋና ሃሳብ መከተል*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ማብራሪያ ነው፤ ይህ ማለት ስለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን ባገኘነው ብርሃን መመላለስ አለብን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን በመተርጎም ረገድ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ እና መንፈስ ቅዱስ ቀዳሚዎች ነችሁ፡፡ ለሌላ ተንታኝ/ሐተታ አቅራቢ ብቻ መተው የለብህም፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ዋናውን ሃሳብ ለይ፡፡ የራስህን የዋና ሃሳብ አከፋፈል ከአምስቱ ዘመናዊ ትርጉሞች ጋር አነጻጽር፡፡ በአንቀጽ መከፋፈሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት ውጤት ባይሆንም፣ የጸሐፊውን ዋና ሃሳብ ለመከተል ግን ቁልፍ ጉዳይ ነው፣ ይህም የአተረጓጎም ዋና መሠረት ነው፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ የሚያወራው አንድ እና አንድ ሃሳብ ነው፡፡

1. አንደኛ አንቀጽ
2. ሁለተኛ አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወ.ዘ.ተ.

## የ7:53-8:11 ምንባብ ዳራ

ሀ. ዮሐንስ 7:53-8:11 የኦሪጂናሉ የዮሐንስ ወንጌል አካል አልነበረም፡፡
ለ. ይህ ክፍል ከዮሐንስ ወንጌል ላለመኖሩ ማስረጃዎቹ (በግሪክ አንድ ቃል ነው)፡-

1. ውጫያዊ ማስረጃ
   ሀ. ከጥንቱ የግሪክ ጹሑፎች ውስጥ አለመኖሩ
      1. ፓፒረስ-P65 (በሦስተኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ)፣ P75 (በሦስተኛው ምዕተ ዓመት)
      2. N- ይህን ቅርጽ የያዘው የግሪክ እና የላቲን ፊደል አጻጻፍ ዘይቤ (በ4ኛው ምዕተ ዓመት፣ ከለ(በ4ኛው ምእተ ዓመት)፣ ምናልባትም ከ "ሀ" እና "ሐ"ም ውስጥ አለመገኘቱ ናቸው።በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ እነዚህ ነገሮች የሉም፤ የተገኙት የጽሑፍ ቅጠሎችም ለዚህ ምንባብ ቦታ የላቸውም።
   ለ. ብዙዎቹ የኂለኞች የግሪክ ጽሑፎች ይህ ክፍል በኦሪጂናሉ ጽሑፍ ውስጥ አለመኖሩን ለማመልከት እንደ አስተሪክ ያሉ ምልክቶችን በላያቸው ያስቀምጣሉ።
   ሐ. በኂለኞች ልዩ ልዩ ጽሑፎች ውስጥ በብዙ ልዩ ልዩ ቦታዎች ተገኝቶአል።
      1. ከዮሐንስ 7:36 በኂላ
      2. ከዮሐንስ 7:44 በኂላ
      3. ከዮሐንስ 7:25 በኂላ
      4. በሉቃስ ውስጥ ደግሞ ከ21:38 በኂላ
      5. ከሉቃስ 24:53 በኂላ
   መ. ከጥንታውያኑ ትርጉሞች ውስጥም አይገኝም
      1. ከጥንቱ የላቲን ትርጉም
      2. ጥንታዊነት ካለው የሦሪያ ትርጉም
      3. ከቀደሙት "ፔሽታ" ከሚባለው (የኂለኞቹ የሦሪያ) ቅጂዎች
   ሠ. ከጥንት የቤተክርስቲያን አባቶች ስለዚህ የምንባብ ክፍል ምንም አስተያየት የለም (እስከ 12ኛ ምዕተ ዓመት)
   ረ. በኮዴክስ D (ቤዛኢ)፣ በ6ኛው ምዕተ ዓመት የምዕራባውያን ጽሑፎች፣ የላቲን ቫልጌት፣ እና የኂለኞች የ"ፔሽታ" የጥንት የሦሪያ ዕትሞች ውስጥ ይገኛል።
2. ውስጣዊ ማስረጃ
   ሀ. የቃላትና የአጻጻፍ ዘይቤው ከዮሐንስ ይልቅ ከሉቃስ ጽሑፎች ጋር ይመሳሰላል። በአንዳንድ የግሪክ ጽሑፎች ውስጥ ከሉቃስ 21:38 እና 24:53 በኂላ ይገኛሉ።

   ለ. ከዳስ በዓሉ፣7:1-52፣8:12-59፤ በኂላ ኢየሱስ ከአይሁድ መሪዎች ጋር ያደረገውን የውይይት ፍሰት ፈጽሞ የሚጥስ ነው።
   ሐ. በተመሳሳዮቹ ወንጌሎች ውስጥ በተጓዳኝ አይገኙም።

3. **ለምሳሌ** በBruce M. Metzger's *A Textual CommeNtary oN the Greek New TestameNt*, pp. 219-221 የተሟላ ቴክኒካል ማብራሪያ ይመልከቱ።

ሐ. ይህ ታሪክ ምናልባት በኢየሱስ ሕይወት የተከናወነ እውነተኛ ትውፊት ሊሆን ይችላል። ኢየሱስ ያደረጋቸው ነገር ግን የወንጌል ጸሐፊዎች ያልጻፉዋቸው ሌሎች ብዙ ክንውኖች አሉ (ዮሐ.20:30-31)። የወንጌል ጸሐፊዎች ራሳቸው በእስትንፋሰ መለኮት የተመሩ ነበሩ፤ ምንም እንኳ በኢየሱስ የተከናወነ እውነተኛ ታሪክ ቢሆንም በመጀመሪያዎቹ በእስትንፋስ መለኮት የተመሩ ጸሐፊዎች ያልተካተተን ታሪክ የኂለኞቹ ጸሐፊዎች የመጨመር መብት የላቸውም። የኢየሱስን ቃሎች እና ሥራዎች፣ የመምረጥና ለአንባቢም በሚስማማ መልኩ ማዘጋጀት በመንፈስ ቅዱስ ምሪት አብርሆትን ያገኙ የመጀመሪያዎቹ ጸሐፊዎች ድርሻ ብቻ ነው። ይህ ምንባብ ግን ከመጀመሪያ የሌለ እና የእግኢአብሔር መንፈስ የሌለበት ነው፤ ስለሆነም በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ መካተት የለበትም!

መ. እኔ በዚህ ምንባብ ላይ አስተያየት ለመስጠት አልመረጥኩም፤ ምክንያቱም ይህ ምንባብ የዮሐንስ ብዕር ውጤት ነው ብዬ አላምንም ፤ ስለሆነም የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት የዮሐንስ ወንጌል ኣካል አይደለም (ምንም እንኳ ታሪካዊ ቢሆንም)።

**NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 8፥12-20**

**[12]ደግሞም ኢየሱስ፦ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ብሎ ተናገራቸው። [13]ፈሪሳውያንም። አንተ ስለ ራስህ ትመሰክራለህ፤ ምስክርነትህ እውነት አይደለም አሉት። [14]ኢየሱስ መለሰ አላቸውም። እኔ ስለ ራሴ ምንም እንኳ ብመሰክር ከወዴት እንደመጣሁ ወዴትም እንድሄድ አውቃለሁና ምስክርነቴ እውነት ነው፤ እናንተ ግን ከወዴት እንደ መጣሁ ወዴትም እንድሄድ አታውቁም። [15]እናንተ ሥጋዊ ፍርድን ትፈርዳላችሁ፤ እኔ በአንድ ሰው ስንኳ አልፈርድም። [16]የላከኝ አብ ከእኔ ጋር ነው እንጂ ብቻዬን አይደለሁምና እኔ ብፈርድ ፍርዴ እውነት ነው። [17]የሁለት ሰዎችም ምስክርነት እውነት እንደ ሆነ በሕጋችሁ ተጽፎአል። [18]ስለ ራሴ የምመሰክር እኔ ነኝ፥ የላከኝም አብ ስለ እኔ ይመሰክራል። [19]እንግዲህ። አባትህ ወዴት ነው? አሉት። ኢየሱስ መልሶ፦ እኔንም ወይም አባቴንም አታውቁም፤ እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር አላቸው። [20]ኢየሱስ በመቅደስ ሲያስተምር በግምጃ ቤት አጠገብ ይህን ነገር ተናገረ፤ ጊዜው ገና አልደረሰምና ማንም አልያዘውም።**

8:12 ***"ደግሞም ኢየሱስ፡- ……. ተናገራቸው"*** "ብዙዎች" የሚል ቃል በዚህ ምዕራፍ አልተጠቀሰም፡፡ ይህ ምናልባት የበዓሉን መጠናቀቅ እና ኢየሱስ ብቻውን በቤተመቅደስ አካባቢ በመዘግየት ለአይሁድ መሪዎች እያስረዳ እና እየመሰከረ ይመስላል፡፡ ሆኖም ኢየሱስ ራሱን ለመግለጥ በበዓሉ የሚከናወነውን የውኃውን እና የማብራቱን ሥርዓት ተጠቅሟል፡፡

▣ ***"እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ"*** ምዕ.6:7 እና 8 ኢየሱስ ስለራሱ በተለዋጭ ዘይቤ ከተጠቀመበት ከእሥራኤል "የምድረበዳው መቅበዝበዝ/ጉዞ" ጋር የሚመሳሰል ይመስላል፡፡

1. ምዕራፍ 6 "መና" እና "የሕይወት እንጀራ" የሚሉትን ይጠመቀማል፡፡
2. ምዕራፍ 7 "ውኃ" እና "ሕያው ውኃ" የሚሉትን ይጠቀማል፡፡
3. ምዕራፍ 8 "ብርሃን" እና "ሼክናህ ክብር" ይጠቀማል፡፡

ይህ የብርሃን ተለዋጭ ዘይቤ በመላው የዮሐንስ ወንጌል በተደጋጋሚ አግልግሎት ላይ ውሎአል (1:4-5፡8-9፤3:19-21፤9:5፤12:46)፡፡

ይህ ምንን እንደሚያመለክት ክርክሮች አሉ፡፡

1. የጥንት ዘመን የጨለማ ፍርሃት
2. በብ.ኪ. የእግዚአብሔር የማዕረግ ስም (መዝ.27:1፤ኢሳ.62:20፤1ኛ ዮሐ.1:5)
3. የዳስ በዓላትን ታሪካዊ ዳራ፣በዳሱ ውስጥ በሴቶች አደባባይ ያለ ብርሃን የሚሰጥ ማራኪ ዕቃ፣
4. የእግዚአብሔር መገኘት ምልክት የሆነውን በምድረበዳው ጉዞ ወቅት የተገለጠውን የክብር ደመና የሚያስታውስ
5. በብ.ኪ. የሚገኝ መሲሃዊ ስም/ማዕረግ (ኢሳ.42:6፣49:6፤ሉቃ.2:32)

የአይሁድ የሕግ መምህራንም "ብርሃን" የሚለውን ቃል የመሲሁ የማዕረግ ሥም አርገው ይጠቀሙበት ነበር፡፡ የዳስ በዓሉ በሚከበርበት ጊዜ በሴቶች ግቢ የሚበራው ግዙፍ መብራት የኢየሱስ ንግግር መነሻ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ የብርሃን መሲሃዊ አመላካችነት እና በ1:4፣8 የሚገኘው ልዩ ማመሳከሪያ በቤተመቅደሱ ውስጥ ከሚከናወነው ሥርዓት ጋር የሚመሳሰል ሲሆን ስለኢየሱስ የእርሱን እውነተኛ መነሻ ገላጭ ነው፡፡

በዚህ ቦታ የሚገኘው "እኔ" በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ካሉት ከሰባቱ አንዱ ነው (ገላጭ ቃል ይከተለዋል)፡፡

1. እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ (6:35፣41፣46፣51)
2. እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ (8:12፤9:5፤1:4፣9፤12:46)
3. እኔ የበጎች በር ነኝ (10:7፣9)
4. እኔ መልካም እረኛ ነኝ (10:11፣14)
5. እኔ ትንሣኤ እና ሕይወት ነኝ (11:25)
6. እኔ መንገድ፣ እውነት እና ሕይወት ነኝ (14:6)
7. እኔ እውነተኛ የወይን ግንድ ነኝ (15:1፣5)

እነዚህ ልዩ የሆኑ የኢየሱስን ማንነት የሚገልጡ ቃላት የሚገኙት በዮሐንስ ውስጥ ብቻ ነው፡፡ ዮሐንስ መዳንን ከእነዚህ የማንነት ገላጭ ቃላት አንጻር ያየዋል፡፡ በእርሱ ልንታመን ይገባል፡፡

▣ ***"የዓለም"*** ይህ (*ኮስሞስ* በ14:17 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡) የሚያመለክተው የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ዓለም አቀፍ ክልል ነው (3:16)፡፡

▣ ***"የሚከተለኝ"*** ይህ የአሁን ጊዜ ድርጊትን የሚያመለክት ግሥ ነው፡፡ በመጀመሪያ ክርስትና የኃይማኖት ሥርዓት አለመሆኑ መታወስ አለበት፤ ይልቁንም ክርስትና ከክርስቶስ ጋር ከሚደረግ ግላዊ ኅብረት የተነሳ የሆነ የደቀ መዝሙርነት ሕይወት ነው (ማቴ.28:18-20፤1ኛ ዮሐ.1:7)፡፡

▣ ***"በጨለማ አይመላለስም"*** ይህ ሠይጣን "የማያምኑትን ሃሳብ አሳወረ" (2ኛ ቆሮ.4:4) የሚለውን የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስታውስ ነው፡፡ ከዚህም በላይ "ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴም ብርሃን ነው" (መዝ.119:105) የሚሉትንና የመሳሰሉትን በብ.ኪ. የሚገኙትን የእግዚአብሔር ቃል ምንባቦች የሚያስታውስ ነው፡፡

"ብርሃን"ን የተቀበሉ ልዩ ሕይወት ይኖራሉ (1ኛ ዮሐ.1:7)!

▣ ***"የሕይወት ብርሃን"*** ኢየሱስ የእግዚአብሔር ሕይወት ያለው እና እግዚአብሔር ለሰጠው ለእርሱ ለተከታዮች የሚሰጠው ነው (ማቴ.5:14)፡፡

8:13 ***"ፈሪሳውያንም"*** በ1:24 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

▣ ***"ምስክርነትህ እውነት አይደለም"*** አይሁድ መረጃን በተመለከተ በሕግ የተጻፋውን ይናገራሉ (ማለት የሁለት ምስክሮችን አስፈላጊነት፣ ዘሑ.35:30፤ዘዳ.17:6፤19:15-21)፡፡ ኢየሱስ ቀደም ስለዚህም ተቃውሞ ተናግሮ የነበረ (5:31) እና ብዙ ምስክሮችን አቅርቦ ነበር፡፡ በዚህ አውድ ምስክሩ አብ ነው!

8:14፣16 (ብመሰክር….ብፈርድ) እነዚህ ቃላት ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ሲሆን ይህም ድርጊትን ለመፈጽ አቅም መኖሩን ያመለክታል፡፡ በምዕራፍ 8 የሚገኙት አብዛኞቹ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገሮች እንደዚህ ዓይነት ናቸው፡፡

▣ **"ከወዴት እንደመጣሁ ወዴትም እንደምሄድ አውቃለሁ"** ይህ አሁንም "ከላይ እና ከታች" ያለ ሁለትዮሽ አስተሳሰብ **(ዱዋሊዝም)** ነው። ኢየሱስ ከአባቱ ጋር የነበረውን ቅድመ ሕልውና፣ ተልዕኮውን፣ እና ነብያዊ የጊዜ ሰሌዳውን ያውቃል (ዮሐ. 1:1-4፣14-18፤7:28-29፤13:1፤17:5)።

▣ **"እናንተ ግን ከወዴት እንደመጣሁ ወዴትም እንድሄድ አታውቁም"** ይህ ከምዕራፍ 7 ጋር ተያያዥነት ያለው ይመስል። ኢየሱስ የት እንደተወለደ አያውቁም (ቁ.41-42) ወዴትም እንሚሄድ አያውቁም ነበር (7:34-36፤8:21)። በ1:8 ላይ ያለውን የኢየሱስ ምስክሮች የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።

8:15 **"እናንተ *ሥጋዊ* ፍርድን ትፈርዳላችሁ"** ይህም ምዕራፍ 7ና የሚያሳታውስ ነው (ቁ.24)። በ1:14 ላይ ‹*ሥጋ*› (*ሳርክስ*) የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።

▣ **"እኔ በአንድ ሰውስ እንኳ አልፈርድም"** አንዳንዶች በዮሐንስ 3:17 እና 9:39 መካከል ግጭት እንዳለ ያስባሉ። ኢየሱስ ሊፈርድ አልመጣም፤ ሕይወትን ሊሰጥ እንጂ። የእርሱን የመምጣቱን እውነታ ተረድተው እርሱን አምነው ያልተቀበሉ ሁሉ ተፈርዶባቸዋል (3:18-21)።

8:16-18 አሁንም ይህ በፍርድ ቤት ለተያዘ ጉዳይ የሁለት ምስክሮችን አስፈላጊነት የሚያሳይ ነው (ዘሑ. 35:30፤ዘዳ.17:6፤19:15)። ኢየሱስ ከአብ ጋር ያለውን አንድነት በማያጠራጥር ቃላት አረጋግጦአል (7:29፤14:9)። በ1:8 ላይ ያለውን የኢየሱስ ምስክሮች የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።

8:16

NASB (1970),
NJB, REB — **"የላከኝ"**
NASB1995), NKJV, NRSV,
NIV — **"የላከኝ አብ"**

በሁለቱ የNASB ትርጉሞች መካከል ልዩነት እንዳለ ሁሉ እንዲሁ በUBS[3,4] ም አለ

1. UBS[3] "አብ" በ "C" ደረጃ (MSP[39,66,75], N2, B, L,T, W)
2. UBS[4] "አብ" በ "A" ደረጃ (MSS N*, D, *የሦሪያ ትርጉሞች እና የጥንት ኂለኛ ትርጉሞች ውስጥ አይገኝም*)

ኢየሱስ በፍጹም ብቻውን አይደለም! አብ ሁልጊዜ ከእርሱ ጋር ነው (ቁ.16፣29፤16:32)፣ ምናልባትም በመስቀል ላይ ከዋለበት ጊዜ በስተቀር (ማር.15:34)።

የኅብረት ደስታ እና ፍጹምነት የመዳን መሰረት ነው። እግዚአብሔር ፍጥረትን የፈጠረበት ዓላም ከእርሱ ጋር ኅብረት የሚያደርግን አንድን ሰው ፈልጎ ነው፣ ስለዚህ እርሱ (ማለት ክርስቶስ ዮሐ.1:3፤1ኛ ቆሮ.8:6፤ቆላ.1:16፤ዕብ.1:2) በያህዌ መልክ እና ምሳሌ ፈጠራቸው (ዘፍ.1:26፣27)። ከእርሱ ጋር ኅብረትን ማጣት የኃጢአት ውጤት ነው። የዚህ ኅብረት መታደስ ደግሞ የኢየሱስ ተልዕኮ ግብ ነው!

8:19 **"አባትህ ወዴት ነው?"** እስከአሁን ድረስ ገና ኢየሱስን የሚያውቁት በቁሳዊ ማንነቱ እና በተራ ሰውነት ደረጃ ነው። ዕውቀት አልባው እና ኩሩው አእምሮአቸው ለእውነት ዝግ ነበር (ቁ.27)። ይህ የተሳሳተ መረዳታቸው የዮሐንስ ወንጌል ሥነ ጽሑፋዊ ባሕሪ ነው።

▣ **"እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር"** ይህ የሁለተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ነው። ይህ ብዙውን ጊዜ "ከእውነት የተቃረነ" ይባላል። "እኔንስ ብታውቁኝ፣ አሁን ግን አታውቁኝም፣ ቀጥሎ አባቴን ታውቁ ነበር፣አሁን ግን አታውቁትም።" ይህ መሪ ቃል ከ5:37 (የ7:28ን የተሟላ ማስታወሻ ይመልከቱ።) ጀምሮ በተደጋጋሚ ይገኛል። የዮሐንስ ወንጌልን አስተዋጽኦ መሥራት አስቸጋሪ ነው፤ ምክንያቱም ተደጋግሞ ወይም ተደራርቦ አምሮ እንደተሠራ ስጋጃ ወይም የተወሳሰበ እና የተደጋገመ ጣፋጭ ቃና ያለው የሙዚቃ ቅንብርን ስለሚመስል ነው።

8:20 **"በግምጃ ቤት አጠገብ ይህን ተናገረ"** ይህ ጥቅስ ከአይን ምስክር የተገኘ ሌለው የኤዲቶሪያል አስተያየት ይመስላል። ግምጃ ቤቱ የተለየ ሕንፃ አልነበረም። የረቢዎች ትውፊት (Shekalim 6) እንደሚለው የጥሩምባ ቅርጽ ያላቸው አሥራ ሦስት የሚሆኑ መሰብሰቢያዎች ነበሩ፤ እያንዳንዱ ለተለየ ዓላማ የተለየ ነበር። በዳስ በዓል ጊዜ ግዙፍ መብራቶች ብርሃን በሚሰጡበት በሴቶች አደባባይ ይቀመጥ ነበር።

▣ **"ጊዜው ገና አልደረሰም ነበርና"** በ2:4 ላይ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ።

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 8፥21-30

[21]ኢየሱስም ደግሞ። እኔ እሄዳለሁ ትፈልጉኛላችሁም በኃጢአታችሁም ትሞታላችሁ እኔ ወደምሄድበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም አላቸው። [22]አይሁድም። እኔ ወደ ምሄድበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም ማለቱ ራሱን ይገድላልን? እንጃ አሉ። [23]እናንተ ከታች ናችሁ፥ እኔ ከላይ ነኝ፤ እናንተ ከዚህ ዓለም ናችሁ፥ እኔ ከዚህ ዓለም አይደለሁም። [24]እንግዲህ። በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ አልኋችሁ፤ እኔ እንደሆንሁ ባታምኑ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁና አላቸው። [25]እንግዲህ። አንተ ማን ነህ? አሉት። ኢየሱስም፦ ከመጀመሪያ ለእናንተ የተናገርሁት ነኝ። [26]ስለ እናንተ የምናገረው የምፈርደውም ብዙ ነገር አለኝ፤ ዳሩ ግን የላከኝ እውነተኛ ነው እኔም ከእርሱ የሰማሁትን ይህን ለዓለም እናገራለሁ አላቸው። [27]ስለ አብ እንደ ነገራቸው አላስተዋሉም። [28]ስለዚህም ኢየሱስ፦ የሰውን ልጅ ከፍ ከፍ ባደረጋችሁት ጊዜ እኔ እሆን ዘንድ አባቴም እንዳስተማረኝ እነዚህን እናገር ዘንድ እንጂ ከራሴ አንዳች እንዳላደርግ በዚያን ጊዜ ታውቃላችሁ። [29]የላከኝም ከእኔ ጋር ነው፤ እኔ ደስ የሚያሰኘውን ዘወትር አደርጋለሁና አብ ብቻዬን አይተወኝም አላቸው። [30]ይህን ሲናገር ብዙዎች በእርሱ አመኑ።

**8:21-22** **"እኔ ወደምሄድበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም፤ ማለቱ ራሱን ይገድላልን? እንጃ"** የቁ.22 ጥያቄ "አይገድልም" የሚል መልስን የጠብቃል። እነርሱ ምንም እንኳ ንግግሩን ባያስተውሉም (7፡34-36) ከሞቱ ጋር ያያይዙት እንደነበር ከአውዱ ግልጽ ነው። ከዮሴፍ ወልደ ኮሪዮን (ጆሴፈስ) እንደምንረዳው ራስን በራስ ማጥፋት እጅግ በጣም የከፋውን የሲኦል ፍርድን ያስከትላል። ጥያቄያቸው ኢየሱስ ራሱን በራሱ ከገደለ ወደዚህ ቦታ መሄድ እንዳለበት እንደሚያስቡ የሚያመለክት ይመስላል።

**8:21** **"በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ"** ይህ ቃል በቃል "በራሳችሁ/በሠራችሁት ኃጢአት ትሞታላችሁ" ማለት ነው። "ኃጢአት" የሚለው ቃል በቁ. 21 ላይ ነጠላ መደብ ሲሆን በቁ. 24 ላይ ደግሞ የብዙ ቁጥር መደብ ነው። ይህ በመጀመሪያ ኢየሱስ እንደ ክርስቶስ አለመቀበላቸውን (ቁ.24) ያመላክታል። ይህ በርግጥ በሦስቱ ተመሳሳዩች ወንጌላት ይቅር የማይባል ኃጢአት ነው። መሪዎቹ ከቃሎቹ እና ተአምራቶቹ የተገለጠውን የመገኘቱን ታላቅ ብርሃን አይተው ኢየሱስን አልተቀበሉትም።

ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ከማርቆስ ማብራሪያዬ የወሰድኩዋቸውን ማስታወሻዎች ይመልከቱ።

**ማርቆስ 3:29** **"በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚሳደብ ሁሉ"** ይህ በቅድመ ጴንጤቆስጤ ታሪካዊ ሥፍራ ውስጥ መታየት አለበት። ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው የእግዚአብሔር እውነት ተቀባይነት እንዳጣ ለማመልከት ነው። የዚህ ክፍል ትምህርት "ይቅር የማይባል ኃጢአት" ተብሎ የሚታወቅ ነው። በሚከተሉት መሥፈርቶች መሠረት ሊብራራ ይገባዋል፡-

1. በብ.ኪ. "በታሰበበት" እና "ያልታሰበበት ኃጢአት" መካከል ያለ ልዩነትን (ዘሑ.15:27-31)
2. በዚህ አውድ ውስጥ የኢየሱስ የራሱ ቤተሰቦች አለማመን ከፈሪሳውያን አለማመን ጋር ተቃርኖአዊ ንጽጽር ተደርጓል።
3. የኃጢአት ይቅርታ ዓረፍተ ነገሮች በቁ.28 ላይ
4. በተመሳሳዮቹ ወንጌላት ያለ ልዩነት፣ በተለይ "የሰው ልጅ" (ማቴ.12:32፤ ሉቃ.12:10) ወደ "የሰው ልጆች" (ማቴ.12:31፤ ማር.3:28) መለወጡ።

በእንዚህ ከላይ በተጠቀሱት ብርሃንነት ሲታይ በመገኘቱ ታላቅ ብርሃን እና እውቀት ኢየሱስ እንደ እግዚአብሔር መገለጥ እና የመዳን መሣሪያ ተቀባይነት በማጣቱ ኃጢአት ተሰርቷል። እነዚህ ይህንን ኃጢአት የሠሩት የወንጌልን ብርሃን ወደ ሠይጣን ጨለማነት ለውጠውታል (ማር.3:30)። የመንፈስ ቅዱስን ወቀሳ እና ሰበት/አቅራቦት ተቃውመዋል (ዮሐ.6:44፣65)። ይቅር የማይባል ኃጢአት በአንዲት ነጠላ ድርጊት ወይም ቃል ምክንያት አይደለም በእግዚአብሔር የተቃወመው፤ ነገር ግን ቀጣይነት ባለው በፈቃደኝነት ላይ በተመሠረተ አለማመን (ማለት ጸሐፍት እና ፈሪሳውያን) የተደረገ በክርስቶስ የተገለጠን አምላክ መቃወም ስለሆነ ነው።

ይህ ኃጢአት ሊሰራ የሚችለው ለወንጌል በተጋለጡ ግለሰቦች ብቻ ነው። የኢየሱስን የምስራች ቃል በግልጽ የሰሙ እና የተቃወሙት ናቸው ለዚህ ኃጢአት የበለጠ ኃላፊ የሚሆኑት። ይህ በተለይ የወንጌል መልእክትን በገፍ በሚሰሙት፣ ነገር ግን በሚቃወሙት በዘመናዊው ባሕል ውስጥ ላሉት (ማለት አሜሪካ፣ ምዕራባዊያን ባሕል) እውነት ነው።

**8:23** **"እናንተ ከታች ናችሁ፣ እኔ ከላይ ነኝ"** ይህ የዮሐንስ ሌላው ከላይ ወደ ታች ቀጥ ያለ ዱዋሊዝም (ሁለትዮሽ) (ማለት ታች እና ላይ 7:35-36፤ 18:36) ነው።

የዮሐንስ ከላይ በሆነው ኢየሱስ እና ከታች በሆኑት አይሁድ መካከል ያለው ተቃርኗዊ ንጽጽር ዱዋሊዝምን (ሁለትዮሽን) ሰርተውታል፤ ይህ ወንጌላት መካከል ልዩ ነው። ተመሳሳዮቹ ወንጌላት (ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ) የሁለት የአይሁድ ዘመናትን ያነጻጽራሉ፡- ክፉ የሆነውን የአሁን ዘመን እና የወደፊቱን የጽድቅ ዘመን። ይህ ልዩነት የጎንዮሽ/አግድም እና ከላይ ወደ ታች ቀጥ ያለ ዱዋሊዝም (ሁለትዮሽ) ነው። ኢየሱስ በተለያዩ ሥፍራዎች እነዚህን አስተምሯልን? ምናልባት ዮሐንስ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርት በግል የሰጠውን ትምህርት በሚዘግብበት ጊዜ ተመሳሳዮቹ ወንጌላት የኢየሱስን የአደባባይ ትምህርቶች ዘግበዋል ።

▣ **"እናንተ ከዚህ ዓለም ናችሁ"** ዓለም በክፉ ላይ የተመሠረተ ነው (2ኛ ቆሮ.4፡4፤ ኤፌ.2፡2፤ ነጻ 1ኛ ዮሐ.5፡19)። በ14፡17 ላይ ‹ዓለም› (*ኮስሞስ*) የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመለከቱ።

8፡24 **"ባታምኑ"** ይህ የሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ሲሆን ድርጊትን ለመፈጸም አቅም/ዕድል አለ ማለት ነው።

▣

| | |
|---|---|
| NASB,NKJV | "እኔ እርሱ እንደሆንሁ እናንተ ባታምኑ" |
| NRSV,JB | "እኔ እርሱ እንደሆንሁ ባታምኑ" |
| TEV | "እኔ ያው እኔ እንደሆንሁ ባታምኑ" |
| NJB | "እኔ እርሱ እንደሆንሁ ባታምኑ" |

ይህ ቃል ኢየሱስ ስለራሱ መለኮታዊ ባሕሪ ያለውን እጅግ ጠንካራ ራስ ግንዛቤዎች አንዱ ነው (ወይም ይህ አውድ "መሲህን" የሚያመልክት ነው ለማለት ይቻላል)። በብ.ኪ. ለያህዌህ የተሰጠውን ስም/ማዕረግ ይጠቀማል ("እኔ" ዘፀ.3፡14)። ይህ በዮሐንስ ውስጥ ከታወቁት የ"እኔ" ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ግልጽ/እርግጠኛ የሆነ ነው። ይህ አድራጊ የሌለው ዓረፍተ ነገር ነው (4፡26፤6፡20፤8፡24፣25፣58፤13፡19፤18፡5፣6፣8)። በ2፡23 ላይ ያለውን የዮሐንስን "ማመን" የሚለውን ቃል አጠቃቀም በተመለከተ ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።

8፡25 **"አንተ ማን ነህ?"** የአይሁድ ባለሥልጣናት ስለስድብ ለመክሰስ ሕጋዊ መሠረት ይፈልጉ ነበር (ማቴ.26፡57-68፤ማር.14፡53-65)! ሊገድሉት ይፈልጉ ነበር። መረጃ አልነበረም የሚፈልጉት፤ ነገር ግን ሊፈርዱበት ነበር።

ኢየሱስ በግልጽ በዮሐንስ ውስጥ (ከተመሳሳዮቹ ወንጌላት በተለየ) ራሱን ይገልጣል ። ቃሎቹ (ማለት ቁ.24) እና *ሥራዎቹ* (ማለት በሰንበት መፈወሱ) *ሥልጣኑን* ያሳያሉ።

▣

| | |
|---|---|
| NASB | "ከመጀመሪያ ለእናንተ የተናገርኩት ነኝ" |
| NKJV | "ከመጀመሪያ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ስነግራችሁ የነበርኩት እኔ ነኝ" |
| NRSV | "ለእናንተ ለምን እናገራለሁ" |
| TEV | "ከመጀመሪያ ጀምሮ የተናገርኳችሁ ነኝ" |
| NJB | "ከሁሉ ነገር በፊት የተናገርኳችሁ ነኝ" |

ዋናው የግሪክ ጽሑፍ በቃላቶች መካከል ክፍተት አልነበረውም። ስለዚህ አውዱን የሚመጥን ለማድረግ የግሪክ ፊደሎች ይከፋፈሉ/ዘርዘር ይደረጉ ነበር። የትርጉሞች ልዩ ልዩ መሆን ከተለያዩ ጽሑፎች ጋር የተያያዙ አይደሉም፤ የቃል መዘርዘር እንጂ። እነሆ አማራጮች፡-

1. *ሆቴ* (*hote*)- ከመጀመሪያ ተናግሬያችኋሁ (NASB,NKJV,TEV,NJB,NIV)
2. *ሆ ቲ* (*ho ti*) ሴሜቲክ የቃለ አጋኖ ፈሊጣዊ የአነጋገር - ከእናንተ ጋር ፈጽሜ ተነጋግሬያለሁ (NRSV,TEV የግርጌ ማስታወሻ)

ይህ ምናልባት በሰብትዋጀንት የዘፍ 1፡1 (ፍጥረት) ትርጉም እና በዮሐ.1፡1 (አግልግሎቱ) "መጀመሪያ" የሚለው ከዮሐንስ የቃል ጨዋታዎች አንዱ ነው። ኢየሱስ ከ"መጀመሪያ" በቃሎቹ እና በሥራዎቹ ሁሉን ይነግራቸው ነበር!

8፡26-27 እነዚህ መሪ ቃላት በዮሐንስ ውስጥ አጽንኦትን ለመስጠት ተደጋግመው ተጽፈዋል።

1. አብ ላከኝ (3፡17፣34፤4፡34፤5፡36፣38፤6፡29፣44፣46፤7፡28-29፤8፡16፣26፣42፤10፡36፤11፡42፤12፡49፤14፡24፤15፡21፤17፡3፣18፣21፣23፣25፤20፡21)
2. እግዚአብሔር እውነት ነው (3፡33፤7፡28)
3. የኢየሱስ ትምህርቶች ከእግዚአብሔር ዘንድ ነበር (3፡11፤7፡16-17፤8፡26፣28፣40፤12፡49፤14፡24፤15፡15)
4. ኢየሱስ አባቱን ገለጠ (1፡18፤8፡26-29፤12፡49-50፤14፡7፣9)

▣ **"ዓለም"** በ1፡10 ላይ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ።

8፡27 በጸሐፊው የተሠጠ ሌላው ኢዲቶሪያል አስተያየት። የእርሱን ግልጽ ተለዋጭ ዘይቤ እና ተምሳሌታዊ ቋንቋ ከገባቸው፣ እነርሱ እንደሌሎች አይሁድ እርሱን ለመግደል ይሞክሩ ነበር (5፡18፤8፡59፤10፡33)። ንግግሮቹ ስውሮች አልነበሩም!

8፡28 **"የሰውን ልጅ ከፍ ከፍ ባደረጋችሁት ጊዜ"** ይህ በብ.ኪ. ዘሑ.21፡4-9 ላይ የተመለከተውን እና በዮሐ. 3፡14 የተጠቀሰውን ታሪክ የሚያስታውስ ነው። ይህ ቃል እንደሌሎቹ በዮሐንስ ውስጥ እንደሚገኙት ቃላት ሁሉ ሁለት ትርጉም አለው። በመስቀል ላይ "ከፍ ከፍ" (3፡14፤12፡32፣34) አለ፣ ነገር ግን በየሐዋ.2፡33 እና ፊልጵ.2፡9 በተጻፈው አይነት "ከበረ" ማለት ሊሆን ይችላል። ኢየሱስ ሊሞት እንደመጣ ያውቅ ነበር (ማር.10፡45)።

▣ **"የሰው ልጅ"** ይህ ኢየሱስ ለራሱ የመረጠው የማዕረግ ስም ነው፡፡ ምክንያቱም በረቢዎች አይሁዳዊነት ውስጥ እንደነበው ወታደራዊ ወይም ብሄራዊ ስሜት አልነበረውም፡፡ ኢየሱስ ይህንን ስም የመረጠበት ምክንያት ከሁለቱም ማለት ከሰብዓዊነቱ (ሕዝ.2:1፤መዝ.8:4) እና አምላክነቱ (ዳን.7:13) ጋር የተያያዘ ስለሆነ ነው፡፡

▣ **"እኔ እሆን ዘንድ .... በዚያን ጊዜ ታውቃላችሁ"** ደቀ መዛሙርቱ እና ቤተሰቦቹ እንኳ እስከ (7:39) ጴንጤቆስጤ በኂላ ድረስ ሙሉ ለሙሉ አላወቁትም! መንፈስ ዓይን በሚከፍት ኃይሉ መንፈሳዊ ዓይን እና ጆሮ ባላቸው ሁሉ ላይ መጣ! ለተለየ ሰዋስዋዊ ማረጋገጫ በቁ.24 ላይ "እኔ እንደሆንሁ" በሚለው ሥር ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ፡፡

1. እርሱ ነው (ማለት መሲህ)
2. አባቱን የሚገልጥ (5:19-20)
3. እርሱ እና አባቱ አንድ ናቸው (ቁ.29)

**8:29 "አብ ብቻዬን አይተወኝም"** ኢየሱስ ከአብ ጋር ያለው ኅብረት አዛልቆታል (8:16፤16:32)፡፡ በመስቀል ላይ እያለ የተቋረጠው ኅብረት አስቸጋሪ የሆነበት ለዚህ ነበር (ማር.15:34)፡፡

**8:30 "ብዙዎች በእርሱ አመኑ"** "ማመን" የሚለውን ቃል በዚህ ምንባብ ውስጥ መጠቀም ታላው እድል ነው፡፡ ከጥቂት አድማጮች በኩል ያለን ጠባብ እምነት የሚያመለክት ይመስላል (ማቴ.13፤ ማር.4)፡፡ መሲህ ማለት ምን እንደሆነ በመረዳታቸው ላይ በመመሥረት እርሱን እንደ መሲህ ለመቀበል ፈቃደኞች ነበሩ፡፡ የ8:30-58 አውድ እነርሱ እውነተኛ አማኞች እንዳልነበሩ (2:23-25) በግልጽ ያሳያል፡፡ በዮሐንስ ውስጥ ብዙ የእምነት ደረጃዎች አሉ፤ ሁሉም ግን ወደ መዳን የሚመሩ አይደሉም፡፡ በ2:23 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

> NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 8÷31-33
> **[31]ኢየሱስም ያመኑትን አይሁድ፡፡ እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ፤ [32]እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኂል አላቸው፡፡ [33]እነርሱም መልሰው፡፡ የአብርሃም ዘር ነን ለአንድም ስንኳ ከቶ ባሪያዎች አሊሆንም፤ አንተ፡፡ አርነት ትወጣላችሁ እንዴት ትላለህ? አሉት፡፡**

**8:31 "ብትኖሩ"** ይህ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ቃል ሲሆን ለድርጊት ዕድል መኖሩን ያመለክታል፡፡ ቀጣይነት ባለው እምነት ላይ ያለው ትኩረት በዮሐንስ 15 ውስጥ በግልጽ ተብራርቷል፡፡ በወንጌላውያን የወንጌል እወጃ ውስጥ የጠፋው ነገር ይህ ነው፡፡ ቃሉ ሊታመን (5:24)፣ ሊታዘዙት፣እና ሊኖሩት ይገባል፡፡ በ1ኛ ዮሐ. 2:10 ላይ "መኖር" የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

> **ልዩ ርዕስ፡ የመጽናት አስፈላጊነት**
>
> *በምሥራቃውያን የጥንድ የአነጋገር ወይም የቋንቋ ስልት መሠረት የተመሰረተ በመሆኑ ምክንያት ከክርስቲያን ሕይወት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን ለማብራራት አስቸጋሪ ነው፡፡ እነዚህ ጥንድ አስተሳሰቦች እርስ በርሳቸው የሚጋጩ ይመስላሉ፤ ሆኖም ሁለቱም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ናቸው፡፡ ምዕራባውያን ክርስቲያኖች አንዱን የመምረጥና ተቃራኒውን ያለመቀበል ዝንባሌ አላቸው፡፡ በምሳሌ ሳስረዳ፡*
>
> *ሀ. መዳን በክርስቶስ ለማመን የሚደረግ የመጀመሪያ ውሳኔ ብቻ ነው ወይስ የሕይወት ዘመን የደቀመዝሙርነት ሕይወት?*
>
> *ለ. መዳን ከልዑል እግዚአብሔር በጸጋ ብቻ የተደረገ ምርጫ ወይስ ለመለኮታዊ ሥጦታ የሚደረግ ሰው ዘር የንስሐ እና ማመን ምልሽ?*
>
> *ሐ. መዳን አንዴ ከተቀበሉ የማያጡት ነው ወይስ ቀጣይነት ያለው ትጋት የሚያስፈልገው?*
>
> *ጽናት በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ቀጣይነት ያለው ጉዳይ ነው፡፡ ችግሩ በአ.ኪ. ውስጥ የሚጋጩ ከሚመስሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ይጀምራል፡፡*
>
> *ሀ. የዋስትና ምንባባት*
>
> 1. *የኢየሱስ ቃሎች* (ዮሐ.6÷37፤1÷28-29)
> 2. *የጳውሎስ ቃሎች* (ሮሜ 8÷35-39፤ኤፌ.1÷13፤2÷5፣8-9፤ፊልጵ.1÷6፤2÷13፤2ኛ ተሰ.3÷3፤2ኛ ጢሞ.1÷12፤4÷18)
> 3. *የጴጥሮስ ቃሎች* (1ኛ ጴጥ.1÷4-5)
>
> *ለ. የመጽናት አስፈላጊነት ምንባባት*
>
> 1. *የኢየሱስ ቃሎች* (ማቴ.10÷22፤13÷1-9፣24-30፤24÷13፤ማር.13÷13፤ዮሐ.8÷31፤15÷4-

10፤ራዕ.2÷7፣17፣20፤3÷5፣12፣21)

2. የጳውሎስ ቃሎች (ሮሜ 11÷22፤1ኛ ቆሮ.15÷2፤2ነ ቆሮ.13÷5፤ ገላ.1÷6፡3፡4፤ 5÷4፤6÷9፤ፊልጵ.2÷12፤3÷18-20፤ቆላ.1÷23)
3. የዕብራውያን ጸሐፊ ቃሎች (2÷1፤3÷6፣14፤4÷14፤6÷11)
4. የዮሐንስ ቃሎች (1ኛ ዮሐ. 2÷6፤2ኛ ዮሐ.9)
5. የአብ ቃል (ራዕ.21÷7)

መጽሐፍ ቅዱሳዊ መዳን ከልዑል እግዚአብሔር ፍቅር፣ ምህረት፣ እና ጸጋ የተነሳ የሚሰጥ/የሚገኝ ነው፡፡ የመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት ከሌለ ማንም ሰው ሊድን አይችልም (ዮሐ.6፡44፣65)፡፡ አምላክ በመጀመሪያ ይመጣን ዓላማውን ይፈጽማል፤ ሰዎች ደግሞ በእምነት እና በንስሐ (ሁለቱም መጀመሪያ እና ቀጣይ ናቸው) ምላሽ ይፈልጋል፡፡ እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር በቃል ኪዳን ግንኙነት ይሠራል፡፡ እዚህ ጋ እድሎች እና ኃላፊነቶች አሉ!

መዳን ለሰው ሁሉ የተሰጠ ነው፡፡ የኢየሱስ ሞት የሚጋፈጠው/የሚገናኘው ከወደቀው ዓለም ኃጢአት ጋር ነው፡፡ እግዚአብሔር በኢየሱስ በኩል ለገለጠው ፍቅሩ እና ጉብኝቱ በአምሳሉ የተፈጠረ ሁሉ ምላሽ ይሰጥ ዘንድ መንገድን አዘጋጅቷል፡፡

በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ካልቪናዊ ካልሆኑ አቅጣጫዎች የበለጠ መረዳት ከፈለጉ፣

1. Dale Moody. *The Word of Truth*, Eerdmaℵs, 1981 (pp.348-365)
2. Howard Marshall, *Kept by the Power of God*, Bethaℵy Fellowship, 1969
3. Rober Shaℵk, *Life iℵ the Soℵ*, Westcott, 1961 ይመልከቱ፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ሁለት የተለያዩ ችግሮችን ይሰነዝራል፡- (1) ዋስትናን እንደ ፈቃድ ወረቀት በመረዳት ስግብግብ/ራስ ወዳድ እና ፍሬቢስ ሕይወት መኖር (2) በግላቸው ኃጢያት እና አገልግሎት የሚደክሙትን ማበረታታት ናቸው፡፡ ችግሩ የተሳሳተ ቡድን የተሳሳተ መልእክትን መውሰዱ እና በተወሰኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባቦች ላይ ብቻ በመመሥረት ሥነ-መለኮታዊ ሥርዓትን መገንባቱ ነው፡፡ ጥቂት ክርስቲያኖች በሚያሳዝን ሁኔታ የዋስትና መልዕክቶችን ይፈልጋሉ፤ ሌሎች ደግሞ ጥብቅ ማስጠንቀቂያን! አንተ በየትኛው ቡድን ውስጥ ነህ?

▣ **"እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ"** ኢየሱስ በታዛዥ ሕይወት ላይ ያተኩራል (ትዕዛዞቹ ቁ.51፣52፣55፤16፡15፣21፣23፣24፤15፡10፣20፤17፡6፤ ሉቃ.6፡46፤ 2ኛ ዮሐ.9)፡፡ ይህ ጥቅስ "ሼማ" (*Shema*) የሚለውን ቃል ትርጉም ያንጸባርቃል፤ ይህ የዕብራይስጥ ቃል ሲሆን "ለማድረግ መስማት" የሚል ትርጉም አለው (ማለት፡- ዘዳ.6፡4-6)፡፡

8፡32 **"ታውቃላችሁ"** ይህ "ማወቅ" የሚለው ቃል የብ.ኪ.ንን ትርጉም የሚወስድ ሲሆን በተለይ "ግላዊ ግንኙነት" ማለት እንጂ የ"አእምሮአዊ እውነት"ን ማለት አይደለም (ዘፍ.4፡1፤ ኤር.1፡5)፡፡ እውነት ስብዕና ያለው ነው! ይህ ቃል (ሁል ጊዜም በትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚገኝ) የሰው ልጅ በጥረቱ የሚያገኘውን የተከማቸ ዕውቀትን አያመለክትም፡፡ ይህ ነፃ ያልሆኑትን የሰው ልጆች በመከፋፈል እና በማሰር አረጋግጦአል፡፡ በዚህ ቦታ የሚነገርለት "እውነት" ወንጌል እና የኢየሱስ ክርስቶስ ስብዕና ነው፡፡ ከእርሱ የተለየ እውነት፣ ሰላም ወይም ተስፋ የለም!

8፡32፣40፣44፣45፣46 **"እውነት"** ይህ የአውዱ ቁልፍ ሃሳብ ነው፡፡ ይህ ቃል ሁለት አንደምታዎች አሉት፡-

1. ተአማኒነት
2. እውነት እና ሃሰተኝነት

ሁለቱም በኢየሱስ ሕይወት እና አገልግሎት ውስጥ የነበሩ ናቸው፡፡ እርሱ የወንጌል ዋና መልዕክት እና ግብ ነው፡፡ እውነት በመጀመሪያ ስብዕና ያለው ነው፡፡ ኢየሱስ ስብዕና ያለውን አብን ይገልጣል፡፡ ይህ ቃል ብዙውን ጊዜ ከአውዱ ተገንጥሎ ይወሰድ እና ትምህርት በሚሰጥባቸው ሥፍራዎች ውስጥ አገልግሎት እንዲሰጥ ይገደዳል፡፡ ጭብጦች፣ እውነተኛ ጭብጦች እንኳ፣ እወነተኛ የሆኑ ብዙ ጭብጦች እንኳ አንድን ሰው ነፃ አያወጡትም (መክ.1፡18)፡፡ በ6፡55 እና 17፡3 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

8፡32 **"አርነት ያወጣችኋል"** አማኞች ከሕግ (ወግ) አጥባቂ ሥርዓት፣ ከኃይማኖት ሥርዓት፣ እና ተግባር ተኮር ከሆነው ከሰዎች ኃይማኖት ነፃ ናቸው፡፡ ሆኖም ነፃ የወጡ አማኞች ራሳቸውን ስለወንጌል ያስተሳስራሉ (ሮሜ.14፡1-15፡6፤1ኛ ቆሮ.8-10)፡፡

8፡33 **"የአብርሃም ዘር ነን ለአንድም ስንኳ ከቶ ባሪያዎች አሊሆንም"** እውር የሆነ በዘር ላይ የተመሠረተ ኩራት እንዴት ሊሆን እንደሚችል አስገራሚ ነው፡፡ ግብፅስ፣ ሦሪያስ፣ ባቢሎንስ፣ ፋርስስ፣ ግሪክስ፣ እና ሮምስ?

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 8÷34-38
[34]ኢየሱስ መለሰ፥ እንዲህ ሲል፦ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ኃጢአት የሚያደርግ ሁሉ የኃጢአት ባርያ ነው። [35]ባርያም ለዘላለም በቤት አይኖርም፤ ልጁ ለዘላለም ይኖራል። [36]እንግዲህ ልጁ አርነት ቢያወጣችሁ በእውነት አርነት ትወጣላችሁ። [37]የአብርሃም ዘር መሆናችሁንስ አውቃለሁ ነገር ግን ቃሌ በእናንተ አይኖርምና ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ። [38]እኔ በአባቴ ዘንድ ያየሁትን እናገራለሁ፤ እናንተም ደግሞ በአባታችሁ ዘንድ ያያችሁትን ታደርጋላችሁ።

**8:34 "ኃቲአትን የሚያደርግ ሁሉ የኃጢአት ባሪያ ነው"** ኢየሱስ በቁ 33 ላይ ስለቁ. 32 የተሳሳተ ግንዛቤ ከወሰዱት "አርነት ያወጣችኋል" ከሚለው ሐረግ በስተኋላ ወዳለው መንፈሳዊ እውነታ ሊመራቸው እየሞከረ ነው። ይህ ቃል በቁ. 21 እና 24 ላይ ኢየሱስ ካደረጋቸው ጠንካራ ክሶች ጋር የሚያያዝ ነው። በእነዚህ የማይጠቅሙ ተከታዮች ላይ የሰነዘረው ነቀፋ በቁ.44-47 ተጠናቋል።

ፍራንክ ስተጅ በኒው ቴስታሜንት ቴዎሎጂ () መጽሐፉ እንደተናገረው "የሰው አሳዛኝ ሁኔታ እሱም እስራቱ ራሱን ነፃ ለማውጣት የመሞከሩ ውጤት ነው" (ገጽ 31)።

በዚህ ቦታ ያለው ግሥ የአሁን ጊዜ ድርጊት ገላጭ ሲሆን ይህም "ማድረግ" የሚለው ግሥ በቀጣይነት የሚሠራ ኃጢአትን ያመለክታል። ኃጢአትን በቀጣይነት ማድረግ አንድ ሰው እውነትን (ኢየሱስን) "ያለማወቁ" ማስረጃ ነው። በ1ኛ ዮሐ.3:6፣9 ላይም "ኃጢአት ማድረግ" የሚል ተመሳሳይ የሆነ የአሁን ጊዜ ግሥ አለ!

ጥያቄው "አማኞች ኃጢአት ይሠራሉን?" የሚል ነው። መልሱ "አዎ" ነው (ሮሜ 7፤ 1ኛ ዮሐንስ)። ክርስቲያኖች ከኃጢአት ጋር ይታገላሉ፤ ነገር ግን የጠፉቱ በኃጢአታቸው ይደሰታሉ፤ አያውቁትምም!

NET የተባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም (ገጽ 1921 ቁ. 21) ጥሩ አስተያየትን በማከል በዮሐንስ ውስጥ የተገለጠው አውዳዊ ኃጢአት "አለማመን" (ይቅር የማይባል ኃጢአት) እንደሆነ ይናገራል። ይህ በስነምግባራዊ አውድ ሳይሆን "በመዳን አውድ ማመን" ላይ ነው። በ1ኛ ዮሐንስ ውስጥም የተገለጠው "ኃጢአት" የሆነው አለማመን (ለሞት የሆነ ኃጢአት) ነው!

**8:35** ይህ ጥቅስ ከቁ.34 ጋር በቀጥታ አይያያዝም ከቁ.36 ጋር እንጂ። ኢየሱስ በረቢያዊ ይሁዲነት (በእስራኤል መምህራን የአይሁዳዊነት ትምህርት) ያልሆነ እውነተኛው ልጅ ነው (ዕብ.1:2፤3:6፤5:8፤7:28)። መጨረሻ የሌላቸውን ደንቦች እና ሥርዓቶች መፈጸም ሳይሆን በእርሱ ማመን ብቻ አንድን ሰው አርነት ሊያወጣው ይችላል (ቁ.32)።

▣ **"ዘላለም"** በ6:58 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።

**8:36 "ቢያወጣችሁ"** ይህ የሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ሲሆን ለድርጊት አቅም መኖሩን ይናገራል።

**8:37 "ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ"** (5:18፤7:1፣19፤8:27፣40፤11:53)።

▣ **"ቃሌ በእናንተ አይኖርምና"** ይህ ሐረግ በተለያየ መንገድ ሊተረጎም ይችላል። The Bible iN TweNty Six TraNsilatioNs የተባለው ጠቃሚ የጥናት መርጃ ነው።

1. "ቃሌ በውስጣችሁ በነፃነት ባለመኖሩ ምክንያት" AmericaN StaNdard VersioN
2. "በውስጣችሁ ቦታ ስለሌለው" The New TestameNt by HeNry Alford
3. "በመካከላችሁ ምንም ስለአላደረገ" The New TestameNt: A New TraNslatioN by James Moffatt
4. "በውስጣችሁ ምንም ቦታ ስላላገኘ" The emphasized New TestameNt: A New TraNslatioN by J. B. Rotherham
5. "ቃሌ በልባችሁ ውስጥ ቦታ በማጣቱ ምክንያት" The Four Gospels by E. V. Rieu

አሁንም ችግሩ ወንጌልን የመቀበል ወይም ያለመቀበል ጉዳይ ነው። ይህ የመዳን ጉዳይ ነው እንጂ በሂደት የሚመጣ የሞራል ዕድገት ጉዳይ አይደለም።

**8:38 "ያየሁትን"** ይህ የተፈጸመ ድርጊት አመልካች ግሥ ሲሆን ከኢየሱስ ቅድመ ሕልውና እና አሁን ከአባቱ ጋር ካለው ግንኙነት ጋር ተያያዥነት ያለው መሆኑን ያመለክታል (ቁ.40፣42)።

▣ **"እናንተም ደግሞ በአባታችሁ ዘንድ ያያችሁትን ታደርጋላችሁ"** በዚህ ቦታ ለመጀመሪያ ጊዜ "አባት" ተብሎ የተገለጠው ምናልባትም የአይሁድን ልማድ ለመግለጽ ይሆናል (ኢሳ.29:13)። ሆኖም በቁ.41-44 ስያሜው ሠይጣንን/ዲያብሎስን የሚገልጽ ነው። "ሙሴን" የሚደግፍ የሚመስለው ድርጊታቸው፣ ሃሳባቸው፣ እና ቃላቸው መንፈሳዊ ዝንባሌአቸውን በግልጽ ያሳይል። የሰው ልጆች መንፈሳዊውን ዓለም ለመያዝ መነሳሳት አይችሉም። ሁለት ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ምንጮች (የዱዋሊዝም አስተሳሰብ አይደለም) አሉ - እግዚአብሔር/ክርስቶስ/መንፈስ ወይም ሠይጣን/እና የእርሱ የሆነው! አንድ ሰው እንዴት ለወንጌል ምላሽ ሊሰጥ እንደሚችል (1:12፤3:16፤10:1-18፤14:6) መንፈሳዊ ዝንባሌው ይገልጣል!
ከዚህ ሐረግ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥቂት ምንባባዊ አማራጮች አሉ።

1. "አባት" ለሚለው ሁለቱም ማነጻጸሪያዎች ያህዌህን ("ያንተ" የሚል ተውላጠ ስም የለውም) ሊያመለክቱ ይችላሉ።
2. ግሡ ትዕዛዛዊ እንጂ አመልካች አይደለም።

(Bruce M. Metzger, *A Textual CommeNtary oN the Greek New TestameNt*, p.225 ይመልከቱ።)::

**NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 8፥39-47**
**[39]*መልሰውም። አባታችንስ አብርሃም ነው አሉት። ኢየሱስም፦ የአብሃም ልጆች ብትሆኑ የአብርሃምን ሥራ ባደረጋችሁ ነበር።***
**[40]*ነገር ግን አሁን ከእግዚአብሔር የሰማሁትን እውነት የነገርኋችሁን ሰው ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ፤ አብርሃም እንዲህ አላደረገም። [41]እናንተ የአባታችሁን ሥራ ታደርጋላችሁ አላቸው። እኛስ ከዝሙት አልተወለድንም አንድ አባት አለን እርሱም እግዚአብሔር ነው አሉት። [42]ኢየሱስም አላቸው። እግዚአብሔርስ አባታችሁ ከሆነ በወደዳችሁኝ ነበር፤ እኔ ከእግዚአብሔር ወጥቼ መጥቻለሁና፤ እርሱ ላከኝ እንጂ ከራሴ አልመጣሁምና። [43]ንግግሬን የማታስተውሉ ስለ ምንድር ነው? ቃሌን ልትሰሙ ስለማትችሉ ነው። [44]እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ። እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ፤ እውነትም በእርሱ ስለ ሌለ በእውነት አልቆመም። ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፥ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና። [45]እኔ ግን እውነትን የምናገር ስለ ሆንሁ አታምኑኝም። [46]ከእናንተ ስለ ኃጢአት የሚወቅሰኝ ማን ነው? እውነት የምናገር ከሆንሁ እናንተ ስለ ምን አታምኑኝም? [47]ከእግዚአብሔር የሆነ የእግዚአብሔርን ቃል ይሰማል፤ እናንተ ከእግዚአብሔር አይደላችሁምና ስለዚህ አትሰሙም።***

8:39 "*አባታችንስ አብርሃም ነው*" እነርሱ የአብርሃም ዘሮች መሆናቸውን ኢየሱስ አልካደም፤ ነገር ግን እነርሱ የሠይጣን ቤተሰብ ባህሪያት እንዳለቸው ይፋ አድርገዋል (ቁ. 39፣44)። የግል የእምነት ግንኙነት እንጂ በዘር ላይ የተመሠረተ ማንነት ከእግዚአብሔር ጋር እንዲሄዱ አያረጋቸውም (ዘዳ.6:5፣13፤ሮሜ.2:28-29፤9:6)።

▣ "*ብትሆኑ*" ይህ የአንደኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ቢሆንም (በሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ውስጥ የአሁን ጊዜ ድርጊት አመልካች ነው) እንደ ሁለተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ሊያገለግል ይችላል (ቁ.19 እና 42)። የተለያዩ የግሪክ ቅጂዎች ይህንን ቅይጥ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ግሥን ወደ ትዕዛዝ በመለወጥ ለማስወገድና ሞክረዋል። እንዲህም ከሆነ "እናንተ የአብርሃም ልጆች ሆናችሁ ቢሆን ኖሮ (ግን አይደላችሁም) ያን ጊዜ አብርሃም ያደረገውን ታደርጉ ነበር (ግን አላደረጋችሁም)።" UBS[4] በ "B" ደረጃ (አብዛኛውን የተረጋገጠ) ያለውን ቅይጥ ሁኔታዊ ፎርምን ይሠጣል።

8:40 "*ሰው*" ኢየሱስ ራሱን እንደ ያህዌስ ተወካይ አርጎ ብቻ አልነበረም የሚያየው፤ ከያህዌህ ጋር በመለኮት እኩል እንደሆነ፤ ደግሞም እውነተኛ ሰውም እንደሆነ ነው። ይህም የኖስቲኮችን የሐሰት መምህራን በመንፈስ እና ቁስ መካከል ያለውን ዘለአለማዊ ዱዋሊዝም (ሁለትዮሽ) ትምህርት ለመቃወም የተነገረ ጠንካራ ንግግር ነው (1ኛ ዮሐ.1:1-4፤4:1-4)።

**ልዩ ርዕስ፡ ኖስቲካዊነት**

ሀ. በአብዛኛው ስለኑፋቄ እውቀት የምናገኘው በ2ኛው ምዕተ ዓመት ከተጻፉት የኖስቲክ ጽሑፎች ነው። ይሁን እንጂ የኑፋቄው አስተምህሮ በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት (በሙት ባሕር ጥቅሎች) እና በሐዋሪያው ዮሐንስ ጽሑፎች ውስጥ ነበሩ።

ለ. በኤፌሶን (1ኛ ጢሞቴዎስ)፣ በቀርጤስ (ቲቶ) እና በቆላሲ (ቆላስያስ) የነበረው ችግር የኖስቲካዊነት እና የሕግ/ወግ አጥባቂ አይሁዳዊነት አባዜ ተቀያይጦ/ተደባልቆ መታየት ነበር።

ሐ. በሁለተኛው ምዕተ ዓመት ጥቂት የ‹‹ቫለንቲኒያን›› እና የ‹‹ሴሬንቲኒያን›› ኖሰቲካዊነት አስተሳሰቦች እውነት ተብለው ተቀባይነት አግኝተው ነበር።

1. ቁስ እና መንፈስ በአንድነት ዘላለማዊ (ኦንቶሎጂካል ዱዋሊዝም) ናቸው። ቁስ ክፉ ነው፣ መንፈስ ጥሩ ነው። እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ ባሸበረቀ ክፉ ነገር ውስጥ ሊኖር አይችልም።
2. በእግዚአብሔር እና በቁስ መካከል የሚወጡ ነገሮች (‹‹ኢዮንስ› [eoNs] ወይም መልአካዊ/አማልክታዊ ደረጃዎች [aNgelic levels]) ነበሩ። የመጨረሻው ወይም እጅግ በጣም ዝቅተኛው ዓለምን (‹‹*ኮስሞስ*› *kosmos*) የፈጠረው የብሉይ ኪዳኑ ያህዌህ ነበረ።
3. ኢየሱስ እንደ ያህዌህ የወጣ ነው፤ ነገር ግን ደረጃው በጣም ከፍ ያለ ስለሆነ ወደ እውነተኛው አምላክ የቀረበ ነው። አንዳንዶች እርሱን እጅግ በጣም ከፍተኛው አድርገው ይመለከቱታል፤ ነገር ግን አሁንም ከእውነተኛው አምላክ ያነሰ እና በእርግጥ በሥጋ/ተሰግዎ/ ያልመጣ አምላክ ነው (ዮሐ.1፥14)። ቁስ ክፉ እስከሆነ ድረስ ኢየሱስ ሰብዓዊ ሰውነት ሊኖረው እና መለኮት ሊሆን አይችልም። ሰውን መስሎ ተገልጧል፤ ነገር ግን በእርግጥ መንፈስ ብቻ ነበር (1ኛ ዮሐ.1፥1-3፤4፥1-6)።
4. መዳን ልዩ በሆኑ ሰዎች በሚታወቅ ልዩ እውቀት እና በኢየሱስ በማመን የሚገኝ ነው። በሰማያዊ ዓለማት ውስጥ ለማለፍ እውቀት (የይለፍ ቃሎች) ያስፈልጉ ነበር።

መ. የኖስቲክ የሐሰት መምህራኖች በሁለት የሚቃረኑ የስነምባር ሥርዓቶችን ይከራከራሉ።

1. ለጥቂቶች የሕይወት የአኗኗር ዘይቤ ከመዳን ጋር አይያያዝም። ለእነዚህ መዳን እና መንፈሳዊነት በአማልክታዊ ክበብ (*eoNs*) አማካይነት በምስጢራዊ እውቀት (የይለፍ ቃሎች) ውስጥ ተካተዋል።
2. ለሌሎች የአኗኗር ዘይቤ ለመዳን ወሳኝ ነው። በዚህ መጽሐፍ፣ የሐሰት አስተማሪዎች በመናኝ የአኗኗር ዘይቤ ላይ በማተኮር ለእውነተኛ መዳን እንደ ማስረጃ ያቀርባሉ (2፥16-23)።

ሠ. በናግ ሐማዲ ቤተመጽሐፍት (Nag Hammadi Library) የሚገኘው የጀምስ ኤም. ሮቢንሰን እና ሪቻርድ ስሚዝ መጽሐፍ ጥሩ ማመሳከሪያ ነው።

8:41

NASB,NKJV "እኛስ ከዝሙት አልተወለድንም"

NRSV "እኛስ ዲቃላዎች አይደለንም"

TEV "እኛስ እውነተኛ ልጆች ነን"

NJB "እኛስ ከሕግ ውጪ አልተወለድንም"

ይህ ምናልባት በቁ.48 ("ሳምራዊ እንደሆንህ") ከሚለው ክስ ጋር ተያያዥነት ያለው ነው፡፡ አይሁድ ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ የአይሁድ ደም የሌለው ዲቃላ እንደነበር አስረግጠው የሚናገሩ ይመስላሉ፡፡ ኋላ ላይ ረቢያዊ ምንጮች ሮማዊ ወታደር አባት እንደነበረው ይናገራሉ፡፡

▣ "አንድ አባት አለን፣ እርሱም እግዚአብሔር" ይህ ዓረፍተ ነገር በአባታዊ ቃሎች የተገለጸውን (ዘዳ.32፡6፤ኢሳ.1፡2፤63፡16፤64፡8) በብ.ኪ. (ዘዳ.4፡35፣39፤6፡4-5) የነበረው ጠንካራ የአንድ አምላክ አምልኮ ያንጸባርቃል፡፡ ሁለት ምርጫዎች ነበሩ፡- የአይሁድ መሪዎች የእግዚአብሔርን አንድነት አረጋግጠዋል (ዘዳ.6፡4-5)፣ እና ለሙሴ ሕግ መታዘዝ ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት (ዘዳ.6፡1-3፣17፣24-25) ያመጣል ብለው ያምኑ ነበር፡፡ ኢየሱስ ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ እንደሆነ እያወጀ መጣ፡፡ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት መሠረቱ የሕግ ሥራ መሥራት አይደለም፤ ነገር ግን በእርሱ በማመን እንደሆነ ይናገር ነበር፡፡ ግራ መጋባታቸው እና ማመንታታቸው እንዲረዱት አላስቻላቸውም፣ ስለሆነም የመንፈስ ቅዱስ ብርሃን እና የኢየሱስ ታላላቅ ሥራዎች ሰዎችን ወደ እምነት ለማምጣት የሚያስፈልጉት እዚህ ጋ ነው!

8:42 "ከሆነ" ይህ ሁለተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር "የእውነት ተቃራኒ" ይባላል፡፡ "እግዚአብሔር አባታችሁ ቢሆን (ግን አይደለም) በወደዳችሁኝ ነበር (ግን አትወዱኝም)" (ቁ.47)፡፡

8:43 "ቃሌን ልትሰሙ ስለማትችሉ ነው" ይህ መንፈሳዊ ተቀባይነትን እና መረዳትን ይገልጻል፡፡ እነርሱ መንፈሳዊ ጆሮ አልነበራቸውም (ኢሳ.6፡9-10፤ማቴ.11፡15፤13፡9፣15-16፣43፤ማር.4፡9፣23፤7፡16፤8፡18፤ሉቃ.8፡8፤14፡35፤የሐዋ.7፡51፤28፡26-27)፡፡

8:44 "እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ" ምን ዓይነት አስደንጋጭ ቃል ነው በዘመኑ ለነበሩ የኃይማኖት መሪዎች (ቁ.47)፡፡ የቤተሰቡን ባሕሪ የሚጋራው ይህ ሃሳብ በዕብራይስጥ ፈሊጣዊ አነጋገር "የ……ልጆች" (ማቴ.13፡38፤የሐዋ.13፡10፤1ኛ ዮሐ.3፡8፣10) የተገለጸ ነው፡፡ በ12:31 ላይ "ዲያብሎስ" የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

▣ "እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ" ይህ የክፉን ዘላለማዊነት ለመግለጽ አይደለም (ማለት የ"ዞሮስትሪኒዝም" [ZoroastriaNism] ዱዋሊዝም)፤ ነገር ግን በእባብ ውስጥ ባደረ የሐሰት መንፈስ የአዳም እና ሔዋን መንፈሳዊ ፈተና ሃሳብን ያንጸባርቃል እንጂ (ዘፍ.3)፡፡ በእውነተኛው አምላክ እና በእውነተኛው ዲያብሎስ መካከል ያለውን በዓላማ የበለጸገ ተቃርኖአዊ ንጽጽር ልብ ይበሉ!

8:46 "ከእናንተ ስለ ኃጢአት የሚወቅሰኝ ማን ነው?" በዚህ አውድ ይህ የሚገልጸው ስለ ሐሰተኛ ምስክርነት ነው፡፡ ሠይጣን ይዋሻል፤ ነገር ግን ኢየሱስ እውነትን ይናገራል፡፡ ኢየሱስ ትምህርቱን ወይም ንግግሮቹን ትክክል አለመሆናቸውን እንዲያስረዱ ፤ እርሱ ሐሰተኛ መሆኑን እንዲመረምሩ እነዚህን የአይሁድ መሪዎችን ይጋብዛቸዋል፡፡ ይህ ዓረፍተ ነገር በዚህ አውድ ውስጥ እንደ ሥነ-መለኮታዊ አስተምህሮ ከኢየሱስ ኃጢአት አልባነት ጋር ተያያዥነት ያለው አይመስልም፡፡

በዮሐንስ ውስጥ "ኃጢአት" ብዙውን የወደቀው ዓለም የክፋት መርህ፣ ለየት ካለ የኃጢአት ደርጊት ይልቅ በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ ነው፡፡ ከኢየሱስ በስተቀር ሁሉም ነገር በኃጢአት የተበከለ ነው፡፡

> NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 8:48-59
>
> አይሁድ መልሰው፡፡ ሳምራዊ እንደ ሆንህ ጋኔንም እንዳለብህ በማለታችን እኛ መልካም እንል የለምን? አሉት፡፡ ኢየሱስም መለሰ: እንዲህ ሲል፦ እኔስ ጋኔን የለብኝም ነገር ግን አባቴን አከብራለሁ እናንተም ታዋርዱኛላችሁ፡፡ እኔ ግን የራሴን ክብር አልፈልግም፤ የሚፈልግ የሚፈርድም አለ፡፡ እውነት እውነት እላችኊለሁ: ቃሌን የሚጠብቅ ቢኖር ለዘላለም ሞትን አያይም፡፡ አይሁድ፡፡ ጋኔን እንዳለብህ አሁን አወቅን፡፡ አብርሃም ስንኳ ሞተ ነቢያትም፤ አንተም፡፡ ቃሌን የሚጠብቅ ቢኖር ለዘላለም ሞትን አይቀምስም ትላለህ፡፡ በእውኑ አንተ ከሞተው ከአባታችን ከአብርሃም ትበልጣለህን? ነቢያትም ሞቱ፤ ራስህን ማንን ታደርጋለህ? አሉት፡፡ ኢየሱስም መለሰ አለም፡፡ እኔ ራሴን ባከብር ክብሬ ከንቱ ነው፤ የሚያከብረኝ እናንተ አምላካችን የምትሉት አባቴ ነው፤ አላወቃችሁትምም: እኔ ግን አውቀዋለሁ፡፡ አላውቀውም ብል እንደ እናንተ ሐሰተኛ በሆንሁ፤ ዳሩ ግን አውቀዋለሁ ቃሉንም እጠብቃለሁ፡፡ አባታችሁ አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሤት አደረገ: አየም ደስም አለው፡፡ አይሁድም፡፡ ገና አምሳ ዓመት ያልሆነህ አብርሃምን አይተሃልን? አሉት፡፡ ኢየሱስም፦ እውነት እውነት እላችኊለሁ: አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ አላቸው፡፡ ስለዚህ ሊወግሩት ድንጋይ አነሡ፤ ኢየሱስ ግን ተሰወራቸው ከመቅደስም ወጥቶ በመካከላቸው አልፎ ሄደ፡፡

8:48 **"ሳምራዊ እንደ ሆንህ ጋኔንም እንዳለብህ"** እውነተኛ አውዳዊ ትርጉም በዚህ "ሳምራዊ" ተብሎ በግሪክ በተተረጎመው አረማዊ ቃል ውስጥ ተንጸባርቋል ለማለት የሚያስችል ዕድል አለ፡፡ ትርጉሙም "የኢጋንንት አለቃ" ማለት ነው፡፡ ኢየሱስ የአረማዊ ቋንቋ ይናገር ነበር፡፡ ይህ እውነት ከሆነ ኢየሱስ ኃይል የሚያገኘው ከክፉው ነው እያሉ ዘወትር የኃይማኖት መሪዎች የሚከሱትን ክስ እውነት ሊያደርግ ነው፡፡ መልእክቱ እውነት አይደለም ብሎ ለመቃወም ጋኔን አለበት ማለት ደግሞ ይቻላል (ቁ.52)፡፡ ኢየሱስ ሳምራዊ ነበር (4:9) ወይም ጋኔን ነበረበት ማለት (7:20፤8:48፣49፣52፤10:20፣21፣ በ12:31 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡) አንድ ሰው ኢየሱስን እንዳይሰማ ወይም ለመልዕክቱ ምላሽ እንዳይሰጥ የማድረጊያ መንገድ ነበር፡፡ ይህ ፣ያኔ እንደ "አብርሃም አባታችን ነው"፣ ሌላው ለኢየሱስ ወይም ለመልዕክቱ ምላሽ ላለመሥጠት ምክንያት ነበር፡፡

8:49 አብን የማያምን ወልድን ደግሞ አያምንም (1ኛ ዮሐ.5:9-12)፤ አብን የማያውቅ ወልድን ደግሞ አያከብርም (5:23)፡፡ ሆኖም ሁለቱ ውጪያዊ አካላት ያላቸው አንድ ናቸው (10:30፤17:21-23)፡፡

8:50 **"የራሴን ክብር"** በ1:14 ላይ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ፡፡

8:51፣52 **"ቢኖር ….. ቢኖር"** እነዚህ ሁለቱም ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ድርጊት ለመፈጸም እድል መኖሩን ያመለክታል፡፡ መታዘዝ ከእምነት ጋር የተያያዘ መሆኑን ልብ ይበሉ (በቁ.48 ውስጥ የሚኙትን ምንባባት ይመልከቱ፡፡)፡፡

▣ **"ለዘላለም ሞትን አያያይም"** ይህ ጠንካራ የሆነ እጥፍ የሆነ አሉታዊ ጎን ያለው ነው፡፡ ይህ መንፈሳዊ ሞትን እንደሚያመለክት ግልጽ ነው (ቁለ21፣24)፣ አካላዊ ምትን አይደለም (5:24፤6:40፣47፤11:25-26)፡፡ የሞት ፍርሃትንም ሊያመለክት ይችላል (1ኛ ቆሮ.15:54-57)፡፡

የ"ሞት" (ቴናቶስ) አሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሦስት ደረጃዎች ተገልጸዋል፡፡

1. መንፈሳዊ ሞት፣ ዘፍ.2:17፤3:1-24፤ኢሳ.59:2፤ሮሜ 7:10-11፤ያዕ.1:15 (ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙት ተቋርጧል)፡፡
2. አካላዊ ሞት፣ ዘፍ.3:4-5፤5 (ከዓለም ጋር ያለው ግንኙት ተቋርጧል)፡፡
3. ዘላለማዊ ሞት፣ "ሁለተኛው ሞት" ራዕ.2:11፤20:6፣14፤21:8 (ከእግዚአብሔር ጋር የተቋረጠው ግንኙነት ቋሚ ሆነ)፡፡

ለእግዚአብሔር ታላቅ ፍጥረት ሞት የእግዚአብሔር ፈቃድ ተቃራኒ ነው (ዘፍ.1:26-27)፡፡

8:52 ይህ የኢየሱስን ነግግር በተሳሳተ መንገድ እንደተረዱ ያሳያል (ቁ.51)፡፡ እነርሱ ይህን ከአብርሃም እና ከነብያት አካላዊ ሕይወት ጋር ያገናኙታል፡፡

8:53 ይህ ጥያቄ "አይደለም" የሚል መልስን ይጠብቃል፡፡ እንዴት ያለ አስገራም ቃል ነው! ነገር ግን ይህ በትክክል ኢየሱስ ሲናገረው የነበረው ነው፡፡

1. እርሱ ከአብርሃም ይበልጣል፣ ቁ.53
2. እርሱ ከያዕቆብ ይበልጣል፣ 4:12
3. እርሱ ከዮናስ ይበልጣል፣ ማቴ.12:41፤ሉቃ.11:32
4. እርሱ ከመጥምቁ ዮሐንስ ይበልጣል፣ 5:36፤ሉቃ.7:28
5. እርሱ ከሰለሞን ይበልጣል፣ ማቴ.12:42፤ሉቃ.11:31

መላው የዕብራውያን መጽሐፍ ኢየሱስ በሙሴ ላይ፣ አዲሱ ኪዳን በአሮጌው ኪዳን ላይ ያለውን የበላይነት ያሳያል (የዕብራውያን ማብራሪያዬን ከነፃው ኦንላይን በ www.freebiblecommeNtary.org ይመልከቱ፡፡)፡፡

▣ **"ራስህ ማንን ታደርጋልህ"** ነጥቡ በትክክል ይህ ነው! ኢየሱስ በቁ.54 እና 58 ላይ መደምደሚያውን በግልጽ አስቀመጠ እና ተሳድቧል በሚል ሊወግሩት ሞከሩ (ቁ.59)፡፡

8:54 **"ባ….."** ሌላው ሦስተኛው መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ድርጊትን ለመፈጸም እድል መኖሩን ያመላክታል፡፡

▣ **"የሚያከብረኝ"** እዚህ ጋ እጥቅም ላይ የዋለው ክብር በሚለው ስሜት ነው (ሮሜ 1:21፤1ኛ ቆሮ.12:26)፡፡

8:55 **"አላወቃችሁትምም……አውቀዋለሁ"** በዚህ ጥቅስ ውስጥ እንግሊዝኛው "ግኖስኮ" (*giNosko*) እና "ኦይዳ" (*oida*) የተሰኙትን ሁለት የግሪክ ቃሎች ይተረጉማል፤ እነዚህ ቃላት በዚህ አውድ ውስጥ ተመሳሳይ ይመስላሉ (7:28-29)፡፡ ኢየሱስ አባቱን ያውቀዋል ደግሞ ለእርሱ ተከታዮች ይገልጥላቸዋል፡፡ ዓለም (አይሁዳውያን እንኳ) አብን አያውቁትም (1:10፤8:51፤10:3፤17:25)፡፡

8:56 **"አባታችሁ አብርሃም"** ይህ አስገራሚ አነጋገር ነው፡፡ ኢየሱስ "ከአይሁድ፣" "ከሕግ" (8:17)፣ "ከቤተመቅደስ" እና ከእምነት አባት አብርሃም እንኳ ራሱን ያርቃል፡፡ ይህ ከብሉይ ኪዳን ጋር ግልጽ የሆነ መቆራረጥ ነው!

▣ **"ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሴት አደረገ"** ይህ የተፈጸመ ድርጊት አመልካች ነው። አብርሃም ስለመሲሁ ምን ያህል ተረድቶ ነበር? ብዙ ትርጉሞች ይህንን በመፃኢ እሳቤ ይተረጉሙታል። ከዚህ ቀጥሎ ያሉት አማራጮች የተወሰዱት *ዘ ባይብል ኢን ቱዌንቲ ስክስ ትራንስሌሽንስ* ከተሰኘው ነው።

1. "*ማየት ይገባዋልና ፈነደቀ*" -*The Emphasized New TestameNt: A New TraNslatioN* by J. B. Rotherham
2. "*ቀኔን ለማየት ሐሴት አርጓል*" -Revised StaNdard VersioN
3. "በቅርቡ ለማየት ጥልቅ ደስታ ነበረው" -*The Berkeley VersioN of the New TestameNt* by Gerrit Verkuyl
4. "*የሚመጠውን ለማየት*" -*The New TestameNt: AN AmericaN TraNslatioN* by Edgar J. Goodspeed
5. "ቀኔን ያውቅ ዘንድ ሐሴት አድርጎ ነበር" -*The New TestameNt iN the LaNguage of Today* by William F. Beck

በተጨማሪ በሀሮልድ ኬ.ሙልተን የተሻሻለው *አነሊቲካል ግሪክ ሌክሲካን* የሰብትዋጀንትን አጠቃቀም በመውሰድ ግሡን "በጽናት መፈለግ" በሚል ትርጉም አስፍሯል (ገጽ.2)።

▣ **"አየም ደስም አለው"** ይህ ከሁለት ጉዳዮች አንደኛውን ያመለክታል።

1. አብርሃም በዘመኑ መሲሁን በራዕይ አይቶ ነበር (2ኛ "እስድራስ" (Esdras) 3:14)
2. አብርሃም በሰማይ ሆኖ የመሲሁን ሥራ በምድር ያውቅ ነበር (ዕብ.11፡13)

የኢየሱስ ትምህርቶች አጠቃላይ መልዕክት/ነጥብ የአይሁድ ሕዝብ አባት ከፊታቸው ወደነበረው ወደ መሲሁ ዘመን በታላቅ ደስታ ይመለከት እንደነበር ቢሆንም ነገር ግን የአሁኑ "ዘር" (ትውልድ) እንዳልተቀበለው እና እንዳልተደሰተበት ነው። አብርሃም የአማኞች አባት ነው (ሮሜ.2:28-29)፣ እንጂ የማያምኑ አይደለም!

8:57 አሁን የኢየሱስ አድማጮች በቀጥታ ትርጉም እሳቤያቸው ምክንያት ቃሎቹን በተሳሳተ መንገድ ተረድተውታል! ይህ ግራ መጋባት ምናልባትም ዓላማ ነበረው! ማየት ባለመፈለጋቸው ወይም ባለመቻላቸው ምክንያት አያዩም ነበር!

8:58 **"አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ"** ይህ ለአይሁድ ስድብ ነበር፤ ስለዚህም ሊወግሩት ፈለጉ (ዘፀ.3፡12፣14)። እርሱ እያለ የነበረውን በትክክል ተረድተውታል፤ ማለትም እርሱ ቀድሞም የነበረ አምላክ ነበር (4:26፤6:20፤8:24፣28፣54-59፤14:19፤18:5፣6፣8)።

8:59 **"ሊወግሩት ድንጋይ አነሱ"** የኢየሱስ ነገግር ግልጽ ነበር። እርሱ መሲህ እና ከአባቱ ጋር አንድ ነበር። በቁ.31 ላይ "ያመኑት" የተባሉት እነዚህ አይሁዶች አሁን ደግሞ ተሳደበ በማለት ሊወግሩት እየተዘጋጁ ናቸው (ዘሌ.24:16)። የኢየሱስን አዲስ ሥር ነቀል መልእክት መቀበል ለእነዚህ አይሁድ አስቸጋሪ ነገር ነበር።

1. መሲሁ ሲመጣ ያደርጋል ብለው እንደጠበቁት አልነበረም ያደረገው።
2. ቅዱስ የሚሉትን ትውፊታቸውንም ተገዳድሮታል።
3. ጥብቅ የሆነ የአንድ አምላክ እምነታቸውንም ግራ አጋብቷቸዋል።
4. ያህዌ ሳይሆን ሠይጣን "አባታቸው" እንደሆነ በጽኑ ተናግሮአቸዋል።

አንድ ሰው ወይ እርሱን "መውገር" አልያም "መቀበል" ነው ያለበት! መካከለኛ ሥፍራ የለም!

▣ **"ኢየሱስ ግን ተሰወራቸው ከመቅደስም ወጥቶ"** ይህ ጥቅስ ተርጓሚዎች እንዲገምቱ (በግሪኩ ምንባብ ውስጥ ሐረጎች እንዲጨምሩ) ካደረጉዋቸው መካከል አንዱ ነው፡-

1. ተአምር ነበር (ሉቃ.4:30 እና ቃላትና የአጻጻፍ ዓይነት ጭማሪ)
2. ኢየሱስ በሕዝቡ ውስጥ ተቀላቅሎአል ምክንያቱም እርሱ ተሳታፊ አይሁድችን ይመስል ነበር።

መለኮታዊ የሆነ የጊዜ ሠሌዳ ነበር። ኢየሱስ ሊሞት እንደመጣ እና እንዴት፣ መቼ፣ እና የት እንደሚሞት ሁሉ ያውቅ ነበር። "ሠዓቱ ገና አልደረሰም"!

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ማብራሪያ ነው፤ ይህ ማለት ስለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን ባገኘነው ብርሃን መመላለስ አለብን። መጽሐፍ ቅዱስን በመተርጎም ረገድ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ እና መንፈስ ቅዱስ ቀዳሚዎች ነችሁ። ለሌላ ተንታኝ/ሐተታ አቅራቢ ብቻ መተው የለብህም።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተነሱት ታላላቅ ጉዳዮች ላይ ታተኩር ዘንድ እንዲረዳህ እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ተሰጥተውሃል። እነዚህ ጥያቄዎች ማለት ለላቀ መረዳት አእምሮ ቀስቃሾች እንጂ ማሳረጊያዎች አይደሉም።

1. ዮሐንስ 7፡53-8፡11 ያለው ክፍል የዋናው የዮሐንስ ወንጌል ክፍል ነውን? ለምን?
2. "እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ" በማለት የተናገረው የኢየሱስ ቃል ዳራ ምንድን ነው?
3. ፈሪሳውያን ለምንድን ነው ኢየሱስ በጣም የጠሉት?
4. በቁጥር 30 ላይ "ማመን" የሚለውን ቃል ባለበት አውድ ብርሃንነት ግለጽ።

# ዮሐንስ 9

## በዘመናዊ ትርጉሞች የአንቀጽ አከፋፈል

| UBS[4] | NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| *እውር ሆኖ የተወለደው ሰው መፈወስ* | *እውር ሆኖ የተወለደው ማያትን ተቀበለ* | *ኢየሱስ እንደ ሕይወት ብርሃን ራሱን ገለጠ* | *ኢየሱስ እውር ሆኖ የተወለደውን ሰው ፈወሰ* | *እውር ሆኖ የተወለደው ሰው መዳን* |
| 9:1-12 | 9:1-12 | 9:1-12 | 9:1-2 | 9:1-5 |
| | | | 9:3-5 | |
| | | | 9:6-7 | 9:6-7 |
| | | | 9:8 | 9:8-12 |
| | | | 9:9ሀ | |
| | | | 9:9ለ | |
| | | | 9:10 | |
| | | | 9:11 | |
| | | | 9:12ሀ | |
| | | | 9:12ለ | |
| *ፈሪሳውያን ፈውሱን መረመሩ* | *ፈሪሳውያን የተፈወሰውን ሰው አገዱት* | | *ፈሪሳውያን ፈውሱን መረመሩ* | |
| 9:13-17 | 9:13-34 | 9:13-17 | 9:13-15 | 9:13-17 |
| | | | 9:16ሀ | |
| | | | 9:16ለ | |
| | | | 9:17ሀ | |
| | | | 9:17ለ | |
| 9:18:23 | | 9:18-23 | 9:18-19 | 9:18-23 |
| | | | 9:20-23 | |
| 9:24-34 | | 9:24-34 | 9:24 | 9:24-34 |
| | | | 9:25 | |
| | | | 9:26 | |
| | | | 9:27 | |
| | | | 9:28-29 | |
| | | | 9:30-33 | |
| | | | 9:34 | |

| መንፈሳዊ እውርነት | እውነተኛ እይታ እና እውርነት | | መንፈሳዊ እውርነት | |
|---|---|---|---|---|
| 9፡35-39 | 9፡35-41 | 9፡35-41 | 9፡35 | 9፡35-39 |
| | | | 9፡36 | |
| | | | 9፡37 | |
| | | | 9፡37 | |
| | | | 9፡39 | |
| 9፡40-41 | | | 9፡40 | 9፡40-41 |
| | | | 9፡41 | |

## ሦስተኛ የምንባብ ዑደት (ገጽ 5ን ይመልከቱ፡፡)

*በአንቀጽ በመከፋፈል የጸሐፊውን ዋና ሃሳብ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ማብራሪያ ነው፤ ይህ ማለት ስለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን ባገኘነው ብርሃን መመላለስ አለብን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን በመተርጎም ረገድ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ እና መንፈስ ቅዱስ ቀዳሚዎች ናችሁ፡፡ ለሌላ ተንታኝ/ሐተታ አቅራቢ ብቻ መተው የለብህም፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ዋናውን ሃሳብ ለይ፡፡ የራስህን የዋና ሃሳብ አከፋፈል ከአምስቱ ዘመናዊ ትርጉሞች ጋር አነጻጽር፡፡ በአንቀጽ መከፋፈሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት ውጤት ባይሆንም፣ የጸሐፊውን ዋና ሃሳብ ለመከተል ግን ቁልፍ ጉዳይ ነው፣ ይህም የአተረጓጎም ዋና መሠረት ነው፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ የሚያወራው አንድ እና አንድ ሃሳብ ነው፡፡

1. አንደኛ አንቀጽ
2. ሁለተኛ አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወ.ዘ.ተ.

## ከቁ.1-41 ላሉት አውዳዊ እይታዎች

ሀ. በኢየሱስ አገልግሎት የሚደጋገም ተአምር የሆነው የእውሩ መፈወስ በልዩ ልዩ ቴክኒክስ የተደረገ አስደናቂ ነገር ነው፡፡

ለ. የአውሩ መፈወስ መሲሃዊ ምልክት ነበር (ኢሳ.29፡18፤35፡5፤42፡7፤ማቴ.11፡5)፡፡ የዚህ ፈውስ ጠቀሜታ ኢየሱስ የዓለም ብርሃን መሆኑን ባሳየበት ንግግሮቹ የቅርብ አውድ ውስጥ ይታያል፡፡ አይሁድ ምልክት ይፈልጋሉ፤ ብዙ ምልክቶች አይተዋል! ያህዌ ብቻ አይንን መክፈት ይችላል፡፡

ሐ. ይህ ምዕራፍ የሰውየው ከአካላዊ እውርነቱ ነፃ የወጣበት ድርጊት እና የፈሪሳውያን መንፈሳዊ እውርነት ምሳሌ ነው (ቁ.39-41፤ማቴ.6፡23)፡፡

## የቃል እና የሐረግ ጥናት

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 9÷1-12
**1ሲያልፍም ከመወለዱ ጀምሮ ዕውር የሆነውን ሰው አየ፡፡ 2ደቀ መዛሙርቱም፡፡ መምህር ሆይ፥ ይህ ሰው ዕውር ሆኖ**
**እንዲወለድ ኃጢአት የሠራ ማን ነው? እርሱ ወይስ ወላጆቹ? ብለው ጠየቁት፡፡ 3ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰ፡፡**

የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ እንዲገለጥ ነው እንጂ እርሱ ወይም ወላጆቹ ኃጢአት አልሠሩም፡፡ [4]ቀን ሳለ የላከኝን ሥራ ላደርግ ይገባኛል፤ ማንም ሊሠራ የማይችልባት ሌሊት ትመጣለች፡፡ [5]በዓለም ሳለሁ የዓለም ብርሃን ነኝ፡፡ [6]ይህን ብሎ ወደ መሬት እንትፍ አለ በምራቁም ጭቃ አድርጎ በጭቃው የዕውሩን ዓይኖች ቀባና፡፡ [7]ሂድና በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብ አለው፤ ትርጓሜው የተላከ ነው፡፡ ስለዚህ ሄዶ ታጠበ እያየም መጣ፡፡ [8]ጎረቤቶቹም ቀድሞም ሲለምን አይተውት የነበሩ፡፡ ይህ ተቀምጦ ይለምን የነበረ አይደለምን? አሉ፡፡ [9]ሌሎች፡፡ እርሱ ነው አሉ፤ ሌሎች፡፡ አይደለም እርሱን ይመስላል እንጂ አሉ፤ እርሱ፡፡ እኔ ነኝ አለ፡፡ [10]ታድያ፡፡ ዓይኖችህ እንዴት ተከፈቱ? አሉት፡፡ [11]እርሱ መልሶ፦ ኢየሱስ የሚባለው ሰው ጭቃ አድርጎ አይኖቼን ቀባና፡፡ ወደ ሰሊሆም መጠመቂያ ሄደህ ታጠብ አለኝ፤ ሄጄ ታጥቤም አየሁ አለ፡፡ [12]ያ ሰው ወዴት ነው? አሉት፡፡ አላውቅም አለ፡፡

9:1 **"ከመወለዱ ጀምሮ እውር"** ለዚህ ዓይነቱ መዳን ይህ ብቸኛ ምሳሌ ነው፡፡ ለማጭበርበር እድል አልነበረም፡፡

9:2 **"ደቀ መዛሙርቱም"** ከምዕራፍ 6 በኂላ ይህ የመጀመሪያ ጊዜ ነው ደቀ መዛሙርቱ ሲጠቀሱ፡፡ ይህም (1) የአይሁዳውያን ደቀ መዛሙርት በ7፡3 ላይ ስለተጠቀሰ ወይም (2) አሥራ ሁለቱን ሊያመለክት ይችላል፡፡

▣ **"መምህር ሆይ: ይህ ሰው ዕውር ሆኖ እንዲወለድ ኃጢአት የሠራ ማን ነው? እርሱ ወይስ ወላጆቹ?"** ይህ ጥያቄ ብዙ ሥነ መለኮታዊ ክርክርን አስነስቷል፡፡ ሆኖም ከምስራቃውያን ኃይማኖት ሳይሆን ከጥንት አይሁድ አስተሳሰብ/እምነት/የአኗኗር ዘይቤ አንፃር መተርጎም ይገባናል፡፡ በዚህም መሰረት በተለያዩ መንገዶች ሊተረጎም ይችላል፡፡

1. ይህ ከዘፍጥረት 25:22 የተነሳ ረቢዎች እንደሚገምቱት ከመወለድ በፊት የነበረ ኃጢአትን ሊገልጽ ይችላል፡፡
2. ይህ የወላጆቹ ወይም የቀድም አያቶቹ ኃጢአት ባልተወለደው ልጅ ላይ የነበረውን ትጽእኖ ይገልጻል፡፡
3. ይህ በረቢያዊ የኃይማኖት ትምህርት የተለመደ የነበረውን በኃጢአት እና በጨለማ መካከል ያለውን ግንኙነት ይገልጻል፡፡

ይህ ከምስራቃውያን ከዑደታዊው የእንደገና ሥጋ መልበስ ወይም የወደፊቱን ሁኔታ ከሚወስነው ትምህርት ጋር ምንም የሚያገናኘው ነገር የለም፡፡ ይህ የአይሁድ መነሻ ነው፡፡ በJames W.Sire's Scripture TwistiNg, pp.127-144 ላይ ይህ ጉዳይ በጥሩ ሁኔታ ስለተብራራ ይመልከቱ፡፡ት፡፡

9:3 ይህ ክፍል ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ በቁ.2 ላይ ለጠየቁት ጥያቄ የሰጠው መልስ ነው፡፡ ብዙ እውነቶች ተንጸባርቀዋል፡- (1) ኃጢአት እና ጨለማ በራሳቸው የሚገናኙ አይደሉም፤ (2) ችግሮች ሁል ጊዜ ለእግዚአብሔር ባርኮት ዕድልን ይሠጣሉ፡፡

9:4 **"እኛ……እኔ"** እነዚህ ተውላጠ ሥሞች የማይስማሙ መሆናቸው ግልጽ ነው፡፡ ብዙ የግሪክ ቅጂዎች ሰዋስዋዊ ስሙም እንዲሆን ለማድረግ አንደኛውን ወይ ሁለተኛውን ለውጠውታል፡፡ ኢየሱስ የዓለም ብርሃን ነው (እኛም በዘመናችን ይህንን ብርሃን ልናጸባርቅ ይገባል (ማቴ.5:14)) የሚለውን ሥነ መለኮታዊ አቋም የሚያንጸባርቁ ይመስላሉ፡፡

1. **"ሌሊት ትመጣለች"** ከቁ.5 ጋር ሲነጻጸር ግልጽ ተለዋጭ ዘይቤ መሆኑን ያሳያል፡፡ ሌሊት የሚለው ቃል
2. የሚመጣውን ፍርድ
3. የዕድሎች ዘመን መዘጋት/ማክተም
4. የኢየሱስ መከራ መቀበል እና መሰቀልን ሊወክል ይችላል፡፡

9:5 **"በዓለም ሳለሁ"** ይህ ኢየሱስ ሥጋ ለብሶ የተመላለሰበትን/ተሰግዎ/ ዘመን ማለትም ከቤተልሄም እስከ ጎልጎታ/የደብረ ዘይት ተራራዎች ያለውን ጊዜ የሚያመለክት ይመስላል፡፡ ኢየሱስ በዚህ ዓለም የነበረው ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ነበር፡፡ አድማጮቹ ለጥሪው መልስ መስጠት ያለባቸው አሁን ነው፡፡ ይህ ሐረግ በሥነ መለኮት አስተምህሮው ከቁ.4 ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

በእንደዚህ ያለ አውድ ውስጥ ይህን ያህል "እኔ" ሲያይ አንባቢ ሊደነቅ ይችላል!

▣ **"የዓለም ብርሃን ነኝ"** ዮሐንስ ሁልጊዜ "ብርሃን" እና "ጨለማ" የሚሉት ቃላት መንፈሳዊ እውነታዎችን ለመግለጽ በተለዋጭ ዘይቤነት ይጠቀማል፡፡ ኢየሱስ እንደ "ዓለም ብርሃን" (1:4-5፣8-9፤3:17-21፤8:12:9:5፤12:46) በብ.ኪ. ያሉትን መሲሃዊ ምንባቦች (ኢሳ.42:6፤49:6፤51:4፤601፣3) ለያመለክት ይችላል፡፡ በ8:12 ላይ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ፡፡

9:6 **"በምራቁም ጭቃ አድርጎ"** ምራቅ በአይሁዳውያን ዘንድ በየቤቱ ለመፈወሻነት የሚጠቀሙበት ነበር፡፡ በሰንበት ቀን መጠቀም ክልክል ነበር (ቁ.14)፡፡ ወንጌላት ኢየሱስ ምራቁን የተጠቀመባቸውን ሦስት ምሳሌዎች ዘግበዋል (ማር.7፡33፤8፡23፤ እና በዚህ ቦታ)፡፡ ይህንን ተቀባይነት ያለው፣ የሚጠበቅ የፈውስ ዘዴ በመጠቀም ኢየሱስ በአካል ተገኝቶ የዚህን ሰው እምነት አበረታቶአል፤ ነገር ግን ደግሞ የፈሪሳውያንን ወግ እና ልማድ ሆን ብሎ ይገዳደር ነበር!

9:7 **"በሰሊሆም መጠመቂያ"** ሰሎሜ ማለት "የተላከ" ነው። ይህ መጠመቂያ በዳስ በዓል ጊዜ ለሚፈጸም ሥነ ሥርዓት አገልግሎት ይውል ነበር።

▣ **"ትርጓሜውም የተላከ ነው"** "የተላከ" የሚለው ቃል ከኢየሩሳሌም ከተማ የግምብ አጥር ውጪ ከሚገኘው ከግዮን ምንጮች በቧንቧ የሚመጣ የመጠመቂያ ውኃ ከመሆኑ እውነታ ጋር የተያያዘ ነበር። ረቢዎች "የተላከ" የሚለውን ቃል ስለመሲሁ መላክ ከሚያበስሩት ጋር አያይዘውታል። ይህ ሌላው የጸሐፊው ኤዲቶሪያል አስተያየት ነው።

▣ **"ታጠበ"** ይህ እምነቱን በሥራ ያሳየበት ነው። ለኢየሱስ ቃሎች ታዘዘ! ሆኖም ይህ ገና "የሚያድን እምነት" አይደለም (ቁ.11፣17፣36፣38)። ይህ በሂደት ውስጥ የሆነ እምነት ነበር። ከሁሉም ወንጌሎች ይልቅ ዮሐንስ የእምነት "ደረጃዎችን" ይገልጣል። ምዕራፍ 8 "ያመነ" ቡድንን ያሳያል፣ ነገር ግን ለመዳን/ድነት የሆነው እምነት አይደለም (ማቴ.4፤ማር.13፤ የዘሪው ምሳሌ)።

---

**ልዩ ርዕስ፡ መዳንን ለመግለጽ እጥቅም ላይ የዋሉ የግሪክ ግሦች**

*መዳን የሥራ ውጤት አይደለም፤ የግንኙነት እንጂ። አንድ ሰው በክርስቶስ ሲያምን መዳኑ ተፈጸመ ማለት አይደለም፤ ጅምር ብቻ ነው! ይህ የእሳት አደጋ ዋስትና ፖሊሲ፣ ወይም ወደ ሰማይ መግቢያ ቲኬት አይደለም፤ ነገር ግን ክርስቶስን ወደ መምሰል የሚያድግ ሕይወት ነው። በአሜሪካ አንድ ምሳሌያዊ አነጋገር አለን፤ እንዲህ የሚል፣ ጥንዶች ለረዥም ጊዜ አብረው በኖሩ ቁጥር፣ አንድ የመሆናቸው ጅማሬ ይበዛል። ይህ የመዳን ግብ ነው።*

***መዳን እንደ ተፈጸመ ድርጊት*** (AORIST)

- የሐዋ.15÷11
- ሮሜ 8÷24
- 2ኛ ጢሞ.1÷9
- ቲቶ 3÷5
- ሮሜ 13÷11 (የተፈጸመ ድርጊትን ከወደፊት ዝንባሌ ጋር ያያይዛል)

***መዳን እንደ ሕያዋን ሁኔታ*** (PERFECT)

- ኤፌ. 2÷5፣8

***መዳን እንደ አሁን ሁኔታ*** (PRESEՃT)

- 1ኛ ቆሮንቶስ 1፡18፤ 15፡2
- 2ኛ ቆሮንቶስ 2፡15
- 1ኛ ጴጥሮስ 3፡21

***መዳን ወደፊት የሚቀርን ጊዜ በአርኪ ሁኔታ እንደ መጨረስ*** (Future iՃ VERB TEՃSE or coՃtext)

- ሮሜ 5÷9፣10፤10÷9፣13
- 1ኛ ቆሮ.3÷15፤5÷5
- ፊልጵ.1÷28
- 1ኛ ተሰ.5÷8-9
- ዕብ.1÷14፤9÷28
- 1ኛ ጴጥ.1÷5፣9

ስለዚህ *መዳን ለመጀመሪያ ጊዜ በሚደረግ የእምነት ውሳኔ ይጀመራል* (ዮሐ.1÷12፤3÷16፤ሮሜ 10፡9-13)፣ *ሆኖም ይህ በሂደት በኑሮ መውጣት አለበት* (ሮሜ 8÷29፤ገላ.3÷19፤ኤፌ.1÷4፤2÷10)፣ *ይህም አንድ ቀን ያበቃና የሚታይ ይሆናል* (1ኛ ዮሐ.3÷2)። ይህ የመጨረሻ ሁኔታ መክበር ተብሎ ይጠራል። ይህ

1. *የመጀመሪያ መክበር-መጽደቅ* (ከኃጢአት ቅጣት *መዳን*)
2. *አዳኚ መዳን-መቀደስ* (ከኃጢአት *ኃይል መዳን*)
3. *የመጨረሻው መዳን-መክበር* (ከኃጢአት ህልውና *መዳን*)

---

9:8 **"ጎረቤቶቹም"** በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተጠቀሱ ስለዚህ ተአምር የሚመሰክሩ ሦስት ቡድኖች አሉ፡ (1) ጎረቤቶቹ፤ (2) ሰውዬው ራሱ (ቁ.18) ፤ እና ቤተሰቦቹ (ቁ.18) ። ልክ በፈሪሳውያን መካከል እንደነበረው በጎረቤቶቹ መካከል ይህንን ፈውስ በተመለከተ አለመስማማት አለ።

▣ **"ይህ ተቀምጦ ይለምን የነበረ አይደለምን?"** ይህ የግሪክ ጥያቄ "አዎ" የሚል መልስን ይጠብቃል።

9:9 **"እኔ ነኝ"** ይህ ኢየሱስ በ4፡26፤6፡20፤8፡24፣28፣58፤13፡19፤18፡5፣6፣8 ላይ ለራሱ የሚጠቀመው የግሪክ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ይህ ዓይነቱ አነጋገር በራሱ መለኮታዊ አንደምታ እንደማይሰጥ አውዱ ያሳያል። ‹*ኩሪዮስ* (*kurios*) የሚለው ቃል አጠቃቀም በዚህ ምዕራፍ ቁጥር 36 (ጌታ ሆይ) እና ቁጥር 38 (ጌታ ሆይ) ላይ ተመሳሳይ ግልጽ ያለመሆን ችግር አለ።

9:11-12 ይህ ንግግር የሚያሳየው የዚህ ሰው ፈውስ ወዲያውኑ የሆኑ መንፈሳዊ መዳንን እንዳላካተተ ነው። የዚህ ሰው እምነት ያደገው ከኢየሱስ ጋር በነበረው ቀጣይ ግንኙነት ነው (ቁ.35)።

> NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 9፥13-17
> **[13]በፊት ዕውር የነበረውን ሰው ወደ ፈሪሳውያን ወሰዱት። [14]ኢየሱስም ጭቃ አድርጎ ዓይኖቹን የከፈተበት ቀን ሰንበት ነበረ። [15]ስለዚህ ፈሪሳውያን ደግሞ እንዴት እንዳየ እንደ ገና ጠየቁት። እርሱም፦ ጭቃ በዓይኖቼ አኖረ ታጠብሁም አያለሁም አላቸው። [16]ከፈሪሳውያንም አንዳንዶቹ። ይህ ሰው ሰንበትን አያከብርምና ከእግዚአብሔር አይደለም አሉ። ሌሎች ግን። ኃጢአተኛ ሰው እንደነዚህ ያሉ ምልክቶች ሊያደርግ እንዴት ይችላል? አሉ። [17]በመካከላቸውም መለያየት ሆነ። ከዚህም የተነሣ ዕውሩን። አንተ ዓይኖችህን ስለ ከፈተ ስለ እርሱ ምን ትላለህ? ደግሞ አሉት። እርሱም፦ ነቢይ ነው አለ።**

9:13 "ወሰዱት" ይህ ጎረቤቶቹን የሚያመለክት መሆን አለበት።

▣ "ፈሪሳውያን" የአይሁዳውያን መሪዎች በዮሐንስ ውስጥ በሁለት የተለያዩ ቃሎች ተገልጸዋል። "አይሁድ" የተለመደ መጠሪያቸው ነው (ቁ.18፣22)። ሆኖም በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ፈሪሳውያን ተብለው ተጠርተዋል (ቁ.13፣15፣16፣ እና 40። በ1:24 ላይ ያለው ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።

9:14 " ኢየሱስም ጭቃ አድርጎ ዓይኖቹን የከፈተበት ቀን ሰንበት ነበረ" የአይሁድ መሪዎች ልማዳዊ ደንብ (ታልሙድ በተባለው መጽሐፋቸው በጽሑፍ የሰፈረው ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ልማድ) በዚህ ሰው ፍላጎት ላይ ቅድሚያውን ወስዶአል (5:9፤9:16፤ማቴ.23:24)። ይህ ክፍል በአብዛኛው ኢየሱስ ከእነዚህ መሪዎች ጋር ኃይማኖታዊ ነግግርን ለማድረግ በማሰብ ሆን ብሎ ለሰበብ በሰንበት እንደፈወሰ የሚያሳይ ነው። በ5:9 ላይ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ።

9:16 ፈሪሳውያን በኢየሱስ ላይ ለመፍረድ ዘዳ.13:1-5 ያለውን መሠረት አድርገዋል።

▣ "በመካከላቸውም መለያየት ሆነ" ሁልጊዜ በኢየሱስ ምክንያት የዚህ ዓይነቱ መከፋፈል ይፈጠራል (6:52፤7:43፤10:19፤ማቴ.10:34-39)።

9:17 "ነብይ ነው" ይህ ምዕራፍ የዚህን ሰው እምነት ማደግ ያሳያል (ቁ.36፤38)። "ነብይ" ለሚለው በ4፡19 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።

> NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 9፥18-23
> **[18]አይሁድ የዚያን ያየውን ወላጆች እስኪጠሩ ድረስ ዕውር እንደ ነበረ እንዳየም ስለ እርሱ አላመኑም፥ [19]እነርሱንም። እናንተ ዕውር ሆኖ ተወለደ የምትሉት ልጃችሁ ይህ ነውን? ታድያ አሁን እንዴት ያያል? ብለው ጠየቁአቸው። [20]ወላጆቹም መልሰው። ይህ ልጃችን እንደ ሆነ ዕውርም ሆኖ እንደ ተወለደ እናውቃለን፤ [21]ዳሩ ግን አሁን እንዴት እንዳየ አናውቅም፥ ወይም ዓይኖቹን ማን እንደ ከፈተ እኛ አናውቅም፤ ጠይቁት እርሱ ሙሉ ሰው ነው፤ እርሱ ስለ ራሱ ይናገራል አሉ። [22]ወላጆቹ አይሁድን ስለ ፈሩ ይህን አሉ፤ እርሱ ክርስቶስ ነው ብሎ የሚመሰክር ቢኖር ከምኵራብ እንዲያወጡት አይሁድ ከዚህ በፊት ተስማምተው ነበርና። [23]ስለዚህ ወላጆቹ። ሙሉ ሰው ነው፥ ጠይቁት አሉ።**

9:22-23 "እርሱ ክርስቶስ ነው ብሎ የሚመሰክር ቢኖር" ይህ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ሲሆን ድርጊትን ለመፈጸም ዕድል መኖሩን ያመለክታል። ወላጆቹ እነዚህን አይሁዳዊ መሪዎችን ይፈሩ ነበር። ለዚህ ፈውስ ዋጋ የሰጡ ብዙ ምስክሮች ነበሩ፡ (1) ጎረቤቶቹ (ቁ.8-10)፤ (2) የተፈወሰው ሰው ራሱ (ቁ.11-17፣24-33)፤ እና ወላጆቹ (ቁ.18-23)።

> **ልዩ ርዕስ፡- የእምነት ቃል**
>
> ሀ. የእምነት ቃልን ወይም መግለጽን ለማመልከት ‹ሆሞሌጌዎ› (*homolegeo*) እና ‹ኤክሶሞሎጌ› (*exomologe*) የተባሉ ሁለት መልኮች ያሉት የግሪክ ሥርወ ቃል አለ። ያዕቆብ የተጠቀመው ጥምር ቃል ‹ሆሞ› (*homo*)፣ተመሳሳይ፤ ‹ሌጎ› (*lego*) ለመናገር፤ እና ‹ኤክስ› (*ex*) ውጪ/መውጣት ነው። መሠረታዊ ትርጉሙ ተመሣሣይ ነገሮችን መናገር፣ ለመስማማት ነው። በአደባባይ ነግግር ጊዜ ‹ኤክስ› (*ex*) ይጨመራል።
>
> ለ. የዚህ ቃል ስብስብ እንግሊዝኛ ትርጉሞች
> 1. ምስጋና
> 2. መስማማት

3. መናገር
4. መግለጽ
5. መመስከር

ሐ. የቃሉ ስብስብ ሁለት የሚካረኑ የሚመስሉ አጠቃቀሞች አሉት

1. ማመስገን (እግዚአብሔር)
2. ኃጢአትን ማመን

እነዚህ ነገሮች ምናልባት ሰዎች የእግዚአብሔር ቅድስና ኃጢአት አልባነት ከመረዳታቸው የተነሳ የኀለበተ ነው። አንዱን እውነት መመስከር ሁለቱንም መመስከር ነው።

መ. የቃሉ ስብስብ የአ.ኪ. አጠቃቀሞች

1. ቃል መግባት (ማቴ.14÷7፤የሐዋ.7÷17)
2. መስማማት ወይም ከአንድ ነገር ጋር መስማማት (ዮሐ.1÷20፤ሉቃ.22÷6፤የሐዋ.24÷14፤ዕብ.11÷13)
3. ማመስገን (ማቴ.11÷25፤ሉቃ.10÷21፤ሮሜ 14÷11፤15÷9)
4. መስማማት
   ሀ. ከሰው (ማቴ.10÷32፤ሉቃ.12÷8፤ዮሐ.9÷22፤ 12÷42፤ሮሜ. 10÷9፡ፊልጵ.2÷11፤1ኛ ዮሐ.2÷23፤ራዕ.3÷5)
   ለ. ከእውነት (የሐዋ 23÷8፤2ኛ ቆሮ.11÷13፤1ኛ ዮሐ.4÷2)
5. እምነትን በአደባባይ መግለጥ (እምነትን በመግለጥ ሥርዓት ውስጥ የሕገኛነት ዝንባሌ እያደገ መጣ የሐዋ.24÷14፤1ኛ ጢሞ.6÷13)
   ሀ. ስህተትን ሳይምኑ (1ኛ ጢሞ.6÷12፤ዕብ.10÷23)
   ለ. ስህተትን በማመን (ማቴ.3÷6፤የሐዋ.19÷18፤ዕብ.4÷14፤ያዕ.5÷16፤1ኛ ዮሐ.1÷9)

9:22 **"ከምኩራብ እንዲያወጡት"** ይህ ክፍል በግልጽ እንደሚናገረው ወላጆቹ ከምኩራብ እንዳይገለሉ ፈርተው ነበር (12:42፤16:2)። ይህ አኪያሂድ ምናልባት በዕዝራ 10:8 ላይ መሠረት ይሆናል፡፡ ከረቢያዊ ሥነ ጽሑፍ እንደምንረዳው ሦስት ዓይነት መገለሎች ነበሩ፡- (1) ለአንድ ሳምንት፤ (2) ለወር፤ ወይም (3) ለሕይወት ዘመን።

በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት መገባደጃ ጽሑፉን የጻፈው ዮሐንስ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ መመስከር ከምኩራብ እንደሚያስገልል በሚገባ ያውቅ ነበር። እነዚህ ታሪካዊ "የእርግማን ቀመሮች" ከ70 ዓ.ም. የአይሁድ ከጃምኒያ (JamNia) ማንሰራራት በኋላ በፈሪሳውያን የዳበሩ ነበሩ።

▣ **"ከምኩራብ ወጪ እንዲሆን ይገደድ ነበር"** ይህ ጠንካራ የሆነ ኅብረትን የማጥፋት ሂደት ነበር (12:42፤16:2)።

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 9÷24-34

**[24]ስለዚህ ዕውር የነበረውን ሰው ሁለተኛ ጠርተው። እግዚአብሔርን አክብር፤ ይህ ሰው ኃጢአተኛ መሆኑን እኛ እናውቃለን አሉት። [25]እርሱም መልሶ፦ ኃጢአተኛ መሆኑን አላውቅም፤ ዕውር እንደ ነበርሁ አሁንም እንዳይ ይህን አንድ ነገር አውቃለሁ አለ። [26]ደግመውም። ምን አደረገልህ? እንዴትስ ዓይኖችህን ከፈተ? አሉት። [27]እርሱም መልሶ፦ አስቀድሜ ነገርኋችሁ አልሰማችሁምም፤ ስለ ምን ዳግመኛ ልትሰሙ ትወዳላችሁ? እናንተ ደግሞ ደቀ መዛሙርቱ ልትሆኑ ትወዳላችሁን? አላቸው። ተሳድበውም። [28]አንተ የእርሱ ደቀ መዝሙር ነህ፥ እኛ ግን የሙሴ ደቀ መዛሙርት ነን፤ [29]እግዚአብሔር ሙሴን እንደ ተናገረው እኛ እናውቃለን፥ ይህ ሰው ግን ከወዴት እንደ ሆነ አናውቅም አሉት። [30]ሰውዬው መለሰ እንዲህም አላቸው፦ ከወዴት እንደ ሆነ እናንተ አለማወቃችሁ ይህ ድንቅ ነገር ነው፥ ዳሩ ግን ዓይኖቼን ከፈተ። [31]እግዚአብሔርን የሚፈራ ፈቃዱንም የሚያደርግ ቢኖር ያንን እግዚአብሔር ይሰማዋል እንጂ ኃጢአተኞችን እንዳይሰማ እናውቃለን። [32]ዕውር ሆኖ የተወለደውን ዓይኖች ማንም እንደ ከፈተ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ አልተሰማም፤ [33]ይህ ሰው ከእግዚአብሔር ባይሆን ምንም ሊያደርግ ባልቻለም ነበር። [34]መልሰው። አንተ ሁለንተናህ በኃጢአት ተወለድህ፥ አንተም እኛን ታስተምረናለህን? አሉት። ወደ ውጭም አወጡት።**

9:24 **"እግዚአብሔርን አክብር"** ይህ እውነተኛነትን ለማረጋገጥ መሃላ ያለበት ቀመር ነበር (ኢያሱ 7:19)።

9:25 ይህ መልስ ቁ.16ን የሚመለከት መሆን አለበት። ሰውዬው ኃይማኖታዊ ሙግት ማድረግ አይፈልግም፤ ነገር ግን እርሱ ከኢየሱስ ጋር የመገናኘቱን ውጤት አጠንክሮ ይናገራል።

9:27 **"እናንተ ደግሞ ደቀ መዛሙርቱ ልትሆኑ ትፈልጋላችሁን?"** የግሪክ ሰዋስዋዊ ሥርዓት "አይ" የሚል መልስን ይጠብቃል፤ ነገር ግን የተጠየቀው ጥይቁ ኃይለኛ ምፀታዊ እና የዚህን እውር ለማኝ ምስክርነት የሚያሳይ ነበር።

**9:28ሀ "አንተ የእርሱ ደቀ መዝሙር ነህ"** በዚህ ምዕራፍ ይህ ሰው እንዴት አማኝ እንደሆን እውነተኛ ጥያቄ አለ፡፡ በመጀመሪያ የኢየሱስ ፈውስ ከዚህ ሰው ኢየሱስን እንደ መሲህ ከማመኑ ጋር ቁርኝት ያለው አይመስልም፡፡ በኋል ግን ኢየሱስ ይህንን ሰው ተገናኝቶት መሲሃዊ ንግግር ተናግሮታል (ቁ.36-38)፡፡ አካላዊ ፈውስ የግድ መዳንን እንደማያመጣ ይህ ምዕራፍ ያሳይል፡፡

**9:28ለ-29** ይህ ክፍል የኃይማኖት መሪዎች የተጋፈጡትን ችግር ያሳያል፡፡ ከሙሴ ቀስቃሽ ራዕይ ጋር ትውፊታቸውን በማብራራት ዝርዝሩን እኩል ለማየት ሞክረዋል፡፡ አይኖቻቸው በጥላቻ በተሞላ በኃይማኖታዊ ትምህርታቸው ታውሮ ነበር (ማቴ.6:23)፡፡ እነርሱ የሰዎች ልማድ ደቀ መዛሙርት ነበሩ (ኢሳ.29:13)፡፡

**9:29 "ይህ ሰው ግን ከየት እንደሆነ አናውቅም"** ይህ የዮሐንስ ምጸት ሌላው ምሳሌ ነው (7:27-28፤8:14)፡፡ ኢየሱስ የመጣው ከአብ ዘንድ ነበር (8:42፤15:3፤16:28) ነገር ግን በእውርነታቸው ምክንያት ደቀ መዛሙርቱ

1. መነሻውን
2. የተወለደበትን ቦታ አላወቁም ነበር፡፡

**9:30 "ከወዴት እንደ ሆነ እናንተ አለማወቃችሁ ይህ ድንቅ ነገር ነው: ዳሩ ግን ዓይኖቼን ከፈተ"** ይህ የፈሪሳውያንን ክርክር የሚያፈርሰው የዚህ እውር ለማኝ ኃይለኛ ምስክርነት እና የሚመታ ምጸት ሌላው ምሳሌ ነው፡፡

**9:31-33** ይህ ያልተማረ እውር ሰው ከኃይማኖት መሪዎች ይልቅ የተሻለ፣ ወጥ የሆነ ሥነ መለኮት ነበረው፡፡

**9:33 "ባ…."** ይህ ሁለተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ሲሆን "የእውነታ ተቃራኒ" በመባል ይታወቃል፡፡ "ይህ ሰው ከእግዚአብሔር ዘንድ ባይመጣ ኖሮ (ከእግዚአብሔር ዘንድ መጥቷል) እንደዚህ ያለ ነገር ለማድረግ አይችልም ነበር (ነገር ግን ችሎአል)፡፡"

**9:34 "አንተ ሁለንተናህ በኃጢአት ተወለድህ"** የረቢያዊው የአይሁድ ሥርዓት "የውርስ ኃጢአት" የሚል ሃሳብ እንደሌለው ማስታወስ አስፈላጊ ነው (ኢዮ.14:1፣4፡ መዝ.51:5)፡፡ የዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ውድቀት በረቢያዊው የአይሁድ ሥርዓት ውስጥ ምንም ትኩረት አይሰጠውም፡፡ አይሁድ በአንክሮ የሚናገሩት በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ ጥሩ እና መጥፎ አሳብ ‹*የትዘር*› (*yetzer*) መኖሩን ነው፡፡ እነዚህ ፈሪሳውያን በአጽንኦት የሚናገሩት ይህ የተፈወሰው ሰው ምስክርነት እና አስተሳሰብ ዋጋ የሌላቸው እንደሆኑ ነው፤ ምክንያቱም በግልጽ እንደሚታወቀው ኃጢአተኛ ለመሆኑ ማስረጃው እውር ሆኖ በመወለዱ ነው፡፡

▣ **"ወደ ውጭም አወጡት"** ይህ በቀጥተኛ ትርጉም "ወደ ውጭ አውጥተው ጣሉት" ነው፡፡ ማነጻጸሪያው (1) አባልነት እና ተሳትፎ በአጥቢያ ምኩራብ ወይም (2) ከስብሰባው መወገድ ነው፡፡ ቁ.2 ለአውዱ እጅግ በጣም የሚስማማ ይመስላል፡፡

**NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 9:35-41**
**[35]ኢየሱስም ወደ ውጭ እንዳወጡት ሰማ ሲያገኘውም፡፡ አንተ በእግዚአብሔር ልጅ ታምናለህን? አለው፡፡ [36]እርሱም መልሶ፦ ጌታ ሆይ፥ በእርሱ አምን ዘንድ ማን ነው? አለ፡፡ [37]ኢየሱስም፦ አይተኸዋልም ከአንተ ጋርም የሚናገረው እርሱ ነው አለው፡፡ [38]እርሱም፦ ጌታ ሆይ፥ አምናለሁ አለ፤ ሰገደለትም፡፡ [39]ኢየሱስም፦ የማያዩ እንዲያዩ የሚያዩም እንዲታወሩ እኔ ወደዚህ ዓለም ለፍርድ መጣሁ አለ፡፡ [40]ከፈሪሳውያንም ከእርሱ ጋር የነበሩት ይህን ሰምተው፡፡ እኛ ደግሞ ዕውሮች ነንን? አሉት፡፡ [41]ኢየሱስም አላቸው፡፡ ዕውሮችስ ብትሆኑ ኃጢአት ባልሆነባችሁም ነበር፤ አሁን ግን፡፡ እናያለን ትላላችሁ፤ ኃጢአታችሁ ይኖራል፡፡**

9:35
NASB,NRSV,
TEV,NJB **"አንተ በእግዚአብሔር ልጅ ታምናለህን?"**
NKNV **"አንተ በእግዚአብሔር ልጅ ታምናለህን?"**

A እና L የተሰኙት በጥንት ግሪክ የፊደል አጣጣል የተጻፉት ቅጂዎች "የእግዚአብሔር ልጅ" ሲሉ፣ $P^{66}$, $P^{75}$, N, B, D, እና W ደግሞ "የሰው ልጅ" ይላሉ፡፡ ከዮሐንስ አጠቃቀም እና ከጽሑፉ እንደሚገኘው አስረጂ "የሰው ልጅ" የሚለው አጠቃቀም በጣም የተሻለ እና ምናልባትም የመጀመሪያው ነው፡፡ UBS[4] በ "A" ደረጃ "ሰው" ይላል (የተረጋገጠ)፡፡ የጥያቄው ሰዋስዋዊ አወቃቀር "አዎ" የሚል መልስን ይጠብቃል፡፡

9:36
NASB, NKJV, **"ጌታ"**
NRSV, TEV,
NJB **"ጌታ"**

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ይህ ሰው የኢየሱስን ጥሪ ሰምቶ ሲሄድ የሰውዬውን የእምነት ሥነ መለኮታዊ ዕድገት ለመመልከት እንችላለን፡፡

1. ሰውዬው (ቁ.11)
2. ወደ ነብዩ (ቁ.17)
3. "ጌታ" "Sir" የሚል የክብር ማዕረግ ወደ አለው (ቁ.36)
4. ወደ "ጌታ" "Lord" የተሟላ ሥነ መለኮታዊ አጠቃቀም ያለው ቃል (ቁ.38)፡፡

በቁ.36 እና 38 ላይ ያለው የግሪክ ቃል ተመሳሳይ ነው፡፡ ፍቺውን አውድ ብቻ ሊወስ ይችላል፡፡ የአምላክ ስሞችን በሚመለከት በ6፡20 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

9፡38 የተፈወሰውን ሰው መዳን በሚመለከት ይህ የታሪኩ መጨረሻ ነው፡፡ ይህ ጥቅስ በጥቂት የጥንት ግሪክ ቅጂዎች (P[75], N, W) እና በ‹ዲያትሳሮን/DiatessaroN› (አራቱን ወንጌሎች በአንድነት የያዘ የጥንት ቅጂ) ውስጥ አለመኖሩ አስገራሚ ነው፡፡ ሁለት ቃሎችን አልፎ አልፎ ተጠቅሞባቸዋል፡- (1) በ1፡23 እና እዚህጋ ብቻ የሚገኘው "እርሱም.....አለ" የሚለው ሐረግ እና (2) በዮሐንስ ውስጥ እዚህጋ ብቻ የሚገኘው "ሰገደለት" የሚለው ቃል ናቸው፡፡ ይህ ቃል በአብዛኛው ዘመናዊ ትርጉሞች ውስጥ ተካቷል፡፡

9፡39 **"እኔ ወደዚህ ዓለም ለፍርድ መጣሁ"** ይህ ስለመጨረሻው ጊዜ/ሠዓት (እስከቶሎጂካል) ፍርድ ከሚናገረው ከ5፡22፣27 ጋር የሚመሳሰል ይመስላል፡፡ ሆኖም ይህ ከ3፡17-21 እና 12፡47-48 ጋር የሚጣረስ ይመስላል፡፡ ኢየሱስ የሰው ልጆችን ለማዳን ከመምጣቱ ዓላማ፣ ነገር ግን ሰዎች ይህንን የእርሱን ሥጦታ እምቢ ሲሉ ወዲያውኑ በራሳቸቸው ይፈርዳሉ ከሚለው እውነታ ጋር ሊስማማ ይችላል፡፡

▣ **"የማያዩ እንዲያዩ የሚያዩም እንዲታወሩ"** ይህ በተለይ የኢሳያስ ትንቢት ሁለተኛ ፍጻሜ ነበር፡፡

1. ኩሩዎቹ የእሥራኤል ልጆች የእግዚአብሔርን መልእክት አይረዱም ነበር (ኢሳ.6፡10፤42፡18-19፤43፡8፤ኤር.5፡21፤ሕዝ.12፡2)፡፡
2. ንስሐ የሚገቡ እና ትሁታን ድሆች፣ ከሕብረተሰቡ የተንገዋለሉ፣ አካል ጉዳተኞች ይረዱታል (ኢሳ.29፡18፤32፡3-4፤35፡5፤42፡7፣16)፡፡

ኢየሱስ ማየት ለሚፈልጉ ሁሉ የዓለም ብርሃን ነው (1፡4-5፣8-9)፡፡

9፡40 **"እኛ ደግሞ እውሮች ነንን? አሉት"** በግሪኩ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ያለው የቃላት አወቃቀር "አይ" የሚል መልስን ይጠብቃል (ማቴ.15፡14፤23-24)፡፡ ይህ ምዕራፍ የማይፈወስ (ይቅር የማይባል የአለማመን ኃጢአት፣ በ5፡21 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡) የመንፈሳዊ እውርነት ተምሳሌታዊ ድርጊትን እና ሊፈወስ የሚችለውን አካላዊ እውርነትን ያመለክታል!

9፡41 ይህ ጥቅስ አጠቃላይ የሆነ እውነትን ይገልጻል (15፡22፣24፤ሮሜ.3፡20፤4፡15፤5፡13፤7፡7፣9)፡፡ የሰው ልጆች ለበራላቸው ብርሃን ኃላፊ ወይም የተጋለጡ ናቸው!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት መመሪያ ማብራሪያ ነው፤ ይህ ማለት ስለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን ባገኘነው ብርሃን መመላለስ አለብን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን በመተርጎም ረገድ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ እና መንፈስ ቅዱስ ቀዳሚዎች ነችሁ፡፡ ለሌላ ተንታኝ/ሐተታ አቅራቢ ብቻ መተው የለብህም፡፡

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተነሱት ታላላቅ ጉዳዮች ላይ ታተኩር ዘንድ እንዲረዳህ እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ተሰጥተውሃል፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች ማለት ለላቀ መረዳት አእምሮ ቀስቃሾች እንጂ ማሳረጊያዎች አይደሉም፡፡

1. ይህ ምዕራፍ በቅድሚያ የሚያተኩረው መንፈሳዊ ፈውስ ላይ ነው ወይስ አካላዊ ፈውስ ላይ? አካላዊ እውርነት ወይስ መንፈሳዊ?
2. ይህ ሰው ከመወለዱ በፊት እንዴት ኃጢአት ሊሠራ ይችላል?
3. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በየትኛው ነጥብ ላይ ነው ይህ ሰው መዳንን የተቀበለው?
4. ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም የመጣው በዓለም ላይ ሊፈርድ ነው ወይስ ዓለምን ሊያድን?
5. "የሰው ለጅ" የሚለውን ቃል ታሪካዊ ዳራ ግለጽ፡፡
6. እውሩ ሰው ለአይሁድ መሪዎች በመለሰው መልስ ውስጥ ያሉትን ምጸታዊ ነጥቦች ዘርዝር፡፡

# ዮሐንስ 10

## በዘመናዊ ትርጉሞች የአንቀጽ አከፋፈል

| UBS[4] | NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| የበጎች በረት ምሳሌ | ኢየሱስ እውነተኛው እረኛ | ሕይወቱን የሚሰጥ እረኛ ኢየሱስ | የእረኛው ምሳሌ | ማልካም እረኛ |
| 10፡1-6 | 10፡1-6 | 10፡1-6 | 10፡1-5 | 10፡1-5 |
| | | | 10፡6 | 10፡6 |
| ኢየሱስ መልካም እረኛ | ኢየሱስ መልካም እረኛ | | ኢየሱስ መልካም እረኛ | |
| 10፡7-18 | 10፡7-21 | 10፡7-10 | 10፡7-10 | 10፡7-18 |
| | | 10፡11-18 | 10፡11-16 | |
| | | | 10፡17-18 | |
| 10፡19-21 | | 10፡19-21 | 10፡19-20 | 10፡19-21 |
| | | | 10፡21 | |
| አይሁድ ኢየሱስን ተቃወሙት | እረኛው በጎቹን ያውቃል | | ኢየሱስን ተቃወሙት | ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ብሎ አወጀ |
| 10፡22-30 | 10፡22-30 | 10፡22-30 | 10፡22-24 | 10፡22-30 |
| | ኢየሱስን ለመውገር በድጋሚ ሞከሩ | | 10፡25-30 | |
| 10፡31-39 | 10፡31-39 | 10፡31-39 | 10፡31-32 | 10፡31-38 |
| | | | 10፡33 | |
| | | | 10፡34-38 | |
| | | | 10፡39 | 10፡39 |
| | አማኞች በዮረዳኖስ ማዶ | | | ኢየሱስ ወደ ሌላው የዮርዳኖስ ምድር ሄደ |
| 10፡40-42 | 10፡40፡42 | 10፡40-42 | 10፡40-42 | 10፡40-42 |

***ሦስተኛ የምንባብ ዑደት (ገጽ 5ን ይመልከቱ፡፡)***
***በአንቀጽ በመከፋፈል የጸሐፊውን ዋና ሃሳብ መከተል***

*ይህ የጥናት መመሪያ ማብራሪያ ነው፤ ይህ ማለት ስለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን ባገኘነው ብርሃን መመላለስ አለብን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን በመተርጎም ረገድ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ እና መንፈስ ቅዱስ ቀዳሚዎች ናችሁ፡፡ ለሌላ ተንታኝ/ሐተታ አቅራቢ ብቻ መተው የለብህም፡፡*

*ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ዋናውን ሃሳብ ለይ፡፡ የራስህን የዋና ሃሳብ አከፋፈል ከአምስቱ ዘመናዊ ትርጉሞች ጋር አነጻጽር፡፡ በአንቀጽ መከፋፈሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት ውጤት ባይሆንም፣ የጸሐፊውን ዋና ሃሳብ ለመከተል*

ግን ቁልፍ ጉዳይ ነው፣ ይህም የአተረጓጎም ዋና መሠረት ነው፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ የሚያወራው አንድ እና አንድ ሃሳብ ነው፡፡

1. አንደኛ አንቀጽ
2. ሁለተኛ አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወ.ዘ.ተ.

**የቃል እና የሐረግ ጥናት**

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 10፥1-6
**[1]እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ወደ በጎች በረት በበሩ የማይገባ በሌላ መንገድ ግን የሚወጣ እርሱ ሌባ ወንበዴም ነው፤ [2]በበሩ የሚገባ ግን የበጎች እረኛ ነው፡፡ [3]ለእርሱ በረኛው ይከፍትለታል፤ በጎቹም ድምፁን ይሰሙታል፥ የራሱንም በጎች በየስማቸው ጠርቶ ይወስዳቸዋል፡፡ [4]የራሱንም ሁሉ ካወጣቸው በኋላ በፊታቸው ይሄዳል፥ በጎቹም ድምፁን ያውቃሉና ይከተሉታል፤ [5]ከሌላው ግን ይሸሻሉ እንጂ አይከተሉትም፥ የሌሎችን ድምፅ አያውቁምና፡፡ [6]ኢየሱስ ይህን ምሳሌ ነገራቸው፤ እነርሱ ግን የነገራቸው ምን እንደ ሆነ አላስተዋሉም፡፡**

10:1 **"እውነት፣ እውነት"** በ1፡49 ላይ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ፡፡

▣ **"በሌላ መንገድ ግን የሚወጣ ሌባም ወንበዴም ነው"** የመልካሙ እረኛ ወገን ያልሆኑ በበጎቹ በረት ውስጥ እንዳሉ ያስታውሱ (7፡21-23 እና "የስንዴው እና የእንክርዳዱ ምሳሌ" ማቴ. 12፡24-30)፡፡ ችግሩ እግዚአብሔር በነጻ የሰጠውን ሥጦታ ጥቂቶች በሰዋዊ ጥረት ለማግኘት መሞከራቸው ነው (3፡14-16)፡፡ በምዕራፍ 9 ላይ የሚገኘው የፈሪሳውያን ታሪክ ጥሩ ምሳሌ ነው፡፡

10: **"በበሩ የሚገባ ግን የበጎች እረኛ ነው"** በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ብዙ ተለዋጭ ዘይቤዎች መኖራቸው በጣም ግልጽ ነው፡፡ ኢየሱስ እንደ በረት በር፣ ቁ.7፤ እንደገና ደግሞ የበጎች እረኛ (ቁ.11 እና 14)፡፡ ሆኖም ብዛት ያላቸውን ተለዋጭ ዘይቤዎች መጠቀም በዮሐንስም ሆነ በአ.ኪ. እንግዳ ነገር ይደሉም፡፡

1. ኢየሱስ እንጀራ እና እንጀራ ሰጪ ነው (ምዕ.6፡35፣51)
2. ኢየሱስ እውነት እና እውነት ተናጋሪ ነው (ምዕ.8፡45-46 እና 14፡6)
3. ኢየሱስ መንገድ እና መንገድን የሚያሳይ ነው (14፡6)
4. ኢየሱስ መስዋዕት እና መስዋዕትን የሚሰዋ ነው (የዕብራውያን መጽሐፍ)

"እረኛ" የሚለው የማዕረግ ሥም በብ.ኪ. ውስጥ ለእግዚአብሔርም ሆነ ለመሲሁ የተለመደ የማዕረግ ሥም ነበር (መዝ.23፤መዝ.80፡1፤ኢሳ.40፡10-11፤1ኛ ጴጥ.5፡1-4)፡፡ በኤርምያስ 23፤ ሕዝቅኤል 34 እና ኢሳያስ 56፡9-12 ደግሞ የአይሁድ መሪዎች "ሐሰተኛ እረኞች" ተብለዋል፡፡ "እረኛ" የሚለው ቃል "መጋቢ" ከሚለው ቃል ጋር አንድ ነው (ኤፌ.4፡11፤ቲቶ 1:5፣7)፡፡

10:3 **"በጎቹም ድምጹን ይሰሙታል"** ማወቅ እና መታዘዝ በግንኙነት ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ "መስማት" (4፡42፤5፡24፣25፣28-29፤8፡47፤10፡16፣27፤18፡37) እና "ማየት" (3፡3፤12፡40፤20፡8) በዮሐንስ ውስጥ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ ነው ብሎ ማመንን ለመግለጽ ግልጋሎት የሚሠጡ ቃላት ናቸው፡፡

▣ **"የራሱን በጎች በስማቸው ጠርቶ"** ኢየሱስ የራሱን በግል እና በተናጠል (እንደ ያህዌ፣ 10፡29-31) ያውቃቸዋል፡፡ እረኞች ለእንስሶቻቸው፣ በተናጠልም ሆነ በመንጋ ደረጃም ቢሆን ቅጽል ስም መስጠት የተለመደ ነው፡፡

ኢየሱስ የራሱን እውነተኛ በጎች በይሁዳ ሕዝብ ማካከል ከሚኖሩ ሐሰተኛ በጎች መካከል ጠርቶ ማውጣቱ ሥነ መለኮታዊ ድንጋጤን የሚፈጥር ነው፡፡ የቃል ኪዳኑ ሕዝብ እውነተኛ የእግዚአብሔር ሕዝብ አይደሉም፡፡ ይህ የአዲስ ኪዳን ሥር የሰደደ አሳፋሪ ነገር ነው፡፡ የአንድ ሰው የዘር ሐረጉ ሳይሆን የአንድ ሰው እምነቱ የወደፊት ዕጣ ፈንታውን ይወስናል! እምነት ግላዊ እንጂ ብሔራዊ አይደለም፡፡

ኢየሱስን የተቃወሙት አይሁዳውያኑ መሪዎች የእግዚአብሔር ሕዝብ አካል አይደሉም (ቁ.26)፡፡

▣ **"ይወስዳቸዋል"** ይህ መዳንን ብቻ ሳይሆን በየእለቱ እንደሚመራቸውም ያመለክታል (ቁ.4 እና 9)፡፡

10:4 ይህ ምናልባት ብዙ ልዩ ልዩ መንጎችን በአንድ በረት ውስጥ የመጠበቅ ልማድን ሊያመለክት ይችላል፡፡ ሲነጋ እረኛው የራሱን በጎች ይጠራቸዋል ወደ እርሱም ይመጣሉ፡፡

10:5 ቤተክርስቲያን ሁል ጊዜ ከሐሰተኛ እረኞች ጋር ትግል ነበረባት (1ኛ ጢሞ.4:1-3፤2ኛ ጢሞ.4:3-4፤ 1ኛ ዮሐ.4:5-6፤2ኛ ጴጥ.2)፡፡

**10:6 "ኢየሱስ ይህን ምሳሌ ነገራቸው"** "ምሳሌ/Parable" (*parabole*) ብሎ መተርጎም ተገቢ አይደለም፣ ይሁን እንጂ ይህ ቃል (*paroimiaN*) ከሚል ተመሳሳይ ሥርወ ቃል የመጣ ነው፡፡ ይህ ቃል በዚህ ቦታ እና በ16:25፣29 እና 2ኛ ጴጥ.2:22 ውስጥ ብቻ ይገኛል፡፡ ምንም እንኳ ይህ ቃል ለየት ያለ ቢሆንም በጣም ከተለመደው "ምሳሌ/Parable" (በተመሳሳዮቹ ወንጌላት ውስጥ ያገለገለ) ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ይመስላሉ፡፡ "ምሳሌ/Parable" የሚለው ቃል በተለምዶአዊ ግንዛቤ አንድን እውነት ግልጽ ለማድረግ ይረዳ ዘንድ የተለመደ ባሕላዊ ድርጊትን ከመንፈሳዊ እውነታ ጎን ማስቀመጥ ማለት ነው፡፡ ሆኖም ይህ ቃል ከመንፈሳዊ እውር ዓይኖች የተሰወረውን እውነት ያመለክታል (16:29፤ማር.4:11-12)፡፡

▣ **"እነርሱ ግን ….. አላስተዋሉም"** ምዕራፍ 10 ከምዕራፍ 9 ጋር የሚያያዝ ከሆነ "እነርሱ" የሚለው ቃል የሚገልጠው ፈሪሳውያንን ነው፡፡ እንደሚያዩ ይናገራሉ (9:41)፣ ነገር ግን አያዩም (10:20)፡፡ ኃይማኖት መሰናክል ይሆናል እንጂ ድልድይ አይሆንም፡፡

**NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 10÷7-10**
**[7]ኢየሱስም ደግሞ አላቸው፡፡ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ እኔ የበጎች በር ነኝ፡፡ [8]ከእኔ በፊት የመጡ ሁሉ ሌቦችና ወንበዴዎች ናቸው፤ ዳሩ ግን በጎቹ አልሰሙአቸውም፡፡ [9]በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፥ ይገባልም ይወጣልም መሰማሪያም ያገኛል፡፡ [10]ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም፤ እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ፡፡**

**10:7 "እኔ የበጎች በር ነኝ"** ይህ በዮሐንስ ውስጥ ከታወቁት ሰባት የ"እኔ" ዓረፍተ ነገሮች አንዱ ነው፡፡ ይህ ተለዋጭ ዘይቤ ኢየሱስ ብቻ እውነተኛው መንገድ የመሆኑን እውነታ ያጎላል (8፣10፤14:6)፡፡ ይህ ብዙውን ጊዜ እንደ ነውር የሚቆጠር ብቸኛ የወንጌል እውነት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር መገለጥ ከሆነ፣ በመቀጠል ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሰው ትክክለኛ መንገድ አንድ ብቻ አለ - በክርስቶስ ማመን (የሐዋ.4:12፤1ኛ ጢሞ.2:5)፡፡ በ8:12 ላይ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ፡፡

**10:8 "ከእኔ በፊት የመጡ ሁሉ ሌቦችና ወንበዴዎች ናቸው"** ይህ በምዕራፍ 9 እና 10 አውድ የቤተ መቅደስ መታደስ በዓል-ሀኑካ (10:22) ምክንያት በሁለቱ ኪዳኖች መካከል በነበረው ጊዜ የነበሩት የመቃቢያን መሲሃዊ አለሁ ባይነትን እና የእነርሱን ተወላጆች ያመለክታል ለማለት ይቻላል፡፡ ሆኖም ይህ ምናልባት ስለሐሰተኛ እረኞች ከሚናገሩት ከብ.ኪ. ምንባባት ጋር ይያያዛል (ኢሳ.59:9-12፤ ኤርምያስ 23፤ሕዝቅኤል 34፤ እና ዘካሪያስ 11)፡፡

ይህ በከፍተኛ ደረጃ በዘይቤ የተሞላ ቋንቋ እና አሻሚ የቅድመ አያቶች የሕይወት ታሪክ ጸሐፍት ምንባቡን በመለወጥ ወይም በማስፋት ትርጉሙን ለመግለጽ እንዲሞክሩ አድርጎአቸዋል፡፡ አንድ ቅጂ (MS D) በቀላሉ "ሁሉ" የሚለውን አጠቃላይ ቃል ያወጣ እና ብዛት ያላቸው የጥንት ቅጂዎች ($P^{45}$, $P^{75}$, $N^{*}$) ደግሞ "ከእኔ በፊት" የሚለው ሐረግ የላቸውም፡፡

**10:9 "በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል"** ይህ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር እና መፃኢ/የወደፊት ተደርጎ ግሥ ነው፡፡ ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስ ብቸኛ መንገድ ነው (14:6)፡፡ በዚህ አውድ ውስጥ "ይድናል" የሚለው ግሥ ምናልባት ከብ.ኪ. አካላዊ መዳን ትርጉም ጋር የሚያያዝ (ማለት፡- በጎቹ ደህና ናቸው) ነው፡፡ ሆኖም ዮሐንስ ብዙውን ጊዜ ተደራራቢ ትርጉም ያላቸውን ቃሎችን ይመርጣል፡፡ የመንፈሳዊ መዳን ሃሳብ ደግሞ ከዚህ አውድ የራቀ አይደለም (ቁ.42)፡፡

**10:10 "ሌባው"** ይህ የሐሰተኛ እረኞችን የተሰወረ ሃሳብ ያመለክታል፡፡ እንደገና ደግሞ የክፉውን ዓላማም ያንጸባርቃል፡፡ ይህ የግዴለሽነት አስተሳሰብ በሞያተኛ ሠራተኞችም ላይ በቁ. 12-13 ሊታይ ይችላል

▣ **"ሊያጠፋ"** የሚከተለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

### ልዩ ርዕስ፡ ጥፋት (*apollumi*/*አፖሉሚ*)

ይህ ቃል ስለ ዘላለማዊ ፍርድ እና መጥፋት የሥነ መለኮት አስተሳሰቦች ጋር በተያያዘ ታላቅ ግራ መጋባትን የፈጠረ ሰፊ ትርጉሞች ያለው መስክ ነው፡፡ ቃሉ ‹‹አፖ›› [*apo*] እና ‹‹ኦሉሚ›› [*ollumi*] የሚባሉ ሁለት የግሪክ ቃላት ጥምር ሲሆን መሠረታዊው ቀጥተኛ ትርጉምም ማፍረስ፣ ማጥፋት ማለት ነው፡፡

ችግሩ ያለው የዚህ ቃል ዘይቤያዊ አጠቃቀም ላይ ነው። ይህ ቃል በግልጽ በ Louw aאd אida's *Greek-Eאglish Lexicoא of the אew Testameאt, Based oא Semaאtic domaiאs,* vol.2, p. 30. ይታያል። ይህ መጽሐፍ ስለዚህ ቃል ብዙ ትርጉሞችን ይዘረዝራል።

1. ማጥፋት (ለምሳሌ፡- ማቴ.10፡28፤ሉቃ.5፡37፤ዮሐንስ 10፡10፤17፡12፤የሐዋ.5፡37፤ሮሜ 9፡22 ከ vol. 1, ገጽ 232)
2. ማግኘት አለመቻል (ለምሳሌ፡-ማቴ.10፡42፣ vol. 1, ገጽ 566)
3. ማጣት (ለምሳሌ፡-ሉቃ.15፡8፣ vol. 1, ገጽ 566)
4. ሥፍራን አለማወቅ (ለምሳሌ፡- ሉቃ.15፡4, vol. 1, ገጽ 330)
5. መሞት (ለምሳሌ፡- ማቴ.10፡39, vol. 1, ገጽ 266)

Gerhard Kittel, *Theological dictioאary of the אew Testameאt*, vol. 1, p.394 አራት ትርጉሞችን በመዘርዘር ለማስረዳት ይሞክራል፡

1. ማጥፋት ወይም መግደል (ለምሳሌ፡- ማቴ.2÷13፤ 27÷20፤ማር.3÷6፡9፡22፤ሉቃ.6÷9፡ 1ኛ ቆሮ.1÷19)
2. ማጣት ወይም በማጣት መሰቃየት (ለምሳሌ፡- ማር.9÷41፤ ሉቃ. 15÷4፣8)
3. መጥፋት (ለምሳሌ፡- ማቴ. 26÷52፤ማር.4÷38፤ሉቃ.11÷51፤ 13÷3፣5፣33፤ 15÷17፤ዮሐ.6÷12፣27፤ 1ኛ ቆሮ.10÷9፡10)
4. ማጣት (ለምሳሌ፡- ማቴ.5÷29-30፤ማር.2÷22፤ሉቃ.15÷4፣6፣24፣32፤21፡18፤የሐዋ.27÷34)

ኪተል በመቀጠል ‹‹እንደ ተመሳሳዮቹ ወንጌላት ዘገባ ቁ.2 እና ቁ.4 ላይ ያሉት ቃላት ከዚህ ዓለም ጋር ሲያያዙ፣ በሌላ በኩል ደግሞ እንደ ጳውሎስ እና ዮሐንስ አገላለጽ ቁ.1 እና ቁ.3 ላይ ያሉት ከሚቀጥለው ዓለም ጋር ሊያያዙ ይችላሉ›› (ገጽ. 394)።

እዚህ ጋ ነው ግራ መጋባት ያለው። ቃሉ ይህንን የመሠለ ሰፊ እና ልዩ ልዩ ትርጉሞች እና አጠቃቀሞች ያሉት እና የአ.ኪ. ጸሐፊዎች በልዩ ልዩ መንገዶች የተጠቀሙት ነው። ሮበርት ቢ. ጊረድለስቶን፣ ሲኖኒመስ ኦፍ ዘ ኦልድ ቴስታሜንት፣ በተሰኘው መጽሐፉ ገጽ 275-277 ላይ የተናገረውን እወደዋለሁ። እርሱ ቃሉን የሚያገናኘው በግብረ ገባቸው/ሥነ ምግባራቸው ከተበላሹ እና የዘላለምን ሞት ከሚጠባበቁ፤ እና ክርስቶስን ከሚያውቁ እና የዘላለም ሕይወት ካላቸው ጋር ነው። የኋለኛው ቡድን ‹‹የዳነ›› ነው ሲሆን የቀድሞው ቡድን ደግሞ የጠፋ ነው።

እኔ በግሌ ይህ ቃል መጥፋትን ያመለክታል ብዬ አላምንም (cf. E. fudge, *The Fire That Coאsumes*). ‹‹ዘላለም›› የሚለው ቃል በማቴ. 25፡46 ውስጥ ለዘላለማዊ ቅጣት እና ዘላለማዊ ሕይወት የሚያገለግል ነው። ከዚህ ውስጥ አንዱን ዝቅ ማድረግ ሁለቱንም ዝቅ ማድረግ ነው።

▣ "እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ" ይህ ሐረግ ብዙውን ጊዜ ስለ ቁሳዊ ነገሮች የተገባ ተስፋ ተደርጎ ይጠቀሳል፤ ነገር ገን አውዱ የሚነግረን ኢየሱስ ስለሚሰጠን እርሱን በግል ከማወቅ እና ከመንፈሳዊ በረከት ጋር የሚያያዝ እንጂ ስለ ምድራዊ ሃብት አይደለም (ይህ ከ4፡14 እና 7፡38 ጋር ተመሳሳይ ነው)። እውነተኛውን ሕይወት ማወቅ እና የራስ ማድረግን እንጂ በዚህ ዓለም ነገር ከሚገባው በላይ ማግኘትን አይደለም!

ተመሳሳዮቹ ወንጌላት እንደዘገቡልን የኢየሱስ ትኩረት/አጽንኦት በእግዚአብሔር መንግሥት ነገር ላይ ነው፤ እንደዮሐንስ ዘገባ ደግሞ የኢየሱስ ትኩረት በዘላለም ሕይወት ላይ ነው። ማንም ሰው አሁን ይህንን ሕይወት ሊያገኘው ይችላል። የእግዚአብሔር መንግሥት ተከፍቷል።

**NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 10÷11-18**

**[11]መልካም እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል። [12]እረኛ ያልሆነው በጎቹም የእርሱ ያልሆኑ ሞያተኛ ግን ተኩላ ሲመጣ ባየ ጊዜ በጎቹን ትቶ ይሸሻል፤ ተኩላም ይነጥቃቸዋል በጎቹንም ይበትናቸዋል። [13]ሞያተኛ ስለ ሆነ ለበጎቹም ስለማይገደው ሞያተኛው ይሸሻል።**
**[14-15]መልካም እረኛ እኔ ነኝ፥ አብም እንደሚያውቀኝ እኔም አብን እንደማውቀው የራሴን በጎች አውቃለሁ የራሴም በጎች ያውቁኛል፤ ነፍሴንም ስለ በጎች አኖራለሁ። [16]ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፤ እነርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል ድምፄንም ይሰማሉ፥ አንድም መንጋ ይሆናሉ እረኛውም አንድ። [17]ነፍሴን ደግሞ አነሣት ዘንድ አኖራለሁና ስለዚህ አብ ይወደኛል። [18]እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም። ላኖራት ሥልጣን አለኝ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ ይህችን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልሁ።**

10፡11፣14 "መልካም እረኛ እኔ ነኝ" ይህ በብ.ኪ. ለመሲሁ (ሕዝ.34፤23፤ዘካ.11፤1ኛ ጴጥ.5፡4) እና ለያህዌ (መዝ.23፡1፤18፡9፤77፡20፤78፡52፤80፡1፤95፡7፤100፡3፤ኢሳ.40፡11፤ኤር.23፡1፤31፡10፤ሕዝ.34፡11-16) የተሰጠ የማዕረግ ሥያሜ ነበር።

"*መልካም*" ተብለው የተተረጎሙ ሁለት የግሪክ ቃላት አሉ፡- (1) ‹*አጋቶስ* [*agathos*] በዮሐንስ ውስጥ ለነገሮች አገልግሎት ላይ የዋለ እና (2) ‹*ካሎስ* [*kalos*]፡ ይህ ደግሞ በሰብትዋጂንት ውስጥ የክፉ ተቃራኒ የሆነ መልካምን ለመግለጽ አገልግሎት ላይ ውሎአል፡፡ በአ.ኪ. "ውበት፣" "ለጋስ/ጨዋ፣" "ግብረ ገብነት፣" እና "ዋጋ ያለው" የሚል ትርጉም አለው፡፡ እነዚህ ሁለቱ ቃላት በሉቃ.8:15 ላይ በአንድነት አገልግለዋል፡፡ የ8፡12ን ማስታወሻ ይመልከቱ፡፡

**10:11 "*መልካም እረኛ ነፍሱን ስለበጎች ያኖራል*"** ይህ በእግዚአብሔር እና በሰው መካከል በኃጢአት የተበላሸውን ኅብረት ለማደስ ሰውን ከእግዚአብሔር የሚያስታርቀውን የክርስቶስን ምትካዊ የወኪልነት ሞት *ያመለክታል* (ቁ.11፣15፣17፣18)፡፡ እሱ በፈቃዱ በኃጢአት ለተበላሻው የሰው ዘር ሕይወቱን ሰጠ (ኢሳ.52:13-53:12፤ማር.10:45፤2ኛ ቆሮ.5:21)፡፡ እውነተኛ፣ የተባረከ ሕይወት የሚመጣው በእሱ ሞት ብቻ ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ ብሩስ ኤም. መትዝገር የተባለ ሰው አስገራሚ ሃሳብ አለው፡- "‹በባህሪው ዮሐንሳዊ የሆነውን (10:15፣17፤ 13:37፣38፤15:13፤1ኛ ዮሐ.3:16) ‹*ያንድን ሰው ሕይወት ማኖር*› በሚለው አገላለጽ ምትክ የተለያዩ ምስክሮች (P[45], N*, D) በተመሳሳዮቹ ወንጌላት ውስጥ እንደሚታየው (ማቴ.20:28፤ማር.10:45) ‹*ያንድን ሰው ሕይወት መስጠት*› በሚል አገላለጽ ተክተውታል (Bruce M. Metzger, A Textual CommeNtary oN the Greek New TestameNt, p. 230)፡፡

**10:14 "*የራሴን በጎች አውቃለሁ፤ የራሴም በጎች ያውቁኛል*"** ይህ "*ማወቅ*" የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ስሜት/ትርጉም ነው (በ1:10 ላይ ያለው ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡)፡፡ ልክ ወልድ አብን እንደሚያውቅ እና አብ ወልድን፣ እንዲሁ ኢየሱስ በእርሱ የታመኑትን ያውቃል፣ በእርሱ የታመኑትም ያውቁታል፡፡ እነርሱ "አይተውታል" "ሰምተውታልም" (ቁ.4) ደግሞም ምላሽ ሰጥተውታል (1:12፤3:16)፡፡ ክርስትና የግል ግንኙነት ነው (17:20-26)፡፡

**10:15 "*አብ እንደሚያውቀኝ እኔም አብን እንደማውቀው*"** ይህ በዮሐንስ ውስጥ በተደጋጋሚ የሚታይ መሪ ሃሳብ ነው፡፡ ኢየሱስ ይናግር እና ያደርግ የነበረው ከአባቱ ጋር ካለው የግል ግንኙነት ነው፡፡

በቁ.14-15 ላይ በአብ እና ወልድ ማካከል ያለው ምስጢራዊ ግንኙነት በወልድ እና በተከታዮቹ (14:23) መካከል ካለው ምስጢራዊ ግንኙነት ጋር አስደናቂ መስስሎሽ/ማመሳሰል አለው፡፡ ዮሐንስ ምስጢራዊ ኅብረትን የሚገልጸውን የዕብራይስጥ ስሜት ያለውን "ማወቅ" እንጂ አእምሮአዊ እውነታዎችን የሚገልጸውን አልተጠቀመም፡፡ ኢየሱስ አብን ያውቃል፤ ኢየሱስ የሚያውቁ ደግሞ ያውቁታል!

**10:16 "*ከዚህ በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ*"** ይህ በኢሳ.56:6-8 ያለውን ያስታውሳል፡፡ ይህ ክፍል (1) ሳምራውያንን (4:1-42) ወይም (2) የገሊላ ቤተክርስቲያንን እንዲያመለክት አውዱ የሚፈልግ ይመስላል፡፡ ይህ የሚናገረው በክርስቶስ ያላቸውን እምነት የሚለማመዱት ሁሉ ሰለአላቸው አንድነት ነው፡፡ አዲሱ ኪዳን አይሁድን እና አህዛብን አንድ አድርጓቸዋል (ኤፌ.2:11-3:13፤ ደግሞም 1ኛ ቆሮ.12:13፤ገላ.3:28፤ ቆላ.3፡11ን ያስታውሱ)! ዘፍጥረት 3:15 እና ዮሐንስ 3:16ን አዋሃደ!

▣ **"*እንደም መንጋ ይሆናሉ እረኛውም አንድ*"** ይህ ጉል ጊዜ የእግዚአብሔር ግብ ነው (ዘፍ.3:15፤12:3፤ዘፀ.19:5-6)፡፡ የዚህ አንድነት ሥነ መለኮታዊ ዕይታ በኤፌ.2:11-3:13 እና 4:1-6 ተብራርቷል፡፡

**10:17 "*ስለዚህ አብ ይወደኛል*"** ወልድ ነፍሱን ለማኖር እንዳልተገደደ ሁሉ አብም ልጁን ለመስጠት አልተገደደም፡፡ ይህ ክፍል እግዚአብሔር ኢየሱስን ስለመታዘዙ እንደሸለመው ተደርጎ መተርጎም የለበትም (ይህ ብዙውን ጊዜ የማደጎ ልጅነት (*አዶፕሺኒዝም*) በመባል የሚታወቀው ኑፋቄ ነው፤ በዚህ ጽሁፍ መጨረሻ የሚገኘውን አጭር መዝገበ ቃላት ይመልከቱ፡፡)፡፡

▣ **"*ነፍሴን ደግሞ አነሳት ዘንድ አኖራለሁና*"** ይህ ትንሳኤውን ያመለክታል፡፡ እንደሚታወቀው በአ.ኪ. አብ መስዋቱን እንደተቀበለ ለማሳየት ልጁን ያስነሳዋል (ቁ.18ለ)፡፡ ሆኖም በትንሳኤ የሚገለጠው የኢየሱስ የራሱ ኃይል በዚህ ቦታ በጉልህ ተወስቷል፡፡

ይህ ሐረግ አ.ኪ. ብዙውን ጊዜ የመዳንን ሥራ የሦስቱም የእግዚአብሔር (Godhead) አካላት ተግባር መሆኑን በማመልከቱ እጅግ በጣም ጥሩ ዕድል ነው፡፡

1. እግዚአብሔር አብ ኢየሱስን አስነሳው (የሐዋ.2:24፤3:15፤4:10፤5:30፤10:40፤13:30፣33፣34፣37፤17:31፤ሮሜ 6:4፣9፤10:9፤1ኛ ቆሮ.6:14፤2ኛ ቆሮ.4:14፤ገላ.1:1፤ኤፌ.1:20፤ቆላ.2:12፤1ኛ ተሰ.1:10)
2. እግዚአብሔር ወልድ ራሱን ያስነሳል (ዮሐ. 2:19-22፤10:17-18)
3. እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን ያስነሳል (ሮሜ 8:11)

**10:18 "*ሥልጣን አለኝ*"** ይህ በ1፡12 ላይም ያገለገለ ቃል ነው፡፡ "ሥልጣን፣" "ሕጋዊ መብት፣" ወይም "ኃይል" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፡፡ ይህ ጥቅስ የኢየሱስን ሥልጣን እና ኃይል ያሳያል፡፡ ]

**NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 10፥19-21**
**[19]እንግዲህ ከዚህ ቃል የተነሣ በአይሁድ መካከል እንደ ገና መለያየት ሆነ። [20]ከእነርሱም ብዙዎች። ጋኔን አለበት አብዶአልም፤ ስለ ምንስ ትሰሙታላችሁ? አሉ። [21]ሌሎችም። ይህ ጋኔን ያለበት ሰው ቃል አይደለም፤ ጋኔን የዕውሮችን ዓይኖች ሊከፍት ይችላልን? አሉ።**

10:19 ስለ ኢየሱስ የተለያዩ አስተያየቶች እንደ ነበሩ በ6:22፤7:12፣25፣43፤ 9:8-9፣16፤ 10:19-21፤11:36-37፣ ይህ *መሪ ሃሳብ* በመላው ዮሐንስ የቀጠለ ነው። ጥቂቶች ወንጌልን የሚቀበሉበት ሌሎች ደግሞ የሚቃወሙበት ምስጢር በአስቀድሞ መወሰን እና በሰው ነፃ ፈቃድ ትምህርቶች መካከል ያለው ውጥረት ነው!

10:20 "*ጋኔን አለበት አብዶአልም*" ይህ ከሁለት አቅጣጫ በኢየሱስ ላይ የሚሰነዘር የተለመደ ክስ ነው።
1. በዚህ ክፍል፣ በ7:20 ውስጥ እንዳለው፣ ኢየሱስ የአእምሮ ሕመም አለበት ለማለት ይጠቀሙበት ነበር።
2. ይህንን ተመሳሳይ ክስ ፈሪሳውያንም የኢየሱስን የኃይል ምንጭ ለመግለጽ ይጠቀሙበት ነበር (8:48፣52)

10:21 በቁ.21 ላይ ሁለት ጥያቄዎች አሉ።
1. ቁ.21ሀ ‹ኡክ› [ouk], የሚል አለው፣ ይህም "አዎ" የሚል መልስን ይጠብቃል።
2. ቁ.21ለ ‹ሜ› [me], የሚል አለው፣ ይህ "አይ/አያደርግም" የሚል መልስን ይጠብቃል።

James Hewett, New TestameNt Greek, p.171ን ይመልከቱ። ሆኖም ይህ ክፍል የኮይኔ ግሪክ ምን ያህል አስቸጋሪ እና ፈጣን ደንቦች እንዳሉት ያሳያል። የመጨረሻ ወሳኙ ሰዋሰዋዊ መዋቅር ሳይሆን አውድ ነው።

የእውሩ ሰው መፈወስ መሲሃዊ ምልክት ነበር (ዘፀ.4:11፤መዝ.146:8፤ኢሳ.29:18፤35:5፤42:7)። የእስራኤል እውርነት (ኢሳ.42:19) በምዕራፍ 9 ላይ እንደታየው እዚህ ደግሞ ይታያል የሚል ስሜት አለ።

**NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 10፥22-30**
**[22]በኢየሩሳሌምም የመቅደስ መታደስ በዓል ሆነ፤ ክረምትም ነበረ። [23]ኢየሱስም በመቅደስ በሰሎሞን ደጅ መመላለሻ ይመላለስ ነበር። [24]አይሁድም እርሱን ከበው። እስከ መቼ ድረስ በጥርጣሬ ታቆየናለህ? አንተ ክርስቶስ እንደ ሆንህ ገልጠህ ንገረን አሉት። [25]ኢየሱስም መለሰላቸው፥ እንዲህ ሲል፦ ነገርኋችሁ አታምኑምም እኔ በአባቴ ስም የማደርገው ሥራ ይህ ስለ እኔ ይመሰክራል፤ [26]እናንተ ግን እንደ ነገርኋችሁ ከበጎቼ ስላልሆናችሁ አታምኑም። [27]በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ እኔም አውቃቸዋለሁ ይከተሉኝማል፤ [28]እኔም የዘላለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ፥ ለዘላለምም አይጠፉም፥ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም። [29]የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል፥ ከአባቴም እጅ ሊነጥቃቸው ማንም አይችልም። [30]እኔና አብ አንድ ነን።**

10:22 "*የመቅደስ መታደስ በዓል*" ዮሴፍ ወልደ ኮሪዮን ይህንን "የብርሃናት በዓል" ብሎ ይጠራዋል። በዘመናችን ይህ በዓል ሀኑካ ተብሎ እንደሚጠራ ይታወቃል። ይህ በዓል የስምንት ቀናት በዓል ሲሆን በታህሳስ አጋማሽ አካባቢ የሚደረግ ነው። ከክርስቶስ ልደት በፊት በ164 የይሁዳ መቃቢስ ወታደራዊ ድል በኋላ በኢየሩሳሌም የሚደረግ የቤተ መቅደስ መታደስ በዓል ነው። በ168 ከክርስቶስ ልደት በፊት፣ በትንሽዋ ኢሲያ መሪ የነበረው አንቲዮከስ 4ኛ ኤፒፋነስ አይሁድ የግሪክ ባሕልን እንዲያራምዱ ያስገድድ ነበር (ዳን.8:9-14)። በቅዱስ ስፍራ ያለውን መሰዊያ ‹ዜዎስ› ለተባለው አምላክ በማድረግ እንኳ የኢየሩሳሌምን ቤተ መቅደስ ወደ አረማዊ አምልኮ ቅዱስ ስፍራነት ለወጠ። ከካህን ሞዲን ልጆች አንዱ የሆነው ይሁዳ መቃቢያን የሦሪያን ገዢ አሸንፎ እና ቤተ መቅደሱን አጽድቶ ለአምልኮ አዘጋጀው (1ኛ መቃቢያን 4:36-59፤ 2ኛ መቃቢያን 1:18)።

ዮሐንስ የአይሁድ በዓልን ኢየሱስ እንደ ምሳሌ ተጠቅሞት ለአይሁድ መሪዎች፣ለኢየሩሳሌም ነዋሪዎች እና ለኃይማኖት በዓሉ ለመጡት ተጓዦች ራሱን እንዲገልጥ እንደ ጥሩ አጋጣሚ ይጠቀማል (ምዕራፍ 7-11)።

▣ "በሰለሞን ደጅ" ይህ ኢየሱስ ካስተማረበት የሴቶች አደባባይ በምስራቅ አቅጣጫ ያለ የተሸፈነ ቦታ ነው። ከክርስቶስ ልደት በፊት በ586 በሆነው የባቢሎን ምርኮ ጊዜ ይህ ቦታ እንደተረፈ ዮሴፍ ወልደ ኮሪዮን ይናገራል።

10:23 "ክረምት ነበረ" ይህ የዓይን ምስክር ዝርዝር ነው።

10:24 "እንደ…." ይህ የአንደኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ሲሆን በጸሐፊው እይታ ወይም ለጽሑፉ ዓላማ እውነት እንደሆነ የሚገመት ነው። በዚህ አውድ ውስጥ ብዙ አንደኛ መድብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገሮች አሉ (ቁ.24፣35፣37 እና 38)። በቁ.24 የሚገኘው ይህ አገባብ የሚያሳየው ምን ያህል በሥነ ጽሑፍ ችሎታ ውስጥ ሊጠቅም እንደሚችል ነው። እነዚህ ፈሪሳውያን በእውነት ኢየሱስ መሲሁ እንደነበር አላመኑም፤ ሊያጠመዱት ይፈልጉ ነበር።

▣ ***"ገልጠህ ንገረን"*** በዚህ ጥቅስ ውስጥ ብዙ *የሚያነጋግሩ* ነገሮች አሉ፡፡ በመጀመሪያ ኢየሱስ በምሳሌ፣ በዘይቤያዊ ቋንቋ፣ እና አሻሚ በሆኑ ሁለትዮሽ(ዱዋሊስቲክ) ዓረፍተ ነገሮች አስተምሮአል፡፡ በቤተ መቅደስ የተሰበሰበው ሕዝብ ራሱን እንዲገልጥ ይፈልጋል፡፡ በ7:4 ላይ ያለውን *parrhesia/ፓረሄሲያ* የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

*ሁለተኛ፣ በኢየሱስ ዘመን የነበሩ አይሁድ መሲሁ ሥጋ ለብሶ የመጣ አምላክ ነው ብለው አልጠበቁም፡፡ በብዙ ጊዜያት ኢየሱስ ከአብ ጋር አንድ መሆኑን አውስቷል (8:56-59)፣ ነገር ግን በዚህ አውድ ውስጥ ስለ መሲሁ ሲጠይቁ ይታያል፡፡ አይሁድ እንደ ሙሴ የሚሆንላቸውን የተቀባውን ይጠብቁ ነበር (ዘዳ.18:15፣19)፡፡ ኢየሱስ በትክክል የሚጠብቁትን በምዕራፍ 6 ውስጥ አድርጎታል፡፡ ሥራዎቹ በብ.ኪ. ያሉትን ትንቢቶች በተለይ እውሩን በማብራት (ምዕራፍ 9) ፈጽሞታል፡፡ የሚፈልጉት መረጃ ሁሉ ነበራቸው፡፡ ችግሩ መሲሁ እንደ ልማዳቸው በሆነው ውትድርና መሠረት፣ እንዲሁም በብሄራዊ ስሜት ረገድ እንደሚጠብቁት አልሆነላቸውም፡፡*

10:25 ***"እኔ በአባቴ ስም የማደርገው ሥራ ይህ ስለ እኔ ይመሰክራል"*** *ኢየሱስ ድርጊቱ ንግግሩን ያረጋግጥ እንደነበር በአጽንኦት ነግሮአቸዋል* (2፡23፤5፡36፤10፡25፣38፤14፡11፤15፡24)፡፡

10:26 *ምን ዓይነት አስደንጋጭ ዓረፍተ ነገር ነው!*

10:28 ***"እኔ የዘላለምን ሕይወት እሰጣቸዋለሁ"*** *የዘላለም ሕይወት መጠንን እና ጥራትን የተላበሰ ነው፡፡ ይህ የአዲሱ ዘመን ሕይወት ነው፡፡ ይህ በአሁኑ ጊዜ በክርስቶስ በማመን ይገኛል* (3:36፤11:24-26)፡፡

▣ ***"ለዘላለምም አይጠፉም: ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም"*** *ይህ ሁለት ዕጥፍ አሉታዊ ከተፈጸመ ድርጊት አመልካች ግሥ ጋር ነው፡፡ ይህ በአ.ኪ. ውስጥ ከሚገኙት ስለ አማኞች ዋስትና ከሚናገሩት እጅግ ጠንካራ ክፍሎች አንዱ ነው* (6:39)፡፡ *እኛን ከእግዚአብሔር ፍቅር የሚለየን ቢኖር እኛው ራሳችን መሆናች ግልጽ ነው* (ሮሜ. 8:38-39፤ገላ5:2-4)፡፡ *ዋስትና* (በ1ኛ ዮሐ.5፡13 ላይ *ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡) ከመጽናት ጋር ሚዛኑን የጠበቀ መሆን አለበት* (በ8:31 ላይ *ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡)፡፡ ዋስትና በሥሉስ አሃዱ እግዚአብሔር ባሕሪ እና ሥራ ላይ ሊመሠረት ይገባዋል፡፡*

*የዮሐንስ ወንጌል እምነታቸውን በክርስቶስ በዘላቂነት ያኖሩ አማኞችን ዋስትና ይናገራል፡፡ ዋስትናው የሚጀምረው በመጀመሪያ የንስሐ ውሳኔ እና እምነት ሲሆን በእምነት የኑሮ ዘይቤ ይገለጣል፡፡ ሥነ መለኮታዊ ችግሩ ይህ የግል ግንኙነት የራሳችን ወደ ምናደርገው ውጤት ("አንዴ ከዳንክ ሁሌም ዳንክ") የዞረ እንደሆነ ነው፡፡ ቀጣይ እምነት የእውነተኛ መዳን ማስረጃ ነው (ዕብራውያን፣ ያዕቆብ፣ እና 1ኛ ዮሐንስ)፡፡*

10:29

| | |
|---|---|
| NASB,NKJV | **"እነርሱን የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል"** |
| NRSV | **"አባቴ የሰጠኝ ከሌሎች ሁሉ ይበልጣል"** |
| TEV | **"አባቴ የሰጠኝ ከማንኛውም ነገር ይበልጣል"** |
| NJB | **"ሰጥቶኛልና አባቴ ከሁሉ ይበልጣል"** |

*ጥያቄው "ይበልጣል" የተባለው ነገር ምን እንደሆነ ነው :* (1) *እግዚአብሔር ለኢየሱስ የሰጠው ሕዝብ* (NRSV, TEV) *ወይም* (2) *እግዚአብሔር ራሱ* (NASB, NKJV, NJB)፡፡ *የዚህ ዓረፍተ ነገር ሁለተኛ ክፍል የሆነ ሰው የኢየሱስን ተከታዮች ሊነጥቃቸው እንደሚሞክር ያመለክታል፡፡ ከሥነ መለኮታዊ ዕይታ አንጻር ሁለተኛው አማራጭ እጅግ የተሻለ ይመስላል፡፡* በ6:37 ላይ *ዋስትና በሚለው ሥር ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡*

*በአብ ኃይል ላይ የተመሰረተው የአማኞች ዋስትናን በተመለከተ ይህ አስደናቂ ምንባብ ነው! የአማኞች ዋስትና፣ እንደ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነታዎች ሁሉ፣ ውጥረት በሞላበት የቃል ኪዳን ሐረግ ውስጥ ሆኖ ቀርቧል፡፡ ያማኞች የመዳን ዋስትና እና ተስፋ በሥሉስ አሀዱ እግዚአብሔር ባሕሪ፣ ምህረት እና ጸጋ ውስጥ ያለ ነው፡፡ ሆኖም አማኙ በእምነት መቀጠል አለበት፡፡ መዳን በመጀመሪያ በመንፈስ ምሪት በሚደረግ የንስሐ እና የእምነት ውሳኔ ይጀመራል፡፡ ይህ ደግሞ ቀጣይነት ያለው ንስሐ፣ እምነት፣ መታዘዝ እና መጽናት ሊኖረው ይገባል፡፡ መዳን የሥራ ውጤት አይደለም (የሕይወት ዋስትና፣ ወደ ሰማይ መግቢያ ቲኬት)፣ ነገር ግን በክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ያለው የግል ግንኙነት ማደግ ነው፡፡*

*ከእግዚአብሔር ጋር ያለ የትክክለኛ ግንኙነት የማያጠራጥር ማስረጃው የእምነት እና አገልግሎት ሕይወት መለወጥ ነው (ማቴዎስ 7)፡፡ ስለ ሥጋዊ ክርስቲያን ትንሽ ማስረጃ አለ (1ኛ ቆሮንጦስ 2-3)፡፡ እውነተኛው ሕይወት አሁን ክርስቶስን መምሰል ነው እንጂ ስንሞት ወደ ሰማይ መሄዳችን ብቻ አይደለም፡፡ በሕይወታቸው ለሚያድጉ፣ ለሚያገለግሉ፣ ከኃጠአት ጋር እንኳ ለሚታገሉ የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ዋስትና እና ማረጋገጫ እጥረት የለባቸውም፡፡ ነገር ግን ፍሬ ከሌለ፣ ሥር የለም! መዳን በጸጋ ብቻ ነው፣ በእምነት በኩል፣ ሆኖም እውነተኛ መዳን "መልካም ሥራን" ያስከትላል* (ኤፌ.2፡10፤ *ያዕ*.2፡14-26)፡፡

10:30-33 ***"እኔ እና አብ አንድ ነን፡፡ አይሁድ ሊወግሩት ደግመው ድንጋይ አነሡ"*** *ይህ የኢየሱስን መሲሃዊነት እን አምላክነት ከሚገልጡት ጠንካራ ክፍሎች አንዱ ብቻ ነው* (1:1-14፤8:58፤14:8-10፣ *በተለይ* 17:21-26፣ *"አንድ" የሚለውንም ይጠቀማል)፡፡ አይሁድ እሱ ይናገር የነበረው ምን እንደሆነ በሚገባ ገብቷቸዋል እና እንደ ስድብ ስለቆጠሩት* (ቁ.33፤8:59)፡፡ በዘሌ.24:16 *መሠረት ሊወግሩት ተነሡ፡፡*

በክርስቶስ ማንነት ላይ በነበሩት የጥንት ሙግቶች ውስጥ (*ማለት አርዮሱበኩር፤ አትናቴዎስ* -ፍጹም አምላክ) ቁ.30 እና 14:9 ብዘውን ጊዜ በአትናቴዎስ ግምባር ቀደም ተጠቃሾች ነበሩ (The Cambridge Histor of the Bible, vol. 1,p.444 ይመልከቱ፡፡)፡፡ "አርዮሳዊነትን" በተመለከተ በዚህ ጥናት መጨረሻ ያለው አጭር መዝገበ ቃላት ይመልከቱ፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 10÷31-39
**[31]አይሁድ ሊወግሩት ደግመው ድንጋይ አነሡ፡፡ [32]ኢየሱስ፦ ከአባቴ ብዙ መልካም ሥራ አሳየኋችሁ፤ ከእነርሱ ስለ**
**ማናቸው ሥራ ትወግሩኛላችሁ? ብሎ መለሰላቸው፡፡ [33] አይሁድም፡፡ ስለ መልካም ሥራ አንወግርህም፤ ስለ ስድብ፤**
**አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለ ማድረግህ ነው እንጂ ብለው መለሱለት፡፡ [34]ኢየሱስም እንዲህ ብሎ**
**መለሰላቸው፡፡ እኔ፡፡ አማልክት ናችሁ አልሁ ተብሎ በሕጋችሁ የተጻፈ አይደለምን? [35]መጽሐፉ ሊሻር አይቻልምና**
**እነዚያን የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን አማልክት ካላቸው፥ [36]የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ስላልሁ እናንተ አብ**
**የቀደሰውን ወደ ዓለምም የላከውን፡፡ ትሳደባለህ ትሉታላችሁን? [37]እኔ የአባቴን ሥራ ባላደርግ አትመኑኝ፤ [38]ባደርገው**
**ግን፥ እኔን ስንኳ ባታምኑ አብ በእኔ እንደ ሆነ እኔም በአብ እንደ ሆንሁ ታውቁና ታስተውሉ ዘንድ ሥራውን እመኑ**
**[39]እንግዲህ ደግመው ሊይዙት ፈለጉ፤ ከእጃቸውም ወጣ፡፡**

10:31 ይህ ጥቅስ በቁ.30 ኢየሱስ ከተናገረው *ጋር* ይያያዛል፡፡ ኢየሱስ ለሚከሱት ክስ በጣም ረቢያዊ በሆነ ሙግት ይመልስላቸዋል፡፡ ይህ በመሠረቱ *ኤሎሂም* በሚለው በብ.ኪ. ለአምላክ የተሰጠ ስም (ዘፍ.1) ላይ እየተደረገ ያለ የቃላት ጨዋታ ነው፤ ሆኖም በአይነቱ የብዙ ቁጥር ገላጭ ሲሆን ለመላእክት እና ለሰብዓዊ መሪዎችም (መሳፍንት) መጠሪያነት ያገለግል ነበር፡፡ በ6:20 ላይ ያለውን የአምላክ ስሞች የሚለው ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

10:32 *መልካም* (*ካሎስ*) እረኛ ከአብ የሆነውን መልካም (*ካሎስ*) *ሥራዎች* ይሠራል፡፡

10:33 "በሕጋችሁ" ኢየሱስ ከመዝሙረ ዳዊት ነው የጠቀሰው፤ ሆኖም "ሕግ" በማለት ነው (ማለት፡- ቶራህ ማለት "ትምህርት" ነው፣ 12:34፤15:25፤ሮሜ 3:9-19)፡፡ "ሕግ" የሚለው ቃል የሙሴን ጽሑፎች (ቶራህ)፡- ከዘፍጥረት - ዘዳግም ማመልከቱ የተለመደ ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው መላውን ብ.ኪ.ንን ለመግለጥ የቃሉን ሰፊ ጠቀሜታ ነው፡፡

▣ "አማልክት ናችሁ" ኢየሱስ ይህን የወሰደው ከመዝ.82፡6 ነው፡፡ የዕብራይስጡ ቃል ኤሎሂም የሚለው ሲሆን ሰብዓዊ መሳፍንትን ለማመልከት የገባ ነው (በ6፡20 ላይ ያለውን የአምላክ ስሞች የሚለው ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡)፡፡ እነዚህ መሳፍንት (ክፉዎች ቢሆኑም) "የልዑል ልጆች" ተብለው ተጠርተዋል፡፡ እነዚህ አይሁድ ኢየሱስን ይጻረሩ/ይተናኮሉ ነበር፤ ምክንያቱም እሱ ሰው ቢሆንም እንኳ፡- (1) የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ እና (2) ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ነን እያለ ይናገር ነበር፡፡ አሁንም ሌሎች ሰዎች "አማልክት" ተብለው የጠሩ ነበሩ (ዘፀ.4:16፤ 7፡1፤22:8፣9፤መዝ.82:6፤138:1)፡፡

የኢየሱስ ረቢያዊ ሙግት ይህን መስመር የተከተለ ይመስላል፡- መጽሐፉ እውነት ነው፣ ሰዎች *ኤሎሂም* ተብለው ተጠርተዋል፣ ታዲያ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ስላልኩ ለምን ትሳደባለህ ትሉኛላችሁ? *ኤሎሂም* የሚለው ቃል በዕብራይስጥ የብዙ ቁጥር አመልካች ነው፤ ሆኖም በነጠላ ቁጥር አመልካችንት የድርጊት ገላጭ ነጠላ ግሥን ተጠቅሞ የብ.ኪ. አምላክን ለማመልከት እጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በ6፡20 ላይ የአምላክ ስሞች የሚለው ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡ ይህ ምናልባት ዮሐንሳዊ አይነተኛ የቃላት ጨዋታ ነው፡- (1) ሁለት እንደምታዎች/ትርጉሞች ያሉት ቃል፣ እና (2) "አዎ" የሚል መለስ የሚጠብቅ የግሪክ ጥያቄ፡፡

10:35 "(*መጽሐፉ ሊሻር አይቻልምና*)" ዮሐንስ በዘውን ጊዜ ኢየሱስ ከተቃዋሚዎቹ ገር በሚያደርገው ንግግር ላይ አስተያየት ይሰጣል፡፡ ይህ የኢየሱስ ቃል ይሁን ወይም የዮሐንስ አልተረጋገጠም፡፡ ያም ሆነ ይህ፣ ሁለቱ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያለባቸው እስከሆኑ ድረስ ምንም ችግር የለውም፡፡ የጥቅሱ ተዓማኒነት የመጽሐፉን ተዓማኒነት ያሳያል፡፡ ኢየሱስ እና ሐዋሪያት ብ.ኪ.ንን እና ማብራሪያቸውን ልክ እንደ እግዚአብሔር ቃል ይመለከቱታል (ማቴ.5:17-19፤1ኛ ቆሮ.2:9፣13፤1ኛ ተሰ.2:13፤2ኛ ጢሞ.3:16፤1ኛ ጴጥ.1:23-25፤2ኛ ጴጥ.1:20-21፤3:15-16)፡፡

ጳጳስ ኤች.ሲ.ጂ. ሙሌ "እሱ (ክርስቶስ) መጽሐፍ ቅዱስን ፈጽሞ ያምነው ነበር፤ ስለሆነም ምንም እንኳ በውስጡ በጣም እንቆቅልሽ የሚሆኑብኝ ግልጽ ያልሆኑ እና የተወሳሰቡ ነገሮች ቢኖሩትም በጭፍን ሳይሆን በእሱ ምክንያት መጽሐፉን በአክብሮት በማመን እጓዛለሁ" (ገጽ 138) በማለት ይናገራሉ፡፡ **(Bishop H.C.G. Moule iN *The Life of Bishop Moule*)**

10:36 በዚህ ክፍል ኢየሱስ አባቱ እንደመረጠው (ወይም "እንደለየው" ወይም "እንደቀደሰው") እና እንደላከው (እንደ መሲህ) ይናገራል፡፡ ስለዚህ በእርግጥም እሱ "የእግዚአብሔር ልጅ" ተብሎ መጠራት ይገባዋል፡፡ የእስራኤል መሳፍንት እግዚአብሔርን እንደሚወክሉ (መዝ.82:6)፣ እርሱም በቃል እና በሥራ አባቱን ይወክላል፡፡ በ5:24 ላይ ላከ (*አፖስትሎ*) የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

10:37 ይህ በትክክል በቁ.19-21 የተነገረው ነው፡፡ የኢየሱስ ተአምራቶች የእግዚአብሔርን *ሥራ* ያንጸባርቃሉ፡፡

10:37፣38 "ባ......ባ" እነዚህ የአንደኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገሮች ናቸው። ኢየሱስ የአባቱን ሥራ ያደርግ ነበር። ከሆነ ደግሞ ሊያምኑት፣ እሱ እና አብ አንድ እንደሆኑ መተማመን ይገባቸዋል (ቁ.30፣38)። በ1ኛ ዮሐ.2፡10 መኖር (AbidiNg) የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።

10:39 ይህ ኢየሱስ ሊጎዱት ከሚፈልጉ ያመለጠባቸው ብዙ ጊዜያት አንዱ ነው (ሉቃ.4፡29-30፤ ዮሐ.8:59)። ይህ ማምለጥ (1) በታአምራዊ ሁኔታ ይሁን ወይም (2) የኢየሱስ ሰውነት ከሌሎች (ከእነርሱ መካከል እንዲሆን ፈቅደውለት) ጋር ስለሚመሳሰል መለየት አቅቶአቸው አልተረጋገጠም።

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 10፥40-42
[40]ዮሐንስም በመጀመሪያ ያጠምቅበት ወደ ነበረው ስፍራ ወደ ዮርዳኖስ ማዶ እንደ ገና ሄደ በዚያም ኖረ። [41]ብዙ ሰዎችም ወደ እርሱ መጥተው። ዮሐንስ አንድ ምልክት ስንኳ አላደረገም፥ ነገር ግን ዮሐንስ ስለዚህ ሰው የተናገረው ሁሉ እውነት ነበረ አሉ። [42]በዚያም ብዙዎች በእርሱ አመኑ።

10:40 ይህ የሚያመለክተው ዮርዳኖስን ተሻግሮ ከኢያሪኮ ማዶ በቢታኒያ አቅራቢያ ያለ አካባቢን ነው።

10:41 ዮሐንስ መጥምቁ ዮሐንስ ስለኢየሱስ የሠጠውን ማረጋገጫ በድጋሚ ይናገራል (1:6-8፣19-42፤3:22-30፤5:33)! ይህ ምናልባት በመጥምቁ ዮሐንስ ዙሪያ እያደጉ ይመጡ የነበሩትን ኑፋቄዎች ለመከላከል ይሆናል።

10:42 የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስን በተቃወሙት መጠን ከተራው ሕዝብ (በምድሪቱ ላይ ከሚኖሩ) ብዙዎች የእምነት ምላሽ ይሰጡት/ያምኑት ነበር (2:23፤7፡31፤8:30)። በ2:23 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ማብራሪያ ነው፤ ይህ ማለት ስለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን ባገኘነው ብርሃን መመላለስ አለብን። መጽሐፍ ቅዱስን በመተርጎም ረገድ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ እና መንፈስ ቅዱስ ቀዳሚዎች ነችሁ። ለሌላ ተንታኝ/ሐተታ አቅራቢ ብቻ መተው የለብህም።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተነሱት ታላላቅ ጉዳዮች ላይ ታተኩር ዘንድ እንዲረዳህ እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ተሰጥተውሃል። እነዚህ ጥያቄዎች ማለት ለላቀ መረዳት አእምሮ ቀስቃሾች እንጂ ማሳረጊያዎች አይደሉም።

1. ዮሐንስ ብዙውን ጊዜ ተለዋጭ ዘይቤያዊ አነጋገሮችን የሚቀላቅለው ለምንድን ነው? (ለምሳሌ፡- "ኢየሱስ የበጎች በር እና መልካም እረኛ")
2. ስለዮሐንስ 10 የሚናገረው የብ.ኪ. ዳራ ምንድን ነው?
3. የኢየሱስ "ነፍሱን ስለበጎች ማኖሩ" ጠቀሜታው ምንድን ነው?
4. አይሁድ ኢየሱስን አጋንንት አለበት እያሉ መክሰሳቸውን ለምን ቀጠሉበት?
5. የኢየሱስ ሥራዎች በጣም ጠቃሚ የሆኑት ለምንድን ነው?
6. "የአማኞችን ዋስትና" ከ "ቅዱሳን መጽናት" ጋር እንዴት እናገኛኘዋለን?

# የዮሐንስ 11

## ተሻሽለው በወጡ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀጽ አከፋፈል

| UBS[4] | NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| የአልዓዛር መሞት | የአልዓዛር መሞት | የአልዓዛር መነሳት | የአልዓዛር መሞት | የአልዓዛር ትንሳኤ |
| 11:1-16 | 11:1-16 | 11:1-16 | 11:4 | 11:1-4 |
| | | | 11:5-7 | 11:5-10 |
| | | 11:7-16 | | |
| | | | 11:8 | |
| | | | 11:9-11 | |
| | | | | 11:11-16 |
| | | | 11:12 | |
| | | | 11:13-15 | |
| | | | 11:16 | |
| ኢየሱስ ትንሳኤና ሕይወት | ኢየሱስ ትንሳኤና ሕይወት | | ኢየሱስ ትንሳኤና ሕይወት | |
| 11:17-27 | 11:17-27 | 11:17-27 | 11:16-19 | 11:17-27 |
| | | | 11:20-22 | |
| | | | 11:23 | |
| | | | 11:24 | |
| | | | 11:25-26 | |
| | | | 11:27 | |
| ኢየሱስ አለቀሰ | ኢየሱስና ሞት-የመጨረሻው ጠላት | | ኢየሱስ አለቀሰ | |
| 11:28-37 | 11:28-37 | 11:28-37 | 11:28-31 | 11:28-31 |
| | | | 11:32 | 11:32-42 |
| | | | 11:33-34ሀ | |
| | | | 11:34ለ | |
| | | | 11:35-36 | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | 11:37 | |
| አልዓዛር ወደ ሕይወት ተመለሰ | አልዓዛር ከሞት ተነሳ | | አልዓዛር ወደ ሕይወት ተመለሰ | |
| 11:38-44 | 11:38-44 | 11:38-44 | 11:38-39ሀ | |
| ኢየሱስን ለመግደል የተደረገው ሴራ | ኢየሱስን ለመግደል የተደረገው ሴራ | | በኢየሱስ ላይ የተደረገው ሴራ | የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስነ ለመግደል ወሰኑ |
| 11:45-53 | 11:45-57 | 11:45-53 | 11:45-48 | 11:45-54 |
| | | | 11:49-52 | |
| | | | 11:49-52 | |
| | | | 11:53-54 | |
| 11:54 | 11::54 | | | ፋሲካ ቀረበ |
| 11:55-57 | | 11:55-57 | 11:55-57 | 11:55-57 |

### ሦስተኛ የምንባብ ዑደት (አንቀ.5ን ይመልከቱ።)
*በአንቀጽ ደረጃ የመጀመሪያውን ፀሐፊ ዓላማ መከተል*

ይህ ማብራሪያ የጥንት *መመሪያ* በመሆኑ ስለመትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ። እያንዳንዳችን መጓዝ ያለብን ባለን መረዳት መሠረት ነው። በአተረጓጎም ወቅት አንተ፣ መንፈስ ቅዱስና መጽሐፍ ቅዱስ ቅድሚያ የሚሰጣችሁ ናችሁ። በመሆኑም ይህን ጉዳይ በሚያብራራው ሰው ላይ ማድረግ የለብህም።

አንቀጹን ሁሉ በአንድ ቅጽበት አንብበው። ድርጊት ፈጻሚችን ለያቸው፤ የራስህን አከፋፈል ከአምስቱ ትርጓሜዎች ጋር አነፃጽረው። በአንቀጽ መከፋፈል በእግዚአብሔር መንፈስ መነዳት የሚደረግ ባይሆንም (በእስተንፋሰ እግዚአብሔር) የአተረጓጎም ምሠሶ የሆነውን የመጀመሪያውን ጸሐፊ ዋና ዓላመ ለመከተል ግን ቁልፍ ጉዳይ ነው። ማንኛውም አንቀጽ የሚያወሳው አንድና አንድ ጉዳይ ነው።

1. የመጀመሪያ አንቀጽ
2. ሁለተኛ አንቀጽ
3. ሶስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተ

### ሥነ መለኮታዊ ድምዳሜ

የምዕራፍ 11 ሥነ መለኮታዊ ጠቀሜታ
1. የኢየሱ ኃይልና ሥልጣን ቀጣይነት እንዳለው
2. ኢየሱስ ይከብር ዘንድ የአልዓዛር መሞት በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ያለ ነው (ምዕ. 9:3)
3. ማረታ ከኢየሱስ ጋር ያደረገችው ንግግር በንስሐ ለመመለስ ትልቅ ዕድል የሰጣትና ኢየሱስም ራሱን የበለጠ እንዲገልጥ ዕድል የሚሰጥ ነው/የሚያደርግ ነው (ትነሳኤና ሕይወት ቁ.25)

4. ኢየሱስ አሁንም የዘላለም ሕይወትን ይሰጣል (የሚታይ ሥነ-ፍፃሜ)፡፡ ይህም በአልዣዛር ከሞት መነሳት የተገለጠ ነው፡፡ ኢየሱስ በሞትም ላይ ሥልጣን ነበረው!
5. ይሁን እንጂ በዚህ ሁሉ ታላላቅ ተአምራት ውስጥ አለማመን እንደቀጠለ ነው (ማለትም ይቅር የማይባል ኃጢአት፤ ልዩ ርዕስ 5፡21ን ይመልከቱ፡፡)!

## የቃልና የሐረግ ጥናት

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 11፥1-16
[1]ከማሪያምና ከእህትዋ ከማርታ መንደር ከቢታንያ የሆነ አልዓዛር የሚባል አንድ ሰው ታሞ ነበር፡፡ [2]ማርያምም ጌታን ሽቱ የቀባችው እግሩንም በጠጉርዋ ያበሰችው ነበረች፡፡ ወንድምዋም አልዓዛር ታሞ ነበር፡፡ [3]ስለዚህ እህቶቹ ጌታ ሆይ እነሆ የመትወደው ታሟል ብለው ወደ እርሱ ላኩ፡፡ [4]ኢየሱስም ሰምቶ ይህ ሕመም የእግዚአብሔር ልጅ በእርሱ ይከብር ዘንድ ነው እንጂ ለሞት አይደለም አለ፡፡ [5]ኢየሱስም ማርታንና እህትዋን አልዓዛርንም ይወድ ነበር፡፡ [6]እንደ ታመመም በሰማ ጊዜ ያን ጊዜ በነበረበት ሥፍራ ሁለት ቀን ዋለ፣ [7]ከዚህም በኋላ ለደቀማዛሙርቱ ወደ ይሁዳ ደግሞ እንሂድ አላቸው፡፡ [8]ደቀመዛሙርቱ ምምህር ሆይ አይሁድ ከጥቂት ጊዜ በፊት ለወግሩህ ይህልጉ ነበር፡፡ ደግሞሞ ወደዚያ ትሄዳለህን? አሉት፡፡ [9]ኢየሱስም መልሶ ቀኑ አስራ ሁለት ሰዓት አይደለምን ? ኢየሱስም መለሰ፡- ቀኑ አሥራ ሁለት ሰዓት አይደለምን ? በቀን የሚመላለስ ቢኖር የዚህን ዓለም ብርሃን ያያልና አይሰናከልም፤ [10]በሌሊት የሚመላለስ ቢኖር ግን ብርሃን በእርሱ ስለሌለ ይሰናከላል አላቸው፡፡ ይህን ተናገረ፣ [11]ከዚህም በኋላ ወደጃችን አልዓዛር ተኝቶአል፤ ነገር ግን ከእንቅልፉ ላስነሳው እሄዳለሁ አላቸው፡፡ [12]እንግዲህ ደቀ ማዛሙርቱ ጌታ ሆይ ተኛቶስ እንደሆነ ይድናል አሉት፡፡ [13]ኢየሱስ ስለሞቱ ተናግሮ ነበር፤ እነርሱ ግን ስለእንቅልፍ መተኛት እንደተናገር መሰላቸው፡፡ [14]እንግዲህ ያን ጊዜ ኢየሱስ በግልጥ አልዓዛር ሞተ፤ [15]እንድታምኑም በዚያ ባለመኖሬ ስለእናንተ ደስ ይለኛል፤ ነገር ግን ወደ እርሱ እንሂድ አላቸው፡፡ [16]ስለዚህ ዲዲሞስ የሚሉት ቶማስ ለባልነጀሮቹ ለደቀማዛሙረት፡- ከእርሱ ጋር እንሞት ዘንድ እኛ ደግሞ እንሂድ አለ፡፡

11፡1 "አንድ ሰው ታሞ ነበር" ይህም የሚያሳየው ለረጅም ጊዜያት ታሞ እንደነበር ነው፡፡ ይሁን እንጂ ያላለቀው ጊዜ አመልካች "መታመም ጀመረ" ተብሎ ሊተረጎም ይችልል፡፡

▣ "አልዓዛር" ይህ በእብራይስጥ "ኤልኤዘር" ማለት ሲሆን ትርጉሙ "እግዚአብሔር ይረዳል" ወይም "እግዚአብሔር ረዳት ነው" ማለት ነው፡፡ ዮሐንስ አንባቢዎች ኢየሱስ ከማርያም፣ ከማረታ እና ከአልዓዛር ጋር የነበረው ወዳጅነት ያውቃሉ ብሎ ገምቷል (ሉቃ 10፡38-42፣ ይህም በወንጌላት ውስጥ ሰለእነርሱ የተሰጠው ብቸኛው ገለፃ ነው)፡፡

▣ "ቢታንያ" ይህ ሥፍራ በምዕ.1፡28 እና በምዕ 10፡40 ላይ በዮርዳኖስ ወንዝ በኩል ለኢያሪኮ ቅርብ ከሆነው ቢታኒያ የተለየ ነው፡፡ ይሔኛው ቢታኒያ ከኢየሩሳሌም በስተደቡብ ምዕራብ በግምት ሁለት ማይል ርቀት ላይ ልክ እንጀ ደብረ ዘይት ተራራ በተመሣሣይ ሰርጥ ላይ የሚገኝ ነው፡፡ ይህም ሥፍራ ኢየሱስ በኢየሩሳሌም በነበረበት ወቅት የሚወደው ሥፍራ ነበር፡፡

▣ "ማርያም" ይህ በእብራይዕሥጥ "ሚሪያም" ማለት ነው፡፡

▣ "ማርታ" ይህ በአረማይክ "" ለሚለው ቃል ስያሜ ነው፡፡ ታላቅ የሆነችው ማርታ በመጀመሪያ አለመጠቀሷ ያልተለመደ ነው፤ ምናልባት ከሉቃስ 10፡38-42 ጋር ሊዛመድ ይችላል፡፡ 11፡12 "ማርያምም ጌታን ሽቱ የቀባችው እግሩንም በጡጉርዋ ያበሰችው ነበረች" ቁጥር 2 በዮሐንስ የተደረገ ሌላ የኤዲቶሪያል ጭማሪ ነው (ማለትም TEV; NET)፡፡ ይሔኛው የማርያምን ታሪክ (12፡2-8) ከማቴዎስ (26፡6-13) እና ከማርቆስ (24፡3-9) ጋር የሚነፃፀር ነው፡፡ በሉቃ 7፡36 ላይ ሽቱ በመቀባት የተጠቀሰችው ሴት የተለየች ናት፡፡

ይህ ጥቅስ ክስተት የሚገለጸው በወንጌላት ውስጥ ገና ሳላልተመዘገበ ጉዳይ ነው፡፡ የተመዘገበውም በምዕራፍ 12 ውስጥ ነው፡፡ ብዙዎችም የሚገምቱት ዮሐንስ የመልዕክቱ አንባቢዎች ስለዚህ ቤተሰብ ከሌሎች ምንጮች እንዳወቁ ነው፡፡

**ልዩ ርዕስ፡፡ መቀባት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ (BDB603)**

ሀ. ለቁንጂና ጥቅም ላይ ይውል ነበር (ዘዳ.28፡40፤ ሩት 3፡3፤ 2ኛ ሳሙ.12፡20፤ 14፡2፤ 2ኛ ዜና 28፡15፤ ዳን.10፡3፤ አሞ.6፡6፤ ሚክ.6፡15)
ለ. እንግዶችን ለመቀበል (መዝ.23፡5፤ ሉቃ.7፡38፡46፤ ዮሐ.11፡2)
ሐ. ለፈውስ አገልግሎት (ኢሳ.6፡1፤ኤር.51፡8፤ ማር.6፡13፤ሉቃ.10፡34፤ያዕ.5፡14) (ከንጽህና ጋር በተያያዘ

ሕዝ.16:9)

*መ. ለመቃብር ዝግጅት* (ዘፍ.50:2፤2ኛዜና 16:14፤ማር.16:1፤ዮሐ.12:3፣7፤19:39-40)

*ሠ. በኃይማኖታዊ አውድ ጥቅም ላይ ይውል ነበር* (ዘፍ.28:18፤20፤31:13) [*አምድ*]፡- ዘፀ.29:36 [*መሠዊያ*] ዘፀ 30:26፤ 40:9-16፤ዘሌ.8:10-13፤ዘሑ.7:1 (*የማደሪያው ድንኳን*)

*ረ. መሪዎችን ለመሾም*

1. ካህናትን
   - *ሀ.* አሮን (ዘፀ 28:41፤ 29:7፤ 30:30)
   - *ለ.* የአሮንን ልጆች (ዘፀ. 40:15፤ዘሌ.7:36)
   - *ሐ.* የተለመደው ሐረግ ወይም ሹመት (ዘሑ.3:3፤ዘሌ.16:32)
2. *ነገሥታትን*
   - *ሀ.* በእግዚአብሔር (1ኛ ሳሙ.2:10፤ 2ኛ ሳሙ.12:7፤ 2ኛ ነገ.9:3፤6:12፤ መዝ.45:7፤ 59:20)
   - *ለ.* በነብት (1ኛ ሳሙ. 9:16፤ 10:1፤ 15:1:17፤16:3፣12-13፤ 1ኛ ነገ.1: 45፤ 19:15-16)
   - *ሐ.* በካህናት (1ኛ ነገ.1:34፣39፤ 2ኛ ነገ.11:12)
   - *መ.* በሽማግሌዎች (*መሳ.* 9:8:15፤ 2ኛ ሳሙ. 2:7፤ 5:3፤ 2ኛ ነገ. 23:30)
   - *ሠ. ኢየሱስ እንደ መሲሃዊ ንጉሥ* (*መዝ*.2:2፤*ሉቃ*.4:18 [ኢሳ.6:1]፤ የሐዋ.4:27፣ 10:38፤ *ዕብ*.1:9 [*መዝ*.45:7])
   - *ረ.* የኢየሱስ ተከታዮች (2ኛ ቆሮ. 1:21፤ 1ኛ ዮሐ. 2:20-27 [ካሪዝማ]
3. *ምናልባት ነብያት* (ኢሳ.61:1)
4. *የማያምኑ የእግዚአብሔር ማዳን መገለጫዎች*
5. *ቃልን ወይም ማዕረግን "መሲህ" ማለት "የተቀባው" ማለት ነው* (*Anointed*)

11:3 **"እህቶቹ ወደ እርሱ ላኩ"** ኢየሱስ ከዮርዳኖስ ማዶ በነበረው በኋላ መልዕክት ላኩበት፡፡

▣ **"እነሆ የምተወደው ታሟል"** ይህ የሚያመለክተው ኢየሱስ ከዚህ ቤተሰብ ጋር ያለውን ግንኙነት ነው፡፡ ይህም "ፊሎ" የሚለውን የግሪኩን ቃል ነው፡፡ ይህን እንጂ በተለመደው የግሪክ ቋንቋ "ፊሎ" እና "አጋፔ" የሚሉት ቃላት ተለዋዋጭነት አላቸው (ቀ.5፤ 3:35፤5:20)፡፡

11:4 **"ይህ እመም የእግዚአብሔር ልጅ በእርሱ ይከብር ዘንድ ስለ እግዚአብሔር ክብር እንጂ ለሞት አይደለም አለ፡፡"** ይህ የሚያሳየው /የሚያመለክተው/ አልዓዛር መታመሙን አስቀድሞ ያውቅ እንደነበር ነው፡፡ እግዚአብሔር ኃይሉን በእርሱ በመግለጥ አልዓዛርን ከሞት ያስነሳው ዘንድ እንዲሞት ፈቀደ፡፡ ሕመምና ስቃይ አንዳንድ ጊዜ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ሎሆኑ ይችላሉ (9:3፤ የኢዮብ መጽሐፍ፡ 2ኛ ቆሮ. 12:7-10)፡፡

▣ **"የአግዚአብሔር ክብረ"** የኢየሱስ *ሥራዎች የሚያሳዩት* የ"እግዚአብሔርን ክብር" ነው፡፡ በምዕ. 1:14 ላይ ያውን ማብራሪያ ይመልከቱ፡፡

▣ **"የእግዚአብሔር ልጅ በእርሱ ይከብር ዘንድ"** "የእግዚአብሔር" የሚለው ሐረግ በፓፒረስ በተፃፉ የግሪክ P45 ወይም P66 ምንጮች ውስጥ የሚገኝ አይደለም፡፡ የተጠቀሰው ሕመም ለአብም ለወልድም ክብርን የሚያመጣ ነው፡፡ የኢየሱስ ክብር በዚህ ሁኔታ አንድ ሰው ከሚጠብቀው በጣም የተለየ ነው፡፡ በጠቅላላው የዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ቃሉ የሚያመለክተው ወደ ኢየሱስ መስቀልና ስለ እርሱ መክብር ነው፡፡ የአልዓዛርም ከሞት መመለስ የአይሁድ አመራር የኢየሱስን መሞት እንዲፈልጉ ያነሳሳቸው ነገር ነው፡፡

11:5 በዮሐንስ የተሰጠ ሌላ የኤዲቶሪያል ማብራሪያ ነው (ቁ.36)

11:6 **"በነበረበት *ሥፍራ* ሁለት ቀን ዋለ"** ኢየሱስ አልዓዛር እስኪሞት ድረሥ ዘገየ! ኢየሱስ እንዲያው ዝም ብሎ እየቀለደ አልነበረም፤ ነገር ግን በዚህ ሕመም ውስጥ መለኮታዊ ዓላመ /ሐሳብ ነበረው (ቁ.15፤ 9:3)፡፡

11:7 **"ከዚህም በኋላ"** ለደቀማዛሙርቱ "ወደ ይሁዳ ደግሞ እንሂድ አላቸው፡፡" የሚቀጥለው ውይይት የሚያመለክተው ነገር ደቀመዛሙርቱ አይሁድ ኢየሱስን ሊወግሩት እንደፈለጉ አስቀድመው ያውቁ እንደነበር ነው (ቁ.8፤ 8:54፤10:31-39)፡፡ ደቀመዛሙርቱም እምነትና ፍርሃት ያተቀላቀሉበት ግራ የሚያጋባ ሁኔታን ያሳዩበት ነበር (ቁ.16)፡፡ ምንም እንኳን ቶማስ

እንደተጠራጣሪ ደቀመዝር በተለምዶ ቤተሰብም በዚህ ሥፍራ ግን አኪየሱስ ጋር ለመሞት እንደተዘጋጀ እንመለከታለን (ቀ.16)፡፡

ሚካኤል ማአል NT TraNsliNe በሚለው መጽሐፍ (ገጽ 345 ምዕ.43 ላይ) በቁ.7 ላይ "እንሂድ" የሚለውን "እኔ ግን እሄዳለሁ" ብሎ በማሻሻል ግሩም የሆነ ምልከታን ያደርጋል፡፡ ደቀመዛሙርት የፈሩና የተጠራጠሩ የነበረ ቢሆንም ኢየሱስ ግን ልበ ሙሉ ነበር፡፡ ከኢየሱስ ጋር የተባበረው (እንሂድ) በቁ.16 ላይ ቶማስ ብቻ ነበር፡፡

**11:9-10** ይህ ምናልባት ምዕራፉን ወደኋላ በመመለስ ከምዕ. 8:12 እና ከምዕ.9:4-5 ጋር ለማገናኘት የታሰበ ይመስላል (12:35)፡፡ ቁጥር 9ሀ "አዎን" የሚል መላሽን ይጠብቃል፡፡

የእግዚአብሔርን ፈቃድ በሚከተሉ (ማለትም ኢየሱስ) እና በማይከተሉት (ቁ.10 አይሁዶች) መካከል በጣም ግልጽ የሆነ ተቃርኖ ይታያል፡፡ ኢየሱስ አግዚአብሔር በሚመራው መንገድ መሄዱ ስህተትን እየፈፀመ አይደለም፤ ምክንያቱም እርሱ የዓለም ብርሃን ነውና!

ይህ በብርሃንና በጨለማ መካከል ያለ ተቃርኖ የዕብራውያን የጥበብ ሥነ ጽሑፍ እና የኩምራን ጽሑፎች መገለጫ ነው (ማለትም የብርሃን ልጆች ከጨለማ ልጆች ወይም "የብርሃን ልጆች ከጨለማ ልጆች ጋር ያለቸውን ጦርነት"ን የሚያወሡ ጥቅሎች)፡፡

▣ **"ቢኖር…ቢኖር"** እነዚህ ሁለቱም የሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡ ይህም የሚያሳየው ድርጊትን ለመፈጸም ዕድል መኖሩን ነው፡፡

**11:11 "ወዳጃችን አልዓዛር ተኞቶአል"** ይህ ግሥ ያልተፈጸመ የድርጊትን ተቀባይነትን የሚያመለክት ነው፡፡ ደቀመዛሙርት ብዙ ጊዜ ኢየሱስ የሚናገረውን በቀጥታ ስለሚተረጉሙት ኢየሱስ የሚላቸውን ለመረዳት ይቸግራቸው ነበር (ቁ.13)፡፡ ኢየሱስ ሞትን ለመግለጽ ይህን ምሳሌ መጠቀሙ ከብሉይ ኪዳን አጠቃቀም የመነጨ ነው (ዘዳ.31:16፤ 2ና ሳሙ. 7:12፤ 1ኛ ነገ. 1:21፤ 2:10፤ 11:21-43፤14:20፣ ወዘተ)፡፡ "መቃብር" የሚለው የእንግሊዝኛው ቃል እና "እንቅልፍ" የሚለው የግሪኩ ቃል ሥርወ-መሠረታቸው/ምንጫወው/ ተመሣሣይ ነው፡፡

**11:12 "ከሆነ"** ይህ አንደኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ሲሆን ከጸሐፊው እይታ አንፃር ወይም ከሥነ-ጽሑፋዊ ዓላመው ሲል እውነት ተደርጎ የተገመተ /የተወሰደ/ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

▣ **"ተኞቶስ እንደሆነ ይድናል"** ይህ በጥሬ ትርጉሙ "ማዳን" የሚል ሲሆን በብሉይ ኪዳን አጠቃቀሙ "አካላዊ ነፃ መውጣት"ን ያሳያል (ያዕ.5:15)፡፡ አሁንም ደቀመዛሙርት የኢየሱስን ንግግር ሊረዱ አይችሉም፤ ምክንያቱም የኢየሱስን ተምሳሌታዊ ንግግር በጥሬ ትርጉሙ ስለወሰዱት ነው (ማለትም ተኝቶስ ከሆነ)፡፡ ይህ ያለመረዳት ሁኔታ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ጎልቶ የሚታይ ነው (ማለትም ቁ. 23-24)፡፡ እርሱ ከላይ የመጣ ሲሆን እነርሱ ግን ከታች ናቸው፡፡ ያለመንፈስ ቅዱስ እርዳት (ጴንጤቆስጤ) እነርሱ ሊረዱት አይችሉም!

**11:13** ይህ በዮሐንስ የተሰጠ ሌላው ኤዲቶሪያል ማብራሪያ ነው፡፡

**11:14 "ኢየሱስ በግልጥ… አላቸው"** ልዩ ርዕስ በሚለው ላይ በምዕ.7:4 ላይ *parrhesia* (ፓርሄስያ) የሚለውን ይመልከቱ፡፡

**11:15 "እንድታምኑም በዚያ ባለመኖሬ ስለእናንተ ደስ ይለናል"** የአልዓዛር ከሞት መነሣት እርሱ ከአልዓዛር ጋር ወዳጅነት ስላለው ወይም ማርምና ማርታ በጣም በጣም ሰላዘኑ ሳይሆን (ቁ.11) ኢየሱስ (1) የደቀመዛሙርቱን እምነት ለማሳደግ (ቁ.14) እና (2) የአይሁድን ሕዝብ እምነት ለማበረታታት (ቁ.42) ነበር፡፡ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ እምነት ሂደት ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሲያድግ /ማለትም መዕ.2:11)፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ አያድግም (ማለት፡- ተመልካቾች ምዕ. 3:31-59)፡፡

**11:16** ይህ ጥቅስ በግልጽ የሚያሳየው የቶማስን እምነት ነው፡፡ ከኢየሱስ ጋር ለመሞት እንኳ ፈቃደኛ ነበር፡፡ ቀደ መዛሙርት የሰው ልጅ ታላቅ ፍርሃት የሆነውን በሞት ላይ ኢየሱስ ሥልጣን እንዳለው ማየት ፈልገው ነበር፡፡

ቶማስ የሚለው ሥም በአራማይክ "መንትያ" (ሌላ ኤዲቶሪያል ማብራሪያ) ሲሆን ይህም ዲዲሞስ ከሚለው የግሪኩ ቃል ጋር ተመሣሣይነት አለው፡፡ ወንጌላት እንደ ሐዋሪያ ይዘረዝሩታል (ይጠቅሱታል) (ማቴ.10:3፤ ማር. 3:18፤ ሉቃ. 6:15)፤ የዮሐንስ ወንጌልም ስለእርሱ ብዙ ጊዜ ጠቅሷል (11:16፤14:5: 20:24-29፤ 21:2)፡፡ ልዩ ርዕስ በሚለው ሥር የሐዋርያት ስሞች ዝርዝር በሚለው ይመልከቱ፡፡ (1:45)፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 11÷17-27
**[17]ኢየሱስም በመጣ ጊዜ በመቃብር እስከ አሁን አራት ቀን ሆኖት አገኘው፡፡ [18]ቢታንያም አሥራ አምስት ምዕራፍ ያህል ለኢየሩሳሌም ቅርብ ነበረች፡፡ [19]ከአይሁድም ብዙዎች ስለ ወንድማቸው ሊያጽናኑአቸው ወደ ማርታና ወደ ማርያም መጥተው ነበር፡፡ [20]ማርታም ኢየሱስ እንደ መጣ በሰማች ጊዜ ልትቀበለው ወጣች፤ ማርያም ግን በቤት ተቀምጣ ነበር፡፡**

**[21]ማርታም ኢየሱስን። ጌታ ሆይ፥ አንተ በዚህ ኖረህ ብትሆን ወንድሜ ባልሞተም ነበር፤ [22]አሁንም ከእግዚአብሔር የምትለምነውን ሁሉ እግዚአብሔር እንዲሰጥህ አውቃለሁ አለችው። [23]ኢየሱስም፦ ወንድምሽ ይነሣል አላት። [24]ማርታም፡- በመጨረሻው ቀን በትንሣኤ እንዲነሣ አውቃለሁ አለችው። [25]ኢየሱስም፦ ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል፤ [26]ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም፤ ይህን ታምኚያለሽን? አላት። [27]እርስዋም፦ አዎን ጌታ ሆይ፤ አንተ ወደ ዓለም የሚመጣው ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆንህ እኔ አምናለሁ አለችው።**

11:17 "**በመቃብር እስካሁን አራት ቀን ሆኖተ አገኘው**" የአይሁድ ራቢዎች እንደሚሉት የሰው መንፈስ እስከ ሦስት ቀን ድርስ ከአካሉ ጋር አብሮ እንደሚቆይ ይናገራሉ። የአይሁድ ራቢዎችን ተስፋ ከንቱ ባደረገ ሁኔታ አልዓዛር በእውነት ከሞተ በኋላ እስከ አራተኛው ቀን ዘግይቶ መጣ።

11:18 "**አስራ አምስት ምዕራፍ ያህል**" /ሁለት መይል ያህል፡ ቁ.18 በዮሐንስ የተሰጠ ሌላ ኤዲቶሪል ማብራሪዬ ነው።

11:19 "**ከአይሁድም ብዞዎች ስለወንድማቸው ሊያጽናኑአቸው ወደ ማረታና ወደ ማርያም መጥተው ነበር**" ይህ የኢየሱስ ጠላቶች የሆኑትን "አይሁድ" የሚለውን ቃል ለመግለጥ የዋለ ያለተለመደ አጠቃቀም ነው። ይህን እንጂ በዚህ ዓውድ/አገባብ/ የሚያመለክተው በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ነዋሪዎችንና ይህንንም ቤተሰብ የሚያውቁትን ለማሳየት ነው (ቁ.31፣33፣45)።

11:20 **ማርየም ግን በቤት ተቀምጣ ነበር**" በአይሁድ የለቅሶ ሥርዓት የተለመደው አቀማመጥ መሬት ላይ መቀመጥ ነበር፡

**ልዩ ርዕስ፡ የሐዘን ልማዶች**

እሥራኤላውያን የሚወዱትን ሰው በሞት ሲያጡ እና በግላቸው ንስሐ ሲገቡ እንዲሁም ደግሞ በጋራ ስለተደረገ ጥፋት ንስሐ ሲገቡ የሚሰማቸውን ሐዘን በቴለያዩ መንገዶች ይገልጻሉ፡-

1. ከላይ የተለበሰን ካባ መቅደድ (ዘፍ.37÷29፡34፤44÷13፤መሳ.11÷35፤2ኛ ሳሙ.1÷11፤3÷31፤1ኛ ነገ.21÷27፤ኢዮ.1÷20)
2. ማቅ ይለብሱ ነበር (ዘፍ.37÷34፤2ኛ ሳሙ.3÷31፤1ኛ ነገ.21÷27፤ኤር.48÷37)
3. ጫማን ያወልቃሉ፡- 2ና ሳሙ. 15፡30፤ ኢሳ.20፡3
4. እጆችን ራስ ላይ ያደርጋሉ፡- 2ኛ ሳሙ. 13፡9፤ ኤር 2፡37
5. በራስ ላይ አመድ መነስነስ (ኢያ.7÷6፤1ኛ ሳሙ.4÷12፤ ነህ.9÷1)
6. መሬት ላይ መቀመጥ (ሰቆ.2÷10፤ሕዝ.26÷16 (መሬት ላይ መጋደም 2ኛ ሳሙ.12÷16) ኢሳ.47÷1)
7. ደረትን መምታት (1ኛ ሳሙ.25÷1፤2ኛ ሳሙ.11÷26፤ናሆ.2÷7)
8. አካልን መቁረጥ (ዘዳ.14÷1፤ኤር.16÷6፤48÷37)
9. መጾም (2ኛ ሳሙ.1÷16፡22፤1ኛ ነገ.21÷27)
10. በሐዘን ማንጎራጎር (2ኛ ሳሙ.1÷17፤3÷31፤2ኛ ዜና 35÷25)
11. ራሰ በራ መሆን (ጸጉርን በመንጨት ወይም በመላጨት፡- ኤር.48÷37)
12. ጺምን አሳጥሮ መቆረጥ (ኤር.48÷37)
13. ራስን ወይም ፊትን መሸፈን (2ኛ ሳሙ. 15÷30)

11:21፤32 "**ማርታም ኢየሱስን ጌታ ሆይ አንተ በዚህ ኖረህ ብትሆን ወንድሜ ባለሞተም ነበር።**" ይህ ሁለተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፈተ ነገር ነው። ይህም "ከእውነታው የሚቃረን" ማለት ነው። ይህንንም እንዲህ መረዳት ይቻላል፤ "አንተ ከእኛ ጋር ኖረህ ቢሆን በእርግጥ አልነበርክም ወንድሜ አይሞትም ነበር ነገር ግን ሞተ;; በማለት። የማርታና የማርያም ንግግሮች (ቁ.32) ተመሣሣይ ነበሩ። ይህንንም ጉዳይ በአራቱ የሐዘን ቀናት ተወያይተው ነበር ማለት ነው። እነዚህ ሁለተ ሴቶች ኢየሱስ ቀደም ብሎ ባለመምጣቱ የተሰማቸውን ቅሬታ ለመግለጽ ምንም ወደኋላ ያሉ አልነበሩም።

11:22 "**አሁንም ከእግዚአብሔር የምትለምነውን ሁሉ እግዚአብሓር እንዲሰጥህ አምናለሁ**" ማርታ ኢየሱስ ምን እንዲያደርግላት እንደፈለገች በትክክል ለማወቅ ያስቸግራል ምክንያቱም በቁ 39 ላይ በአልዓዛር ው ሕይወት መመለስ ግራ ተጋብታ ስለነበር ነው።

11:23-24 "**ወንድምሽ ይነሳል**" ፈሪሳውያን በመጨረሻው ቀን የሙታን ትንሳኤ እንደሚያምኑ ሁሉ ማርታም ከሞተ በኋላ ሰላለው ሁኔታ ተመሳሳይ ሥነ-መለከታዊ አመለካከት ነበራት። በብሉይ ኪዳንም ስለዚህ አመለካከት የተወሰነ ማስረጃ አለ (ዳን.12:2፤ ኢዮ. 14::4፤19:25-27)። ኢየሱስም ይህንን የአይሁዶች መረዳት ወደ ተግባር በመለወጥ የርሱን ሥልጣንና ኃይል ገለጠ (ቁ.25፤14:6)።

11:24 **"በመጨረሻው ቀን"** *ምንም እንኳ ዮሐንስ ወደያው ስለሚከተለው ድነት (የአሁን ነገር ፍፃሜ) ትኩረት መስጠቱ እውነት ቢሆንም የመጨረሻው ዘመንን ፍርድ አሁንም ይጠብቃል። ይህም ያተገለጠው በተለያዩ መንገዶች ነው፤*

1. ፍርድ/የትነሳኤ ቀን/ 5:28-29፤ 6:39-40፤ 44፣54፤ 11:24፤12:48)
2. "ሰዓት" (4:23፤ 5:25፣28፤ 16::32)
3. የክርስቶስ ዳግም ምፅአት (14:3፤ ምዕ.14:18-19፣ እና 28 እና ምዕ.16:16፣ 22 ኢየሱስ ከትንሣኤ በኋላ ያለውን መልክ እንጂ በዳግም ምፅአት ያለውን መልክ አያሳዩም ማለት ይቻላል)።

11:25 **"ኢየሱስም፡-ትንሳኤና ሕይወት እኔ ነኝ"** ይህ ኢየሱስ "እኔ ነኝ" እያለ ከተናገራቸው ሰባት አረፍተ ነገሮች አንዱ ነው። በአልዓዛር መሞት ማርታ ወንድሟ በሕይወት እንደሚኖር ተበረታታ ነበር። ይህም ተስፋ የተመሠረተው በእግዚአብሔርና በኢየሱስ ማንነትና ኃይል ላይ ነው (5:21) በ18:12 ላይ ያለውን ማብሪሪያ ይመልከቱ።

በጣም የሚያስደንቀው የቀድሞው የፓፒረስ ምንጭ (P[45]) እና የተወሰኑ የላቲን ብሉይ እንዲሁም የሦሪያ እና "የዲያትሳሮን" እትሞች "እና ሕይወት" የሚለውን ሐረግ መግደፋቸው ነው። UBS[3] ለመካተታቸው የ"B" ደረጃን ሲሰጥ UBS[4] ደግሞ የ"A" ደረጃን (እርግጠኛ) ይሰጠዋል።

11:26 **"ሕያው የሆንም የሚምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም"** ይህ ክፍል በጣም አስፈላጊ የሆኑ *ሥነ-ትርጉማዊ ገፅታዎች* አሉት።

1. *ሁሉን አቀፍ የሆነው ተውላጠ ስም "ሁሉም" የሚለው*
2. *የአሁን ጊዜ ገላጭ ግሦች-እምነቱ ቀጣይነት እንዳለው የሚያመለክቱ* (ቀ. 25፣26)
3. *"ሞት" ከሚለው ጋር ሁለት ጊዜ የተጠቀሰው አሉታዊ ቃል፡- "በፍጹም፤ በፍጹም አይሞትም" በማለት መንፈሳዊ ሞትን በግልጽ ያመለክታል።*

*በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ዘላለማዊ ሕይወት ለአማኞች አሁን የሚታይ እውነታ እንጂ ወደፊት ብቻ የሚከሰት አይደለም። በዚህም አልዓዛር የኢየሱስን ቃል እውነትነት ያሳያል። ለዮሐንስ፤ ዘላለማዊ ሕይወት አሁን የሚታይ አውነት ነው።*

11:27 **"አዎን ጌታ ሆይ አንተ ወደ ዓለም የሚመጣው ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆንህ እኔ አምናለሁ"** *ይህ ዓረፍተ ነገር የተገለጸው የድርጊት መጠናቀቅን በሚያመለክት የጊዜ አመልካች ነው። ይህ ኢየሱስ ተስፋ ያተገባው መሲህ እንደሆነ የገለጸችበት ጠንካራ የእምነት አቋሟ ነው። ከሥነ-መለኮት አንጻር ይህ ጴጥሮስ በቂሣርያ ስለኢየሱስ ከሰጠው የእምነት አቋም ጋር ተማሳሳይ ነው* (ማቴ.16)።

*ማርታም እምነቷን ለመግለጽ ያተለያዩ ማዕረጎችን/መጠሪያዎችን ትጠቀማለች፤*

1. *ክርስቶስ/መሲህ፣ የተቀባው የሚለው የግሪኩ ትረጉም)*
2. *የእግዚአብሔር ልጅ (መሲህ ለሚለው የብሉይ ኪዳን ማዕረግ)*
3. *የሚመጣው (አዲሱን የጽድቅ ሕይወት እንደሚያመጣ በእግዚአብሔር የተሰጠው ተስፋ መሆኑን የሚያሳይ የብሉይ ኪዳን ማዕረግ ነው፤ ምዕ.6:4)*

*ዮሐንስ ክርክርን የእግዚእሔርን እውነት ለማስተላለፍ እንደ ሥነ-ጽሑፋዊ ቴክኒክ የጠቀማል። በወንጌላት ውስጥ ስልኢየሱስ ያለው የእምነት አቋሞችን የሚያሳዩ ብዙ ሥፍራዎች አለ* (1:29፣29፣34፣41፣49፤ 4:42፤ 6:44፣ 69፤ 9:35-38፤ 11:27)። *በልዩ ርዕስ ላይ በምዕ 2:23 ላይ እምነት የሚለውን ቃል ዮሐንስ እንዴት እንደተተቀመ የሚገልጸውን ይመልከቱ።*

**NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 11÷28-29**
**[28]ይህንንም ብላ ሄደች። እህቷንም ማርያምን በስውር ጠርታ መምህሩ መጥቶአል ይጠራሻማል አለቻት። [29]እርስዋም በሰማች ጊዜ ፈጥና ተነሳች ወደ እርሱም መጣች።**

11:28 **"መምህር"** የNASB *የማጥኛ መጽሐፍ ቅዱስ* (ገጽ 1540) *የተሸለ ማብራሪያን ይሰጣል፡- "በአንዲት ሴት የተሰጠ ጠቃሚ የሆነ አገላለጽ፤ ረቢዎች ሴቶችን አያስተምሩም* (4:27) *ኢየሱስ ግን ብዙ ጊዜ አሰተምሯቸዋል።"*

**ልዩ ርዕስ፡ ሴቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ**

I. ብሉይ ኪዳን
*ሀ. ከባህል አንጻር ሴቶች እንደ ንብረት ይታያሉ*

1. በንብረት ዝርዝር ውስጥ ተካተዋል (ዘፀ 20÷17)
2. የባሪ ሴቶች አያያዝ (ዘፀ.21÷7-11)
3. የሴቶች መሃላዎች ወይም ቃል ኪዳኖች በማህበረሰቡ ኃላፊነት ባለባቸው ወንዶች ሊሻር ይችላል (ዘሑ.30)፡፡
4. ሴቶች በጦርነት ወቅት እንደ ዘረፋ ይቆጠሩ ነበር (ዘዳ.20÷10-14፤21÷10-14)

ለ. በተግባር የጋራ የሆኑ ባህርያት
1. ወንድና ሴት በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጠሩ (ዘፍ.1÷26-27)
2. አባትና እናትን አክብር (ማክበር ዘፀ 20÷12 ዘዳ. 5÷16)
3. እናትንና አባትን መፍራት (ዘሌ. 19÷3፤20÷9)
4. ወንድና ሴት ናዝራውያን ሊሆኑ ይችላሉ ( ዘሑ. 6÷1-2)
5. ሴት ልጆች የመውረስ መብት አላቸው (ዘሑ.27÷1-11)
6. የቃል ኪዳን ሕዝብ ክፍል ናቸው (ዘዳ.29፡10-12)
7. የአባትንና የእናትን ትምህርት (ቃል መከተል (ምሳ.1÷8፤6÷20)
8. የሔዋን ወንድና ሴት ልጆች ‹የሌዊ ብተሰብ) በቤተመቅደስ ውስጥ አምልኮን ይመሩ ነበር (1ኛ ዜና 25÷5-6)
9. በመጨረሻው ዘመን ወንድና ሴት ልጆች ይተነብያሉ (ኢዮዔ.2÷28-29)፡፡

ሐ. ሴቶች በአመራር ቦታ/ሚና
1. ማርያም፣ የሙሴ እህት ነብይት ተብላ ነበር (ዘፀ. 15÷20-21) እንዲሁም ሚክ.6÷4ን ይመልከቱ፡፡
2. ለማደሪው ድንኳን የሚያገልግሉ ነገሮችን ለመሸመን እግዚአብሔር ሥጦታን ሰጥቷቸው ነበር (ዘፀ.35÷25-26)፡፡
3. ሁሉንም የእሥራኤል ነገዶች የመራች ዲቦራ የተባለች ሴት ነብይት ነበረች (መሳ.4÷4-5፤ 5÷7)
4. ጠፍቶ የነበረውን እና በኂላም የተገኘውን የ‹‹ሕጉን መጽሐፍ›› ታነበው እና ትተረጉመው ዘንድ ንጉሥ ኢዮሲያስ የለመናት ህልዳና ነብይት ነበረች (2ኛ ነገ.22÷14፤2ኛ ዜና 34÷22-27)፡፡
5. የእግዚአብሔር ሰው ንግሥት አስቴር በፋርስ የነበሩትን አይሁድ ከሞት ታደገች፡፡

II. አዲስ ኪዳን

ሀ. ከባህል አንጻር በአይሁድ እና በግሪኮ-ሮማን ዓለም ከተወሰኑ መብቶች ጋር እንደ ሁለተኛ ዜጎች ይቆጠሩ ነበር/ መቄዶንያ ግን በዚህ አትካከትም)/(ከመቄዶንያ በስተቀር)

ለ. ሴቶች በአመራር ሚና
1. ኤልሳቤጥና ማርያም፤ ለእግዚአብሔር የተገኙ የእግዚአብሔር ሰዎች (ሉቃ.1፡2)
2. የእግዚአብሔር ሰው ሃና በቤተመቅደስ ታገለግል ነበር (ሉቃ.2፡36)
3. ሊዲያ አማኝና የቤት ውስጥ ቤተክርስቲያን መሪ (የሐዋ.16፡14-40)
4. የፊልጶስ አራት ደናግለ ሴቶች ነብያት ነበሩ (የሐዋ.21፡8-9)
5. ፌቨን በ ክንክራኦስ ላለቸው ቤተክርስቲያን የሴት ዲያቆን ነበረች (ሮሜ. 16÷1)፡፡
6. ጵርስቅላ ከውሎስ ጋር አብራ የምትሠራና የአጵሎስ አስተማሪ (የሐዋ.18፡26፤ ሮሜ 16፡3)
7. ማርያ፣ ዩሊያን፣ ብልያጦን፣ ስንጣክ፣ የኤረስ እህት፣ እና ከጳውሎስ ጋር ይሰሩ የነበሩ በርካታ ሴቶች ነበሩ (ሮሜ 16÷6-16)፡፡
8. ዩሊያ (KJV)፣ ምናልባትም የሴት የሴት ሐዋርያ ነበረች (ሮሜ. 16÷7)::
9. ኢዮዲያና ሲንጢኬ ከጳውሎስ ጋር አብረው የሚሰሩ (ፊልጵ.4÷2-3)፡፡

III. የዘመናችን አማኝ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎችን ሚዛናቸውን እንዴት ይጠብቃል?

ሀ. የመጀመሪያዎቹን የመልእክቱን ተቀባዮች ብቻ የሚመለከቱትን ታሪካዊና ባህላዊ እውነቶችን ከዘላለማዊ እውነት አንፃር ለሁሉም ቤተክርስቲያናት በሁሉም ዘመን ለሚገኙ ሁሉም አማኞች እውነቱን እንዴት ማስተላለፍ ይቻላል?
1. በመንፈስ ቅዱስ መነዳት መልዕክቱን የጻፈውን የመጀጀመሪያውን ጸሐፊ ዋና ሃሳብ/ዓላማ በደንብ ማጤን አለብን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ በመሆኑም ለእምነትና ለተግባር ብቻኛው ምንጭ ነው፡፡
2. ታሪክ ቀመስ የሆኑ እና በእግዚአብሔር መንፈስ መሪት የተፃፉትን ጽሑፎች ማጤን አለብን፡፡
   ሀ. የእስራኤል (የሐዋ.15፤ገላ.3፤ልማዶች (የቤተክርስቲያ ሥርዓት))
   ለ. የመጀመሪያውን ክፍለ ዘመን የአይሁድ ኃይማኖት የሚያመለክት
   ሐ. የ1ኛ ቆሮንጦስ ውስጥ የተጠቀሱትን ታሪክ ቀመስ የሆኑ የጳውሎስን ጸሑፎች
      1) የአረማዊው የሮም መንግሥት የህግ ሥርዓት (1ኛ ቆሮ.6)

2) ባሪ መሆን (1ኛ ቆሮ.7÷20-24)
3) ጃንደረባነት (1ኛ ቆሮ.7÷1-35)
4) ደናግል (1ኛ ቆሮ.7÷36-38)
5) ለጣኦት የሚሰዋ ምግብ (1ኛ ቆሮ. 8፤ 10÷23-33)
6) በጌታ ራት ላይ የሚከናወኑ ያልተገቡ ነገሮች /ድርጊቶች (1ኛ ቆሮ.11)

3. በተወሰነ ወቅትና በተወሰነ ባህል ውስጥ እግዚአብሔር ራሱን ግልጽ በሆነ ሁኔታ ገልጧል፡፡ እኛ ግን በትኩረት መቀበል ያለብን መገለጡን እንጂ ማንኛውንም ከመገለቱ ጋር የተቆራኙትን ታሪካዊ ሁነቶችን አይደለም፡፡ የእግዚአብሔር ቃል የተጻፈው በተወሰነ ወቅት በተወሰነ ባህል ውስጥ በሰው ቃል የተጻፈ ነው፡፡

ለ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ አተረጓጎም የመጀመሪው ጽሐፊ ዓላማ/ሐሳብ መፈለግ አለበት፡፡ በጊዜው ለማለት የፈለገው ምን ነበር? ለትክክለኛ አተረጓጎም ይህ ወሣኝና መሠረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህን እውነት እኛ ለዘመናችን ሥራ ላይ ልናውለው ይገባል፡፡ አሁን በዚህ ክፍል ላይ በአመራር ላይ ሰላሉት ሴቶች ላይ ችግር አለ (እውነተኛው የአተረጓጎም ችግር የሚከሰተው ቃሉን መተርጎሙ ላይ ነው፡፡ እንደመሪዎች ከሚለዩት መጋቢዎች ይልቅ ብዙ አገልግሎቶች ነበሩ ማለት ነው? ወይስ ሴት ዲያቆናትና ሴት ነብያት እንደጨዋዎች ይታዩ ይሆን? ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንጦስ 14:34-35 እና 1ኛ ጢሞቲዎስ 2:9-15 ላይ ሴቶች በጉባኤ አምልኮ ላይ መምራት እንዳሌለባቸው አስረግጦ መናገሩ በጣም የተገለጠ ነው! ይሁን እንጂ ያንን እውነት ዛሬ እንዴት ነው ሥራ ላይ የማውለው? የጳውሎስም ሆነ የእኔ ባህል የእግዚአብሄርን ቃልና ፈቃዱን ዝም እንዲያሰኘው አልፈልግም፡፡ ምናልባት የጳውሎስ ዘመን ገደብ የበዛበት ሊሆን ይችላል፤ በአንፃሩም ደግሞ እኔ ያለሁበት ዘመን ደግሞ ገደብ የለበትም፡፡

የጳውሎስ ቃላትና አስተምሮዎች ሁኔታዊና የመጀመሪያው ክፍለዘመን እውነቶች ብቻ ናቸው ማለት ለእኔ አይመቸኝም፡፡ የእኔ አእምሮና የእኔ ባህል በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የጻፈን ጸሐፊ መቃወም አለበት ለማለት እኔ ማነኝና?

ይሁን እንጂ የሴተር መሪዎችን በሚመለከት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎች ሲኖሩ ታዲያ ምንድ ነው የማደርገው? (በጳውሎስ ጽሑፎች በሮሜ 16 እንኳ)? ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንጦስ ምዕ. 11-14 ላይ የሰጠው ትንታኔ ነው፡፡ በ11÷5 ላይ ሴቶች ራሳቸውን ሸፍነው በጉባኤ ላይ እንዲሰብኩና እንዲጸልዩ የሚፈቅድ ይመስላል፤ ይሁን እንጂ በ14÷34-35 ላይ ደግሞ ጸጥ እንዲሉ ይፈልጋል፡፡ ሴት ዲያቆናትና (ሮሜ. 16) እና ሴት ነብያት ነበሩ (የሐዋ.21÷9)፡፡ ይህ ልዩነት ነው እንግዲህ ጳውሎስ የሰጠው ማብራሪያ (በሴቶች ላይ ከሚደረገው ማዕቀብ ሰለሚገናኝ) በመጀመሪያው ክፍለመን ለነበሩ የቆሮንጦስና የኤፌሶን ቤተክርስቲያን ብቻ የተወሰነ ነው እንድል ነፃነትን የሚሰጠኝ፡፡ በሁለቱም ቤተክርስቲያናት ውስጥ አዲስ የተመሰረተውን ነፃነት ሴቶች ለመጠቀም ችግሮች ነበሩ፤ ይህም በጊዜው የነበረችው ቤተክርስቲያን የጠፉትን በክርስቶሰ ወንጌል ለመድረስ ችግር በፈጠረ ነበር፤ ወንጌል ይስፋፋና ፍሬያማ ይሆን ዘንድ የነበራቸው ነፃነት መገደብ ነበረበት፡፡

እኔ ያለሁበት ዘመን ከጳውሎስ አንፃር ተቃራኒ ነው፡፡ እኔ ባለሁበት ዘመን ወንጌል ምናልባት ሊገደብ የሚችለው የሰለጠኑና የተማሩ ሴቶች ወንጌልን ካለሰበኩ እንጂ ካልመሩ አይደለም! የጉባኤ አምልኮ ዋነ ግብ ምንድ ነው? ወንጌልና ደቀመዝሙርነት አይደለም? እግዚአብሔር በሴት መሪዎች ሊከብርና ደስ ሊሰኝ ይችላል? መጽሐፍ ቅዱስ በጠቅላላው ‹‹አዎን›› የሚል ይመስላል፡፡

ለጳውሎስ ሐሳብ ራሴን ማስገዛት እፈልጋለሁ፤ ምክንያቱም የእኔ ሥነ-መለኮት ከመጀመሪው የጳውሎስ ነውና፡፡ አሁን በሚታየው የሴቶች እንቅስቃሴ ተፅዕኖ እንዲደርስብኝ ወይም ማስመሰል አልፈልግም! ይሁን እንጂ ቤተክርስቲያን በግል የሚታዩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን ለምሳሌ የባርነትን ተገቢ አለመሆን፣ ዘረኝነትን፣ ልቅ ወሲብን እና አክራሪነት ላይ ምላሽ ለመስጠት ለዘብተኛ ናት፡፡ እንዲሁም ባለንበት ዘመን በሴቶች ላይ በሚደረገው ጥቃት ላይ ተገቢውን መላሽ ለመስጠት ቸልተኛ ናት፡፡ እግዚአብሔር ባሪያንም ሆነ ሴትን በክርስቶስ ነፃ  አውጥቷል፡፡ በቤተክርስቲያን የተሠራ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ  እንዲያሰራቸው አልፈቅድም፡፡

አንድ ሌላ ነጥብ ላንሳ፤ አንድ ተርጓሚ የቆሮንጦስ ቤተክርስቲያን በጣም የተበጠበጠች ቤክርስቲያን ነበረች፡፡ የካሪዝማቲክ ስጦታዎች (የጸጋ) ሽልማት ያሰጡና ያኮሩ ነበር፡፡ ምናልባትም ሴቶች በዚህ ሁኔታ ቱዘውም ሊሆን ይችላል፡፡ በኤፌሶን ባሉ የቤት ውስጥ ቤተክርስቲያናት ሴቶችን ለግል ጥቅማቸው መጠቀሚያ የሚያደርጉና ቅጥረኛ ሰባኪዎች አድርገው የሚጠቀሟቸው የሐሰት መምህራን በኤፌሶን ተጽእኖ እንደደረሰ ጭምር አምናለሁ፡፡

ሐ. ለተጨማሪ ምንባብ አስተያየት

*How to Read the Bible for All Its Worth* **በጎርደን ሊ እና ዳግላስ ስቱዋርት** (ገጽ 61-77)

*Gospel aאd Spirit: Issues iא אew Testameאt Hermeאeutics* **በጎርደን ፊ.** *Hard Sayiאgs of the Bible* **በ ዋልተር ሲ.ኬይዘር፤ ፒተር ኤች ዳቢድስ፤ ኤፍ ኤፍ ብሩስ እና ማንፍሬድ ቲ ብራንች** (ገጽ 613-616፤ 665-667)፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 11÷30-37

[30]ኢየሱስም ማርታ በተቀበለችበት ስፍራ ነበረ እንጂ ገና ወደ መንደሩ አልገባም ነበር። [31]ሲያጽናኑአት ከእርስዋ ጋር በቤት የነበሩ አይሁድም ማርያም ፈጥና እንደ ተነሣችና እንደ ወጣች ባዩ ጊዜ፥ ወደ መቃብር ሄዳ በዚያ ልታለቅስ መስሎአቸው ተከተሉአት። [32]ማርያምም ኢየሱስ ወዳለበት መጥታ ባየችው ጊዜ በእግሩ ላይ ወድቃ። ጌታ ሆይ፥ አንተ በዚህ ኖረህ ብትሆን ወንድሜ ባልሞተም ነበር አለችው። [33]ኢየሱስም እርስዋ ስታለቅስ ከእርስዋም ጋር የመጡት አይሁድ ሲያለቅሱ አይቶ በመንፈሱ አዘነ በራሱም ታወከ፤ ወዴት አኖራችሁት? አለም። [34]እነርሱም፦ ጌታ ሆይ፥ መጥተህ እይ አሉት። [35]ኢየሱስም እንባውን አፈሰሰ። [36]ስለዚህ አይሁድ፡- እንዴት ይወደው እንደ ነበረ እዩ አሉ። [37]ከእነርሱ ግን አንዳንዶቹ፡- ይህ የዕውሩን ዓይኖች የከፈተ ይህን ደግሞ እንዳይሞት ያደርግ ዘንድ ባልቻለም ነበርን? አሉ።

11:30 ይህ ሌላው የሐዋሪያዊ ጸሐፊ የአይን ምስክርነት ዝርዝር ነው፡፡

11:33፡
NASB "በመንፈሱ አዘነ፤ በበራሱም አዘነ/ታወከ"
NKJB "በምፈሱ ቃተተ፤ በራሱ ታወከ"
NRSV "በመንፈሱ በጣም ተረበሸ፤ በራሱም ታወከ"
TEV "ልቡ ተነካ፤ በራሱም ታወከ"
NJB "ኢየሱስ በጣም አዘነ"

ይህ በቀጥታ ትርጉሙ "በመንፈሱ ተረበሸ" ማለት ነው፡፡ ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ቁጣን ለመግለጽ ይጠቀሳል (ዳን.11:30-ሰብትዋጀንት)፤ ማር 11:43፤ 14:5)፡፡ ነገር ግን በዚህ አውድ ጥልቅ የሆነ ስሜትን የሚሳይ ትርጉም ስፈልጋል (ቁ. 38)፡፡ ምንም እንኳ አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱስን የሚብራሩ ይህንን ጠንካራ ስሜት፣ ምናልባትም በሞተ ላይ የተደረገ እንደሆነ ቢያዩትም ኢየሱስ ግን እውነተኛ ያለው ስሜት እንደነበረውና (ቁ.33:35:36:38) አሁንም እንዚህን ስሜቶች ለወዳጆቹ ያሳያቸዋል፡፡

11:35 "ኢየሱስም እንባውን አፈሰሰ" ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እጅግ በጣም አምና ጥቅስ ነው፡፡ ለዚህ ፕላኔት ሞት የእጊኢአብሔ ፈቃድ አይደለም፡፡ ይህ የሰው ልጆች አመጽ ውጤት ነው፡፡ ኢየሱስ ሰዎች የሚወዷቸውን በሞት ሲያጡ ይሰማዋል፡፡ እርሱን የሚከተሉት ሁሉ ስለሚያልፉበት ነገር ሁሉ ይሰማዋል!

የኢየሱስ ማልቀስ በጸጥታና በግል የተደረገ እንጂ በቁ.33 ላይ እንደተጠቀሰው በአደባባይ የተደረገ ዋታ አይደለም፡፡

11:37 ይህ ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ አለው፡፡ ይህ ጥያቄ ማርታ በቁ.21 ላይ እንዲሁም በቁጥር 32 ላይ ማርያም የሰጡት አስተያየት ነበር፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 11÷38-44

[38]ኢየሱስም በራሱ አዝኖ ወደ መቃብሩ መጣ፤ እርሱም ዋሻ ነበረ፤ ድንጋይም ተገጥሞበት ነበር። [39]ኢየሱስ፦ ድንጋዩን አንሡ አለ። የሞተውም እኅት ማርታ። ጌታ ሆይ፥ ከሞተ አራት ቀን ሆኖታልና አሁን ይሸታል አለችው። [40]ኢየሱስ፦ ብታምኚስ የእግዚአብሔርን ክብር እንድታዪ አልነገርሁሽምን? አላት። [41]ድንጋዩንም አነሡት። ኢየሱስም ዓይኖቹን ወደ ላይ አንሥቶ። አባት ሆይ፥ ስለ ሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ። [42]ሁልጊዜም እንድትሰማኝ አወቅሁ፤ ነገር ግን አንተ እንደ ላክኸኝ ያምኑ ዘንድ በዚህ ዙሪያ ስለ ቆሙት ሕዝብ ተናገርሁ አለ። [43]ይህንም ብሎ በታላቅ ድምፅ፡- አልዓዛር ሆይ፥ ወደ ውጭ ና ብሎ ጮኸ። [44]የሞተውም እጆቹና እግሮቹ በመግነዝ እንደ ተገነዙ ወጣ፤ ፊቱም በጨርቅ እንደ ተጠመጠመ ነበር። ኢየሱስም፦ ፍቱትና ይሂድ ተዉት አላቸው።

11:38 "ዋሻ" በዚያ ዘመን በፍልስጥኤም ምድር ዋሻዎች

1. የተፈጥሮ ዋሻዎች ነበሩ (Baba Bathra 6.8)
2. በሸለቆ ግድግዳዎች ላይ ተቆፍረው ክብ ድንጋዮችን በማንሸራተት የሚታተሙ ነበር፤
3. ወደ መሬት ተቆፍረው ትልቅ ድንጋይ ከላይ የሚሸፍናቸው ነበሩ፡፡

በኢየሩሳሌም አካባቢ ከተደረጉት አርኪኦሎጂካዊ ጥናቶች አንፃር የመጀመሪያው አማራም ከሁሉም የተሻለ ነው፡፡

11:39 "ድንጋዩን አንሡ" ትልቅ ድንጋይን ወደ መቃብር አንሸራትቶ መዝጋት /ማተም መቃብሮችን ከዘራፊዎችና ከእንስሳት ለመጠበቅ የሚጠቅም ዘዴ ነበር፡፡

▣ "ከሞተ አራት ቀን ሆኖታል" ይህ የግሪክ ቋንቋ ፈሊጣዊ አባባል ሲሆን በጥሬ ትርጉሙ "የአራት ቀናት ሰው" ማለት ነው፡፡

11:40 "ብ…." ይህ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ሲሆን "አዎን" የሚል መልስን የሚጠብቅ ነው፡፡

▣ **"የእግዚአብሔር ክብር"** የእግዚአብሔር ክብር የተገለጠው በኢየሱስ ድንገት ነበር (ቁ.4)፡፡ ሙሉ ማብራሪያውን በ1:14 ላይ ይመልከቱ፡፡

11:41 **"ኢየሱስ አይኖቹን ወደላይ አንስቶ"** የተለመደው የዕብራዊያን የጸሎት አቋቋም እጅግና አይንን (ከፍቶ ወደ ሰማይ ማሻቀብ ነው፡፡ ይህ ለጸሎት የተጠቀሰ ፈሊጣዊ አባባል ነው (17:1)፡፡

▣ **"ሁልጊዜም እንድትሰማኝ አውቅሁ"** ኢየሱስ አባቱን "ይሰማል" (8:20፣40፤15:15) አባቱም እርሱን "ይሰማል"፡፡ ኢየሱስን "የሚለው" የዘላለም ሕይወት አላቸው፡፡ ይህ ልክ "ማየትና" "መስማት" ከ"መቀበል" (1:12) እና ከ"ማመን" (3:16) ጋር ተነፃፃሪ መሆናቸውን ለማሳየት የተደረገ የቃላት ጨዋታ ነው፡፡ አልዓዛር የኢየሱስን ድምፅ "ሰማ" በሕይወትም ኖር፡፡

11:42 ይህ የሚገልጸው የኢየሱስን ጸሎትና ተአምር ነው፡፡ ኢየሱስ ብዙ ጊዜ ተአምራትን ያደርግ የነበረው የደቀመዛሙርቱን እምነት ለማነቃቃት ነበር፡፡

ከሥነ-መለኮት አንፃር ኢየሱስ አጉልቶ የሚያሣየው እርሱ በሚሠራው ሥራ ውስጥ የእግዚአብሔርን ሥልጣንና ቀዳሚነት ነበር (5:19:30፤8:28፤12:49፤14:10)፡፡ ይህም ተአምር የሚያሳየው ኢየሱስ ከአባቱ ጋር ያለውን የጠበቀ ግንኙነት ነው፡፡ ልዩ ርዕስ በሚለው ላይ በ5:24 ላይ መላክ (Apostollo) የሚለውን ይመልከቱ፡፡

11:43 **"በታላቅ ድምፅ አልዓዛር ሆይ ወደ ውጪ ና ብሎ ጮኸ"** ኢየሱስ አልዓዛርን ለይቶ ባይጠራው ኖር ማለው መቃብር ወደ ውጪ በመጣ ነበር ይባላል!

11:44 ሙታን ለቀብር ሊዘጋጁ በመጀመሪያ በውኃ ይታጠባሉ፤ ከዚያም ሽቶውን ለመከላከል የሚረዱ ቅመማት በተረጨበት የላይነን ልብስ የጠቀለላሉ፡፡ በአይሁድ ልማድ መሠረት ሙታን በሃያ አራት ጊዜ ውስጥ መቃብር ነበረባቸው ምክንያቱም አይሁዶች ሙታናቸውን አካሉ እንዳይፈርስ ምንም ነገር አይቀቡም ነበር፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ የቀብር ልማዶች**

I. ሜሴፖታሚያ
   ሀ. ከሞት በኋላ ላለው ሕይወት ትክክለኛው አቀባበር በጣም አስፈላጊ ነበር፡፡
   ለ. ምሳሌ የሚሆን የሜሶፖታሚያ እርግማን ‹‹ምድር ሬሳህን አትቀበል›› የሚል ነው፡፡
II. ብሉይ ኪዳን
   ሀ. ተገቢ አቀባበር በጣም አስፈላጊ ነበር (መክ.6:3)
   ለ. በፍጥነት የሚካሄድ ነበር (ሳራ በዘፍጥረት 23 እና ራሔል በዘፍ 35:9 እና በዛዳ.21:23
   ሐ. ተገቢ ያሆነ አቀባበር የመጠላትና የኃጢያት ምልክት ነበር፡፡
      1. ዘዳግም 28÷26
      2. ኢሳያስ 14÷20
      3. ኤርምያስ 8÷2፤23:19
   መ. የሚቻል ከሆነ በአቅራቢያው ባለ የቤተሰብ መካነ መቃብር ይከናወን ነበር፡፡
   ሠ. እስከሬን የማድረቅ ሥርዓት፤ በግብ ፅ እንደሚደረግ አልነበረም፡፡ የሰው ልጅ ከአፈር እንደመጣ ሁሉ ወደ አፈር መመለስ አለበት (ለምሳሌ ዘፍ. 3÷19፤ መዝ.103÷14፤ 104÷29
   ረ. በረቢዎች የአይሁድ ሥርዓት ከሙት አካላት ጋር በተያየዘ ለሚደረግ ሥነ-ሥርዓት ያለውን መርከስ ለአካሉ ክብር ለመስጠትና ለመንከባከብና ሚዛንን ለመጠበቅ በጣም አስቸጋሪ ነበር፡፡
III. አዲስ ኪዳን
   ሀ. ቀብር የሚከናወነው ሞትን ተከትሎ በሃያ አራት ጊዜ ውስጥ በፍጥነት ነው፡፡ አይሁዶች ነፍስ ወደ አካሉ ተመልሳ መምጣት ትችላለች ብለው ለሦስት ቀናት ሲጠባበቁ ነበር (ዮሐ.11÷39)፡፡
   ለ. ቀብር ሙት አካልን ማጠብንና በቅመሞች መጠቅለልን የሚያካትት ነበር (ዮሐ.1÷44፤ 19÷39-40)
   ሐ. በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የፍልስጥኤም ምድር በመቃብር የሚደረጉ ምንም ዓይነት የቀብር ሂደቶች በአይሁዶችም ሆነ በክርስቲያኖች ዘንድ አልነበርም፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 11÷45-46
**[45]ስለዚህ ወደ ማርያም ከመጡት፥ ኢየሱስም ያደረገውን ካዩት ከአይሁድ ብዙዎች በእርሱ አመኑ፤ [46]ከእነርሱ አንዳንዶቹ ግን ወደ ፈሪሳውያን ሄደው ኢየሱስ ያደረገውን ነገሩአቸው፡፡**

11:45 **"ስለዚህ..... ከአይሁድ ብዞዎች በእርሱ አመኑ"**:- ይህ ነው የወንጌሉ ማዕከላዊ መልዕክት (ዮሐ.20:30-31)። ይህም ሐረግ በተደጋጋሚ የሚታይ ነው (2:23፤ 7:31፤ 8:30፤ 10:42፤ 11:45፤12:11፡42)። ይሁን እንጂ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ እምነት የተለያዩ ደረጃዎች እንዳሉትና ለማመን የሚያበቃ ብቻ እንዳልሆነ በደንብ መታወቅ አለበት (2:23-25፤8:30)። በምዕ.2:23 ላይ ልዩ ርዕስ የሚለውን ይመልከቱ።

11:46 **"ከእነርሱ አንዳንዶቹ ግን ወደ ፈሪሳዊያን ሄደው ኢየሱስ ያደረገውን ነገሯቸው"** በእንዲህ ዐይነት አስደናቂ ትምህርትና ታላላቅ ተአምራት ፊት እንዲህ ዓይነቱ መንፈሳዊ እውርነት መታየቱ የሚገርም ነው። ይሁን እንጂ ኢየሱስ ሁሉንም ቡዶኖች በሁለት ይከፍላቸዋል፤ እርሱን ለማመን የሚመጡትና ስለእርሱ የተባለውን እውነት የሚቃወሙ፤ እንዲዚህ ዓይነቱ ኃይለኛ ተአምር እንኳ እምነትን አያመታም / አይፈጥርም (ሉቃ.16:30-31)።

> NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 11÷47-53
> [47]**እንግዲህ የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ሸንጎ ሰብስበው። ምን እናድርግ? ይህ ሰው ብዙ ምልክቶች ያደርጋልና። [48]እንዲሁ ብንተወው ሁሉ በእርሱ ያምናሉ፤ የሮሜም ሰዎች መጥተው አገራችንን ወገናችንንም ይወስዳሉ አሉ። [49]በዚያችም ዓመት ሊቀ ካህናት የነበረ ቀያፋ የሚሉት ከእነርሱ አንዱ። እናንተ ምንም አታውቁም፤ [50]ሕዝቡም ሁሉ ከሚጠፋ አንድ ሰው ስለ ሕዝቡ ይሞት ዘንድ እንዲሻለን አታስቡም አላቸው። [51]ይህንም የተናገረ ከራሱ አይደለም፥ ነገር ግን በዚያች ዓመት ሊቀ ካህናት ነበረና ኢየሱስ ስለ ሕዝቡ ሊሞት እንዳለው ትንቢት ተናገረ፤ [52]ስለ ሕዝቡም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን የተበተኑትን የእግዚአብሔርን ልጆች ደግሞ በአንድነት እንዲሰበስባቸው ነው እንጂ። [53]እንግዲህ ከዚያ ቀን ጀምረው ሊገድሉት ተማከሩ።**

11:47 **"የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ሸንጎ ሰብስበው"** ይህ የሚያመለክተው በኢየሩሳሌም ያለውን የአይሁዶች ትልቁን ፍርድ ቤት የሆነውን ነው። ሰባ የሚሆኑ የክልል አካላት ነበሩት። ሊቀ ካህናት የነበሩት ፖለቲካዊና ኃይማኖታዊ ዝንባሌ የነበራቸው ሰዱቃውያን ሲሆኑ እነርሱም የሙሴን መፃህፍት የተቀበሉና ትንሳኤን የሚክዱ ነበሩ። ፈሪሳዊያን ደግሞ የበለጠ ተሰሚነት የነበራቸው፣ ወግ-አጥባቂ የኃይማኖት ቡድኖች ሲሆኑ አቋማቸውም (1) ሙሉውን ያብሉይ ኪዳንን (2) የመላዕክትን አገልግሎት (3) ከሞት በኋላ ያለውን ሕይወት። ነገር ግን እነዚህ ሁለት የማይስማው ቡድኖች ለአንድ ዓላማ መጣመራቸው የሚያስገርም ነገር ነው። በምዕ. 1:24 ላይ ፈሪሳውያን የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ። በምዕ.3:1 ላይ ሸንጎ የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።

▣ **"ይህ ሰው ብዙ ምልክቶች ያደርጋልና"** ኢየሱስን "ይህ ሰው" ማለት ስሙን በንቀት የመጥራት አካሄድ ነው። እንደዚህ ባሉት ተአምራት ልክ እንደ አልዓዛር ከሞት መነሳት ስለራሳቸው አስቀድሞ የነበራቸው ትምክህት አይኖቻቸውን/ህሊናቸውን ሙሉ በሙሉ ማሳወሩ እንዲሁ የሚገርም ነገር ነው (2ኛ ቆሮ. 4:4)።

11:48 **"ብ"** ይህ ሶስተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ነው። ይህም ደርጊት ለመፈጸም እድል መኖሩን ያመለክታል።

▣ **"ሁሉ በእርሱ ያምናሉ"** ቅናት እንዲሁም ሥነ-መለኮታዊ አለመግባባት ኢየሱስን ያለማመናቸውና እርሱን የመፍራታቸው ምንም ነበር፡ "ሁሉ" የሚለው ቃል ምናልባት ሳምራውያንና አረማውያንን ሳያመለክት አይቀርም (10:16)። እንዲሁም ሌላው ለመፍራታቸው ምክንያቱ ፖለቲካዊ ይዛት ነበረው (በሮማዊያን መያዝ)።

▣ **"የሮሜም ሰዎች መጥተው አገራችንን ወገናችንንም ይወስዳሉ"** ይህ ከዮሐንስ ወንጌል ትንቢቶች አንዱ ነው፤ ምክንያቱም ይህ ትንቢት የተሟላው በ70 ዓ.ም. ቲቶ በተባለው የሮም ጄኔራል (በኋላም ገዢ) ነበር።

የሮም አገዛዝ እውነታ የአይሁዶች የመጨረሻው ዘመን (ሥነ-ፍፃሜዊ) ተስፋው ዋናው ክፍል ነው። እግዚአብሔር አንድ ኃይማኖታዊ ወይም ወታደራዊ አካል፤ ልክ እንደ ብሉይ ኪዳን መሣፍንት ከሮም አገዛዝ ነፃ የሚያወጣቸው እንደሚመጣ/እንደሚልክላቸው ያምኑ ነበር። ይሁን እንጂ አስመሳይ መሲሆች ይህን መጠባበቅ ለመፈፀም/ለማሟላት በፍልስጥኤም ምድር አመፅን ጀምረው ነበር።

ኢየሱስም የእርሱ መንግሥት ጊዜያዊ/ፖለቲካዊ አገዛዝ (18:36) ሳይሆን በመላው ዓለም ወደፊት እንደምትስፋፋ ገልፆአል። ኢየሱስም ቀደም ሲል በብሉይ ኪዳን የተነገሩ ትንቢቶችን እንደሚያሟላ ተናገር፤ ነገር ግን በአይሁዳዊነት፣ በሚታይ መልክ እንዲሁም በብሔራዊ ስሜት አይደለም። ለዚህም ነው በጊዜው በነበሩት በአብዛኞቹ አይሁዶች ዘንድ ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረው።

11:49 **በዚያችም ዓመት ሊቀካህናት የነበረ ቀያፋ የሚሉት"** ሊቀ ካህንነት ማለት የእድሜ ልክ ሥልጣንና ወደ ልጅ ጮምር የሚተላለፍ ነው (ዘፀ 28) ነገር ግን ሮማዊያን ድል ካደረጉ ወዲህ ለሐብታሞች ተላልፎ ይሸጥ ነበር። ምክንያቱም በደብረ ዘይት ተራራ እና በቤተመቅደሱ አካባቢ ትርፋመ ንግድ ስለነበር ነው። ቀያፋም ሊቀ ካህን ሆኖ ያገለገለበት ከክርስቶስ ልደት በኋላ ከ18-36 ዓ.ም. ድረስ ነበር (ከ6-15-ከ.ል.በኋላ ያገለግል የነበረው አናንያ አማች)።

11:50-52 ይህ ሌላው የዮሐንስ ምፀታዊ ምሳሌ ነው። ቀያፋ ግን በሚገርም ሁኔታ ወንጌልን እየሰበከ ነበር!

11:50 **"አንድ ሰው ስለሕዝቡ ይሞት ዘንድ እንዲሻለን"** አይሁዶች በአካል ላይ ስለሚደረግ ቅጣት ያላቸው አመለካከት የብሉይ ኪዳን የኋላ ታሪክ ያለው ነው፡፡ አንድ ሰው ደግሞ ይሁን መጥፎ/መላውን ሕዝብ ሊጎዳ ይችላል (ማለትም ለምሳሌ አዳም/ሔዋን፤ አካን)፡፡ ይህ ሐሳብ በተለይም ንስሐ በመግባት ቀን የነበረው የብሉይ ኪዳን የመሥዋእት ሥርዓትን መሠረት የሚያጠናክር ነው (ዘሌ. 16)፡፡ በዚህም ምንም ኃጢአት ወይም ነበር የሌለበት እንስሳ የመላውን ሕዝብ ኃጢአት ይሸከማል፡፡ ይህም ከኢሳያስ 53 ላይ ያለ የመሲሁ ሐሳብ ነው፡፡ በአዲስ ኪዳንም አዳም/የክርስቶስ ተምሳሌት የሆነው በሮሜ 5፡12-21 ይህንን ሐሳብ ያንፀባርቃል፡፡

11:51

| | |
|---|---|
| NASB;REV;NET | **"ኢየሱስ ሊሞት እንዳለው"** |
| NKJV;NIV;REB | **"ኢየሱስ ይሞታል"** |
| NRSV | **"ኢየሱስ ሊሞት ነበር"** |
| NJB | **"ኢየሱስ ሊሞት ነበር"** |

"NIDOTTE" የተባለው ማብራሪያ በ2ኛው ቅጽ፤ ገጽ 326 ላይ melle ("አለበት""የግድ"፤ "እርግጠኛ ለመሆን") ለሚለው ግሥ ጥሩ የሆነ ሥነ-መለኮታዊ ማብሪሪያን ይሠጣል፡፡ ይህም እግዚአብሔር በክርስቶስ የማዳን ሥራ ውስጥ ያለውን ፈቃድ የሚያሳይ ነው፡፡

1. ማርቆስ 10:32
2. ማቴዎስ 17:22
3. ሉቃስ 9፡31፡44፤34:21፤ 26:23
4. ዮሐ 7፡39፤ 11፡51፤ 12፡33፤ 14፡22፤ 18፡32

እንዲሁም የይሁዳና የመክዳት ችግር ለማሳየት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

1. ሉቃስ 22:23
2. ዮሐ.6:71፤19:4

ሉቃስ በሐዋሪያት ሥራ ውስጥ ትንቢታዊ መሟለትን ለመልከት ተጠቅመታል (የሐዋ.11:22፤24:15፤26:22)፡፡ ሁሉም የማዳን ሥራዎች በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ያሉ ናቸው (የሐዋ.2:23፤3:18፤4:28፡13:39)!

11:52 **"የተበተኑትን የእግዚአብሔርን ልጆች ደግሞ በአንድነት እንዲሰበስባቸው እንጂ"** ይህ ዮሐንስ ወንጌሉን ሲያዘጋጅ የሰጠው ማብራሪያ ይመስላል፤ ይህም ከምዕ. 10፡16 ጋር ሊነፃፀር የሚችል ነው፡፡ እንዲሁመም ደግሞ

1. ከፍልስጥኤም ምድር ውጭ ያሉትን አይሁዶችን ሊያመለክት ይችላል፡፡
2. ገሚስ አይሁዶች ልክ እንደሳምረዊያንነ ሊያመለክት ይችላል፡፡
3. አህዛብንም ሊያመለክት ይችላል፡፡

ነገር ግን ሦስተኛው አማራጭ ከሁሉም የተሻለ ይመስላል፡፡ የትኛውም ይሁን፤ የኢየሱስ ሞት "ለሚያምነው" የሰው ዘር በሙሉ አንድነትን/ሕብረትን የሚያመጣ ነው (1፡29፣3፡16፣4፡42፤10፡16)፡፡

11:53 **"እንግዲህ ከዚያ ቀን ጀምረው ሊገሉት ተማከሩ"** ይህ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ተደጋግሞ የሚጠቀስ መልዕክት ነው (5:18፤7:19፤8:59፤10:39፤11:8)፡፡

> NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 11÷54
> **[54]ከዚያ ወዲያም ኢየሱስ በአይሁድ መካከል ተገልጦ አልተመላለሰም፤ ነገር ግን ከዚያ በምድረ በዳ አጠገብ ወዳለች ምድር፥ ኤፍሬም ወደምትባል ከተማ ሄደ፤ በዚያም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተቀመጠ፡፡**

11:54 **"ከዚያ ወዲያም ኢየሱስ በአይሁድ መካከል ተገለጠ አልተመላለሰም** ነበር፡፡ ዮሐንስ 12 ኢየሱስ ከኃይማኖት መሪዎች ጋር ያደርገው የመጨረሻው መከራ ነበር፡፡

"ተገለጠ" የሚለው ቃል (7፡26፤11፡54፤18፡20) ብዙውን ጊዜ ትርጉም "በድፍረት" ማለት ነው፡፡ በምዕራፍ 7፡4 ላይ ልዩ ርዕስ የሚለውን ይመልከቱ፡፡

▣ **"ኤፍሬም ወደምትባል ከተማ"** ይህች ከተማ ምናልባተ በሰማርያ ወደምትገኝ ቤቴል ለምትባል ሥፍራ የቀረበች ናት፡

> NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 11÷55-57
> **[55]የአይሁድም ፋሲካ ቀርቦ ነበር፡፡ ብዙ ሰዎችም ራሳቸውን ያነጹ ዘንድ ከፋሲካ በፊት ከአገሩ ወደ ኢየሩሳሌም ወጡ፡፡ [56]ኢየሱስንም ይፈልጉት ነበር፤ በመቅደስም ቆመው እርስ በርሳቸው፡፡ ምን ይመስላችኋል? ወደ በዓሉ አይመጣም ይሆንን? ተባባሉ፡፡ [57]የካህናት አለቆችም ፈሪሳውያንም ይይዙት ዘንድ እርሱ ያለበትን ስፍራ የሚያውቀው ሰው ቢኖር እንዲያመለክታቸው አዘው ነበር፡፡**

**11:55-57** እነዚህ ግሦች ምዕ.11 እና ምዕ.12ን አጣምረው የሚይዙ ናቸው።

**11:55 "ራሳቸውን ያነጹ ዘንድ"** ይህ የሚያመለክተው ለፋሲካ በዓል ዝግጅት የሚደረግ የመንጻት ሥርዓትን ነው። እስከዛሬ ድረስ ኢየሱስ በፍልስጥኤም ምድር ለምን ያህል ጊዜ እንዳስተማረ፣ እንደሰበከ እና እንዳገለገለ አከራካሪ ጉዳይ ነው። ለአንድ ወይም ለሁለት ዓመታት እንደቆየ የወንጌላት አወቃቀር ያሳያሉ። ይሁን እንጂ የዮሐንስ ወንጌል በርከት ያሉ ፋሲካዎች አሉት (ዓመታዊ በዓል)። በእርግጠኝነት የሰፈሩ በሦስት ቦታዎች ላይ ተጠቅሰዋል (2:13፤6:4 እና 11:55)፤ ቢያንስ አረተናው ደግሞ በምዕ.5፡1 ላይ "በዓል" የሚለውን ይጠቁማል።

**11:57** ይህ አዘጋጅ ከዮሐንስ ወንጌል ላይ የሰጠው አስተያየት ነው።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት _መመሪያ_ ሊሆን የሚችል ማብራሪያ ስለሆነ ለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ። እያንዳንዳችን ልንሄድ የሚገባን ባለን መረዳት መጠን ነው። አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጎም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣችሁ ናችሁ። በመሆኑም ይህንን ጉዳይ በሚያብራራው ሰው ላይ ብቻ ልትተው አይገባህም።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት በመጽሐፉ ውስጥ የተነሡትን ዋና ዋና ጉዳዮች በጥሞና እንድታጤናቸው ነው። የተነሡትም ጥያቄዎች እንደ ሃሳብ-አነሳሽ ሆነው እንጂ በቀጥታ አይደለም።

1. ኢየሱስ አልዓዛር እንዲሞት ለምን ፈቀደ?
2. የተፈጸመው ተአምር ማንን የሚመለከት ነበር?
3. በትንሣኤ እና ነፍስን በመመለስ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
4. የአይሁድ መሪዎች በአልዓዛር መነሳት የተቆጡት ለምንድን ነው?

# ዮሐንስ 12

## በተሻሻሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀጽ አከፋፈል

| UBS[4] | NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| በቢታንያ መቀባት | በቢታንያ መቀባት | በቢታንያ መቀባት | በቢታንያ መቀባት | በቢታንያ መቀባት |
| 12:1-8 | 12:1-8 | 12:1-8 | 12:1-6 | 12:1-8 |
| | | | 12:7-8 | |
| በአልዓር ላይ ሴራ | በአልዓር ላይ ሴራ | | በአልዓር ላይ ሴራ | |
| 12:9-11 | 12:9-11 | 12:9-11 | 12:9-11 | 12:9-11 |
| ወደ ኢየሩሳሌም በድል መግባት | በድል መግባት | የሆሳዕና በዓል | ወደኢየሩሳሌም በድል መግባት | መሲሁ ወደ ኢየሩሳሌም ገባ |
| 12:12-19 | 12:12-19 | 12:12-19 | 12:12-13 | 12:12-19 |
| | | | 12:14 | |
| | | | 12:15 | |
| | | | 12:16 | |
| | | | 12:17 | |
| | | | 12:18-19 | |
| አንዳንድ ግሪኮች ኢየሱሰን ፈለጉት | ፍሬያም የስንዴ ቅንጣት/ዘር | የኢየሱስ የአደባባይ አገልግሎት ማብቃት | አንዳንድ ገሪኮች ኢየሱስን ፈለጉት | ኢየሱስ የሚመጣውን ሞትና ክብር ተነበየ |
| 12:20-26 | 12:20-26 | 12:20-26 | 12:20-21 | 12:20-28ሀ |
| | | | 12:22-26 | |
| የሰው ልጅ ከፍ ሊል ይገባዋል | ኢየሱስ በመስቀል ላይ ስለመሞቱ አልቀ. ተናገረ | | ኢየሱስ ስለሞቱ ተናገረ | |
| 12:27-36ሀ | 12:26-37 | 12:27-36ሀ | 12:27-36ሀ | |
| | | | 12:28ለ | 12:28ለ |
| | | | 12:29 | 12:29-32 |
| | | | 12:30-33 | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | | 12:33-36ሀ |
| | | | 12:34 | |
| | | | 12:35-36ሀ | |
| የአይሁድ አለማመን | ምስክርነታችንን ማን አመነ | | የሕዝቡ አለማመን | |
| 12:36ለ-43 | | 12:36ለ-43 | 12:36ለ-38 | 12:36ለ |
| | | | | ማጠቃለያ፡- የአይሁድ አለማመን |
| | | 12:37-41 | | 12:37-38 |
| | | | 13:39-40 | 12:39-40 |
| | ብርሃኑ መመላለስ | | 12:42-43 | 12:42-50 |
| የኢየሱስ ቃል ይፈርዳል | 12:42-50 | | የኢሱስ ቃል ይፈርዳል | |
| 12:44-50 | | 12:44-50 | 12:44-50 | |

**ሦስተኛ የንባብ ዑደት (አንቀጽ 5ን ይመልከቱ፡፡)**
*የመጀመሪውን ጸሐፊ ዓላማ በአንቀጽ ደረጃ መከተል*

ይህ ማብራሪያ የጥናት <u>መመሪያ</u> በመሆኑ ስለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ፡፡ እያንዳንዳችን መሔድ/መጓዝ ያለብን በውስጣችን ባለው መረዳት መሠረት ነው፡፡ አንተ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጎም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣችሁ ናችሁ፡፡ በመሆኑም ይህንን ጉዳይ አስተያየት ባሚሰጠው ሰው ላይ መተው የለብህም፡፡

ምዕራፉን ሁሉ በአንድ ቅጽበት አንብበው፡፡ ስለምን እንደሚናገርም ለያቸው፡፡ የራስህን የአንቀጽ አከፋፈል ከአምስቱ ትርጉሞች ጋር አነጻጽራቸው፡፡ በአንቀጽ መከፋፈል በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት የሚደረግ ባይሆንም (እስትነፋሰ እግዚአብሔር) የአተረጓጎም እምብርት የሆነው የመጀመሪያውን ጸሐፊ ዓላማ ለመከተል ግን ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ ማንኛውም አንቀጽ የሚያወሳው ስለአንድ ጉዳይ ብቻ ነው፡፡

1. የመጀመሪያ አንቀጽ
2. ሁለተኛ አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወ.ዘ.ተ.

**ከቁ1-50 ላሉት ዓውዳዊ መረዳቶች**

ሀ. አራቱም ወንጌላት ኢየሱስ በአንዲት ሴት ስለመቀባቱ ይናገራሉ፡፡ ስለዚህም ይህ ክስተት ለወንጌላቱ ጸሐፊዎች አስፈላጊ ጉዳይ ነበር ማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ማር.14፡3-9፤ ማቴ.2፡6-13 እንዲሁም ዮሐ.12፡2-8፡፡ የሚታንያዋ ማርያም የአልዓዛር እህት ብሎ ሲለያት ሉቃስ 7፡36-50 ደግሞ በገላላ ያለች ኃጢአተኛ ሴት ብሎ ይለያታል፡፡

ለ. ምዕራፍ 12 የኢየሱስን የአደባባ አገልግሎት ማብቃት ይዘግባል (ቁ. 29)። ኢየሱስም በተደጋጋሚ ጊዜያት የአይሁድ መሪዎችን ወደ እምነት እንዲመቱ ሙከራ አድርጎ ነበር። ምዕራፍ 11 የሚያወሳው በኢዩሳሌም ከተማ የሚኖሩትን ሰዎች ወደ ማመን ለማምጣት ያደረገውን ጥረት ነው።

ሐ. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ አምስት አይነት የሰዎች ቡድኖችን እንመለከታለን።

1. የአልዓዛርን ወደ ሕይወት መመለስ የመሰከረው ሕዝብ ቁ 17
2. ከኢየሩሳሌም የመጣው ሕዝብ ቁ. 19።
3. የፋሲካን በዓል ለማክበር የመጡ ቁ 12፣18፣29፣34።
4. ምናልባትም የአህዛብ ወገኖች ቁ.20
5. ምናልባትም ኢየሱስን ያመኑ የአይሁድ መሪዎች ቀ. 42

**የቃልና የሐረግ ጥናት**

**NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 12÷1-8**

**[1]ከፋሲካም በፊት በስድስተኛው ቀን ኢየሱስ ከሙታን ያስነሣው አልዓዛር ወደ ነበረበት ወደ ቢታንያ መጣ። [2]በዚያም እራት አደረጉለት፤ ማርታም ታገለግል ነበር፤ አልዓዛር ግን ከእርሱ ጋር ከተቀመጡት አንዱ ነበረ። [3]ማርያምም ዋጋው እጅግ የከበረ የጥሩ ናርዶስ ሽቱ ንጥር ወስዳ የኢየሱስን እግር ቀባች፤ በጠጕርዋም እግሩን አበሰች፤ ቤቱም ከናርዶስ ሽቱ ሞላ። [4]ነገር ግን ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ አሳልፎ ሊሰጠው ያለው የስምዖን ልጅ የአስቆሮቱ ይሁዳ። [5]ይህ ሽቱ ለሦስት መቶ ዲናር ተሸጦ ለድሆች ያልተሰጠ ስለ ምን ነው? አለ። [6]ይህንም የተናገረ ሌባ ስለ ነበረ ነው እንጂ ለድሆች ተገድዶላቸው አይደለም፤ ከረጢትም ይዞ በውስጡ ከሚገባው ይወስድ ስለ ነበረ ነው። [7]ኢየሱስም፦ ለምቀብርበት ቀን እንድትጠብቀው ተውአት፤ [8]ድሆችስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ይኖራሉና፥ እኔ ግን ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር አልኖርም አለ።**

12፡1 **"ከፋሲካም በፊት በስድስተኛው ቀን"** ይህ በማቴ.26፡2 ላይ ካለው ለየት ያለ የጊዜ ቅደም ተከተል ነው። መታወስ ያለበት ጉዳይ የወንጌላት ቀዳሚው ትኩረት በጊዜ ቅደም ተከተል ላይ አይደለም፤ ይሁን እንጂ የኢየሱስን ስብዕናና (ማንነት) ሠራውን ማሣየት አውነትን አጉልተው ያሳያሉ። ወንጌላት የሕይወት ታሪኮች ሳይሆኑ ትኩረት ለተደረገባቸው ክፍሎች የሚሰጡ የወንጌል ትራክቶች ናቸው።

12፡2 **"እነርሱ"** ይህ በአልዓዛር ከሞት መነሳት ምክንያት ለኢየሱስና ለደቀመዛሙርቱ እራት ያዘጋጁት የቢታንያ ከተማ ሰዎችን የሚያመለክት ይመስላል። ይሁን እንጂ በማቴ.26፡6 ይህ የተከናወነው በለመጻሙ በስምዖን ቤት ነው።

12፡3 **"ዋጋው"** ይህ ፓውንድ የሚለውን የሮም ቃል የሚያመለክት የላቲን ቃል ነው። ይህም 340 ግራም ያህል ነው። ይህ ውድ የሆነ ሽቶ ምናልባትም ለማርያም በጥሎሽ መልክ የተሰጠ ሳይሆን አይቀርም። ብዙዎች ያላገቡ ሴቶች እንዲህ አይነቱን ሽቶ በአንገቶቻቸው ዙሪያ ያደርጉ ነበር;ይለብሱ ነበር።

▣

| | |
|---|---|
| NASB | **"ዋጋው እጅግ የከበረ የጥሩ ናረደዶስ ንጥር"** |
| NKJV | **"ዋጋው እጅግ የከበረ የዘይት ንጥር ወስዳ"** |
| NRSV | **"ከጥሩ የናርዶስ ንጥር የተዘጋጀ ዋጋው እጅግ የከበረ ሽቶ"** |
| TEV | **"ከጥሩ የናርዶስ ንጥር የተዘጋጀ ሙሉና ውድ የሆነ የከበረ ሽቶ"** |
| NJB | **"ዋጋው እጅግ የከበረ ከጥሩ ናርዶስ ንጥር የተዘጋጀ ቅባት"** |

በተጠቀሰው ቅጽል ትርጉም ላይ በግምት የሚነገሩ ብዙ ነገሮች አሉ፤ (1) ጥሩ (2) ፈሳሽ (3) የቦታ ሥም የሚሉ ናቸው። ሽቶው ራሱ ውድ ከሆነና መልካም መዓዛ ካለው የሄማሊያ (ከሂማሊያ የመጣ) ሥራ የሚገኝ ነው። ይህንንም ጄምስ ኤም ፍሪማን Manners and Customs of the Bible ገጽ 379-380 ላይ ይመልከቱ።

▣ **"የኢየሱስን እግር ቀባች"** ሌሎች ወንጌላት ይህንን ክስተት (ምናልባትም አልዓዛርን ከሞት ስላስነሳላት ለኢየሱስ ያቀረበችው ምስጋና ይሆናል። ቁ.2) ሴትየዋ በኢየሱስ ራስ ላይ ሽቶውን እንዳፈሰሰችው ይናገራሉ። ማርያም ግን በትክክል መላውን አካሉን ከራሱ ጀምራ እስከ እግሩ ድረስ እንደቀባችው ይታወቃል። የኢየሱስም እግር የተገለጠበትም ምክንያት ዠርቅ ባለ መደገፊያ ላይ /ጠረጴዛ/ በግራ ክንዱ ተደግፎ ስለነበር ነው።

ይህም ከዮሐንስ ጣምራ አገላለጽ አንዱ ነው። የንጥሩ አስፈላጊነት የመተን አካል ለቀብር ሥርዓት ለማዘጋጀት ነበር (19፡40)። ከሌሎች ደቀመዛሙርት ይልቅ ማርያም ኢየሱስ በቅርብ እንደሚሞት የበለጠ መረዳት ሳይኖራት አይቀርም (ቀ.7)። በምዕ.11፡2 ላይ ልዩ ርዕስ በሚለው መቀባት የሚለውን ይመልከቱ።

▣ **"ቤቱም ከናርዶስ ሽቱ ሞላ"** ይህ በስዕላዊ መልክ የቀረበ የአይን ምስክርነት ገለጻ ነው። ዮሐንስ ፍንትው ባለ ሁኔታ ገጠመኙን ያስተውላል!

12:4 **"የአስቆርቱ ይሁዳ"** "አስቆርቱ" የሚለው ቃል ሁለት መሠረታዊ አመጣጥ አሉት፡፡

1. የይሁዳ ከተማ (ቂርያት ኢያሱ 15:25 ወይም
2. "የነፍሰገዳይ ቤላ/ጩቤ" ለሚለው የተሰጠ ቃል

ከሁሉም የወንጌላት ጸሐፊዎች ይልቅ ዮሐንስ ስለ ይሁዳ ጠንካራ ንግግሮችን ሲናገር ይታያል (ቁ.6)፡፡ ሙሉ ማብራሪያውን በ6:70-71 ላይ ይመልከቱ፡፡

▣ **"አሳልፎ ለሰጠው ያለው"** ይህ ሌላው የአዘጋጁ አስተያየት ነው፡፡ ይህ ቃል ብዙውን ጊዜ እንዲህ አይነት አንድምታ የለውም፡፡ ቃል በቃል ትርጉሙ "አሳልፎ መስጠት" ወይም "መክዳት" ከሕግ አንፃር ሲኖረው፡ ሌላው ደግሞ አንድን ነገር ለሌላው በአደራ መስጠት ማለት፡፡ በ18:2 ላይ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ፡፡

12:5 **"ሦስት መቶ ዲናር"** ዲናር ማለት አንድ ወታደር ወይም የቀን ሠራተኛ የሚያገኘው ነው፡፡

12:6 ይህ ጥቅስ ሌላው የአዘጋጁ አስተያየት ነው፡፡ ከሌሎች ወንጌላት ይልቅ የዮሐንስ ወነግል ይሁዳን ይበልጥ ይኮንነዋል፡፡

▣

| | |
|---|---|
| NASB,NKJV | **"የገንዘብ ከረጢት"** |
| NRSV | **"የጋር የሆነ ገንዘብ ቦርሳ"** |
| TEV | **"የገንዘቡ ከረጢት "** |
| NJB | **"የጋራ የሆነው ገንዘብ"** |

ይህ ቃል ትርጉሙ "ትንሽ ሳጥን" ማለት ሲሆን ቀደም ሲል የሙዚቃ ተጫዋቾች የትንፋሽ ሙዚቃ መቻወታቸውን የሚያስቀምጡበት ነበር፡፡

▣ **"በውስቱ ከሚገባው ይወስድ ስለነበረ ነው"** የግሪኩ ቃል "መሸከም" ይለዋል፡፡ በሁለት የተለያዩ ትርጉሞች ጥቅም ላይ ይውሳል፤ (1) ሳጥኑን ተሸከመ ነገር ግን (2) በሳጥኑም የሚገኙትንም ተሸከመ ለማለት፡፡ ይህ ዓረፍተ ነገር የተካተተው ይሁዳ በቁ. 5 ላይ ለድሆች ግድ እንደሚለው የተናገረው በከረጢቱ ከሚገባው ገንዘብ መስረቁን ለማስተባበል የሰጠው ሰበብ ነበር፡፡

12:7 ይህ እንግዳ የሆነ ጥቅስ ነው፡፡ እንዲህ አይነቱን ልግሥናና መስጠት አንድ ሰው ሲቀበር ካለው ሥርዓት ጋር በማያያዝ በቀላሉ ይገስጸዋል፡፡ ይህም ሌላው የዮሐንስ ትንቢታዊ ዓርፍተ ነገር ነው፡፡

12:8 **"ድሆችስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ይኖራሉና"** ይህ አባባል ከዘዳ.15:4፣11 ጋር የሚዛመድ ነው፡፡ ይህ ድሆችን በሙመለከት ለማንኳሰስ የተሰጠ አስየታየት ሳይሆን የኢየሱስ መሲህነት ትኩረት ለመስጠት ሲባል ነው (ቁ.35፤7:33፡9:4)፡፡ ከብሉይ ኪዳን ጥናት የቅርብ ምሥራቅ ሥ-ጽሁፎች ውስጥ በድሆች መብትና እንክብካቤ ላይ ተወዳዳሪ የማይገኝለት ነበር፡፡

> NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 12:9-11
> **[9]ከአይሁድም ብዙ ሕዝብ በዚያ እንደ ነበረ አውቀው መጡ፥ ከሙታንም ያስነሣውን አልዓዛርን ደግሞ እንዲያዩ ነበረ እንጂ ስለ ኢየሱስ ብቻ አይደለም። [10]የካህናት አለቆችም አልዓዛርን ደግሞ ሊገድሉት ተማከሩ፥ [11]ከአይሁድ ብዙዎች ከእርሱ የተነሣ ሄደው በኢየሱስ ያምኑ ነበርና።**

12:9 **"ከአይሁድም ብዙ ሕዝበብ በዚያ እንደነበረ አውቀው"** ይህ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ "አይሁድ" ለሚለው ያልተለመደ አጠቃቃም ነው፡፡ በአብዛኛው የሚያመለክተው ኢየሱስን የሚቃወሙትን የኃይማኖት መሪዎችን ነው፡፡ ይሁን እንጂ በ11:19፣45 እና በ12:17 ላይ የአልዓዛር ወዳጆችና ሊቀብሩት ከኢየሩሳሌም የመጡትን የሚያመለክት ይመስላል፡፡
12:10 **"የካህናት አለቆችም አልዓዛርን ደግሞ ሊገድሉት ተማከሩ"** ሕያው የሆነውን ምስክር ሊያስወግዱ ፈለጉ! የዚህ መነሻ ሃሳብ ደግሞ ፍርሃት (18:48) እና ቅናት (11:48፤12:11) ነበር፡፡

ኢየሱስ አልዓዛርን ወደ ሕይወት መመለሱ እንግዳና ያልተለመደ ክስተት አድርገው  አስበው ነበር ማለት ነው፤ የአይሁድ መሪዎች መንፈሳዊ እውርነትና መሠረት-የለሽነት በትክክል የወደቀውን የሰውን ልጅ ማንነት የሚያንጸባርቅ ነው፡፡

12:11 ይህ ወደኋላ ተመልሶ ከ11:45 ጋር የሚዛመድ ነው፡፡ በምዕ.2:23 ላይ የዮሐንስን "እምነት" የሚለውን ቃል አጠቃቃም በልዩ ርዕስ ላይ ይመልከቱ፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 12፡12-19
**[12]በማግሥቱ ወደ በዓሉ መጥተው የነበሩ ብዙ ሕዝብ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመጣ በሰሙ ጊዜ፥ [13]የዘንባባ ዛፍ**
**ዝንጣፊ ይዘው ሊቀበሉት ወጡና፡፡ ሆሣዕና፤ በጌታ ስም የሚመጣ የእስራኤል ንጉሥ የተባረከ ነው እያሉ ጮኹ፡፡ [14-**
**15]አንቺ የጽዮን ልጅ አትፍሪ፤ እነሆ፥ ንጉሥሽ በአህያ ውርንጫ ላይ ተቀምጦ ይመጣል ተብሎ እንደ ተጻፈ፥ ኢየሱስ**
**የአህያ ውርንጫ አግኝቶ በእርሱ ተቀመጠ፡፡ [16]ደቀ መዛሙርቱም ይህን ነገር በመጀመሪያ አላስተዋሉም፤ ነገር ግን**
**ኢየሱስ ከከበረ በኋላ በዚያን ጊዜ ይህ ስለ እርሱ እንደ ተጻፈ ይህንም እንዳደረጉለት ትዝ አላቸው፡፡ [17]አልዓዛርንም**
**ከመቃብር ጠርቶ ከሙታን ሲያስነሣው ከእርሱ ጋር የነበሩት ሕዝብ ይመሰክሩለት ነበር፡፡ [18]ስለዚህ ደግሞ ሕዝቡ ይህን**
**ምልክት እንዳደረገ ስለ ሰሙ ሊቀበሉት ወጡ፡፡ [19]ስለዚህ ፈሪሳውያን እርስ በርሳቸው፡፡ አንድ ስንኳ ልታደርጉ**
**እንዳይቻላችሁ ታያላችሁን? እነሆ፥ ዓለሙ በኋላው ተከትሎት ሄዶአል ተባባሉ፡፡**

12:12-19 ይህ ዮሐንስ ኢየሱስ በድል አድራጊነት ወደ ኢየሩሳሌም መገባቱን የሚያመመለክት ሀታታ ነው (ማቴ.21፡1-11፤ማር.11፡1-11፤ሉቃ.19፡24-38)፡፡

**12:12 “ወደ በኣሉ መጥተው የነበሩ ብዙ ሕዝብ”** የአይሁድ ወንዶች የሚያከብሯቸው ሶስት የበዓል ቀናት ነበሩ (ዘፀ.23፡14-17፤ ዘሌ.23፡ ዘዳ.16፡16)፡፡ ከፍለስጥኤም ምድር ውጭ ይኖሩ የነበሩ አይሁዳውያን (ዲሳስፖራ) በኢየሩሳሌም እነዚህን በዓላት ማክበር የሕይወት ዘመናቸው ምኞት ነበር፡፡ በእነዚህ በተወሰኑ በዓላት ቀደም ሲል ከነበረው ሕዝብ ቁጥር ኢየሩሳሌም በሦስትና በአምስት እጥፍ ትቸናነቅ ነበር፡፡ ይህም ሐረግ የሚያመለክተው ስለኢየሱስ ሰምተው ሊያዩ የመተትን ብዙ ሕዝብ ነበር (11፡56)፡፡

**12:13 “የዘንባባ ዛፍ ዝንጣፊ”** ይህ ለዘንባባ ዛፍ ቅርንጫፎች የተሰጠ ያልተለመደ ሐረግ ነው፡፡ የዘንባባ ዛፎች አንዳንዶች እንደሚያምኑት በአንድ ወቅት በደበረ ዘይት ተራራ ተዳፋቶች ሌ ያድጉ ነበር (ጆሲፈስ)፡፡ ሌሎች ደግሞ ከኢያሪኮ የሚጡ ናቸው ብለው ያምናሉ፡፡ የዘንባባ ዛፎች የማሸነፍ ወይም የድል አድራጊነት ምልክት ተደርገው ሳይወሰዱ አልቀሩም (ራዕይ 7፡9)፡፡ በየዓመቱ የዳስ በዓል (ዘሌ.23:40) እና በፋሲካ በኣል (ከመቃብያን ጊዜ የመጣ ባህል) ጥቅም ላይ ይውሉ ነበር፡፡

▣ **“እያሉ ቾሁ”** ይህ ያለተሟላ ጊዜን የሚያመለክት ሲሆንየሚገልጠውም (1) በኃላፊ ጊዜ የተደጋገመ ድርጊት መሆኑን ወይም (2) በኃላፊ ጊዜ የአንድን ድርጊት መጀመር ያሳያል፡፡

▣ **“ሆሳዕና”** ይህ ቃል “አሁን አድን” ወይም “እባክህ አድን” እንደማለት ነው (መዝ.118፡25-26)፡፡ የፋሲካን በዓል ለማድረግ ጉዞ ሊያደርጉ (ወደ ኢየሩደሳሌም) የሕማማት መዝሙር በቃል እየጠቀሱ መናገር የተለመደ ነገር ነው (መዝ.113-118)፡፡ አብዛኞቹ ድርጊቶችና የቃላት ሐረጎች በፋሲካ በዓል ወቅት በየዓመቱ ተደጋግመው የሚፈጸሙ ናቸው፡፡ ነገር ግን አሁን በዚህ የተለየ ወቅት በኢየሱስ የተለየ ትርጉም ማግኘት ጀመረ፡፡ ሕዝቡም የተስማው ስሜት እንዲሁም ፈሪሳውያንም ያስተዋሉት ይህን ስሜት ነበር፡፡

▣ **“በጌታ ስም የሚመጣ”** ይህ በትክክል ኢየሱስ ሲናገር የነበረው ነው፤ የተላከውም እርሱ ነበር ያሕዌን በመወከል፡፡

▣

NASB “የእሥራኤል ንጉሥ”

NKJV,NRSV,
TEV,NJB “የእሥራኤል ንጉሥ”

ይህ ሐረግ የመዝሙሩ ክፍል አልነበረም፤ ነገር ግን የተጨመረው በህዝቡ ነበር፡፡ ይህ በ2ኛ ሳሙ. 7 (1፡49፤19፡19) ኢየሱስ ተስፋ የተገባለት መሲህዊ ንጉሥ መሆኑን በቀጥታ የሚገልጥ ይመስላል፡፡

**12:14 “የአህያ ውርንጫ”** አህዮች የእሥራኤል ነገሥታት የሚቀመጡባቸው ነበሩ (1ኛ ነገ. 1፡33፤38፡44)፡፡ አንድ ንጉሥ ብቻውን ነበር የረሱን አህያ የሚነዳው፤ በመሆኑም ምንም ባለተቀመጠባት ውርንጫ ላይ ኢየሱስ መቀመቱና ምምታቱ በሽጣም አሰፈላጊው ጉዳይ ነበር (ማር.1፡12)፡፡

**12:14-15 “ተብሎ እንደተጻፈ”** ይህ ከዘካ.9፡9 የተወሰደ ነው፡፡ የአህያ ውርንጫ የምታመለክተው የኢየሱስን መሲሐዊ ንጉሥነት ብቻ ሳይሆን ትህትናውንም ጭምር ነው፡፡ ኢየሱስ የመጣው አይሁዳዊያነ እንደጠበቁት መከራ እንደሚቀበል አገልጋይ በአህያ ላይ ተቀምጦ ነበር፡፡

12:16 **"ደቀ መዛሙርቱም ይህን ነገር በመጀመሪያ አላስተዋሉም ነበር"** ይህ ዮሐንስ በሐዘን የሚያስታውሰው የዮሐንስ ሌላው የአይን ምስክርነት ነው። ይህ ተደጋግሞ የሚታይ ነው (2:22፣ 10:6፣16:18፣ ማር.9:32፣ ሉቃ.2:50፣ 9:45፣ 8፣34)። የደቀ ማዛረቱ መንፈሳዊ አይኖች ሙሉ በሙሉ የተከፈቱት ኢየሱስ ካረገ እና ከጴንጤቆስጤ በኋላ ነበር።

▣ **"ነገር ግን ኢየሱስ ከከበረ በኋላ በዚያን ጊዜ ይህ ስለእርሱ እንደተጻፈ ትዝ አላቸው"** ይህ ከመንፈስ ቅዱስ ስራዎች አአንዱ ነው (14:26 እና 2:22)። ይህ ጥቅስ በተቸማሪ ይህ ጥቅስ በተጨማሪ የሚያመለክተው የወንጌል ጸሐፊዎች ወንጌላትን ያዋቀሩት በትንሳኤ ከተነሳው ክርስቶስ ጋር ከነበራች የራሳቸው ልምምድ በመነሳት ነው። ወንጌላት ኢሱስን የሚያቀርቡት በታሪካዊ የሂደት እድገት ሲሆን አቀራረባቸውንም የኢየሱስን ክብር በመሰወር ነበር። ነገር ግን ዮሐንስ ጠቅላላውን ወንጌል የመጽፈው መክበርን ከተጎናጸፈው መሲህ አንፃር ነው። ወንጌላት የሚያንጸባርቁት እነዚህን ከኋላ ያሉትን ትዝታዎች በመሆኑ አማኙ ህብረተሰብ ደግሞ እነዚህን እምነትን የሚያነሳሱ ሰዎችን በጣም የሚፈልጋቸው ናቸው። ስለዚህም እስተንፋስ እግዚአብሔር ያሰባቸው (የኢየሱስና የወንጌል ጸሐፊዎች) ሁለት ታሪካዊ ድባች አሉ ማለት ነው።

▣ "ከከበረ" በምዕ.1:14 ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ።

12:17 በልዩ ርዕስ ላይ የኢየሱስ ምስክር መሆን በሚለው ላይ ምዕ.1:8ን ይመልከቱ። በሐ ላይ ዓመጻዊ መረዳቶች የሚለውንም ይመልከቱ።

12:19 **"ፈሪሳውያን እርስ በርሳቸው …. ተባባሉ"** ይህ ሌላው ትንቢታዊ ጥላ ነው። ይህም የሚዛመደው፣ (1) ከአይሁዳውያን 11:48፣12:11፣ (2) ከአህዛብ ቁ.20-23። ይህ ሁለት ታሪካዊ ድባቦችን የሚያመለክት ነው፦ የኢየሱስን ሕይወትና የቀደመችውን ቤተክርስቲያን።

**NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 12:20-26**
**[20]በበዓሉም ሊሰግዱ ከወጡት አንዳንዶቹ የግሪክ ሰዎች ነበሩ፤ [21]እነርሱም ከገሊላ ቤተ ሳይዳ ወደሚሆን ወደ ፊልጶስ መጥተው። ጌታ ሆይ፥ ኢየሱስን ልናይ እንወዳለን ብለው ለመኑት። [22]ፊልጶስም መጥቶ ለእንድርያስ ነገረው፤ እንድርያስና ፊልጶስ መጥተው ለኢየሱስ ነገሩት። [23]ኢየሱስም መለሰላቸው፥ እንዲህ ሲል፦ የሰው ልጅ ይከብር ዘንድ ሰዓቱ ደርሶአል። [24]እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የስንዴ ቅንጣት በምድር ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች፤ ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች። [25]ነፍሱን የሚወድ ያጠፋታል፥ ነፍሱንም በዚህ ዓለም የሚጠላ ለዘላለም ሕይወት ይጠብቃታል። [26]የሚያገለግለኝ ቢኖር ይከተለኝ፥ እኔም ባለሁበት አገልጋዬ ደግሞ በዚያ ይሆናል፤ የሚያገለግለኝም ቢኖር አብ ያከብረዋል።**

12:20 **"አንዳንዶቹ የግሪክ ሰዎች"** ይህ አባባል የተጠቀሰው አህዛብ ከሚለው አንፃር እንጂ የግሪክ አገር ሰዎች ከሚለው አይደለም።
▣ **"በበዓሉም ሊሰግዱ ከወጡት"** ይህ የአሁን ጊዜን የሚያመለክተው ወደ በዓሉ የመሔድ ልማድ እንደነበራቸው ነው። እነዚህም (1) ወይ እግዚአብሔርን የሚፈሩ (2) አሊያም ደግሞ በበሩ የሚቀመጡ መፃተኞች ነበሩ። የመጀመሪያዎቹ በምኩራብ የነበሩ መደበኛ አምላኪዎች ሲሆኑ ሁለተኞዎቹ ደግሞ በአደባባይ/በግልጽ ወደ አይሁድ እምነት መግባታቸውን ያሳዩ ናቸው።

12:21 **"ለመኑት"** ይህ ያልተሚላ ጊዜን ሲያመልክት (1) ደጋግመው ጠይቀዋል ማለት ነው ወይም (2) መጠየቅ ጀምረዋል ማለት ነው። ኢየሱስን በግል ለመጠየቅ የፈለጉ ናቸው። ይህ ኢየሱስ ከመሞቱ በፊት በትንቢታዊው ሰዓት የመቸረሻዋ ደወል ነበር (ቁ.23)።

12:22 ፊልጶስ/ፈረስ የሚወድ) እና እንድርያስ (ጎበዝ) የግሪክ ስያሜ ያላቸው ሁለት ሐዋሪያት ነበሩ። ምናልባትም ግሪኮችን /አህዛብን) ለመቅረብ እንዲችሉ አጋጣሚን የፈጠረላቸው/የሚፈጥርላቸው/መሰሏቸው ይሆናል።

12:23 **"ሰዓቱ ደርሶአል"** ይህ የድርጊት መፈፀምን የሚያመልክት ነው። ዮሐንስ የኢየሱስን ስቅለትና ትንሳኤ እንደ ኢየሱስ ተልዕኮ የመቸረሻው ክስተት ለማሣየት ብዙውን ጊዜ "ሰዓቱ" በማለት ይጠቅሳል (12:27፣13:1፣32፣17:1)። ኢየሱስም ደግሞ ከእሥራኤል ወደ ተፉት በጎች እንዲመጣ ተናግሯል (ማቴ 15:24)። በመሆኑም አሁን እንግዲህ የእርሱ መልዕክት አህዛብን በወንጌል መድርስ ነው!

▣ **"የሰው ልጅ"** ይህ የአረማይክ ሐረግ ሲሆን ትረጉሙ "የሰው ዘር" ማለት ነው (መዝ.8:4፣ሕዝ.2:1)። ይሁን እንጂ በዳን.7:13 ላ አምላክ/መለኮት የሚለውን ሃሳብ በመያዝ ጥቅም ላይ ውሏል። ይህ ኢየሱስ ስለራሱ የሰተው ማዕረግ ሲሆን ሁለት ባህሪያቱን አጣምሮ የያዘ ነው። ሰውነቱንና አምላክነቱን (1ኛ ዮሐ. 4:1-3)።

▣ **"ይከብር ዘንድ"** የኢየሱስ መሞት ሁል ጊዜ "ከመክበሩ" ጋርየተቆራኘ ነው። "መክበር› የሚለው ቃል በዚህ ዓውድ ውስጥ ብዙ ጊዜያት ተጠቅሷል (ቁ.28-ሁለት ጊዜ፤32 እና 33) ብዙውን ጊዜ የኢየሱስን ሞትና ትንሳኤ ለማሳየት ተጠቅሷል (13:1፤32-17:1)። በ1:14 ላይ ያለውን አስተያየት ይመልከቱ።

12:24 **"የስንዴ ቅንጣት በምድር ወድቃ ካልሞተች"** ይህ በአምስቱም የስሜት ህዋሳቶች እንዲሚስተዋል ሆኖ የቀረበ ክስተታዊና ገላጭ ቋንቋ ነው። አንድ ዘር ብዙ ፍሬዎችን ልታፈራ ትችላለች (15:2፣4፣5፣8፣16፤ 1ኛ ቆሮ.15:36)። የኢየሱስም ሞት እንዲሁ ብዙዎችን ወደ እውነተኛ ሕይወት አምጥቶዋል (ማር.10:45)።

▣ "በ..." በዚህ ክፍል ውስጥ ብዙ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገሮች አሉ፤ ይህም ድርጊቱን ለመፈፀም ዕደል መኖሩን የሚያሳይ ነው (ቁ. 24፣26፣32፣47)።

12:25 **"ነፍሱን የሚወድ ያጠፋታል"** ይህ (ዞ) በሚለው የግሪኩ ቃል የሚደረግ የቃላት ጨዋታ ነው፤ ይህም የሚያመለክተው የሰውን ስብዕና ወይ የሕይወት ኃይል ነው (ማቴ.10:39፤16:24-25፤ማር. 8:34-35፤ሉቃ.9:23-24)። አንድ ሰው ኢየሱስን እናደመነ አዲስ ሕይወትን ወዲያው ይቀበላል። ይህ አዲስ ሕይወት ለግል ጥቅም ሳይሆን ለማገልግለ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ነው። አማኞች ሁልጊዜ የዚህ አዲስ ሕይወት ባለአደራዎች ናቸው። ከኃጢአት ባርነት የወጣነው የእግዚአብሔር አገልጋዮች እንሆን ዘንድ ነው (ሮሜ.6:1-7:6)።

በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ቀ0 ላይ የሚገኙት ሞያተኛ እረኞች በመሸሽ የራሳቸውን ሕይወት "ለማትረፍ" ሲጥሩ ይታያሉ። ኢየሱስ ግን የራሱን ሕይወት አሳልፎ ሰጠ፤ እንዲሁም ደግሞ አማኞች ሊያደርጉ ይገባል (2ኛ ቆሮ. 5:12-15)።

▣ **"ያጠፋታል"** ይህ የአሁን ጊዜን አድራጊ ግሥን አመልካች ነው። የቃሉ ትረጉም "ማጥፋት" ማለት ሲሆን ይህም ሁለደት ድባቦችን ያዘለ ነው። ይህ "የዘላለም ሕይወት" ከሚለው ተቃራኒ ነው። አንድ ሰው በክርስቶስ ካላመነ ያለው አማራጭ ይህ ብቻ ነው። ይህ ጥፋት በይመሰል የሚል እሳቤ የለውም። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ሕብረት ማጣት ነው (ይህም የገሃነም ዋነኛ መለያ ባህሪይ ነው)።

▣ **"የሚጠላ"** ይህ (ዞ) የሚለው የግሪኩ ቃል ነው። በዮሐንስ ወንጌል ላይ፣ (1) መንፈሳዊ ሕይወትን (2) የዘላለም ሕይወትን (3) አዲሱን ሕይወት እነዲሁም (4) የትንሳኤ ሕይወትን ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል። እውነተኛ ሕይወት ያለው ውድቀት ባህሪዩ ከሆነው "በራስ" ላይ ከሚደረግ የጭቆና አገዛዝ ነፃ መውጣት ነው።

▣ **"ነፍሱን"** ይህ ዕብራይስጥ የንፅፅር ዘይቤ ነው። እግዚአብሔር ቀዳሚ መሆን አለበት (የያዕቆብ ሚስቶች፡ ዘፍ. 29:30፣31፤ ዘዳ.21:15፤ ኤሳውና ያዕቆብ ሚል.1:2-3፤ ሮሜ.10-13፣ የአንድ ሰው ቤተሰብ፣ ሉቃ.14:26)።

12:26 "የ...." ይህ ድርጊትን ለመፈፀም ዕድል መኖሩን የሚያሳይ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ አረፍተ ነገር ነው።

▣ **"ይከተለኝ"** ይህ ቀጣይነት ያለውን ሕብረት ለማመልከት/የሚያመለክት የአሁን ጊዜ ድርጊት ፈፃሚ ግሥ አመልካች ነው (ዮሐ.15)። ይህ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ እይታ ትኩረት ያለተሰጠው የድነት ጉዳይ ነው(ልዩ ርዕስ በሚለው የጽናጽ 噍 ሽፈላጊነጽን በ8:31 ላይ ይመልከቱ።)። ጉዳዩም ብዙውን ጊዜ በእግዚአብሔር ልዑላዊነትና በሰው ፈቃድ መካከል ባለው ሥነ-መለኮታዊ ውጥረት ምክንያት ግራ የሚያጋባ ሆኖ ቆይቷል። ይሁን እንጂ ድነትን እንደ ቃል ኪዳናዊ/የቃል ኪዳን ልምምድ አድርጎ መውሰዱ ከሁሉም የተሻለ ነው። ሁል ጊዜም ቀዳሚነቱን የሚወስደው በእርግጥ እግዚአብሔር ነው (6:44፣55) በአንፃሩ ግን እግዚአብሔር ስለጠው የንስሐና የእምነት ዕድል (ማር.1:15-የሐዋ.20:21) የሰው ልጅ ይህን ጉዳይ ቀዳሚ ውሳኔ ለማድረግና ለዘለቄታው በደቀመዝሙርነት ለመቀጠል ኃላፊነትን እንዲወስድ እግዚአብሔር ይጠብቃል። ጽናት እኛ እግዚአብሔርን ለማወቃችን ማስረጃው ነው (ማቴ.10:22፤13:20-21፤ ገላ.6:9፤ 1ኛ ዮሐ. 2:19፤ 4ዕ.2:7፣11፣17፣26፤3:5፣12፣21)።

*መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረገ ክርስቲያናዊ አስተምህሮ እውነት የማይመስሉ ነገር ግን ሊሆኑ የሚችሉ፤ ውጥረትን የሞሉ ጥምረቶችን የያዘ ነው። የምሥራቅ ሥነ-ጹሑፎች በእንደዚህ አይነቶች ተምሳሌታዊ/ምሳሌያዊ እና በተቃራኒ የአስተሳሰብ ዘይቤ የሚታወቁ ናቸው። የዘመኑ ምራባዊያን አንባቢያን እነዚህን ጥምረቶች ብዙውን ጊዜ ከአንድ ጋር ብቻ ይፈርጁታል ምንም እንኳን ሁለቱንም ቢያሳዩም።*

አስተያየቴንም የበለጠ ለማብራራት ከራሴ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ሴሚናር፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥምረቶች የሚለውን አካትቼአለሁ።

የሚጋጩ የሚመስሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አባባሎች፡-

1. አንዳንድ የእግዚአብሔርን ቃል እንደሚወድና እንደሚያምን ሰው ይህ መረዳት በግሌ በጣም አስፈላጊዬ ሆኖ የቆየ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን በትኩረት ለመከታተል የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አንድን አውነት በቅደም ተከተል ሳይሆን በተለየ ሁኔታ ማስተላለፋቸው እውነት ነው። አንድ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪት የተፃፈ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሌላውን በምሪት የተጻፈን ክፍል ሊሠርዘው ወይም ዝቅ ሊያደርገው ፈጽሞ አይችልም! እውነት ሁል ጊዜ የሚመጣው ሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ በማወቅ ነው (አንዳንዱ ብቻ ሳይሆን

ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት የተጻፈ ነው (2ኛ ጢሞ.3፡16-17) እንጂ አንድን ምንባብ/ክፍል መጥቀስ ብቻ አይደለም፡፡

2. ብዙዎች መጽሐፍ ቅዱስዊ እውነቶች/የምሥራቅ ሥነ-ጽሑፍ/ የቀረቡት በቋንቋ ዘዬ ወይም እርስ በርሱ የሚቃረን በሚመስል ጥምረት ነው (ከሉቃስ በስተቀር የአዲስ ኪዳን ጸሐፎወች ሁሉ በተለመደው የግሪክ ቋንቋ የጻፉ የእብራውያን አስተሳሰብ የነበራቸው እንደነበሩ አስታውስ፡፡ የጥበብና የቅኔ ጽሑፎች እውነትን የስተላልፉ የነበሩት በትይዩ መስመሮች ነው፡፡ ተቃራኒ ንፅፅሮች እንደጣምራ ተቃርኖዎች የሚያገለግሉ ናቸው፤ ይህም ‹ሴንቴቲክ› ንፅፅር የሚሠራው እንደ ትይዩ ምንባቦች ነው፡፡ በመጠኑም ቢሆን ሁለቱም እኩል ናቸው፤ ነገር ግን እነዚህ ጣምራ ተቃርኖዎች ከእኛ ልማድን ነገሮችን አቅልሎ ከማየት አንፃር በእርግጥ የማይመቹ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

ሀ. አስቀድሞ መወሰንና የሰው ነፃ ፈቃድ
ለ. የአማኝ ደህንነትና የጽናት አስፈላጊነት
ሐ. የውርስ ኃጢአትና የፈቃድ ኃጢአት
መ. የኢየሱስ አምላክነትና የኢየሱስ ሰውነት
ሠ. ኢየሱስ ከአብ እንደሚተካከልና እንደሚያንስ
ረ. መጽሐፍ የእግዚአብሔር ቃል ነው እና መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ቀል
ሰ. ፍጹምነት እና ኃጢያተኝነት
ሸ. ቅጽበታዊ ቅድስና እና ሂደታዊ ቅድስና
ቀ. ጽድቅ በእምነት (ሮሜ 4) እና ጽድቅ በሥራ (የዕ.2፡14-26)
በ. የክርስትያን ነፃነት (ሮሜ 14፡1-23፤1ኛ ቆሮ. 3፡1-13፣ 10፡23-33) እና የክርስቲያን ኃላፊነት (ገላ.5፡16-19፤ ኤፌ.4፡1)
ተ. የእግዚአብሔር ትልቅነት እና የእግዚአብሔር ቅርበት)
ቸ. እግዚአብሔር ከአእምሮ በላይ ነው እና እግዚአብሔር በቃሉና በክርስቶሰ ይታወቃል
ኘ. ጳውሎስ ድነትን ለመግለጽ የተጠቀመባቸው ምሳሌዎች
   1) ልጅነት
   2) ቅድስና
   3) ጽድቅ
   4) መቤዠት
   5) መክበር
   6) አስቀድሞ መወሰን
   7) መታረቅ
ነ. የእግዚአብሔር መንግሥት አሁን እንደሚገለጥ እና የእግዚአብሔር መንግስት ወደፊት እንደሚኖር
ኘ. ንስሓ እንደ እግዚአብሔር ሥጦታ እና ንስሐ ለደህንነት እንደተወሰነ ምላሽ (ማር.1፡15፤ የሐዋ.20፡21)
አ. ብሉይ ኪዳን እንደማይለወጥ እና ብሉይ ኪዳን እንደተሻረ ና እንደማይጠቅም (ማቴ. 2፡17-19፣ 5፡21-48፤ ሮሜ 7 እና ገላ 3)
ከ. አማኞች አገልጋዮች ወይም አማኞች ልጆች/ሠራሾች

▣ **"እኔም ባለሁበት አገልጋይ ደግሞ በዚያ ይሆናል"** ይህ ጭብጥ በ14፡3፤ 17፡24፤ 2ኛ ቆሮ.5፡8፤ ፊልጵ.1፡23፤ 1ኛ ተሰ.4፡17 ላይ ተደጋግሞ የተነሳ ነው፡፡

እኛ የተፈጠርነው ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረትን ለማድረግ ነው (ዘፍ.1፡26-27)፤ ድነትም በኤደን ገነት ተቋረጦ የነበረውን ሕብረት ማደስ ወይም ወደ ቀድሞው ሁኔታ መመለስ ነው፤ የዮሐንስም ወንጌል አሁን ይህ ሕበብረት እንዲታደስ ትኩረት የሚያደርግ ነው!

**NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 12፡27-36ሀ**
**27አሁን ነፍሴ ታውካለች ምንስ እላለሁ? አባት ሆይ፥ ከዚህ ሰዓት አድነኝ፡፡ ነገር ግን ስለዚህ ወደዚህ ሰዓት መጣሁ፡፡ 28አባት ሆይ፥ ስምህን አክብረው፡፡ ስለዚህም፡፡ አከበርሁት ደግሞም አከብረዋለሁ የሚል ድምፅ ከሰማይ መጣ፡፡ 29በዚያ ቆመው የነበሩትም ሕዝብ በሰሙ ጊዜ፡፡ ነጐድጓድ ነው አሉ፤ ሌሎች፡፡ መልአክ ተናገረው አሉ፡፡ 30ኢየሱስም መለሰ፥ እንዲህ ሲል፦ ይህ ድምፅ ስለ እናንተ መጥቶአል እጂ ስለ እኔ አይደለም፡፡ 31አሁን የዚህ ዓለም ፍርድ ደርሶአል፤ አሁን የዚህ ዓለም ገዥ ወደ ውጭ ይጣላል፤ 32እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ያልሁ እንደ ሆነ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ፡፡ 33በምን ዓይነትም ሞት ይሞት ዘንድ እንዳለው ሲያመለክታቸው ይህን ተናገረ፡፡ 34እንግዲህ ሕዝቡ፡፡ እኛስ ክርስቶስ ለዘላለም እንዲኖር ከሕጉ ሰምተናል፤ አንተስ የሰው ልጅ ከፍ ከፍ ይል ዘንድ እንዲያስፈልገው እንዴት ትላለህ? ይህ የሰው ልጅ ማን ነው? ብለው መለሱለት፡፡ 35ኢየሱስም፦ ገና ጥቂት ጊዜ ብርሃን ከእናንተ ጋር ነው፡፡ ጨለማ እንዳይደርስባችሁ ብርሃን ሳለላችሁ ተመላለሱ፤ በጨለማም የሚመላለስ ወዴት እንዲሄድ አያውቅም፡፡ 36የብርሃን ልጆች እንድትሆኑ ብርሃን ሳለላችሁ በብርሃኑ እመኑ አላቸው፡፡**

12:27 **"ነፍሴ ታውካለች"** ይህ የተሟላ ድርጊት መፈጸምን የሚያመለክት ነው፡፡ አድራጊው አልተገለጸም (አባት፣ሠይጣን.ሁኔታዎች የመሳሰሉት)፡፡ ይህ በአዲስ ኪዳን በብዙ መንገዶች ጥቅም ላይ የዋለ ጠንካራ ቃል ነው፡፡

*ሀ. የሄሮድስ ፍርሃት* (ማቴ.2፡3)

*ለ. የደቀመዛሙርቱ ፍርሃት* (ማቴ.24፡26)

*ሐ. የኢየሱስ ያልተጠበቀ ፍርሃት* (ዮሐ. 12፡26፤13፡21)

*መ. በኢየሩሳሌም ያለችው ቤተክርስቲያን* (የሐዋ.15፡24)

ይህ እንግዲህ የኢየሱስን ሰብአዊ ትግል ሊመጣ ካለው የመስቀል ላይ የስቃይ ስሜት ያዛመደበት የዮሐንስ የአገላለጽ መንገድ ነበር (ማር. 14፡32)፡፡ ዮሐንስ ኢየሱስ በጌቴሴማኒ የነበረውን ሥቃይና መቃተት አልዘገበም፤ ይሁን እንጂ ይህም ተመሳሳይ ሁኔታ ነው የሚናገረው፡፡

▣ **"ከዚህ ሰዓት አድነኝ"** ስለዚህ አባባል ትክክለኛ ትርጉም ላይ ብዙ ክርክር አለ፡፡ ይህ ጸሎት ነው (ማቴ.26፡39)? ወይስ ድርጊቱ መፈጸም እንደሌለበት የሚያሳይ የመደነቅ ምላሽ ነው (NET መጽሐፍ ቅዱስ)

▣ **"ስለዚህ ወደዚህ ሰዓት መጣሁ"** በመለኮታዊ እቅድ መሠረት የኢየሱስ ሕይወት እንደማይለወጥ ሙሉ መረዳት ነበረው (ማቴ.20፡28፤ ማር.10፡45)፡፡

12:28 **"ስምህን አክብረው"** እግዚአብሔር አብም በቁጥር 28ለ ላይ መለሰ፤ "ክብር" የሚለው ቃል የተለያየ ነው፡፡ ሊያመለክት የሚችለውም

1. ከፍጥረት በፊት የነበረውን ክብር (17፡5)
2. የኢየሱስ አብን ማግለጥ (17፡4)
3. የኢየሱ ስቅለትና ትንሳኤ (17፡1)

በምዕ.1፡14 ላይ ያውን ማስታወሻ ይመልከቱ፡፡

▣ **"ድምፅ ከሰማይ"** ረቢዎች ይህንን ባዘ-ኮል (*bath-kol*) ይሉታል፡፡ ከሚልኪያስ ጊዜ ጀምር ከእስራኤል ምንም አይነት ትንቢታዊ ድምጽ አልነበረም፡፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ መረጋገጥ ካለበት ድምፅ ከሰማይ መምጣት ነበረበት፡፡ ወንጌላትም ኢየሱስ በምድር በነበረበት ወቅት እግዚአብሔር ሶስት ጊዜያት እንደተናገረ ይዘግባሉ/ይጠቅሳሉ፡፡

1. ኢየሱ ሲጠመቅ-ማቴ.3፡17
2. ኢየሱስ መልኩ ሲለወጥ ማቴ.17፡5
3. አሁን ደግሞ በዚህ ጥቅስ ላይ

12:29 **"በዚያ ቆመው ከነበሩትም ሕዝብ በሰሙ ጊዜ"** ስለተፈጸመው ክስተት ሁለት አይነት ምልከታዎች አሉ፤ (1) ነጎድጓድ ነው አሉ፡፡ ይህም እግዚአብሔር ብሉይ ኪዳን ውስጥ ሲናገር የተጠቀሰው ነው (2ኛ ሳሙ.22፡14፤ ኢዮ.37፡4፤ መዝ.29፡3፤18፡13፤104፡7) ወይም (2) መልዓክ ተናገረው አሉ፡፡ ይህም ጳውሎስ ከነበረው ልምምድ የተፈጠረው ግራ መጋበት ጋር ተመሳሳይነት አለው (የሐዋ.9፡7/22፡9)፡፡

12:30 **"ኢየሱስም መለሠ እንዲህ ሲል"** ይህ ድምጽ ስለእናንተ መጥቶአል እንጂ ስለእኔ አይደለም" ይህ ሐረግ የሴሜቲክ ንጽጽር ነው፡፡ ይህም ስለእነርሱ ብቻ አልነበረም፤ ነገር ግን አስቀድሞ ለእነርሱ ነበር ማለት ነው (11፡42)፡፡

12:31 **"አሁን የዚህ ዓለም ፍርድ ደርሶአል"** ይህ ተከትሎት ከመጣው ሐረግ አንጻር በትይዩ የተቀናጀ ነው ("የዚህ ዓለም ነገር ወደ ውጭ ይጣላል")፡፡ ይህ መቼ እንደተፈጸመ ተለይቶ የተቀመጠ ጊዜ የለም (የሚከተለው ልዩ ርዕስ የሚለውን ይመልከቱ፡፡)፡፡

ኤፍ.ኤፍ ብሩሰ ANswers to QuestioNs (ገጽ 198) በሚለው መጽሐፋቸው ላይ ሲ.ኤች "የሚታዩ ነገረ-ፍፃሜ" ያሉት በቁጥር 31 ላይ ያለው ሌላው ምሳሌ ከሚሉት ጋር በእርግጠኝነት እስማማበታለሁ፡፡ ለዮሐንስ ኢየሱስ ለሚያምኑት ደህንነትን ለማያምኑት ደግሞ ፍርድን ይዞ እንዲመጣ ነው፡፡ በሌላ አባባል ይህ በሰዋስው ቅርጽ "ትንቢታዊ መሟላት" እንደማለት ነው፡፡ ወደፊት የሚፈጸም አንድ ነገር አሁን እየሆነ እንዳለ መግለጥ ነው፡፡

▣ **"የዚህ ዓለም ነገር"** ይህ የሚያመለክተው አንድ ስዕና ያለውን የክፉ ኃይል ነው (14፡30፤16፡11)፡፡ ይህም በእብራይስጥ "ሠይጣን" "ባላንጣ" (ኢዮብ 1-2) ወይም በግሪኩ "ክፉው" ወይም "ፈታኝ" ማለት ነው (ማቴ.4፡1፤5፡8፤11፤ 13፡39፤25-41፤ ዮሐ.6፡70፤8፡44፤13፡2፤2ኛ ቆሮ.4፡4፤ኤፌ.2፡2)፡፡ እነዚህ ሁለት ስሞች በማቴ.4፡1-11 እና በዮሐ.13፡2፡27 ላይ ካሉት ጋር ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ከሰማይ የተጣለ ስለሆነ ከእንግዲህ ወዲሰሀ ኢየሱስን የሚከተሉትን እየከሰሳቸው አይቀጥል፡፡

## ልዩ ርዕስ፡ ክፋት

በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ ይህ ጉዳይ አስቸጋሪ ነው፡፡

1. ከብሉይ ኪዳን ለመልካም ነገር ትልቅን ጠላት አይገልጥም፤ ነገር ግን የያሕዌ አገልጋይና ለሰው ልጆች አማራጭን የሚሰጥ ክፉ የሰው ዘርን ስለጽድቅ የሚከስ እንደሆነ አድርጎ ነው (ኤ.ቤ. ዳቬድሰን፡ *Old Testament Theology*፡ ገጽ 300-600)
2. ስብዕና ያለው ጠላት የሚለው አስተሳሰብ እያደገ የመጣው ----- ኃይማኖት ጊዜ (ዘራስ ትራኒያኒዝም) ተጽዕኖ በኢንተረ ብብሊካል (Interbiblical) ጊዜ ነበር፡፡ ይህም በዚያ ጊዜያዊ የአይሁድ ኃይማኖችን በከፍተኛ ደረጃ ተጽዕኖ አድርጎበታል፡፡
3. አዲስ ኪዳን የብሉይ ኪዳን ጭብቶችን የወሰደው ሙሉ በሙሉ እና አንድ አይነት ባህሪይ ያላቸውን እያሰባሰበ ነበር፡፡

   ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥነ-መለኮት አንፃር አንድ ሰው ክፋትን ከተመለከው (እያንዳንዱ መጽሐፍ ወይም ለየብቻ የሚጠናበት) ስለክፋት የተለያዩ አመለካከቶች መፈጠራቸው የማይቀር ነው፡፡

ይሁን እንጂ አንድ ሰው ስለክፋት ለማጥናት ልክ የዓለም ኃይማኖቶች ወይም የምስራቅ ኃይማኖቶች እንደሚያደርጉት ከመጽሐፍ ቅዱስ እይታ ውጪ ከሆነ የአዲስ ኪዳን አካሄድ በፋርሳውያን ዱዋሊዝም (dualism) እና የግሪኮ-ሮማን የመናፍስት አምልኮ አስተሳሰብ መጋረዱ ነው/ግልጽ ነው፡፡

በአንፃሩ አንድ ሰው አስቀድሞ ለእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን አስቀድሞ የተገዛ ከሆነ የአዲስ ኪዳን በክፋት ቀይ ያለው አካሄድ ቀጣይነት እንዳለው ውስጥ ይታያል፡፡ ይህንን ጉዳይ የበለጠ ለማብራራት ይችሉ ዘንድ ክርስቲያኖች ከአይሁዶች ተረት ወይም ከእንግሊዝኛ ሥነ-ጽሑፍ (ዳንቴ፤ሚልተን) መጠበቅ አለባቸው፡፡ በዚህ መገለጥ ዙሪያ ብዙ ምስጢር የሆናና ግራ የሚያጋባ ሁኔታዎች አሉ፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ሁሉንም የክፋት ምንጮች፤ ምንጩን/አመጣጡን፣ ዓላማውን ላለመግለፅ ቢመርጥም የክፋትን መሸነፍ ግን ገልጦታል፡፡

ላይ ተጠቅሷል፡፡

በብሉይ ኪዳን ሠይጣን የሚለው(**BDB 966**) ከሦስት የተለያዩ ቡድኖች ጋር የተቆራኘ ይመስላል፤

1. የሰው ከሳሾች (1ኛ ሳሙ. 29፡4፤ 2ኛ ሳሙ.19፡22፤ 1ኛ ነገ.11፡14፤23፡25፤ መዝ. 109፡6)፡፡
2. የመልዓክት ከሳሾች (ሕዝ.22፡22-23፤ ዘካ.3፡1)
3. የአጋንንት ከሳሾች (1ኛ ዜና 21፡1፤1ኛ ነገ.22፡21፤ ዘካ.13፡2)

በዘፍጥረት 3 ላይ የተጠቀሰው እባብ በኋለኛው የዝምታ ጊዜ (400 ዓመታት) ብቻ ነበር፡፡ ሰይጣን ተብሎ የተለየው (የጥበብ መጽሐፍ 2፡23-24፤2 ሄኖክ 3፡13)፡፡ ከዚያም በኋላ እንኳን ረቢያዊ አማራጭነት ነበረው (*Sot9h and Sanh. 29h*)፡፡ በዘፍጥረት 6 ላይ ‹‹የእግዚአብሔር ልጆች ተብሎ የተጠቀሰው በ1 ሄኖክ 54፡6 ላይ ደግሞ ክፉ መላዕክት ተብሎ ተጠቅሷል፡፡ እነዚህም በረቢዎች ሥነ-መለኮት ዘንድ በምንጭነት የሚታወቁ ናቸው፡፡ ይህንም የምለው የሥነ-መለኮቱን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሳይሆን ታሪካዊ እድገቱን ለማሳየት ነው፡፡ በአዲስ ኪዳንም እነዚህ የብሉይ ኪዳን ድርጊቶች ስብዕና ካለው መልአክ ጋር የሚጎዳኝ ነው (ማለትም ሰይጥን) ይህም በ2ኛ ቆሮ.11፡3 እና በራዕ.12፡9በምንጭነት ሊጠቀሱ የሚችሉት (1) ኢዮብ

ከብሉይ ኪዳን ስብዕናን ስለተላበሰ ክፋት መጥቀስ አስቸጋሪ ወይም የማይቻል ነው፡፡ ለዚህም አንዱ ምክንያት የሚሆነው በአንድ አምላክ አምልኮ ላይ የተመሠረተው የእስራኤል እምነት ነበር (1ኛ ነገ.22፡20-21፤ መክ.7፡14፤ ኢሳ.45፡7፤ አሞ.3፡6)፡፡ ማነቸውም ክፉ ነገርም ከያሕዌህ ጋር የሚጎዳኝ ሲሆን ይህም የእርሱን ልዩ መሆንና ቀዳሚነት ለማሳየት ነው (ኢሳ.43፡11፤44፡6፤8፡24፤45፡5-6፤14፡18፤21፡22)፡፡

በምንችንት ሊጠቀሱ የሚችሉት (1) በኢዮብ 1-2፤ ሰይጣን ከእግዚአብሔር ልጆች›› እንደ አንዱ (ማለትም መላእክት) የሚታይበት ወይም (2) ኢሳ.14፤ ሕዝ.28 የሰይጣንን ትዕቢት ለማሳየት ትዕቢትን የተሞሉ የቅር ምሥራቅ ነገሥታትን (ባቢሎንን እና ጢሮስ) በምሳሌነት የተጠቀሱበት (1ኛ ጢሞ.3፡6)፡፡ ስለዚህ አመለካከት የተለያዩ ስሜቶችን አጣምሬአለሁ፡፡ ሕዝቅኤል የኤደን ገነትን የጦሮስን ንጉስ እንደሰይጣን ለመግለጽ ብቻ ሰይሆን (ሕዝ.28፡12-16) የግብፅንም ንጉሥ መልካምንና ድፉን ለግለጽ ተጠቅሞበታል (ሕዝ.31)፡፡ ይሁን እንጂ ኢሳ.14 በተለይም ቁ.12-14 በትዕቢት አማካኝነት ስለተነሳው ትዕቢት የሚገልጽ ይመስላል፡፡ እግዚአብሔር እያንዳንዱንየሰይጣንን ተፈጥሮና ምንጭ መግለጽ ቢፈልግ ከዚህ የተሻለ አማራጭ የለም፡፡

ሁላችንም ከሲስተማቲክ የሥነ-መለኮት አካሂድ ራሳችንን መጠበቅ አለብን፡፡ ይህም የተለያዩና ጥቃቅን እንዲሁም ግራ የሚያጋቡ ጸሐፊዎችን፣ መጽሐፍትን በማጣመር አንዳች መለኮታዊ እንቆቅልሾችን የሚፈጥር ነው፡፡ አልፍሬድ ኤደርሼይም (*The Life and times of Jesus the Messiah,* vol.2, appendices XIII (pp.748-763) and XVI (pp.770-776)) እንደሚለው የረቢያውያን/የረቢዎች አይሁዲነት በከፍተኛ ሁኔታ በፋርሳዊያን የሁለትዮሽ አስተሳሰብ ተጽዕኖ እንደተደረገበት ነው፡፡ በዚህ አቅጣጫ ላይ ረቢዎች ምልካም ምንጮች ሊሆ አይችሉም/አስተማማኝ ምንጮች ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ኢየሱስ በምኩራብ ካለው ትምህርት በፍጹም የተለየ አካሂድ ነበረው፡፡ እንደ እኔ አስተሳሰብ የመላእክት መካከለኛነትና ሕጉን በሲና ተራራ ላይ መስጠቱ አንድ ታላቅ የመላእክት ጠላት/የመላእክት ይዘት ያለው ጠላት የያህዌሕ እና የሰው ዘር ጠላት ነው ለሚለው …… በሩን የከፈተ ይመለስላል፡፡ በጴርሺያን

የሁለትዮሽ አሳብ ሁለት አማልክት አሉ፤ አኪማን(Akimax) እና ኦርማዛ (Ormaza) መልካምና እድል የሚባሉ፡፡ ይህ ሁለትዮሽ በአይሁዳዊነት የተወሳ ወደሆነው የሕግና ሰይጣን ወደሚለው እያደገ መጣ፡፡

የክፋትን ታሪካዊ አመጣጥ በሚመለከት በአዲስ ኪዳን ቀጣይነት ያለው መገለጥ መኖሩ እርግጠኝነት ቢኖረውም ረቢዎች እንደሚናገሩት ግን የተብራራ አይደለም፡፡ ለዚህ አብይ ምሳሌ የሚሆኑን ‹‹ጦርነት በሰማይ ላይ›› የሚለው ነው፡፡ የሰይጣን መውደቅ አስፈላጊ ቢሆንም ዝርዝር ነገሮች ግን አልተሰጡም፡፡ የተሰጠው ነገር እንኳን በዮሐንስ ራእይ የተጋረደ ይመስላል (ራእ.12÷4፡7፡12-13)፡፡ ምንም እንኳን ሰይጣን የተሸነፈና ወደ ምድር የተጣለ ቢሆንም አሁንም እንደ ያህዌህ ባሪያ ሆኖ ያገለግላል (ማቴ.41፤ሉቃ.22፡31-32፤1ኛ ቆሮ.5፡5፤1ኛ ጢሞ.1፡20)፡፡

እንግዲህ ይህን ፍላጎታችንን እዚህ ላይ መግታት ይገባናል፡፡ የሚፈትነንና ክፋትን የተሞላ ስብዕናን የተላበሰ ኃይል አለ፤ ነገር ግን ብቻውን የሆነ አምላክ አለ፡፡ ስለዚህ የሰው ልጅ በሙሉ ለሚወሰደው/ትወሰደው ምርጫ ተጠያቂነት አለበት፡፡ ከድነት በፊትም ሆነ በኋላ መንፈሳዊ ጦርነት አለ፡፡ ድል አድራጊነት ሊመጣ የሚችለው በእግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ክፋትም የተሸነፈ ነው፤ ደግሞም ወደፊት የሚወገድ ነው፡፡

▣ **“ወደ ውጪ ይጣላል”** ይህ የወደፊት የማይሠራ ተግብሮ አመልካች ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ሰይጣን የወደቀበትን ትክክለኛ ጊዜ አይናገርም፡፡ በኢሳ.14 እና ሕዝቅኤል 28 ሰይጣን በሁለተኛ ደረጃ ክርክር/ውይይት ሊደረግበት ይችላል፡፡ ትንቢታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንደ ባቢሎንና ጢሮስ ስላሉት ትእቢተኛ ነገሥታት ይናገራሉ፡፡ የእነርሱ ኃጢአት ያለበት ትዕቢት ሰይጣንን ያንጸባርቃል (ኢሳ.14፡12፣15፤ሕዝ.28፡16)፡፡ ይሁን እንጂኢየሱስ ያለው ሰባው ደቀመዛሙርት ለወንጌል ሲሰማሩ ሰይጣናን ሲወድቅ እንዳየው ነው (ሉቃ.10፡18)፡፡ በብሉይ ኪዳን በመላው ስለ ሰይጣን ታሪካዊ ዕድገት አለ፡፡ በመጀመሪያ እርሱ አገልጋይ መልአክ ነበር፤ በኋላም የእግዚአብሔር ጠላት ሆነ፡፡ ለዚህ አሻሚ የሆነ ጉዳይ ከሁሉም የተሻለው መጽሐፍ የኤ.ቢ.ዳቪድሰን *Old TestameNt Theology* (ገጽ 300-306) ነው፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ ጦርነት በሰማያት ላይ (በራዕይ መጽሐፍ ላይ ከሰጡት ማብራሪያ የተወሰደ)**

ይህንን ፍጥጫ በሚመለከት (ቀኑን) እስከዛሬ ድረስ ብዙ ክርክር አለ፡፡ ኢየሱስም ይህን በሉቃ.10፡18 እና በዮሐ. 12፡31 ላይ የሚጠቅሰው ይመስላል፡፡ ነገር ግን ለዚህ ክስተት የጊዜ ቅደም ተከተል ማስቀመጥ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡

1. ከዘፍጥረት 1፡1 በፊት (ከፍጥረት በፊት)
2. ከዘፍጥረት 1፡1 እና 1፡2 ማካከል (ክፍተተ ጸንሰ ሃሳብ)
3. በብሉይ ኪዳን ከኢዮብ 1-2 በኋላ (ሰይጣን በሰማያት ላይ)
4. በብሉይ ኪዳን ከ1ኛ ነገ.22፡21 በኋላ (ሰይጣን በሰማይ ሠራዊት ስብሰባ ላይ)
5. በብሉይ ኪዳን ከዘካሪያስ 3 በኋላ (ሰይጣን በሰማያት ላይ)
6. በብሉይ ኪዳን እንደ ኢሳ.14፡12፤ሕዝ.28፡15 እና 2.ሄኖክ 29፡4-5 (የእስያ አህጉር ነገሥታት የተፈረዱበት)
7. በአዲስ ኪዳን ከኢየሱስ መፈተን በኋላ (ማቴዎስ 4)
8. በአዲስ ኪዳን ሰባዎቹ ደቀመዛሙርት ተልእኮ ሲሰጣቸው (ሰይጣንን ከሰማይ ሲወድቅ አየው ሉቃ.10፡18)፡፡
9. በአዲስ ኪዳን ወደ ኢየሩሳሌም ኢየሱስ በድል አድራጊነት ሲገባ (የዚህ ዓም ገዢ ወደ ውጭ ተጥሎአል ዮሐ.12፡31)
10. በአዲስ ኪዳን ከኢየሱስ ትንሳኤና ዕርገት በኋላ (ኤፌ.4፡8፤ቆላ.2፡15)
11. በመጨረሻው ጊዜ (ራዕ.12፡7 ምናልባት የተወለደውን ልጅ ፍለጋ ሰማይን ሲወር)

ይህን ጉዳይ ማየት ያለብን በእግዚአብሔርና በክፉ ሠራዊት መካከል እንዳለ ዘላለማዊ ጦርነት ነው፡፡ ይህ ግጭት ፍፃሜው አውሬውና ሠራዊቱ ሲሸነፉ ነው፡፡ በዮሐንስ ራእይ 20 ላይ እንደሚናገረው የክፉ ኃይላት ተለይተው እንደሚወገዱ ነው፡፡

**12፡32 “እኔም ክፍ ያልኩ እንደሆነ”** ይህ የሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ አረፍተ ነገር ሲሆን የሚያሳየውም ለድርጊት መፈጸም ዕድል መኖሩን ነው፡፡ ይህ ቃል ሊኖርው የሚችለው ትርጉም፡-

1. ከፍ አለ (8፡14)
2. ተሰቀለ (8፡28)
3. ከበረ (የሐዋ.2፡33፤5፡31)
4. በጣም ክፍ ከፍ አለ (ፊልጵ.2፡9)

እንግዲህ ይህ በረከት ያለ /ብዙ የቃላት ድባብ ነው የዮሐንስን ወንጌል ልዩ የሚያደርገው፡፡

▣ **“ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ”** ይህ ምናልባት ያህዌን ለእስራኤል ያለውን የቃል-ኪዳን ፍቅር በኤር.31፡3 ላይ የተጠቀሰውንና “በአዲስ ቃል ኪዳን” ላይ የተሰጠውን ክፍል (ኤር.31፡31-34) በተዘዋዋሪ የሚጠቀስ ነው፡፡ እግዚአብሔር በፍቅሩ ሰዎች ወደ እርሱ እንዲመለሱ ይፈልጋቸዋል፡፡ ይህ በተለዋዋጭ ዘይቤ የሚደረግ አገላለጽ በዮሐንስ 6፡44 ተጠቅሶ የተብራራውም በ6፡65 ላይ ነው፡፡

በዚህ ስፍራ “ሁሉን” የሚለው ሁሉን አቀፍ የሆነ ግብዣና የድነት ተስፋ መሆኑን ነው (ዘፍ.3፡15፤12፡3፤ዘፀ.19፡5፤ ኢሳ.2፡204፤ ዮሐ.1፡9፤12፡29፤3፡16፤4፡ 42፤10፡16፤1ኛ ጢሞ.2፡4፤4፡10፤ቲቶ 2፡11፤2ኛ ጴጥ.3፡9፤ 1ኛ ዮሐ.2፡2፤4፡14)!

በዚህ ሀረግ ላይ ክፍ ያለና ትልቅ ትርጓሜ አለ። “ሁሉ” የሚለው የወንድ ፆታን ሊያመልክት ሲችል “ሰዎች ሁሉ” ተብሎ ሊተረጎም ሲችለ ይህንም ማግኘት የሚቻለው ጥንት የግሪክ ምንጮች በP[75], በN2, በB, በL, በW ሲሆን ግዕዝ ፆታ አመልካቹ “ሁሉም ነገሮች” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፤ ይህም የሚኘው በ P[66] እና በN ነው።ግዕዝ ፆታን የሚያመለክተ ከሆነ በቆላ.!፡16-17 ላይ የተጠቀሰውን የክርስቶስን ሰማያዊ የመቤዠት ሥራን ሊያመለክት ሲችለ ይህም ምናልባት በ1ኛ ዮሐ ላይ የገልጽ የተጠቀሰውን የግኖስቲኮችን የስህተት ትምህርት የሚያንጸባርቅ ነው። የUBS[4] መጽሐፍ ቅዱስ ለወንድ ፆታ አመልካች የ”B” ደረጃን (እርግጠኛ የሆነ) ይሰጠዋል።

**12:33 “በምን አይነትም ሞተ ይሞት ዘንድ እንዳለው ሲመለክታቸው ይህን ተናገረ”** ይህ በዮሐንስ የተደረገ ሌላው በኤዲቶሪያል አስተያየት ነው፤ ይህም ከዘዳ 21፡23 ጋር የሚዛመድ ሲሆን በእንጨት ላይ የሚሰቀል “በእግዚአብሔር የተረገመ ነው” የሚል አንደምታ አለው። ለዚህም ነው የኃይማኖት መሪዎች ኢየሱ እንዲሰቀል እንጂ እንዳይወገር ያደረጉት (በድንጋይ)፤ ኢየሱስም ደግሞ ስለሁላችንም የሕግን እርግማን ተሸከመልን (ገላ.3፡13)።

**12:34 “ሕዝቡ ክርስቶስ ለዘላለም እንዲኖር”** ይህ ምናልባት መዝ.69፡4:29፡35-37ን በተዘዋዋሪ ለምጥቀስ የፈለገ የመስላል። ብሉይ ኪዳን ይጠብቅ የነበረው አንድ የሚመጣን መሲህ ብቻ ሲሆን ይህም መሲህ በፍልስጥኤም ምድር ነግሦ የአለምን ሰላም የሚያሰፍን ነው ብሎ ያምናል (መዝ.110፡4፤ኢሳ.9፡7፤ሕዝ.37፡25፤ዳን.7፡14)። “ለዘላለም” ለሚለው በምዕ.6:58 ላይ ልዩ ርዕስ የሚለውን ይመለከቱ።

▣ **“የሰው ልጅ” ሕዝቡ** (ዓውዳዊ መረዳት የሚለውን “ሐ” ላይ ይመልከቱ።) ኢየሱስ ስሰብክና ሲያስተምር (ምናልባት ቁ. 23-24 ለተሰጠው ማዕረግ/መጠሪያ፤ ቁ.30-32 “ከፍ ከፍ” ለሚለው ግሥ) ሰምተው ነበር ማለት ነው፤ ምክንያቱም እርሱ ስለራሱ የሰጠውን ይህንን መጠሪያ ተጠቅመዋልና። ይህ እንግዲህ ሌሎች ኢየሱስን በተሰጠው ማዕረግ የተጠቀመበት ብቸኛው ሥፍራ ነው። ይህ በእርግጥ በአይሁድ ኃይማኖት ውስጥ ዋና መጠሪያ/ማዕረግ አይደለም።

**12:35 “በርሃን ሳለላችሁ ተመላለሱ”** ኢየሱስ አድማጮቹ ለቃሉ ፈጣን ምላሽ ይሰጡ ዘንድ ያነሳሳቸዋል፡ በምድር ላይ የነበረው ጊዜ የተወሰነ ነበር፤ በምድር ላይም የመጨረሻውን ሳምንት ሲጀምር ነው፤ አሁን የተወሰነለትም ሰዓት እንግዲህ ደርሷል (ቁ.23)።

ይህም ክፍል የሚያመለክተው ኢየሱስ ተናገረው ሁሉም ሰው ወንጌል መስማት እንዳለበት መሆኑን የሚያሳይ አንድምታ አለው (የዘሪውን ምሳሌ ይመልከቱ)።

ይህ የሕይወትን ጉዞ/አኗኗር በተለዋዋጭ ዘይቤ መግለጽ ነው (ኤፌ.4፡1፡17፤5፡2፡15)። ይህ በአሁን ጊዜ ያለን የሚሰራ የተገብሮ ትዕዛዝ ነው። ህም እምነት በአንድ ወቅት ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን (ቁ.44-46) ቀጣይነት ያለው ኅብረትና ደቀ መዝሙርነት መሆኑን ኢየሱስ በአጽንኦት ያተናገረበት ነው።

12:36 ይህ ኢየሱስ የዚህ ዓለም ብርሃን መሆኑን የሚያስገነዝበው ጭብጥ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ተደጋግሞ የሚያዩና ትኩረት የተሰጠው ነው (1፡4፡5፡7፡8፡9፤3፡19፡20፡21፤5፡35፤8፡12፤9፡5፤11፡9፡10፤12፡35፡36፡46)። ጨለማና ብርሃን በአይሁድ የጥበብ ሥነ-ጽሑፍ እና በሙት ባህር ጥቅሎች ዘንድ እንደ ሁለት ግልጽ የሆነ ልዩነት እንዳለባቸው ጣምራዎች ነው የሚታዩት።

> NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 12÷36ለ-43
>
> **[36ለ]ኢየሱስም ይህን ተናግሮ ሄደና ተሰወረባቸው።[37-38]ነገር ግን ይህን ያህል ምልክት በፊታቸው ምንም ቢያደርግ፤ ነቢዩ ኢሳይያስ። ጌታ ሆይ፥ ማን ምስክርነታችንን አመነ? የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገለጠ? ብሎ የተናገረው ቃል ይፈጸም ዘንድ በእርሱ አላመኑም። [39-40]ኢሳይያስ ደግሞ። በዓይኖቻቸው እንዳያዩ፥ በልባቸውም እንዳያስተውሉ፥ እንዳይመለሱም፥ እኔም እንዳልፈውሳቸው፥ ዓይኖቻቸውን አሳወረ ልባቸውንም አደነደነ ብሎአልና ስለዚህ ማመን አቃታቸው። [41]ክብሩን ስለ አየ ኢሳይያስ ይህን አለ፥ ስለ እርሱም ተናገረ። [42]ከዚህም ጋር ከአለቆች ደግሞ ብዙዎች በእርሱ አመኑ፤ ነገር ግን ከምኵራብ እንዳያስወጡአቸው በፈሪሳውያን ምክንያት አልመሰከሩለትም፤ [43]ከእግዚአብሔር ክብር ይልቅ የሰውን ክብር ወደዋልና።**

12:37 እንዴት ያለ የሚያሳዝን አስተያየት ነው! መንፈሳዊ እውርነት አስፈሪ ነው (2ኛ ቆሮ.4፡4)። ይህ ጥቅስ ይቅርታ የማይደረግለትን ኃጢአት አጉልቶ ያሳያል (በምዕ.5:21 ላይ ልዩ ርዕስ የሚለውን ይመልከቱ።)።

**12:38 “ነቢዩ ኢሳያስ”** ይህ በኢሳ.53፡1 ላይ መከራን ስለሚቀበለው የእግዚአብሔር አገልጋይ ከሚናገረው ክፍል የተጠቀሰ ነው።

12:39-40 እነዚህ አስቸጋሪ ጥቅሶች ናቸው፡፡ ሰዎች መላሽ እንዳይሰጡ እግዚአብሔር ልባቸውን ያደነድነዋል; እኔ የራሴን አስተያየት ከኢሳ.6:9-10 እና ከሮሜ 11:7 አስገብቻለሁ/ከትቻለሁ (www.freebiblecommeNtary.org የሚለውን ይመልከቱ፡፡)፡፡

ኢሳ.6:9-10 ልክ ያህዌ የራሱን ዓላማ ለኢሳያስ አገልግሎት እንደገለጠ ሁሉ እንዲሁ ደግሞ የእርሱ መልእክት ከይሁዳ የሚያመጣውን ምላሽ ደግሞ እግኢአብሔር ገልጦለት ነበር፡፡

1. ሂድ ቁ.9 DBD229. KB ትዕዛዛዊ
2. ንገር ቁ.9 DBD55፤ KB የተሟላ ድርጊት
3. ስማ ቁ.9 ትዕዛዝንና ፍጹምነትን በሚያሳይ፤ DBD1033 KB 1570
4. አታስተውሉምም ቁ.9 DBD106፤KB122 ይህ በሴሜቲክ ቋንቋ ለስለስ ያለ ትዕዛዝን ለመጥቀስ ያገለግላል፤ ምዕ.1:3፤5:21፤10:13
5. ማየትንም ታያላችሁ፤ ትዕዛዝን እና ፍጹምነትን የሚያሳይ ዓረፍተ ነገር ነው፡፡ BDB906፤KB1157::
6. አትመለከቱምም ቁ.9፤ DBD393፤ KB380 ይህ ዓረፍተ ነገሩ ባልተሟላ ሁኔታ መተላለፉን ያሳያል፡፡
7. ልባቸውን አደንድን (ይህ ቃል በቃል "ሰባ ወይም ወፈረ" ማለት ነው) ቁ.10፤DBD1031፤ KB1566 ትዕዛዛዊ ንግግር ነው፡፡
8. ጆሮአቸውንም አደንቁር ቁ.10፤ DBD457፤ KB455፤ ትዕዛዛዊ ንግግር ነው፡፡
9. አይናቸውንም ጨፍን ቁ.10፤ DBD1044፤ KB1612፤ ትዕዛዛዊ ንግግር ነው፡፡

እነዚህ ትዕዛዛ አዘል ንግግሮች የሚከተላቸው ነገር አለ (ቀደም ሲል ጥቅም ላይ ውለው የነበሩ ያልተሟሉ ግሦች "ማየት":"መስማት":"ማስተዋል" የሚሉት)፡፡ እግዚአብሔር ምላሽ እንደማይሰጡና እንደማይድኑ ያውቃል (ሁሉን በሚያውቅ ማንነቱ ወይም ልባቸውን በማደንደን)፡፡

1. እንዳይመለሱ : DBD996፤KB1427 በፍፁም ድርጊቱን ማፍረስ
2. እንዳልፈውሳቸው DBD996 KB1272 በፍጹም ድርጊቱን ማፍረስ

ነቢዩ ኢሳያስ መልእክቱን ይሰብካል፤ ጥቂቶች ምላሽ ሲሰጡ አብዛኛው የሕብረተሰቡ ክፍል ግን ምላሽ አይሰጥም (ሮሜ 1:24፡26፡28፤ ኤፌ.4:19) ወይም ምላሽ አይሰጡም (29:9፡10፤ ዘዳ.29:4፤ ማቴ.13:13፤ሮሜ.11:8)! ኢሳያስ በዚህ ቦታ ወንጌላዊ አይደለም፤ ነገር ግን ያቃል ኪዳኑ ነብይ ነው (ማቴ.13:13፤ ማር.4:12፤ ሉቃ.8:10)፡፡ የእርሱ መልእክት ተስፋ ለወደፊት እንጂ እርሱ ለነበረበት ጊዜ አልነበረም፡፡

**ሮሜ** 11:7 "ሌሎቹም ደነዘዙ" ይህ የግሪኩ ተደርጎ ግሥ አመልካች ነው፡፡
(2ኛ ቆሮ.3:14)፡፡ የሚታየውም አንደምታ እግዚአብሔር ልባቸውን እንዳደነደነ ነው (ቁ.8-10)፡፡ የማደንደንን ተግባር የሚፈጽመው ክፉው ነው (2ኛ ቆሮ.4:4)፡፡ "ደነደነ" (ፖሮ) የሚለው መታወርን ወይም ግድ የለሽነትን ለማመልከት የዋለ የህክምና ቃል ሲሆን (ሮሜ 11:25፤ 2ኛ ቆሮ.3:14፤ኤፌ.4:18)፡፡ ይህ ቃል ደግሞ በማር.6:52 ላይ በሐዋሪያት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በ9:18 ላይ (skleruNo) ከሚለው የግሪኩ ቃል የሚለይ ነው፤ ይህም ምህረት ከሚለው ተቃራኒ ነው (ዕብ.3:8፡15፤4:7)፡፡

ይህ ጥቅስ በጣም ግልጽና የ11:1-6 ማጠቃለያ (መደምደሚያ) ነው፡፡ አንዳንድ የተመረጡ ሲያምኑ ያተመረጡት ደግሞ ልባቸውን አደንድነዋል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ጥቅስ የተፃፈው እንደ አንድ የነገረ-መለኮት መፈክር ተለይቶ አይደለም፡፡ ነገር ግን ጸንቶ የቆመ የነገረ-መለኮት ክርክር ደአንዱ ክፍል ነው እንጂ፡፡ በዚህ ጥቅስ ላይ በግልጽ በተቀመጠው እና በምዕራፍ 10 ላይ በተገለጠው ሁሉ አቀፍ በሆነው ግብዣ/ጥሪ መካከል ውጥረት አለ፡፡ እዚህ ጋ ምስጢር አለ፡፡ ነገር ግን መፍትሄው ጣምራ የሆ ተቃርኖዎችን አሳንሶ ማየት ወይም ማኮሰስ ሊሆን አይችልም፡፡

12:39 "**ስለዚህ ማመን አቃታቸው**" ይህ ጥገኛ አመልካችን የአሁን ጊዚ አድራጊ ትዕዛዝ ነው፡፡ ከኢየሱስ ጋር የእምነት ጉዞ ማድረግ አልቻሉም፡፡ የሚያደርጋቸው ተአምራት የሳባቸው ቢሆንም ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን ወደ ማመን አላመጣቸውም፡፡ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ "እምነት" ደረጃዎች አሉ፤ ስለሆነም ሁሉም ወደ ድነት አያደርሱም፡፡ በምዕ.8:31-59 ላይ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ፡፡

▣ "**ኢሳያስ ደግሞ**" ኢሰያስ 6:10፤43:8 የሚያመለክተው በኢሳያስ በኩል ለተላለፈው የእግዚአብሔር መልእክት የአይሁዶችን የልብ ድንዳኔን ነው (ኤር.5:21፤ሕዝ.12:2፤ዘዳ.29:2-4)፡፡

12:40 "**ልብ**" የሚከተለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

**ልዩ ርዕስ፡- ልብ**

"ካርዲያ" *Kardia* የሚለው የግሪኩ ቃል leb ልብ የሚለው የእብራይስጡን ቃል (BDB 523) ለማንጸባረቅ በሰብትዋጅንት እና በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተጠቅሷል፡፡ ይህ ቃል በተለያዩ መንገዶች ጥቅም ላይ ውሏል (Bahuer, ArNdt, Giagrich aNd DaNker, *A Greek-ENglish lexicoN* pp.403-404)::

1. የተፈጥሮአዊ ሕይወት ማእከል፤ ለሰው የሚደረግ ተለዋዋጭ ዘይቤ (የሐዋ.14:17፤ 2ኛ ቆሮ.3:2-3፤ ያዕ. 5:5)
2. የመንፈሳዊ ሕይወት ማዕከል (ማለትም ሞራላዊ)

ሀ. እግዚአብሔር ልብን ያውቃል (ሉቃ.16:15፤ሮሜ 8:27፤ 1ኛ ቆሮ. 14:25፤ 1ኛ ተሰሎ.2:4፤ ራዕ.2:23)
ለ. የሰውን ልጅ መንፈሳዊ ሕይወት የሚያመለክት (ማቴ.15:18-19፤ ሮሜ. 6:17፤ 1ኛ ጢሞ. 1:5፤ 2ኛ ጢሞ. 2:22፤ 1ኛ ጴጥ. 1:22)

3. የአስተሳሰብ ሕይወት ማዕከል (እውቀት ማቴ.13:15፤24:48፤ የሐዋ.7:23፤16:14፤28:27፤ሮሜ.1:21፤10:6፤2ኛ ቆሮ.4:6፤ኤፌ. 1:18፤4:18፤ ያዕ.1:26፤ 2ኛ ጴጥ.1:19፤ራእ.18:7፤ ልብ ከአእምሮ ገር ተመሳሳይ ነው በ2ኛ ቆሮ.3:14-15 እና ፊልጵ 4:7)
4. የፈቃድ ማዕከል (ማለትም ፈቃድ የሐዋ.5:4፤11:23፤1ኛ ቆሮ. 4:5፤5:37፤2ኛ ቆሮ.9:7)።
5. የስሜቶቻችን ማዕከል (ማቴ.5:28፤ የሐዋ. 2:26፡37፤7:54፤21:13፤ሮሜ 1:24፤ 2ኛ ቆሮ. 2:4፤7:3፤ኤፌ.6:22፤ ፊልጵ.1:7)።
6. የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ልዩ ሥፍራ (ሮሜ 5:5፤ 2ኛ ቆሮ. 1:22፤ገላ.4:6/ክርስቶስ በልባችን፡-ኤፌ. 3:17/)
7. ልብ የአንድን ሰው ሁለንተና የሚያመለክት ተለዋዋጭ ዘይቤ ነው (ዘይቤያዊ ቋንቋ) ነው (ማቴ.22:37 ከዘዳ. 6:5 የተወሰደ)። ሃሳቦች፣ዓላማዎች፣ ድርጊቶች አንድ ላይ ተቀናጅተው የግለሰቡን ማንነት ያሳያሉ። ብሉይ ኪዳን ጎላ ያለ የቃሉ አጠቃቀም አለው።
ሀ. ዘፍ. 6:6፤8:21 "እግዚአብሔር በልቡ ተጸጸተ" ሆሴ. 11:8-9ንም አስታውል
ለ. ዘዳ.4:29፤ 6:5 "በፍጹም ልብህና በፍጹም ነፍስህ"
ሐ. ዘዳ. 10:16 "ያልተገረዘ ልብ" እና ሮሜ 2:29።
መ. ሕዝ.12:31-32 "አዲስ ልብ"
ሠ. ሕዝ 36:26 "አዲስ ልብ" እና "የድንጋይ ልብ"

12:41 **"ክብሩን ስለ አየ ኢሳያስ ይህን አለ"** ይህ የሚያመለክተው የብሉይ ኪዳን ነቢያት ስለ መሲሁ እነደተነገራቸው አመልካች ነው (ሉቃ 24:27 ይመልከቱ)። በተጨማሪም "ክብር" የሚለውን ማስታወሻ ከ1:14 ላይ ይመልከቱ።

12:42 **"ከአለቆች ደግሞ በእርሱ አመኑ"** የኢየሱስ መልእክት ፍሬ አፍርቶአል (ቁ. 11፤የሐዋ. 6:7)። በምዕ.2:23 ላይ ልዩ ርዕስ የሚለውን ይመልከቱ።

▣ **"አልመሰከሩለትም"** ልዩ ርዕስ በሚለው በ9:22-23 ላይ የእምነት ቃልን መስጠት የሚለውን ይመልከቱ።

▣ **"ከምኩራብ እንዳያስወጡአቸው"** (9:22፤16:2)

12:43 ይህ የሚያመለክተው እውነተኛ እምነት ደካማና በፍርሃት የሞላ ሊሆን እንደሚችል ነው! የዮሐንስ ወንጌል ማመን (ፖሮ) የሚለውን በተለያዩ ትርጉሞች ይጠቀመዋል። መጀመሪያ መሳብ፣ ቀጥሎ ስሜታዊ ምላሽ መስጠት ከዚያም በእውነት ወደ ሚያድን እምነት መሸጋገር ነው።

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 12÷44-50
**[44]ኢየሱስም ጮኸ፥ እንዲህም አለ፥ በእኔ የሚያምን በላከኝ ማመኑ ነው እንጂ በእኔ አይደለም፤ [45]እኔንም የሚያይ የላከኝን ያያል። [46]በእኔ የሚያምን ሁሉ በጨለማ እንዳይኖር እኔ ብርሃን ሆኜ ወደ ዓለም መጥቻለሁ። [47]ዓለምን ላድን እንጂ በዓለም ልፈርድ አልመጣሁምና ቃሌን ሰምቶ የማይጠብቀው ቢኖር የምፈርድበት እኔ አይደለሁም። [48]የሚጥለኝ ቃሌንም የማይቀበለው እርሱ የሚፈርድበት አለው፤ እኔ የተናገርሁት ቃል እርሱ በመጨረሻው ቀን ይፈርድበታል። [49]እኔ ከራሴ አልተናገርሁምና፤ ነገር ግን የላከኝ አብ እርሱ የምለውን የምናገረውንም ትእዛዝ ሰጠኝ። [50]ትእዛዙም የዘላለም ሕይወት እንደ ሆነች አውቃለሁ። ስለዚህ እኔ የምናገረውን አብ እንደ ነገረኝ እንዲሁ እናገራለሁ።**

12:44 **"በእኔ የሚያምን በላከኝ ማመኑ ነው እንጂ በእኔ አይደለም"** የእምነት ግቡ የኋላ የኋላ በአብ ማመን ነው (1ኛ ቆሮ. 15:25-27)። ይህ ተደጋግሞ የሚታይ ሃሳብ ነው (ማቴ. 10:40፤ 5:20)። ወልድን ማወቅ ማለት አብን ማወቅ ነው (1ኛ ዮሐ. 5:10-12)።

12:45 እግዚአብሔር ምን ይመስላል? ኢየሱስን ማየት ማለት እግዚአብሔርን ማየት ነው (14:7-10)!

12:46 ከዘፍጥረት 3 ወዲህ ዓለም ያለው በጨለማ ውስጥ ነው (6:5፡11-12፤8:21፤መዝ.14:3፤ኢሳ. 53:6፤ሮሜ 3:3-23)።

12:47 **"ቃሌን ሰምቶ የማይጠብቀው ቢኖር"** ይህ ድርጊትን ለመፈጸም የሚያስችል እድል መኖሩን የሚያመለክት የሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ነው። ቀጣይነት ያለው መታዘዝ በእምነት በኩል ባለን ኅብረት ወደፊት የመኻዛችን ምልክት

ነው። የድነት እርግጠኝነት የሚወሰነው (በዮሐ.5:13 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።) ባለን የመታዘዝና የድነት ሕይወት ነው (በ2:31 ላይ ልዩ ርዕስ የሚለውን ይመልከቱ። የያዕቆብ እና የ1ኛ ዮሐ. መጻሕፍት)

**12:47-48 "ዓለምን ላድን እንጂ በዓለም ልፈርድ አልመጣሁምና"** ኢየሱስ የመጣበት ዋናው ምክንያት ዓለምን ለመቤዘት ነው። ነገር ግን የእርሱ መምጣት ሰዎች ስለሕይወታቸው እንዲወስኑ የሚያስገድድ ነው፤ የሚቃወሙት ከሆነ በራሳቸው ፍርደዋል ማለት ነው (በ8:31 ላይ ልዩ ርዕስ የሚለውን ይመልከቱ። ዮሐ.3:17-21)።

12:49-50 ኢየሱስ የተናገረው በራሱ ሥልጣን ሳይሆን በእግዚአብሔር ሥልጣን ነው።

12:50

| | |
|---|---|
| NNB,NKJV | |
| NRSV,TEV | **"ትዕዛዙም የዘላለም ሕይወት እንደሆነች"** |
| NET | **"ትዕዛዙም የዘላለም ሕይወት እንደምትሰጥ"** |
| NJB | **"ትዕዛዙም የዘላለም ሕይወት ማለት እንደሆነች"** |
| REB | **"ትዕዛዙም የዘላለም ሕይወት እንደሆነች"** |
| NID | **"ትዕዛዙም ወደ ዘላለም ሕይወት እንደምትመራ"** |
| NET (የግርጌ ማስታወሻ) | **"የትዕዛዙ ፍፃሜ የዘላለም ሕይወት እንደሆነች"** |

የመጀመሪያው አማራጭ ቃል በቃል የተተረጎመው የግሪኩ ጥቅስ ነው። ሌሎች ደግሞ የጥቅሱን ትርጉም የሚያሳዩ ናቸው።

NASB ዮሐንስ 6:68ን በትይዩ ምንባብ መልክ ሲያስቀምጠው፤ የሚካኤል ማጊል *NT TraNsliliNe* ደግሞ ዮሐንስ 17:8ን እንዲሁ ይገልጸዋል። እንዲሁም JBC (ገጽ 457) ዮሐንስ 10:18ን በትይዩ ምንባብ ያቀርበዋል። በአጭሩ የተጠቀሰው ሐረግ በግልጽ አሻሚ ወይም ግራ የሚያጋባ ነው።

በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ለመጀመሪያዎቹ የመልከአክቱ ተቀባዮች ምንም አይነት የተለየ ምልእክት የሌለው "ትዕዛዝ" የሚለው ቃል የነጠላ እና የብዙ ቁጥር መጠሪያዎቹ የመለዋወጥ ባሕሪ አላቸው።

**ልዩ ርዕስ፡- በዮሐንስ ጽሑፎች ውስጥ ‹‹ትዕዛዝ›› የሚለው ቃል አጠቃቀም**

1. የሙሴን ሕግ ለመጥቀስ አንድ ጊዜ ተገልጾአል ዮሐ.8÷5
2. ከአብ ወደ ወልድ
   ሀ. የራሱን የመቤዠት ሥራ መቆጣጠር ዮሐ.10÷18፤12÷49-50፤14÷31
   ለ. ኢየሱስ አብን እንደሚወድ ዓለም ያውቅ ዘንድ ዮሐ.14÷31
   ሐ. ኢየሱስ የአባቱን ትዕዛዝ ጠበቀ 15÷10
3. ከኢየሱስ ለአማኞች
   ሀ. በፍቅሩ መኖር ዮሐ.14÷15፤15÷10
   ለ. እርሱ እንደወደዳቸው እርስበርሳቸው ይዋደዱ ዘንድ ዮሐ.13÷34፤15÷12፡17፤1ኛ ዮሐ. 2÷7-8፤3÷11፡23፤4÷7፡21፤2ኛ ዮሐ.5
   ሐ. ትዕዛዙን መጠበቅ (ማለትም ለ) ዮሐ. 15÷15፡10፡14፤ 1ኛ ዮሐ. 2÷3፡4፤3÷22፡24፤5÷1-3፤ 2ኛ ዮሐ. 6
4. ከአብ ለአማኞች
   ሀ. በኢየሱስ እመኑ 1ኛ ዮሐ.3÷23 (ዮሐ.6÷29)
   ለ. እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት መመሪያ ሊሆን የሚችል ማብራሪያ ስለሆነ ለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ። እያንዳንዳችን ልንሄድ የሚገባን ባለን መረዳት መጠን ነው። አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጎም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣችሁ ናችሁ። በመሆኑም ይህንን ጉዳይ በሚያብራራው ሰው ላይ ብቻ ልትተው አይገባህም።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት በመጽሐፉ ውስጥ የተነሡትን ዋና ዋና ጉዳዮች በጥሞና እንድታጤናቸው ነው። የተነሡትም ጥያቄዎች እንደ ሃሳብ አነሳሽ ሆነው እንጂ በቀጥታ አይደለም።

1. የአልዓዛር እህት ማርያም የኢየሱስን እግር ሽቶ ለምን ቀባች?
2. በዚህ ድርጊት አቀራረብ ላይ የማቴዎስ፣ የማርቆስ እና የዮሐንስ ወንጌላት በመጠኑ ልዩነት አላቸው። ለምን?
3. የዘንባባ ዝንጣፊ እና ከመዝሙር 118 ጥቅስን በመያዝ ሕዝቡ ኢየሱስን የመገናኘቱ አስፈላጊነት ምንድን ነው?
4. ኢየሱስ ግሪኮች እንዲያናግራቸው በጠየቁት ጥያቄ የተነካበት ለምንድን ነበር?
5. በቁጥር 27 ላይ የኢየሱስ መንፈስ የታወከበት ምክንያት ምን ነበር?
6. ዮሐንስ "ማመን" የሚለውን ቃል በተለያዩ ድባቦች የሚጠቀምበትን ምክንያት ግለጽ።

# ዮሐንስ 13

## የተሻሻሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች አንቀፅ አከፋፈል

| UBS[4] | NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| የደቀመዛሙርቶቹን<br>እግር ማጠብ | ጌታ አገልጋይ<br>ሆነ | የመጨረሻ<br>እራት | ኢየሱስ የራሱን<br>ደቀመዛሙርት<br>እግር አጠበ | እግር ማጠብ |
| 13:1-11 | 13:1-11 | 13:1-11 | 13:1 | 13:1 |
| | | | 13:2-6 | 13:2-5 |
| | | | | 13:6-11 |
| | | | 13:7 | |
| | | | 13:8ሀ | |
| | | | 13:8ለ | |
| | | | 13:9 | |
| | ልናገለግል<br>ይገባል | | 13:10-11 | |
| 13:12-20 | 13:12-30 | 13:12-20 | 13:12-17 | 13:12-16 |
| | | | | 13:17-20 |
| | | | 13:18-20 | |
| ኢየሱስ እንደሚከዳ<br>ተነበየ | | | ኢየሱስ<br>እንደሚከዳ<br>ተተነበየ | የይሁዳ ክህደት<br>አስቀድሞ ተናገረ |
| 13:21-30 | | 13:21-30 | 13:21 | 13:21-30 |
| | | | 13:22-24 | |
| | | | 13:25 | |
| | | | 13:26-29 | |
| | | | 13:30 | |
| አዲስ ትዕዛዝ | አዲስ ትዕዛዝ | | አዲስ ትዕዛዝ | የስንብት<br>ንግግሮች |
| 13:31-35 | 13:31-35 | 13:31-35 | 13:31-35 | 13:31-35 |
| የጴጥሮስ መካድ<br>ተተነበየ | ኢየሱስ<br>የጴጥሮስን መካድ<br>አስቀድሞ ተናገር | | ኢየሱስ<br>የጴጥሮስን መካድ<br>አስቀድሞ ተናገረ | |
| 13:36-38 | 13:36-38 | 13:36-38 | 13:36ሀ | 13:36-38 |
| | | | 13:36ለ | |
| | | | 13:37 | |
| | | | 13:38 | |

## *ሦስተኛ የጥናት ዑደት*

### *የመጀመሪያውን ፀሐፊ ዋና ሐሳብ በአንቀፅ ደረጃ መከተል*

*ይህ የጥናት መመሪያ ሊሆን የሚችል ማብራሪያ በመሆኑ ለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጐም ኃላፊነት አለብህ እያንዳንዳችን መንገዝ ያለብን ባለን መረዳት መጠን ሊሆን ይገባል በአተረጓጐም ወቅት አንተ መጽሐፍቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ናቸው በመሆም ይህንን ጉዳይ በሚያብራራው ሰው ላይ ብቻ መተው የለብህም*

*ሙሉውን ምዕራፍ በአንድ ጊዜ አንብበው ዋና ሐሳቦቹንም ለያቸው የራስህን አከፋፈል ከአምስቱ የተሻሻሉ ትርጉሞች ጋር አስተያያቸው በአንቀፅ መከፋፈል በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት የሚካሄድ ባይሆንም ለአተረጓጎም ክህሎት እምብርት የሆነውን የመጀመሪያውን ፀሐፊ ዋና ሐሳብ ለመከተል ግን ቁልፍ ጉደይ ነው እያንዳንዱ አንቀፅ የሚያወሳው ስለአንድ ሐሳብ ብቻ ነው፡፡*

1. *የመጀመሪ አነቀፅ*

2. *ሁለተኛ አንቀፅ*

3. *ሦስተኛ አንቀፅ*

4. *ወ.ዘ.ተ*

## ዓውዳዊ ግንዛቤዎች፣ 13:1-38

*ሀ. የዮሐንስ ወንጌል የኢየሱስን ምልክቶች የሚደመድመው ከምዕራፍ* 12 *ነው፡፡ ምዕራፍ*13 *የሚጀምረው የወደዳቸው እስከመጨረሻው መውደዱን በገለጠበት ሳምንት ነው፡፡*

*ለ. የ NASB የጥናት መጽሐፍቅዱስ የግርጌ ማስታወሻ አስደናቂ ማብራሪያን ይሰጣል፤ የግሪኩ agape* (*አጋፔ*) *እና agapes* (ፍቅር) *ከምዕ* 11-12 *ድረስ ሳምንት ጊዜያት ሲጠቀሱ በምዕ* 13-17 *ላይ ግን ለ*31 *ጊዜያት ተጠቅሷል፡፡*

*ሐ. ሌሎች ወንጌላት እንደሚያደረጉት ዮሐንስ የጌታን ራት*(*Eueharist*) *ኤዘግብም የሚናገረው ግን በዚያች ምሽት በላይኛው የሮብ ላይ ያልተደረገው ንግግር ነበር* (*ምዕ* 13-17 *የወንጌሉን በጣም አስፈላጊው ክፍያ ነው፡፡ ለዚህም ነው የኢየሱስን ማንነትና ሥራውን ልዩና ኃይለኛ በሆነ መንገድ የሚገልጠው*)*፡፡ አንዳንዶች የዚህን ክፍል ግድለት እያደገ የመጣውን የቀድምዎ ቤተክርስትያን የቅዱሱ ቁርባን ሥርዓት ልዩ ትኩረት ዝቅ ለማድረግ ሆን ተብሎ የተደረገ ነው ብለው ያስባሉ፡፡ ዮሐንስ ግን የጌታን መጠመቅ ወይም የጌታራትን በሚመለከት የሚሰጠው ማብራሪ የለም፡፡*

*መ. የዮሐንስ* 13 *ታሪካዊ ዓመድ በሉቃ* 22:24 *ውስጥ ሊታይ የሚችል ነው ደቀመዛሙርት ግን ከመካከላቸው ታላቅ ማን እንደሆነ ግና ሲጨቃጨቁ ይታያሉ፡፡*

*ሠ. ገሐዳዊው የምዕ* 13-17 *መነሻ ቦታ በኢየሩሣሌም የሚገኘው የላይኛው ደርብ ሲሆ* (*ወይም ምናልባት ምዕ* 15-17 *ላይ ወደ ጌቴሴማኒ ሲሔዱ፤* 14:31) *ምናልባትም በዮሐንስ ማርቆስ ቤት ኢየሱስ በይሑዳ በተከዳበት ምሽት፡፡*

*ረ. ኢየሱስ እግር በማጠቡ ጉዳይ ላይ ሁለት ለየት ያሉ ዓላማዎች ያሉ ይመስላሉ፤*
   1. *ቁ* 6-11 *እኛን ተክቶ በመስቀል ላይ የሚሠራውን ሥራ ቀድሞ ያስጠነቅቃል*
   2. *ቁ.* 12-20 *ላይ ትህትናን በሚመለከት ዓላማ ያለውን ትምህርት ይሰጣቸዋል* (*በሉቃ* 22:24 *እይታ*)*፡፡*

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 13፡ 1-11**

**[1]ኢየሱስም ከፋሲካ በዓል በፊት ከዚህ ዓለም ወደ አብ የሚሄድበት ሰዓት እንደደረሰ አውቆ በዚህ ዓለም ያሉትን ወገኖቹን የወደዳቸውን እስከመጨረሻ ወደዳቸው፡፡ [2]እራትም ሲበሉ ዲያቢሎስ በስምዖን ደጅ በአልቆወቱ በይሁዳ ልብ አሳልፎ እንዲሰጠው አሳብ ካገባ በኋላ [3]ኢየሱስ አብ ሁሉን በእጁ እንዲሰጠው ከእግዚአብሔርም እንደወጣ ወደ እዚአብሔርም እንዲሄድ አውቆ [4]ከእራት ተነሳ ልብሱንም አኖረ ማበሻም ጨርቅ ወስዶ ታጠቀ [5]በኋላም በመታጠቢያው**

ውኃ ጨመረ የደቀመዛሙርቱንም እግር ሊያጥብና በታጠቀበት ማበሻ ጨርቅ ሊያብ ጀመረ [6]ወደ ስምዖን ጴጥሮስም መጣ እርሱም ጌታ ሆይ አንተ የእኔን እግር ታጥባለህን? አለው [7]ኢየሱስም መልሶ እኔ የማደርገውን አንተ አሁን አታውቅም በኋላ ግን ታስታውሰዋለህ አለው። [8]ጴጥሮስም የእኔን እግር ለዘላለም አታጥብም አለው። ኢየሱስም ካጠብኩህ ከእኔ ጋር እድል የለህም ብሎ መለሰለት። [9]ስምኦን ጴጥሮስም ጌታ ወይ እጄንና ራሴን ደግሞ እንጂ እግሬን ብቻ አይደለም አለው [10]ኢየሱስም የታጠበ እግሩን ከመታጠብ በቀር ሌላ አያስፈልገውም ሁለንተናው ግን ንፁሕ ነው እናንተም ንፁሐን ናችሁ ነገር ግን ሁላችሁ አይደላችሁም አለው። [11]አሳልፎ የሚሰጠውን ያውቅ ነበርና፣ ስለዚህ ሁላችሁ ንፁሐን አይደላችሁም አለ።

13:1 ከፋሲካ በዓል በፊት ዮሐንስና ወንጌላት የማይስማሙበት ነገር ይህ ዕለት ከፋሲካ በዓል ምግብ በፊት ወይስ ሁሉ የፋሲካ በዓል ምግብ ነው በሚለው ላይ ነው። ሁለቱም የፋሲካውን ምግብ በሐሙስና በስቅለቱ ዕለት ዓርብ ላይ ያደርባታል (19:31) ማር 15 :43 ሉቃ 23:54) የዚህ በዓል ምግብ የሚያስተውሰው የእስራኤላዊያንን ከግብፅ ነፃ መውጣት ነው (ዘፀ 12) ዮሐንስም የሚያረጋግጠው ከተለመደው የፋሲካ በዓል በራት እንደሆነ ነው (18:28፣19:14፣31፣42)።

የኢሴን (*EsseNe*) ማሕበረሰብ የተለየ የቀን አቆጣጠርን በመጠቀሙ ምናልባት የፋሲካን በዓል ከአንድ ቀን በፊት እንዲሆን አድርጎታል (ከሔኖክና ከመቃብያን መጽሐፍት የተወሰደ የፀሐይ ካላንደር ሲሆን የነበረውን የክህነት አገልግሎ ለመቃወም የተዘጋጀ ነበር።

የድሮም የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ አሁን ያለውን ስኮላርሺፕ ሲያጠቃልል "ከፋሲካ በፊት" የሚለው ትክክል ሲሆን ወንጌላትም የሚያረጋግጡት የምግቡን ፋሲካ ምልክትነት ነው ብለው ይገምታሉ። ሁልጊዜም ልናስተውል የሚገባን እውነት ወንጌል የምዕራባዊያን፣ የምክንያትና የውጤት እንዲሁም የታሪካዊ ጊዜ ቅደም ተከተል ጉዳይ አይደለም። ይህም ታሪክ በተለያዩ መንገዶች ይፃፋሉ፤ ይህም ትክክል ወይም ስህተት፣ እውነት ወይም ሐሰት በመሆኑ ብቻ አይደለም። ታሪክ አሁን ለለንበት ጉዳይ /ፍላጎት/ ሁኔታዎች መፍትሔ ይሆን ዘንድ ያለፈውን ጉዳይ መግለፅ ማለት ነው። ትክክለኛው ጉዳይ ግን ታሪክን ማን/ለምን ፃፈው የሚለው ነው። ታሪካዊ ትረካዎችና ወንጌላት ላይ ጥሩ የሆነ ውይይት ለማድረግ የጕርዲን ፊ እና የዳግላስ እስቱዎርት፡- *"How to Read the Bible for all its worth"* (ገጽ 89-126) የሚለው መፅሐፍ ነው።

▣ **"ኢየሱስ ሰዓት እንደደረሰ አውቆ"** "አውቆ" የሚለው የተጠናቀቀ አድርጎ የዘግጽ ነው (ልክ እንደ ቁ.3) ። ኢየሱስ ከአባቱ ጋር ያለውን የተለየ ግንኙነት ቢያንስ ከአሥራ ሁለት ዓመቱ ጀምሮ ያውቅ ነበር (ሉቃ 2:41-51) : በምዕ 12:20-23 ላይ የግሪኮች ወደ እርሱ መምጣት የሚያሳየው የሚምትበትና የሚከብርበት ሰዓት መድረሱነ ነው (2:7:6፣8፣30፣8፣20፣12:23:27፣17:1

▣ **"ከዚህ ዓለም ወደ አብ የሚሄድበት ሰዓት"** የዮሐንስ ወንጌል አሁንም ቀጤ ዱዋሊዝም ላይ ትኩረት ያደርጋል፡- ከላይ እና ከታች (ቁ.3) ኢየሱስ የተላከው (8:42) በአብ ሲሆን አሁን ደግሞ ወደ መጣበት ይመለሳል። ወንጌላት ኢየሱስን የሚያሳዩት አጋድሞ ዱዋሊዝምን እንደሚስተምር አድርገው ነው። የተፈፀመው እና ገና የሚፈፀመው የእግዚአብሔር መንግስት ብለው።

ስለወንጌላት የዘመናችን አንባቢ ምላሽ ሊሰጥባቸው የሚገቡ በርካታ ጥያቄዎች አሉ። ነገር ግን ሁሉ ሲነገር እና ሲለውም እነዚህ ቅዱሣን ፅሑፎች የሚገልጡት በላይ የሚቆም መፅሐፍ ቅዱሳዊ እይታን ነው።

1. አንድ አምላክ ብቻ አለ
2. ልዩ ፍጥረቱ የሆነው የሰው ልጅ በኃጢያትና በአመፅ ውስጥ ወድቋል
3. እግዚአብሔር ሥጋ የለበሰን አዳኝ ልኳል (መሲህ)
4. የሰው ልጅ በእምነት በንስሐ፣ በመታዘዝና በፅናት ምላሽ ሊሰጥ ይገባል
5. እዚአብሔርንና ፍቃዱነ የሚቃወም ስብዕናን የተላበሰ የክፉ ኃይል አለ
6. ማስተዋል የሚችሉ ፍጥረታት በሙሉ በእግዚአብሔር ፊት ኃላፊነት አለባቸው

"መለየት" (*metabaiNg*) የሚለው ቃል በዮሐንስ ፅሑፎች ውስጥ የሚያመለክተው ከወደቀው የዚህ ዓለም ሕይወት (ኃጢያትና አቤፅ) ወደ አዲስ የመንፈስና የዘላለም ሕይወት መሸጋገርን ነው (5:24 13:1 ዮሐ3:14 በገ, 3 ላይ ከተጠቀሰው በስተቀር)

▣ **"የወደዳቸውን"** የግሪኩ ሐረግ በግብፃዊያን ፓፒረስ ላይ የተጠቀሰው (*moultoNs muthigaN; The vocabulary of the Greek New TestNmeNt*) ለ "የቅርብ ዘመድ" (ሉቃ8:19 — 21) ነው።

በዚህ ዓለም ያሉትን" ዮሐንስ ዓለም (*kosmos*) የሚለውን ቃል በተለያዩ በርካታ ትርጉሞች ይጠቀማል።

1. ይህንን ፕላኔት (1:10፣11:9 16:21 17:5፣ 11፣24፣ 21:25)
2. የሰው ልጅ (3:16 ፣ 7,4፣ 11:27፣ 12:19 14:22: 18፣20:37)
3. አመፀኛው የሰው ዘር (1:10፣29:3:16-21-4:42-6:33-7:7-9:39 12:31፡15፡18-17:25)

በ14:17 ላይ ልዩ ርዕስን ይመልከቱ።

▣ **"እስከመጨረሻ ወደዳቸው"** ይህ "*telas*" የሚለው የግሪኩ ቃል ሲሆን የሚያመለክተውም የአንድን ዓላማ መፈፀም ነው፡፡ ይህም ኢየሱስ በመስቀል ላይ የፈፀመውን የማዳን ሥራ የሚያሳይ ነው፡፡ የዚህ ቃል ተመሳሳይ ይዘት ያለው ሌላው ደግሞ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ያለ የተናገረው የመጨረሻው ቃል ነው (19:30)፡፡ "ተፈፀመ" የሚል ይህም ሁኔታ ከግብፃዊያት ፓፒረስ እንደምንረዳው "በሙሉ ተከፍሏል" የሚል አንደምታ አለው፡፡

**13:2 "ለራትም ሲባሉ"** በዚህ ነጥብ ላይ በግሪኩ ምንጮች ላይ ልዩነት አለ፡፡ ልዩነቱ የሚያካትተው በግሪክ አንድ ቃል ብቻ ነው፡፡

1. *geNomeNous* የአሁን ጊዜ በኤዝ አንቀፅ (በእራት ጊዜ) *mss- B- L-W*
2. *geNomeNous* አድራጊ በኮዝ አንቀፅ ነው (ከእራት በኂላ) *mss* $P^{66}$ $N^{2}$ *A D*

የUBS[4] ትርጉም ለመጀመሪያው አማራጭ (#1) የ"B" ደረጃን ይሰጠዋል (ለእርግጠኝነት የቀረበ ማለት ነው)
ምናልባትም ይህ ማለት

1. ከእራት በኂላ
2. ከመጀመሪያው የበረከትፅዎ በኂላ ሂደቱ እጅ መታጠብን ሲፈልግ/ሲያስፈልገው
3. ከዋደተኛው በረከት ድዋ በኂላ

**ልዩ ርዕስ የመጀመሪያው ክ/ዘ የአይሁድ እምነት የፋሲካ በዓል ደንብ**

*ሀ. ፀሎት*
*ለ. አንድ ፅዋ ወይን*
*ሐ. የእጅ እጥበት በአስተናጋጅ መታጠቢያን ለተጋባዥ ማሣለፍ*
*መ. መራራ ቅጠልን በመረቅ ውስጥ ማጥቀስ*
*ሠ. ጠየት እና ዋናው ምግብ*
*ረ. ፀሎት እና መራራ ቅጠልን ለሁለተኛ ጊዜ ማጥቀስ መረቃ*
*ሰ. ሁለተኛው የወይን ፅዋ እና ለልጆች ጥያቄና መልስ* (ዘፀ 12:26-27)
ሽ. *መዝ* 113-114 *መዘመር እና ፀሎት*
*ቀ. ዋናው የሥነ ሥርዓት መሪ እጁን ከታጠበ በኂላ ለእያንዳንዱ ያጠቅላል*
በ. *ሁሉም ሆዱ እስኪሞላ ይበላል፤ በቁራጭ የጠቦት ሥጋ ያበቃል፡፡*
*ተ. እጁን ከታጠቡ በኂላ ሦስተናው የወይን ፅዋ*
*ነ. መዝ* 125-1183 *መዘመር*
*ኘ. የመንግሥቱን መምጣት የሚያመለክተው አራተኛው ፅዋ*
ብዙዎች የጌታ እራት ስርዓት በ"K" ውስጥ እንደተደረገ ያምናሉ፡፡

▣ **"ዲያቢሎስ በስምኦን ደጅ በአስቆሮቱ በይሁዳ ልብ አሳልፎ እንዲሰጠው አሳብ ካገባ በኂላ"** ይህ በአድር ግስ ድርጊት *መፈፀሙን የሚያሳይ ቦዝ አንቀፅ ነው፡፡ ኢየሱስ ይህንን ከመጀመሪያው ያውቀው ነበር* (6:70)፡፡ ክፉም (በ12-31 ላይ ልዩ *ርዕሱን ይመ*) ለረጅም ጊዜያት ይሁዳን ሲፈትነው ነበር፤ ነገር ግን በቁ 27 ላይ ክፉው ሙሉ በሙሉ ተቆጣጠረው፡፡ በ12:40 ላይ ልብ የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመ" ስለይሁዳ በ18:1 ላይ የተሰጠውን ሙሉ ማብራሪያውን ይመ፡፡

**13:3 "ኢየሱስ አብ ሁሉን በእጁ እንደሰጠው አውቆ…"** በቁ1 ላይ እንደተገለፀው ይህ በአድራጊ ግስ ድርጊት መፈፀምን (መጠናቀቁን) የሚያሳይ በዛ አንቀፅ ነው፤ ይህም የግሪኩን አድራጊ ግስን አመልካችን ያስከትላል ይህ ኢየሱስ ስለራሱ ያለውን ግንዛቤና ሥልጣን በሚመለከት ካደረጋቸው አስደናቂ ንግግሮች አንዱ ነው (3:35፣17:2 ማቴ 28:18) የድርሰት ፈፃሚው ግሥ በጣም አስፈላጊ ነበር አብ ኢየሱስ ከመስቀሉ በፊት "ሁሉተን" ሰጥቶት ነበር, እነዚህ ነገሮች የተሰጡት ስለታዘዘ እንደሽልማት ሳይሆን ከማነቱ አንፃር ነበር እርሱ ማን እንደነበር ያውቅ ነበር ከእነርሱ ማናቸው ታላቅ ማን እንደሆነ የሚጣሉትን የሚከራከሩትን የደቀመዛሙርቱን እግር ግን አጠበ!

▣ **"ከእግዚአብሔርም እንዲወጣ"** ይህ በቁ3 ላይ ከተጠቀሱት ሦስት ነገሮች አንዱ ነው ኢየሱስም ያውቅ የነበረው

1. አብ ሁሉን በእጁ እንደሰጠው
2. ከእግዚአብሔር እንዳወጣ
3. ወደ እግዚአብሔርም እንደሚሔድ (7:33፤14:12፤28፤16:5፤10፤17፤28፤20-27)

የመጨረሻዎቹ ሁለቱ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የተለመደው የቀጤዴዋሊዝም ክፍሎች ናቸው፡፡

ሁለኛው ተራ ቁጥር በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ለየት ያለ ሐረግ ነው (8:42፣13:3፣16:28፣30፣17:8) ምጭንና ቦታን የመጥቀስ ድባብ አለው (ከሰማ የመጣ ምላክ መሆኑን) 13:4 "ከእራት ተነሣ" በወንበር ላይ ተቀመጡ ሳይሆን እግሮቻቸውን ወደ ኂላ አድርገው በግራ ክርኖቻቸው ተደግፈው ነበር፡፡

▣ **"ልብሱንም አኖረ"** ብዙው ቁጥር የሚያመለክተው ውጫዊ ልብሱ መሆን ነው (19:23ሐዋ 8:16)፡ ተመሳሳዩ ግስ ደግሞ በ10:11:15:17:18 ኢየሱስ ራሱን ስለመስጠቱ ለማመልከትመጠቀሱ የሚያስደንቅ ነው (ቁ-37)። ይህ ምናልባት የዮሐንስ የአገባብ ስልጡ ይሆናል። የእግር ማጠቡ ሥነሥርዓት ትህትናን ማስተማር አላማው ካደረገ የበለጠ ትምህርት ያለው ይመስላል (ቁ.6-10)።

13:5 **"የደቀመዛሙርቱንም እግር ሊያጥብ"** ይህ የግሪክ ቃል "የሰውነትን የተወሰነ ክፍል ብቻ ማጠብ" ለመግለፅ የሚጠቀስ ነው። በቁ.10 ላይ የተጠቀሰው ቃል ሙሉ መታጠብን ለማመልከት ነው። እግር ማጠብ የባርያዎች ተግባር ነበር። እንዲህ አይነቱን ርቢዎች እንኳን ከደቀመዛሙርቶቻቸው አይጠብቁም። ኢየሱስ፤ አምክነቱን እያወቀ በቅናት እና በጉጉት የተሞሉትን የደቀመዛሙርቱን እግር ለማጠብ ፈቃደኛ ነበር (ይሁዳንም ቢሆን)!

13:6 የጴጥሮስ ጥያቄ የኢየሱስን ሁኔታ የሚቃወም ምዕታዊ መንገድ ይመስላል። ጴጥሮስ ብዙውን ጊዜ ኢየሱስ ምን ማድረግ እንዳለበትና እንደሌለበት እንደሚያውቅ ያስባል (ማቴ 16፡22)

13፡7 ከኢየሱስ ጋር የኖሩት ሐዋርያት ብዙ ጊዜ የእርሱን ትምህርቶችና ድርጊቶች ይረዱም ነበር (2፡22፤10፡6፤12፡16፤14፡26፤16፡18) ይህ ያለመረዳት የቃጤ ዱዋሊዝም አመለካከትን የመግለጫው አንዱ መንገድ ነበር።

13፡8 **"የእኔን እግር ለዘላለም አታጥብም"** ይህ ጠንካራ ጣምራ አሉታዊ ንግግር ሲሆን ይህም ማለት "በፍፁ በምንም አይነት ሁኔታ" እንደማለት ነው "በፍፁም" ለሚለው ቃል በ6፡58 ላይ ልዩ ርዕስን ተመልከት።

▣ **"ካላጠብኩህ ከእኔ ጋር እድል የለህም"** ይህ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ አረፍተ ነገር ነው። ይህ ጥቅስ በተዘዋዋሪ የሚያመለክተው ከተግባራዊ ትምህርቱ ዓላማ የበለጠ በዚህ ሥፍራ እየሆነ እንዳለ ነው። ቁ 6-10 ኢየሱስ በመስቀል ላይ ለኃጢአት የሰጠውን ይቅርታ የሚያዛምድ ይመስላል።

ሁለተኛው ሐረግ ምናልባት የሚያመለክተው ከውርስ ጋር የተያያዘን የብሉይ ኪዳን ውርስን ነው (ዘዳ 12:12፣ጓዳው 20:1:1ክ12:12) ይህ መከልከልን የሚያመለክት ጠንካራ አነጋገር ዘይቤ ነው

13:9 የግሪኩ አሉታዊ ቦዝ አንቀፅ (*ME*) የሚያመለክተው በተዘዋዋሪ ትዕዛዝን የሚጠቅስ ነው፡ "ካላጠብኩህ"

13:10 **"የታጠበ"** ኢየሱስ በዘይቤያዊ አነጋገር ስለመቤዘት እየተናገረ ነው። ጴጥሮስ ታጥቧል (15:3፣ቲቶ3:5) ነገር ግን የጠበቀ ሕብረትን ለማድረግ በንስሐ ሕይወት መቀጠል አለበት (1ዮሐ 1:9)

ሌላው አውዳዊ አማራጭ ደግሞ ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ስለ ይሁዳ መክዳት ነው የሚለው ነው (ቁ11 እና 18)። ስለዚህ ማጠብ (መታጠብ) የሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር (1) የጴጥሮን አካል የሚያመለክት ወይም (2) የሐዋርያትን ቡድን ነው።

▣ **"እናንተም ንፁሐን ናችሁ ነገር ግን ሁላችሁ አይደላችሁም"** "እናንተ" የሚለው የብዙ ቁጥር ሲሆን የሚመለክተውም ከይሁዳ በስተቀር ለኢሱስ የቀረቡትን (ቤተኞች) ደቀመዛሙርትን ነው(ቁ11፣18፣6:70)።

13:11 የ"*TEV*" እና "*NET*" መጽሐፍቅዱሶች ይህንን ጥቅስ በቅንፍ ውስጥ ያስቀምጡታል፤ በፀሐፊው ከተሰጡት የኤዲቶሪያል አስተያየቶች እንደ አንዱ አድርገውም ይተረጉሙታል።

**NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 13÷12-20**
**[12] እግራቸውንም አጥቦ ልብሱንም አንስቶ ዳግመኛ ተቀመጠ፤ እንዲህም አላቸው ያደረግሁላችሁን ታስታውሳላችሁን? [13]እናንተ መምህርና ጌታ ትሉኛላችሁ እንዲ ነኝና መልካም ትላላችሁ። [14]እንግዲህ እኔ ጌታና መምህር ስሆ እግራችሁን ካጠብሁ እናንተ ደግሞ እርስበርሳችሁ አግራችሁን ትተታጠቡ ዘንድ ይገባችኋል። [15]እኔ ለእናንት እንዳደረግሁ እናተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና። [16]እውነት እውነት እላችኋለሁ ባሪያ ከጌታው አይበልጥም መልዕክተኛም ከላከው አይበልጥም። [17]ይህን ብታውቁ ብታደርጉትም ብፁአን ናችሁ። [18]ስለሁላችሁ አልናገርም እኔ የመረጥኳቸውን አውቃለሁ፤ ነገር ግን መጽሐፍ እንጀራዬን የሚበላ በእኔ ላ ተርከቹን አነሣብኝ ያለው የፊጸም ዘንድ ነው። [19]በሆነ ጊዜ እንደሆንሁ ታምኑ ዘንድ ከአሁን ጀምሬ አስቀድሜ ሳይሆን እነግራችኋለሁ። እውነት እውነት እላችኋለሁ። [20]እውነት እውነት እላችኋለሁ ማናቸውንም የምልከውን የሚቀበል እኔን ይቀበላል እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል።**

13:12:20 ከቁ6:10 በተቀራኒው ኢየሱስ እዚህ ላይ ድርጊቱን የሚገልፀው እንደ ትህትና ምሳ ነው። ደቀመዛሙርቱ እየተከራከሩ የነበሩት ከመካከላቸው ማን ታላቅ ነው በሚለው ላይ ነበር (ሉቃ 22:24)። በዚህ አገባብ ኢየሱስ አድ ባሪ የሚያደርገውን ያደርጋል፤ ማን ማለት እደሆነ እንዴት በሥራ ላይ ማዋል እንደሚችል ጭምር ይገልፃል።

13:14 ይህ አንደኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተነገር ነው፡፡ ይህም ከፀሐፊው አስተያየት አንፃር እውነት ተብሎ የተገመተ ወይም ለዓላማው ሲል ነው፡፡

▣ **"መምህርና ጌታ"** በቁ 13 እና 14 ላይ ያለውን ውሱን ገላጭ ተመልከት፤ እንዲሁም የተቀለበሱ ማዕረጎቹንም ተመልከት በስልጣን የሚናገረው እርሱ ነው፡፡ አብን የሚገልጥ መታዘዝንና ታማኝነትን ከሚከተሉት የሚፈልግ እርሱ ነው፡፡ አማኞች እርሱ የሚያደርገውን ሊከተሉት ይገባቸዋል (ቁ-15)

13:14-15 **"እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል"** ይህ አነጋገር እንዲህ አይነቱን የትህትና ድርጊት ሦስተኛው የቤተክርስትያን ደንብ ወይም ድንጋጌ መሆኑን የሚመለክት ነው፡፡ ብዙዎች የክርስትያን ወገኖች (ቡድኖች) አይደለም ይላል ምክንያቱም

1. ከሐዋርያት ሥራ ስለዚህ ጉዳይ መፈፀም ምም የተመዘገበ ነበር የለም
2. በአዲ ኪዳን ይህ ጉዳይ ትኩረት የተሰጠው አይደለም
3. ቀጣይነት ሊኖረው እንደሚገባ ልክ እንደጥምቀት (ማቴ 28፤19) እና የጌታራት (1ቆሮ 11:17-34) ተለይቶ በፍፁም አልተናገረም፡፡

ይህ ማለት ግን በተዘዋዋሪ እንደ አስፈላጊ የአምልኮ ድርጊት ላይሆን ይችላል ማለት አይደለም፡፡ ኢየሱስ የሰጣቸው "ምሣሌ" ትህትና ሳይሆን መስዋዕትነት ስለሚያስከፍል አገልግሎት ነው (15:12-13) ፡፡ 1ዮሐ 3:16 ይህን እንዴት ያብራራዋል ኢየሱስ እስከ መጨራው ይወዳል (ቁ.1) እንዲሁም አማኞች በመቻላቸው ሁሉ ሊወዱት ይገባል (ራስን መስዋዕት የሚያደርግ ግን ሕይወት፤ የአዳም ውድቀት ተቃራኒው)

3:16 **"እውነት እውነት እላችኋለሁ"** ይህ በቀጥታ "አሜን አሜን" ማለት (ቁ20) ይህ በብሉይ ኪዳን "እምነት" ለሚለው ሌላው መልክ ነው (ዕንባ 2-4)፡፡ በዚህ ደረጃ ኢየሱስ ሲጠቀም ብቸናው ነበር (በማኛውም የግሪክ ሥነፅሑፍ)፡፡ ብዙውን ጊዜ የሚጠቀሰው በመጨረሻ ላይ ሲሆን (1) ለመስማማት ሲባል ወይም (2) ንግግርን ለማስረገጥ ሲሆን በዳረኞተ ነገር መጀመሪያ ላይ ሲጠቀስና ሲደገም ሥልጣን ያለው ትኩረትን የሚስብ መሣሪ ነው፡፡ በ1:51 ላይ አሜን የሚለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት፡፡

"ባሪያ ከጌታው አይበልጥም" ይህ እውነትን ለማስተላለፍ የሚጠቅም የመግቢ ሐረግ ነው፡፡

1. ዮሐ 3:16 መልዕክተኛው ከላከው አይበልጥም
2. ዮሀ 15:20
   ሀ. እኔን አሳደውኝ ከሆነ እናንተንም ያሳድዷችኋል
   ለ. ቃን ጠብቀው ከሆነ ቃላችሁን ደግሞ ይጠብቃሉ
3. ሉቃ 6:40(ተመሳሳይ) ነገር ግን ማንም ሰው በደንብ ከተማረ በኋላ እንደ መምህሩ ይሆናል (ማቴ 10:24)
4. ሉቃ 22:27 (ተመሳሳይ) ነገር ግን በመካላችሁ እንደአገልጋይ ነኝ

13:17 **"ይህን ብታውቁ ብታደርጉትም በፁአን ናችሁ"** የመጀመሪያው ፊደል "ከ" ከፀሐፊው እይታ አንፃር አንደኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ነው፡፡ ሁለተኛው "ብ" ድርጊት የመፈፀም አቅምን የሚያሳይ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተነገር ነው፡፡ ካወቅን ማድረግ አለብን (ማቴ 7:2427፡ሉቃ 6-46-49 ሮሜ 2-13 ያኔ 1-22-25-4-11) ግቡ ዕውቀት ሳይሆን ክርስቶስን የመምሰል ሕይወት ነው ይህም የሚያሳየው፡፡ የሚያደርገው ዘንድ ደሞ (ዘዳ 6:4) የሚለውን "*Shema*" (ሼማ) የተባለውን የእብራይስጥ ግሥ ነው::

13:18 **"መጽሐፍ ያለው ይፈፀም ዘንድ"** ይ የሚያመለክተው ይሁዳን ነው፡፡ ይህ በእግዚአብሔር አስቀድሞ መወሰንና የሰው ላይ ነፃ ፈቃድ የሚገኛኙበት ረቂቅ ጉዳይ ነው፡፡

ኢየሱስም ደቀመዛሙርቱ የመጽሐፍ ቅዱስን ትክክለኛነት አምነዋል(በቅዱሳን መፃህፍት አምነዋል)፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሲነገር ሊታመኑ ይገባ (ማቴ5:17-19)፡፡ በርካታ ጊዜያት ዮሐንስ አስቴት ሲሰጥ "የመፃህፍት ቃል ይፈፀም ዘንድ" ይባል (12:14፣13:18፣15:25፣17:12፣19:24፣36)፡፡ ብዙ ጊዜ ብሉይ ኪዳን በክርስቶስ ሕይወት ውስጥ አንዳች ድርጊት ካልተከሰቱ በቀር ለመረዳት ያስችላል (ምሳሌ ወዬ 11:1) ወይም የአዲ ኪዳን ድርጊት የተሰጡ ተስፋዎ በጣምራ ተሟሉበት ነው (ኢሳ 7:14 ወይም ዳንና 27:11:3፣12:11)፡፡

▣ **"በእኔ ላይ ተረከዙነ አነሣብኝ"** ይህ ጥቅስ ከመዝ 41:9 ላይ የተወሰደ ነው፡፡ ጥብቅ ወዳጅነትንና ቃልኪዳን አብሮ በመብላት የሚገልጠው ባህል የይሁዳን አስከፊ ድርጊት ይከርንነዋል በቅርብ ምሥራቃዊያን ባህል ደግሞ አንድ ሰው የውስጥ እግሩን ሲያሳይ የንቀት ምልክት ነው፡፡

3:19 ይህ ጥቅስ ኢየሱስን የተአምራት ምክቶችና ትንቢቶችን ነው (20:31)፡፡ በዮሐንስ ወንጌል እምነት የሚያድግና ቀጣይነት ያለው ልምምድ ነው፡፡ ኢየሱስ የደቀመዛሙርቱን እምነት/መታመን/ ማመንን በየጊዜው ያሳድግ ነበር፡፡ በ9:7 ላይ ልዩ ርዕስን ተመልከት፡፡

ኢየሱስ እምነታቸውን የሚያሳድገው

1. በቃሉ አማካኝነት
2. በድርጊቱ አማኝነት
3. ሁን በሚያውቅ ማንነቱ

ከእግዚአብሔር ጋር በደርቅ ለመኖር ኢየሱስ ፎምና አዲስ "መንገድን አምጥቷል" ይህም የአይውድ ሰዎችን ወግና ልማድ የሚያቋርጥ ነበር

1. ትኩረቱ ሙሴ ሳይሆን እርሱ ነበር
2. ሥራ ሳይሆን ፀጋ

▣ "እኔ እንደሆንኩ" ይህ የሚያመለክተው "ያህዊህ" የሚለውን የእግዚአብሔርን መጠሪ ሲሆን የዚህ ምንጭ ደግሞ "መሆን" የሚል ሐሳብ የእብራይስጡ ግሥ ነው (ዘፀ:14 "እኔ ነኝ") ኢየሱስ አምላክነቱን በሚያሳስብ ሁኔታ የሚጠበቀው (ተስፋ የተገባው) መሲህ እርሱ እንደሆ በዚህ ሥፍራ ያመለክታል (4:26፤8-24፤28፤58 13:19 እና 18:5፣6፣8፣ማቴ 24:5 እና ማር 13:6 እንዲሁም ሉቃ 21:8ን አስተውል) ።

በ6:20 ላይ ለአምላክነት የተሰጡትን ስሞችን ልዩ ርዕስ በሚለው ይመልከቱ።

13:20 ዮሐንስ ብዙውን ጊዜ ቃሉን "እመኑ"*(Pisterio)* "እመኑት" (*pisterieis)* ወይም "ታምኑ ዘንድ" *(pisterieis)* በማለት ክርስትያኖችን ይገልጣል (በ2:23 የዮሐንስን "እምነት")የሚለውን ቃል አጠቃቀም በልዩ ርዕስ ላይ ይሙ) እንዲሁም ደግሞ "መቀበል" ወይም ማስተናገድ በሚል ትርጉም ሌሎች ቃላትን ይጠቀማል (1:12፣5:43-13:20)። ወንጌል አንድን ሰው እና ስለ እለ እርሱ ተነገረውን መጽሐፍቅዱሳዊ እምነት መቀበል የማስተናገድ ሲሆን በአንፃሩም ደግሞ ያንን ሰው ሕይወት መኖርም ጭምር ነው።

▣ "ማናቸውንም የምልከውን የሚቀበል እኔን ይቀበላል" ይህ የኢየሱስ ስልጣን በውክልና ለተሰጣቸው ደቀመዛሙርት የተነገረ ኃይለኛ ንግግር ነው። ይህም ሊሰራ የሚችለው በተለያዩ ደረጃዎች ነው።

1. የአስራ ሁለቱ ሐዋርያት የተልዕኮ ጉዞ (ሉቃ 10:16) እና ሰባዎቹ (ማቴ 10:40)
2. የቤተክርስቲያን ምሥክርነት (ዮሐ 17:20

ወንጌሉን በሚያውጀው ሰው ማንነት ሳይገደብ ስለኢየሱስ የሚነገረው መልዕክት ሕይወትን የመለወጥ ኃይል አለው። ሥልጣኑ ያለው በምድራዊ መልዕክት ውስጥ ሳይሆን በወንጌሉ መልዕክት ውስጥ ነው (የክርስቶስ ወንጌል)።

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 13÷21-30

[21]ኢየሱስ ይህን ብሎ በመንፈሱ ታወከ፣ መስክሮም፡ እውነት እውነት እላችኋለሁ ከእናንተ አንዱ አሳልፎ ይሰጠኛል አለ። [22]ደቀመዛሙርቱ ስለማን እንደተናገረ አመንትተው እርስ በርሳቸው ተያዩ። [23]ኢየሱስም ይወደው የነበረ ከደቀመዛሙርቱ አንዱ በኢየሱስ ደረት ላይ ተጠጋ፤ [24]ስለዚህ ስምኦን ጴጥሮስ እርሱን ጠቅሶ ስለማን እንደተናገረ ንገረን አለው። [25]እርሱም በኢየሱስ ደረት እንዲህ ተጠግቶ፡- ጌታ ሆይ ማን ነው? አለው። [26]ኢየሱስም፡- እኔ ቁራሽ አጥቅሼ የምሰጠው እርሱ ነው ብሎ መለሰለት። ቁራሽም አጥቅሶ ለአስቆሮቱ ለስምኦን ልጅ ለይሁዳ ሰጠው። [27]ቁራሽም ከተቀበለ በኋላ ያን ጊዜ ሰይጣን ገባበት። እንግዲህ ኢየሱስ፡- የምታደርገውን ቶሎ ብለህ አድርግ አለው። [28]ነገር ግን ከተቀመጡበት ስለምን ይህን እንዳለው ማንም አላወቀም፤ [29]ይሁዳ ከረጢቱን የያዘ ስለሆነ፤ ኢየሱስ ለበዓሉ የሚያስፈልገንን ግዛ ወይም ለድሆች ምጽዋት እንዲሰጥ ያለው ለአንዳንዱ መስሎአቸው ነበርና። [30]እርሱም ቁራሹን ከተቀበለ በኋላ ወዲያው ወጣ ሌሊትም ነበር።

13:21 "በመንፈሱ ታወከ" የይሁዳ ክህደት ኢየሱስን በእውነት ያበሰጨ ነበር (ቧ12-27) ላይ ተመሳሳይ ቃል ተጠቅሷል። ኢየሱስ ይሁዳን የመረጠበት ምክንያት ከነበረው መንፈሳዊ አቅም የተነሣ ቢሆንም ለፍሬ ያልበቃ ነበር (ቁ-18)።

▣ "እውነት እውነት" በ15:1 ላይ የተሰጠውን ማብ ይመ

13:22 ይህ አስደናቂ ጥቅስ ነው ለኢሱስ ቅርብ የነበሩት ደቀመዛሙራት አስቀድሞ የተወሰነ የእግዚአብሔር ዕቅድ ከኃዲዎች ያደርገናል ብለው ፈርተው ነበር (ማር 14:19) ይህ አስቀድሞ በመወሰን ላይ ያለው የተለመደ ችግር ነው። የእግዚአብሔር ድርጊቶች የሰውን ነፃ ፈቃድ አይጋፋም ነገር ግን የሚያስከትለውን ውጤት ሊያፍኑት ይችላሉ።

13:23 "ኢየሱስም ይወደው የነበረው" ይህ ዮሐንስ ራሱነ የሚያመለክት ይመስላል (13:23፣25፣19:26-27፣34-35፣20:2-5፣8፣21:7፣20-24)፤ ምዕ 19ቁ26 የሚያረጋግጠው ይህንኑ ነው የዮሐንስ ስም በዚህ ወንጌል ውስጥ በፍፁም አይታይም፤ ኢየሱስ ባለሟሎች (ቤተኞች) ነበሩት አዎን ከሌሎቹ ይልቅ የሚቀርቡት ነበሩ (ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ፣ እና ዮሐንስ) እዲሁም የቅርብ ቤተሰቦም ነበሩ (አልዓዛር ማርያምና ማርታ)።

13:25 ይህ ዓወድ (የሚያመለክተው በመጀመሪያው ክፍለዘመን በነበረው የፍልስጥኤም ምድር የተሰለመደውን የአመጋገብ ሥርዓትን ነው፡፡ ደቀመዛሙርትም የፈረሰ ኮቴ ባለው ጠረጴዛ ሥር ጋደም ብለው በግራ ክንዶቻቸው ተደግፈውና ግሮቻቸውን ወደ ኋላ አጣምረው በቀኝ እጆቻቸው ይበሉ ነበር፡፡ ዮሐንስ ከኢየሳስ በስተቀር ሲሆን ይሁ ደግሞ በስተግራው ነበር (ክብር ሥፍራ)፡፡ ለአቀማመጡ ሥርዓት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተሰጠ ምንም ምክንያት የለምሰ፤ ዮሐንስ ወደ ኋላ ስጠኝ ብሎ ኢየሱስን ይጠይቀው ነበር፡፡

13:26 **"እኔ ቁራሽ አጥቅሼ የምሰጠው"** ይህ የማክበር ምልክት ነበር (ሩት 2:14)፡፡ ይሁዳ ከኢሱስ በስተግራ በኩ ተደግፎ ነበር፤ ይህም የክብር ሥፍራ ነው፡፡ ኢየሱስ አሁንም ቢሆን ይሁዳን ለመመለስ ጥር ያደርግ ነበር፡፡

ኢየሱስ የሚያጠቅሰው ነገር ከመራራ ቅጠልና መረቃ ተዘጋጀ ነበር (ልዩሮስለን በ13:2 ላይ ይመልከቱ፡፡)፡፡ የማርቆስ ወንጌል ተነፃፃሪው (14:20) "ከእኔ ጋር" ብሎ ይገልፀዋል፡፡

▣ **"የአስቆሮቱ"** በ6:71 እና 18:2 ያሉትን ማብራሪዎች እና ልዩ ርዕስን ከዚህ በታች ይመልከቱ፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ አስቆርቱ**

ይሁዳ ለበረከተ ዓመታት ኢየሱስን ሰምቷል፤ ተመልክቷል እንዲሁም በቅርብ ርቀት ከኢየሱስ ጋር ህብረት ነበረው ነገር ግን በግልፅ ለመረዳት እንደሚችለው በእምነት የተመሰረቱ ሕብረት ከኢየሱስ ጋር አልነበረውም (ማቴ 7÷21-23)፡ ጴጥሮስም እንዲሁ ልክ እንደ ይሁዳ ተመሳሳይ ፈታ ነበረበት ነገር ግን ውጤቱ ፈፅሞ የተለየ ነበር፡፡ ይሁዳ በተነሳበት የክህደት ዓላማ ላይ ብዙ ክርክሮች ተካሄደዋል፤

1. በመጀመሪያ ከገንዘብ ጋር የተያያዘ ነበር(ዮሐ 12÷6)
2. በመጀመሪያ ፓላስቲካዊ ነበር (*William Klassen, Judas Betrages or Friend of Jesus?)*
3. መንፈሳዊ ይዘት ነበረው (ዮሐ 13:27)

የሰይጣን ተፅዕኖ በሚመለከት ወይም በአጋንት ሜዝን ሚመለከት በርካታ ጥሩ የሆኑ ምንጮች አሉ (በመንኳቸውም ቅደም ተከተል መሠረት)

1. *Meill F. Unger, Beblical Demonology, Demonons the world Tadey*
2. *Ctionton E. Anord Three crucla Questions About spertual warfore.*
3. *Kurt koch, Christian counseling and occwtism, Demonology past and present*
4. *C. Fred Dickasm. Demon Possessin and the Christian*
5. *John P. newport. Demons, Demon, Demons*
6. *John Wanwiek Moutogomery, Principalities and powers*

ሐሰተኛ ከሆኑ ባህላዊ እምነቶችን ተረቶች ተጠበቅ በማቴ 16÷23 ላይ ኢየሱስን ለመፈታተን ሰይጣን ጴጥሮስ በተመሳሳይ መንገድ ተጠቅምት ነበር፡፡ ይህም ኢየሱስ እንደይሞት ነበር፡፡ ሰይጣን ዛሬም ቢሆን ያው ነው፡፡ ሰይጣን ምንጊዜም የኢየሱስን የማዳን ሥራ በእኛ ውስጥ እንዳለ ለማቆም ይጥራል፡፡

1. የኢየሱስ ደመፈተን ሉቃ4
2. ጴጥሮስን ተጠቅሟል
3. ይሁዳንና የሐይማኖት ሽማግሌዎችን ተጠቅሟል

ኢየሱስ በዮሐ 6÷70 ላይ ይሁዳን ሰይጣን እያለ ይገልፀዋል፡፡ መፅሐፍ ቅዱስ ከክርስትያኖች በራሳቸው ምርጥ በቀላሉ ሊጠቁ ይችላሉ፡

የዚህ ቃል ሥረ-መሰረት በመጠኑ ግልፅ ባይሆንም በርካታ አማራጮች ግን አሉ፤

1. ቁርያት፣ የይሁዳ ከተማ (ኢያ 15÷25)
2. ጻርታን፣ በገሊላ የለች ከተማ (ኢያ 21÷23)
3. ካሮይድስ፡ በኢየሩሳሌም ወይም በአያሪኮ የሚገኝ የታምር ጫካ
4. ስኮርቲያ፣ ሽርጥ ወይም የቆዳ ቦርሣ(ዮሐ 13÷29)
5. አስካራ÷ታላቆ መሞት (እብራይስጥ) ማቴ 27÷5
6. የነፍሰ ገዳየ ቢላ (ግሪክ) ማለትም እንደ ስምኦን ቀናተኛ ነበር (ሉቃ 6-15)

13:27 **"ሰይጣን ገባበት"** ይህ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ "ሰይጣን" የሚለው ቃ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰ ነው፡፡ ይህም በእብራይስጥ "ባላንጣ" ማለት ነው (ሉቃ 22:3 እና ዮሐ 13:2)፡፡ ልዩ ርዕስን በ12:31 ላይ ይመልከቱ፡፡ ይሁዳ ሰይጣን ስለገባበት ኃላፊነት የለበትም ማለት ነው? በመንፈሳዊው ዓለም (እግዚአብሔር የስምኦንን ልብ ሲያውና) ባሉ ድርጊቶችና በሚታየው ዓለም ባለው የሰው ኃላፊነት መካከል ውጥረት አለ፡፡ ሰዎች እንደሚያስቡት በእርግጥ ነፃ አይደለም ሁላችንም በታሪክ፣ በልምድ እንዲሁም በዘራችን የተወሰንን ነን ከእነዚህ ነባራዊ ገደቦች በተጨማሪ መንፈሳዊ ዓለም አለ (እግዚአብሔር፤ መላዕት ሰይጣን እና አጋንንት)፤ ይህ ነው እንግዲህ ሚስጢር የሆነው ይሁን እንጂ ሰዎች ሮቦቶች አይደለም፤ ለድርሰቶቻችን ለምርጫዎቻችንና ለውጤቶቻቸውም ኃላፊነት አለብን ይሁዳም ይህን ፈፅሞታል ብቻውን አልነበረም የፈፀመው ነገር ግን ከምራል አንፃር ለፈፀማቸው ድርጊቶች ኃላፊነት አለበት የይሁዳ መክዳት አስቀድሞ የተነገረ

ነበር (ቁ-18)፤ ሰይጣንም ይህንንም ከበስተጀርባ ያቀነባብር ነበር (ልዩ ርዕስን የክፉት ስብዕና የሚለውን በ12:31 ላይ ይመልከቱ።)። በጣም የሚያሳስነው ነገር ይሁዳን በሙሉ "ያለማወቁ" ወይም ያለማመኑ ነው።

13:29 **"ይሁዳ ከረጢቱን የያዘ ስለሆነ"** ይሁዳ የደቀመዛሙርቱ ገንዘብ ኃላፊነት ነበረበት (12:30)። *ሙሉውን ማብራሪያ* በ18:1 ላይ ይመልከቱ።

13:30 **"ሌሊትም ነበር"** ይህ ጊዜን የሚያመለክት ወይስ መንፈሳዊ መመዘና ዮሐንስ ብዙ ጊዜ ዋ በበርካታ መንገዶ ስንረዳቸው የምንችላቸውን አሻሚ ሐረጎችን ይጠቀማል። (ኒቆዲምስ 3:2፣19:39)።

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 13÷31-35
**[31]ከወጣም በኂላ ኢየሱስ እንዲህ አለው አሁን የሰው ልጅ ከበረ [32]እግዚአብሔርም ስለ እርሱ ከበረ፡ እግዚአብሔር ስለ እርሱ የከበረ ከሆነ እግዚአብሔር ደግሞ እርሱን ራሱን ያከብረዋል ወዲያውም ያከብረዋል። [33]ልጆች ሆይ ገና ጥቂት ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ ትፈልጉኛላችሁ ለአይዳም እኔ ወደምሔድበት እናንተ ልትመጡ አይችላችሁም እዳልኳቸው አሁን ለእናንተ ደግሞ እላችኂለሁ። [34]እርስ በርሳቸው ትዋደዱ ዘንድ እንደ ወደድኂችሁ እናንተ ደግሞ እርስበርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትዕዛዝ እሰጣችኂለሁ። [35]እርስበርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ ደቀመዛሙርት እንደሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ።**

13:31-38 እነዚህ ጥቅሶች ቀደም ሲል በላይኛው ደርብ በተካሄደው የጌታራት ሥነሥርዓት ወቅት ተያያዥ ናት የነበራቸው በደቀመዛሙርቱ ከተጠየቁት ጥያቄዎች የሚመደቡ ሲሆን እነዚህም የታላቅ ዓውድ ንዑስ ክፍሎች ናቸው (13-3614-5:8:22:16:17-19) ኢየሱስ ስለመሔዱ የተናገረው በሐዋርያት ብዙ ጥያቄዎችን እንዲጠይቁ ማድረጉ ግልፅ ሲሆን እነህም ጥያቄዎ መጡትም ኢየሱስ ለማለት የፈለገውን ካለመረዳት የመናጨ ነበር።

1. ጴጥሮስ (13:36)
2. ቶማስ (14:5)
3. ፊልጳስ (14:8)
4. ይሁዳ (የአስቆሮቱ ሳይሆን (14:22)
5. ከደቀመዛሙርቱ አንዳንዶች (16:17-19)

13:31 **"የሰው ልጅ"** ይህ የተመረጠው የኢየሱስ አጠራር ነበር። የዚህ አጠራር የኂላ ታሪክ የሚገኘው በህዝ 2:1 እና በዳን 7:13 ሲሆን የሚያመለክተውም የሰውንና የመለኮት ባህሪያትን ነው። ኢየሱስም ይህን የተጠቀመው ቃሉ በረቢዎች የአይሁድ እምነት ስላልተጠቀሰ ነበር፤ በመሆኑም ቃሉ ብሔራዊም ሆነ ወታደራዊ አንደምታ የለውም ነገር ግን እርሱን ሁለት ባህርያትን ያጠመረ ነበር (1ዮሐ 4:1-3)።

13:32 ከዚህ ጥቅስ ላይ የግሪክ ምንጮች ልዩነቶች አሏቸው። ረጅሙ ጥቅስ የሚገኘው በ*NASB NKJV NRSV TEV NJB* ውስጥ ሲሆን የ $N^C$ $A$ $C^2$ $K$ እና የሶርያ ምንጮችም ይደግፉታል። ይህም ጥቅስ ("እግዚአብሔር ስለ እርሱ የከበረ ከሆነ") ከ *MSS P66* $N^*$, *B-* $C^*$ *D: L: W እና X* ምንጮች ውስጥ ወጥቷል እነዚህ ምናልባት የተሻሉ ምንጮች ናቸው። ግን ፀሐፊዎ ምናልባት በንፅፅሩ ግራ ስለተጋቡ የመጀመሪያውን ሐረግ አስወግደውት ሊሆንም ይችላል።

▣ **"የከበረ ከሆነ"** ቃሉ በቁ 31 እና 32 ላይ አራት ወይም አምስት ጊዜ ተጠቅሷል ሁለት ወይም ሦስት ጊዜያት በግሪኩ የድርጊት አመልካች ጊዜ እንዲሁም የወደፊት ጊዜን ለማመልከት ሁለት ጊዜ ተጠቅሷል። ይህም በኢየሱስ ሞትና ትንሳኤ የተፈፀመውን የእግዚአብሔርን የማዳን ዕቅድ የሚያመለክት ነው (7:39:12:16፣23 17:1:5)። በዚህ ሥፍራ ላይ በኢየሱስ ህይወት ውስጥ ሊከናወኑ ያሉትን ድርጊቶች ያመለክታል እነዚህ ድርጊቶች ለመከሰታቸው አስተማማኝነት ስለነበራቸው የተገለፁ እንደ ኃላፊ ድርጊቶች ነው (የግሪኩ አድራጊ ግሥ)። በ1፡14 ላይ ያለውን ማብ ይመ።

13:33 **"ልጆች ሆይ"** ዮሐንስ ከኤፌሶን አካባቢ ወይም ከነበረበት ከተማ ሆነ የሚፅፈው እንደሽማግሌ ሆኖ ነበር። ይህንኑ ተመሳሳይ ማዕረግ በ1 ዮሐ 2-1-12፣ 28:3:7:18:4:5:21 ለነበሩ የመልዕክቱ ተቀባዮች ይጠቀመዋል። እዚህ ላይም የኢየሱስ ዘይቤያዊ አነጋገር ራሱን ከአብ ጋር ያስተያየት ሌላው መንገድ ነበር። እርሱ አባት፣ ወንድም፣ አዳኝ ፣ጓደኛ ጌታም ጭምር ነው። በሌላ መንገድ ስንገልፀው ደግሞ እርሱ ታላቅ አምላክ እና የቅርብ ጓደኛም ነው።

▣ **"ገና ጥቂት ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ"... ለአይሁድም እንዳልካቸው"** ኢየሱስ ይህን ከበርካታ ሠራት በፊት ለአይሁድ መሪዎች ተነግሮ ነበር (7:33)፤ አሁን ደግሞ ለደቀመዛሙርቱ ይነግራቸዋል (12:35፤14:9፤16:16-19)። ስለዚህም የጊዜው ጉዳይ በመጠኑ አሻሚ መሆኑ ግልፅ ነው።

▣ **"እኔ ወደምሄድበት እናንተ ስትመጡ አይችላችሁም"** የአይሁዳ መሪዎች ሊመጡ አልቻሉም(7:34:36:8:21)፡፡ ደቀመዛሙርትም እስኪሞቱ ድረስ ከእርሱም ጋር ሊሆኑ አይችሉም፤ ሞት ወይም ንጥቀት ተከታዮቹን ከእርሱ ጋር አንድ ያደርጋቸዋል (2ቆሮ 5:8/ተሰ 4,13-18)፡፡

**13:34 "እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ… አዲስ ትዕዛዝ እሰጣችኋለሁ"** "እርስበርስ መዋደድ" አዲስ ትዕዛዝ አይደለም (ሊቀ 19:18፣በ12:50 ላይ "ትዕዛዝ" የሚለውን ልዩ ርዕስ ደመ.)አዲስ የተባለው ነገር አማኞች ኢየሱስ ራሱ እንደወደዳቸው እርስ በርሳቸውም እነዲዋደዱ ነው (15:12-17:1ዮሐ 2:7-8፣3፣16፣23፣4:7-8:10-12:19-20: 2 ዮሐ5)፡፡

ወንጌል ሊቀበሉት የሚገባ ሰው ሊታመን የሚገባ እውነት እና ሊኖሩት የሚገባ ህይወት ነው፡፡(14:15:21:23 15:10:12 1ዮሐ 5:3፤ 2 ዮሐ 5:6 ሉቃ 6:46)፡፡ ወንጌል የሚቀበሉት፤ የሚያምኑትና የሚኖሩት ነው ወይ በፍቃድ የሚኖሩት አለያም ማይኖሩት

*FouNdatioNs for Biblical INterpretatioN* የሚለው የሥነ አፈታት መጽሐፍ ላይ *Biblical Theology of the New TestameNt* በሚለው አንቀጽ ከነስ ኮርሲይ የተነገረውን ንግግደር እወደዋለሁ፤ "የክርስቶስ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ሥራ የፍቅር ሥነ ምግባር ያላቸው ሊሆን ይገባል"(ገላ 5:6:25:6:2 ያኔ 3:17-18 ዮሐ 13-34 1ዮሐ 4:7) (ገጽ 562)

**13:35 "ደቀመዛሙርቱ እንደሆነችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ"** ፍቅር ሊያስመልሰው የሚችለው አንዱ ባህሪ ነው፡፡ አማኞች ሊታወቁ የሚገባቸው በፍቅራቸው ነው (1ዮሐ 3:14፡4:7-21)፡፡

▣ "ቢ…" ይህ ድርጊት ለመፈፀም አቅም መኖሩን የሚያመለክት ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተነገር ነው፡፡ ለሌሎች ክርስትያኖች የምናሳያቸው ድርጊቶች ከኢየሱ ጋር ያለንን ግኑኝነት የሚሳዩ ናቸው (1ዮሐ 2:9-11:4-20-21)፡፡

**NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 13:36-38**
**[36]ስምኦን ጴጥሮስም ጌታ ሆይ ወዴት ትሔዳለህ? አለው፡፡ ኢየሱስም ወደምሔድበት አሁን ልትከተለኝ አትችልም ነገር ግን በኋላ ትከተለኛለህ ብሎ መለሰለት፡፡ [37]ጴጥሮስም፡- ጌታ ሆይ አሁን ልከተልህ አለመቻሌ ስለምንድነው? ነፍሴነ ስንኳ ስለ አንተ እሰጣለሁ አለው፡፡ [38]ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰለት፡- ነፍስህን ስለ እኔ ትሰጣለህን? እውነት እውነት እልሃለሁ፡ ሦስት ጊዜ እስክትክደኝ ድረስ ዶሮ አይጮህም፡፡**

**13:36 "ስምኦን ጴጥሮስም… አለው"** ይህ ኢየሱስ በቁ31 -35 ላይ ለተነገራቸው ንግግሮች ከተነሱት ተያያዥ ጥያቄዎች የመጀመሪያው ነው (13:36:14:5:8:22-16:17-19)፡፡ እነዚህን ጥያቄዎች ደቀመዛሙርቱ በመጠየቃቸውና ዮሐንስ አስታውስአቸው በመዘገቡ በጣም ደስተኛ ነኝ!

**13:37"ነፍሴነ እንኳ ስለአንተ እሰጣለሁ"** ጴጥሮስ ይህ ነበር! ነገር ግን ይህ የወደቀው የሰው ልጅ ምን ያህል ደካማ መሆኑን የሚያሳይ እና ጌታችንም ምን ያህል የተሰጠ እንደነበር የሚያመለክት ነው፡፡

**13:38 "እውነት እውነት"** በ1:51 ላይ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ፡፡

▣ **"ሦስት ጊዜ እስክትክደኝ ድረስ ዶሮ አይጮህም"** ይህ የሮሜ ዶሮ መሆን አለበት፡፡ አይሁዶች በከተማው ውስጥ እንስሳት እንዲኖሩ አይፈቅዱም ነበር ምክንያቱም ቅዱስ አገር ስለነበረች ስለዚህም ነው ብዙዎች ሐብታሞች የአትክልት ሥፍራዎ (ማዳበሪ የሚያስፈልጋቸው) ከከተማው ውጪ ባሉ የደብረዘይት ተራራ ላይ የነበራቸው የጌታ ሴማኒ የአትክልት ሥፍራም ከእነዚህ አንዱ ነበር፡፡

ኢየሱስ ሁሉን ለማፅናናት/ለማበረታት ወደፊት ሲሆን የሚችለውን ነገር ነበር የሚነገረው፡፡ እንደዚህ አይነቱ አሉታዊ ነገር የሚገልጠው ነገር የእርሱን ዕውቀትና ሲመጣ ባለው ነገር ላይ ሁሉ የበላይ መሆኑን ነው (18:17-18:25-27ማቴ 26:31-35 ማር 14:27-31 -ሉቃ 22:31-34)፡፡

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ሊሆን የሚችል ማብራሪያ በመሆኑ ለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ፡፡ እያንዳንዳችን ልንሔድ የሚገባን ባለን መረዳት መጠን ነው፡፡ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጎም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣችሁ ናችሁ፤ በመሆኑም ይህንን በሚያብራራው ሰው ላይ ብቻ ልትተወው የሚገባ አይደለም፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት በዚህ መጽሐፍ ክፍል ባሉት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ በጥሞና እንድትታሰብበት ለመረዳት ይችል ዘንድ ነው፡፡ በመሆኑም ጥያቄዎቹ የቀረቡት እንደ ሐሳብ አነሳሽ እንጂ በግልፅ ወይም በቀጥ አይደለም፡፡

1. ዮሐንስ ትክክለኛውን የጌታሪት ሥነ ሥርዓቱን ለምን አይመዘግብም?
2. ኢየሱስ የደቀመዛሙርትን እግር ለምን አጠበ? እኛስ መተጣጠብ አለብን ማለት ነው?
3. ኢየሱስ ይሁዳን ደቀመዝሙሩ እንዲሆን ለምን መረጠ?
4. አንድ ሰው በእርግጥ ክርስትያን መሆኑን እንዴት ሊያውቅ ይችላል?

# ዮሐንስ 14

## በተሻሻሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀፅ አከፋፈል

| UBS[4] | NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| ኢየሱስ ወደ አብ የሚወስደው መንገድ | *መንገድ እውነት እና ሕይወት* | ከከበረው ኢየሱስ ጋር አማኞች ያላቸው ግንኙነት | ኢየሱስ ወደ አብ የሚወስደው መንገድ | የስንብት ንግግሮች (13፡31-14፡31) |
| 24፡1-14 | 24፡1-6 | 14፡1-7 | 24፡1-4 | 24፡1-4 |
| | | | 14፡5 | 14፡5-7 |
| | አብ ተገለጠ | | 14፡6-7 | |
| | | 14፡8-14 | 14፡8 | 14፡8-21 |
| | 14፡12-14 | | | |
| የመንፈስ ተስፋ | ኢየሱስ ስለሌላ ረዳት ተስፋ ሰጠ | | የመንፈስ ቅዱስ ተስፋ | |
| 14፡15-24 | 14፡15-18 | 14፡15-17 | 14፡15-17 | |
| | የአብና የወልድ በውስጣችን መኖር | 14፡18-24 | 14፡18-20 | |
| | 14፡19-24 | | | |
| | | | 14፡21 | |
| | | | 14፡22 | 14፡22-31 |
| | የእርሱ የሰላም ስጦታ | | 14-23-24 | |
| 14፡25-31 | 14፡25-31 | 14፡25-31 | 14፡25-26 | |
| | | | 14፡27-31*ሀ* | |
| | | | 14፡31*ለ* | |

**ሦስተኛው የምንባብ ዑደት (አንቀጽ 5ን ይመልከቱ፡፡)**
*የመጀመሪያውን ፀሐፊ ዋና ሐሳብ በአንቀፅ ደረጃ መከተል*

*ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ሊሆን የሚችል ማብራሪያ በመሆኑ ለትከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጐም ኃላፊነት አለባችሁ፡፡ እያንዳንዳችን ስንሔድ የሚገባን ባለን መረዳት መጠን ነው፡፡ እናንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጐም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣችሁ ናችሁ፤ በመሆኑም በሚያብራራው ሰው ላይ ብቻ ስትተውት የሚገባ አይደለም፡፡*

*ምዕራፉን በአንድ ቅፅበት አንብቡት፤ ዋና ሐሳቦችንም ለዩ፡፡ የእናንተን የዋና ሐሳብ አከፋፈል ከአምስቱ የተሻሻሉ ትርጉሞች ጋር አስተያየዩ፡፡ ምንም እንኳን በአንቀፅ መከፋፈል በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት የሚደረግ*

ባይሆንም የአተረጓጐም እምብርት የሆነውን የመጀመሪያውን ፀሐፊ ዋና ሐሳብ ለማወቅ ግን ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ እያንዳንዱ አንቀፅ የሚኖረው ዋና ሐሳብ አንድ ብቻ ነው፡፡

1. የመጀመሪያ አንቀፅ
2. ሁለተኛ አንቀፅ
3. ሦስተኛ አንቀፅ
4. ወ.ዘ.ተ

## የዮሐንስ 14:1-31 መነሻ

ሀ. ከዮሐንስ 13 እስከ 17 ድረስ ያለው ምንባብ በምዕራፍ የከፋፈል የለበትም፤ ምክንያቱም ይህ በጌታ ራት ምሽት ወቅት በላይኛው ድርብ የተካሄደ ንግግር በመሆኑ እንደ አንድ ፅሑፍ የሚታይ በመሆኑ ነው፡፡ ኢየሱስ ሰለ መሔዱ ያደረገው ንግግር ደቀመዛሙርት ብዙ ጥያቄዎችን እንዲኖራቸው ያደረገ መሆኑ ግልፅ ነው፤ ይህም አውድ የተዋቀረው ሐዋረያት የኢየሱስን ቃላት ካለመረዳት የተነሳ ካነሷቸው ተከታታይ ጥያቄዎች ነው፡፡
   1. ጴጥሮስ (13:36)
   2. ቶማስ (14:5)
   3. ፊልጶስ (14:8)
   4. ይሁዳ (የአስቆሮቱ ሳይሆን) (14:22)
   5. አንዳንድ የእርሱ ደቀመዛሙርት (16:17-19)

   ዮሐንስ እውነትን ለማስተላለፍ የሚጠቀመው መንገድ ውይይት መሆኑን አስታውስ

ለ. እነዚህ ጥያቄዎች አሁንም ቢሆን አማኞችን የሚረዱ ናቸው፡፡
   1. ከኢየሱስ ጋር በአካል የነበሩት ሐዋርያ እንኳ ኢየሱስን አለመረዳታቸውን ያሣያሉ፡፡
   2. ከተሳሳተ ግንዛቤ የመነመኑትን እነዚህን ቅንነት የተሞሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ ኢየሱስ በጣም ውድና ጥልቅ የሆኑ ቃላትን ተጠቅሟል፡

ሐ. ምዕራፍ 14 የሚጀምረው ኢየሱስ ስለሚመጣው "ረዳት" ባደረገው ንግግር ነው
   1. ኢየሱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ የሰጠው መግለጫ እርሱ ከዚህ ዓለም ወደ አብ ስለሚሄድ ደቀመዛሙርት ከተሰማቸው ፍርሃትና ጭንቀት በተገናኘ ነው (13:33፣36)፡፡
      ሚካኤል ማጊስ፣ *New TestameNt TraNsliNe* (ገጽ 355) በሚለው መጽሐፋቸው ላይ ስለ እነዚህ ፍርሐቶች ኢየሱስ የሰጠውን ዓውዳዊ ምላሾች ጥልቀት በተሞለበት ማስተዋል ይገልፁታል፣
      ሀ. "እኔ አሁን ወደምሔድበት አንድ ቀን እናንተም ከእኔ ጋር ትሆናላችሁ" ቁ. 1-11
      ለ. "እኔ ብሔድ ይሻላችኋል" ቁ. 12-17
      ሐ. "ወደ እናንተም እመጣለሁ፣ ራሴንም እገልጥላችኋለሁ" ቁ. 18-
      መ. "ሰላሜን እሰጣችኋለሁ" ቁ. 27-31
   2. ይህ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ገደብ ያለው ነው፡፡ በዚህ ዓውድ ውስጥ ያልተገለፁ ብዙ እና ወሳኝ የሆኑ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት አሉ፡፡
   3. የመንፈስ ሥራ
      ሀ. እውነትን መግለጥ
      ለ. አማኞችን ማፅናናት ነው፡፡

## የቃልና የሐረግ ጥናት

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 14፡1-7

[1]ልባችሁ አይታወክ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፡ በእኔም ደግሞ እመኑ፡፡ [2]በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፡ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፡ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና፡ [3]ሄጄም ስፍራ ባዘጋጅላችሁ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እድትሆኑ፣ ሁለተኛ እመጣለሁ፣ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ፡፡ [4]ወደምሔድበትም ታውቃላችሁ፡ መንገዱንም ታውቃላችሁ፡፡ [5]ቶማስም፡- ጌታ ሆይ ወደ ምትሔድበት አናውቅም፡ እንዴትስ መንገዱን እናውቃለን? አለው፡፡ [6]ኢየሱስም፡ እኔ መንገድና እውነት፡ ሕይወትም ነኝ፡ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም፡፡ [7]እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር፡፡ ከአሁን ምጀምራችሁ ታውቁታላችሁ አይታችሁትማል አለው፡፡

14:1 **"አይታወክ"** ይህ የአሁን ጊዜ ተደርጎ ግሥ ትዕዛዛዊ ቃል ነው፡፡ ይህም ተቃራኒ ቦዝ አንቀፅ አብሮት ያለ ሲሆን ብዙውን ጊዜ ያለው ትርጉም በሂደት ላይ ያለን ድርጊት ማቆም ነው፡፡ የልባችሁን መታወቅ አቁሙት ማለት ነው፡፡ የኢየሱስ ስለ መሔድ የተናገረው ነገር ትልቅ ጭንቀትን ፈጥሮባቸው ነበር፡፡

▣ **"ልባችሁ"** የብዙ ቁጥሩን ያስተውሉ፡፡ ኢየሱስ ይናገር የበረው ለአሥራ አንዱ ሁሉ ነበር፡፡ "ልብ" የሚለው የእብራይስጥ አጠቃቀም የሚያመለክተው የሰውን ሁለንተና ነው፡፡ አዕምሮ፣ ፈቃድና እና ስሜትን (ዘዳ 6:5፤ ማቴ 22:37)፡፡ በ12:40 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስን ይመልከቱ፡፡

▣ **"በእግዚአብሔር እመኑ፤ በእኔም ደግሞ እመኑም"** እዚህን ሁለ የአሁን ጊዜ ትእዛዛዊ ድርጊት ገላጭ አመልካቾች ወይም የሁለቱም ጥምር ናቸው (NKJV፤ NJB እና NET *መጽሐፍ ቅዱሶች የመጀመሪያውን አመልካተ ሲሉ ሁለተኛውን ደግሞ ትእዛዝ ይሉታል)፡፡ እምነት የተለመደና ቀጣይነት ያለው ነው፡፡ ሰዋሰዋዊ ሚዛኑን የጠበቀው የዚህ ጥቅስ አወቃቀር የሚያመለክተው ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል መሆኑን ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር ሰሚዎቹ የአንድ አምላክ አምልኰን የሚከተሉ አይሁዶች መሆናቸውን (ዘዳ 6:4-6) እና የኢየሱስን የእድአዙር ንግግር (ዙሪያ ጥምጥም) መረዳታቸውን አስተውል (በ14:26 ላይ ሥላሴ የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡)፡፡ በአንድ ስዕለ ኃያል ማመን አንድ ነገር ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ ክርስቲያን መሆን ሌላ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ሐረግ የሚያተኩረው በአስተምህሮ ድንጋጌ ላይ ሳይሆን በኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ላይ ነው፡፡*

24:2 **"በአባቴ ቤት"** "ቤት" የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን የተጠቀሰው የማደሪያውን ድንኳን ወይም ቤተ መቅደሱን ለማመልከት ነበር (2 ሳሙኤል 7)፤ ይሁን እንጂ በዚህ ዓውድ የሚያመለክተው በመንግሥተ ሰማይ ለእግዚአብሔር ቤተሰብ ያለውን ድርሻ ወይም በመቅደሱ ከእርሱ ጋር አብሮ መኖርን ነው (መዝ 23:6፤ 27:4-6)፡፡

▣

| | |
|---|---|
| NASB NRSV | ***"መኖሪያዎች"*** |
| NKJV | **"ትላልቅ ቤቶች"** |
| TEV | **"ክፍሎች"** |
| NJB | **"ብዙ ሥፍራዎች"** |

"ትላልቅ ቤቶች" የሚለው የKJV ትርጉም የሚያሳስት ነው፡፡ የግሪኩ ቃል ትርጉም "ዘላለማዊ መኖሪያዎች" ማለት ነው (14:23)፤ ይህም ቅንጦንትን ሳያመለክት ማለት ነው፡፡ ዋናው ተምሳሌትነት በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ በየዕለቱ አብረው እንደሚመገቡበት ቤት ሁሉ አማኞችም በእግዚአብሔር ማደሪያ የራሳቸው ክፍሎች አሏቸው (TEV NJB)፡፡

ከዚህም ባሻገር በጣም ደስ የሚያሰኘው ነገር በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ቁልፍ ሃሳብ ከሆነው "መኖር" (ዮሐ 15) ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ሥርው ቃል መሆኑ ነው የእኛ መኖሪያ በአብ ዘንድ ፍፁም (የተሟላ) የሚሆነው እኛ በልጁ በኖርን መጠን ነው፡፡

▣ **"እንዲህስ ባይሆን"** ይህ ከፊል ሁለተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተነገር ሲሆን ይህም "ከእውነተኛው ተቃራኒ" ይባላል፡፡

| | |
|---|---|
| NASB, REB, NIV | **"እንዲህስ ባይሆን ባልኳችሁ ነበር"** |
| NKJV | **"እንዲህስ ባይሆን ባልኳችሁ ነበር"** |
| TEV | **"እንዲህስ ባይሆን አልነግራችሁም ነበር"** |
| NJB, NET | **"አለበለዚያ እነግራችሁ ነበር"** |
| YouNg's literal traNslatioN | **"እንዲህ ባይሆን እነግራችሁ ነበር"** |
| New Berklay VersioN | **"ይህ እንዲህ ባይሆን ኖሮ በነገርኳችሁ ነበር"** |
| Williams TraNslatioN | **"ባይኖሩ ኖሮ በነገርኳችሁ ነበር"** |

▣ **"ስፍራ አዘጋጅላቸው ዘንድ እሄዳለሁና"** ይህ መንግሥተ ሰማይ በሚታይ መልኩ ከጀመሪያው አልተሰራችም ማለት ሳይሆን የኢየሱስ ሕይወት፣ ትምህርቶች እንዲሁም ሞቱ ኃጢአተኛ የሆነው የሰው ልጅ ቅድስናን ከተሞላው አግዚአብሔር ጋር አብሮ መኖር እንዲችሉ የሚያደርግ እንደሆነ ለማሳየት ነው፡፡ ኢየሱስ ከሚያምኑት ቀድሞ መሪና ፋና ወጊ ሆኖ ሲሔድ የሚያመለክት ነው (ዕብ 6:20)፡፡

14:3 **"ባዘጋጀላችሁ"** ይህ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ሲሆን ድርጊት ለመፈፀመ እድል መኖሩን ያሣያል፡፡ ኢየሱስም በቅርብ ወደ አባቱ እንደሚሄድና (7:33፤ 16:5፤ 10፣ 10፤ 17፤28) ሥፍራም እንደሚያዘጋጅላቸው ነገራቸው ነበር፡፡

በ*UNited Bible Societies* የተዘጋጀውና በኒውማንና ወይደር የተደረሰው Help for TraNslators የሚለው መጽሐፍ ገጽ 456 ላይ ይህ ሐረግ "እኔ ከሔድኩ በኋላ"፣ "እኔ ስሔድ" ወይም "እኔ ስለምሔድ" በሚል ሐሳብ ለጊዜው ልንረዳው ይገባል ይላል፡፡

▣ "ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ" ይህ ደግሞ መመለሱን ወይም መሞትን የሚያመለክት ነው (2 ቆሮ 5:8፤ 1ተሰ 4:13-18)፡1 ይህ ከኢየሱስ ጋር ፊት ለፊት የሚደረግ ግንኙነት የሚያንፀባርቀው የኢየሱስንና የአብን ግንኙነት ነው (1:1:2)፡፡ ክርስቲያኖችም ኢየሱስና አብ ባላቸው የቅርብ ግንኙነት ተካፋዮች ይሆናሉ (14:23፤ 17:1)፡፡

"እወስዳችኋለሁ" የሚለው ግሥ (ፓራላምባኖ) በተዘዋዋሪ ያለው ትርጉም አንድን ሰው "እንኳን ደህና መጣህ" ማለት ነው፡፡ መንግሥተ ሰማይ ከእግዚአብሔር ጋር የግል ሕብረት ማድረግ ነው፤ ይህ ከ1:12 (ላምባ) የተለየ ነው፡፡ የእነዚህን ሁለት ቃላት የሥነ-አገባብ መደራረብን ለመለየት በጣም አስቸጋሪ ነው፤ ብዙጊዜ ቃላቶቹ ተመሣሣይ ናቸው፡፡

▣ "እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ" መንግሥተ ሰማይ ኢየሱስ ያለት ነው (17:24) መንግሥተ ሰማይ ከስላሴ ጋር ፊት ለፊት ሕብረት የምናደርግበት ነው አዲስ ኪዳን ሙሉ የሆነው ሕብረት የሚከሰተው መቸ እንደሆነበትክክል አይነግረንም፡፡

1. ስንሞት 2 ቆሮ ወይም 5:8
2. ዳግም ሲመጣ 1ተሰ 4:13-18

መጽሐፍ ቅዱስ ከሞት በኋላ ስላለው ሕይወት በሚገርም ሁኔታ ዝም ይላል፡፡ ጥሩና አጭር ማብራሪያ ሊሰጥ የሚችል መጽሐፍ በዊልያም ሄንድሪክስን የተደረሰው *The Bible oN the life Hereafter* የሚለው መጽሐፍ ነው፡፡

**ልዩ ርዕስ ሙታን የት ይኖራሉ**

I. ብሉይ ኪዳን
- ሀ. ሁሉም ሰዎች ወደ ሲኦል ይሔዳሉ (ሥርወ ቃሉ አይታወቅም ጥሣጥ 10 66) ይህም በጥበብ ፅሑፎች እና በትንቢተ ኢሳያስ ብዙውን ጊዜ ሞትን ወይም መቃብርን ለማመልከት የሚጠቀስበት መንገድ ነበር። በብሉይ ኪዳን ጨለማ፣ መረዳት ያለበት ነገር ግን ደስታ የራቀውን ኑሮን ለማመልከት ተጠቅሷል (ኢዮ 10:21-22፤ 38፤17፤ መዝ 107:10፤14)።
- ለ. ሲኦል የሚታወቀው
  1. ከእግዚአብሔር ፍርድ ጋር በተገናኘ (እሳት)፤ ዘዳ 32:22
  2. ከፍርድ ቀን በፊት ያለን ቅጣት ለማሣየት (መዝ 18:4-5)
  3. ከአብይን (ጥፋት) ጋር በተገናኘ፤ ይህም እግዚአብሔር ራሱ የሚደሰትበት ነው ኢዮብ 26:6፤ መዝ 139:8 አምኖ ፣ 9፡2
  4. ጉድጓድ (መቃብር) ከሚለው ቃል ጋር መዝ 16:10፤ ኢሳ 14:15 ሕዝ 31:15-17
  5. ክፉዎች በሕይወት ሳሉ ወደ ሲኦል ይወርዳሉ፤ ሕዝ 16:30 መዝ 55:15
  6. ሰፊ አፍ ባለው እንስሳ ተመስሏል፤ ሕዝ 16:30፤ ኢሳ 5:14፤ 14:19፣ እንባ 2:5
  7. በዚያ የሚኖሩ ሰዎች ሌፋይም ይባላሉ፤ ኢሳ 14:9-11

II. አዲስ ኪዳን
- ሀ. ሲኦል የሚለው የእብራይስጡ ቃል ጥልቅ በሚለው የግሪኩ ቃል ተተርጉሟል (የማይታየው ዓለም)
- ለ. ጥልቅ የሚታወቅበት
  1. ሞትን ያመለክታል፤ ማቴ 16:18
  2. ከሞት ጋር የተያያዘ ነው፤ ራዕ 1:18፤ 6-8
  3. ብዙ ጊዜ ዘላለማዊ ቅጣት ከሚሰጥበት (ገሃነም) ጋር ተመሳሳይነት አለው፤ ማቴ 11:23 (የብሉይ ኪዳን ጥቅስ)፤ ሉቃ 10:15፤ 16:23-24
  4. መቃብር ከሚለው ጋር ብዙውን ጊዜ ተመሳሳበይነት አለው፤ ሉቃ 16:23
- ሐ. ምናልባት ሊከፈል ይችላል (ረቢዎች)
  1. ጽድቅ የሆነው ክፍል ገነት ይባላል (ይህ በእውነት ለመንግሥተ ሰማይ የተሰጠ ስም ነው፤ 2ቆሮ 12:4፤ ራዕ 2:7)፤ ሉቃ 23:43
  2. ክፉ የሆነው ክፍል ድቅድቅ ጨለማ ይባላል፤ 2ጴጥ 2:4 ክፉ መላዕክት ታስረው የሚቆዩበት ሥፍራ (ዘፍ 6፣ 1ሄኖክ)፡፡
- መ. ገሃነም
  1. ይህ ‹‹የሔኖም ልጆች ሸለቆ›› የሚለውን ሐረግ የሚያንፀባርቅ ነው (የደቡብ ኢየሩሳሌም)፡፡ ይህ ልጅን መሥዋዕት በማድረግ ምሌክ የተባለው የሲሮፍ ኒቃውያን የእሳት አምላክ (BDB574)የሚመለከበት ሥፍራ ነው (2 ነገ 16:3፤ 21:6፤ 2 ዜና 28:3፤ 33:6)፤ ይህ. በዘሌ 18:21፤ 20:2-5 መሠረት በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡

2. ኤርምያስ ከአህዛብ የአምልኮ ሥፍራነት እግዚአብሔር ፍርድ ወደሚሠጥበት ሥፍራ ቀይሮታል (ኤር 7:32፤ 19:6-7)፡፡ ከዚያም በ1 ሔኖክ 90:26-27 ሲራክ 1:163 ላይ ደግሞ የእሳት ሥፍራ፣ ዘላለማዊ ፍርድ የሚሠጥበት ተደርጎ ተገልጿል፡፡
3. ኢየሱስ በነበረበት ዘመን የነበሩ አይሁዶች ይህን ልጅን በእሳት በማሳለፍ እና መሥዋዕት በማድረግ አባቶቻቸው ያመለኩበትን ሁኔታ በጣም ከመቃወማቸው የተነሣ ይህንን ሥፍራ በኢየሩሳሌም የቆሻሻ መጣያ ሥፍራ አድርገውታል፡፡ ዘላለማዊ ፍርድን በሚመለከት ኢየሱስ የሰጣቸው ምሳሌዎች ከዚህ ሥፍራ የመጡ ናቸው፡፡ (የእሳት፣ ጭስ፣ ትሎች፣ ክርፋት፣ ማር 9:44፤46)፡፡ ገሃነም የሚለው ቃል የተጠቀሰው በኢየሱስ ብቻ ነው (ከያዕ 3:6 በስተቀር)፡፡
4. ገሃነም የሚለውን ቃል ኢየሱስ እንዴት ተጠቀመው
   ሀ. እሳት፣ ማቴ 5:22፣ 18:9፤ ማር 9:43
   ለ. ዘላማዊ፤ ማር 9:48 (ማቴ 25:46)
   ሐ. የጥፋት ሥፍራ (ነፍስንና ስጋን)፤ ማቴ 10:28
   መ. ከሲኦል ጋር የሚነፃፀር ነው፤ ማቴ 5:29-30፤ 18:19
   ሠ. ክፊዎችን በ‹‹ገሃነም ልጆች›› ይመስላችኋል ማቴ 23:15
   ረ. የፍትሐዊ ፍርድ ውጤት ነው፤ ማቴ 23:33፤ ሉቃ 2:5
   ሰ. ገሃነም የሚለው ሐሳብ ከሁለተኛ ሞት (ራዕ 2:11፤ 20:6፤14) ወይም የእሳት ባህር (ማቴ 13:42፤50፤ ራዕ 19:20፤ 20:10፤ 14-15-21:8) ከሚለው ጋር የሚነፃፀር ነው፡፡ የእሳት ባህር የሰዎች (ከኦል) እና የክፉ መላዕክት (ከጽድቅ ጨለማ፣ 2 ጴጥ 2:4፤ ይሁዳ ቁ.6 ወይም ገደል ሉቃ 8:31፤ ራዕ 9:1-11፤ 20:1፡3) ዘላለማዊ መኖሪያ ነው ማለት ይቻላል፡፡
   ሸ. ከመጀመሪያው የተዘጋጁት ለሰይጣንና ለመላእክት እንጂ ለሰዎች አልነበረም ማቴ 25:41

ሠ. ሲኦል ጥልቅና ገሐነም የመደራረብ ባህሪይ ስላላቸው ማለት የምንችለው
1. ከመጀመሪያው ሁሉም ሰወች ወደ ሲኦል.ጥልቅ ሄደዋል
2. እዚያ የሚኖራቸው ስሜት (ጥሩ.መጥፎ) የሚብሰው ከፍርድ ቀን በኋላ ሲሆን የክፉዎች መኖሪያ ግን ተመሳሳይ ነው (ለዚህም ነው የKJV መጽሐፍ ቅዱስ ጥልቅ.መቃብር የሚለውን ገሃነም (ሲኦል) ብሎ የሚተረጉመው፡፡
3. ስቃይ የሚለውን ከፍርድ በፊት የሚገሰጠው ብቸኛው የአዲስ ኪዳን ምሣሌ በሉቃ 16:19-31 ላይ የሚገኘው ነው (አልዓዛር እና ሐብታሙ ሰው)፡፡ ሲኦል አሁን እንደ ቅጣት ሥፍራ ተገልጿል (ዘዳ 32:22፤ መዝ 18:1-5)፡፡ ይሁን እንጂ አንድ ሰው በአንድ ምሣሌ ላይ ብቻ አስተምህሮን ሊመሠርት አይችልም፡፡

III. በሞትን በትንሣኤ መካከል ያለው ሁኔታ

ሀ. አዲስ ኪዳን ‹‹የነፍስን ሕያውነት›› አያስተምርም፤ ይህም ከሞት በኋላ ስላለው ሕይወት በጥንት ዘመን ከነበሩ አመለካከቶች አንዱ ነው፡፡
1. የሰው ነፍስ አካሉ ከመፈጠሩ አስቀድሞ ነበረች፡፡
2. የሰው ነፍስ ከአካላዊ ሞት በፊትም ሆነ በኋላ ዘላለማዊ ነው
3. ብዙውን ጊዜ የሚታየው አካል እንደ እስር ቤት ሲታይ ሞትም ወደ ቀደመው ሁኔታ እንዲሚመለስ ይታያል፡፡

ለ. አዲስ ኪዳን ከሥጋ ተለይታ በሞትና በትንሣኤ መካከል ስላለች ነፍስ ፍንጭ ይሰጣል
1. ኢየሱስ በሥነጋና በነፍስ መካከል ስላለው ልዩነት ይናገራል፣ ማቴ 10:28
2. አብርሃም አሁን አካል ሊኖረው ይችላል፣ ማር 12:26-27፤ ሉቃ 16:23
3. ሙሴና ኤልያስ መልካቸው ሲቀየር (ሲለወጥ) የሚታይ አካል ነበራቸው፡፡ ማቴ 17
4. ክርስቶስ ዳግሞ ተመልሶ ሲመጣ ከእርሱ ጋር የነበሩት ነፍሳት አስቀድመው አዲሱን አካላቸውን ይለብሳሉ ብሎ ጳውሎስ ያረጋግጣል 1 ተሰ 4:13-18
5. አማኞች በትንሣኤ ቀን አዲስ መንፈሳዊ አካላቸውን እንደሚቀበሉ ጳውሎስ ይገልፃል 1 ቆሮ 15:23፡51

IV. መንግሥተ ሰማይ

ሀ. ይህ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ በሦስት ትርጉሞች ተጠቅሷል
1. ከመሬት በላይ ያለው ከካቢ አየር፣ ዘፍ 1:1፣ 8፣ ኢሳ 42:5፣ 45:18
2. በከዋክብት የተሞላውና ብሩህ የሆነው ሰማይ ዘፍ 1:14፣ ዘዳ 10:14 መዝ 148:4፤ ዕብ 4:14፣ 7:26
3. የእግዚአብሔር ዙፋን የሚገኝበት ሥፍራ ዘዳ 10:14፣ 1ነገ 8:27፣ መዝ 148:4፤ ኤፌ 4:10፣ ዕብ 9:24 (ሦስተኛው ሰማይ 2ቆሮ 12:12)፡፡

ለ. ከሞት ወዲያ ስላለው ሕይወት መጽሐፍ ቅዱስ ብዙም አይገልጥም፣ የዚህም ምክንያት ምናልባት በሐጢያት የወደቁት የሰው ልጆች ይህን የመረዳት አቅም ስለሌላቸው ነው (1ቆሮ 2:9)፡፡

ሐ. መንግሥተ ሰማይ ሥፍራውም ነው (ዮሐ 14:2-3) ስብዕና ያለውም ነው (2ቆሮ 5:6፡8)፡፡ መንግሥተ

ሰማይ ምናልባት የታደሰው የኤደን ገነት ሲሆን ይችላል (ዘፍ 1-2፣ ራዕ 21-22)፡፡ መሬት ወደፊት ትጠራለች እንዲሁም ትታደሳለች (ሐዋ 3:21፣ ሮሜ 8:21፤ 2ጴጥ 3:10)፡፡ የእግዚአብሔር መልክ (ዘፍ 1:26-27) በክርስቶስ ታድሷል፡፡ አሁንም ቢሆን በኤደን ገነት የነበረው አይነት የቀረበ ሕብረት የሚቻል ነው፡፡

ይሁን እንጂ ይህ ዘይቤያዊ ንግግር (መንግሥተ ሰማይ በራዕ 21:9-27 ላይ እንደ ኪዩብ ከተማ) እንጂ ቃል በቃል የሚወሰድ አይደለም፡፡ 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 15 ልክ ዘር ካደገው ተክል እንደሚለይ በሥጋዊው አካል እና በመንፈሳዊው አካል መካከል ያለውን ልዩነት ይገልፃል፡፡ ከዚህም ባሻገር 1ቆሮ 2:9 (ከኢሳ 64:4 እና 65:17 ላይ የተወሰደ ጥቅል) ትልቅ ቃልና ተስፋ ነው እርሱን ስናየው እርሱን እንደምን መሰል አውቃለሁ (1ዮሐ 3:2)፡፡

V. ጠቃሚ ምንጮች

ሀ. ዊልያም ሄንድሪክሰን፤ *The Bible on the life there after*

ለ. ማውሪክ ራውሊንግስ፣ *Beyond on Death's Door*

14:14 **"መንገዱንም ታውቃላችሁ"** ኢየሱስ የተናገረው ንግግር መንገዱስ ስለማወቅ ቶማስ ጥርጣሬውን እንዲገልጥ አድርጎታል፡፡ ኢየሱስ የሰጠው ምላሽ የተገለጸው ብዙውን ጊዜ በብሉይ ኪዳን እንደተጠቀሰው በሦስት ቃላት ተገልጿል፡፡

14:6 **"እኔ መንገድ ነኝ"** በብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት እንደህይዋት ዘይቤ ተደርጐ ይነገር ነበር (ዘዳ 5:32-33፤ 21:29፤ መዝ 27:11፤ ኢሳ 35:8)፡፡ የቀደመችው ቤተክርስቲያን የማዕረግ ስሟ (መጠሪያዋ) "መንገድ" የሚል ነበር ሐዋ ወደ እግዚአብሔር የሚወስደው ብቸኛው መንገድ መሆኑን ነው፡፡ ይህ የዮሐንስ ወንጌል ስነ-መለኰታዊ መሠረት ነው! መልካም ሥራን መሠረት ያደረገ የሕይወት ዘይቤ የእምነት ማስረጃው ነው (ኤፌ 2:8-9፤ 10) እንጂ በራሱ የጽድቅ መንገድ አይደለም፡፡ በ8:12 ላይ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ፡፡

▣ **"እውነት"** "እውነት" የሚለው ቃል በግሪክ ፍልስፍና "እውነት" ወይም "ሐሰት" ወይም "እውነት" ወይም "ምትሃት" የሚል አንደምታ ነበረው፡፡ ይሁን እንጂ ኢየሱስን ይሰው የበሩት ደቀመዛሙርት የአራይክ ቋንቋን የሚናገሩ በመሆናቸው ኢየሱስ የተናጋረው ቃሉ ከብሉይ ኪዳን አንንር የበረውን ትርጉም መሆኑን ተረድተው ነበር፤ ይህም "ታማኝነት" ወይም "እምነት የሚጣልበት" ማለተ ነበር (መዝ 26:3፤ 86:11፤ 119:30)፡፡ ሁለቱም "እውነት" እና "ሕይወት" "መንገዱን" የሚገልጡ ናቸው፡፡ "እውነት" የሚለው ቃል ብዙውን ጊዜ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የሚጠቀስ ሲሆን የሚገልፀውም መለኰታዊ እንቅስቃሴን ነው (1:14፣ 4:23-24፤ 8:32፤ 14:7፤ 15-26፤ 16:13፤ 17:17፣19)፡፡ በ6:55 እና በ17:3 ላይ እውነት በሚለው ላይ የተሰጠውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

▣ **"ሕይወትም"** "ሕይወት" የሚለው ቃል በግሪኩ Zoa (ዞ) ማለት በዮሐንስ የተጠቀሰው የአዲሱን ዘመን ሕይወት ለመግለፅ ነበር፡፡ በብሉይ ኪዳን የአማኝ የሕይወት ዘይቤ የሚነገረው ወደ ሕይወት እንደሚወስድ መንገድ ነበር (መዝ 16:11፤ ምሳሌ 10:17)፡፡ በእነዚህ ሦስት ቃላት ሁሉ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በግል የሚደረግ ሕብረት ውስጥ የሚገኙ ሲሆኑ ይህም በእመነት ከሆነ የኑሮ ዘይቤ ጋር የሚዛመድ ነው፡፡

▣ **"በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም"** እንደት አስደንጋጭ አባባል ነው ምንም እንኳን በጣም የሚገድብ አባባል ቢሆንም አንድ ሰው ከእርሱ ጋር ባለው የግል ሕብረት ምክንያት እግዚአብሔርን ማወቅ እንደሚችል ያመነበት ነው (2 ዮሐ 5:10-12)፡፡ እዚህ ላየ ማዕከላዊ ቦታ የለም፡፡ ይህ ንግግር እውነት ነወ አሊያም ደግሞ ክርስትና ውሸት ነው ማለት ነው፡፡ በብዙ መለኩ ይህ ከዮሐንስ 10 ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡

14:7 **"ከ"** ከዚህ አይነቱ ሁታዊ ዓረፍተ ነገር ጋር በተያያዘ የምንጮች ልዩነት ይታያል፡፣ የUBS[4] መጽሐፍ ቅዱስ የግሪኩ ጥቅስ ልክ P[66]፤ N እና D የግሪክ ምንጮች እንደሚደግፉት የመጀመሪያ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገርን ይደግፋል፡፡ ይህም "አታውቁትም እንጂ ብታውቁት ኖሮ"

"አታውቁኝም እንጂ ብታውቁኝ ኖሮ አባቴን ባወቃችሁት ነበር ነገር ግን አታውቁትም" ተብሎ ሊተረጐም ይችላል፡፡

ምናልባትም "አውነታን መቃረን" በሚል ሐሳብ ሁለተኛ መደብ ሁኔታዊ አረፍተ ነገር ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህም ሊኖረው የሚችለው ትርጉም አታውቁኝም እንጂ አባቴን ታውቁት ነበር ነገር ግን አታውቁትም ተብሎ ሊገለፅ ይችላል፡፡ ይህም አባባል በA, B, C, D[b], K እና X ምንጮች የሚደገፍ ነው፡፡ ይህ አስቸጋሪ ንግግር ነው ምክንያቱም ኢየሱስ በእግዚአብሔር የተላከ መሲህ መሆኑን እና ደህንነት በእርሱ ስም ሐዋርያት አስቀድመው አምነው ነበር ብለን ስለምንገምት ነው፡፡ አዲሱና የመጨረሻው እውነት ሊረዱት የተቸገሩበት ጉዳይ እንደነበር መረዳት ይቻላል ማለት ነው፡፡ የዮሐንስ ወንጌል የእምነት ደረጃዎችን የሚናጋር ይመስላል፡፡ ዓውዱም ሁለተኛ መደብ ዓረፍተ ነገርን የሚደግፍ ይመስላል፡፡ እንዲሁም ደግሞ በቁጥር 2 እና 28 ላይ ተሳሳይ ሁኔታን ያስተውሉ፡፡

▣ "እኔንስ ብታውቁኝ" ኢየሱስ አሁንም ለመነው የሐዋረያት ስብስብ መልእክቱን ያስተላልፋል (ቁ.9)፡፡ ማወቅ የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን ትርጉም የሚናገረው ቅርበት ስላለው የግል ግንኙነት እንጂ እንዲያው የአእምሮ እውቀት ብቻ አይደለም (ዘፍ 4:1 ኤር 1:5)፡፡

▣ "አባቴን ባወቃችሁ" ኢየሱስን ማየት ማለት እግዚአብሔርን ማየት ማለት ነው፡፡ (ዮሐ. 1፡14-18፣ 5፡24፣ 12፡44-45፣ 2ቆሮ 4፡4፣ ቆላ 1፡15፣ ዕብ 1፡3) ኢየሱስ የማይታየው አምላክ ፍጹም አመልካች ነው፡፡ ማንም ኢየሱስን በመቃወም እግዚአብሔርን ለማወቅ ቢሞክር የማይሆን ነገር ነው (1ዮሐ 5፡9-12)፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 14፡1-7
8ፊልጶስ። ጌታ ሆይ፥ አብን አሳየንና ይበቃናል አለው። 9ኢየሱስም አለው፦ አንተ ፊልጶስ፥ ይህን ያህል ዘመን ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቶአል፤ እንዴትስ አንተ። አብን አሳየን ትላለህ? 10እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን? እኔ የምነግራችሁን ቃል ከራሴ አልናገረውም፤ ነገር ግን በእኔ የሚኖረው አብ እርሱ ሥራውን ይሠራል። 11እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ፤ ባይሆንስ ስለ ራሱ ስለ ሥራው እመኑኝ። 12እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል፥ 13እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና፤ አብም ስለ ወልድ እንዲከበር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ። 14ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ።

14፡8 ፊሊጶስም...አለው" ፊሊጶስ ለብቻው (1) እንደ ሙሴ ኢሳያስ ወይም ሕዝቅኤል የእግዚአብሔርን ራዕይ ማየት ፈልጎ ነበር፡፡ (2) እርሱ ሙሉ በሙሉ የኢየሱስን ቃል አላስተዋለም፡፡ ኢየሱስ ፊሊጶስ እርሱን ሲያይና ሲያውቅ ያ ማለት እግዚአብሔርን ማየቱና ማወቁ እንደሆነ ነገረው (ቆላ 1፡15፣ ዕብ 1፡3)፡፡

▣

| | |
|---|---|
| NASB, | "እኛን ይበቃናል" |
| NKJV, | "ለእኛ በቂ ነው" |
| NRSV | "እና እንረካልን" |
| TEV | "የምንሻውም ይኸንን ነው" |
| NJB | "በዚህም ሁሉ እንረካለን" |

እነዚህን ደቀመዛሙርት እንደፈሪሳውያን ሁሉ ምልክ ይሹ ነበር። ይሁን እንጂ አማኞች በመንፈሳዊ ነገር ሁሉ በእምነት እንጂ በማየት መኀዝ የለባቸውም (2ቆሮ 4:18፣ 5:7)። መታመን ከሁሉ በላይ ነው!

14፡9 "ይህን ያህል ዘመን ከእናንተ ጋር ስኖር" አስተውሉ ይህ ብዙ ቁጥርን አመልካች ነው። ሁላቸውም ያስቡ የነበሩት ጥያቄ ነበር ፊሊጶስ የጠየቀው።

14:9 "ይህን ያህል ዘመን ከእናንተ ጋር ስኖር..." የብዙ ቁጥር መሆኑን አስተውል፤ ፊልጶስ የጠየቀው ጥያቄ ሁሉም በአእምሮአቸው ያሰላስሉ የነበረውን ነበር፡፡

▣ "እኔን ያየ አብን አይቶአል" ይህ የተጠናቀቀ ቦዝ አንቀጽ እና የተጠናቀቀ ድርጊት ገላጭ ግሥ ሲሆን ትርጉሙም፤ አይቶአል ደግሞም ያያል ማለት ነው፡፡ ኢየሱስ ፍፁም በሆነ ሁኔታ መለኮትን የሚገልጥ ነው (ቆላ 1:15፤ ዕብ 1:3)፡፡

14:10 በግሪኩ የኢየሱስ ጥያቄ "አዎን" የሚል ምላሽን የሚጠብቅ ነው በ1 ዮሐ 2:10 ላይ "መኖር" በዮሐንስ ፅሑፎች ውስጥ የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

▣ "አታምንምን .... የምነግራችሁን" የመጀመሪያው "አንተ" የሚለው ተውላጠ ስም ነጠላ ሲሆን የሚያመለክተውም ፊልጶስን ነው፡፡ ሁለተኛው "አንተ" የሚለው ተውላጠ ስም ግን የሚያመለክተው የሐዋርያትን ቡድን ነበር (ቁ.7፤10)፡፡ በ1ዮሐ 2:10 ላይ "መኖር" በዮሐንስ ፅሑፎች ውስጥ የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

▣ "እኔ የምነግራችሁን ቃል ከራሴ አልናገረውም ነገር ግን በእኔ የሚኖረው አብ እርሱ ሥራውን ይሠራል"፤ ኢየሱስ ሁሉን ያደርግ የነበረው በአባቱ ስም ነበር (ቁ. 24፤ 5:19፤ 30፤ 9:16-18፤ 8:28፤ 10:38፤ 12:49)፡፡ የኢየሱስ ትምህርቶች ከአብ የመነጩ እውነተኛ ቃላት ነበሩ (ቁ. 24)፡፡

▣ **"ነገር ግን በእኔ የሚኖረው አብ እርሱ ሥራውን ይሠራል"** ይህ በአባትና በልጅ መካከል ያለ የቀረበ ግንኙነት (7:6፤ 8:28፤ 10:38)፤ እንዲሁም ደግሞ በምዕራፍ 17 ላይ ኢየሱስ ባረገው የሊቀ ካህንነት ፀሎት ላይ ትኩረት የተሰጠት፤ የዮሐንሰ ወንጌል ድነትን የሚገልጠው (1) እንደ አስተምህሮ (2) እንደ ሕብረት፤ (3) መታዘዝ እና (4) እንደ መፅናት አድርጐ ነው፡፡

14:11 **"እመኑኝ"** ይህ የአሁን ጊዜ ትዕዛዛዊ ግሥ ወይም የአሁን ጊዜ አመልካች ግሥ ነው (14:1)

በዚህ ጥቅስ የመክፈቻ ሐረግ ላይ ጠቃሚነት ያለው የተወሰነ የምንጭ ልዩነት አለ፡፡ አንዳንድ ቀደምት የግሪክ ምንጮች ($P^{66}$ ፤ $p^{75}$ ፤ N :D :L እና W) "እመኑ" የሚለው ግሥ አመልካች ተውላጠ ስም (that) አስከትለው ይታያሉ፤ ይህም የሚያመለክተው የኢየሱንና የአብን አንድነት መቀበል እንዳለባቸው የሚያሳስብ ነው፡፡ ሌሎተ ምንጮች ደግሞ (MS A aNd B) ቀጥተኛ ያልሆነን ተሳቢ በመጨመር (iN me) እምነቱ ያረፈበትን ተሳቢ ያሳያሉ፡፡ PUBS4 መጽሐፍ ቅዱስ የግሪኩ ሊቃውንት የመጀመሪያው አማራጭ ዋና ነው ብለው ያምናሉ (*Bruce M. Metzgers: A Texual CommeNtary oN the Greek New TestameNt)* ገጽ 244 ለዚህኛው አማራጭ የ "B" ደረጃን ይሰጠዋል፡፡ አብዛኛዎቹ የዘመናችን ትርጉሞች "iN me" የምትለውን ይጠብቁና አመልካች ተውላጠ ስሙን (that) ይጨምሩበታል (የሚታመነውን ነገር ይዘት ለማሣየት)፡፡

▣ **"ባይሆንስ ስለ ራሱ ስለ ሥራው እመነኝ"** ኢየሱስ በሥራው እንዲያምኑ ይነግራቸዋል (ዮሐ 5:36፤ 10:25፤35)፡፡ የእርሱ ሥራዎች በብሉይ ኪዳን የተነገሩትን ትንቢቶች ያሟሉ ነበሩ፡፡ ሥራዎቹ ማን መሆኑን የሚልጡ ናቸው፡፡ ሐዋርያትም ልክ እንደ ሁላችንም በእምነት ማደግ ነበረባቸው!

14:12 **"እውነት እውነት እላችኋለሁ"** በ1:51 ላይ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ፡፡

▣ **"በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እራሱ ደግሞ ያደርጋል"** ማመን የአእምሮ ድርጊት ብቻ ሳይሆን ድርጊትን የተምን ቃል ነው፡፡ "ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል" የሚለው ሐረግ የወደፊት ድርጊት አመልካች ሲሆን ሊኖረው የሚችለው ትርጉምም "ታላላቅ ነገሮችን ያደርጋል" የሚል ነው፡፡ ይህም ምናልባት የሚያመለክተው

1. መልክአ ምድራዊ ክልልን (ማቴ 28:18-20)
2. የአህዛብን የወንጌለ ተልእኰ
3. መንፈስ ከማንኛውም አማኝ ጋር መሆኑን
4. የኢየሱስ የምልጃ ፀሎት (ዕብ 7:25፤ 9:24)፡፡

በ1ዮሐ 3:22 ላይ ፀሎት ያልተገደበ ግን የተገደበ የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

እርሱ ደግሞ ያደርጋል "የሚለው የመጨረሻው ሐረግ ለመጽሐፍ ቅዱሳዊዋ ክርስትና አስፈላጊና ወሣኝ ነገር ነው፡፡ አብ ወልድን እንደላከ ሁሉ ወልድም የራሱን ደቀመዛሙርት ይልካል" "በክርስቶስ መሆን" የዘላለም ሕይወትን ማግኘት ማለት የታላቁ "ተልዕኰ" ዋና ሐሳብ ነው፡፡ ክርስትና አንዳች ድንጋጌ ወይም አንዳች የምንቀበለው ነገር ሳይሆን አዲስ ሕይወትን፣ አዱስ አመለካከትን ማለት ነው! ሁሉንም ነገር የሚለውጥ ነው፤ ተረድተን የምንኖርበት፣ ዕለታዊና የእግዚአብሔርን መንግሥት ማዕከል ያደረገ መሥዋዕትነት የተሞላበት የሕይወት ዘይቤ ሊሆን ይገባል፡፡

በመሆኑም ቤተክርስቲያን አሁን መልሳ ልትኖርበት የሚባው

1. የእያንዳንዱ አማኝ አገልግሎት
2. የታላቁ ተለእኰ ቀዳሚነት
3. ከራስ ወዳድነት ነፃ የሆነ እለታዊ አገልግሎት
4. ክርስቶስን የመምሰል የማያቋርጥ ሕይወት

14:13-14 **"ማናቸውንም ነገር በስሜ በትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ"** ኢየሱስ ፀሎታችንን የሚመልሰው በባህሪው ላይ በመመሥረት መሆኑን አስተውል፡፡ በሐዋ 7:59 ላይ እስጢፋኖስ ወደ ኢየሱስ ፀልዮ ነበር፡፡ በ2ኛ ቆሮ 12:8 ላይም ጳውሎስ ወደ ኢየሱስ ፀልዮአል፡፡ በ15:16 እና በ16:23 ላይም አማኞችም ወደ አብ እንዲፀልዩ ያሳስባል፡፡ በኢየሱስ ስም መፀለይ በፀሎታችን መጨረሻ ላይ እንደ ድግምት ቀመር የምንጠቀመው ሳይሆን በኢየሱስ ፈቃድና ባህርይ መሠረት ላይ መፀለይ ማለት ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ግትር አቋም ከመውሰዳችን በፊት ተነፃፃሪ የሆኑ ምንባቦችን መመልከቱ አስፈላጊነት ያለው ነው፤ አንድ ሰው ማናቸውንም ነገር ብንለምን የሚለውን ሐረግ ሚዛኑን ሊጠብቅለት ይገባል፤

1. "በስሜ" (ዮሐ 14:13-14፤ 15:7፤ 16፤ 16:23)
2. "ለምኑ" (ማቴ 7:7-8፣ ሉቃ 11:5-13፤ 18:1-8)
3. "ሁለቱ ቢስማሙ" (ማቴ 18:19)
4. "እምኖ" (ማቴ 21:22)
5. "ሳይጠራጠር" (ማር 11:22-24፤ ያዕ 1:6-7)
6. "ሳይጠራጠር" (ያዕ 4:2-3)
7. "ትዕዛዞችን ብንጠብቅ" (1ዮሐ 3:22)
8. "እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ" (ማቴ 6:10፣ 1ዮሐ 5:14-15)፡፡

የኢየሱስ ስም ባህርይውን የሚወክል ነው፡፡ ይህም የኢየሱስን ልብና ሐሳብ የሚያመለክት ሌላው መንገድ ነው፡፡ ይህ ሐረግ ብዙ ጊዜ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ይታያል (14:13-14፣ 26:15-16፣ 23-26)፡፡ ኢየሱስን እየመለስን በሂድን ቁጥር የፀሎታችን መልሶች በበለጠ ይመለሳሉ ማለት ነው፡፡ ለአማኞ እግዚአብሔር ሊያደርግላቸው የሚችለው እጅግ የከፋው ነገር ቢኖር በራስ ወዳድነትና ቁሣዊ ነገሮችን በማፍቀር የሚፀልዩትን ፀሎት ምላሽ መስጠት ነው፡ቸ የ1ዮሐ 3:22ን ማብራሪያ ይመልከቱ፡፡

**ልዩ ርዕስ: ውጤታማ ፀሎት**

ሀ. ከእግዚአብሔር ጋር ባለ የግል ግንኙነት የሚወሰን ነው
1. ከአብ ፈቃድ ጋር የሚዛመድ ነው
   ሀ. ማቴ 6:10
   ለ. 1የሐ 3:22
   ሐ. 1ዮሐ 5:14-15
2. በኢየሱስ መኖር
   ዮሐ 15:7
3. በኢየሱስ ስም መፀለይ
   ሀ. ዮሐንስ 14:13-14
   ለ. ዮሐንስ 15:16
   ሐ. ዮሐንስ 16:23-24
4. በመንፈስ መፀለይ
   ሀ. ኤፌ 6:18
   ለ. ይሁዳ 20

ለ. ከአንድ ሰው .ከሰው. መነሻ ሐሳብ ጋር የሚዛመድ ነው
1. የማያወላውል
   ሀ. ማቴ 21:22
   ለ. ያዕ 1:6-7
2. የጐደለን መጠየቅ
   ያዕ 4:3
3. በራስ ወዳድነት መለመን
   ያዕ 4:2-3

ሐ. ከሰው ምርጫ ጋር የሚዛመድ ነው
1. መጽናት
   ሀ. ሉቃ 18:1-8
   ለ. ቆላ 4:2
   ሐ. ያዕ 5:16
2. በቤት ውስጥ ስምምነት ማጣት
   1ጴጥ 3:7
3. ሐጢአት
   ሀ. መዝ 66:18
   ለ. ኢሳ 59:1-2
   ሐ. ኢሳ 64:7

ሁሉም ፀሎት የሚመለስ ቢሆንም ሁሉም ፀሎት ግን ስኬታማ አይደለም፡፡ ፀሉት የሁለትዮች ግንኙነት ነው፡፡ እግዚአብሔር ሊያደርግ የሚችለው በጣም የከፋ ነገር ተገቢ ላልሆነው የአማኞች ጥያቄ መልስ በመስጠት ነው፤ ይህንንም በቆላ 4:3 ላይ የምልጃ ፀሎት የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፤ እንዲሁም ደግሞ በ1ዮሐ 5:14 ላይ

**ልዩ ርዕስ: የእግዚአብሔር ስም/የጌታ ስም**

ይህ በቤተክርስቲያን ውስጥ ስላለው የእግዚአብሔር ሕልውና የማያቋርጥ እንቅስቃሴው የተለመደ የአዲስ ኪዳን ሐረግ ነው፡፡ ይህ አለማታዊ ቀመር ሳይሆን በእግዚአብሔር ማንነት (ባህርይ) ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ ይህ ሐረግ የሚያመለክተው ኢየሱስን እንደ ጌታ በማድረግ ነው (ፊል 2÷11)፡፡

1. አንድ ሰው በኢየሱስ ካመነ በኋላ እምነቱን በጥምቀት ሲገልፅ (ሮሜ 10÷9-13፣ ሐዋ 2÷38፤ 8÷12፤ 16፤ 10÷48፤ 19÷5፤ 22÷16፤ 1ቆሮ 1÷13፤ 15፤ ያዕ 2÷7)
2. መናፍስትን በማስወጣት ወቅት (ማቴ 7÷22፤ ማር 9÷38፤ ሉቃ 9÷49፤ 10÷17፣ ሐዋ 19÷13)
3. በፈውስ ጊዜ (ሐዋ 3÷6፤ 16፣ 4÷10፤ 9÷34፤ ያዕ 5÷14)
4. አልግሎት ሲደረግ (ማቴ 10÷42፤ 18÷5፤ ሉቃ 9÷48)
5. በቤተክርስቲያን የዲሲፕሊን እርምጃ ጊዜ (ማቴ 18÷15-20)
6. ለአህዛብ ወንጌል ሲሰበክ (ሉቃ 24÷47፣ ሐዋ 9÷15፤ 15÷17፤ ሮሜ 1÷5)
7. በፀሎት ወቅት 1ዮሐ 14÷13-14፤ 15÷2፤16፤16÷23 1 ቆሮ 1÷2
8. ክርስትናን ለማመልከት (ሐዋ 26÷9፤ 1ቆሮ 1÷10፤ 2ጢሞ 2÷19፤ ያዕ 2÷7 1ጴጥ 4÷14)

እንደወንጌል ሰባቢዎች፣ አገልጋዮች ምህረት አድራጊዎች፣ አጋንንትን እንደሚያስወጡ ወዘተ የምናደርገው ማናቸውም ነገር በእርሱ ባህርይ (ማንነት)፣ ሐይል እና ቸርነት ነው፡፡ በስሙ፡-

▣ *"ብትለምኑ …" ይህ የሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ አረፍተ ነገር ሲሆን የሚያመለክተውም ድርጊትን ለማከናወን ዕድል መኖሩን ነው፡፡*

▣ *"ማናቸውንም ነገር … ብትለምኑ" በተለምዶ አማኞች በወልድ አማካኝነት በመንፈስ ወደ አብ እንዲሄዱ ይበረታታሉ፡፡ ይህ ጥቅስ ግን በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ኢየሱስ ወደ ራሱ እንዲፀልዩ የተናገረበት ብቸኛው ጥቅስ ነው፡፡*

*ለዚህም ነው ምናልባት አንዳንድ የጥንት የግሪክ ምንጮች "እኔ" የሚለውን የሚገድፉት* (MSS፣ A፣ D፣ L *እና አንዳንድ የላቲን ብሉይኪዳን፣ ቩልጌት፣ ኮፕቲክ የኢትዮጵያ እና የስላቮ እትሞች)፡፡ የ*UBS[4] *መጽሐፍ ቅዱስ መካተቱን የ* "B" *ደረጃን ይሰጠዋል (ለእርግጠኝነት የቀረበ)፡፡ በ*MSS P66፣ P75፣ N፣ B፣ W *እና ጥቂት የላቲን ብሉይኪዳን፣ ቩልጌት እና የሶርያ እትሞች ውስጥ ተካትቷል፡፡*

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 14 ÷15-17

**[15]ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ፣ [16]እኔም አብን እለምናለሁ፣ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አፅናኝ ይሰጣችኋል፡፡ [17]እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው፡፡ ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውስጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ፡፡**

14:15 **"ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ"** *ይህ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ሲሆን የሚናገረውም ድርጊት ለመፈፀም አቅም መኖሩን ነው፡፡ በክርስቶስ የሆነ ለእግዚአብሔር የሚገለፅ ፍቅር የሚገልፀው በመታዘዝ ነው፡፡ "ጠብቁ" የሚለው የወደፊት ድርጊት ገላጭ አመልካች ሲሆን የተጠቀሰው አሁን እንደሚፈፀም ትእዛዝ ነው (ፍሪቨርግ፤ aNalytical Greek New TestameNt፥ ገጽ* 337)፡፡ *መታዘዝ በጣም አስፈላጊው ጉዳይ ነው* (8:51፤ 14:21፤ 23:27፣ 15:10፣1ዮሐ 2:3-5፣ 3:22፤ 24፤ 5:3፤2ዮሐ 6: ሉቃ 6:46)፡፡ *ቁጥር* 21፣ 23፣ *እና* 24 *ትኩረት የሚያደርጉት ተመሳሳይ እውነት ላይ ነው፡፡ መታዘዝ የእውነተኛ መለወጥ ማስረጃ ነው (ያዕ እና 1 ዮሐ)፡፡*

*የNKJV መጽሐፍ ቅዱስ "ትእዛዜን ጠብቁ" የሚል ትእዛዝ ያለው ሲሆን ይህም በMSS A፣ D፣* W፣ *ቩልጌት እና በብዙ የቤተክርስቲያን አባቶች የሚደገፍ ነው፡፡ የUBS[4] መጽሐፍ ቅዱስ ለወደፊት ድርጊት ገላጩ የ ደረጃን (ለመወሰን የሚያስቸግር) ይሰጠዋል፡፡ ይህም በ MSS B፣ L እና በኮፕቲክ ትርጉም እንዲሁም በበርካናታ የቤተክርስቲያን አባቶች ይደገፋሉ፡፡*

14:16 **"ይሰጣችኋል"** በ14:26 *ላይ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ፡፡*

▣

| | |
|---|---|
| NASB NKJV | |
| TEV | **"ሌላ አፅናኝ"** |
| NRSV | **"ሌላ ጠበቃ"** |
| NJB | **"ሌላ ጰራቅሊጦስ"** |

“ሌላ” የሚለው ቃል የግሪኩ (*allos*) ሲተረጉመው “ተመሳሳይ የሆነ ሌላ” ማለት ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ “ሌላው ኢየሱስ” ተብሎ ሲጠራ ቆይቷል (ጂ ካምፕቤል ሞረጋን፣ ልዩ ርዕስ የሚለውን ከሥር ይመልከቱ፡፡)፡፡

ሁለተኛው ቃል (ጰራቅሊጦስ) *(Paraklitos)* የሚለው ሲሆን ይህም በ1ዮሐ 2:1 ኢየሱስን (እንደሚማልድ) እንዲሁም ደግሞ በዮሐ 14:26 እና 16:7-14ላይ መንፈስ ቅዱስን ለመግለን ተጠቅሷል፡፡ በአጠቃላይ ትርጉሙ ሥርወ ቃሉ “አንድን ሰው ለመርዳት አብሮት ያለ” የሚል ሐሳብ አለው፡፡ በመሆኑም “ጠበቃ” የሚለው ቃል ይህን ቃል በትክክል ይተረጉመዋል፡፡ የዚህ ተመሳሳይ የግሪኩ ሥርው-ቃል “ማፅናናት” *(Paraklio)* የሚለው በ2ኛ ቆሮ 1:3-11 ላይ አብን ለመግለን ተጠቅሷል፡፡

“ጠበቃ” *(Paraklitos)* የሚለው ስም ትርጉም የመጣው ከሮም የሕግ ሥርዓት ነው፡፡ “አፅናኝ” የሚለው ትርጉም ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለው በዊክሊፍ ሲሆን የሚያንፀባርቀው በስብትዋጅነት (ኢሳ 33:7፣ 35-4፣ 61:1-2፣ 66:10-19፣ *NIDOTTE* አንቀጽ 1፣ ገጽ 570ን ይመልከቱ፡፡) ያለውን የግሱን መልክ አጠቃቀም ነው፡፡ ይህም ምናልባት ሰይጣን (ከሳሽ) ለሚለው ቃል ተመሣሣይ ነው፡፡

ፊሎ እና ጆሴፈስ ሁለቱም ቃሉን የተጠቀሙት “ማሳጅ” ወይም “አማካሪ” በሚል እሳቤ ነው፡፡

**ልዩ ርዕስ: ኢየሱስ እና መንፈስ**

በመንፈስ እና በወልድ ሥራ መካከል ተመሣሣይነት አለ። ለዚህም ነው ጂ ካምቤል ሞርጋን ሲናገር ከሁሉ የተሻለው ለመንፈስ የሚሰጠው ስም “ሌላው ኢየሱስ” ነው ያለው (ይሁን እንጂ የተለያዩ፣ ዘላለማዊ ስብዕናዎች ናቸው)። የሚከተለውም ንድፍ የወልድንና የመንፈስን ሥራና ማዕረጐች በንፅፅር መልክ የሚያሳይ ነው።

1. መንፈስ “የኢየሱስ መንፈስ” ወይም ተመሳሳይ በሆነ አባባል ተጠቅሷል (ሮሜ 8:9፣ 2ቆሮ 3:17፣ ገላ 4:6፣ 1ጴጥ 1:11)።
2. ሁለቱም በተመሳሳይ ቃላት ተጠርተዋል
   - ሀ. “እውነት”
     1. ኢየሱስ (ዮሐ 14:6)
     2. መንፈስ (ዮሐ 14:17፣ 16:13)
   - ለ. “ጠበቃ”
     1. ኢየሱስ (1ዮሐ 2:1)
     2. መንፈስ (ዮሐ 14:16፣26፣ 15:26፣ 16:7)
   - ሐ. “ቅዱስ”
     1. ኢየሱስ (ሉቃ 1:35፣ 14:26)
     2. መንፈስ (ሉቃ 1:35፣ 4:34)
     3. ሁለቱም በአማኞች ውስጥ ይኖራሉ
3. ሁለቱም በአማኞች ውስጥ ይኖራሉ
   - ሀ. ኢየሱስ (ማቴ 28:20፣ ዮሐ 14:20፣ 23፣ 15:45፣ ሮሜ 8-10፣ 2ቆሮ 13:5፣ ገላ2:20፣ ኤፌ 3:17፣ ቆላ 1:27)።
   - ለ. መንፈስ (ዮሐ 14:16-17፣ ሮሜ 8:9፣11፣ 1ቆሮ 3:16፣ 6:19፣ 2ጢሞ 1:14)
   - ሐ. አብ (ዮሐ 14:23፣ 2ቆሮ 6:16)።

▣ **“ከእናንተ ጋር እንዲኖር” መንፈስ ቅዱስን ለማመልከት ሦስት የተለያዩ መስተፃምሮች ተጠቅሰዋል፡፡**

1. “*Meta*” (ቁ. 16)፣ “ከ”
2. *“Para”* (ቁ. 17)፣ “በ”
3. *“eN”* (ቁ. 17)፣ “በ … ውስጥ”

መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ጋር፣ በእኛ ጐን እና በውስጣችን መሆኑን አስተውል፡፡ የኢየሱስን ሕይወት በአማኞች ውስጥ መግለጥ የእርሱ ሥራ ነው፡፡ እስከ ዘመኑ ፈፃሜ ድረስ ከአማኞች ጋር አብሮ ይኖራል (ቁ. 18፣ ማቴ 28:20)፡፡

መንፈስ ቅዱስ እርሱ መባሉን እናስተውል፡፡ ይህም በተዘዋዋሪ የሚያመለክተው መንፈስ ስብዕና እንዳለው ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ በKJV መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ “it” (ግዑዝን ለመጥቀስ የሚውል) ተብሎ ተጠቅሷል፣ ምክንያቱም “መንፈስ” የሚለው በግሪክ ፆታ የለሽ (Neuter) ስለሆነ ነው (ዮሐ 14:17፣ 26፣ 15:26)፡፡ መንፈስ ሦስተኛው የስላሴ አካል ነው (በ14:26 ላይ ልዩ ርዕስን ይመልከቱ፡፡)፡፡ ስላሴ የሚለው ቃል መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም፣ ነገር ግን ኢየሱስ መለኮት ከሆነ እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ስብዕና ካለው አንዳች የሦስትዮሽ ጥምረት አለ ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር አንድ ማንነት አለው ነገር ግን የማይለዋወጥ ሦስት መገለጫዎች አሉት (በ14:26 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡፣ ማቴ 3:16-17፣ 28:19፣ ሐዋ 2:33-34፣ ሮሜ 8:9-10፣ 1ቆሮ 12:4-6፣ 2ቆሮ 1:2-22፣ 13:14፣ ኤፌ 1:3-14፣ 2:18፣ 4:4-6፣ ቲቶ 3:4-6፣ 1ጴጥ 1:2) ፡፡

“ለዘላለም” ለሚለው በ6:58 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

14:17 **"የእውነት መንፈስ"** በዚህ ሥፍራ ላይ "እውነት" የሚለው እንደ ቁ.6 ተመሳሳይ ድባብ አለው (15:26፤ 16:13፤ 1ዮሐ 4:6)፡፡ እውነት በሚለው ላይ በ6:55 እና 17:3 ላይ ልዩ ርዕስን ይመልከቱ፡፡ መንፈስ የውሸት አባት ከሆነው ከሰይጣን በቃራኒ ነው (8:44)፡፡

▣ **"የ...የ"** ይህ "መንፈስ" *(PNeuma)* ከሚለው ቃል የሚስማማ ፆታ የለሽ ቃል ነው፡፡ ይሁን እንጂ በግሪኩ የወንድ ፆታ አመልካች ተውላጠ ስም ተጠቅሷል (ቁ. 26፤ 15:26፤ 16:7፣ 13:14)፡፡ መንፈስ ቅዱስ ወንድም ወይም ሴት አይደለም፡፡ እርሱ መንፈስ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር እርሱ ልዩ ስብዕና እንዳለው ማስታሱ በጣም ጠቃሚ ጉዳይ ነው፡፡

▣ **"ዓለም ... ሊቀበለው የማይቻለው"** መንፈስ ቅዱስ በፍፁም ተቀባይነት ሊያገኝ የሚተለው በክርስቶስ እምነት ባላቸው ዘንድ ብቻ ነው (1:10-12)፤ እርሱም አማኙ በሚያስፈልገው በማናቸውም ነገር ይረዳዋል (ሮሜ 8:1-10)፡፡ ነገር ግን የማያምነው ዓለም መንፈሳዊ ነገሮችን ሊረዳ ወይም ሊያደንቃቸው አይችልም (1ቆሮ 2:14፤ 2ቆሮ 4:4)፡፡

**ልዩ ርዕስ *Cosmos* (ዓለም) የሚለው ቃል በጳውሎስ አጠቃቀም**

ጳውሎስ *Cosmos* የሚለውን ቃል በበርካታ መንገዶች ይጠቅሰዋል፤

1. ፍጥረት ሁሉ (ሮሜ 1÷20፤ ኤፌ 1÷4፤ 1ቆሮ 3÷28፤ 8÷4፤5)
2. የምንሮርበት ፕላኔት (2ቆሮ 1÷17፤ ኤፌ 1÷10፤ ቆላ 1÷20፤ 1ጢሞ 1÷15፤ 3÷16፤6÷7)
3. ሰዎች (1÷27-28፤ 4÷9፤ 13፣ ሮሜ 3÷6፣19፤ 11÷15፤ 2ቆሮ 5÷19፤ ቆላ 1÷6)
4. ከእግዚአብሔር ተለይቶ የተደራጀና እና የሚሠራ የሰዎች ስብስብ (1÷20-2፤ 2÷12፤ 3÷19፤ 11÷32፤ ገላ 4÷3፤ ኤፌ 2÷2፣12፤ ፊል 2÷15፤ ቆላ 2÷28፣ 20-24)፡፡ ይህ ከዮሐንስ አጠቃቀም ጋር በጣም የሚመሳሰል ነው (1ዮሐ 2÷15-17)፡፡
5. አሁን ያለንበት ዓለም መዋቅሮች (7÷29-31፤ ገላ 6÷14 ከፊል 3÷4-9፣) ይህም ጳውሎስ የአይሁድ መዋቅርን የሚገልጽበት ነው፡፡

በአንዳንድ ሁኔታዎች እነዚህ መደራረቦች ስላሉ ሁሉንም አጠቃቀም ለይቶ ለመመደብ አስቸጋሪ ነው፡፡ ይህ ቃል በጳውሎስ ሐሳብ እንዳሉት እንደ ብዙዎቹ ሊገለጽ የሚገባው አስቀደሞ በተሰነ ፍቺ ሳይሆን በዙሪያው ባለው አውድ መሠረት ነው፡፡ የጳውሎስ ቃላት (የሙያ) ተስማሚነት ያላቸው ነበሩ (ጀምስ ስቴዋርት፤ *A Man in Christ*)፡፡ ጳውሎስ ስርዓትን የተከተለ ሥነ-መለኮትን ለመመሥረት እየጣረ ሳይሆን ዋና ዓላማው ወንጌልን መስበክ ነበር ፤ እርሱም ሁሉን የሚለውጥ ነው!

▣ **"የማያውቀው ... ታውቃላችሁ"** ይህ ምናልባት በዮሐንስ ወንጌል ሌላው ጣመራ አገባብ ነው፡፡ በእብራይስጡ ያለው ድባብ (ትርጉም) የቀረበ የግል ግንኙነት ነው (ዘፍ 4:1፤ ኤር 1:5)፡፡ በግሪኩ ያለው ሃሳብ እውቀት ነው፤ ወንጌል የግልም የእውቀትም ጉዳይ ነው፡፡

▣ **"በውስጣችሁም ስለሚሆን"** መኖር የሚለው ቃል በዮሐንስ ፅሑፎች ውስጥ ቁልፍ ሐሳብ ነው (ምዕራፍ 15፤ በ1ዮሐ 2:10 ላይ ልዩ ርዕስን ይመልከቱ፡፡) አብ በወልድ ይኖራል፤ መንፈስ በአማኞች ይኖራል እንዲሁም ደግሞ አማኞች በወልድ ይኖራሉ፡፡ ይህ መኖር ስሜታዊ ምላሽ ወይም ገለልተኛ የሆነ ውሳኔ ሳይሆን የአሁን ጊዜ ነው፡፡

▣ **"ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር"** ይህንን አባባል "በመካከላችሁ ስለሚሆን" በሚል መረዳት ይቻላል (የብዙ ቁጥር ነው፤ የኤን-አር-ኤስ-ቢ. የግር B ማስታወሻ) ወይም "በውስጣችሁ" ማለትም ይቻላል (የብዙ ቁጥር፤ ኤን.ኤ.ኤስ.ቪ.፤ ኤን.ኬ.ጄ.ቪ.፣ NRSV፣ TEV እና NJB)፡፡ እግዚአብሔር በአማኝ ውስጥ መሆኑ በጣም አስደናቂ ተስፋ ነው፡፡ አዲስ ኪዳን ሦስቱም የስላሴ አካላት በአማኞች ውስጥ እንደሚኖሩ ያረጋግጣል፡፡

1. ኢየሱስ (ማቴ 28:20፤ ዮሐ 14:20፣23፤ 15:4-5፤ ሮሜ 8:10፤ 2ቆሮ 13:5 ገላ 2:20፤ ኤፌ 3:17፤ ቆላ 1:27)፡፡
2. መንፈስ (ዮሐ 14:16-17፤ ሮሜ 8:11፤ 1ቆሮ 3:16፤ 9:19፤ 2ጢሞ 1:14)
3. አብ (ዮሐ 14:23፣ 2ቆሮ 6:16)፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 14÷18-24
**[18]ወላጆች እንደሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም ወደ እናንተ እመጣለሁ፡፡ [19]ገና ጥቂት ዘመን አለ፡ ከዚህም በኋላ ዓለም አያየኝም እናንተ ግን ታዩኛላችሁ እኔ ሕያው ነኝና እናንተ ደግሞ ሕያዋን ትሆናላችሁ፡፡ [20]እኔ በአባቴ**

እንዳለሁ እናንተም በእኔ እንዳላችሁ እኔም በእናንተ እንዳለሁ በዚያን ቀን ታውቃላችሁ፡፡ [21]ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው የሚወደኝንም አባቴ ይወደዋል እኔም እወደዋለሁ ራሴንም እገልጥለታለሁ፡፡ [22] የአስቆሮቱ ያይደለ ይሁዳ፡ ጌታ ሆይ ለዓለም ሳይሆን ራስህን ለእኛ ልትገልጥ ያለህ እንዴት ነው አለው፡፡ [23]ኢየሱስም መለሰ አለውም፡- የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን [24]የማይወደኝ ቃሌን አይጠብቅም የምትሰሙትም ቃል የላከኝ የአብ ነው እንጂ የእኔ አይደለም፡፡

14:18 *"ወላጆች እንደሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም ወደ እናንተ እመጣለሁ"* ኢየሱስ ቀደም ሲል ለደቀመዛሙርት የገባላቸውን ማንኛውንም ተስፋ ከፋሲካ በፊላ በነበረው የመጀመሪያው ድህረ - ትንሳኤ ምሽት ፈጎሞታል (20:19-31)፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያብራሩ ሊቃውንት ዓውዱ በበዓለ ሃምሳ ቀን የመንፈስ ቅዱስን መምጣት እንደሚያመለክት አድርው ያዩታል (ሐዋ 2) ወይ ደግሞ የዳግም ምፅአቱን ያመለክታል ይላሉ (ቁ. 3)፡፡

⊡ *"ገና ጥቂት ዘመን አለ ከዚህም በኋላ ዓለም አያየኝም እናንተ ግን ታዩኛላችሁ"* ቁጥር 20 የሚያሳየው ይህ ከትንሳኤ በኋላ ያለውን መልክ እንደሚያመለክት ነው፡፡ ይህ አረፍተ ነገር /ንግግር/ በቁጥር 20 ላይ ይሁዳ ኢየሱስን ሌላ ጥያቄ ለመጠየቅ ያነሳበት ነው፡፡ ደቀመዛሙርት ኢየሱስ መሲሓዊ መንግሥትን በምድር ላይ እንደመመርት አሁንም እየጠበቁ ነበር (ማቴ 20:20-28 ማር 10:35-45)፤ ከዚህም ባሻገር "ዓለም አያየኝም" ሲላቸው ይበልጥ ግራ ተጋብተው ነበር፡፡ በቁጥር 23 እና 24 ላይ ይሁዳ (የአስቆሮቱ ሳይሆን) ላነሳው ጥያቄ ኢየሱስ የሰጠው ምላሽ ራሱን በእያንዳንዱ ክርስቲያን ሕይወት እንደሚገልጥ ብሎም ዓለም በእነርሱ አማካኝነት እርሱን እንደሚያይ ነው!

⊡ *"እኔ ሕያው ነኝና እናንተ ደግሞ ሕያዋን ትሆናላችሁ"* የኢየሱስ ትንሳኤ እግዚአብሔር ኃይሉን ያሳየበት እና ለሰው ልጆችም ሕይወትን ለመስጠት ፈቃዱን የገለጠበት ነው (ሮሜ 8:9-11፤ 1ቆሮ 15:20-23፣ 50-58)፡፡

14:20 *"በዚያን ቀን"* ይህ ሐረግ ብዙውን ጊዜ የተጠቀሰው ከነገረ - ፍፃሜ አንፃር ባለው ትርጉም ነው (ቀጥሎ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡)፤ ነገር ግን በዚህ ሥፍራ የኢየሱስን ድህረ - ትንሳኤ መስክ ሊያመለክት ይችላል ወይም በበዓለ ሃምሳ ቀን መንፈስ ቅዱስ በሙላት መምጣቱን ሊያሳይ ይችላል፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ በዚያን ቀን**

"በዚያን ቀን" ወይም "ያን ቀን" የሚለው ሐረግ ለፍርድ ወይም ለተሐድሶ እግዚአብሔር የሚያደርገውን ጉብኝት ለማመልከት ከ/ክ/ል/በፊት ከ8ኛው መቶ ክፍል ዘመን የነበሩት ነቢያት የነበራቸው አጠቃቀም ነው፡፡

| ሆሴዕ | | አሞፅ | | ሚክያስ | |
|---|---|---|---|---|---|
| አዎንታዊ | አሉታዊ | አዎንታዊ | አሉታዊ | አዎንታዊ | አሉታዊ |
| 1:11 | 1:5 | | 1:14 (2) | | 2:4 |
| | 2:3 | | 2:16 | | 3:6 |
| 2:15 | | | 3:14 | 4:6 | |
| 2:16 | | | 3:18(2) | | |
| 2:21 | | | 3:20 | | 5:10 |
| | 5:9 | | 6:3 | 7:11(2) | |
| | 7:5 | | 8:3 | 7:12 | |
| | 9:5 | | 8:9(2) | | |
| | 10:14 | | 8:10 | | |
| | | 9:11 | 8:13 | | |

ይህ አይነቱ ሞዴል በተለይ ነቢያት የሚጠቀሙበት ነው፡፡ እግዚአብሔር በጊዜው ለኃጢአት ምላሽን ይሰጣል፤ ነገር ግን ልባቸውንና ክፉ መንገዳቸውን ለሚለውጡ ደግሞ የንስሐና የምህረት እድልም ይሰጣቸዋል የእግዚአብሔርም የመቤዥትና የተሃድሶ ዓላማም ተግባራዊ ይሆናል! እግዚአብሔርም የእርሱን ባህርይ የሚያሟይ ሰዎች አሉት፣ ፍጥረት የተፈጠረበት ዓላማም (የእግዚአብሔርና የሰው ልጆች ያላቸው ህብረት) ይሟላል፡፡

▣ *"ታውቃላችሁ"* ብዙውን ጊዜ "ማወቅ የሚለው ቃል የእብራይስጥ ድባብ ሲኖረው ይህም የግል ሕብረትን፣ የቀረበ ግንኙነትን የሚያመለክት ነው፤ ነገር ግን በዚህ ሥፍራ ላይ "በዚያን" *(hoti)* የሚል አመልካች ቅፅል ሲኖረው ግልፅ የሚያደርገውም የእውቀት ይዘቱን ነው፡፡ ይህ ቃል ማመን እንደሚለው ቃል ጣምራ ትርጉም አለው፡፡ ዮሐንስ ወንጌሉን ለመግለፅ የሚመርጣቸው ቃላት እንደነዚህ አይነቶቹን ነው፡፡ አማኞች ያውቁታል (ያምኑበታል) እንዲሁም ደግሞ ስለእርሱ እውነቱንም ያውቁታል (ያምኑበት ዘንድ)፡፡ በ2:23 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

▣ *"እኔ በአባቴ እንዳለሁ እናንተም በእኔ እንዳላችሁ፣ እኔም በእናንተ እንዳለሁ"* ዮሐንስ ብዙውን ጊዜ ትኩረት የሚሰጠው የኢየሱስንና የአብን አንድነት ላይ ነው (10:38፤ 14:10-11፤ 17:21-23)፡፡ ከዚህም ባሻገር ዮሐንስ አብና

ኢየሱስ በቅርበት እንደተጣመሩ ሁሉ ኢየሱስ እና ተከታዮቹም እንዲሁ የተቆራኙ መሆናቸውን ጨመሮ እውነቱን ያስረዳል (ዮሐ 17)!

14:21 **"ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም"** እነዚህ ሁለት የአሁን ጊዜ የሆኑ ከግል የሚፈጠሩ ቃላት ናቸው፡፡ *መታዘዝ አንገብጋቢ ጉዳይ ነው* (በቁ. 15 ላይ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ፡፡)፡፡ *መታዘዝ የእውነተኛ መለወጥ ማስረጃ ነው* (ቁ. 23)፡፡

*ሐዋርያት አይሁዳዊያን ስለነበሩ ብዙውን ጊዜ በፅሑፎቻቸው የሚጠቅሱት የሴሜቲክ ዘዬ ነበር፡፡ በማንኛውንም የአይሁድ ፀሎት መጀመሪያ ላይ የሚጠቀሙት በዘዳ* 6:4-5 *ላይ ያለውን በተለምዶ "›ሼማ› (Shema) የሚለውን ሲሆን የዚህም ትርጓሜ "ታደርገው ዘንድ ስማ" የሚል ነው! ይህ ነው እንግዲህ የዮሐንስ ማብራሪያ (ያዕ* 2:14-26)፡፡

▣ **"ራሴንም እገልጥለታለሁ"** ይህ ምናልባት ሊያመለክት የሚችለው (1) የድህረ-ትንሳኤ መልኩን (ሐዋ 10:40-41) ወይም (2) ክርስቶስን ይገልጥላቸው ዘንድ የመንፈስ ቅዱሱን መላክ ነው የቁ 26፤ ሮሜ 8:29፤ ገላ 4:19)፡፡ ኢየሱስ (1) አብን መወከሉን (2) ስለአብ መናገሩን (3) ስለ አብ መግለጡን የመነበትና አፅንኦት የሰጠበት ነበር፡፡ ለአማኞችም ኢየሱስ የተናገራቸው እነዚህ ስልጣንን የተሞሉ ቃላት በሐዋርያት ፀሐፊዎች ተመዝግበው መቀመጣቸው ሰለ እግዚአብሔርና ዓላማው የጠራ መረጃ ያገኙ ዘንድ ብቸኛው ምንጭ ነው፡፡ አማኞችም የኢየሱስ ስልጣን እና የቅዱሳት መፃህፍት (በትክክል የተተረጐሙት) ስልጣን የመጨረሻዎቹ እንደሆኑ ያረጋግጡ፡፡ ምክንያት፣ ልምምድ፣ እና ባህል ጠቃሚ ናቸው ይሁን እንጂ የመጨሻዎቹ አይደሉም፡፡

በመንፈስ እና በወልድ ሥራ መካከል መስማማት አለ፡፡ ጂ. ካምፑቤል እንደሚለው ከሁሉ የተሻለው የመንፈስ ስያሜ "ሌላው ኢየሱስ" የሚል ነው፡፡ በ14:16 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

14:22 በቁጥር 19 ላይ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ፡፡

▣ **"ይሁዳ (የአስቆሮቱ ያይደለ)"** ይህ ታዴዎስ ለሚለው ሌላው ስም ነበር (ማቴ 10:3፤ ማር 3:18)፡፡ በ1:45 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

14:23 **"የ … ቢኖር"** ይህ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ሲሆን ድርጊት ለመፈፀም እድል መኖሩን ይናገራል፡፡ ደቀመዛሙርት ለኢየሱስ ያላቸው ፍቅር የሚታየው እርስበራሳቸው ባላቸው ፍቅር ነው (ቁ. 15:21)፡፡

14:24 **"የምትሰሙትም"** በመልእክቱ ተቀባዮች አንፃር የለው ጥያቄ "የምተለሙትም" የሚለው ማንን የሚያመለክት ነው የሚል ነው፡፡ በሰዋሰው ተውላጠ ስሙ ያለው "የምትሰሙትም" በሚለው ውስጥ ነው (የአሁን ጊዜ ድርጊት ገላጭ እና አመልካች ግስ፣ የሁለተኛ መደብ ብዙ ቁጥር)፡፡ ሊያመለክት የሚችለውም፤

1. የኢየሱስን መልዕክት የሚቃወሙ የአለም ሰዎች
2. ኢየሱስ የተናገራቸው ቃላት ከአብ የተላኩ መሆናቸውን አመነው የተቀበሉትን ደቀመዛሙርት (ቁ. 10-11)፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 14÷25-31

[25]ከእናንተ ዘንድ ስኖር ይህን ነግሬአችኋለሁ [26]አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኳችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል። [27]ሰላምን እተውላችኋለሁ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም። ልባችሁ አይታወክ አይፍሩም። [28]እኔ እሄዳለሁ ወደ እናንተም እምጣለሁ እንዳልኋችሁ ሰማችሁ። የምትወዱኝስ ብትሆኑ ከእኔ አብ ይበልጣልና ወደ አብ በመሄዴ ደስ ባላችሁ ነበር። [29]ከሆነም በኋላ ታምኑ ዘንድ አሁን አስቀድሞ ሳይሆን ነግሬአችኋለሁ። [30]ከእንግዲህ ወዲህ ከእናንተ ጋር ብዙ አልናገረም የዚህ ግለም ገዥ ይመጣልና በእኔ ላይም አንዳች የለውም፤ [31]ነገር ግን አብን እንድወድ ዓለም ሊያውቅ አብም እንዳዘዘኝ እንዲሁ አደርጋለሁ፣ ተነሡ ከዚህ እንሂድ።

14:25 **"ይህን"** ይህ በላይኛው ድርብ የተካሄዱትን ትምህርቶች የሚያመለክት መሆን አለበት (ምዕ 13-17፣ ነገር ግን በቁጥር ተለይቶ በቃላት ተገልጿል፤ 15:11፤ 16:1፤ 6፡25፡33)፡፡

14:26 **"መንፈስ ቅዱስ"** ይህ ለስላሴ ሶስተኛው አካል የተሰጠው መጠሪያ በዮሐ 1:33 እና 20:22 ላይ ብቻ የተጠቀሰ ሲሆን በዚህ በዮሐንስ ወንጌልም ተጠቅሷል (በ1ኛ ዮሐ 2:20 ላይ ቅዱሱ የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡)፡፡ ይሁን እንጂ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ በሌሎች በርካታ ስሞችም ይጠራል (ጰራቅሊጦስ፣ የእውት መንፈስ፣ መንፈስ)፡፡

መንፈስን በስብዕና ቃላት የሚያመለክቱ በርካታ ምንባቦች በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይገኛሉ (ማር 3:29፤ ሉቃ 12:12፤ ዮሐ 14:26፤ 15:26፤ 16:7-15፤ ቀጥሎ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡)፡፡ መንፈስ ለሚለው ቃል የግሪኩ ቃል ግዑዛን በመጠቀሙ ምክንያት (14:17፤ ሮሜ 8:26) መንፈስን ለመጥቀስ ግዑዝ አመልካች ተውላጠ ስም የተጠቀሰባቸው በርካታ ጥቅሶች አሉ፡፡

ከዚህም ባሻገር ስለ ስላሴ ሃሳብ አንድ ነገር መናገር አስፈላጊ ነው፡፡ "ስላሴ" የሚለው መጠሪያ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም፤ ይሁን እንጂ የአንዱ እውነተኛ አምላክ ሦስት መገለጦች በበርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ላይ

ተጣምረው ይታያሉ (ቀጥሎ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡)፡፡ ኢየሱስ መለኮት እንዲሁም ደግመ መንፈስ የግል ከሆነ እንግዲህ ከሥነ-መለኮት አንፃር እንደ አንድ አምላክ አምላኪዎች (ዘዳ 6:4-6) የሦስት አንድነትን ለመቀበል እንገደዳለን ማለትም ቀጣይነት (ሂደታዊነት) የሌላቸው መገለጦች የሆኑ ነገር ግን ዘላለማዊ ስብእናዎች የሆኑ!

**ልዩ ርዕስ፡ ሥላሴ**

የሥላሴን ሦስት አካላት እንቅስቃሴ በአንድ ወጥ በሆነ አውደ ተመልከታቸው፡፡ ‹‹ስላሴ›› የሚለው መጠሪያ ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈጠረው በቱርቱስያን እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል አይደለም፡፡ ነገር ግን ሐሳቡ በጣም የተስፋፋ ነው፡፡

ሀ. ወንጌላት
1. ማቴ 3:16-17፤ 28:29 (እና ሌሎች ተመሳሳዮች)
2. ዮሐ 14:26

ለ. ሐዋርያት ሥራ - ሐዋ 2:32-33፤ 38-39

ሐ. ጳውሎስ
1. ሮሜ 1:4-5፤ 5:1፡5፤ 8:1-4፡8-10
2. 1ቆሮ 2:8-10፤ 12:4-6
3. 2ቆሮ 1:21: 13:14
4. ገላ 4:4-6
5. ኤፌ 1:3-14፣ 17፤ 2:18፤3:14-17፤ 4:4-6
6. 1ተሰ 1:2-5
7. 2ተሰ 2:13
8. ቲቶ 3:4-6

መ. ጴጥሮስ 1ጴጥ 1:2

ሠ. ይሁዳ ቁ. 20-21

በእግዚብሔር ውስጥ የብዙ ቁጥር መኖሩ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ፍንጭ አለ፡፡

ሀ. የብዙ ቁጥር ለእግዚአብሔር መጠቀሱ
1. "ኤሎሂም" የሚለው ስም ብዙ ቁጥሮችን አመልካች ነው፡፡ ግን ምን ጊዜም በእግዚአብሔር ሲጠቀም ነጠላ ግስን አመልካች ነው፡፡
2. "እኛ" በዘፍጥረት 1፡26-27፣ 3፡22፣ 11፡7

ለ. የእግዚአብሔር መልአክ መለኮትን በሚታይ መልኩ የወከለ ነበር
1. ዘፍ. 16፡7-13፣ 22፡11-15፣ 31፡11፣13፣ 48፤15-16
2. ዘፀ. 3፡2፣4፤ 13፡21፤ 14፡19
3. መሳፍንት 2፡1፣ 6፡2-23፤ 13፡3-22
4. ዘካሪያስ 3፡1-2

ሐ. እግዚአብሔር እና መንፈሱ የተለያዩ (ዘፍ1:1-2 መዝ 104:30፤ ኢሳ 63: 9-11፤ ሕዝ 37:13-14)

መ. እግዚአብሔር (ያህዌህ) እና መሲል (አዶናይ) የተለያዩ ናቸው መዝ 45:6-7፤ 110:1፤ ዘካ 2:8-11፤ 10:9-12

ሠ. መሲሑ እና መንፈስ የተያዩ ናቸው፤ ዘካ 12:10

ረ. ሦስቱም በኢሳ 48:16፤ 61:1 ላይ ተጠቅሰዋል፡፡

የኢየሱስ መለኮትነት እና የመንፈስ ስብእና አጥባቂ እና የአንድ አምላክ አምልኮ ተከታዮች ለነበሩት ለቀደሙት አማኞች ችግር የፈጠረባቸው ጉዳይ ነበር፡፡
1. ቱርቱስያን - ወልድ ከአብ እንደሚያንስ አስረዳ
2. ኦሪገን - የወልድን እና የመንፈስ መለኮታዊ ማንነት ዝቅ አደረገ
3. አርዮስ - የወልድን እና የመንፈስ መለኮትነት ካደ
4. ምጥሮኪያኒዝም - አንድ አምላክ ተከታታይነት ባው ሁኔታ እንደ አባት፣ ልጅ፣ እና መንፈስ እንደ ተገለጠ የሚያምን

ስላሴ በታሪክ ሁሉ በቅዱሳት መፃህፍት አማካኝነት ሃሳቡ ሲገለፅ የኖረ ጉዳይ ነው፡፡
1. የኢየሱስ መለኮትነት፣ ከአብ ጋር እኩል መሆኑ በ325 ዓ.ም በኒቅያ ጉባኤ ፀደቀ
2. የመንፈስ ሙሉ ስብእና እና መለኮትነት ከአብ እና ከወልድ ጋር እኩል መሆኑ በኮንስታንቲኖፕል ጉባኤ (381 ዓ.ም) ፀድቋል፡፡
3. የስላሴ አስተምህሮ የአውግስቲን ሥራ በሆነው ውስጥ *Deirॐitae* በሙላት ተገልጿል፡፡

እዚህ ላይ ግን እንቆቅል የሆነ ጉዳይ አለ፡፡ አዲስ ኪዳን ግን አንድ መለኮታዊ መንነት ያለው እና ሦስት ዘላለማዊ የስብእና መገለጦች እንዳሉት የሚያረጋግጥ ይመስላል፡፡

**"አብ በስሜ የሚልከው"** በቀደመች ቤተክርስቲያን (4ኛው ክ/ዘመን) ውስጥ መንፈስ ከአብ ነው (ዮሐ 3 :34፤፤ 14:16፤ 16:26) ወይስ ከወልድ ነው የሚሰርፀው (ዮሐ 15:26፤ 16:7፤ ሉቃ 24:49፤ ሐዋ 2:33) በሚል ከባድ ፀብ ነበር፡፡ በኢየሱስ እና በአትናቴዎስ መካከል የበረው የሥነ-መለኰታዊ ጉዳይ ክርክር በእግዚአብሔር አብ እና በወልድ ኢየሱስ መካከል ፍፁም እና ዘላለማዊ የሆነ እኩልነት እና መለኰትነትን የሚመለከት ነበር፡፡

▣ **"ሁሉን ያስተምሯችኋል"** ይህ ግልፅ ሊሆን ይገባል፡፡ መንፈስ ሁሉንም የእውቀት ገፅታወች ለአማኞች አያስተምርም ነገር ግን ስለ መንፈሳዊ እውነት በተለይም ደግሞ ከኢየሱስ ማንነት እና ሥራ ጋር በተያያዘ ወንጌልን ያስተምራል (16:13-14፤ 1ዮሐ 2:20-27)፡፡

**ልዩ ርዕስ ፡ የመንፈስ ስብእና /ማንነት**

በብሉይ ኪዳን ‹‹የእግዚአብሔር መንፈስ›› (ruach) የሚለው የያህዌን አላማ ያከናወነ ኃይል ነበር፡፡ ነገር ግን የግል ሰለመሆኑ ምንም አይነት ፍንጭ የለም (ማለትም፡ የብሉይኪዳን ‹‹ሞቴይዝም››)፡፡ ይሁን እንጂ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የመንፈስ ሙሉ ስብእናና ማንነት በማስረጃ የረጋገጠ ነው፡፡

1. ሲሰደብ ይችላል (ማቴ 12 :31፤ ማር 3:29)
2. ያስተምራል (ሉቃ 12:12፤ ዮሐ 14:26)
3. ይመሰክራል (ዮሐ 15:26)
4. ይመስሳል፤ ይመራል (ዮሐ 16:7-150
5. በ ‹‹ማንነት›› ተጠቅሷል (has፣ ኤፌ 1:14 )
6. ሊያዝን ይችላል (ኤፌ 4:30)
7. ሊጠፋ ይችላል (1ተሰ 5:19

ስለ ስላሴ የሚናገሩ ጥቅሶች ስለሦስት ስብእናዎች ይናገራሉ፡፡

1. ማቴ 28:19
2. 2 ቆሮ 13:14
3. 1 ጴጥ 1:12

መስፈስ የሚሰውም ከሰው ልጅ እንቅስቃሴ ጋር ተያይዟል፡፡

1. የሐዋ. 15፡28
2. ሮሜ. 8፡26
3. 1ቆሮ 12፡11
4. ኤፌ. 4፡30

በሐዋሪያት ስራ በመጀመሪያ ክፍሎች ውስጥ የመንፈስ አፅንኦት ተሰጥቶታል፡፡ ጴንጤቆስጤ የመንፈስ ቅዱስ ስራ መጀመሪያ አልነበረም፡፡ ግን አዲስ ምዕራፍ ነው፡፡ ኢየሱስ ሁልጊዜም መንፈስ ነበረው፡፡ ሉቃስ ቤተክርስቲያን ለአዲስ የአገልግሎት ጅማር እያዘጋጀ ነበር፡፡ አሁንም ቢሆን ኢየሱስ የእርሱ ትኩረት ነው፡፡ መንፈስ አሁንም ቢሆን አዋጭ መንገድ ነው፡፡ እንዲሁም የእግዚአብሔር ፍቅር ይቅርታ እና ተሐድሶ በአምሳሉ ሁሉ ለተፈጠሩ ለሰው ልጆች በሙሉ መደረግ ያለበት ግብ ነው፡፡

▣ *"እኔም የነገርኳችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል" የመንፈስ ዓላማዎች*

1. ሰዎችን ስለኃጢአታቸው መውቀስ
2. ሰዎችን ወደክርስቶስ ማምጣት
3. በክርስቶስ አካል ውስጥ ማጥመቅ
4. ክርስቶስን በልባችሁ ማኖር (17:17-15)
5. ኢየሱስ የነገራቸውን ነገር ሁሉ ማስታወስና ትርጉማቸውን በማብራራት በቅዱሳት መፃህፍት ውስጥ ይመዝገቡ ዘንድ ሐዋርያትን መርዳት (2:22፣ 15:26: 16:13)፡፡

ከትንሳኤው በኂላ ኢየሱስ ራሱ ለሐዋሪያት ብሉይ ኪዳን እንዴት ወደ እርሱ እንደሚያመለክት እና በእርሲም እንደተፈፀመ አስተምሯቸው ነበር፡፡ (ሉቃ 24:13)፡፡

14:27 **"ስለምን እተውላችኋለሁ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ"** የአማኞች ሰላም ከሁኔታዎች ጋር የማያያዝ ሳይሆን እርሱ በሰጠው ተስፋዎች እና በእርሱ ህልውና/መገኘት/ ላይ የተመሠረተ ነው (16:33፤ ፊል 4:7፤ ቆላ 3:15)፡፡

"ሰላም" የሚለው ቃል የተጠቀሰው ከሚታይ ጋር በእግዚአብሔር የሚደረግ ተሐድሶ እና ከግል ስሜት ጋር ደግሞ በተያያዘ በአስቸጋሪ ነገሮች /ሁኔታዎች/ ውስጥ ያለን ፀጥታ ወይም መረጋጋትን ያመለክታል፡፡ የአይሁድ ሠላምታ የሆነውን ሻሎም */Shalom/*ን የሚያንፀባርቅ ሲሆን ትርጓሜውም የችግሮች አለመኖር እና የደስታ ህልውናን ያሣያል (20:19፣21፣ 26፤ 3ዮሐ 14፤ ኤፌ 2፣ 14፤ ዘህል 6: 26፤ መዝ 29:11፤ ኢሳ 9:6)፡፡ ከዚህም ባሻገር ሠላም የአዲሱን ዘመን መምጣት ያበስራል፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ ክርስቲያን እና ሰላም**

*የግሪኩ ቃል የመጀመሪያው ትርጉም ‹‹ቀደም ሲል የፈረስን ነገር እንደገና አፅንቶ ማያያዝ›› የሚል ነው፡፡ አዲስ ኪዳን ስለሰላም የሚናገርባቸው ሦስት መንገዶች አሉ፤*

1. *በክርስቶስ አማካኝነት ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረን ሠላም የሚታየው ገጽታ* (*ቆላ* 1:20)
2. *ከእግዚአብሔር ጋር ያለኝ ትክክለኛ ግንኙነት ስሜታዊው ገፅ* (*ዮሐ* 14:27፣ 16: 33፤ *ፊል* 4:7)
3. *በክርስቶስ አማካይነት የሚያምኑትን አይሁድም ሆነ አህዛብ ወደ አንድ አካል እግዚአብሔር ማምጣቱ* (*ኤፌ* 2:4-17፤ *ቆላ* 3:15)፡፡

*አውማን እና ኒዳ*፣ *A translator's Handbook on Paul's letter to the Romans*፤ (*ገጽ* 92)፣ *ስለ ሰላም ጥሩ የሆነ ማብራሪያ ይሰጣል*፡፡

*"በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን" ሰላም የሚለው ቃል ሰፊ ትርጉም አለው፡፡ በመሠረቱ የሚገልፀው የአንድን ሰው ሕይወት አጠቃላይ ደህንነት ነው፤ በአይሁዳዊያን መካከል እንኳን እንደ ሰላምታ ዘይቤ የተለመደ ጉዳይ ነበር፡፡ ይህ ቃል እንዲህ ያለ ጥልቅ ትርጉም ስላለው በአይዑድ ዘንድ የመሲሑን ድነት ለመጥቀስ እንኳን ይጠቀሙበት ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ‹‹ከእግዚአብሔር ጋር በትክክለኛ ግንኙነት መሆን›› ከሚለው ቃል ጋር በተመሣሣይ ሁኔታ ይጠቀሳል፡፡ እዚህ ላይ የቃሉ ትርጉም የተጠቀሰበት እግዚአብሐር የሰውን ልጅ ከእርሱ ጋር ትክክክለኛ ህብረትን እንዲያደርግ ካለው ተነሣስነት በሰው ልጅ እና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን የተጣመመ/የተስማማ ግንኙነት ለመጥቀስ የታሰበ ይመስላል*፡፡

▣ **"እተውላችኋለሁ"** *ግራንት አስቦርን*፤ *The HermeNeutical Spiral* (*ገጽ* 21) *በሚለው መጽሐፉ የአንድን ቃል ትርጉም በመወሰን ላይ ለአውድ ቅድሚያ ሰለመስጠት በጣም ጥሩ የሆነ ማብራሪያ ይሰጣል*፡፡

**"ተገቢነት ያለው ዓውድ"**

*እንደ እውነቱ ከሆነ ተገቢነት ያለው አውድ በአተረጓጎም ሒደት ውስጥ ወሣኙ ጉዳይ ነው፡፡ ለክፍሌ ተማሪዎች ስናገር በግማሽ ልቡ ያንቀላፋ እና የምጠይቀውን ጥያቄ የማይሰማ ማንሣ ሰው ቢኖር እርሱ ወይመ እርሷ "ዓውድ" ብለው ቢመልሱ ትክክለኛ የመሆናቸው እድል ሃምሳ በመቶ ብቻ ነው፡፡ ቃሉ ራሱ በአንድ ጥቅስ ላይ ብዙ ተፅዕኖዎች ይኖራሉ፡፡ ይህንንም በስዕላዊ መልክ ስናስቀምጡው ከራሱ ከምንባቡ እየራቁ እንደሚሄዱ ተመሳሳይ መንሻ ያላቸው ብዙ ክቦች ማለት ነው፡፡*

*ወደ ማዕከላውው ነጥብ እየቀረብን በመጣን ቁጥር በምንባቡ ትርጉም ላይ ያለው ተፅዕኖ እየጨመረ ይሐዳል፡፡ ለምሳሌ የፅሑፉ አይነት የሚተረጉመው ሰው ንፅፅሮች እንዲለያቸው ይረዳዋል፣ ነገር ግን እነዚህ የተቀረው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በምንባቡ ላይ እንዳለው ተፅዕኖ የጐላ አይደለም፡፡ እኛ ለምሳለ የራዕዩን መጽሐፍ በራዕይ የተሞላ ብቻ አድርገን ስናስበው እንችል ይሆናል፣ ምንም እንኳን በዝምታው ጊዜ እና በሂለኒስቲክ ጊዜ የነበሩት ትንቢቶች (ራዕዮች) ጠቃሚ የሆኑ ንፅፅሮችን የሚሰጡ ቢሆንም ብዙዎች ምልክቶች የተወሰዱት ግን ከብሉይ ኪዳን ነው፡፡ በሌላ ሚዛን የአንድን ቃል ወይም ሐሳብ ትርጉም ለመወሰን በዙሪያው ያለው አውድ የመጨረሻው አስታራቂ (አስማሚ) ነው፡፡ ጳውሎስ አንድን ቃል በፊልጵስዮስ ምዕራፍ 1 ላይ እንደ ፊልጵስዮስ ምዕራፍ 2 መጥቀሱ ምንም አይነት ዋስትና የሚሰጥ አይደለም፡፡ ቋንቋ እንዲያው በዚህ መንገድ የሚሰራ አይደለም ምክንያቱም ማንኛዋም ቃል ብዙ ትርጉሞች ስላሉት እና አንድ ፀሐፊ ቀደም ሲል ቃሉን ከጠቀለበት ይልቅ አሁን የሚጠቀምበት ዓውድ ወሣኝ ስለሆነ ነው፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆንን በዮሐ 14:27 ላይ "a phiemi" ተብሎ የተጠቀሰው ነው፡፡ ይህም "ሰላምን እተውላችኋለሁ" ሲል በ16:28 ላይ ደግሞ "ዓለምን እተወዋለሁ" ይላል፡፡ አንዱን በሌላው ለመረትጐም ያስቸግረናል ምክንያቱም አጠቃቀማቸው በፍፁም የተለያዩ ነውና፡፡ በመጀመሪያው ጥቅስ ኢየሱስ አንድን ነገር ለቀደመዛሙርት ሲሰጣቸው በሁለተኛው ግን አንድን ነገር ከእነርሱ ይወስድባቸዋል (ራሱን!)፡፡ ይቅርታ "ለሚለው የተለመደው የቃሉ አጠቃቀም ከዚህ ባነሰ ሁኔታ ሊገፅም ይችላል (እንደ 1 ዮሐ 1:9)"፡፡ ሌሎች ምንባቦች የትርጉም ገደቡን ለመወሰን ሊረዱን ይችላሉ (ቃሉ የሚኖረውን የተለያየ አንደምታ)፤ ነገር ግን ትክክለኛውን ለማግኘት በዙሪያው ያለው አውድ ነው ሊረዳን የሚችለው (ገጽ 21)፡፡*

▣ **"ልባችሁ አይታወክ"** *ይህ የአሁን ጊዜ ተደርጐ ግስ ትዕዛዝ ሲሆን አሉታዊ ቦዝ አንቀፅን ያጣመረ ነው፤ ይህም በተለምዶ ያለው ትርጉም "በሂደት ላይ ያለን ድርጊት ማቆም የሚል ነው፡፡ የቁጥር* 1 *ድጋሚ ነው፡፡*

14:28 *"የምትወዱኝስ ብትሆኑ" ይህ ልክ እንደ ቁጥር* 7 *ሁለተኛ መደብ ሁታዊ ዓረፍተ ነገር ነው፤ "ከእውነታው የሚቃረን" ይባላል፡፡ ኢየሱስ ወደ አብ ቢሄድና መንፈስንም ቢልክላቸው የተሻለ ነው፤ ይሁን እንጂ እነርሱ በዚህን ጊዜ ይህን አልተረዱም፡፡*

▣ **"ከእኔ አብ ይበልጣልና"** *ይህ የወልድን እኩል አለመሆን ለማሳየት የተናገረ ሳይሆን ከሰው ልጆች ድነት ጋር በተያያዘ በስላሴ ውስጥ ያለውን አሠራር የሚያመለክት ንግግር ነው* (10:29-30)፡፡ *ይህ የወልድ ዝቅ ማለት ለጊዜው ነበር፤ የእግዚአብሔርን መገለጥና የመቤዠት አላማ ለመፈፀም በምድር ሳለ የተከናወነ ነበር* (17:4-5፣ *ፊል* 2:6-11)፡፡ *ይሁን እንጂ አብ ላኪ እንደ መሆኑ ቅድሚያ የተሰጠበት ትርጉም አለ* (13:16፤ 1*ቆሮ* 15:27-28፤ *ኤፌ* 1:3-14)፡፡

14:29 **"አሁን አስቀድሞ ሳይሆን ነግሬአችኋለሁ"** ይህም የሆነበት እመነታቸውን ለማጠንከር ነበር (13:19፣ 16:4)፡፡

14:30
NASB **"የዓለም ገዥ"**
NKJV፣ NRSV
TEV **"የዚህ ዓለም ገዥ"**
NJB **"የዚህ ዓለም አለቃ"**

ይህ የሚያመለክተው እንቅስቃሴ በዚህ ምድር ላይ የሆነውን ሰይጣንን ነው (12:31፣ 16:11፣ 2ቆሮ 4:4 "የዚህ ዓለም አምላክ"፣ ኤፌ 2:2 "በአየር ላይ የሚሠራው አለቃ")፡፡ ምናልባት የይሁዳን መውጣት (መካድ) እንደ ሰይጣን መምጣት ተመልክቶት የሆናል (13:27)፡፡ በ12:31 ላይ ልዩ ርዕስን ይመልከቱ፡፡

▣
NASB፤ NKJV **"በእኔ ውስጥ ምንም የለውም"**
NRSV፤ TEV፤
NJB **"በእኔ ላይ ምንም ስልጣን የለውም"**

ትርጉሙ ሰይጣን ምንም የክስ መሠረት የለውም፣ ምንም ስልጣን የለውም ወይም ከኢየሱስ ጋር የሚያመሳስለው ምንም ነገር የለውም (ዕብ 4:15)፡፡

1. ጀምስ ሞፋት "በእኔ ምንም ሥፍራ የለውም" ብሎ ተርጉሞታል፡፡
2. ዊልያም ኤፍ.ቤክ "በእኔ ላይ ምንም መብት የለውም"
3. ኒው ኢንግሊሽ ባይብል (ኤን.ኢ.ቢ) "በእኔ ላይ ምንም ስልጣን የለውም"
4. ዘ ትዌንቲዝ ሴንቸሪ ኒው ቴስታመንት "ከእኔ ጋር የሚያገናኘው አንዳች የለውም"

14:31 **"ዓለም ሲያውቅ"** ሰይጣን በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ያለ እና የሰውን ልጆችን ለመቤዥት ለእግዚአብሔር ዓላማ የሚሠራ ነው፡፡ የኤ.ቢ.ዳቪድሰንን *the theology of the Old TestameNt* (ገጽ 300-306)፡፡

▣ **"አብም እንዳዘዘኝ እንዲሁ አደርጋለሁ"** ኢየሱስ እንዲሞት የእግዚአብሔር ፈቃድ ነበር (ኢሳ 53:10 ሀ፣ለ፤ ማር 10:45፤ 2ቆሮ 5:21)፡፡ በምዕ 12:50 ላይ "ትዕዛዝ" የሚለው ቃል በዮሐንስ ፅሑፎች ያለው አጠቃቀም የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

▣ **"ተነሱ ከዚህ እንሒድ"** ይህ በመሐል ላይ የተጠቀሰ የአሁን ጊዜ ትዕዛዝ ነው፡፡ ይህ በጣም አስቸጋሪው ሐግ ነው፤ ምክንያቱም በማቴዎስ እኛ በማርቆስ ወንጌላት ውስጥ ይሁዳ እና የወታደር ጭፍሮች ኢየሱስን ለመያዝ ወደ ጌቴሴማኒ የአትክልት ሥፍራ ሲመጡ የተጠቀሰ በመሆኑ ነው፡፡ ነገር ግን በላይኛው ደርብ በተደረገው ንግግር (ምዕ 13-17) ውስጥ ለምን እንደተጠቀሰ የሚታወቅ ነገር የለም፡፡ ምናልባት ኢየሱስ የላይኛውን ደርብ ለቆ ወደ ጌቴሴማኒ እየሔደ በማስተማር ላይ ሊሆን ይችላል (18:1)፡፡

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ሊሆን የሚችል ማብራሪያ በመሆኑ ለምትወስደው የራስህ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ፡፡ እያንዳንዳችን ልንጓዝ የሚገባን ባለን መረዳት መጠን ነው፡፡ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጎም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣችሁ ናችሁ፡፡ ይህንን ጉዳይም በሚያብራራው ሰው ላይ ብቻ ልትተው አይገባም፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄከዎች የተሰጡት በመጽሐፍ አበይት ክፍሎች ላይ በጥሞና እንድታስብባቸው ነው፡፡ ጥያቄዎቹ ሐሳብን ለማነሣሣት እንጂ በራሳቸው ግልፅ ሆነው የቀረቡ አይደሉም፡፡

1. በቁጥር 1 መሠረት በጌይዝም፣ ዴይዝም እና በክርስትና መካከል ያለውን ልዩነት ግለፅ፡፡
2. በቁጥር 6 ላይ ለሚገኙት ሦስት ስሞች የብሉይኪዳን መነሻ ታሪካቸውን ግለፅ
3. አንድ ሰው በቁጥር 13 ላይ ብቻ ተመስርቶ የፀሎት ሥነ-መለኮት ሊመሠርት ይችላል
4. የመንፈስ ቅዱስ ዋናው ዓላማ ምንድነው (ለጠፉትም ሆነ ለዳኑት)
5. ሰይጣን በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ነው ?

# ዮሐንስ 15

## በተሻሻሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀጽ አከፋፈል

| UBS[4] | NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| ኢየሱ የወይን ግንድ ነው ግንድ | እውነተኛው የወይን ግንድ ግንድ | የአማኝ የሕይወት ዘይቤ | ኢየሱስ እውነተኛ የወይን | እውነተኛ የወይን |
| 15፡1-10 | 15፡1-8 | 15፡1-11 | 15፡1-4 | 15፡1-27 |
| | ፍቅርና ደስታ ተፈፀመ | | 15፡5-10 | |
| | 15፡9-17 | | | |
| 15፡11-17 | | | | |
| | | 15፡12-17 | | |
| የዓለም ጥላቻ | የዓለም ጥላቻ | | የዓለም ጥላቻ | ደቀ መዛሙርቱና ዓለም |
| | | | | 15፡18-16፡4ሀ |
| 15፡18-25 | 15፡18-25 | 15፡18-25 | 15፡18-25 | |
| | የሚመጣው ተቃውሞ | | | |
| 15፡26-16፡4ሀ | 15፡26-16፡4 | 15፡26-27 | 15፡26-16፡4ሀ | |

**ሦስተኛው የምንባብ ፅዳት (አነቀ 53 ይመልቱ)**
*በአንቀፅ አከፋፈል ደረጃ የመጀመሪያውን ፀሐፊ ዋና ሐሳብ መከተል*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ሊሆን የሚችል ማብራሪያ ሲሆን ይህ ማለት ለምትወስደው የራስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ። እያንዳንዳችን ባለን መረዳት መጠን ልንጓዝ ይገባናል። ስለዚህም አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጎም ሒደት ላይ ቅድሚያ የሚሰጣች ናቸው። ነገር ግን ይህንን ጉዳይ በሚያብራራው ሰው ላይ ብቻ መተው የለብህም።

ምዕራፉን በአንድ ቅፅት አንብበው፤ ርዕስ ጉዳዩን ለይተህ አውጣቸው። ያንተን አከፋፈል ከአምስቱ የተሻሻሉ ትርጉሞች ጋር አነፃፅራቸው። በአንቀፅ መከፋፈል በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት የሚደረግ ባይሆንም የአተረጓጎም እምብርት የሆነውን የመጀመሪያውን ፀሐፊ ዋና ሀሳብ ለማግኘት ግን ቁልፍ ነገር ነው። እያንዳንዱም አንቀጽ የሚወሳው ስለ አንድ ጉዳይ ብቻ ነው።

1. የመጀመሪያ አንቀጽ
2. ሁለተና አንቀጽ
3. ሶስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተ…

## ለዮሐንስ ወንጌል 15፡1-27 አውዳዊ መረጃዎች /ግንዛቤዎች

ሀ. ይህ አስደናቂነ አስቸጋሪ ምንባብ ነው፡፡ በአንድ በኩል ለአማኞች ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና ፍሬያማ እንዲሆኑ ማበረታችን ሲሰጥ በአንፃሩ ደግሞ ጠንከር ያሉ ማስጠንቀቂዎቸችም አሉት ሥነ መለኮታዊ ልማዶችን በዚህ ሥፍራ ለመወያየት አስቸጋሪ ቢሆንም እንኳ በጣም የምወደውን የመፅሐፍ ቅዱስ ኮሜንታተር የኤፍ ኤፍ ብሩስን ANswers to QuestioNs ከሚለው መጽሐፍ ልጥቀስ፤
"በዮሐንስ 15፡4, 6 ላይ" በእኔ ባትኖሩ ሲል ምን ማለት ነው?
"በዮሐንስ 15፡ 4, 6 ላይ "በእኔ ባትኖሩ" እና "ማንም በእኔ ባይኖር" ሲል ምን ማለቱ ነው? በክርስቶስ አለመኖር ይቻላል?
እንደነዚህ አይነት ምንባቦ በሃላቸው አስቸጋሪዎች አይደሉም፤ አስቸጋሪነቱ የሚመጣው የራሳችንን ምባብ ስናዘጋጅና ሌሎች ቅዱሳን መፃህፍትን ለስነ-መለኮታችን እንደ መሰረት አድርገን ከመጠቀም ፈንታ ከእኛ ሥ-መስኮት ጋር ለማስማማት ጥረት ስናደርግ ነው፡፡ ጌታ ይህን ሲናገር በነበረበት ወቅት በግፅ ምሳሌ የሚሆ እና በእርሱ መኖር ያልቻለ ሰው ነበር፡- እርሱን የካው የአስቆሮቱ ይሁዳ፡- ይሁዳ የተመረጠው እንደሌሎች አሥራ አንድ ጓደኞቹ ነበር (ሉቃ 6፡13፡ዮሐ 6፡70)፤ ከጌታ ጋር የነበራቸው ሕብረትም ለእርሱ በእኩል ደረጃ እንዳልጠቀመው ሁሉ ለእነርሱም የተለየ መብት አላመጣላቸውም፡፡ እስከመጨረሻው በእምነታቸው ስለመቆማቸው ስለቆሙ ቅዱሳን የሚያስተምሩት ግልፅ የሆኑት ምንባቦች የከዳተኝነትን አደገኝነት ከሚገልፁ እኩል ደረጃ ካላቸው ምንባቦች ሰበብ ተደርገው መቅረብ የለባቸውም (ገጽ 71-72)፡፡

ለ. በግሪክ ቋንቋ የኃላፊ ድርጊትን አመልካች የሆነው አንዱ የኃላፊ ጊዜ ግሥ አንድ ሰው ከሥነ-መለኮ አንፃር የአሁን ጊዜ አመልካች ግስን ሲጠብቅ በዚህ አውድ ውስጥ መገኘቱ አስገራሚ ክስተት ነው፡፡ ይህ የኃላፊ ድርጊትን አመልካች ግስ የአንድን ሕይወት ጠቅላላ ባለ መልኩ የሚያመለክት ይመስላል፡፡

ሐ. የአንቀፅ 15 የምዕራፍ 15 የአንቀፅ አከፋፈል /ክፍሎች አስተማማኝ አይደለም ልክ እንደ አንደኛ ዮሐንስ መልዕክት የዮሐንስ ወንጌል የተለያዩ ቀለማት ያሸበረቀ ንድፍን ይመስላል፡፡ የወንጌሉ ንድፎች በተደጋጋሚ የሚከሰቱ መሆናቸውን ማጤን ይቻላል፡፡

መ. "መኖር" (ሜኖ) የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ ለ112 ጊዜያት ያህል ተጠቅሷል፡፡ ከእነዚህም አርባዎች በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ሲገኙ ሃያ ስድስቱ ወይም በመልዕክቶች ውስጥ ተጠቃለዋል፡፡ ይህ ለዮሐንስ ወንጌል ዋነኛው ሥነ-መለኮታዊ ቃል ነው፡፡ በእርሱ መኖር እንችል ዘንድ ምዕራፍ 15 አይነተና የኢየሱስ ትዕዛዝ መገለጫ ቢሆንም ይህ ቀል በወንጌል ውስጥ ሰፊ ስፍራ አለው፡፡

1. ሕጉ ለዘለአለም ይኖራል (ማቴ 5፡17-18) ክርስቶስም ደግሞ እንዲሁ (12፡34)
2. በአገልጋይ ወይም በሎሌ በኩል ሳይሆን በልጅ በኩል የዕብራውያን መፅሐፍ ወደ አዲ የመገለጥ መንገድ ያመለክታል (ዕብ 1፡1-3፤ ዮሐ 8፡35)
3. ኢየሱስ ለዘለአለም የሚወን መብል (6፡29) እና ለዘላለም የሚኖር ፍሬ (12፡34) እንደሚሰጥ ይናገራል፡፡ ሁለቱም ተለዋጭ ዘይቤዎች የሚገልጡት ተመሣሣይ እውነትን ነው፤ ክርስቶስ እንደሚያፈልገን -(1) በመጀመሪ እና (2) በቀጣይነት (በሐይት) (6፡53፤15፡3)
4. መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስ ሲጠመቅ መንፈስ ሲወርድበትና በእርሱም ሲኖር ተመልክቶ ነበር (1፡32)፡፡

ሠ. በ1 ዮሐ 2፡10 ላይ "መኖር" የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

ረ. በቁጥር 11-16 ደቀመዛሙርት የኢየሱስ ደስታ ተስፋ ሲሰጣቸው በቁጥር 17-27 ላይ ደግሞ የኢየሱስ መከራ ተስፋ ሲሰጣቸው እናያለን፤ የመከራውም ዓውድ እስከ 16፡4ለ ድረስ የሚዘልቅ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ሁሉ እርሱ እንደ ወደዳቸው ሁሉ አማኞች ሁሉ እርስ በርሳቸው መዋደድ አለባቸው!

## የቃልና የሐረግ ጥናት

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 15፡1-11

[1]እውነተኛ የወይን ግድ እኔ ነኝ፤ ገበሬውም አባቴ ነው፡፡ [2]ፍሬ የማያፈራውን በእኔ ያለውን ቅንጫፍ ሁሉ ያስወግደዋል፤ ፍሬ የሚያፈራውንም ሁሉ አብዝቶ እንዲያፈራ ያጠራዋል፡፡ [3]እናንተ ስለ ነገርኳችሁ ቃል አሁን ንፁሐን ናችው፤ [4]በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ባይኖር ከራሱ ፍሬ ሊያፈራ እንዳይቻለው፤ እንዲሁ እናንተ ደግሞ በእኔ ባትኖሩ አትችሉም፡፡ [5]እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ፡፡ ያለ እኔ ምንም

**ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል። [6]በእኔ የማይኖር ቢሆን እንደቅርንጫፍ ወደ ውጭ ይጣላል፤ ይደርቅማል፤ እነርሱንም ሰብስበው ወደ እሳት ይጥሉዋቸውማል፥ [7]በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንችሁማል። [8]ብዙ ፍሬ ብታፈሩና ደቀ መዛሙርቴ ብትሆኑ በዚህ አባቴ ይከበራል። [9]አብ ንደወደደኝ እኔ ደግሞ ወደድኳችሁ በፍቅሬ ኑሩ። [10]እኔ የአባቴን ትእዛዝ እንደጠበቅሁ በፍቅሩም እንደምኖር ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ። [11]ደስታዬም በእናንተ እንዲሆን ደስታችሁም እንዲፈፀም ይህን ነግሬአችኋለሁ።**

**15:1 "እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ"** ይህ ኢየሱስ "እኔ" እያለ ከተናገራቸው ንግግሮ አንዱና የታወቀው ነው(4:26፤6:35:8:12:10:7:10:11:14:11:25፤14:6) በብሉይ ኪዳን የወይን ተክል የእስራኤል ምልክት ነበር(*መዝ* 80-16፤*ኢሳያ*:1-7፣ *ኤር* 2:21፡ *ሕዝ* 15:19:10፣ *ሙሴ* 10:1፤ *ማቴ* 21:33፤ *ማር* 12:1-12፤ሮሜ 11:17) *እነዚም ምሳሌዎ* አሉታዊ ስሜት አላቸው የብብ(ኪ) ኢየሱስ እውነተኛው እስራኤላዊ ነበር (ኢሣ 53)። ልክ ሐዋርያው ጳውሎስ የክርስቶስ አካል የክርስቶ ሙሽዕ እና የእግዚአብሔር ህንፃ የሚሉትን ዜቤዎች ለቤተክርስትያን እንደተጠቀሙ ሁሉ ዮሐንስም ወይንን ተጠቀሟል። ይህም እውነት የሚያመለክተው ቤተክርስቲያን እውነተኛ ወይን ከሆው ከኢየሱስ ጋር ካላት ሕብረት የተነሣ እውነተኛዋ እስራኤል መሆኑን ነው(*ገላ* 6:16 1ጴጥ 2:5:9 *ራዕ* 1፤6)። በ 6:55 እና 17:3 ላይ ልዩ ርዕስ የሚለውን ተመልከት፤ በ8:12 ያለውንም ማስታወሻ ተመልክት

*አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎ ደግሞ በላይኛው አርብ ተካሄደ የነበረው የኢየሱስ ትምህርት በ14:31 ላ "ተነሡ። ከዚህ እንደሂድ የሚለው ላይ ያበቃል ብው ይናገራሉ። እንዲ ከሆነ እንዲህ፣ ምዕራፍ 15-17ን ኢሱስ ያስተማረው ወደ ጌቴሴማኒ ይጓዙ በነበረበት ወቅት ነበር ማለት ነው። ሌላው ደግሞ የ "ወይን" አምላክ ምናልባት የተወሰደው ኢየሱስና አሥራ አንዱ ደቀመዛሙርት በዚያ ምሽት በቤተመቅደሱ ሕንፃ አጠገብ ሲያልፍ በነበረበት ወቅት በቤተመቅደሱ ላይ ከነበሩ ወርቃማ ወይራዎች ነበር የሚል አመለካከት አለ።*

▣ **"ገበሬውም አባቴ ነው"** *አሁንም ኢየሱስ ከአባቱ ጋር ያለውን የጠበቀ ግኑኝነትና ለአባቱ ፈቃድ የሚገዛ መሆኑን አስረግጦ ይናገራል።*

**15:2 "ፍሬ የማያፈራውን በእኔ ያለውን ቅርንጫፍ ሁሉ ያስወግዳዋል"** *ይህ የአሁን ተደራእ ቦዝ አንቀፅ በዚህ ግሥ ውስጥ ሁለት ጊዜ ይታል ፍሬ ማፍራት የመብቀል ሂደት ሳይሆን የጽናት ማረጋገጫ ነው* (*ማቴ* 9:16 :20:13:18:21:18-22፣ *ሉቃ* 6:43-45)። *የዚህ ክፍል ዓውድ የሚስገነዝበው ኢየሱስ እየተናገረ የነበረው* (1) *ስለ ይሁዳ መክዳት* (*ቁ* 6፣13-:10፣17፣120 *ወይም* (2) *ስለ ሐሰተና ደቀመዛሙርት* (2 , 23-25:8:30-43፤ 1ዮ 2:19 2ጴጥ2)። *በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የእምነት ደረጃዎች ይታያሉ*።

▣ **"ያጠራዋል"** *ይህ ቃል በቃል "መንፃት" ማለት ነው። ቃሉ የወይን ትሎችን ማጥራት ማለት እሳቤ ፊሎ ተጠቅሞታል* (*BDBD* 386)። *ይህም በአዲስ ኪዳን ብቻ የሚገኝ ነው። ጣምራ ትርጉሞችን ስለያዘ በዮሐንስ ጥቅም ላይ ውሏል* (*ማጥራት እና ማንፃት ቁ*.3፣ 13:10)። *ይህ የአሁን ጊዜ ድርጊት ገላጭን የአሁን ጊዜ አድራጊ ግስን አመልካች ነው። መከራ በሸማኞች ሕይወት ውስጥ ዓላማ አለው* (*ቁ*. 17-22)። *ፍሬ የማፍራት አቅምን ከፍ ያደርጋል፣ አስመሳይነትን ያጋልጣል፣ በእግዚአብሔር እንዲታመኑ ያደርጋቸዋል* (*ማቴ* 13:20-23፣ *ሮሜ* 8:17፣ 1ጴጥ 4:12-16)። *ይህንን አስቸጋሪ እውነት ለመረዳት እነዚህን መፃህፍት ያጢኗቸው/ ይመልከቷቸው፤* (1) *PriNiciples of spiritual Growth by miles StaNford* (2) *The ChristiaN secret of a floppy lofe by HaNNa with all smith.*

*ከምዕራፍ 13-17 ድረስ ያሉት ዓውዳዊ ውህደት ስላላቸው ይህንን የማንፃት ጉዳይ በምዕራፍ 13 ጋር ካለው እግርን ከማጠብ ጋር ማዛመድ የሚቻል ነው። ደቀመዛሙርቱ አንድ ጊዜ የተጠቡ* (*የዳኑ*) *ቢሆንም እግሮቻቸው መታጠብ ያስፈልጋቸው ነበር*(*የማያቋርጥ ይቅርታን ማግኘት ነበረባቸው*)። *በ1ና ዮሐንስ 1:9 ላይ የሚገኘው የአሁን ጊዜ አድራጊ ግሥ ይህን የሚያረጋግጥ ይመስላል። በክርስቶስ "ለመኖር" የሚያስፈልገው መታዘዝ ብቻ አይደለም፣ የማያቋርጥ ንስሐም ጭምር እንጂ!*

*መከራ በአንድ አማኝ ውስጥ ያለው ዓላማ ብዙ አቅጣጫዎች አሉት፤*

1. *ክርስቶስን ወደምስል ያሳድጋል* (*ዕብ* 5:8)
2. *ለኃጢያት ጊዜያዊ ቅጣት*
3. *በወደቀው ዓላማ ውስጥ ሕይወትን ለማቅለል*

*የእግዚአብሔር ዓላማ ለማወቅ ሁልጊዜም አስቸጋሪ ነው፤ ነገር ግን አንደኛው ሁልጊዜ ሲሆን የሚችል ውጤት ነው።*

**15:3 "አሁን ንፁሐን ናችሁ"** *በቁጥር 2 ላይ "ያጠራዋል"* (*ካታይሮ*) *የሚለው ቃል "ያነፃዋል"* (*ካታሮስ*) *ከሚለው የግሪኩ ቃል ጋር ምንጫቸው ተመሳሳይ ነው። ይህ ሙሉው ዓውድ የሚጠቃልለው /የማይዘው ስለ እውነተኛ ደቀመዛሙርት ማረጋገጫዎ ነው። "አሁን" የሚለው ቃል በግሪክ ጥቅስ ጉልቶ የተጠቀሰ ሲሆን ይህም የሚያሣየው የተቀሩ አሥራ አንዱ ደቀመዛሙርት በክርስቶ ዘንድ ያላቸውን ቦ ዋስትናን ና የሰጠ መሆኑን ነው* (*በ*13:10 *ላይ ስለ አስቆሮቱ ይሁዳ የተጠቀሰው ተመሳሳይ ቃል ጋር ምንጩ ሲነግር*)።

▣ **"ስለነገርኳችሁ ቃል አሁን"** (17:17፤ ኤፌ 5:26፣ 1ጴጥ 1:23)።

15፣4

| | |
|---|---|
| NASB, NKJV | "በእኔ ኑሩ፣ እኔም በእናንተ" |
| NRSV | "ከእኔ ኑሩ፣ እኔም በእናንተ እንደምኖር" |
| TEV | "ከእኔ ጋር በመተባበር ኑር፤ እኔም በእናንተ ውስጥ በመተባበር እኖራለሁ። |
| NJB | "በእኔ ሁኑ፣ እኔም በእናንተ እሆናለሁ" |

ይህ የብዙ ቁጥር ትዕዛዝ አዘል አድርጎ ግሥ ነው (ዮሐ 6-56፣ 1ዮሐ 2:6)። ዋናው ሰዋሰዋዊ ጥያቄ ግን ሁለተኛው ሐረግ ገላጭ ወይም ንፅፅር መሆን አለመሆኑ ነው። ብዙ ጊዜ በዚህ ምንባብ ላይ ስለ እውነተኛው የእግዚአብሔር ሰው በመከራ ውስጥ መጽናት ሥነ መለኮታዊ ዶክትሪን ትኩረት የተሰጠበት ነው (ቁ. 4፣ 5፣ 6፣ 7 ፣ 9፣ 10፣ 14- ማር 13:13፣ 1ቆሮ 15:2፣ ገላ 6:9 ፣ ራዕ 2:7፣ 11፣ 17፣26፣3:5፣ 12፤21: 21:7፣ በምዕ 8:31 ላይ ልዩ ርዕስን ይመልከቱ።)። እውነተኛ ጽናት ምንግዜም የመጀመሪያም ቀጣይነት ያለው ምላሽ ነው። ይህ ሥነ መለኮታዊ እውነት በዓላችን ድኔታችንን ለማረጋገጥ ባለን ጉጉት ብዙውን ጊዜ ቻል የሚባል ነው። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊው ዋስትና ብዙውን ጊዜ የሚይዘው፤

1. በእምነታችን ፅናት
2. በንስሐ የህይወት አኗኗራችን
3. ቀጣይነት ባለው መታዘዝ (ያዕቆብ እና 1ኛ ዮሐንስ)
4. ፍሬ በማፍራት (ማቴ 13:23)

በ1ኛ ዮሐንስ 2:10 ላይ "መኖር" የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።

▣ **"ከራሱ ፍሬ ሊያፈራ እንዳይችለው"** ይህ የሚያሳየው በቅድሚ የመለኰት እርዳታ አስፈላጊነትን ነው። "ፍሬ" ለሚለው በቁ 5 ላይ የተሰጠውን ማስታወሻ ይመልከቱ።

▣ **"በወይኑ ግንድ ባይኖር... እናንተ ደግሞ በእኔ ባትኖሩ"** እነዚህ ድርጊት ለመፈፀም አቅም መኖርን የሚያሳዩ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ አረፍተነገሮ ናቸው። የእኛ መንፈሳዊ ስኬት የተያያዘው ከኢሱስ ጋር ባለን ግኑኙነት ነው።

**15:5 "በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ እደርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል"** ይህ የአሁን ጊዜ ድርጊ ፍፃሜ ቦዝ አንቀፅ የአሁን ጊዜ ደርጊት ፈፃሚ አመልች የሚከተለው ነው፡ የማያቋርጠው ሕብረት (የግል የእምነት ሕብረት) ለማያቋርጠው ፍሬያማነት ምንጭ ነው። ፍሬ የአማኞችን አመለካከቶችን እንዲሁም ድርጊቶችን ሊያመለክት ይችላል (ማቴ 7:15-23፤ ገላ 5:22-23፡ 1ቆሮንቶ 13)። አማኞች በክርስቶ የሚኖሩ ከሆነ ስኬታማና ዘለቄታ ያለው የፍሬያማነት ተስፋ ተጋብቶባዋል (ቁ 16)።

▣ **"ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና"** ይህ ጠንካራ የሆ ጥምር አሉታዊ አነጋገር ነው። የህ በቁ5 እና በፊል 4:13 ላይ ለተጠቀሱ አዎንታዊ ንግግር ተቃራኒው ንግግር ነው።

**15:6 "በእኔ የማይኖር ቢሆ እንደቅርንጫፍ ወደ ውጭ ይጣላል"** ይህ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ አረፍተ ነገር ነው። የወይን እንጨት ለማንኛውም የቤት ውስጥ አገልግሎት (ለማገይነት) የማይጠቀም ነበር ምክንያቱመ በፍጥነት የሚነድን ስለሚሞቅም ነበር (ሕዝ 15)። ይህም ይሁዳን ምናልባትም እስራኤልን ለመግለጥ የታሰበ ይመስላል። ይህ ባይሆን እንግዲህ እውነተኛ ያልሆነ እምነትን ለማመልከት በምንአልባት(ማቴ 13:41-42 እና 1ዮሐንስ 2:19 ልዩ ርዕስ የሚለውን በ17:12 ላይ ይመልከቱ።)።

ይህ በእርግጥ ሥነ-ፍፃሜያዊ ሥነ-መለኮት ነው፡ አንድ ቀን ወደፊት "የማሰባሰብ ቀን እና "የማቃጠል ቀን" ይኖራል። እንዴት እንደምንኖር (ኑሮአችን) የሚያሣየው የሕይወታችን ምንጭ ነው። (እግዚአብሔር ወይም ሰይጣን)። በፍሬያቸው ታውቀዋላችሁ ታውቋቸዋላችሁ ይላልና (ማቴ ጋር ገላ 6:7)።

▣ **"እሳት"** ቀጥሎ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።

**ልዩ ርዕስ: እሳት**

እሳት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስለት አዎንታዊ እና አሉታዊ ትርጉሞች አሉት

*ሀ. አዎንታዊ*

1. ያሞቃል(ኢሳ 44:15፤ዮሐ 18:18)
2. ያበራል (ኢሳ 50:11 ማቴ 25-1-13)
3. ያበስላል (ዘፀ 12:8 ኢሳያስ:15-16፣ ዮሐ21:9)
4. ያጠራል (ዚህ 31:22-23፣ ምሳ 17:3 ኢሳ 1:25፣ 6÷6-8አ ኤር 6:29 ሚል 3:2–3)
5. ቅድስናን (ዘፍ15:17 ዘፀ 3:2፣ 19:18 ሕዝ 1:27 ዕብ 12:29)
6. የእግዚአብሔርን ኃይል መስጠት (ሐዋ 2:3)
7. ጥበቃት (ዘካ 2:5)

ለ. አሉታዊ
1. *ያቃጥላል* (ኢያሱ 6:24፤8-8፤11÷11፣ ማቴ 22:27)
2. *ያጠፋል* (ዘፍ 19:24፣ ዘሌ 10:1-2)
3. ቁጣ (ዘ.ህ 21:28፣ ኢሳ 10:16 ዘካ 12:6)
4. *ቅጣት* (ዘፍ 38:24 ዘሌ 20:14፤21:9 ኢያሱ 7:15)
5. *ሐሰት ሥነ-ፍፃሜዊ ምልክት* (ራዕ 13:13)

ሐ. እግዚአብሔር በኃጢያት ላይ ያለፈ ቁጣ በእሳት ዘይቤያዊ አነጋገር ተገልጧል
1. ቁጣው ይነዳል (ወሴ 8:5 ሰፎ 3-8)
2. እሳትን ያፈሳል (ናሆ 1:6)
3. ዘላለማዊ እሳት (ኤር 15-4፤ 17:4)
4. የመጨረሻው ዘመን ፍርድ (ማቴ 3:10፤ 13:40 ዮሐ 15:6 2ተሰ 1:7 2ጴጥ 3:7-10 ፣ ራዕ 8:7÷16:8)።

መ. እንደሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ተምሳሌቶች (እርሾ፡ አንበሣ) እንደ አውዱ እሳት በረከትም እርግማንም ሊሆን ይችላል።

15:7 "በእኔ ብትኖሩ *ቃሎቼም* በእናንተ ቢኖሩ" ይህ ድርጊትን ለመፈፀም *ዕድል* መኖን የሚያሣይ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ አረፍተ ነገር ነው። ፀሎት በቅድስት የሚመስል አይደለም፡ ኢሱስ አዚህ ላይ ዘይቤያዊ አነጋገሩነ በእርሱ ከመኖር በቃ ወደመኖር ይቀይረዋል። ኢየሱስ አብን ይገልጣል እንዲሁም ደግሞ ትምህር፤ ሁለቱም ተለዋዋጭ የመገለጥ ምንጮች ናቸው። ወንጌል ደግሞ ሰውም መልዕክትም ነው።

▣ **"የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል"** ይህ በኃላፊ ጊዜ የተነገረ ትዕዛዝ አዘል አድራጊ ግሥ ነው(ቁ-16)። ይህ ሐረግ ሥህተትን ለማረም ትክክል ባልሆነ ሁኔታ የተፃፈ ጥቅስ ነው። ሁሉንም የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ስትራልግ ጥንቃቄ አድርግ፤ እንዲሁም ደግሞ የተለዩ ጥቅሶች ላይ ብቻ ትኩረት አታድርግ (14:13 ላይ ማስታወሻ)። በ1ዮሐንስ 3:22 ላይ ፀሎት ያልተገደበ ነገር ግን የተገደበ የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ)።

**15:8 "አባቴ ይከበራል"** የአማኞች በህይወታቸው ክርስቶን መምሰል እግዚአብሔርን ስም ክብሩም ሌላ እውነተኛ ደቀመዛሙርት መሆናቸውን ይመሠክራል። በዮሐንስ 13:31-32፣ 14:13፤ 11:4 እና ማቴ 9:8 — 15:31 አብ በወልድ ሥራ እነደከበረ ስታይ አሁን ደግሞ በአማኙ ሥራ ይከበራል (ማቴ 5:16)። በም1:14 ላይ የተሰጠውን ማስታወሻ ይመልከቱ።ቱ
▣

| | |
|---|---|
| NASB | **"ደቀመዛሙርት ብትሆኑ"** |
| NKJV | **"ስለዚህ ደቀመዛሙርት ትሆናላችሁ"** |
| NRSV, TEV | **"ደቀመዛሙርት ብትሆኑ"** |
| NJB | **"ደቀመዛሙርት ብትሆኑ"** |
| REB | **"ስለዚህ ደቀመዛሙርት ሁኑ"** |
| NIV, Good Speed | **"ራሳችሁን ደቀመዛሙት እንደሆናችሁ ብታሳዩ"** |
| NET Bible | **"ደቀመዛሙርት መሆናችሁን ብታሣዩ"** |
| JB | **"ስለዚህ ደቀመዛሙርት ትሆናላችሁ"** |

ልዩነቱ ሊፈጠር ይችላል በግሱ ላይ ካለው የጊዜ አመልካች ልዩነት ነው።
1. ሁኔታ ገላጭ የግሥ አይነት *Mss* P66: *B — D - L* (ምንጮች)
2. ወደፊ የሚሆ አመልካች *Mss N.A* (ምንጮች)

የአማኞች ሕይወት የሚገልጠው (ፍሬ) ማንነታቸውን ነው፡ የግሱ ጊዜ አመልካች የተለወጠና በፍቅር፣ በመታዘዝና በአገልግሎ የተለወጠ ህይወት ያህል በእምነት አስፈላጊ ጉይ አይደለም። እንግዲህ እነዚህ ናቸው የእውነተና አማኝ መለያዎች፡ የዳንነው በፍቅራችን በመታዘዛችን እና በአገልግሎታችን አይደለም (ኤፌ2:8:9) ነገር ግን እነዚህ አማኞች ለመሆናችን ማስረጃዎች ናቸው እንጂ (ኤፌ 2:10)።

"ደቀመዛሙር" የሚለው ቃል በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የተጠቀሰው የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርጉና የእርሱን ባህሪይ የሚያንፀባርቁ እውነተና አማኞችንና ተከታዮችን ለማመልከት ነው። ዮሐንስ "በቤተክርስትያን" (ኤክሌሽያ) የሚለውን ቃል አንድም ጊዜ አይጠቀምም፤ ሰለዚህ "ደቀመዛሙርት" የሚለውን ቃል ክርስትያናዊ ህብረትንና መሰባሰቦችን ለማመላከት ነው። ደቀመዝሙርነት በኦሮጌው ዓለም ውስጥ በየዕለቱ የሚኖር አዲስ ሕይወት ነው። ይህ ሕይወት ፍቅርን፣ ብርሐንን፣ መተዘዝን እንዲሁም ማገልገልን በበላይነት መለያ ባህሪው ያደረገ ነው፡ በዚህም ሌሎች የኢየሱስ ደቀመዛሙርት እንደሆኑ ያውቋቸዋል።

**15፡9 “አብ እንደወደደኝ እኔ ደግሞ ወደድኳችሁ”** ይህ ፍቅርን የተጎነፀ የኅብረት ሠንሰለት የእግዚአብሔርን ቤተሰብ ያስረዳል አብ ወልድን ይወድዳል ወልድም ተከታዮቹን ተከታታዮቹም እርስበርሳቸው።

▣ **“በፍቅሬ ኑሩ”** ይህ ድርጊት ገላጭ ትዕዛዛዊ አረፍተነገር ነው። አማኞች እንዲኖሩ የታዘዙት

1. በፀሎት (ቁ. 7:14-14)
2. በመታዘዝ (ቁ-10፣20፣14፣15፣21፣23፣24)
3. በደስታ (ቁ.11)
4. በፍቅር (ቁ 12፣14፡21፤ 22፤24)

እነዚህ ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን የግል ግኑኝነት የሚያሳይ ማረጋገጫዎ ናቸው። በ1 ዮሐንስ 2፡10 ላይ መኖር የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።

**15፡10 “ትዕዛዜን ብትጠብቁ”** ይህ ድርጊትን ለመፈፀም እድል መኖሩን የሚያሣይ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ አረፍተ ነገር ነው። መታዘዝ የእውነተኛ ደቀመዝሙርነት ማስረጃ ነው (8፡3114፡15-21:23-24 ሉቃ 6፡46)። ኢየሱስ ይህን የተጠቀመው ለአባቱ ታዛዥ መሆኑን ለማሣየት በምሣሌነት ነበር።

▣ **“በፍቅሬ”** ይህ ፍቅር ለሚለው የግሪኩ ቃል (አጋዌ) በተለየ ሁኔታ ቤተክርስትን መጠቀም አስከጀመረችበት ጊዜ ጥቃቶቹም ሆነ ብዙሀኑ በሚጠቀምበት የግሪክ ሥነ-ፅሑፍ ብዙም ጥቅም ላይ አልዋለም ነበር። ከዚያም ይህ ቃል ከራሥ ይልቅ ለሌሎች እንደሚኖር፣ መሥዋዕትነት ያለበት፤ ታማኝ እና በድረጊት የሚገለጥ ፍቅርን ለመግለጥ ጥቅም ላይ መዋል ጀመረ። ፍቅር ድርጊት እንጂ ስሜት አይደለም (3፡16)። የአዲስ ኪዳኑ ቃል አጋፔ ከሥነ-መለኮት አንፃር ሄሶድ (*hesed*) ከሚለው የብሉይ ኪዳኑ ቃል ጋር ተመሳሳይነት ሲኖራቸው ይህም የቃል ኪዳን ፍቅርን ወይም ታማኝነትን ያሣያል።

▣ **“እኔ የአባቴን ትዕዛዝ እንደጠበቅሁ”** ይህ ደርጊት መጠናቀቁን የሚያመለክት ነው። ልክ ኢየሱስ ከአብ ጋር እንደሚዛመድ ሁሉ አማኞችም ከእርሱ ጋር ሊዛመዱ የግድ ነው። በአማኞች መካከል ሊታይ የሚገባ ሐብረት በአብና በውል መካከልም ህብረት አለ (14፡3)።

**15፡11 “ደስታችሁም እንዲፈፀም”** አማኞች የኢየሱስ ሊኖራቸው ይገባል (17፡13)። ደስታ ሌላው የደቀመዝሙርነት ማስረጃ ነው (15፡11[ሁለት ጊዜ] 16፡20፡21፡22፡24፣ 17፡13)። በዚህ ዓለም ላይ ሕመምና ችግር ሲኖሩ በክርስቶስ ግደ ደስታ አለ፤ ሙሉ ደስታ፤ የእርሱ የሆነ ደስታ።

> የNIDOTTE ማብራሪያ ቅፅ 2፣ ገጽ 741 ላይ በዮሐንስ ፅሑፎች ላይ “ደስታ” እና “እንዲፈፀም” የሚሉት ቃላት እንዴት በሥራ ላይ እንዲዋሉ ጥሩ ማብራሪያን ይሰጣል።
>
> “በዮሐንስ ወንጌል እና በዮሐንስ መልዕክቶች ውስጥ በሁለት ቃላት መካከል ብዙ ጊዜ በተደጋጋሚ ጥምረት ይታያል፡- ደስታ (ቻሪ) እንደ ባለቤት እና Plero (ፕሌሮ) የሚለው እንደ ተደርጎ ግሥ፤ ይህ ደስታ የኢየሱስ ደስታ ሲሆ (ዮሐ 15፡11፡17፡13) ሊመጣ የቻለውም በእርሱ መምጣት (3፡29)፣ በቃ (16፡16፡20) እንዲሁም ወደ ደቀመዛሙርቱ (15፡11፡17፡13) በመመለሱ (16፡22) ጭምር ነው። ደቀመዛሙርት ከኢሱስ ጋር በሚያደርጉት የእምነት ሕይወት ጉዞ ልባቸውን የሚሞላውን ሐዘን የህ የኢየሱስ ደስታ ይተካዋል (16፡16፡20)። በመሆኑም የኢየሱስ ደስታ የእነርሱ ደስታ ይሆናል (15፡11፡16፡24)። 1ዮሐ 1፡4)። ይህም ደስታ ደቀመዛሙርት ከኢየሱስ ጋር በሚያደርጉት ጉዞ የሚታወቅ በመሆኑ ፍፁምነትም ያለው ግሡ የተመሠረተው ወይም የሚያመለክተው ይህንን ደስታ የሚፈፅመው እግዚአብሔር ራሱ መሆኑን ነው።”

---

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 15፡12፡17)

**12 እኔ እንደወደድኳችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትዕዛዜ ይህች ናት። 13 ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም። 14 እኔ ያዘዝኳቸሁን ሁሉ ብታደርጉ እናንተ ወዳጆቼ ናችሁ። 15 ከእንግዲህ ወደህ ባሮች አደላችሁም፤ ባርያ ጌታው የሚያደርገውን አያውቅምና ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ፡ ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ለእናንተ አስታውቃአችኋለሁና። 16 እኔ መርጥኳቸሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም አብም በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ እንዲሰጣችሁ፡ ስትሔዱና ፍሬ ስታፈሩ ፍሬ አችሁም ሲኖር ሾም኿ችሁ። 17 እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ ይህን አዛችኋለሁ።**

---

**15፡12 “ትዕዛዜ ይህች ናት”** ኢየሱስ ይህን መልዕክት ብዙ ጊዜ ደጋግሞታል (13፡34፡15፡17፣ 1ዮሐ 3፡11 :23:4፡ 7-8 — 11-12 : 19-21 ፣ 2ዮሐ 2፡5)።

▣ **“እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ”** ይህ የአሁን ጊዜ ትዕዛዛዊ ድርጊ ገላጭ ግሥ፤ የማያቋርጥ ትዕዛዝ ነው። ፍቅር የመንፈስ ፍሬ ነው (ገላ 5፡22)፤ ፍቅር ስሜት ሳይሆን ድርጊት ነው፤ የሚገለጠውም በተግባራዊ ቃላት ነው (ገላ 5፡22-23፤ 1ቆሮ 13)።

▣ **"እኔ እንደወደድኳችሁ"** ይህ በኃላፊ ጊዜ የድርጊት መፈፀምን አመልካች ግሥ ነው፡፡ ይህ መስቀሉን ለመግለፅ የተጠቀሠበት ዜይቤያዊ አገላለፅ ሳይሆ አይቀርም (ቁ.13)፡፡ ሌላው ደግሞ አማኞች ለሌሎች ያሳዩ ዘንድ ራሱን ለየት ባለ ሁኔታ በመሥጠት ፍቅሩን ያሳየበት ነበር (የቆሮ 5፡14-15፡ ገላ2፡20 ፣ 1ዮሐ 3፡16)፡፡

**15፡13 "ነፍሱን ስለወዳጆቹ ከመስጠት"** ይህ የሚያመለክተው በምትክነት የተፈፀመውን የኢሱስን የማዳን ሥራውን ነው (10፡11፡15፡17፣18፣ማር 10፡45 ሮሜ 5፡7-8 2ቆሮ 5፡21፤ ኢሳ 53)፡፡ ይህ ነው እንግዲህ በተግባር የታየ ፍቅር፡ ይህንን ነው ደቀመዛሙርት ተግባራዊ እንዲያደርጉት የተጠሩበት ዓላማ (1ዮሐ 3፡16)፡፡

**15፡14 "እናንተ ወዳጆቼ ናችሁ"** ይህ የግሪኩ (ፊሎስ) የተሰኘው ስም ነው፤ ይህም ብዙ ጊዜ የሚዛመደው ከወዳጅነት ፍቅር (Phile) በኮይኔ(koiNe) ግሪክ "አጋፒኦ" እና "ፊልዮ" የሚሉት ቃላት መለኮታዊ ፍቅርን ለመግለፅ ብዙውን ጊዜ ተመሳሳይ ናቸው (11፡3[ፊልዮ]ን ከ 5[agapao] ጋር አንፃፅረው) Phileo በ5፡20 ላይ የእግዚአብሔርን ፍቅር ይገልፃል፡፡

▣ **"እኔ ያዘዝኳችሁን ሁሉ ብታደርጉ"** ይህ ድርጊትን ለመፈፀም አቅም መኖሩን የሚያመለክት ሦስተኛ ሁኔታዊ አረፍተነገር ነው፡፡ ለወዳጅነቱ አንዳች መሟላት የሚገባን ነገር ይጠቅሳል (ያመለክታል) ይህም እንደለና በፍቅሩም እንደሚኖር ሁሉ፣ የእርሱም ደቀመዛሙርት እንዲሁ ሊሆን ይገባቸዋል፡፡

**15፡15** ኢየሱስ ደቀመዛሙርትን የሚጠቁማቸው (የሚያስገነዝባቸው) (1) ስለእግዚአብሔር ያሉትን እውነቶች (2) ወደፊት ስለሚከሰቱ ጉዳዮች/ሁነቶች ደቀመዛሙርቱ በእምነትና እርሱን በመደገፍ ይችሉ ዘንድ ኃይሉን ያሣያል፡፡ ኢየሱስም ከሰባቱ የሰማውን ለደቀመዛሙርቱ አካፍሎ (3፡32፤8፡26፡40፣12፡49፣15፡15) እነርሱመ ይህን ወደሌሎች ማስተላለፍ ነበረባቸው (ማቴ 28፡20)፡፡

**15፡16 "እኔ መረጥኳችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም"** ብዙ ቁልፍ የሆኑ ሰዋሰዋዊ ነገሮች አሉ፡፡

1. ሁለቱም ግሦች የመሐል አድራጊ ግሥ አመልካች ናቸው፡፡ ኢየሱስ ራሱ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መርጦአቸዋል(6-70፣13፡18፤15፡16፡9)
2. ጠንካራው ተቃራኒ ግላጭ (ነገር ግን)
3. ግላጭ ሆኖ የተነገረው "ሮም" ወይም "እኔ" የሚለው ንግግር

እዚህ ላይ የመለኮት መርጫና የሰው ምርጫ ሚዛን ሲጠብቅ ማየት ይቻላል፡፡ ሁለቱም መጽሐፍቅዱሳዊ ትምህርቶች ናቸው፡፡ አግዚአብሔር ሁልጊዜ የመጀመሪያውን እርምጃ የወሰዳል (6፡44-65፤15፡16፤19)፣ ነገር ግን ሰዎች ምላሽ መስጠት አለባቸው (1፡12፡3፡16፣ 15፡4፤7፤9)፡፡ እግዚአብሔር ከሰው ልጅ ጋር ያለው አድርገች ሁልጊዜ በቃልኪዳን ግኑኝነት ላይ የተመሠረቱ ናቸው (*if …… theN*) በ3፡16 ላይ ልዩ ርዕስ የሚለውን ተመልከት፡፡

"መረጥኳችሁ" የሚለው ግስ በዚህ ዓውድ የሚያመለክተው አሥራ ሁለቱን ነው፡፡ "መረጥኳችሁ" የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን ውስጥ "ለአገልግሎት መመረጥ" የሚል ድባብ /ትርጉም ሲኖረው በአዲ ኪዳን ደግሞ "ለድነት መመረጥ" የሚል ሐሳብ አለው፤ ይህም ሀሳብ በቃላትና በዐረፍተ ነገር ትርጉም ውስጥ እንዳካተተ አድርጓታል፡፡ የአዲስ ኪዳን አማኞች ክርስቶስን ለመምሰል ተጠርተዋል፤ ይህም አገልግሎት የሆነ፤ ከራስ ወዳድነት ነፃ የሆነ፤ ለእግዚአብሔር መንግሥት መሥዋዕት የሚሆን፣ የክርስቶስ አካል ነው፡፡ በራስ ወዳድነት ያተምነው የወደቀው አለም አመለከተ መስበሩነ በግልፅ የሚያመለክት ክስተት ነው፡፡

በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ አሡሩ ሁለቱነ የሚለከት ኢየሱስ የሚናገረው ነገር ለሁሉም አማኞች በተዘዋዋሪ የሚያመለክተው ነገር ያለውን በተግባር የሚፈፀም ነው፡፡ የመጀመሪያውን የደቀመዝሙርነትን ፍሬ የሚመክሉ ናቸው፤ የእነርሱ ግኙኝነት ግን

1. በአይን ምሥክርነት ማስረጃ የፀና መሆኑ (እስትንፋስ እግዚአብሔር)
2. ኢየሱስ ለእነርሱ የነበረው ፈቃድ ዛሬ ለሁሉም አማኞች በመሆኑ ተፈፃሚነት ያለው ነው፡፡

▣ **"ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ ፍሬአችሁም ሊኖር ሽምኳችሁ"** እነዚህ በአሁን ጊዜ ግሥ የተገለጡ ሁኔታ ግላጭ የግሥ አይነቶች ናቸው፤ (1) ልትሄዱ፡ (2) ፍሬ ልታፈሩ (3) ፍሬአችሁም ሊኖር(ልትኖሩ) የሚሉት ናቸው፡፡ አማኞች በተልዕኮ ላይ ናቸው (ማቴ 28፡19-20፤ ሉቃ24፡46-47፤ ሐዋ 1፡8)፡፡ ነገር ግን "ሾምኳችሁ" የሚለው ቃል ሥነ-መለኮታዊ አንደምታ በሐዋ 20፡28 1ቆሮ 12፡28፤ 2ጢሞ 1፡11 ላይ ሊታይ የሚችል ነው፡፡ እንዲሁም ደግሞ ቃሉ በአማኞች ምትክ ክርስቶስ መምቱን ለማመልከት ተጠቅሷል (10፡11፤15፤17-18-15፡13)፡፡

▣ **"በስሜ"** አማኞች የኢየሱስን ባህሪ ሊያሣይ ይገባል፡፡ ይህ ሐረግ "የእግዚአብሔር ፈቃድ" ከሚለው ጋር ተመሣሣይነት አለው 1ዮሐ 5፡14፡፡ በምዕ 14፡13-15 እንደተጠቀሰው ፍቅርና ምላሽ ያገኘ ፀሎት (የተመለሰ ፀሎት) ግኑኙነት አላቸው፡፡ ዮሐንስ 14፡14 ላይ የእግዚአብሔር ስም የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

**15፡17 "እርስበርሳችሁ እንድትዋደዱ ይህን አዛችኋለሁ"** በቁጥር 12 ላይ ያለውን ማለት ወሾ ይመልከቱ፡፡ ምላሽ ያገኘ ፀሎት ከፍቅርና ከወንጌል ተልዕኮ ጋር ግኑኝነት አለው፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 15፡18-25)

**18ዓለም ቢጠላችሁ ከእናንተ በፊት እኔን እንደጠላኝ እወቁ፡፡ 19ከዓለም ብትሆኑ ዓለም የራሱ የሆነውን ይወድ ነበር፡፡
ነገር ግን እኔ ከዓለም መረጥኳችሁ እንጂ ከዓለም ስለ አይደላችሁ፡ ስለዚህ ዓለም ይጠላችኋል፡፡ 20ባርያ ከጌታው
አይበልጥም ብዬ የነገርኳችሁን ቃል አስቡ፤ እኔን አሳደውኝ እንደሆኑ እናንተን ደግሞ ያሳድዷችኋል፤ ቃሌን ጠብቀው
እንደሆኑ ቃላችሁን ደግሞ ይጠብቃሉ፡፡ 21ዳሩ ግን የላከኝን አያውቁምና ይህን ሁሉ ስለ ስሜ ያደርጉባችኋል፡፡ 22እኔ
መጥቼ ባልነገርኳቸውስ ኀጢአት ባልሆነባቸውም ነበር፤ አሁን ግን ለኀጢአታቸው ምክንያት የላቸውም፡፡ 23እኔን
የሚጠላ አባቴን ደግሞ ይጠላል፡፡ 24ሌላ ሰው ያላደረገውን ሥራ በመካከላቸው ባላደረግሁ ኀጢአት ባልሆባቸውም ነበር፡፡
አሁን ግን እኔንም አባቴንም አይተውማል፤ ጠልተውማል፡፡ 25ነገር ግን በሕጋቸው፡ በከንቱ ጠሉኝ ተብሎ የተፃፈው ቃል
ይፈጸም ዘንድ ነው፡፡**

15፡18 "ቢ" የህ ከፀሐፊው አስተያየት አንፃር ወይም ለሥነ ፅሑፋዊ ዓላማው ሲባል እውነት ነው ተብሎ የሚገመት ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ አረፍተነገር ነው፡፡ ዓለም፡ የወደቀው የሰው ልጅ ሥርዓት የኢየሱስን ተከታዮች ይጠላል፡፡

▣ "ዓለም" ዮሐንስ ይህን ቃል በብዙ መንገዶች ይጠቅሰዋል (1) ፕላኔት፡ ለሁሉም የሰው ልጅ የተሰጠው ዘይቤያዊ አነጋገር (3፡16) እና (2) ከእግዚአብሔር ተለይቶ የተደራጀና የሚሠራ ሕብረተሰብ (10፡8፡1ዮሐ 2፡15-17)፡፡
በ14፡17ላይ ልዩ ርዕስ የሚለውን ይመልከቱ፡፡

▣ "ቢጠላችሁ" ይህ የአሁን ጊዜ ድርጊት ገላጭ ግሥን አመልካች ነው፤ ዓለም መጥላቱን ይቀጥላል(ቁ.20)፡፡

▣ "እወቁ" የአሁን ጊዜ ትዕዛዝ አዘል ድርጊት ገላጭ ግሥ ነው፡፡ አማኞች የአዲስ ኪዳንን እውነት ማወቃቸው ከአለም የሚመጣባቸውን መከራ ለመጋለጥ ይረዳቸዋል፡፡

▣ "ከእናንተ በፊት እኔን እንደጠላኝ" ይህ በድርጊ ግላጭ ግሥ ድርጊቱ መፈፀሙን አመልካች ነው፡፡ "እኔን" የሚለው ተውሳጠ ስም ለማጉላት የተጠቀሰ ነው (7፡7)፡፡ ይህም የሚያሳየው ዓለም ለእግዚአብሔር፣ ለተላከው መስህ እና ለሕዝቡመ ያለውን ተቃውሞ ነው(17፡14፣ 1ዮሐ 3፡13)፡፡

አማኞች በክርስቶ ፍቅር አንድ እንደሆኑ ሁሉ በክርስቶስም መከራ አንድ ናቸው (ሮሜ 8፡17፤2ቆሮ 1፡5፤7 ፊልጅ 3፡10 1ጴጥ 4፡13)፡፡ በክርስቶስ ያለን ማንነት ሌላምን፣ ደስታን፣ መከራን እንዲሁም ሞትን የሚያመጣ ነው፡፡

15፡19 "ብ..." ይህ "ከእውነታው ወቃሪን" የሚባለው ሁለተኛ መደብ ሁኔታዊ አረፍተ ነገር ነው፡፡ ይህም አረፍተ ነገር "ከአለምስ ብትሆኑ፣ ከአለም አይደላችሁም፤ ዓለም ራሱ ይወዳችሁ ነበር፤ ነገር ግን አይወዳችሁም ተብሎ መተርጎም አለበት፡፡

15፡20 "አስቡ" ይህ ልክ እንደ ቁ.18 የአሁን ጊዜ ትዕዛዝ አዘል ገላጭ ግሥ ነው፡፡ ወይም የአሁን ጊዜ ትዕዛዝ አዘል ገላጭ ግሥ ሆኖ ምናልባት ጥያቄያዊ (*LB*)፡፡

▣ "ባሪያ ከጌታው አይበልጥም" ይህን ጥቅስ ከ3፡16 ጋር ስናስተያየው ኢየሱስ ምሣሌያዊ ንግግሮችን በተለያዩ መንገዶች እንደተጠቀመ በቀላሉ ማየት ይችላል፡፡

▣ "እኔን አሳደውኝ እንደሆኑ .... ቃሌን ጠብቀው እንደሆኑ" ከፀሐፊው አስተያየት አንፃር የተለጡ ሁለት ሁለተኛ መደብ ሁኔታዊ አረፍተነገሮ ናቸው፡፡ "ማሣይድ" የሚለው ቃል እንደ ጫካ አውሬ /ድሮ እንስሳ መከታተል ማለት ነው፡፡ ስደት በዚህ በወደቀው ዓለም ለአማኞች ተለመደ ነው(ማቴ 5፡10-12፤ ዮሐ 161-3፡17-14 ሐዋ 14፡22 ሮሜ 5፡3-4፤ 8፡17 2ቆሮ 4፡16-18፤6፡3-10፡11፡23-30 ራዕይ 1፡29፤1 ተስ 3፡3 2ጢሞ 3፡12 2ኛ1፡2-4 1ጴጥ4,12-16)፡፡

ይሁን እንጂ አንዳንዶች የሐዋርያትን ቃል ቢቃወምና ቢያሳድዷቸውም እንኳ የሚሰጠን ምላሽ የሚሰጡ እንደሉም አስተውል፡ እነዚህ ራዳቸው የዚህ እውነት ማረጋገጫዎች ናቸውና፡

15፡21 "የላከኝን አያውቁምና" ይህ በግልፅ አብን የሚያመለክት ነው፡፡ በተዘዋዋሪም የሚገልጠው አይሁድም ሆኑ አህዛብ እግዚአብሔርን እንደማያውቁ ነው፡፡ "ማወቅ" የሚለው ቃል የተጠቀሰው ግላዊ ግንኙነትን በሚገልጠው (ዘፍ 4፡1 ኤር 1፡5) ዮሴ መቲክ ትርጉም (ብሉይ ኪዳን) ነው፡፡ የጠፋው ዓለም አማኞችን የሚያሳድድበደት ምክንያት (1) የእርሱ በመሆናቸው እና እርሱንም አስድመው ስላሳደጉት (2) እግዚአብሔርን ስለማያውቁ፡፡

15፡22 "እኔ መጭቼ ባሊሆን" የህ ሌላው ሁለተኛ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ሲሆን ትርጉሙም "ከእውነታው መቃረን" የሚል ነው፡፡ "መጥቼ ባልነግራቸው ኖሮ ነግሬአቸዋለሁ፡፡ ኃጢአት አይሆንባቸውም ነበር፣ ግን ኃጢአትን ያደርጋሉ" ተብሎ ሊተረጎ ይገባል፡፡ ኃላፊነት ከእውቀት ጋር የሚገኝ ነው (በ5፡21ላይ ይቅር የማይባል ኃጢአት በሚለው ልዩ ርዕስን ይመልከቱ፡፡)፡፡ በዚህ ዓውድ ውስጥ ፍሬ አልባ ቅርንጫፎች (ይሁዳ እነ አይሁድ) የተፈጥሮ መገለጥ ብቻ ከነበራቸው

(አህዛብ፤ *መዝ* 19፡1-6 ሮሜ 1፡18-20 ወይም 2፡14-15) ይልቅ እውቀትን ለማግኘት ትልቅ አጋጣሚ ነበራቸው፡፡
15፡23 ኢየሱስን መጥላት እግዚአብሔርንም መጥላት ማለት ነው (ቁ. 24 1ዮሐ 5፡1)፡፡

**15፡24 "ባ"** (ባላደረግሁ) ይህ ሌላው ሁለተና መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተነገር ሲሆን ትርጉሙም፡፡ ከእውነት መቃረን የሚል ነው፡፡ ሊተረጎም የሚገባው፡፡ "ማንም ሰው ሊያደርገው የማይችለውን *ሥራ* በመካከላቸው ባላደርግ ኖሮ (አድርጌዋለሁ) ኃጢአት አይሆንባቸውም ነበር፡ ግን ያደርጋሉ" ተብሎ ነው፡፡

ብርሃን ኃላፊነትን ያመጣል (1፡5፡8፡12፡12፡35፡46 1ዮሐ 1፡5፡2፡8፡9፡11 ማቴ 6፡23)፡፡

▣ **"አሁን ግን እኔንም አባቴንም አይተውማል ጠልተውማል"** እነዚህ ሁለቱም ድርጊት መጠናቀቅን አምልካቾች ናቸው፤ ይህም የሚያሣየው የተወሰነና የማይለውን አመለካከት መሆን ነው፡፡ ኢየሱስን መቃወም አብን መቃወም ማለት ነው (1ዮሐ 5፡9-13)፡፡

**15፡25 "ሕግ"** ወይም "ቶራ" የሚለው ቃል ከመዝ 35፡19፣ 69፡4 የተወሰደን ጥቅስ ለማብራራት/ ለመግለፅ መጥቀሱ አስገራሚ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ቃሉ የሚጠቅሰው ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም ያለውን የሙሴነ ፅሑፎች ለማሣየት ነው፡፡

በዚህ ሁሉ መገለጥ ውስ አይሁድ ኢየሱስን የመቃወማቸው ሚስጢር በግልፅ የሚያሳየው በራሳቸው ፈቃድ ማመን አለመፈለጋቸውን ነበር (ኢሳ 6-9-13፤ ኤር 5፡21፤ ሮሜ 3፡9-18)፡፡

| |
|---|
| NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 15፡26-27)<br>[26]**ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል፤** [27]**እናንተም ደግሞ ከመጀመሪያ ከእኔ ጋር ኖራችኂልና ትመሰክራላችሁ፡፡** |

15፡26 **"እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አፅናኝ.... በመጣ ጊዜ"** አብና ወልድ ናቸው መንፈስ ቅዱስን የሚልኩ (14፡15-26፡15፡2616፡7)፡፡ የመመዘች *ሥራ* (ተግባር) ሁሉን የስላሴ አካላት የሚያካትት ነው፡፡

▣ **"የእውነት መንፈስ"** መንፈስ ቅዱስ አብን እንደሚገልጥ ባለው ትርጉም ነው የተጠቀሰው (14፡17፡26፡15፡26፡16፡13)፡፡ በ6፡55 እና 17፡3 ላይ እውነት በሚለው ልዩ ርዕሳን ተመልከት፡፡

▣ **"ስለእኔ ይመሰክራል"** የመንፈስ ተግባር ኢየሱስና ትምርቶቹን መመስከር ነው (14፡26፣ 16፡13-15፡1ዮሐ 5፡7)፡፡

**15፡27 "እናንተም ደግሞ .... ትመሰክራላችሁ"** "እናንተም ደግሞ" የሚለው አባል ሀሳቡነ ለማጉላት የተጠቀሰ ነው፡፡ ይህ የአሁን ጊዜ አድራጊ ግስ አመልካች ነው፡፡ ይህ ኢየሱስ በምድር ይመላለስ በነበረበት ወቅት (ሉቃ 24፡48) አብረው የነበሩት የአዲ ኪዳን ፀሐፊዎች ብግዚአብሔር መንፈስ ምሪት መፃፋቸውን የሚያመለክት ነው፡፡ ሐዋርያትና ኀደኞቻቸው፡፡ይህንን በ1፡8 ላይ ለኢየሱስ መመስከር እነ የመንፈስ ሰብአዊነት በ14፡26 የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡ ልዩ ርዕስ፡ ለኢየሱስ መመስከር በ1፡8 ላይ እና የመንፈስ ሰብአዊነት በ14፡26

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ሲሆን የሚችል ማብራሪያ በመሆኑ ለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተርጓጎም ኃላፊነት አለብህ፡፡ እያንዳንዳችን ልንሔድ የሚገባን ባለን መረዳት መጠን ነው፡፡ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስቅዱስ በአተርጓጎም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣችሁ ናችሁ፤ በመሆኑም ይህንን በማያብራራው ሰው ላይ ብቻ ልትተው የሚገባ አይደለም፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት በዚህ በጽሐፍ ውስጥ ባሉት ዋና ዋና ጉዳዮች ላ በጥምና እንዲታሰብበት ለመረዳት ይቻል ዘንድ ነው፡፡ በመሆኑም ጥያቆዎቹ የቀረቡት እንደ ሐሳብ- አነሳሽ ሆነው እንጂ በግልፅ ወይም በቀጥታ አይደለም፡፡

1. "መኖር" ምንን ያካትታል;
2. አንድ አማኝ መኖርን ቢያቆምስ? ፍሬ ባይገኝበትስ?
3. የእውንቶኛ ደቀመዝሙርነትን መስረጃዎችን ዘርዝራቸው፡፡
4. መከራ ለክርስትያኖች የተለመደ ካልን ይህ ዛሬ ለእኛ ምን ትርጉም አለው?
5. ቁጥር 16ን በራስህ አባባል ግለፅ፡፡

# ዮሐንስ 16

## የተሻሻሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀፅ አከፋፈል

| UBS[4] | NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| *የአለም ጥላቻ* | *የሚመጣው ተቃውሞ* | | | *ደቀመዛሙርትና አለም* |
| (W: 18-16: 4ሀ) | (W: 26-16: 4) | *ክርስቲያን ከዓለም ጋር ያለው ግንኙነት* | (W:18-16: 4ሀ) | (W: 18-16: 4ሀ) |
| *የመንፈስ ሥራ* | | 16-1-4ሀ | *የመንፈስ ቅዱስ ሥራ* | *የጰራቅሊጦስ መምጣት* |
| | 16-5-15 | 16-4ለ-11 | 16፥4ለ-11 | 16፥4ለ-15 |
| 16፥12-15 | | 16-12-15 | 16-12-15 | |
| *ሐዘን ወደ ደስታ ይለወጣል* | *ሐዘን ወደ ደስታ ይለወጣል* | | *ሐዘንና ደስት* | *ኢየሱስ በቅርብ ይመለሳል* |
| 16፥16-24 | 16፥16-24 | 16:16:24 | 16:16 | 16:16 |
| | | | 16:17-18 | 16:17-28 |
| | | | 16:19-22 | |
| | | | 16:23-24 | |
| *አለምን አሸንፌአለሁ* | *ኢየሱስ ክርስቶስ አለምን አሸንፏል* | | *ዓለምን ማሸነፍ* | |
| 16:25-33 | 16:25-33 | 16:25-28 | 16:25-28 | |
| | | 16:29-33 | 16:29-30 | 16:29-33 |
| | | | 16:31-33 | |

**ሦስተኛ የጥናት ዑደት (አንቀጽ 5ን ይመልከቱ)፡፡**
*የመጀመሪያውን ፀሐፊ ዋና ሐሳብ በአንቀፅ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ሊሆን የሚችል ማብራሪያ በመሆኑ ለምትከተሉው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጐም ኃላፊት አለብህ፡፡ እያንዳንዳችን መንገዝ ያለብን ባለን መረዳት መጠን ሊሆን ይገባል፡፡ በአተረጓጐም ወቅት አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ቅድሚያ የሚሰጣችሁ ናችሁ፡፡ በመሆኑም ይህንን ጉዳይ በሚያብራራው ሰው ላይ ብቻ መተው የለብህም፡፡

ሙሉውን ምዕራፍ በአንድ ጊዜ አንብበው፤ ዋና ሐሳቦቹንም ለያቸው፡፡ የራስህን የርዕስ አከፋፈል ከአምስቱ የተሻሻሉ ትርጉሞች ጋር አስተያያቸው፡፡ በአንቀፅ መከፋፈል በእግዚአብሔር መንስ ምሪት የሚካሄድ ባይሆንም በአተረጓጐም ክህሎት እምብርት የሆነውን የመጀመሪያውን ፀሐፊ ዋና ሐሳብ ለመከተል ግን ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ እያንዳንዱም አንቀፅ የሚያወሳው ስለአንድ ሐሳብ ብቻ ነው፡፡

1. *የመጀመሪያ አንቀፅ*
2. *ሁለተኛ አንቀፅ*

3. ሦስተኛ አንቀፅ

4. ወ.ዘ.ተ

## በዮሐ 16:1-33 ላይ አውዳዊ ግንዛቤዎች

*ሀ. ሥነ - ፅሑፋዊው ዓውድ የሚጀምረው ከ15:18-16፣4ሀ ነው፡፡ የምዕራፍ አከፋፈሎች በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት የሚካሄዱ አይደሉም፤ እንዲሁም ደግሞ ሌሎች ከኋላ የተጨመሩትም እንደ በአንቀፅ መከፋፈል፣ በትልቁ መፃፍ፣ ሥርዓተ ነጥብእና የጥቅስ አከፋፈልም ተመሣሣይ ናቸው፡፡*

*ለ. በመንፈስ ህይወታቸው ለጠፉት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በቁ.* 8-11 *ላይ ተገልጿል፤ እንዲሁ ደግሞ ለዳኑት የሚሠራው ሥራ በቁ.* 12-15፡፡ *ሳሙኤል አኩላስኪ* "The Theology of the New TestameNt" *በሚለው አንቀፁ መንፈስ ቅዱስ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስላለው እንቅስቃሴ ጥሩ የሆነ ማጠቃለያን ይሰጣል፡፡ ሳሙኤል አሎላሰኪ በ* *The ExpositioN Bible CommeNtary* *በሚል መፅሐፉ ባለው* *The Theology of the New TestameNt* *በሚል ፅሑፍ መንፈስ ቅዱስ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስላለው እንቅስቃሴ ጥሩ የሆነ ማጠቃለያን ይሰጣል፡፡*

> *"ምንም እንኳን የአደስ ኪዳን የቅርስና አስተምህሮ ከመጽደቅ ጋር ኅብረት ቢኖረውም ልዩነት ግን አለው" በብሉይ ኪዳን መቀደስ የሚያመለክተው በመጀመሪያ መለየትን ቅዱስና ሐያል በሆነው አምላክ ፊት ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ እግዚአብሐርን ወደሚመስል የሕይወት ጥሪትና ግንኙነት ማደግን ነው፡፡ መቀደስ አንድን ሰው ከክርስቶስ ጋር የሚያገናኝ መንፈሳዊ ሕይወቱንም የሚያድሰው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው፡፡ የአዲስ ኪዳንም ቋንቋ የሚያስላልፈው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው፡፡ የአዲስ ኪዳንም ቋንቋ የሚያስተላልፈው በመንፈስ መጠመቅን* (1ቆሮ 13፡13)፡፡ *በመንፈስ መዘምን* (ኤፌ1፣ 13፤ 14፤ 4/30) *የመንፈስን በውስጣችን መኖር*) (14፤ 17፣ ሮሜ 5፣4፤ 8-9-11፤ 1ቆሮ 3፤16 ፤ 6:19:2 ጢሞ 1:14) *የመንፈስ ቅዱስን ማስተማር* (14:26፤ 16፤ 12-15) *በመንፈስ መሞላትን* (ኤፌ 5:18) *እና የመንፈስ ፍሬን ነው* (ገላ 5:22፤23)፡፡ *መቀደስ በእግዚአብሔር ፊት መቆምን* (ዕብ 10:10) *ከሚያመለክተው ከመጽደቅ ጋር የሚገናኝ ሲሆን ምናልባትም ወደ አዲስ አየነት መረዳት እንደማደግ ተደርጎ የሚወለድም ነው፡፡* (ገጽ 474)

*ሐ. ቁ.*17 *እንደ* 13:36: 14:5:8 *እና* 22 *በሐዋርያት የቀረበ ሌላው ጥያቄ ነው፡፡*

*መ. ብዙዎች እንደሚያምኑት በ*14:31 *ላይ የተጠቀሰው "ተነሡ ከዚህ እንሂድ" የማለው ከ*18:1 *ጋር ሲጣመር የሚያሳየው ከምዕ* 15-17 *ድረስ ያለውን የተናገረው በቤተ መቅደሱና በኢየሩሳሌም ጐዳናዎች አቋርጦ ወደ ጌቴሴማኒ የአትክልት ሥፍራ ሲያመራ እንጂ በላይኛው ደርብ አልነበረም ይላሉ፡፡*

## የቃልና የሐረግ ጥናት

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 16÷1-4

**[1]እንዳትሰናከሉ ይህን ተናግሬአችኋለሁ፡፡ [2]ከምኩራባቸው ያወጡአችኋል፤ ከዚህ በላይ ደግሞ የሚገድላችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል የሚመለስበት ጊዜ ይመጣል፡፡ [3]ይህንም የሚያደርጉባችሁ አብን እኔን ስላላወቁ ነው፡፡ [4]ነገር ግን ጊዜው ሲደርስ እኔ እንደነገርኳችሁ ታስቡ ዘንድ ይህን ተናግሬአችኋለሁ፡፡ ከእናንተም ጋር ስለነበርኩ በመጀመሪያ ይህን አልነገርኳችሁም፡፡**

**16:1**

| | |
|---|---|
| NASB | "እንዳትሰናከሉ" |
| NKJV | "መሰናከል ስለሌለባችሁ" |
| NRSV | "ከመስናከል ለመጠበቅ" |
| TEV | "እምነታችሁን እንዳትተው" |
| NJB | "ወደኋላ እንዳታፈገፍጉ" |

ይህ ስሜት ገላጭ የሆነው የግሪኩ ተደርጐ ግሥ ነው፡፡ ይህ የግሪክ ቃል *jkaNdalizo* ለሚለው ስሜት ገላጭ ተደርጐ ግሥ፤ BAGD 752) በመጀመሪያ ይጠቀስ የነበረው አውሬዎችን ለማጥመድ በሚቀመጥ የማታለያ/የመሳቢያ ምግብ ትርጉምነበር፡፡ ብዙውን ጊዜ ግን ወደ ኋላ ማፈግፈግ" ተብሎ ይተረጐማል (ማቴ 13፤ 21፤ 24፤10 ማር 4፤ 17፤ 14፤ 27፤ 29) በዚህ ዓውድ የተጠቀሰው ይህ ዘይቤያዊ አነጋገር የሚያመለክተው በአይሁድ እንዲሁም በሐይማኖት መሪዎች የጥላቻ ድርጊቶች ምክንያት እንዳይጠመዱ አማኞች ያመለክታል፡፡

16:2 **"ከምኩራባቸው ያወጡአችኋል"** ይህ የሚያመለክተው ከአየሁድ እምነት መገለልን ነው (9:22፤ 34:12:42) አይሁድ እንዴት የማግለልን ሒደት እንደሚያስቡ ብዙም የሚታወቅ ነገር የለም፡፡ ነገር ግን ለጊዜውና በቋሚነት ከምኩራብ አገልግሎቶች የማግለል አሠራር ነበር፡፡ በኋላም በ70 ዓ.ም ከኢየሩሳሌም ውድመት በኋላ በጃሚኒያ ፍልስጥኤም ክርስቶስን እንዲሁም የእርሱ ተከታዮች የነበሩትን ክርስቲያኖችን ከምኩራብ ለማስወጣት "የእርግማን መሐላ" የሚልሐሳብ አመጡ፡፡ ይህም በጨረሻው በክርስቶስ ተከታዮችና በየአካባቢው ባሉ የአይሁድ ምኩራቦች መለያየትን አመጣ፡፡

▣ **"የሚገላችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል የሚመለስበት ጊዜ ይመጣል"** የአይሁድ መሪዎች ያስቡት ነገር በትክክል ይሔው ነበር (ኢሳ 66:5፤ ማቴ 5:10-12፤ 10:32)፡፡ የጨርሴ ሱም ሳውል (ጳውሎስ) እንዲህ ለተሳሳተ የኃይማኖት ቀናተኝነት ጥሩ ምሳሌ የሚሆን ነው (ሐዋ 26:9-11 ገላ 1:13-14)፡፡

16:3 **"ይህንም የሚያደርጉባችሁ"** አንድ የላቀ ሕልውና ላለው አካል ራስን በቅንነትና በመስጠት ማቅረብ ብቻውን በቂ አይደለም፤ ክፋት፣ ስህተት እና ፅንፈኝነት ብዙውን ጊዜ የሚፈጠሩት በእግዚአብሔር ስም ነውና፡፡

▣ **"አብንና እኔን ስላላወቁ ነው"** "ማወቅ" የሚለው ቃል በብሉይኪዳን በጣምየቀረበ፣ ግላዊ የሆነ ወዳጅነትን የመለክታል (ዘፍ 4:1 ኤር 1:5)፡፡ ይህም ኢየሱስን አለመቀበል የላከውን እግዚአብሔርን እንዳለመቀበል ነው የሚል ጠንካራ ንግግር ነው (8:19: 15:21፤ 1ዮሐ 5:9-12)፡፡

ዮሐንስ ብዙውን ጊዜ የዚህን ዓለም መንፈሳዊ እውነትና ድንቁርናን (አለማወቅን) ይናገራል (1፡10፣ 8-19፤፣ 55፣ 15፡21፣ 16፡3 17፡25) ይሁን እንጂ የወልድ ወደዚህ ዓለምመምጣት ዓለምን ለማዳን (3፡16) እና ያምኑበት ዘንድ አብን ለመግለጥ ነበር (17፡23) በክርስቶስ በኩል ዓለም እግዚአብሔርን ያውቅ ዘንድ ለመግለጥ ነበር (17፡23)፡፡

16፡4 ኢየሱስ ወደፊት ስለሚሆንባቸው ነገር መናገሩ አማኞች በመከራና በመገፋት ውስጥሊያልፉ (13፡19፤ 14፡29) እምነታቸውንና መደገፋቸውን ለማበርታት እንደ መሣሪያ የተጠቀመበት ነበር፡፡
"ይህን ተናግሬአችኋለሁ" የሚለው የሚያመለክተው የኢየሱስን የአደባባይ አገልግሎት መጀመር እና የአሥራ ሁለቱን ደቀመዛሙርት ልዩ ጥሪን ነው፡፡

> NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 16÷5-11
> **[5]አሁን ግን ወደ ላከኝ እሄዳለሁ ከእናንተም፡- ወዴት ትሄዳለህ? ብሎ የሚጠይቀኝ የለም፡፡ [6]ነገር ግን ይህን ስለተናገርኋችሁ ሐዘን በልባችሁ ሞልቶአል፡፡ [7]እኔ ግን እውነት እነግራችኋለሁ፤ እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል፡፡ እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና፤ እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ፡፡ [8]እርሱም መጥቶ ስለኃጢአት ስለጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል÷ [9-10]ስለኃጢአት በእኔ ስለማያምኑ ነው፤ ስለጽድቅም ወደ አብ ስለምሄድ ከዚህም በኋላ ስለማታዩኝ ነው፤ [11]ስለፍርድም የዚህ ዓለም ገዢ ስለተፈረደበት ነው፡፡**

16:15 **"ከእናንተም፡- ወዴት ትሔዳለህ? ብሎ የሚጠይቀኝ የለም"** ጴጥሮስ በምዕ 13:36 ላይይህን ጥያቄ የጠየቀ ይመስላል፤ ነገር ግን ኢየሱስ ትቶአቸው ሲዴድ በሚፈጠረው ጥልቅ ሐዘን ላይ ሐሳቡ ተወስደ (ቁ. 6)፡፡ ዮሐንስ 14 1-3 የኢየሱስን ወደ ሰማይ ማረግ ይገልፃል (ሐዋ 1:9-11)፡፡

ይህ ወንጌላት የቃላት ጉዳይ፣ ወይም የንግግር ቅጂዎች አለመሆናቸውን ስናስተውል የሚገባን ሥፍራ ነው፡፡ ለሥነ-መለኮታዊ ዓለማዎች ሲባሉ ከዓመታት በኋላ የተሰጡ ድምዳሜዎች ናቸው፡፡ የወንጌል ፀሐፊዎች፤ በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት አማካኝነት ኢየሱስ የተናገራቸውን ቃላት የመምረጥ፣ የማደራጀት እና የማስማማት (ከሁኔታው) አማራጭ ነበራቸው (በጉርደን ፊ እና ዳግላስ ስቱዋርት የተፃፈውን፡- How to Read the Bible for All Its worth የሚለውን መጽሐፍ ይመ)፡፡ ኢየሱስ ሊናገር የተገባችውን ቃላት በአንደበቱ የማስቀመጥ መብት ሊኖራቸው ይገባ ነበር ብሎ አላምንም፡፡ ይህ የኢየሱስን ቃላት፣ ትምህርቶች፣ እና ድርጊቶች ትኩረት የተደረጉትን አድማጮች ወይም የመልዕክቱ ተቀባዮች በወንጌል ለመድረስ የሚደረግ ሥነ-መለኮታዊ አወቃቀር ምናልባት በወንጌል ታሪኮች መካከል ያለውን ብዙ ልዩነቶች የሚገልፅ ነው፡፡

16:6 **"ኀዘን በልባችሁ ሞልቶአል"** ይህ ድርጊቱ መጠናቀቁን የሚያመለክት ግሥ ነው፡፡ አንድም የላይኛው ድርብ ልምምድ ኀዘን ነበር (14:1፤ 16:6-22)፡፡ "ልብ የሚለው ቃል በእብራይስጥ ሲጠቀስ ትርጉሙ መላውን የሰውን ማንነት ያሳያል፡- ሐሳቡን፣ ስሜቱን፣ እንዲሁም ፈቃዱን በ12:40 ላይ ልብ የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

16:7 **"እኔ እንድሔድ ይሻላችኋል"** የኢየሱስ አካል በአንድ ጊዜ አፅድ ቦታ ላይ ብቻ ነበር መሆን የሚችለው፤ ይህም ለሁሉም ደቀመዛሙርቱ ትምህርቱንና አገልግሎቱን እንዳያዳርስ የወሰነው ነበር፡፡ እንዲሁም ደግሞ በምድር በነበረው ሕይወቱ በቅድሚያ ትኩረት ያደረገው በእስራኤል ላይ ነበር (ማቴ 10:6፤ 15-24)፡፡ የመንፈስ ቅዱስ መምጣት ለሰፋ አገልግሎት (ኤፌ 2:11-3፡13) አዲስ ምዕራፍን የሚከፍት ነው፡፡

"ይሻላችኋል" የሚለው ቃል "ይጠቅማችኋል" ማለት ሲሆን ከኢየሱስ ሞት ጋር በተገናኘ በ11:50 እና 18፡14 ላይ ተጠቅሷል "እኔ ብሔድ" የሚለው ሐረግ በኢየሱስ የመጨረሻው ሳምንት የተፈፀሙት ክስተቶች ሊያጠቃልል ይችላል፡፡

▣ "እኔ ባልሔድ አፅናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና" ድርጊት የመፈፀም አቅም መኖሩን የሚያመለክቱ ሁለት ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገሮች አሉ። የመንፈስ ሙላት ይመጣ ዘንድ ኢየሱስ ልሔድ ነበረበት! ጰራቅሊጦስ *Praclitos* የሚለው ቃል "ጠበቃ" "አፅናኝ" ወይም "ረዳት" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል (14:16፤26:15፤26፤ በ14፤16 ላይ ሙሉ ማብራሪያውን ይመልከቱ።)። ቃሉ የሚገኘው በዮሐንስ ፅሑፎች ውስጥ ብቻ ነው።
በግሪክ ሥነ-ፅሑፍ ቃሉ ይጠቀስ የነበረው ለእርዳታ የሚቆሞን ተከላካይ ጠበቃን ለማመልከት ነበር። በቁ. 8-11 መንፈስ ቅዱስ በዓለም ላይ እንደዳኛ ሆኖ ተገልጿል፤ ይሁን እንጂ በቁ. 12-15 የመንፈስ ቅዱስ ጠበቃነት የተጠቀሰው ከአማኞች አንፃር ነው።

ያው ቃል ጰራቅሊጦስ *Praclitos* በ1ዮሐ 2፤1 ልጅ ለሚለው ተጠቅሷል። የግሪኩ ሥርው ቃል "ማፅናናት" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። በዚህ ትርጉም ግን የተጠቀሰው አብን ለማሳየት ነበር፤ 2ቆሮ 1፤3-11።

▣ "እርሱን እልክላችኋለሁ" መንፈስ የሚመጣው ከአብና ከወልድ ነበር (14፤26)።

16:8 **"እርሱም መጥቶ፡፤ ዓለምን ይወቅሳል"** ሦስቱም (ኃጢአት፣ የመንፈስ የሚመሰክርባቸው አቅጣጫዎች ከሰው ልጆች እና ከኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ሥራ ጋር የሚገናኙ ናቸው፡፡ "መውቀስ" የሚለው "ለመስቀለኛ ጥያቄ" ህጋዊው ቃል ነበር፡፡

ጂ. ቢ. ኬርድ፡- *The LaNguage aNd Imagery of the Bible* (ገጽ 159) በሚለው መጽሐፋቸው ሰለእነዚህ ሦስቱ አቅጣጫዎች ደስ የሚል መረዳት አላቸው፡፡

1. ኢየሱስን ወደ ፍርድ እና ወደምት ማምጣት ስህተት ነው፡፡
2. ሰለኃጢአት ያለው ትርጉም የተሳሳተ ነው፡፡
3. ስለ ጽድቅ የነበረው ግንዛቤ የተሳሳተ ነበር፡፡
4. ስለፍርድ የነበረው ግንዛቤ የተሳሳተ ነበር፡፡

ይህ ከሆነ ደግሞ በኢየሱስ አማካኝነት ወንጌልን በሙላት ይገልጣል፡፡ የእነርሱ ሃይማኖተኝነት ሊያረዳቸው አይችልም፡፡ ኢየሱስን የሚቃወሙትን ሁሉ ፍርድ ይጠብቃቸዋል! "ኃጢአቱም" አለማመን ነው! ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር ብቸኛው መንገድ ኢየሱስ ነው!

"ዓለም" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከእግዚአብሔር ተለይቶ የተደራጀና የሚሰራ የወደቀው የሰው ማህበረሰብ ነው፡፡ በ14፤17 ላይ ልዩ ርዕስን ይመ

16፤9 **"ስለኃጢአት በእኔ ስለማያምኑ ነው"** ወንጌል የሚጀምረው የሰውን ልጅ ኃጢአተኝነት በማስገንዘብና እና የእግዚአብሔርን ፅድቅ አስፈላጊነት በማስገንዘብ ነው፡፡ (ሮሜ 3፡9-18:23 6፤23፤ ኤፌ 2፡1-3)፡፡ ለድነት የመሰናክል ድንጋይ ዋናው ኃጢአት አይደለም ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትና ሥራው አለማመን ነው (ዮሐ 3፤6-21፤ 8፡24፤ 26)፡፡ "ማመን" የሚለውቃል የእውቀትና የስሜት ሐሳቦች አሉት፤ ነገር ግን ከሁሉመ በላይ የፈቃድ ጉዳይ ነው (በ 2፤23 ልዩ ርዕስን ይመ 1፤ ትኩረቱ በአማኙ መልካምነትና ብቃት ሣይሆን እግዚአብሐር ከክርስቶስኢየሱስ በሰጠው ተስፋ ላይ አማኙ በእምነት በሚሰጠው ምላሽ ላይ ነው (ሮሜ 3፤21-30)

16፤10 **"ስለ ፅድቅም"** ይህም ምናልባት የሚያመለክተው

1. ሊመጣ ያለውን የክርስቶስ የመቤዠት ሥራ እና የዚህም አካል የሆነውን ትንሣኤውን (ቁ. 10)
2. በትንሳኤው እንደታየው ክርስቶስ ብቻ በእግዚአብሐር ፊት ፃድቅ መሆኑን እየታወቀ ከእርሱ ውጪ ከእግዚአብሔር ጋር በጽድቅ እየሔዱ እንዳሉ የሚያመስበትን

16፤11 **"ስለፍርድም የዚህ ዓለም ገዢ ሰለተፈረደበት ነው"** የወደቁ መላእክትና በአመች ውስጥ ያሉት የው ልጆች ፅድቅ በሆነው አምላክፊት የሚቆሙበት ቀን አለ (ፊልጵ 2፤ 9-10)፡፡ ምንም እንኳን ሰይጣን በዚህ ዓለም ላይ አሁንም ታላቅ ቢሆንመ (12፤31፤ 14፤30 2 ቆሮ 4፤4 ኤፌ 2፤2 1ዮሐ 5፤19) የተሸነፈጠላት ነው (በተደርጎ ግሥ ድርጊት መፈፀምን አመልካች)፡፡ የሰይጣንም/የዲያብሎስም ልጆች የእግዚአብሔርን ቁጣ መቀበላቸው የማይቀር ነው (8፤44፣ ማቴ 13፤ 88: 1ዮሐ 3፤8-10)፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 16፤12-15

**[12]የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ፥ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም፡፡ [13]ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፤ የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይነግርምና፤ የሚመጣውንም ይነግራችኋል፡፡ [14]እርሱ ያከብረኛል፥ ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና፡፡ [15]ለአብ ያለውን ሁሉ የእኔ ነው፤ ስለዚህ፣ ለእኔ ካለኝ ውስጥ ይነግራችኋል አልሁ፡፡**

16፡12 **"ኡሁን ልትሸከሙት አትችሉም"** "መሸከም" የሚለው ቃል የሚታይ ሸክምን የሚያመለክት ነው፡፡ ደቀመዛሙርትም ሊረዷቸው ካልቻሉት አንዳንድ ነገሮች፤

1. የክርስቶስን መከራ

2. የክርስቶስን ትንሣኤ
3. የቤተክርስቲያንን የወንጌል ተልእኮ

የዘመናችን አንባቢዎች ሊያስታውሱት የሚገባው ነገር በብዙ መንገዶች የክርስቶስ ሕይወት የሚወክለው የሽግግር ወቅትን ነው፡፡ በመሆኑም እስከ ድህረ ትንሳኤና በበዓለ ሃምሳ ቀን መንፈስ ቅዱስ በሙላት እስከመጣበት ጊዜ ድረስ ደቀመዛሙርት ያልተረዷቸው ብዙ ነገሮች ነበሩ፡፡

ይሁን እንጂ ስናስታውስ የሚገባን ሌላው ጉዳይ ደግሞ ከዓመታት በኋላ ወንጌላት የተፃፉት የተወሰኑ ትኩረት የተደረገባቸውን የመልዕክቱን ተቀባዮች በወንጌልለመድረስ መሆንነው፡፡ ስለዚህም ወንጌላት የሚያንፀባርቁት ዘግየት ብሎ የመጣና ብስለት ያለውን ስነ-መለኮት ነው፡፡

16:13 **"የእውነት መንፈስ"** እውነት *alitheia* በብሉይ ኪዳን ድባብ የአንድ ነገር መድነትን ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ አውነተኛነትን ነው፡፡ ይህም ከሁሉ አስቀድሞ የሚያመለክተው የአዲስ ኪዳን መጽሐፎች ፀሐፊዎች በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርተው መፃፋቸውን ነው፡፡ ኢየሱስ በ14፥6 እርሱ እውነት መሆኑን ተናግሯል፡፡ ይህ ለመንፈስ ቅዱስ የሰጠው መጠሪያ ትኩረት የሚያደርገው ኢየሱስን በመግለጥ የሚጫወተውን ሚና ነው (14፥17፤ 26:16፥13-14፤ 1ዮሐ 4፥6፣ 5:7)፡፡ በዮሐ 6፥55 ላይ ማብራሪያውን ይመልከቱ፡፡

▣ **"ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል"** ይህ በሁሉም አቅጣጫ ላይ ያለውን ፍፁም እውነትን ሣይሆን በመንፈሳዊ እውነትና በኢየሱስ ትምህርቶች ብቻ ላይ ያለውን የሚያመለክት ነበር፡፡ ይህም ከሁሉ አስቀድሞ የሚያመለክተው የአዲስ ኪዳን መፅሀፍት ፀሐፊዎች በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርተው መፃፋቸውን ነው፡፡ መንፈስም የመራቸው ልዩና ሥልጣን ባለው መንገድ ነበር፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ መክሉን ለሚያነቡት ሰዎች መንፈስ ቅዱስ የሚያደርገውን የአብረወት ሥራ የሚያመለክት ነው በ6፣55 ላይ እውነት የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡፡ እንዲሁም ደግሞ በ14፣26 ላይ የመንፈስ ቅዱስ ስብእና የሚለውን ይመልከቱ፡፡

---

**ልዩ ርዕስ፡ አብርሆት**

ባለፉት ጊዜያት እግዚአብሔር ራሱን ለሰው ልጆች ግልፅ በሆነ ሁኔታ ገልጧል፡፡ በሥነ መለኮት ይህ መገለጥ ይባላል፡፡ ይህን ራሱን የገለጠበትን ሁኔታ ለመፃፍና ለማስረዳት የተወሰኑ ሰዎችንም መርጧል፤ ይህም በሥነ-መለኮት እስትንፋስ እግዚአብሔር ይባላል፡፡ ቃሉን የሚያነቡት መረዳት ይችሉ ዘንድ መንፈሱንም ልኰላቸዋል፤ ይህም በሥነ-መለኮት አብርሆት ይባላል፡፡ ችግሩ የሚፈጠረው የእግዚአብሔርን ቃል ለመረዳት ይቻለን ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ይሳተፋል ብለን አስረግጠን ስንናገር ነው፤ ይህ ከሆነ ታዲያ ለምንድነው በቃሉ ላይ ብዙ አይነት አተረጓጐሞችን የምናየው?

የተወሰነው ችግር ያለው በአንባቢው ቅድመመረዳት ወይም ግላዊ ልምምዶች ላይ ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ የራሳችንን ሃሳብ ለማስተላለፍ ስንጠቀም ሌላው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሚደረገው ጫና ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ በተወሰኑ አቅጣጫዎች በተመረጡ መንገዶች ብቻ እንዲናገር ማድረጋችን ነው፡፡ ምንም እንኳን በእያንዳንዱ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ተሳትፎ ቢኖርም አብረሆት ከእስትንፋስ እግዚአብሔር ጋር እኩል ሊሆን አይችልም፡፡

ከሁሉም የተሻለው አቀራረብ ግን እያንዳንዱን የጥቅሉን ዝርዝር መተርጐም ሳየሆን የአንቀፁን ማዕከላዊ ሃሳብ ለመረዳት መሞከር ነው፡፡ የመጀመሪያውን ኀሐፊ ማዕከላዊ ሃሳብ ነው፡፡ ርዕሳዊ ሃሳቡን ሊያስተላልፍልን የሚችለው ርዕሳዊ ሃሳቡ ነው መጽሐፉን ወይም ፅሑፉን በንድፈ ደረጃ ማስቀመጥ የመጀመሪያውን ፀሐፊ መነሻ ሃሳብ ለመከተል የሚረዳን ነው፡፡ የትኛውም ተርጓሚ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት አልተረጐመም፡፡ በመሆኑም የመጽሐፍ ቅዱስ ፀሐፊውን የአተረጓጐም ዘዴ እኛ ስንጠቀምበት አንችልም፡፡ እኛ ግን ፀሐፊዎች በዘመኑ ለነበሩት የመልዕክቱ ተቀባዮች ሊያስተላልፉ የፈለጉትን መረዳት ከዚህም ባሻገር ያንን እውነት ለዘመናችን ማስተላለፍ ግዴታችን ነው፡፡ እንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሻሚ ወይም ድብቅ ናቸው፡፡ (እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ) በአንዳንድ ጥቅሶችና ርዕሶች ላይ አለመስማማቶች /አለመግባባቶች ይኖራሉ፤ ነገር ግን እኛ ማዕከላዊውን እውነት መግለፅ የተገባን ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ የመጀመሪያውን ፀሐፊ ዋና ሃሳብ በጠበቀ መልኩ በግል ለሚሰጡ ትርጉሞች ነፃነትን ልንሰጥ ይገባል፡፡ ተርጓሚዎች መሔድ ያለባቸው ባላቸው የመረዳት መጠን ሲሆን ምንጊዜዋ ከመፅሐፍ ቅዱስት ከመንፈስ ቅዱስ ለሚመጣው ተጨማሪ መረዳት ክፍት መሆን አለባቸው ፡፡ እግዚአብሔርም የሚፈርድብን ባን የመረዳት ደረጃ እና ያንንም መረዳት በምንኖረው ኑሮ ነውና፡፡

---

▣ **"የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይነግርምና የሚመጣውንም ይነግራችኋል"** ሊመጡ ያሉት ነገሮች የሚያመለክቱት በቅር ስለሚሆኑት የመመኘርት ክስተቶች ነው፤ ቀራኒዮ፣ ትንሳኤው ዕርገቱ እና በዓለ ሃምሳ፡፡ ይህ ሊመጣ ያለውን (የወደፊቱን) የነቢይነት አገልግሎት አያመለክትም (አጋቦስ፣ ሐዋ 21:10፣ በ14:19 ላይ ትንቢት የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ)፡፡

ኢየሱስ እንዳደረገው መንፈስ እውነትን ከአብ ተቀብሎ ለአማኞች ያስተላልፋል፡፡ ከአብ የሆነው የመንፈስ ቅዱስ መልእክት ይዘቱ ሳይሆን መንገዱ ወይም አሠራሩ ዋናው (ልዩ ርዕስን በ14:26 ላይ ይመ)፡፡ አብ በአሠራር ደረጃ ሁልጊዜ የበላይ ነው (1ቆሮ 15፡27-28)፡፡

16:14-15 **"እርሱ ያከብረኛል: ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና"** የመንፈስ ቅዱስ የመጀመሪያው ሥራ መሲሑን ኢየሱስ ከፍ ማድግና እርሱን መግለጥ ነው (ቁ. 15)፡፡ መንፈስ ቅዱስ የሚያመክተው ራሱን ሳይሆን ኢየሱስን ነው (14:26)፡፡

▣ **"ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው"** እንዴት የሚያስደንቅ ንግግር ነው (3:35፣ 5:20፤ 13:3፤12:10 ማቴ 11:27)፤ ይህ ከማቴ 28:18 ፤ ኤፌ 1:20-22፤ ቆላ 2:10 1ጴጥ 3:22 ጋር ተሳሳይ ነው፡፡

በስላሴ ውስጥ አንዱ ከሌላው የመብለጥ ሳይሆን የግብር ቅደም ተከተል አለ፡፡ ኢየሱስ አብን እንዳሳየ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን ያሣያል፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 16÷16-24

**16ጥቂት ጊዜ አለ÷ አታዩኝምም፤ ደግሞም ጥቂት ጊዜ አለ÷ ታዩኛላችሁም÷ እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና፡፡ 17ከደቀ መዛሙርቱም አንዳንነዶቹም እርስበርሳቸው ጥቂት ጊዜ አለ÷ አታዩኝምም፤ ደግሞም ጥቂት ጊዜ አለ÷ ታዩኛላችሁም፤ ደግሞ ወደ አብ እሄዳለሁና የሚለን ይህ ምንድነው? ተባባሉ፡፡ 18እንግዲህ÷ ጥቂት የሚለው ይህ ምንድን ነው? የሚናገረውን አናውቅም አሉ፡፡ 19ኢየሱስም ሊጠይቁት እንዳወደዱ አውቆ እንዲህ አላቸው፡- ጥቂት ጊዜ አለ÷ አታዩኝምም፤ ደግሞም ጥቂት ጊዜ አለ÷ ታዩኛላችሁም ስላልሁ÷ ስለዚህ እርስ በርሳችሁ ትመራመራላችሁን? 20እውነት እውነት እላችኋለሁ÷ እናንተ ታለቅሳላችሁ ሙሾም ያወጣላችሁ÷ ዓለም ግን ደስ ይለዋል፤ እናንተም ታዝናላችሁ÷ ነገር ግን ኀዘናችሁ ወደ ደስታ ይለወጣል፡፡ 21ሴት በምትወሰድበት ጊዜ ወራትዋ ስለደረሰ ታዝናለች፤ ነገር ግን ሕፃን ከወለደች በኋላ÷ ሰው በዓለም ተወልዶአልና ስለ ደስታዋ መከራዋን ኋላ አታስበውም፡፡ 22እንግዲህ እናንተ ደግሞ አሁን ታዝላናላችሁ፤ ነገር ግን እንደገና አያችኋለሁ፣ ልባችሁም ደስ ይለዋል÷ ደስታችሁንም የሚወስድባችሁ የለም፡፡ 23በዚያን ቀንም ከእኔ አንዳች አትለምኑም፡፡ እውነት እውነት እላችኋለሁ÷ አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል፡፡ 24እስከአሁን በስሜ ምንም አልለመናችሁም፤ ደሰታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበሉማላችሁ፡፡**

16:16 **"ጥቂት ጊዜ አለ"** ይህ ሐረግ ብዙውን ጊዜ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ይጠቀሳል (1:33፣ 12:35፣ 13:33፣ 14:19)፡፡ ስለዚህ ሐረግ ትርጉም በርካታ ፅንሰ-ሐሳቦች አሉ፡፡

1. የድህረ ትንሣኤ መልክ/ገጽታ
2. ዳግም መመለስ
3. የኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ መምጣት

በዚህ ዓውድ መሠረት፤ ቁጥር 1 ብቸኛው አማራጭ ነው (ቁ.22)ደቀ መዛሙርት በዚህ ንግግር ግራ ተገብተው ነበር (ቁ. 17-18)፡፡

16:17 **"ከደቀመዛሙርቱም *አንዳንዶች* እርስ በርሳዣው..."** ይህ ልክ እንደ 13:36፣ 14:5፣ 8:22 ሌላው ጥያቄ ነው፡፡ ኢየሱስ እነዚህን ጥያቄዎች የሚጠቀመው እንደገና ሊያረጋግጣቸው እና ራሱንም ሊገልጥላቸው ነው፡፡ ይህ እውነትን ለመግለጥ ውይይትን መጠቀም የዮሐንስ ወንጌል ወንጌለ ባህሪው ነው፡፡ በዮሐንስ ወነጌል ውስጥ ከኢየሱስ ጋር ወይም ስለኢየሱስ የተደረጉ ሃያ ሰባት ንግግሮች ይገኛሉ፡፡ ከዚህም ባሻገር ኢየሱስን ይሰሙ የነበሩት እርሱ የናገረውን እንዳልተረዱት የሚያሳይመሆኑ የወንጌሉ ሌላው መለያ ነው፣ ምክንያቱም እርሱ ከላይ ሲሆን እነርሱ ደግሞ ከታች ናቸውና፡፡

▣ **"ወደ አብ እሄዳለሁና"** ኢየሱስ ይህን የጠቀሰው በ16:5 ላይ ሲሆን ይህ ልክ በ16:10 ላይ "ገና ጥቂት ጊዜ አለ" ብሎ እንደጠቀሰው ሐረግ ነው፡፡ በዚህ ትርጉም መወረት ይህ ለየት ያለ የመድህነቱ መግለጫ ነው (13:1- 3፣ 16 : 28፣ 17:24)፡፡

▣ **"አታዩኝም ... ታዩኛላችሁ"** በቁ 16 እና 17 ላይ "ማየት" ለሚለው ቃል የተጠቀሱት ሁለት የተለያዩ ቃላት አሉ፡፡ ተመሳሳይም ይመስላሉ፡፡ ይህም ከሆነ እንግዲህ የተጠቀሰው አንድ የጊዜ ገደብ ብቻ ነው፤ ይህም ምናልባት ኢየሱስ በመስቀል ላይ በሞተበት እና በትንሳኤው ማለዳ መካከል ያለው ቀን ነው፡፡

ሌሎች ደግሞ ሁለቱ ግዎችና ሐረጐች የሚያመለክቱት "ሥጋዊ" እይታ እና "መንፈሳዊ" እይታን ነው ሲሉ በዚህም አንፃር የሚያሳዩት (1) በቀራኒዮ እና በእሁድ ማለዳ መካከል ያለውን ጊዜ ወይም (2) በእርገቱ እና በዳግም መመለሱ መካከል ያለውን ጊዜ፡፡

በቁ. 16 እና 17 ያለው ግሥ *Thiorei* በአሁን ጊዜ አመልካች ግሥ መጠቀሱ እና ዳግም (horao) የሚለው ቃል በቁ. 16 እና 17 ላይ መጠቀሱ በመጪ ጊዜ አመልካች ተመሳሳይ ፅንሰ ሐሳብን የሚደግፍ ይመስላል፡፡

16:18 **"አሉ"** ይህ የድርሰት መጠናቀቅን አመልካች ጊዜ ሲሆን ሊኖረው የሚችለው ትርጉም (1) ደጋግመው መናገራቸውን ወይም (2) ማለት መጀመራቸውን ነው፡፡

▣ "የሚለው ይህ ምንድነው?" ከእርሱ ጋር የነበሩት፣ የሰሙት እና ተአምራቱን ያዩት ሁልጊዜ የሚጋራቸውን አይረዱም ነበር (8:27፣ 3:10:6:12:16/ 18:4)፡፡ ይህንን ነው እንግዲህ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት የሚረዳው/የሚያስወግደው፡፡

16:19 **"ኢየሱስም ሊጠይቁት እንደወደዱ አውቆ"** ኢየሱስ ብዙውን ጊዜ የሰዎችን ሐሳብ ያውቅ ነበር (2:25/ 6:61-64፣13:11)፡፡ ይህ በእርግጠኝነት ለመናገር/ለማወቅ የሚያስቸግረው (1) መለኮታዊ ባህሪውይን መሆኑን (2) ስለሰዎችና ሁኔታዎች ያለው መረዳት መሆኑን ወይም (3) ሁለቱንም መሆኑን ነው፡፡

16:20 **"እውነት እውነት እላችኋለሁ"** ይህ ቃል በቃል "አሜን፣ አሜን" ማለት ነው (ልዩ ርዕስን በ1:51 ላይ ይመ)፡፡ "አሜን" የብሉይ ኪዳን ቃል ሲሆን *amaN, emeth, emuNah* ይህም የተጠቀሰው "እምነት" ለሚለው ቃል ነበር (ዕንባ 2:4)፡፡ የመጀመሪያው የቃሉ መሠረት አመጣጥ "መጥናት" ወይም "እርግጠኛ መሆን" ማለት ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ታማኝነት ለመግለፅ ዘይቤያዊ አነጋገር ይጠቀስ ነበር፤ ይህም እምነት ወይም ታማኝነት ለሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሀሳብ መነሻ ነው፡፡ ንግግርን በዚህ ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰው ኡየሱስ ነበር፤ ይህም "ይህ አስፈላጊና የታመነ ንግግር ስለሆነ በጥብቅ ስሙት" የሚልአንድምታ ያለው ይመስላል፡፡

▣ **"እናንተ ታለቅሳላችሁ፤ ሙሾም ታወጣላችሁ"** ይህ በአይሁድ ባህል ሐዘንን ለመግለን የሚደረግ ሲሆን ድምፀን ከፍ አድርጎ ኀዘንን መግለን ነው (11:31፣ 33፤ 20:11)፡፡ የደቀመዛሙርቱን ኀዘን ለመግለፅ ኢየሱስ ነገሩን ለማጉላት "እናንተ" የሚለውን ሦስት ጊዜ ይጠቅሰዋል (ቁ. 20 [ሁለት ጊዜ] እና ቁ. 22)፡፡ መሪነት ማለት

1. አገልጋይነት ነው
2. በዓለም መጠላት ነው
3. እንደ ጌታ መሰደድ ነው፡፡

▣ **"እናንተም ታዝናላችሁ: ነገር ግን ኀዘናችሁ ወደ ደስታ የለወጣል"** ደቀመዛሙርት ባሉበት ግራ መጋባትና አለመረዳት እንዲህ አይነቱ ተስፋ በጣም ታላቅ ነው፡፡ ኢየሱስ የሰጣቸው ማንኛውም የተስፋ ቃል ከትንሳኤው በኋላ በመጀመሪያው እሁድ ምሽት ተፈፅሟል በዚህም፡-

1. እንደማይተዋቸው (14:18/ 16:16፣ 19:20-19)
2. ወደእነርሱም እንደሚመጣ (14:18-16፣ 16:19፣ 20:19)
3. ሰላምን እንደሚሰጣቸው (16:22፣ 20:19)
4. መንፈስን እንደሚሰጣቸው (15:26፤ 20:22)

16:21 **"ሴት በምትወስድበት ጊዜ"** ይህ ዘይቤያዊ አነጋገር በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን የተለመደ ነው፡፡ በተለምዶ የሚጠቀሰው የወሊዱን ድንገተኝነትና የማይቀር መሆኑን ለማጉላት ነው፤ ነገር ግን በዚህ ዳውድ ላይ ትኩረቱ ሕፃኑ ከመወለዱ በፊትና በኋላባው የእናትየው አመለካከት ላይ ነው፡፡ ይህ ዘይቤ ብዙውን ጊዜ ከመጨረሻው ዘመን "የምጥ ጣር" ጋር ተያያዥነት አለው (ኢሳ 26:17-18:66:7-14፣ ማር 13:8)፡፡ ይህ ነው በትክክል ኢየሱስ ለማመልከት የፈለገው እና ከመስቀሉ ባሻገር ያሉት ደቀመዛሙርት (ትንሳኤና እርገት) በትክክል የኢየሱስን ቃል ሊረዱ ያልቻሉት!

16:23 **"በዚያን ቀንም"** ይህ ሌላው የእብራይስጥ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን (ልክ እንደሐፃን ውልደት ቁ. 21) ይህም በተለምዶ ከሚመጣው ዘመን ጋር የተቀራኘ ነው (14:20፤ 16:25:26)፡፡

▣ **"ከእኔ አንዳች አትለምኑም"** በዚህ ጥቅስ ላይ "መለመን" ወይም "መጠየቅ" ለሚለው ሁለት የተለያዩ ቃላት አሉ (ቁ 26)፡፡ የመጀመሪያው የሚያመለክተው "ጥያቄ ጠይቁ" የሚለውን ነው (16:5፣ 19:30)፡፡ ይህ ትክክለኛው ትርጉም ከሆነ ኢየሱስ ያመለክት የነበረው በምዕራፍ 13-17 ውስጥ ላሉት ሁሉም ጥያቄዎቻቸው ነው ማለት ነው (13:36፤ 14:5፣ 8:22፣ 16:17-18)፡፡ ሁለተኛው ቃል ደግሞ የሚያመለክተው የመንፈስ ቅዱስን መምጣት ነው (14:16-31፣ 15:26-27፣ 16:1-15)፤ ይህም ሁሉንም ጥያቄዎቻችሁን የሚመልስ ነው፡፡

በአንዳንድ መንገዶች ይህ ሐረግ የሚያስታውሰኝ "አዲሱን ኪዳንም" (ኤር 31:31-34) ሲሆን በዚህ አዲሱ ዘመን ለሁሉም አማኞች ሙሉ የሆነ መረዳትን እንደሚያመጣላቸው ነው፡፡

▣

| | |
|---|---|
| NASB | **"አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ"** |
| NKJV | **"አብን በስሜ ምንም ብትለምኑት"** |
| NRSV | **"አብን በስሜ ምንም ብትጠይቁት"** |
| TEV | **"ምንም ነገር በስሜ ብትለምኑ አብ ይሰጣችኋል"** |
| NJB | **"ከአብ የምትለምኑትን ማንኛውንም ነገር በስሜ ይረዳችኋል"** |

*ይህ ያልተወሰነ አዛማጅ ሐረግ እንጂ የሁኔታ መሟላትን የሚጠብቅ አረፍተ ነገር አይደለም፡፡ በኢየሱስ ስመ መለመን ማለት ልመናዎቻችንን ልማዳዊ በሆነ ሥርዓት ማጠቃለል ሳይሆን በክርስቶስ ፈቃድ ሐሳብና ማንነት መሠረት መፀለይ ነው* (1ዮሐ 5:13)፡፡ *የ15:16 ማብ ይመ፡፡ ልዩ ርዕስ ፀሎት ያልተወሰነ ነገር ግን የተወሰን የሚለውን በ3፡22 ላይ ይመልከቱ፡፡*

*"በስሜ" ለሚለው ሐረግ ልዩነት ያለው ምንም አለ፤ መሔድ ያለበት ከ"መጠየቅ" ወይስ "መስጠት" ከሚለው ጋር ወይስ ከሁለቱም ጋር? ዓውዱ የሚያመለክተው ፀሎትን ስለሆነ ምናልባት ሊሔድ የሚገባው መጠየቅ" ከሚለው ጋር ነው፤ ምንም እንኳን እውነታው ማንኛውም ከአብ የሚመጣው ነገር በኢየሱስ በኩል ቢሆንም* ("ስሜ" 14:13-14፣ 16፤ 16፡15፤ 24፤ 26)፡፡ *በ14፤14 ላይ የእግዚአብሔር ስም የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡*

**16፤24 *"ለምኑ ትቀበሉማላችሁ"*** *"ለምኑ" የሚለው የአሁን ጊዜ አድራጊ ግሥ አመልካች ነው፡፡ ይህም ፅናትና ቀጣይነት ያለውን የአማኞችን ፀሎት ያመለክታል፡፡ በአንድ ትርጉም አማኞች አምነው አንድ ጊዜ መለመን አለባቸው፤ ነገር ግን በሌላ አንፃር ፀሎት ከእግዚአብሔር ጋር ቀጣይነት ያለው ሕብረት ስለሆነ መለመንን አታቋሙ ማለቱ ነው* (*ማቴ* 7:7-8፣ *ሉቃ* 11:5-13፣ 18:1-8)፡፡

▣ ***"ደስታችሁ ፍፁም እንዲሆን"*** *ይህ ተመሳሳይ ትርጉምን የያዘ ተደርጐ ግሥ አመልካች ነው* (1*ዮሐ* 1:4)፡፡ *የፀሎታችን መልስ የደስታችን ምክንያት ነው! ደስታ የኢየሱስ ተከታዮች ልዩ ባህሪይ ነው* (15:11፣ 26:20፣ 21:24፣ 17:13)፡፡

| NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 16÷25-28 |
|---|
| **[25]*ይህን በምሳሌ ነግኤችኋለሁ፤ ነገር ግን ስለ አብ ለእናንተ በግልጥ የምናገርበት እንጂ ከዚያ ወዲያ በምሳሌ የማልናገርበት ሰዓት ይመጣል፡፡ [26]በዚያን ቀን በስሜ ትለምናላችሁ፤ እኔም ስለ እናንተ አብን እንድለምን የምላችሁ አይደለሁም፤ [27]እናንተ ስለ ወደዳችሁኝ ከእግዚአብሔርም ዘንድ እኔ እንደወጣሁ ስላመናችሁ አብ እርሱ ራሱ ይወዳችኋልና፡፡ [28]ከአብ ወጥቼ ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤ ደግሞ ዓለምን እተወዋለሁ÷ ወደ አብም እሄዳለሁ፡፡*** |

**16:25 *"በምሳሌ ነግሬአችኋለሁ"*** *የኢየሱስ ትምህርቶች ሁለት አይነት ውጤት ነበራቸው፤* (1) *ማስተዋልን ይሰጣሉ* (2) *አስተዋልን ይከለክላሉ* (*ማር* 4:10-11፤ *ኢሳ* 6:9-10 *ኤር* 5:21)፡፡ *የአርማጌዜ ልብ ለሚረዳው ነገር ውጤታማነት ወሣኝ ጉዳይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የዳኑት እንኳን የሚያስተውሏቸው እውነቶች ነበሩ (ስቅለት፣ ትንሣኤ፡ የትንሳኤ መስኰች/መስክ፣ ዕርገት የመሳሰሉት)፡፡*

*ለሁለቱ የኤማሁስ መንገደኞች* (*ሉቃ* 24: 13-35) *የታየው ድህረ - ትንሣኤ ገፅታ ምናልባት ኢየሱስ ሐዋርያቱን እንዴት እንዳስተማራቸው ፍንጭት ይሰጠናል* (*ቁ* 25-27፤32)፡፡ *ኢየሱስ ራሱ በድህረ ትንሳኤ መልኩ ብሉይ ኪዳን እንዴት በሥራ ላየ እንደዋለህ ስለእርሱም አገልግሎት አስቀድሞ እንዴት እንዳስጠነቀቀ አሳይቷል፡፡ ይህም በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ጴጥሮስ ላደረገው ስብከት በምሳለነት የተቀመጠ ነበር* kerygma፣ *ልዩ ርዕስን በ*5:39 *ላይ ይመልከቱ*)፡፡

▣ ***"በግልፅ የምናገርበት"*** *ድፍረት የሚለውን ልዩ ርዕስ በ7፡4 ላይ ይመልከቱ፡፡*

**16:26 *"በዚያን ቀን በስሜ ትለምናላችሁ፣ እኔም ስለ እናንተ አብን እንድለምን የምላችሁ አይደለሁም"*** *ይህ ጥቅስ ጠቃሚ የሆነን እውነት ይገልፅል፡፡ ብዙዎች የዘመናችን ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን በቀጥታ መቅረብ እንደማይችሉ ይሰማቸዋል! ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው*

1. *መንፈስ ለአማኞች እንደሚፀልይ* (*ሮሜ* 8:26-27)
2. *ወልድ ለአማኞች እንደሚማልድ* (1*ዮሐ* 2:1)
3. *ከክርስቶስ የተነሣ አማኞች በፀሎት ወደ እግዚአብሔር በቀጥታ መቅረብ እንደሚችሉ*

**16:27 *"አብ ራሱ ይወዳችኋልና"*** *"መውደድ" ለሚለው የግሪኩ ቃል* Phileo (*ፌሎ*) *ሲሆን በ* 5:20 *ላይ የተጠቀሰው አብ ለኢየሱስ ያለውን ፍቅር ለማመልከት ነው፡፡ ይህም ዮሐ* 3:16*ን* (agapao) *የሚያጠናክር አስደናቂ ንግግር ነው፡፡ እግዚአብሔር ግድ የለሽ አምላክ ሳይሆን ኢየሱስ አብሮት የሚሠራና የሰውን ልጆች የመቤዥርት ሥራን ወይም ዓላማውን የሚፈፅም ነው፡፡*

▣

**NASB** **"ከአብ"**

**NKJV, NRSV**

**TEV, NJB** **"ከእግዚአብሔር"**

*ሁለት የግሪክ ምንጮች አሉ፤* (1) *"እግዚአብሔር" ወይም "አባት" እና* (2) *የመስተፀአምር መኖር ወይም አለመኖር፡፡ "እግዚአብሔር" የሚለው ቃል በ*MSSP[5]: N *ምንጮች ሲጠቀስ፤* " the eNd " *በ* MSSP[3] *እና በ* w

ውስጥ ተጠቅሷል፡፡ ይህ በጣም አስቸጋሪና ያልተለመደ የቃል አፃፃፍ ይመስላል፡፡ ይህ የቴክስትቸዋል ክሪትሲዝም አንዱ የመዋል ባህርይ ሲሆን (ማውጫውን ይመልከቱ፡፡) በጣም አስቸጋሪውና ያልተለመደው ጥቅስ ምናልባት የመጀመያው ሲሆን ፀሐፊዎችም ለመለወጥ ያሰቡት ይመስላል፡፡ የUBS[4] የግሪኩ አዲስ ኪዳን የ "C" ደረጃን ይሰጠዋል (ለመወሰን የሚያስቸግር)

ይሁን እንጂ *Father* የሚለው ቃል በN' ላይ ሲጠቀስ *The Father* የሚለው ደግሞ በ B፣ C፣ D እና L ውስጥ ተጠቅሷል፤ ይህም ለዳውዱ ከሁሉም ይልቅ የሚስማማው ነው፡፡

▣ **"እናንተ ስለወደዳችሁኝ ከእግዚአብሔርም ዘንድ እኔ እንደወጣሁ ስላመናችሁ"** እነዚህ የድርጊት መጠናቀቅን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ መውደድና ማመን ከአብ ጋር ሕብረት ለማድረግ መሠረት የሚሆኑ ናቸው፡፡ በባርክሌይ ኒውማንና በኢውጂን ኢዳ የተፃፈው "A TraNslator's HaNdbook oN the Gospel of JohN" የሚለው መጽሐፍ ላይ ያለው ንግግር በጣም አስደሳች ነው፡፡

"እነዚህም ንግግሮተ የሚያመለክቱት ለዮሐንስ ፍቅር፣ መታዘዝ እና እመነት የሚሉት ሐሳቦች በቀላሉ የሚያሳዩት አንድ ሰው ከወልድ ጋር ያለው ግንኙነት የሚያሳዩ የተያዩ መንገዶች ናቸው" (ገጽ 518)፡፡

"ስላመናችሁ" ለሚለው በ2:23 ላይ ያለው ልዩ ርዕስ፡፡ የዮሐንስ "ማመን" የሚለውን ቃል አጠቃቀም ይመልከቱ፡፡

16:28 **"ከአብ መጥቼ ወደ ዓለም መጥቻለሁ"** ይህ የድርጊት መጠናቀቅን የሚያመለክተው የግሪኩ አድራጊ ግሥ ነው፡፡ ኢየሱስ በቤተልሔመ ተወለደ (ተሰግዋ) እንዲሁም የእሱ መምጣት ያመጣው ውጤት (ዕብ 7:25፤ 9:24፤ 1ዮሐ 2:1)፡፡ ከሁሉም አስቀድሞ እንደነበረ በዮሐ 1:1 ላይ እንደተገለፀው የኢየሱስም ወደ ክብሩና ሥልጣኑ መመለሱ በዚህ ጥቅስ ላይ ተረጋግጧል (17:5፤24)፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 16÷29-33

**29ደቀ መዛሙርቱ፡- እነሆ÷ አሁን በግልጥ ትናገራለህ፣ በምሳሌም ምንም አትነግረም፡፡ 30ሁሉን እንድታውቅ ማንምም ሊጠይቅህ እንዳትፈልግ፣ አሁን እናውቃለን፤ ስለዚህ ከእግዚአብሔር እንደወጣህ እናምናለን፣ አሉት፡፡ 31ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰላቸው፡- አሁን ታምናላችሁን? 32እነሆ÷ እያንዳንዳችሁ ወደ ቤት የምትበታተኑበት እኔንም ለብቻዬ የምትተውበት ሰዓት ይመጣል÷ አሁንም ደርሶአል፤ ነገር ግን አብ ከእኔ ጋር ስለሆነ ብቻዬን አይደለሁም፡፡ 33በእኔ ሳላችሁ ሰላም እንዲሆንላችሁ ይህን ተናግሬአችኋለሁ፡፡ በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሀሰንፌዋለሁ፡፡**

16:29 **"በግልፅ ትናገራለህ"** በ7:4 ላይ ድፍረት *Parrhesia* የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

16:30 ይህ ዓረፍተ ነገር ሊረዱት የሚገባው ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ በቁ. 19 ላይ ያነሡትን ጥያቄ ከማወቁ አንፃር ነው፡፡ ይህ እነርሱ ያደረጉት ንግግር በራሱ የሚያመለክተው የእነርሱን ማድረግ ነገር ግን አሁንም ያልተሟላ እመነት መሆኑን ነው፡፡ ብዙ አይተዋል ብዙም ሰምተዋል፤ ይህ ድርጊት (ቁ. 19) በመረዳታቸው ላይ እንደ ትልቅ የለውጥ ሥፍራ ሊቆጠር ይችል ይሆን፤ ይህ ለእኔ የሚመስሉኝ ጴጥሮስ ሆን ብሎ ከተናገራቸው ነገር ግን ከተነጋገሩ ንግግሮች እንደ አንዱ ነው (*Jerome Biblical commeNtary* ገጽ 456 ይመልከቱ፡፡)

16:31 **"አሁን ታምናላችሁን?"** ይህ ጥያቄ ወይም ንግግር ሊሆን ይችላል፡፡ አብዛኞቹ የዘመናችን የተሻሻሉ የእንግሊዘኛ ትርጉሞች የሚረዱት እንደ ጥያቄ ነው፡፡ በዚህ ወሣኝ ሰዓት እንኳን የሐዋርያቱ እምነት የተሟላ አልነበረም፡፡ የዘመናችንም አማኞች የመጀመሪያ ግን ደካማ እምነታቸው ባላቸው መረዳት መሠረት ለኢየሱስ ምላሽ ሲሰጡ በእግዚአብሔር ዘንድ የተቀባይነት አለው፡፡ የደቀመዛሙርቱም እ ምነት ማጣት የሚገለጠውም ኢየሱስን በመመከራውና በመስቀሉ ወቅት ትተውት ሲሸሹ ነው፡፡

16:32 **"እያንዳንዳችሁ ወደ ቤት የምትበታተኑበት፣ እኔንም ለብቻዬ የምትተውበት ሰዓት ይመጣል"** በግልፅ መረዳት እንደሚቻለው ዮሐንስ ብቻ ነበር በመከራውና በስቅለቱ ጊዜ የነበረው (ማቴ 26:31 ከዘካ 13:7)፡፡ ዮሐንስ 21:1-3 በርካታዎቹ ሐዋርያት ወደ ዓሣ ማጥመድ ተግባራቸው እንደተመለሱ አስተያየትን ይሰጣል፡፡

ኢየሱስ ያጣው የሰውን አብሮነት (ማቴ 26:38፤ 40-41:43:45) እንጂ የመለኮትን አብሮነት አልነበረም (8:16፤29) ይህም አብሮነት የዓለምን ኃጢአት ሁሉ ተሸክሞ (ማቴ 27:45-46) እስከ መስቀሉ ድረስ የዘለቀ ነበር፡፡

▣

| | |
|---|---|
| NASB | **"እያንዳንዳችሁ ወደ ቤት"** |
| NKJV | **"እያንዳንዳችሁ ወደ ራሳችሁ"** |
| NRSV | **"ወደ ራሱ ቤት"** |
| NJB | **"ወደ ራሱ መንገድ"** |
| TEV | **"ወደ ራሳችሁ ቤት"** |

REB, NET
NIV **"ወደ ራሱ ቤት"**

NKJV *ቃል በቃል የተወሰደ ነው፡፡ ብዙዎቹ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች የሚገምቱት የአንድን ሰው ቤት እንደሚያመለክት ነው፡፡ ቡስትማን ደግሞ "ንብረትን" ወይም "ባለቤትነትን" ያመለክታል ብሎ ይገልፃል* (NIDOTTE:- *ቅፅ* 2፣ *ገጽ* 839)፣ *ይህም ኢየሱስን እንደፈጣሪ የሚያመለክት ነው* (1፡3 1ቆሮ 8፡6 ቆላ 1፡16 ዕብ 1፡2 )፡፡

**16፡33 "በእኔ ሳላችሁ ሰላም እንዲሆንላችሁ"** *ይህ የአሁን ጊዜን ስሜት አመለካች አድራጊ ግስ ነው* (14፡27)፡፡ *የሚታየውም ሆነ የማይታየው ሰላም የሚገኙትና የሚጠበቁት በክርስቶስ ውስጥ ነው፣ በ*14:27 *ላይ ያለውን ሰላም የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡*

▣ **"ዓለም"** *ዮሐንስ በዚህ ዓውድ ውሰጥ "ዓለም" ቃል የሚጠቀመው ከእግዚአብሔር ተለይቶ የተደራጀውንና የሚሠራውን የሰውን ማህበረሰብ ነው በ*14:17 *ላይ* KOSMOS *የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመለከታል፡፡*

▣ **"መከራ አለባችሁ"** *ኢየሱስ የተቀበለውን መከራ እነርሱም ይቀበሉታል* (15:18-25 *ማቴ* 5:10-12፣ *ሐዋ* 14:22፣ 1*ተሰ* 3:3) ፡፡ *መከራውም (THLIPSIS) የኢየሱስን ተከታዮች የሚገለጡበት መንገድ ነው፡፡*

*በዮሐንስ ራዕይ ላይ "ቁጣ" በሚለውና "ስደት" በሚለው መካከል ሥነ-መለኰታዊ ልዩነት አለ፡፡ የእግዚአብሔር ቁጣ በአማኞች ላይ አይወድቅም ነገር ግን የማያምኑት ቁጣ በአማኞች ላይ ይሆናል፡፡ "የዚህ ዓለም ብርሃንን" በማጥቃት ዓለም ራሱን እንደ ሰይጣን/ዲያብሎስ ልጆች ይገልጣል፡፡* (1:1-18፣ 3:17-21)፡፡

▣ **"አይዞአችሁ"** *ይህ ትእዛዝ አዘል የአሁን ጊዜ አድርጎ ግሥ ነው* (*ማቴ* 9:2፣ 22፣ 14:27፣ *ማር* 6:50፣ 10:49 *ሐዋ* 23:11)፡፡ *ይህ ለኢያሱ የተነገረውን የያህዌን ቃል የመስላል* (*ኢያ* 1:6፣9፣18፣ 10:25)፡፡

▣ **"እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ"** *ይህ የድርጊት መጠናቀቅን አመልካች ግሥ ነው፡፡ የኢየሱስ ማሸነፍ የተረጋገጠው ከጌቴሴማኒ፣ ከቀራኒዮ፣ እንዲሁም ከባይው መቃብር በፊት ነበር* (*ሮሜ* 8:37፣ 1*ቆሮ* 15:57 2*ቆሮ* 2:14፣ 4:7-15)! *እስከመጨረሻው የሚዘልቅ ዱዋሊዝም የለም! እግዚአብሔር በዙፋኑ ላይ ነው!*

*ኢየሱስ አብን በመውደድና በመታዘዝ ዓለመን አንዳሸነፈ አማኞችም በእርሱ አሸናፊዎች ናቸው፡፡* (1*ዮሐ* 2:13-14፣ 4:4፣ 5:4-5፣ *ራዕ* 3:21፣ 12:11)፡፡

## የውይይት ጥያቄዎች

*ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ሊሆን የሚችል ማብራሪያ በመሆኑ ለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጐም ኃላፊነት አለብህ፡፡ እያንዳንዳችን ልንሔድ የሚገባን ባለን መረዳት መጠን ነው፡፡ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጐም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣችሁ ናችሁ፣ በመሆኑም ይህንን በሚያብራራው ሰው ላይ ብቻ ልትተው የሚገባ አይደለም፡፡*

*እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ባሉት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ በጥሞና እንድታስቡበት ለመረዳት ይቻል ዘንድ ነው፣ በመሆኑም ጥያቄዎቹ እንደ ሐሳብ - አነሳሽ ሆነው እንጂ በግልፅ ወይም በቀጥታ አይደለም፡፡*

1. *በምዕራፍ* 15 *እና በምዕራፍ* 16 *መካከል ያለው ግንኙነት ምንድነው?*
2. *ከ ቁጥር* 5 *ጋር በተዛመደ* 13:36*ን እንዴት ትረዳዋለህ?*
3. *ለሚጠፋው ዓለመ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ምንድነው?*
4. *ለአማኞች የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ምንድነው?*
5. *ከዘመናችን የዲኖሚኔሽን ዝንባሌ አንፃር ቁጥር* 26-27 *አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት ምንድነው /ለምን አስፈላጊ እውነት ሆነ?*

# ዮሐንስ 17

## በተሻሻሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀፅ አከፋፈል

| UBS[4] | NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| የኢየሱስ ፀሎት | ኢየሱስ ስለራሱ ፀለየ | የኢየሱስ የሊቀ ካህንነት ፀሎት | ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ | የኢየሱስ ፀሎት |
| 17 : 1-5 | 17:1-5 | 17:1-5 | 17:1-5 | 17:1-23 |
| | ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ፀለየ | | | |
| 17:6-19 | 17:6-19 | 17:6-19 | 17:6-8 | |
| | ኢየሱስ ለአማኞች ሁሉ ፀለየ | | 17:9-19 | |
| 17:20-26 | 17:20-26 | 17:20-24 | 17:20-23 | |
| | | | 17:24-26 | 17:24-26 |
| | | 17:25-26 | | |

**ሦስተኛ የንባብ ዑደት (አንቀጽ 5 ይመልከቱ፡፡)**
***የመጀመሪያውን ፀሐፊ ሐሳብ በአንቀፅ ደረጃ መከተል***

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ሊሆን የሚችል ማብራሪያ ሲሆን /በመሆኑ/ ለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን መጓዝ ያለብን ባለን መረዳት መጠን ሊሆን ይገባል፡፡ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጎም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣችሁ ናችሁ፡፡ በመሆኑም ይህንን ሐሳብ መጽሐፍ ቅዱስን በሚያብራራው ሰው ላይ መተው የለብህም፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፤ ዋና ሐሳቦችንም ለየቸው፡፡ ያንተን የዋና ሐሳቦች አከፋፈልን ከተሻሻሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ጋር አስተያያቸው፡፡ በአንቀን መከፋፈል በእግዚአብሔር ምሪት የሚናወን ባይሆንም የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም እምብርት የሆነውን የመጀመሪያው ፀሐፊ ዋና ሐሳብ ለማወቅ ግን ቁልፍ ጉዳይ ነው፤ እያንዳንዱ አንቀፅ የሚናገረው ስለ አንድ ዋና ሐሳብ ብቻ ነው፡፡

1. *የመጀመያ አንቀፅ*
2. *ሁለተኛ አንቀፅ*
3. *ሦስተኛ አንቀፅ*
4. *ወዘተ*

**ዓውዳዊ ግንዛቤዎች/መረዳቶች፤ ቁ1-26**

ሀ. *ታሪካዊ መነሻ*
1. ይህ ምዕራፍ የኢየሱስ የሊቀ ካህንነት ፀሎት ሲሆን የፀለየውም፤
   ሀ. ስለራሱ /ቁ. 1-5/
   ለ. ስለ ደቀመዛሙርቱ /ቁ. 6-19/
   ሐ. ወደፊት እርሱን ለሚከተሉት /ቁ. 20-26/

ይህም ፀሎት የተደረገው በልበ ሙሉነት እንጂ ሥልጣንን በመልቀቅ ድባብ አልነበረም (16:33)

2. ይህ ከሁሉም የኢየሱስ ፀሎቶች ረጅሙ ነበር
3. ይህን ምዕራፍ ለመከፋፈል አስቸጋሪ ነው፤ ምክንያቱም ተመሳሳይ መነሻ ሐሳብ ያላቸው በተደጋጋሚ በመገለፃቸው ነው፤ ይህም የዮሐንስ ፅሑፎች መለያ ጠባይ ነው፡፡ ይህ ልክ እንደ ሥጋጃ ምንጣም ንድፎች የመደጋገም ባህሪይ ያለው ነው፡፡ በምዕራፉ ውስጥ ያሉት ቁልፉ ቃላት "ክብር"፤ መስጠት፣ መላክ/ "ስም"፣ "ዓለም" እና "አንድ" የሚሉ ናቸው፡፡
4. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ምንም አልተጠቀሰም፡፡ ይህ ከምዕራፍ 14-16 ድረስ በብዛት መንፈስ ቅዱስ ከመታወቁ አንፃር ያልተለመጠ ነው፡፡

ለ. የደቀመዛሙርት መለያ ባህርያት፤ ቁ. 6-19
1. የተመረጡ ናቸው፡፡
2. የሚታዘዙ ናቸው፡፡
3. እግዚአብሔርንና ክርስቶስን ያውቃሉ
4. እውነትን ይቀበላሉ
5. ኢየሱስ ፀልዮላቸዋል
6. በዓለም ይኖራሉ
7. በእርሱ ኃይል የተጠበቁ ናቸው
8. አብና ወልድ አንድ እንደሆኑ እንዲሁም እነርሱም አንድ ናቸው፡፡
9. የእርሱ ደስታ አላቸዋ
10. ከዚህ ዓለም አይደሉም
11. በእውነት የተለዩ ናቸው
12. እርሱ እንደተላከ የተላኩ ናቸው
13. አብ ኢየሱስን እንደወደደው እንዲሁ እነርሱም ተወደዋል

ሐ. "ክብር" የሚለው ቃል በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ
1. በስብከት ዋጅንት ውስጥ "doxa" ከሚለው የግሪክ ቃል የተተረጐመው ከ25 በላይ የእብራይስጥ ቃላት አሉ፡፡ ዋናው የብሉይ ኪዳን ቃል "kabod" የሚል ሲሆን ይህም ለየት ያለ "ከባድ" "ዋጋ ያለው"፡ "ዝና"፡ "ክብር" ወይመ "ድምቀት/ውበት" ማለት ነው፡፡
2. *doxa* የሚለው የግሪኩ ቃል ከ"ዝና" አንፃር "ማሰብ" ከሚለው ግሥ የመጣ ነው
3. በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ስለዚህ ቃል ብዙ አንደምታዎች አሉ፤
   ሀ. መለኮታዊ ክብር /ቁ. 5:24፣ 1:14፣ 14:40፤ 12:16
   ለ. በኢየሱስ ምልክቶች ትምህርቶች እና የመጨረሻዎቹ ሣምንታት ሥራዎች አማካኝነት የአብ መገለጥ (4:10-22፤ 1:14፤ 2:11፤ 7:18፣ 11:4፣40)
   ሐ. ከሁሉም በተለይ ደግሞ መስቀሉ (ቁ 1:4:7:39:12:123:13:31-32) በእነዚህ አጠቀቀሞች በግልፅ የሚታይ የተወሰነ ግንኙነት አለ፡፡ ዋናው ማዕከላዊ ዕውነት የማይታየው አምላክ በቃልና በሥራ በሰው አምሳል (ኢየሱስ ክርስቶስ) መገለጡ ነው፡፡

**የቃልና የሐረግ ጥናት**

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 17÷1-5
**[1-2]ኢየሱስም ይህንን ተናግሮ ወደ ሰማይ ዓይኖቹን አነሣና እንዲህ አለ አባት ሆይ ሰዓቱ ደርሶአል ልጅህ ያከብርህ ዘንድ በሥጋ ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጠኸው ለሰጠኸው ሁሉ የዘላለም ሕይወት ይሰጣቸውዘንድ ልጅህን አክብተው፡፡ [3]እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት፡፡ [4]እኔ ላደግው የሰጠኸኝን ሥራ ፈፅሜ በምድር አከበርኩህ፤ [5]አሁንም አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረን፡፡**

17:1 "ኢየሱስም ይህን ተናግሮ" ይህ በምዕራፍ 13-16 ላይ በላይኛው ደርብ ላይየተካሄዱትን ንግግሮች የሚያመለክት መሆን አለበት፡፡

▣ "ወደ ሰማይ ዓይኖቹን አነሣና" ይህ የተለመደው የአየሁዳዊያን የፀሎት ሁኔታ ነው፡፡ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚነጋገሩ አይነት እጆች፣ ራስ እና አይኖች ተከፍተውና ተዘርግተው ወደ ሰማይ ማሻቀብ ነው (11:4 ማር 7:34 ሉቃ 18:13 መዝ 123:1)፡፡ ኢየሱስ ብዙ ጊዜ በእንዲህ አይነት ሁኔታ ፤ ይህንንም ከሉቃስ ወንጌል ውስጥ በስረጃ ማረጋገጥ የሚቻል ነው፤ ሉቃ 3:21፣ 5:16፣ 6:12፣ 9:18፣ 28፤ 11:1፤ 22:41-45፤ 23:34፡፡

▣ "አባት" በዚህ ቃል ኢየሱስ አምላክነትን/መለኮትነትን ያረጋግጣል (11:41፤ 12:27፣28 ማቴ 11:25-27፣ ሉቃ 22:42፤ 23:34)፡፡ ኢየሱስ የተናጋረው በአማራማይክ ቋንቋ ነበር፡፡ የኢየሱስ የአራማይክ ቃል Abba የሚል ሲሆን

ይህም ልጅ በቤት ውስጥ አባቱን “ዳዲ” እያለ እንደሚጠራው ማለት ነው (ማር 14:36)፡፡ ይህም አጠራር የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ያልነበሩትን ያስቆጣቸውና ያስደነገጣቸው ሳይሆን አልቀረም፡፡

▣ **“ሰዓቱ ደርሶአል”** ይህም የሚያመለክተው ኢየሱስ የአገልግሎቱን ዓላማና የሚፈፀምበትን ጊዜ ጠንቅቆ እንደሚያውቅ ነው (2:4፣ 7:6፣ 8:30፣ 8:20፣ 12:23፣ 13:1)፡፡ እርሱም በይታወቁ ሁኔታዎች የሚወሰድ/የሚታለል አልነበረም፡፡

▣ **“ልጅህን አክብረው”** ይህ የግሪኩ ትዕዛዝ አዘል አድራጊ ግሥ ነው፡፡ ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ሁልጊዜ ሞቱን የሚያመለክተው በተመሳሳይ ቃላት ነው (ቁ. 4፣ 7:39፣ 12:23፣ 13:31-32)፡፡ ይህ ቃል ኢየሱስ ከፍጥረት በፊት የነበረውን መለኮትነት የሚያሳይ ነው (1:14 እና ቁ. 5:24)፡፡ የኢየሱስ ሥራዎች እግዚአብሔርን ያከብሩት ነበር፡፡ በዚህ ላይ አፀፋ መመለስ የሚል አንደምታን ማየት እንችላለን! በ1:14 ላይ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ፡፡ እንዲሁም ዓውዳው ግንዛቤዎችን በ”ሐ” ላይ ይመልከቱ፡፡

“ልጅ” የሚለው በ1ዮሐ 3:8 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

“ልጅ” በሚለው ላይ የምንሎች ልዩነቶች አሉ፡፡

1. ልጅ ከመስተፃምር ጋር በMSS p[60]፣N፣ B፣ C*፣ W ተጠቅሷል፡፡
2. ልጅ ከተውላጠ ስም ጋር በ በMSS A፣ D፣ C[2]፣ ተጠቅሷል፡፡

የ UBS[4] *መጽሐፍ ቅዱስ* ለቁ. 1 “B” ደረጃን ይሰጠዋል (ትክክል እንደማለት)፡፡

17:2 **“በሥጋ ሁሉ ላይ ሥልጣን”** ይህ ከአንድ ተራ የአናጢ ልጅ የወጣ ታላቅ ንግግር ነው (ዮሐ 5:27፣ 28:18፣ ሉቃ 10:22)፡፡ *“ሥልጣን”* የሚለው ቃል *Exusia* በ1:12፣ 5:27፣ 19:10-11 ላይ ከተጠቀሰው ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው፣ ይህም “ሕጋዊ መብት”፣ “ሥልጣን” ወይም “ኃይል” ተብሎ ሲተረጐም ይችላል፡፡

“በሥጋ ሁሉ” የሚለው ሐረግ ነጠላ ነው (የሰውን ልጅ/ዘር ለመጥቀስ የእብራይስ የአነጋገር ዘይቤ ነው፣ ዘፍ 6:12፣ *መዝ* 65:2፣ 145:21፣ ኢሳ 40:5፣ 66:23፣ ኢዩ 2:28)፡፡

▣ **“ለሰጠኸው ሁሉ”** “ሁሉ” የሚለው ቃል ግዑዝና ነጠላ ነው (7:24)፣ ይህም የሚያተኩረው በደቀመዛሙርት በክርስቶስ አካል ላይ እንጂ በግለሰቦች ላይ አየደለም! ግሱ የድርጊት መጠናቀቅ የሚያመለክት ገላጭ ሲሆን ይህም የሚናገረው ዘላቂነት ስላለው ስጦታ ነው ይህ ሐረግ የሚያረጋግጠው አስቀድሞ ማወቅንና መመረጥን ነው /ቁ. 6:9፣ 12፣ 6:37፣ 39 ሮሜ 8:29-30፣ ኤፌ 1:13-14)፡፡ በብሉይ ኪዳ መመረጥ ለአገልግሎት ነበር፣ በአዲስ ኪዳን ግን ለመንፈሳዊ፣ ለደህንነት እና ለዘላለማዊ ድነት ነው፡፡ አማኞችም እንዲያገለግሉ ተጠርተዋል፡፡ መመረጥ የእግዚአብሔር (የመለኰት) ድርሳ ብቻ ሣይሆን ከሰው ኃላፊት ጋር በቃል ኪዳን መያያዝ/መቆራኘት ያለበት ነው፡፡ መመረጥ በሞት ላይ ትኩረት ያደረገ ሣይሆን በህይወት ላይ ነው! አማኞች ለ “ቅድስና” ተጠርተዋል (ኤፌ 1:4) እንጂ እንደፈለጉ ለመኖር አይደለም፡፡ ስለዚህም ይህ ሐረግ አብ የተወሰኑ ሰዎችን ኢየሱስን እንደሰጠና ለሌሎች አብ የተወሰኑ ሰዎችን ለኢየሱስ እንደሰጠና ሌሎችን ደግሞ እንዳልሰጠው ተደርጐ ግንዛቤ ውስጥ ሊገባ አይገባም፡፡

**ልዩ ርዕስ፣ *መመረጥ***

*መመረጥ የሚያስደንቅ አስተምህሮ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አድሰዋ ለማድረግ ሣይሆን መንገድ ለመሆን፣ ለሌሎች መዳን ምክንያት ለመሆን ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ቃሉ ይጠቀስ የነበረው በመጀመሪያ ለአገልግሎት ነው፣ በአዲስ ኪዳን ደግሞ የአገልግሎት መሠረት የሆነውን ድነትን ለመግለን ነበር፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ተቃራኒ የሚመስሉትን የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነትና የሰውን ነፃ ፈቃድ ለማስታረቅ በፍፁም ጥረት አያደርግም ይልቁንም ሁለቱም ትክክል መሆናቸውን ያረጋግጣል እንጂ ለእንዲህ አይነቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ውጥረት ጥሩ ምሣሌ የሚሆነን በሮሜ 9 ላይ ስለ እግዚአብሔር ሉዓላዊ ምርጫ የሚናገረውን በሮሜ 10 ላይ ስለሰው ልጆች አስፈላጊ ምላሽ (10÷11-13) የሚናገረው ነው፡፡*

*በኤፌ 1÷4 ላይ ያለው ለዚህ ሥነ-መለኮታዊ ውጥረት መፍቻ ሊሆን የሚችል ነው፣ ኢየሱስ በእግዚአብሔር የተመረጠ ሰው እንደሆነ ሁሉ ሰዎች ሁሉ በእርሱ የተመረጡ ናቸው፡፡ (Kari Barth)፡፡ ኢየሱስ ለወደቀው የሰው ዘር ፍላጐት ‹‹አዎን›› ነው (Kari Barth) እንዲሁም የኤፌ 1÷4 ሃሳብ አስቀድሞ የመወሰን ግቡ መንግሥተ ሰማይ ሳይሆን ቅድስና (ክርስቶስን መምሰል) ነው በማለት ያብራራልናል፡፡ እኛም ብዙ ጊዜ ከወንጌል የሚገኙትን ጥቅሞች ስንፈልግ የሚያስፈልጉትን ኃላፊነቶች እንዘነጋቸዋለን! የእግዚአብሔር ጥሪ (ምርጫ) ለአሁንም ለዘላለምም ነው!*

*አስተምህሮቶች የሚመጡት ከሌሎች እውነቶች ጋር እየተዛመዱ እንጂ ተነጥለው አይደለም፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሣሌ የሚሆነን ኅብረ ኰከብ እና አንድ ነጠላ ኰከብ ናቸው፡፡ እንዲሁም ደግሞ በቋንቋ ዘዬ ምክንያት የሚፈጠሩትን ውጥረቶች ልናስወግዳቸው አይገባም (እግዚአብሔር ሩቅ ነው ወይስ እግዚአብሐር ቅርብ ነው፣ ምሣሌ፡- ደህንነት ወይስ ፅናት ኢየሱስ ከአብ ጋር እኩል ነው ወይስ ኢየሱስ ለአብ የሚገዛ ነው፣ የክርስቲያን ነፃነት ወይስ የክርስቲያን ኃላፊነት ወዘተ.)፡፡*

*ቃል ኪዳን የሚለው ሥነ-መለኮታዊ ሐሳብ የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት (ሁልጊዜም ተነሳሽነቱን የሚወልድና ጉዳዩን የሚያመቻች) ከሰው ልጅ በንስሐ በእምነት ምላሽ የመስጠት ኃላፊነት ጋር ያስተሳስረዋል (ማር 1÷15 ሐዋ 3÷16፣ 16፣ 20፣ 21)፡፡ በዚህም እንግዲህ አንዲን አገላለፅ ከመካብና ሌላውን ከመናቅ፣ በጣም ተጠንቀቅ! የራስህ አስተምህሮ ወይም የሥነ-መለኰት ሥርዓት ከማራመድ ተጠንቀቅ!*

*"የዘላለም ሕይወት ይሰጣቸው ዘንድ"* የዘላለም ሕይወት በክርስቶስ አማካኝነት የሚሰጥ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው (5:21፤ 26፤6:40:47፣ 10-28፤ 1ዮሐ 2:25፣ 5:11)፡፡ ይህም ማለት "የእግዚአብሔር ሕይወት ወይም የትንሣኤ ሕይወት" ማለት ነው፡፡ ከጀመሪያው ይህ ሕይወት ጉዳይ ሣይሆን የጥራት ነው (10:10)፡፡

17:3 **"ይህች የዘላለም ሕይወት ናት"** ይህ በዮሐንስ የጨመረ "የዘላለም ሕይወት" ትርጉም ነው፡፡ ይህ እውነት ሁለቱን የክርስትና አብይ እውነቶችን ያሳየናል፡፡ (1) የአንድ አምላክ አምልኮን (ዘዳ 6:4-6) እና (2) ኢየሱስ መለኰት የሆነ ከዳዊት ዘር የመጣ መሲኽ መሆኑን (2 ሳሙ 7)፡፡ ይህ የ"ዘላለም ሕይወት" ለወደፊት የተጠበቀ አንዳች ነገር ሳይሆን አሁን በኢየሱስ ክርስቶስ የሚገኝ ነው፡፡

▣ **"አንተን ያውቁ ዘንድ"** ይህ የአሁን ጊዜ ስሜት ገላጭ ግሥ ነው፡፡ ይህ ስለ እግዚአብሔር ያለን የእዕምሮ እውቀት ብቻ አያመለክትም፡፡ ምንም እንኳን ሊረጋገጥ የሚገባው እውነት ቢኖርም የተጠቀሰው ግን የግል ግንኙነት በሚያመለክት የሴሜቲክ ትርጉም ነው፡፡ ይሁን እንጂ እውነቱ ኢየሱስ የእውነተኛ አምላክ ሙሉና ፍፁም ሆኖ የተገለጠ መሲህ ነው (1:12:14፣ ቆላ 1:15፤ ዕብ 1:3)፡፡ ስለዚህም ሰዎች በእርሱ ሊያምኑ፣ ሊቀበሉት ንስሐ ሉገቡ፣ ሊታዘዙት፣ ሊፀኑበት ይገባቸዋል፡፡

▣ **"እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንክ"** ብሉይ ኪዳን አንድ አምላክ ብቻ መኖሩን ለየት ባለ መንገድ በማሳየት ይታወቃል (ዘፀ 8:10፣ 9:14፣ ዘፀ 4:35፣ 39፣ 6:4፣ 33:26 1ሳሙ 2:2: 2: 2ሳሙ 7:22፣ 1ነገ 8:23፤ ኢሳ 37:20፣ 44:6፤8፤45፤6-7፡14፣ 18፣ 21፣ 22፣ 46፣ 9፤ ዮሐ 5፤44፣ 1ቆሮ 8፣ 4፤6፤ 1ጢሞ 1፡17፣ 2-5 ይሁዳ ቁ.25) ብሉይ ኪዳን የኢግዚአብሔርን ስቶ መሆንና አንድ መሆኑን የሚያመክተው የጥንት ቅርብ ምሥራቅ ሐገራት ሕዝቦች ለብዙ መንፈሳዊ ኑባሬዎች ከነበራቸው አመለካከት ነው፡፡ አንድ አምላክ ብቻ ሲኖር ሌሎችም መንፈሳዊ አሳካላትም አሉ (ዘፀ 15፤11 ዘዳ 3:24 መዝ 86፣ 8፤ 89፤6)፡፡

ባንድ በኩል የብሉይ ኪዳን መፃህፍት የብዙ አማልክት አምልኰን በውስጣቸው ሲያንፀባርቁ ይታያሉ (ብዙ አማልክት *elohim* ነገር ግን ለእስራኤል አንድ አምላክ ብቻ)፡፡ ሙሴም በመፅሐፍቱ የሌሎች መንፈሳዊ አካላትን መኖር የገነዘበ ይመስላል፤ ይህ ማለት የአህዛብ ጣዖታት እውነታ አላቸው ማለት አይደለም፤ እንዲያውም በአይን ከሚታዩት ጣዖታት በስተጀርባ አጋንንት ይሠራሉ (1ቆሮ 10፤19-20)፡፡

ሌላው ቅፅል "እውነት" (አሌቲኖስ) የሚለው ነው፡፡ ይህ ቃል ከተጓዳኙ ቃል ጋር (አሌቲስ) በዮሐንስ ፅሑፎች ውስጥ ብዙውን ጊዜ ይጠቀሳል ነገር ግን ትርጊማቸውን በዚህ ለመደምደም የሚያስቸግር ነው፡፡ እነዚህ ቃላት ሠፋ ያሉ አንደምታዎች አሏቸው (የሥነ-አገባብ ጥናት መስክ)፡፡ የብሉይ ኪዳን ዘይቤያዊ አነጋገር የኋላ ታሪክ እንደሚጠቁመው ታማኝ ዋጋ ያለው ፣ የታመነ (አሜት0 የሚል እሳቤ አለው፡፡ የግሪኩ መነሻ ታሪክ ደግመ ያልተሰፈነ፣ ፊፅሞ የተገለጠ የሚል ሐሳብ አለው፡፡ በአንዳንድ ትርጉምም እውነት የውሸት ተቃራኒ ነው (ቲቶ 1:2)፡፡ በግዘኩ ቃል ላይ ያለው ባዕድ መድረሻ ቃል (ioNs) የሚያመለክተው አንድ ነገር የተሠራበትን ምንጭ (መሠረት) ያመለክታል፡ የሚከተሉትም አጠቃቀሞች ምናልባት ስለ ቃላቱ አጠቃላይ የሆነ ግንዛቤን የሚሠጡ ይሆናሉ፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ ‹‹እውነት›› (ቃሉ) በዮሐንስ ፅሑፎች ውስጥ**

1. እግዚአብሔር አብ
   - ሀ. እግዚአብሔር አውነት.ታማኝ ነው (ዮሐ 3:35፣ 7:18፣ 8:26፣ 17:3፣ ሮሜ 3:4 1ተሰ 1:9፣ 1ዮሐ 5:20፣ ራዕ 6:10)
   - ለ. የእግዚአብሔር መንገዶች እውነት ናቸው (ራዕ 15:3)
   - ሐ. የእግዚአብሔር ፍርዶች እውነት ናቸው (ራዕ 16:7፣ 19:2)
   - መ. የእግዚአብሔር ንግግሮች እውነት ናቸው (ራዕ 19:11)
2. እግዚአብሔር ወልድ
   - ሀ. ወልድ እውነተኛ.እውነት ነው
     1. እውነተኛ ብርሃን (ዮሐ1:19፣ 1ዮሐ 2:8)
     2. እውነተኛ የወይን ግንድ (ዮሐ 15:1)
     3. ፀጋንና እውነትን የተሞላ (ዮሐ 1:14-17)
     4. እርሱ እውነት ነው (ዮሐ 14:6፣ 8:321)
     5. እርሱ የታመነ ነው (ራዕ 3:7-14፣ 19:1)
   - ለ. የወልድ ቃል ምሥክርነት የታመነ ነው (ዮሐ 18:37)
3. የንፅፅር አንደምታ ሊኖረው ይችላል
   - ሀ. የሙሴ ሕግ ወይስ የኢየሱስ ፀጋና እውነት (ዮሐ 1:17)
   - ለ. የምድረበዳው የማደሪያ ድንኳን ወይስ ሰማያዊሙ ድንኳን (ዕብ 8:2፣ 9:1)

4. በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ እንደሆነው ቃሉ ብዙ ድባቦች (ትርጉሞች) በሩት (እብራይስጥ እና ግሪክ)፡፡ ዮሐንስም የሚጠቀማቸው አብን ወልድን እንደ ሰወች፣ እንደተናጋሪወች እና መልእክታቸው ለሚከተሏቸው እንደሚተላለፉ ለመግለፅ ነበር (ዮሐ 4:13፣ 19:35፣ ዕብ 10:22፣ ራዕ 22:6)፡፡
5. ለዮሐንስ እነዚህ ሁለቱ ቅፅሎች አብን አንድና ብቸኛ አምላክ እንደሆነ የሚገልፁ ናቸው (5:44፣ 1ዮሐ 5:20) እንዲሁም ደግሞ ኢየሱስን ለእውቀት ሳይሆን ሰዎችን ለማዳን ዓላማ የእግዚአብሔር እውነተኛና ፍፁም መገለጥ እንደሆነ የሚገልፁ ናቸው፡፡

▣ **"የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን"** ይህ በዮሐንስ በራሱ የተጨመረ የኢዲቶሪያል ማብራሪያ ሊሆን ይችላል፡፡ ኢየሱስ ከአብ "የተላከ" መሆኑን ትኩረት የሰጠበት ተደጋግሞ የሚከሰት ቀጤ ዱዋሊዝም ነው (3:17፣ 34:5፣ 36:38፣ 6:29፣ 38:57፣ 7:29፤ 8:42፣ 10:36፣ 11:42፣ 17:3፣ 8:18፣ 21:25፤ 20:21)፡፡ ረቢዎች አፓስቴሎ የሚለውን ቃል የጠቀሱት አንድ እንደ መንግሥት ተወቀይ የተላከን ሰው ለማስመልከት ነበር፡፡ በ5:24 ላይ መላክ (አፓስቴሎ) የሚለውን ይመልከቱ፡፡

17:4 **"እኔ ... በምድር አከበርኩህ"** (በ13:31-32 ላይ ያለውን ማብ ይመልከቱ፡፡)፡፡ "ክብር" የሚለው ቃል ሊጠቀስ የሚችለው (1) "ክብርን መስጠት" ወይም (2) "የ ... ክብርን መግለጥ" በሚል ትርጉም ነው፤ ቁጥር 6 የሚያመለክተውም 2ኛውን አማራጭ ነው፡፡ የኢየሱስም ተግባሮች ከሆኑት አንዱና ዋነኛው አብን መግለጥ ነበር (1:14፣ 18)፡፡

▣ **"የሰጠኸኝን ሥራ ፈፅሜ"** የግሪኩ መነሻ ቃል telos እንደሚያሳየው "ሙሉ በሙሉ መፈፀም" የሚልነው (4:34፣ 5:36፣ 19:30)፡፡ የተሠራው ሥራ ሦስት ነበር፡፡
1. አብን መግለጥ (1:14፣ 18)
2. የወደቀውን የሰው ዘር መቤዥት (ማር 10:45፣ 2ቆሮ 5:21)
3. የእውነተኛ የሰው ዘር ምሳሌ (13:31፣ 1ጴጥ 2:21)
4. እንዲሁም ደግሞ የኢየሱስ የመማለድ ተግባር ይቀጥላል (1ዮሐ 2:1፣ 7:25፣ 9:24)

17:5 **"ክብር ... አክብረኝ"** ይህ ጥቅስ የሚያመለክተው ክርስቶስ ከፍጥረት በፊት ሁሉ እንደነበረ ነው (1:1፣ 15፣6:62፤ 8:58፤ 16፤ 28፣ 17:11፣ 13: 24፣ 2ቆሮ 8:9፣ ፊል 2:6-11፣ ቆላ 1:17፣ ዕብ 1:3፣ 10:5-8)፡፡ ኢየሱስ አልክቶችንና ተአምራትን በማድረግ ለደቀ መዛሙርቱ "ክብርን" ገልጧል (1:14፣ 2:11፣ 11:4፣ 40፣ 12:28)፡፡ አሁን የመጨረሻው "ክብር" ሞቱ፣ ትንሳኤው እና ወደ ቀደመው ክብሩ በዕርገት መመለስ ነው (ቁ. 24፣ ፊልጵ 2:5-6፣ 17)፡፡ ግሱ የግሪኩ ትዕዛዝ አዘል አድራጊ ግስ ሲሆን የተጠቀሰውም ለአብ የተደረገ ጥያቄ መሆኑን ለማሣየት ነው፡፡ በምዕ 1:14 ላይ ሙሉ ማብራሪያ ይመልከቱ፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 17÷6-19
**[6]ከዓለም ለሰጠኸኝ ሰዎች ስምህን ገለጥሁላቸው፡፡ የአንተ ነበሩ፣ ለእኔም ሰጠሃቸው፤ ቃልህንም ጠብቀዋል፡፡ [7]የሰጠኸኝ ሁሉ ከአንተ እንደሆነ አሁን ያውቃሉ፤ [8]የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቸዋለሁና፤ እነርሱም ተቀበሉት፣ ከአንተም ዘንድ እንደወጣሁ በእውነት አወቁ፣ አንተም እንደ ላክኸኝ አመኑ፡፡**
**[9]እኔ ስለ እነዚህ እለምናለሁ፤ ስለ ዓለም አልለምንም፡ ሰለሰጠኸኝ እንጂ፤ የአንተ ናቸውና፤ [10]የእኔም የሆነ ሁሉ የአንተ ነው የአንተውም የእኔ ነው፤ እኔም ስለእነርሱ ከብሬአለሁ፡፡ [11]ከዚህም በኋላ በዓለም አይደለሁም÷ እነርሱም በዓለም ናቸው÷ እኔም ወደ አንተ እመጣለሁ፡፡ ቅዱስ አባት ሆይ÷ እነዚህን የሰጠኸኝን እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው፡፡ [12]ከእነርሱ ጋር በዓለም ሳለሁ የሰጠኸኝን በስምህ እኔ እጠብቃቸው ነበር፤ ጠበቅኋቸውም፣ መጽሐፉም እንዲፈፀም፣ ከፋጥት ልጅ በቀር ከእነርሱ ማንም አልጠፋም፡፡ [13]አሁንም ወደ አንተ እምጣለሁ፤ በእነርሱም ዘንድ ደስታዬ የተፈፀመ እንዲሆንላቸው ይህን በዓለም እናገራለሁ፡፡ [14]እኔ ቃልህን ስጥቻቸዋለሁ፤ እኔም ከዓለም እንዳይደለሁ ከዓለም አይደሉምና ዓለም ጠላቸው፡፡ [15]ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም እንድታወጣቸው አልለምንም፡፡ [16]እኔ ከዓለም እንዳይደለሁ ከዓለም አይደሉም፡፡ [17]በእውነት ቀድሳቸው፤ ቃልህ እውነት ነው፡፡ [18]ወደ ዓለም እንደላክኸኝ እንዲሁ እኔ ወደ ዓለም ላክኋቸው፤ [19]እነርሱም ደግሞ በእውነት የተቀደሱ እንዲሆኑ እኔ ራሴን ስለ እነርሱ እቀድሳለሁ፡፡**

17:6 **"ስምህን ገለጥሁላቸው"** የእብራይስጥ ስሞች ባህሪን ለመግለፃ ታስበው የሚደረጉ ናቸው (ቁ. 11፤ 12:25-26 መዝ 9:10)፡፡ ከሥራ መለኮት አንፃር ይህ ሐረግ የሚያረጋግጠው ኢየሱስን ማየት ማለት እግዚአብሔርን ማየት እንደሆነ ነው (ዮሐ 1 : 18፣ 12:45፣ 14:8-11፣ ቆላ 1:15፣ ዕብ 1:3) ፡፡

"ስም" የሚለው ቃል በላይኛው ደርብ በተካሄዱት ንግግሮች ውስጥ ከፍ ያለውን ሚና የሚጫወት ነው (14: 13፣ 14፣ 26፤ 15፤ 16፤ 21፤ 16:23፣ 24፣ 26፣ 17:6፣ 11፣ 12:26)፡፡ በምዕራፍ 17 ውስጥ እግዚአብሔርን በሚመለከት ሁለት አስደናቂ መጠሪያዎች ተጠቅሰዋል

1. ቅዱስ አባት ቁ. 11
2. ፃድቅ አባት ቁ. 25

▣ **"የሰጠኸኝ ሁሉ"** በሥነ-መለኰት አንደምታው ይህ የሚናገረው ስለመመረጥ ነው (ቁ. 2:9፣ 24:37:39)፡፡ ማንም ሰው

1. እግዚአብሔር እስካልሰጠ
2. መንፈስ ካልሳበው /ካላመጣው (6:44፣65)
3. ተቀብሎ (1:12) እስካላመኑ (3:16) ወደ ኢየሱስ ሊመጣ አይችልም፡፡

▣ **"ቃልህንም ጠብቀዋል"** መታዘዝ በጣም አስፈላጊ ነው (8:51፣ 55:14:23፣ 15:10:20)፡፡ ይህ በብሉይ ኪዳን "ፍፁም መሆን" በሚል ትርጉም ይጠቀሳል (ኖህ) ዘፍ 6:9 አብርሃም፣ ዘፍ 17:1፤ አስራኤል፣ ዘዳ 18:13፣ ኢዮብ ኢዮ 1:1፡፡ ቃሉ ፍፁም መታዘዝን ወይም ኃጢአት አልባ መሆኑን ሳይሆን የተገለጠውን እውነት ስለመስማት ለማድረግ ያለውን መሻት የሚያሳይ ነው፡፡ አሁንም እዚህ ላይ የሚያመለክተው ደቀ መዛሙርት በኢየሱስ ያላቸውን እምነት፣ በእርሱ መኖራቸውን ኢየሱስ እንደወደዳቸው ሁሉ እርስ በርሳቸው መዋደዳቸውን ነው፡፡

17:7 **"አሁን ያውቃሉ"** ይህ ድርጊት መጠናቀቅን የሚያመለክት አድራጊ ግሥን ነው፡፡ ይህም የመልህክቱን ይዘት የሚያሣይ ነው፡፡ በ2:24 ላይ ዮሐንስ "Hoti" የሚለውን ቃል አጠቃቀም በልዩ ርዕስ ላይ ይመልከቱ፡፡

▣ **"የሰጠኸኝ ሁሉ ከአንተ እንደሆነ"** ኢየሱስ ይናገር የነበረውን ከአብ ለአርሱ የገለጠውን ነበር (8:7፣16፣ 12:48-49 )፡፡

17:8 **"እነርሱም ተቀበሉት"** ኢየሱስ ስለእግዚአብሔር የነገራቸውን መልእክት ተቀበሉ፡፡ እዚህ ላይ የተገለፀ ምንም ቀጥተኛ ተሳቢ የለም፡፡ በ1:12 ላይ መቀበል/መውሰድ የሚለው ቀጥተኛ ተሳቢ ራሱ ኢየሱስን የሚያመለክት ነው፣ እዚህ ላይ ግን ኢየሱስ ስለ እግዚአብሔር ያመጣውን መልእክት ያመለክታል (ቁ. 4)፡፡ ይህም የወንጌልን ሁለት ጣምራ ገጽታወች የሚያጐላ ነው፣ (1) ወንጌል ሰው ነው (2) ወንጌል መልእክት ነው የሚሉ ናቸው፡፡

▣ **"እነርሱም ተቀበሉት ... አመኑ"** ይህ የግሪኩ አድራጊ ግሥ አመልካች ነው፡፡ እነዚህ እውነቶች የሚገልጡት የኢየሱስ ማንነትና መልእክቱ መለኰታዊ መሆናቸውን ነው (5:19፣ 6:68-69፣ 12:48-49፣ 16:30፣ 17:18፣ 21፣ 23፣25)፡፡

17:9 **"እኔ ስለእነርሱ እለምናለሁ"** ኢየሱስ አማላችን (1ጢሞ 2፣5፤ ዕብ 8:6፣ 9:15፣ 12:24) ደግሞም ጠበቃችንም ነው (1ዮሐ 2:1)፡፡ መንፈስ ቅዱስ በዚህ ሥራ ውስጥ እንደሚሳተፍ (ሮሜ 8:26-27) እንዲሁ አብም ይሣተፋል (16:26-27፡፡ በማንኛውም የመቤዥት ሥራ ውስጥ ሁሉ ሦስቱም የሥላሴ አካላት ሁሉ ይሣተፋሉ፡፡)

▣ **"ዓለም"** *Kasmas* የሚለው ቃል በዚህ ምዕራፍ ውስጥ አስራስምንት ጊዜያት ተጠቅሷል ኢየሱስ (1)ለተፈጠረው ግዑዝ ዓለም (17:5፣24) እንዲሁም (2) አማኞች በወደቀው ዓለም ውስጥ ስላላቸው ግንኙነት ግድ ይለዋል (1:10፣ 17:6፣ 9፣ 11፣ 13፣ 14፤ 15፤ 16፤ 17፤ 18፤ 21፤ 23)፡፡ በዮሐንስ ፅሑፎች ውስጥ ይህ ቃል ለየት ባለ መንገድ "ከእግዚአብሔር ተለይቶ የተደራጀና የሚሠራ የሰው ማህበረሰብ" በሚል አንደምታ ተገልጿል፡፡ አንዳንድ ጊዜ በተዘዋዋሪ (1) ግዑዙን ፕላኔት (2) በፕላኔቱ ላይ የሚኖረውን ሕይወት ወይም (3) ከእግዚአብሔር የተለየ ሕይወቱን ይጠቅሳል፡፡ በ14:17 ላይ ልዩ ርዕስን ይመልከቱ፡፡

17:10 **"የእኔም የሆነ ሁሉ የአንተ ነው፣ የአንተውም የእኔ ነው"** ይህ የሚገልጠው በሥላሴ አካላት መካከል ያለውን አንድነት ነው (ቁ. 11፣ 21-23፣ 16፣15)፡፡ ሥላሴ ለሚለው በ14፣ 26 ላይ ልዩ ርዕሱን ይመልከቱ፡፡

▣ **"እኔም ስለ እነርሱ ከብሬአለሁ"** ይህ የድርጊት መጠናቀቅን የሚያሣይ ተደርጎ ግሥ አመልካች ነው፡፡ የደቀመዝሙር ሕይወት ኢየሱስ ለአባቱ (አብ) ክብርን እንደሰጠ ሁሉ ለኢየሱስ ክብርን መስጠት ነው፡፡ እንዴት ታላቅ የሆነ ኃላፊት ነው!

17:11 **"ከዚህም በኋላ በዓለም አይደለሁም"** ይህ የሚያመለክተው (1) ኢየሱስ ወደ አባቱ ሲመለስ የሚሆነውን በቅርብ የሚሆነውን ክስተት (ዕርገት) ወይም (ሐዋ 1:9-10) ወይም (2) የኢየሱስን የአደባባይ አገልግሎት ነው፡፡

▣ **"ቅዱስ አባት"** ይህ "ቅዱስ" የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን እንደተጠቀሰ ሁሉ ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ ኪዳን አብን ለመግለፅ ተጠቅሷል ("ቅዱሱ" 1 ጴጥ1:16)፡፡ ይህ ቅፅል /hagios/ ብዙውን ጊዜ መንፈስ ለመግለፅ ተጠቅሷል (1:33፣ 14:26፣ 20:22)፡፡ ተመሳሳዩም የግሪኩ ሥርው ቃል የደቀመዛሙርቱን መቀደስ (ቁ. 17) (hagiasmos) እና የኢየሱስን መቀደስ (ቁ. 19) (hagiazo) ለመግለፅ ተጠቅሷል፡፡

የቃሉ መሠረተ አመጣጥ "ለእግዚአብሔር አገልግሎት መለማየት" የሚል ነው (ቁ. 17:19)፡፡ ቃሉ ለእግዚአብሔር አገልግሎት ብቻ የተሰጡ ሰዎችን፣ ቦታዎችን እንዲሁም ነገሮችን ለመግለፅ ተጠቅሷል፡ የእግዚአብሔርን ታላቅነት (የእስራኤል ቅዱስ) እንዲሁም ከሚታየው ከምድራውውና ከወደቀው ዓለም የተለየ መሆኑን ያሣያል፡፡ ኢየሱስ ቅዱስ እንዲሆን የእርሱም ተከታዮች እርሱን እየመሰሉ ሲሔዱ "ቅድስናን" ያንፀባርቃሉ፡፡ "SaiNt" የሚለው ቃል መሠረተ አመጣጥ ከግሪኩ ሲሆን ይህም "holy" የሚለው ነው፡1 አማኞችም ቅዱሳን የሚባሉት በክርስቶስ ስላሉ ነው፡፡ ነገር ግን ለእርሱ በኖሩ ቁጥር፣ እርሱን በመሰሉ ቁጥር ቅዱሳን መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ ቅዱስ**

I. ብሉይ ኪዳን
   ሀ. *Kadash* (BDB 872) የሚለው ቃል መሠረት አመጣጥ ግልፅ ባይሆንም ምናልባት የከነዓናዊያን ይሆናል፡፡ የቃሉ መነሻ ክፍል (kd) ትርጉሙ ‹‹ማካፈል›› የሚለ ነው፡፡ ይህም ‹‹ለእግዚአብሔር አገልግሎት መለየት›› የሚለውን የታወቀ አገላለፅ ምንጭ ነው፣ (ከከነዓናውያን ባህል፣ ዘዳ 7÷6፣ 14÷22፤21፤ 26÷19)፡፡
   ለ. በነገሮች በቦታዎች እና በሰዎች ውስጥ ከእግዚአብሔር መገኘት (ሕልውና) ጋር የሚዛመድ ነው፡፡ በዘፍጥረት ውስጥ ባይጠቀስም በዘፀአት፣ በዘሌዋውያን እና በዘህልቁ መፃሕፍት ውስጥ የተለመደ ነው፡፡
   ሐ. በነቢያት ፅሑፎች ውስጥ (ለምሳለ ኢሳያስ አና ሆሴዕ) ቀደም ሲል የነበሩት የማንነት ባህሪያት ነገር ግን ትኩረት ያልተሰጣቸው አሁን ጐልተው ይታያሉ፡፡ የእግዚአብሔርን ማንነት ለማመልከት ተቅሷል (ኢሳ 6÷3)፡፡ እግዚአብሔር ቅዱስ ነው፤ ማንነቱን የሚገልጠውም ሰው ቅዱስ ነው፡፡ ባህሪውንም ለዓለም ሲገልጡ የተባቸው የእርሱ ህዝቦችም ቅዱሳን ናቸው (ቃል ኪዳኑን በእምነት ቢታዘዙት)፡፡
   መ. የእግዚአብሔር ምህረቱና ፍቅሩ ከቃል ኪዳኑ፣ ከጽድቁ፣ እንዲሁም አብይ ከሆኑት ባህሪያት ሥነ-መለኮታዊ ሐሳቦች ጋር የማይነጣጠሉ ናቸው፡፡ እዚህ ላይ እግዚአብሔር ለረከሰው ለወደቀው እና አመፀኛ ለሆነው የሰው ዘር ባለው እይታ ላይ ውጥረት የነገሠበት ይመስላል፡፡ በሮቨርት ቢ. ጊርየልስቶ *syNoNyms of the Old TestameNt* (ገጽ 112-113) በሚል መፅሐፍ ውስጥ እግዚአብሔር እንደ ‹‹መሐሪ›› እና እግዚአብሔር እንደ ‹‹ቅዱስ›› በሚሉ ሐሳቦች መካከል የተፃፈ ማራኪ የሆነ አገላለፅ አለው፡፡

II. አዲስ ኪዳን
   ሀ. ከሉቃስ በስተቀር ሁሉም የአዲስ ኪዳን ፀሐፍት ዕብራዊን ናቸው፡፡ ግን በኮይኔ ግሪክ ጸፅዕኖ ስር የወደቁ ናቸው፡፡ (ያ ማለት የግሪክ ትርጓሜ ሴፐቱ አጀንት - የሰባ ሊቃውንት ትርጉም በመባል በሚታወቀው) ይኸውም ዋናው የግሪክ ቋንቋ ስነፅሑፍ፣ አስተሳሰብ ወይም ሃይማኖት ቃላቶች አልነበሩም የተቆጣጠሩአቸው፡፡
   ለ. ኢየሱስ ቅዱስ ነው፡፡ ምክንያቱም እርሱ እግዚአብሔር ነው፡፡ እናም እንደ እግዚአብሔር (ሉቃ 1:35፣ 4:34፤ የሐዋ 3:14፤ 4:27፣30)፡፡ እርሱ ቅዱስና ጻድቅ ነው (የሐዋ 3:14፣ 22:14)፡፡ ኢየሱስ ቅዱስ ነው፡፤ ምክንያቱም ሃጢአት የለሽ ነው (የሐዋ 8:46፣ 2ቆሮ 5:21፣ ዕብ. 4:1፣ 7:26፣ 1ጴጥ. 1:19፣ 2:22፣ 1ዮሐ. 3:5)፡፡
   ሐ. ምክንያቱም እግዚአብሔር ቅዱስ ነው፡፡ የእርሱም ልጆች ቅዱሳን መሆን አለባቸው (ዘሌዋ 11:44-45፤ 19፤2፣ 20:7፣ 26፤ ማቴ. 5:48፣ 1ጴጥ 1:16)፡፡ ምክንያቱም ኢየሱስ ቅዱስ ነው፡፡ የእርሱም ተከታዮች ቅዱሳን መሆን ይኖርባቸዋል (ሮሜ 8:28-28፣ 2ቆሮ. 3:18፣ ገላ 4:19፣ ኤፌ. 1:7 1ተሰ. 3:13፣ 4:3፤ 1ጴጥ 1:15)፡፡ ክርስቲያኖች ድነትን የተቀበሉት በቅድስና (ክርስቶስን በመምሰል) እርሱን እንዲያገለግሉት ነው፡፡

▣ **"በስምህ ጠብቃቸው"** ኢየሱስ እግዚአብሔር ለእርሱ የሰጠው ጥበቃ መለኰታዊ መገኘት ወይም ሕልውና (የድርጊት መጠናቀቅን አመልካች ግሥ) ለደቀመዛሙርት እንዲሆንላቸው (ቁ. 12) እየፀለየ ነው (የግሪኩ ድርጊት ገላጭ ግሥ)፡፡ ይህም ደቀመዛሙርቱ ልክ እንደ ኢየሱስ በወደቀው ግለም ውስጥ ለማገልገል የሚያስችላቸው ነው (ቁ. 18)፡፡ ይህ፣

1. በአብ
2. በወልድ
3. ለደቀመዛሙርት መካከል ያለው አንድነት (ቁ. 210 አንዱ ጥቅም ነው፡፡

▣ **"እንደእኛ አንድ እንዲሆኑ"** ይህ የአሁን ጊዜ ስሜት ግላጭ ነው፡፡ በስላሴ አካላት መካከል ያለውን የጠነከረ አንድነት የሚያሳይ ነው (ቁ. 21፣ 22፣ 23፣ 10:30፣ 14:10)፡1 ይህ እንግዲህ ለክርስቲይኖች ታላቅ ኃላፊነትን የሚያሳይ ጥያቄ ነው፡፡ ይህ ለአንድነት የቀረበ ጥሪ በዘመናችን የማይታይ ጉዳይ ነው (ኤፌ 4:1-6)፡፡ አንድነት የተነጣጠለችውን የዘመናችንን የአግዝአብሔር ቤተክርስቲያን የሚያስተሳስር ነው፡፡

17:12 **"እኔ እጠብቃቸው ነበር፤ ጠበቅኋቸውም"** የመጀመሪያው ግስ ያላለቀ ድርጊትን ሲያሳይ ሁለተኛው ግን መጠናቀቁን ያሳያል፣ እነዚህ ግሦች ተመሣሣይ ናቸው፡፡ የክፍሉም ሐሳብ የኢየሱስን የማያቋርጥ ጥበቃ ለማመልከት ነው (1ጴጥ 1:3-9)፡፡

ኤም አር ቪንሰንት *Word Studies iN the New TestameNt* (ቅፅ.1) በሚለው በፅሑፉ በሁለቱ ቃላት መካከል ልዩነት እንዳለ ይገልፃል፤ እርሱም እንደሚለው የመጀመሪያው ቃል (ቴሪዮ) መካከል የሚል ሐሳብ ሲኖረው ሁለተኛው ቃል (ፉላስ) መጠበቅ የሚል ትርጉም አለው (ገፅ 496)፡፡

▣ **"ከእነርሱ ማንም አልጠፋም"** ይህ የኢየሱስን የመጠበቅ ኃይሉን የሚከያመለክት ነው (6:37፣ 39፣ 10:28-29)፡፡ ይህ ቃል *appolumi* በሁለት የትርጉም ሐሳቦች ስለተጠቀሰ ለመተርጐም አስቸጋሪ ነው፡፡ ጌርሃርድ ኬተል *Theological DictioNary of the New TestameNt* (ቅፅ 1) በሚለው መጽሐፋቸው ስለዚህ ቃል እንዲህ ይላሉ፡፡ "በአጠቃላይ 2 እና 4 በወንጌላት ውስጥ እንደተጠቀሱት ከዚህ ዓለም አንፃር የተነገሩትን የሚያዛምዱ ሲሆኑ፣ 1 እና 3 ደግመ በጳውሎስና በዮሐንስ መልእክቶች ውስጥ እንደተጠቀሱት ሊመጣ ካለው ዓለም ጋር የሚዛመዱ ናቸው" ገጽ 394፡፡ እርሱም የሚሰጣቸው ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. *"ማጥፋት ወይም መግደል"*
2. *"ማጣት ወይም ማጣትን መጋፈጥ"*
3. *"መጥፋት"*
4. *"መጥፋት"*

ይህ ቃለ ብዙውን ጊዜ የመጥፋትን አስተምህሮ ለመግለፃ ተጠቅሷል፣ ማለትም ያልዳኑ ሰዎች ከፍርድ በኋላ መኖር እንደሚያቆሙ ለማሳሰብ ይህም 12:2ን የሚቃረን ወይም የሚጥስ ይመስላል፡፡ እንዲሁም ደግሞ በወንጌላት ወይም በዮሐንስ እና ጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ ያለውን የልዩነት አንድምታዎች የሳተ ነው፡፡ እነዚህም ክፍሎች የሚያሣዩት አካላዊ ወጽመትን ሳይሆን መንፈሳዊ ጥፋትን በዘይቤየዊ አነጋገር ቃሉን ይገልፁታል፡፡ ልዩ ርዕስን በ10:10 ላይ ይመልከቱ፡፡

▣ **"ከጥፋት ልጅ በቀር"** ይህ በግልፃ የአስቆሮቱ ይሁዳን የሚያመለክት ነው፡፡ ተመሣሣዩ ቃል በ2ተሰ 2:3 ላይ የአመፅ ሰው (በመጨረሻው ዘመን የሚገለጠው የክርስቶስ ተቃዋሚ) የማለውን ለመግለፅ ተጠቅሷል፣ ይህም የእብራይስጥ የአነጋገር ዘይቢ ሲሆን ትርጉሙም "ለጥፋት የተወሰነ" ማለት ነው፡፡ ቀደም ሲል "ከጥፋት ልጅ በቀር ከእነርሱ ማንም አልጠፋም" ተብሎ በተጠቀው "ጥፋት" በሚለው ቃለ ላይ የተደረገ የቃላት መራቀቅ ይመስላል፡፡

ልዩ ርዕስ፣ ክህደት የሚለውን በዮሐንስ 6:64 ላይ ይመልከቱ፡፡

▣ ***"መጽሐፉም እንዲፈፀም"*** ይህ በዮሐንስ 13:18፣ 6:70-71 የተጠቀሰውን መዝ 41:9ን የሚያመለክት ነው፡፡

▣ **"አሁንም ወደ አንተ እመጣለሁ"** ይህ ሊያመለክት የሚችለው

1. የኢየሱስን ፀሎት (ዮሐንስ 17)
2. የኢየሱስን እርገት (ቁ. 11፣ ሐዋ 1)

▣ **"ይህን በዓለም እናገራለሁ"** ይህ ሐረግ ወደ ኋላ ተመልሶ የሚገናኘው

1. 11:42 ሌሎች መስማት እንዲችሉ ኢየሱስ ጮክ ብሎ ይናገራል
2. 15:11 የኢየሱስ ቃላት ከደቀመዛሙርቱ "ደስታ" ጋር የሚዛመድ ነው፡፡

▣ **"በእነርም ዘንድ ደስታዬ የተፈፀመ እንዲሆንላቸው"** ይህ ስሜት ገላጭ አድራጊ ግሥ እና ተደርጐ ቦዝ አንቀፅ ነው፡፡ ምን አይነት አስደናቂ ተስፋ ነው (5:11፣ 16:24) ዮሐንስ አሁንም ይህን የሚደጋገም ሐረግ ሲጠቅሰው ይታያል (1 ዮሐ 1:4 2 ዮሐ 12)፡፡

17:14 **"እኔ ቃልህን ሰጥቸዋለሁ"** እዚህ ላይ "ቃል" የሚለው logos ማለት ነው፣ የግዘኩ rhima በቁጥር 8 ላይ ተጠቅሷል፡፡ ይህ በኢየሱስ ስብእና፣ ትምህርቶች እና ምሳሌዎች የተደረገውን መለኰታዊ መገለጥ ማረጋገጫ ነው፡፡ ኡየሱስ ቃሉን ሰጠ እርሱም ራሱ ቃል ነው፡ በመሆኑም ቃሉ የስብእናም የአውቀትም የዘት አለው፡፡ ሁላችንም የወንጌሉን ሰው እንቀበላለን፣ የወንጌሉንም መልእክት እናምነዋለን፡፡

▣ **"ዓለም ጠላችው"** ከዓለም የሚመጣው ጥላቻ በክርስቶስ ዘንድ ተቀባይነትን የማግኘት ማረጋገጫው ነው (ዮሐ 15:18-20፤ 1ዮሐ 3:13)፡፡

▣ **"ከዓለም አይደሉምና"** አማኞች በአለም ውስጥ ቢኖሩም ከዓለም አይደሉም (ቁ. 16 1ዮሐ 2:15-17)፡፡

▣ **"እኔም ከዓለም እንዳይደለሁ"** ዓለም የሚያመለክተው በዚህ ዓለም ያለውን በመዐ የወደቀውን የሰውንና የመላእክትን ስብስብ ነው (8:23፡፡)ይህ የዮሐንስ ቀጤ ድዋሊዝም ሌላው ምሳሌ ነው፡፡

17:15 **"ከዓለም እንድታወጣቸው አልለምንህም"** ክርስቲያኖች በዚች ዓለም ውስጥ ተልእኰ አላቸው (ቁ. 18፤ ማቴ 28:19-20፤ ሉቃ 24:47፤ ሐዋ 1:8)፡፡ ለእነርሱ ወደ ሰማያዊው ቤታቸው የሚሄዱበት ጊዜ አሁን አይደለም!

▣

| | |
|---|---|
| NASB፤NKJV | **"ክፉው"** |
| NRSV | **"ክፉው"** |
| TEV ፤ NJB | **"ክፉው"** |

ቃሉ ግዑዝ ወይም ተባዕታይ ፆታ ነው፡፡ ይህ ፅሑፍ ብዙውን ጊዜ የሚያመለክተው ስብዕና ያለው የክፉትን (የክፉውን) ኃይል ነው (12:31፤ 13:27፤ 14:30፤ 16:11) ስለዚህም ይህ ቁጥር እንደ ማቴ 5:5/37፤ 6:13፤ 13:19፡38 "ክፉው" የሚለው መሆን አለበት (2 ተሰ 3:3፤ 1ዮሐ 2:13-14፤3:12፤ 5:18-19)፡፡ በ12:31 ላይ ልዩ ርዕስን ይመልከቱ፡፡

17:17 **"ቀድሳቸው"** ይህ የግሪኩ ትዕዛዝ አዘል አድራጊ ግሥ ሲሆን ምንጬም "ቅዱስ" *hagios* የሚለው ነው፡፡ ይህም ሊኖረው የሚችለው ትርጉም፡፡

1. አማኞች ክርስቶስን ለመምሰል ተጠርተዋል (ቁ. 19፤ ሮሜ 8:24፤ ገላ 4:19፤ ኤፌ 1:4 ተሰ 5:23)፡፡ ይህም ሊሆን የሚችለው የእውነት እውቀት በሆነው ሕያው ቃል (ኢየሱስ 10:36) እና በተፃፈው ቃል ነው (መጽሐፍ ቅዱስ 15:13)፡፡
2. "ቀድሳቸው" የሚለው በብሉይ ኪዳን ሐሳብ ዋነኛ ትርጉሙ "ለእግዚአብሔር አገልግሎት መለየት" የማል ነው፡፡ ለምን ዓላማ "መቀደስ" እንደሚያስፈልጋቸው ቁጥር 18 ያብራራል፡፡

ጥያቄው ቁጥር 1 ወይ 2 እውነት ነው ወይ የሚል አይደለም፤ ሁለቱም እውነት ናቸው ምክንያቱም የኢየሱስ ሕይወት ራሱ የሁለቱንም አስፈላጊነት ያሳየ ነውና (ቁ.19)፡፡

የብሉይ ኪዳን ካህናት ለእግዚአብሔር አገልግሎት እንደተለዩ ሁሉ ደቀመዛሙርትም ለእግዚአብሔር አገልግሎት መለየታቸውን ዮሐንስ በተምሳሌት ይገለፀዋል፡፡ የብሉይ ኪዳን ካህናት ለብሉይ ኪዳን የመሥዋዕት ሥርዓቶች እንደ አማላጆች ሆነው አገልግለዋል፣ ነገር ግን ደቀመዛሙርት ያገለገሉት የአዲስ ኪዳንን ፍፁምና በአንድ ጊዜ ለሁሉም መሥዋዕት የሆነውን ክርስቶስን ለመግለጥ ነበር (የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳንን መፃሕፍት የሚከያነፃፅረውን የዕብራዊያንን መፅሐፍ ይመልከቱ፡፡)፡፡

▣ **"ቃልህ እውነት ነው"** እውነት የሚያመለክተው ስለእግዚአብሔር የነገረውን መልዕክት ነው (8:31-32)፡፡ ኢየሱስ የእግዚአብሔር መልዕክት (Logos 1:1:14) እና የእግዚአብሔር እውነት ተብሎ ተጠርቷል (14:6)፡፡ መንፈስም ብዙ ጊዜ የእውነት መንፈስ (14:17፤ 15:26፤ 16:13)፡፡ አማኞች በእውነቱ እንደሚቀደሱ ልብ በል (ቁ. 19 ተደራጊ ቦዝ አንቀፅ) እንዲሁም ደግሞ በንፈሱም ይቀደሳሉ (1ጴጥ 1:2)፡፡ "እውነተኛ፣ እውነት" የማሉትን ቃላት የግሪክ ምንጫቸውን ለማወቅ በ6:55 እና 17:3 ላይ በእውነት ላይ የቀረበውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

"ቃልህ እውነት ነው" የሚለው ከመዝ 118:142 የስብተዋጀንት ትርጉም የተጠቀሰ ሳይሆን አይቀርም፤ "ጽድቅህ ለዘላለም የሚኖር ፅድቅ ነው፣ ቃልህም እውነት ነው" በእርግጠኝነት ለመናገር የሚቻለው ኢየሱስ ምናልባት የታየው እንደ

1. አዲሱ ሙሴ (ዘዳ 18:15)
2. ደቀመዛሙርቱ እንደ አዲስ ካህናት (መቀደስ የሚለው ግስ አጠቃቀም)
3. ሕይወቱ እንደ እውነተኛ አምላክ እውነተኛ መገለጥ
4. የስላሴ አካላት እና የደቀመዛሙርቱ ሕብረት የፍጥረት ዓላማ ፍፃሜ እንደሆነ (ዘፍ 1:26-27)፡፡
5. ኢየሱስ የዘፍ 3:15 ፍፃሜ እንደሆነ

17:18 **"ወደ ዓለም እንደላክኸኝ እንዲሁም"** እስከሞት ድረስ የዘለቀው (2ቆሮ 5:14-15፤ ገላ 2:20፤ 1ዮሐ 3:16) የኢየሱስ መታዘዝና ማገልገል ለእርሱ ተከታዮች ምሳሌነት ያለው ነው (ቁ.19)፡፡ በዮሐንስ 20:21 ላይ እርሱ እንደተላከው ሁሉ እርሱም እነርሱን ወደ ጠፋው ዓለም ይልካቸዋል፡፡ ዓለምን ሊያሸንፍና ሊማርኩ ይገባቸዋል እንጂ ከዓለም ሲወጡ አይገባቸውም፡፡ በ5:21 ላይ መላክ (አፖስቴሎ) የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

17:19 **"እኔ ራሴን ስለእነርሱ እቀድሳለሁ"** በዚህ ዓውድ ውስጥ ይህ ማመልከት የሚገባው ቀራኒዮን ነው! ኢየሱስ የአባቱን ፈቃድ ለማድረግ ራሱን አዘጋጅቷል (ማር 10:45)፡፡

▣ "በእውነት የተቀደሱ እንዲሆኑ" ይህ ተደራጊ ቦዝ አንቀፅ የሆነ ዓላማን የሚያመለክት ሐረግ ሲሆን ይህም የሚያሳየው ውጤቱ መከሰቱንና ቀጣይነት እንዳለው ነው፡፡ ይሁን እንጂ በሚከተሉት ሐሳቦች መሠረት በአግባቡ ላይ ቀጣይነት ያለው ነገር እንዳለ መረዳት ይቻላል፤

1. በመስቀሉ፣ በትንሳኤው እና በእርገቱ ሊመቻ ያለው የክርስቶስ ሥራ
2. የደቀመዛሙርቱ ለኢየሱስ እና ለትምህርቶች የሚሰጠው እምነትን የተሞላ ምንሻ የሚሉት ናቸው፡፡

በ6:55 እና 17:3 ላይ እውነት የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 17፥20-24

[20-21]**ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ: ከቃላቸው የተነሣ በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ ስለ እነዚህ ብቻ አልለምንም፤ አንተ እንደ ላክኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ: አንተ: አባት ሆይ: በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ: እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ፡፡ [22-23]እኛም አንድ እንደሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ፤ እኔም በእነርሱ አንተም በእኔ ስትሆን: በአንድ ፍጹማን እንዲሆኑ: የሰጠኸኝን ክብር እኔ ሰጥቻችኋለሁ፤ እንዲሁም ዓለም አንተ እንደላክኸኝ በወደድከኝም መጠን እነርሱን እንደወደድካቸው ያውቃል፡፡ [24]አባት ሆይ: ዓለም ሳይፈጠር ስለወደድከኝ የሰጠኸኝን ክበሬን እንዲያዩ እኔ ባለሁበት የሰጠኸኝ እነርሱ ደግሞ ከእኔ ጋር ይሆኑ ዘንድ እወዳለሁ፡፡**

17:20 "**በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ**" ይህ የአሁን ጊዜን የሚያመለክት ሲሆን የሚያገለግለው የወደፊቱን ጊዜ ነው፡፡ ይህ ሁሉንም አማኞች የሚጠቃልል ሲሆን በ10:16 ላይ አህዛብንም ጭምር ያመለክታል፡፡ በ2:23 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስን ይመልከቱ፡፡

▣ "**ከቃላቸው የተነሣ**" ይህ *logos* (ሎጐስ) የሚለው ቃል ነው፡፡ በቁ. 14 ላይ በመጠቀሱና በቁ 8 ላይ ከተጠቀሰው *Rhema* (ሬማ) ከሚለው ጋር ተመሳሳይነት ስላለው ደቀመዛሙርቱ በኢየሱስ መገለጣዊ መልእክት ውስጥ ማለፋቸውን የሚያመለክት መሆን አለበት፡፡

17:21 "**ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ**" ይህ ከሥላሴ አንኑት ውጪ ሊሆን አይችልም (ቁ.11:22፣23፤ ኤፌ 4:1-6)፡፡ ይህም ተከታዮቹ እንዳልተከተሉት የሚያሳይ አንዱ የኢየሱስ ትምህርት አቅጣጫ ነው፡፡

▣ "**አንተ እንደላክኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ**" ይህ የአሁን ጊዜ ስሜ ገላጭ አነጋገር ነው፡፡ በኢየሱስ ፀሎት ላይ ውጥረት ያለ ይመስላል፣

ለዓለም አይፀልይም (ቁ. 9) ይሁን እንጂ ሃዳ መከራ ሊያመጣቸው የሚችለውን መልዕክት ደቀ መዛሙርትን አስይዞ ወደ ዓለም ይልካቸዋል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ዓለመን ስለሚወድ (ቁ. 21:23፤ 3:16)፡፡ እግዚአብሔር መላው ዓለም በእርሱ እንዲያምን ይፈልጋል (1ጢሞ 2:4፤ ቲቶ 2:11፣ 2ጴጥ 3:9)፡፡ እግዚአብሔር በመልኩና በአምሳሉ የተፈጠሩትን ሁሉ ይወዳል፤ ኢየሱስም የሞተው ለዓለም ሁሉ ኃጢአት ነው፡፡ በ5:24 ላይ መላክ (አፖስቲሎ) የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

17:22 "**የሰጠኸኝን ክብር ሰጥቻቸዋለሁ**" እነዚህ ሁለቱ የድርጊት መጠናቀቅን አመልካች ግሦች ናቸው፡፡ ክብር የሚለው የተገለጠውን መልዕክት የሚያመለክት መሆን አለበት፡፡ ኢየሱስ የአባቱን ቃል እንደተሸከመ ሁሉ እነርሱም ሊሸከሙ ይገባቸዋል፤ ይህም የእርሱን አቀራረብ (አካሄድ) እንዲሸከሙ የደርጋቸዋል፤ ኤቲ ሮበርትሰን Word Pictures iN the New TestameNt (**ቅፅ** 5) በሚለው መፅሐፋቸው ላይ እንዲህ ይላሉ፤ በ17:24 ላይ የተጠቀሰው ሥጋ የለበሰው ቃል እንጂ (1:14 እና 2:11) የዘላለማዊውን ቃል ክብር አይደለም (ገጽ 280)፡፡

17:23 "**በአንድ ፍፁማን እንዲሆኑ**" ይህ በቁ.19 ላይ እንደተጠቀሰው ተመሣሣይ ትርጉም ያለው ዓላማን የሚያመለክት ሐረግ *(hiNa)* ነው፤ ይሁን እንጂ እንደ ቁ.19 ሁሉ ቀጣይነት ያለው ሐሳብ በወስጡ ስላለው መሠረት የደረገው፣ (1) ሲመጣ ባለው የክርስቶስ ሥራ ወይም (2) ቀጣይነት ስላለው እምነታቸው በተዘዋዋሪም የሚጠቅሰው ደቀመዛሙርት አንድነት መፍጠራቸውንና ይህም ፀንቶ የሚኖር መሆኑን ነው የአንድነት ዓላማውም ወንጌልና መስበክ (መሠራጨት) ነው፡፡

▣ "**በወደድኸኝም መጠን እነርሱን እንደወደድካቸው**" ይህ ተስፋ ነው (16:27 እና 14:21፣23) ነገር ግን መሟላት የሚገባው ሁኔታ አለ፡፡ እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ሕብረትን የሚያደርገው በቃል ኪዳን ነው (እንዲህ ቢሆን --- እንዲህ ይሆናል)፡፡

በዮሐንስ 1-12 ውስጥ መውደድ (*agapeo*) ስምንት ጊዜ ሊጠቀስ ነገር ግን በዮሐ 13-17 ውስጥ ከ31 ጊዜያት ተጠቅሷል፡፡ በላይኛው ደርብ የተካሄዱት ንግግሮች በአብዛኛው የተሞሩት በወልድ ቃላትና ድርጊቶች የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ባህርያት ሲሆን ከዚያም በመቀጠል በትንሣኤው እና በተለይም በደቀመዛሙርት በኩል የበዓለ ሃምሣ ልምምድ፤ እግዚአብሔር ፍቅር ነው (1ዮሐ 4:7-21)፡፡

17:24 **"እኔ ባለሁበት የሰጠኸኝ እነርሱ ደግሞ ከእኔ ጋር ይሆኑ ዘንድ"** እርሱን ለሚከተሉት ሥፍራን ያዘጋጅ ዘንድ ኢየሱስ ወደ ክብሩ ሊመለስ ነው (14:1-3)፡፡ ይህ ዓለም ለእነሱም እንዳልሆነ የእኛም አይደለም! የእርሱ ፍጥረት (ዘፍ 1-2) እና ተምልሶም የሚታደስ ነው (ራዕይ 21-22)፡፡

▣ **"የሰጠኸኝን ክብሬን እንዲያዩ"** "ክብር" የሚለው ቃል በቁጥር 22 እንዳለው ትርጉም እዚህ ላይ ተመሳሳይ እንዳልሆነ ግልፅ ነው፡፡ እዚህ ላይ ኢየሱስ ከፍጥረት በፊት የነበረውን ክብርና ግርማ የሚያካትት ይመስላል፡፡

▣ **"ዓለም ሳይፈጠር"** የሥላሴ አካላት ከፍጥረት በፊትም እንኳን በሥራ ላይ ነበሩ፡፡ ይህ ሐረግ በአዲስ ኪዳን ለብርካታ ጊዜያት ተጠቅሷል (ማቴ 25:34፤ ሉቃ 11:50፤ ኤፌ 1:4፤ ዕብ 4:3፤ 9:26፤ 1ጴጥ 1:20፤ ራዕ 13:8፤ 17:8)፡፡

> NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 17÷25-26
> **25ጻድቅ አባት ሆይ: ዓለም አላወቀህም: እኔ ግን አወቅሁህ እነዚህም አንተ እንደላክኸኝ አወቁ፤ 26እኔንም የወደድክባት ፍቅር በእነርሱ እንድትሆን እኔም በእነርሱ: ስምህን አስታወቅኋቸው፡፡ አስታወቅቸዋለሁ፡፡**

17:25 **"ጻድቅ አባት ሆይ"** ይህ መጠሪያ የሚገኘው በአዲስ ኪዳን ብቻ ነው፡፡ በቁጥር 11 ላይ "ቅዱስ አባት ሆይ" ከሚለው ጋር ተመሣሣይ (ትይዩ) ነው፡፡ ትርጓሜውም የመጣው "ሸንበቆን መለካት" ከሚለው የእብራይስጥ ቃል ነው፡፡ እግዚአብሔር የፍርድ ሁሉ መለኪያ ነው! በ1ዮሐ 2:29 ላይ ልዩ ርዕስን ይመልከቱ፡፡

▣ **"ዓለም አላወቀህም"** ከእግዚአብሔር ተለይቶ የተደራጀውና የሚንቀሳቀሰው ዓለም (የዮሐንስ ልዩ አጠቃቀም) እግዚአብሔርን አያውቅም (17:25) ልጁንም አያውቅም (1:10)፡፡ ዓለም ክፉ እና በክፋት የተሞላ ነው (3:19-20፤ 3:11)፡፡

▣ **"እኔ ግን አወቅሁህ"** ኢየሱስ እግዚአብሔርን በሚመለከት ከሁሉም የላቀውና የጠራው የመረጃ ምንጭ ነው (1:8፤ 3:11)፡፡

17:26 **"ስምህን አስታቅኋቸው"** ይህ ኢየሱስ የአብን ባህሪይና ለሰው ልጆች ያለውን የማዳን ዕቅዱን የሰጠውን መገለጥ የሚያመለክት ነው (ቁ. 6:11፡12፤ ሐዋ 2:23፤ 3:18፤ 4:28) አስታወቅኋቸው የሚለው ቃል በቁ. 25:26 ላይ አምስት ጊዜያት ተጠቅሷል፡፡

▣ **"አስታውቃቸውማለሁ"** ይህ (1) የኢየሱስን ትምህርቶች ግልፅ የሚያደርገው የመንፈስ ቅዱስን ቀጣይነት የለውን መገለጥ ወይም (2) ሊከሰቱ ያሉትን የድነት ሁኔታዎችን ያመለክታል፡፡ የምንባቡ ዓውድ በተዘዋዋሪ የሚገልፀው ቁ. 1ን ነው፡፡ ድነት ስብዕናንም መልዕክትን ውሣኔንና የሕይወት ዘይቤን የመጀመሪያና ቀጣይ እምነትን ያካትታል፡፡ እንዲሁም "ማወቅ" የሚለውን የግሪኩን ሃሳብንና "ማወቅ" የሚለውን የእብራይስጡን ሃሳብ የሚያጠቃልል ነው፡፡

### የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ሊሆን የሚችል ማብራሪያ በመሆኑ ለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጐም ኃላፊነት አለብህ፡፡ እያንዳንዳችን ልንሔድ የሚገባን ባለን መረዳት መጠን ነው፡፡ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጐም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣችሁ ናችሁ፤ በመሆኑም ይህንን በሚያብራራው ሰው ላይ ብቻ ልትተው የሚገባ አይደለም፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ባሉት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ በጥሞና እንድታስበብት ለመረዳት ይቻል ዘንድ ነው፤ በመሆኑም ጥያቄዎቹ እንደ ሐሳብ - አነሳሽ ሆነው እንጂ በግልፅ ወይም በቀጥታ አይደለም፡፡

1. ከስነ-መለኮት አንፃር ይህ ፀሎት ለምን አስፈለገ
2. ይሁዳ ከውጋው የወደቀ አማኝ ነበር
3. የአንድነታችን ዓላማ ምንድነው
4. የኢየሱስ ከፍጥረት በፊት መኖሩ አስፈላጊነት ለምንድነው
5. በዚህ አውድ አንፃር ለእነዚህና ቁልፍ ቃላት ፍቺ ስጥ፡፡
   ሀ. "ክበረ"
   ለ. "ሰጠ"

ሐ. “ማወቅ”
መ. “መላክ”
ሠ. “ስም”
ረ. “ዓለም”

# ዮሐንስ ምዕራፍ 18

## የተሻሻሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀፅ አከፋፈል

| UBS[4] | NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| ኢየሱስ መከዳት እና መያዝ | መከዳትና መያዝ በጌቴሴማኒ | መያዝ፣ ፍርድ እና መሰቀል የኢየሱስ መቀበር<br>(18:1-19:42) | የኢየሱስ ተያዘ | የኢየሱስ ተያዘ |
| 18:1-11 | 18:1-11 | 18:1-11 | 18:1-4 | 18:1-9 |
| | | | 18:5ሀ | |
| | | | 18:5ለ | |
| | | | 18:5ሐ-7ሀ | |
| | | | 18:7ለ | |
| | | | 18:8-9 | |
| | | | 18:10-11 | 18:10-11 |
| ኢየሱስ በሊቀ ካህኑ ፊት ቀረበ | በሊቀ ካህኑ ፊት ቀረበ | | ኢየሱስ በሃናኒያ ፊት ቀረበ | ኢየሱስ በሃናኒያና በቀያፋ ፊት ቀረበ፤ ጴጥሮስ ካደው |
| 18:12-14 | 18:12-14 | 18:12-14 | 18:12-14 | 18:12-14 |
| የጴጥሮስ ኢየሱስን መካድ | ጴጥሮስ ኢየሱስን ካደ | | ጴጥሮስ ኢየሱስን ካደ | |
| 18:15-18 | 18:15-18 | 18:15-18 | 18:15-17ሀ | 18:15-18 |
| | | | 18:17ለ | |
| | | | 18:18 | |
| ሊቀ ካህኑ ኢየሱስን ጠየቀ | ኢየሱስ በሊቀ ካህኑ ተጠየቀ | | ሊቀ ካህኑ ኢየሱስን ጠየቀ | |
| 18:19-24 | 18:19-24 | 18:19-24 | 18:19-21 | 18:19-24 |
| | | | 18:22 | |
| | | | 18:23 | |
| | | | 18:24 | |
| ጴጥርስ ኢየሱስን ደግሞ ካደው | ጴጥሮስ ለሁለተኛ ጊዜ ካደው | | ጴጥርስ ኢየሱስን ደግሞ ካደው | |
| 18:25-27 | 18:25-27 | 18:25-27 | 18:25ሀ | 18:25-27 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ኢየሱስ በጲላጦስ ፊት | በጲላጦስ ሸንጎ | | ኢየሱስ በጲላጦስ ፊት | ኢየሱስ በጲላጦስ ፊት |
| 18:28-38ሀ | 18:28-38 | 18:28-32 | 18:28-29 | 18:28-32 |
| | | | 18:30 | |
| | | | 18:31ሀ | |
| | | | 18:31ለ-32 | |
| | | 18:33-38ሀ | 18:33 | 18:33-19:3 |
| | | | 18:34 | |
| | | | 18:35 | |
| | | | 18:36 | |
| | | | 18:37ሀ | |
| | | | 18:37ለ | |
| | | | 18:38ሀ | |
| ኢየሱስ እንዲሞት ተፈረደበት | የበርናባስን ስፍራ መውሰድ | | ኢየሱስ እንዲሞት ተፈረደበት | |
| (18:38ለ-19:16ሐ) | | | (18:38ለ-19:16ሀ) | |
| 18:38ለ-19:7 | | 18:38ለ-19:7 | 18:38ለ-39 | |
| | 18:39-40 | | | |
| | | | 18:40-19:3 | |

## ***ሦስተኛ የምንባብ ዑደት (አንቀ-53 ይመ)***
***የመጀመሪያው ፀሐፊ ሐሳብ በአንቀፅ ደረጃ መከተል***

*ይህ የጥናት መመሪያ ሊሆን የሚችል ማብራሪያ በመሆኑ ለምትከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለባችሁ። እያንዳንዳችንም መጓዝ ያለብን ባለን መረዳት መሠረት ነው። ስለሆነም እናንተ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጎም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ናቸው። በመሆኑም ይህንን ጉዳይ አስተያየት በሚሰጠው ሰው ላይ ብቻ መተው የለባቸውም።*

*መሉውን ምዕራፍ በአንድ ቅፅበት አንብበው፤ ዋና ሐሳቦችንም ለያቸው። የራስህን ክፋፈል ከአምስቱ ትርጓሜዎች አከፋፈል ጋር አስተያየው። በአንቀፅ መከፋፈል በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት የሚደረግ ባይሆንም የአተረጓጎም ምሳይ የሆነውን የመጀመሪያውን ፀሐፊ ዋና ሐሳብ ለመከተል ግን ጉዳይ ነው። ማንኛውም አንቀፅ የሚናገረው ስለ አንድ ሐሳብ ብቻ ነው።*

1. *የመጀመሪያ አንቀፅ*
2. *ሁለተኛ አንቀፅ*
3. *ሶስተኛ አንቀፅ*

4. ወ.ዘ.ተ

*ሥነ-መለኮታዊ ግንዛቤዎች*፤ 18:1-40

ሀ. ዮሐንስ በጌቴሴማኒ የነበረውን የኢየሱስን *መቃተት* አላካተተውም (ምንም እንኳን ምዕራፍ 17 ሊነፃፀር ቢችልም)፡፡ የዚህም ምንያቱ በግልፅ እንደሚታየው የዮሐንስ ትኩረት ሁኔታዎችን በሚቆጣጠረው የኢሱ ልዩ ባህርይ ላይ በመሆኑ ነው፡፡ በዚህም ኢየሱስ የገዛ ራሱን ሕይወት ለበጎቹ እንደሚያኖር የገለጠበት ሁኔታ ይታያል (10:11፡15፡17፡18)፡፡

ለ. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሚገኙት ክስተቶች ቅደም ተከተል ከሌሎች ወንጌላት በመጠኑ ይለያል፤ ይህም ልዩነት ሲገናኝ የሚችለው፤

1. ከአይን ምሥክሮች ታሪክ አንፃር
2. ከፀሐፊው ሥነ-መለኮታዊ ዓላማ አንፃር ነው፡፡

ሐ. ዮሐንስ ከወንጌላት ለየት ይላል፤ ለምንና እንዴት የሚሉትን ጥያቄዎች ሊቃውንት ሊመልሱት የሚችሉት አይደለም፡፡ እኔ እንዳየሁት በዚህ ጉዳይ ላይ ከሁሉም የተሻለው ምንጭ ብዙ ፅንሰ-ሐሳቦን በውስጡ የሚሰጠው የጎርደን ፊ እና የግለላ ስቱዎርት: How *To Read the Bible for All Its Worth* የሚለው መፅሐፍ ነው፡፡ በግልፅ ማየት እንደሚቻለው የወንጌላት ፀሐፊዎች በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የኢየሱስን ንግግሮችና ሥራዎች

1. ከሌሎች የመምረጥ
2. ከሌሎች ጋር የማስማማት
3. እንዲሁም የማስተካከል ምርጫ ነበረው፡፡

ፀሐፊዎቹ ንግሮንና ሥራዎችን መፍጠር ይችላሉ ብዬ ማሰብ ባልችልም፡ ለተለያዩ ሕዝቦች ኢሱስን ለሙግለጥ ይረዳቸው ዘንድ ለወንጌል ዓላማቸው ሊያስማሟቸው ይችላሉ፡፡ ወንጌላት የተፃፉ የምዕራባዊያን ታሪኮች (የምክንያትና የውጤት እንዲሁም የጊዜ ቅደም ተከተል) ሳይሆኑ የምሥራቃዊያን ታሪኮች ናቸው፡፡ የሕይወት ታሪኮች ሳይሆኑ የወንጌል ትራክቶች ናቸው፡፡

## የቃል እና የሐረግ ጥናት

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 18:1-11
**1ኢየሱስም ይህን ብሎ አትክልት ወዳለበት ስፍራ ወደ ቁድሮን ወንዝ ማዶ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወጣ፤ እርሱም ደቀ መዛሙርቱም በዚያ ገቡ፡፡ 2ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱም ብዙ ጊዜ ወደዚያ ስለተሰበሰቡ አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ ደግሞ ስፍራውን ያውቅ ነበር፡፡ 3ስለዚህ ይሁዳ ጭፍሮችንና ከካህናት አለቆች ከፈሪሳዊያንም ሎሌዎችን ተቀብሎ በችቦና በፋና በጋሻ ጦርም ወደዚያ መጣ፡፡ 4ኢየሱስም የሚመጣበትን ሁሉ አውቆ ወጣና፡- ማንን ትፈልጋላችሁ? አላቸው፡፡ 5የናዝሬቱን ኢየሱስን ብለው መለሱለት፡፡ ኢየሱስ፡- እኔ ነኝ አላቸው፡፡ አሳልፎ የሰጠውም ይሁዳ ደግሞ ከእነርሱ ጋር ቆሞ ነበር፡፡ 6እንግዲህ፡- እኔ ነኝ ባላቸው ጊዜ ወደኋላ አፈግፍገው በምድር ወደቁ፡፡ 7ደግሞም፡- ማንን ትፈልጋላችሁ? ብሎ ጠየቃቸው፡፡ እነርሱም፡- የናዝሬቱን ኢየሱስን አሉት፡፡ 8ኢየሱስ መልሶ፡- እኔ ነኝ አልኋችሁ፤ እንግዲህ እኔን ትፈልጉ እንደሆናችሁ እነዚህ ይሂዱ ተውአቸው አለ፤ 9ይህም፡- ከእነዚህ ከሰጠኸኝ አንዱን ስንኳ አላጠፋሁም ያለው ቃል ይፈፀም ዘንድ ነው፡፡ 10ስምዖን ጴጥሮስም ሰይፍ ስለነበረው መዘዘው: የሊቀ ካህናቱንም ባርያ መትቶ ቀኝ ጆሮውን ቆረጠ፤ የባርያውም ስም ማልኮስ ነበረ፡፡ 11ኢየሱስም ጴጥሮስን፡- ሰይፍህን ወደ ሰገባው ክተተው፤ አብ የሰጠኝን ጽዋ አልጠጣትምን? አለው፡፡**

**18:1 "*ቁድሮን ወንዝ ማዶ*"** "ወንዝ" የሚለው ቃል "የክረምት ምንጭ ወይም"በክረምት የሚሞላ ደረቅ ወንዝ" ማለት ነው፡፡ "ቄድሮን" (*BDBS71*) ማለት (1) ቄዳሮች ወይም (2) ጥቁር ማለት ነው፡፡ ይህ በበጋ ወቅት ሙሉ በሙሉ የሚደርቅ ወንዝ ሲሆን በክረምት ወቅት ግን ፈጣንና የሚያጥለቀልቅ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር ከሞርያም ተራራ የሚወርደው የመሥዋዕቶች ደም የሚደርቅበት ሥፍራ ነበር፡፡ ይህም ምናልባት "ጥቁር" የሚለው ቃል መገለጫ ሲሆን የሚገኘውም በቤተመቅደሱ ተራራ እና በደብረዘይት ተራራ መካከል ነበር (ስብትዋጅንት፣ 2ሳሙ15:23፡2ነገ23፣4:6፡12:2ዜና 15:16፤29:16፤30:14፤31:40)፡፡
በዚህ ጉዳይ ላይ የግሪክ ምንጮ ልዩነት አላቸው፡፡

1. "የቄዳሮች"(*KedrioN*) በMSS $N^C$: B: C: L እና ሌሎች በርካታ ምንጮች
2. (*KEDROU*) በ*MSS* $N^*$: D, እና W
3. (*KEDRON*) በ*MSS* A እና S

አራተኛው የUBS መጽሐፍቅዱስ እትም 3ኛውን አማራጭ ይጠቀማል፡፡

▣ **"አትክልት ወዳለበት *ሥፍራ*"** ይህ ምራፍ በጌቴሴማኒ የነበረውን የኢየሱስን መቃቶት ሙሉ በሙሉ አላካተተውም፤ ነገር ግን በአትክልቱ *ሥፍራ* የሙተዮን ክፍተት ይገልፀዋል፡፡ ይህ ኢየሱስ የሚያርፍበት የተወደደ *ሥፍራ* ነበር (ቁ.2፤ ሉቃ 22:39)፡፡ በግልፅ መረዳት እንደሚቻለው በዚህ ስፍራ በመጨረሻ የሕይወቱ ሣምንት ተኝታ እንደነበር ነው (ሉቃ 21፡37)፡፡

የአትክልት *ሥፍራዎች* በኢሩሳሌም አይፈቀዱም ነበር፤ ምክንያቱም ለመሬቱ የሚስፈልገው ማዳበሪ ከተማይቱን ያረክስ ስለነበር ነው፤ በመሆኑም ብዙዎች ሀብታም ሠዎች የወይን ቦታዎች የፍራፍሬ እርሻ ቦታ ወዘተ በደብረዘይት ተራራ ላይ ነበራቸው፡፡ 18:2 ይህ በዮሐንስ የተሰጠ ሌላ የኤዲቶሪያ ማብራሪያ ነው፡፡

▣ **"ይሁዳ"** ስለ ይሁዳና ስተነሳሳበት ምክንያቶች ብዙ ግምት አለ፡፡ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ብዙውን 29 ይሁዳ የተገለፀው ስሙ እየጎደፈ ነበር (6፡70-71፤12:4፤ 13:2፡26-39፤18:2፡3፡5)፡፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ *ሥመጥር* ተዋናይ" የሚለው የዘመናችን ትዕይንት ይሁዳ ታማኝ ነገር ግን እንዳሰበው ሳይሆንለት የቀረ ተከታይ ኢሱስ የብሉይ ኪዳን አይሁዳዊ መስህ መሆኑን የሚላ ዘንድ የቀረ ተከታይ፤ ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን አይሁዳዊ መስህ መሆኑን ያሚላ ዘንድ ግፊት ለማድረግ የጣረ- ይህም የሮማዊያንን መንግሥት ለመገልበጥ፣ ክፉዎችንም ለመቅጠት፣ ኢየሩሳሌምንም የአለም ዋና ከተማ (መናገሻ) ለማድረግ እንደሆነ ያሣያል፡፡ የሁን እንጂ ዮሐንስ እርሱ የተነሣበትን ሃሳብ እንደለግብግብነትና በሰይጣን እንደተጠነሰሰ ይገልፀዋል፡፡

ዋናው ቸግር ግን የእግዚአብሔር ሉዓላዊነትና የሰው ነፃ ፈቃድ *ሥነ*-መለኮታዊ ጉዳይ ነው፡፡ እግዚአብሔር ወይስ ኢየሱስ ይሁዳን ያግባባው ሰይጣን ተቆጣጥሮት ከሆነ ወይም ኢሱስን እንዲከዳው እግዚአብሔር አስቀድሞ የወሰነ ከሆነ ይሁዳ ለድርጊቶቹ ተጠያቂ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ለእነዚህ ጥያቄዎች በቀጥታ ምላሽ አይሰጥም፤ እግዚአብሔር ታሪክን ይቆጣጠራል፤ የወደፊት ክስተቶችንም ያውቃል፤ ነገር ግን የሰው ልጅ ለምርጫዎች እና ለድርጊቶቹ ኃላፊነት አለበት፡፡ እግዚአብሔር ሰው እንዲሳሳት የሚያግባባ ሳይሆን ወረት የማይለውጠው ታማኝ ጓደኛ ነው፡፡

በዋልያም ክላስን የተፃፈ (1996) ይሁዳን ለመከላከል የሚሞክር አዲስ መፅሐፍ አለ፤ እርሱም፡- Judas Betrayer of FrieNd of Jesus? የሚል ነው፡፡ ምንም እንኳን ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ የሰጠውን ም*ሥ*ክርነት ዝቅ ስለሚያደርገው የማልስማማበት ቢሆንም፣ ደስ የሚያሰኝና ሃሳብ ቀስቃሽ ነው፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ መመረጥ/አስቀድሞ መወሰንና የሥነ-መለኮታዊ ሚዛን አስፈላጊነት**

መመረጥ አስደናቂ አስተምህሮ ነው፡፡ ይሁዳ እንጂ ለማዳላት የሚደረግ ጥሪ ሳይሆን ለሌሎች መዳን ምክንያት ወይም መተላለፊ ለመሆን የሚደረግ ጥሪ ነው በብሉይ ኪዳን ቃሉ አስቀድሞ የጠቀሰ የነበረው ለአገልግሎ ሲሆን በአዲስ ኪዳን ደግሞ ለድነት ነው፡፡ አማኝ የማይታረቁ የሚመስሉትን የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነትና የሰውን ነፃ ፈቃድ ለማስታረቅ ጥረት አያደርግም ነገር ግን ሁለቱም እውነትነታቸውን ያረጋግጣል እንጂ ለመፅሐፍቅዱሳዊው ውጥረት ጥሩ ምሣሌ የሚሆነው በሮሜዳ ላይ የተጠቀሰው የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ምርጫና በሮሜ 10 ላይ የተጠቀሰው የሰው ልጅ አስፈላጊ ምንጭ ነው(10÷11፤13)፡፡

ለዚህ *ሥነ*-መለኮታዊ ውጥረት መፍቻ የሚገኘው ምናልባት በኤፌ 1፡4 ውስጥ ነው፡፡ ኢየሩስ በእግዚአብሔር የተመረጠ ሲሆን በእርሱም ምክንያ ሌሎች ተመርጠዋል (karl Barth)፡፡ ኢየሱስ ለመደቀው የሰው ዘር ፍላጎት የእግዚአብሔር ‹‹አዎን›› ነው(kar Barth) እንዲሁም ኤፌ 1፡4 አስቀድሞ የመመረጥ ግቡ መንግሥተ ሰማይ ሳይሆን መቀደስ (ክርስቶስን መምሰል) ነው የሚለውን ሐሳብ ለማፅኖት የሚረዳ ነው ብዙውን ጊዜ ልባችን ወንጌል በሚያስገኘው ጥቅም ላይ ይሰባል የሁን እጂ ኃላፊነቶችን ችላ ይል የእግዚአብሔር ጥሪ/ ምርጫ) ለጊዜውም ለዘላለምም ነው

ብዙውን ጊዜ አስተምህሮዎች ከሌሎች እወንቶች ጋር ተጣምረው እንጂተነሰለው ተለያይተው አይደለም፡፡ ለዚህ ጥሩ ተምሳሌት የሚሆነን ሕብረኮከብ እና ነጠላ (አንድ) ኮከብ ነው፡፡ እግዚአብሔር እውነትን የሚያቀርበው በምዕራባዊያን ሳይሆን በም*ሥ*ራቃዊያን መረዳቶች ነው፡፡ በዘዴ ምክንያት የተፈጠሩ (ተፃራሌ የሚመልሱ) ንጥያ አስተምህሮታዊ ጥንይችን ልናስወግዳቸው አይገባንም፡፡

1. አስቀድሞ ወወሰን ወይስ የሰው ነፃ ፈቃድ
2. የአማኞች ደህንነት ወይስ የመፅናት አስፈላጊነት
3. የተፈጥሮ ኃጢያት ወይም የፈቃድ ኃጢያት
4. ኃጢአት የለሽነት (ፍፁምነት) ወይስ ኃጢአተኝነትን መቀነስ
5. የመጀመሪያ ቅፅበታዊ ፅድቅና ቅድስና ወይስ ቀጣይነት ያለው ቅድስና
6. የክርስትያን ኃጢያት ወይስ የክርስትያን ነፃነት
7. የእግዚአብሔር ታላቅነት ወይስ የእግዚአብሔር ቅርብነት
8. እግዚአብሔር ሲታወቅ የማይችል ወይስ እግዚአብሔር በቃሉ የሚታወቅ
9. አሁን የምትገለጥ የእግዚአብሔር መንግስት ወይስ ወደፊት የምትገለጥ መንግሥት

10. ንስሐ እንደ እግዚአብሔር ሥጦታ ወይስ ንስሐ ለሰው ቃልኪዳናዊ አስፈላጊ ምላሽ

11. ኢየሱስ እንደ አምላክ ወይስ ኢየሱስ እንደ ሰው

12. ኢየሱስ ከአብ እንደሚተካከል ወይስ ኢየሱስ ለአብ እንደሚገዛ

"ቃልኪዳን" የተሰኘው ሥነ-መለኮታዊ ሃሳብ የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት (ቀዳሚውን ድርሻ ሁል ጊዜ የማወሰድ ነው) መጀመሪያና ቀጣይነት ካለው የሰው ልጆች በእምነት ከሚሰጡት ምላሽ ጋር ያስተሳስራል። አንዱን የጥምረቱን አካል ብቻ ከመደገፍ ሌላውንም ዝቅ ከማድረግ ተጠበቅ እንዲሁም ደግሞ የራስህን ተወዳጅ አስተምህሮወይም ሥነ-መለኮታዊ ሥርዓት ብቻ ከመደገፍም ልትቆጠብ ይገባል።

18:3

| | |
|---|---|
| NASB | **"የሮም ጭፍሮችን"** |
| NKJV | **"የጭፍሮች ክፍል"** |
| NRSV | **"የወታደሮች ክፍል"** |
| TEV | **"የሮም ወታደሮ ቡድን"** |
| NJB | **"ጓድ"** |

ይህ የሮማን ወታደራዊ ክፍል የሚያመለክት ሲሆን አሥረኛ ክፍልና 600 ሰዎችን የሚያቅፍ እና ከቤተመቅደሱ ቀጥሎ በሚገኘው (ሐዋ 21:31:31:33) የአንቶ ኢዮ የጦር ምሽግ ከተማ ላይ የሠፈረ ነው። ነገር ግን ይህን ያህል ቁጥር መጠራቱ የሚያጠራጥር ይመስላል። ሮማውያን ግን በበደላት ምክንያት በኢየሩሳሌም ብጥብጥ እንደይከሰት ተዘጋጅተው ነበር፤ በመሆኑመ ወታደሮን ከቂሣሪያ በባህር በመጓጓዝ አስፈላጊውን ቅድመ ጥንቃቄ መውሰድ ይችል ነበር። ሮማውያን በኢየሱስ የፍርድ ሂደት ውጥ ተሳትፈው ነበር፤ ምክንያቱም አይሁዶች ኢየሱስ እንዲሰቀል አጥብቀው ይሹ ነበርና። ይህ ምናልባት በርካታ ቀናትን ሊፈጅ ይችል ነበር፤ በመሆኑም ይህንን ማድረግ ይችሉ የነበሩት የሮም መንግሥትን ፈቃድና ትብብር ሊያገኙ ብቻ ነበር።

▣ **"ጭፍሮችንና ከካህናት አለቆች"** ሴዋዊያን የሚያገለግሉበትን ቤተመቅደስ የሚጠብቁ ፖሊሶች የሮማን የጦር ሠፈር ያጀቡ ስለነበር ኢየሱስን ለመያዝ አልችሉም ነበር (7:32፤45)።

▣ **"በጋሻ ጦርም"** ጦር የሮም ወታደሮች የሚይዙት ሲሆን (6:64፤13:1:11) ዱላዎች ደግሞ ቤተመቅደሱን በሚጠብቁ ፖሊሶች የሚይዙ ነበር (ማቴ 26-43ማር 14:43፤ ሉቃ 22:52)።

**18:4 "ኢየሱስም የሚመጣበትን ሁሉ አውቆ ወጣና"** ይህ ኢየሱስ ስለ ራሱ መያዝ፣ ወደ ሽንጎ መቅረብና መስቀል ያለውን እውቀት በአፅንኦ የሚያመለክት ነው(10:11፤15፤17፤18)። የኢየሱስ መስቀል አጋጣሚ አልነበረም (ማር 10:45፤ ሐዋ 2:23፤3:18፤14-29)። ይህ ጭብጥ የዮሐንስ ወንጌል ዋና መሰየሙ ሲሆን ምናልባትም በጌቴሴማኒ የነበረውን መቃታትና ስቃይ ያልገለፁበት ምክንያት ተደርጎ ሊወስድ ይችላል።

18:5

| | |
|---|---|
| NASB፤ NJB | **"የናዝሬቱ ኢየሱስን"** |
| NKJV፤NRSV፤ | |
| TEV | **"የናዝሬት ኢየሱስ"** |

**"ናዝሬት"** በሚለው ቃል ላይ ሥረወቃሉን (አወጣጡን/ በሚመለከት አከራካሪ ነገር እንዳለው የሚታወቅ ሲሆን ሊኖረው የሚችለው ትርጓሜ ምናልባት፤ (1) ናዝሬት የሚል (2) ናዝራዊ ማለት (ዘሕ) ወይም (3) ከናዝሬት የመጣ የሚል ነው። የአዲስ ኪዳኑ አጠቃቀም (ማቴ2:23) ቁጥር 3ን ይቀበላል /ያረጋግጣል። አንዳንዶች እንዲያውም የእብራይስጥ ተነባቢዎችን (በLr) "ቅርንጫፍ" ከሚለው የመሲሑ ማዕረግ ጋር ያገናኙታል (Nezer. ኢሳ 11፤14፤19፤60፤21):-

**ልዩ ርዕስ: የናዝሬቱ ኢየሱስ**

አዲስ ኪዳን ኢየሱስን ለመጥቀስ ሚጠቀማቸው በርካታ የተለያ የግሪክ ቃላት፤

*ሀ. የአዲስ ኪዳን ቃሎች*

1. ናዝሬት፡- በገሊላ ያለች ከተማ (ሉቃ1፤ 26፤2፤4፤39፤51፤4፤16፤ሐዋ፤10፤38) ይህ ከተማ ምንም እንኳን በዘመናችን ምንጮች ውስጥ ባይጠቀስም የኋለኞቹ ፅሑፎች ውስጥ ሊገኝ ችሏል።
2. ናዛሬዮስ፤- መልክ አምድራዊ ሥፍራን የሚያመለክት ይመስላል/ሉቃ 4፤ 34፤ 24፤19)፤
3. ናዝራዮስ፤- ከተማን ሊመለክት ይችላል፤ ነገር ግን "ቅርንጫፍ" በሚለው የእብራይስጥ መሲሐዊ አጠራር

ላይ በቃላት መራቀቅም ሊሆን ይችላል (*ጓetzer* ኢሳ 4፣ 2 11-1፤33-2፣ ኤር 23-5፤33-15፤ዘካ 3-8፤6-12፤ በአዲስ ኪዳን ራዕ 22-16)። ሉቃስ ይህንን ቃል ኢየሱስን ለመግለፅ ተጠቅሞታል፤ 18፡37፤ሐዋ 2፡22፤3፡6፤4፤10፤6፤14፡22፡8፣24፡5፤26፡9።

4. ከቁጥር 3 ጋር ሲዛመድ ናዝር የሚል ሲሆን ትርጉሙም "በመሃላ አማካኝነት የተለየ" ማለት ነው።

ለ. ከአዲስ ኪዳን ውጭ ያለው ታሪካዊ አጠቃቀም

1. ከክርስትና በፊት የነበረን የአይሁድ የኑፋቄ ወገንን የሚያመለክት ነበር (በአራማይክ ‹ናስራያ› ይባላል)
2. በአይሁ አካባቢ የክርስቶስን አማኞች ለመግለፅ የሚጠቀሙ ቃል ነበር(ሐዋ 24፡5፤14፤28-22፡"ኖስሪ" ይባላል)።
3. በሶሪያ (በአራማይክ) ቤተክርስቲያናት አማኞችን ለማመልከት የተለመደው ቃል ነበር። በግሪክ ቤተክርስትያናት ደግሞ አማኞችን ለማመልከት ይጠቀሙበት የነበረው ቃል "ክርስትያን" የሚል ነበር።
4. ከኢየሩሳሌም መፍረስ በኋላ ፈረንሳዊያን በጃምኒያ እንደገና በመደራጀት በምኩራብና በቤተክርስትያን መካከል ግልፅ የሆ ልዩነት እንዲኖር አቀነባብረው ነበር። እንዲህ አይነቱ በክርስትያኖች ላይ የተፈፀመው የእርግማን መሐላ ቀመር አማኞችን "ናዝራዊያን" ብለህ በሚጠራው *the Eighteen Benductions(from Berakoth* 28ለ-29ሀ) መጽሐፍ ውስጥ ነው።
   "ናዝራዊያንና መናፍቃን አሁኑኑ ይጥፉ፣ ከሕይወትም መፅሐፍ ይመሳሰሉ፤ ከሚያምኑትም ጋር አይፃፉም" ይላል።
5. በጀስቲን ማርተየር (*Dial* 126፡1) ተጠቅሷል፤ እርሱም ኢሳያስ ኢየሱስን ለመግለጽ የተጠቀመውን *ጓetzer* የሚለውን ቃል ጠቅሷል።

ሐ. የፀሐፊው አስተያየት

በቃሉ ብዙ ፊደላት ምክንያት ተርገሜያለሁ፤ ይሁን እንጂ ይህ በብሉይ ኪዳን ብዙ የሚታይ ነገር አይደለም ምክንያቱም "ኢያሱ" የሚለው ቃል ራሱ በእብራይስጥ ብዙ ፊደላት አሉትና። ትክክለኛውን ትርጉም በሚመለከት እርግጠኛ እንዳልሆ የሚያደርጉኝ የሚከተሉት ነገሮች ናቸው፤

1. "ቅርንጫፍ" (*ጓetzer*) ከሚለው የመሰሐዊ ቃል ጋር ያለው የቀረበ ግኑኝነትና ወይም"ናዘር" ከሚለው ቃል ጋር ያለው ቅርበት (በመሃላ ምክንያት የተለየ)
2. የገሊላ አሉታዊ አንደምታ (በአሉታዊነት መጠቀሱ)
3. ናዝሬት በገሊላ እንደነበረች የሚገልፅ ማረጋገጫ በዘመናች በጣም ትንሽ በመሆኑ

▣ "እኔ ነኝ" ይህ በእብራይስጥ "እኔ ነኝ" በማለት የመሆኑነ ግሥ ሲያመለክት (በ6፡20 ላይ ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።) ያህዌ ከሚለው የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ስም ጋር አይሁዊያን ያገኙታል (ዘፀ 3፡14 እና ኢሳ 41፡4)። ኢየሱስም መስኮ መሆኑም አስደናቂ በሆነ ሁኔታ ሲያፀናው ተመሳሳይ በሆነ ሰዋሰዋዊ አካሄድ ነበር *egocimi* ፤ 4፡26፤8፡24፡25፡58 እና 13፡19። በዚህ ዓውድ ውስጥ ትኩረት ለመስጠጥ ሦስት ጊዜ ተደጋግሟል (ቁ.6፤8) ይህ ሰዋሰዋዊ አወቃቀር ኢየሱስ "እኔ..." እያለ ከሚናገረው ታዋቂ ንግግር የተለያየ ነው።

▣ **"አሳልፎ የሰጠውም ይሁዳ ደግሞ ከእርሱ ጋር ቆሞ ነበር"** ይህ በወንጌሉ ፀሐፊ በዮሐንስ የተሰጠ ሌላ አስተያየት ነው።

**18፡6 "ወደ ኋላ አልግፋገም በምድር ወደቁ"** ዮሐንስ ይህ የዘገበው አስገራሚ የሆነውን የኢየሱስን ባህርይና መገኘት (ሕልውና) ትኩረት ለመስጠት ነበር። ይህ መስገድን ወይም ማምለክን የሚያመለክት ሳይሆን መፍራትን ነው።

**18፡7 "ደግሞም ጠየቃቸው"** ኢየሱስ ምናልባት ትኩረቱን ከደቀመዛሙርቱ ይልቅ ወደ ራሱ እያደረገ ነበር። ይህ በአቅራቢያው ካለው ዓውድ ከቁጥር 8 ጋር የሚስማማ ይመስላል።

**18፡8 "ት...."** ይህ የመጀመሪያ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተነገር ነው፤ እነርሱም እየፈለጉት ነበር።

▣ **"እነዚህ ይሑዱ ተውአቸው"** ይህ የግሪኩ ትዕዛዝ አዘል አድርጊ ግሥ ነው።
ይህ በዘካ 13፡7 የተነገረው ትንቢት ፍፃሜ ነው (ማቴ 26፡31፤ዮሐ 16፡32)።

**18፡9 "ያለው ቃል ይፈፀም ዘንድ ነው"** ይህ 16፡32ን የሚገልጥ ነው፤ ነገር ግን 17፡12 ተጠቅሷል።

**18፡10 "ስምኦን ጴጥሮስም ሰይፉ ስለነበረው መዘዘው፡ የሊቀካህናቱንም ባርያ መትቶ ቀኝ ጆሮውን ቆረጠ"** ጴጥሮስ ዓላማ ታደረገው ጆሮውን ሳይሆን አንገቱን ነበር ይህም የሚያሳየው በኢየሱስ ምትክ ለመሞት ፈቃደኛ እንደነበር ነው። የጴጥሮስ ድርጊት ሊከሰት የቻለው ኢየሱስ በሉቃስ 22-36-38 ላይ የተናገረውን ካለመረዳት የመጣ ይመስላል።

ሉቃስ 22:51 እንደሚነግረን ኢየሱስ የሰውየውን ጆሮ በመዳሰስ እንደፈወሰው ነው፡፡

▣ **"የባርያውም ስም ማልኮስ ነበር"** በዚህ የአዘጋጅ አስተያየት ላይ ዮሐንስ ብቻ ነው ስሙን የሚጠቅሰው፡፡ የወንጌሉ ፀሐፊ በአትክልት ሥፍራው በመሆኑ የአይን ምሥክርነቱን የሚያሳይ ነው!

**18:11 "ፅዋ"** ይህ በብሉይ ኪዳን የአንድን ሰው ፍፃሜ በአሉታዊ ገፅታው ለማመልከት የሚጠቀስ የአነጋገር ዘይቤ ነው (መዝ 11:6፤60:3፤75:8፣ ኢሳ 51:17:22 ኤር 25:15፤16፤27-28)፡፡

ኢየሱስ ለጠየቀው ጥያቄ ሰዋሰዋዊ መልክ"አዎን" የሚል ምላሽን የሚጠብቅ ነው፡፡ ጴጥሮስ ያደርግ የነበረው ነገር ከሁሉ የተሻለውን ማድረግ እንደሚያውቅ ሰው ነበር (ማቴ 16:22:ዮሐ 13:8)፡፡

"ፅዋ" የሚለው ቃል በዚህ ሥፍራ ያለውን አጠቃቀምና በወንጌላት ውስጥ ከተጠቀሰውና በጌቴሴማኒ የነበረውን የኢየሱስን መቃተት ከተገለፀበት "ፅዋ" ከሚለው ጋር ልዩነት አለው፡፡ ለዮሐንስ ኢየሱስ ሁሉን የሚቆጣጠር ነው! ዮሐንስ ኢየሱስን የሚያቀርበው ልበ-ሙሉ እንደሆነና በጭራሽ እንደማይሰራ ነው (ቁ.4፤13፤1፤11)!

> NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 18:12-14
> **[12] እንግዲህ የሻለቃውና ጭፍሮቹ የአይሁድም ሎሌዎች ኢየሱስን ይዘው አሰሩት÷ 13አስቀድመውም ወደ ሐና ወሰዱት፤ በዚያች ዓመት ሊቀ ካህናት ለነበረው ለቀያፋ አማቱ ነበርና፡፡ 14ቀያፋም፡- አንድ ሰው ስለ ሕዝብ ይሞት ዘንድ ይሻላል ብሎ ለአይሁድ የመከራቸው ነበረ፡፡**

18፤12

| | |
|---|---|
| NASB | **"የሻለቃውና ጭፍሮች"** |
| NKJV | **"ወታደሮችና ካፒቴናቸው"** |
| NRSV | **"ወታደሮችና አዛዣቸው"** |
| TEV | **"የሮም ወታደሮ ከአዛዣቸው ጋር"** |
| NJB | **"ጭፍራውን አለቃው"** |

የሮም ወታደራዊ ክፍሎች ስምቻቸው የሚወሰዱት ከሚከተሉት የወታደሮች ብዛት አንፃር ነው::

1. ጭፍራ፡- የሚያመለክተው እስከ 600 ሰዎችን ነው (ቁ.3)
2. አዛዥ፡- ከ1000 የሚጀመር ነው(ሐዋ 21:31፤22:24፤23-10:24:7)፡፡

እነዚህ መጠሪያዎች ኢየሱስን የያዙት የወታደር ክፍልን መብዛትና ማነስ የሚያመለክቱ አይደሉም በፍልስጥኤም ቁ.2 ማለት ትንሽ የወታደር ቡድንን የሚመራ ማለት ነው፡፡

▣ **"አሰሩት"** ይህ ኢየሱስን በተለይ እንደፈሩት የሚያመለክት ሳይሆን የተለመደ አሰራር ስለሆነ ነው (ቁ.24)፡፡

**18:13 "አስቀድመውም ወደ ሐና ወሰዱት"** ከሐናንያና ከቀያፋ በፊት ስለነበረው የፍርድ ሒደት ብዙ የሚያከራክር ነገር አለ፡፡ ወንጌላት ከሐናኒያ ጋር ስለነበረው ጉዳይ የሚጠቅሱት ምንም የለም፡፡ ቁ.24 በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የግርጌ ማስታወሻ ይመስላል፤ ነገር ግን በወንጌላት ውስጥ ያለውን የኢየሱስን የፍርድ ችሎት የሚመለከት ያውን ታሪክ ሙሉ ለማድረግ ዋነኛ ክፍል ነው (ማቴ 26:57፤ማር :53)፡፡

በብሉይ ኪዳን ሊቀካህናት የሕይወት ዘመን ሁሉ (የእድሜልክ) ከመሆም በላይ እያንዳንዱ ሰው ከአሮን ወገን መሆ አለበት፡፡ ይሁን እንጂ ሮማዊያን ይህንን አሠራር የሌዊ ቤተሰብ በገንዘብ እንዲገዛው በማድረግ ለፖለቲካዊ ዓላማቸው ለወጡ፡፡ ሊቀካህኑም በሴቶች ሸንጎ ያለውን የንግድ እንቅስቃሴ ይቆጣጠር ነበር፤ ለዚህም ነው ኢየሱስ በጅራፍ ቤተመቅደሱን ባፀዳበት ወቅት ይህ ቤተሰብ ሊቆጣ የቻለው፡፡

እንደ ፍላቨየስ ጆሴራስ ከሆነ ሐናንያ ከ6-14 ዓ.ም ድረስ የነበረ ሊቀካህን ነው፡፡ እርሱም የተሾመው የሶርያ ገዢ በነበረው በኲሪነስ ሲሆ በኋላም በቨለሪዬስ ግራተስ ተወግዷል፡፡ ከዚያም በኋላ ዘመዶቹ ተከትለውት አገለገሉ (5 ወንዶችንና የልጅ ልጅ) ቀያፋም የሚሉት የወንድሙ ልጅ (18:13) እርሱን ተከትሎት ያገለገለ ነበር፡፡ ሐናኒያ ከሥርዓቱ ጀርባ የነበረው ትክክለኛው ኃይል ነበር ዮሐንስም ኢየሱስ ለመጀመሪያ ጊዜ የተወደው ወደ እርሱ እንደነበር ይገልፃል (18:13፤19-22)፡፡

**18:14** ይህ በዮሐንስ የተጨመረው ሌላው አስተያየት

**18:14** ቁ.15 እና ቁ18 እንደተጨመሩት ይህ በዮሐንስ የተጨመረው ሌላው አስተያየት ነው፡፡

▣ **"ቀያፋ"** የዮሐንስ ዋናው ትኩረት የነበረው ቀያፍ ሳያስበው ስለ ኢየሱስ መሞት ትንቢ መነገሩን ለማሳየት ነበር(11:50)፡፡ እርሱም የሐናንያ አማች ሲሆን ከ18-36 ዓ.ም ድረስ በሊቀ ካህንነት ያገለገለ ነበር፡፡ በ11:49 ላይ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ፡፡

**NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 18÷15-18)**
***[15] ስምዖን ጴጥሮስም ሌላውም ደቀ መዝሙር ኢየሱስን ተከተሉ። ያም ደቀ መዝሙር በሊቀ ካህናቱ ዘንድ የታወቀ ነበረ÷ ወደ ሊቀ ካህናቱም ግቢ ከኢየሱስ ጋር ገባ፤ [16]ጴጥሮስ ግን በውጭ በበሩ ቆሞ ነበር። እንግዲህ በሊቀ ካህናቱ ዘንድ የታወቀው ሌላው ደቀ መዝሙር ወጣ፤ ለበረኛይቱም ነግሮ ጴጥሮስን አስገባው። [17]በረኛ የነበረችይቱም ገረድ ጴጥሮስን፡- አንተ ደግሞ ከዚህ ሰው ደቀ መዛሙርት አንዱ አይደለህምን? አለችው። እርሱ፡- አይደለሁም አለ። [18]ብርድ ነበርና ባሮችና ሎሌዎች የፍም እሳት አንድደው ቆሙ፤ ይሞቁም ነበር፣ ጴጥሮስም ደግሞ ከእነርሱ ጋር ቆሞ ይሞቅ ነበር።***

18:15 ***"ስምኦ ጴጥሮም ሌላውም ደቀመዛሙር ኢየሱስን ተከተሉ"*** ስለዚህ ሌላ ደቀመዝሙር ማንነት ብዙ የሚያከራክር ነገር አለ።

1. የተለመደው ፅንሰ ሐሳብ/አስተሳሰብ የሚለው በ20፡2፤4እና በ8 ከተሰጡት መግለጫዎች አንፃር ሐዋርያው ዮሐንስ ነው የሚል ነው። እንዲ ሌላው ከ19፡25 ጋር የሚገኝ ሲሆ የማርያም እህት ልትሆ የምትችለውን ማርያምን የጠቀሰው ሲሆን፡ ይህም ማለት ከሌዊ ወገን ወይም ከካህን ቤተሰብ የመጣ ሳይሆ አይቀርም የሚል ነው።(የፖሊካርፕ ምስክርነት)።
2. ይህ ምናልባት እንደኒቅድምስና የአርማትያሱ ዮሴፍ ከሊቀ ካህነትና ቤተሰቡ ጋር ግንኙነት እንዳላቸው የማይታወቅ ሰው ሊሆን ይችላል (ቁ 15-16)።

▣ ***"ያም ደቀመዝሙር በሊቀካህናቱ ዘንድ የታወቀ ነበር"*** ይህ "ትውውቅ" ለሚለው ቃል ጠንካራ አገላለፅ ሲሆን "የቅርብ ጓደኛ/ ወዳጅ" የሚል ትርጉም ያለው ይመስላል። (ሉቃ 2:44እና 23:49)። ይህ ዮሐንስ ከሆነ ዓሣን እጠመደ ወደ እየሩሳሌም ያመጣ ዘንድ መላውን ቤተሰብ ሊያካትት የዓሣ ማጥመድ ሥራውን ጭምር የሚያመለክት ነው።

18:17 ***"በረኛ የነበረችይቱም ገረድ ጴጥሮስ፡- አንተ ደግሞ ከዚ ሰው ደቀመዛሙት አንዱ አደይለህምን? አለችው"*** ይህ ሰዋሰዋዊ አደረጃጀት ልክ እንደ ቁ-25 "አዎን" የሚል ምላሽን የሚጠብቅ ነው። ይህም የኢየሱስን ስም ላለመጠቀም ያሳዩትን ንቀት የሚያመለክት ነው። እርሷም የጠየቀችበት ምክንያት ምናልባት፤ (1)በጴጥሮስ ከዮሐንስ ጋር ግኑኝነት ስለነበረው ወይም (2) ከጴጥሮ የገሊላ አነጋገር ዘይቤ ሊሆን ይችላል።

▣ ***"አይደለሁም"*** ጴጥሮስ ስለኢሱስ ለመሞት እንኳ ተዘጋጅቶ ሊሆን ይችላል፤ ይሁን እንጂ ለአንዲት ገረድ እውነተኛ ምላሽ ለመስጠት ዝግጁ አልነበረም በወንጌልነት ውስጥ እነዚህ ሦስቱ ክህደቶች አንድ ላይ ነው የተቀመጡት፣ ነገር ግን በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ሐናዳ ኢሱስን ሲጠይቀው በነበረው ክስተት ተሰይተዋል (ቁ-24)።

"እኔ" የሚለው የጴጥሮስ ንግግር በትክክል ኢየሱስ "እኔ" እያለ የሚናገረው ንግግር ተቃራኒው ነው(ቁ.5)።

18:18 ይህ ታሪክ የተነገረው ግልፅ በሆኑ የአይን ምሥክሮች ዝርዝር ነበር። ሁለቱም ቁጥሮች፤ ማለትም 18 እና 25 ዙሪያ ጥምጥም የንግግር ዘይቤ አላቸው።

**NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 18÷19-24)**
***[19]ሊቀ ካህናቱም ኢየሱስን ስለ ደቀ መዛሙርቱና ስለ ትምህርቱ ጠየቀው። [20]ኢየሱስም መልሶ፡- እኔ በግልጥ ለዓለም ተናገርሁ፤ አይሁድ ሁሉ በሚሰበሰቡበት በምኩራብና በመቅደስ እኔ ሁል ጊዜ አስተማርሁ÷ በስውርም ምንም አልተነገርሁም። [21]ስለ ምን ትጠይቀኛለህ? ለእነርሱ የተናገርሁትን የሰሙትን ጠይቅ፤ እነሆ÷ እነዚህ እኔ የነገርሁትን ያውቃሉ አለው። [22]ይህንም ሲል በዚያ ቆሞ የነበረው ከሎሌዎች አንዱ፡- ከሊቀ ካህናቱ እንዲህ ትመስላለህን? ብሎ ኢየሱስን በጥፊ መታው። [23]ኢየሱስም መልሶ፡- ክፉ ተናግሬ እንደሆንሁ ስለ ክፉ መስክር፣ መልካም ተናግሬ እንደሆንሁ ግን ስለ ምን ትመታኛለህ? አለው። [24]ስለዚህ ሐና እንደታሰረ ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደ ቀያፋ ሰደደው።***

18:19 ***"ሊቀካህናቱም ኢየሱስን ስለደቀመዛሙቱና ስለ ትምህርቱ ጠየቀው"*** ይህ ቀያፍን ሳይሆ ሓናን የሚያመለክት ነው። ሐና ከዙፋኑ (ከሥልጣኑ) በስተኋላ የነበረው ሲሆን የነገሠውም ከ6-15 ዓ.ም ድረስ ነበር። እርሱም ወዲያውም በአማጩ እና በኋላም በአምስት ወንድ ልጆቹና የልጅ ልጅ የተተካ ነበር። በቤተመቅደሱ አካባቢ የነበረውን የግብይት መብት የሚቆጣጠረው ሐና መቅደሱነ ያጠራውን (ምናልባት ሁለት ጊዜ) ለመጠየቅ የተጨነቀ ይመስላል። ሐና ስለ ኢየሱስ ደቀመዛሙርትና ስለሚያስተምረው ትምህደርት ለመጠየቅ ትኩረት መስጠቱ ደስ የሚያሰኝ ነው።

18:20 ኢየሱስ በአደባባይ ማስተማሩ የተረጋገጠ ነው። ይሁን እንጂ ብዙዎቹ ትምህርቶቹ ከህዝቡ የተሸፈኑ መሆናቸው በአንፃሩ እውነት ነው (ማር 4:10-12)። እውነተኛው ጉዳይ ግን በሰሚዎቹ ዘንድ የነበረው መንፈሳዊ እውርነት ነው።

የኢየሱስ ቃላትና የማስተማሪያ መንገዶቹ በወንጌላትና በዮሐንስ ወንጌል መካከል በተለያዩ ሁኔታዎች ተዘግዋል፡፡ ሌሎች ወንጌላት "እኔ…" የሚል ንግግር የሏቸውም፡፡ ኢየሱስ የሚያስተምረው በምሳሌዎች ነው፤ ዮሐንስ ደግሞ ምንም ዓይነት ምሣሌዎችን አልዘገበም፡፡ ለእኔ እንደሚመስለኝ ግን ልዩነቱ ግልፅ ሊሆን የሚችለው ወንጌላት የዘገቡት የኢሱስን የአደባባይ ትምህርቶችን ሲሆን ዮሐንስ ግን በግል የተሰጡት ትምህርቶችን መዘገቡን ስንረዳ ነው፡፡

18:21 **"ስለምን ትጠይቀኛለህ?"** በቁ20 ላይ ኢየሱስ ስለ አደባባይ አገልግሎቱ ባህርይ አረጋግጦ ይናገራል፡፡ ኢሱስ ለሐና እያመለከተ የነበረው ጥያቄዎቹ በአይሁድ ሕግ መሠረት ሕጋዊ እንዳልነበሩ እነዲሁም የአደባባይ እውቀት መሆናቸውን ነበር፡፡

18:22 **"በዚህ ቆም የነበረው ከሌሎች አንዱ.. ኢየሱስን በጥፊ መታው"** ቃሉ በመጀመሪያ ትርጉሙ "በበትር መምታት" ማለት ነው፡፡ ለማሳየት የፈለገው "በመዳፉ በጥፊ መምታት" ነው፡፡ ይህ ኢሳ 50፡6ን በተዘዋዋሪ የሚጠቅስ ነው፡፡ ኢየሱስም ደጋግሞ የሚናገረው ጥፋት ሠርቶ እንደሆ መከለስ እንዳለበት፡ አለበዚያ ለምን እንደሚመታ ነው፡፡

18:23 **"እንደሆንሁ… እንደሆንሁ"** እነዚህ የሁኔታን መሟላት የሚጠብቁ አንደኛ ደረጃ ሁኔታዊ ዓረፍተነገሮች ከፀሐፊው እይታ አንፃር ወይም ለሥነፅሑፋዊ ዓላማው እውነት ተብለው የተገመቱ ናቸው፡፡ ከዚህ ላይ የመጀመሪያው ውሸት የሆነን ነገር የሚያጎለበት የመንገድ ነው፡፡ ኢየሱስም ሐናን የሚቋቋመውም መረጃ እንዲያቀርብ ነበር፡፡

18:24 የእነዚህ ችሎቶች ቅደም ተከተል በወንጌላት ውስጥ ተቀልብሶ ይታያል፡፡

---

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 18፡25-27

[25]**ስምዖን ጴጥሮስም ቆሞ እሳት ይሞቅ ነበር፡፡ እንግዲህ፡- አንተ ደግሞ ከደቀ መዛሙርቱ አይደለህምን? አሉት፡፡ እርሱም፡- አይደለሁም ብሎ ካደ፡፡ [26]ጴጥሮስ ጆሮውን የቆረጠው ዘመድ የሆነ ከሊቀ ካህናቱ ባሮች አንዱ፡- በአትክልቱ ከእርሱ ጋር እኔ አይቼህ አልነበርሁምን? አለው፡፡ [27]ጴጥሮስም እንደገና ካደ፡ ወዲያውም ይሮ ጮኸ፡፡**

---

18:26 **"ጴጥሮስ ጆሮውን የቆረጠው ዘመድ የሆነ ከሊቃካህኑ ዘመዶች አንዱ"** ጴጥሮስ የተጠየቀውን ጥያቄ የላሳቸው ሰው ማንነት ላይ በአራቱ ወንጌላት መካከል የተወሰነ ልዩነት አለ፡፡

1. በማርቆስ ወንጌል፡- የመጀመሪያውን ጥያቄ ያነሳቸው ናት (ማር 14፡69)
2. በማቴዎስ ወንጌል፡- ሌላ ሴት ገረድ ናት(ማር 26:71)
3. በሉቃስ ወንጌል 22:25 ወንድ ነው
4. በዮሐንስ ወንጌል የሊቀካህኑ ባሪያ/ገረድ ናት

ከታሪካዊ መነሻው መረዳት እንደሚቻለው አንድ ሰው ጥያቄውን እንደጠየቀና ሌሎችም እንደተቀሳቀሱት ነው(ቁ.18)፡፡

18:26 **"በአትክልቱ ከእርሱ ጋር እኔ አይቼህ አልነበርሁምን"** በቁ 17 እ በቁ.25 ላይ ከተነሡት ጥያቄዎች በተለየ ይህ ሰወሰዋዊ አይነት "አዎን" የሚል ምላሽን ይጠብቃል፡፡

18:27 **"ጴጥሮስም እንደገና ካደ"** ከማር 14፡71 እና ከማቴ 26:74 መረዳት እንደንችለው ጴጥሮስ የካደው በመራገምና በመማል ነበር፡፡

▣ **"ወዲያውም ዶሮ ጮኸ"** አራቱም ወንጌላት የጊዜውን ሁኔታ ከማለዳው 12፡00 እስከ 3፡00 ድረስ እንደሆነ ያሳያሉ፡፡ አይሁዶች በኢየሩሳሌም ከተማ ውስጥ እንዲገባ አይፈቅዱም፡፡ ስለዚህም መሆን ያለበት የሮማውያን ዶሮ ነው፡፡

ሉቃ 22፡61 ኢየሱስ ወደ ጴጥሮስ እንደተመለከተ ጨምሮበታል፡፡ ሃናኒያና ቀያፋ በተመሳሳይ ቤት እንደሚኖሩ አይነት ይመስላል፡፡ እናም ጠባቂው ኢየሱስን ከሃናኒያ ወደ ቀያፋ እርሱን እንዲያገኘው ወስዶታል፡፡ እናም በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ ነበር፡፡ ኢየሱስ ጴጥሮስን ሊያይ የቻለው፡፡ እነዚህ ሁሉ ነገሮች በቂ ታሪካዊ መረጃ ስለሌለን ለመግለፅ አስቸጋሪ ናቸው፡፡

**NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 18፡28-32**
**[28]ኢየሱስንም ከቀያፋ ወደ ገዡ ግቢ ወሰዱት፤ ማለዳም ነበር፤ እነርሱም የፋሲካን በግ ይበሉ ዘንድ እንጂ እንዳይረክሱ ወደ ገዡ ግቢ አልገቡም። [29]ስለዚህ ጴላጦስ ወደ ውጭ ወደ እነርሱ ወጥቶ፡- ይህን ሰው ስለ ምን ትከሱታላችሁ አላቸው። [30]እነርሱም መልሰው፡- ይህስ ክፉ አድራጊ ባይሆን ወደ አንተ አሳልፈን ባልሰጠነውም ነበር አሉት። [31]ጴላጦም፡- እናንተ ወስዳችሁ እንደ ሕጋችሁ ፍረዱበት አላቸው። አይሁድም፡- ለእኛስ ማንንም ልንገድል አልተፈቀደልንም አሉት፤ [32]ኢየሱስ በምን ዓይነት ሞት ሊሞት እንዳለው ሲያመለክት የተናገረው ቃል ይፈፀም ዘንድ ነው።**

18፡28
NASB NKJV
JB "ወደ ፕራይቶሪየም"
NRSV "ወደ ጲላጦስ መምሪያ"
TEV "ወደ አዛገር ግቢ"

ይህ የሚያመለክተው በኢየሩሳሌም ያለውን የሮማነ መንግስት ባለስልጣናት መኖሪያ ቤት አመልካች ነው። ይህም ምናልባት ከታላቁ ሄሮድስ ቤተመንግስት ቀጥሎ ያለውን ስፍራ ሊያመለክት ይችላል።

**ልዩ ርዕስ፤ የፕራይቶሪየም ጠባቂ**
ፕራይቶሪየም የሚለው ቃል ከመሠረቱ የሚያመለክተው የሮም ጄኔራልን ድንኳን ነበር(ፕራይቶር)፤ ነገር ግን ኮሮማዊያን ድል ማድረግ በኋላ መምሪያዎችን ወይም መኖሪያን ማለትም የፖለቲካ ወይም የወታደራዊ አስተዳደር መኖሪያን ወይም መኖሪያን ለማመልከት ይጠቀስ ነበር(ማቴ 27÷27፤ዮሐ18÷28፤33፤19÷19፤ሐዋ 23÷35)።

ይሁን እንጂ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የሮማዊያን ዓለም ይጠቃል የነበረው የቤተመንግሥቱን ጥበቃ (የክብር ዘብ) የሚያዋቅሩ መኮንኖችን ለማሣየት ነበር። ይህ የተማረው ወታደር ክፍል የተጀመረው በአውግስጦስ ሲሆን በመጨረሻ በጢባርዮስ በሮም የከተመ ነበር። እነርሱም።

1. ተመሣሣይ ማዕረግ ነበራቸው፣ መቶ አለቃዎች
2. እንጂ ክራየን ይቀበሉ ነበር
3. ልዩ መብቶች ነበራቸው
4. ኃያላን በመሆናቸው ምክንያት ለንጉሡ ያላቸው ምርጫ ሁሌም ይከበራል።

ይህ የተማረ፤ በፖለቲካው ኃይል የሆነ ወገን እስከ ኮንስታንቲን ድረስ አልፈረሰም ነበር።

▣ "ማለዳም ነበር" ከሮማዊያን ወረዳ ማወቅ እንደሚቻለው የሮም ባለሥልጣናት ለችሎት ማለዳ (ጎህ ሲቀድ) ይገናኙ ነበር። በግልፅ ለመረዳ እንደሚቻለውም የካህናት አለቆች ልክ ማለዳ ላይ ሕጋዊ ልሆኑትን የምሽት ችሎቶች ሚስጥሩ ሕጋዊነት ይሰጡት ዘንድ ተገናኝተው ነበር። እነርሱመ ኢየሱስን ወዲያውኑ ወደ ጴላጦስ ወሰዱት።

▣ "እነርሱም የፋሲካን በግ ይበሉ ዘንድ እንጂ እንዳይረክሱ ወደ ገዡ ግቢ አልገቡም" ወደ አርማዊ መኖሪ ቢገቡ የፋሲካን በግ ለመብላት ይረክሱ ነበር። አንድን ሰው ከሕጉ ውጭ ለሞት አሳልፈው ሲሰጡ ሳይፅፋቸው የሥርዓት ጉዳዮች የሚዘገን ናቸው መሆኑ ራሱ ምፀታዊ ነው።

ኢየሱስ ከደቀመዛሙርቱ ጋር የፋሲካን በግ በልዩ ነበር የሚለው በወንጌላት መካከል ግልፅ ሆኖ በሚታየው ታሪካዊ ልዩነት አከራካሪ መሆኑን ይህ ጥቅስ የክርክሩ መነሻ ነው (ማቴ 26-17፤ማር 14፡12፤ሉቃ 22:1) እንዲሁም የዮሐንስ ወንጌል ድርጊቱ የተፈፀመው የተለመደው የፋሲካ በዓል የመዘጋጀ ቀን በሆነው ከቀኑ በፊት (ሐሙስ ዕለት) እንተፈፀመ ያሣያል። የዮሐንስ ፅሑፎችን በሚመለከት የታወቀው የሮም ካቶሊክ ሊቀ ሬይምድ ብራውን በጄሮም በቢሊካል ኮሜንታሪ ላይ እንዲህ ሲል አስተያየቱን ሰጥቷል፤

> "በምዕራብ ባህል መሠረት የድርጊቶች ቅደም ተከተል "ከታሪክ" አንፃር በዮሐንስ ወንጌል ሁል ጊዜ የተሻሉ ናቸው ካልን፤ የሚከተለው ምንባብ፡- የምኩራብን ልማድ የሚያውቀው የአይን ምሥክር መፍትሔ የሌላው ችግሮችን ማምጣቱ የማይቀር ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የዮሐንስ ወንጌል ተመሠረተበት የአይን ምሥክርነት ብዙውን ጊዜ በዝርዝር ከተቀመጠው የምኩራብ ንድፍ ይልቅ እውነትን ላዘሉት ክንውኖች ይቀርባሉ ካለን ምንባቡ የበለጠ ለመረዳት የሚያስችል ይሆናል ማለት ነው (ገጽ 458)።"

እንዲሁም ደግሞ የፋሲካን በዓል ለማክበር ሁለት የተለያዩ አማራጭ ቀናት አሉ፡ ሐሙስና ቅዳሜ ዕለት። ከዚህም በላይ "ፋሲካ" የሚለው ቃል የአንድ ቀን በዓል እና የስምንት -ቀናት ፌስቲባል ነው የሚል ሌላው የሚታይ ችግር ነው(የፋሲካ በዓል ከቂጣ በዓል ጋር ተጣምሮ፤ ዘፀ 12)።

▣ **"የፋሲካን በግ ይበሉ ዘንድ"** በጌታ ራት ቀን ላይ አሁንም ችግሮች አሉ። ወንጌላት የፋሲካው ምግብ ነው በማለት በተዘዋዋሪ ይናገራሉ፤ ነገር ግን ዮሐንስ የሚናገረው ከተለመደው ያሲካ ምግብ አንድ ቀን ቀደም ብሎ እነደ ነበር ነው (ዮሐ 19:14 እና ይህ ጥቅስ)። የዚህ መልስ የሚገኘው ምናልባት

1. "ፋሲካ" የሚለው ቃል ሣምንቱን፣ ምግቡና ወይም ልዩ ሰንበትን ሊያመለክት ይችላል በሚለው እውነታ ላይ
2. አንዳንድ የተገነጠሉ የአይድ ወገኖች (EsseNes) ከኢዮቤልዩ የዝምታ ጊዜ መፃህፍት የጨረቃን የቀን አቆጣጠር ይከተሉ ነበር የሚለው እውነታ
3. የዮሐንስ "ጣምራ ትርጉሞች" ከፋሲካ በዓል በፊት የታረደውን ኢየሱስን እንደ እግዚአብሔር በግ የማቅረብ እውነታ (1:29) ነው።

**18:29** እግዚአብሔር በዘፀአት መጽሐፍ ላይ የፈርኦን ስብዕና እንደተጠቀመ እንዲሁ ደግሞ ጲላጦስን ስብዕና ተጠቅሟል። ጲላጦስ የይሁ ገዢ እንዲሆን በ26 ዓ.ም በንጉሱ ጢባርዮስ ተሹም ነበር፤ እርሱም ቫለሪየስ ግራንስን ተክቶት ነበር (እርሱም ሐናን ከሊቀ ካህንነት ያስወገደ ነበር)። ጴላጤናዊው ጲላጦስም አምስተኛው ሮማዊ የይሁዳ አገረ ገዢ ነበር። እርሱም ለማርያን እና ይሁዳን፤ጋዛንና ሙት ባህርን የሚያካትተውን የአርኬላዎልን ግዛት (የታላቁ የሔሮዶስ ወንድ ልጅ) ስተዳድር ነበር። አብዛኞቹ ጲላጦስን ሚመለከቱ መረጃዎች የሚመጡት ከፍላቪስ ይሰራስ ፅሑፎች ነው።

**ልዩ ርዕስ: ጴላጤናዊው ጲላጦስ**

I. ግለሰቡ
   ሀ. የትውልድ ሥፍራውና ጊዜው አይታወቅም
   ለ. የንዑስ ከበርቴው መደብ አባል ነበር
   ሐ. ያገባ ነበር፤ ነገር ግን የሚታወቁ ልጆች የሉትም
   መ. ቀደምት የአስተዳደር ሹመቶች (በርካታ ነበሩ ማለት ነው) አይታወቅም
II. ስብዕናው
   ሀ. ሁለት የተለያዩ አመለካከቶች
      1. ፊሎ (*Legatio* and *Gaum* 299-303) እና ጆሴፊስ (*Antiq.*18:31 and Jewish Wars 2.9.2-4) እንደ ጨካኝና ምህረተየለሽ አድርገው ያሳዩታል።
      2. አዲስ ኪዳን(ወንጌላት፣ የሐዋርያት ሥራ) ደካማ፣ በቀላሉ የሚታለል የሮም ገዢ አድርጎ ያቀርበዋል።
   ለ. ፓውል ባርኔት፤*jesus* and Rise of Early *Christanity* ፤ ገጽ 143-148፤ በእነዚህ ሁለት አመለካከቶች ላይ በቂ የሆነ ትንታኔን ይሰጣል።
      1. ጲላጦስ በ26 ዓ.ም አይሁዳዊ በነበረው ጢባርዮስ አልተሸመም ነበር (*Phlo*፤ *legatio* and *Gaium*፤ገጽ 160-161) ይህም ፀረ-አይሁድ አቋም ባለው በጢባርዮስ ተቀናቃኝ በሆነው ሴጃናል በተባለው ዋና አማካሪ ማለት ነው።
      2. ጢባዮስ የቤተመንግሥቱ ዋና ሐላፊ በነበረው፤ በኋላም ሥልጣን በተቆናጠጠውና አይሁዶችንም እጅግ አድርጎ ይጠላ በነበረው ኤል ኤልዮስ በተባለው ሰው ስልጣኑን አጥንቶ ነበር (*Jasephus* ; *Antig* 18.3 if Jewish Wars 2.9.2-3)::)
      3. ጲላጦስ የሴጃኔስ ጥገኛ ስነበር የእርሱነ ቀልብ/ትኩረት ያገኝ ዘንድ
         ሀ. ሌሎች ገዢዎች ያላደረጉትን የሮምን የኑሮ ዘይቤን ወደ ኢየሩሳሌም ያወጣ ነበር(26ዓ.ም)። እነዚህም የሮም አማልዕክት ምልክቶች አይሁዶችን በጣም ያስቆጡ ነበር (*Jasephus Antig* 18.3.. Jewish Was 2.9.2-3)።
         ለ. የሮም አማልዕክት አምልኮ ተቀረፀበትን ገንዘብ ማሳተም። እንደጆሴፈል አባባል ከሆነ ያደርግ የነበረው ድርጊ ሆነ ብሎ የአይሁድን ሕግና ልማድ ለማፍረስ እንደነበር ነው (*Josephus Antiq18.*4.1-2)።
         ሐ. በኢየሩሳሌም የመጠጥ ውሐ መሔጃ ቦይ ለመገንባት እንዲቻል ከቤተመቅደሱ ግምጃ ቤት ገንዘቡ መውሰዱ (*Josephus*, *Antiq.*18.3.2 *wars* 2.9.3)።

         መ. በኢየሩሳሌም በፋሲካ በዓል ወቅት መሥዋት ያቀረቡ የነበሩትን በርካታ የገሊላ ሰዎችን በመግደል (ሉቃ 13÷12)።
         ሠ. የሮም ጋሻዎችን ወደ ኢየሩሳሌም በ31 ዓ.ም ማምጣቱ። የታላቁ የሔሮድስ ልጅ እንዲያስወግዳቸው ቢጠይቀውም አሻፈረኝ አለ፤ ስለዚህም በባህር ወደ ቂሣርያ ይሔዱ ዘንድ ይፈልግ ወደ ነበረው ወደ ጢባርዮስ ደብዳቤ ፃፉ።
         (*Philo, legation and Gaium,* 299-305)።
         ረ. የተቀደሱ የኃይማኖታቸው ዕቃዎችን ይፈልጉ የነበሩትን በርካታ ሳምራዊያንን በገሪዛን ተራራ

ላይ አሳርዷል (36/37 ዓ.ም)። የህም ሁኔታ የጲላጦስን የበላይ ባለስልጣን (ቫይተልየስ፣ የሶርያ ገዢ) ከስራው እንዲያሰወግደውና ወደሮም እንዲልከው ያደረገ ነው(*Josephus, Antiq.*18.4.1-2)።

4. ሲጀነስ በ31ዓ.ም ሲገደል ጢባርዮስ ወደ ሙሉ የፖለቲካ ሥልጣኑ እንደገና ተመለሰ፤ ስለዚህ ሀ፣ ለ፣ ሐ እና መ የሲጃነስን ተሰሚነት ለማግኘት ጲላጦ ምናልባት የፈፀማቸው ናቸው፤ ሠ እና ረ የዲጃንስን ታማኝነት ለማግኘት ሙከራ የተደረጉ ነገር ግን መልካም ምላሽ ያላገኙ ሊሆኑ ይችላሉ።
5. የአይሁድ ደጋፊ የሆነ ገዢ ወደ ሥልጣን ሲመጣና ለአይሁድ መልካም ይሆኑላቸው ዘንድ ሕጋዊ ደብዳቤ መፃፍ (*philo, legativ and Gaium* 160-161) በኢየሩሳሌም የነበረው የአይሁድ አመራር የጲላጠስን ተጠቂነት በመጠቀም ኢየሱስን ይሰቅለው ዘንድ አግባብተውታል። የባርኔትም ፅንሰ-ሐሳብ እነዚህን ሁለት አመልካቾች በበቂ ሁኔታ ምላሽ ይሰጥባቸዋል።

III. የጲላጦስ ፍፃሜ

ሀ. ከጢባርዮስ ሞት በኂላ እንደገና ወደ ሮም ተጠርቶ ሄደ (37 ዓ.ም)

ለ. እንደገና አልተሾመም

ሐ. ከዚህ በኂላ የነበረው የእርሱ ሕይወት አይታወቅም። ከዚህ በኂላ የመጡ ብሰዙ ፅንሰ ሐሳቦች ቢኖሩም የተረጋገጠ ማስረጃዎች አልነበሩም።

18:30 **"ይህስ ክፉ አድራጊ ባይሆን ወደ አንተ አሳልፈን ባልሰጠነውም ነበር አሉት"** ይህ ሁለተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተነገር ሲሆን ብዙውን ጊዜ "ከእውነታቸው ጋር መቃረን" ተብሎ ይጠራል። ኢየሱስ ክፉ አድራጊ አልነበሩም፤ ይህም ሽመጥን የተሞላ የጲላጦስ ማሳሰቢያ ሲሆን በአይሁድ ኃይማኖታዊ ክሶች መግባት አለመፈለጉን ያስረዳል።

"አሳልፎ መስጠጥ" የሚለው ግሥ ይሁዳን ለመግለፅ "ካደ" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው (6:68፤71፤12:24፤13:2፤11፤21፤18:2፤5)። ሉቃ በጥሬ ትርጉም "አንድን ሰው ለባለስልጣን አሳልፎ መስጠት" ወይም "ወግን ማስተላለፍ" ማለት ነው። ከይሁዳ ጋር በተያያዘ ቃሉ በእንግሊዘና ተርጓሚዎች ዘንድ ያለው ትርጉም ከፍያለና የተነከረ ነው።

18:31 **"ለእኛስ ማንንም ልንገድል አልተፈቀደልንም አሉት"** የአይሁድ አመራር ሕጉን ተላልፏል (ተሳድቧል) ብለው እግዘውታል፤ ነገር ግን ይህንን ክስ ተጠቅመው የሮም ባለሥልጣናት ኢየሱስን እነዲሰቅሉት አድርገዋ። በዛዳ 21:23(መስቀል በአንደኛው ክ/ዘመን ወቅት በነበሩ ረቢዎች ዘንድ በእግዚአብሔር እነደመርገም የሚቆጠር ነበር) ምክንያት የኢየሱስ መስቀል ለአይሁድ መሪዎች አስፈላጊውን ጉዳይ ነበር፤ ኢየሱስም ይህንን አስቀድሞ ተነግሮ ነበር፤ ቁ 32፤3:14፤8:28፤12፤32፤33፤ እና ገላ 3:13።

18:32 **"በምን ዓይነት ምት ሊሞት እንዳለው ሲያመለክት"** ለምንድነው የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስ እንዲሰቀል የፈለጉት ከሐዋርያት ሥራ ምዕ 7 መረዳት እንደሚቻለው ሕጉን ተሳድበዋል የሚሏቸውን በድንጋይ ወግረው ይገድሉ ነበር። ይህ ምናልባት በዛዳ 21:22-23 ላይ ከተጠቀሰው የብሉይ ኪዳን የመስኰት እርግማን ጋር ሊገናኝ የሚችል ነው። ከመጀመሪያው ይህ ያመለክት የነበረው ከሞት በኂላ ያለውን እንቅስቃሴ ማገድን የሚያመለክት ሲሆን ርቢዎች ግን ይህንን ጥቅስ የተረጐሙ ከሮማዊያን የሥቅላት ቅጣት አንፃር ነው። መሲህ ነኝ ባዩን ኢየሱስ፤ በእግዚአብሔር የተረገመውን ይፈልጉት ነበር፤ ይህ እንግዲህ ለወደቀው የሰው ዘር የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ነበር። ኢየሱስ የእግዚአብሔር በግ (1:29) ራሱን በምትክነት አሳልፎ ሰጥቶናል (ኢሳ 53፤2ቆሮ 5:21)፤ ኢየሱስም ስለ እኛ "እርግማን" ሆነ (ገላ 3፤13)።

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 18÷33-38ሀ

**[33]ጲላጦስም እንደገና ወደ ገዡ ግቢ ገባና ኢየሱስን ጠርቶ፡- የአይሁድ ንጉስ አንተ ነህን? አለው። [34]ኢየሱስም መልሶ፡- አንተ ይህን የምትለው ከራስህ ነውን ወይስ ሌሎች ስለ እኔ ነገሩህን? አለው። [35]ጲላጦስ ምልሶ፡- እኔ አይሁዳዊ ነኝን? ወገኖችህና የካህናት አለቆች ለእኔ አሳልፈው ሰጡህ፤ ምን አድርገሃል? አለው። [36]ኢየሱስም መልሶ፡- መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም፤ መንግስቴስ ከዚህ ዓለም ብትሆን÷ ወደ አይሁድ እንዳልሰጥ ሎሌዎች ይዋጉልኝ ነበር፤ አሁን ግን መንግሥቴ ከዚህ አይደለችም አለው። [37]ጲላጦስም፡- እንግዲያ ንጉሥ ነህን? አለው። ኢየሱስም መልሶ፡- እኔ ንጉሥ እንደገኩ አንተ ትላለህ። እኔ ለእውነት ልመሰክር ስለዚህ ተወልጃለሁ።**

**ስለዚህም ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤ ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምፄን ይሰማል አለው። [38ሀ]ጲላጦስ፡- እውነት ምንድ ነው? አለው።**

**18:33 *“ፕራይቱሪየም”*** በ18:22 ላይ ልዩ ርዕሱን ይመልከቱ፡፡

▣ ***“የአይሁድ ንጉሥ አንተ ነህን”*** ኢየሱስ የተከሰሰው በክህደት ነበር (ማቴ 27፡1ማር 15:2፤ሉቃ 23:2 እና ዮሐ 19:3፤12፤15፤19-22)፡፡

**18:34 *“ኢየሱስም መልሶ”*** አንተ ይህን የምትለው ከራስህ ነውን ወይስ ሌሎች ስለ እኔ ነገሩህን? አለው” ጲላጦስ ጥያቄውን ያነሣው ከፖለቲካ ሥልጣን አንፃር ቢሆን ኖሮ የኢየሱስ ይክድ ነበር፤ አይሁድም ሐሳብ ሰጥተውበት ቢሆን ኖሮ የኢየሱስን መሲህነት የሚመለክት፣ ኢየሱስም ያፀናው ነበር፡፡ ጲላጦም የተወላሰበውን የአይሁድን የሐማኖት አስተሳሰብ ለመሞከር/ለመከራከር ዝግጁም አልነበረም (ቁ.35)፡፡

**18:35** የመጀመሪያው ጥያቄ “አይደለም” የሚል ምላሽን የሚጠብቅ ነው፡፡

**18፡36 *“መንግስቴ ከዚህ ዓለም ብትሆን ወደ አይሁድ እንዳልሰጥ ሎሌዎች ይዋጉልኝ ነበር”*** ይህ የሁለተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተነገር ሲሆን “እውነትን መቃረን” ይባላል፡፡ ሊተረጎም የሚገባው “መንግሥቴ ከዚህ ዓለም ብትሆን ፤ በእርግጥም አይደለም፤ ጭፍሮች ይዋጉልኝ ነበር፤ ነገር ግን አይዋጉልኝም”፡፡ “ሎሌዎቹ” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው (1) ደቀመዛሙቱን ወይም (2) መላዕክትን ነው (ማቴ 26:53)፡፡

**18:37 *“ጲላጦስም እንግዲያ ንጉሥ ነህን? አለው”*** ይህ የኢየሱስን ማነትና መንፈሳዊ መንግስቱን የሚገዳደር በአንድ ምድራዊ ባለስልጣን አንደበት ላይ የሚነገር ከባድ ምፅታዊ ንግግር ነው፡፡ ይህም ጥያቄ “አዎን” የሚል ምላሽን የሚጠብቅ ነው፡፡

▣ ***“እኔ ንጉሥእንደሆንሁ አንተ ትላለህ፡፡ እኔ ለእውነት ልመስክር ስለዚ ተወልጃለሁ፤ ስለዚህ ወደ ዓለም መጥቻለሁ፡፡”*** የመጀመሪያው ሐረግ ግልፅ ካመሆኑ የተነሣ ለመትጎም አስቸጋሪ ነው፡፡ ይህ ከማዕረግ ጭምር የተነገረ ንግግር ነው (ማቴ27:11፤ማር15:2፤ሉቃ23:3)፡፡ኢየሱስ ማን እንደነበር እና (ሁለት የተሚሉ ጊዜ አመልካች ግሦች) ለምን እንደመጣም ያውቅ ነበር (ዮሐ13:1፤3 ማር 10:35፤ሉቃ 2:49፤ማቴ 16:22)፤ ጲላጦም ሊረዳው አይችለውም ነበር

▣ ***“ስለዚህ ተወልጃለሁ”*** ኢየሱስ አብን የመግለጥ ሥራውን እመለከተ ነበር (“ለእውነት ስመሰክር”)፡፡ ኢሱስ የመጣበት ሦስት መሠረታዊ ምክንያቶች ነበሩ፡፡

1. የእግዚአብሔርን ማንነትና ላማውን በሙሉና በፍፁም ለመግለጥ (1:18፣3:32)
2. የአለም ኃጢአት ለማስወገድ ነውር እንደሌለበት የእግዚአብሔር በግ መሥዋዕት ለመሆን(1:29)
3. ለእግዚአብሔር እንዴት እንደሚኖሩ እና እንዴት እንደሚያስደስቱት ምሳሌነት ያለውን ሕይወት ለማሣየት

▣ ***“ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምጼን ይሰማል፡ አለው”*** ሁሉም “ማንም ሰው”፤ ማም የሚሉ ቃላትን ስሰማ ውስጤ ይዘላል! ኦ! እግዚእሔር ዘፍ 3:15ን በክርስቶ አማካኝነት እያሟላው ነው! ኢየሱስ በውድቀት ምክንያት የተበላሸውን የእግዚአብሔርን መልክ ወደ ነበረበት ይመልሳል፤ የግልና የጠበቀ ሕብረት አሁንም የሚቻል ነው! ሕብረት አሁን ወደ ነበረበት ተመልሷል (የሚታይ ነገር ፍፃሜ)፡፡

መንፈሳዊ አይኖችና ጆሮዎች ያላቸው (10:3፤16፤27፤18:37) ናቸው እውነትን ሊረዱ የሚችሉት (ማቴ 11:15፤13:9፤16፤43፤ማር 4:9፤23፤ሉቃ 8:8፤10:23፤24፤14:35፤ ራዕ 2:7:11፤17፤29፤3:6፤13፤22)፡፡ አንፃር “የዘላለም ሕይወት”ን ከመቀበል ጋር እኩል ነው፡፡”

**18:38 *“ጲላጦስ፡- እውነት ምንድነው? አለው፡፡”*** ጲላጦስ ይህን ጥያቄ ጠየቀ፤ ነገር ግን መግለፅመረዳት እንደሚቻለው መልሱን ከመቀበሉ በፊት ተወው፡፡ ጲላጦስ እርግጠኛ መሆን የፈለገው ኢየሱስ ለሮም መንግሥት አስጊ አለመሆኑን ነበር ይህንንም ደግሞ አድርጎታል፡፡ በመሆኑም በአይሁድ ባህል መሠረት በፋሲካ ወቅት (ቁ. 39፤ማቴ 27:15) ኢሱስን ሊስተው ጥር አድርጎ ነበር፡፡ ሉቃስ እንደፃፈው ዮሐንስም በወንጌሉ ክርስትና ለሮም መንግሥት አስጊ እንዳልነበር አሳይቷል(18:38ለ:19:4:ሉቃ 23:4፤14፤22)፡፡

> NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 18÷38ለ-40
>
> **38ለ ይህንም ብሎ ዳግመኛ ወደ አይሁድ ወጥቶ፡- እኔስ አንዲት በደልስ እንኳ አላገኘሁበትም፡፡ 39 ነገር ግን በፋሲካ አንድ ልፈታላችሁ ልማድ አላችሁ፤ እንግዲህ የአይሁድን ንጉሥ ልፈታላችሁ ትወዳላችሁን? አላቸው፡፡ 40 ሁሉም ደግመው፡- በርባንን እንጂ ይህን አይደለም እያሉ ጮኹ፡፡ በርባን ግን ወንበዴ ነበረ፡፡**

**18:39 "ልምድ አላችሁ"** ይህ በማቴ 27:15 እ በሉቃ 23 :17 ላይ ተብራርቷል (ነገር ግን ከአዲስ ኪዳን ታሪካዊ መረጃ ውጪ የሚታወቅ አይደለም)።

**18:40 "ሁሉም ደግመው: በርባንን እንጂ ይህን አይደለም እያሉ ጮኹ።"** በግልፅ እንደሚታወቀው በርባን የቀናተኞቹ ፓርቲ (ቡድን) አባል የነበርና፣ ኢሱስ በተወገዘበት ክስ ጥፋተኛ ሆኖ መገኘቱ ምፀታዊ አገላለፅ ነው (ማር 15:7 ሉቃ 23:19፤25)። ይህ ሕዝብ ይጠባቅ የነበረው የእርሱነ ሐሳብ የሚያራምደውን ጀግና ለመደገፍና ለማሞጋገስ ነበር። የአይድ ባለሥልጣናት የኢየሱስን ውግዘት ለማፅናት/ለማረጋገጥ ይህንን አጋጣሚ ተጠቅመውበት ነበር (15:11)።

"በርናባስ" የሚለው ቃል ትርጉም "የአባት ልጅ" ማለት መሆ በራሱ ምፀታዊ ነው። ዮሐንስም እንዲህ አይነቱን በቃላት የመራቀቅ ሁኔታ በወንጌሉ ሁሉ ይጠቅሰዋል። ሕዝቡ "ከአብ ልጅ" ይልቅ "የአባት ልጅ" እንዲፈታ ፈልጓል። ጨለማው በእርግጥም ሙሉ በሙሉ መጥቷል ማለት ነው!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ሊሆን የሚችል ማብራሪያ በመሆኑ ለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ። እያንዳንዳችን ልንሔድ የሚገባን ባለን መረዳት መጠን ነው። አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጎም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣችሁ ናችሁ፤ በመሆኑም ይህንን በሚያብራራው ሰው ላይ ብቻ ልትተወው የሚገባ አይደለም።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ባሉት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ በጥሞና እንድታስቡበት ለመረዳት ይቻል ዘንድ ነው፤ በመሆኑም ጥያቄዎቹ እንደ ሐሳብ አነሳሽ ሆነው እንጂ በግልፅ ወይም በቀጥታ አይደለም

1. ኢየሱስ ይሁዳ እንደሚያገኘው እያወቀ ወደዚያ ስፍራ ለምን ሄደ?
2. ዮሐንስ የኢየሱስን በጌቴሴማኒ መቃተት ያልገለፀው ለምንድነው?
3. ሊቀ ካህኑ ኢየሱስን ወደ ጲላጦስ ለምን ወሰደው?
4. በዮሐንስ ወንጌል እና በሌሎች ወንጌላት መካከል ያሉት ድርጊቶች ቅደም ተከተል ለምን ግራ የሚጋቡ ሆኑ?
5. ለምንድነው ዮሐንስ ጲላጦስ ኢየሱስን ሊለቀው እንደፈለገ የሚያሣየው?

# ዮሐንስ 19

## በተሻሻሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም የአንቀፅ አከፋፈል

| UBS[4] | NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| ኢየሱስ እንዲሞት ተፈረደበት | ወታደሮች በኢየሱስ ላይ አላገጡበት | | ኢየሱስ እንዲሞት ተፈረደበት | ኢየሱስ በጲላጦስ ፊት |
| (18:38ለ-19:16ሀ) | | (18:38ለ-19:7) | (18:38ለ-19:16) | (18:28-19:11) |
| 18:38ለ-19:7 | | 18:38ለ-19:7 | | 18:33-19:3 |
| | | | 18:40-19:3 | |
| | 19:1-4 | | | |
| | የጲላጦ ውሳኔ | | 19:4-5 | 19:4-7 |
| | 19:5-16 | | | |
| | | | 19:6ሀ | |
| | | | 19:6ለ | |
| | | | 19:7 | |
| 19:8-12 | | 19:8-12 | 19:8-9ሀ | 19:8-11 |
| | | | 19:9ለ-10 | |
| | | | 19:11 | |
| | | | 19:12 | ኢየሱስ እንዲሞት ተፈረደበት |
| | | | 19:12-16ሀ | |
| 19:13-16ሀ | | 19:13-16ሀ | 19:13-14 | |
| | | | 19:15ሀ | |
| | | | 19:15ለ | |
| | | | 19:15ሐ | |
| | | | 19:16ሀ | |
| የኢየሱስ መስቀል | ንጉሱ በመስቀል ላይ | | ኢየሱስ ተሰቀለ | ስቅለት |
| 19:16ለ-22 | | 19:16ለ-25ሀ | 19:16ለ-21 | 19:6ለ-22 |
| | 19:17-24 | | | |
| | | | 19:22 | ኢየሱስ እጀጠባብ ተከፋፈሉት |
| 19:23-27 | | | 19:23-24 | 19:23-24 |
| | እነሆ እናትህ | | | ኢየሱስ እና እናቱ |
| | 19:25-27 | 19:25ለ-27 | 19:25-26 | 19:25-27 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | 19:27 | |
| የኢየሱስ መሞት | ተፈጸመ | | የኢየሱስ መሞት | የኢየሱስ መሞት |
| 19:28-30 | 19:28-30 | 19:28-30 | 19:28 | 19:28 |
| | | | 19:29-30ሀ | 19:29-30 |
| | | | 19:30ለ | |
| የኢየሱስ ጎን መወጋት | የኢየሱስ ጎን ተወጋ | | የኢየሱስ ጎን ተወጋ | የተወጋው ጎን |
| 19:31-37 | 19:31-37 | 19:31-37 | 19:31-37 | 19:31-37 |
| የኢየሱስ መቀበር | ኢየሱስ በዮሴፍ መቃብር ተቀበረ | | የኢየሱስ መቀበር | ቀብር |
| 19:38-42 | 19:38-42 | 19:38-42 | 19:38-42 | 19:38-42 |

## ሦስተኛ የንባብ ዑደት (አንቀፅ 5ን ይመልከቱ፡፡)
*የመጀመሪያውን ፀሐፊ ዋና ሐሳብ በአንቀፅ አከፋፈል ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ማብራሪያ እንደሆ መጠን ለምትከተለው የራስህ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ፡፡ እያንዳንዳችንም ልንሄድ የሚገባን ባለን መረዳት መሆን አለበት፡፡ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጎም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣቸሁ ናቸሁ፡፡ ይህንንም ጉዳይ በሚያብራራው ሰው ላይ ብቻ መተው የለብህም፡፡

ምዕራፍን በአንድ ቅፅበት አንብበው፣ ዋና ሐሳቦቹንም ለያቸው፡፡ ያንተን የዋና ሐሳብ አከፋፈሎች ከአምስቱ የተሻሻሉ ትርጉሞች ጋር አስተያያቸው፡ ምንም እንኳ በአንቀፅ መከፋፈል በእግዚአብሔር መንፈስ ሞት የሚደረግ ባይሆንም የአተረጓጎም ዋና ምስል የሆነውን የመጀመሪያውን ፀሐፊ ዋና ሐሳብ ለመከተል ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ እያንዳንዱም አንቀፅ የሚናገረው ስለ አንድ ሐሳብ ብቻ ነው፡፡

1. አንደኛ አንቀፅ
2. ሁለተኛ አንቀፅ
3. ሦስተኛ አንቀፅ
4. ወ. ዘ. ተ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 19÷1-7**
**1በዚያን ጊዜም ጲላጦስ ኢየሱስን ይዞ ገረፈው፡፡ 2ወታደሮችም በእሾህ አክሊል ጎንጉነው በራሱ ላይ አኖሩ ቀይ ልብስም**
**አለበሱት 3እየቀረቡም፡- የአይሁድ ንጉሥ ሆይ ሰላም ለአንተ ይሁን ይሉት ነበር፡፡ ጲላጦም ደግሞ ወደ ውጭ ወጥቶ**
**እነሆ አንዲት በደል ስንኳ እንዳላገኘሁት ታውቁ ዘንድ እርሱን ወደ ውጭ አወጣችኋለሁ አላቸው፡፡ 5ኢየሱስም የእሾህ**
**አክሊል ደፍቶ ቀይ ልብስም ለብሶ ወደ ውጭ ወጣ፡፡ 6ጲላጦስም፡- እነሆ ሰውዬው አላቸው፡፡ የካህናት አለቆችና ሎሌዎች**
**ባዩትም ጊዜ ስቀለው እያሉ ጮሁ፤ ጲላጦም እኔስ አንዲት በደል እንኳ አላገኘሁበትምና እናንተ ወሰናችሁ ስቀሉት**
**አላቸው፡፡ 7አይሁድም መልሰው እኛ ሕግ አለን፤ እንደ ሕጋችንም ሊሞት ይገባል፡፡ ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ**
**አድርጎአልና አሉት፡፡**

19:1 **"ጲላጦስ ኢየሱስን ይዞ ገረፈው"** የጊዜው ቅደም ተከተል እና የዓረፍቱ ቁጥር አስተማማኝ አይደለም፡፡ እንዲሰቀሉ የተፈረደባቸው ሁሉም እስረኞች ተገርፈው ነበር፡፡ ጭካኔን የተሞላ ድርጊት ከመሆኑ የተነሣ ብዙ ሰዎች ይሞቱ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ጲላጦ ከገረፈው በኋላ ሊፈታው ያሰበ ይመስላል (ሉቃ 23:16፡22፤ ዮሐ 19:12)፡፡ ይም ምናልባት የኢሳ 53:5 ቃል መፈፀም ሊሆን ይችላል፡፡

የሮማዊያን ግርፋት በጣም የሚያሰቃይ ህመም ያለው እና ሮማዊያን ላልሆኑት ዜጎች የተጠበቀ ጭካኔን የተሞላ ቅጣት ህመም ያለው እና ሮማዊያን ላልሆኑት ዜጎች የተጠበቀ ጭካኔን የተሞላ ቅጣት ነው፡፡ የሚቀጣ ሰው እጆች በካስማ ላይ ታስረው ጫፍ ላይ አጥንት ወይም ብረት በተሠራበት የቆዳ መግረፊያ ይገረፉ ነበር፡፡ ስለ የግርፋቱ መተን በቃል የተፃፈ ነገር የለም፡፡ አንድ ሰው ከመስቀሉ በፊት በተለምዶ ይደረግ ነበር *(livy xxxIII*:36)፡፡

በሮማዊያን የተደረገውን ግርፋት ለመግለፅ ወንጌላት የተለያዩ ቃላትን ይጠቀማሉ፤

1. ማቴ 27:26፤ ማር 15:15- *Phragelloo*(ፍራጄሎ)፤ መግራፍ ወይም መምታት
2. ሉቃ 23:16፡22 - *Paideuo*(ፔይዲዮ)፡ የመጀመሪያው ትርጉም ልጅን መቅጣት ነው(ዕብ 12:6-7:10)፣ ነገር ግን በዚህ ሥፍራ ላይ ልክ እንደ 2ቆሮ 6:9 ድብደባን ያመለክታል፡፡

ሁሉም ምናልባት ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል ወይም ምናልባት ሁለት ምቶችን ሊያመለክቱ ይችላሉ፤

ሀ. በጲላጦስ የተደረገ አነስተኛ ድብደባ

ለ. ከመስቀሉ በፊት የተደረገ መምታት

19:4

| | |
|---|---|
| NASB | **"አንዲት በደል እንኳ እንዳላገኘሁበት"** |
| NKJV | **"አንዲት ስህተት እንኳ እንዳላገኘሁበት"** |
| ኤን አር. ኤስ. ቪ. | **"አንዲት ምክንያት እንኳ እንዳላገኘሁበት"** |
| TEV | **"እርሱን ለማውገዝ አንድም ምክንያት ላገኝ አልችልም"** |
| NJKB | **"ምንም ነገር አላገኘሁበት"** |

ከዮሐንስ ዓላማዎች አንዱ ክርስትና ለሮም መንግሥት ወይም ባለስጣናቱ ስጋት እንዳልነበር ማሳየት ነበር፡፡ ጲላጦስ በርካታ ጊዜያት ኢየሱስን ለመስቀል መምከሩን ዮሐንስ በወንጌሉ ይዘግባል (18:38፤ 19፤ ሉቃ 23:4፡14፡22)፡፡

19:5

| | |
|---|---|
| NASB፤ NKJV | **"እነሆ ሰውዬው"** |
| TEV፣ NET | **"ተመልከቱ! ሰውዬው ይሔው!"** |
| NRSV፤ NJB<br>REB | **"ሰውዬው ይሔው!"** |

ይህንን ሐረግ ለመረዳት በርካታ መንገዶ አሉ፤

1. ኢየሱስ የለበሰው እንደሚያላግጠብን ንጉስ ነበር
2. ኢየሱስ የተመታው ማፅናኛን ለመለመን ነበር
3. ዘካርያስ 6:12ን በተዘዋዋሪ የሚጠቅስ ነበር ("ቅርንጭፍ" ለሚለው መሲሐዊ መግለጫ)
4. የኢየሱስን ስጋ መልበስ ለመቀበል (ለማረጋገጥ) በኋላ የተሰጠ አፅንኦት (በዮሐንስ ዘመን ለነበረው የግምስቲክ ኑፋቄ ምላሽ)

19:6 **"ስቀለው፣ ስቀለው እያሉ ጮኹ"** የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስ እንዲሰቀል የፈለጉበት ምክንያት በዛዓ 21:23 ላይ ያለው እርግማን ተፈፃሚነት ያገኝ ዘንድ ነበር፡፡ ይህም ጳውሎስ የናዝሬቱ ኢየሱስ የእግዚአብሔር መሲህ (መሲህ) መሆን ለመጠራጠር እንደ ትልቅ ምክንያት ሳይወለድ ምናልባት አይቀርም ይሁን እንጂ ከገላ 3:13 እንደምንረዳው ኢሱስ ኃጢአታችንን በመስቀል ላይ መሸከሙን ነው (ተሸክሟል (ቅላ 2:14)፡፡

▣ **"አንዲት በደል እንኳ እንዳላገኘሁበት"** ጲላጦ ይህንንም ሦስት ጊዜ ይደርግመዋል (18:38፤19:4)

19:7 **"ሊሞት ይገባዋል፤ ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ አድርጎአልና"** ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑንና ከእግዚአብሔርም ጋር አንድ መሆኑን ተነግሯል፡፡ ይህንንም የሰሙት አይሑድ መለኮት መሆኑን ስለመናገሩ ምንም ጥርጣሬ ልነበራቸውም (5:18፤8:53-59፤10:33)፡፡ እውነተኛው አይሁድ ኢየሱስን የከሰሱበት ምክንያት ሕጉን ተሳድቧል የሚል ነበር (ማቴ 20:6፡65)፡፡ ሕግን መሳደብ የሚያስከትለው ቅጣት በድንጋይ መወገር ነበር (ዘሌ24:16)፡፡ ኢየሱስም ስጋ የለበሰ ባይሆን ኖሮ፣ ከፍጥረትም በፊት የነበረ አምላክ ባይሆን ኖሮ በድንጋይ መወገር ነበረበት ማለት ነው!

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 19÷8-12)
[8]ስለዚህ ጲላጦስ ይህን ነገር በሰማ ጊዜ እጅግ ፈራ? [9]ተመልሶም ወደ ገዢ ግቢ ገባና ኢሱስን አንተ ከወዴት ነህ? አለው፡፡ ኢየሱስ ግን አንድ አንኳ አልመለሰለትም፡፡ [10]ስለዚህ ጲላጦስ፡- አትነግረኝምን? ልሰቅልህ ሥልጣን እንዳለኝ ወይም ልፈታህ ሥልጣን እንዳለኝ አታውቅምን አለው፡፡ [11]ኢየሱስም መልሶ፡- ከላ ካልተሰጠህ በቀር በእኔ ላይ ምንም ሥልጣን ባልነበረህም፤ ስለዚህ ለአንተ አሳልፎ የሰጠኝ ኃጢአት የባሰ ነው አለው፡፡
[12]ከዚህ በኃላ ጲላጦስ ሊፈታው ፈለገ ነገር ግን አይሁድ፡- ይህንን ብትፈታው የቄሣር ወዳጅ አይደለህም፣ ራሱን ንጉስ የሚያደርግ ሁሉ የቄሣር ተቃዋሚ ነው እያሉ ጮኹ፡፡

9:8 **"ጲላጦስ ይህን ነገር በሰማ ጊዜ እጅግ ፈራ"** የጲላጦስ ሚስት አስቀድማ ጲላጦስን ስለኢየሱስ አስጠንቅቀው ነበር (ማቴ27:19)፤ አሁን ደግሞ የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስ ራሱን የእግዚአብሔር ደጅ እንደሆነ አረጋግጧል ብለው እየከሰሱት ነው፡፡ ጲላጦስ በከንቱ ነገሮች የሚያምን ስለነበር ፈርቷል፡፡ በጊዜው የግሪክ አማልዕክት እና የሮም ጣኦታት የሰውን ልጆችን በሰው መልክ እየተገለጡ ይጎበኛ ማለት በጣም የተለመደ ነገር ነበር፡፡

19:9
NASB፤ NKJB **"አንተ ከወዴት ነህ?"**
NRSV
TEV፤NJB
TEV **"ከየት ነው የመጣኸው"**

ጲላጦስ እየጠየቀ የነበረው የተወለደበትን ከተማ ሳይሆን የኢየሱስን መሠረት ነበር፡፡ ጲላጦስም በፊቱ የቆመውን ሰው ታላቅነትና የተረዳ ይመስላል፡፡ ኢየሱስ በ19:38 ላይ በሰጠው ማብራሪያ ጲላጦስ ስለ እውነት ከማወቅ የፖለቲካ ዓላማውን ለማሳካት ፍላጎት ቢኖረውም እርሱ ግን ምላሽ አልሰጠውም፡፡

ጲላጦስ ኢየሱስን የሚያደንቁ ነገር ግን ከየት እንደመጣ ያልተረዱ ሰዎችን ተገናኝ (4:12፤6:42፤9:27-28፡41፤8:14፤9:29-30)፡፡ ይህም የዮሐንስ የላይ ታች ዱዋሊዝም አንዱ ክፍል ነው፡፡ ኢየሱስ ከላይ እንደመሆኑ መጠን ከዚ ዓለም የሆነ ማንም ሰው ያለ እግዚአብሔር እርዳታ ሊያውቀው/ሊረዳው/ ሊያየው/ሊሰማው አይችልም(6:44፡65፤10:29)፡፡

▣ **"ኢየሱስ ግን አንድ እንኳ አልመለሰለትም"** ጲላጦ ኢየሱስ የሰጠውን ምላሽ ተረድቶታል ማለት ነው (8:37) አንዳንዶችም ይህንን ሁኔታ ኢሳ53:7 እንደተፈፀመ ያዩታል፡፡

19:10 **"ስለቅልህ ሥልጣን እንዳለኝ አታውቅምን?"** ጲላጦስ በህይወት እና በሞት ላ የፖለቲካ ሥልጣን እንዳለው ይነገራል ነገር ግን ይህ ይህንን መብቱን ከሥርዓት ውጪ ለሆነ አዋኪ ሕዝብ ፈቃድ አሳልፎ ሰጥቷል፡፡ ከሰዋሰው አንፃር ጲላጦስ የጠየቀው ጥያቄ "አዎን" የሚል ምላሽ የሚጠብቅ ነው፡፡

19:11"**ከላይ ካተሰጠህ በቀር በእኔ ላይ ምንም ሥልጣን ባልነበረህም"** ይህ የሁለተኛ መደብ ሁኔታዊ አረፍተነገር ሲሆን "እውነታውን የሚቃረን" እውነት ይባላል፡፡ ኢየሱስ በጲላጦስ ንግግር አልደነገጠም፤ ነገር ግን ማን እንደነበር እና ለምን ዓላማ እንደመጣ ያውቅ ነበር! እግዚአብሔር ከሁሉም የሰው ልጅ ሥልጣን ጀርባ እንዳለ መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጣል (ሮሜ 13:1-7)፡፡

▣ **"ለአንተ አሳልፎ የሰጠኝ ኃጢአቱ የባሰ ነው"** ለመጀመሪያ ጊዜ ሲነበብ የህ የአለቆሮቱ ይሁዳን የሚያመለክት ይመስላል (6:64፡71፤13:11) ነገር ግን አብዛኞቹ የመጽፍ ቅዱስ አብራሪዎች እንደሚያምኑ ኢየሱስን በግልፅ ለሮማዊያን አሳልፎ የሰጠውን ቀያፋን ያመለክታል ይላሉ፡፡ ይህ ሐረግ በጥቅሉ ሲታይ ለመረዳት የምንችለው (1) ሕገ ወጥ የሆኑ የአይሁድ መሪዎችን እንደሚያመለክት ነው (2) የአይሁድ ሕዝብን በጠቅላላው እንደሚያመለክት ነው (ማቴ21:33-46፤ማር 12: 1-12፤ሉቃ 209-19፤ሮሜ 9-11)፡፡

19:12 **"ጲላጦስ ሊፈታው ፈለገ"** ይህ ያልተሟላ ጊዜያትን ገላጭ ሲሆን ይም ማለት በላፊ ጊዜ ሲደጋገም የነበረ ድርጊት ነው፡፡ ጲላጦ ብዙ ጊዜያት ሞክሮ ነበር፡፡

▣ **"ይህንስ ብትፈታው፤ የቄሣር ወዳጅ አይደለመህም"** ይህ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተነገር ሲሆን የሚያመለክተውም ለድርጊት እድል መኖሩን ነው፡፡ የአይሁድ መሪዎች የእነርሱን ነው፡፡ የአይሁድ ኢሱስን ለሞት አሣልፎ የማይሰጥ ከሆነ በሮም ለሚገኙት የበላዮቹ እንደሚያሣውቁ ጲላጦስን እያስፈራሩት ነው፡፡ "የቄሣር ወዳጅ" የሚለው አነጋገር ክብር ያለው ማዕረግ ሲሆን የተሰጠውም በሮም ንጉሥ ነገሥት ነው (አውጉስቶስ ወይም ቤስፓሻጥ በሚል የሚጀምር)፡፡

ቄሣር ለሮም ንጉሥ ነገሥቶ የተሰጠ ማዕረግ ነበር፡፡ ቃሉ ከዮልዮስ ቄሣር የመጣ በኋላም በአውግስጦስ በሥራ ላይ የዋለ ነበር፡፡

**NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 19:13-16**
**[13] ጲላጦስም ይህን ነገር ሰምቶ ኢየሱስን ወደ ውጭ አወጣው፤ በዕብራይስጥም ገበታ በተባለው ጸፍጸፍ በሚሉት ስፍራ በፍርድ ወንበር ተቀመጠ፡፡ [14] ለፋሲካም የማዘጋጀት ቀን ነበር ስድስት ሰዓትም የሚያህል ነበር፤ አይድንም እነሆ ንጉሣችሁ አላቸው፤ [15]እነርሱ ግን፡- አስወግደው÷ ስቀለው እያሉ ጮኹ፡፡ ጲላጦስም፡- ንጉሣችን ልስቀለውን አላቸው፡፡ የካህናት አለቆችም፡- ከቄሣር በቀር ሌላ ንጉሥ የለንም ብለው መለሱለት፡፡ [16] ስለዚህ በዚያን ጊዜ እንዲሰቀል አሳልፎ ሰጣቸው፡፡**

19:13 **"ጲላጦስም ይህን ነገር ሰምቶ ኢየሱስን ወደ ውጭ አወጣው... በፍርድ ወንበር ተቀመጠ"** ጥቅሱ በፍርድ ወንበደሩ ላይ ማን እንደሚቀመጥበት አሻሚ ነው፡፡ ሁለቱም የዊልያምስ እና የጉድስፒድ ትርጉሞች እንደሚያረጋግጡት በወንበሩ ላ የተቀመጠው ኢሱስ ነበር፤ ይህም እርሱ የአይሁድ ንጉሥ መሆኑን ለማፌዝ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ አውዱ እንደሚጠቅሰው ጲላጦ ነው ፍርድን ለመስጠት በወንበሩ ላይ የተቀመጠው፡፡

| | |
|---|---|
| NASB፤ NKJB | |
| NJB | **"በዕብራይስጥም ገበታ በተባለው ደፍደፍ በሚሉት"** |
| NRSB | **"የድንጋይ ንጣፍ በተባለው፤ ወይም በእብራይስጥ ገበታ"** |
| TEV | **"የድንጋይ ንጣፍ በሚሉት ሥፍራ (በዕብራይስጥ ሰው "ገበታ" ይባላል)** |

የእብራይስጥ ወይም የአራማይክ ቃላት ከነፍቺዎቻቸው መጠቀሣቸው የሚያሣየው የዮሐንስ ወንጌል መልዕክት ተቀባዮች አህዛብ መሆናቸውን ነው (ቁ.17)፡፡ የድንጋይ ንጣፍ የሮም መንግሥት ሕጋዊ አዋጅ የሚነገርበት ቦታ ነበር፡፡ "ገበታ" የሚለው ቃል የአራማይክ ትርጉም "የቆሙ ድንጋዮች" ወይም "ከፍ የተደረገ ቦታ" እንደ ማለት ነው፡፡

19:14 **"ለፋሲካም የማዘጋጀት ቀን ነበር"** በዮሐንስ እና በሌሎች ወንጌላት መካከል ጊዜን በሚመለከት በግልፅ የሚታይ ልዩነት አለ፡፡ በሌሎች ወንጌላት ውስጥ ኢየሱስ ከመያዙ በፊት ከደቀመዛሙርት ጋር አብሮ የፋሲካን በዓል ምግብ እንደተከፈለ ይገልፃል (ማር 1542)፤ ነገር ግን በዮሐንስ ውስጥ ምግቡ የቀረበው ከበዓሉ በፊት በማዘጋጀት ቀን ላይ ነበር፡፡ ሙሉ ማብራሪያን በ18:28 ላይ ይመልከቱ፡፡

▣ **"ስድስት ሰዓትም የሚያህል ነበር"** በጲላጦ ፊት ለፍርድ የቀረበበት እና የተሰቀለበት የጊዜ ቅደም ተከተል፤

| | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ |
|---|---|---|---|---|
| የጲላጦስ ፍርድ | | | | 6ኛ ሰዓት 19:14 |
| ስቅለት | | 3ኛ ሰዓት 15:25 | | |
| ጨለማም ወደቀ | 6ኛ-9ኛ ሰዓት 27:45 | 6ኛ-9ኛ ሰዓት 15:33 | 6ኛ-9ኛ ሰዓት 23:44 | |
| ኢየሱስም ጮኸ | 9ኛ ሰዓት 27:46 | 9ኛ ሰዓት 15:34 | | |

እነዚህ የጊዜ ስያሜዎች ሲነፃፀሩ ሁለት የትርጉም አማራጮች አብረው ይነሣሉ፡፡

1. ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ዮሐንስ ከቀኑ 6፡00 ብሎ በመቁጠር የሮማዊያንን ጊዜ ተጠቅሟል (ግሊሶን. ኤል. አርችር፤ *Encyclopedia of Bible Difficulties* (ገጽ 364) እንዲሁም ደግሞ ሌሎች ወንጌላት ከጠዋቱ 12፡00 ሰዓት ብለው የአይሁድን ሰዓት ተጠቅመዋል፡፡
2. ዮሐንስ ለኢየሱስ መስቀል ከኋላ ያለውን ጊዜ በመውሰድ ያረጋግጣል፤ ይህም በዮሐንስ እና በሌሎች ወንጌላት መካከል ካሉት ልዩነቶች ሌላው ምሣሌ የሚሆን ነው፡፡

ከዮሐንስ 1:39 እና 4:6 ላይ መረዳት እንደሚችለው ዮሐንስ የሚጠቅሰው የአይድን ሰዓት እንጂ የሮማዊያንን ጊዜ ይመስላል (ኤም አር. ቪንሰንት፤ *word studies* ቅፅ1 ገጽ 403)፡፡

ለሁሉም ወንጌላት ውስጥ ያሉት የጊዜ ስያሜዎች ምናልባት ምሣሌነት ያላቸው ሊሆን ይችላል ምክንያቱም ሊዛመዱ የሚችሉት፣

1. በየዕለቱ በቤተመቅደስ መሥዋእት በሚቀርብበት ሰዓት ጋር (ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ ቀኑ 9፡00 ሰዓት ድረስ፤ ሐዋ 2:15፤3:1)
2. ከሰዓት በኂላ የፋሲካ ጠበታ የሚታረድበት የተለመደው ጊዜ ይህም በኒሳን ወር በ14ኛው ቀን ከሰዓት በኂላ ማለት ነው፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ እንደዘመናችን የምዕራባዊያን ታሪካዊ ክስተቶች በጊዜ ቅደም ተከተል ላይ ትኩረት የሚያደርግ የጥንት ምሥራቃዊያን መፅሐፍ ነው፡፡

▣ **"እነሆ፤ ንጉሣችሁ"** ልክ ቁጥር 5 ዘካ 6:12ን እንደሚጠቅስ ሁሉ ይህም ሐረግ ዘካ 9:9ን በተዘዋዋሪ የሚጠቅስ ሊሆን ይችላል (ኤፍ. ኤፍ. ብሩስ፤ *ANswers to QuestioNs*፤ ገጽ 72)፡፡

19:15 **"አስወግደው: አስወግደው: ስቀለው"** በግሪኩ ይህ ሐረግ ድርጊት ገላጭ ትዕዛዞች አሉት፡፡ "ስቀለው" የሚለው ሥረወ ቃሉ "ወደ ላይ ማንሳት" ወይም "ከፍ ማድረግ" ሲሆን ይህም ከዮሐንስ ጣምራ አገባቦች አንዱ ሊሆን ይችላል (3:14፤8:28:12:32)፡፡

▣ **"ከቄሣር በቀር ሌላ ንጉሥ የለንም ብለው መለሱበት"** ምፀታዊ አነጋገሩ የሚያስደነግጥ ነው፡፡ እነዚህ የአይሁ መሪዎች ኢየሱስን ለከለሱበት ክ ሙሉ በሙሉ ጥፋተኞች ነበሩ፡፡ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ብቻ ነው የሕዝቡ ንጉስ የሆነው (ንጉስ የሆነው(1ሳሙ 6)፡፡

19:16 **"ሰጣቸው"** በማቴ 27:26-27 እና ማር 15:15-16 ተውላጠ ስ የሚያመለክተው የሮማን ወታደሮች ነው፡፡ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ከመረጃዎች በመነሣት መወሰን የሚችለው ጲላጦስ ለአይሁድ መሪዎች እና ከሥርዓት ውጪ ለነበረው ሕዝብ ምኞት አሳልፎ እንደሰጠ ነው፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 19:17-22

**[17]ኢየሱስንም የዘው ወለዱት መስቀሉንም ተሸክሙ በዕብራይስጥ ጎልጎታ ወደ ተባለው ራስ ቅል ስፍራ ወደሚሉት ወጣ፡፡ [18]በዚያም ሰቀሉት ከእርሱም ጋር ሌሎች ሁለት አንዱን በዚህ አንዱን በዚያ ኢየሱስንም በመካከላቸው ሰቀሉ፡፡ [19]ጲላጦስም ደግሞ ጽሕፈት ጽፎ በመስቀሉ ላይ አኖረ፤ ጽሕፈቱም፡- የአይሁድ ንጉሥ የናዝሬቱ ኢየሱስ የሚል ነበር፡፡ [20] ኢየሱስም የተሰቀለበት ስፍራ ለከተማ ቅርብ ነበርና ከአይሁድ ብዙዎች ይህን ጽሕፈት አነበቡ፤ በዕብራይስጥና በሮማይስጥ፣ በግሪክም ተጽፎ ነበር፡፡ [21] ስለዚህ የአይሁድ ካናት አለቆች ጲላጦን፡- እርሱ የአይሁድ ንጉሥ ነኝ እንዳለ እንጂ የአይሁድ ንጉሥ ብለህ አትፃፍ አሉት፡፡ [22]ጲላጦስስም የጻፍሁትን ጽፌ አለሁ ብሎ መለሰ፡፡**

19:17 **"መስቀሉንም ተሸክሞ"** በመጀመሪያው ክፈለዘመን በነበረው የፍልስጥኤም ምድር የመስቀሉ ቅርፅ በእርግጠኝነት የሚታወቅ አይደለም፡፡ ትልቁ የእንግሊዘኛው ፊደል *T* ትንሹ *t* ወይም *x* ሊሆነ ይችላል፡፡ አንዳንድ ጊዜ በርካታ እስረኞች በአንድ መስቀያ ላይ ይሰቀሉ ነበር፡፡ የመስቀሉ ቅርፅ ምንም ይሁን የተፈረደበት እስረኛ ከተገለፈ በኂላ እንጨት መስቀሉን ተሸክሞ ወደ መስቀያው ቦታ መሔድ ነበረበት (ማቴ 27:22፤ ማር 15:21፤ሉቃ:27፤ 23:26)፡፡

▣ **"በእብራይስጥ ጎልጎታ ወደ ተባለው የራስ ቅል ስፍራ ወደ ሚሉት"** የዚህ ሐረግ ትክክለኛው ትርጉም የሚታወቅ አይደለም፡፡ የእብራይስጡ/የአራማይኩ ቃል ሙሉ የራስ ቅልን የሚመልስ ኮረብታን አያመለክትም ነገር ግን ወደ ኢሩሣሌም በሚወስደው ዋና መንገድ ላይ ያለውን ዝቅተኛ ሥፍራን የሚያመለክት ነው፡፡ ሮማዊያን የሰቀሉት ለአመፅ እንደመቀጣጫ አድርገው ነበር፡፡ የዘመናችን የአርኪዎሎጂ ምርምር የከተማውን ጥንታዊ ቅጥሮች ትክክለኛ ሥፍራ በሚመለከት እርግጠኛ አይደለም፡፡ ኢየሱስም የተገደለው ከከተማው ቅጥር ውጪ በሚገኝ የሚታወቅ የመገደያ ሥፍራ ነበር፡፡

19:18 **"በዚያም ሰቀሉት"** የትኛውም የወንጌላት ክፍል ስለሮማዊያን አሰቃቀስ ዝርዝር ነገር ውስጥ አይገባም፡፡ ካርቴጂያኖች ከፋርሳዊያን እንደተማሩት ሁሉ ሮማዊያንም ከካርቴጂንስ የተማሩት ነው፡፡ ትክክለኛው የመስቀሉ ቅርፅም ቢሆን እንኳ የሚታወቅ አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ ጭካኔን እና ስቃይን የተሞላ ሞት እንደሆነ እናውቃለን፤ ይህም ሲደረግ የነበረው አንድን ሰው ለበርካታ ቀናት በስቃየ እንዲቆይ ነው፤ ሞትም ብዙውን ጊዜ ይከናወን የነበረው እስትንፋስ እንዲወጣ በማድረግ ነበር፡፡ ወና አላማውም የሮምን አገዛዝ የሚቃወሙትን መቀጣጫ እንዲሆናቸው ማሣየት ነበር፡፡

▣ **"ሌሎች ሁለት"** ይህም በማቴ 27:38፤ ማር 15:27 እና ሉቃ 23:33 የተዘገበውን የኢሳ 53:9 ትንቢትን ይፈፀም ዘንድ ነው፡፡

19:19 **"ጲላጦስም ደግሞ ጽሕፈት ጽፎ"** ጲላጦስ ምናልባት በእንጨት ጣውላ ላይ አንድ ሰው የፃፈውን ይህን ማዕረግ በእጁ ጽፎት ይሆናል(*titloN*)፡፡ ማቴዎስ ይህንን "ክስ" ይለዋል (ማቴ 27:37)፤ ማርቆስ እና ሉቃስ ደግሞ ፅሕፈት ይሉታል (*epigraphe* ፤ ማር15:26፤ ሉቃ 23:38)፡፡)

19:20 "በዕብራይስጥና በሮማይስጥ: በግሪክም ተፅፎ ነበር" "ዕብራይስጥ" አራማይክን ያመለክታል (5:2፤19:13፡17፤20:16፤ይሴፈስ: *ANtiq* 2.13.1)። በኢየሱስ ራስ ላይ የተፃፉትን ክሶች ትክክለኛ ፍቺ በሚመለከት በወንጌላት መካከል ያለውን ልዩነት ማተዋሉ በጣም አስፈላጊ ነው።

1. ማቴ 27:37 "ይህ የአይሁድ ንጉስ ኢየሱስ ነው"
2. ማር 15:26 "የአይሁድ ንጉስ"
3. ሉቃ 23:38 "የህ የአይሁድ ንጉሥ ነው"
4. ዮሐ 19:19 "የአይድ ንጉሥ የናዝሬቱ ኢየሱስ"

እያንዳንዱ የተለየ ነው፤ ነገር ግን በመሰረቱ አንድ ነው። ይህም እንግዲህ በወንጌላት መካከል ያለው ታሪካዊ ዝርዝርም እውነት ነው። እያንዳንዱ ፀሐፊ የራሱን ትዝታዎች በመጠኑ ለየት ባሉ መንገዶች መዝግቧል ነገር ግን አሁንም ቢሆን ተመሳሳየ የአይን ምስክሮች ናቸው።

ጲላጦስም አይሁድ በኢየሱስ መስቀል ላይ የሚፈሩትን ማዕረግ በማስቀመጥ የአይሁ መሪዎችን ለማስቆጣት ያደረገው ነበር (ቁ.21022)።

19:22 **"የጻፍኩትን ጽፌ አለሁ ብሎ መለሰ"** እነዚህ ሁለት ያልተሟሉ ጊዜ አመልካች ግሦች ሲሆኑ ትኩረት የሚያደርጉትም የተፃፈው ነገር መጠናቀቁን ወይም የመጨረሻው መሆኑን ነው።

**NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 19:23-25ሀ.**

**[23]ጭፍሮችም ኢየሱስን በሰቀሉት ጊዜ ልብሶን ወስደው ለእያንዳንዱ ጭፍራ አንድ ኢየሱስን በሰቀሉት ጊዜ ልብሶቹነ ወሰደው ለእያንዳንዱ። እጀ ጠባቡም ከላይ ጀምሮ ወጥ ሆኖ የተሠራ ነበር እንጂ የተሰፋ አልነበረም። [24] ስለዚህ እርስ በርሳች ለማን እነዲሆን በእርሱ ዕጣ እጣጣልበት እንጂ አንቀደደው ተባባሉ። ይህም ልብሴን እርስ በርሳቸው ተከፋፈሉ፤ በእጅ ጠባቤም ዕጣ ተጣጣሉበት የሚለው የመጽሐፍ ቃል ይፈፀም ዘንድ ነው። [25ሀ]ጭፍሮችም እንዲህ አደረጉ።**

19:23 **"ለእያንዳንዱ ጭፍራ አንድ ክፍል ሆኖ በአራት ከፋፈሉት"** ወታደሮ በኢየሱስ ልብሶች ላይ እጣ ተጣጣሉ። ይህም ከላይ የለበሳቸውን ብቻ የሚያመለክት ነው። የኢሱስ ልብሶች እንዴት በአራት እንደተከፈለው የሚታወቅ ነገር የለም። አይሁድ ሙሉ በሙሉ ራቁቱነ ቢሆን እንደ ድፍደረት ይቆጥሩት ነበር፤ ይህም በቁጥር 24 ላይ የተጠቀሰው እና ተፈፃሚነት የገኘው ሌላው ትንቢት ነበር (መዝ 22:18)።

▣ **"እጀጠባብ"** ኢየሱስ ከላይ የሚለብሰው ልብስ *himatia* በሚል የብዙ ቁጥር ተገልጿል። ከገላው ቀጥሎ የሚለከለው ረጅም የውስጠኛው ልብስ እጀጠባብ ነበር *ChitoN*:: በእነዚህም መካከል ያለው ልዩነት በማቴ5:40 እና ሉቃስ 6:29 ላይ ይችላል። ይርቃ እንዲህ አይነት ልብሳችን ትሠራ ነበር (ሐዋ 9:39)። የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን አይሁድ ከውስት የሚለበስ የወገብ ልብስ በተጨማሪነት ይለብሱ ነበር። ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ እርቃኑን አልተደረገም ነበር።

የቁጥር 23 የመጨረሻው ሐረግ ከኢየሱስ ጋር አብሮ ይኖር ከነበረው የተጨመረ የአዘጋጁ ማብራሪያ ነው።

▣ **"እጀ ጠባቡም ከላይ ጀምሮ ወጥ ሆኖ የተሠራ ነበረ እንጂ የተሠፋ አልነበረም"** ይህ ምናልባት ሥነ- መለኮታዊ ጠቀሜታ ሊኖረው ይችላል። እንዲህ ያለው እጀጠባብ ያተለመደ ከመሆኑም በላይ ምናልባት ውድ ሊሆን ይችላል። ያለመደ እ ውድ ልብስ መልበስ ደግሞ ከኢሱስ ባህሪይ ውጪ ይመልሳል። ከይሴፈስ(*ANtiq* 3.7.4) እንደምንገነዘበው ሊቀካሁኑ የረቢዎች ልማድ ሙሴ ለብሶት ነበር እንደሚሉት እንዲህ አይነቱነ መጎናፀፊያ ይለብስ ነበር። ይህ ምናልባት ለኢየሱስ

1. እንደ ሊቀካህን ሊገልፀው ይችላል (ዕብራዊያን)
2. እንደ አዲስ ሕግ ሠጠ ሊገልፀው ይችላል

ጣምራ ትርጉሞች በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ሁል ጊዜ የሚችሉ ናቸው፣ ነገር ግን የሚተረጎሙት ሁሉንም ዝርዝሮች አንዳች የተደበቀ ትርጉም እንዳላቸው ከማሰብ መጠንቀቅ አለባቸው፤

19:24 **"ይህም…. የመጽሐፍ ቃል ይፈፅም ዘንድ ነው"** መዝ 22 ሰልቅለቱ የብሉይ ኪዳን መነሻ ሆኖ የሚያገለግል ነው።

1. መዝ 22:1-2 - ማቴ 27:64:ማር 15:34
2. መዝ 22:7-8 - ማቴ 27:39:43፤ማር 15-2:ሉቃ 23:35
3. መዝ 22:15 - ማቴ27:48፤ማር 15:36፤ ሉቃ 23:36፤ዮሐ 19:28፡29
4. መዝ 22:16 - ማቴ 27:35:ማር 15:24:ዮሐ 20:25
5. መዝ 22:18 - ማቴ 27:35፤ማር 15:24፤ ሉቃ 23:34፤ ዮሐ 19:24
6. መዝ 22:27-28 - ማቴ 27:54፤ ማር 15:39፤ ሉቃ 23:47፤ (ዮሐ 20 :3)፤ ማቴ 28:18-20፤ ሉቃ 24:46-47፤ ሐዋ 1:8)።

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 19÷25ለ-27
[25ለ] *ነገር ግን በኢየሱስ መስቀል አጠገብ እናቱ የእናቱም እህት÷ የቀለዮጳም ሚስት ማርያም÷ መግደላዊትም ማርያም ቆመው ነበር፡፡ [26]ኢየሱስም እናቱን ይወደው የነበረውንም ደቀመዝሙር በአጠገቡ ቆም ባየ ጊዜ እናቱን አንቺ ሴት እነሆ ልጅሽ አላት፡፡ [27]ከዚህ በኋላ ደቀመዝሙሩን እናትህ አየኂት አለው፡፡ ከዚም ሰዓት ጀምሮ ደቀመዝሙሩ ወደ ቤቱ*

**19:25 "በኢየሱስ መስቀል አጠገብ እናቱ፣ የእናቱም እህት የቀለዮጃም ሚስት ማርያም፡ መግደላዊትም ማርያም ቆመው ነበር"** በዚህ ሥፍራ ላይ አራት ሰዎች ወይስ ሦስት ስሞች እንዳሉ ብዙ አከራካሪ ነገር አለ፡፡ ምናልባት አራት ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ ምክንያቱም በማርያም ስም የሚጠሩ ሁለት ፈእህቶች ሊኖሩ አይችሉምና፡፡ የማርያም እህት ሰሎሜ በማር 15:40 እና ማቴ 27:56 ላይ ተጠቅሳለች፡፡ ይህ እውነት ነው ካልን ዮሐንስ፤ ያዕቆብ እና ኢየሱስ ዩእህት ልጆች ናቸው ማለት ነው፡፡ የሁለተኛው ክፍለ ዘመን ወግ እንደሚያስረዳው (*Hegesippus*) ቀለዮጃ የዮሴፍ ወንድም እንደነበር ነው፡፡ መግደላዊት ማርያም ኢየሱስ ሰባት አጋንንት ያመጣለት እና ከትንሳኤ በኋላም ለመጀመሪያ ጊዜ ራሱን የገለጠላት ነበረች (20:1-2፤11-18፤ማር 16:1፤ሉቃ 24:1-10)፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ ኢየሱስን የተከተሉት ሴቶች**

*ሀ. ኢየሱስን እና የሐዋርያትን ቡድን ይረዱ የነበሩ ሴቶ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገለፁጽ በሉቃ 8:1-3 ላይ ነበር*

1. *ማርያም፣ መግደላዊት የተባለችው*(ቁ.2)
   - *ሀ. ማቴ*27:56፡61፤ 28:1
   - *ለ. ማር* 15:40፡47፤16:1፡9
   - *ሐ. ሉቃ* 8:2፤ 24:10
   - *መ. ዮሐ* 19:25፤ 20:1፡11፡16፡18
2. *ዮሐና፣ የኩዛ ሚስት(የሄሮስ ገረድ ቁ.3) በሉቃ 24፡10 ተገልፀለች*
3. *ሉዛና* (ቁ.3)
4. *‹‹ባለቸው ነገር ሁሉ ይረዱ የነበሩ ሌሎች ሁሉ››* (ቁ.3)

*ለ. በስቅለቱ ጊዜ እንደነበሩ የተጠቀሱት የሴት ወገኖች*

1. *የማቴዎስ ዝርዝር*
   - *ሀ. መግደላዊት ማርያም* (27:56)
   - *ለ. የያዕቆብ እና የዮሴፍ እናት ማርያም* (27:56)
   - *ሐ. የዘብዴዎስ ልጆች እናት* (27:56)
2. *የማርቆስ ዝርዝር*
   - *ሀ. መግደላዊት ማርያም* (25:40)
   - *ለ. የትንሹ ያዕቆብ እና የዮሣ እናት ማርያም* (15:40)
   - *ሐ. ሰሎሜ* (15:40)
3. *ሉቃስ ‹‹ከገሊላ ጀምሮ የተከተሉት ሴቶች›› ብቻ ይላል* (23:49)
4. *የዮሐንስ ዝርዝር*
   - *ሀ. የኢየሱስ እናት ማርያም* (19:25)
   - *ለ. የእናቱ እህት* (19:25)
   - *ሐ. የቀለዮጳ ማርያም [የኪንግ ጀምስ ቀለዮጳ፤ ይህ ቀለዮጳ ሚስት ወይም የቀለዮጳ ሴት ልጅ ሊሆን ይችላል]* (19:25)
   - *መ. መግደላዊት ማርያም* (19፡25)

*ሐ. የኢሱስን ቀብር የተመለከቱ የሴቶች ስብስብ ተጠቅሷል*

1. *የማቴዎስ ዝርዝር*
   - *ሀ. መግደላዊት ማርያም* (27:61)
   - *ለ. ሌላዋ ማርያም* (27:61)
2. *የማርቆ ዝርዝር*
   - *ሀ. መግደላዊት ማርያም* (15:47)
   - *ለ. የዮሣ እናት ማርያም* (15:47)
3. *ሉቃስ ‹‹ከገሊላ ውጪ ጀምሮ ኢየሱስን የተከተሉት›› ብቻ ይላል* (23:55)
4. *ዮሐንስ መቃብሩን ለልዩ ሰዎች የዘገበው ምንም የለም*

*መ. እሁድ ማለዳ ወደ መቃብሩ ስለመጡ ሴቶች ሰብሰብ*

1. *የማቴዎስ ዝርዝር*
   - *ሀ. መግደላዊት ማርያም* (28:1)

ለ. ሴላዊ ማርም (28:1)

2. የማርቆስ ዝርዝር

ሀ. መግደላዊት ማርያም (16:1)

ለ. ማርያም የያዕቆብ እናት (16:1)

ሐ. ሰሎሜ (16:1)

3. የሉቃስ ዝርዝር

ሀ. ‹‹ወደ መቃብሩም መጡ›› (24÷1-5:24)

(1) መግደላዊት ማርያም (24÷10)

(2) ዮሐና (24÷10)

(3) ማርያም የያዕቆብ እናት (24÷10)

2. ዮሐንስ መግደላዊት ማርያምን ብቻ ይዘረዝራል (20÷1:11)

ሠ. በላይኛው ደርብ እንደተገኙ ሴቶች ተጠቅሰዋል (ሐዋ 1÷14)

1. ‹‹ሴቶች›› (1÷14)

2. የኢየሱስ እናት ማርያም (1÷14)

ረ. በእነዚህ የተለያዩ ዝርዝሮች ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ሴቶች ትክክለኛ ግንኙነት የሚታወቅ አይደለም፡፡ መግደላዊት ማርያም ከሁሉም ይልቅ የቀዳሚነት ሚና እንዳላት ግልፅ ነው፡፡ ‹‹ሴቶች›› በኢየሱስ ሕይወት እና አገልግሎት ውስጥ በሚለው ጥሩ ፅሑፍ የሚገኘው በDictioאary of Jesus aאd the Gospels፣ በIVP የታተመ፣ ገጽ 880-

**19:26 "ይወደው የነበረውንም ደቀመዝሙር"** በወንጌሉ ውስጥ ዮሐንስ በስም ተለይቶ ስላልተጠቀሰ ብዙዎች የሚገምቱት ይህ ራሱን የሚገልጥበት መንገድ እንደሆነ ነው (13:23፤19:26፤21፤7:20)፡፡ በእነዚህ በእያንዳንዱ ጥቅስ ዮሐንስ *agapas*(አጋፔ) የሚለው ቃል ይጠቀሳል፤ ነገር ግን በ20:2 ላይ ተመሳሳይ ሐረግ ግን *phiteo*(ፊሎ) ከሚለው ጋር ይጠቀማል:: እነዚህ ቃላት በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ተመሳሳይ ናቸው፡፡ 3:35(*agapao*) እና 5:203(*phileo*)ን ስታነፃፅር ሁለቱም የሚያሳዩት አብ ለወልድ ያለውን ፍቅር ነው፡፡

**19:27 "ከዚህም ሰዓት ጀምሮ ደቀመዝሙሩ ወደ ቤቱ ወሰዳት"** ይህ በእርግጠኝነት ዮሐንስ ማርያምን ወዲያው ወደ ቤቱ ወሰዳት ማለት አይደለም፣ ምንም እንኳን እርሷ ከሌሎች ሴቶች ጋር በማቴ 27:56 እና በማር 15:40 ውስጥ ባለመጠቀሷ ምክንያት ይህ ሊባል ቢችልም፡፡ ነገር ግን የቆየው ልማድ እንደሚለው ከሆነ ዮሐንስ ማርያምን እስክትሞት ድረስ እንደተንከባከባት እና በኋላም ረጅም እና ሰኬታማ አገልግሎ ወዳገኘበት ትንሹ እስያ (በተለይም ኤፌሶን) መሔዱን ነው፡፡ ዮሐንስ ሽማግሌ እንደመሆኑ መጠን በኤፌሶን የነበሩት ሽማግሌዎች ሰለሶች ኮሉት ነው ስለ ኢየሱስ ሕይወት የነበረውን ትዝታ ሊፅፍ የቻለው (የዮሐንስ ወንጌልን)፡፡

**NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 19÷28-30**
**[28] ከዚህ በኋላ ኢየሱስ አሁን ሁሉ እንደተፈፀመ አውቆ የመፅሐፍ ቃል ይፈጸም ዘንድ፡- ተጠማሁ አለ፡፡ [29]ከዚያም ሆምጣጤ የምላበት ዕቃ ተቀምጦ ነበር፡፡ እርሱመ ሆም ጣጤውን በሰፋነግ ሞልተው በሁሶፕም አድርገው ወደ አፉ አቀረቡለት፡፡ [30]ኢየሱስም ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ፡- ተፈፀመ አለ÷ ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ፡፡**

**19:28 "ኢየሱስ አሁን ሁሉ እንደተፈፀመ አውቆ የመፅሐፍ ቃል ይፈፀም ዘንድ ተጠማሁ አለ"** ከትርጉም አንፃር የተጠቀሰው ክፍል "ተጠማሁ" ወይም "ሁሉም ነገር ተፈፅሟል" የሚለውን ሐረግ ለማመልከት ይሁን ግልፅ አይደለም፡፡ ከባህል አንፃር የሚወለድ(የሚታይ) ከሆነ "ተጠማሁ" የሚለው መዝ 69:21ን ለማመልከት ነው፡፡

**19:29 "ከዚያም ሆምጣጤ የሞለበት ዕቃ ተቀምጦ ነበር"** ይህ የኮመጠጠ እና ርካሽ የሆነ ወይን ጠጅ ነው፡፡ ለውታደሮች ወይም ጠጅ ነው፡፡ ለውተደሮች ወይም ለሚሰቀሉት ይሆን ነበር፤ አርሱም የመስቀል ላይ ሥቃያቸው እንዲቀዩ በትንሽ በትንሹ ይሰጣቸው ነበር፡፡

▣ **"ሆምጣጤ"** ይህ ቃል በቃል ትርጉሙ "ወይንጠጅ" ሲሆን የድሐ ሰዎች መጠጥ ነበር፡፡ ኢየሱስ የኢሩሳሌም ሴቶች ለጋ ወይንጠጅን ሊሰጡት አልተቀበለም ነበር (ማር 15:23፤ ማቴ 27:34)፡፡ ይህን መጠጥ የተቀበለበት ምክንያት ምናልባት በመዝ 22:15 ላይ የተነገረው ትንቢት ይፈፀም ዘንድ ነው፡፡ ኢሱስ ለመናገር እጅግ ዝሎ ስለነበር አንድ ቃል ብቻ በተጨማሪ መናገር ነበረበት፡፡

▣ **"በሶፍነግ ሞልተው፤ በሁሶፕም አድርገው"** አንዳንዶች ይህንን የሚመለከቱት በፋሲካ በዓል ጊዜ ደረግ እንደነበረው (ዘፀ 12:22) እንደ አንድ የተለየ ዕፅዋት ምልክት ነበር፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ቃሉን በሚመለኮት በጥንቱ ፅሑፍ ላይ ግድፈት

እንዳለበት፤ ከመጀመሪያውም የነበረው ትርጉም "ጦር፣ ጋሻ፣ ወይም "በትር" ነበር ብለው ያምናሉ (ኤን. ኢ.ቢ. ነገር ግን REB ወደ ሂሶና ቀይረዋል)፡፡ ማቴዎስ 27:48 እና ማር 15:36 "ሸንበቆ" የሚል ቃል አላቸው፡፡

ብዙዎቹ እዚህ ላይ የጽሁፈት ለውጥ አለ የሚሉበት ምክንያት የሂሶፕ ተክል በጣም ትልቅ ግንድ አልነበረውም (ከ2 እስከ 4 ጫማ ርዝመት ብቻ)፤ ነገር ግን መስቀሎቹ ከመሬት ያን ያህል ከፍቶ ወደ ላይ የሚነሱ አልነበሩም፡፡ እኛ በልማድ ከፍ ላለው መስቀል ያለን ምስል ምናልባት 3:14ን ካለመረዳት የመነጨ ሳይሆን አይቀርም፡፡ የኢየሱስ እግሮች ምናልባት ከመሬት ሁለት ወይም ሦስት ጫማ ከፍታ ላይ ቢሆን ነው፡፡

**19:30 "ተፈፀመ"** ይህ የተሟላ *ተደርጐ ግሥ አመልካች* ነው፡፡ ከሌሎች ወንጌላት የምንረዳው ነገር ይህንን በታላቅ ድምፅ ጮሆ እንደተናገረ ነው (*ማር* 15:37፤ *ሉቃ* 23:46፤ *ማቴ* 27:50) ፡፡ ይህም የሚያመለክተው የተጠናቀቀውን የድነት *ሥራን* ነው፡፡ የዚህ *ቃል ገጽታ* (ሌላው) (*teslos*) ነገብየዊየን ፓፒረስ (ምልተን እና ሚሊጋን) የንግድ አነጋገር ዘይቤ ሲሆን "በሙሉ ተከፍሏል" የሚል ሐሳብ አለው፡፡

▣ **"ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን አሳፎ ሰጠ" "ራሱን አዘንብሎ"** የሚለው ሐረግ "ሊንቀላፋ ነው" ለሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር ነው፡፡ የኢየሱስ *መሞት* ለእደርሱ የፀጥታ ጊዜ ነበር፡፡ ከዚህ *መረዳት* የሚቻል በሞት ጊዜ ጫፍ ያለው *መንፈሳዊ* ከፍል *ከሥጋዊው* ክፍል እንደሚለይ ነው፡፡ ይህም *ከሥጋ* የተለየች የአማኞች ነፍስ በሞት እና በትንሳኤ ቀን *መካከ*ከል እንደምትሆ ነው (2ቆሮ5፤1ተስ4:13-18፡ የሚልያም ሄንድሪክሰንን፡- *The Bible oN the life after* የሚለውን ይመልከቱ፡፡)፡፡

በማር 15:37 እና በሉቃ 23:46 ያሉት ክፍሎች **"ሞተም"** የሚል ቃል አላቸው፡፡ **"መንፈስ"** እና **"ትንፋሽ"** ለሚለው የእብራይስጡ *ቃል* ተመሳሳይ ነው፤ የመጨረሻው ትንፋሽ የታየው *መንፈስ ከሥጋው* እንደተለየ ነበር (ዘፍ 2:7)፡፡

> NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 19÷31-37
>
> **[31]አይሁድም የማዘጋጀት ቀን ስለሆነ ያ ሰንበት ትልቅ ነበርና ሥጋቸው በሰንበት በመስቀል ላይ እንዳይኖር÷ ጭናቸውን ሰብረው እንዲያወርዱአቸው ጲላጦን ለመኑት፡፡ [32] ጭፍሮችም መጥተው የፊተኛውን ጭን ከእርሱም ጋር የተሰቀለውን የሌላውን ጭንሰበሩ፤ [33]ወደ ኢየሱስ በመጡ ጊዜ ግን እርሱ ፈፅሞ እንደሞተ አይተው ጭኑን አልሰበሩም፤ [34]ነገር ግን ከጭፍሮች አንዱ ጎኑን በጦር ወጋው፤ ወዲውም ደምና ውሃ ወጣ፡፡ [35]ያየውን መስክሮአል፤ ምስክሩመ እውነት ነው፤ እናንተም ደግሞ ታምኑ ዘንድ እርሱ እውነት እንዲናገር ያውቃል [36]ይህ የሆነ፡- ከእርሱ አጥንት አይሰበርም የሚል የመፅሐፍ ቃል እንዲፈፀም ነው፡፡ [37] ደግሞም ሌላው መጽሐፍ፡- የወጉትን ያዩታል ይላል፡፡**

**19:31 "*ሥጋቸው በሰንበት በመስቀል ላይ እንዳይኖር*"** *ሙት* አካላት ምድሩን እንዳይበክሉ አይሁድ በጣም ትኩረት የሚሰጡበት ነው (ዘጻ21:23)፤ በተለይም በታላቁ የፋሲካ ሰንበት (ቅዱስ ሰንበት) ወቅት፡፡

▣ **"*ያ ሰንበት ነበርና*"** ይህ በሁለት *መንገዶች ሲተረጎም* የቆየ ነው፤

1. የፋሲካው ምግብ እና የሰንበት ቀን በዚህ *ዓመት* ተገጣጥመው ነበር (አይሁድ የጨረቃ ጊዜ አቆጣጠርን ይጠቀሙ ነበር)፡፡
2. የቂጣ በዓል የሚከበርበት ዕለት ከሰንበት ጋር በዚህ ዓመት *ተጋጥሟል*፡፡

የፋሲካ በዓል እና የቂጣ በዓል (እርሾ የሌለበት) (ዘፀ 12) የ8 ቀናት በዓል ሆነ፡፡

▣ **"ጭናቸውን ሰብረው እንዲያወርዱአቸው"** ይህ *ሁኔታ ቀደም ሲል መከሰቱበግልፅ የሚታወቅ ነው*፡፡ የተሰቀሉ ሰዎችን ጭን ለመሰበር ትልቅ የእንጀጨት *መዶሻን* ይጠቀሙ ነበር፡፡ መስቀል ብዙ ጊዜ ይካሄድ የነበረው ራሳቸውን እንዲስቱ በማድረግ ነበር፡፡ ጭኖችን መስበር ይህንን ያፋጥን ነበር ምክንያቱም የተሰቀለው ሰው ለመተንፈስ ይችል ዘንድ እግሮቹን *መሰብሰብ* (ወደላ) አይችልምና፡፡

**19:33 "እርሱ ፈፅሞ እንደሞተ አይተው፣ ጭኑን አልሰበሩም"** ይህ ምልባት ወደ ኋላ በመመለስ በዘፀ 12:46፤ዘሕ 9:12 እና *መዝ* 34:20 ላይ የተነገረውን ትንቢት ያሟላ ሊሆን ይችላል፡፡

**19:34 "ከጭፍሮች አንዱ ጎኑን በጦር ወጋው፤ ወዲያውም ደምና ውሃ ወጣ"**

ይህ የሕክምና ድባብ ያለው የአይን ምሥክርነት ሲሆን በትክክል *መሞቱን ከማሳየቱም* ባሻገር የመሲሑን የኢየሱስን ሰው *መሆን* በተዘዋዋሪ የሚጠቁም ነገር ነበር፡፡ የዮሐንስ ወንጌልም ሆነ የመጀመሪው የዮሐንስ *መልዕክት* የተፃፉት የኢየሱስን አምላክነት ከሚያምን እና ሰው መሆኑን የማቀበለው የግኖስቲክ ነፋቂ እያደገ በመጣበት ዘመን ነበር፡፡

**19:35** ይህ በዮሐንስ በራሱ የተሰጠ አስተያየት ሲሆን እርሱም(1) በምሽት ለተደረጉ የፍርድ ችሎቶች (2) ለሮማዊያን የፍርድ ችሎት እንዲሁም ደግሞ (3) ለስቅለቱ ብቸኛው የአይን ምስክር ነበር፡፡ ይህ በኢየሱስ ሞት ላይ የተሰጠ አስተያየት ከ20:30-31 *ጋር የሚመሳሰስ* እና የመጽሐፉን የወንጌል ዓላማ የሚያሳይ ነው (21:24)፡፡ በ1:8 ላይ የኢሱስ ምስክር የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

የመጨረሻውን የግሥ ሐረግ በሚመለከት በግሪኩ ምንጭ ላይ ልዩነት ይስተዋላል፡፡ አንዳንድ ጥቅሶች የአሁን ጊዜ አመልካች ቅፅል ሲኖራቸው ሌሎች ደግሞ የግሪኩን ድርጊት ገላጭ ግሥ አላቸው፡፡ ከመጀመሪያውም የግሪክ ድርጊት ገላጭ ግስ ከነበራቸው ል ንደ 20:30-31 በማያምኑ ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የአሁን ጊዜ አመልካች ቅፅል ከሆነ ትኩረት የሚያደርገው ቀጣይነት ባለው እና እያደረገ በሚሄድ እምነት ላይ ነው፡፡

የዮሐንስም ወንጌል በሁለቱ ወገኖች ላይ ትኩረት ያደረገ ይመስላል፡፡

19:37 ይህ ከዘካ 12:10 ላይ የተወሰደ ጥቅስ ሲሆን ይህም ከተሰጡት ታላላቅ ተስፋዎች አንዱ በመሆኑ

1. እስራኤል አንድ ቀን ወደ መሲሑ ኢየሱስ በእምነት ትመለሳለች (ራዕ 1:7)
2. ቀደም ሲል አምነው የነበረው አይሁድ ኢየሱስ ሞት ምክንያት ሲያዝኑ ነበር
3. አህዛብ የሆኑ ሕዝቦችን የሚወክሉትን (12:320 የሮም ወታደሮችን ነው (ማቴ 27:54)፡፡

በጣም ደስ የሚለው ነገር ደግሞ ይህ ጥቅስ የተወሰደው በተለምዶ በወንጌል ፀሐፊዎች ከሚጠቀሰው ከሰብትዋጅንት ምንጭ ሳይሆን ከእብራይስጡ የማዞሬቲክ ምንጭ መሆኑ ነው፡፡ ሰብትዋጅንት "አሳገጠ" የሚል ሲሆየማዞሬቲክ ምንጭ ግን "ወጉት" የሚል ቃል አለው፡፡

---

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 19÷38-42

**[38]ከዚህም በኋላ አይሁድን ስለፈራ በስውር የኢሱስ ደቀመዝሙር የነበረ የአሮማትያስ ዮሴፍ የኢሱስን ሥጋ ሊወስድ ጲላጦን ለመነ፤ ጲላጦስም ፈቀደለት፡፡ ስለዚህም መጥቶ የኢየሱስን ሥጋ ወሰደ፡፡ [39]ደግሞም አስቀድሞ በሌሊት ወደ ኢየሱስስ መጥቶ የነበረ ኒቆዲሞስ መቶ ንጥር የሚያህል የከርቤና የእሬት ቅልቅል ይዞ መጣ፡፡ [40]የኢሱስንም ሥጋ ወሰደው እንደ አይሁድ አገናነዝ ልማድ ከሽቱ ጋር በተልባ እግር ልብስ ከፊኑት፡፡ [41]በተሰቀለበትም ስፍራ አትክልት ነበር÷ በአትክልቱም ማም ገናአልተቀበረበትም አዲስ መቃብር ነበር፡፡ [42]ስለዚህ መቃብሩ ቅርብ ነበርና ስለ አይሁድ ማዘጋጀት ቀን ኢየሱስን በዚያ አኖሩት፡፡**

---

19:38-39 "ዮሴፍ... ኒቆዲሞስ" እነዚ ሁለት ሐብታም እና ተደማጭነት የነበራቸው የሸንጎ አባላት የኢሱስ ድብቅ(ስውር) ደቀመዛሙርት ሲሆን በዚህ ወሣኝ እና አደገና ወቅት ግን ራሳቸውን ሲገልጡ ይታያሉ፡፡

19:39 "**መቶ ንጥር የሚያህል የከርቤና የእሬት ቅልቅል ይዞ መጣ**" ይህ በመጀመሪው ክፍለ ዘመን የነበር እና አይሁድ የሚጠቀሙበት መልካም መዓዛ ያው ለቀብር የሚዘጋጅ ቅመም ነው፡፡ መጠኑ በጣም ብዙ በመሆኑ አብዛኛዎቹ አይሁድ ኢየሱስ እንደ ንጉስ ለመቀበሩ ይህ ምልክት ነው የሚል እይታ አላቸው (2ዜና 16:14)፡፡ በ11:2 ላይ በቅባት ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ /ተጨማሪ የጥናት ርዕስን ይመልከቱ፡፡

---

**ተጨማሪ የጥናት ርዕስ: የቀብር ቅመማ ቅመሞች**

ሀ. ከርቤ፡- ከአርብ ዛፎች የሚገኝ መዓዛ ያለው ሙጫ
1. ይህ ቅመም በብሉይ ኪን አስራሁለት ጊዜያት ተጠቅሷል: በተለይም በጥበብ ፅሑፎች ውስጥ እንደ ሽቶ ተጠቅሷል፡፡
2. ለሕፃኑ ኢየሱስ ሰብአሰገል እጅ መንሻ ካቀረቡለት ሥጦታቸዎ አንዱ ነበር (ማቴ 2:11)
3. ተምሣሌትነቱ በጣም የሚያስደስት ነው(ዘፀ30:23-25)
   ሀ. ‹‹ቅዱስ የቅባት ይዘት›› (ዘፀ 30:23-25) ዝግጅት ውስጥ ተጠቅሷል
   ለ. ለንጉስ እንደሚሰጥ ሥጦታ ተጠቅሷል (ማቴ2:11)
   ሐ. ኢሱስ ሲቀበር ተቀብቶታል (ዮሐ 19:39እና በተምሳሌትነት ደግሞ በዮ11:2)፡፡ ይህም በአይሁድ ልምድ መሠረት በተልሙድ ውስጥ ተጠቅሷል (ቤራኮት 53ሀ)፡፡

ለ. እሬት፡- መልካም መዓዛ ያለው የእንጨት አይነት
1. መልካም መዓዛ ካለው ሽቶ ጋር የተያያዘ ነው (ዘህ 24:6፤መዝ 45:8 ምሳ 7:17፤ መሐልይ ዘሰለሞን 4:14)
2. አስከሬነ በማድረቅ ሂደት ውስጥ ግብፃዊያን ከከርቤ ጋር ደባልቀው ይጠቀሙት ነበር
3. ኒቆዲሞስ ኢየሱስ በሚቀበርበት ጊዜ ብዙ አምጥቶ ኢየሱስን ቀብቶት ነበር(19:39)፡፡ ይህም በአይሁድ ልማድ መሠረት ቦታ ልሙድ ውስጥ ተጠቅሷል (ቤራኮት 6ሀ)፡፡

---

19:40 "የኢየሱስንም ሥጋ መስደው እንደ አይሁድ አገናነዝ ልማድ ከሽቱ ጋር በተልባ እግር ልብስ ከፈኑት" ቅመሞች ጥቅም ላይ የሚውሉት ለሁለት አላማዎች ነበር፤ (1) ሽታውን ለማስወገድ እና (2) ከፈኑን ሥፍራው እንዳለ ለማቆየት ነበር፡፡

19:41 **"በተሰቀለበትም ሥፍራ አትክልት ነበር"** ዮሴፍ እና ኒቆዲሞስ እንዲ በጥድፊያ ያከናውኑበትን ምክንያት መረዳት በጣም አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ ኢየሱስ የሞተው ከቀኑ 9:00 ሰዓት ላይ ሲሆን በመቃብር መሆን የነበረበት ከምሽቱ 12:00 ሰዓት ነው፤ ይህም የአይሁድ የፋሲካ በዓል የሚጀምርበት በመሆኑ ነው፡፡

▣ ***"ማንም ገና ያልተቀበረበት አዲስ መቃብር"*** *ይህ ዙሪያ ጥምጥም የሆነ የተሟላ በዚ አንቀፅ* ነው፡፡ ከማቴ 27:6 እንደምንረዳው ይህ የዮሴፍ የራሱ መቃብር ነበር፡፡ ይህም በማቴ 27:57 የተጠቀሰው ኢሳ 53:9 የፈፀም ዘንድ ነው፡፡

## የውይይት ጥቄዎች

*ይህ የጥናት መመሪያ ሲሆነ የሚችል ማብራሪያ እንደመሆኑ መጠን ለምትከተለው የመፅሐፍ ቅዱስ አተርጓጎም ኃላፊነት አለብህ፡፡ እያንዳንዳችን ልንጓዝ የሚገባ ባለን መረዳት መሠረት ነው፡፡ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ* በአተረጓጎም ወቅተ ቅድሚያ የሚሰጣችሁ ናችሁ፡፡ ይህንንም ጉዳይ በሚያብራራው ሰው ላይ ብቻ ልትተው አይገባህም፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎ የተሰጡት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በተገለፁት ዋና ዋና ጉዳዮች ላ በጥሞና እንዲታሰብበት ነው፡፡ እነዚህም ጥያቄዎች እንደ ሐሳብ- አነሳሽ ሆነው እንጂ ግልፅ ሆነው አይደለም የቀረቡት፡፡

1. ለምንድ ነው ወታደሮች ኢየሱስን የመቱት እና ያላገጡበት?
2. ጲላጦስ በተደጋጋሚ ኢየሱስን ሊለቀው የፈለገበት ጠቀሜታው ምንድ ነው?
3. በቁጥር 15 ላይ ያለው የአይሁድ ካህን ንግግር በጣም አስደናቂ የሆነበት ለምንድ ነው?
4. ስቅለቱ ዝርዝሮች ከወንጌል ወንጌል የሚለይበት ምክንያት ምንድ ነው?
5. ዘዳግም 21:23 የኢየሱስን ስቅለት የሚያዛምደው ከማን ጋር ነው?

# ዮሐንስ 20

## የተሻሻሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች አንቀፅ አከፋፈል

| UBS[4] | NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| የኢየሱስ ትንሣኤ | ባይው መቃብር | ትንሳኤ | ባዶ መቃብር | ባዶ መቃብር |
| 20:1-10 | 20:1-10 | 20:1-10 | 20:1-10 | 20:1-2 |
| | | | | 20:3-10 |
| ኢየሱስ ለማግደላዊት ማርያም ተገለጠ | መግደላዊት ማርያም ከሞት የተነሳውን ጌታ አየች | | ኢየሱስ ለመግደላዊት ማርያም ተገለጠ | ለመግደላዊት ማርያም ተገለጠ |
| 20:11-18 | 20:11-18 | 20:11-18 | 20:11-13ሀ | 20:11-18 |
| | | | 20:13ለ | |
| | | | 20:14-15ሀ | |
| | | | 20:15ለ | |
| | | | 20:16ሀ | |
| | | | 20:16ለ | |
| | | | 20:17 | |
| | | | 20:18 | |
| ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርት ታየ | ሐዋርያት ተልዕኮ ተሰጣቸው | | ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ታየ | ለደቀመዛሙርት መገለጥ |
| 20:19-23 | 20:19-23 | 20:19-23 | 20:19-23 | 20:19-23 |
| ኢየሱስና ቶማስ | ማየትና ማመን | - | ኢየሱስና ቶማስ | - |
| 20:24-29 | 20:24-29 | 20:24-29 | 20:24-25ሀ | 20:24-29 |
| | | | 20:25ለ | |
| | | | 20:26-27 | |
| | | | 20:28 | |
| | | | 20:29 | |
| የመጽሐፉ አላማ | ታምኑ ዘንድ | | የመጽሐፉ አላማ | የመጀመሪያው ማጠቃለያ |
| 20:30-31 | 20:30-31 | 20:30-31 | 20:30-31 | 20:30-31 |

## ሦስተኛ የጥናት ዑደት (ዙር) (አንቀ. 5 ይመልከቱ፡፡)
*የመጀመሪያው ፀሐፊ ዋና ሐሳብ በአንቀፅ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ሲሆን የሚችል ማብራሪያ በመሆኑ ለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ፡፡ እያንዳንዳችን መጓዝ ያለብን ባለን መረዳት መጠን ሊሆን ይባላል፡፡ በአተረጓጎም ወቅት አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ቅድሚያ የሚሰጣችሁ ናችሁ፡፡ በመሆኑም ይህንን ጉዳይ በሚያብራራው ሰው ላይ ብቻ መተው የለብህም፡፡

ሙሉውን ምዕራፍ በአንድ ቁጭት አንብበው፣ ዋና ሐሳቦቹንም ለያቸው፡፡ የራስህን የርዕስ አከፋፈል ከአምስቱ የተሻሻሉ ትርጉሞች ጋር አስተያያቸው፡፡ በአንቀፅ መከፋፈል በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት የሚካሄድ ባይሆንም ለአተረጓጎም ክህሎት እንብርት የሆነውን የመጀመሪያውን ፀሐፊ ዋና ሐሳብ ለመከተል ግን ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ እያንዳንዱም አንቀፅ የሚያወሳው ስለአንድ ሐሳብ ብቻ ነው፡፡

1. የመጀመሪያ አንቀፅ

2. ሁለተኛ አንቀፅ

3. ሦስተኛ አንቀፅ

4. ወዘተ

## በቁ. 1-29 ላይ አወዳዊ መረዳቶች /ግንዛቤዎች/

ሀ. በምዕ 14-27 ላይ ኢየሱስ ለሐዋርያት የገባው ማንኛውም ተስፋ የተፈፀመው በመጀመሪያ ትንሳኤ ምሽት እሁድ ዕለት ነበር፡፡ 16:20ን ይመልከቱ፡፡
ለ. በትንሳኤው ዙሪያ የወንጌል ታሪኮች የሚሰጡት ዝርዝር የሚለዩበት ምክንያት
   1. የአይን ምሥክሮች ታሪክ በመሆናቸው
   2. ዓመታት ስላለፉ
   3. እያንዳንዱ የፃፈው ለተወሰኑ ወገኖች በመሆኑና የተለያዩ ነገሮች ላይ ትንቢት ስላደረገ (ማቴ 28 ማር 16፣ ሉቃ 24)፡፡

### የቃልና የሐረግ ጥናት

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 20፡ 1-10
**[1]ከሳምንቱም በፊተኛው ቀን መግደላዊት ማርያም ገና ጨለማ ሳለ ማለዳ ወደ መቃብር መጣች፡፡ ድንጋዩም ከመቃብሩ ተፈንቅሎ አየች፡፡ [2]እየሮጠችም ወደ ስምዖን ጴጥሮስና ኢየሱስ ይወደው ወደ ነበረው ወደ ሌላው ደቀ መዝሙር መጥታ፡- ጌታን ከመቃብር ወስደውታል፡፡ ወዴትም እንዳኖሩት አናውቅም አለቻቸው፡፡ [3]ስለዚህ ጴጥሮስና ሌላው ደቀ መዝሙር መጥተው ወደ መቃብር ሄዱ፡፡ [4]ሁለቱም አብረው ሮጡ፤ ሌላው ደቀ መዝሙርም ከጴጥሮስ ይልቅ ፈጥኖ ወደፊት ሮጠና አስቀድሞ ከመቃብሩ ደረሰ፤ [5]ዝቅም ብሎ ቢመለከት የተልባ እግሩን ልብስ ተቀምጦ አየ፥ ነገር ግን አልገባም፡፡ [6]ስምዖን ጴጥሮስም ተከትሎት መጣ፡ ወደ መቃብሩም ገባ፤ የተልባ እግሩን ልብስ ተቀምጦ አየ፥ [7]ደግሞም በራሱ የነበረውን ጨርቅ ለብቻው በአንድ ስፍራ ተጠምጥሞ እንደ ነበረ እንጂ ከተልባ እግሩ ልብስ ጋር ተቀምጦ እንዳልነበረ አየ፡፡ [8]በዚያን ጊዜ አስቀድሞ ወደ መቃብር የመጣውም ሌላው ደቀ መዝሙር ደግሞ ገባ፥ አየም፥ አመነም፤ [9]ከሙታን ይነሣ ዘንድ እንዲገባው የሚለውን የመጽሐፉን ቃል ገና አላወቁም ነበረና፡፡ [10]ደቀ መዛሙርቱም ወደ ቤታቸው ደግሞ ሄዱ፡፡**

20:1 **"ከሳምንቱም በፊተኛው ቀን"** የመጀመሪያ የበኩር ፍሬዎች በቤተ መቅደሱ ሲደረጉ የፋሲካን ሰንበት ታላቅ ሰንበት ተከትሎት የሚመጣው የመጀመሪያው የሥራቱን የሆነው እሁድ ነበር፡፡ ኢየሱስ ከሞቱት የመጀመሪያ የበኩር ፍሬ ነው (1 ቆሮ 15:23)፡፡ በሦስት ተከታታይ ምሽቶች የእሁድ ኢየሱስ መታየቱ ዛሬ ሽማኖች እሁድ ዕለት እንዲያመልኩ መንሻ ሊሆን ችሏል (ቁ. 19 :26፡ ሉቃ 24ኘ:36፣ ሐዋ 20:7፣ 1ቆሮ 16:2)፡፡

▣ **"መግደላዊት ማርያም"** እየሱስንና ሐዋርያትን አጅበው ከሚጓዙት ሴቶች አንዷ ናት፡፡ በገሊላ ኢየሱስ ከአጋንንት እስራት ላይ አውጥቶአት ነበር (ማር 16፡9 እና ሉቃ 8:2)፡፡ በስቅለቱም 216 ነበረች ኢየሱስ ሲሰቀል ነበረች፡፡ 19፡25 ላይ ማብ ይመ፡፡

ምንም እንኳን የዮሐንስ ወንጌል ማርያም የመጣችበትን ዓላማ ባይገልጥም ማር 16፡1 እና ሉቃ 23፡56 ላይ ግን በርካታ ሴቶች (ቁ.2) የኢየሱስን አካል በሽቶ ለመቀባት በለዳ እንደመጡ ይገልሉ፡፡ በግልፅ ማየት እንደሚቻለው ዮሴፍግ ኒቆዲሞስ የኢየሱስን አካል መቀባታቸውንወይ አላወቁም አሊያም ተጨማሪ ያስፈልጋልብለው አስበዋል፡፡

▣ *"ገና ጨለማ ሳለ"* እዚህ በግልፅ መናገር የሚቻለው ማርያምና ሌሎች ከቤት ሲመጡ ገና ጨለማ ሳለ ነበር፤ ነገር ግን ሲደርሱ ነግቶ ነበር (ማቴ 28፡1፤ ማር 16፡ 2)፡፡

▣ ***"ድንጋዩም ከመቃብሩ ተፈንቅሎ"*** ይህ መቃብሩ ከተበረበረበት ቦታ "ተወልዷል" ማለት ነው፡፡ ቃል በቃል ሲተረጐም (ይህ በተደ2 ቦዝ አንቀፅ ድርጊቱ መፈፀሙን ያሳያል) (ማቴ 28፡2) ድንጋዩ የተንከባለለው የአይን ምሥክሮች ወደ መቃብሩ ውስጥ ገብተው እንዲያረጋግጡ እንጂ ኢየሱስን ከዚያ ለማውጣት እንዳልሆነ አስተውል፡፡ ምክንያቱም አዲስ አትንሳኤው አካል እንደ ቀደመው ምድራዊ አካሉ የሚወሰን አይደለምና (20፡ 19፤ 26) 20፡2 "እየሮጠችም" ማርያም ኢየሱስ ከመቃብሩ አለመሄዱን ለደቀመዛመርቱ ለመንገር የሔደችው ገና በማለዳው ነበር (ማቴ 28:5)፡፡

▣ ***"ኢየሱስ ይወደው ወደነበረው ወደ ሌላው ደቀመዝሙር"*** መውደድ የማለውን የግሪኩ Pheleo (ፊሎ) ይለዋል፤ ይህም "ወንድማዊ መውደድ (ፍቅር)" የሚል ሀሳብ አለው፡፡ ይሁን አንጂ በብዙሐኑ የግሪክ ቋንቋ (300 ዓ.ዓ - 300 ዓ.ም) አጋቼ (Agapas) ከሚለው ቃል ጋር በተመሳሳይ ይጠቀስ ነበር፡፡ የተጠቀሰው ደቀ መዝሙር የወንጌሉ ፀሐፊ ዮሐንስን ይመስላል (ቁ 4-8 እና 13፡ 23 (23))፡፡ በዚህ ሥፍራ ከጴጥሮስ ጋር ተያይዞ ተጠቅሷል፡፡

▣ ***"ጌታን ወስዶበታል"*** ይህ በግሪኩ በላፊ ጊዜ ድርጊቱ መፈፀሙን የሚያመለክት አድራጊ ግስን አመልካች ነው፡፡ ኢየሱስ ሔዷል፡፡ በማርያም አእምሮ "እነርሱ" የሚለው የሚያመለክተው የአይሁድ መሪዎችን ነው፡፡ በግልፅ መናገር የሚቻለው በላይኛው ደርብ ላይ የነበሩት ሐዋርያትና ደቀመዛመርት በትንሳኤው ምክንያት መደነቅ ሞልቶባቸው ነበር፡፡

▣ ***"እኛ"*** ይህ የሚጠቃልለው መግደላዊት ማርያም፡-የያዕቆብእናት ማርያም፣ ሰሎሜ፣ ዮሐና እና ሌሎች ሴቶችን ነው (ማቴ 28:1፤ ማር 16:1፤ ሉቃ 24:10)፡፡

20:4 ***"ሌላው ደቀመክሙርም ከጴጥሮስ ፈጥኖ ወደፊት ሮጠና አስቀድሞ ከመቃብሩ ደረሰ"*** ዮሐንስ ምናልባት ሁሉ በእድሜ ታናሽ ሳይሆን አይቀርም (ባህል)፡፡

20:5 ***"ዝቅም ብሎ ቢመለከት"*** ይህ ቃል በቃል ሲተረጐም "አጨንቁሮ ማየት" ማለት ነው፡ በዚህም ምክንያት በማለዳው ብርሐንና በጨለመው መቃብር መካከል ተቃርግ ስለነበር ነው፡፡

▣ ***"የተልባ እግሩ ልብስ ተቀምጦ"*** የመጠቅለያው ጨርቅ የት እና እንዴት እንደተቀመጠ በግሪኩ ጥቅስ ተለይቶ አልተጠቀሰም፡፡ የኢየሱስ አካል ተሠርቆ ቢሆን ኖሮ መጠቅለያውም አብሮት ይሄድ ነበር ምክንያቱም ሽቶው የመጣበቅ ባሕሪ ስለነበረው ነው፡፡

20:6 ***"ስምዖን ጴጥሮስም"*** ስምዖን (ኬፋ) የዕብራይስጥ (አረማይክ) ስሙ ነበር፤ ጴጥሮስ (ፔትሮስ) በኢየሱስ የተሰጠው የግሪክ ስያሜው ነው፡፡ በግሪክ ትርጓሜው "የተለየ ድንጋይ ወይም ትልቅ ቋጥኝ" ማለት ነው (ማቴ.16:18)፡፡ በአረማይክ ቋንቋ ፔትሮስ በሚለው እና ፔትራ በሚለው መካከል ምንም ልዩነት የለም፡፡

20:7 ***"በራሱ የነበረውን ጨርቅ"*** ፊቱ የተጠቀለለው በሌላ ልብስ ነበር (11:44)፡፡ ይህም ጨርቅ ያገለግል የነበረው (1) ፊትን ለመሸፈን (2) ፊትን ለመጠምጠም (NJB) ወይም (3) መንጋጋውን በሥፍራው ለማሠር (TEV) ነው፡፡

▣ "ለብቻው በአንድ ሥፍራ ተጠምጥሞ እንደነበረ" በአንድ ሰው አማካኝነት የተለያ ጥንቃቄ መደረጉን የሚያሳይ ቦዝ አንቀጽ ነው፡፡ ይህ ነበር እንግዲህ የዮሐንስን ትኩረት የሳበው እና እንዲያምን ያደረገው (ቁ.8)፡፡

20:8 ***"እየም፡ አመነም"*** ዮሐንስ የተገለጠ (የተጨበጠ) ማስረጃ ስለአየ ኢየሱስ ሕያው እንደሆነ አመነ! ወይስ አምኗል (ቁ.11 እና 19)? በትንሣኤው ማመን ወሳኝ የሆነ ሥነ መለኮታዊ ጉዳይ ነው፡፡

1. ሮሜ 10:9-13
2. 1ኛ ቆሮ.15

1ኛ ቆሮ. 15:12-29 የኢየሱስ ትንሣኤ ከሌለ ሊከተል ስለሚችለው ውጤት ጥሩ የሆነ ማጠቃለያን ይሰጣል! ትንሣኤው (*kerygma*) የቀደሙት ሐዋሪያት ስብከቶች ማዕከላዊ እውነት ነበር፡፡ በ5:39 ላይ ያለውን ተጨማሪ የጥናት ርዕሱን ይመልከቱ፡፡

20:9 "*የመጽሐፉን ቃል ገና አላወቁም ነበርና*" ይህ በጸሐፊው የተሰጠ ሌላው አስተያየት ነው፡፡ ጴጥሮስ በሐዋ.2:27 ላይ በበዓለ አምሳ ቀን የጠቀሰውን መዝሙር 16:10ን ምናልባት ሊያመለክት ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ ኢሳያስ 53 ወይም ሆሴዕ 6:2ን ሊያመለክትም ይችላል፡፡ ደቀ መዛሙርት ሳያውቁ የአይሁድ ሽማግሌዎች ኢየሱስ ስለመነሣቱ አስቀድሞ የተናገረውን (ማቴ.27:62-66) ያውቁ ነበር፤ ምን ዓይነት ምጸታዊ አነጋገር ነው!

ይህ ጥቅስ ምናልባት ለሥነ መለኮት አንጻር የሚያጠናክረው እውነት መንፈስ ቅዱስ በሙላት በደቀ መዛሙርቱ ላይ እንዳልመጣ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ አንድ ጊዜ ከተሰጠ አማኞች የኢየሱስን ቃል እና ሥራውን እንዲረዱ ያስችላቸዋል (2:22፤14:26)፡፡

20:10 ይህ ለማለት የተፈለገው ምናልባት (1) ወደ ገሊላ መመለሳቸውን (ማቴ.20:37፤28:7፤10:16፤ዮሐ.21 ደግሞ በገሊላ ባሕር ዓሣ ሲያጠምዱ ይገልጻቸዋል) ወይም (2) በኢየሩሳሌም ለእነርሱ ወደ ተለየ ሥፍራ መመለሳቸውን ነው፡፡ የድህረ ትንሣኤው ልምምዶች የተከናወኑት በላይኛው ደርብ ላይ ስለነበር ሁለተኛው አማራጭ ሊሆን የሚችል ነው፡፡

> NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 20:11-18
> [11]*ማርያም ግን እያለቀሰች ከመቃብሩ በስተ ውጭ ቆማ ነበር። ስታለቅስም ወደ መቃብር ዝቅ ብላ ተመለከተች፤* [12]*ሁለት መላእክትም ነጭ ልብስ ለብሰው የኢየሱስ ሥጋ ተንቶበት በነበረው አንዱ በራስጌ ሌላውም በእግርጌ ተቀምጠው አየች።* [13]*እነርሱም፦ አንቺ ሴት: ስለ ምን ታለቅሻለሽ? አሉአት። እርስዋም፦ ጌታዬን ወስደውታል ወዴትም እንዳኖሩት አላውቅም አለቻቸው።* [14]*ይህንም ብላ ወደ ኋላ ዘወር ስትል ኢየሱስን ቆሞ አየችው፤ ኢየሱስም እንደሆነ አላወቀችም።* [15]*ኢየሱስም፦ አንቺ ሴት: ስለምን ታለቅሻለሽ? ማንንስ ትፈልጊያለሽ? አላት። እርስዋም የአትክልት ጠባቂ መስሎአት፦ ጌታ ሆይ: አንተ ወስደኸው እንደሆንህ ወዴት እንዳኖርኸው ንገረኝ እኔም እወስደዋለሁ አለችው።* [16]*ኢየሱስም፦ ማርያም አላት። ርስዋ ዘወር ብላ በዕብራይስጥ፦ ረቡኒ አለችው፤ ትርጓሜውም፦ መምህር ሆይ ማለት ነው።* [17]*ኢየሱስም፦ ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ፤ ነገር ግን ወደ ወንድሞቼ ሄደሽ፦ እኔ ወደ አባቴ እና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬ እና ወደ አምላካችሁም ዐርጋለሁ ብለሽ ንገሪአቸው አላት።* [18]*መግደላዊት ማርያም መጥታ ጌታን እንዳየች ይህንም እንዳላት ለደቀ መዛሙርቱ ነገረች።*

20:11 "*እያለቀሰች*" ይህ ቃል በቃል "ድምፅን ከፍ አድርጎ ማልቀስ"ን ያመለክታል (11:31)፡፡ ያልተጠናቀቀ እና በኃላፊ ጊዜ የተነገረ ነው፤ የምስራቃውያን የቀብር ልማዶች በስሜታዊነት የሚታወቁ ናቸው፡፡

20:12 "*ሁለት መላእክት*" ሁለት መላእክት እንደነበሩ ዮሐንስ እና ሉቃስ (24፡23) ይስማሙበታል፡፡ ብዙውን ጊዜ ከሁሉም ነገሮች ሁለቱን የሚጠቅሰው ማቴዎስ (8፡28፤9፡27፤20፡30) አንድ መላእክን ይገልጻል! ይህ እንግዲህ በወንጌላት መካከል ለማስረዳት አስቸጋሪ የሆነው ልዩነት ነው፡፡

*ወንጌላት ከራሳቸው ሥነ መለኮታዊ ዓላማ እና ትኩረት አድርገው ከጸፉላቸው የምልእክቱ ተቀባዮች አንጻር የተመረጡ፣ የሚስማሙ እንዲሁም የተጣመሩ እና ኢየሱስ የተናገራቸው እና የሠራቸው ሥራዎቹ የተሰባሰቡበት የዓይን ምስክሮች ናቸው፡፡ በዘመናችን ያሉ አንባብያን ብዙውን ጊዜ እንዲህ ዓይነት ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ፤*

(1) *ከታሪክ አንፃር ትክክል የሆነው የትኛው ወንጌል ነው?*
(2) *በመንፈስ ቅዱስ ምሪት በጸሐፊው ከተጠቀሰው የበለጠ ስለ አንድ ነገር ክስተት ወይም ትምህርት እንዲሁም ታሪካዊ ዝርዝሮችን እና ትንታኔዎችን ሲፈልጉ ይታያሉ፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች መጀመሪያ መፈለግ ያለባቸው በአንድ የወንጌል መልእክት ውስጥ የመጀመሪያውን ጸሐፊ ዋና ሃሳብ ነው፡፡ ወንጌልን ለመረዳት ይህን ያህል ታሪካዊ ዝርዝር ነገሮች አያስፈልጉንም፡፡*

▣ "*ነጭ ልብስ ለብሰው*" *መንፈሳዊው ዓለም ወይም መንፈሳዊ አካላት የተገለጡት ነጭ ለብሰው ነበር፤*

1. *ኢየሱስ በተራራው ላይ ሲለወጥ የለበሰው ልብስ፦ ማቴ.*17:2፤ *ማር.*9:3፤ *ሉቃ.*9:29፡፡
2. *ኢየሱስ የተቀበረበት መቃብር፡ ማቴ.*28:3፤ *ማር.*16:5፤ *ሉቃ.*24:4፤ *ዮሐ.*20:12፡
3. *መላእክት ኢየሱስ ሲያርግ የሐዋ.*1:10
4. *ቅዱሳን ከከበረው ክርስቶስ ጋር፤ ራዕ.*3:4-5፤18
5. *ሽማግሌዎች (መላዕክት) በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ፡ ራዕ.*4:4
6. *ሰማዕታት በእግዚአብሔር ዙፋን ሥር፡ ራዕ.*6:1
7. *የተቤዡት ሁሉ፡ ራዕ.*7:9፣ 13-14 (*ዳን.*12:10)
8. *የሠማይ ሠራዊት (መላዕክት) በሰማይ፡ ራዕ.*19:14
9. *ለይቅርታ የብሉይ ኪዳን ምሳሌ፡ መዝ.*51:7፤*ኢሳ.*1:18 *የእግዚአብሔር ይቅርታ፤*

20:14 **"ኢየሱስም እንደሆነ አላወቀችም"** መግደላዊት ማርያም ኢየሱስን አላየችውም ነበር፡፡ ለዚህ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮች

1. በአይኖቻቸው እምባ ነበር፡፡
2. ታይ የነበረው ከቸለማው ወደ ብርሃኑ ነው፡፡
3. የኢየሱስ መልክ በመጠኑ የተለየ ነበር (ማቴ.28:17፤ሉቃ.24:16፣37)፡፡

20:15 **"ጌታዬ"** ይህ *kurios* (ኩሪዮስ) የሚለው የግሪክ ቃል ነው፡፡ በዚህ ሥፍራ ላይ የተጠቀሰው ሥነ መለኮታዊ ባልሆነ ትርጉም ነበር (12፡21)፡፡ ሊኖረው የሚችለው ትርጉም "ጌታ"፣ "አቶ"፣ "ባለቤት"፣ "ባል" ወይም "ጌታ" ነው፡፡ ማርያም እየተናገረች ያለችው የመሰላት (1) አትክልት ጠባቂ (2) የአትክልት ባለቤት ነገር ግን በ20፡28 ላይ ሥነ መለኮታዊ አጠቃቀሙን ተመልከት፡፡

▣ **"ከ…."** ከተናጋሪው ሐሳብ አንፃር እውነት ነው ተብሎ የሚገመት አንደኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ነው፡፡ አንድ ሰው ወስዶታል ብላ አምናለች፡፡

20:16 **"ማርያም…..ረቡኒ"** ማርያም የሚለው ቃል በቃል ሚርያም ማለት ነው፡፡ እነዚህ ሁለቱም ቃላት አረማይክ ናቸው (‹እብራይስጥ› ማለት አረማይክ ነው 5:2፤19:13፤17:20)፡ በግልጽ እንደሚታየው ኢየሱስ ስሟን የጠራው ለየት ባለ ሁኔታ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ድርጊት ከኤማሁስ መንገደኞች ጋር አብሮ ሲጸልይ ሳያደርገው አልቀረም (ሉቃ.24፡30-31)፡፡ "ረቡኒ" የሚለው መጨረሻ ያለችው "እኔ"፡- "የኔ ረቡኒ"፣ "የኔ ጌታ"፣ ወይም "የኔ መምህር" የሚል አንደምታ አላት፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ የኢየሱስ ድህረ-ትንሣኤ መልኮች/ግጽታዎች**

ኢየሱስ ትንሣኤውን ለማረጋገጥ ራሱን ለበርካታ ሰዎች አሳይቷል፡፡

1. በመቃብሩ አጠገብ ለነበሩት ሴቶች ማቴ.28፡29
2. አሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት፡ ማቴ.28፡16
3. ስምዖን፡ ሉቃ. 24፡34
4. ሁለት ሰዎች፡ ሉቃ.24፡15
5. ደቀ መዛሙርት፡ ሉቃ.24፡36
6. መግደላዊት ማርያም፡ ዮሐ.20፡15
7. አሥር ደቀ መዛሙርት፡ ዮሐ.20፡17
8. አሥራ አንድ ደቀ መዛሙርት ዮሐ.20፡26
9. ሰባት ደቀ መዛሙርት፡ ዮሐ.21፡1
10. ኬፋ (ጴጥሮስ) 1ኛ ቆሮ.15፡5
11. አሥራ ሁለቱ (ሐዋርያት) 1ኛ ቆሮ.15፡5
12. 500 ወንድሞች፡ 1ኛ ቆሮ.15፡6 (ማቴ.28፡16-17)
13. ያዕቆብ (ምድራዊ ቤተሰቡ)፤ 1ኛ ቆሮ.15፡7
14. ሐዋርያት ሁሉም 1ኛ ቆሮ.15፡7
15. ጳውሎስ 1ኛ ቆሮ.15፡8 (ሐዋ.9)

አንዳንዶች መልኮች ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ኢየሱስ የፈለገው ነገር በእርግጥ ሕያው መሆኑን እንዲያቁ ነበር፡፡

20:17

| | |
|---|---|
| NASB | **"አትንኪኝ"** |
| NKJV | **"አትጠማጠሚ"** |
| NRSV | **"አትያዢኝ"** |
| TEV | **"አትያዢኝ"** |
| NJB | **"አትጠማጠሚ"** |

የKJV ትርጉም "አትንኪኝ" የሚል ትርጓሜ አለው፡- ይህ ትእዛዝ አዘል መካከለኛ ግሥ ሲሆን ከአሉታዊ ቦዝ አንቀፅ ጋር ሲጣመር በሒደት ላይ ያለን ድንገት ማቆም ማለት ነው፡፡ ማርያም አጥብቃ ይዛዋለች ከእርገት በፊት የኢየሱስን አካል መንካት ምንም ዓይነት ሥነ-መለኮታዊ እሳቤ የለውም፡፡ በዮሐንስ 20:26 ላይ የቶማስ እንዲነካው ሲፈቅድለት እንዲሁም በማቴ 28:9 ላይ ሴቶች እግሩን እንዲነኩት ሲፈቅድላቸው ይታያልና፡፡

▣ **"ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና"**ይህ የድርጊት መጠናቀቅን የሚያመለክት ነው፡፡ ከትንሳኤው በኋላ 40 ቀን እስኪሞላው ድረስ (ሐዋ 1:9) ወደ ሰይ አያርግም፡፡

▣ *"ወደ ወንድሞቼ ሂደሽ"* በትንሣኤ የከበረው ጌታ ከነዚህ እጅግ የፈሩ ሰዎችን "ወንድሞቼ" ብሎ ይጠራቸዋል (ማቴ 12:50)፡፡

▣ *"እርጋለሁ"* ይህ የአሁን ጊዜ አመልካች ነው፡፡ ይህ በመካከላቸው ሳለ 40 ቀናት እስኪሞላው ድረስ የተፈፀመ አልነበረም (ሉቃ 24:50-52 ሐዋ 1:2-3)፡፡ ዮሐንስ ባለማቋረጥ የደዋሊዝምን ቀጤ ሁለትዮሽን "ላይ" እና "ታች" እያለ ይጠቀማል፡፡ ኢየሱስ ከአብ ዘንድ የነበረ (ከፍጥረት በፊት) ሲሆን ወደ አባቱም ይመለሳል (መክበር)፡፡

▣ *"ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ"* እንዴት ግሩም የሆነ አባባል ነው! ይሁን እንጂ የአማኞች ልጅነትና የኢየሱስ ልጅነት እኩል መሆናቸውን ይህ እንደማያመለክት መታወቅ አለበት፡፡ እርሱ ፍፁም አምላክና ፍፁም ሰው የሆነ የእግዚአብሔር ልጅ (3:16) ነው፡፡ አማኞች የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል የሚሆኑት በእርሱ ብቻ ነው፡፡ እርሱ ጌታና አዳኝ እንዲሁም ወንድም ነው!

20:18 ማርያምም እንዲሁም ምስክር ነች!

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 20:19-23

**[19]*ያም ቀን እርሱም ከሳምንቱ ፊተኛው በመሸ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ተሰብስበው በነበሩበት አይሁድን ስላፈሩ ደጆቹ ተዘግተው ሳሉ÷ ኢየሱስ መጣ፤ በመካከላቸውም ቆሞ፡- ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው፡፡ [20]ይህንም ብሎ እጆቹንም ጎኑንም አሳያቸው፡፡ ደቀ መዛሙርቱም ጌታን ባዩ ጊዜ ደስ አላቸው፡፡ [21]ኢየሱስም ዳግማኛ፡- ሰላም ለእናንተ ይሁን፤ አብ እንደላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ አላቸው፡፡ [22]ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና፡- መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፡፡ [23]ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው፡፡***

20:19 *"በመሸ ጊዜ"* የአይሁድ የጊዜ የቆጣጠር የሚጀምረውና የሚያበቃው እኩለ ሌሊት ላይ ሲሆን (ዘፍ 1:5) እዚህ ላይ እሁድ ከምሽቱ 12፡00  ሰዓት አካባቢ ነው፡፡

▣ *"ከሳምንቱ ፊተኛው ቀን"* ልክ እንደኛው ሰኞ ዕለት ቅዳሜ የሳምንቱ የመጀመሪያው የሥራ ቀን ነው፡፡ ይህም የኢየሱስን ትንሣኤ ለማክበር/ለማስታወስ ቤተክርስቲያን የምስባሰብብት ቀን ሆኗል፡፡ የዚህንም ንድፍ ያወጣው ራሱ ኢየሱስ ሲሆን ለሦስት ተከታታይ ምሽሮች በላይኛው ደርብ ላይ ራሱን ገልጧል (ቁ19:26 ሉቃ 24:36፡ ሐዋ 20:7/ ቆሮ 16:2)፡፡

*የመጀመሪያው ትውልድ አማኞች በሰንበት ቀን በየአካባቢው ባሉ ምኩራቦች እና በቤመቅደስ በበዓላት ቀናት መሰባሰባቸውን ቀጥለው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ረቢዎች የምኩራብ አባላት ኢየሱስን እንደ መሲህ እንዳይቀበሉ የሚል "የእርግማን መሐላ" የሚል መሥፈርት አመጡ (ከ70 ዓ.ም በኋላ) በዚህ ጊዜ ነው የሰንበት አገልግሎቶችን ለመተው የመረጡት፣ ነገር ግን አይሁድን የትንሣኤው ቀን መሆኑን ለማሰብ ከሌሎች አማኞች ጋር እሁድ እለት መሰብሰባቸውን ቀጠሉ፡፡*

▣ *"ደይቅ ተዘግተው ሣሉ"* ይህ በተደረገ ግሥ ድርጊቱ መጠናቀቁን የሚያሳይ ቦዝ አንቀጽ ነው፡፡ ብዙ ቁጥሮቹ የሚያመለክቱት ከላይና ከታች ያሉ በሮች ሁለቱም መዘጋታቸውን ነው፡፡ ይህም የተጠቀሰው (1) የኢየሱስን መታየት (መስክ) ለማጉላት ወይም (2) ደቀመዛሙርቱ እንዳይያዙ መፍራታቸውን ለማሣየት፡፡

▣ *"ደቀመዛሙርቱ"* ቶማስ አልነበረም፡፡ ከአስራ አንዱ ደቀመዛሙርት በተጨማሪ ሌሎች ነበሩ (ሉቃ 24:33)፡፡

▣ *"ሰላም ለእናንተ ይሁን"* ይህ የሚያሳየው የእነርሱን መደነቅ ምናልባትም መፍራታቸውን ነው፡፡ ኢየሱስ ሰላም እንደሚሰጣቸው ተስፋ ሰጥቷቸዋል (14:27፤ 16:39)፡፡ ይህ ምናልባት የሚያሳየው ሻሎም (*Shalom*) የተባውን የአየሁድ ሠላምታን ነው ኢየሱስም ይህን ሦስት ጊዜ ደጋገመው (ቁ. 19:21:26)፡፡

20:20 *"እጆቹንም ጐኖቹንም አሳያቸው"* ዮሐንስ ከሌሎች ወንጌላት ይልቅ የኢየሱስን ጐን መወጋት ትኩረት ማድረጉ በገልፅ ይታያል (19:37፤ 20:25)፡፡ በሉቃ 24:39 እና 20:16 ካልሆነ በስተቀር እግሮቹ አልተጠቀሱም የኢየሱስ የከበረ አካል የመስቀሉን ምልክት /አሻራ/ ያስታውሳል (1 ቆሮ 1:23 ገላ 3:1)፡፡

▣ *"ጌታን"* ይህ መጠሪያ በዚች ስፋራ የጠቀሰው ያህዌህ ከሚለው የብሉይ ኪዳን መጠሪያ በሙሉ ሠነ-መለኮታዊ ትርጓሜው ነው (ዘፀ 3:14)፡፡ በብሉይ ኪዳን ለእግዚአብሔር አብ የተሰጠውን ለኢየሱስ መጠቀማቸው የአዲስ ኪዳን ፀሐፊዎች የኢየሱስን ፍፁም አምላክነት ማመናቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ በ3:19 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

20:21 **"አብ እንደላከኝ"** ይህ የድርጊት መጠናቀቅን አመልካች ነው (27:8) ፡፡ በቤተክርስቲያን መለኮታዊ ትእዛዝ አላት (ማቴ 28:20 ሉቃ 24:47፤ ሐዋ 1:8)፡፡ አማኞች የሰጣቸውን ተልእኮ አስቀድሞ ዋጋ በተከፈለበት ተልእኮ ላይ ነው (2ቆሮ 5:14-15/ ዮሐ 3:16)፡፡

"መላክ" ለሚለው ቃል ኢየሱስ ሁለት የተለያዩ ቃላትን ይጠቅሳል፡፡ በዮሐንስ ወንጌል እነዚህ ቃላት ተመሳሳይ ናቸው፤ ይህምበምዕ 8 ላይ በግልፅ የሚታይ ሲሆን Pempo (ፔምፖ) የሚለው ደግመ በ8:42 ላይ መላክ (Apostello) የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

20:22 **" እኛ አለባቸው"** ይህ "እፍ" በሚለው ላይ የተደረገ የቃላት ጨዋታ ነው፡፡ የእብራይስጡ Raach (ሩእክ) እና የግሪኩ PNeuma (አውማ) ያላቸው ትርጉም "ትንፋሽ"፤ "ንፋስ" ወይም "መንፈስ" ማለት ነው፡፡ ይህ ተመሳሳይ ግስ በሰብ ተዋጅንት በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔርን የመፍጠር ሥራ (ዘፍ 2:7) እና የእስራኤልን መታደስ (ሕዝ 375:9) ለመዋቀስ ውሏል፡፡ "እነርሱ" የሚለው ተውላጠ ስም የሚያመለክተው ከሐዋርያት ይልቅ በርከት ላሉ ሰዎች ነው (ሉቃ 24:33) ፡፡

▣ **"በመንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ"** ይህ ድርጊት ፈፃሚ ትእዛዛዊ ግሥ ነው፡፡ ይህ ከመንፈስ ቅዱስ መምጣት ጋር እንዴት ሲገናኝ እንደሚችል ግለፅ አይደለም፡፡ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርት የገባውን ተስፋ ሁሉ መጀመሪያ በታየበት ጊዜ ፈጽሞታል፡፡ ይህ ሁኔታ መንፈስ ኢየሱስን ከጥምቀት በኋላ በአገልግሎት እንዳዘጋጀው ሁሉ ደቀመዛሙርቱንም ለሚመጣው አዲስ የአገልግሎት ተልእኮ ጋር ሊዛመድ የሚችል ነው፡፡
ይህ ጥቅስ የቀደመችው ቤተክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ የሚሰርፀው ከአብ ወይስ ከአብና ከወልድ ነው በሚለው ጥያቄ ላይ ይጠቀስ የነበረ ነው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ሦስቱም የሥላሴ አካላት በመቤዠት ተግባር ውስጥ ተሳትፎ ያደርጋሉ፡፡

ጆርጅ ላይ *A Theology of the New TestameNt* በሚለው መጽሐፋቸው ላይ ለዚህ ክፍል ሊሆኑ የሚችሉ አተረጓጎሞችን በማጠቃለል ያስቀምጣሉ፡፡

"ይህ ምንባብ (ክፍል) መንፈስ ቅዱስ በበዓለ ሃምሳ ቀን ከመምጣቱ አንፃር" ተግዳሮቶችን የሚፈጥር ቢሆንም በሦስት መንገዶች ምናልባት የሚፈታ ይሆናል፡፡ ዮሐንስ ስለ በዓለ ሃምሳ ቀን ስላላወቀ የዮሐንስ በዓለ ሃምሳ እንዲሆን ታሪኩን ለውጦታል፤ ወይም በወቅቱ ሁለት የመንፈስ ስጦታዎች ነበሩ ወይም የኢየሱስ እፍ ማለት በእውነተኛው በዓለ ሃምሳ የተሰጠን ቃል ኪዳን የሚያመለክት እና ተስፋ የሚያደርግ ነው ማለት ነው (ገጽ 289)፡፡
በNET በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በ24ኛው የግርጌ ማስታወሻ ላይ (ገጽ 1965) እንደሚያረጋግጠው ይህ ጥቅስ የሚያሳስበው ዘፍ 2:7ን (Lxx) ነው፡

በዘፍጥረት አካላዊ ሕይወት እንደተሰጠ ሁሉ በአዲስ ኪዳን ደግሞ የዘላለም ሕይወት ተሰጥቷል፡፡ "የእግዚአብሔር እስትንፋስ" የሰጠው ትኩረት ይህቄበመንፈሱ አማካኝነት ለሕዝቡ ተሃድሶን እንዳመጣ ከሚናገረው ከሕዝ መዕ 37 ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡

20:23 **"ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው"** እነዚህ ሁለት የሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ አረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡ ይህ ሁኔታ የሚያጐላው ወንጌልን ከሚሰብኩትና በእምነት ምላሽ በሚሰጡት መካከል ያለውን ግንኙነት ነው፡፡ ወንጌልን የተረዳ አንድ ሰው ወንጌልን ለማካፈል ምርጫው ሲያደርግ በአንፃሩም ደግሞ ሌላው ሰምቶ ለመቀበል ምርጫን ያደርጋል፡፡ ሁለቱም ሁኔታወች አስፈላጊዎች ናቸው፡፡ ይህ ጥቅስ ለተጠሩት ሰዎች የተለየ ሥልጣንን የሚያጐናፅፍ ሳይሆን ለሚመሰክሩት ግን ህይወትን የሚሰጥ ኃይልን ያጐናፅፋቸዋል፡፡ ይህ ስልጣን ኢየሱስ በነበረበት ወቅት ተልእኮ በተሰጣቸው በሰባዎቹ ደቀ መዛሙርት ህይወት ውስጥ የታየ ነው፡፡

▣ **"ኃጢአታቸው ሁሉ ይቀርባቸዋል"** ይህ ሰዋሰዋዊ አወቃቀር ፍፁም ተደርጐ ግሥ አመልካች ነው ተደርጐ ግሱ የሚያመለክተው በወንጌል ስብከት የእግዚአብሐር ይቅርታ በሙሉ በሙሉ የሚገኝ መሆኑን ነው፡፡ የሚጠቀሙበት ከሆነ አማኞች የመንግስተ ሰያት መክፈቻዎች አላቸው (ማቴ 16:19)፡፡ ነገር ግን ይህ ተስፋ ለቤተክርስቲያን እንጂ ለግለሰቦች አይደለም፡፡ ይህም ከሥነ መለኰት አንፃር በማቴ 18:18 ላይ "መሠርና መፍታት ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡"

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 20÷24-25
**[24]ነገር ግን ከአስራ ሁለቱ አንዱ ዲዲሞስ የሚሉት ቶማስ ኢየሱስ በመጣ ጊዜ ከእነርሱ ጋር አልነበረም፡፡ [25]ሌሎቹም ደቀ መዛሙርት፡- ጌታን አይተነዋል አሉት፡፡ እርሱ ግን፡- የችንካሩን ምልክት በእጆቹ ካላየሁ ጣቴንም በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ እጄንም በጐኑ ካላገባሁ አላምንም አላቸው፡፡**

20:24 **"ነገር ግን ከአስራ ሁለቱ አንዱ ዲዲሞስ የሚሉት ቶማስ ኢየሱስ በመጣ ጊዜ ከእነርሱ ጋር አልነበረም"** በግሪክ ዲዲሞስ ማለት "መንትያ" ማለት ነው (11:16)፡፡ ብዙ ጊዜ ይህን ክልል ሰዎች የሚጠቅሱት የቶማስን ተመራማሪነት

ለመግለፅ ነው፡፡ ነገር ግን 11:16ን አስተውኦ ከሌሎች ወንጌላት ይልቅ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ቶማስ በብዛት ተጠቅሷል (11:16፤ 14:35፤ 20:24፤ 26:27፤ 28፤ 29፤ 21፤21)፡፡
20:25 **"ካላ … አላምንም"** "ካላ" የሚለው የሦስተኛ መደብ አረፍተ ነገር ሲሆን ጣምራ አሉታዊ ድባብን ያዘለ ነው፡፡ ካላየሁ እና ካልነካሁ በፍፁም በፍፁም አላምንም ማለት ነው፡፡ኢየሱስም ይህን ጥያቄውን አክብሮ ተቀብሎታል፡፡ ኢየሱስ በደቀ መዛሙርት እምነት ውስጥ የሠራው (1) በተአምራቶቹ እና (2) በትንቢቶቹ ነበር፡፡
የኢየሱስ መልእክት ፍፁም አዲስ ከመሆኑ የተነሳ የወንጌሉን እውነትና አንድምታዎችን ይረዱን ከህይወታቸው ጋር ያዋህዱ ዘንድ ጊዜን ይሰጣቸው ነበር፡፡

▣ **"ምልክት"** ቀጥሎ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ መልክ (TUPOS)**

*Tupos* የሚለው ቃል የተለያዩ አጠቃቀሞች አሉት፡፡

1. Moultoɴ aɴd Milligaɴ. *The Vocabulary of the Greek ɴew Testameɴt* P. 645
   ሀ/ ንድፍ
   ለ/ ዕቅድ
   ሐ/ ዘዴ (የአፃፃፍ)
   መ/ ድንጋጌ
   ሠ/ ፍርድ ወይም ውሣኔ
   ረ/ ለፈዋሽ አምላክ በስዕለት የሚቀርብ የሰው አካል ሞዴል
   ሰ/ የሕግ መመሪያን ለማስገደድ ማስከበርን የሚልፅ ግሥ
2. Louw aɴd ɴida, *Greek Eɴglish Lexicoɴ*, Vol 2. P. 249
   ሀ/ ምልክት (ዮሐ 20÷250)
   ለ/ መልክ (ሐዋ 7÷43)
   ሐ/ አርአያ (ዕብ 8÷5)
   መ/ ምሳሌ (1ቆሮ 10÷6፤ ፊልጵ 3÷17)
   ሠ/ የመጀመሪያው (ሮሜ 5÷14)
   ረ/ ዓይነት (ሐዋ 23÷25)
   ሰ/ ይዘቶች (ሐዋ 23÷25)
3. Harold K. Moultoɴ, *the Aɴalytical Greek Lexicoɴ Revised*, P. 411
   ሀ/ አሻራ፣ ምልክት (ዮሐ 20÷25)
   ለ/ ድንበር መከለል
   ሐ/ መስክ (ሐዋ 7÷43)
   መ/ ቀመር፣ ዘዴ (ሮሜ 6÷17)
   ሠ/ ቅርፅ፣ ፍሬ ነገር (ሐዋ 23÷25)
   ረ/ ምሳሌ (1ቆሮ 10÷6)
   ሰ/ ተስፋ የሚደረግ ምሳሌ ዓይነት (ሮሜ 5÷14፤ 10÷11)
   ሸ/ ሞዴል ንድፍ (ሐዋ 7÷44 ዕብ 8÷5)
   ቀ/ የሞራል ንድፍ (ፊልጵ 3÷17፣ 1ተሰ 1÷17 2ተሰ 3÷9፡ 1ጢሞ 4÷12 1ጴጥ 5÷3) በዚህ ደውድ ቁጥር 1 ከሁሉም የተሻለ ይመስላል፡፡ ወንጌለ አስተምህሮና የህይወት ዘይቤ እሳቤዎች ያሉት ነው፡፡ በክርስቶስ ያለው ነን የድነት ሰጦታ ክርስቶስን የመምሰል ሕይወት የሚጠይቅ ነው፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 20÷26-29

**[26]ከስምንት ቀን በኋላም ደቀ መዛሙርቱ ደጋግመው በውስጥ ነበሩ÷ ቶማስም ከእነርሱ ጋር ነበረ፡፡ ደጆች ተዘግተው ሳሉ ኢየሱስ መጣ፤ በመካከላቸውም ቆሞ፡- ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው፡፡ [27]ከዚያም በኋላ ቶማስን፡- ጣትህን ወደዚህ አምጣና እጆቼን እይ፤ እጅህንም አምጣና በጐኔ አግባው፤ ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን አለው፡፡ [28]ቶማስም፡- ጌታዬ አምላኬም ብሎ መለሰለት፡፡ [29]ኢየሱስም፡- ስለ አየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁአን ናቸው አለው፡፡**

26 **"ከስምንት ቀን በኋላም"** ይህ ሳምንት ለመግለፅ የሚጠቀሙት የእብራይስጥ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው፡፡ ይህ ሌላው የእሁድ ምሽት ነበር፡፡ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ በሦስት ተከታታይ የእሁድ ምሽቶች በላይኛው ደርበ ላይ የታየበት (ምናልባትም በማርቆስ ቤት) ለሚቀጥለው ክርስቲያናዊ አምልኮ መሥራት የተጣለበት ነበር፡፡ ቁ. 193 ይመልከቱ፡፡

26:27 “*ያመንክ እንጂ ያላመንክ አትሁን*” አለው፡፡

20:27 “*ያመንክ እንጂ ያላመንክ አትሁን*” ይህ የአሁን ጊዜ መካከለኛ ትእዛዛዊ እና ቦዝ አንቀፅ ያለው ሲሆን የሚያመለክተውን በሂደት ለይ ያለን ድርጊት ማቆምን ነው፡፡ ሁሉም አማኞች ጥርጣሬና እመነትን ያጣመረ አስገራሚ ማንነት አላቸው፡፡

20:28 ከስነ መለኮት አንፃር ቶማስ እምነቱን መግለጡ ከጡ .17 ጋር የሚገናኝ ነው፡፡ ቶማስ የእምነት አቋሙን የገለጠበት ሁኔታ የብሎይ ኪዳን የኋላ ታሪክ ያለው፣ ይህዌህ ኤሎሂም (ዘፍ 24) አብረው አንድ ላይ ሲጠቀሱ ስሙ “ጌታዬ አምላኬ” ተብሎ ይተረጐማል፡፡ ኢየሱስ ይህንን አምላክነቱን የሚገልጠውን አጠራር ሙሉ በሙሉ ተቀብሎታል፡፡ የዮሐንስ ወንጌል ምዕ 1 ቁ.1 የናዝሬቱ ኢየሱስን አምላክነት የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ኢየሱስ አምላክነቱንም በዮሐንስ በርካታ ጊዜያት ጠቅሷል (8:58፣ 10:30፣ 14:9፣ 20:28) እንዲሁም ሐዋርያትም ይህንኑ ያረጋግጣሉ (ሐዋ 20:28፣ ሮሜ 9:5 ፊልጵ 2:6-7 ቆላ 1: 15-17፣ 2ተሰ 1:12፣ ቲቶ 2:13 ዕብ 1:18 2 ጴጥ 1:11 1ዮሐ 5:20)፡፡

20:29 ይህ የመክፈቻ ሐረግ ዓረፍተ ነገር ወይም “አዎን” የሚል ምላሽ ሊኖረው የሚችል ጥያቄ ሊሆን ይችላል፡፡ ሰዋሰዋዊ አወቃቀሩ ግልፅ አይደለም፣ ይህም በ17:20 ላይ ካለው የባርኮች ንግግር ጋር ተመሳሳይ ነው (1 ጴጥ 1:8)፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 20÷30-31

**30ኢየሱስም በዚህ መጽሐፍ ያልተፃፈ ሌላ ብዙ ምልክት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ፣ 31ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተፅፎአል፡፡**

*ካሮስ ኤፍ ኤች ሔንሪ* the *Expositor's Bible CommeNtary (ቅፅ 1) ባለው 'The Authrotty aNd INspiratioN of the Bible""* በሚለው የመግቢያ ፅሑፉ ርእስ ላይ እንዲህ ይላል፡፡

“የኢየሱስን ሥጋ መልበስ ጨምሮ በፍጥረትም ይሁን በድንነት ታሪክ መጽሐፍ ቅዱስ ክስተቶችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ዓላማው አይደለም፡፡ ነገር ግን የተጠቀሱት መፍሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች ለሰው ልጅ አፈስፈላጊ የሆነውን በቂ የመዳን መንገድን ማሳየት ነው፡፡ ምንም እንኳን የመጽሐፍ ቅዱስ ፀሐፊወች አንድን የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ከተያየ አቅጣጫዎች እና ዓላማ አንፃር አንዳንድ ጊዜ የሚያዩት ቢሆንም የሚያስተላልፉት መልእክት ግን አስተማማኝና በቂ ነው ማቴዎስ አብዛኛውን የኢየሱስ አግልግሎት ለትምህርት ያመች ዘንድ ርዕሳዊ በሆነ ሁኔታ አዋቅሮታል፡፡ ሉቃስ ደግሞ በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ያለውን ነገር የኃይማኖት ማስተማሪያ መፅሐፍ (ትምህርትን)” በሚገድብ መልኩና ሥርዓት ባው ሁኔታ ታሪኩን ይዘግባል (1:4)፡፡ የዮሐንስ ወነጌል በግልፅ የሚያብራራው አራተኛውን ወንጌል የተመሠረተበትን የለውጥ ፈላጊ አቋንም ማሳየት ነው (20:30፣31)” (ገጽ 27-28)፡፡

- “**ሌላ ብዙ ምልክት በደቀመዛሙርቱ ፊት አደረገ**” እነዚህን “ምልክቶች” በበርካታ መንገዶች መረዳት ይችላል፡፡
    1. እርሱ በእርግጥ ሕያው እንደነበር የሚያሳዩ ምልክቶች
       ሀ/ የችንካሩን ምልክት በእጆቻቸው መንካታቸው
       ለ/ ከእነርሱ ጋር አብሮ ብላቱ (ሉቃ 24:43)
    2. ለየት ያሉና ያስመዘገቡ ምልክቶችን በፊታቸው ማድረጉ
    3. ወንጌላትን እንዲዘግቡ ለማዘጋጀት ይችል ዘንድ የሕይወት ሥራውን ለመግለጥ (ባለፈው ላይ ትኩረት ማድረግ)

20:31

NASB, NKJV “*ታምኑ ዘንድ*”
TEV, NJB
NRSV “*መጥታችሁ ታምኑ ዘንድ*”

አንዳንድ ቀደምት የግሪክ ምንጮች $P^{66}$፣ N,B እና ኦሪገን የጠቀሳቸው የግሪክ ጥቅሶች የዮሐንስ ወንጌል የተፃፈው አማኞች በእምነታቸው እየረቱ እንዲሄዱ መሆኑን የሚያመለክት የአሁን ጊዜ ሁኔታ አመልካች አገላለን አለው፡፡

ሌሎች የግሪክ ምንጮች (SV2፣ A፣C፣ D፣ L፣ N፣ W) ዮሐንስ ወንጌሉን የፃፈው ለማያምኑት መሆኑን የሚያመላክት ስሜት ገላጭ ግሥ አላቸው፡፡ ለዚህም $UBS^4$ የኃላፊ ጊዜ ድርሰት አመልካች ግስን P”C”ደረጃን ይሰጠዋል (ለመወሰን የሚያስቸግር ደረጃ ማለት ነው) ይህ ጥቅስ በዮሐንስ ወንጌል የተገለጠው ዓላማ ነው፡፡ ዮሐንስ እንደሌሎች ወንጌላት ሁሉ የወንጌል ትራክት ነው ማለት ይቻላል፡፡

“ክርስቶስ” ይህ “መሲህ” ለሚለው የእብራይስጡ ቃል የግሪኩ ትርጓሜ ሲሆን ቃል በቃል “የተቀባው” ማለት ነው፡፡ ይህ የዳዊት ዘር የሆነውና አዲሱን የጽድቅ ሕይወት እንደሚያመጣ በብሉይ ኪዳን ትንቢት የተገነገረለት ነው፣ የናዝሬቱ ኢየሱስ (1:45) የአይሁድ መሲህ ነው (1:45)፡፡

ይህ ለኢየሱስ የተሰጠው ማዕረግ በቀደመው የወንጌሉ ክፍል ይገኛል (1:41) ይሁን እንጂ “መሴህ” ሳይሆን “ጌታ” የሚለው ማዕረግ ኢየሱስ በአህዛብ ዓውድ የተጠቀሰበት ማዕረግ ነው (ሮሜ 10:9-13፣ ፊልጵ 2:9-11)፡፡

“መሲህ” ለሚለው ሃሳብ ስነ ፍፃሜያዊ አንደምታዎች የነበረው

1. ለፈሪሳውያን - ፖለቲካዊና ብሔራዊ ተስፋዎች
2. ራዕይነህ /ትንቢታዊ ለሆኑ የአየሁዳዊያን ስነ ፅሑፍ ፋሲካዊ፤ አለም አቀፋዊ ተስፋዎች

▣ **"የእግዚአብሔር ልጅ"** ይህ ማዕረግ በወንጌላት ውስጥ በጥቂቱ የተጠቀሰ ቢሆንም (ምናልባት አህዛብ ሲረዱት ባለመቻላቸው ምክንያት) በዮሐንስ ወንጌል ግን ቀደም ብሎ ተጠቅሷል (1:14፡34፤49)፡፡ ኢየሱስና አብ የነበራቸውን አስደናቂ ግንኙነት ዮሐንስ የገለጠበት ሁኔታ ነበር Lhuios የሚለውን ቃል ይጠቀማል፡፡ ዮሐንስ ይህን ቁርኝትን የሚያሳይ ዘይቤን በበርካታ መንገዶች ይገልፀዋል፡፡

1. ማዕረግ
2. "አንጾኪያ ልጅ" ከሚለው ጋር አያይዞ (MoNogeNes፤ 1:18/ 3-16፤ 1ዮሐ 4:9 )
3. "አብ" ከሚለው ማዕረግ ጋር በማጣመር (20:17)

በ1ዮሐ 3:8 ላይ የእግዚአብሐር ልጅ የሚለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ሊሆን የሚችል ማብራሪያ በመሆኑ ለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጐም ኃላፊነት አለብህ፡፡ እያንዳንዳችን ልንሔድ የሚገባን ባለን መረዳት መጠን ነው፡፡ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጐም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣችሁ ናችሁ፤ በመሆኑም ይህንን በሚያብራራው ሰው ላይ ብቻ ልትተው የሚገባ አይደለም፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ባሉት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ በጥሞና እንድታስቡበት ለመረዳት ይቻል ዘንድ ነው፤ በመሆኑም ጥያቄዎቹ እንደ ሐሳብ - አነሳሽ ሆነው እንጂ በግልፅ ወይም በቀጥታ አይደለም፡፡

1. ወደ መቃብሩ የመጣው ማን ነበር? መቼ? ለምን?
2. ደቀመዛሙርት ትንሣኤውን ያልተጠባበቁት ለምን? ነበር የጠበቀው ሰው ነበር ?
3. ማርያም ኢየሱስን ልትለየው ያልቻለችው ለምን ነበር?
4. ኢየሱስ ማርያምን አትንኪኝ ያላት ለምንድነው?
5. ቁ. 22-23ን በራስህ አባባል ግለፃቸው?
6. ቶማስን ተጠራጣሪ ማለት ተገቢ ነውን?
7. እኛ ባለንበት ዘመን ሳይሆን ኢየሱስ በነበረበት ዘመን "ማመን" የሚለውን ቃል አብራራው፡፡ ?

# ዮሐንስ ምዕራፍ 21

# የተሻሻሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች አንቀፅ አከፋፈል

| UBS[4] | NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| ኢየሱስ ለሰባቱ ደቀመዛሙርት ተገለጠ | ደቀመዛሙርት በባህሩ ዳርቻ ቁርስ በሉ | ቀጣይ | ኢየሱስ ለሰባት ደቀመዛሙርት ተገለጠ | በጥብርያስ ባህር ዳርቻ የሆነው መገለጥ |
| 21:1-14 | 21:1-14 | 21:1-3 | 21:1-3ሀ | 21:1-3 |
| | | | 21:1-3ለ-5ሀ | |
| | | 21:4-8 | | 21:4-8 |
| | | | 21:5ለ | |
| | | | 21:6 | |
| | | | 21:7-10 | |
| | | 21:9-14 | | 21:9-14 |
| | | | 21:11-14 | |
| ኢየሱስና ጴጥሮስ | ኢየሱስ ጴጥሮስን አጸናው | | ኢየሱስና ጴጥሮስ | |
| 21:15-19 | 21:15-19 | 21:15-19 | 21:15ሀ | 21:15-19 |
| | | | 21:15ለ | |
| | | | 21:15ሐ-16ሀ | |
| | | | 21:16ለ | |
| | | | 21:16ሐ-17ሀ | |
| | | | 21:17ለ | |
| | | | 21:17ሐ-19 | |
| ኢየሱስና የተወደደው ደቀ መዝሙር | የተወደደው ደቀ መዝሙርና የእርሱ መጽሐፍ | | ኢየሱስና ሌላው ደቀ መዝሙር | |
| 21:20-23 | 21:20-25 | 21:20-23 | 21:20-21 | 21:20-23 |
| | | | 21:22 | |
| | | | 21:23 | ሁለተኛ ማጠቃለያ |
| 21:24 | | 21:24025 | 21:24 | 21:24 |
| | | | ማጠቃለያ | |
| 21:25 | | | 21:25 | 21:25 |

**ሦስተኛ የምንባብ ዑደት (አንቀ 53 ይመ)**
***በአንቀፅ ደረጃ የመጀመሪያውን ፀሐፊ ዋና ሐሳብ መከተል***

*ይህ የጥናት መመሪያ ሊሆን የሚችል ማብራሪ በመሆኑ ለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ፡፡ እያንዳንዳችን መጓዝ ያለብን ባለን መረዳት መጠን ሊሆን ይገባል፡፡ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጎም ወቅት ቅድምያ የሚሰጣቸው ናቸው፡፡ ይህንን ጉዳይ በሚያብራራው ሰው ላይ መተው የለብም፡፡*

*ምዕራፉን በአንድ ቁጭታ አንብበው ዋና ሃሳቦን ለያቸውም የራስህን የርዕስ አከፋፈል ከአምስቱ የተሻሻሉ ትርጉሞች ጋር አስተያያቸው፡፡ በአንቀፅ መከፋፈል በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት የሚደረግ ባይሆንም ለአተረጓጎም ክህሎት እምብርት የሆነውን የመጀመሪያውን ፀሐፊ ዋና ሀሳብ ለመከተል ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ እያንዳንዱም አንቀፅ የሚያወሳው ስለ አንድ ሀሳብ ብቻ ነው፡፡*

1. *የመጀመሪያ አንቀፅ*

2. *ሁለተኛ አንቀፅ*

3. *ሦተኛ አንቀፅ*

4. *ወ.ዘ.ተ*

**ቁጥር 1-25ን የሚመለከቱ አውዳዊ መረዳቶች/ግንዛቤዎች**

ሀ. *ምዕራፍ 21 የተጨመረ ነው በሚል እሳቤ ላ ብዙ ክርክር አለ ምክያቱም ወንጌሉ የሚያበቃው በ20፡31 ላ ይመስላል፡፡ ይሁን እንጂ ምዕራፍ 21፡3 ያስቀረ (የገደፈ) ምም አይነት የግሪክ ምንጭ የለም፡፡*

ለ. *ቁጥር 25 ብዙውን ጊዜ በኋላ የተጨመረ ነው የሚል ሐሳብ አለ ምክንያቱም በአንዳነድ ምንጮች ዮሐንስ 7፡53-8፡11 ከቁጥር 24 በኋላ ስለገባ ነው፡፡*

ሐ. *ምንም አንኳን የዮሐንስ ወንጌል ወሣኝ ምዕራፍ ባይሆንም፤ ምዕራፍ 21 በእርግጠኝነት የተወደደው ከሐዋርያው እጅ ነበር፡፡ የቀደመችውን ቤተክርስትያን ሁለት ጥየቄዎችን የሚመልስ ነው፡፡*

1. *ጴጥሮስ ወደ ኂላ ተመልሶ ነበርን?*
2. *ዮሐንስ ረጅም ዕድሜ ኖሯል የሚባለውስ?*

**የቃልና የሐረግ ጥናት**

> NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 21፥1-3
> **[1]ከዚህ በኂላ ኢየሱስ በጥብርያዶስ ባህር አጠገብ ለደቀ መዛሙርቱ እንደ ገና ተገለጠላቸው፤ እንዲህም ተገለጠ፡፡ [2]ስምዖን ጴጥሮስና ዲዲሞስ የሚባለው ቶማስ ከገሊላ ቃና የሆነ ናትናኤልም የዘብዴዎስም ልጆች ከደቀ መዛሙርቱም ሌሎች ሁለት በአንድነት ነበሩ፡፡ [3]ስምዖን ጴጥሮስ፡- ዓሣ ላጠምድ እሄዳለሁ አላቸው፡፡ እነርሱም፡- እኛም አንተ ጋር እንመጣለን አሉት፡፡ ወጥተውም ወደ ተንኳይቱ ገቡ፤ በዚያችም ሌሊት ምንም አላጠመዱም፡፡**

**21:1 "ጥብርያይስ ባሕር"** *ጥብር ሃይል በገሊላ አውራጃ የምትገኝ የሮም የአስተዳደር ከተማ ነበረች፡፡ የውሃውም አካል ደግሞ "የገሊላ ባህር" (6፡1) ወይም የጌንሳሬጥ ባህር (ማቴ 14፡34፤ማር 6፡35፤ሉቃ5፡1) ሲባል በብሉይ ኪዳን ደግሞ"ኬኔሬት የባሕር ወሽመጥ" ይባል ነበር (ዚህል 34፡17፤ኢያሱ 11፡2፤12፡3፤13፡27፤19፡35፡1ነገ15፡20)፡፡*

▣ **"እደገና ተገለጠላቸው"** *ግሱ "በሙሉ ወይም በግልፅ መታየት" የሚል ትርጉም ያዘለ ነው (1፡31፤2፡11፤7፡4፤9፡3፤1ዮሐ1፡2፤2፤2፡28፤3፡2፤4፤9)፡፡ በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ "ለታላቁ ተልዕኮ" መነሻ ምክንያት የሆነ በገሊላ አገር በተራራ ላይ የተካሄደ ስብሰባ ነበር (16፡32፡28፡10፡16)፡፡ በዮሐንስ ወንጌልም ኢሱስ ራሱነ የገለጠበት ቦታ የጥብር ያይሰ ባህር ነበር፡፡ በዚህ ድንገተኛ መገለጥ የቀድሞው ቤክርስትን አፅንኦት የሰጠችባቸውን ሁለት መሠረታዊ ጥያቄዎችን ኢየሱስ ሲመልስ እንመለከታለን፡፡*

1. *ጴጥሮስ ወደ ቀድመው የመሪነት ሥፍራው ተመልሷል ወይ?*
2. *ጌታ እስኪመጣ ድረስ ዮሐንስ እንደማይሞት በአለ ታሪክ የሚነገረውስ?*

21:2 "**ደዲሞስ የሚባለው ቶማስ**" በ1:45 ላይ ስለ ሐዋርያት ስም የተሰጠውን ልዩ ርዕስ ተመልከት፡፡
እዚሀ ላይ በግልፅ ማየት እንደሚችለው ከአሥራ አንዱ ሰባቱ ወደ አሳ ማጥመድ ሥራቸው እንደተመለሱ ማየት ይችላል፡፡

▣ "**የዘብዮዎስም ልጆች**" ይህ የሚያመለክተው ያዕቆብንና ዮሐንስን ነው (ማቴ 4:21)፡፡ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ያዕቆብም ሆነ ዮሐንስም በስም አልተጠቀሡም፡፡ 21:3 "ስምኦ ጴጥሮስም፡- ዓሣ ላጠምድ እሄዳለሁ አላቸው" ይህ የአሁን ጊዜን አመል ካች ነው፡፡ ይህንን ዓሣ የማጥመድ ጉዞን በሚመለከት የተለያዩ ፅንስ ሃሳቦች አሉ፤

1. ኢየሱስ የወሰነው የመሰብሰብ ጊዜ እስኪደርስ
1. ኢየሱስ የወሰነው የመገናኘት ጊዜ እስኪያልፍ ድረስ ዝና ለማየት የተደረገ ጉዞ የሚል (ማቴ26-32-28:7:10)
2. ገንዘብን ለማግኘት ዓላማ ሲባል ነበር የሚል
3. የቀደመውን የጴጥሮን ዓሣ የማጥመድ ሙያውን ለማነሣሣት የሚል ይህ ምዕራፍ ከሉቃ5 ጋር በጣም ተመሳሳይነት አለው፡፡

▣ "**በዚያችም ሌሊት ምንም አላጠመዱም**" በአንድ ወቅት ሕሙማንን ለስራ ወሰና አጋንንትን ለማስወጣት ይችሉ የነበሩ ሰዎች በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ ተአምራትን ማድረግ እንዳልቻሉ ስናስተውል ይገባል፡፡ ይህ ግስ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በየትኛውም ሥፍራ ዓሣን ለማጥመድ አልተጠቀሰም፡፡ ብዙውን ጊዜ የሚጠቀሰው ሰዎችን ለመያዝ ነው፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 21:4-8

**[4]በነጋም ጊዜ ኢየሱስ በባህር ዳር ቆመ፤ ደቀመዛሙርቱ ግን ኢየሱስ መሆኑን አላወቁም፡፡ [5]ኢየሱስም፡- ልጆች ሆይ÷ አንዳች የሚበላ አላችሁን? አላቸው፡፡ የለንም ብለው መለሱለት፡፡ [6]እርሱም፡- መረቡን በታንኳይቱ በስተቀኝ ጣሉት ታገኙማላችሁ አላቸው፡፡ ስለዚህ ጣሉት፤ በዚህም ጊዜ ከዓሣው ብዛት የተነሣ ሊጎትቱት አቃታቸው፡፡ [7]ኢየሱስ ይወደው የነበረውም ደቀ መዝሙር ጴጥሮስን፡- ጌታ እኮ ነው አለው፡፡ ስለዚህ ስምዖን ጴጥሮስ ጌታ መሆኑን በሰማ ጊዜ ዕራቁቱን ነበረና ልብሱን ታጥቆ ወደ ባህር ራሱን ጣለ፡፡ [8]ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ግን ከምድር ሁለት መቶ ክንድ ያህል እንጂ እጅግ አልራቁም ነበርና ዓሣ የምለውን መረብ እያሰቡ በጀልባ መጡ፡፡**

21:4 "**ደቀመዛሙርቱ ግ ኢሱስ መሆኑን አላወቀም**" ኢየሱስን ማወቅ ባለመቻላቸው ጉዳይ ላይ ብዙ ፅንሰ ሐሳቦች አሉ፡፡

1. በጣም መሽቶ ነበር
2. በጣም ርቆ ነበር
3. በጣም ደክሟቸው ነበር
4. ኢየሱስ በመጠኑ ለየት ብሎ ነበር (ዮሐ 21:12 :ማቴ.28:16-17:ሉቃ 24:13)
5. በመለኮት ኃይል እንዳያስተውሉ ሆነው ነበር (ሉቃ24:16)

21:5 "**ልጆች ሆይ**" ይህ በተለዋጭ ዘይቤያዊ ንግግር የተላለፈ ነው፡፡ በአዲ ኪዳን ውስጥ "ልጆች" ለሚለው በተለመደ ሁኔታ የሚጠቀሱ ሁለት ቃላት አሉ፡፡ ይህኛው *PaidioN* (ፔይዲዮን) ብዙም የማይጠቀልና በጣም ከተለመደው *tekNioN* ከሚለው ቃል በዮሐንስ ወንጌልና በ1ና ዮሐንስ መልዕክት ውስጥ ተጠቅሷል፡፡ ይህ ቃል የተጠቀሰ በዮሐ4:49 እና 16:21 እንደገና በዚህ ሥፍራ ብቻ ነው፡፡ እነዚህ ቃላት በተመሳሳይ ሁኔታ በ1ዮሐንስ፤*PaidioN* በ2:13:18 ተብለው ሲጠቀሱ ነገር ግን በ2:1:12-28 ላይ ደግሞ *TekNioN* ተብለው ተጠቅሰዋል፡፡

▣ "**አንዳች የሚበላ አላችሁን?** ይህ "ዓሣ" የሚለው ቃል () የሚያመለክተው ከዳቦ ጋር የሚበላ ማንኛውም ምግብ ሲሆን በዚህ ዓውድ ግን የተፈለገው "ዓሣ" ነው፡፡ ይህም ጥያቄ "የለንም" የሚል ምላሽ የሚሰጠው ነው፡፡

21:6 ኢየሱስ ሲያደርግ የነበረው ልክ በመጀመሪያ በሉቃ 5:1-11 ሲጠራቸው እንደ ነበረው ሁኔታ ነበር፡፡ እንደዚሀ ምዕራፍ ባህሪይ (በቁ 15 ላይ ያለውን ይመልከቱ፡፡) ታንኳ ለሚለው ሁለት የግሪክ ቃል ይጠቀሳሉ፡- በቁ.3 እና 6 እንዲሁም (ትንሽ ታንኳ) በቁ 8፡፡ ዮሐንስም በምዕራፍ ውስጥ ያለውን ሥነ ፅሑፉም ልዩነት ብዙ ጊዜ ያሣያል፡፡
21:7 "ኢየሱስ ይወደው የነበረው ደቀመዝሙር "ይህ የሚያመለክተው የወንጌሉን ፀሐፊ ራሱ ሐዋርያው ዮሐንስን ነው (13:23:20:2:3:8:21:20)፡፡ ዮሐንስ በወንጌል ውስጥ በፍፁም አልተጠቀሰም፡፡

▣

| | |
|---|---|
| NASB | "ልብሱን ታጥቆ (ለሥራ አውስቶት ነበርና)" |
| NAJB | "ልብሱነ ታጥቆ (ጥሎት ነበር) |
| NRS | "ጥቂት ልብሶን ለብስ ራቁቱነ ነበርና" |
| TEV | "ልብሱነ በሰውነቱ ላይ ጠመጠመ (ልብሱን አውልቆ ነበርና)" |
| NJB | "ጴጥሮስ ልብሱን በሰውነቱ ላይ አሰረ (ምንም በላዩ አልነበረምና)" |

በመጀመሪያው ክፍለዘመን በፍልስጥኤም ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ካባ ይለብሱ ነበር፡፡ ጴጥሮስም ካባወንጅ አውልቆ ከውስጥ የለበሰውን ስለ ልብሱ እስከ ወገቡ ድረስ ወደታች አውርዶ ነበር፡፡

▣ **"ጌታ እኮ ነው"** *kurios* (ኩሪየስ) የሚውለው የግሪክ ቃል "ጌታ" ክቡር "ባለቤት" ለሚሉት ቃላት መጠሪያ ነው፡፡ በአንዳንድ አውዶች(አውዶች)ትህትናን ሲያመለክት በተቃራኒው በሌሎች የኢየሱስን መለኮትነት (አምላክነት) የሚሲረግጥ ሥነ-መለኮታዊ አንደምታ አለው፡፡ በዚህ ዓውድ ግን ፊእነዚህ ዓሣ የጥሞዮች በባህሩ ዳሮች ከሞት የተነሳውን ጌታ እና የከበረውን ኢየሱስ አስተዋሉት!

የዚህ ትርጓሜ ምንም የሚመጣው ከብሉይ ኪዳን ሲሆን ይህም የህዋህ እንደ ጌታ የሚተረጐምበት ነው፡፡ ይህም የተከሰተው አይሁዶች ይህን የቃል ኪዳን ስም ለመለኮት ለመስጠት ስለ ፈሩ ነበር፡፡ ስለዚህም *kurias* ከሚለው ቃል ጋር ተዛማጅነት ያለውን ሌላ AdoNai (አይናይ) የሚል የእብራይስጥ ቃል ተኩበት፡፡ በምዕ 3፡9 ላየ ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡ በፊልጵሲዩስ 2፡9-11 ጌታ የሚለው ማዕረግ ከማንኛውም ስም በላይ ነው፡፡ ይህ የቀደመችው ቤተክርስትያን በጥምቀት ሥርዓት ጊዜ ሰው ኃጢያቱን ሲናዘዝ የሚውልየው ፀሎት አንዱ ክፍል ነበር "ኢየሱስ ጌታ ነው" የሚል (ሮሜ 10፡9-13)፡፡

21፡8 **"ሌሎች ደቀመዛሙርት"** በግልፅ ለማየት እንደሚችለው የቅርብ የሆኑት ቀረቤት ያላቸው) ደቀመዛሙርት ከጴጥሮስና ከዮሐንስ ጋር ዓሣ ለማጥመድና የተወሰነ ገንዘብ ለማግኘት ሄደዋል፡፡ (ከኢየሱስ ጋር ከሚጓዙት ሴቶች ላይ ከእንግዲህ ጥገኛ ሊሆን አይችሉም)፡፡

▣ **"ዓሣ የምላውን መለስ"** በዚህ በዘገየ ሰዓት /ቀን እንኳ ኢየሱስ አሁንም

1. እምነታቸውን ይጠግን ነበር
2. የሚያስፈልጋቸውን ይሰጣቸው ነበር
3. ትንሳኤውን ሥልጣኑን (በተፈጥሮ ላይ) ያስረግጥ ነበር፡፡

**NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 21÷9-14**
**[9]ወደ ምድርም በወጡ ጊዜ ፍምና ዓሣ በላዩ ተቀምጦ እንጀራም አዩ። [10]ኢየሱስም፦ አሁን ካጠመዳችሁት ዓሣ አምጡ አላቸው። [11]ስምዖን ጴጥሮስም ወደ ጀልባይቱ ገብቶ መቶ አምሳ ሦስት ታላላቅ ዓሦች ሞልቶ የነበረውን መረብ ወደ ምድር ጐተተ፤ ይህንም ያህል ብዙ ሲሆን መረቡ አልተቀደደም። [12]ኢየሱስም፦ ኑ፥ ምሳ ብሉ አላቸው። ከደቀ መዛሙርቱ አንድ ስንኳ። አንተ ማን ነህ? ብሎ ሊመረምረው የደፈረ አልነበረም፤ ጌታ መሆኑን አውቀው ነበርና። [13]ኢየሱስም መጣና እንጀራ አንሥቶ ሰጣቸው፥ እንዲሁም ዓሣውን። [14]ኢየሱስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ ሲገለጥላቸው ይህ ሦስተኛው ጊዜ ነበረ።**

21፡9 **"ፍምና ዓሣ በላይ ተቀምጦ አንጀራም አዩ"** የዚህ ማለዳ ቁርስ ዋናው ዓላማ ሕብረት ለማድረግና ለሥነ-መለኰታዊ ግንዛቤ ነበር፡፡ ሥነ-መለኰታዊ አንደምታዋቹም፡፡

1. ይህ ክፍል በሌላ ሥፍራ እንዲሁ እሳት እየሞቀ በነበረበት ወቅት ኢየሱስን መካዱን የሚያሣይ ነው (18፡18)፡፡ ይህ ቃል እዚህም እዚያም ይገኛል፡፡
2. የዮሐንስ ወንጌል የተፃፈው የኢየሱስን ስብዕና የሚክደውን የት የግኖ ቲሲዝምን የኑፍቄ ትምህርት ለመቃወም ነበር፡፡ ኢየሱስም በዚህ ስፍራ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሲበላ ታይቷል፡፡

21፡10 በዚህ አንቀፅ ውስጥ ዓሣ ለሚለው ሀብት ቃላት ተጠቅሰዋል፡፡ (1) በቁ 9፤10 እና 13 ቃሉ *opsarioN* (አፕሳሪዮን) ሲባል ይህም ትንሽ ዓሣ ማለት ነው፡፡ (2) በቁ 6፡8 እና 11 ላይ ቃሉ *ickthus* (ኢክተስ) ሲባል ይህም ትልቅ ዓሣ ማለት ነው፡፡ በዚህ ዓውድ ላይ ሁለቱም እየተለዋወጡ ተጠቅሰዋል፡፡

21፡11 **"መቶ ሃምሣ ሦስት"** ከዓውድ አንፃር ይህ ቁጥር ምንም የሚያሣየው ምልክት የለም፤ እንዲያው የአይን ምሥክርነት ዝርዝር ለመስጠት ያህል ብቻ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የቀደመችው ቤተክርስትያን ተገቢ ያልሆነ አካሄድ ሁሉንም ቁጥሮችና ዝርዝሮችን የተለየ ትርጓሜ እነዳላቸው እንድታስብ አስገድዳለች፡፡ እነዚህም ትርጓሜዎች

1. ሲሪል መቶዎቹ አህዛብን ሃምሣዎቹ አይሁድን እንዲሁም ሦስት ሥላሴን ይወክላል ይላል፡፡
2. አገስቲን ይህ ቁጥር የሚያመለክተው አስርቱን ትዕዛዛትና ሰባቱን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ነው፤ ይህም አሥራ ሰባት ይሆና ይላል፡፡ እያንዳንዱን 1፤2፤3፤4 እያን እስከ 17 ቆጥረን ብንደምራቸው ውጤቱ 153 ይሆናል፡፡ አገልቲንም እንደሚለው እነዚህ በህጉና በይው ወደ ኢየሱስ የመጡት ጠቅላላ ቁጥራቸው ነው ይላል፡፡
3. ጀሮም ደግሞ የሚለው 153 ሰዎ መሆናቸው የሚያመለክተው ሁሉም ሕዝቦች ወደ ጌታ እንደሚመጡ ነው፡፡ ይህ ሚስጢራዊ ፍቺ አለው ብሎ የሚደረግ የአተረጓጐም ዘዴ (አሊጐሪዝም) የፀሐፊውን ብልጠት ወይም ችሎታ ያሣያል እንጂ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የፃፈው የመጀመሪው ፀሐፊ ሃሳብ አይደለም፡፡

▣ **"ይህን ያህልም ብዙ ሲሆን መረቡ አልተቀደደም"** ይህ የዓይን ምስክርነት ዝርዝር አሊያም የተባለው አምር ነው ማለት ነው፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 21÷15-19
**[15]ምሳ ከበሉ በኋላም ኢየሱስ ስምዖን ጴጥሮስን፡፡ የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን? አለው፡፡ አዎን ጌታ ሆይ፥ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው፡፡ ግልገሎቼን አሰማራ አለው፡፡ [16]ደግሞ ሁለተኛ፡፡ የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ትወደኛለህን? አለው፡፡ አዎን ጌታ ሆይ፥ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው፡፡ [17]ጠቦቶቼን ጠብቅ አለው፡፡ ሦስተኛ ጊዜ፡፡ የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ትወደኛለህን? አለው፡፡ ሦስተኛ፡፡ ትወደኛለህን? ስላለው ጴጥሮስ አዘነና፡፡ ጌታ ሆይ፥ አንተ ሁሉን ታውቃለህ፤ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው፡፡ ኢየሱስም፦ በጎቼን አሰማራ፡፡ [18]እውነት እውነት እልሃለሁ፥ አንተ ጐልማሳ ሳለህ ወገብህን በገዛ ራስህ ታጥቀህ ወደምትወደው ትሄድ ነበር፤ ነገር ግን በሸመገልህ ጊዜ እጆችህን ትዘረጋለህ፥ ሌላውም ያስታጥቅሃል ወደማትወደውም ይወስድሃል አለው፡፡ [19]በምን ዓይነት ሞት እግዚአብሔርን ያከብር ዘንድ እንዳለው ሲያመለክት ይህን አለ፡፡ ይህንም ብሎ፡፡ ተከተለኝ አለው፡፡**

21:15"ስምዖን.. የኖኅ ልጅ" ኢየሱስ "ስምኦን ጴጥሮስ" ብሎ እንደሰጠው አስተውል ምክንያቱም ይህ ሰው አለት እንጂ ሌላ ምንም ሊባል አይችልም! የስምኦንን አባት በሚመለከት የተለያዩ ምንጮች የሚሉት አላቸው፤

1. ዮሐንስ የሚሉ N[1] B C D L W
2. ዮኛ ነው የሚሉ A C[2]
3. የሰረዙት/ያወጡት M[*]

1፡42ን ተከትሎ (P[66], P[72], N, B[*], L:W) ዩ.ቢ.ኤስ[4] አንደኛውን አማራጭ የ "B" (ለእርግጠኝነት የቀረበ) ደረጃን በመስጠት ይቀበለዋል ፡፡

▣ **"ትወደኛለህን... ትወደኛለህን... ትወደኛለህን"** ጴጥሮስ በሊቀካህኑ ፊት ሦስት ጊዜ እንደ ካደው የሚያሳይ ነው(18፡17፡25፡27) በዚህ ክፍል ውስጥ ልዩ ተቀውሞዎችንና መመሳሰሎችን ማየት ይችላል፡፡

1. የወዳጅ ፍቅር *Philes* እና የእግዚአብሔር ፍቅር *agagao*
2. ጠቦትና በግ
3. *ታውቃላችሁ giNosko*
4. *ሁሉን ማወቅ giosks* እና *ማወቅ Gida*

ይህ አጠቃቀም የሚያመለክተው ከስነ-ፅሁፋዊ ልዩነት ወይም ሆን ተብሎ ተቃርኖን ለመፍጠር የታሰበበት መሆን አለመሆኑ እስከ አሁን ድረስ አስፈካሪ ጉዳይ ነው፡፡ ዮሐንስ በተለይም በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ልዩነቶን ሲጠቀም ይስተዋላል("ልጆች" "ታንኳ" እና "ዓሣ" ለሚሉት ለእያንዳንዳቸው ሁለት ቃላትን ተጠቅሟል)፡፡ በዚህ ዓውድ ውስጥ በግሪኩ *agapao* እና *phileo* መካከል የተወሰነ ልዩነት ያለ ይመስላል፤ ነገር ግን በብዙሐኑ የግሪክ ቋንቋ ተመሳሳይ ስለሆኑ ሲተው የሚችሉ አይደሉም (3፡35፤5፡20፡11፡3፡5)፡፡

▣ **"ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን?"** ይህ ከጥያቄው ዓላማ አንፃር አገባቡ አሻሚ ነው፡፡ አንዳንዶች እንዲህ ሲሉ የሚያመለክተው፡፡
አንዳንዶች በዚህ ጉዳይ እንዲህ ሲሉ ይከራከራሉ፡፡

1. ዓሣ ማስገርን እንደሥራ ያመለክታል ይላሉ፡፡
2. ጴጥሮ ለኢየሱስ የነበረው የቀደመው ፍቅር ከሌሎች ደቀመዛሙር የሚበልጥ ነው ይላል (ማቴ 26፡33፤ማር 14፡29 ዮሐ 13፡37)፡፡
3. ታላቅ ሊሆን የሚወድ የሁሉ አገልጋይ መሆን እንዳበት ያመለክታል ይላሉ (ሉቃ 9፤46-45፤22፡24-27)፡፡

▣ **"ግልገሎቼን አሰማራ"** ይህ የአሁን ጊዜን የሚያሳይ ትዕዛዛዊ ድርጊ ገላጭ ግሥ ነው፡፡ እነዚህ ሦስቱም ንግሮች ተመሳሳይ ሰዋሰዋዊ ቅርፅ አላቸው (ቁ 16 እና 17) ነገር ግን ትንሽ ደዊት ያለ አፃፃፉ አለቸው(በጎቼነ ጠብቅ እና በጎቼን አሰማራ)፡፡

21:17፡ **"ጌታ ሆይ አንተ ሁሉን ታውቃለህ"** ጴጥሮስ ቸኩሎ አለመነገርን እየተረዳ ያለ ይመስላል /እየተማረ/ ነው፡፡ በዚህም መልካም የሆነ ሥነ-መለኮትን ይገልፃል፡፡(2፡25፡6፡61፤64፤13፡11፤16፡30)፡፡

▣ **"እንድወድህ አንተ ታውቃለህ"** በቁ 16 *oida* እና ቁ.17 *oida* እና *giNosko* በሚሉት መካከል "ታውቃለህ" ለሚለው ቃል በግሪኩ ላይ ለውጥ አለ፤ ነገር ግን ትክክለኛው ምክንያት የተረጋገጠ አይደለም፤ ምናልባትም ለውጥን ሊያመለክት ይችላል፡፡

21:18 **"እጆችህን ትዘረጋለህ"** ይህ ምናልባት ግብራዊ ስያሜ ሊሆን ይችላል፡፡ ቃሉም አገልግሎት ላይ ይውል የነበረው(1) በቀደመችው ቤተክርስትያን እና (2) በግሪክ ሥነ-ፅሑፍ "መስቀል" የሚለውን ቃል ለማመልከት ነበር፡፡

21:19 **"በምን አይነት ሞት እግዚአብሔርን ያከብር ዘንድ እንዳለው ሲያመለክት"** ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው የቤተክርስትን ልማድ እንደሚያስረዳው ጴጥሮስ የሞተው ራሱን ወደታች ተዘቅዝቆ እንደ ነበር ነው፡፡ *The Ecclesrastrcal History* ቅፅ 3፤1 ላይ ኢዩሲበል ሲናገር "ጴጥሮስ በጳንጠስ፣ በገላትያ፣ በቢተኒ፣ በቀጀይቅያ እና በእስያ ለሚገኙ የአይሁድ ዲያስፓራ ህብረተሰብ (ማህበረሰብ) እንደሰበከ ይተመናል፡፡ ወደሮምም ከተጓዘ በኂላ በራሱ ጥያቂ (ምርጫ) ተዘቅዝቆ እንዲሰቀል ተደርጓል፡፡" በ1፡14 ላይ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ፡፡

▣ **"ተከተለኝ"** *ይህ አሁን ጊዜን ትዕዛዛዊ አድርጊ ግስን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ ከጴጥሮስ ተሃድሶና ሹመቱ ደግሞ ለአመራር መፅደቁን የሚያመለክት ነው፡፡ ከጴጥሮስ ደግሞ መታደስና የእርሱም ለአመራር የተሰጠው የአገልግሎት ጥሪ እንደገና መጽደቁን የሚያሳይ ነው* (ማቴ 4፡19-20)፡፡

> NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 21÷20-23
> [20]**ጴጥሮስም ዘወር ብሎ ኢየሱስ ይወደው የነበረውን ደቀ መዝሙር ሲከተለው አየ፤ እርሱም ደግሞ በእራት ጊዜ በደረቱ ተጠግቶ። ጌታ ሆይ፥ አሳልፎ የሚሰጥህ ማን ነው? ያለው ነበረ። [21]ጴጥሮስም ይህን አይቶ ኢየሱስን። ጌታ ሆይ፥ ይህስ እንዴት ይሆናል? አለው። [22]ኢየሱስም፦ እስክመጣ ድረስ ይኖር ዘንድ ብወድስ፥ ምን አግዶህ? አንተ ተከተለኝ አለው። [23]ስለዚህ፦ ያ ደቀ መዝሙር አይሞትም የሚለው ይህ ነገር ወደ ወንድሞች ወጣ፤ ነገር ግን ኢየሱስ፦ እስክመጣ ድረስ ይኖር ዘንድ ብወድስ ምን አግዶህ? አለው እንጂ አይሞትም አላለውም።**

21:20 **"ኢየሱስ ይወደው የነበረውን ደቀመዝሙር"** ይህ በ13፡25 ላይ ያለውን ታሪክ ያመለክታል፡፡ *እንዲህ ባለ ሚስጢራዊ ትርጉምን በተላበሰ ሁኔታ ለምን እንደተሰየመ ግን ግልፅ አይደለም* (13፡23፡19፡26፤20፡2፡21፡17፡20)፡፡ *በዚህ ጉዳይ ላይ ምናልባት ሊሆኑ የሚችሉ ፅንሰ-ሐሳቦች፤*

1. *በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የነበረው በዕላዊው የአይሁድ ሥነ-ፅሑፍ ፀሐፊውን በስም አይጠቀሰውም*
2. *ዮሐንስ ኢየሱስን ይከተል በነበረበት ወቅት በጣም ወጣት ነበር፡፡*
3. *ዮሐንስ በኢየሱስ መከራና በስቅለቱ ወቅት ሁሉ አብሮ የቆየ ብቸኛው ሐዋርያ ነበር፡፡*

21:22 **"እስከመጣ ድረስ ይኖር ዘንድ ብወድስ ምን አግዶህ"** *ይህ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ነው፡፡ ሁላችንም ማስተዋል ያለብን ነገር ትኩረት መስጠት ያለብን የተሰጡትን ስጦታዎችና አገልግሎቶች እንጂ እግዚአብሔር ለሌሎች ባቀደው ጉዳይ ላይ በማያገባን ልንገባ አይደለም፡፡ ምናልባትም የምዕራፍ* 21 *መጨመር ይህ አለመረዳት ለመመለስ ይመስላል፡፡ በግልፅ እንደማታየው ዮሐንስ እስከ ኢየሱስ ዳግም መመሰል ድረስ ሊኖር እንደሚችል* (*ዮሐንስ ስለ ዳግም ምፅአት parousia ይናገር ነበር፤* 14፡23፣ 1ዮሐ 3፡2) *ቀደም ሲል ጭምጭምታ ነበር* (*ምናልባትም የግኖስቲኮች*)፡፡

▣ **"አንተ ተከተለኝ"** *ይህ የዮሐንስ ወንጌልን ጥሪ የሚያጠቃልል ነው* (10፡27፤ 12፡26፤1፡19፡22)፡፡ *ይህ ትኩረት የሚያደርገው የወንጌልን ግላዊ አቅጣጫ ሲሆን "እመኑ" የሚለው ደግሞ የወንጌልን ይዘት የሚያተኩር ነው፡፡*

> NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 21፡24
> [24]**ስለእነዚህም የመሰከረ ይህንንም ፅፎ ያለ ይህ ደቀመዝሙር ነው፤ ምስክሩም እውነት እንደሆነ እናውቃለን፡፡**

21:24 **"ስለእነዚም የመሰከረ ይህንም ፅፎ ያለ"** *የህ የሚመለክተው* (1) *ቁ.*20-23 (2) *ምዕራፍ* 21 *ወይስ* (3) *ሙሉን ወንጌልን ይህን? ምላሹ* (*መልሱ*) *አስተማማኝ አይደለም፡፡*

▣ **"ምስክሩም እውነት እንደሆነ እናውቃለን"** *"እኛ" የሚለው ተውላጠ ስም በተለይ የሚያመለክተው ወገን የትኛው እንደሆነ አይታወቅም፡፡ ሌሎች የዮሐንስን ወንጌል እንደተቀበሉት በቀላሉ ማወቅ የሚችል ነው፤ የህ ምናልባት የሚመለክተው የኤፌሶን ቤተክርስትያንን ሽማግሌዎችን ነው፡፡ ይህም አካባቢ ዮሐንስ የኖረበት፡ ያገለገለበትና የሞተበት ሥፍራ ነው፡፡ የቆየው የቤተክርስትያን ልማድ እንደሚከራከረው ሌሎች ሰዎች ሁሉ ስለሞቱና በኢየሱስ ማንነት ላይ የነፋቂ ትምህርቶች በመስፋፋታቸው ዮሐንስ የራሱን ወንጌል እንደ ፃፈ የኤፌሶን ሽማግሌዎች አረሳስተውታል የሚል ነው በ*1፡8 *ላይ ስለ ኢየሱስ መመስከር የሚለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት፡፡*

> NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 21÷25)
> [25]**ኢየሱስም ያደረገው ብዙ ሌላ ነበር ደግሞ አለ፤ ሁሉ በእያንዳንዱ በጋራ ለተፃፉት መፃህፍት ዓለም ራሱ ባልበቃቸውም ይመስከኛል፡፡**

21:25 “ቁጥር 25 አስቸጋሪ የሆነበት በሁለት ምክንያቶች ነው(1) በበርካታ ምንጮች ዮሐንስ 7፡53-8፡11 የገባው በቁ24 እና 25 መካከል ነው (2) ይህም ሁኔታ የታወቀው በብሪትሽ ሙዚየም ውስጥ በአልትራ ቫዮሌት ጨረር በመጠቀም ነበር። ይህ ጥቅስ በተለይ የሚያመለክተው የወንጌል ፀሐፊዎ ክስተቶችን ሲመዘግቡ እየመረጡ እንደ ነበር ነው። ሁሉጊዜ ሊጠየቅ የሚገባ የስነ አፈታት ጥያቄ “ለምንድነው ታድያ እንዲህ ባለ ሁኔታ ክስተቶቹን የዘገቡትና አራቱንም ወንጌላት ተጣድፈው ያላጣመሩት?” የሚል ነው (የጎርዲን ሲ እና ዳግለስ እስቱዋርትን *How to Read the Bible for All its worth* የሚለውን ይመልከቱ።)።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ሊሆን የሚችል ማብራሪያ በመሆኑ ለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጐም ኃላፊነት አለብህ፡፡ እያንዳንዳችን ልንሔድ የሚገባን ባለን መረዳት መጠን ነው፡፡ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጐም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣችሁ ናችሁ፤ በመሆኑም ይህንን በሚያብራራው ሰው ላይ ብቻ ልትተው የሚገባ አይደለም፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ባሉት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ በጥሞና እንድታስቡበት ለመረዳት ይቻል ዘንድ ነው፤ በመሆኑም ጥያቄዎቹ እንደ ሐሳብ - አነሳሽ ሆነው እንጂ በግልፅ ወይም በቀጥታ አይደለም፡፡

1. ዮሐንስ 21 ከሉቃስ 5 ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?
2. ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን ወዲያውኑ ለይተው ያላወቁበት ምክንያት ምን ነበር?
3. ኢየሱስ ይወደው የነበረው ደቀ መዝሙር ማን ነው?
4. ኢየሱስ ጴጥሮስ እንደሚወደው ሦስት ጊዜ የጠየቀበት ምክንያት ምንድን ነው?
5. ኢየሱስ ዮሐንስ  ዳግም እስኪመለስ እንደሚኖር አስረግጦ ተናግሮአልን?
6. በቁጥር 24 ላይ የተጠቀሰው ማን ነው?
7. ቁጥር 25 ከመጀመሪያውም የነበረ ጥቅስ ነው?

# 1ኛ ዮሐንስ መልዕክት

## የ1ኛ ዮሐንስ መልእክት መግቢያ

### የመጽሐፉ አስደናቂነት

ሀ. የመጀመሪያው የዮሐንስ ምልእክት ለአንድ ግለሰብ ወይም ለአንዷት ቤተክርስቲያን የተጻፈ ደብዳቤ አይደለም፡፡
1. የዮሐንስ መልእክተ የተለመደው የደበዳቤዎች የመግቢያ ሰላምታ የለውም (ከማን፣ለማን)
2. የዮሐንስ መልእክት ለግለሰብ የቀረበ ሰላምታ ወይም የመዝጊያ መልእክት የለውም፡፡

ለ. በመልእክቱ የግለሰብ ስሞች አልተጠቀሱም፡፡ ይህ ደግሞ ብዙዎች ቤተክርስቲያናት ለምሳሌ እንደ ኤፌሶንና ያዕቆብ የመሳሰሉት ካልሆነ በስተቀር በታም ያልተለመደ ነው፡፡ በአዲስ ኪዳን የጸሐፊው ማንነት ያልተካተተበት መልእክት ቢኖር የዕብራዊያን መልእክት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የመጀመሪያው የዮሐንስ መልእክት የተፃፈው ከሐሰት መምህራን የተነሳ (ግኖስቲክ) ውስጣዊ ችግር በቤተክርስቲያን እየተጋፈጡ ላሉት አማኞች ነው፡፡

ሐ. ይህ መልእክት በአጻጻፉ (በድርሰቱ) በጣም ኃይለኛ ሥነ-መለኮት ነው፡፡
1. የኢየሱስ ማዕከላዊነት
   ሀ. ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው መሆኑ
   ለ. ድነት የሚገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንጂ ረቂቅ በሆነ ልምምድ ወይም ምስጢራዊ እውቀት አይደለም (የሐሰት መምህራን)
2. ለክርስቲያናዊ የኑሮ ዘይቤ የሚያስፈልገው (የእውነተኛ ክርስትና መለያዎች)
   ሀ. የወንድማማች መዋደድ
   ለ. መታዘዝ
   ሐ. ዓለምን መጥላት
3. በናዝሬቱ ኢየሱስ በማመን የዘላለም ድነትመረጋገጥ (“አሁን” የሚለው 27 ጊዜያት ተጠቅሷል፡፡
4. የሐሰት መምህራን እንዴት ማወቅ እንደሚቻል

መ. የዮሐንስ መልእክቶች (በተለይ የመጀመሪያው) አብዛኛው ሕዝብ በሚጠቀምበት የግሪክ ቋንቋ ከጻፉት የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች በጣም ያልተወሳሰበው ሲሆን ጽሁፎቹ ጥቅል የሆነውንና የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ እውቀት በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ እግዚአብሔር ብርሃን ነው፤ 1÷5፤ እግዚአብሐር ፍቅር ነው 4÷8፡16፤ እግዚአብሔር መንፈስ ነው ዮሐ. 4÷24፡፡

ሠ. የዮሐንስ መልእክት ለዮሐንስ ወንጌል እንደሽፋን ደብዳቤ የታሰበ ነው ለማለት ይቻላል፤ ምክንያቱም ሁለቱም መጻህፍት በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የነበረው የግኖስቲኮች ኑፋቄ የኗላ ታሪክ ስለነበራቸው ነው፡፡ የዮሐንስ ወንጌል ከወንጌል ግፊት አንፃር ሲሆን አንደኛ ዮሐንስ ደግሞ የተጣፈው ለአማኞች ነው (ደቀ መዝሙርነት)፡፡
የታወቀው የመጽሐፍ ቅዱስ አባራሪ ዌስትኮት ሲያረጋግጥ/ሲናገር የዮሐንስ ወንጌል የሚያጸኛው የኢየሱስን አምላክነት ሲሆን አንደኛ ዮሐንስ ደግሞ የኢየሱስን ሰው መሆን ነው ብሎ ያስረግጣል፡፡ ስለዚህ እነዚህ ሁለቱ መጻሕፍት አብረው የሚሄዱ ናቸው!

ረ. ዮሐንስ የሚጽፈው በተቃራኒ አገላለጦች ነው (የሁለትዮሽ ሃሳብ)፡፡ ይህም የሙት ባህር ጥቅሎችና የሐሰት መምህራን መለያ ባህሪ ነው፡፡ የመጀመሪው ዮሐንስ የተቃርኖ ሃሳብ የተገለጠበት ሥነ ጽሑፍ ግሳዊ (ብርሃን እና ጨለማ) እና ዘይቤያዊ ነው (አዎንታዊ ዓረፍተ ነገር አሉታዊ ዓረፍተ ነገርን ይከተላል)፤ ይህም ቀጥ ያለ ሁለትዮሽ አስተሳሰብን ከሚከተለው የዮሐንስ ወንጌል የተለየ ነው (ኢየሱስ ከላይ እና ሁሉም ሰዎች ከታች)፡፡

ሰ. እየተደጋገሙ ከሚነሱት የዮሐንስ ችብጦች የተነሳ 1ኛ ዮሐንስን በቅደም ተከተል ማዋቀር በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡

### ጸሐፊው

ሀ. የአንደኛ ዮሐንስ ጸሐፊ ጉዳይ እንደሌሎቹ ጽሑፎች ጉዳይ አከራካሪ ጉዳይ ነው፡- የዮሐንስ ወንጌል፣ 1ኛ ዮሐንስ፣ 2ኛ ዮሐንስ እና የዮሐንስ ራእይ፡፡

ለ. ሁለት ዓይነት አቋሞች አሉ፡፡
1. ባህላዊ

ሀ. በቀደመችው ቤተክርስቲያን የነበሩ የቤተክርስቲያን አባቶች ዘንድ የተወደደው ሐዋሪያ ዮሐንስ 1ኛ መልእክትን ጽፏል የሚል የሁሉም ድምዳሜ አለ፡፡

ለ. የቀደመችው ቤተክርስቲያን የምትሰጠው ድምዳሜ

1) የሮሙ ክሌመንት (ከ-ክ.ል. በኋላ 90) በተዘዋዋሪ 1ኛ ዮሐንስን ይጠቅሳል፡፡
2) የሰምርኔው ፖሊካርፐ *PhilippiaNs* 7 (ከክ.ል.በ.150-160) 1ኛ ዮሐንስን ይጠቅሳል፡፡
3) የጀስቲን ማርቲየር *Dialogue* 123:9 (ከክ.ል.በኋላ 150-160) 1ና ዮሐንስን ይጠቅሳል፡፡
4) 1ኛ ዮሐንስ በተዘዋዋሪ የተጠቀሰባቸው ጽሑፎች
   ሀ. የአንጾኪያው ኢግናቲየስ (የተጻፉበት ጊዜያት እርግጠኛ ባይሆኑም ከክ.ል.በኋላ በመጀመሪያዎች መቶ አመታት)
   ለ. የሃይሪፖሊሱ ፓፒየስ (ከክ.ል. በኋላ ከ50-60 ዓመታት መካከል የተወለደውን ከክ.ል. በ በ155 አካባቢ የሞተው)
5) የሊዮኑ ኢራኒየስ (ከክ.ል.በኋላ 130-202) 1ኛ ዮሐንስ ከሐዋሪያው ዮሐንስ ጋር ያገናኘዋል፡፡ በኑፋቄ ትምህርቶች ላይ ወደ 50 የሚሆኑ መጽሐፍትን የጻፈው የቀድሞው ቱርቱሊያን (ቱርቱልያን) ብዙ ጊዜ 1ኛ ዮሐንስን ይጠቅስ ነበር፡፡
6) የጸሐፊነቱን ሥፍራ ለሐዋሪያው ዮሐንስ የሚሰጡ ሌሎች ቀደምት ጽሑፎች፡- ክሌመን፣ ኦሪገን እና ዳዮኒሲየስ፣ ሦስቱ አሌክሳንደሪያዊያን፣ የሙራቶሪየን ፍራግመንት የሚባሉት (180-200 ዓ.ም.)፣ አውስቢየስ (3ኛው ክፍለ ዘመን)
7) ጀሮም (4ኛ ክፍለ ዘመን ሁለተኛው አጋማሽ) የዮሐንስን ጸሐፊነት አጥብቆ ያመነበት ነው፤ ነገር ግን በዘመኑ ሌሎች እንዳልተቀበሉት ተናግሯል፡፡
8) የምሱዩስቲያው ቴዎዶር፡- የአንጾኪያ ቤተክርስቲያን ጳጳስ (392-428 ዓ.ም) የዮሐንስን ጸሐፊነት አልተቀበሉትም፡፡

ሐ. ዮሐንስ ቢሆን፡ ስለሐዋሪያው ጳውሎስ ምን የምናውቀው ነገር አለ?/ምንድን ነው?

1) የዘብዴዎስ ልጅ እና የሰሎሜ ልጅ ነው፡፡
2) ከወንደሙ ያዕቆብ ጋር በገሊላ ባህር ላይ አሳ ያጠምድ የነበረ (ምናልባት ብዙ ጀልባዎችም ሳይኖሩት አልቀረም)፡፡
3) የእርሱ እናት የኢየሱስ እናት የነበረችው የማርያም እህት ናት ብለው እንዳንዶች ያምናሉ (ዮሐ.19:25፤ ማር.15:20)፡፡
4) ሃብታም እንደነበር ግልጽ ነው ምክንያቱም
   (ሀ) በሥሩ አገልጋዮችን/ሠራተኞችን ቀጥሮ ነበር (ማር.1:20)
   (ለ) ብዙ ጀልባዎች ነበሩት፡፡
   (ሐ) በኢየሩሳሌም ቤት ነበረው (ማቴ.20:20)፡፡
5) ዮሐንስ በኢየሩሳሌም በነበረው የሊቀ ካህኑ ቤት የመገናኘት አጋጣሚ ነበረው፤ ይህም የሚያሳየው አንድ የሚታወቅ ሰው መሆኑን ነው (ዮሐ.18:15-16)፡፡

መ. የጥንት ቤተክርስቲያን ባህል ዮሐንስ ከሌሎች ሐዋሪት ይልቅ ረጅም እድሜ የኖረ ማርያምም በኢየሩሳሌም ከሞተች በኋላ በትንሹ እስያ ወደሚገኘው ትልቁ ከተማ ሄዶ እንደከተመ ይመሠክራል፡፡ (የጥንት ቤተክርስቲያን ባህል)፡፡ ከዚህ ከተማ ነው ወደ ፍጥሞ ደሴት በግዞት የሄደውና በኋላም ከግዞት ወደ ኤፌሶን ተለቆ የመጣው (ኢዩስበስም ፖሊካርፐን፣ ፓፒየስን እና ኢራኒየስን ይጥቅሳል)፡፡

2. የጊዜያችን እስኮላርሽፕ ምን ይላል?

ሀ. ብዙዎች የዘመናችን ተመራማሪዎች በሁሉም የዮሐንስ ጽሑፎች ውስጥ በተለይም በሐረጎች፣ በቃላት፣ እና በሰዋስዋዊ ቅርፅ ተመሣሣይነት እንዳለ ይገነዘባሉ፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ሊሆ የሚችሉት ጽሑፎቹን ለይት የሚያደርጉት ፍጹም ተቃርኖዎች ናቸው፤ ሕይወት እና ሞት፤ እውነት እና ሐሰት የሚሉት፡፡ ይህም ተመሳሳይ የሆነ የሁለትዮሽ ተቃርኖ በሌሎች የዘመኑ ጽሑፎችም የሚሰተዋል ነበር፡፡ የሙት ባህር ጥቅሎችና የግኖስቲክ ጽሑፎች፡፡

ለ. በልማድ ከዮሐንስ ጋር የተቆራኙት አምስቱ መጻሐፍት መካከል ባለው ግንኙነት ላይ ብዙ ጽንስ ሃሳቦች አሉ፡፡ አንዳንድ ወገኖች ፀሐፊነቱን ለአንድ ሰው ለሁለት ሰው ለሦስት ሰዎች ወዘተ እያሉ ይሰጣሉ፡፡ ከሁሉም ይበልጥ ተቀባይነት ያለው አቋም ግን ምንም እንኳን ሁሉም ጽሑፎች በብዙ የእርሱ ደቀ መዛሙርት የተጻፉ ሊሆኑ ቢችሉም ሁሉም ግን የአንድ ሰው ሃሰብ ውጤቶች ናቸው የሚለው ነው፡፡

ሐ. በግሌ ያለኝ እምነት ደግሞ ሽማግሌው ሐዋሪያ ዮሐንስ አምስቱንም ጽሑፎች ሁሉ የፃፋቸው በአገልግሎቱ መጨረሻ በኤፌሶን ነው የሚል ነው፡፡

3. የጸሐፊነቱ ጉዳይ የአተረጓጎም ሳይንስ ጉዳይ እንጂ የእስትንፋሰ እግዚአብሔር ጉዳ አይደለም፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ጸሐፊውማ የኋላ ኋላ እግዚአብሔር እንደሆነ የታወቀ ጉዳይ ነው፡፡

**ዘመን/ጊዜ - ይህ በቀላሉ ከጸሐፊው ማንነት ጋር የቴያዘ ነው**

ሀ. እነዚህን ደብዳቤዎች በተለይም 1ኛ ዮሐንስን ሐዋሪው ዮሐንስ ጽፎአቸው ከሆነ እየተነጋገርን ያለው የመጀመሪው ክፍለ ዘመን ሊጠናቀቀወ ለነበሩት ጊዜያት ነው ማለት ነው፡፡ ይህም ሁኔታ የግኖስቲክን የስህተት ሥነ መለኮታዊ /ፍልስፍናዊ አስተምህሮ አካሄድ ለማመን የሚያመች እና 1ኛ ዮሐንስ ካለው የቃላት አጠቃቀም አንጻር ("ልጆች ሆይ")፤ አንድ ሽምገል ያለ ሰው በእድሜ ከእርሱ ከሚያንሱት ታካጊ አማኞችን የሚመክራቸው ይመስላል፡፡ ዴሮምም ሲናገር ከኢየሱስ ክርስቶስ መሰቀል በኂላ ዮሐንስ ለ68 ዓመታት እንዲኖር ነው፤ ይህም ከመጀመሪያው የቤተክርስቲያን ልማድ ጋር የሚስማማ ነው፡፡

ለ. ኤ.ቲ.ሮቨርተሰን 1ኛ ዮሐንስ የተጻፈው በ85-95 ዓ.ም መካከል ሲፃፍ የዮሐንስ ወንጌል ደግሞ በ95 ዓ.ም. ተጽፎአል ብሎ ያምናል፡፡

ሐ. *The New INterNatioNal CommeNtary series* በአይ. ሐዋርድ የተፃፈው እንደሚያረጋግጠው ከ60 እስከ 100 ዓ.ም. ያሉት ዓመታት የዮሐንስ ጽሑፎች የተፃፉበትን ጊዜ ለሚመረምረው የዘመናችን ሥነ መለኮት የሚቀርብ እንደሆነ የሳያል፡፡

**የመልእክቱ ተቀባዮች**

ሀ. የቆየው ልማድ እንሚያስረዳው ምልእክቱ የተፃፈው ኤፌሶንን ዋና ከተማው ላደረገው በትንሹ ኢስያ (ምዕራባዊ ቱርክ) ለሚገኘው የሮም አውራጃ ነበር፡፡

ለ. መልእክቱ የተጻፈው በስህተት አስተማሪዎች የተነሳ ተግዳሮት ለገጠማቸው (እንደ ቆላሲይስና ኤፌሶን) በትንሹእሲያ ለሚገኙ ውስን ለሆኑት የቤተክርስቲያን ወገኖች የተፃፈ ይመስላል፡፡ በተለይም

1. የክርስቶስን ሰው መሆኑ የሚክደው ነገር ግን መለኮትነቱን የሚቀበለው ዶሴቲክ ግኖስቲክ የተባለው የኑፋቄ ትምህርት
2. ሥነ-መለኮትን ከኤቲክስ/ሞራል የለየው የኑፋቄ ትምህርት

ሐ. አውግስጦስ ደግሞ (በ4ኛው ክፍል ዘመን) የሚለው መልእክት የተፃፈው ሎፓርቲያንስ (ባቢሎን) ነው፡፡ እርሱንም ተከትሎ ካሊዮፒረስ (6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመጀመሪያው አካባቢ) ይህንን ሃሳብ ይደግፋል፡፡ ይህ የመጣው ምናልባትም "የተመረጠችው እመቤት" እና "ባቢሎን ያለችው" የሚሉት ሐረጎች ከፈጠሩት ግራ መጋባት ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህም ሐረጎች በድጋሚ በ1ኛ ጴጥ. 5:13 እና 2ኛ ዮሐንስ 1 ላይ የተጠወቀሱ ናቸው፡፡

**ኑፋቄ**

ሀ. መልእክቱ በራሱ አንድን የኑፋቄ ትምህርት ለመቃወም የተፃፈ ነው ("ካልን....1:6 እና "የሚል....2:9፤4:20 /ዲያትሪብ/)፡፡

ለ. የ1ኛ ዮሐንስን መልእክት ውስጣዊ ማስረጃዎች በማመን ስለ ኑፋቄው መሠረታዊ ነገሮችን ማወቅ እንችላለን

1. የኢየሱስ ክርስቶስነ ተሰግዎ ይክዳል፡፡
2. ኢየሱስ ክርስቶስ በድነት ውስጥ ያለውን ማእከላዊነት ይክዳሉ፡፡
3. ተገቢ የሆነው የክርስትና የሕይወት ዘይቤ አለመኖሩ
4. እውቀት ላይ ያተኮረ አካሂድ (ብዙ ጊዜ ምስጢራዊ)
5. ገለልተኛ የመሆን አባዜ /አካሂድ

ሐ. የመጀመሪው ክፍል ዘመን ድባብ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የነበረው የሮም ዓለም በምሥራቅና ምዕራብ ኃይማኖቶኞች መካከል ከፍተኛ ፉክክርና ሽኩቻ የሰፈነበት ነበር፡፡ የገሪክና የሮም አማልክት ፓንቲየንስ ጥሩ ስም አልነበራቸውም፡፡ የሚስጢር ኃይማኖቶች በወቅቱ ስመጥር ነበሩ፤ ምክንያቱም ከአምላክ ጋር ልላለው የግል ግንኙነት እና ስውር እውቀት ላይ ትኩረት ይሰጡ ስለነበር ነው፡፡ ዓለማዊው የግሪክ ፍልስፍና ኘነኛ የነበረና ከሌሎች የዓም አመለካከቶች ጋር የተቀየጠ ነበር፡፡ እንግዲህ በዚህ የሽኩቻ ጊዜ ነበር አንድና ብቸኛ አቋም ይዞ የክርስትኛ እምነት ብቅ ያለው (ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር የሚወስደው ብቸኛ መንገድ ነው ዮሐ.14:6፡፡ የኑፋቄው ትምህርት ምንም ዓይነት የኂላ ታሪክ ይኑረው ጠባብ የመሰለውን ክርስትና ለሰፊው የግሪክ-ሮም አድማጮች አሳማኝና በእውቀት ተቀባይነት ይኖረው ዘንድ የተደረገ ጥረት ነበር፡፡

መ. ዮሐንስ ምልእክቱን ለማን እንደፃፈው የሚያመለክቱ አማራጮች

1. የግኖስቲሲዝም አስተምህሮ

ሀ. የዚህ ስህተት አስተምህሮ መሠረታዊ አካሄድ፦ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የነበረው የዚህ ኑፋቄ መሠረታዊ አስተምህሮ በመንፈስና በቁስ መካከል የማንነት (ዘላለማዊነት) ዱዋሊዝም ላይ ትኩረት የሰጠ ይመስላል፡፡ መንፈስ (ከፍ ያለው አምላክ) መልካም ሆኖ ሲታይ ቁስ ደግሞ ከመጀመሪያውም ክፉ ተደርጎ ይታይ ነበር፡፡ ይህም ሁለትዮሽ ሃሳባዊ እና አካላዊ፣ ሰማያዊና ምድራዊ፤ የማይታይና የሚታይ ተብሎ የተጠቀሰውን የፕላቶኒዝም አካሄድን የሚመስል ነው፡፡ እንዲሁም ደግሞ ሌላው ስውር የሆነ እውቀት ለደህንነት በጣም አስፈላጊው ጉዳይ እንደሆነ ከልክ ያለፈ አጽንኦት የመስጠቱ ጉዳይ (ነፍስ በመላዕክት ተፈጥሮ አልፋ ወደ መለኮትነት እንድትሸጋገር የሚያድርግ ምስጢራዊ ቁልፍ) ነው፡፡

ለ. በ1ኛ ዮሐንስ የኋላ ታሪክ ያሉና በግኖስቲሲዝም አስተምህሮ ውስጥ በግልጥ የሚታዩ ሁለት ዕይነት አቀራረቦች አሉ፤

1) ዶሴቲክ ግኖስቲሲዝም የሚባለው ሲሆን ይህም ቁስ ክፉ ነው ብሎ ስለሚያምን የኢየሱስን ፍጹም ሰውነት የሚክድ፤
2) ሴሪንቲያን ግኖስቲሲዝም የሚባለው ሲሆን ይህም ክርስቶስን ከፍ ባለው አምላክና በክፉው መካከል እንዳለ የሚያምን ነው፡፡ ይህ "የክርስቶስ መንፈስ" ሰው የነበረው ኢየሱ ሲጠመቅ በውስጡ እንዳደረበት እና ከመሰቀሉ በፊት ለቆት እንደሄደ የሚያምን አኬሄድ ነው፡፡
3) ከእነዚህ ሁለቱ ወገኖች አንዳንዶች ‹አሴቲዝምን" (ሰውነት የሚሻው ከሆነ መጥፎ ነው ማለት ነው") ተግባራዊ ሲያደርጉ ሌሎች አነቲኖሚያኒዝምን (ሰውነት የሚሻከሆነ አድርግለት የሚል) ተግባራዊ ማድረግ ጀመሩ፡፡ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን አካባቢ ስለነበረው የግኖስቲክ አስምህሮ ነባራዊ ዕድገት የሚያስረዳ ምንም አይነት ማስረጃ የለም፡፡ እስከሁለተኛውም ክፍለ ዘመን የተጠናቀረ አንድም አይነት መረጃ የለም፡፡ ስለ ግኖስቲሲዝም ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ይቻል ዘንድ የሚከተሉትን ምንጮች ይመልከቱዋቸው፡፡

   ሀ. *The GNostic ReligioN* by HaNs JoNas, Published by Beam press.

   ለ. *The GNostic Gospels* by Elaiac Pegels, Pubalished by RaNdome House.

   ሐ. *The Nag Hammadi GNostic Geztr aNd The Bible* by ANdrew Helmbold.

2. አግኖቲዬስ በጽሑፎቹ (to the SmyrNaeaNs iv-v) የኑፋቄውን ሌሎች ምንጮችን ይጠቅሳል፡፡ በዚህም የአስተምህሮው ተከታዮች የኢየሱስን ተሰግዎ እንደሚክዱና የአንተኖሚያንስን የኑሮ ዘይቤ እንደሚከተሉ አመልክቷል፡፡
3. ሌላው ዝቅተኛ ግምት የሚሰጠው ስለ ኑፋቄው በምንጭነት የሚጠቀሰው የአንጾኪያው ሜንደሮ (*AgaiNst Heressies* XXIII) ነው፤ይህም በኢራኒየስ ጽሑፎች ውስጥ ብዙ ጊዜ የሚታወቅ ሲሆን ይህም ሰው የሳምራዊው ስምኦን ተከታይና የሥውር እውቀት ዋና አቀንቃኝ የነበረ ነው፡፡

ሠ. በዘመናችን የኑፋቄው ገጽታ

1. ሰዎች ክርስቲያናዊ እውነትን ከሌሎች የአስተሳሰብ ሥርዓቶች ጋር ለማጣመር ሲሞክሩ የዚህን የኑፋቄ መንፈስ ከእኛ ጋር እንዳለ መረዳት እንችላለን፡፡
2. ሰዎች በእምነት ካለው ኅብረትና የኑሮ ዘይቤ ውጪ ለ"ትክክለኛ" አስተምህር የበለጠ ትኩረት ስሰጡ የዚህን ኑፋቄ ከእኛ ጋር መኖር መረዳት እንችላለን፡፡
3. ሰዎች ክርስትናን በአእምሮ የመጠቁ እና ታላላቅ ሰዎች ብቻ የሚከተሉት አድርገው ውማሰብ ስለመጡ የዚህን ኑፋቄ ከእኛ ጋር መሆኑን እንረዳለን፡፡
4. የኃይማኖት ሰዎች ወደ አሴድሲዝም ወይም አንቲኖሚያኒዝም ሲቀየሩ የዚህን ኑፋቄ መኖር ያሳያል፡፡

**ዓላማ**

ሀ. በአማኞች ላይ ተግባራዊ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡

1. ደስታን ለመስጠት (1:14)
2. እግዚአብሔርን የመምሰል ህይወት እንዲኖሩ ለማበረታታት (1:7፤2:1)
3. ከዓለም ይልቅ እርስበርሳቸው አጥብቀው እንዲዋደዱ (4:7-21)
4. ከዓለም ይልቅ (2:15-17) እርስበርሳቸው አጥብቀው እንዲዋደዱ (4:7-21)
5. በክርስቶስ ስላላቸው ድነት ማረጋገጫ (ዋስትና) ለመስጠት (5:13)፡፡

ለ. ለአማኞች የዶክትሪን ትኩረት የሚሰጥ ነው፡፡

1. የኢየሱስ መለኮትነት ከሰውነቱ የሚለየውን አስተምህሮ ይነቅፋል፡፡
2. እግዚአብሔርን ለመምሰል መንፈሳዊነት ብቻ ሳይሆን በአእምሮም የመተቁ መሆን ያስፈልጋል የሚለውን ትምህርት ይቃወማል፡፡
3. አንድ ሰው ከሌሎች በመለየት መዳን ይችላል የሚለውን አስተምህሮ ይቃወማል፡፡

**የመጀመሪያው የምንባብ ዑደት (አንቀስ 5ን ይመልከቱ)**

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ሲሆን የሚችል ማብራሪያ ሲሆን ለምትወስደው የራስህ ትርጉም ኃላፊነት አለብህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን ባለን የብርሃን መጠን ልንጓዝ ይገባል። አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጎም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣቸሁ ናችሁ። ይህንን ጉዳይ ለሚያብራራው ሰው ብቻ መተው የለብህም።

ሙሉውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መጽሐፍ በአንድ ቅጽበት አንብበው። በራስህ ቃላት የመጽሐፉን ማዕከላዊ ጭብጥ ግለጽ።

1. የጠቅላላው መጽሐፍ ጭብጥ፣
2. የሥነ ጽሑ ዓይነቱን፣

**ሁለተኛው ምንባብ ዑደት**

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ሊሆን የሚችል ማብራሪያ ሲሆን ለምትወስደው የራስህ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን መጓዝ ያለብን ባለን መረዳት መጠን ነው። አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጎም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ናቸው።

ሙሉውን መጽሐፍ ለሁለተኛ ጊዜ በአንድ ቅጽበት አንብበው። ዋና ዋና ጉዳዮችን (ነጥቦችን) እያንዳንዳቸውን በአንድ ዓረፍተ ነገር በቅደም ተከተል አስቀምጣቸው/ዘርዝራቸው።

1. የመጀመሪያው ጽሑፍ ርዕስ/የመጀመሪያው ምዕራፍ ርዕስ
2. የሁለተኛው ጽሑፍ ርዕስ/የሁለተኛው ምዕራፍ ርዕስ
3. የሦስተኛው ጽሑፍ ርዕስ/የሦስተኛው ምዕራፍ ርዕስ
4. የአራተኛው ጽሑፍ ርዕስ/የአራተኛው ምዕራፍ ርዕስ
5. ወዘተ.

# አንደኛው የዮሐንስ መልክት 1፡1-2፡2፣

## የአዳዲስ መፀሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀፅ  አከፋፈል *

| UBS[4] | NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| የህይወት ቃል | የሰማነውን ያየነውንና የዳሰስናቸውን | መግቢያ | የሕይወት ቃል | ቃል ስጋመሆንና የከአብና ከልጁ ጋር ያለን ህብርት |
| 1፤1-4 | 1፤1-4 | 1፤1-4 | 1፤1-4 | 1፤1-4 |
| እግዚአብሔር ብርሃን ነው | ከርሱ ጋርላለን ሕብረት መሰረቶቹ | ስለኃሊጢያት ሊኖረን ያሚገባ ትክክለኛ አመለካከት | እግዚአብሔር ብርሃን ነው | በብርሃን መመላለስ |
| 1፤5-10 | 1፤5-2፡2 | 1፡5-10 | 1፡5-7 | 1፡5-7<br>የመጀመሪያ ቅድመ ሁኔታ፡ ከኃጢያት መንፃት |
| | | | 1፡8-10 | 1፤8-2፡2 |

**ሦስተኛው ዙር የንባብ ክፍል (የቀድሞውን ትርጉም ይመልከቱ)**
*የመልክቱ ፀሐፊ ሊያስተላልፍ የፈለገው መልዕክት አንቀጽ ባንቀጽ ሲታይ፤*

ይህ የጥቅስ ማብራሪያ የጥናት መምሪያ ነው፡፡ ማለትም አጥኚው ለመሰለው አተረጎጎም ኃላፊነት ይወስዳል፡፡ እያንዳንዳችን በተቀበልነው ብርሃን መመላለስ አለብን፡፡ በአተረጓጎም ሂደት አጥኚው መፀሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ በመሆኑም አጥኚው ይህንን ጉዳይ ለጥቅስ ማብራሪያ ፀሐፊዎች መተው የለበትም፡፡

ይህንንም ምዕራፍ በአንድ ጊዜ ያንብቡ፡፡ የክፍሉን ርዕሰ ጉዳዮች ይለዩ፣ በአንቀጽ ተከፋፍለው ከላይ ከተጠቀሱት አዳዲስ ትርጉሞች ጋር ያነጻጸሩ፡፡ ትቅሶችን በአንቀጽ መከፋፈል የጥቅስ አተረጓጎም መሠረታዊ መርህ የሆነውን የደራሲውን ሀሳብ ለማግኘት ቁልፍ ድርሻ ቢኖረውም ከመጀመሪያውም በመገለጥ የተሰጠው የመጽሐፉ አካል አልነበረም እያንዳንዱም አንቀጽ አንድ መልዕክት ብቻ ይኖረዋል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተ

*ተመስጧዊ ባይሆኑም፣ የአንቀጽ ምድቦች የሚከተለውን የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ ለመረዳት ቁልፍ ናቸው፡፡ እያንዳንዱ ዘመናዊ ትርጉም አንቀጾቹን መድቦ ማጠቃለያውን እንዲያቀርብ ተደርጓል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድ ማዕከላዊ ርዕሰ-ጉዳይ፣ እውነት፣ ወይም እሳቦት አለው፡፡ እያንዳንዱ ቅጂ ያንን ርዕስ በራሱ የተለየ መንገድ አጽዕሮቱን አስፍሯል፡፡ ጽሑፉን ስታነበው፣ የትኛው ትርጉም በርዕሰ ጉዳይም ሆነ በቁጥር ምድቦች ከአንተ መረዳት ጋር እንደሚስማማ ራስህን ጠይቅ፡፡

በእያንዳንዱ ምዕራፍ በቅድሚያ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ይኖርብናል፣ እንዲሁም ርዕሰ ጉዳዮቹን መለየት (አንቀጾቹን)፣ አኪያም የእኛን መረዳት ከአዲሶቹ ትርጉሞች ጋር ማወዳደር አለብን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ልንረዳ የምንችለው የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ ምን እንደሆነ የሱን አምክኖአዊ (ሎጂክ) እና አቀራረቡን ስንረዳ ነው፡፡ ዋነኛው ጸሐፊ ብቻ ነው ተመስጧዊው– አንባብያን መልዕክቱን ለመቀየርም ሆነ ለማሻሻል መብት የላቸውም፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢዎች ተመስጧዊውን እውነት በየዕለቱና በሕይወታቸው ሁሉ ተግባራዊ ለማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

**ማስታወሻ፦ ሁሉም ሙያዊ ቃላትና አጽሕሮተ ቃላት በሙሉ በቅጥያ አንድ፣ ሁለት፣ እና ሦስት ላይ ተብራርተዋል፡፡**

## ስነ መለኮታዊ መነሻው

A. የመልዕክቱ መግቢያ፡ በዮሐንስ ወንጌል መቅድም (1፡1-18) ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ስለነበረው ሁኔታ ከሚገልፀው መግቢያ ጋር ተመሳሳይነት አለው። ይህም ከዘፍጥረት 1፡1 (ስለ ስነ ፍጥረት) ከሚገልፅው ጋር አንድ ነው። ሆኖም በዚህ ጥቅስ ኢየሱስ በአደባባይ አገልግሎት መጀመሩን ለማመልከት ተጠቅሷል።

B. ትኩረቱም ፡
   1. ኢየሱስ ክርስቶስ ፍፁም ሰው መሆኑን
      ሀ. የሰው ልጅ የስሜት ህዋሳትን የሚያመለክቱትን ቃላት ማለትም ዕይታን ድምጹን ንኪኪን (ቁ1|3 ያስተያዩ) በመጠቀም ኢየሱስ በእውነትም ሰው መሆኑን ያሳያል።
      ለ. ለኢየሱስ በተጠቀሱ ማዕረጎች
         (1) የህይወት ቃል (ቁ.1 ይመልከቱ)
         (2) ልጁም ኢየሱስ ክርስቶስ (ቁ 3 ይመ.)
   2. የናዝሬቱ ኢየሱስ መለኮታዊነት
      ሀ. በቅደመ አለም (ከአለም መፈጠር በፊት መኖሩ (ቁ 1|2)
      ለ. *ሥጋ መሆኑ* (ቁ 2)

   እነዚህ እውነቶች ኖስቲሳዊያን ስለ አለም ባላቸው የተሳሳተ ትምህርት ላይ ያነጣጠሩ ናቸው።

## የቃላት አገባብ ጥናት

ሀ. ቁጥር 1-4
   1. ቁጥር 1-3ሀ ያሉት ቃላት መጀመሪያ በተፃፈበት በግሪክኛ አንድ አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ
   2. " እንነግራችኋለን " (ቁ 3)የሚለው ቃል አብይ ግስ የሐዋሪያትን ትምህርት ዋንኛ የትኩረት ነጥብ ያመለክታ።
   3. በቁ 1 አራት አዛማጅ አንቀጾችን እናገኛለን። እነሱም ትኩረት መስጠት ወደ ተፈለገበት ዋንኛ ይዘት ያመለክታሉ።
      ሀ. " ከመጀመሪያው የነበረውን "
      ለ. "የሰማነውን"
      ሐ. "በዐይኖቻችን ያየነውን›.
      መ. " የተመለከትነውንና በጆቻችን የዳሰስነውን "
   4. ቁጥር 2 የክርስቶስን *ሥጋ* መሆን በሚገልፀው ክፍል የሚጠቃለል አረፍተ ነገር ነው። የዚህ አረፍተ ነገር የተለየ ሰዋሰዋዊ አገባብ የአንባቢውን ሀሳብ ወደ ጭብጡ ለመሳብ ሆን ተብሎ የተደረገ ነው!
   5. ቀጥር 3 እና 4 ህብረትና ደስታ ፡ እነዚህ የዮሐንስን ሐዋሪያዊ መግለጫ ግብ የሚያመለክቱ የአይን ምስክርነት መግለጫዎች የቅዱሳት መፀሐፍት አንደኛው መለኪያዎችም ነበሩ።
   6. የቁጥር አንድን የንግግር ጊዜያት የሃሳብ ፍሰት ስንመለከት
      ሀ. በሀላፊ ጊዜ የተገለጸው ሂደታዊ እንቅስቃሴ (ከመጀመሪያውም የነበረ መሆኑን ለማመልከት)
      ለ. ተከናውነው ያለፉ ግን ውጤታቸውን የሚያሳዩ ግሶች (ሁል ጊዜ እውነት የሆነውን ለመግለጽ)
      ሐ. ባልተወሰነ ሀላፊ ጊዜ (በጊዜና በሁኔታ የተወሰኑ ምሳሌዎችን ለመግለጽ አገልግለዋል)

ለ. ቁጥር 1 ፡5-2፡2
   1. 1፡5-2፡2 የገቡት ተውላጠ ስሞች በጣም አሻሚ ናቸው ሆኖም ከቁትር 5 በስተቀር ሁሉም እግዚአብሔር አብን ያመለክታሉ። (ተመሳሳዩን ከኤፌሶን 1፡3-14 ይመ.)
   2. እ...| እን... የሚሉ ወደ ፊት ሊከናወን የሚችል ድርጊት የሚገልፁ ሦስተኛ መደብ ሁኔታ አመልካች አረፍተ ነገሮችን ያመለክታሉ።
   3. የሚከተሉት አገላለፆች በመካከላቸው የጎላ ስነ መለታዊ የሃሳብ ልዩነት አላቸው።
      ሀ. ሀጢያትን በሚመለከት በኃላፊና በአሁን ጊዜ ግሶች የተጠቀሰበት ሁኔታ
      ለ. በነጠላ ቁጥር "ኃጢአት" እና በብዙ ቁጥር ‹ኃጢአቶች› ተብሎ የተጻፈበት ሁኔታ

## መናፍቃን

ሀ. የመናፍቃን የተሳሳቱ አባባሎችን በቁጥር 1፡6|8|10፤2፡4|6|9 ላይ እናገኛለን።

ለ. ቁጥር 5-10 እግዚአብሔርን በማወቅ (ሰነ መለኮት) እና እግዚብሔርን በመከተል (ግብረ ገብ) መካከል ያለውን ልዩነት ለመግለጽ የተሞከረባቸው ናቸው። አገላለጹም ኖስቲሳዊያን በውቀት ላይ የበለጠ ትኩረት የሰጡበትን ሁኔታ ለመቀልበስ የተደረገ ነው። እግዚአብሔርን የሚያውቁ ባህሪያቱን በአኗኗራቸው ይገልጻሉ።

ሐ. ቁጥር 1-8- .2ከ ቁጥር 3፡ 6-9 ጋር ባንድነት መታየት የሚገባቸው የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው። ሁለት የተለያዩ ስህተቶችን ለማቃናት የተገለጹ ይመስላል።
   1. ስለ መለኮታዊ ስህተት (ኃጢአት የለም)
   2. የግብረ ገብ ስህተት(የኃጢአት ጉዳይ አያሳስብም )

መ. 1ኛ ዮሐ. 2፡1-2 ኃጢአትን በጣም አቅልሎ መመልከት (አንቲኖሚያኒዝም) እና በክርስቲኖች መካከል ከሚያገረሸው በስጋዊ አዕምሮ የመፍረድ፣ ለባህላዊ ሥራዓቶች ዕውቅና የመስጠትና የምንና ሕይወት ላይ የማትኮር ችግሮች መካከል ገደብ ለማበጀት የተደረገውን ጥረት ያሳያሉ፡፡

**የቃላትና የሐረግ ጥናት**

> **NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 1:1-4**
> **[1]ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያውም ስለነበረው |የሰማነውን |በአይናችንም ያየነውን የተመለከትነውንና እጃችን የዳሰሱትን እንናገራለን፡፡ [2]ሕይወትም ተገለጠ | እኛም አይተነዋል፤እንመሰክርለታለንም፡፡ በአብ ዘንድ የነበረውን |ለኛም የተገለጠልንን የዘላለም ሕይወት እንነበግራቸኋለን፤ [3]እናንተም ከእኛ ጋር ህብረት እንዲኖራችሁ |ያየነውንና የሰማነውን እንነግራችኋለን፤ ህብረታችንም ከአብ ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው፡፡ [4]ደስታችሁም ፍፁም ይሆን ዘንድ ይህን እንጽፍላችኋለን፡፡**

1:1 "ስለ" መልእክቱ ሁለት ሀሳቦችን ለማስተላለፍ በግኡዝ ጾታ ስመ ምትክ ይጀምራል፡፡ እነሱም
1. ስለ ኢየሱስ ያለውን መልዕክት
2. ስለ ኢየሱስ ማንነት (1፡8|10፤2፡20|24፤3፡11|14)፡፡ የወንጌል መልዕክት| ማንነትና ህይወትም ነው!

▣ "የነበረው" ይህ የሀላፊ ጊዜ ሂደታዊ ሁኔታ ገላጭ ግስ ክርስቶስ ከመጀመሪውም የነበረ መሆኑን ይገልጣል፡፡ (ይህውም በዮሐንስ ጹህፎች በተደጋጋሚ የተጠቀሰ ጭብጥ ነው፡፡ ቁጥር 2፤የሐ1፡1|15፤ 3፤13፤8፡57-58|17፡5 ያስ.) አገላላጹም የመለኮታዊነቱ አንደኛው ማሳያ ነው፡፡ ኢየሱስ አብን የሚገልጸው ከመጀመሪያውም ከአብ ጋር ስለ ነበር ነው፡፡

▣ "ከመጀመሪያው" ቃሉ ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 እና ዮሐንስ ወንጌል ምእራፍ 1 ያመለክታል፡፡ በዚህ ክፍል ኢየሱስ ይፋ አገልግሎት መጀመሩን ለማመልከት ነው፡፡(ተጨማሪ የጥናት አርዕስት፡ አርኬ ዮሐ. 1፡1 ይመ.)፡፡ የኢየሱስ መምጣት "ሁለተኛ ዕቅድ አይደለም) ወንጌል ምንም ጊዜ ቢሆን የእዚአብሔር ድህነት የማወጀት ዕቅድ ነበር (አፍጥረት 3፡15፤ የሐዋሪያት ሥራ 2፡23፤ 3፡18፤3፡29) ይህ ሐረግ በዚህ አገባብ አስራሁለቱ ሐዋሪያት ከክርስቶስ ጋር በአካል የተገናኙበትን ሁኔታ ለማመልከት ተጠቅሷል፡፡

ዮሐንስ" መጀመሪያ"(አርኬ) የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ በተደጋጋሚ ይጠቀማል፡፡ በመሰረቱ ቃሉ የተጠቀሰባቸውን ቦታዎች በሁለት ክፍሎ ማየት ይቻላል፡፡

1. በስነ ፍጥረት
   - ሀ. ዮሐንስ ወንጌል 1፡1|2 (ኢየሱስ ከመጀመሪያውም ነበር)
   - ለ. ዮሐ 8|44፤1ኛ ነገስት 3፤8 (ሰይጣን ከመጀመሪያውም ነፍስ ገዳይና ሀሰተኛ ነበር)
   - ሐ. ራዕይ 3፡14|21፡6|13 (እየሱስ የመጀመሪያውና የመጨረሻው)
2. በኢየሱስ ሥጋ መሆንና ይፋዊ አገልግሎቱ
   - ሀ. ዮሐንስ 8፡25፤16፡4፤ 1ኛ ዮሐንስ 2፡7 [ሁለት ጊዜ ] ፤ 3፡11፤ 2ኛ ዮሐ 5፡6 (በኢየሱስ ትምህርቶች)
   - ለ. ዮሐ 15፡27፤16፡4 (ከኢየሱስ ጋር)
   - ሐ. 1ኛ ዮሐ 1፡1 (እየሱስ ይፋ አገልግሎት ከመጀመሩ ጋር በተያያዘ)
   - መ. ዮሐ ወንጌል 6፡64 (እየሱስን ያላመኑና አሳልፈው ስለሚሰጠው ከመጀመሪያውም ያውቅ ነበር)
3. የጥናት ጥቅሱ አውደ ንባብ ከላይ በተራ ቁጥር ሁለት የተጠቀሰውን ይደግፋል፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ ዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 1 ከ1ኛ ዩሐንስ ምዕራፍ 1 ንጽጽር**

| | <u>ወንጌል</u> | <u>መልዕክት</u> |
|---|---|---|
| 1. | በመጀመሪያ(1፡1|2 | ከመጀመሪያው (1፡1) |
| 2. | ቃል (ሎጎስ) (1፡6) | ቃል ( ሎጎስ) (1፡1) |
| 3. | ሕይወት (ዞኤ) (1፡4) | ሕይወት (ዞኤ) (1፡1|2) |
| 4. | እራሱ ብርሃን (1፤4) | እግዚአብሔር ብርሃን ነው(1፤5) |
| 5. | ብርሃንም ተገለጠ(1፡4) | ብርሃንም ተገለጠ( 1፡5) |
| 6. | ጨለማ (1፡5) ብርሃንም | ተገለጠ(1፡5) |
| 7. | ስለብርሃን ምስክርነት ( 1፡6-8) | ስለብርሃን ምስክርነት (1፡3|5) |
| 8. | ሰዎችም ወደ እግዛቤሔር እንዲቀርቡ (1፡7|12-13) | ሰዎችም ወደ እግዚአቤሔርእንዲቀርቡ ( 1፡3) |
| 9. | ክብሩን አይተን ( 1፡14). | ክብሩን አይተን( 1፡1-3) |

▣ "እኛ" ሁሉም ሐዋሪያት የጋራ የሆነ ነገር ግን እያንዳንዱ በግሉ የሚሰጠውን ምስክርነት ያመለክታል(ማለትም የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች) ይህ የጋራ የሆነ ምስክርነት 1ኛ ዮሐንስ የተለየ ገጽታ ነው፡፡ ቃሉ ከ50 ጊዜ በላ ተጠቅሶ እናገኛለን፡፡

አንዳንዶች ይህን ጥቅል ስመ ምትክ ‹የዮሐንስ የተለመደ አገላለጽ› ይሉታል፡፡ ይህንንም የዮሐንስ ትምህርት ጠባቂዎችና አስተማሪዎች የተለየ ሰነ መለኮታዊ እይታን ያሳያል፡፡

▣ "**የሰማነውን . . . ያየነውን**" ሁለቱም የሀላፊ ጊዜ ድርጊት ሂደታዊ ውጤት አመልካቾች ሲሆኑ ትኩረቱም ውጤታቸው ቀጣይ መሆኑን ማመለከት ነው ዮሐንስ ከስሜት ሕዋሳት ጋር በተገናኘ በቁጥር 1 |3 ቦዝ አንቀጾችን በመጠቀም የናዝሬቱ ኢየሱስ የህይወትና የአይን ምስክር መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

▣ "**የተመለከትነውን … የዳሰስነውን**" በሀላፊ ጊዜ የተጠቀሱት ሁለቱ ቃላት ትኩረት የሚሰጣቸውን የተወሰኑ ድርጊቶችን ያመለክታሉ፡፡ "የታየ"ማለት በቅርበት ማየትን (ዮሐ 1፡14 ያስ.) " የተዳሰሰ" ማለት በጥልቀት የተመረመረ (ዮሐ 20፡20|27 |ሉቃስ 24፡39 ያስ.) ያመለክታሉ፡፡

"የተዳሰሰ ወይም "የተያዘ" በግሪክኛ (ሴላፖዎ) በሁለት የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ተጠቅሶ እንመለከታለን፡፡ በዚህና በሉቃስ 24፡39 ቃሉ በሉቃስ| ከትንሣኤ በኋላ ከክርስቶስ ጋር በተገናኘ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ በ1ኛ ዮሐንስም ተመሳሳዩን አገባብ ለመግለጽ ተጠቅሷል፡፡

▣ **የሕይወት ቃል** (ሎጎስ)፣ በዮሐንስ ወንጌል መግቢያ እንደተጠቀሰው (1፡1 ያስ.)ሎጎስ የተሰኘው ቃል የግሪካዊያንን የሀሰት ትምህርት መምህራን ትኩረት ለመሳብ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአይሁዳዊያን የህይወት ታሪክ መነሻ ውስጥ የተለየ ቦታ ነበረው፡፡(ዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 1 መግቢያን ያስ.) በዚህ ክፍል ሀረጉ የወንጌሉን ይዘትና ውጤቱን ያመለክታል፡፡

1፡2 ይህ ጥቅስ "ሕይወት" የሚለውን ቃል የሚገለጸው አረፍተ ነገር ክፍል ነው

▣ "**ሕይወት**" ***ዞዌ*** (በቁጥር 2 ጊዜ) በዮሐንስ ጽሁፎች መንፈሳዊ ሕይወት|የትንሳኤ ሕይወት|አዲስ ሕይወት|ወይም ከእግዚአብሔር የሆነውን ለመግለጽ በወጥነት አገልግሏል (1፡4፤3፡15|36[ሁለት ጊዜ]፤ 4፡14|36፤ 5፡24[ ሁለት ጊዜ] |26[ ሁለትጊዜ]|29፣39|40|6፡27|33|35|40|47|48፣51|53|54|63|68፣8፡12፣10፡10፣28፣11፡25፣12፡25፣50፣14፡6፣17፡2፣3፤20፡3 1፤1ኛዮሐ.1፡1፣2፤2፡25፤3፡14፣15፤5፡11፣12፣13፣16፣20)፡፡ ኢየሱስ ራሱን "ሕይወት" ብሎ ጠርቷል (ዮሐ.14፡6)፡፡

▣ "**ተገለጠ**" በዚህ ጥቅስ ውስጥ ቃሉ ሁለት ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ ሁለቱም የሀላፊ ጊዜ የድርጊት አመልካች ግስ በመሆን ያገለግላሉ፡፡ ድርጊት ገላጮች ብዙን ጊዜ የእግዚአብሔር አብን ስራዎች ያመለክታሉ፡፡ (ፖነራው) ያለውን ነገር ወደ ብርሃን ማውጣትን ይገልፃል፡፡ እነዚህ የተለመዱ የየሐንስ ቃላት ናቸው (ዮሐንስ 1፡31 ያስ.)፡፡ ሀላፊ የንግግር ጊዜ በመጠቀም ሀሰተኞች የካዱትን የእየሱስን ስጋ መሆን አጽኖት ለመስጠት ነው፡፡

▣ "**እንመሰክራለን**" ይህ የአሁን ጊዜ፣ አዲራጊ አመልካች ግስ የዩሃንስን የህይወት ልምምድ ያመለክታል፡፡ ቃሉ በፍርድ ቤት የሚሰጥ የምስክርነት ቃል ነው፡፡ በልዩ ትምህርት ክፍል ስለኢየሱስ መመስከር ዮሐ. 1፡8 ይመልከቱ፡፡

▣ "**እናወራላችኋለን**" ይህና በተመሳሳይ ሁኔታ በአሁን ጊዜ አድራጊ አመልካች የተገለጸ ሲሆን በትምህርቱና በጽሁፎቹ የተገጠውንና የተመዘገበውን የዮሐንስን የታመነ ምስክርነት መረጃ ያመለክታል፡፡ይህ የቁጥር 1-3 አብይ ግስ ሲሆን ሁለት ጊዜ ተጠቅሷል(ቁ 2 እና 3)፡፡

▣ "**ከአብ ዘንድ የነበረውን**" እንደ ቁጥር 1| ይኸኛውም እየሱስ በፊትም የነበረ መሆኑን ያረጋግጣል ከዮሐንስ 1፡1 ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ አምላክም ሥጋ ሆነ (የሐ 1፡14 ያስ.) እየሱስን ማወቅ እግዚአብሔርን ማወቅ ነው፡፡(ዮሐንስ 14፡8-11) በዚህም ዮሐንስ ከላይ ወደ ታች ከታች ወደ ላይ የሆነውን የሁለትዮሽ ህብረት ለመግለጽ የተጠቀመበት ምሳሌአዊ መግለጫ ነው፡፡

1፡3 "**ያነውንና የሰማነውን ለእናንተ ደግሞ እናወራላችኋለን**" ይህ ከቁጥር አንድ የቀጠለ የቁጥር ሁለት ቅጥያ አረፍተ ነገር 5ኛው አዛማች አንቀጽ ነው፡፡ ስለ ማየት በቁጥር 1 የተጠቀሰውን ይደግማል፡፡

▣ "**እናወራላችኋለን**" ከላይ እንደተጠቀሰው ከቁጥ1-3 አብይ ግስ ያሁን ጊዜ አድራጊ አመልካች ግስ ነው፡፡እግዚአብሔርን ማወቅ ከልጆቹም ጋር ህብረት ማድረግን ጭምር ይጠይቃል!

▣ "**ከእኛ ጋር ህብረት እንዲኖራችሁ**" በዚህ አንቀስ ውስጥ (ሂና) የሚለው ቃል አድራጊው ሊያከናውነው በሚችለው ግስ መጠቀሱ የወንጌሉን ቃል ከዚህ በፊት ያልሰሙና ኢየሱስንም ያላዩት ሰዎችም ቢሆኑ በሐዋሪያት የምስክርነት ቃል በማመን መዳን እንደሚችሉ ለመግለጽ ነው፡፡ (ዮሐንስ 17 ፡20፤20፡29-31 ያስ.) ይህም የመገለጥ ፀጋ በሚያስገኘው ህብረት

ውስጥ የሚገኘውን“ ደስታ”| “ሰላም” “እርግጠኛነትን” ያመለክታል፡፡! ቤተ ክርስቲን የአማኞች ማህረሰብ| የምዕመናን ህብረት ናት! ወንጌል ለአለም ሁሉ ነውና፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ *ኮይኖኒያ***

“ህብረት ”(ኮይኖኒያ) የተሰኛው ቃል

1. ከሰዎች ጋር ያለንን የተቀራረበ ግንኙነት
   - *ሀ.* ከልጁ ጋር (1ኛዮሐ 1፡6፤ 1ኛቆሮ 1፡9 ያስ.)
   - *ለ.* ከመንፈስ ቅዱስ ጋር (2ኛ ቆሮ 13፡13፤ ፊልጶስ 2፡1)
   - *ሐ.* ከአብና ከወልድ ጋር (1ኛ ዮሐ 1፡3 ያስ.)
   - *መ.* ከሌሎች የቃልኪዳን ወንድሞችና እህቶች (1ኛ ዮሐ 1፡7 ሐዋሪያት ሥራ 2፡42፤ገላቲያ 2፡9 ፊሊሞና17)
2. ከነገሮች ጋር ያለውን የተቀራረበ ግንኙነት
   - *ሀ.* ከወንጌል ጋር (ፊልጶስ 1፡5፤ፊሊሞና 6)
   - *ለ.* ከክርስሰቶስ ደም ጋር (1ኛ ቆሮ 10፡16 ያስ.) (ፊልጶስ 3፡10፤4፡14 1ኛ ጴጥሮስ 4፡13)
   - *ሐ.* ከጨለማ ጋር አለመተባበር (2ኛ ቆሮ 6፡14)
   - *መ.* መከራን አብሮ በመካፈል (ፊልጵ.3፡10፡4፡14፤1ኛ ጴጥሮስ4፡13)
3. በልግስና በመስጠት አገልግሎት (ሮሜ 12፡13፤15፡26፤2ኛቆሮ 8፤4፤9፡13፤ፊልጶስ 4፡15፤ ዕብ 13፡16)
4. በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል እግዚአብሔር በነፃ ስጣታው የሰው ልጆችን ከራሱና እርስ በእርስ ወንድማማቾች እና የእትማማቶች ህብረት በመመስረት ሥራው፤

ይህም ከታች ወደ ላይ(ሰው ከፈጣሪ) ህብረት ውጤት የሆነው የጎንዮሽ ህብረት (ሰው ከሰው ) ያመለክታል፡፡ ከዙህ በተጨማሪ የክርስቲያን ማህበረሰብ አስፈላጊነትና ደስታንም ያመለክታል፡፡ቃሉ ብቻ ሳይሆን የተተቀሰበት የንግግር ጊዜ ጭምር የክርስቲያን ህብረት ጅማሬና ቀጣይነት ያረጋግጣል፡፡(1፡3፤[ሁለት ጊዜ]|6፡7 ያስ.) ክርስትና ህብረት ነው ነው !

**ልዩ ርዕስ፡ ክርስትና ህብረት ነው**

- *ሀ.* ዩሐንስና ጴጥሮስ የተጠቀሚቸው የህብረት ምሳሌዎች
  1. አካል
  2. የእርሻ ማሳ
  3. ህንፃ
- *ለ.* “ቅዱሳን” የሚለው ቃል ሁሌም ብዙ ቁጥርን ያመለክታል(ፊልጶስ 4፤21|በዚህ ጥቅስም ቢሆን ጥቅስም ህብረትን ያመለክታል)
- *ሐ.* የነማርቲን ሉተር የተሃድሶ ዘመን ትኩረት የነበረው ያማኝ ካህን የመሆን ሃሳብ በመሠረቱ መጸሐፍ ቅዱስአዊ አይደለም ምክንያቱም ምእመናን ሁሉም ካህናት ናቸውና ዘፀአት 19፡6፤ 1ኛ ጴጥሮስ 2፡5|9፤ራዕይ 1፡6)
- *መ.* እያንዳንዱ ምዕመን መንፈሳዊ ስጦታ የተቀበለው ለመንጋው የጋራ ጥቅም ነው፡፡( ቆሮ 12፡7 ያስ.)
- *ሠ.* የእግዚአቤሔር ሰዎች ውጤታማ የሚሆኑት በህብረት ውስጥ ነው፡፡ አገልግሎቱም ህብረት ነውና (ኤፌ 4፡11-12)

▣ **“ከአብ … ከልጁም ከእየሱስ ክርስቶስ ጋር”** *እነዚህ ሀረጋት የመሰተዋድዳዊና የተወሰነ አመልካች ሰዋሰውዊ ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የቃላት አገባቡ ኢየሱስ ከአብ ጋር ያለውን እኩልነትና መለኮታዊነቱን ያመለክታል* (ዮሐ 5፤18|10፡33|19፡7 *ያስ.) የሐሰት ትምህርት መምህራን እንደሚሉት ሳይሆን መንፈስ የሆነው አብ በሥጋ ከተገለጠው ከልጁ ተለይቶ ሊኖር አያችልም* (1ዮሐ 2፡23፤5፡10-12 ያስ.)፡፡

በአብና በልጁ መካከል ያለው ህብረት በዮሐ 14፡23 ከተጠቀሰው አንዱ በሌላኛው የመገኘት ሀሳብ ጋር አንድ ነው፡፡

1:4 **“ይህን እንጽፍላችኂለን”** ጠቅላላ መልዕክቱን ወይም ከቁጥር 1-3 የተጠቀሰውን ሊመለክት ይችላል፡፡ ተመሳሳይ አሻሚ አገላለጽ በ2:1 መልዕክቱን ስለ ጻፈበት ዓላማ በገለጸበት ክፍል እንመለከታለን (2:1)::

▣ **“ደስታችሁም ፍጹም ይሆን ዘንድ”**በሁኔታዎች ሊወስን በሚችል የሀላፊ ጊዜ (ዮሐ 15፡11፤16፡20፤20|22|24፤17፡13|2ኛ ዮሐ 12|3ኛዮሐ 4) *የአማኞች ደስታ ከአብ ከልጁም ከኢሱስ ክርስቶስና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ባለ ህብረት ፍጹም ይሆናል፡፡ ይህ ትምህርት ከሀሰተኞች መምህራን አጥፊ ነፋቂ አኳያ ሲታይ በጣም አስፈላጊ መረዳት ነው፡፡ ዮሐንስ መልክቱን የጻፈባቸው ምክንያቶች፤*

1. ከእግዚአብሔርና ከመንፈሰዊ ልጃቹ ጋር ስላለው ህብረት ለመግለጽ፣
2. በዚህም ስለሚገኝ ደስታ፣

3. ስለሕይወት ቃል እርገጠኛ ስለመሆን ፣
4. በአሉታዊ ጎኑ|ከኖስቲስዊያን የስህተት ትምህርት አኳያ አማኞችን ለማዘጋጀት፡፡

የጥቅሱን አተረጓጎም በሚመለከት በትርጉም ሥራዎች ልዩነት አለ፡፡
1. ደስታችን- ኤም ኤስ ኤስ ጰ፣ቢ|ኤል፣ኤን ኤ ኤስ ቢ|ኤን አር ኤስ ቪ|ኤን ጄቢ|
2. ደስታችሁ-ኤም ኤስ |ኤስ| ኤ|ሲ|ኤን ኬጄቪ

ዩቢኤስ 4ኛ ቁጥር 1 ን ይደግፋል "እኛ" ሲል የሐዋሪያትን የአይን ምስክርነት ወይም የአማኞችን ምስክርነት ለመግለጽ ነው፡፡ በ1ኛ ዮሐንስ ክርስቲያኖች እርግጠኛ እንዲሆኑ ከሚገልፀው አኳያ ከሆነ ምዕመናንን በሙሉ ያመለክታል፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 1.5-2፡2
[5]ከእርሱ የሰማነው ለእናንተም የምንነግራችሁ መልክት|እግዚአብሔር ብርሃን ነው፡፡ ጨለማ እየተመላለስን ከእርሱ ጋር ኃብረት አለን ብንል እንዋሻለን እውነትንም እንኖረውም፡፡ ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ|እኛም በብርሃን ብንመላለስ እርስ በእርሳችን ኃብረት አለን፡ የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል፡፡
[8]የለብንብም ብንል|ራሳችንን እናስታለን፣እውነትም በእኛ ውስጥ የለም፡፡[9]ኃጢአታችንን ብንናዘዝ ታችንን ይቅር ሊለን|ከዐመጻ ሁሉ ሊያነፃን እርሱ ታማኝና ጻድቅ ነው፡፡[10] ኃጢአት አልሠራንም ብንል|እርሱን ሐሰተኛ እናደርገዋለን፣ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም፡፡ 2.ልጆቼ ሆይ፡ ይህን የምጽፍላችሁ ኃጢአት እንድትሠሩ ነው፡፡ ነገር ግን ማንም ኃጢአት ቢሠራ|በአብ ዘንድ ጠበቃ አለን፡ እርሱም ጻድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡[2] እርሱም የኃጢአታችን ማስተሰሪያ ነው፡፡ ይኸውም ለዓለም ሁሉ ኃጢአት እንጂ ለእኛ ብቻ አአይደለም፡፡

1.5. **"ከእርሱ የሰማናት ... መልዕክት"** በተውሳጠ ስምነት የገባው "እኛ " የሚለው ቃል ዮሐንስም ሆነ ሌሎችም የዓይን ምስክሮች እና በምድራዊ አገልግሎቱ ከየሱስ የሰሙትን ተከታዮችን ያመለክታል፡፡ 2፡1 "እናንተ" በማለት በቀትታ አንባቢዎቹን ይጠቅሳል፡፡ እነዚህ ምናልባትም በትንሿ እስያ የሚገኙ አቢያተ ክርስቲያናት ይሆናሉ፡፡
"እኛ የሰማነው"የሚለውን ያለፈ ድርጊት ውጤት በአሁን ውጤት አመልካች ግስ መጠቀሱ በአካል ህያው ምስክር መሆኑን አጉልቶ ለማሳየት(1፡ 1-4) በተደጋጋሚ የሚጠቀስ ቃል ነው፡፡ በዚህም ኢየሱስ ሲያስተምር ሐዋሪያው ዮሐንስ በአካል የነበረበትን ሁኔታ ለመግለፅ ተጠቅሟል፡፡ በዚህም ዮሐንስ የራሱን ሳይሆን የኢየሱስን መገለጥ ስመሰክር እንመለከታለን!"እኔ ነኛ" የሚለው የወንጌሉ መልዕክት እየሱስ ሲናገር የሰማው አንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

▣ **"ከእርሱም"** በመላው 1፡5-2፡2 ኢየሱስን ለማመልከት የገባ ስመ ምትክ ነው፡፡ ኢየሱስ አብን ለመግለጥ መጥቷል(ዮሐ 1፡18 ያስ. ከስነ መለኮታዊ ፋይዳው አንጻር እየሱስ የመጣበትን ዓላማ በሶስት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡
1. አብን ለመግለጥ (1፡5 ያሰ.)
2. ለአማኞች የሕይወት ምሳሌ ለመተው (1፡7 ያስ.)
3. ኃጢአተኛ በሆነው የሰው ልጅ ምትክ ለመሞት (1፡7፤2፡2 ያስ.)

▣ **"እግዚአብሔር ብርሃን ነው"** ባልተወሰነ አመልካች መጠቀሱ የመገለጥና ግብረገባዊ የሆነውን የእግዚአብሔርን ባህሪ በአጽኖኦት ለማመልከት ነው፡፡ (መዝ.27፡1፤ኢሳያስ 60፡20 ሚካ 7፡8 1ኛ ጢሞ 6፡16 ያዕ 1፡17 ያስ.)፡፡ ኖስቲሳዊያን የስህተት ትምህርት መምህራን ብርሃንና ዕውቀትን ብቻ ያመለክታል ብለው ያስተምራሉ፡፡ ዮሐንስ ግን የስነምግባር ንፅህናን ጭምር እንደሚመለክት ይገልጻል፡፡ "ብርሃንና ጨለማ" የተለመዱ ቃላት ናቸው (የሁለቱም ባህሪያት ሃሳብ በሙት ባህር ጥቅልሎችና በጥንታዊ የኖስቲሳያዊን ሥራዎች ውስጥ ያገለግል ነበር) ለመልካምነትና ለክፋት መገኘት ምሳሌ ሆኖ ይጠቀሳል፡፡(ይህም ዮሐ 1፡5፤8፡12፤12፡46) በተጨማሪም ኖስቲሳያዊን ነገሮችን መንፈስና ቁስ አካል በማለት የሚከፋፍሉትንም ሊያመለክት ይችላል ቃሉን ዮሐንስ ቀለል ባለ ነገር ግን ጥልቅ በሆነ የሰነ መለኮት አገላለጽ ስለ ክርስቶስ አምላክነት የገለፀበት መንገድ ነው፡፡ ሌሎች ተመሳሳይ ቃላት (1) "ፍቅር ነው፡፡" (ከ 4፡8|16ያስ.) እና (2) እግዚአብሔር መንፈስ ነው፡፡ (ዮሐንስ 4፡24 ያስ) እግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ያሉ እንደ እየሱስ (ዮሐ 8፡12 95) |ባህሪውን ማንጸባረቅ አለበት(ማቴ 5፡14) እነዚህ በፍቅር በይቅርታና በንጽህና እውነተኛ የህይወት ለውጥ የመኖሩ ማረጋገጫዎች ናቸው፡፡

▣ **"ጨለማም በእርሱ ዘንድ ኮቶ የለም"** በሁለት አሉታዊ ቃላት መጠቀሱ ለጉዳዩ ክብደት ለመስጠት ነው፡፡ይህም የማይለወጠውን እግዚአብሔርን 嫘ቅድስና ባህሪይ ያመለክታል (1ኛ ጢሞ 6፡16፤ያዕቆ 1፡17 መዝ 102፡27 ሚል 3፡6)

1፡6. **"ብንል"** ከበርካታ ለሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ አረፍተ ነገር መጀመሪያው ሲሆን የሐሰትኖችን አቋም ያመለክታል 1፡8|10፤2፡4|6|9) እነዚህ አገላለፆች የሀሰተኞችን አባባል ለመለየት ብቸኛ መንገዶች ናቸው፡፡ በዚህ ክፍል የተገለፁት ጥንታዊና የመጀመሪያዎቹ ኖስቲሳዊያን ናቸው፡፡
ስነጽሁፋዊ አቀራረቡ በተቃዋሚዎች ላይ የተሰነዘረ የቃላት ጥቃት ሲሆን እውነት በጥያቄና መልስ መልክ የሚቀርብበት መንገድ ነው፡፡ አቀራረቡ በሚልኪያስ ትንቢት በግልጽእንመለከታለን፡፡ (1፡2|6|7፤12፤2፡14|17፤3፡7|14)እና በሮሜ መልክት(2፤3|17|21|23፤1፤3|7-8|9|31፤፤9፤4፡1፤6፡1፤7፡7 ያስ)

▣ **"ከርሱ ጋር ህብረት አለን"** ሐሰተኞች የህብረት መሠረት እውቀት ነው ብለው ያስተምራሉ፡፡ይህም ከፕሌቶ ተወሰደ የግሪካዊን ፍልስፍና ነው፡፡ ሆኖም ዮሐንስ ክርስቲያኖች ክርስቶስን የሚመስል ህይወት በመኖር እንደሚታወቁ ይገልፃል፡፡ (ቁ 7፤ዘለ 19:2፤20:7፤ ማቴ 5:48 ያስ.) ተጨማሪ የትምህርት አርዕስት 1:3 ይመ.)

▣ **"በጨለማም ብንመላለስ"** "መመላለስ" ሊሆን የሚችል ድርጊት አመልካች የአሁን ጊዜ ግስ ነው ግብረገባዊ የሕይወት ዘይቤን ለመግለጽ መፀሐፍ ቅዱስ የሚጠቀመው ምሳሌ ነው (ኤፌ 4:1|17፤5:2|15 ያስ.) እግዚአብሔር ብርሃን ነው ጨለማም በርሱ የለም ልጆቹም እርሱን ሊመስሉ ይገባል ማቴ 5፤48)

▣ **"እንዋሻለን፤እውነትንም አናደርግም"** እነዚህ ሁለት የአሁን ጊዜ አመልካች ግሶች ናቸው፡፡ ዮሐንስ ሀሰተኛ የሚላቸው የተላዩ የሐይማኖት ሰዎች (1:10፤2:4|20፤4:20፤ኢሳያስ 29:13 ያስ.) የአኗኗር ዘይቤ በልባችን ያለውን ይገልጣል (ማቴ 7ያስ.)እውነት በዮሐንስ ጽሁፎች የሚለውን ከተጨማሪ የትምህርት አርዕስት 6:55 ይመልከቱ፡፡

1:7 **"ነገር ግን .... በብርሃን ብንመላለስ"**ይህ ሌላኛው ቀጣይ ድርጊት አመልካች የአሁን ጊዜ ግስ ነው፡፡ "መመላለስ" አዲስ ኪዳን የክርስቲያኖችን አኗኗር የሚገልጽበት ምሳሌአዊ አባባል ነው፡፡ (ኤፌ 4:1፤5:2|15 ይመ.)

የአሁን ጊዜ ግስ እና "መመላለስ" የሚለው ቃል ከክርስቲን ሕይወት ጋር እንዴት እንደተገናኛ ያገናዝቡ፡፡ እውነት የምናውቀው ብቻ ሳይሆን የምንኖርበት ነው! በዮሐንስ ፅሁፎች እውነት ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ ተጨማሪ ትምህርት አርዕስት 6:55 እና 17: 3 ይመልከቱ፡፡

▣ **"እርሱ በብርሃን እንዳለ"** አማኞች ማሰብም ሆነ መኖር ያለባቸው እግዚአሔርን የመምሰል ህይወት ነው፡፡ (ማቴ5:48 ይመ.) በዚህ ጨለማ አለም የእርሱን ባህሪ ማንጸባረቅ ይኖርብናል፡፡ ድህነነት በዘፍጥረት 3 በፍጥረት ውድቀት ምክኒያት ከሰዎች ህይወት የጠፋውን እግዚአብሔርን የመምሰል ባህሪ መመልስ ነው፡፡ (ዘፍ 1:26|27)

▣ **"ለእያንዳንዳችን ህብረት አለን"** ህብረት ተብሎ የተተረጎመው በግሪክኛው ኮይኖኒያ ማለት በሰዎች መካከል በጋራ ተሳትፎ ላይ የተመሠረተ ግንኙነትን ያመለክታል፡፡ (ከተጨማሪ የትምህርት አርዕስት ጥናት 1:3 ይመ.) ክርስትና የክርስቶስ ህይወት ላይ የተመሠረተ የአማኞች ህብረት ነው፡፡ የይቅርታ ህይወቱን ከተቀበልን የፍቅር አገልግሎቱንም መቀበል ይኖርብናል፡፡ (1ኛዮሐንስ 3:16 ያስ.) እግዚአብሔርን ማወቅ የተጨበጠ ህብረትና እርሱን የመምሰል ህይወት እንጂ ምናባዊ እውነት ብቻ አይደለም፡፡ የክርስትና ግቡ ስንሞት ስለምንወርሰው ሰማይ ብቻ ሳይሆን በምድራዊ ህይወት ሳሉ ክርስቶስን የመምሰል ጉዳይ ጭምር ነው፡፡ ኖስቲሳዊያን ግን ምናብዊ ዕውቀት ላይ ብቻ ያተኩራሉ፡፡ ነገር ግን አንድ ሰው ከ እግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ህብረት ካለው ከክርስቲያን ወገኖቹ ጋር ጤናማ ግንኙነት ይኖረዋል፡፡ ለሌሎች ክርስቲኖች የፍቅር መታጣት ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት ላይ ችግር መኖሩን ያንፀባርቃል (4:20-21እና ማቴ 5:7፤6:14-15፤18:21-35)::

▣ **"የኢየሱስ ደም"** ክርስቶስ ራሱን መስዋት ያረገበትን ሞት ያመለክታል፡፡ (ኢሳ 52:13-53|12፤ማርቆስ 10:45 2ኛ ቆሮ 5:21) 2: 2" በምትካችን መሞቱ የኃጢያታችን ማስተሰሪያ መሆኑን" ከሚገልፀው ጋር አንድ ነው፡፡መጥምቁ ዮሐንስ " እነሆ የዓለምን ሀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ "በማለት የሰጠው ምስክርነት ይህንኑ ያመለክታል(ዮሐ 1:29) የክርስቶስ ሞት በበደለኛ ምትክ የተፈጸመ የንፁህ ሰው ሞት ነው፡፡

ጥንታዊው የኖስቲሳዊያ አመለካከት ኢየሱስ ፍጽም ሰው መሆኑን ይክዳል፡፡ ዮሐንስ " ደም የሚለውን ቃል በመጠቀም"የኢየሱስን ፍጽም ሰው መሆን ይረጋገጣል፡፡

የመጀመሪያዎቹ ግሪክኛ እጅ ፁሕፎች ቅጅ ስሙን በሚመለከት ልዩነት ይታይባቸዋል፡፡

1. ኢየሱስ - ኤን ኤስብ |ኤን አር ኤስቪ አርኢብ|ኤን ኢቲ
2. ክርስቶስ - ኤም ኤስ ኤስ፣ ጆ፣ቢ|ሲ
3. ኢእየሱስ ክርስቶስ - ኤን ኬጄ

ባርት ዲ ኤርማን፣ *ዘ ኦቶዶክስ ኮራፕሽን ኦፍ ስክሪፕቸር* በተሰኘው መፀሐፉ ጥንታዊያን ፀሐፊዎች ፁህፎችን ሲገለብጡ በወቅቱ የነበሩትን የሀሰት ትምህርቶችን ለማቃናት ሲሉ ይበልጥ ለማብራራት በማሰብ ያዛቡበትን ሁኔታ በማውሳት በምሳሌነት ከሚያቀርባቸው ጥቅሶች አንዱ ይህ ነው፡፡ሦስተኛው ተራቁጥር አማራጭ ጥንታዊ የእጅ ጹሕፎች መካከል ያለውን ልዩነት የሚያስታርቅ ይመስላል፡፡

▣ **"ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል"** ይህ በአሁን ጊዜ አድራጊ አመልካች ግስ የተጠቀሰ ነው፡፡"ኃጢአት"የተሰኘው ቃል ባልተወሰነ አመልካች የተጠቀሰ ነው፡፡ ይህም የኃጢአት አይነቶችን ሁሉ ለማመልከት ነው፡፡ጥቅሱ ስለአንድ ጊዜ ከኃጢአት መንጻት (ድነት ቁ 7) ላይ ለማትኮር ሳይሆን ስለተከታታይ የመንጻት(ሂደት(የክርስትና ህይወት ቁ 9) ሲያመለክቱ ሁለቱም የክርስትና ሕይወት ልምምድ ክፍል ናቸው(የሐንስ 13:10 ያስ.)

1:8. **"ኃጢአት የለብንም ብንል"** ይህ ሌላኛው ሦስተኛ መደብ ሁኔታን አመልካች ዐ.ነገር ነው አማኞችን ጨምሮ በወደቀው አለም ኃጢአት እውን መሆኑን (ሮሜ 7 ያስ.) ያረጋግጠል፡፡ የዮሐንስ ወንጌል ይህን ጉዳይ በተደጋጋሚ ይገልፃል (9:41፤15:22|24፤19:11) ይህ ጥቅስ አሁንም ሆነ ጥንት የስነ መግባር ሀላፊነት ሽሽትን ይቃወማል፡፡

▣ **"ራሳችንን እናስታለን"** ይህ ሐረግ በግሪከኛው ባለማወቅ ምክንያት የሚፈፀም ስህተት ሳይሆን አንድ ሰው ሆነ ብሎ እውነትን የሚክድበትን ሁኔታ ያመለክታል።

▣ **"እውነትም በእኛ ውስጥ የለም"** ቅዱስ በሆነው በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባነትን ማግኘት ኃጢያታችንን የመካድ ሳይሆን የተደረገልንን መቀበል ነው።(ሮሜ 3፡21-31) "እውነት "ስለኢየሱስ ያለውን መልክት ወይም ስለኢየሱስ ስለራሱ ሊሆን ይችላል።(የሐ 14፡6) ተጨማሪ የጥናት አርዕስት (የሐ 6፡55 እና 17፤3 ይመ.)

1:8፣9 **"ብ…"** እነዚህ ወደ ፊት ሊፈፀሙ የሚችሉ ሦስተኛ መደብ ሁኔታን አመልካች ዐ.ነገሮችን ናቸው።

1:9 **"ብንናዘዝ"** ይህ ቃል " መናገርና እና" "አንድነት " ከሚሉ ጥንድ ግሪክኛ ቃላት የተመሠረተ ሲሆን አማኞችም ከእግዚአብሔር ጋር በመስማማት ቅድስናውን እንዳጓደሉ መቀደሳቸውን ለማሳየት ነው።(ሮሜ 3፡23) በአሁኑ ጊዜ መጠቀሱ ሂደቱ ቀጣይ መሆኑን ያመለክታል። ኑዛዜውም የሚካትታቸው።

1. ኃጢያቱን አምኖ የመመላለስ(ቁ 9)
2. ኃጢያት መፈፀምን በይፋ መቀበል(ማቴ 10፡32፤52፡5፤16) እና
3. ከተጠቀሰው ኃጢያት በንስሀ መመለስ(ማቴ 3፡6፤ ማር 1፡5፤ሐዋ ሥራ19፡18፤ያዕ 5፡16) ናቸው።

በ1ኛ ዮሐንስ ይህን ሀሳብ በተደጋጋሚ ይገልጻል (1፡9፤4|2|3|15፤ 2ኛ ዮሐንስ 7፤ያስ.) የኢየሱስ ሞት የኃጢያት ማስተሰሪ ነው።ሆኖም ኃጢያተኛው ሰው ለመዳን ለዚህ ስጦታ ምላሽ መስጠትና ሂደቱንም መቀጠል ይኖርበታል። (ዮሐ 1፡12፤3፡16) ተጨማሪ የጥናት አርእስት፡ መናዘዝ (ዮሐንስ 9፡22-23 )ይመልከቱ።

▣ **"ኃጢአታችንን"** በብዙ ቁጥር መጥቀሱን ያስተውሉ። የተወሰነ የኃጢአት አይነትን ለማመልከት የተተቀሰ ነው።

▣ **"የታመነ ነው"** ይህም እግዚአብሔር አብን ያመለክታል(ዛ 7፡9፤37፡4፤ መዝ 36፡5፤40፡10፤89.1|2|5|8፤ 92፡2፤119፤90፤ ኢሳ 49፡7፤ሮሜ 3፤3፤1ቆሮ 1፡9፤10፡13፤ 2ቆሮ 1፡18 1 ተሰ 5፡24 2ኛጢሞ 2፡13) የእግዚአብሔር አብ የማይለወጥ|የምህረትና የታማኝነት ባህሪው የማይናወጥ ተስፋችን ነው። ይህ ሐረግ እግዚአብሔር ስለ ቃሉ ታማኝ መሆኑን (ዕብ 10፡23፤11፤11) በተጨማሪም በኤር 31፡34 ስለኃጢያት ይቅርታ ስለገባው አዲስ ቃል ኪዳን ታማኝነቱም ሊያመለክት፡ችላል።

▣ **"ፃድቅ ነው።"** አውደ ንባቡ እንደሚያመለክተው ከሆነ ጻድቅ የሆነው እግዚአብሔር ቅዱሳን ያልሆኑትን የሰው ልጆች እንዲሁ ምህረት የሚያረግላቸው ስለማይመስል ቃሉ እንግዳ ሊሆንብን ይችላል። ሆኖም የቃሉ ስነመለኮታዊ አግባብ ትክክል ነው። ምክኒያቱም እግዚአብሔር ኃጢያትን በቀላሉ ባያልፈውም የይቅርታ መንገዱንም ምትክ ሆኖ በሞተልን በኢየሱስ አዘጋጅቷል(ሮሜ 3፡21-31) ተጨማሪ የትምህርት አርእስት 2፡29 ይመልከቱ።

▣ **"ይቅር ሊለን … ሊያነፃን"** አድራጊ ኃላፊ ጊዜ የሚያመለከቱና በሁኔታ የተወሰኑት ሁለቱ ግሶች በአውዳቸው ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። የኃጢያተኛውን መመለስና ከእግዚአብሔር ጋር ላለው ኃብረት የመንፃት ሂደቱ ቀጣይ መሆኑን አመልካች ናቸው። (ኢሳ 1፡8፤38፡17፤43፡25፤44፤22፤መዝ 103፡3|11-13፤ሚክ 7፡19)፡ የወንጌሉን እውንት የካዱ ሐሰተኞች ድነት ያስፈልጋቸዋል። በኃጢአት የወደቁ አማኞችም ሕይወታቸውን ማደስ ይኖርባቸዋል። ዮሐንስ የመጀመሪዎቹን በውስጥ ታዋቂነት፣ ያኚለኞቹን በግልጽ የሚናገር ይመስላል።

1:10 **"ብንል"** ከላይ ለ 1፡6 የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ።

▣ **"ኃጢአትን አላደረግንም"** የአድራጊው ያለፈ ተግባር ውጤቱ በሁኔታዎች በሚወሰን ግስ መገለጹ ከዚህ በፊት ኃጢአትን ያላደረገ ማንም ቢኖር አሁንም ኃጢያተኛ እንደማይሆን ለማመልከት ሲሆን በነጠላ ቁጥር መገለጹ ማንኛውንም አይነት ኃጢአት ለማመልከት ነው። ኃጢአትን ማድረግ በግሪክኛው ዒላማን መሳት እንደማለት ሲሆን ኃጢአት የእግዚአብሔር ቃል ተገለጠውን መፈጸምም ሆነ አለመፈጸም ሊያመለክት ይችላል። ለሐሰተኞች ግን ድነት፡ ከሕይወት ጋር ሳይሆን ከዕውቀት ጋር የተያያዘ ይመስላቸዋል።

▣ **"ሐሰተኛ እናደርገዋለን"** ወንጌል ሰዎችን ሁሉ ከኃጢአተኝነት በታች ዘግቷል (ሮሜ 3፡9-18|73፤5፡1፤11፡37) እግዚአብሔር (ሮሜ 3፡4 ያስ.) ወይም ኃጢአት የለብንም የሚሉ ከሁለት አንደኛቸው እየዋሹ ነው።

▣ **"ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም"** አገላለጽ ሁለት ነገሮችን በአንድነት ይዟል። "ሎጎስ" ኢየሱስንና መልክቱን ሁለቱንም በአንድነት ሊያመለክቱ ይችላል።(1፡1|8፤ ዮሐንስ ወንገል 14፡6) ዮሐንስ ይህን ብዙውን ጊዜ "እውነት"በማለት ይገልፀዋል።

2:1 **"ልጆቼ ሆይ"** ታናሽነትን ለማመልከት በ1ኛ ዮሐንስ ሁለት የተለያዩ ቃላትን ተጠቅሟል።

1. ቴክኖን (2፡1|12|28፤3፤7|18፤4፡4|፤5፡21፡5 ዮሐንስ 13፡33ያስ.)

2. *ፖይዶን* (2፡14|18 *ያስ.*)

*ሁለቱም ቃላት ተመሳሳይ በመሆናቸው የተለያየ ሥነ መለኮታዊ ትርጓሜ የላቸውም፡፡ እነዚህ የፍቅር ቃላት ምናልባትም ከዮሐንስ እድሜ መግፋት ጋር በተያያዘ ሊሆን ይችላል፡፡*

*ኢየሱስ ልጆች የሚለውን ቃል ደቀመዛሙርትን ለማመልከት ተጠቅሟል ዮሐንስ* 13፡33፡፡

▣ **"ኃጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ"** *ውጤቱ ቀጣይ በሆነ የኃላፊ ጊዜ ግስ መጠቀሱ ምናልባት የኃጢተኝነትን ሕይወት ለይቶ ለማሳየት* (3፡6|9 *ያስ.*) *እና ከፈተና የተነሳ ከኃጢያት ጋር እየታገሉ ካሉ ክርስቲያኖች ጋር ለማነጻጸር የተነገረ ነው፡፡ በዚህም ሁለት ወደ ጫፍ ያወጡ አመልካቾች ለማስታረቅ እየሞከረ ነው፡፡*

1. *ኃጢአትን አቅሎ መመልከት*(*ሮሜ* 6፡1፤1*ኛዮሐ* 1፡8-10፤3፤6-9፤5፤16)
2. *ክርስቲያን የድፍረት ኃጢአትን በቀላሉ ማየት እንደለለበትና ጥብቅ አቋም ስለመያዝ ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለት አመላካቶች ከሁለት የተለያዩ የኖስቲሳዊን ትምህርት ቤቶች የመነጩ ይመስላል፡፡አንደኛው ወገን ድነት የዕውቀት ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ሰዎች በሥጋቸው ምንም ቢያደርጉ ልዩነት አያመጣም ምክንያቱም ሰውነታችን ርኩስ ነውና ሲል፤ሌላኛው ወገን አካላችን ርኩስ በመሆኑ ፍላጎቱ ላይ ገደብ ሊጣልበት ይገባል | መጨቆን አለበት ይላል፡፡*

▣ **"ማንም ኃጢያት ቢያደርግ"** *አባባሉ ክርስቲያኖችን ጨምሮ በሌሎችም ላይ ወደ ፊት ሊከሰት እንደሚችል ለማሳየት ሦስተኛ መደብ የተወሰነ ሁኔታን አመልካች ግስ የተነገረ ዐረፍተ ነገር ነው፡፡*

▣ **"በአብ ዘንድ ጠበቃ አለን"** *በአሁኑ ጊዜ አድራጊ አመልካች ግስ የተነገረ ዐረፍተ ነገር ሲሆን ዮሐንስ አሁንም ስለ እኛ ቀጣይ የምልጃ ስራ በሰማያዊ ስፍራ በቆመልን ጠበቃ (ጴራቂልጦስ) አማካኝነት እያቀረበልን መሆኑን፡፡ ቃሉ ስለእኛ ለመከራከር ወይም በውክልና ከኀናችን የቆመ የሕግ አዋቂን የምወክል ቃል ነው፡፡ ቃሉ(ፖራ) ከጎን እና (ከሌዊ) ተጠሪ ከሚሉ ሁለት ቃላት የተመሰረተ ሲሆን በዮሐንስ ወንጌል በምድር ጠበቃችን ሆኖ ስለሚላከው ስለመንፈስ ቅዱስ የተነገረ ነው፡፡* (*ዮሐንስ* 14፡16|25፤15፡26፤16፡7 *ከዚህ ሌላ ኢየሱስን ለማመልከት ብቻ ተጠቅሷል ዮሐንስ* 14፡16፤*ሮሜ* 8፡34፤*ዕብ* 4፡14-16፤7፡25፤9፡24)*ሐዋሪያው ጳውሎስ የክርስቶስን የምልጃ ሥራ ለማመልከት በሮሜ* 8፡34፣ *በዚሁ መልክቱ ስለመንፈስ ቅዱስ አማላጅነት ሮሜ* 8፡26 *ተመሳሳይ ሀሳብ ለማስተላለፍ ተጠቅሟል፡፡ ሁለቱም አፍቃሪ አባታችን በእርሱ ምትክ የላካቸው ናቸው፡፡*

▣ **"ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ"** *ይህ መለኮታዊ ባህሪይ ለእግዚአብሔር አብ ተጠቅሷል* (1፤9) *የኢያሱስን መለኮታዊነቱን ለማረጋገጥ የተለያዩ ስነጽሑፍዊ ዘይቤዎችን ተጠቀመዋል፡፡*

1. *ለእግዚአብሔር የሚጠቀሱ ማዕረጎችን ለኢየሱስ በመጥቀስ፣*
2. *ኢሱስ ያደረጋቸውን የእግዛቢሔርን ሥራዎች መጥቀስ፣*
3. *ተመሳሳይ ሰዋሰዋዊ አግባብ ያላቸውን አመልካች መስተዋድዶችና በተሳቢነት የሚገቡ ግሶችን ለሁለቱም በመጠቀም ኃጢያተኛ አለመሆኑን (ጻድቅ| እግዚአብሔርን መምሰሉ)*

*ከ* 3፡5፤2*ቆሮ* 5፡21፤*ዕብ* 2፡18፤4፡15፤7፡26፤1*ጴጥ* 2፡22) *እርሱ የእግዚአብሔር ጽድቅ ለሰዎች የተገለጠበት መንገድ ነው፡፡*

2:2

NASB

| | |
|---|---|
| NKJV | **" እርሱ የኃጢአታችን ምትክ ነው "** |
| NRSV | **"እርሱ የኃጢአታችን ማስተሰሪ ነው "** |
| TEV | **"ክርስቶስ ኃጢያታችን ይቅርታ ምክኒያት ነው፡፡ "** |
| NJB/RSV | **"እርሱ የኃጢያታችን ማስተሰሪያ መስዋዕት ነው "** |

*ሂላስሞስ የተሰኘው ቃል በሰባ ሊቃናት ትርጉም የታቦቱ የስርየት መክደኛን ለማመልከት ተጠቅሷል የቃል ኪዳኑ ታቦት የስሪየት መክደኛ የማስተሰርያው ስፍራ ወይም የምህረቱ መገኛ ስፍራ ነው፡፡ ኢየሱስ ራሱን በእኛ በደል ፋንታ በእግዚአብሔር ፊት አቀረበ* (4፡10፤*ሮሜ*3፡25 *ያስ.*)

*በግሪክ እና ሮማዊያን የማንጻት ልማድ ቃሉ ከተለዩት አምላክ እንደገና ለመታረቅ የሚያቀርብ ማማለጃ ነው፡፡ በአይሁዳዊን አስተሳሰብ መሠረት የሰባ ሊቃናትን ትርጉም ወደ ተለመደው ተራ ግሪክኛ ሲተረጎሙ በዚህ ሃሳብ አልነበረም፡፡ በስፐቱጀንትና በዕብራዊያን* 9፡ 5 *መሠረት ለመላው እስራኤል የማስተሰርያ ስርዓት የሚፈጸምበትን የስሪየት መክደኛውን ያመለክታል* (*ዘሌዋያን* 16 *ያስ.*)

*ቃሉ እግዚአብሔር ስለኃጢአት ያለውን ሀሳብ እንደቀየረ ሳይሆን ኃጢአተኞችን ለመዋጀት ያለውን የማዳን ጥንትዊ አቅሙን ያመለክታል፡፡ ሌ ማን ኢን ክራይስት በተሰኛው የጀምስ ስቲዋርትስ መጽሐፍ ገጽ* 214-224 *ርዕሰ ጉዳዩ በሚገባ ተብራርቷል፡፡ ይህን ማድረግ የሚቻልበት አንደኛው መንገድ ቃሉ እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ያደረገልንን ሥራ በሚገልጽ መልኩ ምትክ መስዋዕት ወይም የኃጢአታችን ምትክ ብሎ መተርጎም ነው፡፡*

*ዘመናዊ የእንግሊዘኛ የትርጉም ሥራዎች ይህን ከመስዋዕት ጋር የተያያዘ ቃል የሚገለጹበት መንገድ ይለያያል፡፡ "የኃጢአተኞችን ምትክ" እግዚአብሔር ኢየሱስን በእኛ ኃጢአት ምትክ አደረገው* (*ሮሜ* 1፡18፤*ኤፌ* 5፡6፤*ቆ* 3፤6)

የእግዚአብሔር ቅድስና በኃጢአተኛው የሰው ልጅ እጅ ነው። ይህም በክርስቶስ አገልግሎት ውስጥ ታይቷል (ሮሜ 3፤25|2ቆሮ 5፡ 21፤ዕብ 2፡7 ያስ)

*ሲ ኤች ዶድን የመሳሰሉ አንዳንድ ሊቃውንት የአረማዊያን (ግሪካዊያን) ሃሳብ የሆነውን (የተቆጡ አማልክትን ማብረጃ ምትክ ክፍያ ሃሳብ ለያህዌ መጠቀስ የለበትም ይላሉ።*

ስለዚህ ማስተሰርያ የሚለውን ቃል ይመርጣሉ። የኢየሱስ አገልግሎት የሰው ልጆችን በደል ምትክ በእግዚአብሄር ፊት ከማቅረብ ጋር የተያያዘ (የሐ 1፡29፤3፡16) እንጂ ከእግዚአብሔር ቁጣ ጋር መያያዝ የለበትም፡ ይላሉ። ሆኖም ሁለቱም ሀሳብ መጸሐፍ ቅዱሳዊ ነው።

▣ **"የኃጢአታችን ማስተሰሪያ ነው።"** ይኸውም ለዓለም ሁሉ ኃጢአት እንጂ ለእኛ ብቻ ኤደለም። ለአሁን ብቻ ሳይሆን ለወደፊትም ጭምር የተከፈለው መስዋዕት ኃይል እንዳለው ለማመልከት (4፡14፤ዮሐ 1፡29፤3፡16|17|12፤47፣ሮሜ 5፡18፤1ጢሞ 4፡10፤ቲቶ 2.11፤ዕብ 2፡9፤7፡25 ያስ.) ኢየሱስ የሞተው ለኃጢአት ያውም ለዓለም ሁሉ ኃጢአት ነው። (ዘፍጥረት3፡15 ያስ) ሰዎች ከመዳን ሊግዳቸው የሚችለው ብቸኛው ነገር ኃጢአት ሳይሆን አለማመን ነው። በመሆኑም የሰው ልጅ እግዚአብሔር ላዘጋጀው ድነት በእምነት|በንስሐ በመታዘዝ ምላሽ መስጠት አለበት ወደ ኋላ ሳይል ምላሽ መስጠቱን መቀጠል ይጠበቅበታል!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥቅስ ማብራሪያ የጥናት <u>መምሪያ</u> ነው። ማለትም አጥኚው ለመሰለው አተረጎጎም ኃላፊነት ይወስዳል። እያንዳንዳችን በተቀበልነው ብርሃን መመላለስ አለብን። በአተረጓጎም ሂደት አጥኚው መፀሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ናቸው። በመሆኑም አጥኚው ይህንን ጉዳይ ለጥቅስ ማብራሪያ ፀሐፊዎች መተው የለበትም።

የሚከተሉት የውይይት ጥያቄዎች በዚህ የጥናት ጽሁፍ የተመለከትናቸውን ዋናዋና ርዕሰ ጉዳዮች እንዲያስታውሱ ያግዞታል። ጥያቄዎቹ አንድ የተወሰነ መልስ ያላቸው ሳይሆን የተለያዩ ሀሳቦችን እንዲያነሱ የሚግዙ ናቸው።

1. ዮሐንስ አምስቱን የስሜት ሕዋሳት የሚያመለክቱ ግሶችን በብዛት የሚጠቅሰው ለምንድነው?
2. በቁጥር 7 እና 9 ላይ የተጠቀሱትንና ስለመሰዋዕት የሚገልጹ ቃላትን ይዘርዝሩ
3. ዮሐንስ የሚወግዛቸው የመናፍቃን ትምህርቶችን ይግለጹ
4. ቁጥር 9 ሁለቱንም ማለትም ኖስቲሳዊያንና አማኞችን የሚያመለክተው እንዴት ነው?
5. "መናዘዝ" የሚለው ቃል ትርጉሙ ምንድን ነው? ያብራሩ።

# አንደኛው ዮሐንስ 2:3-27

## የዘመናዊ የትርጉ ሥራዎች የምዕራፍ አከፋፈል

| UBS[4] | NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| ክርስቶስ ጠበቃችን | ከእርሱ ጋር ያለን ኅብረት መሠረቱ<br>(1:5-2:2) | መታዘዝ | ክርስቶስ ረዳታችን | በብርሃን መመላለስ<br>(1:5-2:28) |
| | | | | 1ኛ ቅድመ ሁኔታ፡- ከኃጢያት ነፃ መውጣት (1:8-2:3) |
| 2:1-6 | እርሱን የማወቃችን መመዘኛ | 2:1-2 | 2:1-2 | 2ኛ ቅድመ ሁኔታ፡- የፍቅር ትዕዛዛቱን መጠበቅ |
| | 2:3-11 | 2:3-6 | 2:3-6 | 2:3-11 |
| አዲሱ ትዕዛዝ | | እርስ በርስ መዋደድ | አዲሱ ትዕዛዝ | |
| 2:7-14 | | 2:7-11 | 2:7-8 | |
| | የመንፈሳዊ ዕድገት ደረጃቸው | በክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር ያለ እውነተኛ ኅብረት | 2:9-11 | 3ኛ ቅድመ ሁኔታ፡- ከዓለም መለየት |
| | 2:12-14 | 2:12-14 | 2:12-13 | 2:12-17 |
| | ዓለምን አትውደዱ | በዓለም ያሉትን መውደድ | 2:14 | |
| 2:15-17 | 2:15-17 | 2:15-17 | 2:15-17 | |
| የክርስቶስ ተቃዋሚ | የመጨረሻው ዘመን ክህደት | በእውነተኛ እምነት መጽናት | የክርስቶስ ተቃዋሚ | 4ኛው ቅድመ ሁኔታ፡- ከክርስቶስ ተቃዋሚዎች መጠበቅ |
| 2:18-25 | 2:18-23 | 2:18-35 | 2:18-19 | 2:18-28 |
| | | | 2:20-21 | |
| | እውነት በእናንተ ይኑር | | 2:22-23 | |
| | 2:24-27 | | 2:24-25 | |
| 2:26-27 | | 2:26-27 | 2:26-27 | |

**ሦስተኛ የንባብ ዑደት (ገጽ 5ን ይመልከቱ)**
*የመጀመሪያውን ጸሐፊ ዋና ሃሳብ በአንቀጽ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥቅስ ማብራሪያ የጥናት መመሪያ ነው ማለትም አጥኚው ለመሰለው አተረጓጎም ኃላፊነት ይወስዳል፡፡ እያንዳንዳችን በተቀበልነው ብርሃን መመላለስ አለብን፡፡

በአተርጓጎም ሂደት አጥኚው መፀሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ በመሆኑም አጥኚው ይህንን ጉዳይ ለጥቅስ ማብራሪያ ፀሐፊዎች መተው የለበትም፡፡

ይህንንም ምዕራፍ በአንድ ጊዜ ያንብቡ፣ የክፍሉን ርዕስ ጉዳዮች ይለዩ፣ በአንቀጽ ተከፋፈለው ከላይ ከተጠቀሱት አዳዲስ ትርጉሞች ጋር ያነጻጸሩ፡፡ ትቅሶችን በአንቀጽ መከፋፈል የጥቅስ አተረጓጎም መሰረታዊ መርህ የሆነውን የደራሲውን ሀሳብ ለማግኘት ቁልፍ ድርሻ ቢኖረውም ከመጀመሪያውም በመገለጥ የተሰጠ የመጽሐፉ አካል አልነበረም፡፡ እያንዳንዱም አንቀጽ አንድ መልዐት ብቻ ይኖረዋል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተ …

## አውዳዊ ግንዛቤዎች፡- 2:3-27

ሀ. ከሚደጋገሙ ጭብጦች የተነሳ ለ1ኛ ዮሐንስ የዕርዕስት ማውጫ ማዘጋጀት አስቸጋሪ ነው፡፡ ሆኖም አብዛኞቹ ተርጓሚዎች የምዕራፍ ሁለት ጭብጥ የምዕራፍ አንድ ቀጣይ መሆኑን ይስማሙበታል፡፡ ይኸውም በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ ጉዳይ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ይመልከታል፡፡

ለ. 2ኛው ምዕራፍ ልክ እንደ ምዕራፍ አንድ ሁሉ መልዕክቱን ከሐሰተኞች ክርክር ጋር ያስተያያል፡፡ በመሆኑም በሁለቱ ምዕራፎች መካከል የመዋቅር ተመሳሳይነትም አለ፡፡

| ምዕራፍ 1 | ምዕራፍ 2 |
| --- | --- |
| 1. ብንል….. (ቁ.6-7) | 1. እያለ…. (ቁ.4-5) |
| 2. ብንል….. (ቁ.8-9) | 2. እያለ….. (ቁ. 6) |
| 3. ብንል….. (ቁ.10) | 3. እያለ …. (ቁ. 8-11) |

ሐ. አውደ ንባቡ የእውነተኛ አማኝ መገለጫዎችን ይዘረዝራል (2:3-25)
1. ኃጢአትን ለመናዘዝ ዝግጁ መሆን (አሁንም ሆነ በቀጣይነት) (1:5፤2:22)
2. ሁሌም ታዛዥ መሆን (2:3-6)
3. ሁሌም አፍቃሪ መሆን (2:7-11)
4. ክፉን ማሸነፍ መቻል (2:12-14)
5. ዓለምን አለመውደድ (2:15-17)
6. ጸንቶ መኖር (2:19)
7. ትክክለኛ አስተምህሮ (2:20-24፤4:1-3)

መ. የተለያዩ ስለመለኮታዊ ጽንሰ ሃሳቦች (2:18-19)
1. "የመጨረሻው ሰዓት" (ቁ.18)
   ሀ. ይኸኛውና "የመጨረሻ ቀኖች" ክርስቶስ በቤተልሄም ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዳግመኛ ምፃቱ ያለውን ጊዜ ያመለክታል፡፡የእግዚአብሔር መንግስት መጥታለች ሆኖም ገና ሙሉ በሙሉ እውን አልሆነችም ፡፡
   ለ. በሁለቱ ኪዳናት መካከል ይኖሩ የነበሩት አይሁድ በሁለት ዘመናት መካከል እንደሚኖሩ ያስቡ ነበር| በጊዜያቸው የነበረው ክፉው ዘመንና በመንፈስ ምሪት ወደ ፊት የሚኖሩበት የተቀደሰው ዘመን ናቸው፡፡ብሉይ ኪዳን በግልጽ ያላስቀመጠው ነገር ቢኖር የክርስቶስ የመጀመሪያ ለድነት መምጣቱና የማዳን ሥራውን የሚያበቃበት ዳግመኛ ምጽቱ ናቸው፡፡ እነዚህ ዘመናት አንደኛው በሌላኛው ውስጥ ይከታተል፡፡ ተጨማሪ ትምህርት 2:17 ይመልከቱ፡፡
   ሐ. ሰዓቱ (ካይሮስ) ያልተወሰነ ጊዜን የሚያመለክት ምሳሌያዊ አገላለጽ ነው፡፡(ዮሐ 4:21|23፤5:25|16:)

2. "ተቃዋሚ"(ቁ.18)
   ሀ. "ተቃዋሚ" የሚለውን ቃል የሚጠቀመው ዮሐንስ ብቻ ነው፡፡ (2፤18|22፤4:3፤2 ዮሐንስ 7) በ2: 18 በነጠላና በብዙ መጠቀሱን ያስተውሉ (2 ዮሐንስ 7)
      1) ስለ ተጠቀሰውና በመጨረሻው ዘመን ስለሚገለጠው ስለዚህ ሰው ማንነት ሌሎች የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍሎችም ይገለጻሉ፡፡
         ሀ. ዳንኤል-"አራተኛው አውሬ"(7:7-8|23-26፤9:24-27 ያስ.)

ለ. ኢየሱስ- "የጥፋት ርኩሰት" (ማ 13፤ማቴ 24 ያስ.)
ሐ. ጳውሎስ - የአመፅ ሰው (2 ተስ.2)

2) የሐንስ በዘመኑ መጨረሻ ሊገለጥ ባለው የአመጽ ሰው እና አሁን እየሠራ ባለው የአመፅ መንፈስ መካከል ያለውን ሁኔታ ለይቶ ይገልጻል (2:18፤4:3፤ 2የሐ 7፤ ማ 13:6|22፤ ማቴ 24:5|24 ያስ.)
3) ፀረ ክርስቶስ በሚለው ቃል ውስጥ "ፀረ" በመስተዋድዳዊ አገባቡ(1) በተቃዋሚነት ወይም (2).በክርስቶስ ምትክ የምገለጥ ማለት ነው፡፡ቃሉ በነጠላና በብዙ ሲነገር የራሱ የሆነ መልክት አለው (ቁ 18) ዓለም በእግዚአብሔር ልጅ ተቃዋሚዎች ተሞልታለች(ከላይ ቁ 1 ይመ.)
*ሀ. አንጥያኮስ ኤጵፋኔዮስ 4ኛ* (ትንቬ ቀንድ ዳን 8:11-36-45)
ለ. ኔሮ እና ዶሚቲያን(ራሳቸውን አማልክት አረገው የቆጠሩ)
ሐ. ፀረ ሃይማኖት የነበረው ኮሚዮንዝም)
መ. ዓለማዊ መሠረት ያለው የሰብአዊነት አስተሳሰብ

ክርስቶስን ባይቃወሙም ራሳቸውን አንደ ክርስቶስ የቆጠሩ(ከላይ ቁ.2 ይመ.)
ሀ) በማር 13:6|22 እና ማቴ 24:5|24 የተጠቀሱት የስህተት መምህራን
ለ) ዘመናዊ የባዕድ አምልኮ መሪዎች
ሐ) የክርቶስ ተቃዋሚ (ዳን.7.8፤9:23-26|24-27፤ 2 ተሶ. 2:3፤ ራዕ. 13)

4) በየዘመኑ የነበሩት ክርስቲያኖች ክርስቶስን ከሚክዱ የሐሰት መምህራንና ኢየሱስ ነን ከሚሉ ሐሰተኞች ጋር ተጋፍጠዋል፡፡ ነገር ግን አንድ ቀን|በመጨረሻው ዘመን ልዩ ሆኖ የሚገለጠው (እርሱም የክርስቶስ ተቃዋሚ) ራሱን እንደ መሢህ በመቁጠር ክርስቶስንም በመቃወም ሁለቱንም ተላብሶ ይገለጣል፡፡

3. "በእናንተ ውስጥ ይኑር" (ቁ 19:24:27:28)
   ሀ. አብዛኞች ዘመናዊ ወንጌላዊያን ክርስቲያኖች በመጀመሪያው የሰዎች የእምነት ውሳኔ ልዩ ትኩረት ይሰጣሉ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ግን ከዚህ ይልቅ ደቀመዝሙር የመሆን ጉዳይ ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡
   ለ. የመዳናችን እርግጠኝነት ትምህርት በእምነት ከመጽናት ትምህርት ተነጥሎ መታየት የለበትም፡፡ ከተጨማሪ ትምህርት ጥናት ፀንቶ ስለመኖር በዮሐ 8:31 ይመልከቱ፡፡ሁለቱም የምርጫ ወይም የአማራጭ ጉዳይ ሳይሆን ሁለቱንም የመያዝ ጉዳይ ነው፡፡ መፅሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ነው፡፡ በርግጥ መጽናት መጽሐፍ ቅዱስዊ ማስጠንቀቂያ ነው (ከዮሐንስ ምዕራፍ 15 ያስ.)!
   ሐ. ስለመጽናት አስፈላግነት ሌሎች ጥቅሶች ማቴ 10፤22፤15:1-9|18-13 ማር 13፤13፤8:31፤15:1-27፤1ቆሮ 15:2፤ገላ6:1፤ራዕ 2:2|7፤11|17|26፤3:5|12|፤21:7 ተጨማሪ የትምህርት ክፍል "መኖር" 2:10 ይመልከቱ፡፡

## የቃልና የሐረግ ጥናት

> NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 2:3-6
> **[3]ትዕዛዛቱንም ብንጠብቅ | በዚህ እንዳወቅነው እናውቃለን፡፡ [4]አውቄዋለሁ የሚል ትዕዛዛቱንም የማይጠብቅ ውሸተኛ ነው እውነትም በእርሱ ውስጥ የለም፡፡ [5]ቃሉን ግን የሚጠብቅ ሁሉ በእርሱ የእግዚአብሔር ፍቅር በእውነት ተፈጽሟል፡፡ በእርሱ እንዳለን በዚህ እናውቃለን፤ [6]በእርሱ እኖራለሁ የሚል እርሱ እንደተመላለሰ ራሱ ደግሞ ሊመላለስ ይገባዋል፡፡**

2:3 **"በዚህ እንዳወቅነው እናውቃለን"** ቃል በቃል እርሱን ማወቃችንን እናውቃለን፡፡ አድራጊ አመልካች የአሁን ጊዜ|የኃላፊ ጊዜ የድርጊት ቀጣይ ውጤት ገላጭ አመልካችን ተከትሎ የገባ አገላለጽ በኖስቲሳዊያን ትምህርት የተጠቁት የዚያን ዘመን ክርስቲያኖች ከዚህ አንፃር ስለመዳናቸው እርግጠኛ እንዲሆኑ የሚያደርግ ነው፡፡

"ማወቅ" ተብሎ የተጠቀሰው ቃል የተወሰደው በግል ያለንን መቀራረብ ከሚገልፀው የዕብራዊያን የቃላት አጠቃቀም (ዘፍ 4:1፤ኤር 1:50 እና ስለ አንድነገር ምንነት ወይም ስለ አንድ ሰው ማንነት ማወቅን ከሚገለጽው የግሪካዊያን አጠቃቀም የተወሰደ ነው፡፡ የወንጌል እውነት ስለአንድ ነገር ማንነትም ሆነ ስለ እርሱ ምንነት የማወቅ ጉዳይ ነው፤፡ በዚህ ክፍል ትኩረቱ፡

1. እግዚአብሄርን ማወቅ እንችላለን፣
2. ስለ እኛ ማድረግ የሚፈልገውን እናውቃለን፣
3. ማወቃችንንም እናውቃለን (5:13 ያስ.)፡፡

እግዚአብሔርን የማወቃችን አንድኛው ማረጋገጫ ከውስጥ የሚገፋን ሀሳብና *ሥራችን* ነው፡፡ (ማቴ 7፤ያዕቆብ|1ኛ ጴጥ) ይህም በተደጋጋሚ የተገለጸ የ1ኛው ዮሐንስ መልዕክት ጭብት ነው (2:3|5፤3፤24፤4:13፤5:2|13 ያስ.)

"ማወቅ " የተሰኘው ቃል በሁለት ግሪክኛ ቀላት(ግኖስኩ እና ኦዳይ) በዮሐንስ ጽሕፎች የተጠቀሰ ሲሆን (በ1ኛ ዮሐንስ ባሉት 5 ምዕራፎች ብቻ 27 ጊዜ ተጠቅሷል፡፡) ብዙሃኑ ተራው ሕዝብ በሚነጋገርበት ኮይኔ ግሪክኛ ሁለቱም ቃላት የተለየ

የትርጉም አግባብ እንደሌላቸው ያመለክታል፡፡ በመሆኑም አጠቃቀሙ የአጻጻፍ ዘይቤ ምርጫ ጉዳይ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ እዝህ ላይ የሐንስ ኤፒግኖስኩ የተሰኘውንና ጥልቅ የትምህርት ዕውቀትን የሚገልጽ ቃል አለመጠቀሙን ያስተውሉ፡፡

ዮሐንስ የጻፈው አማኞችን ለማበረታታትና ለሀሰተኞች ክርክር ምላሽ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ከተቀሩት የአዲስ ኪዳን መፅሐፎች በበለጠ የዮሐንስ ወንጊልና የ1ኛ ዮሐንስ መልክት "ማወቅ" የተሰኘውን ቃል ይጠቀማል፡፡ የወንጌል እውነትን በማወቅ እርግጠኛ ስለመሆን የሚገልጽው የዮሐንስ መጽሐፍ|ስለ በወንጌል እውነት የመኖር ዘይቤና ስለመታዘዝ ከሚገልጽው (የያቆብ መጽሐፍ) መካከል ሚዛን ለመጠበው ያስችላል፡፡

▣ "ብ…" ወደፊት ልፈጽም የሚችል ሁኔታን የሚያመለክት ሦስተኛ መደብ ሁኔታን አመላካች ዐረፍተ ነገር ክፍል ነው፡፡

▣ **"ትዕዛዛቱንም ብንጠብቅ"** በሁኔታ ላይ የተመሠረተ የአሁን ጊዜ አመልካች ይዘት እንዳለው ያስተውሉ፡፡ በእግዚአብሔር በኩል ሲታይ አዲስሱ ትዕዛዝ፣ ቅድመ ሁኔታ የለበትም ከሰው አንጻር ሲታይ ግን በእምነት ንስሀ በመግባትና በመታዘዝ ምላሽ በመስጠት ቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡(2፤3-5፤3፤22|24፤5:2|3፤የዮሐ8:51-52፤14:15|21|23፤ 15:10፤እራዕ 2:26፤3:8:70፤12:17፤14:12) እውነተኛ የህይወት መገለጫው ለብርሃን (ለኢየሱስና ለወንገል) መታዘዝ (ሉቃ.6:46) ነው፡፡ በብላይ ኪዳን ሳይቀር መታዘዝ ከመስዕዋት ይበልጣል(1ሳሙ 15:22፤ኤር 7:22-23) መታዘዝ ለመዳናችን ዋስትና አይሰጥም ሆኖም የዳንን መሆናችንን ያረጋግጣል፡፡ ሥራ የመዳን መሠረት አይደለም (ኤፌ 2:8-9)፣ ግን የድነት ፍሬ ነው፡፡(ኤፌ 2:10 ያስ.)

2:4 **"የሚል"** ዮሐንስ የሐሰተኞችን ትምህርት፡ ለመቃወም የሚጠቀምበት አይነተኛ የስነጽሁፍ አቀራረብ ነው፡፡

▣ **"አውቄዋለሁ"** ሐሰተኞች ከምሏቸው አያሌ ነገሮች አንዱ ይኸ ነው፡፡(1:6|8|10፤2:4|6|9 ያስ.) ይህ ተቃውሞ (እናውቃለን የምሉትን) ያመለክታል፡፡ የዚህ ተመሳሳይ አገላለፅ በሚልክያስ፣ በሮሜ እና በያዕቆብ እናገኛለን ሐሰተኞች እንደሚያውቁ ይናገራሉ፡፡(የድርጊት ውጤት ሂደታዊነትን በሚያመለክት ግስ) እደተገለጸው እግዚአብሔርን እንደሚያውቁ ቢናገሩም ድነትን እግዚአብሔር ከመምሰል ሕይወት ለመነጠል ይሞክራሉ፡፡ መጽደቅን ከመቀደስ ለይተው ይመለከታሉ፡፡ስለ እግዚአብሔር የተለየ (ምስጢራዊ) ዕውቀት እንዳላቸው ይናገራሉ፡፡ ሆኖም የሕይውት ምስክርነታቸው እውነተኛ የልብ ሀሳባቸውን ይገልጣል፡፡

▣ **"ትዕዛዛቱንም የማይጠብቅ"** በግስነት የገባ ስም ገላጭ ሲሆን ይህም የተለመደው የሕይወት ዘይቤ አኗኗራችን መንፈሳዊ ዝንባሊያችንን እንደምያሳይ ለማመልከት ነው፡፡(ማቴ 7) ቁጥር 4 እውነትን በአሉታዊ መልክ ሲገለጽ ቁጥር 5 ተመሳሳዩን እውነት በአውንታዊ መልኩ ይገልጻል፡፡

▣ **"ውሸተኛ ነው"** እያወቁ መሳት የባሰ ጥፋት ነው! በአንጻሩ መታዘዝ የእውነተኛ ሕይወት ለውጥ ምልክት ነው፡፡ በፍሬያቸውም ይታወቃሉ ማቴ፡7 ያስ.)

ዮሐንስ ሐሰተኞች ናቸው የሚላቸው በርካታ የሐይማኖት ሰዎች መምህራንና ሰባኪዎች) አሉ፡፡ (1:6|10፤2:4|20፤4:20) እነዚህ ሃይማኖተኛ ናቸው ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር የቀና ህብረት ያላቸውም፡፡

2:5 **"ቃሉን ግን የሚጠብቅ ሁሉ"** የሕይወት ልምድ የሆኑ ድርጊቶችን ለመግለጽ ቀጣይ ውጤት ገላጭ ቢሆን አድራጊ አመላካች ግስ የዩ ቢ ኤስ ደራሲያን ሌ ሃንድ ቡክ ኢን ዘ ሌተርስ ኦፍ ጆን (በሃስ|ጆንጌ| እና ስዌል ግሪራብል) በዚህ ግሪክኛ የሰዋ ሰው አወቃቀር ላይ ጥሩ ትንታኔ ይሰጣሉ፡፡ ባልተወሰነ አመልካች የሚጠቀሱ አገናዛቢ ስመ ምትኮች በ 3:17|22፤4:15፤5:15፤ 3ዮሐ 5 መታዘዝ የአንድ ቃል ኪዳን እምነት መሠረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ይህም የ1ኛ ዮሐንስና የያዕቆብ መልክት አብይ መልክት ነው፡፡አንድ ሰው ሕይወት የሆነውን ቃሉንና በአኗኗር የሚገልጸውን የተጻፈውን ቃሉን እየጣሰ እግዚአብሔርን አውቃለሁ ማለት አይችልም፡፡(3:6|9 ያስ.)

▣ **"በእርሱ የእግዚአብሔር ፍቅር በእውነት ተፈጽሞአል"** ይህ ዓረፍተ ነገር ውጤቱ ሂደታዊ የሆነ የተደራጊ አመልካች ሆኖ ድርጊቱ የተጠናቀቀ መሆኑን ለማመልከት ነው፡፡ (4:12|17|18 ያስ.) ሰዋሰዋዊ አተረጓጎምን ስነመለከት ድርጊት ተቀባዩ፡

1. ስለ እኛ ያለውን የእግዚአብሔርን ፍቅር (4:12 ስ፣)
2. እኛ ለእግዚአብሔር ስለሚኖረን ፍቅር(5:3 ያስ.) ወይም
3. በልባችን ስላለው ስለ አጠቃላይ የፍቅር ሁኔታ| ስለ የትኛው እንደሚያመለክት ግልጽ አይደለም፡፡

ፍጹም(ቴሎስ 4፤12፤17-18 ያስ.) ማለት የበሰለ |ሙሉ ለተመደበበት ሥራ ብቁ እና ዝግጅ ሆኖ መገኘት (ኤፌ 4:12|) |እንጂ ኃጢአተኛ አይደረግም ማለት አይደለም (1:8-10)

▣ **"በእርሱ እንዳለን በዚህ እናውቃለን"** በዚህም ጥቅስ ትኩረቱ በአማኞች ላይ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ሕብረት እምነትን ማዳበር እንድንችል በእርሱ የመሆን ሀሳብ (መኖር) ቁ 6 ያስ.) በዮሐንስ መልክት በተደጋጋሚ የተጠቀሰ ጭብጥ ነው፡፡(የሐ.14:20|23፤15:4-10፤17:21|23፤26፤1የሐ 2፡ 24-28፤3:6|24፤4:13:16 ያስ.)

2:6 “በእርሱ እኖራለሁ” ለተጨማሪ ትምህርት 2፡1 የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ፡፡አዲስ ኪዳን አብ በልጁ እንዳለ (ዮሐንስ 5፡20 ያስ.) አብና ወልድም በእኛ እንዳሉ (ዮሐ14፡23 እና 17፡21 ያስ.) በእርሱ ስለመኖሩ እርግጠኝነት በሚገለጸው ክፍል|በእርሱ እንኖራለሁ (ባልተወሰነ የአሁን ጊዜ)በሚመለክት ማሳሰቢያ ወንጌል በሰዎች መብትና ኃላፊነት ላይ የተመሠረተ መሆኑን ለማመልከት ተጠቅሷል፡፡

▣ “እርሱ እንደተመላለሰ ራሱ ደግሞ ሊመላለስ ይገባዋል” እውነተኛ እምነት በኑሮ የሚግለጽ መሆኑን የሚያመለክት (ያዕቆብ 2፡14-26) ሌላኛው አገላለጽ ነው፡፡ እምነት የውሳኔ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ዕለት በዕለት ክርስቶስን በሚመስል አኗኗር የምገለጽ ነው፡፡ ከክርስቶስ ጋር ቀጣይነት ባለው መልኩ ባለን ግንኙነት የሚገለጽ ተለምዶአዊ ጉዳይ ነው፡፡ የዘላለም ህይወት የሚታይ ገጽታ አለው ! ይህ ከ 6፡7 ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ መንግስተ ሰማያት ስንሞት የምንወርሰው ጉዳይ ብቻ አይደለም አሁን በሕይወት ሳለን ክርስቶስን በመምሰል መኖር ጭምር እንጂ (ሮሜ 28፡29-30፤2ቆሮ 3፡18፤ገላቲያ 4፡19፤ኤፌሶን 1፡4፤1ኛተሰሎንቄ 3፡13፤4፡3፤1ኛጴጥ 1፡15) ለማገልገል ድነናል እርሱ እንደ ተላከ እኛም ተልዕኮ አለን እርሱ ሕይወቱን ለሌሎች እንደሰጠ እኛም እንዲሁ እራሳችንን እንደ አገልጋይ ማየት አለብን፡፡ (1ኛ ዮሐ 3፡16 ያስ.)

"እርሱ ጋር" ቃል በቃል “ያ” በዮሐንስ ጽሁፎች የተለመደ ምሳሌአዊ አገላለጽ ነው፡፡ (ዮሐ 2፡21፤19፡35፤1ኛ ዮሐ 2፡6፤3፡3፤5፡7፤16|4፤17)፡፡ በተደጋጋሚ ልብን በሚነካ መልኩ ተጠቅሷል(ዮሐ 7፡11፤9፡12|28፤19፡21 ያስ.)

“ያ…” የሚለው ኢየሱስን የሚያመለክት ከሆነ በቁጥር 6 “በእርሱ”የሚለው ማንን ያመለክት ይሆን? ዮሐንስ ሆን ብሎ አሻሚ የሆኑ አገላለጾችን ይጠቀማል ቃሉ አብን ሊያመለክት ይችላል(ዮሐንስ 15፡1-2|9-10 ያስ.)ወይም ልጁን ሊያመልክትም ይችላል(ዮሐ 15፡4-6 ያስ.) ተመሳሳይ አሻሚ አገላለጽ “ቅዱሱ” በሚል በቁ.20 ተገልፅል፡፡

> NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 2፡7-11
> **7 ወዳጆች ሆይ÷ ከመጀመሪያ የነበረቻችሁ አሮጌ ትእዛዝ እንጂ አዲስ ትእዛዝ አይደለችም፤ አሮጌይቱ ትእዛዝ የሰማችኋት ቃል ነት፡፡ 8ዳግመኛ አዲስ ትዕዛዝን እጽፍላችኋለሁ፡ ይህም ነገር በእርሱ በእናንተም እውነተኛ ነው ጨለማው ያልፋልና እውነተኛውም ብርሃን አሁን ይበራል፡፡ 9በብርሃን አለሁ የሚል |ወንድሙንም የሚጠላ እስከ አሁን በጨለማ አለ፡፡ 10ወንድሙን የሚወድ በብርሃን ይኖራል፡ ማሰናከያም የለበትም፡፡ 11ወንድሙን የሚጠላ ግን በጨለማ አለ፡ በጨለማም ይመላለሳል፡ የሚሄድበትንም አያውቅም፡ ጨለማው አይኖቹን አሳውሮታልና፡፡**

2፡7 “ወዳጆች ሆይ” ዮሐንስ ብዙውን ጊዜ አንባቢዎቹን በፍቅር ቃላት ይጠራቸዋል፡፡(2፡1 ያስ.)ቃሉ አብ በተለመደ መልኩ ወደ ልጁ ለማምልከት በተጠቀመበት ወቅት (ማቴ 3፡17 ያስ.) እና በመገለጥ ተራራ(ማቴ 17፡5 ያስ.) ተጠቅሟል በዮሐንስ ጽሁፎች የዳኑትን ይወክላል (3፡2|21፤4፡7|11፤ እና 3ኛየሐንስ 1፡2|5|11) የመልክቱ ተቀባዮች “ወንድሞች”ናቸው(ኤም ኤስ ኬ|ኤል|ኤን ኬጄቭ) ሆኖም የሐንስ ይህን ቃል የተጠቀመው 3፡13 ላይ ብቻ ነው፡፡

"ወደጆች" የሚለው ቃል ግን በትላልቅ የግሪክ ፊደላት (አንካል) የመጀመሪያዎቹ የእጁ ጽሁፎች (ℵ|ኤ|ቢ|ሲ|ፕ እና በቩልጌት |ፔሽታ|የኮፒትክ የአርሜንያን የትርጉም ሥራዎች የተደገፈ ነው፡፡(ብሩስ ሜትዝጌር|ኤ ቴክስቹዋል ኮሜንታሪ፣ *ኦን ዘ ግሪክ ኒው ቴስታሜንት*| ገጽ 708 ይመ.)

▣ “ከመጀመሪያ የነበረቻችሁ አሮጌ ትዕዛዝ እንጂ የምጽፍላችሁ አዲስ ትዕዛዝ አይደለችም” ይህ አገላለጽ የዮሐንስ ጽሁፍ መለያ ገጽታ ነው (ዮሐንስ 13፡34፤15፡12| 17 ያስ.) ከጊዜ አንጻር ሲታይ ትዕዛዙ አዲስ አይደለም ከአይነት አኳያ ሲታይ ግን አዲስ ነው፡፡ አማኞች ክርስቶስ እንደወደዳቸው እርስ በእርሳቸው እንዲዋደዱ ታዘዋል (ዮሐንስ 13፡34 ያስ.)

"የቆየው ትዕዛዝ " በሁለት መልኩ ሊታይ ይችላል፡፡

1. የሙሴ ህግ (ማለትም ዘሌ 19፡18)
2. በዮሐንስ ወንጌል የተጠቀሱው የኢየሱስ ትዕዛዝ (ዮሐ 13፡34፤15፡12|17 ያስ.)፤

▣ “አሮጌይቱ ትዕዛዝ” በ 2፡3 “ትዕዛዝ” ተብሎ የተጠቀሰው ቃል በብዙ ቁጥር ሲሆን በዚህ ቁጥር ግን በነጠላ ቁጥር ነው፡፡ ይህም ፍቅር የትዕዛዝትሁሉ ፍጻሜ መሆኑን ለማመልከት የተነገረ ነው (ገላ5፡22፤ 1ቆሮ 13፡13 ያስ) ፍቅር የወንጌል ቅደመ ሁኔታ ነው፡፡

▣ “የሰማችኋት ቃል ናት” ባልተጠናቀቀ አድራጊ አመልካች ግስ የተናገረ ሲሆን አንባቢው ለመጀመሪያ ጊዜ ከወንጊል መልዕክት ጋር የተዋወቀበትን ሁኔታ ለማስታወስ የተናገረ ነው፡፡ (24፤1፡1፤3፡11፤ 2ዮሐንስ 5-6)

▣ “የሰማችኋት” ቀደም ሲል “ከመጀመሪያ ”ያለውን ቃል ለማመልከት የተናገረ ነው፡፡

2፡8 “በእርሱ…እውነተኛ ነው” የዚህ ሰመ ምትክ ቦታ በቁ 7 ሴቴ ሲሆን ግዑዝ ፆታ ከሆነው የትዕዛዝ ጋር እንድስማማ ሲሆን ይህም መላውን የወንጌል መልዕክት ለማመልከት የተነገረው ነው፡፡ ተመሳሳይ የስመ ምትክ ለውጥ በኤፌ 2፡8-9 ይገኛል፡፡

▣ **"ጨለማው ያለፋልና"** ይህ 2ኛ መደብ የአሁን ጊዜ አመልካች ነው፡፡(እንደ ኤ. ቲ ሮበርትሰን *Word Pictures iN the New TestameNt* ገጽ 212) ከሆነ በክርስቶስ እግዚአብሔርን ለሚያውቁ አዲስ ዘመን መጥቷል በልባቸውና በአዕምሯቸው እየደመቀ ይሄዳል ይህም የምናውቀውና (እየተረዳ ነው የምንሄድ የመጨረሻው ዘመን ትምህርት ክፍል ነው)

▣ **"እውነተኛውም ብርሃን አሁን ይበራል"** ኢየሱስ የዓለም ብርሃን ነው፡፡(የዮሐንስ 1፡4-5|9፤8፡12 ያስ.) ይኸውም የእውነት |የመገለጥ የግበረገብ ንጽህናን ይመለከታል፡፡ የ1፡5 እና 1፡7 ማብራሪያ ይመልከቱ አዲስ ዘመን መጥቶአል!

2:9 **"ወንድሙን የሚጠላ"** በግስነት የገባ ገላጭ የአሁን ጊዜ አድራጊ አመልካች ሲሆን ታቅዶ የሚከናወን ቀጣይነት ያለውን ሀሳብ ያመለክታል ጥላቻ በጨላማ የመሆን ምልክት ነው፡፡(ማቴ 5፡12-26 ያስ.)

2:10 **"ወንድሙን የሚወድ በብርሃን ይኖራል"** የአሁን ጊዜ ግሶች በዚህ አንድ ጎልተው ይታያሉ ፍቅር አማኞች የሚወዳቸውና ከእውነትና ከብርሃን የቆሮ ትዕዛዝ ነው (3፡11|24፤4፡7|11|21 ያስ.

**ልዩ ርዕስ፡ "ብትኖሩ" በዩሐንስ ጽሁፎች**

የዮሀንስ ወንገል በአብና በወልድ መካከል ያለውን ልዩ ህብረት ይገልጻል፡፡ ባለዉ የጋራ መቀራረብ አንዱ ለሌላኛው የመገዛትና የእኩልነት ሀሳብ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በመሳው ወንጌል ኢየሱስ ከአባቱ የሰማውን ይናገራል አባቱ ሲያረግ ያየውን ያደርጋል እንደ አብ ፍቃድ እንጂ በራሱ ምንም ነገር አያድርግም ነበር፡፡

ይህ ጥብቅ ህብረት በእየሱስና በተከታዮቹ መካከል የአገልጋይነት ምሳሌ ለመተው ነው፡፡ ይህ በምስራቁ ዓለም እንደሚታየው የአንድ ሰው በሌላኛው የመዋጥ ( ምስትስዚም) ሳይሆን በግበረ ገብ በጥሩ የአኗኗር ዘይቤ የመመሳሰል ጉዳይ ነው፡፡ ህብረቱም (1) ወንጌል የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ከማወቅ፤(2) እየሱስ በእግዚአብሔር ቃል የተገባ(መሢህ በመሆኑ ክርሱ እንድንማርና እንድንታዘዘው የተገባ)፤እና (3) ግብረ ገባዊ( የክርስቶስ ባህሪይ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎችን ማስገኘቱን ያሳያል፡፡

እየሱስ እውነተኛ እስራኤላዊ መሆን|ትክክለኛው የሰው ልጆች ልክ አስከምን ድረስ እንደሆነ ያረጋገጠ በመሆኑ ምሳሌያችን ነው፡፡ አዳምንም መምሰል እንደነበረበት አሳይቷል፡፡ እየሱስ "የእግዚአብሔር ትክክለኛ መገለጫ ነው፡፡ "የወደቀውን ሰዎች ማንነት (1)እግዚአብሔርን መገለጥ፤(2) ስለ እኛ መሞት(በምትካችን)፤ እና(3) ለሰዎች የሕይወት ምሳሌ በመተው በትክክል መልሷታል፡፡."መሆን" (ሜኖ) የሚለው ክርስቶስን የመምሰል ሕይወት ግቡ ምን እንደሆነ ያሳያል (ሮሜ8፡29 ያስ.) |ከውድቀቱ መመለስን(ዘፍ 3 ያስ.)

ይኸ የእግዚአብሔር ከፍጥረቱ ጋር እንደገና መተባበር የህብረት ዓላማ በሐዋሪያው ጳውሎስ በክርስቶስ "መሆን "እና በሐዋሪያው ዩሐንስ "በእኔ ብትኖሩ" በሚል ተገልጽል፡፡
የዩሐንስን አጠቃቀም ያስተውሉ

1. መሆን በአባትና ልጅ መካከል
   ሀ. አባት በልጁ (ዩሐ 10፡38፤14፡10|11|20፤17፤21|23)
   ለ. ልጅ በአባት (ዩሐ 10፡38፤14፡10|11|20፤17፡21)
2. በመላክትና በአማኞች መካከል
   ሀ. አብ በአማኞች (የዩሐንስ 14፡20|23 1ዩሐንስ 3፡24፤4፡17-13|15)
   ለ. አማኞች በአብ (ዮሐንስ 14፡20|23|17፡21፤1 ዮሐንስ 2፡24፤27፤4፡13|10)
   ሐ. ወልድ በአማኞች (ዮሐንስ 6፡ 56፤14፡20|23፤15፡4|5፤17፡21|23)
   መ. አማኞች በወልድ (ዮሐንስ 6፡56፤14፡20|23|15፡4፡5፡7፤ 1ዮሐ 2፡6፤24፡27|28)
3. ሌሎች የመኖር ሀሳቦች (በአውንታዊ ጉኑ)
   ሀ. የእግዚአብሔር ቃል
      1) በአሉታዊነት (ዮሐ 5፡38፤37፤1ዮሐ 1፡10፤2ዮሐንስ 9)
      2) በአዎንታዊነት (ዮሐንስ15፡9-10፤17፡26፤ 1ዮሐንስ 3፡17ጰ4፡16)
   ለ. የእግዚአብሔር ፍቅር (ዮሐንስ 15፡9-10፤17፡26፤ 1ዮሀንስ 3፤17፤4፡16)
   ሐ. የእግዚአብሔር መንፈስ
      1. በልጁ ላይ(ዮሐንስ 1፡32)
      2. በአማኞች ላይ(ዮሐንስ 14፡17)
   መ. መታዘዝ በእግዚአብሔር መኖር ነው፡፡(ዮሐንስ 15፡10፤ 1ዮሐንስ 3፡23)
   ሠ. ፍቅር ብርሃን መሆን ነው( 1ዮሐንስ 2፡10)
   ረ. የእግዚአብሔር ዕቅድ ማድረግ በእርሱ መኖር ነው ( 1ዮሐንስ 2፡17)
   ሰ. በመቀባት መኖር (ዮሐንስ 2፡27)
   ሽ. በእውነት መኖር (2ዮሐንስ2)
   ቀ. ልጁ ይኖራል (ዮሐንስ 8፡35፤12፤34)

4. ሌሎች የመኖር ሀሳቦች (በአሉታዊነት)
   ሀ. የእግዚአብሔር ቁጣ (ዮሐንስ 3፡38)
   ለ. በጨለማ መኖር (ዮሐንስ12፡46)
   ሐ. ወደ ውጭ መጣል|መቃተል(አለመኖር) (ዮሐንስ 15፤6)
   መ. ኃጢያተኝነት (አለመኖር) (1ዮሐንስ 16፡3፡36)
   ሠ. አለማፍቀር (አለመኖር) (2ዮሐንስ 3፡14)
   ረ. ነፍስ ገዳይነት (በዘላለም ሕይወት አለመሆን) (1ዮሐንስ3፡15)
   ሰ. በሞት (1ዮሐንስ 3፡14)

▣
NASV, NKJV "የመሰናከያ ምክንያት የለውም"
NRSV "ለእንዲህ አይነቱ ሰው ማሰናከያ የለበትም"
TEV "በእኛ ለሌሎች ማሰናከያ የሚሆን ምንም አይነት ነገር የለም"
NJB "በእርሱ ለመሰናከል ምክኒያት የሚሆን ነገር የለም"

ለዚህ ጥቅስ የሚሆኑ ሁለት አተረጓጎሞች ይኖራሉ፡፡
1. በፍቅር የሚኖሩ አማኞች ሊሰናከሉ አይችሉም (ቁ.11 ያስ.)
2. በፍቅር የሚመላለሱ አማኞች ለሌሎች መሰናክል ምክኒያት ልሆኑ አይችሉም (ማቴ 18፡6፤ሮሜ 14፡13፤1ቆሮ 8፡13 ያስ.) ሁለቱም ትክክል ነው! ወንጌል ለአማኞችም ሆነ ላላመኑትም ጥቅም ነው፡፤(ለሁለቱም ሌሎች አማኞችም ለጠፋትም)

በብሉይ ኪዳን "መሰናክል "ከእምነት (ፀንቶ መቆም|ቀጥ ብሎ በመቆም) በተቃራኒ ይጠቀሳል፡፡ የእግዚአብሔር ፍቃድ እና ትዕዛዛቱ በቀና መንገድ ወይም ጎዳና ይመሰላሉ፡፡ መሄድ|መራመድ ለአኗኗር ዘይቤ በምሳሌነት መጠቀስ ያለበት በዚህ ሁኔታ ነው፡፡

ተጨማሪ የትምህርት ክፍል ማመን|እምነት እና ታማኝነት የሚሉ የብሉይ ኪዳን ቃላት በዮሐንስ 1፡14 ላይ በዚህ መልክ ማየት ይኖርበታል፡፡

**2:11 #ወንድሙን የሚጠላ ግን በጨለማ አለ: በጨለማም ይመላለሳል$** በአሁን ጊዜ የተነገረ የስም ገላጭ አድራጊ ግስ (የሚጠላ) ተከተሎ የአሁን ጊዜ አድራጊ አመላካች (ይመላለሳል) ተጠቅሶ እንመለከታለን፡፡ ጥላቻ ያለማመን ምልክት ነው፡፡ (3፡15፤4፡20 ያስ.) ብርሃንና ጨለማ፣ፍቅርና ጥላቻ በአንድ ሰው ውስጥ በአንድነት ሊገኙ አይችሉም፡፡ ይህን ዮሐንስ በአጭርና ግልጽ በሆነ ሁኔታ ገልፃል፡፡ አማኞች ብዙን ጊዜ በማስመሰል፣ባለ መውደድና በመገፋት ብዙ ይታገላሉ፡፡ ዮሐንስ ግን መሆን ያለበትን ያስቀምጣል፡፡ ወንጊል ፈጣንም ሆነ ሂደታዊ የሆነ የሕይወት ለውጥ ይመጣል፡፡

▣ **"ጨለማው አይኖቹን አሳውሮታልና"** ይህ በኃጢያተኛነት ባህሪይ የሚኖሩ አመኞችን (2ጴጥሮስ 1፡5-9) የሰይጣንን ሥራ (2ኛቆሮ4፡4) ሊያመለክት ይችላል፡፡ ሦስት የሰው ልጅ ጠላቶች አሉ፡፡ እነዚህም፡ (1) በኃጢያት የወደቀው ዓለማዊ ሥርአት ፣(2) ለእያንዳንዱ ሰው የተመደበው ፈታኝ መንፈስ፣ሰይጣን ፣እና (3) የወደቀው ማንነታችን ፣አዳማዊ ባህሪይ(ኤፌ 2፡2-3፣16፤ያዕቆብ 4) ናቸው፡፡

**NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 2÷12-14**
**[12] ልጆች ሆይ÷ ኃጢያታችሁ ስለ ስሙ ተሰርዮላችሁኂልና እጽፍላችኂለሁ፡፡ [13]አባቶች ሆይ÷ ከመጀመሪያ የነበረውን አውቋችኂልና እጽፍላችኂለሁ፡፡ ጎበዞች ሆይ÷ ክፉዉን አሸንፋችኂልና እጽፍላችኂለሁ፡፡ ልጆች ሆይ÷ አብን አውቃችሁታልና እጽፍላችኂለሁ፡፡ [14]አባቶች ሆይ÷ ከመጀመሪያ የነበረውን አውቃችሁታልና እጽፍላችኂለሁ፡፡ ጎበዞች ሆይ÷ ብርቱዎች ስለሆናችሁ የእግዚአብሔርም ቃል በእናንተ ስለሚኖር ክፋውንም ስላሸነፋችሁ እጽፍላችኂለሁ፡፡**

2:12-14 "እጽፍላችኂለሁ" (ኤን ኤ ኤስ ብ 1970) ከሚለው በስተቀር በዚህ ጥቅስ ውስጥ ያሉ ግሶች በሙሉ ጽፌላችኂለሁ (ኤን ኤ ኤስ ብ 1995) ዮ.ቢ.ኤስ[4ኛ] እንደተተረጎመው ቀጣይ ኃላፊ ጊዜ ውጤት አመልካች በሆነ ግስ ተጠቅሷል ይህም ትኩረቱ የሀሰተኞችን የትምህርት ውጤት ለማመልከት እንደነበር ከፍ ብሎ በተመለከትናቸው የትምህርት ክፍሎች አገባብ መረዳት ይቻላል፡፡ በአሁኑ ክፍል ግን ትኩረቱ በአማኞች ላይ ነው፡፡እነሱንም በሦስት ማረጎች ይጠራቸዋል ልጆቹ አባቶች እና ጎበዛዝት ከዚህ ክፍል በእርግጠኝነት የአኗኗር ዘይቤን የሚያመልከት ሀሳብ አናገኝም፡፡ በመሆኑም አማኞችን በሦስት ክፍልን የምናይበት ሁኔታ የለም፡፡ በአጠቃላይ መልኩ አማኞች በሙሉ እርግጠኛ ሲሆኑ የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች ይዘረዝራል፡፡
አማኞች ማወቅ የሚገባቸው አራት ነገሮች

1. *ኃጢያታቸው እንደተሰረየላቸው* (ቁ 12)
2. *ክፉውን እንዳሸነፉ* (ቁ 13)
3. *ከአብና* (ቁ 14) *እና ከልጁ* (ቁ 13-14)*ጋር ህብረት እንዳላቸው*
4. *በእግዚአብሔር ቃል ብርቱዎች መሆናቸውን* (ቁ.15)

እነዚህ ዝርዝሮች (1) እጽፍላችኋለሁ እና (2) ስድስት ጊዜ ምክኒያትን በሚገልጸው "እና" (በግ ሪክኛው *ሆቲ*) በሚገልጸው ሰዋሰዋዊ አግባብ ተገልጿል፡፡

▣ 2:12 **"*ኃጢያታችሁ ስለስሙ ተሰርላችኋልና*"** የእየሱስ አገልግሎት ለሰው ልጆች ብቸኛው የቅሬታ ተስፋ ነው (ውጤቱ ቀጣይ የሆነ ኃላፊ ጊዜ ተደራጊ አመልካች ግስ) *መገለጹን ያስተውሉ፡፡ በዕብራዊያን መረዳት ስም ማንነትንም ሆነ ባህሪይን በተመሳሳይ ሁኔታ ይወክላል* (3:23፣2ዮሐንስ፤ሮሜ 10:9-13፤ፊልጲ 2:6-11 ያስ.)

ስድስት ጊዜ "እና" (ሆቲ) አንቀፅ ከቁጥር 12-14 መዘርዘሩ ምክንያታዊ አንቀጽን ለማመልከት (ኤን ኤስ ቢ፣ ኤን አር ኤስ ቭ፣ኤን ጄ ቪ) "እና" ወይም በዐረፍተ ነገር መግቢያ መልክ እንዲያገለግል የተጠቀሰ ስነፅሁፋዊ እውነታን ገላጭ ሊሆን ይችላል (ስለዚህ፣ ኤን ኢ ቲ ይመ.)፡፡

2:13 **"*ከመጀመሪያ የነበረውን*"** በ1ኛ ዮሐንስ የተጠቀሱት ስመ ምትኮች አሻሚ ናቸው፡፡ እግዚአብሔር አብን ወይም እግዚአብሔር ወልድን ሊያመለክቱ ይችላሉ፡፡ በዚህ ጥቅስ አውደ ንባብ ግን ኢየሱስን *ያመለክታል፡፡* ቀድሞም የነበረውንና ከዚያ በኋላ ያለውን ሁኔታ አምላክነቱንም *ያመለክታል* (ዮሐንስ 1:1፣15፤13፤8:48-59፤17:5፣24፤ 2ቆሮ 8:9፤ፊልጶ 2:6-7 ቆላ 1:17፤ዕብ 1:3 ያስ.)

▣ **"አሸንፋችኋልና"** ይህ በ1 ዮሐንስ በተደጋጋሚ የተነገረ የተስፋ ቃል እና ማሳሰቢያ ነው፡፡ (2:14፤4:4፣5፤18-19 ያስ.) የኃላፊ ድርጊት ቀጣይ ውጤት፣ አድራጊ አመልካች ጥርቅም ውጤት ሂደት፤ በዚህ ክፍል ቀጥተኛና ግልጽ በሆነ (አሁን በግልጽ የሚታወቅ ነገር ግን ወደ ፊት ልንወርሰው ያለ ድል ሀሳብ ሲያመለክት፣ በዮሐንስ ወንጌል በተደጋጋሚ የተጠቀሰ ማሳሰቢያ ነው፡፡) አማኞች ድልነሺዎች ናቸው ሆኖም ገና ካልተፈጸሙ የእግዚአብሔር መንግስት ገጽታዎች የተነሳ ፣አሁንም ገና ከኃጢያት ጋር እንታገላለን፣እንፈተናለን፣እንሰደዳለን እንሞታለን፡፡

▣ **"ክፉውን"** ይህ ሰይጣንን የሚያመለክትና በቁ 14 ላይ የተጠቀሰ ነው፡፡ቁጥር 13 እና 14 ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ተጨማሪ ትምህርት ዮሐንስ 12:31 ላይ ይመልከቱ፡፡

▣ **"አብን አውቃችኋልና"** "ዕውቀት" የሚለው ቃል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሀሳብ በጣም የተቀራረበ ኅብረት ለሚመለከት በአይሁድ የመረዳት ሀሳብ ያካተተ ነው፡፡(ዘፍ 4:1፤1:5ያስ.) እና "ስለነገሮች ተጨባጩን" የማወቅ ግሪክኛ ሀሳብ ያካተተ ወንጌል ራሱን ክርስቶስን ማወቅና ስለራሱ ስለኢየሱስ ማንነት ማወቅንና በሕይወት ኑሮ ማሳየት ጭምር ያካትታል፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ ማወቅ (በዘዳግም መጻሐፎች አጠቃቀም የተወሰዱ ምሳሌዎች)**

"ማወቅ" (BDB ገጽ 393) የሚለው የዕብራይስጡ ቃል የተለያየ አገባብ (በቃላት ትርጓሜ አንፃር *ቃል*፡
1. ጥሩና መጥፎን መለየት-ዘፍ 3:22፤ኢሳ 7:14-15፤ዮናስ 4:11
2. በመረዳት ማውቅ ዘዳ 9:2፣3፣6፤18:21
3. በሕይወት ልምድ ማወቅ- ዘዳ 3:19፤4:35፤8:2፣3፣5፤11:2፣20:20፤31:13፡አዲሱ 23:14
4. *መረዳት* ዘዳ 4:39፡11:2፣29:16
5. በግል ፣በአካል ማወቅ
   *ሀ.* በአካል- ዘፍ 29:5፤ዘዳ 1:18፤ዘዳ 22:2፤33:9
   ለ. አምላክ -ዘዳ 11:28፤13:2፣6፣13፤28:64፤29:26፤32:17
   ሐ. *ያህዌ* - ዘዳ 4:35፣39፤29:6፤ኢሳ 1:3፤56:10-11
   *መ.* በግበረ *ሥጋ* ግንኙነት - ዘፍ 4:17፣25፤24:16፤38:26፤
6. በትምህርት የተገኘ ክህል ወይም ዕውቀት ኢሳ 29:11፣12፤አሞፅ 5:16
7. ጥበበኛ ስለመሆን ዘዳ 29:4፤ምሳ 1:2፤ኢሳ 29:24
8. የእግዚአብሔር *ዕውቀት*
   *ሀ.* የሙሴ ዘዳ 34:10
   ለ. የእስራኤል ዘዳ 31:21፣27፣29

2:14 **"ብርቱዎች ስለሆናችሁ"** ጥንካሪያቸው በቃሉ ከመኖር እንደሆነ ያስተውሉ፡፡ ይህም በኤፌ 6:10-18 ከተሰጠው ማሳሰቢያ፣ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ የምንኖርበት ቃል ወንጌሉ ነው፡፡ እርሱም በዕውቀትም በኑሮም የሚገልጽ ነው፡፡ ይህን

እንድንቀበል ሁኔታዎችን የሚያመቻችና በግል ወስነን እንድንቀበል የሚረዳን እግዚአብሔር ነው። ውሳኔውና መከተላችንም፣እውነትም ሆነ የመታመናችን ጉዳይ ሁሉም ከእርሱ ነው።

▣ **"የእግዚአብሔር ቃል በእናንተ ስለሚኖር "** ይህ ቃልን ሰውኛ ባህሪይ ያላበሰ አገላለጽ ነው። (ወንጌል ቁ.24 ያስ) የዮሐንስ -15 ምሳሌ ነው። በዮሐንስ 5፡38 እና 8፡37 በአሉታዊ ጉኑ ተጠቅሷል።

▣ **"ክፉውንም ስላሸነፋችሁ"** ይህ የእውነተኛ ቅዱሳንን ፅናት በአትኩሮት ለመግለጽ የተጠቀመው አገላለጽ ነው። በተጨማሪም በቁጥር 17፣19፣24፣27፣28፣፤5፡18 እና 2ኛ ዮሐንስ 9 የቅዱሳን መዳን እርግጠኛነት ሀሳብ በእውነት የተዋጁት እስከመጨረሻው መጽናት ይጠበቅባቸዋል ከሚለው ጋር አብሮ መታየት ይኖርበታል። (ራዕይ 2፡7፤11፡17፣26፤3፡5፣12 ያስ) ተጨማሪ የትምህርት አርዕስት የመጽናት አስፈላጊነት የሚለውን ርዕስ በዮሐንስ 8፡31 ላይ ይመልከቱ። ይህ ከኃጢያት ነፃ መሆንን አያመለክትም በክርስቶስ ስለ ተጠናቀቀ ሥራ ምናባዊ እይታ ነው።(ሮሜ 6 ያስ.)

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 2፡15-17
**15፡16ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ፤ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፥ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም። 17ዓለሙም ምኞቱም ያለፋሉ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል።**

2፡15 "አትውደዱ" የአሁን ጊዜ አድራጊ አመልካች ትዕዛዛዊ ሆኖ በአሉታዊ ስም ገላጭ ግስ የተነገረ ዐ ነገር ሲሆን ሂደታዊ የሆነ ድርጊት ለማቋረጥ ሲፈለግ የሚናገር ነው። በዚህም ዓለምን የመውደድ ገጽታ የነበረው የአንደኛውን የኖስቲሳዊያንን መምህራንን ገፅታ ነው።

▣ *"ዓለምን"* ይህ ቃል በሁለት የተለያየ መንገድ ሥራ ላይ ውሏል በአዲስ ኪዳን (1) የሚታየውን ግዑዝ ዓለም ወይም ፍጥረታትን (የዮሐንስ 3፡16፤16፡33፣ 1ዮሐንስ 4፡14)እና (2) ከእግዚአብሔር ሀሳብ ውጪ የተደራጀውንና የሚንቀሳቀሰውን የሰው ልጅ(1ዮሐ 2፡15-17፤3፡1፣13፤4፡45፤5፡4-5፤19) የመጀመሪያው የፍጥረት መጀመሪያ(ዘፍጥረት 1-2ያስ.) እና ሁለተኛው በኃጢአት ምክኒያት የወደቀውን ፍጥረት(ዘፍጥረት 3 ያስ.) ያመለክታል። ተጨማሪ የጥናት አርእስት፡ ኮስሞስ14፡17 ይመልከቱ።

**ልዩ ርዕስ፡ የሰው ልጅ መንግስት**

I. *መግቢያ*
  ሀ. የቃሉ ትርጓሜ - መንግስት ሰዎች ፍላጎታቸውን ለማስጠበቅ ራሳቸውን የሚያደራጁበት ሁኔታ ነው።(ዘፍጥረት 4እና 11) ሰዎች ማኃበራዊ እንስሳ ናቸው (በኃጢያት ከመውደቃቸው በፊትም ቢሆን)(ዘፍጥረት 2፡18 ያስ.) ቤተሰብ፣ዘር እና ሕዝቦች መንግስትን ይመሰርታሉ።
  ለ. ዓላማ - እግዚአብሔር ከስርዓት አልበኝነት ይልቅ የተደራጀ አሠራርን ስለሚመርጥ ነው።
    1. የሙሴ ህግ ፣በተለይ አስርቱ ትዕዛዛት በማህበረሰቡ ውስጥ የሚኖረውን የእግዚአብሔርን ፍቃድ ያሳያል።ሕጉ አምልኮን ከሕይወት ጋር ያመጣጥናል።
    2. ጥንታዊ የኢስራኤል መለኮታዊ አስተዳደር ከሰማይ የተሰጠ ቢመምስልም እንኳን መፅሀፍ ቅዱስ የትኛውንም የአስተዳደር ሥርዓት አይደግፍም። ዲሞክራሲም ሆነ ካፒታልዝም መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደሉም። ክርስቲያን ባለበት በየትኛውም የአገዛዝ ሥርአት ውስጥና ለክርስትና በሚገባ ሥርዓት መመላለስ አለበት። የክርሲቲያን ዓላማ የወንጌል ስርጭትና አገልግሎት እንጂ አብዮት ማካሄድ አይደለም ምክኒያቱም ሁሉም ምድራዊ መንግስታት ያልፋሉና!
  ሐ. የሰው ልጅ የአገዛዝ ስርዓት አመጣጥ
    1. የሮም ካቶሊክ ቤተክርሲቲያን የሰው ልጅ በኃጢያት ከመውደቁ በፊትም ቢሆን የአስተዳደር ስርዓት ፍላጎት ነበረው ብላ ታምናለች። ይህን ሀሳብ መጀመሪያ ያመነጨው አርስቶትል ይመስላል። እርሱም ሰው ማኃበራዊ እንስሳ ነው። ይል ነበረ። በዚህ አባባሉ "መንግስታት ለተቃና ሕይወት የቆሙ ናቸው ማለት ነው።
    2. ፕሮቴስታንቶች በተለይም ማርቲን ሉተር፣የሰው ልጅ አገዛዝ በኃጢያት በመውደቁ የወረሰው መሆኑን ይገልጻል። ይህንንም "የእግዚአብሔር ግራ እጅ ነው" ብሎ ይጠራ ነበር እግዚአብሔር ክፉ ሰዎችን የሚቆጣጠረው ክፋዎችን ወደ ስልጣን በማምጣት ነው ይል ነበር።
    3. ካርል ማርክስ ፣ጥቂት የነቃ አዕምሮ ያላቸው ብዙሃኑን በቁጥጥር ስር የሚያኖሩበት መንገድ ነው ይል ነበር።

II. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች

ሀ. ብሉይ ኪዳን

1. እስራኤል በሰማይ ላለው የእግዚአብሔር ስርዓት ምሳሌ ናት በጥንታዊት እስራኤል ያህዌ ንጉሥ ነው ትኦክራሲ የእግዚአብሔርን ቀጥተኛ አገዛዝ ይገልጻል (1ሳሙ 8፡4-9 ያስ.)
2. የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት በሚሾማቸው ሰዎች በግልጽ ይታያል፡፡
   ሀ. ነገስታትን በሙሉ ዳን 2፡21፤4፡17፣24-25
   ለ. በመሢሁ አገዛዝ ዳን 2፡44-45
   ሐ. ናቡኬዴናጾር (አዲስቱ ባቢሎን) ፣ኤር 276፤ዳን 5፡28
   መ. ዳግማዊ ቂሮስ ( የፔርሽያው) 2ኛ ዜና 36፡22ዕዝራ 1፡1 ኢሳ 44፡28፤45፡1
3. የእግዚአብሔር ሰዎች ለወራሪ መንግስታትና ለቀኝ ገዥዎችም ቢሆን ታማኝና ተዛዥ መሆን ይኖርባቸዋል
   ሀ. ዳንኤል 1-4፣ናቡከዴናጾር (አዲስቱ ባቢሎን)
   ለ. ዳንኤል 5፣ብልጣሶር (አዲስቱ ባቢሎን)
   ሐ. ዳንኤል 6፣ዳርዮስ (ፔርሽያ)
   መ. ዕዝራና ነህሚያ(ፔርሽያ)
4. ከምርኮ የተመለሰችው ይሁዳ ለዳርዮስና ለወራሾቹ መጸለይ ነበረባት
   ሀ) ዕዝራ 6፡10፤7፡23
   ለ) አይሁድ ለምድራዊ ባለስልጣኖቻቸው መደለይ ነበረባቸው፣ሚሽናህ፣አቮት 3፡2

ለ. አዲስ ኪዳን

1. ኢየሱስ ለምድራዊ መንግስታት አክብሮት ነበረው፡፡
   ሀ) ማቴ 17፡24-27፣ግብር በማከፋፈል (ለሃይማኖትና ማሕበራዊ ባለስልጣናት፣1ኛጴጥ 2፡17)
   ለ) ማቴ 22፡15-22፤ማር 12፡13-17፤ሉቃ 20፡20-26 ፣ለሮም መንግስት ቀረጥ መክፈል እንዳለበት በመግልጽ በዚህም ለሮማዊያን ባለስልጣናት ስለመገዛት፤
   ሐ) ዮሐንስ ፡19፡11፣ ኢግዚአብሔር ምድራዊ መንግስታት እንዲኖሩ በመፍቀዱ
2. ጳውሎስ ስለምድራዊ መንግስታት ከጻፈው፡
   ሀ. ሮሜ 13-5 ባለስልጣናትን በእግዚአብሔር የተሸሙ በመሆናቸው አማኞች ሊታዘዙላቸው ይገባል፡፡
   ለ. ሮሜ 13 6-7 አማኞች ባለስልጣናትን ማክበርና ግብር መክፈል እንዳለባቸው
   ሐ. 1ጴጥ 2፡1-3 አማኞች ለባለስልጣናትን መጸለይ እንዳለባቸው፡፡
   መ. ቲቶ 3፡1 አማኞች ለባለስልጣናትን መገዛት አለባቸው
3. ጴጥሮስ ስለ ምድራዊ መንግስታት ከጻፈው፡፡
   ሀ. ሐዋ ሥራ 4፡1-31፤5፡29 ጴጥሮስና ዮሐንስ በሸንጎ ፊት ( ለባለስልጣናት ስለምንገዛበት ቅድመ ሁኔታ በገለፁበት
   ለ. 1ጴጥ 2፡13-17 ለማህበረሰቡ ጥቅምና ለወንጌል ሥርጭት ሲባል ለባለሥላጣናት መገዛት እንደሚገባ በገለፀበት፤
4. ዮሐንስ ስለምድራዊ መንግስታት ከጻፈው
   ሀ. ራዕይ 17፣አመንዝራይቱ ባቢሎን ላይ የተላለፈው ፍርድ ከእግዚአብሔር በተቃራኒ ስለቆሙት መንግስታት
   ለ. ራዕይ 18፣ያመንዝራይቱ ባቢሎን ጥፋት

III. ማጠቃለያ

ሀ. ሰብአዊ መንግስታት (በወደቀው ዓለም) በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው ይህ ገዥዎቹ ከእግዚአብሔር በመሆናቸው ሳይሆን እግዚአብሔር ለክብሩ ስለሚጠቀማቸው ነው፡፡ የትኛውም የአስተዳደር አይነት ከሌላይኛው የሚበልጥበት ሁኔታ የለም፡፡

ለ. ለባለ ስልጣናት መጸለይ የአማኞች መንፈስዊ ተግባር ነው፡፡

ሐ. መንግስትን ማክበርና ግብር መክፈል ለክርሲቲያኖች የተገባ ተግባር ነው፡፡

መ. ሰብአዊ አገዛዝ መሃበራዊ ስርኣትን ለማስፈን አላማ የቆሙ ናቸው፡፡ይህን ተግባር ለማስፈፀም የተቀመጡ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው፡፡

ሠ. ሰብአዊ አገዛዝ የመጨረሻና ዘለለማዊ አይደለም ስልጣኑ የተገደበ ነው፡፡ መንግስታት ከተመደበላቸው ገደብ አልፈው ስልጣናቸውን ሲጠቀሙ አማኞች ያለመገዛት የሂልና ነጻነት አላቸው ኦግስቲን የተባለው የቤተክርስቲያን አባት ዘ ሲቲ ኦፍ ጎድ በተሰኘው መጽሐፉ “እኛ የሁለት ዓለም ዜጎች ነን አንደኛው ጊዜያዊ ሌላኛው ዘላለማዊ (ፊልጵ 3፡20 ያስ.)” ያለው ለዚህ ነው፡፡ በሁለቱም መንግስታት ኃላፊነት አለብን፣የመጨረሻውና ከፍተኛ ቦታ የምንሰጠው ግን ለእግዚአብሄር መንግስት ነው፡፡ ለእግዚአብሄር በምሆነው ጉዳይ በግልም ሆነ በጋራ ትኩረት የሚደረግባቸው ነጥቦች አሉ፡፡

ረ. አማኞች በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ በመንግስታዊ ሥራዎች እንዲሳተፉ ቢቻል መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆኑ መርሆዎችን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ማደፋፈር ይኖርብናል።
ሰ. የግለሰቦች የሕይወት ለውጥ ማህበራዊ ለውጦችን መቅደም አለበት ምድራዊ መንግስታት ሰለመጨው ዘመን ተስፋ ሊጣልባቸው የሚያስችል ነገር የላቸውም። ምንም እንኳን እግዚአብሔር ቢጠቀማቸውም ሁሉም ሰብአዊ መንግስታት፣ከእግዚአብሔር ርቀው የሚንቀሳቀሱ በኃጢአት የወደቀው የሰው ልጅ መገለጫዎች ናቸው። "ዓለም" በሚለው የዮሐንስ አገላለጽ የተመለከተው ይኸው የፍጽምና ጉድለት ነው (1ዮሐንስ 2፡15-17 የስ )።

▣ **"በዓለም ያሉትን"** ይህም በዓለም ቁሳዊ ነገሮችን (ቁ.16 ያስ) ወይም እንደ ሥልጣን ኃይል ፣ተደማጭነትን የመሳሰሉ የዓለም ገጸ በረከቶችን ሊያመለክት ይችላል (ሮሜ 12፡2፤ራዕ 1፡27 ያስ.) በዚህ የወደቀው ዓለም ሥርዓት ከእግዚአብሔር ርቆ የሰውን ልጆች ፍላጎት ለማሟላት ጥረት ያደርጋል። ሰዎች በራሳቸው ጥረት ብቻ ሕይወታቸውን መምራት እንደሚችሉ ያደርጋል ከእግዚአብሔር ከመደገፍ ውጪ ተስፋ የምናደርግባቸው ተቋማት ሁሉ ከአምላክ የተለየ ሕይወት እንዲንኖር የሚያደርግ ከሆነ ጣኦት ሊሆንብን ይችላሉ። ለዚህ በምሳሌነት ሊጠቀሱ የሚችሉት(1) ሰብአዊ መንግስታት ስርዓት፤(2) ሰብአዊ የትምህርት ሥርዓት፤(3) ሰብአዊ የኢኮኖሚ ስርዓት፤(4) የሕክምና ተቋማት ወዘተ.....

አውግስቲን በትክክል እንደገለጸው የሰው ልጅ ያለ እግዚአብሔር ሊደፈን የማይችል አንድ የሕይወት ክፍል አለው። እኛ ግን እነዚህን ነገሮች በምድራዊ ነገሮች ለመሙላት ጥረት እናደርጋለን። ሆኖም እውነተኛ ሰላምና ስኬት ማግኘት የምንችለው በእግዚአብሔር ብቻ ነው። ግለኝነት ከኤደን የሚያስወጣ እርግማን ነው!

▣ "ቢ..." ይህ ሦስተኛ መደብ ሊሆን የሚችል ድርጊት አመልካች ዐ.ነገር ክፍል ነው። የምነወደው ነገር የሰይጣን ወይስ የእግዚአብሔር የማን መሆናችንን ያሳያል።

2:16 **"የሥጋ ምኞት"** ይህ በሀጢያት የወደቀውን ራስን የመውደድ ማንነት ያመለክታል (ገላ 5፡16-21፤ኤፌ 2፡3፤1ጴጥ 2፡11 ያስ) ተጨማሪ የትምህርት አርዕስት ሥጋ (ሣራክስ) ዮሐንስ 1፡14 ይመልከቱ

▣ **"የአይን አምሮት** "አይሁድ ፣አይን የነፍስ መስኮት ነው ብለው ያስባሉ ኃጢያት ከአስተሳሰባችን ይጀምራል ከዚህም በህይወታችን መስራት ይጀምራል ሥራችንም አድጎ የሕይወት ልምድ ይሆናል (ዮሐንስ 19፡13)

▣ **"ስለ ገንዘብም ትምክሕት"** ከእግዚአብሔር ውጪ ያለውን የሰው ልጅ ትምክህት ያመለክታል (ለምሳሌ የሀብት መጠን መመከት) ታዋቂው የካቶሊክ ሊቅ የሆነው ራይሞንድ ብራውን፣በጀሮም ኮሜንተሪ ጥራዝ 2 እንዳብራራው።

"ትምክህት (አልዞኒያ) በያዕቆብ 4፡16 ላይ ጭምር የተጠቀሰ ሲሆን ከተራ ትምክህት የዘለለና፣ትዕቢት ከልክ ያለፈ ትምክህት፣ሌሎችን የመናቅ ራስን ፍፁም አርጎ የመመልከት ትምክህት ነው።"

ሕይወት ወይም ኑሮ (ባዮስ) ፣ምድራዊ፣የሚታይና ጊዜያዊ የሆነውን የዚህን አለም አኗኗር ያመለክታል (ይህም የሰው ልጅ እንሰሳትና ዕፀዋት የሚመሳሰሉበትን ያመለክታልከ 1ዮሐ 3፡17 ጋር ያስተያዩ) የዚህን አይነት ሕይወት የኖስቲስዊያን የሐሰት ትምህርት መምህራን ዳግመኛ ያልተወለደውን የሰው ልጅ ባህሪይ ያመለክታል።እኛ ግን በእግዚአብሔር ዕርዳታ ከዚህ መጥተናል። ይህ ሕይወት ያላደጉ ክርስቲያኖችን ሕይወትም ልያመለክት ይችላል!

▣ " **ከዓለም ስለሆነ እንጂ ከአባት ስለአልሆነ"** ክርስቲያኖች አለምን መውደድ የሌለባቸው በሁለት ምክኒያቶች ነው።

1. ዓለምን መውደድ ከእግዚአብሔር ባለመሆኑ (ቁ 16)
2. ዓለም የሚያልፍ በመሆኑ (ቁ 17)

2:17 **"ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ"** የአሁን ጊዜ ሁለተኛ መደብ አመልካች (2፡8 ያስ) የአይሁድን የዓለም ሂደት ደረጃ አመዳደብ ያሳያል፤ አሁን ያለው፣ ሊመጣ ያለውና አዲስ አለም እና እያለፈ ያለው አሮጊውን አመጻኛው ዓለም (ሮሜ 8፡18-25 ያስ)

**ልዩ ርዕስ:ይህ ዓለም ፣የሚመጣው ዓለም**

የብሉይ ኪዳን ነቢያት መጪውን ጊዜ የአሁን ጊዜ ቀጣይ አርገው ይመለከታሉ ለነሱ መጪው ጊዜ ምድራዊቷ እስራኤል የሚታደስትበት ጊዜ ነው፡፡ ምንም እንኳን እንደ አዲስ ቀን ቢመለከቱም (ኢሳ 65:17፤66:22) የአብረሃም ልጆች በያህዌ ላይ በማመፅ መቀመጣቸው በሁለቱ ኪዳንና መካከል በተጻፉት ትንቢታዊ መጽሐፍት (1ኛሄኖክና 4ኛባሮክ) የአዲስ ሥርዓት ሀሳብ አመንጭተዋል፡፡ እነዝህ ጽሁፎች ሁለቱንም ዘመናት፣ አሁን በሰይጣን ቁጥጥር ስር ያለውንና በመንፈስ ቅዱስ ተጽዕኖ ጽድቅ የምሰፍንበትና በመሢሁ የሚመሠረተው አዲሱ ዘመን በማለት ልዩነታቸውን ያሳያሉ፡፡

ባለንበት የመጨረሻው ዘመን ስነመለኮታዊ ትምህርት ፣«መንፈሳዊ መገለጥ ይበልጥ የተብራራበት» በመሆኑ በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት በግልጽ ይታያል፡፡ አዲስ ኪዳን ሁለቱን መንፈሳዊ አላማት መኖር(ለጊዜው የሁለት ጊዜያት) መኖር ያረጋግጣል፡፡

| ኢየሱስ | ጳውሎስ | በዕብራዊያን መልክት |
|---|---|---|
| ማቴ 12:32 | ሮሜ 12፤2 | 1:2 |
| ማቴ 13:22፣29 | 1ቆሮ 1:20፤2:6፣8፤3:18 | 6:5 |
| ማርቆስ 10:30 | 2ቆሮ 4:4 | 11:3 |
| ሉቃ 16:8 | ገላ 4 | |
| ሉቃ 18:30 | ኤፌ 1:21፤2:17፤6:12 | |
| ሉቃስ 20:34-35 | ጢሞቲዎስ 6:17 | |
| | 2ጢሞቲዎስ 4:10 | |
| | ቲቶ 2:12 | |

ካልተጠበቁና አንደኛቸው በሌላኛው ውስጥ ከሚካተቱ የመሢሁ ዳግመኛ መምጣት ጋር ከተያያዙ ትንቢቶች የተነሳ የአይሁድ የሁለት ዘመን ትምህርትም አንደኛው በሌላኛው ውስጥ የተካተተበትን ሁኔታ እንመለከታለን፡፡ የክርስቶስ ሥጋ መሆን የአዲስ ዘመን ጅማሬ ነው (ዳን 2:44-45) ሆኖም ብሉ ኪዳን ምጽቱን እንደ ፈራጅና እንደ ድልነሽ ይገልጸዋል፡፡ መጀመሪያ መከራን እንደምቀበል አገልጋይ እንደሚገለፅ (ኢሳ 53፤ዘካ 12:10)፣ትሁትና ራሱን ዝቅ በማድረግ (ዘካ 9:9) እንደሚገልጽ መተንበዩንም እንመለከታለን፡፡ ዳግመኝ ምጻቱ በብሉይ ኪዳን እንደተተነበየ በኃይልና በስልጣን ይሆናል(ራዕ 19 86) የዚህ የሁለት ደረጃ የትንቢት ፍጻሜ የአሁን ዘመን የትንቢቱ ጅማሬ መጪውን ጊዜ (ገና ያልተጠናቀቁ ነገሮችን) ይይዛል፡፡ ይህም በተፈጸሙ እና ገና ባልተፈጸሙ የአዲስ ኪዳን ትንቢቶች መካከል ያለ ውጥረት ነው!

▣ **"የእግዚአብሔርን ፍቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላላም ይኖራል ፡፡"** የዘላላም ሕይወት ከአኗኗር ጋር እንዴት እንደተገኛኘ (ቃል በቃል በዘመኑ ውስጥ መኖር ነው፡፡) የዘላለም ሕይወት በፍቅር የሚገለጽ እንጂ የመጀመሪያው እምነት ውሳኔ (ማቴ 25:31-46፤ያዕ 2:14-26 ያስ.) ጋር የተያያዘ አይደለም፡፡ ተጨማሪ የትምህርት አርዕስት የእግዚአብሔር ፍቃድ ዮሐ 4:34 ይመልከቱ፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 2:18-25

**[18]ልጆች ሆይ÷ መጨረሻው ሰዓት ነው÷ የክርስቶስም ተቃዋሚ ይመጣ ዘንድ እንደሰማችሁ አሁን እንኳ ብዙዎች የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ተነስተዋል፤ ስለዚህም መጨረሻው ሰዓት እንደሆነ እናውቃለን፡፡ [19]ከእኛ ዘንድ ወጡ÷ ዳሩ ግን ከእኛ ወገን አልነበሩም፡ ከእኛ ወገንስ ቢሆኑ ከእኛ ጋር ጸንተው በኖሩ ነበር፤ ነገር ግን ሁሉ ከእኛ ወገን እንዳልሆኑ ይገለጡ ዘንድ ወጡ፡፡ [20]እናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብላችኋል÷ ሁሉንም ታውቃላችሁ፡፡ [21]እውነትን የምታውቁ ስለሆናችሁ÷ ውሸትም ሁሉ ከእውነት እንዳልሆነ ስለምታውቁ እንጂ እውነትን ስለማታውቁ አልጽፍላችሁም ፡፡ [22]ክርስቶስ አይደለም ብሎ ኢየሱስን ከሚክድ በቀር ውሸተኛው ማን ነው? አብንና ወልድን የሚክድ ይህ የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው፡፡ [23] ወልድን የሚክድ ሁሉ አብ እንኳ የለውም፤ በወልድ የሚታመን አብ ደግሞ አለው፡፡ [24]እናንተስ ከመጀመሪያ የሰማችሁት በእናንተ ጸንቶ ይኑር፡፡ ከመጀመሪያ የሰማችሁት በእናንተ ቢኖር÷ እናንተ ደግሞ በወልድና በአብ ትኖራላችሁ፡፡ [25]እርሱም የሰጠን ተስፋ ይህ የዘላለም ህይወት ነው፡፡**

2:18 "**ልጆች ሆይ** " የ2:1 ማብራሪያ ይመልከቱ

▣ **"መጨረሻው ሰዓት ነው"** የመጨረሻው ሰዓት የሚለው ቃል ያለ አመልካች (በዚህ ጥቅስ ብቻ) ተጽፎ እናገኛለን ልክ እንደ "መጨረሻ ቀኖች " የክርስቶስን ዳግመኛ መምጣት ለማመልከት በአዲስ ኪዳን ከተጠቀሱት ሐረጋት አንዱ ነው፡፡ (ከዮሐንስ 6:39-40, 44 ያስ.) በዮሐንስ ጽሐፎዎች ይህ መሠረታዊ ጽንሰ ሃሳብ ነው፡፡ ምክንያቱም በዘመናችን አብዛኞቹ ተርጓሚዎች "ግልጽ የሆነ የመጨረሻው " ዘመን ስነ መለኮታዊ ትምህርቶች " (የሺህ ዓመት መንግስት አሁን ሆኗል የሚለው ትምህርት የሚለው የ ሲ ኤች ዶድ ትምህርት ተጽዕኖ አድርጎባቸዋልና፡፡ ዮሐንስ ለየትና ጠንክር ባለ አገላለጽ በክርስቶስ መምጣት የእግዚአብሔር መንግስት እውን መሆኗን ያስተምራል፡፡ ይኸው ጽሁፍ በተጨማሪ ወደ ፊት የሚከናወኑ (ድርጊቶች ወይም ዘመናት) እንዳሉ ይገልጻል፡፡ ሁለቱም አመለካከቶች ትክክል ናቸው፡፡ ሀሳቡ በአዲስ ኪዳን

ከሚገኙ በተፈጸሙና ገና ባልተከናወኑ የመጨረሻው ዘመን ትምህርቶች (ስለ ምጻቱ) ተቃራኒ ከሚመስሉ ትምህርቶች አንዱ ነው።እነዚህም ከፍ ብሎ እንደተመለከትነው በአይሁድ እምነት ሁለት የተለያዩ ዘመናት ሲሆን አሁን አንደኛቸው በሌላኛው ተተክተው እንመለከታለን።

▣"**የክርስቶስ *ተቃዋሚ*..... የክርስቶስ *ተቃዋሚዎች*** " ይህ ገላጭ ሐረግ በብዙና በነጠላ ቁጥር መገለጹን፣የተወሰነ አመልካች አለመኖሩን ያስተውሉ (ኤም ኤስ ኤስ ℵ፣ቢ፣ሲ መሠረት) በአዲስ ኪዳን በዚህ መልክ ሲጠቀም የምንመለከተው ዮሐንስ ብቻ ነው (2፡18፣22፤4፡3፤2 ዮሐ.7) ለተጨማሪ ማብራሪያ 2፡3-27፣ዲ ይመልከቱ

▣ "**ይመጣ ዘንድ**" የአሁን ጊዜ አመልካች ግስ የተራው ሕዝብ መነጋገሪያ በነበረው (ኮይኔ) ግሪክኛ አንዳንድ ግስች ሥራ ላይ በማይውሉበት ጊዜ ሌሎች ግሶች የዚህን ሚና ተክተው ይጫወታሉ። እነዚህ ወካይ ግሶች ተደራጊ ቢሆኑም እንደ አድራጊ ይተረጉማሉ። በዚህ ክፍል በአሁን ጊዜ መገለፁ የወደፊት ድርጊት ቢሆንም ስለመፈጸሙ እርገጠኛ መሆንን ያመለክታል። የክርስቶስ ተቃዋሚ እየመጣ ነው። በርካታ እርሱን መሳይ ሀሰተኛ መምህራን ወይም ሀሰተኛ መሢሆችም (ተቃዋሚዎች) ተገልጿል።

በስነ መለኮታዊ አተያይ ክርስቶስ መች እንደሚመጣ ስለማይታወቅ በማንኛውም ጊዜ ሐሰተኛውን *መሢህ* በማዘጋጀት ወደ ዓለም ያመጣል።

▣ "**ተነስተዋል** " ይህ የድርጊ ውጤት አድራጊ አመልካቾች ነው። የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ አሁንም በዚህ በኃጢአት በወደቀው ዓለም ውስጥ በንቃት እየሰራ ሲሆን ወደ ፊት ይገለጻል። በአንዳንድ ተረጓሚዎች ይህ ቃል በዮሐንስ ዘመን የነበረውን የሮሜ ግዛት ይመለከታል ሲሉ ሌሎች ደግሞ ወደ ፊት ሊነሳ ያለውን የዓለም ኃያል መንግስት ይመለከታልይላሉ። በብዙ መልኩ ሁለቱም የሚፈጸሙ ይመስላል! የመጨረሻው ሰዓት ሥጋ ለብሶ በተገለጠበት ጊዜ ተጀምሯል በዳግመኛ ምጽቱ የመጨረሻው ይሆናል።

2፡19 "**ከእኛ ዘንድ ወጡ ዳሩ ግን ከእኛ ወገን አልነበሩም**" ይህ በአጥቢያ ቤተክርስቲያን የሚታይ የሐሰተኛ መምህራን አይነተኛ መገለጫ ነው። (ማቴ 7፡21-23፤13፡1-9፣18-23፣24-30 ያስ.) በእውነትና በፍቅር መጽናት አለመቻል እውነት አማኞች አለመሆናቸውን ያመለክታል። የኑፋቄ ትምህርት ሁሉም ከውስጥ ይነሳል!

የ1ኛ ዮሐንስ ፀሐፊ በቃላት ምርጫ ላይ ጥንቁቅ መሆኑ በቁጥር 19 ላይ በትክክል ተንጸባርቋል።

1. ሐሰተኞች መምህርን ከኛ መካከል ወጡ(በኃላፊ ጊዜ)
2. ከእኛ ወገን አልነበሩም (የኃላፊ ድርጊት ቀጣይ ውጤት አመልካች)
3. ከእኛ ወገን ቢሆንማ ኖሮ ከእኛ ጋር ፀንተው በኖሩ ነበር (ሁለተኛ መደብ ሁኔታን አመልካች ግስ የኃላፊ ኃላፊ ጊዜ ሂደታዊ ድርጊት አመልካች ጋር) ተጨማሪ የጥናት አርዕስት፣ የአመጽ ሰው ዮሐንስ 17፡12 ይመልከቱ።

▣ "**ቢ...**" በሁለተኛ መደብ ሁኔታን አመልካች ግስ ፣የተጨባጭ እውነታ ተቃራኒ የሆኑ ነገሮችን ለማመልከት የተነገረ ነው። ከእኛ ወገን አልነበሩም እንጂ ቢሆንማ ከእጂ ጋር ጸንተው በኖሩ ነበር፤ስለዚህ አልነበሩም ተብሎ ሊተረጎም ይችላል።

▣ "**ከእኛ ጋር ጸንተው በኖሩ ነበር**" የኃላፊ ኃላፊ ጊዜ ሂደታዊ አድራጊ አመልካች እስከመጨረሻ በኃላፊ ጊዜ የተጠናቀቀ ድርጊት አመልካች የተነገረ ሲሆን ጸንቶ የመቆምን አስፈላጊነት ለማጉላት ከተጻፋት ክፍሎች አንዱ ነው (ቁ 24፣27፣28) እውነተኛ እምነት ጸንቶ ይቆማል ፍሬም ያፈራል (ማቴ 13፡1-23 ያስ) ተጨማሪ የጥናት ርዕስ ዮሐንስ 8፡31 ላይ ይመልከቱ።

2፡20 "**ከቅዱሱ ቅባት ተቀብላችኋል**" እናንተ በግሪክኛው ብዙ ቁጥር ክርሲትያኖች ህብረት ከወጡት ጋር በማስተያየት የተናገረ ነው። በምስራቃዊያን ምስጥራዊ ልምምድ ተፅኖ ስር የወደቁጥ ኖስቲሳዊያን ከአማልክት ጋር የሚያገኛቸውን የተለየ የዕውቀት ቅባት እንደሚያገኙ ተምረዋል። ዮሐንስ ግን ከአምላክ የተቀቡት (የተለያየ ዕውቀት) ያላቸው አማኞች እንድሆኑ ያስገነዝባል።

**ልዩ ርዕስ፡ ቅዱሱ**

ቅዱሱ የሚለው ቃል የሚከተሉትን ሊያመለክት ይችላል።

1. እግዚአብሔር አብ (የእስራኤል ቅዱስ በሚል የተጠቀሰባቸውን የብኪ ክፍሎች ስ.)
2. እግዚአብሔር ወልድ (ማርቆስ 1፡24፤ሉቃ 4፡34 ዮሐንስ 6፡6፤4፡14 ያስ.)
3. እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ (መንፈስ ቅዱስ የሙሴን የማዕረግ ስም ዮሐንስ 1፡33፤14፡26፤20፡22 ያስ)

በሐዋሪያት ሥራ 10፡38 ሥላሴን በመቀባት ሥራ እንመለከታለን ጌታ ኢየሱስ ተቀብቷል(ሉቃ 4፡18፤ሐዋ.ሥራ.4፡17፤10፡38 ያስ.) በዚህ ክፍል አማኞችን ሁሉ በሚያካትት መልክ ሰፋ ብሎ ተጠቅሷል (1ኛ ዮሐንስ 2፡27) ቅዱሱ የሚለው ቅዱሳን በሚል መግለፁ ምናልባት ተቃዋሚ እና ተቃዋሚዎች ከሚለው ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ለመግለጽ ይመስላል።( 1 ዮሐንስ 2፡18 ያስ.) በብሉይ ኪዳን በሚታይ ሁኔታ መቀባት (ዘጸአት 29፡7፤30፡25፤37፡29) ይህም ለተለየ ሥራ በእግዚአብሔር ተጠርተውና ተዘጋጅተው የሚወጡትን (ነቢያት፣ ካህናት እና ነገስታትን) ያመለክታል። ‹‹ክርስቶስ›› የሚለው የዕብራስጥ ቃል ‹‹የተቀባው›› ወይም መሢህ ማለት ነው።

▣ "ቅባት " ተጨማሪ የትምህርት አርዕስ "ቅባት" የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ዮሐ 11፡2 ይመልከቱ

▣

NSB "እናንተ ሁላችሁም ታውቃላችሁ "
NKV "እናንተ ሁሉንም ታውቃላችሁ"
NRSV "እናንተ ሁላችሁም ታውቃላችሁ "
NJB "ሁላችሁም ዕውቀትን ተቀበላችሁ"

ከኖስቲሳዊያን የሐሰት ትምህርት አኳያ አገላለፁን መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ሀሰተኞች ግን ድፍረት በተሞላበት ሁኔታ ምስጥርዊ ዕውቀት እንዳላቸው ይናገራሉ፡፡ ዮሐንስ ክርስቲያኖች መሠረታዊ ዕውቀት እንዳላቸው(ቁ፡27)፤ዮሐንስ 16፡7-14፣ኤር 31፡34 )ነገር ግን ዮሐንስ እንደሚገልጸው ስለመንፈሳዊ ነገሮች ወይም ስለመንፈሳዊው ዓለም ጥልቅ ዕውቀት ባይኖረውም (3፡2 ያስ.) በቅባት ከተመሰለው ከመንፈስ ቅዱስ ወይም ከወንጌሉ ዕውቀትና የሕይወት ልምምድ እውነት አላቸው፡፡

ሐረጉን በሚመለከት በግሪክኛ እጅ ፅኁፎች መካከል ልዩነት አለ፡፡ ኤን ኬጄ ቪ በትላልቅ ፊደላት የተጻፉትን (አንካል) ኤ፣ሲ፣እና ኬ መሰረት በማድረግ ሁሉ (ፖንታ) ግኡዝ ፆታ አመልካች በቀጥተኛ ተሳቢነት መሠረት ይተረጉማል፡፡ በአንፃሩ ኤን ኤ ኤስ ቢ ጽ ቢ እና ፐ መሠረት ሁላችሁ (ፖንቴስ) ወንዴ ፆታ ብዙ ቁጥር አመልካች መሠረት ይተረጎማል፡፡ በዚህም እናንተ ሁላችሁም በሚለው የዐረፍተ ነገሩ ባለቤት ላይ ማትኮሩን ያመለክታል፡፡ ሙሉ መገለጥ አለን ከሚሉ ሀሰተኞች አቋም አኳያ ሁለተኛው አተረጓጎም የተሻለ ነው፡፡ ዩቢ ኤስ 4ኛ የቢ ደረጃ ይሰጠዋል (ይበልጥ ትክክለኛ) መሆኑን ለመግለጽ ቅባቱ እና ዕውቀቱ ለተመረጡና የተለየ ዕውቀትና መንፈሳዊነት ላላቸው የተወሰኑ ሰዎች ብቻ ሳይሆን ለአማኞች ሁሉ ተሰጥቷል!

2፡21 ይህ ጥቅስ የዮሐንስ ጽሁፍ አንባቢዎች ስለመዋጀታቸው እርግጠኝነትና እውነትን ስለማውቃቸው እምነት እንዳላቸው ይገልጻል በዚህ ጥቅስ እርግጠኛ የሆኑት አማኞች ለሚጠሙት የወንጌል ዕውቀት ምላሽ ከመንፈስ ቅዱስ ቅባት የተሰጠ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

2፡22 "ውሸተኛው ማን ነው?" ይህ ሀረግ የተወሰነ አመላካች አለው በመሆኑም ዮሐንስ ከሁለት አንዱን ማለትም

1. በተለይ የሐሰት ትምህርት አስተማሪ የሆነውን (ምናልባትም ሰሪነትዮስ)
2. ዋንኛውን ሐሰተኛ የወንጌል ተቃዋሚ (5፡10 ያስ.) ሊያመለክት ይችላል፡፡

"ሐሰተኛው፣ የክርስቶስ ተቋሚ " ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው የክርስቶስ ተቋሚ መንፈስ በየዘመናቱ ሁሉ አለ፣"የ" የተሰኘው ቦታን አመልካች መሠረታዊ ትርጓሜው(ሁለቱን አገላለጾች) ፣"እየሱስ ክርስቶስ አይደለም ብሎ መካድ ወይም "ክርስቶስን ነኝ" በማለት ለመተካት መሞከር ሁለቱንም ይገላጻል፡፡

▣ "ክርስቶስ አይደለም ብሎ ኢየሱስን ከሚክድ" የጀሮም የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ በገጽ 408 ጥቅሱን በጥሩ ሁኔታ ይገልፀዋል፡፡

"ጸሐፊው ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን ትንቢት ፍጻሜ ወይም አይሁድ የሚጠብቁት መሴህ መገለጡን ለማመልከት ብቻ አልነበረም በዚህ ክፍል ‹ክርስቶስ› አዲስ ኪዳን እየሱስን በይበልጥ በሚጠቅስበት ስሙ ማንነቱን በሙላት ለመግለጽ፣"ቃሉና ሥራው ለሰው ልጆች የተገለጠ መለኮታዊ አዳኝ መሆኑን ጭምር ነው፡፡ (ሐዋ ሥራ 2፡31፤ሮሜ 1፡4)"

በጥቅሱ ሊተላለፍ የተፈለገው መልዕክት

1. ለኖስቲሳዊ ክርክር የተሰጠ ስነመለኮታዊ ምላሽ
2. የቤተክርሲቲያን ከአይሁድ ምኩራብ መለየት በግልጽ የሚያመለክት የፖሌስታይን የአቋም መግለጫ ሲሆን፤ ምናልባትም ከአይሁድ የሀይማኖት ሊቃውንት የጀማኒያ ጉባኤ (70 ዓ.ም) ውግዘት ምላሽ ሊሆን ይችላል፡፡
3. "ኢየሱስ ጌታ ነው " እንደሚለው ፣ይሄኛውም አማኞች ሲጠመቁ የሚሉት ሊሆን ይችላል፡፡

2፡22-23 "ወልድን የሚክድ ሁሉ" ኖስቲሳዊ መምህራን እግዚአብሔርን እንደሚያውቁ ቢናገሩም፣ኢየሱስን ግን ይክዱታል፣ አያምኑበትም፣ስፍራውንም ያሳንሳሉ (4፡1-6፤5፡11-12፣ዮሐንስ 5፡23 ያስ.)

በሁለተኛው ክፍለ ዘመን ከልደት በኃላ ከነበረው የኖስቲሳዊያን ጽሁፎች፣የአዲስ ኪዳን ጥንታዊ የጥቅስ ማብራሪያዎች እና የጥንት ቤተክርሲቲያን አባቶች መሠረት የኖስቲሳዊያን ትምህርቶች፡

1. ኖስቲሳዊያን ክርስትናን ከግሪክ ፍልስፍና (ፐሌቶ) እና ከሩቅ ምስራቅ ሚስጥራዊ ሀይማኖታዊ ልምምዶች ጋር ለማዋሀድ ይጥሩ ነበር
2. መንፈስ ጥሩ ነው ሥጋ ግን ርኩስ ነው ብለው ስለሚያምኑ ክርስቶስ መለኮት ነበር ነገር ግን ሥጋዊ ባህሪ አልነበረውም በማለት የመለኮትን ሥጋ መልበስ ይክዳሉ፡፡
3. ስለ ድህነት ባላቸው ትምህርት ለሁለት ይከፈላሉ
   ሀ. መዳን ከመላክት ሀይል (አዮን) በሚመጣ ልዩ ዕውቀት በመሆኑ የነፍስ መዳን በገሀዱ አለም በሚታየው ሥጋዊ ሥርአት ጋር የተያያዘ አይደለም፡፡

ለ. ሌላኛው ወገን ስጋዊ ስርአት (ቆላ 2:20-23ያስ.) ከፍተኛ ትኩረት ስለሚሰጥ ሥጋዊ ፍላጎትን መግደልና አለማዊ አኗኗርን መካድ ለድህነት ወሳኝ ነው ብለው ያምናሉ፡፡

2:23 ይህ ጥቅስ በመጀመሪያዎቹ የእጅ ጽሁፍ መልክት ተቀባዮች በትላልቅ ፊደላት (አንካል) በተጻፉት ኬ እና ኤል መሠረት የተተረጎመ ነው፡፡ በግሪክኛ ትላልቅ ፊደላት (አንካል) የመጀመሪያ ጽሁፎች ℵ፣A፣B፣C ምንጮች የተደገፈ ነው፡፡ ሁለተኛውና አብን የሚጠቅሰውን ተመሳሳይ አገላለጽ በአጋጣሚ ዘሎታል፡፡

▣ "የሚታመን" በቁጥር 22 [ሁለት ጊዜ ቁ.33 አንድ ጊዜ እና ቁ 26 አንድ ጊዜ] "የሚክድ"ተብሎ ለተጠቀሰው ተቃራኒ ነው፡፡ተጨማሪ የትምህርት አርእስት፡ ‹መመስከር› ዮሐንስ 9:22-23 ይመልከቱ፡፡

▣ "በወልድ" ከአብ ጋር ህብረት ሊኖር የሚችለው በወልድ በማመን ነው፡፡ (5፡10-12፣13 ያስ.) በእየሱስ ማመን የምርጫ ጉዳይ አይደለም ወደ አብ ብቸኛው መንገድ ነው፡፡ (ዮሐንስ 5፡23፤14፡6 ሉቃ 10፡16 ያስ.)

2:24 "እናንተስ" ይህ በዮሐንስ ጽሁፍ አንባቢዎች ከጉባኤው ህብረት የወጡትን ሀሰተኞች መምህራንና ተከታዮቻቸውን በማነጻጸር ትኩረት ሰጥቶ የተናገረበትን ሁኔታ ያመለክታል፡፡ (ቁ. 27 ያስ.)

▣ "ከመጀመሪያ የሰማችሁት በእናንተ ቢኖር" ይህ የአሁን ጊዜ አድራጊ ትእዛዛዊ ዐ ነገር ነው፡፡ ሰዋስዋዊ ትኩረቱ እናንተ (በግሪክኛው በዐ. ነገሩ መጀመሪያ ላይ ይገኛል፡፡) ከሐሰተኞች መምህራን በተቃራኒ ወንጌሉ አብሮ እንደሚኖር ሰውኛ ዘይቤ አላብሶ ሲናገር እንመለከታለን፡፡ ክርቲያኖች ሀሰተኞችን ድል የመንሳታቸው አንደኛው ማረጋገጫው ይሄው የወንጊሉ በውስጣችን መኖር እንደ ሆነ ይገልጻል፡፡ ሌላኛው ማረጋገጫ ስለቅባቱ በተጠቀሰባቸው በቁጥር 20 እና 27 ላይ ይገኛል፡፡ወንጊል እንደመልክትም አብሮ በመገኘት ጭምር ነው፡፡ "ከመጀመሪያውም" ከሚለው ሀረግ ጋር (ቁጥር 13፣14፣24[ሁለት ጊዜ]ያስ.) በአንድነት ተጠቅሷል፡፡ በዚህም የእግዚአብሔር ቃል መልክትም አካልም የመሆን ማለትም ጽሁፍም ህያውም እንደ ሆነ (1፡8፣10፤2፡20፣24) እንመለከታለን! ተጨማሪ የጥናት አርዕስት፡ መኖር 2፡10 ይመልከቱ፡፡

▣ "ቢ…" ይህ የሦስተኛ መደብ በሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ዐ.ነገር ክፍል ማለትም አፈጻጸሙ ወደ ፊት በሚሆኑ ነገሮች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ይህም "በመጽናት" እንዲቀጥሉ የሚያሳስብ፤ በመታዘዝ አለመጽናት በእውነት ያለመኖር ምልክት መሆኑን ያሳያል፡፡ (2፡18-19ያስ.)አኗኗራችን የመጽናታችን ምልክት ሲሆን በእምነታችን እርግጠኞች እንድንሆን ያደርገናል፡፡ (ዮሐንስ 15ያስ.) መጽናት መልክቱን የመቀበል እና ከአብ እና ወልድ ጋር ህብረት እንዳለን ያመለክታል፡፡(ዮሐንስ 14፡23 ያስ.) የኑሮ ዘይቤ በአውንታዊ መልኩ(ፍቅር) እና በአሉታዊ ጎኑ ቃሉን ባለመቀበል ማንነታችንን ይገልጻል፡፡

2:25 "እርሱም የሰጠን ተስፋ ይህ የዘላለም ህይወት ነው" በዚህ ቁጥር የተጠቀሰው ስመ ምትክም አሻሚ ነው፡፡ እግኢዘብሔር አብን ወይም ወልድን ሊያመለክት ይችላል፡፡ ይሄ ምንልባት ሆን ተብሎ (2ጴጥሮስ) የተደረገ ሊሆን ይችላል፡፡ዐ.ነገሩ ዮሐንስ 3፡15-16 እና 6፡40 ከተጠቀሰው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ያማኞች ተስፋ በእግዚአብሔር ባህሪ እና የተስፋ ቃሎች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ (ኢሳ 45፡33፤55፡11 ያስ.) ከስላሴ ጋር ያለን የጠበቀ ህብረት የተገባልን ተስፋ አለ፣እርሱም የዘላለም ሕይወት ነው፡፡ (5፡13 ያስ.) የዘላለም ህይወት የሚታዩ ባህሪያት አሉት፡፡

**NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 2፡26-27**
**[26]ስለሚያስቷችሁ ሰዎች ይህን ጽፌላችኋለሁ፡፡ [27]እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል÷ ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም፣ ነገር ግን የእርሱ ቅባት ስለሁሉም እንደሚያስተምራችሁ÷ እውነተኛ እንደሆነ÷ ውሸትም እንዳልሆነ÷ እናንተንም እንዳስተማራችሁ÷ በእርሱ ኑሩ፡፡**

2:26 "ስለሚያስቷችሁ ሰዎች" ይህ የአሁን ጊዜ አድራጊ ስም ገላጭ ሀረግ ነው፡፡ በየዘመናቱ አሳቾች አሉ (ማቴ 7፡15፤24፡2 ዮሐንስ 7ያስ.)እነዚህ ሀሰተኞች በማህበረ ምእመናን መካከል ኑቁ ተሳታፊዎች እና ትጉ የሀይማኖት ስርአት ፈጻሚዎች ናቸው፡፡

2:27 "ቅባት" ይህ የቅባቱ ሥራ ወይም የወንጌልን እውነት ሳይሆን የቅባቱን ውጤት የሚያመለክት አገላለጽ ነው፡፡ መቀባት በብሉይ ኪዳን ሰዎች ለልዩ አገልግሎት የሚጠሩበትና ለእግዚአብሔር ሥራ የሚደረገውን ዝግጅት ያመለክታል፡፡ ነቢያት፣ካህናትና ነገስታት ይቀባሉ፡፡ የቃሉ መሠረታዊ አመጣጥ መሲህ ከሚለው ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በዙህ ጥቅስ በመንፈስ ቅዱስ ቅባት የሚገኘውን የልብና የአዕምሮ እርፍትና መረጋጋት ያመለክታል፡፡ ተጨማሪ የትምህርት አርዕስት፡ "መቀባት በመጽሀፍ ቅዱስ" ዮሐንስ 11፡2 ይመልከቱ፡፡

ሐሰተኞች ከእግዚአብሔር ልዩ መገለጥ (ቅባት) እንዳላቸው ቢገልፁም ዮሐንስ ግን አማኞች በመንፍስ ቅዱስ ባመኑበት ጊዜ እውነተኛውን ቅባት የተቀበሉ ስለመሆናቸው፣በመንፍስ ቅዱስ እንደተሞሉ እና በእግዚአብሔር ቃል ጸንተው እንደሚኖሩ ያረጋግጣል፡፡

▣ **"የተቀበላችሁት"** ይህ የኃለፊ ጊዜ አድራጊ አመልካች ሲሆን አንድ የተወሰነ ድርጊት በኃላፊ ጊዜ መጠናቀቁን ያመለክታል።"ቅባቱ" ሰምታችኋል ቁ 24 ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው። የወንጌሉን እውነት መቀበል(1) እያንዳንዱ ሰው በእምነት(ዮሐንስ 1:12፤3:16 እና(2) ወንጌል የእውነት አካል መሆኑን(2ዮሐንስ9-10፤1ቆሮ 15:1-4፣ይሁዳ 3 ያስ.) እነዚህ ሁለት ሥራዎች በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ይከናወናሉ።

▣ **"ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም"** ቁጥር 27 ከቁጥር 20 ጋር ተመሳሳይ ነው። (አዲሱ ቃልኪዳን ከኤር 31:34 ያስ.) ዮሐንስ በተደጋጋሚ የሚጠቅሰው የመልክቱ ጭብጥ ነው (ቁጥር 20፣24፣27) ሲይሆን የእኛ የመጨረሻ እና የማይለወጥ አስተማሪ መንፈስ ቅዱስ እንጂ ኖስቲሳዊያን አስተማሪዎች አይደሉም። ይህ ማለት ግን አሁንም ሆነ በጥንት ቤተክርሲቲያን የመምህራን ቢሮም ሆነ የማስተማር ፀጋ የለም ማለት አይደለም (ኤፌ 4:11፤ሌዋ ሥራ 13:1፣2ቆሮ 12:28ያስ.) በአጭሩ መሠረታዊ የደህነት ትምህርት ከመንፈስ ቅዱስና ከመጸሐፍ ቅዱስ ውጭ ከሌላ የተለየ መገለጥ ወይም ስጦታና ሰብአዊ መምህራን እንደማይመነጭ ይገልጻል። እነዚህ የትምህርት መሣሪያዎች ቢሆንም በአብዛኛው ምንጭ አይደሉም።

▣ **"የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉ እንዲያስተምራችሁ: እውነተኛም እንደሆነ ውሸትም እንዳልሆነ"** ይህ መንፈሳዊውን እውነት ያመለክታል። እያንዳንዱ ምዕመን ሂሊናው ይመራል በስነ መግባርም ሆነ የእውነት ዕውቀትን በሚመለከት ለመንፈስ ቅዱስ ምሪት ንቁና ፍቃደኛ ሆነን መገኘት አለብን።

▣ **"እናንተንም እንዳስተማራችሁ በእርሱ ኑሩ"** ይህ የአሁን ጊዜ አድራጊ አመልካች ትዕዛዛዊ ዐ.ነገር ነው።ዮሐንስ የመልክቱ አባቢዎች ለእምነታቸው እርግጠኛነት ማረጋገጫ ከሆኑት አንዱን ማለትም "መኖር" ወይም "መጽናት" የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ በተደጋጋሚ ይጠቀማል። (ዮሐንስ 15 ያስ.) መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ እምነት እግዚአብሔር ቅድሚያ በመውሰድ ሁኔታዎችን የሚያመቻችበት ሲሆን ሰዎች ደግሞ ከመጀመሪያው ለዚህ ምላሽ መስጠትና በእምነት መኖር መቀጠል (መጽናት) አለባቸው! በመታዘዝ የመጽናት ጉዳይ የሁለቱም ማለትም መለኮታዊና የሰዎችን ድርሻ ያካተተ ነው። ተጨማሪ የጥናት አርእስት ፡መኖር 2: 10 ይመልከቱ።

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥቅስ ማብራሪያ የጥናት <u>መመሪያ</u> ነውማለትም አጥኚው ለመሰለው አተረጎጎም ኃላፊነት ይወስዳል። እያንዳንዳችን በተቀበልነው ብርሃን መመላለስ አለብን። በአተረጓጎም ሂደት አጥኝው መፀሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ናቸው። በመሆኑም አጥኚው ይህንን ጉዳይ ለጥቅስ ማብራሪያ ፀሐፊዎች መተው የለበትም።

የሚከተሉት የውይይት ጥያቄዎች በዚህ የይናት ጽሕፍ የተመለከትናቸውን ዋናዋና ርዕሰ ጉዳዮች እንዲያስታውሱ ያግዛታል። ጥያቄዎቹ አንድ የተወሰነ መልስ ያላቸው ሳይሆን የተለያዩ ሀሳቦችን እንዲያነሱ የሚግዙ ናቸው።

1. የሀሰት ትምህርት መምህራንን እምነቶች ይጥቀሱ።
2. በእርግጥ መዋጀታችንን ማወቅ የምንችልባቸውን ማረጋገጫዎች ይጥቀሱ።
3. በልማድ ሀጢትና እንዳንዴ በምንወድቅባቸው ሀጢያቶች መካከል ያለውን ልዩነት ይግለጹ።
4. በቅዱሳን የእምነት ጽናትና በአማኞች መቀደስ መካከል ያለውን ግኑኝነት ይግለጹ።
5. ሦስቱ የሰው ልጅ ጠላቶች እነማናቸው?

# የዮሐንስ መልዕክት 2:28-3:24

## በተሻሻሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀፅ አከፋፈል

| UBS[4] | NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| የእግዚአብሔር ልጆች | የእግዚአብሔር ልጆች | ለእውነተኛው እምነት መታመን | የክርስቶስ ጠላት | እንደ እግዚአብሔር ልጆች መኖር |
| (2:28-3:10) | | (2:18-19) | (2:18-19) | (2:18-19) |
| 2:28-3:3 | 2:28-3:3 | 2:28 | 2:28-29 | |
| | | 2:29 | የእግዚአብሔር ልደች | 2:29-3:2 |
| | | የእግዚአብሔር ልጅነት በተገቢ ጠባይ ይገለጣል | | |
| | | 3:1-10 | 3:1-3 | የመጀመሪያው ግዴታ፤ ኃጢአትን ማስወገድ |
| | ኃጢአት እና የእግዚአብሔር ልጅ | | | 3:3-10 |
| 3:4-10 | 3:4-9 | | 3:4-6 | |
| | | | 3:7-8 | |
| | የፍቅር ትዕዛዝ | | 3:9-10 | |
| እርስበርሳችን እንዋደድ | 3:10-15 | አንዱ ሌላውን ይውደድ | እርስበርሳችን እንዋደድ | ሁለተኛው ግዴታ፤ ትዕዛዙን መጠበቅ እና ደስ የሚያሰኘውን ማድረግ |
| 3:11-18 | | 3:11-18 | 3:11-12 | 3:11-24 |
| | በሥራና በእውነት መዋደድ | | 3:13-18 | |
| በእግዚአብሔር ፊት ያለን ድፍረት | 3:16-23 | የክርስቲያን ዋስትና | በእግዚአብሔር ፊት ያለን ድፍረት | |
| የእውነት መንፈስ እና የሐሰት መንፈስ | | 3:19-24 | 3:19-24 | |
| | 3:24-4:6 | | | |

**ሦስተኛው የምንባብ ኡደት (አንቀፅ 53ን ይመልከቱ)**
*የመጀመሪያውን ፀሐፊ ዋና ሐሳብ በአንቀፅ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ሊሆን የሚችል ማብራሪያ በመሆኑ ለመትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጐም ኃላፊነት አለብህ። እያንዳንዳችን ስንጓዝ የሚገባን ባለን መረደት መጠን ነው። አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጐም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣችሁ ናችሁ። ይህንንም ጉዳይ በሚያብራራው ሰው ላይ ብቻ ልትተው የሚገባ አይደለም።

ምዕራፉን በአንድ ቅፅበት አንብበው፤ ዋና ዋና ሐሳባችንም ለያቸው። የራስህን የአንቀፅ አከፋፈል ከአምስቱ የተሻሻሉ ትርጉሞች ጋር አነፃፅር። ምንም እንኳን በአንቀፅ መከፋፈል በእግዚአብሔር መንፈስ መነዳት የሚደረግ ባይሆንም የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጐም ምሦሦ የመጀመሪያውን ፀሐፊ ዋና ሐሳብ ለመከተል ግን ቁልፍ ጉዳይ ነው፤ እያንዳንዱም አንቀፅ የሚናገረው ስለ አንድ ዋና ሐሳብ ብቻ ነው።

1. *የመጀመሪያው አንቀፅ*

2. *ሁለተኛው አንቀፅ*

3. *ሦስተኛው አንቀፅ*

4. ወዘተ

## አውዳዊ ግንዛቤዎች

ሀ. የምዕራፍ 2 ሐሳብ የተሰነዘረው በግኖስቲክ የሐሰት መምህራን ላይ ነው (በተለይም የኢየሱስን ስብእና በሚክዱስ በይሴቲክ ግኖስቲክስ ላይ)

ለ. ምዕራፍ 3 ድነትን (ጽድቅን) ከሥነ-ምግባር ትምህርት እና ግብረ-ገብነት (መቀደስ) የለያዩትን የሐሰት መምህራንን በተዘዋዋሪ በመጥቀስ ይጀምራል፡፡ ቢሆንም ምዕራፍ 3 የበለጠ በቀጥታ የሚመለከተው አማኞችን ነው፡፡

## የቃል እና የሐረግ ጥናት

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 2 :28-3:3
**28አሁንም ልጆች ሆይ÷ በሚገለጥበት ጊዜ እምነት እንዲሆንልን በመምጣቱም በእርሱ ፊት እንዳናፍር በእርሱ ኑሩ፡፡ 29ጻድቅ እንደሆነ ካወቃችሁ ጽድቅን የሚያደርግ ሁሉ በእርሱ እንደተወሰደ እናውቃለን፡፡**
**1የእግዚአብሔር ልደች ተብለን ስንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንዲሰጠን እዩ÷ እንግዲሁም ነን፡፡ ስለዚህ ምክንያት ዓለም እርሱን ስላላወቀው እኛን አያውቀንም፡፡ 2ወላጆች ሆይ÷ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን÷ ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠም፡፡ ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና÷ እርሱን እንድንመለስ እናውቃለን፡፡ 3በእርሱም ይህን ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ንጹሕ እንደሆነ ራሱን ያነጻል፡፡**

2:28 በቁጥር 28፣ 29 ወይም 3:1 ላይ አዲስ አንቀፅ ሊጀመር ይገባል ወይ በሚለው ላይ መፍሐጽ ቅዱሱን በሚያብራሩ ሊቃውንት መካከል ብዙ ክርክር አለ፡፡ በቁጥር 27 እና 28 መካከል ካለው መደጋገም የነሣ የአንቀፅ አከፋፈሉ ምናልባት ከዚህ ሊጀምር ይገባል፡፡

▣ "**ልጆች**" በ2:1 ላይ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ፡፡

▣ "**በእርሱ ኑሩ**" ይህ የአሁን ጊዜ ድርጊት ገላጭ ትዕዛዛዊ ቃል ነው፡፡ ይህ ክርስቲያን ፅናት እንዲኖረው ለማድረግ የተጠቀሰ (ቁ. 15፤ 24) ሦስተኛ መደብ የአሁን ጊዜን አመልካች ትእዛዝ ነው፡፡ በዮሐንስ 8:21 እና 1ዮሐ 2:10 ላይ ያለውን ስለመጽናት አስፈላጊነት የሚናገረውን ልዩ የጥናት ርዕስ ይመልከቱ፡፡

ከተውላጠ ስሙ ቀደም ብለው የሚመጡት ብዙውን ጊዜ ለመለየት የሚያስቸግሩ ናቸው፤ ነገር ግን በዚህ አንቀፅ ውስጥ ግልፅ ናቸው፡፡

1. "በእርሱ" ቁ 28ሀ - ኢየሱስ
2. "በእርሱ" ቁ. 28ለ - ኢየሱስ
3. "የእርሱ" ቁ. 28ለ - ኢየሱስ
4. "ጻድቅ እንደሆነ" ቁ. 29 - አብ
5. "ከእርሱ እንደተወለደ" ቁ. 29 - አብ (ማብራሪያውን ይመልከቱ)
6. "እርሱን ስላላወቀው" 3:1 - አብ (ዮሐንስ 15:21፤ 16:2-3)
7. "ቢገለጥ" 3:2- ኢየሱስ
8. "እርሱን እንድንመለስ" 3:2- ኢየሱስ
9. "እናየዋለንና" 3:2 - ኢየሱስ
10. "እርሱ እንዳለ" 3:2- ኢየሱስ
11. "በእርሱም" 3:3 - ኢየሱስ
12. "እርሱ ንፁሕ እንደሆነ" 3:3-ኢየሱስ

ዓውድ፣ ዓውድ፣ ዓውድ፣ በጣም ወሳኝ ነገር ነው፡፡

▣ "**ቢገለጥ**" ይህ ልክ እንደ ቁጥር 29 ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ነው፤ እንዲሁም በ3:2 ላይ የተገለፀው "ቢመለስ" ከሚለው ጋር ተመሣሣይ ነው፡፡ ይህ ማለት እርግጠኛ ያልሆነ ድርጊትን ለማስተላለፍ ሳይሆን እርግጠኛ ያልሆነ ጊዜን ለማሳየት ነው (ይህም በ3:3 ላይ አዲስ ኪዳን "ተስፋ" የሚለውን ቃል ከተጠቀመበት መንገድ ጋር ተመሳሳይነት አለው)፡፡

▣ **"እምነት እንዲህንልን"** እምነት (ፓርሄስያ) የሚለው የግሪኩ ቃል "በነፃነት መናገር" ከሚለው ሥርወቃል የተወሰደ ነው። እርግጠኝነት አሁን የምንኖርበት የሕይወት ዘይቤ ሲሆን የተመሠረተውም በአማኙ እውቀት እና በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ባለው እምነት ላይ የተመሠረተ ነው።

በዮሐንስ 7:4 ላይ ድፍረት የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።

NASB **"በእርሱ ፊት እንዳናፍር"**
NKB **"በፊቱ እንዳናፍር"**
NRSB **"በእርሱ ፊት በኃፍረት እንዳንወድቅ"**
TEV **"ከፊቱ በኃፍረት እንዳንደበቅ"**
NJB **"ከእርሱ ፊት እንዳናፍር"**

ይህ የግሪኩ ተደርጎ ግሥ ስሜት ገላጭ ሲሆን ሊኖረው የሚችለው አንደም፦

1. አማኙ ራሱ ያፍራል ማለት ነው (NASB፣ TEV፣ NJB)
2. አማኙ እንዲያፍር ሲደረግ ማለት ነው (NRSV)

አማኞች የክርስቶስን ዳግም መመለስ ሊናፍቁት እና ሊጠብቁት ይገባቸዋል፤ ነገር ግን ለራሳቸው ግላዊ ፍላጐት እና ለዚህ ዓለም ደስታ የሚኖሩት በመገለጡ በእርግጥ የሚደነቁበት እና የሚያፍሩበት ነው! የአማኞች ፍርድ ጊኤውን የሚጠብቅ ጉዳይ ነው (2 ቆሮ 5:10)።

▣ **"በመምጣቱም"** ይህ ዳግም ምፅአትን የሚያመለክት ነው። ፓውሮሲያ የሚለው ቃል በሁሉም የዮሐንስ ፅሑፎች ውስጥ በዚህ ሥፍራ ብቻ የተጠቀሰ ሲሆን በቅርብ የሚፈጸምን የአንድን ንጉሥ ጉብኝት የማመልከት ድባብ አለው።
ይህ ቃል በቃል "እስከ ፓውሮሲያ" የሚለው ትርጉም "ሕልውና ወይም መገኘት" የሚል ሲሆን የንጉሥን ጉብኝት የሚያመለክት ነው። ለዳግም ምፅአት የተጠቀሱት ሌሎች የአዲስ ኪዳን ቃላት፤

1. EpiphaNeia (ኤፒፓንያ) ፦ "ፊት ለፊት መገለጥ"
2. Apokalupsis (አፖካሉፕሲስ)፦ "መገለጥ"
3. "የጌታ ቀን" እና የዚህ ሐረግ ልዩ ልዩ ድባቦች

---

**ልዩ ርዕስ፡ ስለ ክርስቶስ መመለስ የተጠቀሱ የአዲስ ኪዳን ቃላት የሰው ልጆች ኢየሱስን የሚገናኙበት** (እንደ አዳኝና ዳኛ/ፈራጅ) በሚመጣበት የተለየ ቀን ያለው ሥነ-መለኮታዊ ትኩረት በጳውሎስ መልዕክቶች ውስጥ በርካታ ስያሜዎች የተሰጠው ነው፡፡

1. ‹‹የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቀን›› (1ቆሮ 1÷8)
2. ‹‹የጌታ ቀን (1ቆሮ 5÷5፤ 1ተሰ 5÷2፤ 2ተሰ 2÷2)
3. ‹‹የጌታ ኢየሱስ ቀን›› (1ቆሮ 5÷5፤ 2ቆሮ 1÷4)
4. ‹‹የኢየሱስ ክርስቶስ ቀን›› (ፊል 1÷6)
5. ‹‹የክርስቶስ ቀን›› (ፊል 1÷10፤ 2÷16)
6. በእርሱ ቀን (የሰው ልጅ) (ሉቃ 17÷24)፡፡
7. ‹‹የሰው ልጅ በሚገለጥበት ቀን›› (1ቆሮ 1÷7)
8. ‹‹የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ›› (1ቆሮ 1÷7)
9. ‹‹ጌታ ኢየሱስ ከሰማይ ሲገለጥ›› (1ተሰ 2÷19)
10. ‹‹በጌታ በኢየሱስ በመምጣቱ እና በመገለጡ ፊት›› (1 ተሰ 2÷19)

የአዲስ ኪዳን ፀሐፊዎች የኢየሱስን መመለስ የሚያመለክቱባቸው ቢያንስ አራት መንገዶች አሉ፡፡

1. Epiphaאeia:- ኃይለኛ እና የሚያዋበረብር ብርሃንን የሚያመለክት ሲሆን ከሥነ-መለኮት አንፃር (ከሥርወ-ቃሉ አንፃር ባይሆንም) ‹‹ክብር›› ከሚለው ጋር የሚገናኝ ነው፡፡ በ2ጢሞ 1÷10፤ ቲቶ 2÷11 እና 3÷4 ላይ የኢየሱስን ወደዚህ ምድር መምጣት (ተሰግዎ) እና ዳግም መምጣቱን የሚያመለክት ነው፡፡ በ2 ተሰ 4÷8 ላይ የተጠቀሱትን ሦስቱን ዋና ዋና ቃላት የሚያካትት ነው፤ 1ጢሞ 6÷14፤ 2ጢሞ 4÷1፤ 8፤ ቲቶ 2÷13፡፡
2. Paraousia በተዘዋዋሪ የሚያመለክተው ሕልውናን ሲሆን ቃሉ ከመጀመሪያው የሚያመለክተው ንጉሳዊ ጉብኝትን ነው ይህ በስፋት የሚጠቀስ ቃል ነው (ማቴ 24÷3፤ 27፤ 37፤ 39፤ 1ቆሮ 15÷23፤ 1ተሰ 2÷19፤ 3÷13፤ 4÷15፤ 5÷23፤ 2ተሰ 2÷1፤8፤ ያዕ 5÷7፣ 8፤ 2ጴጥ 1÷6፤ 3÷4፡ 12፤ 1ዮሐ 2÷28)፡፡
3. Apokalupsis (or apocalypsis): ለማሣየት ዓላማ ሲባል አንድን ነገር መግለጥ ማለት ነው፡፡ ይህ የአዲስ ኪዳን የመጨረሻው መጽሐፍ ስም ነው፡፡ (ሉቃ 17÷30፤ 1ቆሮ 1÷7፤ 2ተሰ 1÷7፤ 1ጴ 1÷7፤ 4÷13)
4. Phaאeroo: ወደ ብርሃን ማምጣት ወይም በሚታይ ሁኔታ አንድን ነገር ማሣየት ወይም መግለጥ ማለት ነው፡፡ ቃሉ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተለያዩ የእግዚአብሔር መገለጦችን ለማሣየት ተጠቅሷል፡፡ ቃል ልክ እንደ የክርስቶስን መጀመሪያ መምጣት (1ጴጥ 1÷20፤ 1ዮሐ 1÷2፤ 3÷5፤ 8፤ 4÷9) እና ዳግም

መምጣት ሊያመለክት ይችላል (ማቴ 24÷30፤ ቆላ 3÷4፤ 1ጴጥ 5÷4፤ 1ዮሐ 2÷28፤ 3÷2)፡፡

5. ‹‹መምጣት›› ለሚለው የተለመደው መጠሪያ erchomai የሚለው ሲሆን ይህም አንዳንድ ጊዜ የክርስቶስን መመለስ ለማመልከት ይጠቀሟል (ማቴ 16 ÷ 27-28፤ 23 ÷ 39፤ 24 ÷ 30፤ 25 ÷ 31፤ ሐዋ 1÷10-11፤ 1ቆሮ 11÷26፤ ራዕይ 1÷7፡8) ፡፡
6. ከዚህም ባሻገር ‹‹የጌታ ቀን›› ከሚለው ሐረግ ጋር ይጠቀሳል (1ተሰ 5÷2)ይህም የእግዚአብሔርን የበረከት (ትንሣኤ) እና የትንሣኤ ቀንን የሚያመለክት የብሉይ ኪዳን መጠሪያ ነው፡፡

አዲስ ኪዳን በመላው የተፃፈው በብሉይ ኪዳን የአለም እይታ ሲሆን በአፅኦት የሚገልጠውም፡፡

ሀ. የአሁኑን ክፉና አመፁን የተሞላ ዘመን

ለ. ሊመጣ ያለውን አዲሱን የጽድቅ ዘመን

ሐ. በንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የሚገለጠውን የመሲሁን (የተቀባውን) ዘመን ለማሣየት

ቀጣይነት ስላለው መገለጥ ሥነ-መለኰታዊ ግምት ያልፈለገበት ምክንያት የእስራኤልና መሲሑን መጠበቅ የአዲስ ኪዳን ፀሐፊወች በመጠኑም ቢሆን ያሻሻሉት ስለሆነ ነው፡፡ ወታደራዊ እንዲሁም ብሔራዊ (የእስራኤል) አንደምታ ካለው የመሲሁ አመጣጥ ይልቅ ሁለት አይነት አመጣጦች አሉ፡፡ የመጀመሪያው አመጣይ መለኰት ሥጋ ለብሶ ሲፀነስ እና የናዝሬቱ ኢየሱስ መወለድ ነው፡፡ እርሱ የመጣውእንደ ዳኛወይም ወታደር/ጦረኛ ሆኖ ሳይሆን በኢሳ 53 ላይ እንደተጠቀሰው ‹‹መከራን የሚቀበል አገልጋይ›› ሆኖ ነበር፤ ከዚህም ባሻገር በዘካ 9÷9 ላይ እንደተጠቀሰው በውርንጫዋ አህያ (የጦር ፈረስ ወይም ንጉስ የሚቀመጥባት በቅሎ ሳይሆን) ተቀምጦ ነበር፡፡ የመጀመሪያው መምጣት በምድር ላይ የእግዚብሔርን መንግሥት መመሥረት የሚያበስረውን አዲሱን የመሲሑን ዘመን ነው፡፡ በአንድ በኩል የእግዚአብሔር መንግሥት በዚህ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ገና ሩቅ ነው፡፡ ይህ ነው እንግዲህ በሁለቱ የመሲሒን መምቶች መካከል ውጥረት እንዲፈጠር የሚያደርገው፤ ይህም ሁኔታ ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ ሁለቱን

የአይሁድ ዘመናት ቢያንስ ደብዛዛ አሊያም ምንም የማይታይ ያደረ ክስተት ነው፡፡ እንደ እውነታው ከሆነ ይህ ጣምራ አመጣጥ የሚያተኩረው ያህዌህ የሰው ልጆችን ሁሉ ለማዳን ካለው ዓላማ አንፃር የመነጨ መሆኑ የሚታወቅ ነው (ዘፍ 3÷15፤ 12÷3፤ ዘፀ 19÷5 እና የነቢያት ስብከቶች /መልዕክቶች)፡፡ በተለይም ኢሳያስ እና ዮናስ፡፡

ቤተክርስቲን የብሉይ ኪዳን ትንቢቶችን መፈፀም እየጠበቀች አይደለችም፡፡ ምክንያቱም አብዛኞቹ ትንቢቶች የመጀመሪያውን መምጣት የሚያመለክቱ ናቸውና (*How to Read the Bible for all Its Worth: ገጽ 165-166*)፡፡ አማኞች የሚጠብቁት እና ተስፋም የሚያደርጉት የነገሥታት ንጉሥ እና የጌታዎች ጌታ የሆነውን በክብር መምጣት፣ በሰማይም እንደሆነው በምድር የሚፈፀመውን አዲስን የጽድቅ ዘመን ታሪካዊ መሟላት ይጠብቃሉ (ማቴ 6÷10)፡፡ የብሉይ ኪዳን አቀራረቦች ስህተት ሳይሆኑ ነገር ግን ያልተማሉ ነበሩ፡፡ የብሉይ ኪዳን ነብያት በያህዌህ ኃይልና ሥልጣን አስቀድመው እንደ ተናገሩት ተመልሶ ይመጣል፡፡

ሁለተኛው መመለስ መፅሐፍ ቅዱሳዊ ቃል አይደለም ነገር ግን ሐሳቡ የአዲስ ኪዳን በመላው የአለም እይታ

2:29 "እንደ … ካ" ይህ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ሲሆን ድርጊት ለመፈፀም ዕድል መኖሩን ያመለክታል፡፡ በዚህ ሥፍራ አማኞች በጋራ የሚኖራቸውን እውቀት የሚያመለክት በተቃራኒው ደግሞ የስህተት አስተማሪዎች ያጡትን እውቀት ያመለክታል፡፡

▣ **"እወቁ"** በሰዋሰው ቅርፅ የህ ቀጣይነት የለውን እውቀት የሚያመለክት የአሁን ጊዜ አመልካች ግሥ ነው ወይም የአማኝን አስፈላጊ እውቀት የሚያመለክት የአሁን ጊዜ ድርጊት ገላጭ ትእዛዝ ነው፡፡ መንፈስ ያላቸውን ሁሉ አማኞች በመጥቀስ ዮሐንስ የጠቀሰው "እወቁ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው አመልካች ቃል መሆኑን ነው፡፡

▣ **"እርሱ"** ቁጠር 28፣ 2:1፤ እና 3:7 የሚያመለክቱት ኢየሱስን ነው፡፡ ይሁን እንጂ "ከእርሱ እንደተወለደ" የሚለው የመጨረሻው ተውላጠ ስም እግዚብሔር አብን የሚያመለክት ይመስላል ምክንያቱም "ከእርሱ እንደተወለደ" የሚለው ሐረግ ብዙ ጊዜያት ተደጋግሞ ተጠቅሷል (3:9፤ 4:7፤ 5:1፤ 4:18፤ ዮሐ 1:13)፡፡

▣ **"ጻድቅ - - - ጽድቅ"** ይህ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ የሚጠበቅ ባህርይ ነው፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ ጽድቅ**

"ጽድቅ" የሚለው ሐሳብ በጣም ወሳኝ በመሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ የሆነ ሐሳቡን በሚመለከት ሰፋ ያለ ጥናት ሊያደርግ ይገባል፡፡

በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ባህርይ የተገለፀው እንደ "ትክክል" ወይም "ፃድቅ" ተደርጐ ነበር (BDB841)፡፡ የሜስፓተሚያው ቃል ራሱ የመጣው ከወንዝ ዳር መቃ ሲሆን ይህም የግድግዳዎችን እና የአጭሮችን የጐን ውሃ ልክ ለመለካት የሚያገለግል የግንባታ መሣሪያ ነበር፡፡ እግዚአብሔርን የራሱን ባህርይ ለማሣየት በተምሣሌትነት

እግዚአብሔርም ሕብረቱን ሊጠግን እና ሊያድስ ተስፋን ሰጠ (ዘፍ 3:15)፡፡ ይህንንም ያደረገው በራሱ ፈቃድ እና በራሱ አንድያ ልጅ አማካኝነት ነበር ምክንያቱም የሰው ልጆች የተፈጠረውን ክፍተት በራሳቸው ሊያድሱት አልቻሉምና (ሮሜ 1:8-3:30)፡፡

ከውድቀትም በኋላ ተገድሶን በሚመለከት የእግዚአብሔር የመጀመሪያው እርምጃ የተመሠረተው በእርሱ ጥሪ እና የሰው ልጆች በሚሰጡት የመመለስ፣ የመተመን እና የመታዘዝ ምላሽ ነበር፡፡ በውድቀት ምክንያት የሰው ልጆች ተገቢ የሆነውን እርምጃ ሊወስዱ አልቻሉም (ሮሜ 3:21-31፣ ገላ 3)፡፡ ለዚህም እግዚአብሔር ራሱ ነበር ቃል ኪዳን የሚሰብሩትን ,የሚያፈርሱትን የሰውን ልጆች ከራሱ ጋር ለማስታረቅ እርምጃን የወሰደው፣ ይህንንም ያደረገው፣

1. በክርስቶስ አማካኝነት የሰው ልጆች ያላቸውን ጽድቅ በማወጅ (ማስረጃነት ያለው ጽድቅ)
2. በክርስቶስ አማካኝነት ለሰው ልጅሁሉ ጽድቅን በነፃ በመስጠት (ክርስቶስን መምሰል፣ የእግዚአብሔር መልክ መታደስ)

ይሁን እንጂ እግዚአብሔር የሚፈልገው ቃልኪዳናዊ ምላሽ ነው፡፡ እግዚአብሔር ይደነግጋል (በነፃ ይሰጣል) ደግሞም ቸርነትን ያደርጋል፣ ነገር ግን የሰው ልጆች፣

1. በንስሐ
2. በእምነት
3. በህይወት በሚታይ መታዘዝ
4. በመፅናት ምላሽ ሊሰጡ እና በምላሹም ሊቀጥሉበት ይገባል፡፡

በመሆኑም ጽድቅ ቃል-ኪዳናዊ እና ምላሽ ያለው በእግዚአብሔር እና ከፍጥረት ሁሉ የበላይ በሆነው የሰው ልጅ መካከል የሚፈፀም ድርጊት ነው፡፡

በእግዚአብሔር ባህርይ፣ በክርስቶስ ሥራ እና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሰጪነት ላይ በመመሥረት በግሉ እና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ተገቢውን ምላሽ መስጠት የሰው ልጅ ያስፈልገዋል፡፡ ሐሳቡ ‹‹በእምነት መጽደቅ›› ይባላል፡፡ ሐሳቡ በወንጌላት ውስጥ ተገልጿል፣ ነገር ግን በነዚህ ቃላት ውስጥ አይደለም፡፡ ሐሳቡ ከሁሉም አስቀድሞ የተገለፀው በጳውሎስ ሲሆን እርሱም ‹‹ጽድቅ›› የሚለውን የግሪክ ቃል በተያዩ ከ100 ጊዜያት በላይ ተጠቅሞበታል፡፡

ጳውሎስ፣ የተማሪ ረቢ እንደመሆኑ መጠን dikaiosuɜe የሚለውን የእብራይስጡን ቃል SDO ተብሎ በስብተዋጅነት የተጠቀሰውን ቃል (ከግሪክ ፅሑፍ ሳይሆን) ተጠቅሞበታል፡፡ በግሪክ ፅሑፎች ቃል የተያያዘው መለኮት ወይም ሕብረተሰብ ከሚጠብቀው መሥፈርት አንፃር የተስማማን አንድን የሚያመለክት ነው፡፡ በእብራይስጥ ትርጉሙ ግን ሁልጊዜ ቃል የተዋቀረው ከቃል ኪዳን ቃላት አንፃር ነው፡ ያህዌህ ትክክለኛ እና ግበረ ገባዊ አመላክ ነው፡፡ እግዚአብሔርም የእርሱ ሕዝብ ባህርይውን እንዲያንፀባርቅ ይሻል፡፡ የተቤዥ የው ልጅም አዲስ ፍጥረት ይሆናል፡፡ ይህ አንዲስነት እግዚአብሔርን መደምሰስ አዲስ የሕይወት ዘይቤ ይለወጣል (የሮም ካቶሊክ የጽድቅ ትኩረት)፡፡ እስራኤል ከመጀመሪያውም በእግዚአብሔር ትእዛዝ የምትተዳደር ስለነበረች በዓለማዊው (የህብረተሰብ ልማቶች) እና በተቀደሰው (በእግዚአብሔር ፈቃድ) መካከል ምንም ግልፅ ልዩነት አልነበረም፡፡ ይህም ልዩነት ወደ እንግሊዘኛው ‹‹ትክክል›› (ከማህበረሰቡ ጋር የሚዛመድ) እና (ከኃይማኖት ጋር የሚዛመድ) ተብሎ በዕብራይስጥ እና በግሪክ ቃላት ውስጥ ተገልጿል፡፡

የኢየሱስ ወንጌል (የምሥራቹ ቃል) የወደቀው የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ሕብረት ተሃድሶን ማግኘቱን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህም የተፈፀመው በአብ ፍቅር፣ ምህረት እና ፀጋ፣ በወልድ ሕይወት፣ ሞት እና ትንሣኤ፣ በመንፈስ ቅዱስ የማያቋርጥ መቃተት እና ወደ ወንጌል ማምጣት ነው፡፡ ጽድቅ የእግዝአብሔር ነፃ ሥጦታ ነው ነገር ግን እግዚአብሔርን በመምሰል ውስጥ መገለጥ አለበት (ወንጌል ነፃ መሆኑን ትኩረት በሚያደርጉት የተሃድሶ እንቅስቃሴ አራማጆች እና በፍቅር እና በመተመን የተለወጠ ህይወት ላይ ትኩረት የሚያደርገው የሮም ካቶሊክ ትኩረት ላይ ኦገስቲን ያለውን አቋም ያንፀባርቃል)፡፡ ለተገድሶ አራማጆች ‹‹የእግዚአብሔር ጽድቅ›› የሚለው ቃል ያለው አንደምታ በድርጊት የሚለጥ ሲሆን (ኃጢአተኛውን የው ልጅ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዲያኝ የማድረግ አካሄድ (የሥፍራ ለውጥ ቅድስና) ሲሆን

ለካቶሊኮች ደግሞ ከውስጥ ስት ጋር አብሮ የሚሄድ ነው (Subjective geжitive) ሲሆን ይህም እግዚአብሔርን በሒደት የበለጠ እየመሰሉ መሄድ የሚል ሐሳብ አለው (ልምዳዊ ቀጣይነት ያለው ቅድስና)፡፡ እንደ እውነታው ከሆነ ሁለቱንም የሚያካትት ነው !!

በእኔ አመለካከት ዘፍጥረት 4 እስበ ራዕይ 20 ድረስ ያለው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሚዘግበው በኤደን ገነት የነበረውን ሕብረት መታደስ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር እና የሰው ልጅን በምድራዊ ሁነት ሲጀምር (ዘፍ 1-2) እንዲሁ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ በተመሣሣይሁነት ይጨርሰዋል (ራዕይ 21-22)፡፡ የእግዚአብሔር መልክ እና ዓላማ ተሐድሶን ያገኛል!

ከላይ የተጠቀሱትን ውይይቶች በመረጃ መልክ ለማስቀመጥ ይቻል ዘንድ የግሪክ ቃላትን ስብስብ የሚከያመለክትን የሚከተሉትን የተመረጡ የአዲስ ኪዳን ምንባቦችን አስተውል፡፡

1. እግዚአብሔር ጻድቅ ነው (እግዚአብሔር ፈራጅ ነው ከሚለው ጋር ብዙ ጊዜ የሚያያዝ ነው)

   ሀ. ሮሜ 3 : 26

   ለ. ተሰ 1:5-6

ሐ. 2ጢሞ 4:8
መ. ራዕይ 16:5
2. ኢየሱስ ጽድቅ ነው
ሀ. ሐዋ 3:14፣ 7:52፤ 22:14 (የመሲሑ ማዕረግ)
ለ. ማቴ 27:19
ሐ. 1ዮሐ 2:1፥ 29፣ 3:7
3. እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ያለው ፈቃድ ጽድቅ ነው
ሀ. ዘሌዋዊያን 19:2
ለ. ማቴዎስ 5:48 (5:17-20)
4. እግዚአብሔር ጽድቅን የሚሰጥበት እና የሚፈጥርበት መንገድ
ሀ. ሮሜ 3:21-31
ለ. ሮሜ 4
ሐ. ሮሜ 5:6-11
መ. ገላ 3:6-14
ሠ. በእግዚአብሔር የተሰጠ
1. ሮሜ 3:24፤ 6:23
2. 1ቆሮ 1:30
3. ኤፌ 2:8-9
ረ. በእምነት የሚቀበሉት ነው
1. ሮሜ 1:17፤ 3:22፣ 26፤ 4:3፣ 5፣ 13፤ 9:30፤ 10:4፣ 6፣ 10
2. 2ቆሮ 5:21
ሰ. ወልድ በሠራው ሥራ
1. ሮሜ 5:21
2. 2ቆሮ 5:21
3. ፊልጵ 2:6-11
5. የእግዚብሔር ፈቃድ እርሱን የሚከተሉት ፃድቃን እንዲሆኑ ነው
ሀ.ማቴ 5:3-48፤ 7:24-27
ለ. ሮሜ 2:13፤ 5:1-5፤ 6:1-23
ሐ. 1ጢሞ 6:11
መ. 2ጢሞ 2:22፤ 3:16
ሠ. 1ዮሐ 3:7
ረ. 1ጴጥ 2:24
6. እግዚአብሔር ዓለምን በጽድቅ ይፈርዳል
ሀ. ሐዋ 17:31
ለ. 2ጢሞ 4:8

ጽድቅ የእግዚአብሔር ባህርይ ሲሆን ለኃጢአተኛው የሰው ዘር በክርስቶስ አማካኝነት እንዲያው በነፃ የተሰጠ ነው። ጽድቅ፣
1. የእግዚአብሔር ድንጋጌ ነው
2. የእግዚአብሔር ሥጦታ ነው

▣ "እንደተወለደ" ይህ ያልተሟላ ተደርጎ ግሥ አመልካች ሲሆን ትርጉሙ በአንድ ውጫዊ አካል አማካኝነት የሰከነ ሁኔታን መያዝ ማለት ሲሆን ይህም በእግዚአብሔር አብ የመጣ ነው (ዮሐ 3:3)። ክርስትናን ለመግለፅ (ቤተሰብ ነው) በዝምድና መተሣሠርን የሚያሣይ ሌላ ተምሳሌት መጠቀሱን (3:9) ማስተዋል አስፈላጊ ነው። ይህንንም በ3:100 ላይ ይመልከቱ።

**3:1 "እንዴት ያለውን ፍቅር እንደሰጠን እዩ"** በዚህ ሥፍራ እና በጠቅላላው 1ኛ ዮሐንስ ውስጥ ፍቅርን ለመግለፅ የተጠቀሱት ቃላት agapao (ግሥ) ወይም agape (ስም) ናቸው (2:5፣ 15፤ 3:1፣ 16፣ 17፤ 4:7፣ 8፣ 9፣ 10፣ 12፣ 16፣ 17፣ 18፤ 5:3)። ይህ ቃል ብዙውን ጊዜ ባይሆንም በጥንቱ ግሪክ ይጠቀስ ነበር። በዚህም የቀደመችው ቤተክርስቲያን እንደገና ቃሉን ከወንጌል አንፃር ፍቺ የሰጠችበት ይመስላል። ቃሉ የሚወክለው ጥልቀት ያለውን የፍቅር ሕይወትን ነው። ቃሉንም "እንደ እግዚአብሔር ራሱን የመስጠት ፍቅር" ማለት ተገቢነት ያለው አይመስልም፤ ምክንያቱም ቃሉ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ Phileo (ፊሎ) ከሚለው ጋር በተመሣሣይነት ተጠቅሷልና። (5:20፤ 11:3፣ 36፤ 12:25፤ 15:19፤ 16:27፤ 20:2፤ 21:15፣ 16፣ 17)።
ይሁን እንጂ ቃሉ አማኞች እርስ በርሳቸው ያላቸውን ፍቅር ለመግለፅ ሁልጊዜ መጠቀሱ (1ዮሐንስ) በጣም ደስ የሚል ነው። እምነታችን እና ከኢየሱስ ጋር ያለን ሕብረት ከእግዚአብሔር እና ከሰዎች ጋር ያለንን ሕብረት ይለወጣል!

▣ **"አብ … እንደሰጠን"** ይህ ድርጊት ገላጭ አመልካች ነው፡፡ እግዚአብሔር በክርስቶስ አማካኝነት የሰጠውን የድነት ሥጦታ ለመግለፅ ይህ ጊዜ ገላጭ መጠቀሱ የአማኝን ደህንነት በሚመለከት አንዱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ሊሆን ይችላል (ዮሐ 6:35-40፤ 10:1፤ ኤፌ 2:5፣ 8፤ 3:14፤ 5:1)፡፡ በዮሐ 6:37 ላይ ስለ ክርስቲያን ደህንነት /እርግጠኝነት/ የተሰጠውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስ ይመልከቱ፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ አዲስ ኪዳን ስለ አንድ ሰው ድነት የሚያቀርበው ማስረጃ ይህ የተመሠረተው በኢየሱስ ባለው**

አዲሱ ቃልኪዳን ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ (ኤር 31 ÷31-34፤ ሕዝ 36÷22- 38)፡፡

1. የእግዚአብሔር ባህርይ (ዮሐ 3÷16)፣ የወልድ ሥራ (2ቆሮ 5÷21) እና የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት (ሮሜ 8÷14-16) የሰወ ብርቱ ጥረት፣ ለመታዘዝ የሚከፈል ደመወዝ ወይም ድንጋጌ አይደለም፡፡
2. ሥጦታ ነው (ሮሜ 3÷24፤ 6÷23፤ ኤፌ 2÷5-9)
3. አዲስ ሕይወት፣ አዲስ እይታ ነው (ያዕቆብ እና ዮሐንስ)
4. እውቀት ነው (ወንጌል)፣ ሕብረት ነው (በኢየሱስ ማመን)፣ አዲስ የኑሮ ዘይቤ ነው (መንፈስን ማዕከል ያደረገ ክርስቶስን መምሰል)፡፡ በዚህ ውስጥ አንዱ ብቻ ሣይሆን ሦስቱም መጣመር አለባቸው፡፡
5. ለ1ዮሐንስ 2÷3፣ 3÷3 ሐ ላይ በተሰጡት አውዳዊ ግንዛቤዎች ላይ የእውነተኛ ድነት መፈተኛዎችን ይመልከቱ፡፡

▣ **"ተብለን ልንጠራ"** ይህ በግሪክ በተደራጊነት ሁኔታ ገላጭ ግሥ ሲሆን የተጠቀሰው በአክብሮት መጠሪያ ድባብ ነው ("የእግዚአብሔር ልጆች") ይህ በእግዚአብሔር በራሱ የተሰጠ ነው፡፡

▣ **"የእግዚአብሔር ልጆች"** ይህ የ2:29-3፣ 10 ትኩረት ነው፡፡ ይህም የእግዚአብሔር ድነታችን በሚመለከት ቀዳሚ ድርሻውን መውሰዱን የሚያረጋግጥ ነው (ዮሐ 6:44፣ 65)፡፡ ዮሐንስ አማኙ ከመስኮት ጋር ያለውን አዲስን ግንኙነት ለመግለፅ ቤተሰባዊ ቃላትን ይጠቅሳል (2:29፤ 3:1፣ 2፣ 9፣ 10፤ ዮሐ 1:12)፡፡

ዮሐንስ (ዮሐ 3:3) እና ጴጥሮስ (1ጴጥ 1:3፣ 23) *"ዳግመኛ መወለድ"* ወይም "ከላይ መወለድ" ለሚሉት ሐረጉች የዝምድና ተምሳሌቶችን መጠቀማቸው ደስ የሚከያሰኝ ሲሆን ጳውሎስ በአንፃሩ "ጉዲፈቻ" የሚል የዝምድና ተምሣሌት ይጠቀማል (ሮሜ 8:15፣ 23፤ 9:4፤ ገላ 4:15 ኤፌ 1:5) እንዲሁም ደግሞ ያዕቆብ አማኙ በክርስቶስ አማካኝነት ያገኘውን አዲሱን ግንኙነት ለመግለፅ "መወለድ" (ያዕ 1:18) ወይም "ማምጣት" የሚሉትን ተምሳሌቶችን ይጠቀማል፡፡ ክርስትና ቤተሰባዊነት ነው፡፡

▣ **"እንዲሁም ነን"** ይህ የአሁን ጊዜ አመልካች ነው፡፡ ይህ ሐረግ በኪንግ ጀምስ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኝም፤ ምክንያቱም ኪንግ ጀምስ ትርጉም በተመሠረባቸው ከኋላ በመጡት የግሪክ ምንጮች (K እና L) ውስጥ ያልተካተተ በመሆኑ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ሐረግ በበርካቶች የጥንት የግሪክ ምንጮች ውስጥ ይታያል ($P^{47}$፣ N፣ A፣ B እና C)፡፡ ዮቢ.ኤስ[4] ለዚህ መካተት የ "A" ደረጃን ይሰጠዋል (እርግጠኛ ማለት ነው)፡፡ ይህንንም በጥቅስ ላይ የሚሰጠውን ትችት በማውጫ ሁለት ላይ ይመልከቱ፡፡

▣ **"ዓለም እኛን አያውቀንም"** "ዓለም" የሚለው ቃል ከሥነ-መለኮት አንፃር ከ2:15-17 ጋር በተሳሳይነት ሁኔታ የተጠቀሰ ነው፡፡ ዓለም የሚያመለክተው ከእግዚአብሔር ተለይቶ የተደራጀ እና የሚሠራ የሰዎች ማህበረሰብ ነው፡፡ (ዮሐ 15: 18-19፤ 17: 14-15)፡፡ መከራ እና ከአለም የሚደርስብን ጥላቻ በክርስቶስ ዘንድ ላለን ሥፍራ ማስረጃ የሚሆን ነው (ማቴ 5: 10 - 16)፡፡

▣ **"ስለዚህ ምክንያት ዓለም እርሱን ስላላወቀው"** ይህ አብን ለማመልከት እንደሆነ ግልፅ ነው፤ ምክንያቱም በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ኢየሱስ በተደጋጋሚ ዓለም እንደሚያውቀው ይናገራልና (ዮሐ 8:19፣ 55፤ 15:18፣ 21፤ 16:3)፡፡ በ1 ዮሐንስ የተጠቀሱት ተውላጠ ስሞች አሻሚ ናቸው (በ2:28 ላይ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ)፡፡ በዚህ ዓውድ መሠረት ሰዋሰዋዊው ቅፅል አብ ሲሆን በቁ.2 ላይ ያለው ሥነ-መለኮታዊው መግለጫ ግን ወልድ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ይህ ሆን ተብሎ የሚደረግ አሻሚነት ሊሆን ይችላል ምክንያቱም ኢየሱስን ማየት አብን ማየት ነውና (ዮሐ 12:45፤ 14:9)፡፡

3:2 **"ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠም"** ይህ የሚናገረው ዮሐንስ ስለ መጨረሻው ጊዜ ክስተቶች መግለፅ አለመቻሉን ነው (ሐዋ 1:7) ወይም ስለትንሣኤው አካል ትክክለኛ ተፈጥሮ አለመረዳቱን ነው (1ቆሮ 15:35-49)፡፡ ከዚህም ባሻገር 2:27 የሚገልፀው በሁሉም አቅጣጫ ጥልቀትና ሠፊ እውቀት መያዝን አይደለም፡፡ ኢየሱስ ራሱ እንኳን በሥጋ በነበረበት ወቅት ስለዚህ ክስተት የነበረው እውቀት ውሱን ነበር (ማቴ 24:36፤ ማር 13:22)፡፡

▣ **"ዳሩ ግን ቢገለጥ"** ጊዜን አመልካች ቃል ሦስተኛ መደብ ሁታዊ አረፍተ ነርን የሚያስተዋውቅ ነው፡፡ በዚህ ሥፍራ የተጠቀሰው ስለዳግም መመለስ ለመጠየቅ ሳይሆን የጊዜውን አለመታወቅ ለመግለፅ ነበር፡፡ ዮሐንስ፤ ምንም እንኳን አሁን በሚገኝ ሙሉ ድነት ላይ ትኩረት ቢያደርግም ዳግም መመለሱን ይጠብቃል፡፡

▣ **"እርሱን እንድንመስል"** ይህ ክርስቶስን ፈፅመን መምሰል እንዳለብን የሚያካትት እውነት ነው (2ቆሮ 3 :18፤ ኤፌ 4:13፤ ፊል 3:21፤ እና ቆላ 3:4)፡፡ ይህም በአብዛኛው "መክበር" ተብሎ ይጠራል (ሮሜ 8:28-30)፡፡ የድነታችንም ፍፃሜ ነው! ይህ በመጨረሻው ጊዜ የሚደረገው መለወጥ በእግዚአብሔር አመሳል በተፈጠሩት በሰው ልጆች ዘንድ ያለው የእርሱ አምሣል ሙሉ በሙሉ የመመለሱን (የመታደሱን) ሁኔታ የሚያመለክት ነው (ዘፍ 1:26፤ 5 :1፤ 9:6)፡፡ በዚህም ከእግዚአብሔር ጋር በጣም የቀረበ ሕብረትን ማድረግ የሚችለ መሆኑን መረዳት እንችላለን!

▣ **"እርሱ እንዳለ እናየዋለንና"** ኢዮብ እግዚአብሔርን ለማየት ናፍቆ ነበር (ኢዮ 19:25-27)፡፡ ኢየሱስም ደግሞ ልበ - ንጹሐን እግዚአብሔርን እንደሚያዩት ይነግረናል (ማቴ 5:8)፡፡ እርሱን በሙላት ማየት ማለተ እና እርሱን እንድንመለስ እንለወጣለን ማለት ነው (1ቆሮ 13 :12)፡፡ ይህም አማኝ ጌታ ዳግም ሲመለስ መክበሩን ያመለክታል (ሮሜ 8:29)፡፡ "ፅድቅ" ከኃጢአት ቅጣት ነፃ መሆን ከሆነ፣ እንዲሁም ደግሞ "መቀደስ" ማለት ከኃጢአት ኃይል ነፃ መውጣት ከሆነ "መክበር" ደግሞ ከኃጢአት ህልውና ነፃ መውጣት ማለት ነው!

3:3 *Pas* የሚለው የግሪኩ ቃል ከ2:29 እስከ 3:10 ድረስ ሰባት ጊዜ ተጠቅሶ ይታያል፡፡ ምንም ለየት ያሉ ነገሮች የሉትም፡፡ ዮሐንስ እውነትን የሚየቀርበው ሙሉ በሙሉ በግልፅ ጥርት ባለ ሁኔታ ነው፡፡ ከነዚህም አንዱ ለምሳሌ የእግዚአብሔር ልጅ ወይም የዲያብሎስ ልጅ የሚለው ነው (2:29፤ 3:3፣ 4፣ 6 (ሁለት ጊዜያት) 9:10)፡፡

▣ **"ይህን ተስፋ"** በጳውሎስ ይህ ቃል ሁልጊዜ የሚያመለክተው የትንሳኤን ቀን ነው (ሐዋ 23:6፤ 24:15፤ 26:6-7፤ ሮሜ 8:20-25)፤ 1ተሰ 2:19፤ ቲቶ 2:13፤ 1ጴጥ 1:3፣ 21) ፡፡ ይህም አንድ ክስተት በእርግጠኝነት ነገር ግን አሻሚ በሆነ የጊዜ ሁኔታ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ዮሐንስ እንደሌሎቹ የአዲስ ኪዳን ፀሐፊዎች "ተስፋውን" ብዙ ጊዜ ደጋግሞ አይናገረውም፤ ይህም ዮሐንስ በፅሑፎች የተጠቀመበት ብቸኛው ሥፍራ ነው፡፡ ዮሐንስ ትኩረት የሚያደርገው አሁን በክርስቶስ "መኖር" ባለው ጠቃሜታና ግዴታዎች ላይ ነው! ይሁን እንጂ ይህ ማለት ዮሐንስ በመጨረሻው ዘመን ክፋት ፍርድ እንደማያገኝ (2:18) እና አማኝም በፍፃሜው እንደማይከብር (3:1-3) ለመናገር ፈልጐ አይደለም፡፡

▣ **"እርሱ ንጹሕ እንደሆነ ራሱን ያነፃል"** ይህ የአሁን ጊዜ አድራጊ ግሥን አመልካች ነው፡፡ ንጽሕና አስፈላጊ ጉዳይ ነው /ማቴ 5:8፣ 48)፡፡ እኛም ልክ በዮሐንስ 1:12 ላይ እንደተገለፀውና በእርሱ ዘንድ ተቀባይነትን እናገኝ ዘንድ እንደተባበርን ሁሉ በቅድስና ሒደት ውስጥም ከእርሱ ጋር አብረን ልንሠራ (ልንተባበር) ይገባናል (2ቆሮ 7:1፤ ያዕ 4:8፣ /ጴጥ/: 22፤ 2ጴጥ 3:13፣ 14)፡፡ ይህንን ድነታችንን በሚመለከት በእግዚአብሔር በኩል (ሉዓላዊነቱ) እና በእኛ በኩል (የሰው ነፃ ፈቃድ) ያለውን ውጥረት ሕዝ 18:31ን ከ36:26-27 ጋር በማነፃፀር በግልፅ ማየት እንችላለን፡፡ እግዚአብሔር ምንጊዜም ቀዳሚውን ኪዳኑ የሚወስድ ሲሆን (ዮሐንስ 6:44፣ 65) በሌላ በኩል ደግሞ የቃል ኪዳኑ ሕዝብ በንስሐና በእምነት እንዲሁም ቀጣይነት ባለው የንስሐ፣ የእምነት የመታዘዝ፣ የማምለክ እና ፀንቶ በመቆም ሕይወት ምላሽ ይሰጡ ዘንድ ይሻል፡፡
ይህ ኢየሱስ በዮሐንስ 17፤ በተለይ በቁ 17 እና 19 ላይ ያደረገውን የሊቀ ካህንነት ፀሎት በተዘዋዋሪ የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም፡፡ እርሱ ራሱን ሲያነፃ እርሱን የሚከተሉትም ራሳቸውን ያነፃሉ፡፡ የአንድ መሠረታዊ ሥርወቃል የተለያዩ መልኮች መጠቀሳቸው በመጠኑ የሚደንቅ ነው፡፡

1. ዮሐንስ 17:17፣ 19 — hagiazo (hagios፤ ዮሐንስ 10 :36 )፡፡
2. 1ዮሐንስ 3:3- hagNizo (hagNos፤ ዮሐንስ 11:15 )፡፡

## ስለ 3 : 4-10 አውዳዊ ግንዛቤዎች

ሀ. ይህ ምግባብ በክርስቲያን ፍፁማዊነት (ሮሜ 6) አንዳንዴም ሙሉ የመቀደስ ሕይወት ተብሎ በሚጠራውና ተደጋጋሚ በሆነው የክርስቲያን በደል (ሮሜ 7) መካከል አወዛጋቢ ሆኖ የቆየ ርዕሰ ጉዳይ ነው፡፡

ለ. ይህ ክፍል ለመደመሪያዎች የመልዕክቱ ተቀባዮች የነበረውን ትርጉም ባለን መረዳት ላይ ተፅዕኖ እንዲያደርግ ሥነ-መለኮታዊ አድልኦን ልንፈቅድለት አይገባም፡፡ ከዚህም ባሻገር ይህንን ክፍል በሚመለከት የራሳችን ነፃ የሆነ የጥናት አቋምሙሉ እስከሚሆን ደረስ እና ዮሐንስ በምዕራፍ 3 እና በመላው የመጀመሪያው የዮሐንስ መልዕክት ውስጥ ምን እንደሚል እስካላረጋገጥንድረስ ሌሎች ክፍሎች በዚህ ክፍል ጥቅስ ላይ ተፅዕኖ እንዲያደርጉ መፍቀድ የለብንም፡፡

ሐ. ይህ ክፍል የሁሉም አማኞች ዋና ግብ የሆነው ከኃጢአት ነፃ መውጣትን በግልፅ የሚያቀርብ (የሚያሳይ) ነው፡፡ ተመሳሳይ ሳብም በሮሜ 6 ላይ ተጠቅሷል፡፡ እኛም ኃጢአት የሌለበትን ሕይወት ልንኖር የምንችለው በክርስቶስ ኃይል ብቻ ነው፡፡

መ. ይሁን እንጂ ይህ ምንባብ ከጠቅላላው የአንደኛ ዮሐንስ መልዕክት ሠፊ ዓውድ ጋር ሊስማማ ይገባዋል፡፡

1. 1:8-2:2ን በትኩረት ሳናጤን (ክርስቲያኖች አሁንም እንደሚበድሉ ይህንን ምግባብ መተርጐም ስህተት ይ ይጥለናል፡፡)
2. የጠላላውን የመጀመሪያ ዮሐንስ መልዕክትን ዓላማ ለማፍረስ ከመነሣት ሃሳብ ይህንን ምግባብ የመንተረጉም ከሆነ የድነት ዋስትናን በሚመለከት ለስህተብ መምህራን የምንሰጠው ምላሽም እንዲሁ ሥህተት ላይ ይወድቃል፡፡
3. ኃጢአት የለሽነት ወይም ኃጢአትምንም እንዳይደለ ከሚከራከሩት የስህተት አስተማሪዎች አንፃር ምንባቡ መዛመድ አለበት፡፡ ምናልባት 1:8፣ 2:2 ስለ ስህተት አስተማሪዎች አንደኛውን ፅንፍ ላይ ምላሽ ሲሰጥ 3:1-10 ደግሞ በሌላው ጉዳይ ላይ ምላሽ ይሰጣል፡፡ የአዲስ ኪዳን መልዕክቶችን መተርጐም ግማሹን የቴሌፎን ንግግርን የመስማት ያህል መሆኑን ልናስታውስ ይገባል፡፡

ሠ. በእነዚህ ሁለት ምንባቦች መካከል እርስ በርሱ የሚጋጭ የሚመስል ሐሳብ ያለ ይመስላል፡፡ በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ያለው ኃጢአት በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተደጋግሞ የሚወሳ ችግር ነው (ሮሜ 7)፡፡ ይህመ ልክ በአስቀድሞ መወሰን እና በሰው ነፃ ፈቃድ ወይም በአማኝ ዋስትና እና ፀንቶ መቆም ተመሣሣይ የሆነን ዲያሌክቲካዊ ውጥረት የሚፈጥር ነው፡፡ ተቃራኒ የሚመስለውም ጉዳይ ሥነ-መለኮታዊ ሚዛንን ከመስጠቱም ባሻገር አላስፈላጊ የጽንፈኝነትን አቋም የሚያስወግድ ነው፡፡ ከዚህም ጋር በተያያዘ የስህተት አስተማሪዎች ኃጢአትን በሚመለከት ሁለት አይነት ግድፈቶችን ያቀርባሉ፡፡

ረ. ይህ ጠቅላላው ሥነ-መለኮታዊ ውይይት የተመሠረተው በሚከተሉት መካከል ባለው አለመግባባት ላይ ው፤

1. በክርስቶስ ያለን ሥፍራ
2. ይህንንም ሥፍራ ለማሟላት እንዲቻል በዕለታዊው ኑሮአችን የምናደርገው ተግባራዊ ጥረት
3. አንድ ቀን ድል የእኛ እንደሚሆን የተሰጠን ተስፋ!

እኛ በክርስቶስ ምክንያት በኃጢአት ከሚመግበን ቅጣት (በእግዚአብሔር ዘንድ እንዲያው ተቀባይነትን ማግኘት ነፃ ነን)፤ ነገር ግን አሁንም ቢሆን መጋደላችን (ቀጣይነት ያለው ቅድስና) የሚቀጥል ሲሆን አንድ ቀን ግን ከኃጢአት ሕልውና ነፃ እንወጣለን (መክበር)፡፡ ይህም መጽሐፍ በቅድሚያ የያስገነዘበን ነገር ኃጢአት እንዳለብን እና ኃጢአት አልባ ወደ ሆነ ሕይወት እንደምንጓዝ ነው፡፡

ሰ. ሌላው አቋም ደግሞ የሚመጣው ከዮሐንስ ሥነ-ፅሑፍ ዱዋሊዝም ነው፡፡ ዮሐንስ ግልፅ እና ጥርት ባሉ ምድቦች ፅፏል (እንዲሁም በሙት ባህር ጥቅሎች ላይም ተገኝተዋል)፡፡ ለእርሱ አንድ ሰው በክርስቶስ ሲሆን ፅድቅ ሲሆን በዲያብሎስ ሲሆን ደግሞ ኃጢአተኛ እንደሆነ ነው፡፡ ሌላ ሦስተኛ ምድብ አልነበረም፡፡ ይህም ዙሪያ ጥምጥም፣ ባህላዊ፣ የትር ጊዜ፣ የቀብር ብቻ እንዲሁም ደግሞ የፋሲካ ብቻ ክርስትና ለሆነው ሕይወት እንጂ "ማንቂያ ጥሪ" ሆኖ የሚያገለግል ነው!

ሸ. በዚህ አስቸጋሪ ርዕስ ላይ ያሉ አንዳንድ ምንጮች (ማመሳከሪያዎች)

1. በዚህ ምንባብ ላይ ላሉ ለሰባቱ ልማዳዊ አተረጓጐሞች "*The Epistles of JohN*" የሚለው እና በ *"TyNdale New TestameNt CommeNtaries"* ውስጥ ያለው (በጅን.አር.ስቶስ ተፅፎ በ*EardmaN's* የታተሙ) (ገፅ 130-136)፡፡
2. ፍፁምነት በሚለው አቋም ላይ በጥሩ ሁኔታ ለመነጋገር ChristiaN Theology፣ ቅፅ 2፤ ገጽ 140 (በኤች.አር.ሎን ዊሊ ተፅፎ በ አሳታሚ የታተመው)
3. በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ስላለው ተደጋጋሚ በደል አስተምህሮ ለመነጋገር በቢ.ቢ. ዎር ፊልድ የተፃፈው እና *"The presbyteriaa aNd Reformed Published CompaNy"* አሳታሚ ድርድት የታተመውን ይመልከቱ፡፡

## የቃል እና የሐረግ ጥናት

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 3 ÷ 4-10

**4ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ ዓመፅን ደግሞ ያደርጋል ÷ ኃጢአትም ዓመፅ ነው፡፡ 5እርሱም ኃጢአትን ሊያስወግድ እንደተገለጠ ታውቃላችሁ ÷ በእርሱም ኃጢአት የለም፡፡ 6በእርሱ የሚኖር ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም ኃጢአን የሚያደርግ ሁሉ አለየውም አላውቀውምም፡፡ 7ልጆች ሆይ ማንሣ አያስታችሁ፤ እርሱ ፃድቅ እንደሆነ ጽድቅን የሚያደርግ ጻድቅ ነው፡፡ 8ኃጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው÷ ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ኃጢአትን ያደርጋልና፡፡**

**ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዝአብሔር ልጅ ተገለጠ፡፡ 9ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም÷ ዘሩ በእርሲ ይኖራልና፤ ከእግዚአብሔርም ተወስዶአልና፣ ኃጢአትን ሊያደርግ አይችልም፡፡ 10የእግዚአብሔር ልጆችና የዲያብሎስ ልጆች በዚህ የተገለጡ ናቸውና፡፡ ጽድቅን የማያደርግና ወንድሙን የማይወድ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም፡፡**

3:4

| | |
|---|---|
| NASB | *"ኃጢአትን የሚያደርግሁሉ ዓመፅን ደግሞ ያደርጋል"* |
| NKJV | *"ኃጢአትን የሚያደርግ ማንም ሰው የህግ ጥሰትን ይፈፅማል "* |
| NRSV | *"ኃጢአትን የሚያደርግ ማንም ሰው ቢኖር በህዓ ጥሰት ጥፋተኛ ይሆናል"* |
| TEV | *"ኃጢአትን የሚያደርግ ማንም ሰው የእግዚአብሔርን ህግ በመጣስ ጥፋተኛ ነው"* |
| NJB | *"ኃጢአትን የሚያደርግ ማንም ሰው ክፉን ያደርጋል"* |

"ማንም" የሚለው ተውላጠ ስም በቁጥር 6 ላየ ፊተኛ ሆኖ ተጠቅሷል፡፡ ይህም ዓውድ ሁሉንም የሰው ዘር የሚመለከት ነው!

ይህ የአሁን ጊዜ አድራጊ ግሥ ቦዝ አንቀፅ እና የአሁን ጊዜ አድራጊ ግሥ አመልካች ነው፡፡ እነዚህ የአሁን ጊዜ ገላጭ ግሦች ትኩረት የሚያደርጉት የተለመደውን፣ ቀጣይነት የለውን እና በድርጊት የሚገለጠውን የሕይወት ዘይቤን ሲሆን ይህም በ2:1-2 ላይ ካለው የአድራጊ ግሥ ገላጭ ጋር ተቃራኒ የሆነ ነው፡፡ ይሁን እንጀ የዚህ ምንባብ ሥነ-መለኮታዊ ችግር (1:7-10ን ከ3:6-9 ጋር ያነፃፅሩ) በጊዜያት ገላጭ ግሥ አማካኝነት ሙሉ በሙሉ የሚፈታ አይደለም፡፡ ይህ ሊፈታ የሚችለው በሁለቱ የግኖስቲክ ሐሰት መምህራን ታሪካዊ ዳራ እና በአጠቃላይ የመጽሐፉ ዓውድ ነው፡፡

ሌላው ይህን ምንባብ ልዩ የሚደርገው "ዓመፅ" የሚለውን ቃል መጠቀሙ ነው፡፡ ይህ የሚናገረው ሕግን ስለመጣስ (የሙሴ ሕግ ወይም ማህበራዊ ልማዶች) አይደለም፡፡ ይህ ተመሳሳይ ቃል በ2 ተሰ 2:3-7 ላይ የክርስቶስን ተቃዋሚ ለማመልከት ተጠቅሷል፡፡ ቃሉ ምናልባት የአንድን ህግ ጥሰት ለማመልከት ሳይሆን ስለኃጢአት የተሰጠ ሙሉ ፍቺ (ዮሐ 9:41 ሮሜ 14:23፤ ያዕ 4:17፤ 1ዮሐንስ 5:17) ሳይሆን አይቀርም፤ ይህም ክርስቶስን የመምሰል ተቃራኒ ነው (ቁ. 5)፡፡

3:5 **"ተገለጠ"** ይህ የግሪኩ ተደርጐ ግሥ አመልካች ሲሆን የሚናገረውም ስለ ኢየሱስ ሥጋ መልበስ ነው (ቁ. 8፤ 2ጢሞ 1:10)፡፡ PaNeroo የሚለው ተመሣሣይ ግሥ በቁጥር 2 ላይ ስለ ዳግም መምጣቱ በሚናገረው ላይ ሁለት ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ እርሱ በመጀመሪያ ሲመጣ እንደ አዳኝ ሆኖ ሲሆን (ማር 10:45፤ 2ጢሞ 1:10) ዳግም ሲመለስ ግን እንዲፈረጅ ሆኖ ነው፡፡ ተወዳጅ ከሆኑት አስተማሪዎች አንዱ የሆነው ቢስ ሄንድሪክስ The letters of JohN በሚለው ማብራሪያው ላይ እንዲህ ይላል፤

> "ክርስቶስ የመጣበትን ዓላማ በሚመለከት ጠልቀው ከሚገቡት ኃይለኛ ንግግሮች የሚኙት በዚህ ቁጥር እና በቁጥር 8 ላይ ያሉት ሁለቱ ናቸው፡፡ እርሱ ኃጢአትን ለማስወገድ በእግዚአብሔር የተላከ ነበር (3:5)፤ የዲያብሎስንም ሥራ ያፈርስ ዘንድ የገለጠም ነበር (3:8)፡፡ በለላ ሥፍራ ደግሞ ሉቃስ ኢየሱስ የመጣበት ዓላማ የጠፉትን ሊፈልግ እና ሊያድን እንደሆነ በወንጌሉ መዝግቦታል (ሉቃ 19:10)፡፡ የዮሐንስም ወንጌል የሚገልፀው ኢየሱስ የመጣው በጐቹ የተትረፈረፈ ሕይወት ይኖሩ ዘንድ ነው ይላል (ዮሐ 10:10)፡፡ ማቴዎስም ኢየሱስ የመጣበትን ዓላማ ኢየሱስ የሊውን ስም በሚመለከት በሰጠው ፍቺ በተዘዋዋሪ ይገልፀዋል፤ ሕዝቡንም ከኃጢአታቸው ያድናቸዋል ይላል (ማቴ 1:21) በእነዚህ ሁሉ አገላለፆች ላይ ያለው መሠረታዊ እውነት ኢየሱስ የሰው ልጅ በራሱ ማድረግ ላልቻለው ነገር መፍትሔ ለመስጠት መምጣቱን ማመልከታቸው ነው፡፡" (ገጽ 79-80)፡፡

▣ **"ኃጢአትን ሊያስወግድ"** ይህ የግሪኩን ግሥ ሁኔታ ገላጭ ነው፡፡ ድርጊቱ የተመሠረተው የሰው ልጅ በሚሰጠው ምላሽ ላይ ነው (ንስሐ እና እምነት)፡፡ የዚህ ንግግር የኂላ ታሪክ የሚገናኘው ከሁለት ምንጮች ጋር ነው፡፡

1. በተምሳሌትነት የእስራኤልን ኃጢአት ከድንኳኑ ተሸክመው (በ1:29 መጥምቁ ዮሐንስ የመጠቀሰው) ወደ ምድረበዳ ከሚሰደዱት ፍየሎች አንዱ በምልክትነት የሚገለፅበት የመቤዥርት ቀን (ዘሌ 16)
2. ኢየሱስ በመሥቀል ላይ ለሠራው የተሰጠ መግለጫ (ኢሳ 53:11-12፤ ዮሐ 1:29፤ ዕብ 9:28፤ 1ጴጥ 2:24)፡፡

▣ **"በእርሱም ኃጢአት የለም"** ይህ የአሁን ጊዜ ድርጊት ገላጭን አመልካች ነው፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ያለ ኃጢአት መሆን (ዮሐ 8:46፤ 2ቆሮ 5:21፤ ዕብ 4:15፤ 7:26፤ 1ጴጥ 1:19፤ 2:22) በውክልና በምትክነት ስለ እኛ ሊፈፀመው የማዳን (የመቤዥርት) ሥራ መሠረት የሆነ ነው (ኢሳ 53)፡፡ "ኃጢአት" የሚለው ክፍል በነጠላ ቁጥር መጠቀሱን ያስተውሉ፡፡

የመጀመሪያው የኃጢአት ድርጊትን ሲያመለክት ሁለተኛው ግን የእርሱን የጽድቅ ባህርይ ያመለክታል፡፡ ዋናው ግብ ግን አማኞች በክርስቶስ አማካኝነት የቦታ ለውጥ ቅድስና እና ቀጣይነት ያለው ቅድስናን ከእርሱ ጋር እንደሚካፈሉ ሲገልፅ ኃጢአት ለክርስቶስም ሆነ ለእርሱ ተከታዮች እንግዳ ነገር መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ መቀደስ**

ኃጢአተኞች በንስሐ እና በእምነት ወደ ኢየሱስ ሲመለሱ በቅፅበት በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነትን እንደሚያገኙ እና እንደሚቀጥሉ አዲስ ኪዳን ያረጋግጣል፡፡ ይህም በክርስቶስ ያላቸው አዲስ ሥፍራ ነው፡፡ በዚህም የእርሱ ጽድቅ ለእነርሱ ሆኗል (ሮሜ 4)፤ ነውር የሌላቸው እና ትክክል ተብለዋል (ሕጋዊነት ያለው የእግዚአብሔር ማዳን)፡፡

በተቃራኒው ደግሞ አዲስ ኪዳን አማኞች እንዲቀደሱ ያሳስባል፡፡ ይህ በተጠናቀቀው የኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ላይ የቆመ የአማኝ ሥነ-መለኮታዊ ሥፍራ እና በአመለካከቱ እና በእለታዊ ኑሮው ክርስቶስን እንዲመስል የተደረገ ንጌ ነው፡፡ ድነት ነው፡፡

| የመጀመሪያ ምላሽ | ቀጣይነት ያለው ክርስቶስን መምሰል |
|---|---|
| ሐዋ 20÷23፤ 26÷18 | ሮሜ 6÷19 |
| ሮሜ 15÷16 | 2ቆሮ 7÷1 |
| 1ቆሮ 1÷2-3፤ 6÷11 | ኤፌ 1÷4፤ 2÷10 |
| 2ተሰ 2÷13 | 1ተሰ 3÷13፤ 4÷3-4፣ 7፤ 5÷23 |
| ዕብ 2÷11፤ 10÷10፣ 14፤ 13÷12 | 1ጢሞ 2÷15 |
| 1ጴጥ 1÷12 | 2ጢሞ 2÷21 |
| | ዕብ 12÷14 |
| | 1ጴጥ 1÷15-16 |

3:6 **"በእርሱ የሚኖር ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም"** ልክ እንደ 3:4 ሁሉ ይህም ሌላው የአሁን ጊዜ አድራጊ ቦዝ አንቀፅ እና የአሁን ጊዜ አድራጊ ድርጊት ገላጭ ነው፡፡ ይህም ምንባብ ከ1:8-2:2 እና 5:16 ጋር በተቃርኖ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡

▣ **"ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ አላየውም፣ አላውቀውምም"** ይህ ጥቅስ ሁለት የተሟሉ ድርጊት ገላጭ አመልካቾች የሚከተሉት አንድ የአሁን ጊዜ ድርጊት ገላጭ ቦዝ አንቀፅ አለው፡፡
በፅናት የሚቀጥል ኃጢአት የሚያሳየው አንድ ሰው ክርስቶስን እንዳላውቀው እና እንደማያውቀው ነው፡፡ በኃጢአታቸው ፀንተው የሚቀጥሉ ክርስትያኖች

1. የክርስቶስን ተልኳኮ ያፋልሳሉ
2. ክርስቶስን የመምሰል ግብ ያፋልሳሉ
3. የግለሰቡን መንፈሳዊ መሠረት ያሣያሉ (ዮሐ 8:44

3:7 **"ማንም አያስታችሁ"** ይህ የአሁን ጊዜ ድርጊት ገላጭ ትዕዛዝ ከአሉታዊ ቦዝ አንቀፅ ጋር የተጣመረ ሲሆን በተለምዶ የሚያመለክተው በሂደት ላይ ያለን ድርጊት ማቆም ነው፡፡ የሐሰት አስተማሪዎች መኖር (2:26) 1ኛ ዮሐንስራ ባጠቃላይ እና 1:7-10 እና 3:4-10ን በተለይ ለመረት ይቻል ዘንድ ሥነ መለኰታዊውንም መረዳት ለማግኘት ታሪካዊ ሁኔታውን የሚያዘጋጅ ነው፡፡
▣ **"ጽድቅን የሚያደርግ ጽድቅ ነው"** ይህ ጥቅስ ከጠቅላላው አውድ ተለይቶ ሊታይ የማይችል እና የአስተምህሮ አቋምን ለማራመድ የታሰበ አይደለም ("የሥራ ፅድቅ")፡፡ የሰው ልጆች በራሳቸው ጥረት ወደ ቅዱሱ እግዚአብሐር መቅረብ እንደሚይችሉ አዲስ ኪዳን በግልፅ ይናገረናል፡፡ ሰዎች በራሳቸው ጥረት አይድኑም፣ ይሁን እንጂ የሰው ልጆች በክርስቶስ የተፈፀመ ሥራ ላይ የተመሠረተውን የእግዚብሔርን ድነት ሥጦታ ለመቀበል ምላሽ መሥጠት አለባቸው፡፡ የእኛ ጥረቶች ወደ እግዚአብሔር አያቀርቡንም፡፡ ጥረቶቻችን ክፍሉን እንዳገው የሚያሣዩ ናቸው፡፡ በግልፅም የሚያሣዩትም የእኛን መንፈሳዊ ሁኔታ (ራዕ 22:11) እና ከደህንነት በኂላ ያለንን ብስለት ነው፡፡ እኛ የምንድ ነው በመልካም በሥራ ሳይሆን "መልካም ሥራን" ለመሥራት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ነፃ ሥጦታ ዋናው ግብ ክርስቶስን የሚመለሱ ተከታዮችን ማፍራት ነው (ኤፌ 2:8-9፣ 10)፡፡ እግዚአብሔር ለማንኛውም አማኝ ያለው የመጨረሻው ፈቃድ አማኝ ሲሞት መንግሥተ ሰማያትን ማውረስ (ምክንያታዊ ጽድቅ) ሳይሆን ክርስቶስን መምሰል ነው (ጊዜያዊ መቀደስ)፤ ይህም አሁን የሚፈፀም ነው (ማቴ 5:48፤ ሮሜ 8:28-29፤ ገላ 4:19) ! ጽድቅን በሚመለከት የቃል ጥናት ለማድረግ በ2:29 ላይ ጽድቅ የሚለውን ይመልከቱ፡፡

3:8 **"ኃጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው"** ይህ የአሁን ጊዜ ድርጊት ገላጭ ቦን አንቀፅ ነው፡፡ ልክ የዲያቢሎስ ልጆች በኑሮአችው እንደሚታወቁ ሁሉ (3:10፤ ማቴ 7:13፤ ኤፌ 2:1-3) የእግዚአብሔር ልጆች እንዴት እንደሚኖሩ ይታወቃሉ፡፡

▣ **"ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ኃጢአትን ያደርጋልና"** ይህ የአሁን ጊዜ ድርጊት ገላጭ አመልካች ነው፡፡ ዲያብሎስ ከመጀመሪያው ኃጢአትን ሲያደርግ የነበረ ነው (ዮሐ 8:44)፡፡ ይህ የሚያመለክተው ፍጥረትን ወይስ የመላዕክትን አመፅ
ከሥነ መለኰት አንፃር ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ ያመፀው መቼ እንደነበር ለመገመት አስቸጋሪ ነው፡፡ ኢዮብ 1:2፤ ዘካ 3 እና 1 ነገ 22:19-23 ሰይጣን የእግዚአብሔር አገልጋይ እና የመላዕክት አለቃ እንደነበረ የሚያሣዩ ይመስላሉ፡፡ የምሥራቃዊያን ነገሥታት (ባቢሎን፤ ኢሳ 14:13-14 ወይም ጢሮስ፣ ሕዝ 28: 12-16) ትዕቢት፣ አመፅ እና መሻት (ምኞት) የሰጥየንን አመፅ ለማሣየት እንደ ተጠቀሱ ማየት የሚቻል ነው (ምናልባት ሣይሆን)፡፡ ይሁን እንጂ በሉቃ 10:18 ላይ ኢየሱስ ሲነገር ሰይጣንን እንደመብረት ከሰማይ ሲወድቅ እንዳየው ሲገልፅ በአንፃሩ ደግሞ በትክክል መች እንደነበረ አይገልፅም፡፡ መገለጥ ካለመኖሩ የተነሣ የክፋት መሠረት እና ዕድገቱ የሚታወቅ አይደለም፡፡ ተለይተው የተቀመጡትን፣ አሻሚ የሆኑትን፣ እና በምሥል መልክ የተጠቀሱትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶችን በሥርዓት ከማስቀመጥ እና ከአክራሪነት አቋም ልንጠነቀቅ ይገባል! ሰይጣን በብሉይ ኪዳን ከተገለፀው አገልጋይቱ አንስቶ በጠላትነት እስከሚለጥ ድረስ ያለውን ጥሩ ውይይር ለማድረግ በኤ.ቢ. ዳቢድሰን የተፃፈው እና በቲ ኤን ቲ ክላሪክ የታተመው Old TestameNt Theology (ገጽ 300-306) የሚለው መጽሐፍ ከሁሉመ የተሻለ ነው፡፡

▣ **"የእግዚአብሔር ልጅ"** ቀጥሎ ያለውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስ ይመልከቱ፡፡

**ልዩ ርዕስ: የእግዚአብሔር ልጅ**

ይህ ኢየሱስን በሚመለከት በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከተሰጡት መጠሪያዎች ዋነኛው ነው፡፡ ቃሉ መለኮታዊ አንደምታዎች አሉት፡፡ ቃሉ ኢየሱስን ‹‹ልጅ›› ወይም ‹‹ልጄ›› ብሎ ሲያካትት እግዚአብሔርንም እንደ ‹‹አባት›› ይገልፃል፡፡ ቃሉ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከ124 ጊዜ በላይ ተጠቅሷል፡፡ በዳን 7:13-14 ላይ ኢየሱስ ‹‹የሰው ልጅ›› ተብሎ የተጠቀሰበት መለኮታዊ አንደምታ አለው፡፡

በብሉይ ኪዳን ‹‹ልጅ›› የሚለው መጠሪያ አራት የተለዩ ወገኖችን ሊያመክት ይችላል፡፡

1. መላዕክት (በተለምዶ በብዙ ቁጥር፤ ዘፍ 6:2፤ ኢዮ 1:6፤ 2:1)
2. የእሥራኤልን ንጉሥ (2ሣሙ 7:14፤ መዝ 2:7፤ 89:26-27)
3. የእሥራኤል ሕዝብ በጠቅላላው (ዘፀ 4:22፤ ዘዳ 14:1፤ ሆሴ 11:1፤ ሚል 2:10)
4. የእሥራኤል ፈራጆች (መዝ 82:6)

ኢየሱስን በሚመለከት የሚገናኘው ሁለተኛው አጠቃቀም ነው፡፡ በዚህ መሠረት ‹‹የዳዊት ልጅ›› እና ‹‹የእግዚአብሔር ልጅ›› ሁለቱ ከ2ሳሙ 7፤ መዝ 2 እና ‹‹የዳዊት ልጅ›› እና 89 ጋር የሚዛመዱ ናቸው፡፡ በብሉይ ኪዳን በእስራኤል ዘንድ እንደተጠቀሰው እንደ አንዱ ‹‹በቅባት ከሚታወቁት›› እንደ አንዱ የሥነ-ፍፃሜው ንጉሥ (የመጨረሻው ዘመን ንጉሥ) ካልሆነ በስተቀር በብሉይ ኪዳን ‹‹የነው›› ‹‹የእግዚአብሔር ልጅ›› የሚለው መጠሪያ ከራዕይ ጋር ተያያዥነት ባላቸው የአይሁድ የመጽሐፍ ቅዱስ ዘን ሥራወች ውስጥ መሲሐዊ አንደምታ አለው (2 ኤስራደስ 7 :28፤ 13:32፣ 37፣ 52፤ 14:9 እና 1 ሔኖክ 105:2)፡፡

ኢየሱስን እንደሚመለከቱ መጠን በአዲስ ኪዳን ታሪካዊ ዳራው በበርካታ ክፍሎች ማጠቃለያ ተሰጥቶበታል፡፡

1. ከሁሉ አስቀድሞ መሆኑ (ዮሐ 1:1-18)
2. የተለየ (በድንግና) ውልደቱ (ማቴ 1:23፤ ሉቃ 1:31-35)
3. ጥምቀቱ (ማቴ 3:17፤ ማር 1:11፤ ሉቃ 3:22 ከሰማይ የመጣሙ የእግዚአብሔር ድምፅ በመዝ 2 ላይ የተጠቀሰውን ሰማያዊ ንጉሥነቱን በኢሳ 53 ላይ ከተገለፀው መከራን ከሚቀበለው አገልጋይ ጋር ያጣምረዋል)፡፡
4. በሰይጣን መፈተኑ (ማቴ 4:1-11፤ ማር 1:12፣ 13፤ ሉቃ 4:1-13፡፡ ልጅነቱን እንጠራጠር ተፈተነ ወይም ከመስቀሉ ውጪ ዓላማው እንዲሳካ በተለያዩ መንገዶች ተፈተነ) ፡፡
5. ተቀባይነት በማያገኙ ዘንድ የተሰጠው ምሥክርነት
   ሀ. አጋንንት(ማር 1:23-25፤ሉቃ 4:31-37፣41፤ማር 3:11-12፣ 5-7)
   ለ. የማያምኑት (ማቴ 27:43፤ ማር 14:61፤ ዮሐ 19:7)
6. በደቀመዛሙርቱ የተሰጠው ምሥክርነት
   ሀ. ማቴ 14:33፣ 16:16
   ለ. ዮሐ 1:34፣ 49፣ 6:69፤ 11-27
7. ስለራሱ የሰጠው ማረጋገጫ
8. እግዚአብሔርን እንደ አባት ለመግለፅ የተጠቀመበት ዘይቤያዊ አነጋገር
   ሀ. "አባት" የሚለውን መጠሪያ ለእግዚአብሔር መጠቀሙ
      1. ማርቆስ 14:36
      2. ሮሜ 8:15
      3. ገላትያ 4:6

   ለ. ከመለኮት ጋር ያለውን ሕብረት ለመግለፅ አባት (Pater) የሚለውን መጠሪያ ደጋግሞ መጥቀሱ

ለማጠቃለል "የእግዚአብሔር ልጅ" የሚለው መጠሪያ ቀደም ሲል ብሉይ ኪዳንን እና የተሰጡትን ተስፋዎች እና ምንነታቸውን ለሚያውቁት ትልቅ ሥነ-መለኮታዊ ነበረው፤ ነገር ግን የአዲስ ኪዳን ፀሐፊዎች ቃሉ ከአህዛብ ጋር በመጠቀሱ ደስተኞች አይደሉም ምክንያቱም አረማዊያን የኋላ ታሪካቸው ከ"አማልዕክት" ጋር የተሳሰረ በመሆኑ እና ሴቶችን ከሚወልዷቸው ልጆቻቸው ጋር ‹‹ታላላቅ›› ወይም "ኃያላን" ብሎ የመገመት አካሄድ ስለነበረው ነው፡፡

▣ **"ተገለጠ"** ይህ PaNeroo (ፓኔሮ) የሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙም "ግልፅ ይሆን ዘንድ ወደ ብርሃን ማምጣት ማለት ነው፡፡ 5 እና 8 ቁጥሮች በትይዩነት የተቀመጡ ሲሆን ሁለቱም ቃሉን በተደራጊነት ስለሚጠቀሙ የሚያመለክተውም ክርስቶስ በሥጋ መገለጡን ነው (1:2)፡፡ በስህተት መምህራን በኩል የበረው ችግር ወንጌል ለእነርሱ ግልፅ ባለመሆኑ ሳይሆን የራሳቸው ሥነ-መለኮታዊ/ፍልስፍናዊ አጀንዳ ስለነበራቸው ነው፡፡

▣ **"የዲያብሎስን ሥራ እንዲናያፈርስ"** የኢየሱስ በጊዜው እና በሥጋ መገለጡ ለ "ማፍረስ" (luo የሚለው ግሪኩን አድራጊ ግሥን ሁኔታ ገላጭ) ነበር፤ ይህም ማለት "መፍታት" ወይም "ነፃማውጣት" ወይም "ማፍረስ" ማለት ነው፡፡ ኢየሱስ ይህን በቀራኒዮ መስቀል ላይ አድርጉታል፤ ነገር ግን የሰው ልጆች እርሱን በእምነት በመቀበል ለተጠናቀቀው እና ነፃ ሥጦታ ለሆነው (ሮሜ 3:24፤ 6:23፤ ኤፌ 2:8 ምላሽ ሊሰጡበት ይገባል (ዮሐ 1:12፤ 3:16)፡፡

"የተጠናቀቀ ነገር ግን አሁንም ገና" የሚለው ኪዳን ውስጥ ያለው ውጥረት የሚገናኘው ከክፋት መፍረስ ጋር ነው፡፡ ዲያብሎስ ተሸንፏል፤ ነገር ግን ፍፁም የሆነው የእግዚአብሔር መንግሥት ፍርድ እስከሚገለጥ ድረስ አሁንም በአለም ውስጥ በትጋት ይሠራል፡፡

3:9 **"ከእግዚአብሔር የተወለደ ማንም"** ይህ የአሁን ጊዜ ድርጊት ገላጭ አመልካች ግሥ ሲሆን ይህም የግሪኩ ድርጊት ገላጭ ግሥን ሁኔታ የሚገልፀው እና ሁለት ጊዜ በ2:1 ላይ ከተጠቀሰው ጋር የሚቃረን ነው፡፡ ይህንን ንግግር በሚመለከት ስላለው ጠቀሜታ ሁለት አይነት ፅንሱ ሐሳቦች አሉ፤

1. ይህ የሚገናኘው ከግኖስቲስ አስተማሪዎች ጋር ሲሆን በተለይም ደግሞ ድነትን ከእውቀት አንፃር እያዩ በማሳነስ ብለውም የሞራላዊ የህይወት ዘይቤን አስፈላጊነት የሚያስወግዱትን የተለዩ ቡድኖች ያመለክታል፡፡
2. የአሁን ጊዜ ገላጭ ግሥ የሚከያተኩረው ቀጣይነት ያለው ልማዳዊ የሆነን የኃጢአት ድርጊትን (ሮሜ 6:1) እንጂ የተለዩ የኃጢአት ድርጊቶችን አይደለም (ሮሜ 6:15)፡፡

ይህ ሥነ-መለኮታዊ ልዩነት በሮሜ 6 ላይ (በክርስቶስ አንዳ ያለኃጢአት መሆን) እና በሮሜ 7 ላይ (አማኙ ከአማኙ ከኃጢአት ለመላቀቅ የሚያደርገው የማያቋርጥ ትግል) የተብራራ ነው፡፡

የቁጥር 1 ታሪካዊ አቀራረብ ከሁሉም የተሻለ ይመስላል፤ ነገር ግን ቁጥር 2 መላሽ የሚሰጠበትን አሁን ባንበት ዘመን እውነቱን ተግባራዊ የማድረጉን አስፈላጊነትንም ቸል ስልለው አይገባም፡፡ በዚህ አስቸጋሪ ጥቅስ ላይ ጥሩ ውይይት ለማድረግ ይቻል ዘንድ በዋልተር ኬይዘር፣ ፒተር ዴቪድስ፣ ኤፍ.ኤፍ.ብሩስ እና ማንፍሬድ ብራውች የፃፈው Hard SayiNg of the Bible (ገጽ 736-739) የሚለው ተመራጭ ነው፡፡

▣ **"ዘሩ በእርሱ ይኖራልና"** ይህ የአሁን ጊዜን አመልካች ድርጊት ገላጭ ግሥስ ነው፡፡ "ዘሩ" በሚለው ሐረግ ትርጓሜ ላይ በርካታ ፅንሰ-ሐሳቦች አሉ፤

1. አውገስቲን እና ሉተር የእግዚአብሔር ቃል ያመለክታል ይላሉ (ዮሐ 3:5፣ 6፣ 8፤ 1ዮሐ 3 :24፤ 4:4፣13)፡፡
2. ሌሎች መለኮታዊ ተፈጥሮን ወይም አዲስ ማንነትን ያመለክታል ይላሉ (2ጴጥ 1:4፤ ኤፌ 4:24)፡፡
3. ምናልባትም ክርስቶስን እንደ "አብርሃም ዘር" ሊያመለክት ይችላል (ሉቃ1:55፤ ዮሐንስ 8:33፣ 37፣ ገላ 3:16)
4. አንዳንዶች "ከእግዚአብሔር የወለደ" ከሚለው ሐረግ ጋር ተመሣሣይ ነው ይላሉ፡፡
5. በሰው ልጆች ውስጥ ያለውን የመለኮት ፍንጣቂን ለመናገር ግኖስቲኮች የሚጠቅሱት እንደነበር ግልፅ ነው፡፡

ቁጥር 4 ምናልባት ከእነዚህ ፅንሰ-ሐሳቦች ከሁሉም የተሻለው ዓውዳዊ አማራጭ ሲሆኑ ነው፤ ነገር ግን ዮሐንስ ቃሉን የተጠቀመው /የመረጠው/ አደገኛ የሆነውን የግኖስቲክ ኑፋቄን ለመቃወም ነበር (ቁጥር 6)፡፡

3:10 "ይህ የቁጥር 4-9 ያለው መደምደሚያ /የማጠቃለያ ሃሳብ ነው፡፡ ጥቅሱ የሚይዘው ሁለት የአሁን ጊዜ አመልካች ድርጊት ገላጭ ግሦችን እና ሁለት የአሁን ጊዜ ድርጊት ገላጭ ቦዝ አንቀፆችን ሲሆን የሚያመለክቱትም ድርጊት በሒደት ላይ መሆኑን ነው፡፡ ከሥነ - መለኮት አንፃር ይህ ኢየሱስ በተራራው ላይ ካደገው ንግግር በትይዩ የሚቀመጥ ነው (ማቴ 7:16-20)፡፡ አንድ ሰው የሚኖረው ኑሮ የአንድን ሰው (የውየውን) የልብ ሁኔታ እና መንፈሳዊ መረዳቱን የሚያሳይ ነው፡፡

ይህ ለ2:29 የተሰጠ አሉታዊ ምላሽ ነው::

▣ **"የእግዚአብሔር ልጆች እና የዲያብሎስ ልጆች"** ይህ የዮሐንስን የሴሜቲክ ቋንቋ የኋላ ታሪክን የሚያሣይ ነው፡፡ ዕብራይስጥ የጥንት የሴሜቲክ ቋንቋ እንደመሆኑ መጠን ያለ ምንም ቅፅሎች ሰዎችን ለመግለፅ "የ --- ልጅ---" የሚለውን ሐረግ ይጠቀማል፡፡

> NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 3÷11-12
> **[11]‹‹ከመጀመሪያ የሰማችኂት መልዕክት፡- እርስ በርሳችን እንዋደድ የምትል ይህች ናትና [12]በክፉው እንደነበረ፤ ወንድሙንም እንደ ገደለ እንደቃየል አይደለም፤ ስለምንስ ገደለው? የገዛ ሥራው ክፉ÷ የወንድሙም ሥራ ጽድቅ ስለነበረ ነው፡፡**

3:11 **"መልዕክት"** ይህ የግሪክ ቃል (aggelia፤ በተለምዶ ANgelia ተብሎ ይተረጐማል) በ1ዮሐ 1:5 እና 3:11 ላይ ብቻ ተጠቅሷል፡፡ የመጀመሪያው አጠቃቀም አስተምህሮታዊ ይመስላል፤ ሁለተኛው ግን ግብረ-ገባዊ ነው፡፡ ይህም ከዮሐንስ ሁለት የክርስትና አቅጣጫዎች ጋር ሚዛኑን ለመጠበቅ ነው (1:8፣10፤2:20፣24፤ 3:14)፡፡

▣ **"ከመጀመሪያ የሰማችኂት"** ይህ ሐረግ ኢየሱስን እንደ እግዚአብሔር ሕያው ቃል (ዮሐ 1 :1) እና የእግዚአብሔርን ቃል እንደሚገልጥ (1:1፤ 2:7፣ 13፣ 14፣24፤ 2ዮሐ 5:6) አድርጐ በማዛመድ የሚያቀርብ ሥነ-ፅሑፋዊ መንገድ ነው::

▣ **"እርስ በርሳችን እንዋደድ"** ይህ አማኞች በእውነት ለመቤዥታቸው ማስረጃ ነው (ቁጥር 10፣ 14)፡፡ ይህ የሚያመለክተው የኢየሱስን ቅሎች ነው (ዮሐንስ 13:34-35፤ 15:12፣17፤ 1ዮሐ 3:23፤ 4:7-8፣ 11-12፣ 19-21)፡፡

3:12 **"ቃየል"** የቃየል ታሪክ በዘፍጥረት 4 ውስጥ ተገልጿል፡፡ የቃየል መሥዋዕት እና የአቤል መሥዋዕት በተቃርኖ የተገለፀበት ትክክለኛው መረጃ የሚገኘው ዘፍ 4:4 ነው (ዕብ 11:4)፡፡ የቃየል ድርጊቶች የሚገልጡት የሰውን ልጅ ውድቀት ተፅዕኖ ነው (ዘፍ 4:7፤ 6:5፣ 11-12፣ 13ለ)፡፡ በሁለቱም የአይሁድ እና የክርስትና ልማዶች (ዕብ 11:4፤ ይሁዳ 11) ቃየል ክፋትን የተሞላ አመፅ ምሣሌ ሆኖ ይገለጣል፡፡

▣ “ከክፉው እንደነበረ” ይህ ሰዋሰዋዊ አወቃቀር ነጠላ የወንድ ፆታ ገላጭ (ክፉው፣ ቁ.10) ወይም ግዑዝ ፆታ አመልካች (ከክፉ) ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ተመሣሣይ የሆነ ሰዋሰዋዊ አሻሚነት በማቴ 5:37፤ 6:13፤ 13:19፣ 38፤ ዮሐ 17:15፤ 2ሰ 3:3፤ 1ዮሐ 2:13፣ 14፤ 3:12፤ እና 5:18-19 ላይም የሚገኝ ነው፡፡ በበርካታ ሁኔዎች አውዱ በግልፅ የሚያሳየው ሰይጣንን ነው (ማቴ 5:37፤ 13:38፤ ዮሐንስ 17:15)፡፡

**NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 3÷13-22**
**[13]ወንድሞች ሆይ ዓለም ቢጠላችሁ አትደነቁ፡፡ [14]እኛ ወንድሞችን የምንወድ ስለሆንን ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ተሻገርን እናውቃለን፤ ወንድሙንመ የማይወድ በሞት ይኖራል፡፡ [15]ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነስሰ ገዳይ ነው፣ ነፍሰገዳይም የሆነ ሁሉ የዘላለም ሕይወት በእርሱ እንዳይኖር ታውቃላችሁ፡፡ 16 እርሱ ስለእኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶአልና፣ በዚህ ፍቅርን አውቀናል፣ እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል፡፡ 17 ነገር ግን የዚህ ግለም ገንዘብ ያለው፡፡ ወንድሙም የሚያስፈልገውን ሲያጣ አይቶ ያልራራለት ማንም ቢሆን፣ የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ እንዴት ይኖራል? 18 ልጆቼ ሆይ፣ በሥራ እና በአውነት እንጂ በቅልና በአንደበት አንዋደድ፡፡ 19ልባችንም በእኛ ላይ በሚፈርድበት ሁሉ ከአውነት እንደሆንን በዚህ እናውቃለን በፊቱም ልባችንን እናሳርፋለን፣ 20 እግዚአብሔር ከልባችን ይልቅ ታላቅ ነውና ሁሉንም ያውቃል፡፡ 21 ወዳጆች ሆይ ልባችንስ ባይፈርድብን በእግዚአብሔር ዘንድ ድፍረት አለን፣ 22 ትእዛዙንም የምንጠብቅና በፊቱ ደስ የሚያሰኘውን የመናደርግ ስለሆንን የምንለምነውን ሁሉ ከእርሱ እናገኛለን፡፡**

3:13 “አትደነቁ” ይህ የአሁን ጊዜ ትዕዛዛዊ ድርጊት ገላጭ ግሥ ከአሉታዊ ቦዝ አንቀፅ ጋር የተጣመረ ሲሆ ብዙውን ጊዜ ያለው ትርጉም በሂደት ላይ ያለን ድርጊት ማቆም ነው (1ጴጥ 4: 12-16)፡፡ የምንኖርበት ዓለም አድልኦ የነገሰበት እና እግዚአብሔርም እንዲሆን አስቀድሞ የፈለገው አልነበረም፡፡

▣ “ቢ ...” ይህ የመጀመሪያ ደመደብ ሁኔታዊ አረፍተነገር ሲሆን ከፀሐፊው አመለካከት ወይ ለሥነ-ፅሑፋዊ ዓላማው ሲባል እውነት ተደርጐ የሚወስድ ነው፡፡

▣ “ዓለም ቢጠላችሁ” ዓለም ኢየሱስን ጠልቶአል፤ ደግመም የእርሱን ተከታዮችም ይጠላል፡፡ ይህ በአዲስ ኪዳን የሚገኝ የተለመደ ጭብጥ ሲሆን (ዮሐ 15:18፤ 17: 14፤ ማቴ 5 5:10-11፤ 2ጢሞ 3:12) አንድ ሰው አማኝ ለመሆኑ ሌላው ማረጋገጫ ነው፡፡

3:14 “እናውቃለን” ይህ የአሁን ጊዜን የሚያመለክት ድርጊት ገላጭ ግሥ ነው (Oida የሚለው መፈፀምን የሚያመለክት መልክ ሲኖረው ነገር ግን የአሁን ጊዜ ትርጉም ያመለክታል)፡፡ ይህ ሌላው የተለመደው ጭብቅ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ልጆች በራስ መተማመን የሚገናኘው (1) ከአእምሮ መለወጥ ጋር (2) ከድርጊት መለወጥ ጋር ነው፡፡ እነዚህም በግሪኩ እና በእብራይስጡ “ንስሐ” የሚለው ቃል መሠረታዊ ትርጉሞች ናቸው፡፡

▣ “ከሞት ወደ ሕይወት እንደተሻገርን” ይህ ሌላው የተጠናቀቀ ድርጊት ገላጭ ግሥ አመልካች ነው (ዮሐ 5:24)፡፡ አንዱ ከሞት ወደ ሕይወት ለመሻገራችን ማስረጃ እርስበርሳችን መዋደዳችን ነው (በ6:37 ላይ የክርስቲያን ማረጋገጫ የሚለውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስ ይመልከቱ)፡፡ ሌላው ደግሞ አለም እኛን ይጠላናል፡፡

▣ “እኛ ወንድሞችን የምንወድ ስለሆንን” ይህ የአሁን ጊዜን የሚያመለክት ድርጊት ገላጭ አመልካች ግሥ ነው፡፡ ፍቅር የእግዚአብሔር ቤተሰብ ዋናው መለያው ነው (ዮሐ 13:34-35፤ 15:12፣ 17፤ 2ዮሐ 5፤ 1ቆሮ 13፤ ገላ 5:22) ምክንያቱም ፍቅር የእግዚአብሔርም ባህርይ ስለሆነ ነው (4:7-21)ፍቅር የሰውልጅ ከእግዚአብሔር ጋር ላለው ሕብረት መሠረቱ ሳይሆን የሕብረቱ ውጤት ነው፡፡ ፍቅር የድነት መሠረት አይደለም፣ ነገር ግን ሌላው የድነት ማረጋገጫ ነው፡፡

▣ “ወንድሙን የማይወድ በሞት ይኖራል” ይህ የአሁን ጊዜ ቦዝ አንቀፅ ሲሆን ከአሁን ጊዜ አመልካች ድርጊት ገላጭ ግሥ ጋር በመጣመር እንደ ባለቤት ተጠቅሷል፡፡ አማኞች በፍቅር እንደሚኖሩ ሁሉ የሚያምኑትም በጥላቻ መኖራቸውን ይቀጥላሉ፡፡ ጥላቻ ልክ እንደፍቅር ሁሉ የአንድ ሰው መንፈሳዊ መረዳት ማስረጃው ነው፡፡ የዮሐንስን ፍፁም የሆነ የዱዋሊስቲክ ምድቦችን አስታውስ፤ አንዱ በፍቅር ሲኖር ሌላው ደግሞ በሞት ውስጥ ይኖራል፤ እዚህ ላይ ምንም አይነት መካከለኛ ሥፍራ የለም፡፡

3:15 “ማንም” ዮሐንስ ይህንን ቃል ከ 2:29 ጀምሮ ለ8 ጊዜያት ተጠቅሞታል፡፡ የዚህም ጠቃሚነት ደግሞ ዮሐንስ ለሚናገረው ነገር ምንም ሌላ አማራጭ አለመኖሩን ያሳያል፡፡ ሁለት አይነት ሰዎች አሉ፡፡ የሚወዱ እና የሚጠሉ ዮሐንስም ሕይወትን የሚመለከተው በጥቁር እና ነጤ ወይም ፍፁም ተቃራኒ በሆኑ አቅጣጫዎች ነው፡፡

▣ **"ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ ነው"** ይህ የአሁን ጊዜ ድርጊት ገላጭ ቦዝ አንቀፅ ነው (ጠጣይነት ያለው፣ የታወቀ ጥላቻ)፡፡ ኃጢአት በመጀመሪያ በኃሳብ ይፈጠራል፡፡ በተራራው ስብከት ላይ ኢየሱስ እንዳስተማረው ጥላቻ ከነፍሰ ገዳይነት፤ እንዲሁም መጐምጀት ከዝሙት ጋር እኩል ነው (ማቴ 5:21-22)፡፡

▣ **"ነፍሰ ገዳይም የሆነ ሁሉ የዘላለም ሕይዋት በእርሱ እንዳይኖር ታውቃላችሁ"** ይህ አባባል ነፍሰ ገዳይ የሆነ ክርስቲያን መሆን አይችልም ማለት አይደለም፡፡ ኃጢአት ይቅር የሚባል ነው፤ ነገር ግን የሕይወት ዘይቤ ድርጊቶች ልብን ይገልጣሉ፡፡ ይህ አባባል የሚያሳየው በተለመደ ሁኔታ ሌላውን የሚጠላ ክርስቲያን ሊሆን እንደማይችል ነው፡፡ ፍቅር እና ጥላቻ ሁለቱም በፍፁም የሚቃረኑ ናቸው! ጥላቻ ሕይወትን ሲነጥቅ ፍቅር ደግሞ የራሱን ሕይዋት ይሰጣል፡፡

3:16 **"አውቀናል"** ይህ የተጠናቀቀ አመልካች ግሥ ነው፡፡ በቁጥር 15 ላይ የተጠቀሰው የግሪኩ ቃል Oida የሚለው ሲሆን በዚህ ግን giNosko የሚለው ተጠቅሷል፡፡ እነዚህም በዮሐንስ ፅሑፎች ውስጥ በተመሳሳይ ሁኔታ ተጠቅሰዋል፡፡

▣ **"ፍቅርን በዚህ"** ኢየሱስ ፍቅር ምን እንደሚመስል የመጨሻውን ምሣሌ አሳይቷል፡፡ አማኞች የእርሱን ፈለግ ሊከተሉ ይገባል (2ቆሮ 5: 14-15)፡፡

▣ **"እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶአልና"** ይህ የግሪኩ ጊዜ ገላጭ ግሥ ሲሆን የኢየሱስን ቃላት በመጠቀም የቀራኒዮን መስቀል ያመለክታል (ዮሐ 10:11፣ 15፣ 17፣ 18፤ 15:13)፡፡

▣ **"ይገባናል"** አማኞች የኢየሱስን ምሣሌነት ሊከተሉ ይገባል (2:6፤ 4:11)፡፡

▣ **"ስለወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ"** ምሣሌው ክርስቶስ ነው፡፡ እርሱ ነፍሱን ስለሌሎቹ እንደሰጠ ክርስቲያኖችም አስፈላጊ ከሆነ ነፍሳቸውን ለወንድሞቻቸው አሳልፈው ሊሰጡ ይገባል፡፡ ለራሥ ወዳድነት መሞት

1. የውድቀት (የሰው ልጅ) ተቃራኒው ነው
2. የእግዚአብሔር መልክ መታደስ ነው
3. ለጋራ ጥቅም መኖር ነው (2ቆሮ 5:14-15፤ 2:5-11፤ ገላትያ 2:20፤ 1ጴጥ 2:21)፡፡

3:17 **"ነገር ግን የዚህ ዓለም ገንዘብ ያለው፣ ወንድሙንም የሚያስፈልገውን"** እነዚህ በአሁን ጉዜ የግሱን ሁኔታ የሚገልጡ ናቸው፡፡ በቁጥር 16 ላይ ራስን አሳልፎ መስጠት አሁን በተግባር ወንድምን በመርዳት የሚገለጥበት ነው፡፡ እነዚህ ጥቅሶች በያዕቆብ ከተጠቀሱት ጋር ተመሣሣይነት አላቸው (ያዕ 2:15፣ 16) ፡፡

▣ **"ሲያጣ አይቶ ያልራራለት ማንም ቢሆን"** ይህ በግሪኩ የግሡን ሁኔታ የሚገልፅ አድራጊ ግሥ ነው፡፡ ቃሉ ቃል በቃል ሲተረጐም "መጨፈን" እንደማለት ነው፡፡ ይህም ስሜትን ለመግለፅ የሚውል የእብራይስጥ የአነጋገር ዘይቤ ነው፡፡ ከዚህም በላይ ድርጊቶቻችን አባታችን ማን መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው፡፡

▣ **"የእግዚአብሔር ፍቅር"** ይህ ደግሞ በታሳቢነት ወይም በባቤትነት የተገለፀ አነጋገር ወይም ሆን ተብሎ አሻሚ እንዲሆን የተደረገ ነው፡፡

1. ለእግዚአብሔር ያለ ፍቅር
2. እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ፍቅር
3. ሁለቱም

ቁጥር 3 ከዮሐንስ ፅሑፎች ጋር የሚስማማ ነው፡፡

3:18 **"በቃልና በአንደበት አንዋደድ"** ድርጊት ከቃላት ይልቅ በጉልና ይናገራሉ (ማቴ 7:24፤ ያዕ 1:22-25፤ 2:14-26)፡፡

▣ **"በሥራ እና በእውነት እንጂ "** "እውነት" የሚለው ቃል የሚገርም ነው፡፡ አንድ ሰው "ሥራ" ለሚለው ለምሳሌ "ተግባር" ሉጠብቅ ይችላል፡ ቃሉ ግልፃ (ኤን ጂ ቢ) ወይም እውነት (TEV) ፤ ልክ "መልዕክት" የሚለው ቃል በ1:5 እና 3:11 ላይ አስምህሮንና የሕይወት ዘይቤን ትኩረት እንደሚያደርግ "እውነት" የሚለውም ቃል እንዲሁ ነው፡፡ አንድ ሰው የሚሠራው ሥራ እና የተነሣበት መነሻ ሐሳብ የሰጪውን አዕምሮ ለማስደሰት ለታይታ ብቻ የሚደረግ ሳይሆን እግዚአብሔርን ከመውደድ የሚመነጭ መሆን አለበት፡፡

3:19 **"በዚህ እናውቃለን"** ይህ የሚያመለክተው ቀደም ሲል የተገለጠውን ከፍቅር የመነጨ ድርጊቶችን ነው፡፡ ይህ የወደፊቱን ጊዜ የሚያሳይ መሐከለኛ አመለካች ሲሆን እውነተኛ መለወጥን የሚያሳይ ማስረጃ ነው፡፡

▣ **"ከእውነት እንደሆንን"** የአማኞች በፍቅር የተሞላ የሕይወት ዘይቤ ሁት ነገሮችን ያሳያል፡፡ (1) እነርሱ ከእውነቱ ጋር መሆናቸውን እና (2) የእነርሱ ሕሊና ንፁህ መሆኑን ነው፡፡ በዮሐ 6:55 ላይ እውነት የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

3:19-20 እነዚህ ሁለት የግሪክ ጥቅሶች እንዴት መተርጐም እንዳለባቸው ብዙ ግራ የሚያጋባ ነገር አለ፡፡ አንደኛው ሊሆን የሚችለው አተረጓጐም ትኩረት የሚያደርገው በእግዚአብሔር ፍርድ ላይ ሲሆን ሌላው የሚያተኩረው የእግዚአብሔርን ምህረት ነው፡፡ ከአመዱ አንፃር ሁለተኛው አማራጭ ከሁሉ ጥልቅ ትክክል ይመስላል፡፡

3:20-21እነዚህ ሁለት ጥቅሶች ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ አረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡

3:20

| | |
|---|---|
| NASB | **"ልባችንም በእኛ ላይ በሚፈርድበት ነገር ሁሉ"** |
| NKJV | **"ልባችን በእኛ ላይ የሚፈርድብን ከሆነ"** |
| NRSV | **"ልባችን በእኛ ላይ ሲፈርድብን"** |
| TEV | **"ሕሊናችን የሚወቅሰን ከሆነ"** |
| NJB | **"የራሳችን ስሜት የሚፈርድብን እንኳ ቢሆን"** |

አማኞች በውስጣቸው የሚሰማቸውን ሐዘን እግዚአብሔር ለሕይወታቸው ካለው *መሥፈርት* አንፃር እንዳልኖሩት በልምምዶቻቸው ያውቁታል፡፡ ይህም እግዚአብሔር ለእነርሱ ያለው ፈቃዱ ነው (ሮሜ 7)፡፡ እነዚህ በውስጣቸው የሚሰሟቸው ሕመሞች ከመንፈስ ቅዱስ (ንስሐ እንዲገቡ) ወይም ከሰይጣን ሊሆኑ ይችላሉ (ጥፋትን የሚያስከትል ወይም መልካም ምሥክርነትን እንዲያጡ)፡፡ ተገቢ የሆነ እና ተገቢ ያልሆነ ጥፋተኝነት /በደለኝነት/ አለው፡፡ አማኞች ልዩነቱን የእግዚአብሐርን ቃል በንበብ/የእርሱን መልዕክተኞች በማድመጥ/ ያውቃሉ፡፡ ዮሐንስ በእግዝአብሔር ፍቅር መለኪያ እየኖሩ ነገር ግን አሁንም ከኃጢአት ጋር የሚታገሉ ክርስቲያኖችን ለማፅናናት እየሞከረ ነው /የኃጢአትን ድርጊት እና የኃጢአትን ይቅርታ/፡፡ በዮሐንስ 12:40 ላይ ልብ የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

▣ **"*ሁሉንም ያውቃል*"** እግዚአብሔር የተነሣንበትን እውነተኛ ሐሳብ ያውቃል (1ሳሙ 2:7፤ 16:7፤ 1ነገ 8:39፤ 1ዜና 28:9፤ 2ዜና 6:30፤ *መዝ* 7:9፣ 44:21፤ ምሳሌ 15:11፤ 20:27፤ 21:2፤ ኤር 11:20፤ 17:9-10፤ 20:12፤ ሉቃ 16:15፤ ሐዋ 1:24፤ 15:8፤ ሮሜ 8:26፣27)፡፡

3:21 **"ልባችንስ ባይፈርድብን"** ይህ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ አረፍተ ነገር ነው፡፡ ክርስቲያኖች አሁንም ከራሳቸው እና ከኃጢአት ጋር ይታገላሉ (2:1፤ 5:16-17)፡፡ አሁንም ቢሆን ፈተናዎችን የሚጋፈጡትና ምላሽ የሚሰጡት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ነው፡፡ ብዙ ጊዜም ሕሊናቸው ይወቅሳቸዋል፡፡ የሜቶዲስት ዝማሬ (ያልታወቀ ርዕስ ና ደራሲ) እንዲህ ይላል፡፡

*"ማንም ኦ.ጌታ ሆይ ሙሉ እረፍት የለውም፤*
*ማንም በሙላት ከኃጢአት ነፃ አልሆነም›*
*እነዚህ የሚደክው በሙላት ያገለግላሉ*
*የውስጣቸውንም ሕፀፅ ወዲያውም ይረዳሉ፡፡"*

የወንጌል እውቀት፣ ከኢየሱስ ጋር ያለ ጣፋጭ ሕብረት ለእግዚብሐር ሁሉን አዋቂነት እና ለመንፈስ ቅዱስ የተሰጠ ሕይወት ልባችንን ያሣርፉታል (መዝ 103:8-14)!

▣ **"በእግዚአብሔር ዘንድ ድፍረት አለን"** ይህ የሚናገረው በእግዚአብሔር ሁሉን አዋቂነት ፊት ያለን እድለ እና ነፃነት ነው፡፡ ይህ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የተደጋመ ቃል እና ሐሳብ ነው (2:28፤ 3:21፤ 4:17፤ 5:14፤ ዕብ 3:6፤ 10:35፤ በ2:28 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ)፡፡ ይህ ሐረግ ለአማኞች ያለውን ዋስትና በሚመለከት ሁለት ጥቅሞችን ያስተዋውቃል፡፡

1. አማኞች በእግዚአብሔር ፊት ሙሉ ድፍረት እንዳላቸው
2. የሚለምኑትን ሁሉ ከእርሱ እንደሚያገኙ

3:22 **" *የምንለምነውን ሁሉ ከእርሱ እናገኛለን*"** ይህ የአሁን ጊዜ ግሥ አመልካች እና የአሁን ጊዜ አመልካች አድራጊ ግሥ ነው፡፡ ይህም በማቴ 7:7፤ 18: 19 ዮሐንስ 9:31፤ 14:13-14፤ 15:17፣16፤ 16:23/ ማር 11:24፤ ሉቃስ 11:9-10 ላይ ያለውን የኢየሱስን ንግግሮች የሚንፀባርቅ ነው፡፡ እነዚህ የቃሉ ተስፋዎች አማኙ በፀሎት ብለው ልምምድ በጣም የሚለዩ ናቸው፡፡ ይህ ጥቅስ ያልተወሰነን (ያልተገደበን) የፀሎት ምላሽ በሚመለከት ተስፋን የሚሰጥ ይመስላል፡፡ ይህ ሥነ-መለኮታዊ ሚዛንን ለመጠበቅ እንዲያስችል ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን ጥቅሶች ለማነፃፀር የሚረዳ ነው፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ ፀሎት፤ ያልተገደበ ነገር ግን የተገደበ**

*ሀ. ወንጌላት*

1. አማኞች ተግተው እንዲፀልዩ እና እግዚአብሐርም ‹‹መልካም ነገሮችን›› (ማቴዎስ) ወይም ‹‹መንፈሱን›› እንደሚሰጣቸው (ሉቃ) ማቴ 7:7-11፤ ሉቃ 11:5-13፡፡
2. በቤተክርስቲያን ውስጥ የእርምት እርምጃ ከመውሰድ አንፃር አማኞች (ሁለት) በፀሎት አንድ ይሆኑ ዘንድ ተጠቅሷል (ማቴ 18:19)
3. በአይሁድ እምነት የፍርድ አሰጣጥ አውድ አማኞች ሳይጠራጠሩ እንዲለምኑ ተገልጿል (ማቴ 21:22፤

ማር 11:23-24)።

4. በሁለት ምሣሌዎች አውድ (ቁ. 1-8 አመፀኛው ዳኛ እና ቁ. 9-11 ፈሪሳዊው እና ቀራጩ) አማኞች ከአህዛብ ፈራጆች እና ራሳቸውን ከሚያፀድቁ ፈሪሳዊያን በተለየ ሁኔታ ማድረግ ወይም ፅድቅን መግለጥ እንደሚገባቸው ተጠቅሷል። እግዚብሔር የሚሰማው በትህትናና በንስሐ የሚቀርቡትን ነው (ሉቃ 18:1-14)።

ለ. የዮሐንስ ፅሑፎች

1. ኢየሱስ በፈወሰው አይነ ሥውር አውድ አንፃር የፈሪሳዊያን መንፈሳዊ እውርነት ተገልጧል። የኢየሱስ ፀሎት የተመለሰው እግዚአብሔርን ስለሚያውቅ እና እንደ ፈቃዱም ስለሚኖር ነው (ዮሐንስ 9:31)።
2. የዮሐንስ የላይኛው ደርብ ንግግር (ዮሐንስ 13-17)
   ሀ. 14:12-14 እምነትን የተሞላ ፀሎት ባህሪይ
      1. ከአማኞች የሚመጣ ነው
      2. በኢየሱስ ስም መጠየቅ
      3. አብ እንዲከበር መሻት
      4. ትዕዛዙን መጠበቅ (ቁ. 15)

   ለ. 15:7-10 የአማኞች ፀሎት የሚታወቅበት መለያ
      1. በኢየሱስ መኖር
      2. ቃሉ በእነርሱ ውስጥ መኖሩ
      3. አብ እንዲከብርበት መሻት
      4. ትዕዛዛቱንም መጠበቅ (ቁ. 10)
   ሐ. 1515-17 የአማኞች ፀሎት የሚታወቅበት መለያ
      1. መመረጣቸው
      2. ፍሬን ማፍራታቸው
      3. በኢየሱስ ስም መጠየቅ
      4. እርስ በእርስ በመዋደድ ትዕዛዙን መፈፀም
   መ. 16:23-24 የአማኞች ፀሎት መታወቂያ
      1. በኢየሱስ ስመ መጠየቅ
      2. ደስታ ሙሉ ይሆን ዘንድ መሻት
3. የመጀመሪያው የዮሐንስ መልዕክት (1ኛ ዮሐንስ)
   ሀ. 3:22-24 የአማኞች ፀሎት የሚታቅበት
      1. ትዕዛዛቱን መጠበቅ (ቁ. 22፤ 24)
      2. በተገቢው መኖር (በአግባብ መኖር)
      3. በኢየሱስ ማመን
      4. እርስ በርስ መዋድድ
      5. በእርሱ መኖር እና እርሱም በእኛ መኖሩ
      6. የመንፈሱ ሥጦታ መኖር
   ለ. 514-16 የአማኞች ፀሎት የሚታወቅበት
      1. በእግዚአብሔር ዘንድ ባለ ድፍረት
      2. እንደ ፈቃድ መፀለይ
      3. አማኞች አንዱ ለሌላው በመፀለይ
   ሐ. ያዕቆብ
      1. 1:5-7 አማኞች በተያዩ ፈተናዎች ውስጥ ሲያልፉ ሳይጠራጠሩ ጥበብን እንዲለምኑ
      2. 4:2-3 አማኞች በቅን ልብ መጠየቅ አለባቸው
      3. 5:13-18 የጤና ችግር የሚያጋጥማቸው አማኞች የሚበረታቱት
         ሀ. ሽማግሌዎች እንዲፈልዩላቸው መጠየቅ
         ለ. በእምነት መፀለይ እንደሚያድን
         ሐ. ኃጢአታቸው ይቅር እንዲባል መፀለይ
         መ. ኃጢአትን ለሌላው መናዘዝ እና አንዱ ለሌላው መፀለይ ሐ(ከ1ዮሐ 5:16 ጋር የሚመሳሰል)

ለውጤታማ ፀሎት ቁልፍ ጉዳይ ግን ክርስቶስን መምሰል ነው። ይህ ነው በኢየሱስ ስም መፀለይ የሚባለው ከሁሉም የከፋው እግዚአብሐር ለብዙዎች ክርስቲያኖች ምናልባት ሊያደርግላቸው የሚችለው ነገር በራስ ወዳድነት ለተሞላ ፀሎታቸው መልስ በመስጠት ነው! በአንድ በኩል ሁሉም ፀሎቶች ይመለሳሉ፡ በፀሎት ትልቅ ዋጋ ያለው ዋጋ አማኙ እግዚአብሔርን በመታመን በፊቱ የሚያሳልፈው ጊዜ ነው።

▣ **"ትእዛዙንም የምንጠብቅና በፊቱ ደስ የሚያሰኘውን የምናደርግ ስለሆንን"** በዚህ አውድ ውስጥ ፀሎት ምላሽ ያገኝ ዘንድ የሚያስፈልጉትን ሁለት መሥፈርቶችን ተመልከታቸው፡፡

1. መታዘዝ
2. እግዚብሔርን ደስ የሚያሰኘውን ማድረግ (ዮሐ 8:29)፡፡

1ዮሐንስ ስኬታማ ክርስቲያናዊ ሕይወትን እና አገግሎትን እንዴት ማድረግ እንዳለብን የሚያሳይ መፅሐፍ ነው፡፡

> NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 3÷23-24
> **[23]ትዛዚቱም ይህች ናት፣ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናምን ዘንድ ትእዛዙንም እንደሰጠን እርስ በርሳችን እንዋደድ ዘንድ፡፡ [24]ትእዛዙንም የሚጠብቅ በእርሱ ይኖራል እርሱም ይኖርበታል፤ በዚህም በእኛ እንዲኖር ከሰጠን ከመንፈሱ እናውቃለን፡፡**

**3:23 "ትእዛዚቱም ይህች ናት ... እናምን ዘንድ ... እንዋደድ ዘንድ"** "ትእዛዝ" የሚለውን ቃል ስንመለከተው ሁለት ሁኔታዎች ያሉት ነጠላ ቁጥር ነው፡፡ የመጀመሪያው ሁኔታ የግል እምነትን የሚመለከት ነው፤ "እናምን ዘንድ" የሚለው ግሥ የግሪኩን ድርጊት ገላጭ ግሥን ሁኔታን የሚያመለክት ነው (ዮሐንስ 6:29፣ 40)፡፡ ሁለተኛው ሁኔታ ደግሞ ግብረ ገባዊ ነው፡፡ ፤ "እንዋደድ ዘንድ" የሚለው ግሥ የአሁን ጊዜ ድርጊት ገላጭ ግሥን በሚያመለክት ሁኔታ የተገለጠ ነው (3:11፤ 4:7)፡፡ ወንጌል ሊታመን የሚገባ መልዕክት ልንቀበለው የሚገባ ሰው እንዲሁም ሊኖሩት የሚገባ የሕይወት ዘይቤ ነው!

▣ **"በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናምን ዘንድ"** "ማመን" የሚለው ሐሳብ መፅሐፍ ቅዱሳዊ እምነትን ለመረዳት ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ *amaN* የሚለው የብሉይ ኪዳን ቃል የሚያመለክተው "ታማኝነትን"፣ "መታመንን"፣ "መደገፍን" ወይም "ታማኝነትን" ነው (በ1ዮሐንስ 2:10 ላይ በብሉይ ኪዳን ቃል ላይ የተሰጠውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ)፡፡ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የግሪኩ ቃል (*pisteuo*) በሦስት የተለያዩ የእንግሊዘኛ ቃላት ተተርጉሟል፤ ማመን፣ እምነት፣ ወይም መታን (በ2:33 ላይ የግሪኩን ቃል በሚመለከት ተጨማሪ የጥናት ርዕሱን ይመልከቱ)፡፡ ቃሉ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ላይ ያለውን መታመን ብዙም አያመለክትም፡፡ ይህ የእግዚአብሔር ባህርይ፣ መገለጥ እና ተስፋ እንጂ የወደቀው የሰው ልጅ ታማኝነት ወይም መታን ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህ የተዋጀው፣ የወደቀው የሰው ለጅ ማንነት አይደለም፤ የማይናወጥ መሠረትን የሚያኖር የእግዚአብሔር ማንነት ውጤት እንጂ!

"በስሙ" ማመን ወይም "በስሙ" መፀለይ የሚለው ሐሳብ የሚያንፀባርቀው በቅርብ ምሥራቃዊያን ዘንድ ስሙ ግለሰቡን እንደሚያመለክተ ወይም እንደሚወክል ነው፡፡

1. ኢየሱስን ማቴ 1:21፣ 23፣ 25፤ 2:22፤ 10:22፤ 12:21፤ 18:5፣20፤ 19:29፤ 24:5፣9፤ ዮሐ 1:12፤ 2:23፤ 3:18፤ 14:23፤ 15:21፤ 17:6፤ 20:31፡፡
2. አብን ማቴ 6:9፤ 21:9፤ 23:29፤ ዮሐ 5:43፤ 10:25፤ 12:13፤ 17:12፡፡
3. ሥላሴን ማቴ 28:19

ይህንን ጥቅስ በሚመለከት አጠር ያለ ማብራሪያ ልስጥበት፡፡ *Word Pictures iN the New TestameNt* (ገጽ 288) በሚለው መፅሐፋቸው ላይ ኤ.ቲ.ሮቨርትሰን ሲፀልዩ "ማመን" የሚለው ግሥ በሚመለት የግሪኩ ምንጭ ያለውን ችግር ይገልፃሉ፡፡ "B"፣ "K" እና "L" የተባሉት የግሪክ ምንጮች ድርጊት ገላጭ ግሦች ሲኖራቸው "N"፣ "A" እና "C" የተባሉት የግሪክ ምንጮች ደግሞ የአሁን ጊዜ ድርጊት ገላጭ ግሦች አሏቸው፡፡ ስለዚህም ሁለቱም ከአውዱ እና ከዮሐንስ የአፃፃፍ ዘይቤ ጋር የሚስማሙ ናቸው፡፡

**3:24 "ትእዛዙንም የሚጠብቅ በእርሱ ይኖራል"** እነዚህ ሁለቱም የአሁን ጊዜ ገላጮች ናቸው፡፡ መታዘዝ ከመኖር ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ ፍቅር እኛ በእግዚብሔር፤ እግዚአብሔርም በእኛ ለመኖሩ ማረጋገጫ ነው (4:12፣ 15-16፤ ዮሐንስ 14:23፤ 15:10)፡፡ በ2:10 ላይ መኖር የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

▣ **"... ከሰጠን ከንፈሱ"** ዮሐንስ እውነተኛ አማኞችን ለመፈተሽ አንዳንድ ማረጋገጫዎችን ይጠቅሳል (ሮሜ 4:13፤ 8:14-16፤ ለ2:3-27 ሐ የተሰጡትን አውዳዊ ግንዛቤዎትን ይመልከቱ)፡፡ ሁለቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተገናኙ ናቸው፡፡

1. ስለ ኢየሱስ መናገር (መመስከር) (ሮሜ 10:9-13፤ 1ቆሮ 12:3)
2. ክርስቶስን የሚመስል ሕይወት (ዮሐንስ 15፣ ገላ5:22፤ ያዕቆብ 2:14-26)፡፡

### የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ሊሆን የሚችል ማብራሪያ እንደመሆኑ መጠን ለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ፡፡ እያንዳንዳችን ስንጓዝ የሚገባን ባለን መረዳት መጠን ነው፡፡ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጎም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣችሁ ናችሁ፡፡ ይህንንም ጉዳይ በሚያብራራው ሰው ላይ ልትተወው አይገባም፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተናነሱትን አቢይ ጉዳዮች እንድታጤናቸው ነው። ጥያቄዎቹ እንደ ሐሳቡ አነሳሽ ሆነው እንጅ በቀጥታ የቀረቡ አይደሉም።

1. ከ11-24 ያሉትን ጥቅሶች የሚያስተሳስራቸው ጭብጥ ምንድነው? (ዮሐ 2:7-11)
2. የቁጥር 16ን እና 17ን ግንኙነት አብራራ። ነፍሳችንን አሳልፈን መስጠት ወንድማችንን በሚያስፈልገው መርዳት እንዴት ይነፃፀራል?
3. ከ19-20 ያሉት ጥቅሶች በእግዚአብሔር ፍርድ ላይ የሚያተኩሩ ናቸው ወይስ የእግዚአብሔርን ምህረት?
4. ዮሐንስ በቁጥር 22 ላይ ስለፀሎት የተናገረውን ከዕለታዊ ሕይወታችን ጋር እንዴት እናዛምደዋለን?
5. ክርስቲያን ኃጢያቱን መቀበል እና መናዘዝ አለበት የሚለውንና ክርስቲያን ኃጢአት የሌለበት ነው። የሚለውን ዮሐንስ የማይታረቁ የሚመስሉ ሐሳቦችን የገለአት የሌለበት ነው የሚለውን ዮሐንስ የማይታረቁ የሚመስሉ ሐሳቦችን የገለፃቸውን እንዴት ማስታረቅ ይቻላል?
6. ዮሐንስ በአኗኗር ዘይቤ ላይ ከፍተኛ ትኩረት የሰጠበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል
7. "ዳግም መወለድ" በሚለው ሐሳብ ላይ ያሉትን ሥነ-መለኮታዊ እውነታዎችን ግለፅ?
8. ይህ ምንባብ ከዕለታዊ ሕይወታችን ጋር የሚዛመደው እንዴት ነው?

# 1ዮሐንስ ምዕራፍ 4

## በተሻሻሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀፅ አከፋፈል

| UBS[4] | NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| የእግዚአብሔር መንፈስ እና የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ | የእውነት መንፈስ እናየስህተት መንፈስ | እውነትን እና ስህተትን መመርመር | የእውነት መንፈስ እና የስህተት መንፈስ | ሦስተኛው ቅድመ ሁኔታ የክርስቶስ ተቃሚንና ዓለም መመርመር |
| | 3:24-4:6 | | | |
| 4:1-6 | | 4:1-6 | 4:1-3 | 4:1-6 |
| | | | 4:4-6 | የፍቅር እና የእምነት ምንጭ |
| | | | | (4:7-5:13) |
| እግዚአብሔር ፍቅር ነው | እግዚአብሔርን በፍቅር ማወቅ | የተባረከ ፍቅር | እግዚአብሔር ፍቅር ነው | የፍቅር ምንጭ |
| 4:7-12 | 4:7-11 | 4:7-12 | 4:7-10 | 4:7-5:4 |
| | እግዚአብሔርን በፍቅር ማየት | | 4:11-12 | |
| | 4:12-16 | | | |
| 4:13-16ሀ | | 4:13-16ሀ | 4:13-16ሀ | |
| 4:16ለ-21 | ፍፁሙ ፍቅር | 4:16ለ-21 | 4:16ለ-18 | |
| | 4:17-19 | | | |
| | በእምነት መታዘዝ | | 4:19-21 | |
| | 4:20-5:5 | | | |

**ሦስተኛ የመንባብ ዑደት (አንቀፅ 5ን ይመልከቱ)**
*የመጀመሪውን ፀሐፊ ዋና ሐሳብ በአንቀፅ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ማብራሪያ ስለሆነ ለምትከተለው የመጽሐፍቅዱ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ፡፡ እያንዳንዳችን ልንጓዝ የሚገባ ባለን መረዳት መጠን ነው፡፡ አንተ መጽሐፍቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጎም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ናቸው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ቅፅበት አንበበው፤ ዋና ዋና ሐሳቦንም ለያቸው፡፡ ራስህን ዋና ሐሳቦች አከፋፈል ከአምስቱ የተሻሻሉ ትርጉሞች ጋር አነፃፅራቸው ምንም እንኳን በአንቀፅ መከፋፈል በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት የሚካሄድ ባይሆንም የአተረጓጎም መሠረት የሆነውን የመጀመሪያው ፀሐፊ ዋና ሐሳብ ለመከተል ግን ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ እያንዳንዱም አንቀፅ የሚያወሳው ስለ አንድ ጉዳይ ብቻ ነው፡፡

1. *የመጀመሪያ አንቀፅ*
2. *ሁለተኛ አንቀፅ*
3. *ሦስተኛአንቀፅ*

4. ወ.ዘ.ተ

**አውዳዊ ግንዛቤዎች፤ 4:1-21**

*ሀ. ዮሐንስ 4 ለየት ያለ ሥነ-ፅሑፋዊ ክፍል ሲሆን የሚነገረውም ክርስቲያኖች ስለ እግዚአብሔር የሚናገሩትን እንዴት መርምረው ማረጋገጥ እንደሚችሉ የሚገልፅ ነው። ይህም ምንባብ የሚዛመደው*

1. *የክርስቶ ተቃወሚዎች ተብለው ከሚጠሩት የሐሰት ነቢያት ጋር* (2:18-25)
2. *ለማታለል ከሚሞክሩት ጋር* (2:26፤3:7)
3. *ምናልባትም ለየት ያለ መንፈሳዊ እውነት አለን ከሚሉ ጋር* (3:24)

*የቀደሙትን ክርስትያኖች ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ለመረዳት እንዲችለው እንደሰው መገንዘብ ያለበት ነገር ቢኖር ብዙዎ ስለእግዚአብሔር አብዝተው ይናገሩና እናውቀዋለን ይሉ እንደነበር ነው*(1ቆሮ 12:10፤14:29፤ 1ተሰ 5:20-21፤ 1ዮሐ 4:1-6)። *በጊዜውም አዲስ ኪዳን በራሱ ተሟልቶ የሚገኝም አልነበረም። በመሆኑም በመንፈስ የሚደረግ ምርመራ*(*መመርመር*) *የአስተምህሮ እና የማህበራዊ መመዘኛዎችን የሚያካትት ነበር*(*ያዕቆብ* 3:1-12)።

*ለ. ተደጋግመው ከሚነሱ ጭብጦች የተነሣ 1ኛ ዮሐንስ በቅደም ተከተል ለመዘርዘር በጣም የሚያስቸግር ነው፤ ይህ በምዕራፍ 4 ላይ በእውነት በግልፅ የሚታወቅ ነገር ነው። ይህ ምዕራፍ በተለይም አማኞች እርስ በራሳቸው አጥብቀው ሊዋደዱ* (ቁ 7-21፤2:7-12 *እ* 3:11-24) *በሚገባቸው ጉዳይ ላይ ቀደም ሲል ደጋግሞ ባነሳቸው እና ትኩረት በሰጠባቸው ምዕራፎች ላይ ያተኮረ ይመስላል።*

*ሐ. ዮሐንስ የሚፅፈው የስህተት መምህራንን ለመቃወም እና እውነተኛ አማኞችን ለማደፍረስ ነው። ይህንንም የሚያደርገው በርካታ መመዘኛዎችን በመጠቀም ነበር።*

1. *የአስተምሮ መመዘኛ* (*በኢየሱስ ማመን*፤ 1ዮሐ 2:18-25፤4:16፡14-16፤5:1፡5፡10)
2. *የሕይወት ዘይቤ መመዘኛ* (*መታዘዝ*፤ 1ዮሐ 2:3-7፤3:1-10፡22-24)
3. *ማህበራዊ መመዘኛ* (*ፍቅር* 1ዮሐ 2:7-11፤3:11-18፤4:7-12፡16-21፤5:1-2)።

*የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ከተለያዩ የስህተት አስተማሪዎች ጋር የሚዛመዱ ናቸው። 1ኛ ዮሐንስ የሚመለከተው* (*የሚናገረው*) *ስለ ግኖስቲክ የሐሰት አስተማሪዎች ነው። በ1ኛ ዮሐንስ መግቢያ ላይ ትፋቂ የሚለውን ይመልከቱ። ሌሎች የአዲስ ኪዳን ክፍሎችም ሌሎች ትፋቂዎች ላይ ይናገራሉ* (*ዮሐ*1:13፤*ሮሜ* 10:9-13፤ 1*ቆሮ* 12:3)። *በመሆኑም እያንዳንዱ አውድ ለየትኛው ኑፋቄ ምላሽ እንደተሰጠበት ተለይቶ ሊጠና ይገባዋል። ከበርከታ ምንጮች ሥህተቶች ነበሩ፤*

1. *ከአይሁድ ወግ አጥባቂዎች*
2. *ከግሪክ ፊላሳፎች*
3. *የተለየ መንፈሳዊ መገለጥ ወይም ልምምዶች አሉን ከሚሉት*

## የቃል እና የሐረግ ጥናት

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 4:1-6

**[1]ወዳጆች ሆይ÷ መንፈስን ሁሉ አትመኑ÷ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደ ሆነ ምርምሩ፤ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና። [2]የእግዚአብሔርን መንፈስ በዚህ ታውቃላችሁ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ የሚታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው። [3]ኢየሱስ ክደርስቶስም በሥጋ እንደመጣ ማይታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም፤ ይህም የክርስቶስ ተቃዋሚው መንፈስ ነው፤ ይህም እንዲመጣ ሰምታችኋል አሁንም እንኳ በዓለም አለ። [4]ልጆች ሆይ÷ እናንተ ከእግዚአብሔር ናችሁ። አሸንፋችኋቸውማል÷ በዓለም ብለው ይልቅ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና። [5]እነርሱ ከዓለም ናቸው፤ ስለዚህ ከዓለም የሆነውን ይናገራሉ ዓለሙም ይሰማቸዋል። [6]እና ከእግዚአብሔር ነን፤ እግዚአብሔርን የሚያውቅ ይሰማናል፤ ከእግዚአብሔር ያልሆነ አይሰማንም። የእውነትን መንፈስ እና የስህተትን መንፈስ በዚህ እናውቃለን።**

4:1 "*አትመኑ*" *ይህ የአሁን ጊዜ ትዕዛዛዊ ቃል ከአሉታዊ ቦዝ አንቀፅ ጋር የተጣመረ ሲሆን በዙውን ጊዜ ያለው ትርጉም በሂደት ላይ ያለን ድርጊት ማቆም የሚል ነው። ሊሆን የሚገባው የክርስትያኖች ዝንባሌም ጠንካራ ዮሆነ ስብዕናን ተቀባይነት ያላቸውን ክርክሮች ወይም ተአምርታዊ ክስተቶች ከእግዚአብሔር እንደሆኑ መቀበል ነው። የሐሰት አስተማሪዎች* (1) *ስለ እግዚአብሔር እንደሚናገር* (2) *ከእግዚአብሔር ልዩ መገለጥ እንዳለቸው ትኩረት ያደርጋል።*

**ልዩ ርዕስ፡ ክርስትያኖች አንዱ በሌላው ላይ ሊፈርዱ ይገባል?**

*ይህ ጉዳይ መታየት ያለበት በሁለት መንገዶ ነው፡፡*

1. *አማኞች አንዱ በሌላው ላይ እንዳፈርዱ ታዘዋል* (*ማቴ*7፥1-5፤*ሉቃ* 6፥37፣ 42፤*ሮሜ*2፥1-11፤ *ያዕ* 4፥11-12)፡፡
2. *አማኞች መንፈሳዊ መሪዎችን መመዘን እንደሚኖርባቸው ታዘዋል* (*ማቴ* 7፥6፡15-16፤ 1*ቆሮ* 14፥29፤ 1*ተሰ* 5፥21፤ 1*ጢሞ* 3፥1-3፤ *እና ዮሐ* 4፥1-6)

*አግባብ የሆነ መመዘኛዎችን ለማድረግ ጥቂት መስፈርቶችን ማየት ጠቃሚ ነው፡፡*

1. *ምዘና ሊሆን የሚገባው ለመለየት ዓላማ ነው* (1*ዮሐ* 4፥1 *ለመለየት ‹‹ምርምር›› ይላል*)
2. *ምዘና ሊሆን የሚገባው በትህትናና በጭምትነት ነው* (*ገላ* 6፥1)
3. *ምዘና ከግል ጉዳይ አንፃር ሊሆን አይገባም* (*ሮሜ* 14፥1-23፤ 1*ቆሮ* 8፥1-13፤10፥23-33)
4. *ምዘና ‹‹ነቀፌታ የሌለባቸውን›› ሰዎች ከቤተክርስትያን ወይም ከህብረተሰቡ መለየት የሚያስችል መሆን አለበት*(1*ጢሞ* 3)፡፡

▣ ***"መንፈስን ሁሉ"*** *መንፈስ የተጠቀሰው ከሰው ስብእና አንፃር ነው፡፡ በ*4፡ 6 *ላይ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ፡፡ ይህም ከእግዚአብሔር የታሰበውን መልዕክት የሚያመለክት ነው፡፡ ኑፋቂ የሚመጣው ከቤተክሮስትያን ውስጥ ነው* (2፡19) *የስህተት መምራን ለእግዚአብሔር ቀንተው እንደሚናገሩ ያስረግጣሉ፡፡ ዮሐንስ ከሰው ንግግር እና ድርጊት በስተጀርባ ሁለት አይነት መንፈሳዊ ምንጮች እንዳሉ ያስረዳል፡- እግዚአብሔር ወይም ሰይጣን፡፡*

▣ ***"ነገር ግን መናፍስትን መርምሩ"*** *ይህ በአሁን ጊዜ የተለገፀ ትዕዛዛዊ ቃል ነው፡፡ ይህ ልክ እንደ ፀሎት፣ ወንጌል መስበክ እና መስጠት ሁሉ ለሁሉም አማኝ መንፈሳዊ ሥጦታም* (1*ቆሮ* 1210፤1429) *እንዲሁም ደግሞ ወሣኝ የሆነ ጉዳይ ነው፡፡ በግሪከ dokimazo ለሚለው ቃል "ለይቶ ለማወቅ" የሚል ድባብ አለው፡፡ አማኞች ሁል ጊዜ ከሁሉም የከፋው አስካልተረጋገጠ ድረስ ስለሌሎች ከሁሉ የተሸለውን ሊያስቡ ይገባል* (1*ቆሮ* 1347፤1*ተስ* 520-21)

**ልዩ ርዕስ፡ መወርወር ለሚለው የተሠቱ የግሪክ መጠሪያዎች እና የእነርሱ እንደምታዎች**

*አንድ ሰው ለአንድ ዓላማ መመርመር በሚል ሐሳብ ላይ የሚጠቀሱ ሁለት የግሪክ ቃላት አሉ፤*

1. *ይኪማዘ፣ ይኪሚዮን፣ ይኪማሲያ*

   *ይህ ቃል የብረት አቅላጭ (ሠሪ) ቃል ሲሆን ትርጉም የአንድን ነገር እውነተኝነት ማረጋገጥ የሚል ነው፤ በተምሣሌት አንድ ሰው ማለት ነው)፤ ይህም በእሳት የሚፈተን ነው፡፡ እሳቱም እውነተኛውን ብረት ሲገልጠው በአንፃሩም ደግሞ ቆሻሻውን በማቃጠል ያመግረዋል (ያጠራዋል)፡፡ ይህም የሚታይ ሒደት ለእግዚአብሔር፣ ለሰይጣን ለሰው ጠንካራ ዘይቤያዊ አነጋገር የሆነ ነው፡፡ ቃሉ አንድ ነገር ተቀባይነትን ያገኝ ዘንድ በአዎንታዊ መልኩ የሚጠቀስ ነው፡፡ በአዲስ ኪዳንም መመርመር ተጠቅሶ እናገኘዋለን፡፡*

   *ሀ. በሬዎችን ለመፈተን፡- ሉቃ* 1419
   *ለ. ራሳችንን ለመፈተን፡-* 1*ቆሮ* 1128
   *ሐ. እምነታችንን ለመፈተን ያዕ* 13
   *መ. እግዚአብሔርን እንኳን ለመፈተን፡- ዕብ* 3፥9

   *የእነዚህ ምርመሪዎች (ፈተናዎች) ውጤቶች በአዎንታዊ መልኩ የሚታይ ናቸው* (*ሮሜ*1፥28፤14፥22፤16፤2*ቆሮ*፥10፡18፤13፥3፤ *ፊል* 2፥27፤ 1*ጴጥ* 1፥7)፤ *በመሆኑም ቃሉ የሚያስተላልፈው መልዕክት አንድ ሰው ሲመዘን ወይም ሲረጋገጥ የሚለውን ሃሳብ ነው፡፡*

   *ሀ. ዋና ያለው ይሆን ዘንድ*
   *ለ. መልካም ይሆን ዘንድ*
   *ሐ. እውነት ይሆን ዘንድ*
   *መ. ጠቃሚ ይሆ ዘንድ*
   *ሠ. የከበረ ይሆን ዘንድ*

2. *ፔራዞ፣ ፔራስመስ*

   *ይህ ቃል ብዙውን ጊዜ ሥህተትን ለመፈለግ ወይም አንድ ነገር ተቀባይነትን እንዳያገኝ ለማድረግ የሚደረግ ፈተና የሚል ሃሳብን የያዘ ነው፡፡ ቃሉ ብዙውን ጊዜ ኢየሱስ በምድር በዳ መፈተኑን ለማሣየት ይጠቀላል፡፡*

   *ሀ. ኢየሱስን ለማጥመድ የሚደረገውን ጥረት ያሣያል* (*ማቴ* 4 ፥ 1 ፤ 16 ፥ 1 ፤19፥3፥22፥18፥35፤*ማር* 1፥13፤ *ሉቃ* 4፥38፤ *ዕብ*2፥18)፡፡
   *ለ. ይህ ቃል (ፔራዘን) ለሰይጣን እንደተሰጠ ማዕረግ ተጠቅሷል፤ ማቴ* 4፥3፤ 1*ተስ* 3፥5)፡፡
   *ሐ. እግዚአብሔርን እንዳንፈታተን በሚል ሐሳብ በኢየሱስ ተጠቅሷል* (*ማቴ* 14፥17፤*ሉቃ* 4፥12) *ወይም ክርስቶስን እንዳንፈታተን* (1*ቆሮ*10፥9)፡፡ *ከዚህም ባሻገር ቃሉ ጥረት ተደርጎ ያልተሣካ ነገርን ያመለክታል* (*ሐዋ* 9፥20፤ *ይጠቀሣል* (1*ቆሮ* 7፥5፤10፥9፡13፤ *ገላ* 6፥1፤1 *ተስ* 3፥5፤ *ዕብ*2፥18፤ *ያዕ*1፥2፡13፡14፤ 1*ጴጥ*4፥12፤ 2*ጴጥ* 2፥9)፡፡ *እግዚአብሔደር ሦስቱ የሰው ልጅ ጠላቶች (ማለትም አለም፣ ሥጋ እና ሰይጣን) በተወሰነ ጊዜ እና ቦታ እንዲገለጡ ይፈቅዳል፡፡*

▣ **"ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና"** ይህ የተጠናቀቀ ድርጊት ገላጭ አመልካች ግሥ ነው (ኤር 14: 14፣ 23: 21፣ 29: 8፣ ማቴ 7:15፣24:11:24፣ ሐዋ 20:28-30፣ 2ጴጥ 2:1፣ 1ዮሐ 2:18-19፡24፣37፣2ዮ 7)። ይህ በተዘዋዋሪ የሚመለክተው ቤተክርስትንን ለቀው መውጣታቸውን (የቤት ውስጥ ቤተክርስትያናት) ነገር ግን አሁንም ስለእግዚአብሔር እንደሚናገሩ ነው።

4:2 **"የግዚአብሔርን መንፈስ በዚህ ታውቃላችሁ"** ሰዋሰዋዊ ገፅታው በአሁን ጊዜ የተገለጠ ድርጊት ገላጭ አመልካች ግሥ ነው (ንግግር) ወይም በአሁን ጊዜ በአድራጊ ግሥ የተገለጠ ትዕዛዝ ነው (ትዕዛዝ)። እንደዚሁም ደግሞ በ2:27 ላይ "መኖር" የሚለው እና በ2:29 ላይ "ማወቅ" በሚለው የግሡ አይነት ላይ አሻሚ ነገር አለ። መንፈስ ቅዱስ ሁልጊዜ የሚያጎላው ኢየሱስን ነው (ዮሐ 14:26:15:26:16:13-15)። ይህ ተመሳሳይ የሆነ መመዘኛ በ1ቆሮ 12፣3 ላይ በሚገኘው የጳውሎ ፅሑፍ ውስጥ ሊታይ የሚችል ነው።

▣ **"የሚታመን መንፈስ ሁሉ"** ይህ የአሁን ጊዜን የሚያሳይ ድርጊት ገላጭ አመልካች ግሥ ነው። ይህም የሚያመለክተው ቀጣይነት ያለውን እውነትን የመግለፅ ሁኔታ እንጂ የቀደመውን እምነት ማፅናት አይደለም። "የሚታመን" የሚለው ቃል "ተመሳሳይ" እና "መነገር" ከሚሉት ቃላት የመጣ ጥምር ቃል ሲሆን ትርጓሜውም "ተመሳሳይ ነገርን መነገር" የሚል ነው። ይህ በ1ኛ ዮሐንስ ውስጥ ተደጋግሞ የሚታይ ጭብጥ ነው(1 ዮሐንስ 1:9፣ 2: 23፣ 4: 2-3፣ 4:15፣ ዮሐንስ9:22፣ 2ዮሐንስ7 7)። ይህም የተዘዋዋሪ የሚገልፀው ውስን፣ በሰዎ ራት የሆነ እና በድምፅ የሚገለጥን አንድ ሰው የኢሱስ ክርስቶስን ወንጌል መቀበሉን እና ለዚህም መስጠቱን በተዘዋዋሪ የሚያመለክት ነው። በዮሐንስ 9:22 ላይ ያለውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስን ይመልከቱ።

▣ **"ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ.. ከእግዚአብሔር ነው"**ይህ የተጠነቀቀን ድርጊት የሚገልጥ በዝ አንቀፅ ነው። ይህ ዮሐንስ በመፅሐፉ ለሚቃወመው የሥህተት መምህራን (ግኖስቲኮች) በጣም አስፈላጊ የሆነ የአስተምህሮ መመዘኛ ነው። የዚህም መሠረታዊ አቋም ኢየሱስ ፍፁም ሰው (በሥጋ የመጣ፣ ይህምግኖስቲኮች የማይቀበሉት ነው) እንዲህም ደግሞ ፍፁም አምላክ መሆኑን (1:1-4፣ 2ዮሐንስ7፣ ዮሐንስ1:14፣ 1ጢሞ 3:16)ማለየት ነው። ድርጊቱ መጠናቀቁን የሚያሳየው የጊዜ አመልካች የሚያረጋግጠው የኢየሱስ ስብዕና ጊዜያዊ ሳይሆን ቋሚ መሆኑን ነው። ይህ ያነሰ ግምት የሚሰጠው አልነበረም። ኢየሱስ በእውነት በሰውነት አንድ ነው እንዲሁም ደግሞ በመለኮትም አንድ ነው።

4:3 **"ኢየሱስ ክርስቶስም በሥጋ እንደመጣ የማይታመን መንፈስ ሁሉ"** የአዲስ ኪዳኑ የቀድሞ የላቲን ትርጉም እና የቀደመውን ፀሐፊዎች እንደ ክሌመንት፣ የአሌክሳደሪያም አሪገን፣ ኢራኒየስ እና ተርቱልያን Levi የመፍታትን በሚል ሐሳብ መግለፃቸው የሚያስደስት ሲሆን ይህም በአንፃሩ በተዘዋዋሪ የሚያመለክተው ኢየሱስን የሰው መንፈስ እና የተለየ የመለኮት መንፈስ ብሎ የመክፈል አንደምታ ያው ሲሆን ይህም የሁለተኛው ክፍለዘመን የግኖስቲክ ፅሑፎች መለያ ባህሪይ ነበር። ነገር ግን ይህ የጥቅስ መጨመር በመሆኑ የሚያንፀባርቀውም የቀደመችውን ቤተክርስትን ሕይወት እና ከግኖስቲክ የኑፋቄ አስተምህሮ ጋር የተደረገውን የምትሽረት ትግል ነው *(The Orthodox corruptioN of scripture(ገጽ* 125-135) የሚለውን በባርት ኤርሃሮት የተፃፈውን ይመልከቱ)።

▣ **"የክርስቶስ ተቃዋሚው መንፈስ"** እዚህ ላይ ቃሉ (2:18-25) የተጠቀሰው ክርቶስን ለመቃወም እጂ እርሱ ያለውን ሥፍራ ለመለወጥ አይደለም።

▣ **"ይህም እንዲመጣ ሰምታችኋል፣ አሁንም እንኳን በዓለም አለ"** ይህ የተጠናቀቀ ድርጊትን አመልካች ግሥ ሲሆን በተዘዋዋሪ የሚጠቅሰው ዮሐንስ ቀደም ሲል ይህን ጉዳይ ማንሳቱን እና ተያያዥነቱም ቀጣይ መሆኑን ነው። በግሪክ ቋንቋ "ἡ" የሚለው ተውላጠ ስም "መንፈስ" ከሚለው ግዑዝ አመልካች ጋር የሚገጥም ነው። ልክ እንደ 2:18 ይህ ሐረግ የሚያንፀባርቀው የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ አሁን መጥቷል ደግሞም ይመጣል የሚለውን ነው። እነዚህ የግኖስቲክ የሐሰት መምህራን በተዘፍጥረት 3 ላይ ከተጠቀሰው ክፍት እስከተገለጠበት እና ደግሞም በመጨረሻም ዘመን የክርስቶስ ተቃዋሚ ሆኖ እስከሚገለጥ ድረስ (2ተሰለንቂ 2፣ ራዕይ 13) ተያያዝነት ያላቸውን የሐሰት መረጃን፣ የሐሰት የኑሮዘይቤን፣ በዘመናት ሁሉ የሐሰት አቋምን በማራመድ የሚታወቁ ናቸው።

3:4-6 **"እናንተ... እርሱ.... እኛ"** እነዚህ ሁሉም ተውሳጠ ስሞች ትኩረት የተሰጠባቸው ናቸው። በዚህም መልሶ የተሰጠባውን (ትኩረት የተደረገባቸውን) ሦስት ወገኖን ማየት እንችላለን።

1. እውነት አማኞችን (ዮሐንስ እና የመልዕክቱ ተቀባዮች)
2. የሐሰት አስተማሪዎች (የግስቲከ መምህራንና የእነዚህ ተከታዮች)
3. የዮሐንስ ሚስዮናዊ ወይም የሥነ-መለኮታዊ ቡድን (ወገን)

ተመሣሣይ የሆነ ሐሳብ በዕብራዊያን 6 እና 10 ውስጥ መመልከት ይቻላል።

4:4 **"አሸንፏቸውማል"** ይህ የድርጊት መጠናቀቅን የሚያመለክት ግሥ ነው። ይህም በአስተምህደሮ መመዘግብ እና በአሸናፊው የክርስትና ሕይወት ላይ የተሰጠ መግለጫ ይመስላል። ለእነርሱም ሆነ ለእኛ በጣም አስደናቂ የሆነ የማበረታቻ ቃል ያለው ነው!

ዮሐንስ ትኩረት የሰጠው ክርስትያን በኃጢአት እና በክፋት ላይ ያለውን የድል አድራጊነት ሕይወት ነው፡፡ እርሱም ይህንን ቃል (*Nikao)* በ1ኛ ዮሐንስ ውስጥ (2:13፡14፤4፤5:4፡5) 6 ጊዜ፣ በዮሐንስ ራዕይ11 ጊዜያት፣ በዮሐንስ ወንጌል (16:33) ደግሞ አንድ ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ የህ "ማሸነፍ" ለሚለው የተጠቀሰ ቃል በሉቃስ (11:22) አንድ ግዜ እና በጳውሎ መልዕክቶች ደግሞ ሁለት ጊዜ ተጠቅሷል (ሮሜ3:4፤12:21)፡፡

▣ ***"በዓለም ካለው ይልቅ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና"*** *ይህ መለኮት በሰው ውስጥ መኖሩን ትኩረት ለመስጠት የተደረገ* ነው፡፡ እዚህ ላይ የአብን መኖር ለማመለክት የተሰጠ መግለጫ ይመስላል (ዮሐንስ 14:23፤ 2ቆሮ 6:16)፡፡ አዲስ ኪዳንም ትኩረት የሚደርገው (1) የወልድን በውስጣችን መኖር (ማቴ 28:20፤ ቆላ 1:27) እና (2) የመንፈስ ቅዱስን በውስጣችን መኖር ነው (ሮሜ 8:9፤ 1ዮሐንስ 4:13)፡፡መንፈስ እና ወልድ ተጠምረው ይገለጣሉ (ሮሜ 8:9፤2ቆሮ 3:17፤ ገላ 4:6፤ ፊል 1:19፤ 1ጴጥ 1:11)፡፡ በዮሐንስ 14:15 ላይ ያለውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስ ይመልከቱ፡፡

"በዓለም ካለው" የሚለው ሐረግ የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ሰይጣንን (ዮሐንስ 12:31፤ 14:30፤ 16:11፤ 2ቆሮ 4:4፤ ኤፌ2:2፤ 1ዮሐንስ 5:19) እና የእርሱን ተከታዮች ነው፡፡ በ1ኛ ዮሐንስ ያለው "ዓለም" የሚለው ቃል ሁል ጊዜ አሉታዊ አንደምታ አለው (ከእግዚአብሔር ተለይቶ የተደራጀና የሚሰሩ የሰዎች ማህበረሰብ፤ በዮሐንስ 14:17 ላይ ያለውን *kasmos* የሚለውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስ ይመልከቱ)፡፡

**4:5 "እነርሱ ከዓለም ናቸው"** ይህ በግልፅ የሚታይ ምንጭ ነው፡፡ በዚህ ሥፍራ የተጠቀሰው "ዓለም" የሚለው ቃል የወደቀው የሰው ዘር ከእግዚአብሔር ተለይቶ የሚፈልገውን ሁሉ ለማሟላት ጥረት የሚያደርግን የሰው ዘር በሚያመለክት ሁኔታ ነው(ዘፍ 2:15-17)፡፡ ይህም በጠቅላላው የሚያመለክተው የወደቀውን የሰው ዘርን በሙሉ የትምክህተኝነት መንፈስ ነው! ለዚህም ምሣሌ የሚሆነው ቃየል ነው(3:12)፡፡ ሌሎች ምሣሌዎች ደግሞ (1) ኤልያስ እና የበአል ነቢያት (1ነገሥት 18) እና (2) ኤርምያስ እና ሐናን (ኤርምያስ 28)፡፡

▣ ***"ዓለሙም ይሰማቸዋል"*** *ሌላው የክርስትያን መምህራንና የስህተት መምህራን ማስረጃ ማን እንደሚሰማቸው ማወቁ* ላይ ነው (ዮሐንስ 15:19፤1ጢሞ 4:1)፡፡

**4:6 "እግዚአብሔርን የሚያውቅ ይሰማናል"** ይህ የአሁን ግዜ ድርጊት ገላጭ በዛ አንቀፅ ነው፡፡ እውነተኛ አማኞች የሚሰሙ እና ለሐዋርያዊ እምነት ምላሽ የሚሰጡ ናቸው፡፡ አማኞች እውነተኛ ሰባኪያንን አስተማሪዎችን በመልዕክታቸው ይዘት እና ማንሊሰማቸው እንደሚገባ በመረዳት ማደራጀት ይችላሉ፡፡

▣ ***"የእውነት መንፈስና የስህተትን መንፈስ በዚህ እናውቃለን"*** *ይህ ምናልባት መንፈስ ቅዱስን* (ዮሐንስ 14:17፤15:26፤16:13፤ 1ዮሐንስ 4:6፤5:7)እና ክፉ መንፈስን ሰይጣን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል፡፡ አማኞች ሁል ጊዜ የመልእክቱን ምንጭ መለየት መቻል አለባቸው፡፡ ሁለቱም በእግዚብሔር ስም እና ስለእግዚአብሔር በሚናገሩ ሰዎች ሊተላለፍ ስለሚችሉ ነው፡፡ አንዱ ኢየሱስን እና ክርስቶስን መምሰል ከፍ ሲያደርግ ሌላው ደግሞ የሰውን ግምት እና ግላዊ ነፃነትን የሚያጎላ ነው፡፡

ፎሽርስ ጊርድልስቶን፤ *SyNoNyms of the old TestameNt* በሚለው መጽሐፋቸው ላይ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለውን "መንፈስ" በሚለው አጠቃቀም ላይ ማራኪ የሆነ ውይይትን ያቀርባሉ፤

1. ክፉ መናፍስት
2. የሰው መንፈስ
3. መንፈስ ቅዱስ
4. መንፈስ ቅዱስ በሰው መንፈስ ውስጥ እና በሰው መንፈስ በኩል የሚፈጥራቸው ነገሮች
   ሀ. "የባርነት መንፈስ ሳይሆን ወይም የልጅነት መንፈስ" - ሮሜ 8:15
   ለ. "ራስን የመግዛ መንፈስ" -1ቆሮ4:21
   ሐ. "የእምነት መንፈስ" - 2ቆሮ 4:13
   መ. "እርሱነ በማወቅ የጥበቡ እና የመገለጥ መንፈስ"- ኤፌ1:17
   ሠ. "የፍርሃት መንፈስ ሳይሆን የኃይል የፍቅር እና ራሱን የመግዛት መንፈስ፡- 2ጢሞ1:7
   ረ. "የስህተት መንፈስ እና የእውነት መንፈስ" 1ዮሐንስ 4:6 (ገጽ 61-63፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 4÷7-14

**[7]ወዳጆች ሆይ÷ ፍቅር ከእግዚአብሔር ስለሆነ የሚወደውም ሁሉ ከእግዚአብሔር ስለ ተወለደ እግዚአብሔርንም ስለሚያውቅ÷ እርስ በርሳችን እንዋደድ፡፡ [8] ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም÷ እግዚአብሔር ፍቅር ነው፡፡ [9]በዚህ የእግግዚአብሔር በእኛ ዘንድ ተገለጠ÷ በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና፡፡ [10]ፍቅርም እንደዚህ ነው፤ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደወደደን ስለኃጢአታችንም ማስተሰርያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደ ላከ እንጂ እና እግዚአብሔርን እንደወደድነው አይደለም፡፡ [11]ወዳጆች ሆይ÷ እግዚአብሔር እንዲህ አድርጎ ከወደደን እኛ ደግሞ እርስ በርሳችን ልዋደድ ይገባናል፡፡ [12]እግዚአብሔርን ማም ከጀቶ አላየውም እርስ በርሳችን ብንዋደድ እግዚአብሔር በእና ይኖራል ፍቅሩም በእኛ ፍፁም ሆኖአል፡፡ [13]በመንፈስ ስለሰጠን÷ በእርሱ እንድንኖር እርሱም በእኛ እንዲኖር በዚህ እናውቃለን፡፡ [14]እኛም አይተናል አባትም ልጁን የዓለም መድኃኒት ሊሆን እንደላከው እንመስክራለን፡፡**

4:7 **"እርስበርሳችን እንዋደድ"** ይህ የአሁን ጊዜ ገላጭ ግሥን ሁኔታ አመልካች ነው፡፤ በሕይወት ዘይቤ የሚገልጥ ዕሉታዊ ፍቅር የሁሉም አማኞች የተለመደ ባህርይ ነው(1ቆሮ 13፤ገላ5:22)፡፡ ይህ በዮሐንስ ፁሁፎች ውስጥ ተደጋግሞ የሚታይ ጭብጥ እና የግብረገብ መመዘና ዋነኛ ባህርይ ነው(ዮሐንስ 13:34፤15:12፡117፤ 1ዮሐንስ 2:7-11፤ 3:11:23፤ 2ዮሐንስ5፤ በሐ ላይ የተሰጡትን አውዳዊ ግንዛቤዎችን ይመልከቱ)፡፡ የግሱነ ሁኔታን የሚገልፀው ሐረግ መሥማማትን የሚያሣይ ነው፡፡

▣ **"ፍቅር ከእግዚአብሔር ስለሆነ"** የፍቅር ምንጩ(ቁ.16) የሰው ለጋስነት፣ ሐዘኔታ እና ስሜት ሳይሆን ራሱ እግዚአብሔር ነው፡፡ ይህ ከመጀመሪያውም ስሜታዊ ሳይሆን ዓላማ ያለው ተግባር ነው (አብ ስለእኛ ልጁ እንዲሞት መላኩ፤ ቁ10፤ ዮሐንስ 3:16)፡፡

▣ **"የሚወደውም ሁሉ ከእግዚአብሔር ስለተወለደ እግዚአብሔርንም ስለሚውቅ"** እነዚህ ግሦች የተጠናቀቁ ተደራጊ ግሶች እና የአሁን ጊዜን አመልካች ግሦች ናቸው፡፤ ዮሐንስ አማኝ ከመሆን ጋር የሚጠቀማቸው የተለመዱ ቃላት ከአከላዊ መወለድ (በሥጋ) ጋር የተዛመዱ ናቸው (2:29፤3፤5:1፤4:18፤ ዮሐንስ 3:3:7:31፤19:11)፡፡

"ማወቅ" የሚለው ቃል የሚያንፀባርቀው ቀጣይነት ያለውን የቅርበት ግኑኝነት የእብራይስጥ ትርጉም ነው (ዘፍ4:1፤ኤር 1:5)፡፡ ይህ በ1ዮሐንስ ውስጥ ከሰባ አምስት ጊዜ በላይ የተጠቀሰ ተደጋጋሚ መልዕክት ነው፡፡ በዮሐንስ 1:10 ላይ ያለውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስን ይመልከቱ፡፡

4:8 **"ፍቅር የሌለበት እግዚአብሔር አያውቅም፤ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና"** በኑሮ ዘይቤ የሚገለጥ ፍቅር እግዚአብሔርን ለማወቅ እውነተኛው መፈተኛ ነው፡፡ ይህ ጥልቀት ካላቸው ከዮሐንስ ቀለል ያሉ ንግግሮች አንዱ ነው፤ "እግዚአብሔር ፍቅር ነው" የሚለው "እግዚአብሔር ብርሃን ነው" (1:5)፤ "እግዚአብሔር መንፈስ ነው" (ዮሐ 4:24) ከሚሉት ጋር የሚስማማ ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ፍቅር እና የእግዚአብሔርን ቁጣ ለማቃረን ከሚረዱ መንገዶች አንዱ ዛዳ 5:9ን እና 7:9ን ማነፃፀር ነው፡፡

4:9 **"በዚህም የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ"** ይህ የግሪኩ ተደራጊ ግሥ አመልካች ነው(ዮሐንስ 3:16፤2ቆሮ 9:15፤ ሮሜ 8:32)፡፡ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን በመላክ እና በምትካችን እንዲሞት በማድረግ ለእኛ ያለውን ፍቅር በግልፅ አሳይቷል፡፡ ፍቅር ድርጊት እንጂ ስሜት አይደለም፡፡ አማኞች በእለታዊ ኑሮአቸው ሁሉ ክርስቶስን መምሰል ይገባቸዋል (1ዮሐንስ 3:16)፡፡ እግዚአብሔርን ማወቅ ማለት እርሱ እንደወደደን እንዲሁ መውደድ ነው፡፡

▣ **"እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና"** ይህ የተጠናቀቀ ድርጊትን አመልካች ግሥ ነው፤ የኢየሱስ ተሰግዎ እና ውጤቱ ፀንቶ የሚኖር ነው! ሁሉም የእግዚአብሔር በረከቶች በክርስቶስ አማካኝነት ይመጣሉ፡፡

"አንድ ልጅ" የሚለው ቃል *MoNogeNe*s(ሞኖጄነስ) ማለት ሲሆን የሚያመለክተውም "ድንቅ"፣ "አንድ አይነት" የሚል እንጂ በግብረ ሥጋ ግንኝነት የመጣ ልጅ ማለት አይደለም፡፡ በድንግልና መውለድ ለእግዚአብሔርም ሆነ ለማርያም የግብረሥጋ ግንኙነት ልምምድ ጉዳይ አልነበረም፡፡ ዮንስም ይህንን ቃል ኢየሱስን ለማመልከት በርካታ ጊዜያት ይጠቅሰዋል (ዮሐንስ1:14፡18፤ 3:16፡ 18፤ 1ዮሐንስ 4:9)፡፡ ተጨማሪ ማብራሪያን በ3:16 ላይ ይመልከቱ፡፡ ኢየሱስ ድንቅ እና በተለየ መንገድ (በማንነት) ትርጉመ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ድንቅ እና በተለየ መንገድ (በማንነት) ትርጉም የእግዚአብሔር ልጅ ነው፡፡ አማኞች የእግዚአብሔር ልጆች የሚባሉት በውርስ መንገድ ብቻ ነው፡፡

▣ **"በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ"** ይህ የግሪኩን ድርጊት ገላጭ ግሥን ሁኔታ የሚያሳይ ሲሆን በተዘዋዋሪ የሚያመለክተው ሊሆን የሚችልን ነገር በመሆኑ በእምነት የሚደረግን ምላሽ አስፈላጊነት ያሣያል፡፡
የተሰግዎ ዋና አላማ የዘላለም ሕይወት እና የተትዘፈረፈ ሕይወት ነው (ዮሐንስ 10:10)፡፡

4:10 **"ፍቅርም እንደዚህ ነው"** የእግዚአብሔር ፍቅር በኢየሱስ ሕይወት እና ሞት ውስጥ በጉልህ የሚታይ ነው (ሮሜ 5:6:8)፡፡ ኢየሱስን ማወቅ እግዚአብሔርን ማወቅ ነው፤ እግዚአብሔርንም ማወቅ ደግሞ መወደድ ማለት ነው::

▣ **"እኛ እግዚአብሔርን እንደወደድነው አይደለም"** አዲስ ኪዳን በአለም ኃይማኖቶች መካከል በጣም የሚያስደንቅ ነው፡፡ በተለምዶ ኃይማኖት የሰው ልጅ እግዚአብሔርን መፈለጉነ የሚያሳይ ነው፤ ነገር ግን ክርስትና ማለት እግዚአብሔር የወደቀውን የሰውን ልጅ መፈለጉን የሚያሳይ ነው፡፡ አስደናቂው እውነት እኛ ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር ሳይሆን እርሱ ለእኛ ያለው ፍቅር ነው፡፡ እርሱ በኃጢአታችንና በእኔነታችን፣ በአመፃችን እና በትእቢታችን ገና ሳለን የፈለገን አምላክ ነው፡፡ የክርስትና እምነት ታላቅ እውነት ደግሞ እግዚአብሔር የወደቀውን የሰው ዘር መውደዱ እና ሕይወት - ለዋጭ የሆነውን ግኙኝነት መፍጠሩ እና ያንንም መጠበቁ ነው፡፡

የተለያዩ ምንጮች ከግሡ መልክ ጋር የሚዛመዱ ናቸው፡፡

1. መውደድና በመውደድ መቀጠል፤ የተጠናቀቀ ድርጊት፡- *MSB*
2. መውደድ፤ የግሪክ አድራጊ ግሥ፡- *MSN*

የዩቢኤስ[4] መጽሐፍቅዱስ ለተጠናቀቀው የጊዜ አመልካች የ"*B*' ደረጃን ይሰጠዋል (ለእርግጠኝነት የቀረበ)፡፡

▣ **"ስለ ኃጢአታችንም ማስተሰር ይሆ ዘንድ ልጁን እንደላከ"** በ2:2 ላይ ያለውን ማብራሪያ ይመልኩቱ፡፡

4:11"ከ..." ይህ የመጀመሪያ መደብ ሁኔታዊ አረፍተነገር ሲሆን ከፀሐፊው እይታ አንፃር ወይም ለስነፅሑፋዊ አላማው ሲባል እውነት ተደርጎ የሚገመት ነው፡፡ እግዚአብሔር በእርግጥ ይወደናል (ሮሜ 8:31)!

▣ **"እርስ በርሳችን ልንዋደድ ይገባል"** እርሱ አስቀድሞ ስለወደደን እርስ በርሳችን ስንዋደድ ይገባናል፡፡ የዚህ ንግግር አስፈላጊነት የሚያሳየው የሐሰት አስተማሪዎችን አፍራሽ አመለካከት እና ድርጊት ነው፡፡

4:12 **"እግዚአብሔርን ማንም ከቶ አላየውም"** ይህ የተጠናቀቀን ድርጊት የሚያሳይ መሐከለኛ አመልካች ግሥ ነው፡፡ ይህ ቃል በተዘዋዋሪ የሚገልፀው "አንድን ሰው ወይም አንድን ነገር በትኩረት መመልከትን"ነው(ዘፀ33:20-23፤ዮሐንስ 1:18፤5:37፤6:46፤ 1ጢሞ 6:16)፡፡ በምሥራቃዊያን ኃይማኖቶች መጠነኛ የሆነ ተፅዕኖ ከመኖሩ የስህተት አስተማሪዎች ከእግዚአብሔር ዘንድ ወይም ስለ እግዚአብሔር አንዳች አይነት መገለጥ እነዳደላችው አፅንተው ይናገሩ ነበር ማለት ይችላል፡፡ ኢየሱስ የመጣው አብን በሙላት ለመግለጥ ነው፡፡ በመሆኑም ኢየሱስን ትኩር ብለን በመመልከት እግዚአብሔርን እናውቃለን!

▣ "ከ..." ይህ ሦስተኛ ሁኔታው አረፍተነገር ሲሆን ድርጊት ለመፈፀም አቅም መኖሩነ ያሣያል፡፡

▣ **"ፍቅሩም በእና ፍፁም ሆኖአል"** ይህ በዙሪያ ጥምጥም የተነገረ ተደራጊ በዚ አንቀፅ ነው፡፡ የሚወዱ ክርስትያኖች ፍፁም ሆኖ የሚኖርን የእግዚአብሔር ፍቅር ማረጋገጫ ናቸው(2:5፤4:17)፡፡

▣ **"እግዚአብሔር በእኛ ይኖራል"** በ2:10ላይ ያለውን መኖር የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

4:13 **"ከመንፈሱ ስለሰጠን"** ይህ ድርጊት መጠናቀቁን የሚያመለክት ግሥ ነው" የመንፈስ ቅዱስ በውስጣችን መኖር (3:24፤ሮሜ8:9) እና እኛንም የመለወጡ ኃይሉ የእውነተኛ ድነታችን ማስረጃው ነው (ሮሜ8:16)፡፡ ቁጥር 13 ስለመንፈስ የተሰጠ የማይታይ ምሥክር ሲሆን ቁጥር 14 ደግሞ የሚታይ የሐዋርያት ምሥክርነት ይመስላል፡፡ ሦስቱ የሥላሴ አካላት ምሥክርነት በቁጥር 13:14 ላይ በግልፅ ይታያል፡፡ በዮሐንስ 14:26ላይ ስለ ሥላሴ የተሰጠውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

"አይተናል" የሚለው በቁጥር 12 ላይ እንደተጠቀሰው ተመሳሳ የግሪክ ቃል ሲሆ ትርጓሜውም "አንድን ነገር በትኩረት መመልከት" ማለት ነው፡፡ በዮሐንስ 1:8 ላይ የኢየሱስ ምሥክር መሆን የሚለውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስ ይመልከቱ፡፡

▣ **"አባትም ልጁን... እንደላከው"** ይህ የተጠናቀቀ ድርጊት አመልካች ግሥ ነው፡፡ አብ እግዚአብሔር ወልድን ወደ ዓለም የመላኩ እውነታ(ዮሐንስ 3:16) መንፈስ (ጥሩ) ቁሳዊ ነገር ደግሞ መጥፎ ነው የመለውን የግኖስቲኮችን የሐሰት ትምህር የሚያፈርስ ነው፡፡ ኢየሱስ መለኮት የነበር እና በኃጢአት የተሞላው ክፉ አለም ውስጥ የተላከ እና ዓለምንም ሆነ እኛን (ሮሜ 8:15-25) ከዘፍጥረት 3(ገላትና 3:13) እርግማን እንዲዋጀን የተላከ ነበር፡፡

▣ **"የዓለም መድኒት ሊሆን"** አብ ኢየሱስን የድነት መንገድ አድርጎ የመጠቀሙ እውነታ ድነት የሚገኘው በመላዕክት ደረጃ ካለ ልዩ እና የተሰወረ እውቀት ነው የሚለውን የግኖስቲኮችን የሐሰት ትምህርት የሚያፈርስ ነው፡፡ እነርሱም እነዚህን የመላዕክት ደረጃዎች *eoNs* (ኢዎንስ) ወይም በታላቁ አምላክና ቀደም ካሉት ቁሶች ይህችን አለም በፈጠረው አነስ ያለ አምላክ መካከል ያለ መላዕክት የሥልጣን አለም ነው ብለው ይጠሩታል፡፡

"የዓለም መድኃኒት" የሚለው ሐረግ (1) ለአማልዕክት የተሰጠ መጠሪያ ነበር (ዜዎስ) እና (2) ለሮም ቄሣር የተለመደ መጠሪያ ነው፡፡ ለክርስትያደን ግን ኢየሱስ ብቻ ነው ይህ ማዕረግ ሊኖረው የሚችለው (ዮሐንስ 4:42፤1ጢሞ 2:4፤4:10)፡፡ ይህ ነበር እንግዲህ ከበታች ባሉት ቄሣሮች አማኝነት ስደትን እና መከራን በትንሹ እስያ በክርስትያኖች ላይ ያስከተለው፡፡

ይህ ሐረግ ሁሉን አቀፍ መሆኑን አስተውል፡፡ ሁሉም ምላሽ ሲሰጡ ብቻ ነው እርሱ የሁሉም አዳኝ ሊሆን የሚችለው (የጥቂቶች ብቻ አይደለም) (ዮሐንስ 1:12:3:16፤ ሮሜ5:18፤10:9-13)፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 4÷15-21

**[15]ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በሚታመን ሁሉ እግዚአብሔር በእርሱ ይኖራል፤ እርሱም በእግዚአብሔር ይኖራል፡፡[16]እኛም እግዚአብሔር ለእኛ ፍቅር አውቀናል አምነንማል፡፡ እግዚአብሔር ፍቅር ነው በፍቅርም የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል፡፡ እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል፡፡ [17] በፍርድ ቀን ድፍረት ይሆንልን ዘንድ ፍቅር በዚ ከእኛ ጋር ተፈጽሞአል፤ እርሱ እንዳለ እኛ ደግሞ እንዲሁ በዚህ አለም ነንና፡፡ [18]ፍፁም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሃት የለም፤ ፍርሃት ቅጣት አለውና የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም፡፡ [19]እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን፡፡ [20] ማንም ፦ እግዚአብሔርን እወዳለሁ እለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው፡፡ ያየው ወንድሙን የማይወድ ያለየውን እግዚአብሔርን ሊወደው እንዴት ይችላል? [21]እግዚአብሔርንም የሚወድ ወንድሙንም እንዲወድ ይህች ትእዛዝ ከእርሱ አለችን፡፡**

**4:15"ኢየሱስን የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በሚታመን ሁሉ"** ይህ የግሪኩ ገላጭ ግሥ ሁኔታን አመልካች ነው። "መታመን" ለሚለው ቃል በቁጥር 2 ላይ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ። የክርስትያን የእውነት ከሚያረጋግጡ ሦስት የዮሐንስ መመዘኛዎች አንዱ ስለ ኢየሱስ ማንነት እና ሥራ ላይ ያለው ሥነ-መለኮታዊ እውነት ነው (2:22-23፣41-6፤ 5፤1:5)። ይህ በዮሐንስ የመጀመሪያው መልዕክት እና በያዕቆብ መልዕክት ውስጥ ከተገለጠው መታዘዝ እና ተግባራዊ ፍቅር ጋር የሚስማማ ነው። ክርስትና ስብእነ ያለው፣ የእውነት አካል እና በኑሮ የሚገለጥ ነው።
በ"ሐ" ላይ የተላጡትን አውዳዊ ግንዛቤዎችን ይመልከቱ።

"ሁሉ" የሚለው አጠቃላይ ቃል ማንም ሰው፣ ሁሉም ሰው ወደ እርሱ ይመጣ ዘንድ ታላቅ የሆነ የእግዚአብሔር ግብዣ(ጥሪ) ነው። ሁሉም ሰዎች በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩ ናቸው (ዘፍ 1:26-27፤5:3፤9:6)። እግዚአብሔር በዘፍ 3:15 ላይ መመዡትን እንደሚያመጣ ቃል ገብቷል። እርሱም ለአብርሃም ያደረገው ጥሪ ዓለምን ይደርስ ዘንድ ያደረገለት ጥሪ ነበር (ዘፍ12:3፤ዘፀ19:5)። የኢየሱስ ሞት ለኃጢአት ችግር ምላሽ የሰጠ ነበር(ዮሐንስ:16)። ማንም ሰው ሊድን የሚችለው እግዚአብሔር ለሚያደርግለት የንስሐ፣ የእምነት፣ የአገልግሎ የመታዘዝ እና ፀንቶ የመቆም ጥሪ ምላሽ ሲሰጥ ብቻ ነው። የእግዚአብሔር ጥሪ ለሁሉም "ኑ" የሚል (ኢሳያስ 55)።

**ልዩ ርዕስ፡ የቦብ ኢቫንጀሊካል አመለካከት**
አንባቢ ሆይ እዚህ ነጥብ ላይ ትንሽ ግራ መጋባት ገጥሞኛል የእኔ በሥርዓት የተዋቀረ ሥነ-መለኮት ስለ ካልቪኒዝም ወይም ዲስፔንሴሽናል ሳይሆን ታላቁ ተልእኮ የመንፈስ ስርጭት ነው (ማቴ 28÷18-20፤ ሉቃስ 24÷46-47፤ ሐዋ 1÷8)። እግዚአብሔር በአምሳኩ ለተፈጠሩት (ዘፍ 1÷26-27) የሰው ልጆች መመዘኛ የዘላለም እቅድ እንዳለው አምናለሁ (ዘፍ 3÷15፤12÷3፤ ዘፀ 19÷5-6፤ ኤር 31÷31-34፤ ሕዝ18፤ 36÷22-39፤ ሐዋ 2÷33፤ 3÷18፤4÷28፤13÷29፤ ሮሜ3÷9-18፡ 19-20፡21-31)፡፤ ቃል ኪዳኖች በክርስቶስ አንድ ሆነዋል (ገላ3÷28-29፤ ቆላ 3÷11)። ኢየሱስ ተሰውሮ የነበር ነገር ግን አሁን የተገለጠ የእግዚአብሔር ምስጢር ነው (ኤፌ2÷11-3÷13)! የእግዚአብሔር ቃል ቁልፍ (ወሳኙ ነገር) እስራኤል ሳትሆን አዲስ ኪዳን ነው።

ይህ ቀዳሚ የሆነ መረዳት ሁሉንም የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎሞችን ያዛባል፡፤ በእርሱ አማካኝነት ሁሉንም ክፍሎች አነባለሁ፤ በእርግጥ ይህ የሁሉም ግራ መጋባት ነው(ሁሉም ተርጓሚዎች የሚጋሩት እውነት) ነገር ግን ይህ በእግዚአብሔርን ቃል በመረዳት የሚደረግ አስቀድሞ ተገመተን ነገር መጠየቅ ነው።

▣ **"እግዚአብሔር በእርሱ ይኖራል፤ እርሱም በእግዚአብሔር የኖራል"** ይህ እግዚአብሔርን ከሰው ልጆች ጋር ያለውን የቃል ኪዳን መዋቅር የሚያሳይ ነው። እግዚአብሔር ሁልጊዜም የቀዳሚነቱነ ሥፍራ ይወስዳል፣ አጀንዳውን ያዘጋጃል፤ ለቃልኪዳኑም መሠረትን ይሰጣል፣ ነገር ግን የሰው ልጆች ምላሽ ለመስጠት እና በምላሻችንም ሊቀጥሉበት ይገባል።

መኖር ቃል ኪዳን የሚፈለገው መሥፈርት ነው፤ ይሁን እንጂ አስደናቂም ተስፋ ነው (ዮሐንስ15) የዩንቨርሱ ፈጣሪ፣ የእስራኤል ቅዱስ፣ በወደቁት የሰው ልጆች ውስጥ (በውስጣቸው ሲኖር) እንግዲህ አስተውል (ዮሐ14:31)!
በ2:10 ላይ መኖር የሚለውን ተጫሪ የጥናት ርዕስ ይመልከቱ።

**4:16"እኛም… አውቀናል፣ አምነንማል"** እነዚህ ግሦች የተጠናቀቀ ድርጊትን አመልካች ናቸው። አማኞች በክርስቶስ ባለ የእግዚአብሔር ፍቅር ያለቸው ድፍረት የሕብረታቸው መሠረት ነው። በ5:13 ላይ የተሰጠውን ሞስትና የሚለውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስ ይመልከቱ።

▣ **"እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን"** ይህ የአሁን ጊዜ ድርጊት ገላችን አመልካች ሲሆ ቀጣይነት ያለውን የእግዚአብሔርን ፍቅር ያመለክታል።

▣ **"እግዚአብሔር ፍቅር ነው"** ይህ አስፈላጊ እውነት ተደግሟል (ቁ.8) ።

**4:17 "ፍቅር በዚህ ከእኛ ጋር ተፈፅሞአል"** ይህ *telos*(ቴሎስ) ከሚለው የግሪክ ቃል (ቁ.12) የመጣ ነው። ይህም ያለ ኃጢአት መሆንን ሳይሆን ሙሉነትን፣ ብስለትን እና ፍፁምነትን የሚያሳይ ነው።

▣ **"ከእኛ ጋር"** የህ መስተዋድድ (meta) "በእኛ ውስጥ" (TEV፣ NJB)፣ "በመካከላችን" (ኤን ኬጀቪ፣ ኤን አር ኤስቪ፣ አመት፣ አርኢቢ) ወይም "ከእኛ ጋር" (ኤን ኤ.ኤስ.ቢ) ተብሎ ልንረዳው እንችላለን።

▣ **"ድፍረት ይሆንልን ዘንድ"** ከመጀመሪያው የዚህ ቃል ትርጉም የንግግር ነፃነት ማለት ነው፡፤ ዮሐንስ ይህንን ቃል በሰፊው ይጠቅሰዋል /2:28፤3:21፤5:14)። ቃ የሚናገረው ቅድስን አምላክ ለመቅረብ ያለንን ድፍረት ነው (ዕብ3:6፤10:35)። በ2:28 ላይ የተሰጠውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስ ይመልከቱ።

▣ **"በፍርድ ቀን ድፍረት ይሆንልን ዘንድ… እርሱ እነዳለ እኛ ደግሞ እንዲሁ በዚህ ዓለም ነንና"** ክርስቲያኖች ኢየሱስ እንደወደደው ሊወዱ ይገባል (3:16፤4:11)። በእርሱ እንደደረሰው ሊጠሉ እኛ ሊሰደዱ ይችላሉ፣ ነገር ግን ለእርሱም

እንደሆነው በአብ እና በመንፈሱ ሊወደዱ ይችላሉ፡ የሰው ልጆች ለተሰጣቸው ለዚህ ሕይወት አንድ ቀን መልስ ይሰጣሉ (ማቴ 25:31-46፤2ቆሮ 5:10፤ራዕይ 20:11-15)። የፍርድ ቀን በክርስቶስ ላሉት የሚያስፈራ አይደለም።

**4:18"በፍቅር ፍርሃት የለም"** እግዚአብሔርን እንደ አባት ስናወቀው እንደ ዳኛ አንፈራውም። ሁሉም ባይሆን አብዛኛዎቹ በክርስትና ውስጥ ያሉ ንግግሮች ፍርሐትን የተሞሉ ናቸው። ፍርድን መፍራት፣ ኩነኔን መፍራት ገሃነምን መፍራት። ይሁን እንጂ በተዋጁ ሰዎች ሕይወት ውስጥ አስደናቂ ነገር ይሆናል። በፍርሃት የሚጀምረው ነገር ባለመፍራት ያበቃል።

▣ **"ፍርሃት ቅጣት አለውና"** ይህ ብዙም የማይጠቀስ ቃል ሲሆን በዚህ *ሥፍራ* እና በማቴ 25:46 ብቻ ተጠቅሷል (*የግሡ አይነት* በ2ጴጥ 2:9 ላይ ተጠቅሷል) ይህም በተጨማሪ የነገረ-ፍፃሜ መነሻ ቦታን ነው። የአሁን ጊዜ አመልካች *ግሥ* ሲሆን ይህም የእግዚአብሔር ቁጣ ጊዜያዊ (በጊዜው የሚሆን) እና *ሥነ*-ፍፃሜያዊ (በመጨረሻው ጊዜ) ነው። የሰውልጆች ስብእናን፣ እውቀትን፣ ምርጫን እና የሚያስከትለውንም ውጤት በሚያካትት ሁኔታ በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥረዋል (ዘፍ 1:26-27)። ይህ ምዕላዊ ዩኒቨርስ ነው። ሰዎች የእግዚአብሔርን ሕግ አይጥሱትም፣ ነገር ግን ራሳቸውን በእግዚአብሔር ሕግ ላይ ይጥሉታል እንጂ!

4:19 **"እኛ እወደዋለን"** ይህ የአሁን ጊዜን የሚገልጥ አመልካች *ግሥ* ነው። የኤንኬጀቪ መጽሐፍ ቅዱስ "እኛ እንወደዋለን" በሚለው ላይ ቀጥተኝ ተሳቢን ይጨምራል። ለቀጥተኛው ተሳቢ ያሉት የምንጮ አማራጮች፤

1. በአንድ የግሪክ ምንጭ (*N*) "እግዚአብሔር" (*toN theoN*) የሚለው ተጨምሮበታል።
2. *የዕብራይስጡ ምንጭ ደግሞ "እርሱ"(autoN) የሚለው ተጨምሮበታል (kjv)*
3. በቩልጌት ደግሞ "እርሱ በርሳችን" የሚለው ተጨምሮበታል።

ቀጥተኛ ተሳቢዎች ምናልባት ከኃላ የተደረጉ ጭማሪዎች ሳይሆኑ አይቀርም። የዩቢኤስ[4] መጽሐፍ ቅዱስ ለግሡ የ"A" ደረጃን ብቻ ይሰጠዋል (እርግጠኛ ማለት ነው)።

▣ **"እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና"** ይህ ቁጥር 10 ተደጋግሞ ትኩረት የተሰጠበት ነው። እግዚአብሔር ሁል ጊዜ የመጀመሪውን እርምጃ ይወስዳል (ዮሐንስ 6:44፡65) ነገር ግን የወደቀው የሰው ዘር ምላሽ መስጠት አለበት (ዮሐንስ 1:12፤3:16) አማኞች በእርሱ ማንነት ይተመናሉ እንዲሁም ደግሞ በእርሱ ታማኝነት ይደገፋሉ። ፍቅርን የተሞላው፤ በተግር የሚገለፀው የእግዚአብሔር ባህርይ ለተቤዠው የሰው ዘር ተስፋው እና ዋስትናው ነው።

4:20 **"ማንም... እያለ"** ይህ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ አረፍተ ነገር ሲሆ ድርጊት ለመፈፀም እድል መኖሩን ያመለክታል። ይህ ዮሐንስ ባነጻው ነጥብ ላይ ትኩረት ለማድረግ እንዲረዳው የሐሰት አስተማሪዎችን ንግግሮች የሚጠቅስበት ሌላው የዮሐንስ ምሣሌ ነው (1:6:8:10፤2:4፡6)። ይህም *ሥነፁሑፋዊ* ቴክኒክ በቃላት መንደፍ ይባላል (ሚልኪያስ፣ ሮሜ፣ እና ያዕቆብ)።

▣ **"እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ"** በሕይወታችን የሚታየው ፍቅር ክርስትያኖች መሆ አለመሆናችንን በግልፅ የሚያሳይ ነው(ማር 12:2834)። *መጋጨት ያለ ነው፤ ነገር ሥር* የሰደደ ጥላቻ የማይቻል ጉዳይ ነው(የአሁነ ጊዜ አመልካች)። በዮሐንስ 4:4ላይ ያለውን ዘረኝነት የሚለውን ልዩ የጥናት ርዕስ ይመልከቱ።

▣ **"ሐሰተኛ ነው"** ዮሐንስ በርካታ "አስመሳይ" አማኞችን ሐሰተኞች ይሳቸዋል (2:4፡22:4:20)። ከዚህም በላይ ዮሐንስ ሐሰትን የሚሰብኩትን እግዚአብሔርን ሐሰተኛ እንደሚያደርጉት ይገልፃል (1:6:10፤5:10)። በእርግጥም ደግሞ ራሳቸውን የሚያታልሉ ወግ አጥባቂዎችም ነበሩና!

4:21 ይህ ጥቅስ ለምዕራፍ መደምደሚያን ይሰጣል! ፍቅር ሊከላከሉት የማይቻል የእውነተኛ አማኝ ማስረፋ ነው። በአንፃሩመ ደግሞ ጥላቻ የክፉው ፍሬ ነው። የሐሰት መምህራንም መንጋውን በመከፋፈል ግጭትንም ያስከትሉ ነበር።

▣ **"ወንድሙን"** "ወንድም" የሚለው ቃል አሻሚ ትርጉመ እንዳለው ሊታወቅ ይገባል። የቃሉ ትርጉም ምናልባት"የሆነ ክርስትያን" ወይም "የሆነ ሰው" ማለት ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ ዮሐንስ አማኞችን "ወንድም"ብሎ በተደጋጋሚ መጥቀሱ በተዘዋወሪ የመጀመሪያውን የሚያመለክት ነው (ጢሞ 4:10)።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ማብራሪያ ስለሆነ ለምትከተለው የራስህ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ። እያንዳንዳች ልንገዝ የሚገባን ባለን መረዳት መጠን ነው። አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጎም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ናችሁ። ይህንንም ጉዳይ በሚያብራራው ሰው ላይ ብቻ ልትተው አይገባም።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተነሱትን አቢይ ጉዳዮች ተጨናቸው ዘንድ ነው፡፡ ጥያቄዎቹ እንደሐሳብ ቀስቃሽ ሆነው እንጂ በራሳቸው ቀጥተና አይደሉም፡፡

1. የእውነተኛ ክርስትና ሦስት አቢይ መመዘኛዎችን ዘርዝር፡፡
2. አንድ ሰው ሌላው ለእግዚአብሔር በማስመሰል መናገሩን እንዴት ያውቃል?
3. ሁለቱን የእውነት ምንጮች ዝርዝር (የሚታዩና የማይታዩ)፡፡
4. “የዓለም መድኃኒት” የሚለው መጠሪያ አስፈላጊነት ምንድ ነው?
5. ሐሰተኞችን የሚገልጡ ተግባሮች ዝረዝር (የሐሰት አማኞች)፡፡

# 1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ 5

## በተሻሻሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀፅ አከፋፈል

| UBS[4] | NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| እምነት ዓለምን ማሸነፍ ነው | በእምነት መታዘዝ | አሸናፊ እምነት | በዓለም ላይ ያለን ማሸነፍ | |
| | 4:20-5:5 | | | |
| 5:1-5 | | 5:1-5 | 5:1-5 | የእምነት መሠረት |
| ስለ ወልድ ምስክርነት | የእግዚአብሔር ምስክር እውነተኝነት | | ስለ ኢየሱስ መስክርነት | 5:5-13 |
| 5:6-12 | 5:6-13 | 5:6-12 | 5:6-12 | |
| የዘላለም ህይወት | | ማጠቃለያ | የዘላለም ሕይወት | |
| 5:13-15 | በፀሎት ያለን ድፍረት እና ምህረት | 5:13 | 5:13-15 | ለኃጢአተኞጭ ፀሎት |
| | 5:1417 | 5:14-17 | | 5:1417 |
| 5:16-17 | እውነቱ ማወቅ፤ ሐሰቱን መቃወም | | 5:16-17 | የመልዕክቱ ማጠቃለያ |
| 5:18-21 | 5:18-21 | 5:18-20 | 5:18 | 5:18-21 |
| | | | 5:19 | |
| | | | 5:20 | |
| | | 5:21 | 5:21 | |

**ሦስተኛ የምንባብ ዑደት (አንቀፅ 5ን ይመልከቱ)**
*የመጀመሪያውን ፀሐፊ ዋና ሐሳብ በአንቀጽ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ማብራሪያ ነው፤ ስለሆነም ለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ፡፡ እያንዳንዳችን ልንጓዝ የሚገባን ባለን መረዳት መጠን ነው፡፡ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጎም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣችሁ ናችሁ፡፡ ይህንንም ጉዳይ በሚያብራራው ሰው ላይ ብቻ መተው የለብህም፡፡

ምዕራፉን በአንድ ቅፅበት አንብበው፤ ዋ ሐሳቦቹንም ለያቸው፡፡ የአንተን የዋና ሐሳብ አከፋፈል ከአምስቱ የተሻሻሉ ትርጉሞች ጋር አስተያያቸው፡፡ ምንም እንኳን በአንቀፅ መከፋፈል በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪ የሚደረግ ባይሆም የአተረጓጎም ምሦሦ የሆነውን የመጀመሪያውን ፀሐፊ ዋና ሐሳብ ለመከተል ግን ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ እያንዳንዱም አንቀፅ ያለው ዋና ሐሳብ አንድ ብቻ ነው፡፡

1. የመጀመሪያ አንቀፅ
2. ሁለተኛ አንቀፅ
3. ሦስተኛ አንቀፅ
4. ወ.ዘ.ተ

## የቃል እና የሐረግ ጥናት

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 5÷1-4
[1]ክርስቶስ ነው ብሎ በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ተወልዶአል፤ ወላጁንም የሚወድ ሁሉ ከእርሱ የተወለደውን ደግሞ ይወዳል። [2]እግዚአብሔርን ስንወድ ትእዛዙንም ስናደርግ የእግዚአብሔር ልጆች እንድንወድ በዚህ እናውቃለን። [3]ትእዛዛቱን ልንጠብቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ይህ ነውና ትእዛዛቱም ከባዶ አይደሉም። [4]ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና። ዓለምንም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው።

5:1"ሁሉ" (ሁለት ጊዜ) *pas* (ፓስ) የሚለው ቃል በ1ኛ ዮሐንስ ውስጥ በደጋጋሚ ተጠቅሿል (1ዮሐንስ2:29፤3:3፡4፡6[ሁለት ጊዜ] 9፡10፤4:7፤5:1)። ዮሐንስ በግልፅ ለይቶ ካስቀመጣቸው ሥነ-መለኮታዊ ምድቦች ገለልተኛ የሆነ ማንም የለም። ይህ ሰዎ ኢየሱስ ክርስቶስን ይቀበሉ ዘንድ የተደረገ የእግዚአብሔር አጠቃላይ ጥሪ ነው (ዮሐንስ 1:12፤3:16፤1ጢሞ 2:4፤2ጴጥ3:9)። ይህም ጳውሎስ በሮሜ 10:9-13 ላይ ካደረገው ታላቅ ጥሪ ጋር ተመሳሳይ ነው።

▣ **"የሚያምን"** ይህ የአሁን ጊዜ ድርጊት ገላጭ በዛ አንቀፅ ነው። ይህ "እምነት"፤ "መታመን" ወይም "ማመን" ተብሎ ሊተረጎም የሚችል የግሪኩ ቃል ነው (ስም- *pistis*፤ ግሥ - *pistevo*)። ይህም እንጂ በ1ኛ ዮሐንስ እና በመጋቢያን መልዕክቶች ውስጥ (1ኛ እና ለኛ ጢሞቴዎስ እና ቲቶ) ቃሉ በአስተምህሮታዊ ይዘት ብዙ ጊዜ ተጠቅሿል (ይሁዳ3:20)። በወንጌላት እና በጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ ቃሉ ለግላዊ እምነት እና መሠጠት ተጠቅሷል። ወንጌል ልናምንበት የሚገባ እውነት እንዲሁም ደግሞ ልንታመንበት የሚገባ ሰው ነው፤ 1ኛ ዮሐንስ እና የያዕቆብ መልዕክትም ግልፅ እንደሚያደርገው ሊኖሩት የሚገባ የፍቅር እና የአገልግሎት ሕይወት ነው።

በዮሐንስ 2:23 ላይ ያለውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስ ይመልከቱ።

▣ **"ክርስቶስ ነው ብሎ በኢሱስ የሚያምን"** ይህ የሐሰት አስተማሪዎች ኑፋቄ የሚሽከረከረው ፍፁም አምላክ ሆኖ በተገለጠው (ቁ.5) እና ሰው በሆነው የኢሱስ ማንነት እና ሥራ ላይ ነው። የናዝሬቱ ኢየሱስ ተስፋ የተሰጠው መሲህ ነው፤ መሲሁም ደግሞ በሚገርም ሁኔታ (ከብሉይ ኪዳን) መለኮት ነው። ይህ ሐረግ "የእግዚአብሔረ ልጅ" የሚለው ሐረግ (4:15፤5:5) ተጨምሮበት ምናልባት በጥምቀት ጊዜ (2:2) ለመሐላ የሚጠቀሙበት ነው። በእርግጠኛነት ይህ ለኢየሱስ መሲህነት የተሰጠው ማረጋገጫ የብሉይ ኪዳን የኃላ ታሪክ ካላቸው ሕዝቦች ጋር ነው (አይሁድ፣ መፃተኞች እና እግዚአብሔርን የሚፈሩ) የሚዛመደው።

▣ **"ከእግዚአብሔር ተወልዶአል"** ይህ የተጠናቀቀ ድርጊት ተቀባይ አመልካች ሲሆን ትኩረት የሚያደርገው በውጫዊ አካል (እግዚአብሔር ቁ.4፡18፤2:29) የተደረገ የድርጊት ድምዳሜ ወደ ዘላለማዊ ማንነት የተሸጋገረን ነው።

▣

| | |
|---|---|
| NASB | **"ከእርሱ የተወለደውን ደግሞ ይወዳል"** |
| NKJB | **"ከእርሱ የተወለደውን ደግሞ ይወዳል"** |
| NRSB | **"ወላጁንም የሚወድ ልጁንም ደግሞ ይወዳል"** |
| TEV | **"አባቱንም የሚወድ ልጁንም ደግሞ ይወዳል"** |
| NJB | **"አባቱንም የሚወድ ልጁንም ይወዳል"** |

ይህ ሐረግ ምናልባት የሚያመለክተው አብ ኢየሱስን መውደዱን ነው ምክንያቱም (1) ነጠላ ቁጥር (2) የግሪኩ ጊዜ አመልካች ግሥ እና (3) የሐሰት አስተማሪዎች ኢየሱስ ከአብ ለመነጠል የሚያደርጉትን ሥነ-መለኮታዊ አካሄድ የሚጠቅስ ስላለ ነው። ይሁን እንጂ ሁላችንም አንድ አባት ስላለን የክርስትኖችን እርስ በርስ መዋደድ(ቁ.2) የሚያመለክተው ተደጋጋሚ መልእክት ጋር ሊዛመድ ይችላል።

5:2 ይህ ሐረግ ፣ ከቁጥር 3 ጋር በመጣመር የ1ኛ ዮሐንስን አቢይ መልዕክቶች ከሆኑት አንዱን ይደግማል። ፍቅር የእግዚአብሔር ፍቅር የተገለፀው ቀጣይነት ባለው ፍቅር (2:711፤4:7-21) እና መታዘዝ ነው (2:3-6)። የእውነተኛ አማኝ ማስረጃዎችንም ያስተውሉ።

1. እግዚአብሔርን ይወዳል
2. የእግዚአብሔርን ልጅ ይወዳል (ቁ.1)
3. የእግዚአብሔርን ልጆች ይወዳል (ቁ.2)
4. ይታዘዛል (ቁ.2፡3)
5. ያሸንፋል (ቁ.4-5)

5:"**ትእዛዛቱን ልንጠብቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ይህ ነውና**" የተጠቀሰው ግሥ የሚታይ ወይም ክስተት ያለው ወይም ሁለቱንም ሊሆን ይችላል፡፡ ስሜትን የሚነካ ሳይሆን በእግዚአብሔርም ጉዳይ ነው(2:3-4፤3:22፡24፤ዮሐንስ 14:15፡ 21፡ 23፤ 15:10፤2ዮሐንስ6፤ራዕይ 12:17፤ 14:12)፡፡

▣ "**ትእዛዛቱም ከባዶች አይደሉም**" አዲስ ኪዳን ኃላፊነቶች አሉት (ማቴ 11:29-30፤ ኢየሱስ "ቀንበር" የሚለውን ቃል ይጠቀሳል፤ ርቢዎች የሙሴን ሕግጋት ለመግለፅ ይጠቅሱታል ማቴዎስ 23:4)፡፡ እነርሱም እኛ ከእግዚአብሔር ጋር ካለን ሕብረት የሚመጡ እንጂ ለዚያ ሕብረት መሠረት አይደሉም፡፡ የሕብረቱ የተመወረተው በእግዚአብሔር ፀጋ ላይ እንጂ በሰው መልካም ሥራ ወይም ችሎታ አይደለም (ኤፌ2:8-9)፡፡ የኢየሱስ መመሪያዎች ምንም ሕግ ከሌላቸው (መሪን የመጡ) ወይም ብዙ ወጐች ካላቸው (ህግ አጥባቂዎች) የስህተት አስተማሪዎች በጣም የተለዩ ናቸው! እግዚአብሔርን እና ሕዝቡን ባገለገልኩ ቁጥር መርን መውጣትንና ሕግ አጥባቂነትን በጣም ልፈራቸው የሚገቡ ሁለት ፅሁፎች እንደሆኑ መቀበል እንዳብኝ አምናለሁ፡፡

በዮሐንስ 12:50 ላይ ያለውን የአሪቱ -ቃላት አጠቃቀም የሚለውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስ ይመልከቱ፡፡

5:4

NASB

NRSB "ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ"

TEV፤NJB "የእግዚአብሔር ልጅ ሆኗል"

የግሪኩ ጥቅስ "ሁሉ"(*pas*) የሚለውን በቁትር1 እንደተጠቀሰው ሁሉ ቃሉን አፅንኦት ለመስጥ ይጠቀመዋል፡፡ የግዑዝ *ነጠላ ቁጥር አመልካች* "ሁሉ" ተብሎ በመተርጎም ተጠቅሷል፡፡ ይሁን እንጂ ዓውዱ ግላዊ አንደምታን የሚፈልግ ነው (በአንድ ቃል ዙ መግለፅን) ምክንያቱም ቃሉ "የተወለደ" ከሚለው *የተጠናቀቀ ድርጊት ተቀባይ ቦዝ አንቀፅ* ጋር የተጣመረ ስለሆነ ነው፡፡ ዓለምን የሚያሸንፈው በኢየሱስ ያመነ ብቻ ነው (4:4፤2:13፡14)፡፡

▣ "**ዓለምን ያሸንፋልና" "ያሸንፋል**" የሚለው *Nikaõ* (2: 13፡ 14፣ 4: 4፤ 5:4፡5) የአሁን ጊዜ ድርጊት ገላጭ አመልካች ግሥ ነው፡፡ በቁጥር 4 ላይም ተመሳሳይ ሥርወ ቃሉ ሁለት ጊዜያት ተጠቅሷል፡፡

1. ስም፡- "የሚያሸንፈው"፤ *Niké*
2. የግሪኩ ድርጊት ገላጭ ቦዝ አንቀፅ፤ *Niké* "የሚያሸንፈው"

ኢየሱስ አስቀድም ዓለምን አሸንፏል (የተጠናቀቀ ድርጊት አመልካች ግሥ፤ ዮሐንስ 16:33)፡፡ አማኞች ከእርሱ ጋር ሕብረት ስላላቸው ዓለምን የሚያንሸንፍበት ኃይል ደግሞ አላቸው (2:13-14፤4:4)፡፡

በዚህ ሥፍራ "ዓለም" የሚለው ቃል ትርጉም "ከእግዚአብሔር ተለይቶ የተደራጀ እና የሚሠራ የሰዎች ማህበረሰብ ማለት ነው፡፡ እኔ ነፃ ነኝ የማለት አመለካከት (ስሜት) የሰው ልጅ መድቀት እና ዓመፅ መለያ ማንነት ነው (ዘፍ3)፡፡ በዮሐንስ 14:17 ላይ ያለውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስ ይመልከቱ፡፡

▣ "**የሚያሸንፈው**" ይህ "አሸንፏል" የሚለው ግሥ የስሙ መደብ ነው (*Nikos*) በቁጥር4 መጨረሻ ላይ የግሪኩ ድርጊት ገላጭ ቦዝ አንቀፅ ተመሳሳይ ሥርወ-ቃል ተጠቅሷል፡፡ እንደ ገና ደግሞ *Nikos* ለሚለው ቃል ሌላ ቦዝ አንቀፅ በቁትር-5 ላይ ተጠቅሷል፡፡ ክርስቶስ ዓለምን ሰላሸነፈ አማኞችም ደግሞ ዓለምን ያሸንፋሉ ደግሞም እያሸንፉ ይሄዳሉ፡፡ ልክ በግሪኮች ዘንድ የድል አምላክ (ሴት) ዝነኛ እንደነበር ሁሉ "*Nikos"* የሚለው ቃል በቴኒስ ጫማ አምራች ዘንድም የታወቀ ነው፡፡

▣ "**እምነታችን**" ይህ በዮሐንስ ፅሑፎች ሁሉ "እምነት" (*Pistis*) የሚለው የሰው መደብ በብቸኝነት የተጠቀሰ ነው፡፡ ምናልባት ከልክ በላይ ትኩረት የተሰጠበትን "ትክክለኛ ሥነ-መለኮት" (እንደ እምነት ሥርዓቶች) ወይስ በየዕለቱ ክርስቶስን መምሰል በሚሉ ሁለት ጉዳዮች ላይ በጣም ተቸግሮበት ሊሆን ይችላል፡፡ ግሡ (*Pisteuõ*) በዮሐንስ በስፋት ተጠቅሶ ይታያል፡፡ እምነታችን ድልን ያመጣል፤ ምክንያቱም

1. ከኢየሱስ ድል ጋር የተገናኘ ነው
2. ከእግዚአብሔር ጋር ባለን አዲስ ግኑኝነት ጋር የተገናኘ ነው
3. በውስጣችን ከሚኖረው ከመንፈስ ቅዱስ ኃይል ጋር የተገናኘ ነው

በዮሐንስ 1:7፤2:23 እና 1ዮሐንስ 2:10 ላይ ያለውን ተጨማሪ የጥናት ርዕሶችን ይመልከቱ፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 5÷5-12

**[5]ኢየሱስም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆ ከሚያምን በቀር ዓለምን የሚያሸንፍ ማነው [6]በውሃና በደም የመጣ ይህ ነው እርሱም ኢየሱስ ክርስቶ በውኃውና በደሙ እንጂ በውኃው ብቻ አይደለም፡፡ [7]መንፈስም እምነት ነውና የሚመሰክረው መንፈስ ነው፡፡ [8]የሚመሰክሩት መንፈሱ ውኃው ደሙም ሦስት ናቸውና ሦስቱም በአንድ ይስማማሉ፡፡ [9]የሰውን ምስክር ብንቀበል የእግዚአብሔር ምስክር ከእርሱ ይልቅ ስለ ልጁ የመሰከረው የእግዚአብሔር ምስክር ይህ ነውና፡፡ [10]በእግዚአብሔር ልጅ የሚያምን በነፍሱ ምስክርነት አለው፡፡ በእግዚአብሔር የማያምን እግዚአብሔር ሌላ ልጁ የመሰከረውን ምስክር ስላለመነ ሐሰተኛ አድርጎታል፡፡ [11]እግዚአብሔርም የዘላለምን ሕይወት እንደሰጠን ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው፡፡ [12]ልጁ ያለው ሕይወት አለው የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም፡፡**

**5:5 “ኢየሱስም የእግዚአብሔር ልጅ”** ይህ ጥቅስ በቁጥር 4 ላይ የተጠቀሰውን የእምነታችንን ይዘት የሚገልፅ ነው፡፡ የእኛ ማሸነፍ የተመሠረተው ፍፁም ሰው ፍፁም አምላክ ሆኖ በተገለጠው ሆኖ በተገለጠው ኢየሱስ ግለን መታመን ነው(4:1-6)፡፡ አማኞች ኢየሱስ (1) መሲህ መሆኑን (2) የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ (ቁጥር1)፤ (3) የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን (ቁጥር 5:10)፣ እና (4) ሕይወት መሆኑን እንደሚያረጋግጡ አስተውል፡፡ በ2:23 ላይ “ማመን” በሚለው ግስ ላይ ተያይዘው የሚገኙ የግሥ ሐረጎችን የሚዘርዝረውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስን ይመልከቱ፡፡

▣ **“የእግዚአብሔር ልጅ”** በ3:8 ላይ ያለውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስ ይመልከቱ፡፡

**5:6 “የመጣ ይህ ነው”** ይህ የግሪኩ ድርጊት ገላጭ ቦዝ አንቀፅ ሲሆ ትኩረት የሚያደርገውም የሐሰት አስተማሪዎች የካዱትን የኢየሱስን ተሰግዎ (ኢየሱስ እንደ ሰው እና እንደ አምላክ) እና መሥዋዕት የተሞላበት ሞቱን ነው፡፡

▣ **“በውኃና በደም”** “ውሃ” የሚለው የኢየሱስን አካላዊ ውልደት (ዮሐንስ 3:1-9)፤ “ደግሞ” የሚለው የእርሱን አካላዊ ሞት የሚያመለክት ይመስላል፡፡ የግኖስቲክ የኑፋቄ አስተማሪዎ የኢየሱስን እውነተኛ ሰውነት በሚቃወሙበት አውድ እነዚህ ሁለት ልምምዶች የእርሱን ሰብአዊነት የሚያጠቃልሉና የሚያሳዩ ናቸው፡፡

ሌላው ከኖስቲክ የኑፋቄ አስተማሪዎች ጋር የሚዛመደው አማራጭ (*ceriNthus*) ደግሞ “ውኃ” የኢሱስን ጥምቀት ማመልከቱ ነው፡፡ እርሱም ይህን ሲያፀኑ “የክርስቶስ መንፈስ” ሰው ወደሆነው ኢየሱስ በጥምቀቱ መጥቶ (ውሃ) ከዚያም ሰው የሆነው ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሲሆን ተለየው ይላሉ (ደም፣ ለሚለው ጥሩ ማብራሪያ ማጠቃለያ በNASB የጥናት መጽሐፍቅዱስ፤ ገጽ 185 ላይ ይመልከቱ)፡፡

ሦስተኛው አማራጭ ደግሞ ከኢየሱስ ሞት ጋር የሚዛመድ ነው፡፡ ኢየሱስ ጎትን በጦር ሲወጋ “ደምና ውሃ” ወጣ ይላል (ዮሐንስ 19:34)፡፡ የሐሰት አስተማሪዎችም ምትክነት ያለበትን የኢየሱስን ሞት ዝቅ ያደረጉበት ሊሆን ይችላል፡፡

▣ **“የሚመሰክረው መንፈስ ነው”** የመንፈስ ቅዱስ ሚና ወንጌልን መግለጥ ነው፡፡ እርሱም ሰለኃጢአት የሚወቅስ፣ ወደ ክርስቶ የሚመራ፣ በክርስቶ አካል የሚያጠምቅ እና ክርስቶስ በአማኞች ሕይወት ውስጥ እንዲሳል የሚያደርግ የሥላሴ አካል ነው (ዮሐንስ 16:7-15)፡፡ መንፈስ ሁል ጊዜ የሚመሰክረው ስለ ራሱ ሳይሆን ስለ ክርስተቶስ ነው (ዮሐንስ 15:26)፡፡

▣ **“መንፈስም እውነት ነውና”** (ዮሐንስ 14:17፤15:26፤16:13፤1ዮሐንስ4:6)፡፡ ለተጨማሪ የጥናት ርዕስ 6:55 እና 173ን ይመልከቱ፡፡

**5:7** ይህ በእንግሊዘኛ ትርጉሞች ላይ ቁጥር 6፤7 እና 8 የትመጀመርና ማብቃት እንዳለባቸው ያለውን የተወነ ግራ መጋባት ነው፡፡ በኪንግ ጄምስ ትርጉም ላይ የሚገኘው የቁጥር 7 ክፍል ላይ “በሰማይ አብ፣ ቃሉ እና መንፈስ ቅዱስ ሦስቱም በአንድ ይስማማሉ” የሚለው በሦስቱ ዋና ዋና በሆኑት የጥናት ግሪክ የአዲስ ኪዳን ምንጮች ውስጥ አይገኝም፤ አሌክሳንድሪነስ (A)፣ ቫቲካነስ (B)፣ ወይም ሳይነይስቲካስ (N) ወይም በቤዛንታን ተዛማዊ ምንጮች ውስጥም አይገኙም፡፡

1. Ms 61፤ በ16ኛው ክፍለዘመን ቀን ያለው
2. Ms 88 በ12ኛው ክፍለ ዘመን የተመዘገበ፤ በዚህም ህዳጉ ከኃላ በመጣ አካል የገባ
3. Ms 629፣ በ14ኛው ወይም በ15ኛው ክፍለ ዘመን የተመዘገቡ
4. Ms 635 በ11ኛው ክፍለ ዘመን የተመዘገበ በዚህም ህዳጉ በኃላ በመጣ አካል ተጨምሮ የገባ

ይህ ጥቅስ በሥላሴ የአስተምህሮ ክርክሮች ላይ በየትኛው የቀደመችው የቤተክርስትያን አባቶች ዘንድ እንኳ አልተጠቀሰም፡፡ ከአንድ የላቲን ድህረ ምንጭ በስተቀር (*sixto-clemeNtiNe*) በሌሎች የጥንት ትርጉሞች ውስጥም የለም፤ በላቴን ብሉይ ወይም በጀሮም ቩልጌት ውስጥም አይገኝም፡፡ ነገር ግን በ385 ዓ.ም ላይ የሞተው ስፔይናዊው የኑፋቄ አስተማሪ ፕሪሲሊያን በፃፈው የድርሰት ፅሑፍ ላይ ይገኛል፡፡ ጥቅሱ በ5ኛው ክፍለ ዘመን በሰሜን አፍሪካ እና በጣልያን ባሉ የቤተክርስትያን አባቶች ዘንድ ተጠቅሷል፡፡ በግልፅ ለመነጋገር፣ ይህ ጥቅስ በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት በተፃፈው የመጀመሪያው የዮሐንስ መልዕክት አንዱ ክፍል አይደለም፡፡

የአንድ አምላክ (ምኖቴይዝም) በሦስት ስብዕናዎች መገለጥ (አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ) ይህ ጥቅስ ተቀባይነት ስላጣ በመጽሐፍ ቅዱሣውው አስተምህሮ ላይ ጥቅስ ተቀባይነትን ስላጣ በመጽሐፍ ቅዱሣዊው አስተምህሮ ላይ የሚያመጣው ተፅዕኖ የለም ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ ሥላሴ የሚለውን ቃል በፍፁም ባይጠቀመውም ብዙዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ስለ ሦስቱ የሥላሴ አካላት ተግባር አብሮ መሥራት ይናገራል፤

1. ኢየሱስ ሲጠመቅ (ማቴ 3:16-17)
2. ታላቁ ተልዕኮ (ማቴ 28:19)
3. የተላከው መንፈስ (ዮሐንስ 14:26)
4. ጴጥሮስ በበዓለ ሃምሳ ቀን ባደረገው ስብከት (ሐዋ 2:33-34)
5. ጳውሎስ ስለ ሥጋና ስለ መንፈስ ባደረገው ንግግር (ሮሜ8:7-10)
6. ጳውሎስ ስለመንፈሳዊ ሥጦታዎች ባደረገው ንግግር (1ቆሮ 12:4-6)
7. በጳውሎስ የጉዞ እቅድ (2ቆሮ 1:21-22)
8. በጳውሎስ ቡራኬ (2ቆሮ 13:14)
9. ጳውሎስ ስለ ዘመን ሙላት ባደረገው ንግግር (ገላ4:4-6)

10. ጳውሎስ ለአብ ባደረገው የምስጋና ፀሎት (ኤፌ 1:3-14)
11. ጳውሎስ አህዛብ ቀደም ሲል ተሌቴው እንደነበሩ በገለፀበት ንግግር (ኤፌ2:18)
12. ጳውሎስ ስለ እግዚአብሔር አንድነት ባደረገው ንግግር (ኤፌ 4:4-6)።
13. ጳውሎስ ስለ እግዚአብሔር መልካምነት ባደረገው ንግግር (ቲቶ 3:4-6)።
14. የጴጥሮ የመግቢያ ሰለምታ (1ጴጥ 1:2)።

በሥላሴ ርዕስ ላይ በዮሐንስ 14:26 ላይ ያለውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስ ይመልከቱ።

5:8 "*መንፈሱና ውኃው ደሙም ሦስት ናቸውና ሦስቱም በአንድ ይስማማሉ*" በብይ ኪዳን አንድን ነገር ለማፅደቅ ሁለት ወይም ሦስት ምሥክሮች ያስፈልጉ ነበር (ዘዳ 17:6፤19:15)። በዚህ ሥፍራ ደግሞ ኢየሱስ ፍፁም ሰውእና ፍፁም አምላክ ለመሆኑ የኢየሱስ ሕይወት ታሪካዊ ክስተቶች ቀርበዋል። በዚህ ጥቅስ ላይ "ውሃ" እና "ደም" ከ"መንፈስ" ጋር በተደጋጋሚ ተገልፀዋል። "ውሃ" እና "ደም" የሚሉ ቃላት በቁጥር 6 ላይ ተለልፀዋል። "መንፈስ" የሚለው እርግብ ስለወረደበት የኢየሱስን ጥምቀት ሊያመለክት ይችላል። እነዚህ ሦስቱ በሚወክሉበት ጉዳይ ላይ ትክክለኛ ታሪካዊ አገላለፅ ላይ የተወሰነ አለመስማማት ያለ ይመስል። ሦስቱም ነገሮች በአንፃሩ ደግሞ የኢየሱስን እውነተኛ ስብእና ከሚቃወሙት የሐሰት አስተማሪዎች ጋር የሚገኙ መሆን አለባቸው።

5:19 "ብ..." ይህ ሦስተኛ ሁኔታዊ አረፍተ ነገር ሲሆ ከፀሐፊው አስተያየት ወይም ለሥነ-ፅሑፋዊ ዓላማው ሲባል እውነት ተደርጎ የሚገመት ነው። ዮሐንስ የሚፅፍላቸው የመልዕክቱ ተቀባይ የሆኑት ቤተክርስትያናት ቀደም ሲል የግኖስቲክ የሐሰት መምህራን ስበከት ወይም ትምህርታቸውን በግልፅ ሰምተው ስለነበር ግራ መጋባት ነበረባቸው።

▣ "**የሰውን ምሥክር ብንቀበል የእግዚአብሔር ምሥክር ከእርሱ ይልቅ ይበልጣል**" ይህ የመለኮት ምስክርነት በዚህ አውድ የሚያመለክተው

1. የመንፈስ ቅዱስን ምሥክርነት
2. ኢየሱስ በምድር የነበረውን ሕይወቱን እና ሞቱን የሚመሰክሩ ሐዋርያት (ለምሳሌ፤ 1:-3)።

▣ "**ስለ ልጁ የመሰከረው**" ይህ የተጠናቀቀ ድርጊት አመልካች ግሥ ሲሆን በተዘዋዋሪ የሚያመለክተው በኃላፊ ጊዜ ወደ ድምዳሜ ደርሶ አሁንም ያለን ድርጊት ነው። ይህም ምናልባት የሚያመለክተው ኢየሱስ ሲጠመቅ (ማቴ3:17) ወይም በተራራው ላይ ሲለወጥ(ማቴ 17:5፤ ዮሐንስ 5:32፡37፤8:18) በድምፅ የተሰጠን ማረጋገጫ ወይም የሁለቱ በቃሉ ውስጥ መጠቀስ (ወንጌላት) ነው። በዮሐንስ 1:8 ላይ ስለ ኢየሱስ መመስከር የሚለውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስ ይመልከቱ።

5:10 "**በንፍሱ ምስክር አለው**" ይህንን ሐረግ በሁለት መንገዶች መተርጎም ይቻላል፤

1. መንፈስ በአማኞች ውስጥ ያለው ምስክርነት (ሮሜ 8:16)
2. የወንጌል እምነት(ራዕይ 6:10፤12:17፤19:10)።

በዮሐንስ 1:8 ላይ ለኢየሱስ መመስከር የሚለውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስ ይመልከቱ።

▣ "**ሐሰተኛ አድርጎታል**" ይህ ሌላው የተጠናቀቀ ድርጊት አመልካች ግሥ ነው። ሐዋርት ስለ ኢየሱስ የሚሰጡትን ምሥክርነት የሚቃወሙ እግዚአብሔርን ይቃወማሉ (ቁ12) ምክንያቱም እግዚአብሔርን ሐሰተኛ አድርገውታልና።

▣ "**ስላላመነ**" ይህ ሌላው የተጠናቀቀ ድርጊት አምልካች ሲሆን ዳግም ያልተወለዱትን ሰዎች ሁኔታ ላይ ትኩረት ያደርጋል።

5:11-12"**እግዚአብሔርም የዘላለምን ሕይወት እንደሰጠን**" ይህ የግሪኩ ድርጊት ገላጭ አመልካች ግስ ሲሆን ያለፈን ድርጊት ወይም የተጠናቀቀን ድርጊት ያመለክታል (ዮሐንስ3:16)። የዘላለም ሕይወት በዮሐንስ 17:3 ለይ ተገልጿል። በአንዳንድ ሁኔታዎች ሐረጉ የሚያመለክተው ኢየሱስ ራሱን (1:2፤5:20) ሲሆን በሌሎች ደግሞ በክርስቶስ ባላቸው እምነት (5:13፤ዮሐንስ 3:16) ከእግዚአብሔር የሚቀበሉት ሥጦታ ነው (2:25፤5:11፤ዮሐንስ 10:28)። አንድ ሰው በግሉ ከወልድ ጋር በእምነት ሳቀራኝ ከአብ ጋር ሕብረት ሊኖረው አይችልም።

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 5፥13-15)
**[13]የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሄር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ። [14]በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው። እንደ ፈቃድ አንዳች ብንለምን ይሰማናል። [15]የምለምነውንም ሁሉ እንዲሰማልን ብናውቅ ከእርሱ የለመነውን ልመና እንደተቀበልን እናውቃለን።**

5:13 "**በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ**" ይህ የአሁን ጊዜ ድርጊት ገላጭ በዚህ አንቀፅ ሲሆን ቀጣይነት ባለው እምነት ላይ ያተኩራል። ይህ ስሙን በጥንቆላ ወይም በሚስጢራዊ ሁኔታ መጠቀም (በእግዚአብሔር ሰዎች ላይ አይሁድ ያላቸው

ሚስጢራው አካሄድ፣ *kabbalah*) ሳይሆን ስምን ለግለሰብ ምትክበማድረግ ጥቅም ላይ ማዋል የሚለው የብሉይ ኪዳን አጠቃቀም ነው፡፡ በዮሐንስ 2:23 ላይ ተጨማሪ የጥናት ርዕስን ይመልከቱ፡፡

▣ **"ታውቁ ዘንድ"** ይህ የግሡን ድርጊት መጠናቀቅ ሁኔታ የሚያመለክት ነው (oida መጠናቀቅን የሚያሳይ መደብ አለው፣ ነገር ግን በአሁን ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ የአንድ ሰው ድነት ዋስትና ቁልፍ ሃሳብ የሆነ እና የ1ኛ ዮሐንስ መልዕክት ዓላማ ብዙ ጊዜ የተገለፀበት ነው፡፡ በጠቅላላው መልዕክት ውስጥ "ማወቅ" ተብለው የተተረጎሙ ሁለት የግሪክ ተመሳሳ ቃላት አሉ (*oida aNd giNõskõ*):: የዘላለም ሕይወት ዋስንና የሁሉም አማኞች ርዕስ ነው፡፡
ከዚህም ባሻገር ደግሞ ከቦታ እና ከባህል ዓውድ ምክንያት የተነሣ የድነት ዋስትናቸውን የማያውቁ እውነተኛ አማኞ መኖራቸው የሚታወቅ ነው፡፡ ይህም ጥቅስ በሥነ መለኮታዊ ሃሳቡ ከዮሐንስ ወንጌል ማጠቃለያ ጋር የሚመሳሰል ነው (20:31)፡፡

የማጠቃለያ ዓውዱ (5:13-20) አማኞች ሊያውቁ የሚገባቸው ሰባት ነገሮች ይዘረዝራል፡፡ ስለወንጌል ያላቸው እምነት ያላቸው የአለም እይታ በክርስቶስ ካላቸው እምነት ጋር ሲዋሃድ ለድነት ዋስትና መሠረት ነው፡፡

1. አማኞች የዘላለም ሕይወት አላቸው (ቁ.3 *oida* የተጠናቀቀ የድርጊት ሁኔታን የሚገልፅ)
2. እግዚአብሔር የአማኞችን ፀሎት ይሰማል (ቁ.15፤*oida*፤ የተጠናቀቀን ድርጊት አመልካች ግሥ)
3. እግዚአብሔር የአማኞችን ፀሎት ይመልሳል (ቁ.15፣ የተጠናቀቀ ድርጊት ገላጭ አመልካች ግስ)
4. አማኞች ከእግዚአብሔር ተወልደዋል (ቁ.18 *oida* የተጠናቀቀ ድርጊት ገላጭ አመልካች ግሥ)
5. አማኞች ከእግዚአብሔር የወጡ ናቸው (ቁ.19፣ *oida* የተጠናቀቀ ድርጊት አመልካች ግሥ)
6. አማኞች መሲሑ መጥቶ መረዳትን እንደሰጣቸው ያምናሉ (ቁ.29፣ *oida* የተጠናቀቀ ድርጊት አመልካች ግሥ)
7. አማኞች እውነተኛውን ያውቃሉ፡- አብን ወይም ወልድን ቢሆን (ቁ.20 *giNaskõ* የተጠናቀቀ ድረጊት ሁኔታን የሚገልፅ ግሥ)

## ልዩ ርዕስ፡ የድነት ማረጋገጫ

ሀ. አማኞች መዳናቸውን ሊያውቁ (1ዮሐንስ 5:13) ይችላሉ? አንደኛ ዮሐንስ ሦት መመዘኛዎች አሉት
   1. አስተምህሮ (እምነት) (ቁ. 1:5፡10፤2:18-25፤ 4:1-6፡ 14-16፤ 5:11-12)
   2. የኑሮ ዘይቤ (መታዘዝ)(ቁ. 2-3፤2:3-6 ፤ 3:1-10፤ 5-18)
   3. ማህበራዊ (ፍቅር) (ቁ. 2-3፤ 2:7-11፤ 3:11-8፤ 4:7-12፡16-25)

ለ. የድነት ማረጋገጫ ዲኖሚኔሽናል ጉዳይ ሆኗል
   1. ጆን ካልቪን የድነት ማረጋገጫን መሠረት ያደረገው በእዚአብሔር ምርጫ ላይ ነው፡፡ እርሱም በዚህ ሕይወት ውስጥ በፍፁም እርግጠኞች ስንሆን አንችልም፡፡
   2. ጆን ዋስሊይ የድነት ማረጋገጫን የመሠረተው በኃይማኖታዊ ልምምድ ላይ ነበር፡፡ እርሱ እንደሚለው ከምናውቀው ኃጢአት በላይ የመኖር ችሎታ አለን ይላል፡፡
   3. የሮም ካቶሊክ እና የክርስቶስ ቤተክርስትያን የድነት ማረጋገጫን የመሠረቱት ሥልጣን ባሉት ቤተክርስትያን ላይ ነበር፡፡ አንድ ሰው ያለበት ቡድን ለድነት ማረጋገጫው ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡
   4. አብዛኞቹ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት የመጽሐፍ ቅዱስ ተስፋዎችን በአማኞች ህይወት ውስጥ በሚከሰተው የመንፈስ ፍረረ ጋር ያገናኙታል (ገላ 5፡22-23)፡፡

ሐ. እኔ እንደሚመስለኝ የወደቀው የሰው ዘር የመጀመሪያው የድነት ማረጋገጫው የሚያያዘው ከሥላሴ አምላክ ባህሪይ ጋር ነው፡፡
   1. የእግዚአብሔር አብ ፍቅር
      ሀ. ዮሐንስ 3:16፤10:28-29
      ለ. ሮሜ 8:31-39
      ሐ. ኤፌሶን 2:5፤8-9
      መ. ፊልጲስዮስ 1:6
      ሠ. /ጴጥሮስ/:3-5
      ረ. ዮሐንስ 4:7-21
   2. የእግዚአብሄር ወልድ ድርጊቶች
      ሀ. በምትካችን መሞቱ
         1. ሐዋርያት ሥራ 2:23
         2. ሮሜ 5:21
         3. 2ቆሮንቶስ 5:21
         4. 1ዮሐንስ 2:2፤4:9010
      ለ. የሊቀካህናት ፀሎት (ዮሐንስ 17:12)

ሐ. ቀጣይነት ያለው ምልጃ
1. ሮሜ 8:34
2. ዕብራዊያን 7:25
3. 1ዮሐንስ 2:1
3. የእግዚአብሔር መንፈስ አገልግሎ
ሀ. መጥራት (ዮሐንስ 6:44፡65)
ለ. ማተም
1. 2ቆሮንቶስ 1:22፤5:5
2. ኤፌሶን 1:13-14፤ 4:3
ሐ. ማረጋገጫን መስጠት
1. ሮሜ 8:6-17
2. 1ዮሐንስ 5:7-13

መ. ነገር ሰዎች እግዚአብሔር ለሚሰጣቸው የቃል ኪዳን (መጀመሪያም ደግሞም ቀጣይነት ባለው ሁኔታ) ምላሽ መስጠት አለባቸው፡፡
1. አማኞች ከኃጢአታቸው መመለስ አለባቸው (ንስሐ)፤ በክርስቶስ አማካኝነት ወደ እግዚአብሔር መምጣት አለባቸው (እምነት)
ሀ. ማርቆስ 1:15
ለ. ሐዋርያት 3:16፡19፤ 20:21

2. አማኞች በክርስቶ የተሰጣቸውን የእግዚአብሔርን ቸርነት መቀበል አለባቸው
ሀ. ዮሐንስ 1:12፤ 3:16
ለ. ሮሜ 5:1 (በምሳሌነት 10:9-13)
ሐ. ኤፌሶን 2:5፡8-9
3. አማኞች በእምነታቸው መቀጠል አለባቸው
ሀ. ማርቆስ 13:13
ለ. 1ቆሮንቶስ 15:2
ሐ. ግላትያ 6:9
መ. ዕብራዊያን 3:14
ሠ. 2ጴጥሮስ 1:10
ረ. ይሁዳ 20-21
ሰ. ራዕይ 2:2-3፡ 7፡10፡17፡19-26፤ 3:5፡10፡11፡21
4. አማኞች ሦስቱመ መመዘኛዎች ያጋጥሟቸዋል
ሀ. የእመተምሕሮ (ቁ.5:10፤2:18-25፤4:1-6፡14-16)
ለ. የኑሮ ዘይቤ (ቁ. 2-3፤ 2:3-6፤ 3:1-10)
ሐ. ማህበራዊ (ቁ. 2-3፤ 2:7-11፤ 3:11-18፤ 4: 7-12፡ 16-21)

ሠ. የድነት ማረጋገጫ አስቸጋሪ ነው፤ ምክንያቱም
1. አማኞች ብዙውን ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያተሰጠን ተስፋ ይፈልጋሉ፡፡
2. አማኞች ብዙውን ጊዜ ወንጌልን አይረዱም
3. አማኞች ብዙውን ጊዜ በፈቃዳቸው በኃጢአት ፀንተው ይኖራሉ (1ቆሮ3:10-15፤ 9:27፤ 1ጢሞ 1:19-20፤ 2ጢሞ 4:10፤ 2ጴጥ1:8-11)
4. አንዳንድ የስብዕና አይነቶች (እንከን የለሽ መሆን የሚፈልጉ) ከሁኔታ ጋር ያልተያያዘን የእግዚአብሔርን ፍቅር እና ቸርነት በፍፁም ሊቀበሉ አይችሉም)
5. በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሐሰት ምሥክርነቶች ይገኛሉ (ማቴ13:3-23፤ 7:21-23፤ ማር4:14-20፤ 2ጴጥ 2:19-20፤ 1ዮሐ2:18-19

▣ 5:14 **"በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው"** ይህ በተደጋጋሚ የሚነሳ መልዕክት ነው (2:28፤3:21፤4:17)፡፡ እግዚአብሔር ፊት ስንቀርብ (ዕብ 4:16) ስንቀርብ የሚኖረንን ድፍረት ወይም ነፃነት ይገልፃል፡፡ በ2:28 ላይ ለውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስ ይመልከቱ፡፡

▣ **"ብ"** ይህ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ አረፍተነገር ሲሆን ድርጊት ለመፈፀም እድል መኖሩን ያመለክታል፡፡

▣ **"እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንለምን"** በዮሐንስ ንግግሮች ውስጥ አማኝ እግዚአብሔርን ለመፈለግ ያለው ችሎታ የተገደበባቸው አይመስልም፡፡ እንዴት እና ለምን ዓላማ እንደሚፀልይ የሚሉት የእውነተኛ አማኝ ማስረጃዎች ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ በተጨማሪነት ፀሎት የራሳችን ፈቃድ እንዲፈፀምልን የምንፀልይበት ሳይሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ በህይወታችን እንዲፈፀም የምጠይቅበት እንደሆነ መገንዘብ እንችላለን (3:22፤ማቴ 6:10፣ ማር 14:36)። በ3:22 ላይ ሙሉ ማብራሪያውን ይመልከቱ። ለተጨማሪ የጥናት ርዕስ በዮሐንስ 4:34 የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚለውን፤ እንዲሁም ደግሞ በ3:22 ላይ ደግሞ ፀሎት፤ ያተገደበ ነገር ግን የተገደበ የሚለውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስ ይመልከቱ።

**ልዩ ርዕስ: የምልጃ ፀሎት**

I. *መግቢያ*

ሀ. ከኢየሱስ ምሣሌነት የተነሣ ፀሎት ታላቅን ትርጉም ያዘለ ነው።

1. የግል ፀሎት፤ ማርቆስ 1÷35፤ ሉቃስ 3÷21፤ 6÷12፤ 9÷29፤ 22÷29-46።
2. መቅደሱን ማጥራት፤ ማቴ21÷13፤ ማር11÷17፤ ሉቃስ 19÷46
3. የፀሎት ሞዴል፤ ማቴ 6÷5-13፤ ሉቃስ 11÷2-4።

ለ. ፀሎት ማለት አንድ ተጨባጭ ነገርን ስብዕና ባለው፣ ስለ እኛ ግድ በሚለው በእኛ ምትክ ሊደርግልን ፈቃደና በሆነ አምላክ ፊት የምንፀልየው ነው።

ሐ. እግዚአብሔር በብዙ ሥፍራዎች ውስጥ (ያዕቆብ 4÷2) የልጆቹን ፀሎት ለመመለስ ራሱነ ገድቧል።

መ. የፀሎት ዋናው ዓላማ ከሥላሴ አምላክ ጋር የምናደርገው ሕብረት እና የምናሳፈው ጊዜ ነው።

ሠ. የፀሎት ገደቡ አማኞችን የሚመለከተው ማንኛውም ሰው ወይም ነገር ነው። አንድ ጊዜ አምነን ልንፀልይ እንችላለን ወይም የምንፀልይበተ ጉዳይ በሐሳባችን ሲመላለስም ደጋግመን ልንፀልይ እንችላለን።

ረ. ፀሎት በርካታ ነገሮችን ሊያካትት ይችላል

1. የሥላሴ አምላክን ማወደስ እና ማድነቅ
2. እግዚአብሔርን ስለ መገኘቱ ሕብረት ስለማድረጉ እና ስለቸርነቱ ማመስገን
3. ያለፈውንና የአሁኑን ኃጢአታችንን መናዘዝ
4. የሚሰሙንን መሻቶች እና የሚያስፈልጉንን ነገሮች መጠየቅ
5. የሌሎችን ፍላጎቶ በአብ ፊት በማቅረብ በምልጃ መፀለይ

ሰ. የመልጃ ፀሎት ረቂቅ ነገር ነው። እኛ ከምናደርግላቸው ይልቅ የምንፀልይላቸውን ሰዎች እግዚአብሔር በበለጠ ይወዳቸዋል። ነገር ግን የእኛ ፀሎት ብዙውን ጊዜ በእኛ ብቻ ሳይሆን በእርሱ ውስጥ ለውጥን፣ ምላሽን መሻትን ይፈጥርባቸዋል።

I. *መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ*

ሀ. ብሉይ ኪዳን

1. አንዳንድ የምልጃ ፀሎት ምሣሌዎች
   - ሀ. አብርሃም ስለ ስም የለመነበት፤ ዘፍ 18÷22
   - ለ. ሙሴ ለእስራኤል ፀለየ
     - (1) ዘፀአት 5÷22-23
     - (2) ዘፀአት 32÷31
     - (3) ዘዳግም 5÷5
     - (4) ዘዳግም 9÷18፡25
   - ሐ. ሳሙኤል ለእስራኤል ፀለየ፤
     - (1) 1ሳሙኤል ለ7÷5-6፡8-9
     - (2) 1ሳሙኤል 12÷16-23
     - (3) 1ሳሙኤል 15÷11
   - መ. ዳዊት ስለራሱ ህፃን ፀለየ፤ 2ሳሙኤል 12፡16-18
2. እግዚአብሔር የሚማልዱትን ይፈልጋል፣ ኢሳያስ 59÷16
3. የምናወውቀው፣ ያልተናዘዝነው ኃጢአት ወይም ንስሐ የማይገባ ልብ ፀሎታችን ላይ ተፅዕኖን ያመጣል።
   - ሀ. መዝ 66÷18
   - ለ. ምሳሌ 28÷9
   - ሐ. ኢሳያስ 59÷1-2፤ 64÷7

ለ. አዲስ ኪዳን

1. የወልድ እና የመንፈስ የምልጃ አገልግሎት
   - ሀ. ኢየሱስ
     - (1) ሮሜ 8÷34
     - (2) ዕብራዊያን 7÷25
     - (3) 1ዮሐንስ 2÷1
   - ለ. መንፈስ ቅዱስ፣ ሮሜ 8÷26-27
2. የጳውሎ የምልጃ አገልግሎት
   - ሀ. ለአይሁድ ይፀልያል

(1) ሮሜ 9÷1
(2) ሮሜ 10÷1
ለ. ለቤተክርስትያናት ይፀልል
(1) ሮሜ 1÷9
(2) ኤፌሶን 1÷16
(3) ፊልጲስዮስ 1÷3-4÷9
(4) ቅላስይስ 1÷3፡9
(5) 1 ተስሎንቂ 1÷2-3
(6) 2 ተስሎንቄ 1÷11
(7) 2ጢሞቴዎስ 1÷3
(8) ፊልሞስ፤ ቁ.4
ሐ. ጳውሎስ ቤተክርስትያናት ለእርሱ እንዲፀልዩለት ጠይቋል
(1) ሮሜ 15÷30
(2) (2ቆሮንቶስ 1÷11
(3) ኤፌሶን 6÷19
(4) ቆላስይስ 4÷3
(5) 1ተስሎንቄ 5÷25
(6) 2ተስሎንቄ 3÷1
3. የቤተክርስትያን የምልጃ አገልግሎት
ሀ. አንዱ ስለሌላው ይፀልያል
(1) ኤፌሶን 6÷18
(2) 1ጢሞቴዎስ 2÷1
(3) ያዕቆብ 5÷16
ለ. ለተለያዩ ወገኖች ፀሎት አስፈልጎ ነበር
(1) ለጠላቶቻችን፣ ማቴ÷44
(2) ለክርስትያን ሠራተኞች፤ ዕብራዊያን 13÷18
(3) ለገዢዎች፣ 1ጢሞቴዎስ 2÷2
(4) ህመምተኛና ያዕ 5፡13-16
(5) ወደኋላ የተመለሱ 1ዮሐ 5፡16
የተነሳንበት ዓላማ /ፍላጎት/
1. አለማወላወል፣ ማቴ 21÷22፤ ያዕቆብ 1÷6-7
2. ትሑት እና ንስሐ የሚገባ ልብ፣ ሉቃ 18÷9-14
3. የሚጎድለንን መጠየቅ ያዕቆብ 4÷3
4. ራስ ወዳድነት፣ ያዕቆብ 4÷2-3
ሐ. ሌሎች ሁኔታዎች
1. ጽናት
ሀ. ሉቃስ 18÷1-8
ለ. ቆላስይስ 4÷2
2. ሳያቋርጡ መጠየቅ
ሀ. ማቴዎስ 7÷7-8
ለ. ሉቃስ 11÷5-13

5:15 "ብ" ይህ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ አረፍተ ነገር ሲሆ (ነገር ግን heaN እና አምላካቹ ጋር፤ የኤ.ቲ.ሮቨርትሰንን፣ *Word Pretures iN the New TestameNt* (ገጽ.243) የሚለውን ይመልከቱ ከፀሐፊው እይታ ወይም ስሥነ-ፅሁፋዊው ዓላማ ሲባል እውነት ነው ተብሎ የተገመተ ነው፡፡

1. *ei* ከሚለው ይልቅ *eaN* የሚለውን ግሥ ይዟል (ሐዋ 8፡31፤1ተስ 3:8)
2. ከግሱ ሁኔታ አመልካ ጋር eaN ተጣምሮ ይገኛል (መጠየቅ)፤ ይህም ለሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተነገር ሰዋሰዋዊ አወቃቀር የተለመደ ነው፡፡
3. በቁጥር 14 እና 16 ላይ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገሮች አሉ፡፡
4. የክርስትያን ፀሎት ሥነ መለኮት ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የተያያዘ ነው (ቁ.14) እንዲሁም ደግሞ ከኢየሱስ ስም ጋር ይያያዛል (ቁ.13)

▣ *"እናውቃለን"* ይህ ደግሞ ሌላው የተጠናቀቀ ድርጊት አምልካች ግሥ ሲሆን ከቁጥር 14 ጋር የሚስተያይ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሰምቶ ምላሽ ለልጆቹ የሚሰጥበት አማኝ ባው የድነት ማረጋገጫ መሠረት ነው፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 5፡ 16-17
**[16] ማንም ወንድሙን ሞት የማይገባውን ኃጢአት ሲያደርግ ቢያየው የለምን÷ ሞትም የማይገባውን ኃጢአት ላደረጉ ሕይወት ይሰጥለታል፡፡ ሞት የሚገባው ኃጢአት አለ ስለዚያ እንዲጠይቅ አልልም፡፡ [17]ዓመፃ ሁሉ ኃጢአት ነው÷ ሞትም የማይገባው ኃጢአት አለ፡፡**

5:16 "ቢ..." ይህ ሦተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተነገር ሲሆን ድርጊት ለመፈፀም እድል መኖሩን ያመለክታል፡፡ ቁጥር 16 ትኩረት የሚያደርገው ለክርስትያን ጓደኞቻችን ልንፀልይላቸው እንደሚስፈልገን (ገላ 6:1፤ ያዕቆብ 5:13-18) ይህም በተወሰኑ ገደቦች ሊሆን እንደሚገባው (ለሞት ለሚደርስ ኃጢአት ሳይሆን)፤ ይህም ደግሞ ከሐሰት አስተማሪዎች ጋር የተያያዘ ይመስላል (2ጴጥሮስ2)፡፡

▣ ***"ማንም ወንድሙን ሞት የማይገባውን ኃጢአት ሲያደርግ ቢያየው"*** ዮሐንስ በርካት የኃጢአት ምድቦችን ይዘረዝራል፡፡ አንዳንቹ የሚገናኙት (1) ሰውዬው ከመለኮት ጋር ባለው ግኑኝነት (2) ሰውየው ከሌሎች አማኖች ጋር ካለው ሕብረት ጋር እንዲሁም ደግሞ (3) ከዓለም ጋር ካለ ግኑኝነት ነው፡፡ የመጨረሻው ኃጢአት በኢየሱስ ክርስቶ ያለውን እምነት መቃወም ነው፡፡ ይህ ነው ሞት የሚገባው ኃጢአት ደብሊው.ቲ.ኮርነርስ *ChristiaN DoctriNe* በሚል መፅሐፋቸው እንዲህ ይላሉ፤

> "አለማመን ሲባል አንድን አስተምህሮ ወይም ቀኖናን አለመቀል ማለት አይደለም፡፡ አንድ ሰው ምዕላዊም ሆነ መንፈሳዊ መረዳትን ሲቃወም፤ል በተለይም ደግሞ ያ መረዳት ከኢሱስ ክርስቶስ አንፃር ሲሆን አለማን ይባላል፡፡ እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ስለራሱ የሰጠውን የመጨረሻ መገለጥ መቃወም ማለት ነው፡፡ ይህም መረዳት ግልፅ እነ ሆን ተብሎ የሚፈፀም ከሆነ ሞት የሚገባው ኃጢአት ይሆናል (1ዮሐንስ5:13-17)፡፡ በመሆም ይህ ምዕላዊ የሆነ ራስን ማጥፋት ነው፡፡ የራስን መንፈሳዊ ዓይኖች እንደማውጣት ይቆጠራል፡፡ ይህም ከፍተኛ የመረዳት ባለጠግነት ከሌሊ በስተቀር ሊሆን የሚችል አይደለም፡፡ ክርስቶስ የእግዚአብሔር መገለጥ መሆኑን እያወቀ ሆንብሎ በፈቃደኝነት መገለጡነ መቃወም ነው፡፡ ይህ ሆን ብሎ በፈቃደኝነት መገለጡነ መቃወም ነው፡፡ ይህ ሆን ብሎ በራስ ላይ አደጋን መጋበዝ /መጥራት/ ነው" (ገጽ 135-136)፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ ኃጢአት ሞት የሚገባው ምንድ ነው?**

*ሀ. የሥነ-አፈታት ምልከታዎች*
1. ትክክለኛ መረዳት ይኖር ዘንድ ከ1ኛ ዮሐንስ ታሪካዊ ዳራ ጋር መዛመድ አለበት
   ሀ. የግኖስቲክ የኑፋቄ አስተማሪዎች በቤተክርስትያናት መኖር (2:19፡26፤3:7፤ 2ዮሐንስ 7)
      (1) ‹‹ሴሬንቲያን›› ግኖስቲክ ሰው የሆነው ኢየሱስ ሲጠመቅ የክርስቶስን መንፈስ ተቀበለ ከዚያም ደግሞ የክርስቶስ መንፈስ በመስቀል ላይ ከመሞ በፊት ትቶት ሄደ ብለው ያስተምሩ ነበር (5:6-8)
      (2) የደሴቲክ ግኖስቲክ ደግሞ ኢየሱስ መለኮታዊ መንፈስ እንጂ እውነተኛ ሰው አልነበረም ይላሉ(1:1-3)፡፡
      (3) ግኖስዚም ስለ ሰው ልጅ አካል በሁለተኛ ክፍለ ዘመን በሁለት መንገድ የገልፀዋል፡፡
         (ሀ) ድነት ለአእምሮ የሚገለጥ እውነት ስለሆነ የሰው አካል  ከመንፈሳዊው ዓለም ጋር አብሮ ሊሄድ አይችልም፡፡ ስለዚም ምንም ነገር ቢያስፈልገው ሊያደርገው የሚችለው ነገር ማለት ነው፡፡ እነዚህ ብዙውን ጊዜ *aNtiNomiaN* (አንቲኖሚያን) ወይም አጉራ ዘለል (liberti*N*e) ግኖስቲኮች ይባላሉ፡፡
         (ለ) ሌላው ወገን ደግሞ ሲደመድም ሰውነት ከመጀመሪያውም ክፉ ስሆነ (የግሪኮች አስተሳሰብ) ማንኛውም አካላዊ ፍላጎ ወይም መሻት ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፡፡ እነዚህም ባህታዊያን ግኖስቲኮች ይባላሉ፡፡
   ለ. እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች ቤተክርስቲያንን ቢለቁም (2:19) ተፅዕኖአቸው አላበቃም፤
2. ትክክለኛ ግንዛቤ ከጠቅላላው የመፅሐፍ ሥነ-ፅሑፋዊ ዓውድ ጋር የሚዛመድ መሆን አለበት
   ሀ. አንደኛ ዮሐንስ የተፃፋ የሐሰት አስተማሪዎችን ለመቃወም እና እውነተና አማኖች ያላቸውን ዘላለማዊ የድነት ለማረጋገጥ ነበር፡፡
   ለ. እነዚህ ሁለት ዓላማዎ በእውነተኛ አማኞች መመዘኛዎች ውስጥ ሊታዩ ይችላሉ፤
      (1) አስተምህሮታዊ
         (ሀ) ኢየሱስ በእውነት ሰው ነበር (1:1-3፤4:14)
         (ለ) ኢየሱስ በእውነት አምላክ ነበር (1:2፤5:20)
         (ሐ) ሰዎች ኃጢአተኞች ከመሆናቸው በላይ ለቅዱስ እግዚአብሔርም ተጠያቂነት አላቸው (1፥6:10)
         (መ) ሰዎች ይቅርታን አግኝተው በእግዚአብሔር ፊት በጽድቅ ይሆናል ይህም ሊሆን የሚችለው
            i. በኢየሱስ ሞት (1:7፤2:1-2፤3:16፤4:9-10፤ 14፤5:6-8)

ii. በኢየሱስ በማመን (1:9፤3:23፤4:15፤5:1፡4-5፡10-12:13)

(2) ተግባራዊ (አዎንተዊ)

(ሀ) በህይወት ዘይቤ የሚለጥ መታዘዝ (2:3-5፤ 3:33:24፤5:2-3)

(ለ) በህይወት ዘይቤ የሚገለጥ ፍቅር (2:10፤3:11፡14፡18:23፤ 4:7፡11-12፡16-18፡21)

(ሐ) በህይወት ዘይቤ ክርስቶስን መምሰል (በፈቃዱ ኃጢአትን አይፈፅምም፡ (1:7፤ 2:6፡29፤ 3:6-9፤ 5:18)

(መ) በሕይወት ዘይቤ የተገለጠ ክፋትን ማሸነፍ (2:13፡14፤4:4፤5:4

(ሠ) ቃሉ በእረነርሱ ይኖራል (1:10፤2:14)

(ረ) መንፈሱ አላቸው (3:24፤4:4-6፡13)

(ሰ) ፀሎታቸው ይመለሳል (5:14-15)

(3) ተግባራዊ (አሉታዊ)

(ሀ) በኑሮ የሚገለጥ ኃጢአት (3:8-10)

(ለ) በተግባር የሚታይ ጥላቻ (2:9፡11፤3:15፡ኸ))

(ሐ) በተግባር የሚታይ አለመታዘዝ (2:4፤3:4)

(መ) ዓለምን መውደድ (2:15-16)

(ሠ) ክርስቶ መካድ (አብንና ወልድን ይክዳል፤ 2:22-23፤ 4:2-3፤ 5:10-12)

3. ትክክለኛ መረዳት ተጓደኝ ከሆነው የተለየ ጥቅስ ጋር መዛመድ አለበት (5፤16-17)

ሀ. በቁጥር 16 ላይ ‹‹ወንድም›› የሚለው ቃል ሞት የማገባውን ኃጢአት ለሚያደርጉ ወይም ሞት የሚገባውን ኃጢአት የሚያደርጉትን የሚመለከት ነው?

ለ. ኃጢአትን የሚሠሩ በአንድ ወቅት የቤቴክርስትያን አባላት ነበሩ (2:19)?

ሐ. የሚከተሉት ጠቀሜታ ምንድ ነው?

(1) ‹‹ኃጢአት›› ከሚለው ጋር ምንም መስተፃምር አለመኖሩ

(2) ‹‹ማየት›› የሚለው ቃል እንደ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ከግሪኩ ድርጊት ገላጭ አመልካች ግሥ ጋር መጣመሩ?

(መ) አንድ ኃጢአትን የሰራው ሰው ራሱ በዓሉ ንስሐ ሳይገባ ሌላው ክርስትን በፀለየበት ፀሎት (ያዕቆብ 5:15-16) የዘላለም ሕይወትን እንዴት (*zôê*) ሊያገኝ ይችላል?

(ሠ) ቁጥር 17 ከኃጢአት አይነቶች ጋር እንዴት ይዛመዳል (ሞት የሚገባው፤ ሞት የማገባው)?

ለ. ሥነ-መለኮታዊ ችግሮች

1. አንድ ተርጓሚ ይህንን ጥቅስ ቀጥሎ ካሉት ጋር ማገናኘት አለበት?

ሀ. በወንጌላት ውስጥ የተጠቀሰው ‹‹ይቅር የማይባል ኃጢአት››?

ለ. በዕብራዊያን 6 እና 10 የተጠቀሱ ‹‹ከጌታ ቤት የወጡ›› ከሚለው?

የ1ኛ ዮሐንስ መልዕክት ዓውድ ኢየሱስ በነበረበት ወቅት ከነበሩት ፈረሳዊያን ይቅር የማይባል ኃጢአት (ማቴ 12:22-27፤ ማር3:2-29) እና በዕብራዊያን 6 እና 10ላ ከተጠቀሱት ያላመኑ አይሁድ ጋር የሚነፃፀር ይመስላል፡፡ እነዚህ ሦስቱ ወገኖች (ፈሪሳዊያን፤ ያላመኑ አይሁድ እና ግኖስቲክ የሐሰት መምህራን) ወንጌልን በግልፅ ሰምተዋል፤ ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስን ለማመን አልፈለጉም፡፡

2. የዘመናችን የዲኖሚኔሽን ጥያቄዎች ይህንን ጥቅስ ለማየት ሥነ-መለኮታዊ ልዩነት መፍጠር አለባቸው?

ኢቫንጀሊካሊዝም የክርስትናን ልምምድ ጀምሬ ከሚገባው በላይ አጉልቶ የእውነተኛ እውነት በኑሮ ውስጥ መገለጥን ግንቸል ብሏል፡፡ የዘመናችን ሥነ-መለኮታዊ ጥያቄዎች የመጀመሪያዎቹን ዘመን ክርስትያኖችን ባስደነገጠ ነበር፡፡ እኛ ሁል ጊዜም በተመረጡ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ላይ እርግጠኞች መሆን የምንፈልግ፣ እንዲሁም ደግሞ ተገቢ መስሎ ከታየን ድምዳሜ አንፃር መሠረት ልንይዝ እንሻለን፡፡

የእኛ ሥነ-መለኮታዊ ጥያቄዎች፣ ጥርጣሬዎች፣ ልዩነቶች የሚያንፀባርቁት ነገር ቢኖር ዋስትና ማጣታችንን ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱ ከመሰጠን መረጃ ይልቅ የበለጠ መረጃን ስለምንፈልግ ሥርዓትን የተከተለው ሥነ-መለኮታችን ጥቂት ጥቅሶን ከመጽሐፍ ቅዱስ በመቆንጠር አመክንዮን፣ ለየት ያለ ይክትሪንን እና የእኛ ያሆነው በማጣመር ትልቅ ድርን እናደራለን፤

ኢየሱስ በማቴዎስ 7እና በማርቆስ 7 ላይ የተነገረች ቃላት ለቀደመችው ቤተክርስቲያን በቂ ነበር፤ ኢየሱስ የሚፈልገው ደቀመዛሙርትን እንጂ ውሳኔዎን፣ የረጅም ጊዜ የሕይወት ዘይቤ እምነት ወይም የአጭር ጊዜ ስሜታዊ እምነትን አይደለም (ማቴ13:10-23፤ ዮሐንስ8:31-59)፡፡ ክርስትና ትናንትና ብቻ የተደረገ ድርጊት በንስሐ፣ በእምነት፣ በመታዘዝ እና በመፅናት የሚሄድ ቀጣይነት ያለው ሕይወት ነው፡፡ ክርስትና መንግሥተ ሰማን ለመጨስ ትናንትና የገዛነው ትኬት ወይም አንድን ሰው ራስን በራስ ወዳድነት ከተምነው ሕይወቱ እና አምላክ የለሽ ኑሮ ራሱን ይጠብቅ ዘንድ የሚገዛው የእሳት አደጋ ኢንሹራንስ አይደለም፡፡

3. ኃጢአት ሞት የሚገባው አካላዊ ወይስ ዘላለማዊ ሞትን ያመለክታል? ዮሐንስ zôêየሚለው ቃል በዚህ ዓውድ መጥቀስ የሚያመለክተው ዘላለማዊ ሞትን ነው፡፡ እግዚአብሔር ኃጢአት የሚያደርጉ ልጆችን ወደ ራሱ ይወስዳቸዋ ማለት ይችላል? ይህ ዓውድ በተዘዋዋሪ የሚጠቅሰው (1) የክርስትያን ወገኞችን ፀሎት (2) በዳዩ ሌሎች አማኞች ይታደሱ ዘንድ በግሉ የሚወልደው ንስሐ፤ ነገር ግን በአማኙ ሕብረተሰብ ላይ ነቀፋን የሚያመጣ ሕይወትን የሚቀጥሉበት ከሆነ ውጤቱ ‹‹ያለጊዜው›› ወይም ከዚህ ዓለም ቀድም መሰናበት ይሆናል (*whe*ጽ *critics Ask*፤ በኖርማን ጌይሰለር እና ቶማስ ሆው(ገጽ 541)፡፡

▣ *"ሕይወት ይሰጥለታል"* በዚህ *ሥፍራ ያለው ሥነ-መለኮታዊ እና የቃላት ችግር "ሕይወት"*(zõê) *የሚለው ቃል ነው*፡፡ በተለምዶ በዮሐንስ ፅሑፎች ውስጥ ይህ የሚመለክተው ዘላለማዊ ሕይወትን ነው፤ ነገር ግን ይህ ዓውድ የሚያመለክተው የማንነትን ወይም የይቅርታና መታደስ ይመስላል (*ያዕቆብ* በ5:13-15 ላይ *"መዳን"* ብሎ እንደሚጠቀሰው በብዙው ይመስላል)፡፡ የተፀለየበት: ግለሰብ "ወይም" ተብሎ ስለተጠቀሰ የሚያመለክተው አማኝ መሆኑን ነው (በራሱ በዮሐንስ ለመልዕክቱ ተቀባዮች የተጠቀሰ)፡፡

5:17 *ሁሉም ኃጢአት አደገኛ ነው፤ ነገር ግን ለአለማን በስተቀር ኃጢአት ደግሞ በንስሐ እና ክርስቶስን በማመን ይቅር ሊባል ይችላል* (*የመጀመሪያ*፤ *ማር*1:15፤*ሐዋ*20:21፤ *ቀጣይነት ያለው፡*- 1ዮሐ 1:19)፡፡

**NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 5:18-20**
**[18]ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን እንዳደርግ÷ ነገር ግን ከእግዚአብሔር የተወለደው ራሱነ እንዲጠብቅ ክፋውም እንዳይነካው እናወቃለን፡፡ [19]ከእግዚአብሔር እንደሆንን ዓለምም በሞላው በክፋው እንደተያዘ እናውቃለን፡፡ [20]የእግዚአብሔርም ልጅ እንደመጣ÷ እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደሰጣን እናውቃለን፡፡ እውነተኛው በሆነው በእርሱ አለንታ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡**

5:18 *"እናውቃለን"* በ5:13 *ላይ ሁለተኛ አንቀፅ ላይ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ*፡፡

▣ *"ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን እንዳያደርግ"* ይህ *የድርጊት መጠናቀቅን የሚያሳይ በዝ አንቀፅ ነው*፡፡ ይህም 3:6 እና 9ን በግልፅ *መደገፉን ያሣያል*፡፡

ዘላለማዊ ሕይወት የሚታይ ባህርያት አሉት፡፡ በመሆኑም አጉራዘለል የሆኑት የግኖስቲክ ኑፋቄ ተከታታዮች የህይወት ዘይቤ የሚያሳየው ልባቸው አለመለወጡን ነው (*ማቴዎስ* 7)፤

ዮሐንስ ሁለት አይነት የሐሰት አስተማሪዎችን ይገልፃል፡፡ አንደኛው ምንም አይነት ኃጢአት አለመሥራተን (1:8-2:1) ሲሆ ሌላው ወገን ደግሞ ኃጢአት ምንም አይነት ተያያዥነት እንደሌለው የሚያምነው (3:4-10፤ እንዲሁም በዚህ *ሥፍራ*)፡፡ ኃጢአት በመጀመሪያ ሊናዘዙት የሚገባ እና በመጨረሻም የሚወገድ ነው፡፡ ችግሩ ኃጢአት ነው፣ በቀጣዩነትም ደግሞ (ባለማቋረጥ) ችግር ነው(5:21)፡፡

*ብሩስ ሜትገር*፤ *A Textual CommeNtary of the Greek New TestameNt* (*ገጽ* 718) በሚለው *መጽሐፋቸው ላይ* እንደሚያረጋግጡት ከሆነ የምንጩ ልዩነት የተከሰተው ኮፒ የሚያደርገው ሰው "ከእግዚአብሔር የተወለደ" የሚለው ሐረግ ምንን ያመለክታል ብሎ ባሰበው ላይ፤

1. ኢየሱስ- ስለዚህ *autoN* ከሁሉም በተሻለ ይስማዋል (A*፤ B)
2. *አማኞች*- ስለዚህ *eautoN* ከሁሉም በተሻለ *ተመራጭ* ነው(N A[c])

የዩቢ. ኤስ[4] *መጽሐፍቅዱስ* ለቁጥር1 የ"B" ደረጃን ይሰጠዋል (ለእርግጠኝነት የቀረበ)፡፡

▣ *"ነገር ግን ከእግዚአብሔር የተወለደ ራሱን እንዲጠብቅ" የመጀመሪያው ግሥ* በግሪኩ ድርጊት ተቀባይ በዝ አንቀፅ ሲሆን ይህም በአንድ ውጫዊ አካል ድርጊቱ መፈፀሙን ያመለክታል (*መንፈስ*፤ ሮሜ8:11)፡፡ ይህ ተሰግዖን ያመለክታል፡፡

*ሁለተኛው ግሥ "ራሱን"* (*AutoN*) ከሚለው ጋር የተጫመረ የአሁን ጊዜ ድርጊ ገላጭ አመልካች ግስ ነው፡፡ ይህም ቃል በቃል "ከእግዚአብሔር የተወለደ ራሱነ ምን ጊዜም ጠብቃል" የሚል ነው፡፡ ይህ የሚያመለክተው ክርስቶስ አማኞችን ያለማቋረጥ እንደሚያፀናቸው ነው፡፡ ይህ ትርጉም የቀድሞ የግሪክ ምንጮችን *A** እና *B**ን የተከተለ ነው፡፡ እንዲህ አ.መ.ት ትርጉሞች ውስጥ ይገኛል፡፡

የ N እና A[c] ምንጮ ሌላ ተውላጠስም አላቸው፡- "ራሱን ይጠብቃሉ" (*eautoN*) የሚል፡፡ ይህም የሚያመለክተው ከእግዚአብሔር የተወለደ ራሱን ለመጠበቅ አንዳች ኃላፊነት እንደለበት ነው፡፡ በዚህ *ሥፍራ* የተጠቀሰው "የተወለደው" የሚለው *ግሥ* ኢሱስን በመለኮት ከአማኞች አንፃር በ3:3 እና 5:21ላይ ተጠቅሷል፡፡ ይህም በተጨማሪ በኬ.ጄ.ቪ. እና ኤን.ኤስ.ቪ. የእንግሊዝኛ ትርጉሞች ውስጥም ይገኛል፡፡

▣

| | |
|---|---|
| NASB | **"ክፉውም እንዳይነካው"** |
| NKJV | **"ጨካኙም እንዳይነካው"** |
| NRSV | **"ክፉውም እንዳይነካው"** |
| TEV | **"ክፉው ሊጎዳቸው አይችልም"** |
| NJB | **"ክፉው በእርሱ ላይ አንዳች የለውም"** |

ይህ በአሁን ጊዜ የተለፀ መካከለኛ አመልካች ሲሆን ክፉም "ሊያጠምደው" አይችልም ማለት ነው፡፡ ሌላው በዮሐንስ ፅሑፎች ውስጥ ብቸኛ አጠቃቀም የሚገኘው በዮሐንስ ወንጌል 20:17 ላይ ነው፡፡ ክርስትያኖች እንደሚፈተኑ ከመጽፍ ቅዱስ ወንጌል 20:17 ላይ ነው፡፡ ክርስትያኖች እንደሚፈተኑ ከመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ከልምድ ግልፅ የሆነ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን ሐረግ በሚመለከት ሦስት ዐቢይ ፅንስ - ሐሳቦች አሉ፤

1. *አማኞች ሕግን በመጣስ ከሚመጣባቸው እርግማን ነፃ ናቸው*

2. ኢየሱስ ስለ እና ይፀልያል (1ዮሐንስ 2:1፣ ሉቃስ 22:32-33)።
3. ሰይጣን ድነታችንን ሊወስድብን አይችልም (ሮሜ 8:31-39) ምንም እንኳን የእግዚአብሔርን ምሥክርነት በሕይወታችን ውስጥ ያለውን ምሥክርነት ሊያጣምም፣ ምናባትም በቁጥር 16-17 *መሠረት አማኝን ያጊዜው* ከዚህ *ዓለም እንዲለይ ማድረግ* ቢችልም፣

5:19 **"ከእግዚአብሔር እንደሆንን....እናውቃለን"** ይህ አንድ አማኝ በኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን አስተማማኝ እምነት እና አመለካከት ነው (4:6) ሁሉም ነገር የተመሠረተው በዚህ አስደናቂ እውነት ላይ ነው (ቁ.13) በ5:13 ላይ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ።

▣ **"ዓለምን በሞላው በክፉው እንደተያዘ"** ይህ በአሁን ጊዜ የተገለፀ መካከለኛ አመልካች ነው (ዮሐንስ12:31፣ 14:30፣ 16:11፣ 2ቆሮ 4:4፣ ኤፌ 2:2፣6:12)። ይህም የተቻለው (1) በአዳ ኃጢአት (2) በሰይጣን አመፅ (3) እያንዳንዱ ሰው ኃጢአትን ለማድረግ ባለው የራሱ ፈቃድ ነው።

5:20 **"እናውቃለን"** ሙሉ ማብራሪያውን በ5:13 ሁለተኛ አንቀፅ ይመልከቱ።

▣ **"የእግዚአብሔርም ልጅ እንደመጣ"** ይህ የአሁን ጊዜ አመልካች ድርጊ ገላጭ ግሥ መለኮት የሆነው ወልድ ሥጋ መልበሱን ያረጋግጣል። ይህ ደግሞ በዚህ ዓለም ያለ ነገር ሁሉ ክፉ ነው የሚል አቋም ላላቸው የግኖስቲክ የኑፋቄ አስተማሪዎች ዋናው ችግር ነው።

▣ **"ልቡና እንደሰጠን"** ይህ ሌላው የተጠናቀቀን ድርጊት አመልካች ነው። አስፈላጊ የሆነውን መረዳት የሚሰጡት የግኖስቲክ የሐሰት አስተማሪዎ ሳይሆኑ ኢየሱስ ራሱ ነበር። ኢየሱስ በራሱ ሕይወት፣ ድርጊቶች፣ ትምህርቶቹ፣ ሞቱ እና ትንሣኤው አማካኝነት አብን በሙላት ገለጠው፣ እርሱ የእግዚአብሔር ሕያው ቃል ነው፣ ከእርሱ በስተቀር ማም ሰው ወደ አብ ሊወጣ አይቻልም (ዮሐንስ 14:6፣1ዮሐንስ 5:10-12)።

▣ **"እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን: እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፣ እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው"** የመጀመሪያው ሐረግ፡- "እውነተኛም በሆነው በእርሱ" የሚለው የሚያመለክተው እግዚአብሔር አብን ነው(በ6:55 እና ዮሐንስ 17:3 ላይ ያለውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስ ይመልከቱ)፣ ነገር ግን በሁለተኛው ሐረግ "እውነተና አምላክ" የሚለው ለመለየት አስቸጋሪ ነው። በዓውዱ አብን የሚያመለክት ይመስላል ነገር ግን በስነ-መለኮት ወልድን ሊያመለክት ይችላል። በተለምዶ በዮሐንስ ፅሑፎች ውስጥ እንደሚገኘው ሰዋሰዋዊው አሻሚነት ሆን ተብሎ የተደረገ ሊሆን ይችላል ምክንየቱም አንድ ሰው በአብ ለመሆን አስቀድሞ በወልድ ሊሆነ ይገባልና (ቁ.12)። የአብ እና የወልድ መለኮት እና እውነተኛነት የተፈለገው ሥነ-መለኮታዊ ግፊት ሊሆን ይችላል (ዮሐንስ 3:33፣ 7:28፣8:26)። አዲ ኪዳን የናዝሬቱ ኢሱስን ፍፁ አምክነት ያረጋግጣል (ዮሐንስ 1:1፡18፣ 20:28፣ ፊልጵ 2:6:2:13፣ ዕብ 1:8)። ይሁን እንጂ የግኖስቲክ የሐሰት አስተማሪዎችም ቢሆኑ የኢየሱስን መለኮትነት ባረጋገጡ ነበር (ቢያንስ በመለኮት መንፈስ ማደር)።

5:21

| | |
|---|---|
| NASB | **"ከጣዖታት ራሳችሁን ጠብቁ"** |
| NKJV፣NRSV | **"ከጣዖታት ራሳችሁን ጠብቁ"** |
| TEV | **"ከሐሰተኛ አማልዕክት ራሳችሁን ጠብቁ"** |
| NJB | **"ከሐሰተኛ አማልዕክት ተጠበቁ"** |

ይህ የግሪኩ አድራጊ ግሥ ትዕዛዛዊ ቃል፣ በጥብቅ የተነገረ አጠቃላይ እውነት ነው። ይህም ክርስትያኖች በሚደሰቱበት ቅድስትና (ኤፌ1:4፣ 1ጴጥ1:5) በንቃት መሳተፋቸውን የሚያመለክት ነው።(3:3)።

ጣዖታት የሚለው ቃል (በዮሐንስ ፅሑፎች ውስጥ ሁለት ጊዜ ብቻ ተጠቅሷል፣ በዚህ ሥፍራ እና በራዕ 9:20 ላይ በተጠቀሰ የብሉይ ኪዳን ጥቅስ) የሐሰት አስተማሪዎችን የሕይወት ዘይቤ እና አስተምህሮዎችን ወይም ደግሞ የሙት ባህር ጥቅሎች ይህን ቃል "ኃጢአት" በሚለው ትርጉም ስለሚወስዱት፣ "ጣዖት" እና "ኃጢአት" ተመሣሣይ ናቸው።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ማብራሪያ ስለሆነ ለምትከተለው የመጽሐፍቅዱስ አተርጓጎም ኃላፊነት አለብህ። እያንዳንዳችን ልንጓዝ የሚገባን ባለን የመረዳት መጠን ነው። አንተ፣ መፅሐፍ ቅዱስ፣ እና መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጎም ወቅት ቅድሚ የሚሰጣቸው ናቸው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተነሱት አቢይ ጉዳዮች እንድታጤናቸው ነው። ጥያቄዎች የቀረቡት በራሣቸው ቀጥተኛ ሆነው ሣይሆን እንደ ሐሳብ አነሣሽ ሆነው ነው።

1. አማኞች በክርስቶስ መሆናቸውን የሚያውቁበትን ሦስት መመዘናዎችን ዘርዝር
2. በቁ.6 እና 8 ላይ ያሉት “ውሃ” እና “ደም” የሚሉት ቃላት ምንን ያመለክታሉ?
3. ክርስትያኖች መሆናችንን ማወቅ እንችላለን? ክርስትያኖች መሆናቸውን የሚያውቁ አንዳንዶች ይኖሩ ይሆን?
4. ለሞት የሚያደርስ ኃጢአት ምንድነው? በአማኝ ሊፈፀም ይችላል?
5. ከፈተና ነፃ የሚያወጣን የእግዚአብሔር የጥበቃው ኃይል ወይስ የራሣችን ጥረት?

# 2ኛ ዮሐንስ መልዕክት

## ተሻሽለው በቀረቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀፅ አከፋፈል

| UBS[4] | NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| ሰላምታ<br>ሰላምታ | ለተመረጠችው<br>እመቤት | | መግቢያ | ሰላምታ ማቅረብ |
| ቁ 1-3 | ቁ. 1-3 | ቁ. 1-2 | ቁ 1-3 | ቁ 1-3 |
| እውነት እና ፍቅር | በክርስቶስ ትዕዛዝ<br>እውነት እና<br>የፍቅር ሕግ መሄድ | | እውነት እና ፍቅር | የፍቅር ሕግ |
| ቁ 4-11 | ቁ 4-6 | ቁ 4-6 | ቁ 4-6 | ቁ 4-5 |
| | | | | ቁ 6 |
| | | | | ተቃዋሚዎች ተጠንቀቁ |
| | ከሐሰተኛ የክርስቶስ<br>የክርስቶስ ጠላቶች | | | |
| | ቁ 7-11 | ቁ 7-11 | ቁ 7-8 | ቁ 7-11 |
| | | | ቁ 9-11 | |
| የመጨረሻ ሰላምታ | ዮሐንስ የለንበት<br>ሰላምታ | | የመጨረሻ ቃላት | |
| ቁ 12-13 | ቁ. 12-13 | ቁ. 12 | ቁ. 12 | ቁ. 12 |

### አጭር መግቢያ

የሁለተኛ ዮሐንስ መልዕክት ከአንደኛ ዮሐንስ መልዕክት ጋር በመልዕክቱ እና የአጻጻፍ ዘይቤው ግልጽ የሆነ ተዛምዶ አለው፡፡ ይህም ምናልባት መልዕክቶች በተመሳሳይ ጊዜ የተፃፈ በመሆናቸው ነው፡፡ የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የግል መልዕክቶች /ደብዳቤዎች ለየት ያለ ባህርይ በአንድ ጥቅል እና በአንድ የፓፒረስ ገጽ ላይ መጻፋቸው ነበር፡፡

የመጀመጀሪያው የዮሐንስ መልዕክት ለበርካታ ቤተክርስቲያኖች (በእርግጥ ለሁሉም ቤተክርስቲያኖች ነበር) እንደተጻፈ ሁሉ የሁለተኛ ዮሐንስ መልዕክትም ለአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያንና መሪም (ምንም እንኳን አብዛኞቹ የአዲስ ኪዳን መልዕክቶች ለመላው ቤተክርስትያን የሚነበቡ ቢሆንም) ነበር፡፡ ይህም መልዕክት በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን  በትንሹ እስያ (ቱርክ) ትገኝ ለነበረችው ቤተክርስቲያን ሕይወት ለመቃኘት እንደ አንድ አስደናቂና አ ነስ ያለ መልእክት የሚታይ ነው፡፡

### አንደኛ የምንባብ ኡደት (ገጽ 5 ን ይመልከቱ)

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ማብራሪያ በመሆኑ ለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ፡፡ እያንዳንዳችንም መጓዝ ያለብን ባለን መረዳት መረት ነው፡፡ ስለሆነም አንተና መጽሐፍቅዱስን መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጎም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ናችሁ፡፡ ይህንንም ጉዳይ በሚያብራራው ሰው ላይ ብቻ መተው አይገባህም፡፡

ጠቅላላውን የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍል በአንድ ቅጽበት አንብበው የጠቅላላውን መጽሐፍ ማዕከላዊ ጭብጥ /መልዕክት በራደህ አባባል ግለጸው፡፡

*ተመስጧዊ ባይሆኑም፣ የአንቀጽ ምድቦች የሚከተለውን የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ ለመረዳት ቁልፍ ናቸው፡፡ እያንዳንዱ ዘመናዊ ትርጉም አንቀጾቹን መድቦ ማጠቃለያውን እንዲያቀርብ ተደርጓል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድ ማዕከላዊ ርዕሰ-ጉዳይ፣ እውነት፣ ወይም እሳቦት አለው፡፡ እያንዳንዱ ቅጂ ያንን ርዕስ በራሱ የተለየ መንገድ አጽዕሮቱን አስፍሯል፡፡ ጽሑፉን ስታነበው፣ የትኛው ትርጉም በርዕሰ ጉዳይም ሆነ በቁጥር ምድቦች ከአንተ መረዳት ጋር እንደሚስማማ ራስህን ጠይቅ፡፡

በእያንዳንዱ ምዕራፍ በቅድሚያ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ይኖርብናል፣ እንዲሁም ርዕሰ ጉዳዮቹን መለየት (አንቀጾቹን)፣ አኪያም የእኛን መረዳት ከአዲሶቹ ትርጉሞች ጋር ማወዳደር አለብን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ልንረዳ የምንችለው የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ ምን እንደሆነ የሱን አምክኖአዊ (ሎጂክ) እና አቀራረቡን ስንረዳ ነው፡፡ ዋነኛው ጸሐፊ ብቻ ነው ተመስጧዊው– አንባብያን መልዕክቱን ለመቀየርም ሆነ ለማሻሻል መብት የላቸውም፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢዎች ተመስጧዊውን እውነት በየዕለቱና በሕይወታቸው ሁሉ ተግባራዊ ለማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

**ማስታወሻ፦ ሁሉም ሙያዊ ቃላትና አጽሕሮተ ቃላት በሙሉ በቅጥያ አንድ፣ ሁለት፣ እና ሦስት ላይ ተብራርተዋል፡፡**

1. የጠቅላላው መጽሐፍ ጭብጥ

2. የአጻጻፍ ዘይቤው (መንገዱ)

## ሁለተኛው የምንባብ ዑደት (ገጽ 5 ይመልከቱ)

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ማብራሪያ በመሆኑ ለምትከተለው የመጽሀፍ ቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ፡፡ እያንዳንዳችንም መጓዝ ያለብን ባለን መረዳት መሰረት ነው፡፡ አንተ መጽሐፍቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጎም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣችሁ ናችሁ፡፡ ይህንንም ጉዳይ በሚያብራራው ሰው ላይ ብቻ መተው አይገባህም፡፡

ጠቅላላውን የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍል በአንድ ጊዜ አንብበው ዋና ዋና ሐሳቦችን በዝርዝር በማስቀመጥ ብዙ ሐሳቦችን በአንድና አረፍተ ነገር እያንዳንዱን ዋና ሐሳብ በአንድ አረፍተ ነገር ግለፀው፡፡

1. የመጀመሪያው ክፍል ዋና ሐሳብ

2. የሁለተኛው ክፍል ዋና ሐሳብ

3. ሦስተኛው ክፍል ዋና ሐሳብ

4. አራተኛው ክፍል ዋና ሐሳብ

5. አምስተኛው ክፍል ዋና ሐሳብ

## ሶስተኛ የምንባብ ዑደት (ገጽ 5 ን ይመልከቱ)

*የመጀመሪያውን ፀሐፊ ዋና ሐሳብ በአንቀጽ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ማብራሪያ በመሆኑ ለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ፡፡ እያንዳንዳችንም መጓዝ ያለብን በውስጣችን ባለው መረዳት መሰረት ነው፡፡ አንተ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈሳዊ ቅዱስ በአተረጓጎም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣችሁ ናችሁ፡፡ ይህንንም ጉዳይ በሚያብራራው ሰው ላይ ብቻ መተው አይገባህም፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው ዋና ዋና ሐሳቦቹን ለይተህ አውጣቸው፡፡ የራስህን አከፋፈል ከአምስቱ የተሻሻሉ ትርጉሞች የአንቀጽ አከፋፈል ጋር አስተያየው፡፡ በአንቀጽ መከፋፈል በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት የሚደረግ ባይሆንም የአተረጓጎም ምጽዋ የሆነውን የመጀመሪያውነስ ዋና ሐሳብ ለመከተል ግን ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ የሚናገረው ስለ አንድ ዋና ሐሳብ ብቻ ነው፡፡

1. የመጀመሪያ አንቀጽ

2. ሁለተኛ አንቀጽ

3. ሶስተኛ አንቀጽ

4. ወ.ዘ.ተ

## የቃል እና የሐረግ ጥናት

> NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 1-3
> **[1] ሽማግሌው በእውነት ለመረዳት እኔ ብቻ ሳልሆን እውነትን የሚያውቁ ሁሉ ለሚወዷት ለተመረጠችው እመቤትና ለልጆቿ፤ [2] በውስጣችን ከሚኖርና ከእኛ ጋር ለዘላለም ከሚሆን እውነት የተነሳ፣ [3] ከእግዚአብሔር አብና የአብ ልጅ ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ምሕረትና ሰላም በእውነትና በፍቅር ከእኛ ጋር ይሆናል፡፡**

**ቁ. 1 "ሽማግሌው"** ይህ መጠሪያ (*Presbuteros*) የተጠቀሰው የ2ኛ እና የ3ኛ ዮሐንስ መልዕክቶችን ፀሐፊ ለመለየት ይቻል ዘንድ ነው፡፡ ይህ መጠሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ እና የተለያዩ ትርጉሞችን ያዘለ ነው፡፡

የዮሐንስ ጽሑፎች የፀሐፊውን መጠሪያ በተለያዩ መልኮች ይገልጹል፡፡

1. ወንጌል "የተወደደው ደቀመዝሙር" የሚለው ሐረግ ይጠቅሳል
2. የመጀመሪያው መልዕክት ተመሳሳይ ነው
3. ሁለተኛው እና ሶስተኛው መልዕክቶች "ሽማግሌው" የሚል መጠሪያ አላቸው፡፡
4. የራዕይ መጽሐፍ ከራዕይ መጻሕፍት አጻጻፍ ለየት ባለ ሁኔታ ፀሐፊውን "አገልጋዩ ዮሐንስ" ብሎ ይጠራዋል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስን በሚያብራሩ እና ባለመቃመንት መካከል የእዚህን መልዕክቶች ፀሐፊ በሚመለከት ብዙ የሚያከራክር ጉዳይ አለ፡፡ እነዚህ መልዕክት ሁሉም ሥነ-ልሣናዊና የአፃፃፍ ዘይቤ ተመሳሳይነት እና ልዩነት አላቸው፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ ግን በሁሉም መጽሐፍቅዱስ አስተማሪዎች ዘንድ ተቀባይነት ያገኘ ምንም አይነት ማብራሪያ የለም፡፡ በእኔ በኩል ግን ለሁሉም መልዕክቶች የሐዋሪያው ዮሐኝስን ፀሐፊነት እቀበላለሁ፣ ነገር ግን ይህ የሥነ-አፈታት ጉዳይ እንጂ የእስትንፋስ እግዚአብሔር ጉዳይ አይደለም፡፡ እንደ እወንተው ከሆነ የመጽሕ ቅዱስ ዋናው ደራሲ የእግዚአብሔር መንፈስ ነው፡፡ ይህም ሚዛን የሚፋ መገለጥ ነው ነገር ግን በዘመናችን ያሉት የአጻጻፍ ዘይቤውን ወይም የአወቃቀር /የማሰባሰብ/ ስልቱን ያለማወቅ ችግር እንዳላቸው ግልጽ ነው፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ ሽማግሌ**

1. የመላዕክትን ስብሰባ የሚፈጥሩትን የእግዚአብሔርን መላዕክት ለማመልከት ተጠቅሷል (ኢሳ 24፡23 ያለ)፡፡ በራዕይ መጽሐፍ ላይ የተጠቀሱትን የመላዕክት ፍጥረታትን ለማመልከት ተመሳሳይ ቃል ተጠቅሷል (4-4፡10፤5÷5፡6፡8፡11፡14፤
   7÷11፡ 13፤11÷16፤ 14÷13፤ 19÷4)
2. በብሉይ ኪዳን (ዘፀ 3÷16 ዘሕል 11÷16) የጎሳ መሪዎችን (*zaqen*) ለማመልከት ተጠቅሷል፡፡ በኋላም ከኢየሩሳሌም የተሰበሰቡትን የአይሁድ ሽማግሌዎችን ሸንጎ ለማመልከት በስራ ላይ ውሏል (ማቴዎስ 21÷23፤26÷57)፡፡ ኢየሱስ በነበረበት ጊዜም ይህ ሰባ አባላት ያሉት አካል ምግባር ብልሹ በነበረው ክህነት ተቆጣጥሮት ነበር፡፡
3. የአዲስ ኪዳን አጥቢያ ቤተክርስቲያን መሪዎችን ለማመልከት ተጠቅሷል፡፡ ይህም ከሶስቱ ተመሳሳይ መጠሪያዎች አንዱ ነበር (እረኛ፣ ጠባቂእና ሽማግ 1÷5 7፤ ሐዋ 20÷17 28)፡፡ ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ራሳቸውን በአመራር ቡድን ውስጥ ለማካተት ቃሉን ተጠቅመው ነበር (1 ጴጥ 5÷1 2ዮሐንስ 1፤3 ዮሐንስ 1)፡፡
4. . በአመራር ውስጥ ያሉትን ሳይሆን በቤተክርስትያን ውስጥ በእድሜ የገፉ ሰዎችን ለማመልከት ተጠቅሷል (1ጢሞ 5÷1፤ ቲቶ 2÷2)፡፡

▣ **"ለተመረጠችው እመቤትና ለልጆቿ"** ይህንን መጠሪያ በሚመለከት ብዙ ክርክር አለ፡፡ ነገር ግን ብዙዎቹ ለማረጋገጥ እንደሞከሩት ይህ የተጻፈው ኤሌክታ ተብላ ለምትጠራው እመቤት፡በግሪኩ ቋንቋ የተመረጠ ወይም የተጠራ ለማለት ነው (አሌክሳአንደሪያው ክሌመንት) ወይም ደግሞ ካይሪያ የሚለውን በግሪክ እመቤት የሚለውን የሚያመለክት (አትናትዎስ) ነው በማለት ይናገራሉ፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ቤተክርስቲያንን እንደሚያመለክት ከጀሮም ሀሳብ ጋር ስስማማ በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፤

1. ለቤተክርስቲያን የተሰጠው የግሪኩ መጠሪያ የሴት ጾታ ነው (ቁ. 1)፡፡
2. በሰብትዋጅንት "የተመረጠ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሕዝብ ወገንን ነው (1ኛ ጴጥ 2:9) ፡፡
3. ይህ ምናልባት ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ሙሽራ እንደመሆኗ እሷን ለማመልከት ሊሆን ይችላል (ኤፌ 5:25-32፤ ራዕ 19:7-8፤ 21:2)፡፡
4. ይህች ቤተክርስቲያን በውስጧ ያሉ አባላት ልጆች ተብለው ተጠርተዋል (ቁ. 13)፡፡
5. ይህች ቤተክርስቲያን እንደሌላ ቤተክርስቲያን የተጠቀሰች እህት ቤተክርስቲያን ነበራት (ቁ. 13)፡፡
6. በጠቅላላው ምዕራፍ ውስጥ በነጠላ ቁጥር እና በብዙ ቁጥሮች መካከል የቃላት መራቀቅ ወይም ጨዋታ ያለው ይመስላል (ነጠላ ቁጥር፡- በቁጥር 4፡5፡13፣ ብዙ ቁጥሮች፡- በቁጥር 6፡8፡10፡12)
7. በ1ኛ ጴጥ 5:13 ውስጥ ቃሉ በተመሳሳይ ሁኔታ ተጠቅሷል፡፡

▣ **"ለ…"** ይህ በብዙ ቁጥር የወንድ ጾታ ተውላጠስም መሆኑ የሚደንቅ ነው፤ ምክንያቱም የሴት ጾታ አመልካች የሆነውን "እመቤት" የሚለውን ወይም የጉዕዝ ጾታ አመልካች ጥቅስ ልጆች የሚለውን የሚያያዝ ነውና፡፡ እኔ እንደማስበው ከሆነ ይህ ዮሐንስ ሐረጉን በምልክትነት የሚጠቀምበት መንገድ ነው፡፡

▣ **"ለምወዳቸው"** ዮሐንስ *phileo* (ፊሎ) የሚለውን ቃል በዮሐንስ ወንጌል እና የዮሐንስ ራዕይ ውስጥ *agapao* (አጋፔ) ከሚለው ቃል ጋር በተመሳሳይነት ይጠቀሰዋል፡፡ ነገር ግን በአንደኛ ፣ በሁለተኛ እና በሶስተኛ ዮሐንስ መልዕክቶቹ ውስጥ *አጋፔ* የሚለውን ቃል ብቻ ይጠቀማል (ቁ. 3፡5፡6፤1 ዮሐንስ 3:18ን ያስ.)፡፡

▣ **"እውነት"** እውነት የሚለው ቃል በተደጋጋሚ የሚጠቀስ ጭብጥ ነው(ቁ. 1 (ሁለት ጊዜያት፡ 2፡3፡4) በቁጥር 9ኝ ላይ ያለው "ይህንን ትምህርት" የሚለው ሐረግ እና ቁጥር 10 ላይ "እውነት" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ይሄ መጠሪያ

ትኩረት የተሰጠው ምናልባት በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለው ይህን ኑፋቄ በዚህ ትንሽ መልዕክት ውስጥ (ቁ. 4፤7-10) ከ1ኛ ዮሐንስ መልዕክት ጋር ተመሳሳይነት ሳይኖረው አይቀርም፡፡

"እውነትን" የሚለው ሶስት ነገሮችን ሊያመለክት ይችላል፤ (1) በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ መንፈስ ቅዱስን (14:17ን ያስ.) (2) ራሱን እየሱስ ክርስቶስን (ዮሐንስ 8:32፤ 14:6ን ያስ.) እና (3) የወንጌሉን ይዘት (1ዮሐንስ 3:23 የስ.)፡፡ በ6:55 እና 17:3 ላይ ያለውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስ ይመልከቱ፡፡

**ቁ. 2 "በእኛ ስለሚኖር"** ይህ የአማኞችን "መኖር" የሚገልጽ እና ዮሐንስ ከሚጠቀማቸው የተወደዱ መጠሪያዎች አንዱ የሆነው የአሁን ጊዜ ድርጊት ገላጭ የሆነ ቦዝ አንቀጽ ነው፡፡ በ2:10 ላይ የሚገኘውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስ ይመልከቱ፡፡ ይህ በአማኞች ውስጥ የሚያድረውን መንፈስ ቅዱስን የሚያመለክት ይመስላል (ሮሜ 8:9 ወይም ልጅ፤ ሮሜ8:9-10ን የስ.)፡፡ ሁሉም የሥላሴ አካላት ከአማኞች ጋር ወይም ከአማኞች ውስጥ ይኖራሉ (ዮሐንስ 14:23ን ያስ. )፡፡

▣ **"ከእኛ ጋር ለዘላለም ስለሚሆን"** እውነት ሁልጊዜም ከሁሉም አማኞች ጋር ለዘላለም የሚኖር ነው፤ እንዴት አይነት የሚያስደንቅ ዋስትና ነው! በ1ኛ ዮሐንስ 5:13 ላይ ያለውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስ ይመልከቱ፡፡ ይህ "እውነት" ሁልጊዜ የሚረጋገጠው በፍቅር ነው፣ ለእግዚአብሔር ባለን ፍቅር፣ ለመሰል የቃል ኪዳን ወንድሞቻችን ወይም እህቶቻችን ባለን ፍቅር፣ እንዲሁም ደግሞ ለጠፋው አለም ባለን ፍቅር ጭምር ነው (1ኛ ዮሐንስ 4:7-21ን ያስ.)፡፡

ለዘላለም የሚለው ቃል በቃል "ሁል ጊዜ" ማለት ነው (ዮሐንስ 4:14፤ 6:51፡58፤8:35፡51፤10:28፤11:26፤12:34፤13:8፤14:16፤1ኛ ዮሐንስ 2:17) ፡፡ በዮሐንስ 6:58 ላይ ለዘላለም የሚለውን ተጨማሪ የጥናት ዕርስ ይመልከቱ፡፡

**ቁ. 3 "ጸጋና ምሕረት ሰላምም"** ከሁለት ነገሮች በስተቀር በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የነበረ የግሪኮች ደብዳቤ ወይም መልዕክት ለየት ያለ መግቢያ ነው፡፡ በመጀመሪያ ክርስቲያናዊ የመልዕክት ድባብ ሊኖረው ዘንድ መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበታል፡፡ "ሰላምታ" ለሚለው ቃል የግሪኩ መጠሪያ ***ቻይሬይን*** ይባላል፡፡ ይህም ***ጸጋ*** የሚል ትርጉም ወዳለው ***ቻሪስ*** ወደሚለው ቃል ተለውጧል፡፡

ይህ መግቢያ ከመጋቢያን መልዕክቶች ጋር ተመሳሳይ ነው፤ 1ጢሞ 1:2፤ 2ጢሞ 1:2፤ እነዚህ ሁለቱ መጠሪያዎች ጳውሎስ በገላትያ እና በ1ኛ ተሰሎቄ መልዕክቶች በጠቀሳቸው መግቢያዎች ውስጥ በድጋሜ ተጠቅሰዋል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የተለመደው ሰዋስዋዊ አወቃቀር የሚያሳየው ጸሎትን ወይም ለመልካም ጤንነት ያለን ምኞት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የ2ኛ ዮሐንስ መልዕክት መለኮታዊ ውጤት ያለው ከእግዚአብሔር ጋር ጸንቶ የመቆም ተስፋን ያዘለ ንግግር ነው፡፡

ከስነ መለኮት አንጻር በእነዚህ መጠሪያዎች መካከል ያለው ቅደም ተከተል ሆን ተብሎ የታሰበበት ሊመስል ይችላል፡፡ ጸጋና ምህረት የሚያንጸባርቁት እግዚአብሔር በክርስቶስ አማካኝነት ለወደቀው የሰው ዘር ያመጣውን ነጻ የሆነ ድነትን እና የእርሱን ማንነት ነው፡፡ ሰላም በአንጻሩ የሚያንጸባርቀው የእግዚአብሔርን ስጦታ መቀበልን ነው፡፡ በዚህም አማኞች ፍጹም የሆነ ለውጥን ይለማመዳሉ፡፡ በሰው ልጅ የደረሰው ውድቀት በሰው ሁለንተናዊ ሕይወት ላይ ተጽኖ እንዳመጣ ሁሉ ድነትን ሁለንተናዊ ሕይወቱ ላይ ተሃድሶን ያመጣል፡- በቅድሚያ የስፍራ ለውጥን በማምጣት (በእምነት መጽደቅ) ከዚያም ደግሞ በውስጡ በሚኖረው የእግዚአብሔር መንፈስ አማካኝነት ሥር-ነቀል ለውጥ ያለው አመለከታከት በማምጣት፤ ይህም ደግሞ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ክርስቶስን የመምሰል ሂደት (ሂደታዊ ቅድስና) የሚረጋገጥ፡፡ በዚህም በሰው ዘር ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር መልክ (ዘፍ 1:26-27ን ያስ.) ተሃድሶን ያገኛል!

ሌላው አማራጭ ሊዛመድ የሚችለው ከሃሰት አስተማሪዎች አንጻር ለእነዚህ ሶስት መጠሪያዎች ያለው ፍላጎት ወይም መሻት ነው፡፡ እነርሱም ስለ "ጸጋ" እና "ምህረት" ይጠይቃሉ፤ "ከሠላም" በስተቀር ሁሉንም ነገሮች ደግሞ አምጥተዋል፡፡
እዚህ ላይ በጣም ደስ የሚለው ነገር በሁሉም የዮሐንስ ጹሁፎች ውስጥ ***ምህረት*** የሚለው ቃል በብቸኝነት መጠቀሱ ነው፡፡ "ጸጋ" የሚለው ቃል በዚህ ስፍራ ብቻ ተጠቅሷል እንዲሁም በወንጌል ውስጥ፡- 1:14፡16፡17 እና በዮሐንስ ራዕይ ውስጥ (1:4፤22:21)፡፡

የጀሮም የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ እንደሚገልጸው እነዚህ ሶስት ቃላት ከብሉይ ኪዳን ቃልኪዳን ጋር ተያያዥነት እንዳላቸው ነው (ገጽ. 412)፡፡

የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች (ከሉቃስ በስተቀር) ዕብራውያን ሊቃውንት የነበሩ እና በኮይኔ ግሪክ የጻፉ ነበሩ፡፡ ለዚህም ነው አብዛኛዎቹ የአዲስ ኪዳን ቃላት የሰብተዋጅት መነሻ ያላቸው፡፡

▣ **"ከእግዚአብሔር አብና ከአብ ልጅ ከኢየሱስ ክርስቶስ"** ሁለቱም ስሞች ከ የሚል መስተዋድድ አላቸው፤ ይህም በሰዋስው ስርዓት ሁለቱንም በእኩል ደረጃ ያስቀመጠ ነው፡፡ ይህ የኢየሱስ ክርስቶስን ፍጹም የሆነ መለኮትነቱን ሰዋስዋዊ በሆነ መንገድ ያረጋገጠ ነው፡፡

▣ **"የአብ ልጅ"** በ1ኛ ዮሐንስ መልእክት ውስጥ ቀጣይ ትኩረት ደግሞ አንድ ሰው ወልድ ሳይኖረው አብ ሊኖረው እንደማይችል ነው(1ዮሐንስ 2:23፤4:15፤5:10ን የስ.)፡፡ የሐሰት አስተማሪዎች ከእግዚአብሔር ጋር ለየት ያለ ህብረት እንዳላቸው በአጽንኦት ቢናገሩም የወልድን ማንነትና ስራውን ግን ያንኳስሱ ነበር፡፡ ዮሐንስም ደጋግሞ የሚናገረው ነገር ኢየሱስ (1) የአብ ሙሉ መገለጥ መሆኑን እና (2) ወደ አብ የሚያደርስ ብቸኛው መንገድ መሆኑ ነው (ዮሐንስ 14:6)፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 4-6
**[4]ትእዛዝ ከአብ እንደተቀበልን ከልጆችሽ በእውነት የሚሄዱ አንዳንዶችን እለ አገኘኒቸው እጅግ ደስ ብሎኛል። [5]አሁንም እመቤት ሆይ ÷እርስ በርሳችን እንድንዋደድ አለምንሻለሁ። ይህች ከመጀመሪያ በእኛ ዘንድ የነበረች ትእዛዝ ናት እንጂ አዲስ ትእዛዝን እንደምጽፍልሽ አይደለም። [6]እንደ ትእዛዛቱም እንሄድ ዘንድ ይህ ፍቅርነው ከመጀመሪያ እንደሰማችሁ: በእርስዋ ትሄዱ ዘንድ ትእዛዙ ይህች ናት።**

**ቁ..4 "እጅግ ደስ ብሎኛል"** ይህ የግሪኩ ድርጊት ተቀባይ ገላጭ ግስ ነው። ምናልባት ሽማግሌው ይህን የሰማው በየስፍራው ከሚጓዙ የቤተክርስትያኑ አባላት ሊሆን ይችላል።

▣ **"ከልጆችሽ በእውነት የሚሄዱ አንዳዶችን ስለ አገኘኃቸው"** ይህ የሚያመለክተው
1. በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ እግዚአብሔርን የሚመስሉ እና የሚወዱትን አንዳንዶችን ወይም
2. በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ያሉትን እና አንዳንዶችን ከእውነት መንገድ የወጡትን መናፍቃንን ነው።

▣ **"ትእዛዝ በአብ እንደተቀበልን"** ይህ የግሪክ ድርጊት ገላጭ አመልካች ግስ ሲሆን የሚያመለክተውም ኢየሱስ እንደወደዳቸው ሁሉ እነርሱም እርስ በርሳቸው ይዋደዱ ዘንድ የተሰጠን ትዕዛዝ የሚያመለክት ነው (ዮሐንስ 13:34-35፤15:12፤ 1ዮሐንስ 3:11፤ 4:7፡11-12፡21)።

**ቁ. 5 "ከመጀመሪያ በእኛ ዘንድ የነበረች"** ይህ ያልተጠናቀቀን ድርጊት አመልካች ግስ ሲሆን የኢየሱስን ትምህርት መጀመር የሚያመለክት ነው (1 ዮሐንስ 2:7፡24፤ 3:11)። የትእዛዙ ይዘት "እርሰበርሳችሁ ተዋደዱ" (ቁ5 ን ያስ) እና ኢየሱስ በስጋ እንደመጣ እውቅና መስጠት በሚሉ ንግግሮች በድጋሚ የተረጋገጠ ነው (ቁ. 7ን ያስ(። የትእዛዙ ይዘት ያለው ስብእና ያለው እና በአኗኗር ዘይቤ የሚገለጽ መሆኑን ማስተዋል ያልፈልጋል።

▣ **"እርስ በርሳችን እንድንዋደድ"** ይህ በአሁን ጊዜ የግሱን ሁኔታ የሚገልጽ ነው ! በዚህ ጥቅስ መጨረሻ ላይ መሔድ የሚለው ግስ እንደሆነ፡ የመናፍቃን ገለልተኛ መሆን እና በጥላቻ መሞላት ባህሪይ ነበር። ይህም አንድ ሰው ክርስትያን መሆን አለመሆኑን ከሚመዘንባቸው ሶስት ነገሮች አንዱን ያመለክታል። በአንደኛ ዮሐንስ መልእክት ውስጥ የሚገኙት እነዚህ መመዘኛዎች ፍቅር፤ የአኗኗር ዘይቤ እና አስተምህሮ ናቸው። እነዚህም መመዘኛዎች በሁለቱም ዮሐንስ መልእክት ውስጥም በድጋሚ ተጠቅሰው እናገኛቸዋለን።
1. ፍቅር (ቁ. 5፤ 1ዮሐንስ 2:7-11፤3:11-18፤4:7-12፡16:21፤5:1-2
2. መታዘዝ (ቁ. 6፤ 1ዮሐንስ 2:3-6፤3:1-10፤5:2-3)
3. የአስተምህሮ ይዘት (ቁ.7፤1ዮሐንስ 1:1፤2:18-25፤4:1-6፤14-16፤5:1፡5:10 ያስ)

**ቁ. 6 "ይህ ፍቅር ነው"** ፍቅር (አጋፔ) ቀጣይነት ያለው (የአሁን ጊዜ ድርጊት ገላጭ) ድርጊት እንጂ ስሜት ብቻ አይደለም። ፍቅር የእውነተኛ አማኞች ሁሉ "ምልክት" ነው (1 ቆሮንቶስ 13፤ ገላ 5:22፤ 1 ዮሐንስ 4:7-21 ያስ.)።

▣ **"ከመጀመሪያ"** በ1 ዮሐንስ 1:1 ላይ ያለውን ማብራሪያ የመልከቱ። እኔ እንደማስበው በ1ኛ ዮሐንስ እና በ2ኛ ዮሐንስ ላይ ሐረጉ የተጠቀሰው የኢየሱስን የአደባባይ አገልግሎት መጀመር ለማመልከት ይመስላል።

▣ **"በእርስዎ ትሄዱ ዘንድ"** ክርስትና ለመጀመሪያ ጊዜ መሰጠታችንን እና የአኗኗር ዘይቤ ለውጥ የምናሳይበት ነው (1 ዮሐንስ 2:6)። ምንም እንኳን የአኗኗር ዘይቤያችን የሚያድነን እንዳልሆነ ቢታወቅም እኛ መዳናችንን ግን የሚያረጋግጥ ነው (ኤፌ 2:8-9 እና 2:10 ያስ.)።

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 7-11
**[7]ብዙ አሳቾች ወደ ዓለም ገብተዋልና እነርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ በስጋ እንደመጣ የማያምኑ ናቸው። ይህ አሳቹና የክርስቶስ ተቃዋሚው ነው። [8]ሙሉ ደመወዝን እንድትቀበሉ እንጂ የሰራችሁትን እንዳታጠፉ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። [9]ለሚወጣ ሁሉ በክርስቶስም ትምህርት ለማይኖር ነው አምላክ የለውም፤ በክርስቶስ ትምህርት ለማይኖ ሰው አምላክ የለውም፤ በክርስቶስ ትምህርት ለሚኖር አብና ወልድ አሉት። [10]ማንም ወይ እናንተ ቢመጣ ይህንም ትምህርት ባያመጣ በቤታች አትቀበሉት። ሰላምም አትበሉት፤ [11]ሰላምም የሚለው ሰው በክፉ ስራው ይከፈላልና።**

**ቁ.7 "ብዙ አሳቾች"** "አሳቾች" የሚለው ቃል የመጣው "ፕላኔ" ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን "ፕላኔት" የሚለው የእንግሊዝኛው መጠሪያ የተገኘበት ነው። በቀደመው ዘመን የሰማይ አካላት ካርታ በመነሳት ይጠኑ (ዚዲያክ) ነበር። ከዋክብቶች በተወሰነ ዛቢያ ይንቀሳቀሱ ነበር (ፕላኔቶች) ነገር ግን አንዳንድ ከዋክብት ባልተስተካከለ ሁኔታም ይንቀሳቀሱ ነበር። በመሆኑም ቀደምት (የጥንት ሰዎች) "ተንከራታች" በማለት ይጠራቸው ነበር። ይህም በዚያቤናዊ አነጋገር ከእውነቱ ራቀቅ ብለው የሚንከራተቱን ለማመልከት ነው።

እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች እንዲሁ ዝብ ብለው በእውነት የተሳሳቱ ወይም ወንጌሉን ሆነው አይደለም፡፡ በዮሐንስ ጽሑፎች ለሬሳዊያን እና የሐሰት አስተማሪዎች ግልጽ የሆነውን የወንጌል እውነት ላይ ያው ነበር፡፡ እንጂ ለዚህም ነው የእነርሱ አመጽ ወይም ተቃውሞ "ምህረት የሌለው ኃጢአት" ወይም "ሞት የሚገባው ኃጢአት" የሚባለው (በ1ኛ ዮሐንስ 5:16 ላይ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ)፡፡ ከዚህም በላይ በጣም የሚያሳዝነው ነገር ደግሞ ሌሎችም ወደ ጥፋት እንዲሄዱ ምክንያት መሆናቸው ጭምር ነው፡፡ አዲስ ኪዳንም የሐሰት አስተማሪዎች እንደሚገለጡ እና ብዙ ችግርችን እንደሚከተሉ በግልጽ ያስቀምጣል (ማቴ 9:15፤24:11፡24፤ ማር 13:22፤ 1ዮሐንስ 2:26፤3:7፤4:1)፡፡

▣ **"ወደ ዓለም ገብተዋልና"** በዚህ ስፍራ ላይ ዓለም ተብሎ የተጠቀሰው የሚታየው ፕላኔታችን ነው፡፡ እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች የክርስቶስን ቤተክርስቲያን ለቀዋል (1 ዮሐንስ 2:9ን ያስ) ወይም ደግሞ በሚሲናዊነት ተልዕኮአቸው ላይ ናቸው (3ኛ ዮሐንስን ያስ.)፡፡

▣ **"የማያምኑ"** ይህ በግሪክ ሆሞሎጂዮ የሚል መጠሪያ (ቃል) ሲሆን በተዘዋዋሪ የሚጠቀሰው በክርስቶስ ያለን እምነት በአደባባይ መግለጽን ነው፡፡ በዮሐንስ 9:22-23 ላይ መታመን ወይም መመስከር የሚለውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስ ይመልከቱ፡፡

▣ **"ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንድመጣ"** እነዚህ አሳቾች ስለክርስቶስ ማንነት ያላቸውን የሐሰት ትምህርት ቀጥለውበታል፡፡ ይህ ጥቅስ በ1ኛ ዮሐንስ 4:1-6 ያለውን "መናፍስትን መርምሩ" የሚለውን ሐሳብ በተለይም ከኢየሱስ ፍጹም ደብእና ጋር ባለው ዝምድና (ዮሐንስ 1:14፤ 1ጢሞ 3:16ን ያስ) የመመርመሩን አስፈላጊነት በድጋሚ ይገልጸዋል፡፡ ኖስቲሲዝም በመንፈስ (እግዚአብሔር) እና (ሥጋ) መካከል ያውን ዘላለማዊ ሁለትዮሽ (ዱዋሊዝም) አስረግቶጦ ይናገራል፡ ስኖስቲሳዊያን ኢየሱስ አምላክ እና ፍጹም ሰው ሊሆን አይችልም ነበር፡፡

በቀድሞው የኖስቲሳዊያን አስተሳሰብ ቢያንስ ሁለት ሥነ-መለኮታዊ አካሄዶች ያሉ ይመስላል፤

1. የኢየሱስን ስብእና መካድ (ይሴቲክ) በሰው መልክተገልጧል እንጂ መንፈስ ነበር
2. ኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞቱን መካድ ይህ ወገን (ሰርንቲያን) እንደሚለው "የክርስቶስ መንፈስ" ሰው የሆነው ኢሱስ ሲጠመቅ አርፎበት ከመስቀሉ በፊት ደግሞ ተለየው የሚለው ነው

"በሥጋ እንደመጣ" የሚለው የአሁን ጊዜ ግሳጭ ቅጽል ዮሐንስ የሴቴንቲያን ኖስቲሲዝምን እንዲሁም ደግ 1ኛ ዮሐ 4፣1-6 የይሴቲክ ኖስቲሲዝምን የተቃወመበት መንገድ ነው ማለት ይቻልል፡፡

▣ **"ይህ አሳቹና የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው"** በ1ኛ ዮሐንስ 2፣18 ውስጥ በብዙ ቁጥር የተገለጠው " የክርስቶስ ተቃዋሚዎች" በሚለው እና በነጠላ ቁጥ የተገለጠው "አሳች" መካከል ልዩነት ወለ፡፡ በብዙ ቁጥር የተገለጡት በዮሐንስ ዘመን የመጡ እና ቤተክርስትያችንም ለቀው የሔዱ ሲሆን (ዮሐንስ 2፣19ን ያስ፣ ነገር ግን በነጠላ ቁጥር የተገለጠው ደግሞ ወደፊት የሚመጣውን ያመለክታል (በ2ኛ ተሰሎንቄ 2 ላይ "የአመፅ ሰው" የሚለውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስ ይመልከቱ)፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ጥቅስ ነጠላው ቁጥር የተጠቀሰው በ1ኛ ዮሐንስ 2፣18-25 ላይ እንደተጠቀሰውብዙ ቁጥር ነው፡፡ ቁ.8 በራሳችሁ ተጠንቀቁ" ይህ በአሁን ጊዜ የተገለጠ ትእዛዝ እዛል ገላጭ ግስ ነው፡፡ ይህ ቃል ከክፉ ለመጠበቅ የሚሰጥን ማስጠንቀቂያ ለማሳየት " ተመልከቱ" (blepo)የሚለው የአነጋገር ዘይ ነው(ማቴዎስ 24፣4፤ ማርቆስ 13፣5፤ ሉቃ 21፣8 ሐዋ13፣40፤ 1ቆሮ 8፣9፣10-12፤ ገላ 5-12፤ ዕብ 12-25)፡፡ አማኞች ስህተት ለመለየት ሃላፊነት አለባቸው ምክንያቱም፤

1. ወንጌልን ያውቃሉ
2. መንፈሱ ስላላቸው
3. ከክርስቶስ ጋር የማያቋርጥ ህብረት ስላላቸው

▣

| | |
|---|---|
| NASB | **"የሠራችሁትን እንዳታጠፉ"** |
| NKJV | **"የሠራናቸውን እነዚያን ነገሮች እንዳናተፋ"** |
| NRSV | **"የሠራነውን እዳታጠፉ"** |
| TEV | **"የሠራነውን አታጠፉም"** |
| NJB | **"ወይም ሁሉም ስራችን ይጠፋል"** |

ከመጀመሪያው ተወላጠ ስም ጋር በተያያዘ በግሪክ ምንጭ ላይ ልዩነት አለ፣ "እናንተ" (NASB፣ኤን.አር.ኤስ፣ቪ.) ወይም "እኛ" (NKJV) መሆን አለበት? የዋ.ቢ.ኤስ 4ጥቅስ "እናንተ" የሚለውን ሰደግፍ ይህም ያለው ትርጉም በሐዋርያት የምስክርነት መልዕክቱ የተለካላቸው አማኞች የወንጌልን ግቦች ምናልባት አልራጸመም ይሆናል የሚል ነው፡፡

▣ **"ሙሉ ደመወዝን እንድትቀበሉ"** ይህ የግሪኩ ሁኔታ ገላጭ ግስ ሲሆን ወንጌሉን መቀበላቸውን ወደ ኂላ ተመልሶ ይጠቁማቸዋል፡፡ የግሉን ሁኔታ ገላጭ ከድነቶች ጋር የሚያያዝ አይደለም፤ ነገር ግን በእነርሱ አማካኝነት የሚፈጸመው የወንጌል መስፋፋት እና ብስለት እንጂ (1ቆሮ 9:27፤15:10፡14:58፤2ቆሮ 6:1፤ገላ 2:2፤ ፊል 2:16፤ 1 ተሰ 2:1፤3:5)፡፡

**ቁ.9**

| | |
|---|---|
| NASB | **"ለሚወጣ ሁሉ በክርስቶስም ትምህርት ለማይኖር ሰው"** |
| NKJV | **"ለሚያምጽ ሁሉ እና በክርስቶስም አስተምህሮ ለማይኖር ማንም ሰው"** |

NRSV "በክርስቶስ ትምህርት የማይኖር ማንም ሰው"
TEV "ከክርስቶስ ትምህርት ጋር አብሮ የማይቆይ ነገር ግን ከኋላው የሚሄድ ማንም ሰው"
NJB "በክርስቶስ ትምህርት የማይኖር ነገር ግን የሚወጣ ማንም ሰው"

በመጀመሪያ ፓስ የሚለውን አሉታዊ አነጋገር እናስተውል፡፡ የወንጌል ጥሪ ለ "ሁሉ" ነው ነገር ግን እድሉ ለሐሰት መምህራንም ጭምር ነው፡፡ ይህ ሊከሰት የሚችለው የኑፋቄ ትምህርት በሁለት የአሁን ጊዜ ድርጊት ገላጭ ቦዝ አንቀጾ ተጠቅሷል፦ "የሚወጣ ሁሉ" እና "የማይኖር" ተብለው፡፡ የመጀመሪያው "መውጣት" የሚለው ቃል የሐሰት አስተማሪዎችን ለማሳየት የተጠቀሰ ሲሆን ይህም በተዘዋዋሪ ሐዋርያት ከሰጡት ምስክርነት ይልቅ እውነቱን አልፈው መሄዳቸውን ያሳያል፡፡

አማኞች በውስጣቸው በሚኖረው የእውነት ቃል ይታወቃሉ (ዮሐንስ 8:31፤15:7፤ 1ዮሐንስ 2:14፤ በአሉታዊ፦ ዮሐንስ 5:38፤ 1 ዮሐንስ 1:10)፡፡ በዮሐንስ 8:31 ላይ መጽናት የሚለውን እና በዮሐንስ 6:64 ክህደት የሚሉትን ተጨማሪ የጥናት ርዕሶችን ይመልከቷቸው፡፡
የስም ወይም የተወላጠ ስም ሁኔታን አመልካች ("በክርስቶስ") ሊያመለክት የሚችለው፤

1. የክርስቶስ ትምህርቶች
2. ስለ ክርስቶስ የነበሩትን ትምህርቶች
3. የተለመዱት የዮሐንስ ጣምራ ትርጉሞች

ስም ወይም ተውላጠ ስም አመልካቾች ብዙ እና ግልጽ ያልሆኑ ናቸው! ለማለት የተፈለገውን የሚወስነው የምንባቡ አውድ ብቻ ነው፤ ብዙውን ጊዜ በዚህ ስፍራ ላይ ተደራርበው እንደሚታዩት ማለት ነው፡፡

▣ **"አምላክ የለውም "** በቁጥር 2 ላይ "የክርስቶ ትምህርት" እና "እውነት" በትይዩ የተቀመጡ ናቸው የሐሰት አስተማሪዎች እና ተከታዮቻቸው ምንም አይነት ደመወዝ የላቸውም (ቁ. 8ን ያስ.)፡፡ እነርሱ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የጠፉ እና ከእግዚአብሔር የተለዩ ናቸው፤ ምክንያቱም አንድ ነው አብ እንዲኖረው ወልድ ይኖረው ዘንድ ግድ ነውና (1ዮሐንስ 5:10-12 ያስ.)፡፡ "የለውም" የሚለው ግስ (ሁለት ጊዜ፤ የአሁን ጊዜ ድርጊት ገላጭ ግስ) ከእግዚአብሔር ጋር የተጠቀሰው በዚህ ስፍራ እና በ1 ዮሐንስ 2:23 ላይ ብቻ ነው፡፡

ቁ. 10 "ቢ..." ይህ የመጀመሪያ መደብ ሁኔታዊ አረፍተ ነገር ሲሆን ከፀሐፊው እይታ እና ከሥነ-ጽሑፋዊ ዓላማው አንጻር እውነት ነው ተብሎ የተገመተ ነው፡፡ የሐሰት መምህራን መምጣታቸው የማይቀር ጉዳይ ነው!

▣ **"በቤታችሁ አትቀበሉት"** ይህ የአሁን ጊዜ ድርጊት ገላጭ ትዕዛዝ ከአለታዊ ቦዝ አንቀጽ ጋር የተጣመረ ሲሆን በተዘዋዋሪ የሚያመለክተው በሂደት ላይ ያለ ድርጊትን መቆም ነው (አውዱ ሊወስነው ይገባል)፡፡

"በቤታችሁ" የሚለው የክርስትያንን እንግዳ ተቀባይነት ሊያመለክት ይችላል (ማቴ 25:35፤ ሮሜ 12:13፤ 1 ጢሞ 3:2፤ቲቶ 1:8፤ ዕብ 13:2፤ 1ጴጥ 4:9 ወይም 3 ዮሐንስ 5-6)
ነገር ግን ከዓውዱ አንጻር ስንመለከተው ከስፍራ ስፍራ የሚንቀሳቀስን አንድ አገልጋይ በቤት ውስጥ ላለች ቤተክርስትያን ንግግር እንዲያደርግ መጋበዝን ሊያመለክት ይችላል (ሮሜ 16:5፤ 1ቆሮ 16:19፤ ቆላ 4:15፤ ፊል 2)፡፡

▣ **"ሰላምም አትበሉት"** ይህ ከአለታዊ ቦዝ አንቀጽ ጋር የተጣመረ ሌላው የአሁን ጊዜ ድርጊት ገላጭ ትእዛዝ ነው፡፡ ራሳችሁን "ክርስትያን ነኝ" ብሎ ከሚጠራው ከእንዲህ አይነቱ ሰው ጋር አታመዳደሉ፡፡ ማንኛውም አይነት ሕብረት ምናልባት እንዲህ አይነቱን ሰው ከመቀበል አንጻር የሚታይ ነው (ቁ. 11ን ያስ.)፡፡ ይህ ንግግር በዘመናችን በስራ ላይ ለማዋል አስቸጋሪ ነው፡፡ ብዙዎች ክርስትያኖች እንደሆኑ ይናገራሉ፡፡ ነገር ግን ከእነርሱ ጋር ሕብረት ለማድረግ በንግግር ሁሉ ትሁትን ሁነን ስንቀርብ ይገባል፡፡ አሁንም ቢሆን ክርስትያን መሪዎች ከኑፋቄ ጋር ከመተባበር መጠንቀቅ አለባቸው፡፡ ይህ በእርግጥ የክርስትያን ዳኖሚነሽኖችን (ቤተ-እምነቶችን) የሚመለከት አይደለም!

> NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 12-13
> **[12]እንድጽፍላችሁ የምፈልገው ብዙ ነገር ሳለኝ በወረቀትና በቀለም ስጽፈው አልወድም ዳሩ ግን ደስታችሁ ፍጹ እንዲሆን ወደ እናንተ ልመጣ አፍ ለአፍም ልናገራችሁ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ [13]የተመረጠችው የእህትሽ ልጆች ሰላምታ ያቀርቡልሻል፡፡**

ቁ.12 **"እንድጽፍላችሁ የምፈልገው ብዙ ነገር አለኝ"** ይህ ከ3ኛ ዮሐንስ 13-14 መደምደሚያ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

▣ **"ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን"** ይህ የመልዕክቱን ዓላማ በግሉ ሁኔታ አመልካችነት የተገለጹ ዙሪያ ጥምጥም ንግግር ነው ("እንዲሆን" የሚለው ዓላማ አመልካች ሐረግ ድርጊቱ ሊፈጸም እንደሚችል የሚያሳይ ነው፡፡ ይህም በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የተለመደው ጭብጥ ነው (ዮሐንስ 3:29፤15:11፤16:24፤17:13፤ 1ዮሐንስ 1:4)፡፡ ይህ ደስታ የተመሰረተው፤

1. በመምህሩ መኖር ላይ ነበር
2. እርሱ ይዞት በመጣው የእውነት እውቀት ላይ ነበር

ዮሐንስ በቁጥር 4 ላይ "ደስታውን" የገለጸው ቀጣይነት ባለው የፍቅር እና የመታዘዝ ሕይወት ነበር።

**ቁ. 13** ይህ ጥቅስ እንደ ቁጥር 1 ሁሉ እህት ቤተክርስትያንን እና አባላቶቹን ለመናገር ዘይቤያዊ የንግግር ቋንቋን ይጠቀማል።

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ማብራሪያ በመሆኑ ለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ። እያንዳንዳችን ልንጓዝ የሚገባን ባለን መረዳት መሰረት ነው። አንተ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስቅዱስ በአተረጓጎም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ናችሁ። ይህንን ጉዳይ በሚያብራራው ሰው ላይ ብቻ ልትተወው አይገባህም፡-

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የቀረቡት በዚህ የመጽሐፍ ክፍል ውስጥ የተነሱትን አብይ ጉዳዮች ላይ በጥሞና እንድታሰብሏቸው ነው። ጥያቄዎች የቀረቡት እንደ ሐሳቡ አነዳሽ ሆነው እንጂ በራሳቸው ቀጥተኛ አይደሉም።

1. በ1ኛ ዮሐንስ መልዕክት ውስጥ የሚገኙ እና በ2ኛ ዮሐንስ መልዕክት ውስጥ የተደገመች ሦስቱን መመዘኛዎች ዘርዝራቸው።
   ሀ.
   ለ.
   ሐ.
2. ይህ መልዕክት የተፃፈው ለአንዲት እመቤት ወይስ ለቤተክርስትያን ?
3. መናፍቃን በእግዚአብሔር ሕዝብ ጉባኤ መካከል መኖራቸውን ከዚህ አጭር መልዕክት እንዴት ልታውቅ ትችላለህ?
4. በቁጥር 7 ላይ የተገለጸው አሳችእና የክርስቶስ ተቃዋሚ ማን ወይም ምንድነው?
5. በአዲስ ኪዳን ውስጥ ጠላቶቻችንን እንድንቀበላቸው እና እንድንወዳቸው ከተጣለብን አደራ /ትዕዛዝ አንጻር ቁጥር 10 እና 11 የሚታፈኑ ናቸው?

# 3ኛ ዮሐንስ መልእክት

## ተሻሽለው በቀረቡ የመጽሐፍቅዱስ ትርጉሞች የአንቀጽ አከፋፈል

| UBS[4] | NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| ሰላምታ | ለጋይዮስ የቀረበ ሰላምታ | | መግቢያ | መልእክትና ሰላምታ |
| ቁ. 1 | ቁ. 1-4 | ቁ. 1 | ቁ. 1ሀ | ቁ. 1-4 |
| | | | ቁ. 1ለ | |
| | | ቁ. 2-4 | ቁ. 2-4 | |
| ቁ. 2-4 | | | | |
| እርዳታ እና ስለቸርነት | ጋይዮስ ተመስገነ ተቃውሞ | | ጋይዮስ ምስክርነት | |
| ቁ. 5-8 | ቁ. 5-8 | ቁ. 5-8 | ቁ. 5-8 | ቁ. 5-8 |
| | ዲዮስጥራጢስ እና ዲሜጥሮስ | | ዲዮጥራጢስ እና ዲሜጥሮስ | ዲዮስጥራጢስ መንገድ ተጠበቁ |
| ቁ. 9-10 | ቁ. 9-12 | ቁ. 9-10 | ቁ. 9-10 | ቁ. 9-11 |
| ቁ. 11-12 | | ቁ. 11-12 | ቁ. 11 | ዲሞጥሮ ተመስከረለት |
| | | | ቁ. 12 | ቁ. 12 |
| የመጨረሻ የስንብት ሰላምታ ሰላምታ | የመጨረሻ ቅጣይ ሰላምታ | | የመጨረሻ የስንብት ሰላምታ ሰላምታ | |
| ቁ. 13-15 | ቁ. 13-15 | ቁ. 13-14 | ቁ. 13-14 | ቁ. 13-15 |
| | | ቁ. 15 | ቁ. 15ሀ | |
| | | | ቁ. 15ለ | |

### አንደኛ የምንባብ ዑደት (ገጽ 5ን ይመልከቱ)

ይህ የጥናት መመሪያ ማብራሪያ በመሆን ለምትከተለው የመጽሐፍቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ እያንዳንዳችንም መጓዝ ያለብን ባለን መረዳት መሰረት ነው፡፡ ስለሆነም አንተ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጎም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ኛችሁ፡፡ ይህንንም ጉዳይ በሚያብራራው ሰው ላይ ብቻ መተው አይገባህም፡፡

ጠቅላላውን የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍል በአንድ ጊዜ አንብበው የጠቅላላውን መጽሐፍ ማዕከላዊ ጭብጥ /መልዕክት በራስህ አባባል ግለፀው፡፡

1. የጠቅላላው መጽሐፍ ጭብጥ

2. የአጻጻፍ አይነት (ዘይቤው)

### ሁለተኛው የምንባብ ዑደት (ገጽ 5ን ይመልከቱ)

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ማብራሪያ በመሆኑ ለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ፡፡ እያንዳንዱችንም መንዝ ያለብን ባለን መረዳት መጠረት ነው፡፡ ስለሆነም አንተ መጽሐፍቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጎም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣችሁ ናችሁ፡፡ይህንንም ጉዳይ በሚያብራራው ሰው ላይ ብቻ መተው አይገባህም፡፡

ጠቅላላውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ዋና ዋና ሐሳቦችን በዝርዝር በማስቀመጥ እያንዳንዱን ዋና ሐሳብ በአንድ አረፍተ ነገር ግለፀው፡፡

1. የመጀመሪያው ክፍል ዋና ሐሳብ

2. የሁለተኛው ክፍል ዋና ሐሳብ

3. የሶስተኛው ክፍል ዋና ሐሳብ

4. የአራተኛው ክፍል ዋና ሐሳብ

5. ወ.ዘ.ተ

### ሦስተኛ የምንባብ ዑደት (ገጽ 5ን ይመልከቱ)
*የመጀመሪያውን ፀሐፊ ዋና ሐሳብ በአንቀጽ ደረጃ መከተል.*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ማብራሪያ በመሆኑ ለምትከተለው የመጽሐፍቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ፡፡ እያንዳንዳችንም መንዝ ያለብን ባለን መረዳት መሠረት ነው፡፡ ስለሆነም አንተ፣መጽሐፍቅዱስእና መንፈስቅዱስ በአተረጓጎም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ናችሁ፡፡ ይህንንም ጉይ በሚያብራራው ሰው ላይ ብቻ መተው አይገባህም፡፡

ጠቅላላውን መፅራፍ በአንድ ጊጊ አንብበው ዋና ዋና ሐሳቦችን ለያቸው፡፡የራስህን የዋና ሐሳቦች አከፋፈል ከአምስቱ ተሻሽለው የቀረቡ ትርጉሞች አከፋፈል ጋር አስተያየው፡፡ ምንም እነኳ በአንቀጽ መከፋፈል በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት የሚረዳ ባይሆንም የአተረጓጎም ምሶሶ የሆነውን የመጀመሪያ ፀሐፊ ዋና ሐሳብ ለመከተል ግን ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድ ዋና ሐሳብ ብቻ አለው፡፡

1. አንደኛ አንቀጽ

2. ሁለተኛ አንቀጽ

3. ሶስተኛ አንቀጽ

4. አራተኛ አንቀጽ

5. ወ.ዘ.ተ

## አውዳዊ ግንዛቤዎች፡-3ኛ ዮሐንስ

### መግቢያ

ሀ. ይህ አነስተኛ መልእክት ሦስተኛ ዮሐንስ ተብሏል ምክንያቱም ከ2ኛ ዮሐንስ መልዕክት በመጠኑ አነስ ስለሚል ነው፡፡ እኔ እንደሚመስለኝ 2ኛ እና 3ኛ ዮሐንስ መልዕክቶች በመጀመሪያው ክፍለዘመን መጨረሻ አካባቢ፣ በትንሹ እስያ ምናልባትም በሮም አውራጃ ለምትገኘው አጥቢያ ቤተክርስትያን ሚዛናዊ የሆነ መልዕክትን የሚሰጥ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡
ለ. 2ኛ ዮሐንስ የሚያተኩረው ሐሰተኛ ስፍራ ስለሚዘዋወሩ ሰባኪዎች ሲሆን 3ኛዮሐንስ የሚያተኩረው ደግሞ ከስፍራ ስፍራ የሚዘዋወሩ ክርስትያን ሰባኪዎችን በመገደፊ ላይ ነው፡፡
ሐ. በ3ኛ ዮሐንስ መልዕክት ውስጥ ተለይተው የተጠቀሱ ሶስት የተለያዩ ሰዎች አሉ፣
   1. ጋይዮስ (የመልዕክቱ ተቀባይ በሆነችው አጥቢያ ያለ የእግዚአብሔር ሰው)

ሀ. በሌላ የመጽሐፍቅዱስ ክፍሎች ውስጥ ጋይዮስ ተብለው የተጠቀሱ ሶስት ሰዎች አሉ፤የመቄይኒያው ጋይዮስ፤ ሐዋ 19:29፤ የደርቤው ጋይዮስ፤ ሐዋ 20:4 እና የቅሮንቶሱ ጋይዮስ ሮሜ 16:23፤1ቆሮ 1:14

ለ. "የሐዋርያት መተዳደሪያ ደንብ" ተብለው የሚታወቁት ጽሑፎች በ3ኛዮሐንስ ውስጥ የተጠቀሰውን ጋይዮስ በዮሐንስ የተሾመ የጴርጋሞን ኤጲስ ቆይስ አድርገው ይዘረዝሩታል፡፡

2. ዲዮጢራጢስ የመልእክቱ ተቀባይ በሆነችሁ አጥቢያ የሚገኝ ችግር ፈጣሪ ሰው)

ሀ. ይህ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለዚህ ሰው የተጠቀሰ ስፍራ ነው፡፡ የዚህ ሰው ስም እምብዛም የማይታወቅ ሲሆን የሰሙ ትርጉምም "ዜውስን የሚንከባከብ" ማለት ነው፡፡ "ዜውል" ማለት "መንገደኞችን የሚከላከል" ማለት ሆኖ ሳለ ይህ ሰው ከ"ዜውስ" ጋር መጠቀሱ ምፅጠታዊ አነጋገር ነው፡፡

ለ. የዚህ ሰው አመለካከት በቁጥር 9-10 ላይ ተገልጦ ይታያል፡፡

3. ዲሜጥሮስ (የዮሐንስን መልዕክት ወደ ተቀባይዋ አጥቢያ ይዞ የሄደው ሰው)

ሀ. ይህ ሰው ከስፍራ ስፍራ ከሚጓዙ ሚሲዮናዊያን አንዱ እና በኢፌሶን ከሚኖረው ዮሐንስ መልዕክቱን ያደረሰ ሰው መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

ለ. "የሐዋርያት መተዳደሪያ ደንብ" ተብሎ የሚጠራው ዲሜጥሮስን በዮሐንስ የተሾመ የፊላፊልፊያ አጥቢያ አዲስ ቆይስ ብሎ ይዘረዝረዋል (ይጠቅሰዋል)፡፡

መ. የቀደመችው ቤተክርስትያን ተጓዥ የሐኑ ሰባኪዎችን /አስተማሪዎችን/ ወንጌላዊያንን እንዴት መመዘንና መረዳት እንዳለበት ተግዳሮቶች ነበሩባት፡፡ ከሁለተኛው ክፍለዘመን የሆነ እና በመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና ውስጥ ያልተካተተ *The Didache or The TheatiNg of the Tweve Apostles* የተሰኘ የቀድሞ ጽሑፍ እነዚህ መመሪያዎች አሉት፤

**ምዕራፍ 11- አስተማሪዎችን፣ ሐዋርያትን እና ነብያትን በሚመለከት**

"ከዚህ ቀደም ሰምታች የነበረውን ነገር ማንም ሰው መጥቶ እነዚህን ነገሮች ቢያስተምራችሁ ተቀበሉት፡፡ ነገር ግን አስተማሪው ራሱ ከሚያስተምረው ዘወር ብሎ ሌላ ነገር የሚያስተምርና ወደጥፋት የሚመራ ከሆነ እራሱን አትስሙት፤ ነገር ግን ጽድቅን እና የጌታን እውቀት ለመጨመር የሚያስተምር ቢሆን ግን ጌታን እንደተቀባችሁት እርሱንም ተቀበሉት፡፡ ሐዋርያትን እና ነብያትን በሚመለከት በወንጌል ድንጋጌ መሰረት አድርጉ፡፡ ማንም ወደ እናንተ የሚመጣን ሐዋርያ ጌታን እንደምትቀበሉ ተቀበሉት፤ ነገር ግን ከአንድ ቀን በቀር ሊቆይ አይገባውም አስፈላጊ ከሆነ የሚቀጥለው ቀን ይሁን፤ ነገር ግን ለሶስት ቀናት የሚቆይ ከሆነ እርሱ ሐሰተኛ ነቢይ ነው ማለት ነው፡፡ ሐዋርያው የሚሄድ ከሆነ 2ዙር እስኪጠቀለል ድረስ ከዳቦ በስተቀር ምንም ነገር አይወስድ፤ ነገር ግን ገንዘብ የሚጠይቃችሁ ከሆነ እርሱ ሶስተኛ ነቢይ ነው(ገጽ 380)፡፡

**ምዕራፍ 12፤ ክርስትያኖችን መቀበል**

"ነገር ግን ማንም በመንፈስ ሆኖ ገንዘብ ወይም አንዳች ነገር ስጡኝ ቢላችሁ ልትሰሙት አይገባም፡፡ ነገር ግን ይህን የሚለው እርዳተን ስለሚፈልጉ ሰዎ ከሆነ በእርሱ ላይ አትፍረዱበት፡፡

ነገር ግን ማንም በጌታ ስም የሚመጣን ሰው ተቀበሉት ከዚያም መርምሩትና እውቀት ምክንያቱም ግራና ቀኙን መረዳት አለባችሁና፡፡ ከሩቅ ስፍራ የመጣ ከሆነ በቻላችሁት መጠን እርዱት ይህም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ለሁለት ወይም ለሶስት ቀናት ብቻ መሆን አለበት፡፡ ነገር ግን አንጥረኛ ሆኖ ሳለ ከእናንተ ጋር ለመኖር የሚፈቅድ ከሆነሰርቶ ይብላ ነገር ግን ምንም የማይነግድ ከሆነ ክርስትያን እንደመሆናችሁ መጠን ይህንን በመመልከት ያለ ስራ ከእናተ ጋር ሊቀመጥ አይገባውም፡፡ ነገር ግን ያለንንም ማድረግ የማይፈቅድ ከሆነ እርሱ በክርስቶ ስም የሚያጭበረብር ነው፡፡ ከእንደዚህ አይነቱ ራቁ ተለዩም (ገጽ381)፡፡

**የቃል እና የሐረግ ጥናት**

| |
|---|
| NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 1<br>[1]**ሽማግሌው በእውነት እኔ ለምወደው ለተወደደው ለጋይዮስ፡፡** |

**ቁ.1"ሽማግሌው"** ሽማግሌ የሚለው መጠሪያ "መጋቢ" ወይም እና "ኤልስቆይስ" ከሚለው መጠሪያ ጋር ተመሳሳይ ነው (ቲቶ 1:5፡7፤ሐዋ 20:17፡28 ያስ.)፡፡ ሙሉ ማብራሪያውን በ2ኛ ዮሐንስ ቁጥር 1 ላይ ይመልከቱ፡፡

▣ **"ለተወደደው"** ይህ የዮሐንስ መልእክቶች መለያ ባህርይ ነው (1ዮሐንስ 2:7፤ 3:2፡21፤4:1፡11 ፤ 3ኛ ዮሐንስ 1:2:5፡11) ነገር ግን በዮሐንስ ወንጌል እና በዮሐንስ ራዕይ ውስጥ አማኞችን ለመግለጽ አልተጠቀሰም፡፡

▣ **"ጋይዮስ"** የዚህች አጥቢያ መጋቢ/እረኛ ጋይዮስ ወይም ዲዮስንራጢስ በሚለው ላይ ብዙ አከራካሪ ነገር አለ፡፡ በዚህም ስፍራ ከመገኘው መጠነኛ መረጃ ብቻ በመነሳት የከረረ አቋም ለመያዝ የሚያስቸግር ነው፡፡ በቁጥር 9 ላይ"ቤተ ክርስትያን" እና "ዋናቸው" የሚሉት ቃላት ስለተገለጹ ዲዮስጠራጠስ የአንድ የቤት ውስጥ ቤተክርስትያን መሪ በአንጻሩ ደግሞ ጋይዮስ በቅርበት ያለች የሌላዋ የቤት ውስጥ ቤተክርስትያን መሪ እንደነበሩ መገመት ይቻላል፤ ነገር ግን ይህ ከግምትነት የሚያልፍ አይደለም፡፡

▣ “በእውነት እኔ ለምወደው” “ፍቅር እና እውነት” በዮሐንስ መልእክቶች ውስጥ ሁልጊዜ በጣምራ የሚገኙ ናቸው (2ዮሐንስ 1:2፡3፡4፤ 3ኛ ዮሐንስ 1:3፡4፡8:12)። እውነትም ሊያመለክት የሚችለው፤

1. መንፈስ ቅዱስን (ዮሐንስ 14:7ን ያስ.)
2. ልጁን ኢየሱስን (ዮሐን 8፣32፤14:6ን ያስ.)
3. የወንጌሉን ይዘት (1ዮሐንስ 2:2፤3:23 ያስ.) ነው።

> **NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 2-4**
> **2 ወዳጅ ሆይ ነፍስህ እንደሚናውን በነገር ሁሉ እንዲከናወን ደህና ጤና እንዲኖርህ እደያለሁ። 3ወንድሞች መጥተው አንተ በእውነት እንደምትሄድ ስለ እውነትህ ሲመሰክሩ እጅግ ደስ ብሎኛል። 4 ልጆቼ በእውነት እንዲሄዱ ከመስማት ይልቅ የሚበልጥ ደስታ ያለኝም።**

**ቁ.** 2 **“እጸልያለሁ”** ይህ በግሪክ ቋንቋ የአንድን መልእክት የጅማሬን የሚከተል ነው። ይህ የሚገልጸው ለመልእክቱ ተቀባዮች መከናወንና ጤንነት ያለውን ጸሎት ወይም መልካም ምኞትን ነው። ይህ በጊዜው አንድ የተወደደን ሰው ሰላምታ የሚቀርብለት መንገድ ነበር። ነገር ግን ይህ አባባል በዘመናችን አሜሪካ የገነነው “የጤናና የብልጽግና ወንጌልን” ለመጥቀስ የሚያገለግል ሊሆን አይችልም። የጎርደን ፊን (የካሪዝማቲክ ሊቅ) *The Disease of the Health, Wealth Gospel* የሚለውን መጽሐፍ ይመልከቱ። በፈውስ ላይ ያለኝን አመለካከት ለማወቅ በያዕቆብ ምዕራፍ 5 ላይ በኦንላይን የሚገኘውን WWW.freebibelecommeNtary.org ዌብሳይት ይመልከቱ።

▣ **“ነፍስህ እንደሚከናወን በነገር ሁሉ እንዲከናወንልህና ጤና እንዲኖርህ”** ይህ በመጀመሪያው ክፍለዘመን በነበረው የግሪክ-ሮማዊያን ዘመን የነበረ የተለመደ የፀሎት መክፈቻ ነው። ነገር ግን ይህ “ጤንነት፣ ሐብትን እና ብልጽግናን” ለሚሰብኩ ሰባኪዎች እንደመረጃ እንዲጠቀስ አልነበረም የተፃፈው። ከአውዳቸው ተገንጥለው የሚጠቀሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ማንኛውንም ነገር ለማረጋገጥ አገልግሎት ሊውሉ ይችላሉ። ይህ ጥቅስ በዘመኑ ለማለት ያስፈለገውን ሐሳብ በዘመናችንም ሊል አይችልም። በመንፈስ ቅዱስ መነዳት የጻፈው ብቸኛው ሰው የመጀመሪያው ፀሐፊ ብቻ ነው። እኛም የእርሱን ሐሳብ ስንከተል እንጂ የራሳችንን ሐሳብ ልናስገባበት አይገባንም!

▣ **“ነፍስህ”** ይህ *psuche (soul)* የሚለው መጠሪያ *pNeuma* (ኒውማ) ከሚለው ጋር ተመሳሳይነት አለው።እነሱም የራስን ወይም የልብእናን መለያ ለማመልከት ይጠቀሳሉ። ይህ ግን የተከፋፈለን የሰውን ሁለንተኛ (አካል፣ ነፍስ፣ መንፈስ) አያመለክትም። ሰዎች አንድ ናቸው (ዘፍ2:7ን ያስ.)። እኛ ነፍስ ነን እንጂ የለንም ቁ.3 “እጅግ ደስ ብሎኛልና” (2 ዮሐንስ 4፤ ፊልጵ 4:10ን ያስ.)።

▣ **“መጥተው…ሲመሰክሩ”** እነዚህ ሁለቱም የአሁን ጊዜ የዝ እንቀጾች ሲሆኑ በተዘዋዋሪ የሚያመለክቱም

1. የዚህ ቤተክርስትያን አባላት በየጊዜው ወደ ኤፌሶን እየሄዱ ለዮሐንስ ሪፖርት ያደርጉ ነበር።
2. የሚመስሉ ሚሲዮናዊያን የጋይዮስን ቸርነት ሪፖርት ያደርጉ ነበር።

ምናልባት ዮሐንስ ሽማግሌ እንደመሆኑ መጠን በቀላሉ መጓዝ ባለመቻሉ የቤተክርስትያኖችን እድገትና ያለበትን ሁኔታ ሲሰማ ይድ ነበር።

▣ **“በእውነት እንዲሄዱ”** ይህ ሐረግ በስነ-መለኮት “በብርሃን ብንመላለስ” (1 ዮሐንስ 1:7ን ያስ.) ከሚለው ጋር የሚነጻጸር ነው። ክርስትና ከመጀመሪውም አንዳች ድንጋጌ፣ ሥነ-ሥርዓት፣ ወይም አባል የሚሆኑበት ተቋም ሳይሆን ከክርስቶ ጋር ሕብረት በማድረግ የሚኖሩት ሕይወት ነው። የቀደመችው ቤተክርስትያን በመጀመሪያ ተብላ ትጠራ የነበረው “መንገድ/ጎዳና” ተብላ ተብላ ነበር (ሐዋ 9:2፤19:9፡23፤24: 22)። እውነት የእውቀት (ይዘት) ጉዳይ ብቻ አይደለም ነገር ግን ሕብረትም ጭምር እንጂ (አንዱ ሌላውን መውደድ ይችል ዘንድ የሚያደርገው ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ሕብረት)። በዮሐንስ 6:55 እና 17:3 እውነት በሚለው ላይ ያሉትን ተጨማሪ የጥናት ርዕሶችን ይመልከቱ።

**ቁ.**4 **“ልጆቼ”** ይህ በዮሐንስ መልእክቶች ውስጥ የተለመደው ስያሜ ነው (1 ዮሐንስ 2: 12፡13፡18፡18፤3: 7፡18፤4:4፤5:12)። በዚህ ሥፍራ ትኩረት የተሰጠው (1) የዮሐንስ ሐዋሪያዊ ስልጣን ወይም (2) በትንሹ እስያ (ምዕራባዊ ቱርክ) ውስጥ በምትገኘው የሮም አውራጃ ውስጥ ላሉ ቤተክርስትያኖች እና ክርስትያኖች ለፍቅር የተጠቀመው ስያሜ ነው፤ይህም ሥፍራ ዮሐንስ የመጨረሻውን የአገልግሎት ጊዜውን ያሳለፈበት ነበር።

> **NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ ቁጥር 5-8**
> **5ወዳጅ ሆይ÷ምንም እንግዶች ቢሆኑ÷ ለወንድሞች በምታደርገው ሁሉ የታነ ስራ ትሰራለህ÷ እነርሱም በማኅበር ፊት ስለ ፍቅርህ መስክረዋል፤ ለእግዚአብሔር እንደሚገባ አድርገህ በጉዞአቸው ብትረዳ መልካም ታደርጋለህ፤ 7ከአህዛብ አንዳች ሳይቀበሉ ስለ ስሙ ወጥተዋልና። 8እንግዲህ ከእውነት ጋር አብረን እንድንሰራ እኛ እንዲህ ያሉትን በእንግድነት ልንቀበል ይገባናል።**

**ቁ.5 “*የታመነ ስራ ትሰራለህ*”** እነዚህ በጋይዮስ የሚደረጉ ስራዎች በቁጥር 9 እና 10 ላይ ከተጠቀሱት የዲዮጥራጢስ ስራዎች በትክክል ተቃራኒዎች ናቸው፡፡ በዮሐንስ 1:7 እና ዮሐንስ 1:4 ላይ *ማመን፣ መታመን፣* እምነት እና *ታማኝነት* በሚል ርዕስ ላይ ያለውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስ ይመልከቱ፡፡

▣ “*በምታደርገው ሁሉ*” ይህ *eaN* ከሚለው ጋር የተጣመሩ አዛማጅ ተውላጠ ስም የሆነና ወደፊት ሊሟላ ይችላ በሚል ተስፋ የተገለጹ የግሪኩ የመካከለኛ ግስ ሁኔታን አመልካች ነው፡፡ ጋይዮስ ተጓዥ የነበሩትን ሚሲዮናዊያን በማንኛውም ጊዜ እና አጋጣሚ ይረዳቸው ነበር፡፡

▣ “*ምንም እንግዶች ቢሆኑ*” ቤተክርስትያን እነዚህን ከስፍራ ስፍራ የሚጓዙ ክርስትያን ሚሲዮናዊያንን ልትረዳቸው ይገባት ነበር፤ ነገር ግን በአጥቢያዊ በነበረው ሁኔታ ምክንያት ጌታን ከማውቃቸው፣ ከማገልገላቸው እና ኢየሱስ ክርስቶስን ከመወደዳቸው በስተቀር ስለእነርሱ ምንም የመያውቃቸውን እነዚህን ወንድሞች ጋይዮስ ይረዳቸው ነበር፡፡

**ቁ. 6 ”*እነርሱም በማህበር ፊት ስለፍቅርህ መስክረዋል*”** የቀደመችው ቤተክርስትያን (በኤፌሶን የምትገኘው) በማህበር በሚሰበሰቡበት ጊዜ የሚሲዮናዊያንን ሪፖርት ይሰሙ እንደነበር ግልጽ ነው፡፡

---

**ልዩ ርዕስ፡ ቤተክርስትያን (ኤክሲስያ)**

ይህ ኤክሲስያ የሚለው የግሪኩ ስያሜ ከሁለት ቃላት የመጣ ነው፡፡ “የወጡ” እና “የተጠሩ” የሚሉ፡፡ በመሆኑም ስያሜው የሚያመለክተው በመለኮት ተጠርተው የወጡትን ነው፡፡ የቀደመችው ቤተክርስትያን ይህንን ስያሜ ከዓለም (ሐዋ 19÷23:39:41 ያስ.) እና የሰብትዋጅንት ምንጭ የእስራኤልን “ማህበር” (Qahal, DBD 874፤ ዘሕ 19÷3፤20÷4ን ያስ.) የሚለውን ስለሚጠቀም ነው፡፡ እነርሱም ስያሜውን የተጠቀሙበት የብሉይ ኪዳን ቀጣይ ሕዝቦች መሆናቸውን ለማመልከት ነበር፡፡ እነርሱም አዲሲቷ እስራኤል (ሮሜ 2÷28-29፤ ገላ 6÷16፤1ጴጥ 2÷5:9፤ ራዕይ 1÷6)፤ የእግዚአብሔር ዓለም አቀፋዊ የወንጌል ተልዕኮ ሙላት ናቸው (ዘፍ 3÷15፤ 12÷3፤ ዘፀ 19÷5-6፤ማቴ 28÷18-20፤ ሉቃ 24÷47፤ ሐዋ 1÷8)፡፡

ይህ ስያሜ በወንጌላት እና በሐዋርያት ስራ ውስጥ በተለያዩ ትርጉሞች ይጠቀሳል፡፡

1. ዓለማዊውን የከተማ ውስጥ ግኑኝነትን ያመለክታል፡፡ ሐዋ 19÷32:39:41
2. በክርስቶስ ያሉ ሁሉም የእግዚአብሔር ሕዝብ ማቴ 16÷18 እና ኤፌሶን
3. በአጥቢያ ያሉ በክርስቶስ ያሉ የአማኞች ጉባኤ፤ ማቴ 18÷17፤ ሐዋ 5÷11 (በእነዚህ ጥቅሶች በኢየሩሳሌም ያለችውን ቤተክርስትያን ይመለከታል)፡፡
4. በእስጢፋኖስ ስብከት የእስራኤል ሕዝብ በጥቅሱ ሐዋ 7÷38
5. በአንድ አካባቢ ያለ የእግዚአብሔር ሕዝብ፤ ሐዋ 8÷3 (ይሁዳ ወይም የፍልስጥኤም ምድር)

---

▣ “*መልካም ታደርጋለህ*” ይህ በግብፃዊያን ፓፒረስ ላይ ተጽፎ የሚገኝ የግሪኮች ፊሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ይህም “ሰላም” የሚለውን ለማመልከት ነው (ሐዋ 10:33 ን ያስ.)፡፡ በ *MoultoN* እና *MilligaN* የተጻፈውን፡- *The Vocabulary of the Greek TestameNt* የሚለውን መጽሐፍ ይመልከቱ፡፡

▣ “*በጉዞአቸው ብትረዳ*” ይህ ተጓዥ የሆኑ ሚሲዮናዊያንን የማስታጠቅ (የማዘጋጀት) ለእነርሱ የሚፀለይን እንዲሁም በሚያስፈልጋቸው ሁሉ መረዳትን ለመግለጽ የተጠቀመው ቴክኒካዊ የአነጋገር ስልት ነው (ሐዋ 15:3፤ ሮሜ 15:24፤ 1ቆሮ 16:16፤ 2ኛ ቆሮ 1:16፤ቲቶ 3:13)፡፡

▣ “*ለእግዚአብሔር እንደሚገባ አደርገህ*” ይህ ጠቀሜታ ባለው፣ ፍቅር በተሞላበት እና በተትረፈረፈ መንገድ /ሁኔታ ማለት ነው (ቆላ 1:10፤ 1 ተስ 2:12)፡፡ አማኞች የወንጌል አገልጋዮችን ሊይዟቸው/ሊንከባከቧቸው የሚገባ ማንን እንደሚያገለግሉ በተረዱበት መጠን ነው (ኢፌ 4:1 ን ያስ.)፡፡

**ቁ.7**

| | |
|---|---|
| NASB፤አር.ኢ.ቤ | **“ወጥተዋልና”** |
| NKJV | **“መውጣት ጀምረዋል”** |
| NRSV | **“ጉዞአቸውን ጀምረዋል”** |
| TEV፤NJB | **“ጀምረዋል”** |

ይህ የተለመደ ግስ የሚጠቀሰው

1. በ1ኛ ዮሐንስ 2:19 ላይ ከቤተክርስትያን አፈንግጠው የሚወጡትን የሐሰት አስተማሪዎችን ለማሳየት
2. በ1ኛ ዮሐንስ 4:1 ላይ ወደ ዓለም የወጡትን የሐሰት ነብያትን ለማሳየት
3. በ2ኛ ዮሐንስ ቁጥር 7 ላይ ወደ ዓለም የሚወጡትን ብዙ አሳቾች ለማሳየት
4. በ3ኛ ዮሐንስ ቁጥር 7 ላይ የተጠቀሱትን እና ወደ ዓለም የሚሄዱትን (ወደ ዓለም) እውነተኛ የሐዋሪያት ምሥክሮችን ለማሳየት፡፡

▣

NASB "ስለሰው"
NKJV "ስለ ስሙ ሲሉ"
NRSV "ስለ ክርስቶስ ሲሉ"
TEV "ክርስቶስን በማገልገላው"
NJB "በጠቅላላው ስለስሙ ሲሉ"

ይህ "ስሙ" የሚለው የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት እና ስራውን የሚያሳይ ምሳሌ ነው። አማኞች በስሙ እንዳመኑ ሁሉ (ዮሐንስ 1:12፤3:18፤ሮሜ10:9፤ 1ቆሮ12:3፤ ፊል2:9-11ን ያስ.) በስሙ ይቅርታን ያገኛሉ (1ኛ ዮሐንስ 2:13)፤ ስለ ስሙም ሲሉ ያደርጋሉ (ማቴ10:22፤ 24:9፤ማር13:13፤ ሉቃ21:12፡17፤ ዮሐንስ 15:21፤ 20:31፤ሐዋ4:17፤ 5:41፤ 9:14፤ ሮሜ1:5፤1ጴጥ 4:4:16፤ራዕይ 2:3)።

▣

NASB "ከአህዛብ አንዳች ሳይበቀሉ"
NKJV "ከአህዛብ ምንም ሳይወስዱ"
NRSV "ከማያምኑት ምንም ድጋፍ ሳይበሉ"
TEV "ከማያምኑት ምንም አይነት እርዳታ ሳይበሉ"
NJB "በማያምኑት ላይ ለምንም ነገር ጥገኛ ሳይሆን

ይህ ሐረግ ልክ ኢየሱስ በማቴዎስ 10:5-15 ላይ ለአስራ ሁለት እንደተናገረው እና ለሰባዎቹ በሉቃስ 10:4-7 ላይ እንዳረጋገጠው እነዚህ የወንጌሉ ምስክሮች በእግዚአብሔር ቸርነት እና ባለጠግነቱ ላይ መተመናቸውን የሚያመለክት ነው። ይህ በመጀመሪያ ክፍለ ዘመን የኃለኞቹ ዓመታት ላይ አረማውያንን ወይም የማያምኑትን "አህዛብ" በማለት በተዘዋዋሪ የተጠቀሰ አባባል ነው (ማቴ ሰ:47፤ 1ጴጥ2:12፤4:3)። አማኞች ሁሉ የወንጌልን ስራ ሊደግፉ ይገባል! አንድ ሰው የሚያደርገው መልካም ስራ የልቡን ማንነት ይገልጣልና።

ዮሐንስ በነበረበት ጊዜ ብዙዎች ከስፍራ ስፍራ የሚዘዋወሩ አስተማሪዎች ስለገንዘብ እና ክብር ያስተምሩ ነበር። የእግዚአብሔር አስተማሪዎች /ሰባኪዎች/ ወንጌላዊያን ሊረዱ የሚገባቸው ስለቃላቸው ሳይሆን መሥዋዕት ነትን ለሚከፍሉበት ስለጌታቸው የወንጌል ተልዕኮ ነው።

**ቁ.8 "ይገባናል"** ይህ ብዙውን ጊዜ የሚደጋገም ምራላዊ ተግሳጽ ነው (ዮሐንስ 13:14፤19:7፤ 1ዮሐንስ 2:6፤ 3:16፤ 4:11ን ያስ.)። ኦፌሊዮ የሚለው መጠሪያ ቃል በቃል ትርጉም በገንዘብ እዳ ውስጥ መሆን ማለት ሲሆን ነገር ግን በዚህ ስፍራ የቃሉ ትርጉም ለአንድ ሰው መገደድ ወይም ባለ ዕዳ መሆን በሚል ሃሳብ በሥዕላዊ መልክ ቀርቧል።

▣ **"እንዲህ ያሉትን… ስንቀበል"** እንግዶችን መቀበል /እንግዳ ተቀባይነት የቀደመችው ቤተክርስትያን ትከተል የነበረው በጣም አስፈላጊው ተግባር ነበር ምክንያቱም በየአካባቢው በነበሩት ትናንሽ የመመገቢያ ቦታዎች ከነበረው አሳዛኝ ከሆኑ ግብረ ገባዊ ሁኔታዎች የተነሳ (ማቴ 25:35፤ ሮሜ 12:13፤/ጢሞ 3:2፤5:10፤ ቲቶ 1:8፤ዕብ 13:2፤1 ጴጥ 4:9)።

▣ **"ከእውነት ጋር አብረን እንድንሰራ"** አማኞች ሚሲዮናዊያንን በረዱ መጠን በእነርሱ የእምነት እና የእውነት ስራቸውም ተካፋዮች ይሆናሉ ማለት ነው። ይህ ነው የወንጌል መርሕ! ክርስትያናዊ መስጠትን በሚመሉት ያሉት የአዲስ ኪዳን መመሪያዎች በ2ኛ ቆሮንቶስ 8-9 ውስጥ ተገልጸው ይታያሉ።

> **NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 9-10**
> **[9]ወደ ቤተክርስትያን ዳፍሁ ነገር ግን ዋናቸው ሊሆን የሚወድ ዲዮጠራጢስ አይቀበለንም። [10]ስለዚህ÷እኔ ብመጣ÷በእኛ ላይ በክፉ ቃል እየለፈለፈ የሚያደርገውን ስራውን አሰዋስባለሁ፤ ይህም ሳይበቃው እርሱ ራሱ ወንድሞችን አይቀበልም÷ሲቀበሉ አችውም የሚወዱትን ከልክሎ ከቤተክርስትያን ያወጣቸዋል።**

**ቁ.9 "ወደ ቤተክርስትያን ጻፍሁ"** ይህ ምናልባት 1ኛ ወይም 2ኛ ዮሐንስን ወይም የጠፋውን መልዕክት ሊያመለክት ይችላል፤ ነገር ግን ከሁሉም ይልቅ 2ኛ ዮሐንስን ሊያመለክት ይችላል። በቁጥር 6 ላይ ቤተክርስትያን (ኤክሌስያ) የሚለውን ተጨማሪ የጥናት ርዕስን ይመልከቱ።

▣ **"ዋናቸው ሊሆን የሚወድ ዲዮጥራጢስ"** ይህ የአሁን ጊዜን አመልካች ቦዝ አንቀጽ ነው። ይህ "ፍቅር" (ፊሎ) እና "የመጀመሪያ ደረጃን መያዝ" (ፕሮታም) ከሚሉ ስያሜዎች የተገኘ ጭምር ስያሜ ወይም መጠሪያ ነው። ይህ ጥምር ቃል በአዲስ ኪዳን ብቻ የተጠቀሰ ሲሆን ሁለተኛው ስያሜ ግን በቀላ1:18 ላይ የክርስቶስን ቀዳሚ ስልጣን (ፊተኛ መሆን) ለማመልከት ተጠቅሷል። ይህ ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ "የሥልጣን ደለላ" ወይም "የቤተክርስትያን አለቃ" ተብሎ የተጠቀሰ ነው። ይሁን እንጂ ይህ የእርሱን መነሻ ሐሳብ የሚያመለክት አይደለም። እንዲህ አይነቱ ራስ ወዳድ ሰው በየትኛውም የቤተክርስትያን ዘመን ያለ ነው!፤ ኖስቲላዊ መሆን አለመሆኑ የሚታወቅ እና የተረጋገጠ ባይሆንም ምናልባት ደግሞ ሊሆን የሚችል እርስ አለሙ።

ጀምስ ዱን:- *UNity aNd Diversity iN the New TestameNt* (ገጽ 392) በሚለው መጽሐፋቸው ላይ ዲዮስጠራጢስን እንደ “ቀድሞው ካቶሊሲዝም” ይመለከቱታል፡፡

“በተለይም የዮሐንስ ግላዊነት በመጋቢያን ዘንድ የነበረውን ቤተክርስትያንን በተቋም ደረጃ የማየት አዝማሚያን (ከገጽ 129 በላይ፤ እንዲሁም ደግሞ የዕብራዊያን እና የራዕይ መፅሐፍን፡- 31-2:3) በቀጥታ መቃወሙ አሳማኝ በሆነ ሁኔታ ግንዛቤን አግኝቷል፡፡ እንዲሁም ደግሞ የዮሐንስ ጽሑፎች ኢግናቲየስ በነበረበት ዘመን በነበረችው ቀደሞት ካቶሊካዊት ቤተክርስትያን ዘንድ የነበረውን የቁርባን ሥርዓት የሚቃወምም ይመስላል (“ዘ ሜዲሲን ኦፍ ኢ ምራሊቲይ” ኤፌ 20-2) (ከቁ. 41 በላይ ያለውን ይመልከቱ)፡፡ ከሁሉም ይበልጥ ደግሞ አስደሳች የሆነው “ሽማግሌ” ተብሎ በ3ኛ ዮሐንስ ቁ. 9 ላይ የተጠቀሰውን ዲዮስጥራጢስ ላይ የተደረገው ጥቃት ነው፡፡ ዲዮጢራጢስ ቢያንስ ይህንን ቤተክርስትያን ተቆጣጥሮት ነበር፡- የሚመጡትን ክርስትያኖች ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆን ብቻ ሳይሆን ሊቀበሉ አቸውም የሚወዱትን ከልክሎ “ከቤተክርስትያን በማስወጣት” ጭምር እንጂ ዲዮስጥራጢስ በሌላ አባባል ያደርግ የነበረው እንደ ንጉሳዊ ኤጲስ ቆይል ነበር ማለት ይቻላል (ኢግናቲየስ፤ ኢፌ 6:1፤ትሮስ፡- 7:2፤ ስምር 8:1ን ያስ.) ለዚህም ነው “ሽማግሌው” ይህን በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለውን የበላይነት እና የሥልጣን ጥመኝነትን በሚመለከተ በመቃወም የጻፈው (ፊሎፕሮቲዮን)፡በሌላ አባባልም 3ኛ ዮሐንስ እንደ 1ኛ እና 2ኛ ዮሐንስ ከተመሳሳይ ምንጭ እንደመጡ በመገመት ከቀድሞው ይልቅ እየተጠናከረ ለመጣው የካቶሊክ ኃይማኖት ተቀባይነት ያለው ስምምነት ወይም ፀረ-ተቋማዊ (ቤተክርስትያንን) እንዲሁም ግለሰባዊ ቅድስናን በሚመለከት የቀረበ ተቃውሞ ነው ማለቱ ከሁሉም የተሻለ እይታ ነው”

▣ **“አይቀበለንም”** ዲዮስጥራጢስ የሚቀመጠው የዮሐንስን ሥልጣን ብቻ አልነበረም፤ ነገር ግን የሐዋርያትን አመራር እና አመራሩንም የሚከተሉትንም በጽኑ በመቃወም ጭምር እንጂ!

**ቁ.10. “ብ…”** ይህ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ አረፍተ ነገር ሲሆን ድርጊትን ለመፈጸም ሃይል መኖሩን የሚያመለክት ነው፡፡

▣ **“የሚያደርገውን ስራውን አሳስባለሁ”** ዮሐንስ የዚህን ሰው መነሻ ሐሳብ (ቁ. 9) እና ድርጊቱን (ቁ. 10) በግልጽ ማስረዳት ይፈልጋል፤

1. NASB - “በእኛ ላይ በክፉ ቃል እየለፈለፈ”
   NKJV - “በተንኮል አዘል ቀላት እየቀባጠረ”
   NRSV - “እኛን በሐሰት እየከሰሰን”
   TEV - “ስለ እና የሚላቸው አስደንጋጭ ነገሮች እና የሚናገራቸው ውሸቶች”
   NJB - “እኛን በሚመለከተ የሚያስራጨው ክፉ ቃላት”
2. “እርሱ ራሱ ወንድሞችን አይቀበልም”
3. “ሊቀበሉአቸውም የሚወዱትን ከልክሎ”
4. “ከቤተክርስትያን ያስወጣቸዋል”

ይህ ሰው ከሁሉም ይልቅ ትኩረትን የሚሻ እና ያለውንም እውቅና ከማንም ጋር ለጋራ የማይፈልግ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር ከእርሱ ጋር የማይስማሙትን ወይም ሳይስማሙ የሚችሉትን ከቤተክርስትያን ያስወጣቸዋል፡፡

▣ **“ከቤተክርስትያን ያወጣቸዋል”** ይህ ተመሳሳይ ጠንካራ ግሥ (ኤክባሎ) በዮሐንስ 9:34፡35 ላይ ኢየሱስ የፈወሰው እና ከምኩራብም ተገፍቶ የመጣውን አይነስውር ለመግለጽ ተጠቅሷል፡፡
ከዚህም ባሻገር ይህ ግስ ሰይጣንን ስለማስወጣት በዮሐንስ 12:31 ላይ ተጠቅሷል፡፡

NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 11-12
**[11]“ወዳጅ ወይ÷ በጎ የሆነውን እንጂ ክፉን አትምሰል፡፡ በጎ የሚያደርግ ከእግዚአብሔር ነው፤ ክፉን የሚያደርግ ግን እግዚአብሔርን አላየውም፡፡ [12]ለድሜጥሮስ ሁሉ ይመሰክሩለታል÷ እውነት ራስዋም ትመሰክራለታለች እኛም ደግሞ እንመሰክርለታል÷ ምስክርነታችንም እውነት እንደሆነ ታውቃላችሁ፡፡**

**ቁ.11 “ክፉን አትምሰል”** ይህ የአሁን ጊዜ ትእዛዝ አመልካች መሐከለኛ ግስ ሲሆን ብዙውን ጊዜ የሚያሳየው በሂደት ላይ ያለን ድርጊትን ማቆም ነው፡፡ የግሪኩን *ሚሚዮማይ* የሚለውን ስንመለከት *ቀዳ* የሚለውን የእንግሊዘኛውን መጠሪያ እናገኛለን፡፡ ምሳሌ የሚሆኑንን ሰዎ በጥንቃቂ መምረጥ አለብን፡፡ እነዚህም ሰዎች በቤተክርስትያን ውስጥ ያሉ ብስለት ያላቸው ሰዎች ሊሆኑ ይገባል (2ተስ 3:7፡9፤ዕብ 6:12፤13:7)፡፡ ዲሜጥሮስ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን የሚችል ሲሆን ዲዮስጥራጢስ ደግሞ መጥፎ ምሳሌ የሚሆን ነው፡፡

▣ **“በጎ የሚያደርግ ከእግዚአብሔር ነው”** የዮሐንስ መልእክቶች አንድ ሰው ክርስትያን መሆኑን የሚመዝንባቸው ሶስት መመዘኛዎች አሏቸው፡፡ ይህም የሚያመለክተው፤ የመታዘዝ መመዘኛን ነው (1 ዮሐንስ 2:3-6፡28-29፤3:4-10፤5:18፤2 ዮሐንስ6)፡፡ ሌሎቹን ሁሉን መመዘኛዎች በሚመለከት ደግሞ በተዘዋዋሪ የተጠቀሰ አለ፤ (1) አስተምህሮ (ቁ. 3-4) እና (2) ፍቅር (ቁ. 1-2:6)፡፡

▣ **"ክፉን የሚያደርግ ግን እግዚአብሔርን አላየውም"** የሐሰት አስተማሪዎች እግዚአብሔርን በቅርበት እንደሚያውቁት በአፅንኦት ይናገራሉ፤ ነገር ግን ሕይወተኛው በአምላክ የለሸንት እና ፍቅር የለሸንት የተሞን ነው፡፡ ይህም የሚያንጸባርቀው ጽላት የአእምሮ እውቀት ጉዳይ እንደሆነ እና በዕለታዊ ሕይወታቸው ምንም አይነት ሕብረት እንደሌላ የሚሚገቱ ሥርዓት አልበኛ የሆኑ ኖስቲሳዊያን የሚያራምዱትን አቋም ነው፡፡

**ቁ.** 12 **"ለድሜጥሮስ ሁሉ ይመሰክሩለታል"** ይህ ያልተጠናቀቀ ተደርጎ ግስ አመልካች ነው፡፡ ይህ ምናልባት የ3ኛ ዮሐንስን መልዕክት ለጋይዮስ የመጣውን ሚስዮናዊውን ዴሜጥሮስን በሚመለከት የተላከ የምስጋና መልዕክት /ምስክርነት በእርግጥ የሚመስል ነው፡፡ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለሚገኙ ሌሎች ምስክርነቶች ሐዋ 18:27፤ ሮሜ 16:1፤ 1ቆሮ 16:3፤2ቆሮ 3:1፤8:16-24፤ቆላ4:10ን ይመልከቱ፡፡

▣ **"እውነት ራስዎም"** እውነት (በዮሐንስ 6:55 እና 17:3 ላይ ያለውን ተጨማሪ መልዕክት ይመልከቱ) የዲሜጥሮስን መልካም ምስክርነት ለመመስከር እንደሌላ ምስክር ስብእናን ተላብሶ ቀርቧል፡፡

▣ **"ምስክርነታችንም እውነት እንደሆነ ታውቃላችሁ"** ዮሐንስ ደጋግሞ ስለኢዮሱስ ክርስቶስ የሰጠውን የራሱን ምስክርነት አስረግጦ ይናገራል (ዮሐንስ 19:35፤21:24ን ያስ.) ፡፡

| |
|---|
| NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 13-14<br>**[13]ልጽፍልህ የምፈልገው ብዙ ነገር ነበረኝ÷ዳሩ ግን በቀለምና በብርዕ ልጽፍልህ አልወድም፤ [14]ነገር ግን ወዲያው ላይህ ተስፋ አደርጋለሁ፤አፍ ለአፍም እንነጋገራለን፡፡** |

ቁ.13 ይህ ከ2ኛ ዮሐንስ 12 ጋር በጣም ተመሳሳይ ነው፡፡

| |
|---|
| NASB (የተሻሻለው) ምንባብ፡ 14ለ<br>**[14ለ]ሰላም ለአንተ ይሁን፡፡ ወዳጆች ሰላምታ ያቀረቡልሃል፡፡ ወዳጆችን በየስማቸው እየጠራህ ሰላምታ አቅርብልኝ፡፡** |

**ቁ.**14 **"ሰላም ለአንተ ይሁን"** ይህ የእብራይስጡን ሻሎም (ሉቃ 10:5ን ያስ) እንደሚያመለክት ፈሊጣዊ/ዘይቤያዊ አነጋገር ነው፡፡ አባባሉ "ሄሎ" ወይም "ደህና ሁን" ማለትም ሊሆን ይችላል፡፡ አባባሉ የችግሮችን አለመኖር ብቻ ሳይን የእግዚአብሔርንም በረከት የሚገልጽ ነው፡፡ እነዚህም ከሞት የተነሳው ኢየሱስ ክርስቶስ በላይኛው ደርብ/ክፍል (ዮሐንስ 20:19፤21፡26ን ያስ.) የሚያመለክቱ ቃላት ናቸው፡፡ ጳውሎስ ኤፌ6:23ን ያስ.) እና ጴጥሮስ (1ጴጥ 5:14) ሁለቱም የእግዚአብሔርን ሕዝብ በሚመለከት በመልዕክቶቻቸው እንደመዝጊያ ጸሎት ጠቅሰውታል፡፡

▣ **"በየስማቸው"** ይህ ለግለሰብ የሚነገር ፈሊጣዊ የአነጋገር ዘይቤ ነው፡፡ በግብጻውያን ዘንድ ጥቅም ላይ በመዋል የታወቀ ነው፡፡

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ማብራሪያ በመሆኑ ለምትከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ኃላፊነት አለብህ፡፡ እያንዳንዳችን ልንጓዝ የሚገባን ባለን መረዳት መሰረት ነው፡፡ አንተ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስቅዱስ በአተረጓጎም ወቅት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ናችሁ፡፡ ይህንን ጉዳይ በሚያብራራው ሰው ላይ ብቻ ልትተወው አይገባህም፡-

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የቀረቡት በዚህ የመጽሐፍ ክፍል ውስጥ የተነሱትን አብይ ጉዳዮች ላይ በጥሞና እንድታሰብሷቸው ነው፡፡ ጥያቄዎች የቀረቡት እንደ ሐሳቡ አነዳሽ ሆነው እንጂ በራሳቸው ቀጥተኛ አይደሉም፡፡

1. ጋይዮስ እና ዲዮስጥራጢስ እርስ በርሳቸው ስለማይግባቡበት ሁኔታ በርካታ ፅንሰ-ሐሳቦች አሉ፡፡ ከእነዚህም አስተያየቶች ጥቂቶቹ፤
   ሀ. ሥነ-መለኮታዊ ምክንያቶች
   ለ. ማህበራዊ ምክንያቶች
   ሐ. የቤተክርስትያን ሁኔታዎች ምክንያቶች
   መ. ግብረ-ገባዊ /ሞራላዊ ምክንያቶች
   እነዚህ ምክንያቶች ከ3ኛ ዮሐንስ መልዕክት ጋር እንዴት ሊዛመዱ እንደሚችሉ ግለጽ፡፡
2. 2ኛ ዮሐንስ እና 3ኛ ዮሐንስ የሚዛመዱት እንዴት ነው?
3. በ1ኛ ዮሐንስ የሚገኝ እና በ2ኛ እና በ3ኛ ዮሐንስ ውስጥ ተደጋግመው የተጠቀሱትን የክርስትያን ድነትን የሚያረጋግጡ 3 መመዘኛዎችን ዘርዝር፡፡

## ተጨማሪ መግለጫ አንድ

## የግሪክ ሰዋሰዋዊ ቃላት አጭር መግለጫዎች

የኮኔ ግሪክ፣ ዘወትር ሔለናዊ ግሪክ የሚባለው፣ በሜዲትራኒያን የዓለም ክፍል አካባቢ ከታላቁ አሌክሳንደር ጀምሮ (336-323 ቅልክ) ዋነኛ ቋንቋ በመሆን አገልግሏል፤ ለ800 ዓመታት ገናና ሆኖ አክትማል (300 ቅልክ – 500 ዓም)። እሱም ቀለል ያለ የጥንታዊ ግሪክ አልነበረም፣ ነገር ግን በብዙ መንገዶች አዲሱ ግሪክ ሆኖ በጥንታዊው ቅርብ ምስራቅና በሜዲትራኒያን የዓለም ክፍል ሁለተኛ ቋንቋ ሆኖ ነበር።

የግሪኩ አዲስ ኪዳን በአንዳንድ መንገዱ የተለየ ነበር፣ ምክንያቱም ተጠቃሚዎቹ ከሉቃስና ከዕብራውያን ጸሐፊ በተቀር፣ ምናልባት አራማዊን እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተጠቅመው ይሆናል። ስለዚህ፣ ጽሑፎቻቸው የአራማዊ ፈሊጦችና መዋቅራዊ ቅርጾች ስላሉባቸው ነው። በተጨማሪም፣ ከሴፕቱዋጊንት (የግሪኩ የብሉ ትርጉም) ያነቡም ይጠቅሱም ነበር፣ ይህም ደግሞ በኮኔ ግሪክ የተጻፈው። ነገር ግን ሴፕቱዋጊንት ደግሞ የተጻፈው የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ግሪክ ባልሆነ የአይሁድ ሊቃውንት ነው።

ይህም አዲስ ኪዳንን ወደ ጥብቅ ሰዋሰዋዊ መዋቅር ወዳለው እንዳንገፋው እንደ ማስታወሻ ያገለግላል። እሱ የተለየ ያልሆነና ብዙ የሚጋራው ያለው ነው (1) ሴፕቱዋጊንት፤ (2) የግሪክ ጽሑፎች ለአብነትም የጆሴፈስ፤ እና (3) በግብፅ የተገኘው የወረቀት ጽሑፍ። ታዲያ እንዴት አድርገን የአዲስ ኪዳንን ሰዋሰዋዊ ትንታኔ እናካሂዳለን?

የኮኔ ግሪክ ሰዋሰዋዊ ባሕርይና የአዲስ ኪዳን ኮኔ ግሪክ ተወራራሽ ናቸው። በብዙ መንገዱ ሰዋሰውን በቀላል መልክ የማቅረብ ጊዜ ነበር። ጽሑፉ ዋነኛው መመሪያችን ይሆናል። ቃላቶች ትርጉም የሚኖራቸው በሰፊ ጽሑፍ ነው፤ ስለሆነም፣ ሰዋሰዋዊ መዋቅርን መረዳት የሚቻልበት ብርሃን (1) የጸሐፊው የተለየ ያጻጻፍ ስልት፤ እና (2) የተለየ የጽሑፍ አካል ነው። በግሪክ ቅርጾችና መዋቅሮች ላይ ለድምዳሜ የሚሆን ተስማሚ መግለጫ የለም።

ኮኔ ግሪክ በመጀመሪያ ግሣዊ ቋንቋ ነበር። ዘወትር ለትርጓሜው ቁልፉ የግሡ ዓይነትና ቅርጽ ነው። በብዙ ዋነኛ ሐረጎች ግሡ በመጀመሪያ ይመጣና፣ ዋነኛ ጠቀሜታውን ያስከትላል። የግሪክን ግሥ ለመተንተን ሦስት የሚሆኑ መረጃዎች የግድ ያሻሉ፡ (1) መሠረታዊ አጽንኦት የሰጠው ጊዜ፣ ድምጸት (ገቢር/ተገብሮ) እና ሁኔታው (ገጠመኙ ወይም የግሡ ርባታ)፤ (2) የተለየው ግሥ መሠረታዊ ፍቺ (ሥርወ ቃል)፤ እና (3) የጽሑፉ አወራረድ (አገባብ)።

I. ጊዜ

ሀ. ጊዜ ወይም ገጽታ የሚያካትተው የግሥን የተጠናቀቀ ድርጊትና ያልተጠናቀቀ ድርጊትን ግንኙነት ነው። ይህም ዘወትር "የተጠናቀቀ" እና "ያልተጠናቀቀ" በመባል ይታወቃል።

1. የተጠናቀቀ ጊዜ የሚያተኩረው የድርጊትን መከናወን ነው። አንድ ነገር ከመሆኑ ውጪ ተጨማሪ መረጃ አይሰጥም! አጀማመሩ፣ አካሄዱ ወይም ማብቃቱ አይካተትም።
2. ያልተጠናቀቀ ጊዜ የሚያተኩረው የአንድን ድርጊት ቀጣይነት ነው። linear action (ተሸጋጋሪ ድርጊት፣ በመካሄድ ላይ ያለ ድርጊት፣ ቀጣይ ድርጊት፣ ወዘተ።

ለ. ጊዜያቶች፣ ጸሐፊው ድርጊቶች እንዴት እንደተካሄዱ በተመለከተበት አግባብ ሊመደቡ ይችላሉ

1. ሆኗል = ያልተጠናቀቀ ግሥ
2. ሆኖአል እናም ውጤቱም ይገኛል = የተጠናቀቀ
3. ባለፈው ጊዜ ተጠናቋል እናም ውጤቱ ይኖራል፣ አሁን ግን አይደለም = በኃላፊ ጊዜ የተጠናቀቀ
4. እየሆነ ነው = የአሁን
5. ሆኗል = ያልተጠናቀቀ
6. ይሆናል = የወደፊት

እነዚህ ጊዜያቶች ለትርጓሜ እንዴት እንደሚረዱ ተጨባጭ ምሳሌ ሊሆነን የሚችለው "መዳን" የሚለው ቃል ነው። እሱም በበርካታ የጊዜያት ዓይነቶች ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን ከሂደቱንም ሆነ ፍጻሜውን ያመላክታል።

1. የድርጊት ግሥ – "ድኗል" (ሮሜ. 8፡24)

2. የተጠናቀቀ – “ድኗል እናም ውጤቱ ይቀጥላል” (ኤፌ. 2፡5፣8)

3. የአሁን – “የዳነ” (1ኛ ቆሮ. 1፡18፤ 15፡2)

4. የወደፊት (የትንቢት) – “ይድናል” (ሮሜ. 5፡9፣ 10፤ 10፡9)

ሐ. በግሥ ጊዜያቶች ላይ በማተኮር፣ ተርጓሚዎች፣ ዋናው ጸሐፊ ራሱን ለመግለጽ የመረጠበትን ምክንያት ይቃኛሉ። መደበኛው “ከስም በፊት የሚመጣቅ ግሥ” ጊዜያቱ ያልተጠናቀቀ የተግባር ግሥ ነበር። እሱም መደበኛው “ያልተወሰነ፣” “ያልተለየ፣” ወይም “ዘወትር ከስም በፊት” የሆነ ግሥ ነው። በበርካታ የተለያዩ መንገዶች ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል ጽሑፉ በሚወስነው መሠረት። እሱም አንድ ነገር መሆኑን ያሳያል። የኃላፊ ጊዜው ገጽታ ጥቅም ላይ የዋለው በአመላካች ተግባር ነው። ሌላ ጊዜ ጥቅም ላይ ከዋለ አንድ ልዩ ነገር አጽንዖት ተሰጥቶታል ማለት ነው። ግን ምን?

1. የተጠናቀቀ ጊዜ። ይህ የሚናገረው የተጠናቀቀ ድርጊትን ከሚኖረው ውጤት ጋር ነው። በአንዳንድ አገባቦች ያልተፈጸመ ጊዜ (የድርጊት ግሥ) እና የአሁን ጊዜን የደባለቀ ነው። ብዙውን ጊዜ የሚያተኩረው የተገኘው ውጤት ላይ ወይም የድርጊት መጠናቀቅ ላይ ነው። ለምሳሌ፡ ኤፌ. 2፡5 እና 8፣ “ድናችኋል፣ በመዳናችሁም ቀጥላችኋል።”
2. በኃላፊ ጊዜ የተጠናቀቀ። ይህም እንደ ተጠናቀቀ ጊዜ ሆኖ የሚኖረው ውጤት ያበቃበት ነው። ለምሳሌ፡ “ጴጥሮስ ከበሩ በስተውጭ ቆሞ ነበር” (ዮሐንስ 18፡16)።
3. የአሁን ጊዜ። ይህ የሚያሳየው ያላበቃለት ወይም ያልተጠናቀቀ ድርጊትን ነው። ትኩረቱም ብዙውን ጊዜ በሁኔታው ቀጣይነት ላይ ነው። ለምሳሌ፡ “በእርሱ የሚኖር ሁሉ ኃጢአትን በመሥራት አይቀጥልም፣” “ማንም ከእግዚአብሔር የተወለደ ኃጢአትን በመፈጸም አይቀጥልም” (1ኛ ዮሐንስ 3፡6 እና 9)።
4. ያልተጠናቀቀ ጊዜ። በዚህ ጊዜ ከአሁን ጊዜ ጋር ያለው ግንኙነት ከተጠናቀቀ እና በኃላፊ ጊዜ ከተጠናቀቀው ጊዜ ጋር ያለው ግንኙነት ተመሳሳይ ነው። ያልተጠናቀቀው የሚያሳየው ያላበቃለትን ድርጊት ማለትም ተጀምሮ አሁን ያበቃለትን ወይም ባለፈው ጊዜ የነበረውን ድርጊት መጀመሪያ ነው። ለምሳሌ፡ “ከዚያም ሙሉው ኢየሩሳሌም ወደ እሱ መውጣታቸውን ቀጠሉ” ወይም “ከዚያም ሞላው ኢየሩሳሌም ወደ እሱ መውጣት ጀመሩ” (ማቴ. 3፡5)።
5. የትንቢት ጊዜ። ይህ የሚያሳየው ዘወትር በመጪው ጊዜ የሚፈጸምን ንድፍ አመላካች ነው። የሚያተኩረውም አሁን በተፈጠረው ሁኔታ ሳይሆን ወደፊት ሊፈጠር በሚችለው ላይ ነው። ዘወትር የሚናገረውም የሁኔታዎቹን እውንነት ነው። ለምሳሌ፡ “ብፁዓን ናቸው… እነሱ ወደፊት…” (ማቲ. 5፡4-9)።

II. የግሥ ጊዜያት (ድምጸት)

ሀ. የግሥ ጊዜያት የሚገልጸው የግሥን ድርጊትና የባለቤቱን ግንኙነት ነው።

ለ. የአሁን ጊዜ ተራ፣ የሚጠበቅ፣ ያልተጋነነ መንገድን ይዞ ለማለት የሚፈልገውን ባለቤቱ የግሡን ድርጊት ሲከውን ነው።

ሐ. ተገብሯዊ ጊዜ ማለት ባለቤቱ የድርጊቱ ተቀባይ ሲሆን ማለት በውጭ አካል የተደረገውን። በውጭ አካል የሚፈጸመው ድርጊት በግሪክ አኪ ሲመለከት በሚከተለው መስተጻምራት እና አግባቦች ላይ ይታያል፡

1. ቀጥተኛ ሰዋዊ አድራጊ በ(hupo) ሲፈጸምና በስም፣ በተውላጠ ስምና በቅጽል የሚታይበት አግባብ ሰከሰት (ማቲ. 1፡22፣ ሐዋ. 22፡30)።
2. ሰዋዊ መካከለኛ ፈጻሚ በ(dia) በስም፣ በተውላጠ ስምና በቅጽል የሚታይበት አግባብ ሲከሰት (ማቲ. 1፡22)።
3. ሰዋዊ ያልሆነ ፈጻሚ፣ ዘወትር በ(en) በቁሳቁሳዊ አግባብ።
4. አንዳንድ ጊዜ በሰዋዊ ሆነ ሰዋዊ ባልሆነ ፈጻሚ፣ በቁሳዊ አግባብ ብቻ።

መ. መካከለኛ ጊዜ ማለት ባለቤት የግሡን ተግባር ሲፈጽም እና እንዲሁም በቀጥታ በግሡ ድርጊት ላይ በቀጥታ ሲገባ ነው። ዘወትር ከፍ የተደረገ ሰዋዊ ፍላጎት የግሥ ድምጸት ተብሎ ይጠራል። ይህ አወቃቀር በተመሳሳይ መንገድ ለሐረጉ ወይም ለዓረፍተ ነገሩ ባለቤት አጽንዖት ይሰጣል። ይህ አወቃቀር በእንግሊዝኛ አይገኝም። እሱም ሰፋ ያለ የግሪክ ፍቺ እና ትርጉም አግባብ አለው። ለዚህ ዓይነት የሚሆኑ ጥቂት ምሳሌዎች፡

1. አነጻጻሪ – የባለቤቱ ቀጥተኛ ድርጊት በራሱ ላይ። ምሳሌ፡ "ራሱን ሰቀለ" (ማቴ. 27፡5)።
2. የታሰበበት – ባለቤት ድርጊቱን ለራሱ ይፈጽማል። ምሳሌ፡ "ሰይጣን ራሱን እንደ ብርሃን መልአክ ይለውጣል" (2ኛ ቆሮ. 11፡14)።
3. ባለ ሁለት ወገን – የሁለት ባለቤቶች ውስጣዊ ድርጊት። ምሳሌ፡ "እርስ በርሳቸው ተመካከሩ" (ማቴ. 26፡4)።

III. አኳኋን (ወይም አገባብ)

ሀ. በኮኔ ግሪክ አራት አገባቦች አሉ። እነርሱም የግሥን እውነታዊ ግንኙነት ይጠቁማሉ፣ ይሄውም በተቻለ መጠን ጸሐፊው በራሱ ሐሳብ። አገባቦች በሁለት ሰፋፊ ምድቦች ይከፈላሉ፤ እውነታን የሚጠቁሙ (ጠቋሚ) እና በውስጥ ያለ አቅም ጠቋሚዎች (መሻታዊ ሁኔታ (አጠራጣሪ)፣ ትዕዛዝ አንቀጽ እና አማራጫዊ ናቸው።)

ለ. አመላካች አገባብ ሁነኛ አገባብ ሲሆን የተከናወነን ወይም ተከናውኖ የነበረን ማለትም ቢያንስ በጸሐፊው ልቦና የነበረን ለመግለጽ የሚያገለግል ነው። ይህም ብቸኛው የግሪክ አገባብ ሆኖ ትክክለኛን ጊዜ የሚገልጽ ነው፣ እዚህም ቢሆን ይህ ገጽታ ሁለተኛ ነው።

ሐ. ተያያዥ አኳኋን የሚገለጠው በምናልባታዊ የትንቢት ድርጊት ነው። አንድ ነገር ገና አልሆነም፣ ነገር ግን የመሆን ዕድል አለው። ከትንቢታዊ አመላካች ጋር በርካታ የሚጋራው አለው። ልዩነቱ መሻታዊው የሚገልጸው የተወሰነ ደረጃ ያለው አጠራጣሪነትን ነው። በእንግሊዝኛ ይህ ዘወትር "ይችላል፣" "ነበር፣" "ምናልባት፣" "ምናልባት።"

መ. አማራጫዊ ሁኔታ የሚገልጸው በንድፈ ሐሳባዊ ደረጃ ሊሆን የሚችለውን ነው። ከመሻታዊው አንድ ደረጃ ከእውነታ ቀደም ብሎ ይገኛል። አማራጫዊው አጠራጣሪነትን የሚገልጸው በተወሰኑ ሁኔታዎች ነው። አማራጫዊው በአዲስ ኪዳን አልፎ አልፎ ነው የሚገኘው። በጣም የታወቀው ድግግሞሻዊ አጠቃቀሙ የሚገኘው በታወቀው የጳውሎስ ሐረግ፣ "እንዲህስ አይሁን" (ኪጀቅ፣ "እግዚአብሔር አያርገው")፣ የሚለው አስራ አምስት ጊዜ (ሮሜ. 3፡4፣ 6፣ 31፤ 6፡2፣ 15፤ 7፡7፣ 13፤ 9፡14፤ 11፡1፣ 11፤ 1ኛ ቆሮ. 6፡15፤ ገላ. 2፡17፤ 3፡21፤ 6፡14) ጥቅም ላይ ውሏል። ሌሎች ምሳሌዎችም ተሰ. (?) 1፡38፣ 20፡16፣ ሐዋ. 8፡20፣ እና 1ኛ ተሰ. 3፡11።

ሠ. ትዕዛዛዊ ሁኔታ አጽንዖት የሚሰጠው ሊሆን የሚችል ትዕዛዝ ላይ ሆኖ አጽንዖቱ ግን በተናጋሪው ፍላጎት ላይ ነው። እሱም በፍቃድ ላይ የተመሠረተውን ብቻ አማራጭ አመላክቶ እንዲሁም በሌላው ሁኔታዊ አማራጭ ላይ ነው። ትዕዛዛዊ ሁኔታ በጸሎት እና በሦስተኛ መደብ ጥያቄዎች ላይ ልዩ አጠቃቀም አለው። እነዚህ ትዕዛዛት በአኪ የሚገኙት በአሁን እና በግብር ግሦች ነው።

ረ. አንዳንድ ሰዋሰዎች ቦዝ አንቀጽን እንደሌለኛው ሁኔታዊ ዕይነት ይመድቧቸዋል። እነዚህም በግሪክ አኪ የተለመዱ ናቸው፣ ብዙውን ጊዜ ግሳዊ ቅጽል በሚል። ከሚቀራረቡት ከዋናው ግሥ ጋር ተጣምረው ይተረጎማሉ። ቦዝ አንቀጽን ለመተርጎም የተለያየ ሰፋ ያለ አማራጭ አለ። እዚህ ላይ በርካታ የእንግሊዝኛ ትርጓሜዎችን መቃኘቱ ይበጃል። *መጽሐፍ ቅዱስ በሃያ ስድስት ትርጉሞች* በቤከር የታተመው ደኅና አድርጎ ይረዳል።

ሰ. የድርጊት አንቀጽ አመላካች፣ ሁነኛ ወይም "ያልተለየ" አንድን ሁኔታ (ድርጊት) ለመመዝገብ ይሆን ነበር። ማንኛውንም ጊዜ፣ ድምጸት ወይም የተለየ ትርጓሜያዊ ጠቀሜታ ያለው ሲሆን ይህም ዋነኛው ጸሐፊ ለማለት የፈለገውን ነው።

IV. የግሪክኛ ችሎታ ለሌለው ሰው የሚከተሉት የጥናት መርጃዎች አስፈላጊውን መረጃ ሊሰጡት ይችላሉ፡

ሀ. ፍሪበርግ፣ ባርባራ እና ጢሞቲ። *የተተነተነ የግሪክ አዲስ* ኪዳን። ግራንድ ራፒድስ፡ ቤከር፣ 1988።

ለ. ማርሻል፣ አልፍሬድ።   *ኢንተርላይነር (መስመራዊ) የግሪክ እንግሊዝኛ አዲስ ኪዳን።* ግራንድ ራፒድስ፡ ዞንደርቫን፣ 1976።

ሐ. ሞውንሲ፣ ዊሊየም ዲ. *የግሪክ አዲስ ኪዳን ቃላታዊ ትንታኔ።* ግራንድ ራፒድስ፡ ዞንደርቫን፣ 1993።

መ. ጭምቅ ሐሳቦች፣ ሬይ. *የግሪክ አዲስ ኪዳን ጠቀሜታዎች።* ናሽቪሊ፡ ብሮድማን፣ 1950።

ሠ. በከፍተኛ ትምህርት ተቀባይነት ያለው የኮኔ ግሪክ የተልእኮ ኮርስ ከሞዲ መጽሐፍ ቅዱስ ተቋም፣ ቺካጎ፣ IL ይገኛል።

V. ስሞች

ሀ. ከአገባብ አኳያ፣ ስሞች የሚመደቡት በየጉዳዩ ነው። ጉዳዩ ከስሙ አኳያ መልኩ የተቀየረ ሲሆን ይህም ከግሡ እና ከሌሎቹ የዓረፍተ ነገሩ ክፍሎች ጋር ያለውን ግንኙነት ያመለክታል። በኮኔ ግሪክ ብዙዎቹ የጉዳዮ ተግባራት የሚጠቀሙት በመስተጻምሮች ነው። የጉዳዩ መልክ የተለያዩ በርካታ ግንኙነቶችን እንደመግለጡ መጠን፣ መስተጻምሮች ለእነዚህ ተግባራት የሚሆኑ ግልጽ መለያዎችን ያስቀምጣሉ።

ለ. የግሪክ ጉዳዮች በሚከተሉት ስምንት መንገዶች ይመደባሉ፡

1. ሳቢዎቹ ጉዳይ ጥቅም ላይ የሚውሉት ለስያሜ ሲሆን ዘወትርም የዓረፍተ ነገሩ ወይም የሐረጉ ባለቤት ይሆናሉ። በተጨማሪም ስም አመልካች ግሦችን እና ቅጽሎችን ከአያያዥ ግሦች ጋር "የመሆን" ወይም "የመኖር" ለመጠቀም ያስችላል።
2. አገናዛቢ ጉዳይ ጥቅም ላይ የሚውሉት የተለየ ባሕርይ ወይም ይዘት ለቃሉ እና ከእሱም ጋር ለተጎዳኙት የሚሰጥ መሆኑን ለመግለጽ ነው። "ምን ዓይነት?" የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል። ብዙውን ጊዜም የእንግሊዝኛውን መስተጻምር "የ"ን በመጠቀም ይታወቃል።
3. የስም፣ የተውላጠ ስምና የቅጽል ጉዳዮች ተመሳሳይ የሆነ መልኩ የተቀየረ እንደ አገናዛቢ ያለ ይጠቀማል፣ ነገር ግን መለያየትን ነው የሚያሳየው። ዘወትር የሚገለጸውም በጊዜ፣ በቦታ፣ በምንጭ፣ በመነሻ ወይም በደረጃ ያለውን ልዩነት ለማሳየት ነው። ብዙውን ጊዜም የእንግሊዝኛውን መስተጻምር "ከ"ን በመጠቀም ይታወቃል።
4. ቀጥተኛ ያልሆነ ተሳቢ (የስም) ጥቅም ላይ የሚውለው ግላዊ መሻትን ነው። ይህም አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ገጽታዎችን ያሳያል። ይህም ዘወትር ቀጥተኛ ያልሆነ ተሳቢ ነው። ብዙውን ጊዜም የእንግሊዝኛውን መስተጻምር "ወደ"ን በመጠቀም ይታወቃል።
5. አቅጣጫዊ ጉዳይ ቀጥተኛ ያልሆነ ተሳቢ ተመሳሳይ የስም፣ የተውላጠ ስምና የቅጽል ጉዳዮች ዓይነት ሲሆን፣ ነገር ግን የሚያሳየው አቅጣጫን በቦታ፣ በጊዜ፣ ወይም በአመክናኦአዊ ወሰን ነው። ብዙውን ጊዜም በእንግሊዝኛው መስተጻምር "በውስጥ፣ በላይ፣ በ፣ በመሐል፣ በጊዜ፣ በ፣ በላይ እና በላይ"ን በመጠቀም ይታወቃል።
6. መገልገያዊ ጉዳይ ቀጥተኛ ካልሆነው ተሳቢ እና ለመገልገያዊ ጉዳዮች መልኩ የተቀየረ ተመሳሳይ ነው። እሱ የሚገልጸው ምንነቱንና መስተጋብሩን (ተያያዥነቱን) ነው። ብዙውን ጊዜም የእንግሊዝኛውን መስተጻምር "በ"ን ወይም "ጋር"ን በመጠቀም ይታወቃል።
7. ቀጥተኛ ባለቤታዊ ጉዳዮች ጥቅም ላይ የሚውሉት የአንድን ድርጊት ድምዳሜ ለመግለጽ ነው።ዋናው ጠቀሜታው ለቀጥተኛ ባለቤት ነው። "ምን ያህል ሩቅ?" ወይም "እስከ ምን ድረስ?" የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል።
8. የስም መልኮች ጉዳይ ጥቅም ላይ የሚውለው ቀጥተኛ ባለቤትን ነው።

VI. መስተዋድድ እና አያያዦች

1. ግሪክ በጣም ቁልጭ ያለ ቋንቋ ነው፣ ምክንያቱም በርካታ አያያዦች ስላሉት። እነሱም ሐሳቦችን ያያይዛሉ (ሐረጎች፣ ዓረፍተ ነገሮች፣ እና አንቀጾችን)። በጣም የተለመዱ ስለሆኑ፣ በሚቀሩበት ጊዜ በተለይ በትንታኔ ጊዜ

ትርጉም ይኖረዋል። እንደ እውነቱ ከሆነ እነዚህ መስተዋድዶች እና አያያዦች የጸሐፊውን ሐሳብ አቅጣጫ ያመላክታሉ። ብዙውን ጊዜ ጸሐፊው በትክክል ምን ለማለት እንደፈለገ ለመወሰን በጣም ጠቃሚ ናቸው።

2. ከዚህ ቀጥሎ የጥቂት መስተዋድዶች እና አያያዦች እና ትርጉሞቻቸው ይቀርባል፣ (ይህ መረጃ ባብዛኛው የተገኘው ከ ኤች. ኢ. ዳና እና ጆሊየስ ኬ. ማንቲ *የግሪክ አዲስ ኪዳን የሰዋሰው መመሪያ)* ላይ ነው።

*ሀ.* ጊዜ አያያዦች

1) epei, epeid e, hopote, hote, hotan (ተሳቢ) - "*መቼ*"
2) *hoes*, - "በ... ጊዜ"
3) *hotan, epan* (ተሳቢ) — "*መቼም* ቢ*ሆን*"
4) *hoes, achiri, mechri* (ተሳቢ) — "እስከ... *መቼ*"
5) *priv* (ንዑስ አንቀጽ) - "በ*ፊት*"
6) *hos* - "ከ... ጀምሮ" "*መቼ*" "እንደ"

**ለ.** *አመክኖአዊ አያያዦች*

1) *ተግባር*
   a) *hina* (ተሳቢ), *hopos* (ተሳቢ), hos - "እንደ...*መሆኑ*" "እንደ"
   b) *hoste* (አቀላጣፊ ንዑስ አንቀጽ ተሳቢ) "እንደ"
   c) *pros* (አቀላጠፊ ንዑስ አንቀጽ ተሳቢ) ወይም eis (አቀላጠፊ ንዑስ አንቀጽ ተሳቢ) "እንደ"
2) ውጤት (በሰዋሰዋዊ ቅርጾች ተግባርና ውጤት መካከል የቀረበ ተወራራሽነት አለ)
   a) (ንዑስ አንቀጽ ይህ በጣም የተለመደ ነው) - "እንደ...*መሆኑ*" "እንደ"
   b) *hiva* (ተሳቢ) - "ስለሆነም"
   c) *ara*- "ስለዚህ"
3) *መንሥኤ* ወይም ምክንያት
   a) (ምክንያት/መነሻ ወይም ሳቢያ/ድምዳሜ) — "ለ፣" "ምክንያት"
   b) *dioti, hotiy* - "ምክንያቱም"
   c) *epei, epeide, hos*- "ከ... ጀምሮ"
   d) (ከ ተሳቢ) እና (አቀላጣፊ ተሳቢ ንዑስ አንቀጽ) "ምክንያት"
4) ተገቢ አስተያየት
   a) *ara, poinum, hoste*-"ስለሆነም"
   b) *dio* (ጠንካራው ምርመራዊ ተገቢ አስተያየት) — "በዚህም ምክንያት)
   c) *oun* "ስለሆነም" "ስለዚህ" "ከዚያም" "በዚህም ሳቢያ"
   d) *toinoun* "በመሠረቱ"
5) ተጻራሪ ወይም ተቃርኖ
   a) *alla* (ጠንካራ ተቃርኖ) - "ግን፣" "በተቀር"
   b) *de* - "ግን፣" "ቢሆንም፣" "ገና፣" "በሌላ በኩል"
   c) *kai* - "ግን"
   d) *mentoi, oun* - "ቢሆንም"
   e) *plên* "ቢሆንም ግን" (በአብዛኛው ሉቃስ ላይ)
   f) *oun* - "ሆኖም"
6) አወዳዳሪ
   a) *hôs*, (አወዳዳሪ ሐረጎችን ያሳያል)
   b) *kata* (በድብልቆች katho, kathoti, kathôsper, kathaper)
   c) *hosos* (በዕብራይስጥ)
   d) ê — "ከ...ይልቅ"
7) ተከታታይ ወይም ተለጣጣቂ
   a) *de* - "እና" "አሁን"
   b) *kai* - "እና"
   c) *tei* - "እና"
   d) *hina, oun* - "እንደ"
   e) *oun* "ከዚያም" (በዮሐንስ)

ሐ. ግነታዊ አግባብ

1) *alla* - "በርግጠኝነት" "አዎን" "በእውነቱ"
2) *ara* - "በርግጥ" "በእውነቱ " "በርግጥ "
3) *gar* - "ግን በርግጥ" "በርግጠኝነት" "በርግጥ "

4) *de* - "በርግጥ"
5) *ean* - "እንኳን"
6) *kai* - "እንኳን" "በርግጥ" "በእውነቱ "
7) *mentoi* "በርግጥ"
8) *oun* "በርግጥ" "እንደ ምንም"

VII. *ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገሮች*

*ሀ. ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር አንድ ወይም ከዚያም በላይ የሆኑ ሐረጎችን የያዘ ነው። ይህ ሰዋሰዋዊ መዋቅር ለትርጓሜ ይረዳል። ምክንያቱም እሱ ነባሩ ግሥ ድርጊቱን ያደረገበትን ወይም ያላደረገበትን ሁኔታዎች፣ ምክንያቶች ወይም መንሥኤዎች ስለሚያሳይ ነው። አራት ዓይነት ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገሮች አሉ። አካሄዳቸውም ከጸሐፊው አስተሳሰብ ወይም ሊል ለፈለገው እውነት ወደ ሆነው መሻት ነው።*

*ለ. አንደኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር የሚገልጸው ድርጊትን ወይም ከጸሐፊው አስተሳሰብ አኳያ ትክክል ይሆናል ተብሎ የሚታመንበትን ወይም ሊል ከፈለገው አንጻር ነው— ምንም እንኳ "እንደሁ" በሚል ቢገለጥም። በብዙ ጽሑፎች "ከ... ጀምሮ" በሚል ቢተረጎምም* (ማቴ. 4:3፤ ሮሜ.8:31)። *ቢሆንም ይህ ግን ሁሉም አንደኛ መደቦች ከእውነታ ጋር ትክክል ናቸው ማለት አይደለም። ብዙውን ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውሉት አንድን ነጥብ በክርክራዊ መንገድ ወይም ስህተት ያለበትን አጉልቶ በማሳየት ነው* (ማቴ. 12:27)።

*ሐ. ሁለተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ብዙውን ጊዜ "ከሐቅ ጋር ተጻራሪ" በመባል ይታወቃል።እሱም ነጥቡን ለመጥቀስ ትክክል ያልሆነን ነገር ወደ እውነት ያመጣል። ለምሳሌ፡*

1. *"በርግጥ ነቢይ ቢሆን ኖሮ፣ አይደለም እንጂ፣ ማን እና እንዴት ያለች ሴት እንደያዘችው ባወቀ ነበር፣ ግን አይደለም"* (ተሰ. 7:39)።
2. *"ሙሴንስ ብታምኑት፣ አታምኑትም እንጂ እኔን ታምኑኝ ነበር፣ ግን አታምኑም"* (ዮሐንስ 5፣46)።
3. *"ሰዎችን ባስደስት ኖሮ ግን፣ አላደርገውም እንጂ የኢየሱስ ክርስቶስ ባርያ ጨርሶ ባልሆንኩን ነበር፣ ነገር ግን ነኝ"* (ገላ. 1:10)

*መ. ሦስተኛ መደብ ሊሆን የሚችል የትንቢት ድርጊትን ያመላክታል። ዘወትር የድርጊቱን የመሆን ግምት ያስቀምጣል። ዘወትርም ሊደርስ የሚችልን ያሳያል። የነባሩ ግሥ ድርጊት ርግጠኛ ባልሆነ መልኩ በሐረጉ ላይ ተመልክቷል። ምሳሌዎች ከ1ኛ ዮሐንስ፡* 1:6-10፤2:4፣6፣15፣20፣21፣24፣29፤ 3:21፤ 4:20፤ 5፣14፣16።

*ሠ. አራተኛው መደብ ሊደርስ ከሚችል ራቅ ያለ ነው። በአኪ እምብዛም አይገኝ። እንደ እውነቱ ከሆነ የተሟላ አራተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር አይገኝም፣ ሁለቱንም የሁኔታዊ ክፍሎች መግለጫ ሊያሟላ የሚችል። ለከፊል አራተኛ መደብ ምሳሌ የሚሆን የመክፈቻ ሐረግ በ1ኛ ጴጥ.* 3:14። *ለከፊል አራተኛ መደብ መዝጊያ ሐረግ የሚሆን ምሳሌ ሐዋ.* 8:31።

VIII. ክልክሎች

*ሀ. የአሁን ጊዜ ያልተጠናቀቀ፣ እኔ በሚል አገባብ (ግን የተለየ ያልሆነ) በሂደት ላይ ያለ ድርጊት መቆሙን አጽንዖት ይሰጣል። ጥቂት ምሳሌዎች፡ "ሀብታችሁን በምድር ላይ ማከማቸታችሁን አቁሙ..."* (ማቴ. 6:19)፤ *"ስለ ሕይወታችሁ መጨነቃችሁን አቁሙ..."* (ማቴ. 6:25)፤ *"ሥጋችሁን ለኃጢአት በመስጠት ክፉ የመፈጸሚያ መሣርያ አታድርጉ..."* (ሮሜ. 6:13)፤ *"የእግዚአብሔርን ቅዱስ መንፈስ ማሳዘን አይኖርባችሁም..."* (ኤፌ. 4:30)፤ *እና "በወይን ጠጅ አትስከሩ..."* (5:18)

ለ. ያልተጠናቀቀ ድርጊት እኔ በሚል አገባብ "አንድን ድርጊት ወይም አትጀምር ወይም አትፈልም" ለሚለው አጽንዖት ይሰጣል። ምሳሌዎች፡ "እንደዛለማድረግ እንኳ አታስቡ..." (ማቲ. 5፡17)፤ "አትጨነቁ..." (ማቲ. 6፡31)፤ "አሳፋሪ መሆን አይኖርባችሁም..." (2ኛ ጢሞ. 1፡8)።

ሐ. ጥንድ አሉታ በተያያዥ አኳኋን የሚገለጠው በእጅጉን አጽንዖታዊ አሉታ ነው። "ፈጽሞ በፍጹም" ወይም "በምንም ምክንያት ቢሆን" ምሳሌዎች፡ "እሱ ፈጽሞ፣ በፍጹም ሞትን አያይም" (ዮሐንስ 8፡51)፤ "እኔ በፍጹም፣ ፈጽሞ..." (1ኛ ቆሮ. 8፡13)።

IX. መስተአምር

ሀ. በኮኔ ግሪክ የተወሰነ መስተአምር "ው" (the) ከእንግሊዝኛው ጋር ተመሳሳይ ጠቀሜታ ነው ያለው። ዋነኛው ተግባሩ "አመላካችነት" ሆኖ ለሚመለከተው ቃል፣ ስም ወይም ሐረግ አጽንዖት ማሰጠት ነው። አጠቃቀሙ በአዲስ ኪዳን ከጸሐፊ ጸሐፊ ይለያያል። የተወሰነው መስተአምር ለሌሎች ተግባራትም ሲውል፡

1. እንደ አመላካች ተውላጠ ስም ለተቃርኗዊ አግባብ፤
2. ቀደም ሲል ለተጠቀሰ ባለቤት ወይም ሰው እንደ ማጣቀሻ ምልክት
3. የዓረፍተ ነገሩን ባለቤት በአያያዥ ግሥ በሚገልጽ በሆነ መንገድ። ምሳሌዎች፡ "እግዚአብሔር መንፈስ ነው፣" ዮሐንስ 4፡24፤ "እግዚአብሔር ብርሃን ነው፣" 1ኛ ዮሐንስ 1፡5፤ "እግዚአብሔር ፍቅር ነው፣" 4፡8፣16።

ለ. የኮኔ ግሪክ እንደ እንግሊዝ "አንድ" (a እና an) ዓይነት የተወሰነ መስተአምር የለውም። የዚህ ያልተወሰነ መስተአምር አለመኖር ማለት፣

1. በአንድ ነገር ባሕርይ ወይም ዓይነት ላይ ያተኩራል።
2. በአንድ ነገር ምድብ ላይ ያተኩራል።

ሐ. የአኪ ጸሐፍት በስፋት የሚለያዩት በመስተአምር አጠቃቀማቸው ነው።

X. በግሪክ አዲስ ኪዳን አጽንዖት የሚታዩባቸው መንገዶች

ሀ. በአዲስ ኪዳን አጽንዖት የሚሰጥባቸው ስልቶች ከጸሐፊ ጸሐፊ ይለያያሉ። ከሁሉም የተሻሉት ቋሚ እና መደበኛ ጸሐፍት ሉቃስ እና የዕብራውያን ጸሐፊ ናቸው።

ለ. ቀደም ሲል ያልተጠናቀቀ ድርጊት የአሁን አመላካች መደበኛና ለአጽንዖት ያልተለየ ዳሩግን ሌላ ማንኛው ግሥ፣ ድምጸት ወይም አኳኋን ትርጉማዊ ጠቀሜታ እንዳለው ተመልክተናል። ይህም ማለት ያልተጠናቀቀ ድርጊት የአሁን አመላካች ተገቢያዊ በሆነ የሰዋሰው ሁኔታ ጥቅም ላይ አይውልም ማለት አይደለም። ለምሳሌ፡ ሮሜ. 6፡10 (ሁለት ጊዜ)

ሐ. በኮኔ ግሪክ የቃላት ቅደም ተከተል

1. የኮኔ ግሪክ ተለዋዋጭ የሆነ የቃላት ቅርጽ ያለው ቋንቋ ሲሆን እንደ እንግሊዝኛው የቃላት ሥርዓት ሳይሆን ራሱን የቻለ ነው። ስለዚህም ጸሐፊው መደበኛውን የቃላት ቅደም ተከተል እነዚህን ለማሳየት ይለዋውጠዋል...
   ሀ. ጸሐፊው ለአንባቢው አጽንዖት እንዲሰጥ የፈለገውን

   ለ. ጸሐፊው ለአንባቢው ያስገርማል ብሎ ያሰበውን

ሐ. ጸሐፊው በጥልቀት የተሰማውን ጉዳይ

2.ተገቢው የግሪክ የቃላት ቅደም ተከተል ጉዳይ ገና እልባት አላገኘም። ቢሆንም፡ ይሆናል የብሎ የታሰበው ተገቢ ቅደም ተከተል

ሀ. ለአያያዥ ግሦች

(1) ግሥ
(2) ባለቤት
(3) ማሟያ

ለ. ለተሻጋሪ ግሦች

(1) ግሥ
(2) ባለቤት
(3) ተሳቢ
(4) ቀጥተኛ ያልሆነ ተሳቢ
(5) መስተጻምራዊ ሐረግ

ሐ. ለስማዊ ሐረጎች

(1) ስም
(2) አጎላማሽ
(3) መስተጻምራዊ ሐረግ

3. የቃላት ሥርዓት ለማብራራት (ለትርጓሜ) ፍጹም ጠቃሚ ነጥብ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ፡

ሀ. "ለእኔና ለበርናባስ የኅብረት ቀኝ እጃቸውን ሰጡን" (ገላ. 2፡9)። "የኅብረት ቀኝ እጃቸውን" ተከፍሎ ጠቀሜታውን ለማመልከት ከፊት ለፊት ሆኗል።

ለ. "ከክርስቶስ ጋር" (ገላ. 2፡20)፣ ከፊት ሆኗል። ሞቱ ማዕከላዊ ነው።

ሐ. "ጥቂት በጥቂት እና በበርካታ የተለያዩ መንገዶች ነበር" (ዕብ. 1፡1)፣ ከፊት ሆኗል። ይህም እግዚአብሔር ራሱን እንዴት እንደገለጠ ነው አከራካሪ የሆነው እንጂ የመገለጥን እውነት በመቃረን አይደለም።

መ. ዘወትር የተወሰነ መጠን ያለው አጽንዖት ያሳያል

1. የተውላጠ ስሞች መደጋገም፣ በግሡ በተለያየ መልኩ ቀደም ሲል የነበረው። ምሳሌ፡ "እኔ፣ ራሴ፣ ከእናንተ ጋር በርግጥ እሆናለሁ..." (ማቴ. 28፡20)።
2. በቃላት፣ በሐረጋት፣ በዐቢይ ሐረጋት ወይም በዓረፍተ ነገሮች መካከል መኖር የሚገባው መስተጻምር ወይም ሌሎች አያያዥ ቃላት አለመኖር። ይህም (asyndeton) ("ያልታሰረ") በመባል ይታወቃል። አያያዡ ቃል እንዲኖር ተጠብቆ መቅረቱ ትኩረትን ይስባል። ለምሳሌ፡

ሀ. የብፁአን ትሩፋቶች (ሰባቱ)፣ ማቴ. 5፡3 (ዝርዝሩን ለማግነን)

ለ. ዮሐንስ 14፡1 (አዲስ ርዕስ)

ሐ. ሮሜ. 9፡1 (አዲስ ክፍል)

መ. 2ኛ ቆሮ. 12፡20 (ዝርዝሩን ለማግነን)

3. በተመለከተው ጽሑፍ ውስጥ የሚገኝ የቃላት ወይም የሐረጎች መደጋገም። ምሳሌ፡ "ለክብሩ ምስጋና" (ኤፌ. 1፡6፣ 12 እና 14)። ምስጋናው ጥቅም ላይ የዋለው የእያንዳንዱን የሥላሴ አካል ሥራ ለማሳየት ነው።
4. ጥቅም ላይ የዋለ ፈሊጥ ወይም ቃል (ድምጽ) በቃላት በካከል የሚኖረው ሚና

ሀ. ተለዋጭ ቃል - ስም አይጠሬ ቃላትን ቀይሮ በሌላ መጠቀም ለምሳሌ "እንቅልፍ" ን ለሞት (ዮሐንስ 11፡11-14) ወይም "እግሮች" ለወንድ ብልት (ሩት 3፡7-8፤ 1ኛ ሳሙ. 24፡3)።

ለ. ኀናዊ አገላለጽ - ለእግዚአብሔር ስም ቃላትን መለወጥ፣ ምሳሌ "የሰማይ መንግሥት" (ማቴ. 3፡21) ወይም "ከሰማይ የሆነ ድምፅ" (ማቴ. 3፡17)።

ሐ. ዘይቤያዊ አገላለጾች

(1) የማይቻል ግነት (ማቲ. 3፡9፤ 5፡29-30፤ 19፡24)፡፡
(2) የተለዩ ግነታዊ አገላለጾች (ማቲ. 3፡5፤ ሐዋ. 2፡36)፡፡
(3) ሰዋዊ ዘይቤዎች (1ኛ ቆሮ. 15፡55)፡፡
(4) ውስጠ ወይራ (ገላ. 5፡12)
(5) ቅኔያዊ አንቀጾች (ፊሊ. 2፡6-11)፡፡
(6) በቃላት መካከል ያሉ ድምፆች
    (ሀ) "ቤተ ክርስቲያን"

i. "ቤተ ክርስቲያን" (ኤፌ. 3፡21)
ii. "ጥሪ" (ኤፌ. 4፡1፣4)
iii. "የተጠራ" (ኤፌ. 4፡1፣4)

(ለ) "ነጻ"

i. "ነጻ ሴት" (ገላ. 4፣31)
ii. "ነጻነት" (ገላ. 5፡1)
iii. "ነጻ" (ገላ. 5፡1)

መ. ዘይቤአዊ ቋንቋ - ብዙውን ጊዜ ባህላዊ እና የተለየ ቋንቋን (ዘዬ) የሚያሳይ ነው፡

1) ይህ የ "ምግብ" ዘይቤአዊ አጠቃቀም ነበር (ዮሐንስ 4፡31-34)፡፡
2) ይህ የ "መቅደስ" ዘይቤአዊ አጠቃቀም ነበር (ዮሐንስ 2፡19፤ ማቲ. 26፡61)፡፡
3) ይህ የዕብራይስጥ የማወዳደሪያ ፈሊጥ ነው፡ "ጠላ" (ዘፍ. 29፡31፤ ዘዳ. 21፡15፤ ተሰ. 14፡36፤ ዮሐንስ 12፡25፤ ሮሜ. 9፡13)
4) "ሁሉም" ወይም (በተቃርኖ) "ብዙ፡፡" ኢሳ. 53፡6 ("ሁሉም")ን ከ53፡11 እና 12 ("ብዙ") ጋር አነጻጽር፡፡ ቃላቶቹ እንደ ሮሜ. 5፡18 እና 19 እንደታየው ተመሳሳይነትን ያመለክታሉ፡፡

5. በነጠላ ቃል ምትክ ሙሉ ሐረጋዊ ቋንቋ መጠቀም፡፡ ምሳሌ፡ "ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፡፡"
6. የስሞች፣ የቅጽሎች፣ የተውሳከ ግሦች (የርስ በርሱ) ልዩ አጠቃቀም
   ሀ. መስተአምሩ (ጠባያዊ ቦታ) ሲይዝ "አንድ ዓይነት" በሚል ይተረጎማል፡፡

   ለ. ያለ መስትአምር (በአንቀጹ ቦታ) ሲይዝ አረጋጋጭ አገናዛቢ ተውላጠ ስም በሚል ይተረጎማል– "ራሱ፣" "ራሷ፣" ወይም "ራሱ፡፡"

ሠ. ግሪክኛ ያልሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ አጽንዖትን በተለያየ መንገድ ሊረዳ ይችላል፡

1. በትንተናዊ ቃላት አጠቃቀም፣ ማለትም በግሪክኛውና በእንግሊዝኛው ጽሁፍ በየመስመሩ በተጻፈው፡፡
2. የእንግሊዝኛን ትርጓሜዎች በማነጻጸር፣ በተለይም ከተለያዩ የትርጓሜ ንድፈ ሐሳቦች አኳያ፡፡ ምሳሌ፡ "የቃል በቃል" ትርጓሜዎችን በማነጻጸር (ኪጀት፣ አኪጀት፣ አመት፣ አአሶመቅ፣ የተመት፡ አየተመት) ከ "ታደሰው አቻ" (ዊሊያምስ፣ አዓአት፣ አእመቅ፣ የተእመቅ፣ ኢበቅ፣ አኢመቅ፣ TEV ?እት)፡፡ ሻል ያለ ማብራሪያ ደግሞ *መጽሐፍ ቅዱስ በሃያ ስድስት ትርጉሞች* በቤከር የታተመው ላይ ይገኛል፡፡
3. ባለ *አጽንዖታዊ መጽሐፍ ቅዱስ* በጆሴፍ ብራያንት ሮዘርሃም (ክሪገል፣ 1994)
4. የጥሬ ትርጉም አጠቃቀም
   ሀ. *የአሜሪካ መደበኛ ትርጉም* የ1901

   ለ. *ለወጣቶች ተስማሚ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም* በሮበርት ያንግ (ጋርዲያን አሳታሚ፣ 1976)፡፡

ለተገቢ ትርጓሜ ሰዋሰዋዊ ጥናት አስፈላጊ ነው፣ አስቸጋሪ ቢሆንም፡፡ እነዚህ አጠር ያሉ መግለጫዎች፣ አስተያየቶች እና ምሳሌዎች የተፈለጉት ግሪክኛ አንባቢ ያልሆኑ ሰዎችን ለማበረታታትና በቅጹ ውስጥ የተመለከቱትን ሰዋሰዋዊ መግለጫዎች እንዲያገናዝቡ ነው፡፡ በርግጥ እነዚህ መግለጫዎች ቀለል ብለው ነው የቀረቡት፡፡ ቀኖናዊና ሊተጣጠፍ በማይችል መልኩ ጥቅም ላይ መዋል አይኖርባቸውም፤ ዳሩግን ወደ አዲስ ኪዳን አገባብ የተሻለ መረዳት የሚወስዱ ደረጃዎች ናቸው፡፡ እነዚህ መግለጫዎች አንባቢዎች የሌሎችን የጥናት መርጃዎች አስተያየቶችን ለምሳሌም፣ የአዲስ ኪዳን ስልታዊ ሐተታዎችን ለመረዳት ያስችሏቸዋል፡፡

የራሳችንን ትርጓሜ ከመጽሐፍ ቅዱስ በምናገኛቸው ጽሑፎች ላይ በመመሥረት ልንመረምረው ይገባል። ሰዋሰው በጣም ከሚረዱን ዓይነቶች መካከል አንዱ ነው፤ ሌሎች ዓይነቶች ደግሞ እንደ ታሪካዊ መቼት፣ ሥነጽሑፋዊ ጽሑፎች፣ የየዘመኑ የቃላት አጠቃቀም፣ እና አቻዊ አንቀጾች ይገኙበታል።

## ተጨማሪ መግለጫ ሁለት

## ጽሑፋዊ ትንተና

ይህ ርዕሰ ጉዳይ በዚህ መልኩ የቀረበው በዚህ ሐተታ ውስጥ የሚገኙትን ጽሑፋዊ ማስታወሻዎች ለማብራራት ነው:: ቀጣዩ ማውጫ ጥቅም ላይ ይውላል::

I. የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱሳችን ጽሑፋዊ ምንጮች
   ሀ. ብሉይ ኪዳን

   ለ. ሐዲስ ኪዳን

II. "የመለስተኛ ትንተና" ወይም "ጽሑፋዊ ትንተና" ተብሎ የሚጠራው ንድፈ- ሐሳባዊ ችግሮች አጭር ማብራሪያ
III. ለተጨማሪ ንባብ የተጠቀሱ ምንጮች

I. የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱሳችን ጽሑፋዊ ምንጮች
   ሀ. ብሉይ ኪዳን

1. ማሶረቲክ ጽሑፍ (ማጽ) - የዕብራይስጥ ተናባቢ ጽሑፍ የተቀናበረው በራቢ አቂባ በ100 ዓ.ም ነው:: አናባቢው የሚያመለክተው የአነጋገር ዘዬን፣ የህዳግ ማስታወሻዎችን ሥርዓተ- ነጥብ እና አስረጅ ነጥቦች ከስድስተኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም መካተት ተጀምሮ በዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም የተጠናቀቀው ነው:: የተከናወነውም የአይሁድ ሊቃውንት ክፍል ከሆኑት ማሶራተስ በሚባሉት ነው:: የተጠቀሙበትም የጽሑፍ ዓይነት፣ በሚሽናህ፣ ታልሙድ፣ ታርጉምስ፣ ፔሺታ፣ እና ቫልጌት አንድ ዓይነት ነው::
2. ሴፕቱዋጊንት (ሰባ) - ከባህል አኳያ ሴፕቱዋጊንት የተጻፈው በሰባ የአይሁድ ሊቃውንት ሲሆን በ70 ቀናት ለአሌክሳንደሪያ ቤተ-መጻሕፍት ሆኖ በንጉሥ ፐቶለሚ 2ኛ (285-246 ቅ.ል.ክ) ነው:: ትርጉሙ የተዘጋጀው ምናልባት በአሌክሳንደሪያ በሚኖሩ የአይሁድ መሪዎች ጥያቄ ሊሆን ይችላል:: ይህ ልምድ የመጣው፣ "ከአሪስታስ መልእክት" ነው:: ሰባ የተመሠረተው በተደጋጋሚ ከዕብራይስጥ ጽሑፋዊ ባህል ከራቢ አቂባ (ማጽ) በተለየ መልኩ ነው::
3. የሙት ባሕር ጥቅሎች (ሙባጥ) - የሙት ባሕር ጥቅሎች የተጻፉት በሮማ ቅ.ል.ክ ባለው ጊዜ (200 ቅ.ል.ክ እስከ 70 ዓ.ም) ሲሆን በአይሁድ የተለዩ ክፍሎች በሆኑ "ኤሰንስ" በተባሉ ተለይዎች ነው:: የዕብራይስጥ የብራና ጽሑፎች የተገኙት፣ በሙት ባሕር አካባቢ በበርካታ ቦታዎች ሲሆን፣ ከሁለቱም ማለት ከማጽ እና ከሰባ በተለየ መልኩ የዕብራይስጥ ጽሑፋዊ ቤተሰብ ናቸው::
4. የእነዚህ ጽሑፎች ንጽጽር፣ ተርጓሚዎች ብሉይ ኪዳንን እንዲረዱት እንዴት እንደሚረዳ ጥቂት የተወሰኑ ምሳሌዎችን ስንመለከት
   ሀ. ሰባው ተርጓሚዎችንና ሊቃውንትን ማጽ (ማሲኒክ ጽሑፍ) ይገነዘቡ ዘንድ ረድተዋቸዋል

      (1) ሰባ በኢሳ. 52፡14፣ "ብዙዎች <u>በእሱ</u> ይደነቁበታል::"

      (2) ማጽ በኢሳ. 52፡14፣ "ብዙዎች <u>በአንተ</u> ይገረሙ ነበር"

      (3) በኢሳ.52፡15 ተውላጠ ስሙ ልዩነቱ በሰባ ላይ ያለው ተረጋግጧል

         (ሀ) ሰባ፣ "ስለሆነም ብዙ ሕዝቦች በእሱ ይደነቁበታል"

         (ለ) ማጽ፣ "እሱ ብዙ ሕዝቦችን ይረጫል"

   ለ. ሙባጥ (ሙት ባሕር ጥቅሎች) ተርጓሚዎችንና ሊቃውንትን ማጽ (ማሲኒክ ጽሑፍ) ይገነዘቡ ዘንድ ረድተዋቸዋል

      (1) ሙባጥ በኢሳ. 21፡8፣ "እናም ነቢዩ ጮኸ፣ በቆምኩበት መጠመቂያው ማማ..."
      (2) ማጽ በኢሳ. 21፡8፣ "እናም ጩኸኩ አንበሳው! ጌታዬ፣ ሁልጊዜ በመጠበቂያው ማማ ላይ ቆሚያለሁ ቀኑን..."

   ሐ. ሁለቱም ሰባ እና ሙባጥ ኢሳ. 53፡11ን ለማብራራት ረድተዋል

      (1) ሰባ እና ሙባጥ፣ "ከነፍሱ መከራ በኋላ ብርሃንን ያያል፣ ይደሰታል"

(2) ማጽ፣ "ያያል… ከነፍሱ መከራ በኋላ፣ ይደሰታል"

ለ. አዲስ ኪዳን

1. ከ5,300 በላይ የእጅ ጽሑፎች ከግሪክ አዲስ ኪዳን በሙሉ ወይም በከፊል ጠፍተዋል። 85 የሚሆኑት በፓፒረስ የተጻፉ ሲሆኑ 268 ደግሞ በቁም ጽሕፈት የተጻፉ የብራና ጽሑፎች ናቸው። ቆይቶም፣ ወደ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም ቅጥልጣይ ጽሑፍ እየተስፋፋ መጣ። የግሪክ ጽሑፎች የተጻፉት በቁጥር 2700 ይሆናሉ። በተጨማሪም 2100 የሚሆኑ ቅጂዎች የቅዱሳት መጻሕፍት ጽሑፎች ዝርዝር ለአምልኮ የሚሆኑ ሌክሽናሪስ ብለን የምንጠራቸው አሉ።
2. 85 የሚሆኑት የግሪክ የእጅ ጽሑፎች የአዲስ ኪዳንን የተወሰኑ ክፍሎች የያዙትና በፓፒረስ ላይ የተጻፉት ሙዝየሞች ውስጥ ተቀምጠዋል። አንዳንዶቹ በሁለተኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም ያስቆጥራሉ፣ ነገር ግን አብዛኞቹ የሦስተኛውና የአራተኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም ናቸው። ከእነዚህ ጽሑፎች አንዳቸውም የተሟላ አዲስ ኪዳንን አልያዙም። እነዚህ ጥንታዊ የአዲስ ኪዳን ቅጂዎች ናቸው ማለት ግን በራሱ ጥቂት ልዩነት አላቸው ማለት አይደለም። አብዛኞቹ የእነዚህ ቅጂዎች ለአካባቢው ጥቅም ይውሉ ዘንድ በችኮላ የተጻፉ ናቸው። በሂደቱ ላይ ጥንቃቄ አልነበረም። በመሆኑም ብዙ ልዩነቶች አሏቸው።
3. ኮዴክስ ሲናይቲክስ፣ በዕብራይስጥ ፊደል ( ) (አሌፍ) ወይም (01) በመባል የሚታወቀው፣ በቅዱስ ካተሪኒ ገዳም በሲና ተራራ በቲስቼንዶርፍ ተገኝቷል። ዓመቱም ከ4ኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም ሲሆን በውስጡም የብኪን ሰባ እና የግሪክን አኪ ይዟል። እሱም "የአሌክሳንደሪያ ጽሑፍ" ዓይነት ነው።
4. ኮዴክስ አሌክሳንድሪነስ፣ "ሀ" ወይም (02) በመባል የሚታወቀው፣ የ5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የግሪክ የእጅ ጽሑፍ በአሌክሳንደሪያ ግብፅ የተገኘው፣
5. ኮዴክስ ቫቲካነስ፣ "ለ" ወይም (03) በመባል የሚታወቀው፣ በሮም በቫቲካን ቤተ መጻሕፍት የተገኘ ሲሆን፣ ዓመቱም ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዓ. ም እኩሌታ ነው። በውስጡም የብሉይ ኪዳን ሰባ እና የግሪክን አዲስ ኪዳን ይዟል። እሱም "የአሌክሳንደሪያ ጽሑፍ" ዓይነት ነው።
6. ኮዴክስ ኤፍራሚ፣ "ሐ" ወይም (04) በመባል የሚታወቀው፣ የአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የግሪክ የእጅ ጽሑፍ በከፊል የተበላሸው፣
7. ኮዴክስ ቤዜ፣ "መ" ወይም (05) በመባል የሚታወቀው፣ የአምስተኛ ወይም የስድስተኛ ክፍለ ዘመን የግሪክ የእጅ ጽሑፍ ነው። "የምዕራብ ጽሑፍ" ተብሎ ከሚጠራው ዋንኛው አስረጅ ነው። በውስጡም በርካታ ተጨማሪዎች የያዘ ሲሆን እንዲሁም ዋነኛው የግሪክ እማኝ ሆኖ በኪንግ ጀምስ ትርጉም ላይ አገልግሏል።
8. የአኪ MSS በሦስት ሊመደብ ይችላል፣ እንዲያውም በአራት፣ አንዳች ባሕርይ በሚጋሩ።
   (ሀ) የአሌክሳንደሪያ ጽሑፍ ከግብፅ

   (1) ገ75፣ ገ66 (200 ዓ.ም አካባቢ)፣ ወንጌላት የተጻፉበት
   (2) ገ46 (225 ዓ.ም አካባቢ)፣ የጳውሎስ መልእክቶች የተጻፉበት
   (3) ገ72 (ከ225-250)፣ የጴጥሮስና የይሁዳ መልእክቶች የተጻፉበት
   (4) ኮዴክስ ለ፣ ቫቲካነስ የሚባለው (325 ዓ.ም)፣ ሙሉውን ብኪ እና አኪ የያዘ
   (5) ከዚህ የጽሑፍ ዓይነት የተጠቀሱ ምንጮች
   (6) ሌሎች MSS የዚህን የጽሑፍ ዓይነት የሚያሳዩት ?፣ C፣ L፣ W፣ 33፣

   (ለ) ከሰሜን አፍሪካ ምዕራባዊ ጽሑፍ

   (1) ከሰሜን አፍሪካ የቤተክርስቲያን አባቶች የተጠቀሰ፣ ተርቱሊያዊ፣ ሲሪያዊ፣ እንዲሁም የጥንታዊ ላቲን ትርጉሞች
   (2) ከኤሪናዩስ የተጠቀሱ
   (3) ከቲታን እና ከጥንታዊ ሲሪያ ትርጉሞች የተጠቀሱ
   (4) ኮዴክስ መ "ቤዚ" የዚህን ጽሑፍ ጻይነት የሚከተል

   (ሐ) ከኮንስታንቲኖፐል የምዕራብ ባይዛንታይን ጽሑፍ

   (1) የዚህ ጽሑፍ ዓይነት ከ80% በላይ የሚሆነውን የ5300 MSS ያንጸባርቃሉ
   (2) በአንቲሆች በሶርያ የቤተክርስቲያን አባቶች የተጠቀሰ፣ ካፓዶቅያ፣ ክሪሶስቶም፣ እና ቴሮዶሬት
   (3) ኮዴክስ ሀ፣ በወንጌላት ብቻ
   (4) ኮዴክስ ሠ (ስምንተኛ ክፍለ ዘመን) ለሙሉ አኪ

   (መ) አራተኛው ሊሆን የሚችል ዓይነት "ቂሳሪያዊ" ከፓልስታይን

   (1) በቅድሚያ የታየው በማርቆስ ብቻ ነው
   (2) ጥቂት አስረጅዎች ገ45 እና W

II. "የመስስተኛ ትንታኔ" ወይም "የጽሑፋዊ ትንታኔ" ንድፈ ሐሳባዊ ችግሮች

ሀ. ልዩነቶች እንዴት ተፈጠሩ?

1. ሳይታወቅ ወይም በድንገት (አብዛኛው ሰፊ ክፍል የተፈጠረበት)
   ሀ. በዓይን የተፈጠረ ስህተት፣ ማለትም በእጅ በሚጻፍበት ጊዜ ሁለት ተመሳሳይ ፊደላት ላይና ታች መስመር ይዘው ሲመጡ ሁለተኛውን ጽፎ በመጀመሪያው መስመር ላይ ያሉትን ቃላት እንዳለ መግደፍ (ሆሞቲሉቶን)

      (1) የዓይን መሳሳት ጥንድ ቃላትን ወይም ሐረግ መግደፍ (ሀፕሎግራፊ)
      (2) የሐሳብ መስረቅ ሐረግን ወይም መስመርን ሲደግሙ፣ የግሪክ ጽሑፍ (ዲቶግራፊ)

   ለ. የጆሮ ስህተት፣ በቃል ሲነገር በተጻፈ ወቅት የተሳሳተ ንባብ ሲቀርብ የሚፈጠር (ኢታሲዝም)፡፡ ብዙውን ጊዜ ይህ የተሳሳተ ንባብ ተመሳሳይ ድምፅ ባላቸው የግሪክ ቃላት ይፈጠራል፡፡

   ሐ. የቀድሞዎቹ የግሪክ ጽሑፎች ምዕራፍም ሆነ የስድ ንባብ ክፍሎች አልነበራቸውም፣ ጥቂት ወይም ምንም ሥርዓተ ነጥብ ነበራቸው፣ በፊደልና ፊደል መካከልም ክፍተት አልነበረም፡፡ እናም መልእክቶቹን በተለያየ ቦታ መክፈልም ሆነ ሌሎች ቃላትን መመሥረት ይቻል ነበር፡፡

2. ሆንተብሎ
   ሀ. የሚቀዳውን ጽሑፍ ሰዋስዋዊ ቅርፅ ለማሻሻል ሲባል ይደረጉ የነበሩ ለውጦች

   ለ. ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች ጋር አረጋጋጭ እንዲሆኑ ይደረጉ የነበሩ ለውጦች (የአቻዎች ኅብር)

   ሐ. ሁለት እና ከዛ በላይ የሆኑ የተለያዩ ምንባቦችን ወደ አንድ ወጥ ጽሑፍ ለመቀየር ሲባል የተደረጉ ለውጦች፣ (ድብለቃ)

   መ. በጽሑፉ ውስጥ ስህተት ያለ መስሎ ሲታሰብ ለማስተካከል የተደረጉ ለውጦች (1ኛ ቆሮ. 11፡27 እና 1ኛ ዮሐንስ 5፡7-8

   ሠ. ከተጨማሪ መረጃ፣ ከታሪካዊ አቀማመጥ ወይም ከተገቢ ትርጓሜ አንጻር በአንድ ጸሐፊ የሰፈረ በግርጌ ማስታወሻ በሌለኛው ጸሐፊ ደግሞ በጽሑፉ ውስጥ እንዲካተት ሲደረግ (ዮሐንስ 5፡4)

ለ. የጽሑፋዊ ትንታኔ መሠረታዊ መርሖዎች (በዋንኛው የጽሑፉ ንባብ ላይ ልዩነቶች ሲኖሩ ለመወሰን የሚሆን አመክኖአዊ መመሪያ)

1. በጣም አስቸጋሪው ወይም ሰዋሰዋዊ አገባቡ እንግዳ የሆነው ዋነኛው ጽሑፍ ሊሆን ይችላል
2. ቅልጥፍ ያለው ጽሑፍ ዋነኛው ሊሆን ይችላል
3. ከዋናው ጋር በታሪክ ይቀራረባል ስለሚሰጠው ብዙ ክብደት የሚሰጠው ለጥንታዊው ጽሑፍ ነው፣ ሌላው እኩል ሆኖ
4. MSS በመልክዓ ምድራዊ የሚለያዩት ብዙውን ጊዜ ዋነኛውን ምንባብ ይዘዋል
5. ደከም ያሉት የእምነት መግለጫዊ ጽሑፎች፣ በተለይም ከዋናዎቹ የሥነ-መለኮት ማብራሪያዎች ጋር የሚገናኙት የእጅ ጽሑፎቹ ጊዜ ሲለወጡ፣ እንደ ሥላሴ ያሉት ፣ በ1ኛ ዮሐንስ 5፡7-8 የተመለከቱት ይመረጣሉ፡፡
6. የዋናውን ጽሑፍ በተሻለ መልኩ ሊገልጹ የሚችሉ ሌሎች ጽሑፎች
7. እነዚህን አስቸጋሪ ልዩነቶች ሚዛን ለመጠበቅ የሚረዱ ማሳያ ሁለት ጥቅሶች
   ሀ. የጄ. ሃሮልድ ግሪንሊስ መጽሐፍ፣ *የአዲስ ኪዳን ጽሑፋዊ ትንታኔ መግቢያ*፣ "ማንኛውም የክርስቲያን መሠረተ እምነት በአከራካሪ ጽሑፍ መሆን የለበትም፤ የአኪ ተማሪም ጽሑፉ፣ ተመስጧዊ ከሆነው ከዋናው ጽሑፍ የተሻለ ቀጥተኛና ከመሠረተ እምነት አኳያ የጠነከረ እንደሆነ ከመፈለግ መጠበቅ ይኖርበታል" (ገ. 68)

   ለ. ደብልዩ. ኤ. ክሪስዌል ለጌርግ *ጋሪሰን የበርሚንግሃም ኒውስ* ሲናገር እሱ (ክሪስዌል) የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ሁሉ ተመስጧዊ ናቸው ብሎ አያምንም፣ "ቢያንስ ቢያንስ ሁሉንም ቃላት ለዘመናዊው ሰው የቀረበው በምዕት ዓመታት ተርጓሚዎች" አለ ክሪስዌል፤ "በጽሑፋዊ ትንታኔ በጣም የማምን ነኝ፡፡ ይህ እንግዲህ፣ እንደማስበው፣ የማርቆስ 16ኛ ምዕራፍ የመጨረሻው አጋማሽ አጠራጣሪ ነው፤ ተመስጧዊ

አይደለም፣ የተደባለቀ ፈጠራ ነው… እነዚያን የእጅ ጽሑፎች ወደ ኋላ መለስ ብላችሁ ብታነጻጽሩ እንደ ማርቆስ ወንጌል መደምደሚያ ያለ አታገኙም። አንዱ ጨምሮት ይሆናል።

የበቁ የSBC አባቶች እንደሚከራከሩት ከሆነ "ተጨማሪ" ነገሮች መኖራቸውን በዮሐንስ 5 ያለው በቤተሳይዳ መጠመቂያ የኢየሱስ ሁኔታ ማስረጃ ነው። ሁለቱንም የተለያዩ የይሁዳን የራሱን መግደል ሁኔታዎች የገለጸበት (ማቲ. 27 እና ሐዋ. 1)፡ "ይህ የተለየ ዓይነት ራስን የመግደል ሁኔታ ነው፣" ይላል ክሪስዌል። "በመጽሐፍ ቅዱስ ቢሆን ኖሮ፣ ለዚህ መግለጫ በኖረው ነበር። እናም ሁለቱ የይሁዳ ራሱን የመግደል ሁኔታዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ፣" ክሪስዌል ጨምሮም፣ " ጽሑፋዊ ትንታኔ በራሱ አስደናቂ ጥበብ ነው። ጊዜያዊ አይደለም። ተዳፋሪነትም አይደለም። በእንቅስቃሴ ላይ ያለና ማዕከላዊ ነው…"

III. የእጅ ጽሑፍ ችግሮች (ጽሑፋዊ ትንታኔ)

ሀ. ለተጨማሪ የንባብ ምንጮች ጥቆማ

1. *መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንታኔ፡ ታሪካዊ፣ ሥነጽሑፋዊ እና ጽሑፋዊ፣* በአር. ኤች. ሃሪሰን

2. *የአዲስ ኪዳን ጽሑፍ፡ አስተላለፉ፣ ጥፋቱ እና ዳግም መመለሱ* በብሩስ ኤም. ሜዝገር

3. *የአዲስ ኪዳን ጽሑፋዊ ትንታኔ መግቢያ፣* በጄ. ኤች ግሪንሊ

## መግለጫ ሶስት

## የቃላት ፍቺ

**ልጅነት መወከል**፦ ይህ ጥንት የነበረ አስተሳሰብ ሲሆን ኢየሱስ ከመለኮታዊነት ጋር የነበረውን ህግኙነት ያጣቅሳል። ፅንሰ ሃሰቡ መሰረት የሚያደርገው ኢየሱስ በማንኛውም መንገድ ሰው ሲሆን ልጅነትን ያገኘው በእግዚአብሔር በተለየ መልኩ ማለትም በጥምቀቱ /በማቴ 3፡17፤ ማርቆስ 1፡11/ ወይም /በሮሜ 1፡4/ በተመለከተው መሰረት ነው። ኢየሱስ ምሳሌያዊ በሆነ መልኩ በዚህ ዓይነት እንደኖረ እግዚአብሔርም በአንዳንድ ሁነቶች /በጥምቀትና በትንሳኤ/ እነደ ገዛ ልጁ እንደሆነው /ሮሜ 1፡4 ፊሊጵ 2፡9/ በተመለከተው መሰረት ያሳያል። ይህ የእምነት መግለጫ በ8ኛው ክፍለ ዘመን የነበረ የአናሴ ቤተ-ክርስቲያን ጥስታዊ አስተሳሰብ የነበረ ነው። አምለሰክ ሰው ሆነ /ስጋዊ/ ከማመልከት ይልቅ ገለባብጦ ሰው እንዴት አምላክ እንደሆነ ያመላክታል።

ኢየሱስ አምላክ የሆነው ወለድ ቀድሞ መለኮት ምሳሌያዊ ሕይወት በመኖሩ እግዚአብሔር አከበረው ብሎ በቃላት ለማስረዳት ይቸግራል። እሱ ከቀድሞ ጀምሮ አምላክ ከሆነ እንዴት ክብርን ይሸለማል? እሱስ ቀድሞ የነበረ መለኮታዊ ክብር እያለው እንዴት ተጨማሪ ክብር ይሰጠዋል? እርግጥ ይህን ልንደርስበት በርግጥ ይቸግረናል፤ ማለትም አብ ኢየሱስን በተለየ መልኩ የአባቱን ፍቃድ በመፈጸሙ መከበሩን ለማሳየት ይሆናል።

**የአሌክሳዳሪያ አስተምህሮት**፦ ይህ ዓይነቱ የመጽሐፍ ቅዱስ የትርጓሜ አግባብ በግብፅ አሌክሳንደሪያ በ2ኛው ክፍለ ዘመን የተጀመረ ነው። መነሻ ያደረገውን መሰረታዊውን ፊሎአዊ የፍቺ መርህ ተከታይ የሆነው ጀሎን ያመላክታል። ተምሳሌታዊ ዘዴ በመባል የታወቃል። እስከ ተሃድሶ ዘመን ድረስ በቤተ ክርስቲያን ሲሰራበት ኖሯል። የተርጓሚው ሊቃውንት ሲረገንና አውስጢኖስ ናቸው። /ለተጨማሪ መረጃ የMoises Silva "ቤተክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን አሳስታ ተርጉማው ይሆን?" የሚለውን አንብብ /1987 ዓ.ም/።

**አሌክሳዳሪያ**፦ ይህ በ5ኛው ክፍለ ዘመን በአሌክሳዳሪያ የተገኘ የግሪክ /ቅርፅ/ የብራና ፅሑፍ ሲሆን፣ በውስጡም ብሉይ ኪዳን፣ የራዕይና አብዛኛውን ሐዲስ ኪዳን ያካተተ ነው። ፅሁፉ የግሪኩን አዲስ ኪዳን ቅጂ በተመለከተ ዋናኛው ማጣቀሻ ነው። /ከማቴዎስ፣ ከዮሐንስ ወንጌል አንዳንድ ክፍሎች እና ከሁለተኛ ቆሮንቶስ በቀር/ይህ ጽሑፍ ማለትም ልዩ ስሙ "ሀ" የተባለውና የቫቲካሉ ጽሑፍ ልዩ ስሙ "ለ" የተባለው በንባብ ላይ ሲሰማ በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቆች አማካኝነት በብዙ አገባቦች እንደ ዋነኛ ተደርገው ይወሰዳሉ።

**ተምሳሌታዊ**፦ ይህ አይነቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ በመጀመሪያ የተስፋፋው በአሌክሳንደሪያ የአይሁድ እምነት ነው። እያገነነ የመጣው በአሌክሳንደሪያው ፊሎ ነው። የመሰረታዊ እምነቱም ፍላጎት ቅዱሳት መጻሕፍትን እንደየሰው ባህል፣ ፍልስፍናና ስርዓት በማጣጣም የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪካዊ መቼት /ቦታና ጊዜ/ ስነጽሁፋዊ ይዘት በመተው ነው። በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙትን የተሸሸጉትን እያንዳንዳቸውን ትርጓሜዎች በመመርመር ላይ ያተኩራል። ኢየሱስ በማቴስ 13 እንዲሁም ጳውሎስ በገላትያ 4 እውነትን ለመግለጽ የተጠቀሙበትን ተምሳሌት ያመላክታው። ዳሩ ግን ይህ ተምሳሌታዊ ሳይሆን ጽሑፋዊ መልክ የያዘ ነው።

**ስርወቃላዊ ትንታኔ**፦ ይህ አንደኛው የምርምር ዘዴ ሲሆን በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኙትን የግሪክ ስርወ ቃላት ለመለየት ይረዳል። በግሪክ የፊደል ተራ መሰረት ቅርጹና ዋናው መግለጫ /ትርጓሜ/ የያዘ ነው። ግሪክኛን ለሚያነሱ አማኞች ሰዩ ትርጓሜ አያይዞ በማስቀመጥ የግሪክን የሐዲስ ኪዳን ሰዋሰውና ስነጽሑፋዊ አገባብ ለመረዳት ያስችላል።

**የቅዱሳት መጻሕፍት ተመሳስሎ**፡- ይህ ሐረግ ለማስረዳት የሚሻው ሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነና እርስ በርሱ የሚቃረን ሳይሆን የሚደጋገፍ እንደሆነ ለማመላከት ነው።

ይህ አይነቱ በውል የተቀመረ አቀራረብ ቃሉን መሰረታዊ በሆነ መልኩ በንጽጽር በማስቀመጥ የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍሎች ይተረጉማል።

**አሻሚ ትርጓሜ**፡- ይህ የሚያመላክተው አሻሚ ትርጓሜ ያላቸውን የጽሑፍ ሰነዶችን ሲሆን ሁለትና ከዚያም በላይ ፍቺ ሲኖር፤ ወይም ሁለትና ከዛ በላይ የሆኑ ነገሮች በአንድ ጊዜ በማጣቀሻነት ሲቀርቡ የሚከሰት ነው። ዮሐንስ ሆን ብሎ በዚህ ዘዴ ተጠቅሟል /ማለትም በእጥፍ አገባብ/

**ሰዋዊ ምዕላድ**፤ ይህ አይነቱ ፍቺ ከሰው ልጆች ጋር የተያያዘውን ሲማመላክት ጥሬ ቃሉም ሃይማኖታዊ ቋንቋዎችን ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ቁርኝት ነው። ስርወ ቃሉ ከግሪክኛ የመጣ ሲሆን የሰው ልጅ ማለት ነው። ፍቺውም እኛ ስለ እግዚአብሔር የምንናገረው በሰውኛ ዘይቤ ማለት ነው። እግዚአብሔር በአካላዊ፣ በማህበረሰባዊ፣ በስለልቦናዊ ቃላት ከሰው ልጆች ጋር በተጓዳኝ /ዘፍ 34፤ 1ኛ ነገስት 22፡19-23/ እንደተጻፈው ሲነገር ማለት ነው። እርግጥ ይሄ ተመሳስሎ ብቻ ነው። ያም ሆነ ይህ ከሰው ልጆች በቀር ልንጠቀምበት የምልኝልበት ምድብ ወይም ቃል የለም። ስለሆነም ስለ እግዚአብሔር ያለን እውቀት እውነትን ተንተርሶ ውስንነት እንዳለው ያመላክታል።

**የአንቲሆች አስተምህሮት**፡- ይህ አይነቱ የመጽሐፍ ቅዱስ የትርጓሜ ዘዴ በአንቲሆች ሶሪያ በ3ኛው ክፍለ ዘመን የተንሰራፋ ሲሆን የአሌክሳንደሪያ ግብጽን ተምሳሌታዊ ዘዴ የሚቃረን ነው። መሰረታዊ እምነቱን ለመጽሐፍ ቅዱስ ታሪካዊ ትርጓሜ ላይ ያተኩራል። መጽሐፍ ቅዱስን እንደማንኛውም የሰው ልጆች ስነጽሑፍ ይተረጉማል። ይህ አስተምህሮት ከክርስቶስ ክልዔ /ሁለት/ ባሕርይ አለው ከሚለው /ንስጥሮሳዊ/ አስተምህሮትና ወይም ደግሞ አንድ ባሕርይ አለው /ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው/ ከሚለው አስተምህሮት መሐል በተነሳው ውዝግብ ውስጥ ገብቶ እንደነበር ይታወቃል። ኋላም በሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ተነቅፎ እንደመናፍቅ ስለተወሰደ ወደ ፋርስ ሊሄድና ድጋሚ ሊቋቋም ቢሞክርም ውል ያለው አቋም ሳይዝ ቀርቷል። መሰረታዊ የአተረጓም መርሆቹ ግን ለትርጓሜ አግባብ ይሆኑ ዘንድ ለሉተርፐ ለካልቪን የፕሮቴስታንት የተሀድሶ አራማጆች ጥቅም ላይ ሊውል ችሏል።

**አንቲሄትካል**፡- ከሶስቱ አንደኛው ዓይነት ገላጭ ጽሑፋዊ ዘዴ ሲሆን የእብራይስጥን የቅኔ ሐረጎች ተዛምዶ ያመላክታል። ፍቺያቸው የማይገጣጠሙትን የቅኔ ሐረጎች/ዘውጎች ተዛምዷቸውን ይመለከታል/ምሳሌ 10፡1፤15፡1/።

**ራዕያዊ ስነጽሑፍ**፡- ይህ በአብዛኛው፤ በተለየ መልኩ የአይሁድ የስነጽሑፍ ዘውግ ነው። ይህ ዓይነቱ ምስጢራዊ ጽሑፍ ከአዩዳውያን በውጭ ኃያላት ይወረሩና ሲገዙ የሚዘወተር ነው። በጽሑፉ ይዘትም እግዚአብሔር ዓለምን እንደፈጠረ፣ ሙላዋ የሱ እንደሆነችና መበገቴት እንደሚችሉ አመላክቶ ለእስራኤልም የተለየ ዓላማ እንደሚጠነቀቅለት ያሳያል። ስነ ጽሑፉ የመጨረሻው ድል የሚገኘው በእግዚአብሔት ልዩ ክንድ እነደሆነ አጽንዖት ይሰጣል።

ጽሑፉ በጣም ተምሳሌታዊና ምስል ከሳች ምስጢራዊ ቃላት ይበዙበታል። ብዙውን ጊዜ እውነትን በቀለማት በቁጥሮች በምስል ከሳች ሁኔታ በሕልሞች በመላእክታዊ ክስታ በምስጢራዊ ቃላት የሚገለጽ ሆኖ ጊዜ በሰናይና በክፉ መሐል በመንታዊ ሰይፉ ከፍሎ ያልፋል።

የዚህ ዘውግ አነዳንድ ምሳሌዎች 1ኛ በብሉይ ኪዳን ሕዝቅኤል/36-48/ ዳንኤል /ምዕ 7-12/ ዘካሪያስ እና ዘርፍ ሲሆን ደግሞ ማቴ 2 ማር 13 2ኛ ተሰሎ 2 እና ራዕይ ናቸው።

**አፖሎጅስት፡-** ይህ የግሪክ ስርወ ቃል ሕጋዊ ተከላካይ የሚል ነው። ከስነ-መለኮት አንደኛው የትምህርት ንዑስ ዘርፍ ሲሆን ለክርስትና እምነት ተገቢ የመከራከሪያ ማስረጃና አመክኗዊ የክርክር አግባብን ይቀምራል።

**ቀዳማይ፡-** ይህ ቃል ቀደም ሲል ከተሄደበት አግባብ ጋር ጥብቅ መሰረታዊ ቁርኝት ያለው ነው። የሐሳብ አወራረዱም ቀደም ሲል ከወጡትና ከተቀበልናቸው ትርጓሜዎች መርሆች ወይም አቋሞች በመመስረት እንደ እውነት በመቀበል መቀጠል ነው። ያለ ምንም ተጨማሪ ምርምርና ትንታኔ የምንቀበላቸውን ማለት ነው።

**አርዮሳዊነት፡-** አርዮስ በአሌምሳንደሪያ ግብፅ ፕሬስቤታሪያን ቤተ-ክርስትያን በ3ኛ እና በ4ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ የነበረ ነው። አጽንዖት ሰጥቶ የሚከራከረው ምሳሌ 8፡22-31 ያለውን ቃል ሲሆን እየሱስ ቀድሞ እንደነበረ ቢቀበልም መለኮትነቱ ክዷል። /ከአብ ጋር መስተካከል የለበትም ባይ ነው።/ ከአሌክሳንደሪያው ጳጳስ ተቋውሞ የገጠመው ሲሆን ይህም ከ318 ዓ.ም አንስቶ ለብዙ ዓመታት የቆየ ክርክር ነው። አርዮሳዊነት በተለይ የምስራቅ ቤተክርስቲያን መሰረተ እምነት ተደርጎ ተወስዶ ነበር። በ325 ዓ.ም በአቅያ የተሰበሰቡት ሊቃውንት አርዮስን አውግዘውና ነቅፈው ተወልድን የተካከለ መለኮትነት አጽንተዋል።

**አርስጣጣሊስ፡-** የጥንታዊቷ ግሪክ ፈላስፋ ሲሆን የፕላቶ ተማሪና የታለቁ እስክስድር /አሴክሳንደር መምህር ነው። የሱ ተጽዕኖ እስካሁን ድረስ በዘመናዊው ጥናትና አስተምህሮት ላይ የጸና ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት በማስተዋልና ምደባዊ ፈር በያዘ የማስተማር። ስልት አጽንዖት በመስጠቱ ነው። ይህም አንደኛው የሳይንሳዊ ምርምር ዘዴ እንደሆነ ይታወቃል።

**አውቶግራፐር፡-** ይህ ለጥናታዊውና ወጥ ለሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች የተሰጠ ስያሜ ነው። እነዚህ ጥንታዊ ወጥ የብራና ጽሑፎች ሙሉ በሙሉ ጠፍተዋል። የቅጂ ቅጂ ብቻ ነው ያለው ይህም የጽሑፋዊ ይዘት ልዩነቶችን በዕብራይስጥና በግሪክ የብራና ጥንታዊ ጽሑፎች መሐል ሲፈጥር ችሏል።

**ቤዛ፡-** ይህ የ6ኛው ክፍለ ዘመን የግሪክና የላቲን ጽሑፍ ነው። የሚል መለያ ሲኖረው ወንጎላትንና ግብረ-ሐዋርያትን እንዲሁም አንዳንድ መልዕክቶችን አካቷል። ከዚህም በላይ ሌሎት በርካታ ስንክሳሮችን /ጽሑፎችን/ ይዟል። በኪንግጀምስ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂ ወስጥ መካተት ስላለባቸው መሰተር ጥሏል። /እንደ መነሻ ሆኗል።

**አድልዎ፡-** ይህ ቃል የሚያመለክተው በአንድ ነገር ወይም አመለካከት ላይ ቀደም ተብሎ የተያዘ አድሏዊ ግትር አቋምን ነው። አእምሮ በአንድ ነገር ከተያዘ ማድላቱ የማይቀር መሆኑል ያሳያል። ቀደም ብሎ የተያዘ ፍርደ-ገምድላዊ አቋምን ያመላክታል።

**መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረዳት፡-** ይህ ቃል በተለተ መልኩ ጥቅም ላይ የሚውል ነው። ይህም ማለት የመጀመሪያው ፀሐፊ በዘመኑ ምን ለማለት እንደፈለገና አሁን በዘመናችን በምን መልኩ ተግባራዊ እንደምናደርገው ያለውን ያካትታል። መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረዳት ቃሉን ስልጣናዊ መመሪያ አድርጎ መውሰድ ነው። የሆነ ሆኖ የትርጓሜ መዛባት እንዳይከሰት የመጽሐፍ ቅዱስን ትርጓሜ በታሪካዊና በሰዋሰዋዊ ዘዴ ብቻ መወሰኑ ይበቃል።

**ደንብ፡-** ይህ ቃል በተለይ ተመስጧዊ በሆነ ሁኔታ በተመስጧዊ የሆኑትን ጽሑፎች ይመለከታል፡፡ ይህም ሁለቱንም የብሉይና የሐዲስ ቅዱሳት መጻሕፍትን ያካትታል፡፡

**ማዕከለ ክርስቶስ፡-** ይህ ቃል የኢየሱስን ማዕከላዊነት ያመላክታል፡፡ ቃሉን ለመጠቀም የተፈለገው ኢየሱስ የመጽሐፍ ቅዱስ ጌትነቱን የሚያሳየውን ጽንሰ ሐሳብ ለማሳየት ነው፡፡ ብሉይ ኪዳን ወደ እሱ አመላካች ነው፡፡ እሱም የቃሉ ፍጻሜና ግብ ነው /ማቴ 5፡17-48/

**ሐተታ ትርጓሜ፡-** ይህ የተለየ ዓይነት የሐተታ መጽሐፍ ነው፡፡ ለመጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ ዳራ ያስነብባል፡፡ እያንዳንዱ የመጽሐፍ ክፍልን ትርጓሜ ለመስጠት ይሞክራል አንዳንዶች በተግባራዊ አያያዝ ላይ ሲያተኩሩ ሌሎች ደግሞ በጽሑፍ ቴክኒካዊ አግባብ ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ፡፡ እነዚህ የትርጓሜ መጻሕፍት በጣም ጥቅም ይሰጣሉ፡፡ ዳሩ ግን ከእነሱ በፊት አጥኚው ግለሰብ የራሱን ጥናት መካሄድ ይጠበቅበታል፡፡ እነዚህ የትርጓሜ መጻሕፍት ሐተታዎችን መቀበል የሚገባው በወል መርምሮ መሆን ይገባል፡፡ ለዚሁም የተለያዩ ትርጓሜዎችን ከተለያየ ስነ-መለኮታዊ ትምህርቶች አቋም አኳያ መመልከቱ ተመራጭ ነው፡፡ ቃላት ዝርዝር ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ምርምራዊ መጽሐፍ ነው፡፡ በብሉይም ሆነ በሐዲስ ያሉትን ቃላት ሁሉ በየአገባባቸው በዝርዝር የያዘ ነው፡፡ በብቁ መንገድ እገዛ ያደርጋል፡፡ 1/ እያንዳንዱን የእንግሊዝኛ ቃል ምን መሆን እንዳለበት ከዕብራይስትና ከጽርዕ/ግሪክ/ እንደሆነ ያመላክታል 2/አንቀጾችን በማነጻጸር የመሳሳይ የሆነ የግሪክ ወይም የዕብራይስጥ ቃል ጥቅም ላይ መዋሉን ለማወቅ ያስችላል፡፡ 3/ሁለት የተለያዩ የዕብራይስጥም ሆነ የግሪክ ቃላት በተመሳሳይ የእንግሊዝኛ ቃል ተርጉመው እንደሆነ ያመላክታል፡፡ 4/ቃላቶች በምን ያህል ድግግሞሽ በየትኞቹ መጻሕፍትና ጸሐፋት እነደተፈረጉ ያሳያል፡፡ 5/ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ተጠቀሰው ቃል አመላካች የሆነ አንቀፃ ያሳያል /ዋልተር ክላርክ የብሉይ ኪዳን ግሪክኛ እንዴት ጥቅም ላይ እነደዋለ የጥናት መረጃ መጽሐፍ ገጽ 54-55፡፡

**የሙት ባሕር ጥቅሎች፡-** ይህ የሚያመለክተው የጥንታዊ ጽሑፍ ጥቅሎች የሆኑ በዕብራይስጥና በአረሚክ የተፃፉ ሙት ባሕር አጠገብ በ1947 የተገኙትን መጻሕፍትን ነው፡፡ እናዚህ ጥቅሎች ሃይማኖታዊ ቤተ-መጽሐፍት ሲሆኑ የይሁዳነት ክፍል የሆኑ በ1ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩትን ነው፡፡ የሮማ የግዛት መስፋፋትና በ60ዎቹ የተካሄዱት የቀናኢነት ውጊያዎች ገዳም በመሰሉና በዋሻዎች ውስጥ በሸክላ ታሽገው እንዲቀመጡ እንዳስገደደ ይገመታል፡፡ ጥቅሎች የ1ኛው ክፍለ ዘመን ፍልስጤምን ታሪካዊ መቼቶችን እንድንገነዘብና ማሰራዊ ጽሑፎች የሚባሉትን ትክክለኛነት እንድንረዳ /ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበረውን/ አስችለውናል፡፡ በአድሕሮት በመባል ይታወቃሉ /ሙ/ባ/ጥ/ የሙት ባሕር ጥቅሎች፡፡

**ዲዳክተር፡-** ይህ አይነቱ ተአመክንዮ አገባብ ከአጠቃላይ መርሕ ተነስቶ ወደ ዝርዝር ሁኔታ ውስጥ የሚገባ ሎጂካዊ አስተሳሰብ ነው፡፡ ከአንደክቲቭ አስተሳሰብ ተቃራኒ ነው፡፡ ማለትም ሳይንሳዊ የሆነውን ከዝርዝር አስተውሎች በመነሳው ወደ አጠቃላይ ንድፈ ሃሳብ የሚያደርሰውን፡፡

**ዲያሌክቲካዊ፡-** ይህ አይነቱ የአስተሳሰብ ዘዴ ተቃራኒ የሆኑትን ነገሮች ያስቀምጥና /አይዎ/ በሁለቱም በኩል ያለውን ተቃርኖና ተዛምዶ የሚመረምር ነው፡፡ ብዙ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮቶች ዲያሌክታካዊ ጥንዶች አሏቸው፡፡ ለአብነትም ቀድሞ የተወሰነና - ነጻ ፍቃድ ደሕንነት - ጥረት እምነት ስራ ውሳኔ ስርዓታዊት ክርስትያናዊ ነጻነት ክርስትያናዊ ሐላፊነት፡፡

**ዲያስፖራ፡-** ይህ ቃል የግሪክ ሲሆን ከነዓናዊ አይሁዶች አገራቸው ውጭ ያሉትን ከመልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ከተስፋይቱ ምድ ዳርቻ ወጭ የሚኖሩትን አይሁዳውያን ለመጥራት የሚጠቀሙብት ነው፡፡

**ፍጹማዊ አቻነት**፡- ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ የትርጓሜ ሐሳብ ሲሆን ትርጓሜዎቹም ቃል በቃል አቻ እና አንድ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ከዕብራይስጥም ሆነ ከግሪክ አቻውን አግኝተው መተርጎም የሚገባው ሲሆን ይህ ከልሆነም በሐረግ መልክ ሐሳብ በጥንቃቄ ከምንጩ ሳይዛባ እንዲተረጎም ይደረጋል። በእነዚህ ሁለት ንድፈ ሐሳቦች መሐል ፍጹማዊ አቻነት መነሻ ጽሑፉን አተኩሮ ይዞ በዘመናዊ ሰዋሰውና ፈሊጥ መተርጎም ይኖርበታል ይላል። የእነዚህ የትርጓሜ ንድፈ ሐሳቦች ትንታኔ መጽሐፍ ቅዱሳን እንዴት በመረዳት እናንብብ ገጽ 35 በሚለው ሰፊ እና ስታዋርት መጽሐፍ ላይ /ሮበርት ባራቸር/ መግቢያ በሰጡበት እናገኘዋለን።

**ኤሌክቲክ**፡- ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው የመጽሐፉን ቅኝት ለማከናወን ብቻ ነው። ጠቀሜታውም የተለያዩ ንባቦችን ከግሪክ ጽሑፎች ውስጥ በመምረጥና በመመርመር ዋነኛውን ወጥ ጽሑፍ ጋር ለመድረስ የሚያስችል ነው። ከግሪክ ጽሑፎች መሐከልም ዋነኛውን ተንተርሰው በግል አስተያየት መልክ የተሰጡትን አይቀበልም።

**ኤሲጀሲስ**፡- ይህ የኤክሰሳይስ ተቃራኒ ነው። ማለትም ኤክሲጂሰሲ ከዋነኛው ጸሓፊ ሐሳብ ያፈነገጠ /የወጣ/ ከሆነ ኤሲጀሲስ ደግሞ ባዕድ ሐሳብ ወይም አስተያየት ውስጥ ማጨቅን/በብዛት መግባትን ማስገባትን/ ይመለከታል።

**ስርወቃል**፡- ይህ የስርወ ቃላት የማጥኛ ዘዴ ሆኖ መነሻው ከምን እንደሆነ ይመረምራል። ከቃሉ ስር ፍቺ በመነሳትም ቃሉ እንዴት እቅም ላይ እነደዋለ ለማወቅ ያስችላል። በትርጓሜ ጊዜ ግን ኢቲሞለጂ ዋነኛ የትኩረት ነጥብ አይደለም። አወዳዊ ፍቺና የቃሉ አገባብ ነው የሚተኮርበት።

**ኤክሰጀሲስ**፡- የተወሰነ አንቀጽን ለመተርጎም የሚውል ቃል ነው። ይህም ማለት ከጽሑፉ ወጣ ባለ መልኩ በመርመር የዋነኛ ጸሐፊውን ሃሳብ ለመረዳት የሚያስችል ነው። ከታሪካዊ ዳራና መቼት /መቼ እና የት/ ስነ ጽሑፋዊ ፈርጅ ለዋሰውና ወቅታዊ የቃሉን ፍቺ ይቃኛል።

**ዣነ**፡- የፈረንሳይ ቃል ሲሆን የተለያዩ የስነጽሑፍ ዘውጎች ማለት ነው። ተመሳሳይነት ያላቸውን የስነጽሑፍ ዓይነቶች አንድ ላይ ይመድባቸዋል። ለምሳሌም ታሪካዊ ትረካ ቅኔ ምሳሌ ትንቢታዊ /ምስል ከሳች/ ሕጋዊ ይገኙበታል።

**ግኖስቲስዝም**፡- ስለዚህ ጉዳይ ያለን እውቀት የሚመነጨው በሁለተኛው ክፍለ ዘመን ከነበሩይ የግኖስጢክ ጽሑፎች ሲሆን አስተሳሰቡ ግን ከ1ኛው ክፍለ ዘመን ከነበሩት የግኖስጢክ ጽሑፎች ሲሆን አስተሳሰቡ ግን ከ1ኛው ክፍለ ዘመን ወይም ቀደም ሲል የነበረ ነው።

አንዳንዶች እንደሚሉት የቫለንታይን እና የቀረንታይን የ2ኛው ዘመን ግኖስጢስ 1/ቁስ አካልና መንፈስ ዘላለማዊ ሲሆኑ አንድነትም ምንታኤም /ሁለትነትም/ ይዘው። ቁስ አካል ክፉ ሲሆን መንፈስ ግን ሰናይ ነው። መንፈስ የሆነው እግዚአብሔር በቀጥታ ክፉ ነገርን በማበጀት ውስጥ አይገባም። 2/በእግዚአብሔርና በቁስ አካል መካከል የረጅም ጊዜ ወይም የመላዕክታዊ ደረጃ አለ። የመጨረሻው ወይም ዝቅተኛው ያህዌህ? /YHWH/ ሲሆን አለማትን የመሰረተ ነው። አንዳንዶች ከፍተኛ አድርገው በመመሰጥ ከእግዚአብሔር ያነሰ /በመለኮትነቱ ሳይሆን/ የሰው አካል ለብሶ መለኮት ሲሆን አይቻለውም። እሱ መንፈስ ነው 1ኛ ዮሐ. 1፡1-3 4፡1-6 /እና 4/ ደሕንነት ሊገኝ የሚችለው በኢየሱ በማመንና የተለያየ እውቀት በማግኘት ይህም ልዩ እውቀት በልዩ ሰዎች የሚታወቅ ነው። እውቀት /የማለፊያ ቃል/ ወደ መንግስተ ሰማያት ለመግባት ያስፈልጋል። የአይሁድ የሕግ እውቀትም ወደ እግዚአብሔር ለመድረስ ይህ እንደሚያስፈልግ ያመለክታሉ።

የግኖስቲክስ የሀሰት መምህራን ሁለት ዓይነት ስነ ምግባራዊ ተጻራሪ ስርዓቶች ያስቀምጣሉ፡፡ 1/ለአንዳንዶች የአኗኗር ስርዓት /ዘዬ/ ከደሕንነት ጋር ምንም ዓይነት ተዛምዶ የለውም፡፡ ለእነሱ ደሕንነትና መንፈሳዊነት ምስጢራዊ እውቀት /የማለፊያ ቃል/ በሚሰለው የተጎዳኘ በመላዕክት ክልል ነው ይላሉ፡፡ ወይም 2/ለሌሎች ደግሞ የአኗኗር ስርዓት በደሕንነት ላይ ትልቁ ነጥብ ነው፡፡ ለተሻለ የሕይወት ዘይቤም አጽንኦን በመስጠት ለእውነተኛ መንፈሳዊነት በማስረጃ ያቀርባሉ፡፡

**ሄርሜኒዩኒክስ፡-** ቴክኒካዊ ቃል ሲሆን ለ ኤክሴጂሲስ እንደ መርሕ ያገለግላል፡፡ ሁለትዮሽ የሆነ የተወሰነ መመሪያና ተሰጢዊ ጥበብ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ወይም የተቀደሰ በሚል ሄርሜሊዮኒክስ በሁለት ምድብ ማለትም፡- አጠቃላይ መርህና ዝርዝር መርሆች በሚል፡፡ ይህም ከተለያዩ መከጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙ ስነ ጽሑፎች ጋር ይዛመዳል፡፡ እያንዳንዱ የተለየ የስነጽሑፍ ዘውግ የየራሱ የተለየ መመሪያ ያለው ሲሆን ከሌሎች ጋር ደግሞ ግምቶችንና የትርጓሜ አገባቦችን ይጋራል፡፡

**ኃየር ክርቲዝም፡-** ይህ የመጽሐፍ ቅዱሳዊ የትርጓሜ አገባብ /ደንብ/ ሲሆን አተኩሮቱም በአንድ በመጽሐፍ ቅዱስ መጽሓፍ ላው በታሪካዊ መቼትና በስነጽሑፋዊ መዋቅር ላይ ነው፡፡

**ፈሊጥ፡-** ይህ ሐረግ የተለያዩ ባህሎችን ተንተርሶ ከዋናው ቃል ትርጉም ጋር ያልተያዘ ትርጉም የሚሰጥ ነው፡፡ አንዳንድ ዘናዋ ምሳሌዎች፤ የመጥፎ ጥሩ ነው ገደልከኝ የሚሉ አሉ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስም የዚይ ተመሳሳይ የሆኑ ሐረጎች አሉት፡፡

**ማብራሪያ፡-** ይህ ስያሜ የተሰጠው እግዚአብሔር ለሰው ልጆች መናገሩን ለማመልከት ነው፡፡ ሙሉ ጽንሰ ሐሳቡ የሚገልጸው በሶስት መልክ ነው፡፡ 1/ራዕይ እግዚአብሔር በሰው ታሪክ ውስጥ መስራቱ 2/ ተመስጦ፡- ለድርጊቱ ተገቢ የሆነ ትርጓሜ እና ፍቺ ለተመረጡ ሰዎች በተመስጦ በማስታወቅ መዝግበው ለሰው ልጅ እንዲያስተላልፉ ማድረጉ 3/ማብራሪያ፡- መንፈሱን ለሰው ልጆች በሰጡት ስለ እሱ እንዲያውቁና እንዲያስተውሉ ማስቻሉ፡፡

**ኢንዳክሪቭ፡-** የሎጂክ አንዱ ዘዴ ሲሆን ከዝርዝር ነገሮች ተነስቶ ወደ አጠቃላይ የሚተነትን ነው፡፡ ለዘመናዊው ሳይንስ በተግባር ዘዴ በመሆን በማገልገል ላይ ነው፡፡ ዘዴው በመሰረቱ የአርስቶትል ነው፡፡

**ኢንተርላይነር፡-** ይህ የምርምር መሳሪያ ዘዴ ዓይነት ሲሆን የመጽሓፍ ቅዱስን ቋንቋ የሚያነቡትን እንዲተነትኑና ፍቂውንና መዋቅሩን እንዲረዱ ያስችላል፡፡ የእንግሊዝኛውን ትርጉም ቃል በቃል በማስቀመጥ ከዋናው የመጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋ ጋር አነጻጽሮ ያስቀምጣል፡፡ ይህ የምርምር አግባብ ትንተናዊ ስርወቃልን በመደባለቅ ለሰው ልጆች የተናገረው መሰረታዊ ለሆኑት የዕብራይስጥና ግሪክ ፍችዎች መልክ ይሰጣል፡፡

**ተመስጦ፡-** ይህ ጽንሰ ሐሳብ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የተናገረው የመጽሐፍ ቅዱስን በጸሐፍት በትክክልና በግልጽ መገለጡን እንዲያፍሩ ነው፡፡ ሙሉ ጽንሰ ሐሳቡ በሶስት መልኩ ይገለጻል፡፡

1/መገለጥ /ራዕይ/ እግዚአብሔር በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ መስራቱ 2/ ተመስጦ ለድርጊቱ ተገቢ ይርጓሜ እና ፍቺ ለተመረጡ ሰዎች በተመስጦ ለማስታወቅ መዝግበው ለሰው ልጅ እንዲያስተላልፉ 3/ ብርሃነ /ማብራሪያ/ መንፈሱን ለሰው ልጆች በመስጠት እሱ ሽሽግነት እንዲያውቁና እንዲያስተውሉ ማስቻል፡፡

**የገለጻ ቋንቋ፡-** ይህ ብሉይ ኪዳን የተጻፈውንና ፈሊጦቹን ለማገናኘት ታስቦ ነው። እሱም የዓለማችንን የአበጋገር አግባብ በአምስቱ የስሜት ሕዋሳት በማስመርኮዝ ያቀርባል። ሳይንሳዊ ገለፃ ማለት ግን አይደለም።

**ሕጋዊነት፡-** ይህ አዝማሚያ የሚያመለክተው ለሕግጋትና ለክብረ በዓላዊ አምልኮተ ስነስርዓት አፅንኦት የመሰጡትን ነው። የሰው ልጆች የሚያደርጉትን ደንቦችና ስርዓቶች እግዚአብሔር ይቀነለዋል ብሎ መወሰን ነው። ግንኙነትን ዝቅ የሚያደርግና ክዋኔዎችን ከር የሚያደርግ ሆኖ ሁለቱንም ኪዳናዊ ግንኙነቶች /በቅዱሱ በእግዚአብሔርና በኃጢያተኛው ሰውነት እንደሚካሀወድ ያስምጣል።

**ጽሑፋዊ ፍቺ፡-** ይህ የጽሑፋዊ ፍቺ ላይ የሚያተኩር እና ታሪካዊ የአተረጓጎም ዘዴ የሆነውን የአንቲሆችን ባህል ይከተላል። ይህም ማለት ትርጓሜ መያዝ ያለበት ተራ ወኔና ግልጽ የሆነውን ፍቺ በሰው ልጆች ቋንቋ እንዳለ ነው ይላል። ይህም ማለት ግን በተምሳሌታዊ ቋንቋ የተጻፉ ክፍሎች መኖራቸውን አይክድም።

**ጽሑፋዊ ዘውግ /ክፍል፡-** ይህ የሰው ልጆች መግባቢያ የሆነ የጽሑፍ ክፍሎችን ማለትም ቅኔ ታሪካዊ ትረካ የመሳሰሉትን ያካትታል። እያንዳንዱ ዓይነት ስነ ጽሑፍ የየራሱ የትርጓሜ አገባብ ሲኖረው በተጨማሪም ለሁሉም የስነ ጽሑፍ መርሖችን ይከተላል።

**ጽሑፋዊ አሃድ፡-** ይህ የሚያመለክተው ዋነኞቹን የመጽሐፍ ቅዱስ ያስተሳሰብ ክፍሎችን ነው። ይህም በጥቂት ምንባቦች አንቀጾች ወይም ምዕራፎች ሊዘጋጅ ይችላል። በየራሱ ሙሉ የሆነና ማዕከላዊ የጽሑፍ ዓይነት የያዘ ነው።

**ሎወር ክርቲዝም፡-** /ቴክስቲወሐነ ክርትዝም/ ተመልከት የእጅ ጽሑፍ /የብራና ጽሑፍ/። ይህ ቃል የግሪኩን የሐዲስ ኪዳን ልዩ ልዩ ኮፒዎች ያመላክታል። ብዙውን ጊዜ በልዩ ልዩ ዓይነት ይመደባሉ። 1/ከተጻፈባቸው ቁሳቁስ /ፓፒረስ፤ ብራና/ ወይም 2/ የጽሑፍ የራሱ ቅርጽ /በካፒታል/ በቁም ጽሑፍ ወይም በቅጥልጣይ መሆኑ። በአጽሕሮተ ቃልም "MS" የብዙ ቁጥር ይባላሉ።

**ማአሶሬቲክ ቴክስት፡-** የዘጠነኛውን ክፍለ ዘመን በብሉይ ኪዳን የዕብራይስጥ የእጅ ጽሑፎችን ያመለክታል። ይህም በአይሁዳዊ ጠበብት የተጻፈና አካባቢ ድምጾችን ተጓዳኝ እዝሎችን የግርጌ ማስታወሻዎችን ያካተተ ነው። ለእንግሊዝኛው ብሉይ ኪዳን የሚሆነው ጽሑፍ ከዚህ የተገኘ ነው። ጽሑፍ በታሪካዊ መልኩ በዕብራይስጥ እንደሆነ የተረጋጠ ሲሆን በተለይ ትንቢተ ኢሳያስ በሙት ባሕር ጥቅሶች ታውቋል። በአጽሕሮትም "MS" ይባላል።

**ሚኢቶናሚ፡-** ከንግግር ክፍሎች ሆኖ የአንድ ነገር ስም ከሌላው ጋር በተጓዳኝ በመጥቀስ የሚገለጥበት ነው። ለምሳሌ ጀበናው እተፈላ ነው ሲል በጀበናው ውስጥ ያለው ውኃ እየፈላ ነው ለማለት ነው።

**ሙርአቶርያን ፍራግመንትስ፡-** ይህ የደንብ /የሕግ/ መጻሕፍትን ዝርዝር ያካተተ ኪዳን ክፍል ነው። የተጻፈውም በሮሜ ከ200 ዓ.ም ቀደም ብሎ ነው። እነዛኑ 27 የሐዲስ መጽሐፍት በፕሮቴስታንት አዲስ ትርጉም ነው። ይህም በሮም ግዛት የሚገኙት የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ዋነኞቹ የቤተክርስቲያን ምክር ቤቶች /በ4ኛው ክፍለ ዘመን ከነበሩት/ በፊት እንደተበጀ ያመላክታል።

***ተፈጥሯዊ መገለጥ***፡- ይህ እግዚአብሔር ራሱን ለሰዎች የሚገልጽበት አንደኛው ክፍል ነው። ተፈጥሯዊ ስርዓትን /ሮሜ 1፡19-20/ እና ሞራላዊ የሕሊና ሚዛንን /ሮሜ 2፡14-15/ ያካትታል። በመዝሙር 19፡1-6 እና ሮሜ 1-2 ተጽፏል። ከልዩ መገለጥ ይለያል፤ ማለትም የእግዚአብሔር የራሱ መገለጥ በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በናዝሬቱ ኢየሱስ ማለት ነው።

ይህ የስነ መለኮት ምድብ እንደገና አጸንዖት እየተሰጠው እንደ ሁግሮስ በመሳሰሉ ክርስቲያን ጸሐፍት በአሮጌው ዓለም ንቅናቄ ላይ ተመልክቷል። እነሱም ይህን ምድብ ሁሉም እውነት የእግዚአብሔር እውነት እንደሆነ ያጸኑበታል። ተፈጥሮ በእግዚአብሔር ለማወቅ የተከፈተ በር ነው ይህም ካልተመሰጥ /ከመጽሐፍ ቅዱስ/ ይለያል ዘመናዊው ሳይንስ የተፈጥሮ ስርዓትን እንዲያጠና ነጻነትን ይሰጠዋል። እንደኔ አስተያየት ለዘመናዊው ሳይንሳዊ የምዕራቡ ዓለም ለመመስከር አዲስ አስደናቂ ዕድል ነው እላለሁ።

***ንስጥሮሳዊነት***፡- ንስጥሮስ በ5ኛው ክፍለ ዘመን የኮንስተንበኖፐል ፓትርያርክ የነበረ ነው። የተማረውም በንሪሆች ሶርያ ሲሆን የመከራከሪያ ነጥቡም ኢየሱስ ሁለት ባሕርያት ሲኖሩት አነደኛው ሙሉ ለሙሉ ሰው፤ ሌላኛው ሙሉ ለሙሉ መለኮት ነው ባይነው። ይህም ከአሌክሳንደሪያው የኦርቶዶክስ አንድ ባሕሪ /በተዋህዶ/ ከሚለው ያፈነገጠ ነው። የንስጥሮስ ዋነኛው አትኩሮቱ ለማርያም የተሰጠው የአምላክ እናት የሚለው ስያሜ ነው። ንስጥሮስ በሌክሳንደሪያው ሲሪል ነቀፋ ገጥሞታል። ይህም ዞሮ ዞሮ በተማረበት በአንቲሆች ማለት ነው። በወቅቱ አንቲሆች የታሪካዊ ሰዋሰዋዊ ጽሑፋዊ አገባብ ያለው የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትረጓሜ ማዕከል ስትሆን አሌክሳንደሪያ ደግሞ በአራትዮሹ /ተምሳሌታዊ/ ጉባዔያት የትምህርት ትርጓሜ ማዕከል ነበረች። ንስጥሮስ ከማዕረጉ ወርዶ በግዞት እንዲቀመጥ ተደርጓል።

***ዋነኛው ጸሐፊ***፡- ይህ  የሚያመለክተው ዋነኞቹን የቅዱሳን መጻሕፍት ጸሐፊዎችን ነው።

***ትይዩ አንቀጾች***፡- እኒህ የጽንሰ ሐሳብ ክፍሎች፤ መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የተሰጠ እና ፍጹም የሆነው የሆነው ተርጓሚም እሱ እንደሆነ፤ አደናጋሪ የመሰሉንን እውነቶች እንኳ ሚዛናዊ በሆነ መልኩ የሚፈታ ነው። ይህም አንድ ሰው ግልጽ ያልሆነለትን አሻሚ አንቀጽ ሲተረጎም ሲሻ ሊረዳው ይችላል። አንቀጾቹ በተጨማሪም ግልጽ ተዛማጅ ክፍሎችን በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ከቅዱሳት መጻሕፍት ያመላክታሉ።

***አጽሕሮት***፡- ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ይረጓሜ ንድፈ ሐሳብ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ቃል በቃል የተረገና ተያያዥነት ቅርጽ የያዘ ሆኖ የእንግሊዝ ቃል ለዕብራይስጥም ሆነ ለግሪክ ቃል ፍቺነት ተፈልጎ፤ የክፍሉ /የአንቀጹ/ ፍሬ ሐሳ ዝቅ ባለ ግምት ከዋናው ጽሑፍ ጋር እየተያየ የሚተረጎምበት ነው።  ከእነዚህ ሁለት ዓይነት ንድፈ ሐሳቦች ፍጹም አቻዎች የሚባለው ግን ዋናውን ጽሑፍ በዘመናዊ ሰዋሰው እና በዘይቤና በፈሊጥ ለመተርጎም የሚሞክር ነው። ይህን በተመለከተ ደህና መብራሪያ /የትርጉም ንድፈ ሓሳቦች /በ Fee እና Stuart መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት በመረዳት እናንብ ገጽ 35 ተመልከት።

***አንቀጽ***፡- ይህ በስድ ንባብ የሚደረግ ዋነኛው የትርጓሜ ክፍል ነው። አንድ ዋነኛ ሃሳቡን ይዞ እያዳበረ ይሄዳል። አንዳንድ በአነቀጽ ላይ ብቻ አኩረን ትርጉሙን ስነሻ /አናሳ አንቀጽ ላይ/ የዋናውን ጸሐፊ ሃሳብ ላናገኘው እንችላለን።

***ፖራኮሊዝም***፡- ይህ የሚያሳየው በአድሏዊነት የተያዘን የአጥቢያ ስነመለኮታዊና ባህላዊ ጉድኝትን ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን ፍጹም ባህል /የባህሎች ሁሉ የበላይነት/ እና የአተገባበር እውነቱን ግምት ውስጥ እያስገባም /አይቀጠልም/።

**አያም**፡- ይህ የሚያመላክተው ተቃራኒነት ያላቸው የመሰሉ እውነቶችን ሲሆን /ይሆናሉ አይሆኑም/ የሚል መልክ ይዞ ነው። እውነትን የሚያቀርበው ተቃራኒ አቅጣጫዎችን ይዞ ነው። ብዙዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች የሚቀርቡት በዚህ /አያም/ ወይም በዲያሌክታካዊ ጥንዶች ተቃርኖ አገባብ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታዎች ተለያይተው እንደተቀመጡ ከዋክብት ሳይሆኑ ምድብ ምድብ በያዙ የክዋክብት ክምችት ይመስላሉ።

**ፕላቶ**፡- ከጥንታዊ ግሪክ ፈላስፎች አንደኛው ነው። የሱ ፍልስፍና የጥንታዊዋን ቤተክርስትያን በአሌክሳንደሪያ ግብፅ ሊቃውንት እንዲሁም በአውግስጦስ አማካኝነት ተጽዕኖ አሳድሯል። ፕላቶ በምድር ላይ ያለ ማንኛውም ነገር የመንፈሳዊ ዓለም ግለባጭ /ቅጅ/ ነው ብሎ ያምናል። የስነመለኮት ጠበብት በኋላ ይህን ተፕላቶን አስተሳሰብ ቅርፆች/ሐሳቦች በሚል ለመንፈሳዊ ተግባር ጥቅም ላይ አውለውታል።

**ቅድመ ግምት**፡- ይህ ስለ አንድ ነገር ቀድመን የምናስበው ወይም የምንገምተው ነው። ጽሑፉን ከመመርመራችን በፊት ብዙ ጊዜ አስተያየትና ፍርድን /አቋምን/ ስለ አንድ ነገር ማድረግ ይዘወተርብናል። ይህ ቅድመ ግምት፤ አድልዖ በመባልም ይታወቃል። ግምት ወይም ቅድመ እውቅና ይባላል።

**ፕሩፍ ቴክስቲንግ**፡- ይህ ተግባት ከለን በቁጥር ብቻ /ሙሉ ክፍልን ሳይሆን/ ወይም ዋናውን የክፍሉን አጠቃላይ ሃሳብ ሳይሆን የመተርጎም ስራ ነው። ይህም ቁጥሮቹን ከዋናው የጸሐፊው ሐሳብ ባፈነገጠ መልኩ የግል አስተያየትን በሚካተት የመጽሐፍ ቅዱስን ስልጣን ትቶ ማለት ነው።

**ይሁዳዊ መምህርነት**፡- ይህ ዓይነቱ የአይሁድ ሕዝቦች የኑሮ ስርዓት የተጀመረው ከ586-538 ቅ.ል.ክ ከባቢሎን ግዞት በኋላ ነው። የአይሁድ ቀሳውስትና ቤተመቅሰሱ ከቀሩ በኋላ የአጥቢያ ምኩራቦች የአይሁድ ብሔራዊ የዕምነት ማዕከላት ለመሆን ቻሉ። እነዚህ አጥቢያ ማዕከላት የአይሁድ ባህል፤ ሕብረት የአምልኮና የቅዱሳት መጻሕፍት ጥናት ማካሄጃ በመሆን የብሔራዊ ሃይማኖታዊ የትኩረት ማዕከላት ሆነዋል። በጁሊየስ ዘመን እነዚህ የጸሐፍት ሃይማኖት ተብለው የሚታወቁት ቀሳውስቱ ጋር በትይዩ መልኩ አገልግለዋል። በ70 ዓ.ም ከኢየሩሳሌም መውደቅ በኋላ ጸሐፍቱ አካል የፈሪሳውያን የበላይ ለመሆን ከመቻሉም በላይ የአይሁድን ሃይማኖታዊ ሕይወት መቆጣጠር ችሏል። ባሕርዩም ተግባራዊ ሕጋዊ ትርጓሜዎች ላይ የሚያተኩር ሆኖ ባህላዊ /ስነ ቃለዊ/ የሆነውን ዘዴ በመጠቀም ታልሙድን ማብራራት ነው።

**ራዕይ**፡- ይህ እግዚአብሔር ሰለው ልጆች የሚናገርበትን ጽንሰ ሐሳብ የሚገልጽ ስያሜ ሙሉ ሐሳቡ ብዙውን ጊዜ በሶስት መንገዶች ይገለባል። 1/ራዕይ፡- ማለትም እግዜአብሔርን በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ የሚከናውነውን 2/ ተመስ፡- እሱ ትክክለኛውን ትርጓሜ ለድርጊቱ ሁሉ የሚሰጥበትን ይህም በተመረጡ ሰዎች አማከኝነት ሆኖ መዝግበው ለሰው ልጆች የሚያስተላልፍበት አገባብ። 3/በማብራሪያ ማለትም መንፈስን በመስጠት የሰው ልጆችን በማገዝ ስለ እሱ ይበልጥ እንዲረዱ ማድረግን ያጠቃልላል።

**የቃላት የዓረፍተነገር ትርጉም**፡- ይህ አጠቃላይ የቃላት ትርጉም ጋር የተያያዙ ደረጃዎችን ያመላክታል። በመሰረቱ የቃላት የተለያየ ትርጉም በየአግባቡ /በየጽሑፉ/ /በየወርዱ/ የሚታየበት ነው።

**ሴፕቱኤጀንት**፡- የዕብራይስጥ ብሉይ የግሪክ ትርጉም ነው። ከባህል አንፃር በሰባ የአይሁድ ሊቃውንት በሰባ ቀናት ተጽፎ ለአሌክሳንደሪያ ግብፅ የተፃፈ እንደሆነ ይነገራል። ባሕላዊ ጊዜውም 250 ቅ.ል.ክ እነደሆነ ሲገመት /በተግባር ግን ጽፎ ለመጨረስ ከመቶ ዓመት በላይ እነደወሰደ ይገመታል/ ይህ ትርጉም ጠቀሜታው የላቀ ሲሆን፤ ይህም 1/ጥንታዊ የሆነውን ጽሑፍ ከዕብራይስጥ ማስረቲካ ጋር እንዲነጻጸር 2/የአይሁድን የትርጉም አገባብ በ3ኛው ክፍለ ዘመን ከክርስቶስ ልደት በኋላ የነበረውን ያሳየናል። 3/የአይሁድን ሜስነክ መረዳት /አስተሳሰብ/ ማለትም ክርስቶስን ካለመቀበላቸው በፊት የነበረውን ያሳያል። አጽሕሮቱም "LXX" ነው።

**ሲናቲኮስ**፡- የ4ኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም የነበረ የግሪክ የብራና ጽሑፍ ነው። የተገኘውም ቲስከስዶርፍ በተባለ የጀርመን ሊቅ በቅድነት ናተሪኒ ገዳም፤ በጃቤሳ መሳ የተባለ ባሕላዊ ስም ባለው በሲናይ ተራራ ክልል ነው። ይህ የብራና ጽሑፍ /የእጅ ጽሑፍ/ በዕብራይስ የመጀመሪያ ፊደል በሆነው በአልፋ [x] ይታወቃል። እሱም ብሉይ ኪዳንና የተጠቃለለውን ሐዲስ ኪዳንን ይዟል። በጣም ጥንታዊ ከሆኑት የተለየ የእጅ ጽሑፎች አንደኛው ነው።

**የመንፈሳዊ**፡- ይህ ቃል ተምሳሌታወኰ ከማድረግ ጋር ተመሳሳሰይ ሲሆን ሃሳቡም ታሪካዊና ተራ የሆነውን የዕሁፉን ክፍል በማስቀረት በልቶ መስፈርት የመተርጎም አግባብ ነው።

**ተመሳሳይ**፡- ይህ የዕሁፉን ፍቺ ያመለክታል። 15/ምንም እንኳ ሁለት ቃላት ፍፁም ተመሳሳይ ትርጉም ባይኖራቸውም /በጣም የተቀራረቡ ከመሆናቸው የተነሳ በአረፍተ ነገር አወቃቀር ላይ የትርጉም ለውጥ ሳይኖር አንዱ አንዱን ሊተካው ይችላል። በተጨማሪም የእብራይስጥ ቅኔ ከሆኑት 3 የትይዩ ዘርፎች አንደኛውን ለመመስረት ያስችላል። በዚህ መሰረት ባለሁለት መስመር የሆኑትን ቅኔዎች /ግጥሞች/ ያመላክታል። /መዝ 1-3-3/

**ሰዋሰዋዊ**፡- ይህ የግሪክ ቃል ሲሆን የአረፍተ ነገርን አወቃቀረአ ያሳያል። ይህም የአረፍተ ነገር አደራደር ሙሉ አስተሳሰብን እንዲገልፅ ተደርጎ ሲዋቀር ያለውን ያሳያል።

ሳይንዚቲካል፡- ከእብራይስጥ ቅኔ /ግጥሞች ከሶስቱ አይነቶች አንደኛውን ያመለክታል። ይህም የቅኔ /የግጥም/ መስመሮች /ሀረጎች/ አንደኛው ከአንደኛው በመቀናጀት አጠቃላይ ስሜት ሊሰጡ በሚችሉ መልኩ ሲዋቀሩ ነው። አንዳንዴም ተለዋዋጭ ይባላል። /መዝ 19፡7-9/

ስልታዊ የስነ መለኮት ትምህርት፡- ይህ ትርጉም ደረጃው አይነት የመፅሀፍ ቅዱስን እውነት ህብር እና ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ሲያቀርቡ ነው። ከታሪካዊነቱ ይልቅ ሎጂካዊነቱ /ምክንያታዊነቱ/ ያመዝናል። የክርስትና የስነመለኮት ትምህርት በየምድቡ በማድረግ /እግዚአብሄር፣ ሰው፣ ሀጢያት፣ ደህንነት ወዘተ/ እያለ ይቀርባል።

**ታልሙድ**፡- ይህ የአይሁድ የስነ ቃል /ባህል መለያ ነው። አይሁድ እግዚአብሄር በሲና ተራራ ላይ ለሙሴ በቃሉ እንደተናገረው ያምናሉ። በተግባር ሲታይ ግን ለዓመታት የተከማቸ። የአይሁድ መምህራን የጥበብ ክምችት ነው። ሁለት ዓይነት የተለያዩ የዕሁፍ ቅጂዎች /እትሞች/ አሉት ታልሙድ እነሱም የባቢሎኑና ያልተጠናቀቀው በአጭር የተፃፈው የፍልሰጥሙ /የከነአኑ/።

**የቃሉ ምርመራ**፡- ይህ የቅዱሳን መፃህፍትን ጡናት ማካሄድ በተመለከተ ነው። ይህ አይነቱ ጥናት አስፈላጊ የሚሆነው ዋነኞቹ ፅሁፎች ስለማይገኙ ቅጂዎቹ የተለያዩ በመሆኑ ነው። ልዩነቶችን ለማብራራትና በተቻለ መጠን ወደ ዋነኞቹ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ፅሁፎች መነሻ ለማድረስ ነው ብዙውን ጊዜ ዝቅተኛው ምርመራ ይባላል።

**የፅሁፍ አቀባበል፡-** ይህ ስያሜ የተሰፋፈው ወደ እኤልዚጎር ትርጉም ከሆነው በ1633 የግሪክ አዲስ ኪዳን እትም ነው። በመሰረቱ ይህ የግሪክ የአዲስ ኪዳን የወጣው /የተገኘው/ ጥቂት ቀደም ሲል ተፅፈው ከነበሩ የግሪክ የእጅ ፅሁፎች እና የላቲን እትሞች ማለትም ከአራሳመስ /1510-1535/ እስጢፋኖስ /1546-1559/ እና ኤልዚጎር /1624-1678 ከተፃፉት ነው የአዲስ ኪዳን ፅሁፋዊ ምርመራ /ገፅ 27 መግቢያው ላይ ኤቲ ሮበርትስን/ የባይዘንታይን /የግሪክ/ ፅሀፀፍ በተግባር ሲታይ ፅሁፎችን መቀበል ነው ብሏል። የባይዘንታይን ፅሁፍ የመጨረሻው ዝቅተኛው የሆነ በጣም ጠቃሚ ከሆነፀ ከሶስቱ ከቀደምት የብራና /የእጅ ፅሁፎች/ /በምዕራብ በሌክሳንደሪያና በባይዘንታን/ ካሉት የሚመደብ ነው። በውስጡም በእጅ ሲፃፍ ለዘመናት የተደረጉትን ግድፈቶች /ስህተቶች/ አከማችቶ ይዟል። ሆኖም ግን ኤ ቲ ሮበርትሰን ደግሞ እንዳለው፣ ፅሁፎቹ የተወልን ነገር በውስጡ ያለው ተገቢ ፅሀፍ ነው ብሏል /ገፅ 21 ላይ/ ይህ የግሪክ ፅሀፍ /በተለይም የአራስመስ 3ኛ እትም በ1522 /የንጉስ ጀምስ እትም ማለትም 1611 ዓ.ም የታተመውን መሰረት እንደሆነ ይታመናል።

**ቶራ፡-** ይህ የዕብራይስጥ ቃል ማስተማር ማለት ነው። እሁም ለሙሴ ፅሁፎች /ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም/ ያለውን የሚያካትተ ርዕስ ነው። ይህ ለአይሁድ ታላቅ ስልጣን /ተቀባይነት/ ያለው ክፍል ነው።

**ታይፖሎጂካል፡-** ይህ ጥልቀት ያለው ሙያዊ ትራጓሜ ነው። ብዙውን ጊዜ የሀዲስ ኪዳን እውነት ከብሉይ ኪዳን ተምሌታዊ መልኩ የሚያስጠቅስና የሚያስማማ ነው። የትርጉም ምድብ ዋነኛው የአሌክሳደሪያን ዘዴ የተከተለ ነው። የዚህ አይነቱን ትርጉም በአግባቡ አለማከናወንን ለማስቀረት ትርጓሜው ሲካሄድ በተወሰኑ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች መሆን ይኖርበታል።

**ቫአቲካነስ፡-** ይህ የ4ኛ ክፍለ ዘመን የግሪክ የእጅ ፅሑፍ ነው። የተገኘውም በቫቲካን ቤተመጽሀፍት ሲሆን ዋናውን ብሉይ ኪዳን ተነባቢት /ራዕይ/ እና አዲሰ ኪዳንን ያካትተዋል። የተወሰኑ ክፍሎች ማለትም ከዘፍጥረት፣ ከዕብራውያን፣ ከሌዋውያን ሆኖም የተወሰኑ ክፍሎች ማለትም ከዘፍጥረት፣ ከዕብራውያን፣ ከሌዋውያን ፊሊሞና እና ከራዕያ ጎድለውበታል። ዋናውም የቃሉን የእጅ ጽሑፍ በመወሰን በኩል በጣም ጠቃሚ የሆነ ጽሑፍ ነው። መለያውም ፊደል "ቢ" ነው።

**ቫሰጌት፡-** ይህ የጀሮም የላቲን ትርጉም የሆነ መጽሀፍ ቅዱስ ነው። ይህ የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ዋነኛ ትረጉም ተደርጎ ተወስዷል። በ380 ዓ.ም ነው የተፃፈው።

**ጥበባዊ ሥነ-ጽሁፍ፡-** ይህ ቃል የሥነ-ጽሑፍን ዘውግ/ዓይነት/ የተለመደ ዓይነት ሆኖ በቅርብ ምስራቅ የጥንት አካባቢ /ዘመናዊው ዓለም/ የሆነውን ያመለክታል። ይህ በቅኔ/በግጥም/በምሳሌያዊ አነጋገር፣ በወገዊ ጽሁፍ አማካኝነት አዲሱን ትውልድ ለማስተማርና ስኬታማ ሕይወት እንዲኖር የሚያስችል ነው። መልእክቱም ለአጠቃላይ ለማህበረሰቡ ሳይሆን በግለሰቦት ላይ ያተኮረ ነው። የታሪክን ሁኔታ በማጣቀስ አይጠቀምም፣ ይልቁንም የሕይወትን ልምድና አስተውሎትን ይቃኛል። ከመጽሀፍ ቅዱስ ከእዮብ ከመሃልየ ማሃልየ የሚታሰበው የያህዌን መገኘትና ማምለክን ሲሆን ይኼውም መንፈሳዊ ዓለም አስተሳሰቡ በግልፅ በየሰው የሕይወት ልምድ በሁሉም ጊዜ እንደማይደረግ ያታወቃል።

እነደ ሥነ-ጽሁፍ ዘርፍ በአጠቃላይ እውነት ላይ ያተኩራል። ይህ የሥነ-ጽሑፍ ክፍል /ዕይነት/ግን በእያንዳንዱ ሁኔታ ጥቅም ላይ አይውልም። እነዚህ አጠቃላይ ሀሳቦች በእያንዳንዱ ሰው ባለበት ሁኔታ ላይ የማይከናወኑ ናቸው።

እነዚህ እነዚህ ፅሑፎች የሕይወትን ጠንካራ /ዋነኛ/ ጥያቄ ያነሳሉ። ብዙውን ጊዜ ሀይማኖታዊ ሆነው ባህል የሚደባለቁ አመለካከቶችን /ኢዮብ/መክብብ/ ያነሳሉ /ይከራከራሉ/። ለሕይወት ጥያቄዎች ሚዛናዊ ምላሽ በመስጠት በተለይ አሰዛኝ/ሰቆቃዊ/ በሆኑት ላይ ያተኩራሉ።

**ወርድ ፒክቸር እና ወርደ ቪው፡-** እነዚህ ተጓዳኝ ቃላት ናቸው። ሁሉም ፍልስፍናዊ ጽነሰ ሃሰቦች ሲሆኑ በአፈጣጠር ላይ ያተኩራሉ። የዓለም ምስል የሚሰጠው እንዴትን ሲያመለክት ስለአፈጣጠር ደግሞ የዓለም አመለካከት የሚለው ማን የሚለውን ያሳያል። እነዚህ ቃላት በተለይ ዘፍጥረት 1-2 ለመተርጎም በመጀመሪያ በመጀመሪያ ማን፣ የሚለውን ያነሳሉ "እንዴት" የሚለውን የአፈጣጠር ጥያቄ ትተው።

**ያህዌ፡-** ይህ የእግዚአብሄር የቃል ኪዳን ስም በአዲስ ኪዳን ነው። ይህም ዘፀአትን 3.14 ያለውን ያነትናል። ይህ የዕበራይስጥ ምክነያታዊ ስም በመጥቀስ መሆን የሚሰውን ያሳያል። አይሁዶች ይህን ስም ለመጥራት ፍርሐት አለባቸው ምንም አንኳ ቢቀበሉትም። በመሆኑም ወደ ዕብራይስጥ ለውጠው አዶናይ/ጌታ/ ይሉታል። በዚህም ምክንያት ነው ይህ የቃል ኪዳን ስም ወደ እንግሊዝኛ የተተረጎመው።

### ተጨማሪ መግለጫ አራት

### የእምነት መግለጫ

በግል በተለይ በእምነት መግለጫም ሆነ የዕምነት ማስታወቂያ ብዙ አያሳስበንም ይልቁንም መጽሐፍ ቅዱስን ማፅናቱ ይሻለኛል። ዳሩ ግን እኔ የዕምነት ሁኔታ ለመረዳትና ለመፈተሽ ለሚፈልጉ የዕምነት መግለጫው ይረዳቸው ይችላል። በርካታ ሥነ-መለኮታዊ ሕጸጾችና የተዛቡ አመለካከቶች ባሉበት ሁኔታ የእኔን ሥነ- መለኮታዊ ትምህርት አጭር ማጠቃለያ አቀርባለሁ።

1. መጽሀፍ ቅዱስ ብሉይም ሆነ አዲስ ኪዳን ሁለቱም ተመስጧዊ የሆነ የማይወድቅ /የማይሻር / ሙሉ ሥልጣን ያለው የእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ቃል ነው።

ቃሉ የራሱ የእግዚአብሔር መገለጥ ሲሆን በመንፈሳዊ ምሪት በሰዎች አማካኝነት የተመዘገበ /የተፃፈ/ ነው። ስለ እግዚአብሄር ንፁህ እውነት እና ስለ ተግባሩ የሚገልፅ ብቸኛ ምንጭ ነው። እሱም ለራሱ ቤተክርስቲያን የዕምነትና የተግባር ብቸኛ ምንጭ ነው።

2. አንድ ብቻውን የሆነ ዘለዓለማዊ ፈጣሪ የሚቤዥ እግዚአብሔር አለ። እሱም የሚታየውንም ሆነ የማይታየውንም የሁሉም ነገር ፈጣሪ ነው። ራሱን በአፍቃሪነቱና በጠባቂነቱ /በተንከባካቢነቱ/ የገለፀ ሲሆን ራሱም ፍፁምና /መልካም/ ትክክለኛ ነው። ራሱን በሦስት አካላት ገልጧል። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በእኩል አካል የተለያዩ ባህርያ ግን አንድ የሆነ።

3. እግዚአብሔር ከቃሉ ጋር ሁሌም ነው። እናም ዘለዓለማዊ እቅድ ለፍጥረቱ ያለ ሲሆን ይህም ማስተካከያ የማይደረግለት በእያንዳንዱ ሰው ነፃ ፍቅር ላይ ያተኮረ ነው። ያለ እግዚአብሔር እውቅናና ፍቃድ የመሆን ነገር የለም ይህም ቢሆን ግን ለሰዎችም ሆነ በመላእክት ነፃ ፍቀድን ፈቅዷል። እየሱስ አብ የመረጠው ሰው ነው። ሁሉም የሚመረጡት በሱ ነው። የእግዚአብሄር የሁኔታዎች ቀድመ እውቅና የሰው ልጆችን ቅድመ ፅሑፍ ቃሉን ከመቀበል ለመወሰን አያዳግታቸውም። እያንዳንዳችን ለምናስበውም ሆነ ለምንሰራው ሃላፊነትን እንወስዳለን።

4. የሰው ልጅ ምንም እንኳን በእግዚአብሄር አምሳል ቢፈጠርና ከሃጥያት ነፃ ቢሆንም በእግዚአብሄር ላይ ማመፅን መረጠ። አዳምና ሄዋን ምንም እንኳ ከተፈጥሮ በሆነ ወኪል ቢፈተኑም ፈቅደውና ወደው በግለኝነት በወሰዱት አቋም ሃላፊነት አለባቸው። የእነሱ አመፅ ነው የሰው ልጅንም ሆነ ፍጥረትን ለጉዳት የዳረገው። እኛ ሁላችንም ከእግዚአብሔር ምህረት ከአዳም ለወረስነውም ሆነ በሰውነታችን ለፈፀምነው አመፅ ያስፈልገናል።

5. እግዚአብሔር ይቅርታውንና ምህረቱን ለወደቀው ሰውነታችን ስጥቶናል። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ብቸኛ ልጅ ሰው የሆነ፣ ያለ ሃጥያት የተመሳለሰ እኛን ውጦ በሞተልን፣ የሰው ልጆችን የአሃጢአት ቅጣት ተቀበለ። እሱ የደህንነት መንገድና ከእግዚአብሔር ጋር ለሚምረው ስውረት ብቸኛ መንገድ ነው። ስለደህንነት ሌላ ምንም መንገድ የለም ራሱ ሰርቶ በጨረሰው ሥራ ከማመን በስተቀር።

6. እያንዳንዳችን በግል የእግዚአብሔርን ይቅርታ ስጦታ በእየሱስ የሆነውን ደህንነት መቀበል ይኖርብናል። ይንንም ማግኘት የሚቻለው በእግዚአብሔር ተስፋ በማመን፣ በኢየሱስ በኩል ፍቃደኝነት ከሃጢአት መራቅ ነው።

7. ሁላችንም ሙሉ ምህረት እና መመለስ የምናገኘው ክርስቶስ እምነትና ሃጢአት በመመለስ ነው። የአዲስ ህይወቱ ማስረጃም በተለመደና እየተለወጠ ባለ ህይወቱ ይታወቃል። እግዚአብሄር ለሰው ሰጆች ያለው ዓላማ አንድ ቀን በመንግስተ ሰማያት የሚሆን ሳይሆን አሁን ክርስቶስ በመሰለ ሕይወት መመሳለስ ነው። በትክክል መቤዠትን ያገኙ በስህተት ሃጢአት ቢሰሩም በዕምነታቸው ቀጥለውበት በንሥሐ ህይወት በሕይወት ዘመናቸው ሊመላለሱ ይገባል።

8. መንፈስ ቅዱስ ሌላው እየሱስ ነው። እሱም በዓለም ላይ አለ፣ የጠፉትን ወደ ክርስቶስ ለመምራትና በዳኑትም ክርስቶስ የመሰለ ሕይወት እንዲኖሩ በማስቻል። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ደህንነታችን ስንቀበል ይሰጡናል። እነርሱም የእየሱስ ሕይወትና አገልግሎቶች ሲሆኑ ለአካሉ ለቤተክርስቲያን የተሰጡ ፀጋዎቹ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍላጎቱንና ሐሳቦቹን ለማስፈፀም በመንፈስ ፍሬ የሚታዩ ናቸው። መንፈስ ቅዱስ ፊት እንደነነረ አሁንም ይጠራል።

9. አብ ከሙታን የተነሳውን ኢየሱስ ክርስቶስን የሁሉም ፈራጅ አድረጎታል። ወደ ዓለም ይመለሳል በሁሉም የሰው ልጆች ላይ ለመፍረድ በኢየሱስ ያመኑና ስማቸውም በበጎ ሕይወት መጽሀፍ ላይ የፃፈ ሰማያዊ የከበረ አካላቸውን በዳግም ምፅአቱ ያገኛሉ ከእሱም ጋር ለዘለዓለም ይሆናሉ። የእግዚአብሄርን እውነት ለመቀበል ያልፈለጉ ለዘለዓለም ከእግዚአብሄር ህብረትና ደስታ ይለያሉ። ከሰይጣንና ከመልአክቱ ጋር ይፈረድባቸዋል።

ይህ በእውነቱ የተጠናቀቀና የጠለቀ ባይሆንም የልቤን ሥነ-መለኮታዊ መዓዛ ይሰጣቸሗል ብዬ አምናለሁ። ጽሑፉን እወደዋለሁ።

"ከአስፈላጊዎች ሁሉ — ህብረት፣ ከምርጫዎች- ነፃነት ከሁሉም ነገር- ፍቅር"